

ስካን በማድረግ ያግኙን
Scan and contact us on

ብርሃነ ሰላም ማተሚያ ድርጅት

የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ውሣኔዎች ቁጥር-27

የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ውሣኔዎች



ለላቀና ተደራሽነት ላለው የዳኝነት አገልግሎት እንተጋለን!
We strive for an efficient and accessible judicial service!

ቅጽ - 27

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
ጠቅላይ ፍርድ ቤት



የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት

ሰበር ሰሚ ችሎት ውሣኔዎች

ቅጽ-27

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

ጠቅላይ ፍ/ቤት

የሕግ ጥናት እና ምርምር ዳይሬክቶሬት

መጋቢት 2017 ዓ.ም.

አዲስ አበባ

ድህረ-ገፅ፡-www.fsc.gov.et
ስልክ፡-+251-11-1-55-34-00/011-1-11-04-32
ፋክስ፡-+251-111-56-55-33
የመ.ሣ.ቁ. 6166
ነፃ የስልክ መስመር፡- 992

የክቡር ኢ.ፌ.ዴ.ሪ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዝደንት መልዕክት



በፌዴራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀጽ 10 ንዑስ አንቀጽ 2 መሰረት አስገዳጅ የሆኑ ውሳኔዎች በዚሁ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 3 መሰረት በኤሌክትሮኒክና በሕትመት ሚዲያዎች የማሰራጨት ኃላፊነት በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ላይ ተጥሏል። ከአምስት ያላነሱ ዳኞች በተሰየሙበት የሰበር ችሎት የሚሰጠው ውሳኔ አስገዳጅ መደረጉ ውሳኔዎችን ወጥነትና ተገማችነት የሚያሻሽል የተገልጋዮችን እንግልት እንዲቀንስ ታስቦ የተቀየሰ በመሆኑ በአስራ ሁለቱም ክልሎች የሚገኙ ፍርድ ቤቶች እንደዚሁም በከተማ አስተዳደር የሚገኙ ፍርድ ቤቶች እንደማንኛውም ሕግ የውሳኔያቸው መሰረት አድርገው ሊጠቅሷቸው እና ሊጠቀሙባቸው ይገባል። ይህ ሊሳካ የሚችለው ውሳኔዎች በወቅቱ ተደራሽ ማድረግ ከተቻለ መሆኑ ግልጽ ነው። ይህን ታሳቢ በማድረግ ፍርድ ቤቱ ሰበር ሰሚ ችሎት አስገዳጅ የሕግ ትርጉም የሰጠባቸውን ውሳኔዎች የመጀመሪያውን ቅጽ ማሳተም ከጀመረበት ከ1997 ዓ.ም አንስቶ 26 ቅጾችን ማሳተም የቻለ ሲሆን አሁን ደግሞ 27ኛውን ቅጽ እነሆ አቅርቦላችኋል።

ከዚህ በተጨማሪ ውሳኔዎችን በፍርድ ቤቱ ድረ-ገጽ ተደራሽ ለማድረግ እንዲሁም በአካል ለሚቀርቡ ጠያቂዎች ቅጂዎችን በመስጠት ተደራሽ ለማድረግ ጥረት ተደርጓል በመደረግም ላይ ይገኛል። እነዚህ ጥረቶች ቢኖሩም ሁሉንም ውሳኔዎች በሚፈለገው ደረጃ በቀላሉ ተደራሽ ለማድረግ ተችሏል ሊባል ስለማይቻል የሕግና የአሰራር ማሻሻያዎችን በማድረግ አስገዳጅ ትርጉም የተሰጠባቸውን ውሳኔዎች የመለየት፣ በፍጥነት በድረ-ገጽ ተደራሽ ማድረግ ስራ እየተከናወነ በመሆኑ የተሻለ አፈጻጸም እንደሚኖር እና በተደጋጋሚ ለሚነሱ ጥያቄዎችም ምላሽ ይሰጣል ተብሎ ይታመናል። የውሳኔዎች ተደራሽነት

ሙሉ በሙሉ እስከሚሳካ እና የተገልጋዩ ፍላጎት እስከሚሟላ ድረስ እየተደረጉ ያሉ ጥረቶች ሳያሰልሱ የሚቀጥሉ መሆኑን በዚህ አጋጣሚ ማረጋገጥ እንወዳለን፡፡

ከተደራሽነት ባሻገር እነዚህ ውሳኔዎች ምርምርና ጥናትን ማገዝ፣ የሕግ ጽንሰ ሐሳብ ተዋስዖን (Discourse) ማዳበር እና የሕግ እሳቤና ሳይንስ ፅድነት አስተዋጽዎ ማድረግ ተጠባቂ ውጤት ነው፡፡ በዚህ ረገድ የውሳኔዎች ትችት እንዲሁም በሚያነሱት አከራካሪ ጉዳይ ላይ ተጨማሪ ጥናት ተደርጎ የሕግ አስተምህሮና ሳይንስ የሚያድግበት እድል መፈጠር እንዳለበት ይታመናል፡፡ በመሬት ላይ ያለው እውነት ሙሉ በሙሉ ተስፋ የሚያስቆርጥ ነው ባይባልም የሚፈለገው ደረጃ አለመድረሱ የሚስተዋል ነው፡፡ ከዚህ በፊት እንደገለጽነው በዚህ ረገድ የሚደረገው ጥረት በሁሉም ባለድርሻ አካላት ታስቦበትና ታቅዶ ሊሰራበት የሚገባ በመሆኑ ትኩረት እንዲሰጠው በዚህ አጋጣሚም ለማስገንዘብ እንወዳለን፡፡

በዚህ አጋጣሚም የተወደዳችሁ አንባብያን በተለይም የሕግ ሞያ ማህበረሰብ አባላት ለፍትህ መስፈን እና ለሕግ የበላይነት መከበር የሚደረገው ጥረት ውስጥ የበኩላችሁን እንድትወጡ እንዲሁም የፌዴራል ፍርድ ቤቶች እያካሄዱ ላሉት የለውጥ እንቅስቃሴ እንደ ከዚህ ቀደሙ ሁሉ አሁንም የበኩላችሁን አስተዋጽኦ ማድረጋችሁን አጠናክራችሁ እንድትቀጥሉ ስል በፌዴራል ፍርድ ቤቶች ስም አደራ ለማለት እወዳለሁ፡፡

መልካም ንባብ፡፡

አመሰግናለሁ !!!

ቴዎድሮስ ምህረት ከበደ

የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ጠቅላይ ፍርድ ቤት

ፕሬዝደንት

የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሕግ ጥናት እና ምርምር ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር

መልዕክት

የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ላለፉት 20 ተከታታይ ዓመታት ሰበር ሰሚ ችሎት አስገዳጅ የሕግ ትርጉም የሰጠባቸውን ውሳኔዎች በቅጽ ማሳተም መቆየቱ የሚታወቅ ነው፡፡ በዚህም ውሳኔዎቹ ከጊዜ ወደ ጊዜ ብዛታቸው እየጨመረ የመጣ ሲሆን ተቋማችንም በተቻለው መጠን እነዚህን በተለይም በማናቸውም ደረጃ በሚገኙ ፍርድ ቤቶች እንደ ሕግ የሚጠቀሱትን ውሳኔዎች በህትመትም ሆነ በሌሎች ዘዴዎች ሲያሰራጭ እና ለሕብረተሰቡ ተደራሽ ሲያደርግ ቆይቷል፡፡ እነሆ በዚህ ዓመትም 27ኛ ቅጹን ሲያቀርብላችሁ ከፍተኛ ደስታ ይሰማዋል፡፡

የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ከአምስት ያላነሱ ዳኞች በተሰየሙበት የሚሰጡ እና አስገዳጅ የሕግ ትርጉም የተሰጠባቸው ውሳኔዎች በተለይም የሕግ ትርጉም የተሰጠበት ነጥብ በቀጣይ በሚነሱ ተመሳሳይ ጉዳዮች ላይ እንደ ሕግ የሚጠቀስ እና በሀገራችን በኢትዮጵያ በየትኛውም ደረጃ ላይ ያሉ ፍርድ ቤቶች የሚሰጧቸው ውሳኔዎች መሰረት ሊሆኑ እንደሚገባቸው በፌዴራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀጽ 10 ንዑስ አንቀጽ 2 ላይ በግልጽ ተደንግጎ ይገኛል፡፡ ይህም ማለት እነዚህ የሕግ ትርጉም የያዙ ውሳኔዎች በፌዴራል ደረጃም ሆነ በክልሎች የሚገኙ ፍርድ ቤቶች እንደዚሁም በከተማ አስተዳደር የሚገኙ ፍርድ ቤቶች እንደማንኛውም ሕግ የውሳኔያቸው መሰረት አድርገው ሊጠቅሷቸው እና ሊጠቀሙባቸው ይገባል፡፡ ይህንንም ታሳቢ በማድረግ አስገዳጅ የሕግ ትርጉም የተሰጠባቸውን ውሳኔዎች በማሳተም በተቻለ ፍጥነት ተደራሽ ለማድረግ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት አሁንም ጥረቱን አጠናክሮ በመቀጠል ላይ ይገኛል፡፡ ቅጾቹን በማሳተም ተደራሽ ከማድረግም በተጨማሪ በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይፋዊ ድረ-ገጽ ላይም እንዲጫን በማድረግ ይበልጥ ተደራሽነቱን በማስፋት ላይ ይገኛል፡፡ በዚህ አጋጣሚም የተወደዳችሁ አንባብያን በተለይም የሕግ ሞያ ማህበረሰብ አባላት በቅጽ ከሚታተሙት ውሳኔዎች በተጨማሪ ሌሎች የሰበር ሰሚ ችሎት ውሳኔዎችን ከፍርድ ቤቱ ድረ-ገጽ ወይም ትክክለኛ የመዝገብ ቁጥሩን ብቻ በመያዝ እና ዳይሬክቶሬቱ ጋር በአካል በመምጣት ያለምንም ተጨማሪ ወጪ ማግኘት የምትችሉ መሆኑንን ለመግለጽ እንወዳለን፡፡

አመሰግናለሁ !!!

መልካም ንባብ

አሮን ደጎል ሃብቱ

የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ጠቅላይ ፍርድ ቤት

የሕግ ጥናት እና ምርምር ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር

የፌ/ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የህግ ትርጉም የሰጠባቸው ውሣኔዎች ማውጫ /ቅፅ 27/

ተ.ቁ	የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ	ተከራካሪ ወገኖች	ውሣኔው የተሰጠበት ቀን	ገጽ
ፍትሐብሔር ሥነ-ሥርዓት					1
1.	ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት ትክክለኛ ፍትሕ ለመስጠት የሚረዳ ተጨማሪ ማስረጃ ማያያዝ የሚችል መሆኑ በተደነገገው መሰረት ፍርድ ቤት በዚህ ድንጋጌ ማዕቀፍ ማስረጃ መቀበሉ የሥነ-ሥርዓት ሕግ ጥሰት ተፈጽሟል የማያስብል ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 345(1)(ለ) እና 327(3)	200929	ሕዳሴ ቴሌኮም አ/ማ እና እነ አቶ ገዛኸኝ ለማ (2 ሰዎች)	30/02/2014 ዓ.ም	2
2.	ከሳሽ ለክስ ምክንያት በሆነዉ ነገር ወይም ክሱ በተመሰረተበት ነገር ሀብት ላይ ጥቅም ወይም መብት ያለዉ መሆኑን ካላረጋገጠ ክስ አቅርቦ ዳኝነት ለመጠየቅ እንደማይፈቀድለት በተደነገገው መሰረት ባል ወይም ሚስት በግለሰብ ተወክለዉ ዳኝነትና እንዲወሰንልኝ ብሎ ለመጠየቅ በሕግ አግባብ የዉክልና ስልጣን የተሰጣቸዉ ወይም ከሕግ የመነጨ መብት ሳይኖር የባልና ሚስት ንብረት ክርክር በተመለከተ በባልና ሚስት የጋራ ንብረት ላይ የጋራ የባልና ሚስት እዳ ያለ በመሆኑ የጋራ እዳ ተብሎ ይወሰንልኝ በሚል የሚቀርብ ክርክር ተከፋዩ (ገንዘብ ጠያቂው) ወይም ባለመብት የተባለው ሰው ከባልና ሚስት ገንዘብ አለኝ ብሎ ሳይጠይቅ (ክስ ሳያቀርብ ወይም ጣልቃ ገብቶ ሳይከራከር) የባልና ሚስት የጋራ እዳ ነው ተብሎ ውሳኔ የማይሰጥ	181649	አቶ ደጋረጋ ሙሉ እና ወ/ሮ ዉብናት ላቀ	መስከረም 26 ቀን 2013 ዓ.ም	6

ተ.ቁ	የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ	ተከራካሪ ወገኖች	ውሣኔው የተሰጠበት ቀን	ገጽ
	ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.33 [2]				
3.	✍ ፍርድ ቤቶች መጥሪያ ሲልኩ ተከሳሽ የሆነው ወገን የተፈጥሮ ሰው ወይም የንግድ ድርጅት መሆን አለመሆኑን በመለየት በሥነ-ሥርዓት ሕግ በተዘረጋው ሥርዓት አግባብ መጥሪያው ወጪ መሆኑንና መድረሱን በማረጋገጥ የመደመጥ መብት መከበሩን የመከታተልና የመቆጣጠር ኃላፊነት ያለባቸው ስለመሆኑ ✍ ተከሳሽ/አመልካች ነጋዴ ቢሆንም የንግድ ድርጅት ባለመሆኑ በንግድ ሕግ መሠረት የተመዘገበ የንግድ ማሕበር/ድርጅት ካልሆነ የሚቀርበው ክስ በንግድ ሥሙ ቀርቦ ክርክር የማይመራና የንግድ ድርጅት ባለመሆኑ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 97 የተመለከተውን የመጥሪያ አደራረስ ሥርዓት ሊከተል የሚችል ስላለመሆኑ ✍ ነጋዴ ሥራውን ሊሰራለት የሚችል ሠራተኛ መቅጠር የሚችል ቢሆንም ሠራተኛው ነጋዴውን ወክሎ መጥሪያ ለመቀበል ሥልጣን ያለው መሆኑ እስካልተረጋጠ ድረስ የሥነ-ሥርዓት ሕግ ዓላማ የሆኑትን አንዛራዊ እውነት የመፈለግና ፍትሐዊነትን በሚያሳካ መልኩ የመደመጥ መብትን በተሟላ አግባብ በሚያስከብር ሁኔታ ለሕጉ ውጤት ሊሰጠው ስለሚገባ መጥሪያው ሊደርስ የሚገባው በአካል የተፈጥሮ ሰው ለሆነው ለነጋዴው ስለመሆኑ	200023	አንሲፍ ኮንስትራክሽ እና አቶ ጥላሁን አበበ	ጥቅምት 29 ቀን 2014 ዓ/ም	11

ተ.ቁ	የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ	ተከራካሪ ወገኖች	ውሣኔው የተሰጠበት ቀን	ገጽ
	✍ የድርጅት ሰራተኛ መጥሪያ ለመቀበል ውክልና እስከሌለ ድረስ መጥሪያውን አልቀበልም ማለት የድርጅት ሠራተኛ መጥሪያውን አልቀበልም ብለዋል በሚል ክርክሩ ተከሳሽ ድርጅት በሌለበት መታየቱና በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 78 መሠረት ያቀረበው ማመልከቻ ውደቅ መደረጉ በሥነ-ሥርዓት ሕግ የተዘረጋውን የመደመጥ መብት ያላከበረ ስለመሆኑ				
4.	✍ ከይግባኝ ማስፈቀጃ ማቅረቢያ ጊዜ ጋር በተያያዘ የሚቀርበዉ ክርክር በባህሪዉ ፍርድ ቤት በእራሱ የእራሱን ዉሳኔ/ትዕዛዝ ሊከልስ ከሚችልባቸዉ ሁኔታዎች ዉስጥ የማይካተት በመሆኑ ፍርድ ቤት የይግባኝ ማቅረቢያ ጊዜ አላለፈበትም የሚል ትዕዛዝ ከሰጠ በኋላ እንደገና ይህንኑ ትዕዛዝ እራሱ በመከለስ የማቅረቢያ ጊዜዉ አላለፈም በማለት ሊወስን የሚችልበት የህግ ምክንያት የሌለ ስለመሆኑ ✍ የይግባኝ ማስፈቀጃ ሲቀርብ ፍርድ ቤቱ የፈቃድ ጥያቄ ማመልከቻው ተቀባይነት ያገኛል ብሎ ሲያስብ መልስ ሰጪ ወይም ተጠሪ የሆነ ወገን አስተያየት እንዲሰጥ ማድረግ ሲገባ አስተያየት እንዲሰጥ አለመደረጉ የስነ ስርዓት ግድፈት የተፈጸመበት መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ ስህተቱ ሊታረም የሚችለው ደረጃውን ጠብቆ ይግባኝ በማቅረብ ስለመሆኑ የፍ/ስ/ስ/ህ/ቁጥር 325/3	201028	የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት ሶማሌ ሪጅን እና አቶ አህመድ እስማኤል የሱፍ	ጥቅምት 05 ቀን 2014 ዓ/ም	15

ተ.ቁ	የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ	ተከራካሪ ወገኖች	ውሣኔው የተሰጠበት ቀን	ገጽ
5.	በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.182(2) እንደተመለከተው ክርክር የሚወሰነው በተጠየቀው ዳኝነት አግባብ ሲሆን ፍርድ ቤትም ከቀረበው ዳኝነት አኳያ ከግራ ቀኙ ክርክር በመነሳት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 246 እና ተከታዮቹ መሠረት በተነሱት ጉዳዮች ጭብጥ መስርቶ ውሳኔ የመስጠት ኃላፊነት ያለበት ስለመሆኑ	226569	አቶ ይስማው ድረስ እና እነ አቶ ባህሩ ዓለሙ (2 ሰዎች)	ሚያዚያ 26 ቀን 2015 ዓ/ም	19
6.	በክርክር ሂደት ተከሳሽ ንብረት በማሸሽ ወይንም ለሌላ ሰው በማስተላለፍ የክርክሩን ሂደት ውጤት አልባ በማድረግ ከሳሽ ላይ የማይተካ ጉዳት ሊያደርስ የሚችልበትን ሁኔታ ለማስቀረት ከፍርድ በፊት ንብረት እንዲያዝ ወይንም እንዲታገድ የሚሰጠው ትዕዛዝ የተከሳሽን የንብረት መብት ከማገድ አልፎ በኢኮኖሚ እንቅስቃሴ ላይም አሉታዊ ተፅኖ ሊያስከትል ስለሚችል የሚሰጠው ትዕዛዝ እነዚህን ተነፃፃሪ መብቶች ያማከለ መሆን ያለበት ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 147 እና ተከታይ ድንጋጌዎች	206183	እነ ወ/ሮ ማኔ ጫፋ (2 ሰዎች) እና አቶ ተስፋዬ ቡንዳሬ	ጥቅምት 30 ቀን 2014 ዓ/ም	24
7.	ፍርድ ቤት በህግ የተረጋገጠን መብት ከማስከበር/ከማክበር በዘለለ እራሱ መብት ሊፈጥር የማይችልና በፍርድ ቤት የሚሰጥ ማንኛውም ውሳኔ ስርዓቱን ጠብቆ እስካልተለወጠ ወይም እስካልተሻሻለ ድረስ ተፈፃሚ ሆኖ ሊቀጥል የሚገባ ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ አንቀጽ 5 እና አንቀጽ 212	223405	ራዕይ በሲዳሞ ተራ ልማትና ንግድ አ/ማህበር እና ወ/ሮ ነኢማ ጫሞላ	ጥር 29 ቀን 2015 ዓ.ም	28

ተ.ቁ	የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ	ተከራካሪ ወገኖች	ውሣኔው የተሰጠበት ቀን	ገጽ
8.	በዕርቅ ስምምነት መሰረት እልባት ያገኘ ጉዳይ ባልተሻረበት ወይም ባለተለወጠበት ሁኔታ በስምምነት አልቋል ተብሎ ውሳኔ ባረፈበት ንብረት ላይ ውርስ እንዲጣራ በሚል የዳኝነት ጥያቄና ክርክር የፍርድ ቤትን ውሣኔ/ትዕዛዝ አስገዳጅነትና ተፈፃሚነት መርህንና የፍ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 5/1/ የሚጥስ ስለመሆኑ	221679	አቶ አብዱሰላም ፋራህ እና አቶ አደም ኡመር	ጥቅምት 1 ቀን 2015 ዓ/ም	35
9.	በክርክር ሂደት ክርክሩ ተጠቃሎ ከመወሰኑ በፊት በግልጽ በከፊል የተወሰነ ካለና ከቀጠለው ክርክር ጋር ተያያዥነት የሌለው እስከሆነ ድረስ መብትን ለማስከበር በጉዳዩ ላይ ይግባኝ ማቅረብ የፈለገ ተከራካሪን የሚከለክል የሥነ-ሥርዓት ሕግ ድንጋጌ የሌለ ሲሆን በሌላ በኩል ተከራካሪው ክርክሩን አጠቃሎ ይግባኝ ወይም የሠበር አቤቱታ ከማቅረብም ግን ሊከለከል የማይገባ ስለመሆኑ የፍብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 234(1(ረ)	185154	ወ/ሮ አበባየሁ ብርሌ እና እነ አቶ ሙሉዓለም ፈንታ (2 ሰዎች)	ግንቦት 27 ቀን 2013 ዓ/ም	40

ተ.ቁ	የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ	ተከራካሪ ወገኖች	ውሣኔው የተሰጠበት ቀን	ገጽ
10.	አንድ ጉዳይ ስልጣን ባለው ፍርድ ቤት ታይቶ ውሳኔ ያገኘ መሆኑ ከተረጋገጠ አዲስ የቀረበውን ክስ በድጋሚ አይቶ ውሳኔ መስጠት የሥነ ሥርዓት ሕግን አይነተኛ ዓላማ የማያሳካ እና በተመሳሳይ ጉዳይ ላይ የተጣረሰ ውሳኔ ሊሰጥ የሚችልበትን ዕድል የሚፈጥር በመሆኑ ፍርድ ቤቶች ሕጉን በጥብቅ ሊተገብሩት የሚገባ ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 5 ንዑስ ቁጥር (1)	242542	እነ ወ/ሮ ሳፊያ በከር (2 ሰዎች) እና አቶ አብዲ መሐመድ	ጥቅምት 26 ቀን 2016 ዓ.ም	43
11.	✍ ፍርድ ቤቶች በተከራካሪዎች የሚቀርቡ ክርክሮችን ለጉዳዩ ተገቢነት ባለው ማስረጃ ማጣራት ያለባቸው ስለመሆኑ የፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 136፣ 145፣ 257-259 እና ሌሎች የስነ ስርዓት ሕግ ድንጋጌዎች ✍ ተቀናሽ እንዲደረግ ወይም እንዲቻቻል የሚጠየቅ ገንዘብ መቅረብ ያለበት ለመጀመሪያ ክስ መልስ በሚሰጥበት የመጀመሪያ ጊዜ መሆን ያለበት ሲሆን አንደኛው ከሳሽ ተከሳሽ ሌላኛው የተከሳሽ ከሳሽ ሆኖ እንደቀረበ የሚቆጠርና ፍ/ቤትም በዋናው ክስ እና በመቻቻል ጥያቄው ውሳኔ እንደሚሰጥ የተመላከተ በመሆኑ ከዚህ አንፃር የመቻቻል ጥያቄው የተከሳሽ ከሳሽነት ክስ በሚመራበት አግባብ ሊቀርብ የሚገባ ስለመሆኑ የፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 236 እና ተከታዮቹ ድንጋጌዎች	198033	የሺ ኃ/የተ/የግ/ማህበር እና የኢትዮጵያ መኪና መገጣጠሚ ኩባንያ (አምቹ)	ጥቅምት 5 ቀን 2014 ዓ/ም	47

ተ.ቁ	የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ	ተከራካሪ ወገኖች	ውሣኔው የተሰጠበት ቀን	ገጽ
12.	✍ የግራ ቀኙ ተከራካሪ ወገኖች ለክርክር ይጠቅመናል በማለት በከሳሽነት ወይም በተከሳሽነት ጊዜ የሚያቀርቡትን ማስረጃ አሟጦ የማሰማት መብት በህገ መንግስቱ አንቀፅ 20(4) በተደነገገው መሰረት ተከሳሽ ለክሱ መልስ በሰጠበት ወቅት በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ አንቀፅ 234(1)(መ) መሰረት ከመከላከያ መልሱ ጋር የሰው ማስረጃ ዝርዝር አያይዘው ያቀረቡ ስለመሆናቸው ከሳሽ ካቀረቡት መልስ ጋር ተያይዞ የማስረጃ ዝርዝር አብሮ የቀረበ መሆኑ አከራካሪ ባልሆነበት ፍርድ ቤት የተከሳሽ ማስረጃን ያልሰማበትን ምክንያት ካለ በመዝገብ ውስጥ በግልፅ ሳይጠቅስ ተከሳሽ በተቃራኒ ማስረጃ አላስረዱም በማለት የሚሰጥ ውሳኔ ማስረጃ የማሰማት ህገ መንግስታዊ መብትን የሚጥስ ስለመሆኑ ✍ ተከሳሽ የሰነድ ማስረጃ ከመንግስታዊ ተቋም በፍርድ ቤት በኩል እንዲቀርብ አመልክቶ/ታ እንዲቀርብ የተጠየቀው የሰነድ ማስረጃ እና መከላከያ መልሶች ጋር ተያይዘው የቀረቡ የሰው ምስክሮች ቃል ሳይሰማ ተከሳሽ በማስረጃ አላስረዱም በማለት የሰው ማስረጃም ሆነ በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ አንቀፅ 145 መሰረት በፍርድ ቤት በኩል እንዲቀርብ የተጠየቀው ማስረጃ ሳይቀርብ እና ሳይሰማ የሚሰጥ ውሳኔ ተገቢነት የሌለው ስለመሆኑ	237965	ም/ኢንስፔክተር በሱፍቃድ እስጢፋኖስ እና ወ/ሮ ትዕግስት እስጢፋኖስ	26/07/2016 ዓ.ም	55

ተ.ቁ	የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ	ተከራካሪ ወገኖች	ውሣኔው የተሰጠበት ቀን	ገጽ
13.	በመደበኛ ፍርድ ቤት ከሚሰጥ ውሳኔ በተለየ ሁኔታ በግልግል ዳኝነት በተሰጠ ውሳኔ ላይ ይግባኝ የሚቀርበዉ በዘፈቀደ ሳይሆን በተወሰኑ ሁኔታዎች ላይ ብቻ ስለመሆኑ የፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ህግ አንቀጽ 351	232079	ሕብረት ኢንሹራንስ አ/ማህበር እና አቶ አብነት ሉሉ	መጋቢት 25 ቀን 2016 ዓ.ም	58
14.	ለይግባኝ ክርክር አመራር በፍትሐ ብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 337 እና 338/1 መሰረት የይግባኝ ማመልከቻዉንና የመጀመሪያዉ ደረጃ ፍርድ ቤት ፍርድ የሰጠበትን መዝገብ ግልባጭ በመመርምርና ይግባኝ ባይን በመስማት መልስ ሰጭ ቀርቦ እንዲከራከር ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት ትእዛዝ ከሰጠ የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ እንዲሁም ሕግን መርምሮ እንደነገሩ ሁኔታ በፍ/ብ/ስ/ስ/ሕግ ቁጥር 341፣343/1 እና 348/1 መሰረት ዉሳኔ ሊሰጥ ይገባል እንጂ ወደኋላ ተመልሶ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 337ን በመጥቀስ የይግባኝ ማመልከቻዉን በመሰረዝ መወሰን የሚችልበት ሥነ ሥርዓት አግባብ የሌለ ስለመሆኑ	202581	ወ/ሮ ረሂማ አብዱላሂ እና እነ ከዲር ዮሱፍ በከር (2 ሰዎች)	26/02/2014 ዓ.ም	64
15.	ፍርድ ቤት ማስረጃ ተቀብሎ ከመመርመሩ ወይም ምስክሮች ከመስማቱ አስቀድሞ በመጀመሪያ ደረጃ ለቀረበለት እና ማናቸውም ተከራካሪ ወገን ላቀረበው መቃወሚያ ውሳኔ መስጠት ያለበት፤ የነገርን ጭብጥ መያዝ የሚቻለውም የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ እንዳለ ከተወሰነ በኋላ ስለመሆኑ	222041	አማን ባርጌቾ እና ነጃት ባርጌቾ	ጥቅምት 04 ቀን 2015 ዓ.ም	69

ተ.ቁ	የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ	ተከራካሪ ወገኖች	ውሣኔው የተሰጠበት ቀን	ገጽ
	የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 244/1 እና 246/1				
16.	በፍርድ ቤት ትዕዛዝ የክርክር ተካፋይ የሚሆኑ ሰዎች ለክርክሩ የግድ አስፈላጊ የሆኑ (indispensable party) ባልተሳተፉበት ክርክር መብት እና ጥቅማቸው ወይንም ግዴታቸውን የሚነካ ተካፋይ ባልሆኑበት ክርክር የሚሰጠው ፍርድ ወይንም ውሳኔ ውጤት የማይኖረው ሰዎች ሲሆኑ እና በክስ በተከሳሽነት ተካፋይ መሆን የሚገባውን ከሳሽ ያላጣመረው ቢሆንም ለቀረበዉ ክስ የመከላከያ መልስ እንዲሰጥበት በፍርድ ቤት ሊታዘዝ የሚገባ ስለመሆኑ የፍትሐ ብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 39(1) እና 40(2)	246384	አቶ ተባረክ ዘሩ እና ወ/ሮ ጨዋነሽ በርቱ	መጋቢት 25 ቀን 2016 ዓ.ም	73
17.	በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 320/1 መሰረት ይግባኝ ወይም የሰበር አቤቱታ ማቅረብ የሚቻለዉ በመጨረሻዉ ዉሳኔ ላይ ሲሆን አንድ ዉሳኔ የመጨረሻ ዉሳኔ ነዉ የሚባለዉ ደግሞ በዚሁ ሕግ በቁጥር 320(3 እና 4) ጣምራ ንባብ መሰረት ማንም ሰዉ እንዲታሰር ወይም በማረፊያ ቤት ተይዞ እንዲቆይ የተሰጠ ትእዛዝ ካልሆነ በስተቀር እንዲሁም ከሥረ ነገሩ ፍርድ በፊት አንድ ተከራካሪ ወገን በእጁ ያለዉን ንብረት ለሌላዉ ወገን እንዲያዛዉር የተሰጠ ዉሳኔ ካልሆነ በስተቀር በሥረ ነገሩ ላይ የመጨረሻ ፍርድ ከመሰጠቱ በፊት ጊዜያዊ አገልግሎት ባለዉ ትዕዛዝ ላይም ሆነ በሥረ ነገሩ ላይ የመጨረሻ ፍርድ ከመሰጠቱ በፊት በመጀመሪያ ደረጃ	249817	ወ/ሮ ላዋይ መሃሪ እና አቶ ባወቀ አምባዉ	መጋቢት 25 ቀን 2016 ዓ/ም	79

ተ.ቁ	የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ	ተከራካሪ ወገኖች	ውሣኔው የተሰጠበት ቀን	ገጽ
	መቃወሚያነት በሚቀርብ መከራከሪያ ላይ በሚሰጥ ዉሳኔ ላይ ብቻ ይግባኝ ማቅረብ የማይቻል ስለመሆኑ				
18.	ህጋዊ ሰውነት ያለው አካል ሕጋዊ ተግባራትን የሚያከናውነው ህጋዊ ውክልና ባለው የተፈጥሮ ሰው መሆኑና ተወካይ ወኪል በመሆኑ ብቻ ወካይን በመወከል ባከናወነው ሕጋዊ ተግባርና ወካዩ በሚከሰስበት ጉዳይ ተወካይ በግል የሚከሰስበት ህጋዊ ምክንያት የሌለ በመሆኑ ከወካይ ጋር በአንድነት ሲከሰስ ልከሰስ አይገባም የሚል መቃወሚያ ሲያቀርብ ሊከሰስ አይገባም በሚል ከክርክሩ ውጪ ማድረግ የሚገባ ስለመሆኑ የፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 33/3 እና የፍ/ሕ/ቁጥር 2199	225462	የክርስቶስ አካል ቤተክርስቲያን (2 ሰዎች) እና ወ/ሮ አልማዝ ባዩ	ጥቅምት 29 ቀን 2015 ዓ/ም	82
ውል					**88**
19.	በውል ላይ ከተመለከተዉ ውጪ በሆነ ሌላ ዕቃ የውሉ ስራ የተከናወነ መሆኑ ተጠቅሶ የተሰራለት ተዋዋይ ወገን ይህንን እንዲያዉቅ በዕቅድ ተካቶ ከተላከለት በኋላ መልስ አለመስጠቱ የተሻሻለዉን ዉል እንደተቀበለዉ የሚያስቆጠር ሳይሆን፣ የስራ ዕቅድ ዉሉን መሠረት በማድረግ አፈፃፀሙን አስመልክቶ ስራዉን በሚሰራዉ አካል የሚዘጋጅ የድርጊት መርሃ ግብር እንጂ በፍትሐብሔር ህግ አንቀጽ 1684(2) ላይ በተመለከተዉ አግባብ እንደ የዉል ማሻሻያ ሃሳብ (offer for amendment of contract) የማይወሰድ ስለመሆኑ	217867	ኤቦካ ኮንስትራክሽን ኃ/የተ/የግ/ማህበር እና በአ/አበባ ከተማ አስተዳደር የቁጠባ ቤቶች ልማት ኢንተርፕራይዝ	ጥቅምት 04 ቀን 2015 ዓ.ም	89

ተ.ቁ	የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ	ተከራካሪ ወገኖች	ውሣኔው የተሰጠበት ቀን	ገጽ
20.	✍ የቤት ሽያጭ ውል የተደረገውና ግዥዮም የተፈፀመው ቤቱ ግማሽ የውርስ ድርሻ በሆነና ውል ሰጪ/ሻጭ በሙሉ ንብረቱ ላይ ውሉን ለመፈፀም መብት የሌላቸው፣ ግማሽ ድርሻ ላይ ወራሾችም ሳይፈቅዱና ሳይስማሙ በሽያጭ ውሉ ባለመሳተፋቸው ከትክክለኛው ባለመብት ያልተገዛና ውሉም በማይንቀሳቀስ ሀብት ምዘገባ ክፍል የተመዘገበ ካልሆነ የተደረገው የሽያጭ ውል ተገቢውን ሕግና አሠራር ተከትሎ የተፈጸመ ባለመሆኑ ውሉ ፈራሽ ስለመሆኑ የፍ/ሕ/ቁ. 1678፣ 1808 እንዲሁም 2878 ✍ ወራሾችም የሽያጭ ሂደቱን በጊዜው ያውቁ ነበር በሚል የሚቀርብ ክርክር ቤት ገዥው ግዥ ሲፈጽሙ ከሻጭ ውጪ ሌሎች ወራሾች እንዳሉ እያወቁ አንድ ጠንቃቃ ገዥ በሕግ ሆነ በአሠራር ሊያደርገው የሚገባውን ተገቢውን ጥንቃቄ የማድረግ ኃላፊነት ሳይወጡ ቤቱን የገዙ መሆኑን የሚያስገነዝብ ስለመሆኑ	195919	እነ ወ/ሮ ጌጤ ዶሪ (4 ሰዎች) እና እነ አቶ ዶሪ ሻሎ (2 ሰዎች)	ጥቅምት 01 ቀን 2014 ዓ/ም	95
21.	✍ ሻጭ የቤት ሽያጭ ውል ከማድረጉ በፊት የቤቱ ባለቤትነት ላይ ሰነዱንና ቤቱን እንዲያስረክብ ክስ ተመስርቶ ቤቱ ላይ እግድ ከመሰጠቱ በፊት ተከሳሽ/ሻጭ ቤቱን በሽያጭ ውል ለ3ኛ ወገን አስተላልፎ ይህ ገዥዮም በክርክሩ ሳይሳተፍ ሻጭ በክርክሩ ተረትቶ ቤቱን ለከሳሽ እንዲያስረክብ ውሳኔ የተሰጠ ቢሆንም የቤት ሽያጭ ውሉ ሲፈፀም ገዥው አንድ ጠንቃቃ ገዥ	196963	አቶ ደሣለኝ ሲሳይ እና እነ ወ/ሮ ድማም ተክሉ (2 ሰዎች)	04/02/2014 ዓ.ም	99

ተ.ቁ	የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ	ተከራካሪ ወገኖች	ውሣኔው የተሰጠበት ቀን	ገጽ
	በሕግ ሆነ በአሠራር ሊያደርገው የሚገባውን ጥንቃቄ የማድረግ ኃላፊነት በመወጣት፣ ውሉም የተፈጸመው ሻጭ ቤቱን ገዝቶ ሕጋዊ ሠነድ በቤቱ ላይ ካወጣበት በኋላ ሕጋዊ ባለቤት እንዳለው በማረጋገጥ በውል አዋዋይ ፊት የተደረገ ከሆነ ግብይቱ ሕግን መሠረት ያደረገ በመሆኑ የሕግ ጥበቃ ሊደረግለት የሚገባ ስለመሆኑ የፍ/ሕ/ቁ. 1723(1) ገዥ ውሉን የማይንቀሳቀስ ሀብት መዝገብ ላይ እንዲጸፍ በማድረግ ካርታ ያወጣበት ከሆነ ውሉ ሦስተኛ ወገኖችን ላይም ውጤት ያለው ስለመሆኑ የፍ/ሕ/ቁ. 2878 ንብረት በሻጭ ስም ከመመዝገቡ እና ወደ ገዥ በሽያጭ ውል በሠነድ ከመዛወሩ በፊት መብቱ የማን ነው የሚለውን ሻጭ የማጣራት ኃላፊነት በሕግ የሌለበትና ንብረቱ ላይ በፍርድ ቤት እግድ ከመሰጠቱ በፊት የተዛወረ ከሆነ ከሳሽ ክስ ካቀረበ በኋላ ሽያጭ ውሉ መደረጉ ሆነ የተሸጠበት ዋጋ የተደረገውን ግብይት ቀሪና ውጤት አልባ የማያደርገው ስለመሆኑ				

ተ.ቁ	የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ	ተከራካሪ ወገኖች	ውሣኔው የተሰጠበት ቀን	ገጽ
	፞ ገዥ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 41 መሠረት ጣልቃ ገብተው ክርክር ያስነሳውን ቤት፣ ሻጭ በስማቸው ካርታ አውጥተው የያዙትን፣ ሥልጣን ባለው አካል የተመዘገበና ስመ-ሀብቱ ተላልፎ የባለቤትነት ማረጋገጫ ያወጣሁበት ነው በማለት ጣልቃ ገብ ከሆኑ፣ ምንም እንኳን ከሳሽ በንብረቱ ላይ መብት ያላቸው ስለመሆኑ በፍርድ የተረጋገጠላቸው ቢሆንም፣ ይህ መብታቸው ከመረጋገጡ በፊት ተከሳሽ/ሻጭ በስማቸው የነበረውን ንብረት ለሦስተኛ ወገን ለሆኑት ገዥ ያስተላለፉ በመሆኑ፤ ከሦስተኛ ወገን መብት አኳያ ንብረቱን ከሳሽ ሊረከቡ የማይችልና ክርክር ያስነሳው ንብረት ሕጋዊ ባለመብት ገዥ በመሆናቸው ከሻስ ንብረት ለመረከብ ያቀረቡት ክስ ውድቅ ሊደረግ የሚገባ ስለመሆኑ				
22.	፞ ገዢ የገዛው እቃ ላይ ጉድለት ያለበት ከሆነ ጉድለቱን ለሻጩ ባሳወቀ በአንድ አመት ውስጥ ጉድለቱ እንዲስተካከልለት ክስ ካላቀረበ ክሱ በይርጋ እንደሚታገድ የተደነገገ ቢሆንም ሻጩ እቃውን ወይም የሚሸጠውን ነገር ለገዢ በሚሸጥበት ወይም በሚያስረክብበት ወቅት እቃው ጉድለት ያለበት መሆኑን እያወቀ ጉድለት እንደሌለ አድርጎ ወይም ጉድለቱ እንዳይታወቅ አድርጎ በማጭበርበር ለገዢ መሸጡ ወይም ማስረከቡ ከተረጋገጠ ክስ የማቅረቢያ ጊዜው በአንድ አመት ይርጋ የማይገደብ ሲሆን በተቃራኒው ሻጩ በሽያጭ ወይም በርክክብ ወቅት የፈጸመው የማጭበርበር ድርጊት	197008	አዲት ሰርቪስ ኮርፖሬሽን እና ፀጋ ረታ አስመጪ ኃላ/የተ/የግ/ማህበር	05/02/2014 ዓ.ም	104

ተ.ቁ	የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ	ተከራካሪ ወገኖች	ውሣኔው የተሰጠበት ቀን	ገጽ
	ከሌለ ጉድለቱን ገዢው ለሻጭ ባሳወቀ በአንድ አመት ውስጥ ክስ ካላቀረበ ክሱ በይርጋ የሚታገድ ስለመሆኑ የፍ/ሕ/ቁጥር 2298(1) ☞ የፍታብሄር ሕግ ቁጥር 2298 ድንጋጌ አላማ ሻጩ በፈጸመው የማጭበርበር ተግባር የወንጀል ድርጊት በመሆኑ በአንድ አመት ውስጥ ክስ አልቀረበም በሚል በወንጀል ድርጊቱ ተጠቃሚ እንዳይሆን ለመከላከል ሲሆን ይህ ማለት ግን የማጭበርበር ድርጊት ከተፈጸመ ምንም አይነት የክስ ማቅረቢያ የጊዜ ገደብ አይኖረውም ማለት ሳይሆን የማጭበርበር ድርጊቱ እንደ ይርጋ ማቋረጫ ጊዜ ተወስዶ የአንድ አመቱ የይርጋ ጊዜ የማጭበርበር ድርጊቱ ከተፈጸመ ጊዜ ጀምሮ እንደ አዲስ መቁጠር የሚጀምር ስለመሆኑ ☞ የሻጭ አጭበርባሪነት የሚለው አገላለጽ ምን አይነት እና መቼ የሚፈጸም የሻጩን ድርጊት የሚያመለክት ነው የሚለው በተመለከተ በፍ/ህ/ቁጥር 2297 ሻጩ የሸጠውን ነገር ጉድለቶች ያሉበት መሆኑን ገዢው እንዳያውቃቸው በተንኮል ደብቋቸው ከሆነ ሻጩን ከሀላፊነት የሚያድኑ የውል ቃሎች ቢኖሩ ሻጩ ከተጠያቂነት ማምለጥ እንደማይችል የሚያመለክትና ይህም ማለት ሻጩ ለገዢ በሸጣቸው ነገሮች ላይ ጉድለት መኖሩን እያወቀ በተንኮል በሸያጭ ወቅት ምንም አይነት ጉድለት እንደሌለባቸው አስመስሎ ከሸጠ ወይም ከሸያጭ በኋላም ቢሆን ጉድለቱ				

ተ.ቁ	የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ	ተከራካሪ ወገኖች	ውሣኔው የተሰጠበት ቀን	ገጽ
	እንዳይታወቅ ለማድረግ ሻጩ የማጭበርበር ድርጊት የፈጸመ በመሆኑ ተጠያቂ የማያደርገው የውል ቃል እንኳን ቢኖር ውሉ ተፈጻሚ የማይሆን እና ሻጩ በኃላፊነት እንደሚጠየቅ የሚያመለክት ስለመሆኑ የፍ/ሕ/ቁጥር 2297 እና የፍ/ህ/ቁጥር 2298/1				
23.	የቤት ሽያጭ ውል ከተደረገ በኋላ እንደ ውሉ ባለመፈጸሙ ሻጭ በውሉ መሠረት ቤቱን እና የቤቱን ሠነዶች ሆነ ሌላ አስፈላጊ ተግባር እንዲፈጽሙ ክስ ከቀረበ ውሉ የፍ/ሕ/ቁ. 1723 በሚያዘው አግባብ በውል አዋዋይ ፊት ያልተደረገ ቢሆንም ሻጭ ውል መኖሩን ያመነ ከሆነ በሻጭ እና በገዥ መካከል ሕጋዊ የሆነ የፀና ውል አለ ማለት የሚቻል ሲሆን የፀና ውል ካለ ደግሞ ሻጭ በውል የገባውን ግዴታ፤ በፍ/ሕ/ቁ. 1731(1) እንደተደነገገው ውል በተዋዋዮች መካከል እንደ ሕግ የሚቆጠር ስለሆነ እና ውል እንዲፈጸም የተጠየቀው የማይንቀሳቀስ ንብረት ላይ በመሆኑ ገዥ ልዩ ፍላጎት ንብረቱ ላይ እንዳለው ግምት ስለሚወሰድ፤ ሻጭ የመፈጸም ግዴታ ያለበት ስለመሆኑ	171678	ኒው ክሬሽን ኢንተርናሽናል ቤተክርስቲያን እና ጭላሎ ኢንተርፕራይዝ ኃ/የተ/የግል ማህበር	ታህሳስ 22 ቀን 2012 ዓ/ም	109

ተ.ቁ	የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ	ተከራካሪ ወገኖች	ውሣኔው የተሰጠበት ቀን	ገጽ
24.	✍ የውል ስምምነት ሰነድ ርዕሱ የመኖሪያ ቤት ቀብድ ውል ስምምነት የሚል ሆኖ ይዘቱም ተዋዋይ ወገኖች ውሉን በውል እና ማስረጃ ፅ/ቤት ለወደፊት ቀርበው ሲዋዋሉ ሻጭ ቀሪውን ገንዘብ በመቀበል ቤትና ይዞታውን ለገዢ ለማስረከብ መስማማታቸውን እንጂ ከፍ ሲል በተጠቀሰዉ ውል በሰፈረው ሃሳብ መሰረት ተዋዋይ ወገኖች ውልና ማስረጃ ቀርበው የተደረገ የቤት ሽያጭ ውል ስምምነት አመለኖሩንና እንዲሁም ተደርጓል የተባለው የመኖሪያ ቤት ቀብድ ውል ስምምነትም ቢሆን የሻጭ ባልሆነና ከካርታ ውጪ ያለ የመንግስት ይዞታ ጭምር ላይ የተደረገ ከሆነ ከአመሰራረት ጋር በተያያዘ ተደራራቢ የህግ ክፍተት ያለበትና በጥቅሉ የህጉን መሰፈርት በጠበቀ እና በተሟላ መልኩ የተቋቋመ ባለመሆኑ የህግ ጥበቃ የማይደረግለት ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ.1723(1)፣1678(ለ)፣1715(1)፣2266፣2879 እና ሌሎችም ✍ በቅድሚያ በተዋዋይ ወገኖች መካከል በህግ አግባብ የተቋቋመ ውል ኖሮ ነገር ግን ሻጩ ወይም ቀብዱን የተቀበለው ወገን ይህ በመካከላቸዉ በህጉ አግባብ የተቋቋመዉን እና የፀናውን ውል በራሱ ፍቃድ ማፍረስ ከፈለገ የተቀበለውን ቀብድ አጠፌታ ለሌላኛው ወገን መልሶ በመክፈል ውሉን በነፃነት ማፍረስ የሚችል ሲሆን ነገር ግን በግራ ቀኙ መካከል በሃሳብ ደረጃ	227366	አቶ ሰለሞን ደቻሳ እና አቶ አየለ አበቴ	29/09/2015 ዓ.ም	114

ተ.ቁ	የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ	ተከራካሪ ወገኖች	ውሣኔው የተሰጠበት ቀን	ገጽ
	እና ጅማሮ የቀረ ረቂቅ እንጂ በህጉ አግባብ የተደረገ ቤት ሽያጭ ውል በሌለበት ሁኔታ በፍ/ብ/ህ/ቁ.1815 (1) ስር እንደተመለከተው ተዋዋይ ወገኖች ውለታው ከመደረጉ በፊት እንደነበሩበት ሁኔታ እንዲመለሱ በማደረግ ሻጭ የተቀበለውን ገንዘብ ብቻ ለገዢ እንዲመልስ ይደረጋል እንጂ ረቂቅ ውሉን መሰረት በማድረግ የተቀበለውን ገንዘብ አጠፊታ ሊከፍል የሚገደድበት የህግ አግባብ የሌለ ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ.1883 እንዲሁም 1885(2)				
	ንብረት				120
25.	ከጋራ ሀብት የተገኘ የኪራይ ገንዘብ ያካፍለኝ ክስ በፍ/ሕ/ቁ. 1170(2) እንደተመለከተው የንብረት ፍሬ ማለት ሀብቱ በየጊዜው የሚሰጠው አበልና ነገሩም እንደተመደበበት ጉዳይ ከዚህ ላይ ለመውሰድ ልማድ በሚፈቅደው መሠረት የሚገኝ ሁሉ ሲሆን የጋራ የማይንቀሳቀስ ንብረት ተከራይቶ የሚገኘው ገቢ በድንጋጌው ማዕቀፍ ውስጥ የሚወድቅ፣ በፍ/ሕ/ቁ. 1264(1) መሠረት ካልተከፋፈለው የጋራ ንብረት ላይ የሚገኘው ፍሬ፣ ጥቅም ያልተከፋፈለ እንደሆነና በንዑስ ቁጥር ሁለት ላይ እንደተደነገገው እያንዳንዱ የጋራ ባለሀብት በማንኛውም ጊዜ ክፍያ እንዲደረግ መጠየቅ የሚችልና የጋራ ሀብት ላይ የሚገኝ ፍሬ ከጋራ ባለሀብቱ አንዱ ወገን ክፍያ እንዲደረግ	197753	አቶ ሙሉጌታ ሩጋ እና ወ/ሮ ፍሬሕይወት ተፈራ	የካቲት 24 ቀን 2014 ዓ/ም	121

ተ.ቁ	የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ	ተከራካሪ ወገኖች	ውሣኔው የተሰጠበት ቀን	ገጽ
	ሲጠይቅ የሚከፋፈል በመሆኑ ክሱ በይርጋ ሊታገድ የማይገባ ስለመሆኑ				
26.	የሀብት ይወገድልኝ ክስ የሚያቀርብ ሰው ማረጋገጥ የሚጠበቅበት ዋና ዋና ፍሬ ነገሮች ሀብት ተፈጠረበት የተባለውን ንብረት/ሀብት/ ባልተጭበረበረ መንገድ በእጁ አድርጎ በእውነት የሚያገበት መሆኑን እና በዚሁ ይዞታው ላይ በተከሰሰው ሰው/አካል ህገ ወጥ በሆነ መንገድ ሀብት የተፈጠረበት መሆኑን በአንፃሩ የባለሃብትነት መብት የማይንቀሳቀስ ንብረት ባለሃብት የሆነ ሰው ከንብረቱ ላይ መብት ሳይኖረው ከህግ አግባብ ውጭ ንብረቱን በእጁ ባደረገው ሰው ወይም ንብረቱን በያዘው አካል ላይ ክስ በማቅረብ የሚያስመልስበት ህጋዊ መብት (Right to bring Petutary Action) ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ/1140፣ 1146 እና 1149 ድንጋጌዎች ጣምራ ንባብ እና የፍ/ብ/ህ/ቁ/1206	220031	አቶ ሸፋ ኢብራሂም እና በሻዱ ቱፋ ዋንታሎ	ጥቅምት 03 ቀን 2015 ዓ/ም	126
27.	✍ ምንም እንኳን የገጠር መሬት ሽያጭ ውል ሲደረግ መሬቱ የገጠር የነበረ ቢሆንም ክሱ በቀረበበት ጊዜ ይዞታው ለከተማ አገልግሎት የዋለ መሆኑን ከክርክሩ መረዳት ከተቻለ የቀረበው ክስም የከተማ ይዞታዬ ይለቀቅልኝ የሚል ከሆነ መሬቱ በከተማ አስተዳደር ሥር ከገባበት ጊዜ ጀምሮ መሬቱ የከተማ እንጂ የገጠር ባለመሆኑ ክርክሩ በገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ሕግ ሊታይ የሚችልበት አግባብ የሌለ ስለመሆኑ	220882	ወ/ሮ እሌኒ መኮንን እና አቶ ጢቆ ደግፌ	ጥር 30 ቀን 2015 ዓ.ም	132

ተ.ቁ	የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ	ተከራካሪ ወገኖች	ውሣኔው የተሰጠበት ቀን	ገጽ
	✍ መሬት በገጠር አስተዳደር ክልል ሥር እያለ የተደረገ የውል ሕጋዊነት መታየት ያለበት ክርክሩ በተነሳበት ጊዜ መሬቱ በሚተዳደርበት ሕግ መሰረት ስለመሆኑ ✍የከተማ መሬት መሠረቱ የገጠር መሬት ቢሆንም፤ ጉዳዩ መታየት ያለበት ክሱ በቀረበ ጊዜ በሥራ ላይ ያለው የከተማ መሬትን ለማስተዳደር የወጣው ሕግ ወይስ ውሉ በተፈፀመ ጊዜ የነበረው የገጠር መሬት አስተዳደር እና አጠቃቀም ህግ ? የሚል ሆኖ መሬት በከተማ አስተዳደር ሥር ከገባ በኋላ ለቀረበ ክስ መሬቱ በገጠር ቀበሌ ሥር በሚገኝበት ጊዜ የተደረገውን የገጠር ቤት ሽያጭ ውል መሠረት በማድረግ የሻጭ ባለሀብትነት በፍትሐ ብሔር ሕግ ቁጥር 1189 መሠረት ቀሪ ሆኖ ፤ በፍትሐ ብሔር ሕግ ቁጥር 1184, 1189, 2875 እና ተከታይ ድንጋጌዎች መሠረት በግዥ የተላለፈ ለክርክር መነሻ የሆነ ቤት እና ይዞታ እንዲለቀቅ የሚሰጥ ውሳኔ በኢ.ፌዲ.ሪ ሕገ መንግስት አንቀጽ 40(1) እና የፍትሐ ብሔር ህግ ቁጥር 1204 እና 1205 መሠረታዊ ንብረት የማፍራት መብት የሚገድብ ስለመሆኑ				
28.	አንድ ባለንብረት ንብረቱን የመገልገል መብቱ የሌላኛዉን ወገን ጥቅም እንዳይነዳ በህግ የተጣለ ወሰን ያለበት በመሆኑ በራስ ይዞታ የተተከለ ዛፍ በስሩ እና በቅርንጫፍ ወደ ሌላ ሰው ይዞታ አልፎ በንብረት ላይ ጉዳት ቢያደርስ ምንም እንኳን በመካከል መንገድ መኖሩ ቢገለጽም ዛፎቹ	154712	አቶ ረጋሳ መልካሙ እና እነ ካየሶ ክርባ (2 ሰዎች)	ህዳር 28 ቀን 2011 ዓ.ም	140

ተ.ቁ	የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ	ተከራካሪ ወገኖች	ውሣኔው የተሰጠበት ቀን	ገጽ
	በቅርንጫፎቻቸዉና በስሮቻቸዉ በጎረቤት ንብረት ላይ ጉዳት ስለማድረሳቸዉ በባለሙያ ታይቶ የተረጋገጠ እዉነታ ከሆነ ተጎጂ ወገን አንድም በራሱ ጉዳቱን የማስወገድ አሊያም በፍርድ ሃይል ጉዳቱ እንዲወገድ ዳኝነት የመጠየቅ መብት በሕግ የተጠበቀ ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህግ አንቀጽ 1212				
	ውርስ				**143**
29.	✍ የውርስ ሀብት በሆነ ይዞታ ላይ በአንደኛው ወራሽ በራስ ወጪና ሌሎች ወራሾች ሳይቃወሙ ቤት ከተሰራ ቤቱን የሰራው እና ሌሎች ወራሾች በተሰራው ቤት ላይ ስላላቸው መብት አድማስ በሚመለከት የውርስ ሀብት አከፋፈል እስከሚፈፀም ድረስ በወራሾች መካከል ውርሱ ሳይነጣጠል የሚቆይ እና ወራሾቹ በዚህ ባልተከፋፈለ የውርስ ሀብት ላይ ያላቸው መብት በፍትሐ ብሔር ህግ ስለ የጋራ ባለሃብትነት በሚመለከተው የህግ ድንጋጌዎች የሚወሰን ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ/1060(1) እና (2) ✍ የወራሾች የጋራ በሆነ ይዞታ ላይ በአንደኛው ወራሽ የተሰራው ቤት በራስ ወጪ የተሰራ ለመሆኑ ከተረጋገጠ አውራሻቸው በህይወት ኖሩም አልኖሩም በይዞታው ላይ ቤቱን ሲሰሩ ከአውራሻቸውም ሆነ ከሌሎች ወራሾች ቤቱ እንዳይሰራ የቀረበ ተቃውሞ የነበረ ለመሆኑ የቀረበ	178714	ወ/ሮ ፋጡማ አልቃድር እና እነ ወ/ሮ ፋጡማ ሲራጅ (4 ሰዎች)	ሚያዝያ 28/2012 ዓ.ም	144

ተ.ቁ	የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ	ተከራካሪ ወገኖች	ውሣኔው የተሰጠበት ቀን	ገጽ
	ክርክርም ሆነ የተረጋገጠ ነገር ከሌለ ያለተቃውሞ የተሰራ ቤት ለመሆኑ ግምት የሚያስወስድ፣ ቤቱ የግል ሀብት የሚሆንና የቤቱ ግምት ተከፍሎ ከሌሎች ወራሾች ጋር እኩል የሚካፈሉበት የህግ አግባብ የሌለ ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ/ 1179(1)				
30.	➢ አንድ ተናዛዥ ልጁን ወይንም ወደ ታች የሚቆጠር ተወላጅን ያለ በቂ እና አሳማኝ ምክንያት ከውርስ ከነቀለ ኑዛዜው ፈራሽ ስለመሆኑ የፍትሐ ብሔር ሕግ ቁጥር 938(1) ➢ ኑዛዜ በሕግ የተመለከቱ ፎርማሊቲዎችንና ሁኔታዎችን አሟላቶ እስከተገኘ ድረስ የተናዛዡ ፍላጎት ማሳያ በመሆኑ ሊከበር ስለሚገባ ፈራሽ መሆን አለበት የሚል ተከራካሪ ወገን ሊፈረስ ይገባል የሚልበትን ምክንያት መግለጽ ያለበት ስለመሆኑ የፍትሐ ብሔር ሕግ ቁጥር 857(1) ፣ 892 ፣ 909 ፣ 949 ድንጋጌዎች ጣምራ ንባብ	245258	እነ ሳምራዊት አረጋ (2 ሰዎች) እና ደረሰ ታደሰ	መጋቢት 26 ቀን 2016 ዓ.ም	151
31.	አንድ ኑዛዜ አድራጊ ያለኑዛዜ ሊወርሱ የሚችሉ ተወላጆችን በኑዛዜ በግልጽ ምክንያት ጠቅሶ ከውርስ መንቀል እንደሚችል እና ምክንያቱ ከውርስ ለመንቀል የሚያበቃ መሆኑን ካልሆነ በስተቀር የምክንያቱን ትክክለኛነት መመርመር አስፈላጊ ስላለመሆኑ የፍ/ሕ/ቁጥር 937 እና 938	236850	እነ አቶ መስፍን ዱባለ ወልደየስ (3 ሰዎች) እና ወ/ሮ አልማዝ ዱባለ ወልደየስ	ግንቦት 29 ቀን 2015 ዓ/ም	157

ተ.ቁ	የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ	ተከራካሪ ወገኖች	ውሣኔው የተሰጠበት ቀን	ገጽ
32.	የሚች የውርስ ንብረት ወራሽ ባልሆኑ ሰዎች ሲያዝ ህጻናት የነበሩ የሚች ወራሾች በመብታቸው መስራት እና ንብረቱ እንዲለቀቅ ክስ ማቅረብ የሚችሉት እድሜያቸው 18 ዓመት ሲሞላ ሲሆን የውርስ ንብረቱ ሲያዝ አካለ መጠን ላልደረሱ የሚች ልጆችም ተፈጻሚነት ያለው የይርጋ ጊዜ 10 ዓመት ሲሆን ይህ የ10 ዓመት ጊዜ መቆጠር የሚጀምረው እድሜያቸው 18 ዓመት ከሞላ ጊዜ ጀምሮ ስለመሆኑ	239453	እነ አቶ መስፍን ባልቻ አሩሲ (7 ሰዎች) እና እነ አቶ ሙሉጌታ አለሙ (13 ሰዎች)	ሐምሌ 26 ቀን 2015 ዓ/ም	161
33.	✍ በውርስ አጣሪ ሪፖርት መሰረት የውርስ ሐብት የክፍፍል ውሳኔ እንዲሰጥ እንጂ ቀጥታ በውርስ አጣሪ ሪፖርት መሰረት የቀረበ የአፈጻጸም ጥያቄ በሌለበት የውርስ አጣሪ ሪፖርትን መሰረት አድርጎ አፈጻጸም እንደተጠየቀ በማድረግ አፈጻጸም ሊጠየቅ አይችልም በሚል የሚቀርብ ክርክር ተገቢነት የሌለው ስለመሆኑ ✍ በውርስ ማጣራት መዝገብ ላይ የቀረበ ክርክር በማስረጃ ተጣርቶ ተቀባይነት ሳያገኝ የቀረ ቢሆንም በውርስ ሀብት ክፍፍል ወቅት የተነሳው ክርክር አስቀድሞ ውርሱ ሲጣራ በጭብጥነት ተይዞ ውሳኔ ያገኘ ጉዳይ ከሆነ ክርክር የቀረበው የክፍፍል ክስ መልስ ሲሰጥ በመሆኑ ከውሳኔ በፊት ክሱን በብይን ውድቅ የሚደረግበት እድል ባይኖርም በውሳኔ ወቅት በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 5(1) መሠረት ጉዳዩ አስቀድሞ በፍርድ ያለቀ ነው ተብሎ	231538	እነ ወ/ሮ ተናኜ ታፈሰ ወርቅነህ (3 ሰዎች) እና አቶ ቴዎድሮስ ታዬ አበጋዝ (3 ሰዎች)	ሚያዝያ 25 ቀን 2015 ዓ/ም	165

ተ.ቁ	የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ	ተከራካሪ ወገኖች	ውሣኔው የተሰጠበት ቀን	ገጽ
	ክርክሩ ውድቅ የሚደረግ ስለመሆኑ				
34.	ሚች በኑዛዜ የሚያስተላልፈው ንብረት የራሱን ንብረት በመሆኑ ሚች ባደረገው ኑዛዜ በውርስ ያስተላለፈው በድርሻው ላይ ብቻ ሳይሆን የሌላ ሰውን ድርሻ ጨምሮ ከሆነ ኑዛዜው ሊፈርስ የሚገባው መሉ በመሉ ሳይሆን በሌላው ሰው ድርሻ ላይ የተደረገው የኑዛዜ ክፍል ብቻ እንጂ ኑዛዜው መሉ በመሉ እንዲፈርስ በሚል ውሳኔ የሚሰጥ ስላለመሆኑ የፍ/ብ/ሕ/ቁ 829 እና ተከታይ ድንጋጌዎች	243484	እነ ወ/ሮ ነጻነት ደምሴ (3 ሰዎች) እና ሲሳይ ታደሰ	መጋቢት 30 ቀን 2016 ዓ.ም	171
35.	✍ አንድ ሰው ኑዛዜ መነበቡን (መፍሰሱን) ያውቃል ለማለት በአካል ወይንም በተወካይ ኑዛዜው ሲነበብ ወይም ሲፈስ መገኘት አልያም ስለ ክፍያ፣ድልድል አመዳደብ ሃሳብ በአጣሪው የተነገረው እንደሆነ ስለመሆኑ የፍትሐ ብሔር ሕግ ቁጥር 973 እና 974(1) ✍ ኑዛዜ ሲነበብ(ሲፈስ) በአካል ያልነበሩ፣ ያልተወከሉ አልያም ስለ ክፍያ፣ ድልድል አመዳደብ ሃሳብ በውርስ አጣሪ ያልተነገራቸው ሰዎችን የሚመለከተው በፍትሐ ብሔር ሕግ ቁጥር 974(2) ሥር የተመለከተው ይርጋ ፍፁም(absolute) ይርጋ ስለመሆኑ	245055	ወ/ሮ ኤልሳቤጥ እሸቱ እና እነ ወ/ሮ ማህደር እሸቱ (2 ሰዎች)	መጋቢት 27 ቀን 2016 ዓ.ም	176

ተ.ቁ	የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ	ተከራካሪ ወገኖች	ውሣኔው የተሰጠበት ቀን	ገጽ
36.	፞ በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 839 እስከ 840 በተመለከቱት ድንጋጌዎች መሰረት አውራሽ ለውርስ አይገባም የተባለ ስለመሆኑ ወይም በዚሁ ሕግ በቁጥር 854 (1) ድንጋጌ መሰረት ውርሱን አልፈልግም ያለ ስለመሆኑ የቀረበ ተቃራኒ ክርክር ከሌለ ጉዳዩ ይመለከተኛል በሚል ሌላ ተከራካሪ ወገን የሚቀርብ ተቃራኒ ክርክር እና ማስረጃ ካለ የዚህ ዓይነቱ ክርክር እና ማስረጃ እስከሚቀርብበት ጊዜ ድረስ ለውርስ አይገባም ያልተባለ እና ውርሱን አልፈልግም ያላለ ስለመሆኑ ግምት የሚወሰድና በፍትሐ ብሔር ሕግ ቁጥር 830 ድንጋጌ ስር የተመለከቱትን መስፈርቶች የሚያሟላ በመሆኑ የመውረስ መብት ያለው ስለመሆኑ ፞ አንድ ተተኪ ወራሽ የመውረስ መብት የማይኖረው አውራሹ የሆነ ሰው በሕይወት እያለ የመውረስ መብቱን ተግባራዊ በማድረግ ውርሱን ተካፍሎ ሲገኝ ስለመሆኑ ፞ ለአንድ ውርስ ወራሽ የሆነ ሰው ውርሱ ከተከፈተ በኋላ የሞተ እንደሆነ የወራሽነቱ መብቶች ለእርሱ ወራሾች የሚተላለፉና ወራሽ በህይወት እያለ ውርስ አልተከፈተም የሚባል ከሆነም አለመከፈቱ የወራሽነት መብት መተላለፍ ረገድ የሚያስከትለው ለውጥ የሌለ ስለመሆኑ የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 826፣ 833	132787	ወጣት አቡ ተሊሉ እና ----------	ታህሳስ 24 ቀን 2009 ዓ.ም	182

ተ.ቁ	የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ	ተከራካሪ ወገኖች	ውሣኔው የተሰጠበት ቀን	ገጽ
	ቤተሰብ				**185**
37.	በጋብቻ ውስጥ የተፈራ ንብረት የባልና ሚስት ወይም የተጋቢዎቹ የጋራ ሀብት ሆኖ በጋብቻ ወቅት የተፈራ መሆኑ ከመረጋገጡ በተጨማሪ ሁለም ተሳትፎ የነበራቸው ከሆነ በዚህ ሁኔታ የተፈራ ንብረት እኩል መብት እያላቸው የአንደኛው ድርሻ ከሌላው ወገን ድርሻ በተለየ ሁኔታ የተረጋገጠ ሳይኖር የሚያንስበት ህጋዊ የሆነ ምክንያት የሌለ ስለመሆኑ የአ.ብ.ክ.መ ቤተሰብ ህግ አንቀጽ 73/1/ እና 74/1/	130957	ወ/ሮ አንሻ ሰይድ እና እነ ሸህ ሁሴን አደም (3 ሰዎች)	ታህሳስ 24 ቀን 2009 ዓ.ም	186
38.	✍ የጉዲፈቻ ልጅነት አለ ይባል ዘንድ የጉዲፈቻ ስምምነት መኖርና ይኸው ስምምነት ለፍርድ ቤት ቀርቦ በዳኞች መጽደቅ የሚኖርበት ሲሆን ይህ ካልሆነ ግን በህግ እይታ ውጤት ያለው የጉዲፈቻ ልጅነት አለ ለማለት የማይቻልና መሰል ጉዳይ የህግ ጉዳይ በመሆኑ ፍርድ ቤት በራሱ አንስቶ ሊወስንበት አይችልም የሚባል ስላለመሆኑ የፍትሐ ብሔር ህግ በቁጥር 804(1)፣የአማራ የቤተሰብ ህግ አዋጅ ቁጥር 79/95፣የፌዴራል የቤተሰብ ህግ አዋጅ ቁጥር 213/1992 አንቀጽ 194 እና 205 ✍ ልጅ እና ወራሽ ለመሆን የሚያስችል በፍ/ቤት የጸደቀ የጉዲፈቻ ስምምነት ማስረጃ በሌለበት ሁኔታ ህጋዊ ልጅ ነኝ በማለት ከፍርድ ቤት የተወሰደ	199906	ከበደ ተፈራ እና እነ መሬማ እሸቱ (3 ሰዎች)	ጥቅምት 5 ቀን 2014 ዓ/ም	189

ተ.ቁ	የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ	ተከራካሪ ወገኖች	ውሣኔው የተሰጠበት ቀን	ገጽ
	የወራሽነት ማስረጃ ተሰርዞ የተወሰደው ማስረጃ ሊመልስ የሚገባ ስለመሆኑ የፍ/ህ/ቁ 998 (1)				
39.	ባል ወይም ሚስት በትዳር ውስጥ እያሉ በግላቸው በስጦታ ያገኙት የንግድ መደብር ባለሀብት የሆኑበትን ንብረት በሽያጭ ውል ማስተላለፋቸው የተሻሻለውን የቤተሰብ ሕግ አዋጅ ቁጥር 213/1992 አንቀጽ 57፤ የፍትሐ ብሔር ሕግ ቁጥር 1204፤ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የቤቶች ልማት አስተዳደር ቢሮ የመንግስት ቤቶች አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 4/2009 ቁጥር 24(ረ) እና የንግድ ሕጉን ለጉዳዩ አግባብነት ያላቸውን ድንጋጌዎች መሠረት ያደረገ ነው የሚባል ስለመሆኑ	221097	አቶ ሙሉጌታ ዘውዱ እና እነ ወ/ሮ ሄለን ደረሰ (4 ሰዎች)	ጥቅምት 1 ቀን 2015 ዓ/ም	195
40.	ፊ ክሳሽ ሊከሰስበት ሲችል ሆነ ብሎ በመቀነስ ባስቀረው ሀብት ምክንያት እንደገና ሌላ ክስ ማቅረብ የማይችል ስለመሆኑ እና ከሳሽ ያቀረበው ክስ በአንድ ጉዳይ ላይ የተመሰረተ ሆኖ የሚጠይቀው ዳኝነት ግን ከአንድ በላይ ሲሆን ፍርድ ቤት ሳይፈቅድለት ሊጠይቅ ይገባው ከነበረው ዳኝነት ውስጥ በከፊል ራሱ ቀንሶ ባስቀረው መብት እንደገና ሊከሰስበት የማይችል ስለመሆኑ የፍትሀ ብሄር ስነ ስርዓት ህግ አንቀጽ 216 (3)፣ (4) ድንጋጌ እንደ አግባብነቱ በቤተሰብ ክርክሮችም ተፈፃሚነት አይኖረውም የማይባልና ጉዳዩን በቤተሰብ ህግ ስለጋብቻ ንብረት ማጣራት ከተደነገጉት ድንጋጌዎች እና በተለይም ከግራ ቀኙ ክርክር ይዘት አንፃር መመልከቱ ተገቢ ስለመሆኑ	196971	ወ/ሮ ሠርካለም አበበ እና አቶ አፈወርቅ ቅጣው	ጥቅምት 22 ቀን 2014 ዓ/ም	202

ተ.ቁ	የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ	ተከራካሪ ወገኖች	ውሣኔው የተሰጠበት ቀን	ገጽ
	✍ የፍትሐብሄር ሥነ ሥርዓት ህግ ድንጋጌዎች ተፈፃሚነት የሚኖራቸው በቤተሰብ ህግ ባልተመለከቱ የሥነ ሥርዓት ጉዳዮች ላይ ብቻ ሲሆን በባልና ሚስት የጋብቻ ንብረት ክርክር ብቻም ሳይሆን ጋብቻው የፈረሰው በሞት ቢሆን እንኳ በህይወት ባለው ተጋቢ እና በሟች ወራሾች መካከል የንብረት ክፍፍልን በተመለከተ ክርክር የተነሳ እንደሆነ የባልና ሚስትን ሀብት ስለማጣራት በቤተሰብ ህግ በምዕራፍ 5 የተደነገጉት ድንጋጌዎች ተፈፃሚነት ያላቸውና የጋብቻ ንብረት ማጣራትና ክፍፍል ጉዳይ የቤተሰብ ህግን ድንጋጌዎች በጥብቅ ተከትሎ ሊፈፀም የሚገባ ስለመሆኑ የተሻሻለው የፌዴራል የቤተሰብ ህግ አዋጅ ቁጥር 213/1992 አንቀጽ 108 እና 109				
41.	ጋብቻ በፍቺ ዉሳኔ እስከፈረሰበት ድረስ ባልና ሚስት በትዳር አብረዉ እየኖሩ ያፈሩት የመኖሪያ ቤት፤ ቤቱ የተሰራው በባል ወይም በሚስት በዉርስ የተገኘ ቤትና ቦታ ለልማት ተወስዶ በተሰጠ ምትክ ቦታና በተከፈለ የካሳ ገንዘብ በመሆኑ ቤቱ የግል ሀብቴ ነዉ በሚል የሚቀርብ ክርክር፣ የካሳ ገንዘቡ ለቤቱ ሥራ የዋለ ስለመሆኑ በፌዴራል የቤተሰብ ሕግ አንቀጽ 58 መሰረት ቤቱ የግል ሀብት እንዲባልልኝ በማለት ለፍ/ቤት አቤቱታ ቀርቦና ፍ/ቤትም ቤቱ የባል ወይም የሚስት የግል ሀብት ነው ብሎ ያፀደቀበት አግባብ ካልሆነ በቀር ቤቱ የጋራ ሀብት	203715	ወ/ሮ ፀሐይ አስራት እና አቶ አሰፋ ማሞ	ጥር 23 ቀን 2014 ዓ.ም	208

ተ.ቁ	የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ	ተከራካሪ ወገኖች	ውሣኔው የተሰጠበት ቀን	ገጽ
	እንጂ የግል ሀብት ነው ሊባል የማይችል ስለመሆኑ				
42.	የመካድ ክስ የሚያቀርብ ሰዉ በህግ የልጁ አባት እንደሆነ ግምት የሚወሰድበት ሰዉ ወይም በህግ ይህን ክስ የማቅረብ መብት የተሰጣቸዉ ሆኖ፣ ክሱ የመካድ ክስ ነዉ ለማለት የሚቻለዉም ከሳሹ የመካድ ክስ የቀረበበት ልጅ የተወለደዉ አባት ነዉ ተብሎ የህግ ግምት የተወሰደበት ሰዉ እናቱ በጋብቻ ወይም እንደ ባልና ሚስት አብረዉ ሲኖሩ በነበረበት ወቅት መሆኑን ተቀብሎ ነገር ግን በሌላ ምክንያት ልጁ በህግ አባቱ ነዉ የተባለዉ ሰዉ ልጅ አለመሆኑን በመጥቀስ የቀረበ ክስ ሲሆን ስለመሆኑ የተሻሻለዉ የፌዴራል የቤተሰብ ህግ አዋጅ ቁጥር 213/92 ከአንቀጽ 167 እስከ 178	234422	እነ ወ/ሮ ሙሉ ጥበቡ (4 ሰዎች) እና እነ ወ/ሮ አዜብ አሰፋ አበራ (2 ሰዎች)	ሚያዚያ 30 ቀን 2015 ዓ.ም	213
43.	✍በህግ ጥበቃ በሚደረግለት ግኑኝነት ውስጥ ያልተወለደ ልጅ አባት ነው የተባለ ግለሰብ የአባትነት ጉዳይ በህግ ግምት የሚወሰድበት ባለመሆኑ የልጁን መወለድ ለመቃወም የሚቀርብ ክስ አባትነትን ስለመካድ በሚቀርበው አኳኋን ሊሆን ይገባል የሚባልበት የህግ መሰረት የሌለ ስለመሆኑ ✍ አባትነትን ፈቅዶ የተቀበለ እና በፍርድ ቤት ውሳኔ “አባት ነህ” የተባለው ሰው ወይም ከዚሁ ሰው መብቱ የተላለፈለት ሰው የመካድ ክስ	238021	ወ/ሪት አብነት ሐብታሙ ካሴ እና ህፃን ናፍቆት ሐብታሙ ካሴ	ሐምሌ 25/2015 ዓ.ም	219

ተ.ቁ	የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ	ተከራካሪ ወገኖች	ውሣኔው የተሰጠበት ቀን	ገጽ
	ለማቅረብ ህግ የማይፈቅድለት ስለመሆኑ የተሻሻለዉ የፌዴራል የቤተሰብ ህግ አዋጅ ቁጥር 213/92 አንቀፅ 168፣ 170 እና 174 ድንጋጌዎች ጣምራ ንባብ				
	የዳኝነት ስልጣን				226
44.	የፍርድ ቤት ብሔራዊ የመዳኘት ሥልጣን ከሀገሮች ሉዓላዊነት፣ የሚሠጠው ፍርድ በሌሎች ሀገሮች ዕውቅና ሊሠጠውና ሊፈጸም የሚችል መሆን አለመሆኑ እና ከተከሳሽ መብት ጋር የተያያዘ መሠረቱ ዓለም አቀፍ ሕግና የታወቁ የሕግ መርሆዎች ሆኖ የአንድ ሀገር ፍርድ ቤት ጉዳዩን ለመመልከት ከተከሳሹ ወይም የክርክሩ ምክንያት የሆነው ተግባር ከተፈጸመበት ወይም አከራካሪ የሆነው ንብረት ከሚገኝበት ቦታ ጋር በቂ የሆነ ግንኙነት ያለው ሆኖ ሲገኝ ወይም ተከሳሽ የሆነው ወገን በሀገሪቱ ፍርድ ቤቶች ለመዳኘት ያለው ፈቃድ ላይ መሠረት በማድረግ የሚወሰን ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 25	196411	እነ ወ/ሪት መሠረት አማረ (10 ሰዎች) እና አቶ ክብሮም አሮን	ሰኔ 23 ቀን 2013 ዓ.ም	227

ተ.ቁ	የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ	ተከራካሪ ወገኖች	ውሣኔው የተሰጠበት ቀን	ገጽ
45.	✍የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ከሚያስተዳድራቸዉ የመንግሥት ቤቶች እና የድሬዳዋ ከተማ አስተዳደር የሚያስተዳድራቸዉ ሆኖ ለንግድ፣ለመኖሪያ ወይም ለሌላ አገልግሎት በመስጠት ላይ ካሉ የመንግሥት ቤቶች ጋር በተያያዘ የሚነሱ ጉዳዮችን (ክሶችን) የመዳኘት ሥልጣን የከተሞቹ ፍርድ ቤቶች ሥልጣን ነዉ በሚል የተደነገገው ግልጽ በሚያደርግ አካኂኝ ከቤቶቹ ጋር በተያያዘ የሚነሳ የይዞታ እና የባለቤትነት መብቶች የመፋለም ክሶች (The petitory action and the possessory action) ወይም ሌላ ማንኛዉም ክርክር በሚል ሰፋ ባለ አካኂኝ መደንገጉን የሚያሳይ ስለመሆኑ የተሻሻለዉ የአዲስ አበባ ከተማ ቻርተር አዋጅ ቁጥር 361/1995 አንቀጽ 41(1/ረ) እና በድሬዳዋ ከተማ አስተዳደር ቻርተር አዋጅ ቁጥር 416/1996 አንቀጽ 33(1/ረ) ✍የፌዴራል ፍርድ ቤቶች ዳኝነት ሥልጣን የሚሆነዉ የአዲስ አበባ እና የድሬዳዋ ከተሞች አስተዳደሮች የሚያስተዳድሯቸዉንና ለንግድ፣ ለመኖሪያ ወይም ለሌላ አገልግሎት በመስጠት ላይ ካሉ የመንግሥት ቤቶች ዉጭ በሆኑት የፌዴራል መንግሥቱን ንብረቶች በተመለከተ የሚነሱ ጉዳዮች ማለትም ከፌዴራል ሦስቱም የመንግሥት አካላት እና ከፌዴራል የልማት	244107	እነ ዮሀንስ ተስፋዬ (4 ሰዎች) እና የአዲስ ከተማ ክፍለ ከተማ ወረዳ 08 ቤቶች አስተዳደር ፅ/ቤት	ሰኔ 24 ቀን 2016 ዓ/ም	231

ተ.ቁ	የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ	ተከራካሪ ወገኖች	ውሣኔው የተሰጠበት ቀን	ገጽ
	ድርጅቶች ንብረቶች ጋር በተያያዘ የሚቀርቡ ማናቸዉም ክሶች በተመለከተ ስለመሆኑ የፌዴራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀጽ 5(1/ደ)ን ከአዋጁ አንቀጽ 5(1/ሰ) እና በአዋጅ ቁጥር 361/1995 አንቀጽ 41(1/ረ) እና በአዋጅ ቁጥር 416/1996 አንቀጽ 33(1/ረ) ☞ የፌዴራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 1234/2013 ከጸናበት ከጥር 13 ቀን 2013 ዓ/ም ጀምሮ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 5(1/ደ) ስር በተደነገገዉ መሠረት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በሚያስተዳድራቸዉ ቤቶች ላይ የባለቤትነት መብት በመፋለም የሚቀርብ ክስ የመዳኘት ሥልጣን የአዲስ አበባ ከተማ ፍርድ ቤቶች በመሆኑ አዋጅ ቁጥር 1234/2013 ከጸናበት ቀን ጀምሮ በሰ/መ/ቁጥር 32276 (ቅጽ 5) ላይ የተሰጠዉ የሕግ ትርጉም ተፈጻሚነቱ ቀሪ ስለመሆኑ				
46.	የአንድ ሀገር ፍርድ ቤት በጉዳዩ ላይ ብሔራዊ የዳኝነት ሥልጣን አለው ወይስ የለውም ለማለት መሠረት ተደርጎ የሚወሰደው ከተከሳሽ ጋር ያለው ግንኙነት መለኪያ አንዱ ሲሆን፤ ይኸውም ከተከሳሽ ሰው ወይንም (action impersonal) የሕግ ይሁን የተፈጥሮ ሰው ዜግነቱ ወይንም መደበኛ መኖሪያው ከፍርድ ቤቱ ጋር ያለው ቁርኝት፤ ለክሱ ምክንያት የሆነው	221715	ሚ/ር ይቤዝን አውግስቲን አሌክስ ፈረዝ እና ሚስ ማርካዬት ጎርክሊን ሱዛን ግራሲያ	ጥቅምት 29 ቀን 2015 ዓ/ም	236

ተ.ቁ	የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ	ተከራካሪ ወገኖች	ውሣኔው የተሰጠበት ቀን	ገጽ
	ድርጊት (Act) ውል፤ ከውል ውጪ የተፈፀመበት ከሀገር ጋር ያለው ቁርኝት፤ ለክሱ ምክንያት የሆነው ንብረት (property) ተንቀሳቃሽ ይሁን የማይንቀሳቀስ የሚገኝበት አልያም የተከሳሽ ፈቃድ (consent) መኖር ወይንም አለመኖር መለኪያዎች ተደርጎ የሚወሰድ ሲሆን ከዚህ ባለፈም በጉዳዩ ላይ ያለው ብሔራዊ ጥቅምና ፖሊስ (National interest or public policy) መኖሩ ሲረጋገጥ ክሱ የቀረበበት ሀገር ብሔራዊ የዳኝነት ሥልጣን አለው ሊባል የሚችል ስለመሆኑ				
47.	✍ በዉል የተፈጠረ መብት በሰዉ ላይ ግዴታን የሚፈጥር ሲሆን ክስ የሚቀርብበትን ፍርድ ቤት በመምረጥ ረገድ በፍ/ብ/ስ/ስ/ህግ አንቀጽ 24(1) ለከሳሽ ወገን የተተወ ሲሆን ነገር ግን የጉዳዩ መነሻ ዉል ቢሆንም በተለይም የማይንቀሳቀስ ንብረት የሚመለከት ሲሆን የግዛት ዳኝነት ስልጣኑ የሚለየዉ በፍ/ብ/ስ/ስ/ህግ ቁጥር 25 ስር በተደነገገዉ አግባብ ሲሆን የቀረበው ክስ ቤትን ለመረከብ የቀረበ ከሆነ በፍ/ብ/ስ/ስ/ህግ ቁጥር 25(1/ሐ) እንደተመለከተዉ ጉዳዩ በንብረቱ ላይ ያለዉን መብት ለማስወሰን የቀረበ በመሆኑ ክሱ መቅረብ የሚገባዉ ንብረቱ የሚገኝበት ግዛት ክልል ባለዉ ፍርድ ቤት ስለመሆኑ ✍ ክርክር የግዛት ስልጣንና የስረ ነገር ስልጣን አጣምሮ የያዘ ከሆነ ጉዳዩ ለተከራካሪ ወገኖች አመቺነት በሚል ምክንያት ለተከራካሪ ወገኖች ምርጫ	212543	ካንትሪ ክለብ ዴቬሎፕርስ ሪል ስቴት ኃላ.የተ.የግ.ማህበር እና ወ/ሮ እናኑ ዘለቀ	ጥር 24 ቀን 2015 ዓ.ም	242

ተ.ቁ	የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ	ተከራካሪ ወገኖች	ውሣኔው የተሰጠበት ቀን	ገጽ
	የማይተውና ክሱ ንብረቱ በሚገኝበት ግዛት ክልል ፍርድ ቤት መቅረብ ያለበት ስለመሆኑ				
48.	ፍርድ ቤት ጉዳዩን የማየት የሥረ ነገር ሥልጣን የለኝም ካለ በፍትሐ ብሔር ሥነ ሥዓት ሕግ ቁጥር 9(1) እና 231 (1) (ለ) መሠረት የክስ አቤቱታው ተቀባይነት የለውም በማለት መዝገቡን ዘግቶ ተከራካሪዎቹን ማሰናበት ሲገባ በፍትሐ ብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 244(2) (መ) መሠረት የቀረበን መቃወሚያ ተቀብሎ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 245 መሠረት መርምሮ ክሱ በይርጋ ይታገዳል በሚል የሚሰጥ ውሳኔ የሥነ ሥርዓት ህግን ያልተከተለ ስለመሆኑ	223548	እነ አቶ በላይ ዘለቀ እና (2 ሰዎች) የቴፒ ከተማ ማዘጋጃ ቤት	ጥር 25 ቀን 2015 ዓ.ም	250
49.	ፍ/ቤት አንድን ጉዳይ ለማየት የሥረ-ነገር የዳኝነት ስልጣን አለዉ ወይስ የለዉም የሚለዉን አስመልክቶ ተከራካሪ ወገኖች ከዚህ አንጻር የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ባያነሱም ፍ/ቤት በራሱ ተነሳሽነት በማንሳት ተገቢ ነዉ ያለዉን ዉሳኔ ሊሰጥበትና የቀረበዉን ክስ ዉድቅ በማድረግ ስልጣን ላለዉ ፍ/ቤት ጉዳዩን ማቅረብ እንደሚቻል በማመልከት መወሰን የሚገባ ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.9 (1)፣ 231 (1፣ ለ)፣ 244 (3) እና 245 (2) ድንጋጌዎች	200482	ወ/ሮ ሐቢባ ሸምሱ ስሩር እና አቶ ቴዎድሮስ ገብሩ ብዛ	ህዳር 27 ቀን 2014 ዓ.ም	255

ተ.ቁ	የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ	ተከራካሪ ወገኖች	ውሣኔው የተሰጠበት ቀን	ገጽ
	ንግድና ኢንሹራንስ				260
50.	✍ ለከባድ ጭነት ተሽከርካሪ በተሰጠ የመድን ሽፋን ውል ክፍል ላይ ሰው የመጫን አቅምን በሚመለከት በተገለሉ ጉዳዮች መሰረት መድህን ተቀባዩ በሚመለከተው ባለስልጣን በሚሰጠው የባለቤትነት ማረጋገጫ ሊብሬ ላይ ከተገለጸ አንድ ሰው በላይ ትርፍ ጭኖ ጉዳት ከደረሰ መድህን ሰጪው ካሳ እንደማይከፍል ተገልፆ በተሰጠ የመድህን ሽፋን፣ ተሽከርካሪው ከተፈቀደለት የመጫን አቅም በላይ በትርፍነት ጭኖ ሲጓዝ አደጋ ከደረሰ የመድህን ሰጪው የካሳ ክፍያ ኃላፊነት ውድቅ የሚደረግበት አግባብ በሚመለከት የተደረገው ውል በተዋዋዮች መካከል ሊኖር የሚገባውን የቅንነት እና የመተማመን ግንኙነት እንዲሁም በጉዳዩ ውስጥ ያለውን ልማዳዊ አሰራር መሰረት በማድረግ በቅን ልቦና ሊተረጎም የሚገባ ስለመሆኑ የፍ/ሕ/ቁጥር 1732 ✍ በሀገራችን ለጭነት ተሽከርካሪዎች የሚሰጠው የባለቤትነት ማረጋገጫ ደብተር (ሊብሬ) ላይ በጋቢና እንዲጭኑ የተፈቀደላቸውን የሰው ብዛት በሚመለከት አሽከርካሪውን የማይጨምርና በዘርፉ በዳበረው አሰራርም የጭነት ተሽከርካሪዎች በአብዛኛው ያለረዳት ሹፌር የማይንቀሳቀሱ በመሆኑ በሊብሬውም አንድ ሰው ተብሎ የተገለፀው በዘርፉ ከዳበረው ልማድ ጋር ተገናዝቦ ሲተረጎም ሹፌርን እና ረዳት ሹፌርን የማይጨምር ስለመሆኑ	194093	እነ አቶ ሐይማኖት አበራ (2 ሰዎች) እና ፀሀይ ኢንሹራንስ ኩባንያ	ጥቅምት 29 ቀን 2014 ዓ/ም	261

ተ.ቁ	የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ	ተከራካሪ ወገኖች	ውሣኔው የተሰጠበት ቀን	ገጽ
51.	በመድህን ሽፋን ውል መሰረት ተሽከርካሪ ትርፍ ጭኖ ሲጓጓዝ ለሚደርስበት አደጋ መድህን ሰጪው ካሳ ለመክፈል የማይገደድ በመሆኑ የመድን ሽፋን የተሰጠው ተሽከርካሪ ትርፍ መጫን ለአደጋ መንስኤ ሆኗል ወይስ አልሆነም የሚለው በማስረጃ ሊረጋገጥ የሚገባው በመድህን ውል ላይ በግልጽ አደጋው ትርፍ በመጫኑ ምክንያት የደረሰ እንደሆነ (loss caused by overloading) ካሳ የማያስከፍል መሆኑ የምክንያት እና የውጤት ግንኙነትን በሚያመላክት ሁኔታ በውሉ በግልፅ ተገልፆ ሲገኝ ስለመሆኑ የፍ/ሕ/ቁጥር 1731፣ 1733፣ የንግድ ሕግ ቁጥር 663 እንዲሁም በሀገራችን የተሽከርካሪ የጭነት መጠን የአየር ፀባይን፣ የመንገዶችን የጥራት ደረጃና የመልከዓ ምድር አቀማመጥን መሰረት አድርጎ በሊብሬ ወይም በባለቤትነት ማረጋገጫ የሚወሰንበት ነባራዊ ሁኔታ።	202174	ብርሀን ኢንሹራንስ ኩባንያ አክሲዮን ማህበር እና አቶ ዝናቡ ጌታነህ	ጥቅምት 29 ቀን 2014 ዓ/ም	266
52.	አንድ በባንክ ዕዳ ምክንያት በጨረታ የተሸጠን ንብረት እንዲለቅ የሚጠየቅ ባለዕዳ በጨረታ ሂደቱ ላይ ጉድለት አለበት የሚል ከሆነ ጉዳት መድረሱን አረጋግጦ ክስ ከሚያቀርብ በስተቀር ቤት እንድለቅ መጠየቁ የሁከት ተግባር ነው በሚል የሁከት ክስ ለማቅረብ የሚችልበት የህግ አግባብ የሌለ ስለመሆኑ በባንክ በመያዣ ስለተያዘ ንብረት የወጣ አዋጅ ቁጥር 97/1990 እና ማሻሻያ አዋጅ ቁጥር 216/1992	208270	ተካልኝ ጫላ ገቢሳ እና እነ ኦሮሚያ ኢንተርናሽናል ባንክ አ.ማ (2 ሰዎች)	ጥቅምት 26 ቀን 2014 ዓ.ም	271

ተ.ቁ	የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ	ተከራካሪ ወገኖች	ውሣኔው የተሰጠበት ቀን	ገጽ
53.	በመርህ ደረጃ አግባብነት ያለዉ የፍትሐብሄርና የንግድ ህግ ለቼክ የሰጡት ዋና ዓላማ ለመያዣነት እንዲያገለግል ነው ባይባልም እንደማንኛዉም ሊተላለፉ እንደሚችሉ ሰነዶች በመያዣነት ወይም በዋስትና ሊሰጥ እንደሚችልና ይህ በሚሆንበት ጊዜ ግን በንግድ ህግና በፍትሐብሔር ህግ ላይ በተቀመጡት ግልፅ ድንጋጌዎች መመራት ያለበት ስለመሆኑ የን/ህ/ቁ 950ና የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2866 የመያዣ ዉል ስምምነት በሚደረግ ጊዜ ውሉ መከተል ስላለበት ፎርም በተመለከተ በግልፅ የተደነገገ ስለመሆኑ የን/ህ/ቁ. 952 እና የፍ/ብ/ህግ ቁ. 2828 ቼክ በዋስትናነት አይሰጥም በሚል በሕግ የተደነገገ ክልከላ ባለመኖሩ በመርህ ደረጃ ቼክ ለዋስትና ሊሰጥ የሚችል ሲሆን ቼኩ የተሰጠዉ ለዋስትና አላማ እንደሆነ ተገልፆ በጽሁፍ የዋስትና ዉል ስምምነት ካልተደረገ በስተቀር ቼክ ለዋስትና አላማ ተሰጥቷል በሚል የሚቀርብ ክርክር ተቀባይነት የሌለው ስለመሆኑ	166392	ሚ/ር ሳሚ ሳዲቅ ራቲብ እና እነ አቶ ቴዎድሮስ ታደሰ ወላንሳ (2 ሰዎች)	ሚያዚያ 26 ቀን 2012 ዓ.ም	278

ተ.ቁ	የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ	ተከራካሪ ወገኖች	ውሣኔው የተሰጠበት ቀን	ገጽ
54.	✍ በባንክ በመያዣ ስለተያዘ ንብረት የወጣ አዋጅ ቁጥር 97/1990 አንቀጽ 3 እና 4 ላይ እንደተመለከተዉ ባንክ ለዕዳ በመያዣ የያዘዉን ንብረት በሐራጅ በመሸጥ ዋናዉን ገንዘብ እና ወለድ ለመሰብሰብ ለሚያካሄደዉ የሐራጅ ሽያጭ ሂደት ጋር በተያያዘ ስልጣኑ የባንኩ ሲሆን መደበኛ ፍ/ቤት ባንክ ያካሄደዉ የሐራጅ ሽያጭ በአግባብ ነዉ ወይስ አይደለም? የሐራጅ ሽያጩ ሊፈርስ ይገባል ወይስ አይገባም? የሚሉትን ነጥቦች አይቶ ለመወሰን ስልጣን የሌለውና መደበኛ ፍ/ቤት አንድ ባለዕዳ የሐራጅ ሽያጭ ያለ አግባብ የተደረገ ስለሆነ እንዲፈርስልኝ ወይም እንዲሰረዝልኝ በማለት የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.445 በመጥቀስ ያቀረበዉን ክስ በመቀበል ክርክር በማካሄድ ዉሳኔ መስጠት አዋጁ የወጣበትን ዓላማ ዋጋ የሚያሳጣ ስለመሆኑ ✍ አንድ ባለዕዳ ከሐራጅ ሽያጭ ጋር በተያያዘ ጉዳዩን ለመደበኛ ፍ/ቤት ማቅረብ የሚችለዉ የሐራጅ ሽያጩ ያለ አግባብ ከሕግ ዉጭ የተደረገ ነዉ የሚል ከሆነ በዚህ ምክንያት የደረሰበት ጉዳት ካለ አግባብነት ባለዉ ማስረጃ በማስደገፍ ክስ አቅርቦ ካሳ እንዲከፈለዉ ዳኝነት ከመጠየቅ ዉጭ የሐራጅ ሽያጩ እንዲፈርስ ወይም እንዲሰረዝለት የሚጠይቅበት የሕግ አግባብ የሌለና በዚህ ድንጋጌ መሰረት ደረሰብኝ የሚለዉን ካሳ አግባብነት ባለዉ ማስረጃ በማስደገፍ ስልጣን ላለዉ መደበኛ ፍ/ቤት አቅርቦ ከመጠየቅ	153867	ዓባይ ባንክ አ.ማ እና ዶ/ር ታርቆ አለነ	ሐምሌ 27 ቀን 2010 ዓ.ም	291

ተ.ቁ	የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ	ተከራካሪ ወገኖች	ውሣኔው የተሰጠበት ቀን	ገጽ
	በስተቀር ሐራጁ እንዲፈርስ ክስ ማቅረብ የማይችል ሲሆን መደበኛ ፍ/ቤት በዚህ አዋጅ አግባብ የሚቀርብ ክስ የካሳን ጥያቄ የሚመለከት ካልሆነ በስተቀር ጨረታ እንዲፈርስ በማለት የሚቀርበውን ክስ ተቀብሎ ግራ ቀኞቸውን አከራክሮ ተገቢ የሆነ ውሳኔ ለመስጠት ስልጣን የሌለው ስለመሆኑ				
	አፈፃፀም				297
55.	ለአፈፃፀም አቤቱታ ምክንያት ለሆነዉ ዉሳኔ መነሻ የሆነዉ ሁከት ይወገድ ክስ ሲቀርብ አዋሳኞቹንም በአራት አቅጣጫ በመጥቀስ ከሆነ የዉሳኔ ይዘትም አዋሳኙ ከተጠቀሰዉ ይዞታ ዉስጥ የሚገኘዉ ይዞታ የፍርድ ባለመብት በመሆኑ ለአፈፃፀሙ መነሻ ለሆነዉ ዉሳኔ ምክንያት በሆነዉ ክስ ላይ የተጠቀሰው የይዞታ መጠን እና በተሰጠዉ ዉሳኔ በክሱ ላይ አዋሳኞቹ የተጠቀሰዉ ይዞታ የፍርድ ባለመብት መሆኑን የሚያሳይ ከሆነ በአዋሳኙ የተመለከተዉ የይዞታ መጠን ቀሪዉ ይዞታ ፍርድ ያላላረፈበት ነዉ ለማለት የሚያስችል ባለመሆኑ ይዞታዉ ተለክቶ በታወቀዉ መጠን እና በክስ ላይ በተጠቀሰዉ መጠን መካከል ልዩነት በመፈጠሩ ብቻ ቦታው ላይ ፍርድ አላረፈም በማለት መቀነሱ የፍርዱን ትክክለኛ ይዘት ያላገናዘበ በመሆኑ በፍርዱ ላይ አዋሳኙ የተጠቀሰዉ ይዞታ ለፍርድ ባለመብት የሚፈጸም ስለመሆኑ	201128	ወ/ሮ መሠረት ኃይሉ እና ወ/ሮ ቢቂልቱ በየነ	ጥቅምት 03 ቀን 2014 ዓ.ም	298

ተ.ቁ	የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ	ተከራካሪ ወገኖች	ውሣኔው የተሰጠበት ቀን	ገጽ
	የፍት/ብ/ሥነ ሥርዓት ህግ ሰባተኛ መጽሐፍ አንቀጽ 371				
56.	በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህግ ቁጥር 441 እና 442 ድንጋጌዎች መሰረት ለፍርድ አፈጻጸም ሲባል ንብረት በሀራጅ እንዲሸጥ ሲታዘዝ በሀራጅ የተሸጠው ንብረት ዋጋ በሙሉ የሚከፈለው ገዢው ንብረቱን መግዛቱ ከተረጋገጠበት ጊዜ ጀምሮ በ15 ቀን ውስጥ እንደሆነ የተደነገገው አገላለጽ የህጉ ድንጋጌ ገዢ ጨረታ ያሸነፈበትን ገንዘብ በህጉ በተመለከተው ጊዜ ካልከፈለ ሌላ ሃላፊነት የሚጥልበት መሆኑን በአስገዳጅ ሁኔታ እና በጥብቅ የደነገገ በመሆኑ በሃራጅ ማስታወቂያ ላይ የተገለጸው የ15 ቀን መክፈያ ጊዜ በዳኞች ትእዛዝ ሊሻሻል የማይችል ስለመሆኑ	251605	ወ/ሮ ምህረት መኮንን እና እነ ወ/ሮ ትርሲት መኮንን (2 ሰዎች)	መጋቢት 23 ቀን 2016 ዓ.ም	302
57.	ምንም እንኳ በፍ/ብ/ሥ/ሥርዓት ህግ አንቀጽ 421 መሠረት በቀረበ ክስ መነሻነት የሚሰጥ ውሳኔ እስከሚታወቅ ድረስ በፍ/ብ/ሥ/ሥርዓት ህግ አንቀጽ 418 መሠረት የሚቀርብ የመቃወም አቤቱታን ዉድቅ በማድረግ የሚሰጥ ውሳኔ እንደፀና የሚቆይ ስለመሆኑ በድንጋጌዉ የተመለከተ ቢሆንም፣ ለመቃወም አቤቱታው ምክንያት የሆነዉን ንብረት በተመለከተ የቀረበ ክስ ታይቶ ውሳኔ እስከሚሰጥ ድረስ በአፈፃፀም መዝገብ ላይ ንብረቱን አስመልክቶ የሚሰጥ ዉሳኔ/ትዕዛዝ በሂደት ላይ ያለዉን ክርክር ዉጤት የሚጎዳ መሆኑ ከተረጋገጠ ንብረቱን አስመልክቶ የቀረበ ክስ እልባት እስኪሰጠው ድረስ ንብረቱን በተመለከተ የሚሰጥ/የተሰጠ የአፈፃፀም ትዕዛዝ	184585	ታግሮ ቢዝነስ ኃ/የተ/የግ/ማህበር እና እነ ወ/ሮ ማእበል ፍጹም (4 ሰዎች)	ታህሳስ 15 ቀን 2013 ዓ.ም	307

ተ.ቁ	የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ	ተከራካሪ ወገኖች	ውሣኔው የተሰጠበት ቀን	ገጽ
	ለጊዜዉ ታግዶ እንዲቆይ የማይደረግበት ምክንያት የሌለ ስለመሆኑ				
	የወንጀል ህግ				**315**
58.	✍ በአስተዳደራዊ ውሳኔ ከሚያስከትለው ቅጣት በተጨማሪ የወንጀል ተጠያቂነት የሚያስከትል ስለመሆኑ በግልጽ በህግ በተደነገገ ጊዜ በአስተዳደራዊ ውሳኔ መቀጣት የወንጀል ተጠያቂነት ሊያስቀር የሚችል ካለመሆኑም በላይ በአንድ ወንጀል ድጋሚ ቅጣት የመከልከልን ጥያቄ የሚያስነሳ ሊሆን የማይችል ስለመሆኑ ✍ በአንድ ወንጀል ድጋሚ ቅጣት የመከልከል ጥያቄ ሊነሳ የሚችለው በፍርድ ቤት ጉዳዩ ታይቶ ተገቢ ነው የተባለው ውሳኔ በተሰጠበት ጉዳይ በድጋሚ በዚሁ ጉዳይ በወንጀል የተከሰሰ መሆኑ ሲረጋገጥ በመሆኑ ድርጅት በአስተዳደራዊ ውሳኔ ተቀጥቶ እያለ በድጋሚ በወንጀል ሊቀጣ አይገባም በሚል የሚነሳ የሕግ ክርክር ስለድጋሚ ቅጣት ክልከላ መርህ (principle of double jeopardy) የተቀመጡትን መመዘኛዎች የሚያሟላ ባለመሆኑ ተቀባይነት የሌለው ስለመሆኑ የወንጀል ሕግ ምዕራፍ አንድ አንቀጽ 3፣የታክስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 983/2008 አንቀጽ 100 ንኡስ አንቀጽ 1፣አንቀጽ 108 እና አንቀጽ 120(1)	237423	የጦሳ ነጋዴዎች አጠቃላይ ንግድ ሥራ አክሲዮን ማኅበር እና የኢፌዲሪ ፍትህ ሚኒስቴር	መጋቢት 26 ቀን 2016 ዓ/ም	316

ተ.ቁ	የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ	ተከራካሪ ወገኖች	ውሣኔው የተሰጠበት ቀን	ገጽ
	አሠሪ እና ሰራተኛ				323
59.	✍ አንድ ሰራተኛ በአሰሪው ድርጅት ሲቀጠር የሌላ መስሪያ ቤት ሠራተኛ መሆን ያለመሆኑን ተጠይቆ እዉነታዉን በመደበቅ በአሰሪው ድርጅት መቀጠሩን የሚያሳይ ክርክር እና ማስረጃ ባልቀረበበት ሁኔታ በሌላ ድርጅት ተቀጥሮ መስራቱ ብቻዉን በአሰሪው ላይ የማታለል ድርጊት ፈጽሟል ለማለት የሚያስችል ህጋዊ ምክንያት የሌለ በመሆኑ ሰራተኛው ሌላ መስሪያ ቤት ሠራተኛ መሆኑ እንደ ጥፋት በመቁጠር ከስራ ማሰናበት ህጋዊ ነዉ በማለት አሰሪው የሚያቀርበዉ ክርክር ተቀባይነት የሌለው ስለመሆኑ ✍ ስራዉ በህገ-ወጥ መንገድ የተቋረጠበት ሠራተኛ ወደ ስራዉ ተመልሶ ለመስራት ፍላጎት ያለዉ መሆኑ ከተረጋገጠ፣ ክርክሩ የቀረበለት የስራ ክርክር ችሎት ሠራተኛዉ ወደ ስራዉ እንዲመለስ የመወሰን ግዴታ ያለበት ሲሆን ሠራተኛዉ ካሳ ተከፍሎት እንዲሰናበት መወሰን የሚችለዉ ወደ ስራዉ መመለሱ በአሠሪዉ ስራ ላይ ከፍተኛ ችግር የሚያስከትል መሆኑን የተረዳ እንደሆነ ብቻ በመሆኑ ፍርድ ቤት ሠራተኛዉ ወደ ስራዉ ሊመለስ አይገባም በሚል ድምዳሜ ላይ ከመድረሱ በፊት የሠራተኛዉ ወደ ስራዉ መመለስ በአሠሪዉ ላይ ከፍተኛ ችግር የማድረስ ዉጤት የሚያስከትል መሆን አለመሆኑን በአግባቡ የማጤን እና የመመርመር ኃላፊነት ያለበት	202393	የኢትዮጵያ ወንጌላዊት ቤተ-ክርስቲያን መካነ ኢየሱስ እና ወ/ሮ አይናበባ ተፈራ	ጥቅምት 03 ቀን 2014 ዓ.ም	324

ተ.ቁ	የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ	ተከራካሪ ወገኖች	ውሣኔው የተሰጠበት ቀን	ገጽ
	ስለመሆኑ አሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁጥር 1156/2011 እንቀፅ 43(3)				
60.	የስራ ቅጥሩ በሚመለከተዉ አካል ይሁንታ የሚፈጸም መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ አንድ አሠሪ ከዉጭ አገር ሠራተኛ ጋር በሚያደርገዉ ውል ውሉ ጸንቶ የሚቆይበትን ጊዜ በተመለከተ ተስማምተዉ የሚያስቀምጡት የጊዜ ገደብ ህጋዊ ዉጤት ያለዉ በመሆኑ አሠሪዉ የወሊ ጊዜ ሲያበቃ ዉሉን አቋርጦ ሠራተኛዉን የማሰናበት መብት የሚኖረው ስለመሆኑ	200687	አይካ አዲስ ጨርቃ ጨርቅ ኢንቨስትመንት ግሩፕ ኃ/የተ/የግ/ማህበር እና አቶ ኢብራሒም አይዶግዱ	30/02/2014 ዓ.ም	329
61.	ሰራተኛ የሚሰራው ስራ የአሰሪው ቋሚ ስራ ከሆነ፣ስራዉ አልፎ አልፎ የሚሰራ እና ሰራተኞችም ስራዉ ሲኖር ተጠርተዉ ለሰሩት ስራ ደመወዝ በየአስራ አምስት ቀን የሚከፈላቸዉ መሆኑ አሰሪው የቀን ሰራተኞች ናቸዉ ብሎ ቢከራከርም የሥራ ውል መኖር የሚወሰነው በስራዉ ላይ እንጂ በቆይታዉ ጊዜ አለመሆኑን የህጉ ይዘት የሚያስገነዝብ ስለሆነ ስራዉ አልፎ አልፎ የሚሰራ ስራ በመሆኑም ሆነ ደመወዝ በየአስራ አምስት ቀን መከፈሉ እንዲሁም ለስራዉ ቋሚ የስራ መደብ አለመኖሩ ብቻ ግንኙነታቸዉ በአሰሪና ሰራተኛ አዋጅ የሚሸፈን አይደለም ሊያሰኝ የማይችልና በአሰሪውና በሰራተኛው መካከል ያለው የስራ ውል በአሰሪና ሰራተኛ አዋጅ የሚሸፈን ስለመሆኑ	203557	አቶ መላኩ አብረሃ (3 ሰዎች) እና ኢትዮ ቴሌኮም ሰሜን ምስራቅ ርጅን	ጥቅምት 30 ቀን 2014 ዓ.ም	336

ተ.ቁ	የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ	ተከራካሪ ወገኖች	ውሣኔው የተሰጠበት ቀን	ገጽ
	የአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁ/1156/2011 አንቀጽ 3/2/፣ 4/1/				
62.	✍ በአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁጥር 1156/2011 አንቀጽ 2(10) ላይ በተቀመጠው የስራ መሪ ልዩ ሁኔታ ወይም ማግለያ መሰረት አንድ ሠራተኛ የሥራ አመራር ፖሊሲዎችን የሚያወጣና የሚያስፈጽም ወይም ሠራተኞን የሚቀጥር እና የማሰናበት ዕርምጃ የመዉሰድ ተግባራትን የሚያከናዉን የሥራ መሪ ነው ሊባል የሚችለው ሠራተኛዉ ከእነዚህ አንዱን ወይም ከዚያ በላይ ሥራዎችን የሚሠራ መሆኑ በማስረጃ ሲረጋገጥ ስለመሆኑ ✍ አንድ ቀጣሪ የስራ መሪ ነዉ ተብሎ ሊፈረጅ የሚችለው በህግ የሥራ የመሪ ተግባራት ተብለዉ የተዘረዘሩትን ስራዎች ለማከናዉን ስልጣን የተሰጠዉ መሆኑ ሲረጋገጥና ስራ አስኪያጅ የሚል ስያሜ መያዙ በራሱ የስራ መሪ የማያሰኝና ዋነኛ መስፈርቱ የስራ መሪ የሚያሠኙ ጉዳዮችን በሚመለከት የመወሰን ስልጣንና ተግባር መኖሩ አለመኖሩ ላይ የሚመሰረት ስለመሆኑ	209295	አቶ አፈወርቅ መንግስቱ እና ወጋገን ባንክ አ.ማ	የካቲት 30 ቀን 2014 ዓ/ም	343

ተ.ቁ	የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ	ተከራካሪ ወገኖች	ውሣኔው የተሰጠበት ቀን	ገጽ
	ከውል ውጪ ኃላፊነት				**348**
63.	የክስ ምክንያት ከውል ውጭ ካሣ እንዲከፈል ከሆነ በፍ/ሕ/ቁ. 2143(1) መሠረት ከውል ውጪ ጉዳት ከደረሰ በሁለት ዓመት ጊዜ ውስጥ ካልቀረበ የካሣ ክስ በይርጋ የታገደ እንደሚሆን በተደነገገው መሰረት ክስ የቀረበው በሕጉ ከተመለከተው የሁለት ዓመት የይርጋ ጊዜ ካለፈ በኋላ ቢሆንም ጉዳቱ በወንጀል የሚያስቀጣ ከሆነ የይርጋ ዘመኑ በወንጀል ይርጋ ጊዜው ልክ የሚሆንና ከፍጥነት ወሰን በላይ በማሽከርከር አካል ላይ በቋሚነት ለደረሰ ጉዳት የጉዳት አድራሹ ተሽከርካሪ ባለቤት ላይ ክስ ሲቀርብ የፍ/ሕ/ቁ. 2143(2) ለጉዳዩ ተፈጻሚነት ያለው ስለመሆኑ	199777	የኢትዮጵያ ኮንስትራክሽን ሥራዎች ኮርፖሬሽን - የርብ ግድብ መስኖ ልማት ፕሮጀክት፣ ሕፃን አብርሃም ግዛቸው፣ የኢትዮጵያ መድን ድርጅት	ጥቅምት 04 ቀን 2014 ዓ/ም	349
	የወንጀል ሥነ ስርዓት ህግ				**354**
64.	በወንጀል የተከሰሰ ሰው መከላከያ ማስረጃ እንዲያቀርብ የሚታዘዘው በዓቃቤ ህግ ማስረጃ የተረጋገጠበትን ክስ እና ማስረጃን እንዲያስተባብል ሲሆን ማስተባበል ማለት ደግሞ የተከሳሹን የወንጀል ድርጊት እና ጥፋተኝነት አረጋግጠዋል በተባሉት ማስረጃዎች ላይ በአንድም ይሁን በሌላ መንገድ ጥርጣሬ እንዲፈጠር በማድረግ በማስረጃዎቹ የማስረዳት አቅም ላይ መተማመን እንዳይኖር ማድረግ በመሆኑ ከተከሰሰው ሰው የሚጠበቀው በመከላከያ ማስረጃው በቂ እና አሳማኝ በሆነ መልኩ	212950	አቶ ቶቼኖ ቶማ እና የደቡብ ክልል ጠቅላይ ዐቃቤ ህግ	ህዳር 30/2014 ዓ.ም	355

ተ.ቁ	የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ	ተከራካሪ ወገኖች	ውሣኔው የተሰጠበት ቀን	ገጽ
	ማስረዳት ሳይሆን የዐቃቤ ህግ ማስረጃን አስመልክቶ ቀድሞ በተያዘው አቋም ላይ ጥርጣሬን መፍጠር ብቻ ስለመሆኑ የወንጀል ህግ ሥነ ሥርዓት ቁጥር 141 እና 142				
65.	✍ በወንጀል በተጠረጠረ ሰዉ ላይ ምርመራ ማድረጊያ ጊዜ በፍርድ ቤት እየተሰጠ ቆይቶ በወንጀል መርማሪ እና/ወይም በዐቃቤ ሕግ የተጠየቀዉን ተጨማሪ የምርመራ ማከናወኛ ጊዜ ፍርድ ቤቱ ባለመፍቀድ እስከ 15 ቀን ድረስ ዓቃቤ ሕግ ክስ እንዲመሰርት በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 109/1 መሰረት የሰጠዉ ትእዛዝ ጸንቶ እያለ እና የተሰጠዉ ክስ መመስረቻ ጊዜ ካለቀ በኋላ በተጠርጣሪዉ ላይ ክስ ሳይመሰረት ተጠርጣሪዉን በእስር ላይ ማቆየት ተገቢነት የሌለው ስለመሆኑ የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 17/2 እና በተባበሩት መንግሥታት የሲቪልና የፖ'ለቲካ መብቶች ቃል ኪዳን አንቀጽ 9/1 ✍ በወንጀል ምርመራ ሂደት የዋስትና መብት እንዲጠበቅለት ተጠርጣሪዉ ጥያቄ አቀርቦ ጥያቄዉ ተቀባይነት ከአጣ በኋላ የዋስትና ጥያቄ ለማቅረብ የሚያስችል አዲስ ሁኔታ ሲፈጠር ይህንኑ አዲስ ሁኔታ መሰረት በማድረግ ለዚያዉ ፍርድ ቤት ተጠርጣሪዉ የዋስትና መብት ጥያቄ በድጋሚ ለማቅረብ ሥነ ሥርዓታዊ መብት ያለው በመሆኑ በዚህ አግባብ አዲስ ሁኔታ በመፈጠሩ ወይም ዐቃቤ ሕግ ክስ እንዲመሰረት የተሰጠዉ ጊዜ ክስ	252231	አቶ አየለ ዳመና እና የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ	ጥቅምት 12 ቀን 2016 ዓ/ም	359

ተ.ቁ	የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ	ተከራካሪ ወገኖች	ውሣኔው የተሰጠበት ቀን	ገጽ
	ሳይመሰረት በማለቁ ምክንያት የተያዘ (የታሰረ) ሰዉ በዋስትና ለመለቀቅ የሚያቀርበዉ ጥያቄ አግባብነት ካለዉ ሕግ አንጻር ሳይመረመር በደፈናዉ ጥያቄዉ ቀድሞ ተቀባይነት ያላገኘ ነዉ በሚል የተያዘዉ ሰዉ ክስ ሳይመሰረትበት ላልተወሰነ ጊዜ ታስሮ እንዲቆይ የሚያደርግ ትእዛዝ/ዉሳኔ ተገቢነት የሌለው ስለመሆኑ ፞ የመያዣ፣ የብርበራ፣ የቀነ ቀጠሮ፣...የዋስትና መብት ጥያቄ የሚመለከቱ ሥነ ሥርዓታዊ ጉዳዮች የሙስና ወንጀሉን የማየት ሥልጣን ባለዉ ፍርድ ቤት እንዲታዩ መደረጉ የተከሳሹን መብት የሚያጣብብ ወይም ማስረጃ እንዲጠፋ ምክንያት የሚሆን ወይም ተገቢ ላልሆነ ወጪ የሚዳርግ መሆኑን አግባብ ያለዉ የሙስና ወንጀልን ለመመርመር እና/ወይም ለመክሰስ ሥልጣን የተሰጠዉ አካል ካመነበት እንደ ሁኔታዉ በአቅራቢያዉ በሚገኝ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት እንዲታይ ሊወሰን የሚችል በመሆኑ የወንጀል ምርመራ ለማድረግ የሚያስፈልገዉን ጊዜ ቀጠሮ ጉዳይ እና የዋስትና መብት ጥያቄን አይቶ ለመወሰን የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት እንዲሁም የዉክልና ሥልጣናቸዉ ያልተነሳባቸዉ የክልሎች ጠቅላይ ፍርድ ቤቶች ሥልጣን ያላቸው ስለመሆኑ የተሻሻለው የፀረ ሙስና ልዩ የሥነ-ሥርዓትና የማስረጃ ሕግ አዋጅን ለማሻሻል የወጣ አዋጅ ቁጥር 882/2007 አንቀጽ 7/5 እና የ.ኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ				

ተ.ቁ	የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ	ተከራካሪ ወገኖች	ውሣኔው የተሰጠበት ቀን	ገጽ
	መንግሥት አንቀጽ 80/2				
66.	✍ በወንጀል ቅጣት አወሳሰን ውስጥ የሚቀርቡት የቅጣት ማክበጃ እና ማቅለያ ምክንያቶች ላይ የግራ ቀኙ መከራከሪያ ሊሰማ እንደሚገባ በወንጀል ህግ ሥነ ሥርዓት ቁጥር 149(3) የተደነገገው የሚቀርበው የቅጣት አስተያየት የተያዘውን መነሻ የወንጀል ቅጣት ከፍ አልያም ዝቅ የማድረግ ውጤት ያለው በመሆኑ ምክንያት ስለትክክለኛነቱ በተገቢ አክኋን ለማጥራት ስለመሆኑ ✍ የሚቀርብ የቅጣት አስተያየት የህግ ወይም የፍሬ ነገር ሊሆን የሚችልና የህግ ከሆነ እንደየሁኔታው በፍርድ ቤት ግምት የሚወሰድበት በመሆኑ ያን ያክል የግራ ቀኙን መገናኘት እና ክርክር ማቅረብ ላይፈልግ የሚችል ሲሆን ሆኖም አስተያየቱ የፍሬ ነገር ከሆነ የተባለው ምክንያት ስለመኖሩም ሆነ ስላለመኖሩ ግልፅ ጥያቄ እና ክርክር መቅረብ ያለበት በመሆኑ በቅጣት አወሳሰን ሂደት የተከራካሪ ወገኖችን መቅረብ/መገኘት/ የግድ የሚል ስለሆነ ከዚህ አኳያ ተገቢውን መከራከሪያ ለማቅረብ ደግሞ ከመነሻውም የክርክሩ አካል መሆንን የሚጠይቅ በመሆኑ ጉዳዩ በሌለበት የተወሰነበት ተከሳሽ የፍሬ ነገር የቅጣት አስተያየት አቅርቦ የሚከራከርበት የህግ አግባብ የሌለ ስለመሆኑ	188086	አቶ ገ/መድህን ብርሃነ እና የትግራይ ክልል ፍትህ ቢሮ	ሚያዝያ 28/2013 ዓ.ም	366

ተ.ቁ	የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ	ተከራካሪ ወገኖች	ውሣኔው የተሰጠበት ቀን	ገጽ
	✍ በወንጀል ህግ ሥነ ሥርዓት ቁጥር 202(3) ስር የተመለከተው በቅጣት ውሳኔ ላይ በይግባኝ የመከራከር መብት ተከሳሹ ባይኖርም በህግ ረገድ ፍርድ ቤት በራሱ ተነሳሽነት በቅጣት ማቅለያነት መያዝ ሲገባው ያልያዘውን አልያም በቅጣት ማክበጃነት መያዝ ሳይኖርበት በተሳሳተ የህግ አተረጓጎም የተያዘ የቅጣት ማክበጃ ምክንያትን ብቻ የሚመለከት ስለመሆኑ				
	ልዩ ልዩ				**370**
67.	የመንግስት ቤት በኪራይ ውል ተከራይቶ የሚኖር ተከራይ በውርስ ከሌሎች ወራሾች ጋር ባገኘው ኮንደሚኒየም ቤት ላይ ያለው መብት የጋራ ባለሀብትነት መብት እንጂ ብቸኛ ወራሽ ካልሆነ የኮንደሚኒየም ቤት በውርስ አግኝቶ እየተጠቀመ ቤት አለው በሚል የኪራይ ውሉን በማቋረጥ ቤቱን እንዲያስረክብ የሚወሰድ እርምጃ አግባብነት የሌለው ስለመሆኑ የፍታብሔር ህግ ቁጥር 826 ንዑስ አንቀጽ 2፣ህግ ቁጥር 1060 ንዑስ አንቀጽ 2 እና የፍታብሔር ህግ ቁጥር 1266 እና ተከታይ ደንጋጌዎች	115221	አቶ ግርማ ወ/ትንሳኤ እና የልደታ ክፍል ከተማ ወረዳ 5 አስተዳደር	25/08/2008 ዓ/ም	371
68.	በፍ/ብ/ህ/ቁ 163(1) ስር እንደተመለከተው የጠፋ ሰው ጋብቻ የመጥፋቱ ማስታወቅ ፍርድ የመጨረሻ በሆነበት ቀን የሚፈርስ ሲሆን በአንዳንድ ጠፍቷል የማለት ማስታወቅ ውጤት መስጠቱ የሚቀረው ጠፋ የተባለው ሰው የመጣ እንደሆነ ስለመሆኑ የተደነገገው ይህም ቢሆን ግን ጋብቻን	213917	አቶ ነስሬ መሐመድ እና ወ/ሮ ዘምዘም መሐመድ	ጥቅምት 29 ቀን 2015 ዓ/ም	374

ተ.ቁ	የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ	ተከራካሪ ወገኖች	ውሣኔው የተሰጠበት ቀን	ገጽ
	በተመለከተ ወደ ነበረበት እንዲመለስ የማድረግ ውጤት ይኖረዋል ተብሎ የማይወሰድና የመጥፋትና የፍቺ ውሳኔ ተሰርዞ ከፈቃድ ውጪ ወደ ነበሩበት ጋብቻ እንዲመለሱ በሚል የሚቀርብ ጥያቄ ተቀባይነት የሌለው ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህግ አንቀጽ 170(1)(ሀ)				
69.	የአንድን በማመልከቻ በምዝገባ የገባ የንግድ ምልክት መሰረታዊ ባህሪ (essential feature) በመውሰድ ወይም የንግድ ምልክቱን እንዳለ ወስዶ በምልክቱ ላይ የተወሰነ ጭማሪ ወይም ለውጥ በማድረግ የቀረበ የንግድ ምልክት መሳከርን ሊያስከትል የሚችል ተመሳሳይነት ያለው ነው ሊባል የሚችል ስለመሆኑ የንግድ ምልክት ምዝገባና ጥበቃ አዋጅ ቁጥር 501/1998 አንቀጽ 2(12)፣ እና ከአንቀጽ 5 እስከ 7	209040	አቶ አብርሃም ጌታሁን እና አቶ ኃይለሥላሴ አስረስ	የካቲት 30 ቀን 2014 ዓ/ም	380
70.	✍ የገጠር መሬት የመጠቀም የይዞታ መብት የሚገኘዉ በመንግስት በሚደረግ ድልድል፣በዉርስ ወይም በስጦታ ወይም የግል ባለሀብት ከሆነ ደግሞ በኢንቨስትመንት ዉል ሲሆን በገጠር መሬት የመጠቀም የይዞታ መብት አለኝ የሚል ሰዉ ከእነዚህ በአንደኛዉ አግባብ ይዞታዉን ያገኘ ስለመሆኑ ማስረዳት የሚጠበቅበት ስለመሆኑ የፌዴራል የገጠር መሬት አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 456/97 አንቀጽ 5/3/	199697	አቶ ሰሃኔ አህመድ አብዲ እና አቶ መሀመድ አብዲ መዶቤ	ጥቅምት 5 ቀን 2014 ዓ.ም	385

ተ.ቁ	የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ	ተከራካሪ ወገኖች	ውሣኔው የተሰጠበት ቀን	ገጽ
	✍ የገጠር መሬት በተመለከተ የሚነሳ አለመግባባት አስቀድሞ ግራ ቀኙ በሚያደርጉት ውይይትና ስምምነት ወይም በመረጡት ሽማግሌዎች እንዲታይ በማድረግ ወይም በክልል የገጠር መሬት አስተዳደር ህግ በሚወሰነዉ መሰረት ሊታይ የሚችል ሲሆን ከዚህ ሌላ አቤቱታዉን ለሚመለከተዉ ፍርድ ቤት ማቅረብ የሚቻልና ጉዳዩ ለፍርድ ቤት ሲቀርብ ፍርድ ቤቱ በሽማግሌዎቹ ውሳኔ እና ማስረጃ ይዘት ሳይወሰን ሌሎች አግባብነት ያላቸዉን ማስረጃዎችን በመስማትና በመመርመር የበኩሉን ዉሳኔ መስጠት የሚችል ስለመሆኑ የፌዴራል የገጠር መሬት አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 456/97 አንቀጽ 12				
71.	የከተማ ቦታ የሊዝ መብት በሽያጭ የሚተላለፍበትን አግባብ በሚመለከት የሊዝ መብት ማስተላለፍ መብቱ የተመሰረተበትን የከተማ ቦታና በእላዩ ላይ የሰፈረ ሕንጻ (ግንባታ) ጭምር የሚመለከትና የሊዝ መብቱ የሚሸጥበትን ዋጋ ከመወሰን፣ መብቱን ለሦስተኛ ወገን ከማስተላለፍ አኳያ ሊሟሉ የሚገባቸዉ ቅድመ ሁኔታዎች መሟላታቸዉን በማረጋገጥ የሊዝ ዉል ከገዥ ጋር ከመዋዋልና ስመ ሀብቱን ወደ ገዥ ከማስተላለፍ አንጻር የሚመለከተዉ የመንግስት አካል የሚኖረዉ ተሳትፎ እንደተጠበቀ ሆኖ በባለመብቱና በገዥ መካከል የሚደረገዉ ዉል ግልጽ የሽያጭ ሥርዓትን በመከተል መደረግ የሚኖርበት ስለመሆኑ	225796	አቶ ይስሀቅ ጥበቡ እና እነ ወ/ሮ ሐመረ ጥጋቡ (2 ሰዎች)	ጥቅምት 29 ቀን 2015 ዓ/ም	391

ተ.ቁ	የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ	ተከራካሪ ወገኖች	ውሣኔው የተሰጠበት ቀን	ገጽ
	የከተማ ቦታን በሊዝ ስለመያዝ የወጣ አዋጅ ቁጥር 721/2004 አንቀጽ 24፣ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የከተማ መሬት ሊዝ ደንብ ቁጥር 49/2004 ከአንቀጽ 38 እስከ 41 እና የፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 1723/1				
72.	✍ አግባብ ያለዉ አካል ሳይፈቅድ የተያዘ ይዞታ ወደ ሕጋዊ ሥርዓት እንዲገባና በሊዝ ሥርዓት እንዲተዳደር ካልተደረገ በአዋጅ ቁጥር 721/2004 አንቀጽ 26/4 በተደነገገዉ መሰረት አግባብ ያለዉ አካል የማስለቀቂያ ትእዛዝ መስጠትና ካሣ መክፈል ሳያስፈልግ የ7 የሥራ ቀናት የጽሁፍ ማስጠንቀቂያ ብቻ ይዞታዉን ለያዘዉ ሰዉ በአካል በመስጠት ወይም በቦታዉ በሠፈረዉ ንብረት ላይ በመለጠፍ የማስለቀቅ ሥልጣን ያለው ሲሆን በሕግ የተጣለበትን ማስጠንቀቂያ የመስጠት ግዴታ ሳይወጣ መሬቱ በሕገ-ወጥ መንገድ ተይዟል በሚል ብቻ በመሬቱ ላይ የሰፈረ ንብረት የሚያወድም ወይም በንብረቱ ላይ ጉዳት እንዲደርስበት የሚያደርግ ከሆነ በደረሰዉ ጉዳት ልክ ካሣ የመክፈል ኃላፊነት ያለበት ስለመሆኑ	238091	አቶ ካህሱ ወ/ትንሳይ እና እነ በኮልፌ ቀራንዮ ክፍለ ከተማ የመሬት ልማት የመሬት ባንክ እና ማስተላለፍ ጽ/ቤት (4 ሰዎች)	ግንቦት 30 ቀን 2016 ዓ/ም	399
73.	በይዞታ መሬት በቋሚነት ጥቅም እንዲያገኝ (እንዲለቅ) ለሚደረግ የገጠር መሬት ባለይዞታ አመታዊ ገቢው በ10 ተባዝቶ የሚከፈለው የመፈናቀያ ካሳ ላይ በተጨማሪ ይዞታውን ለተወሰነ ጊዜ እንዲለቅ በተደረገ ጊዜ መሬቱ እስከሚመለስ ድረስ ያለው ጊዜ ታስቦ ተደራቢ የማፈናቀያ ካሳ ሊከፍል	234339	የኢትዮጵያ መንገዶች አስተዳደር፣ እና የአቱጋ ማርያም ቤተክርስቲያን፣	መጋቢት 25 ቀን 2016	412

ተ.ቁ	የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ	ተከራካሪ ወገኖች	ውሣኔው የተሰጠበት ቀን	ገጽ
	የማይችል ስለመሆኑ ለሕዝብ ጥቅም ሲባል የመሬት ይዞታ የሚለቀቅበትንና ለንብረት ካሣ የሚከፈልበትን ሁኔታ ለመወሰን የወጣ አዋጅ ቁጥር 455/1997 አንቀጽ 8(1)		ሱር ኮንስትራክሽን		
74.	✍ የንግድ ውድድርና እና የሸማቾች ጥበቃ አዋጅ ቁጥር 813/2016 አንቀጽ 11 መሰረት የውህደት ስምምነት ወይም ቅንብር ከንግድ ውድድር እና ሸማቾች ጥበቃ ባለስልጣን ፍቃድ ሳይገኝ ተፈፃሚ ሊሆን እንደማይችል በአዋጁ አንቀጽ 9/2 የተደነገገ በመሆኑ ባለስልጣኑ ፍቃድ የሚሰጠው ደግሞ ውህደቱ በንግድ ውድድር ላይ አሉታዊ ተጽኖ የሌለው መሆኑን ካጣራ በኋላ በመሆኑ አሉታዊ ተጽኖ መኖር አለመኖሩን ለማጣራት ባለስልጣኑ ውህደት መደረጉን እንዲያውቀው ማድረግ የግድ ስለመሆኑ ✍ በአዋጁ አንቀጽ 9/3/ለ መሰረት በአንድ ሰው ወይም በብዙ ሰዎች በተዘዋዋሪ ወይም በቀጥታ የንግድ ማህበር አክስዮኖችን፤ ሴኩሪቲዎችን ወይም ንብረቶችን የራስ ማድረግ እንደ ውህደት ተግባር ይቆጠራል እስከተባለ ድረስ ይህ ውህደት ተፈፃሚነት እንዲኖረው በአዋጁ አንቀጽ 9/2 መሰረት የውህደቱ ፈጻሚ/አድራጊ ነጋዴ ቢሆንም ባይሆንም ውህደቱን ለባለስልጣኑ ማስታወቅ ግዴታ ያለበትና ነጋዴ ባልሆኑ አክስዮን ማህበር	210819	የንግድ ውድድር እና ሸማቾች ጥበቃ ባለስልጣን እና ሐያት ሆስፒታል ሜዲካል ኮሌጅ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር	ታህሳስ 26 ቀን 2015 ዓ/ም	416

ተ.ቁ	የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ	የሰ/መ/ቁ	ተከራካሪ ወገኖች	ውሣኔው የተሰጠበት ቀን	ገጽ
	አባላት መካከል የተደረገ የአክስዮን ሽያጭም እንደ ውህደት የሚቆጠር በመሆኑ ይህንን ውህደት በአዋጁ አንቀጽ 9/2 መሰረት የአክስዮን ማህበሩ ለባለስልጣኑ የማሳወቅ ግዴታ ሊኖርበት የሚገባ ስለመሆኑ ð በማህበር አባላት መካከል የተደረገ የአክስዮን ሽያጭ ውህደት በተመለከተ የንግድ ውድድር እና ሸማቾች ጥበቃ ባለስልጣን የውህደት ማስታወቂያ ደርሶት የአክስዮን ግዢው ምን ተጽኖ ሊኖረው እንደሚችል ባልመረመረበት ሁኔታ በማህበር አባላት መካከል የተደረገው የአክስዮን ሽያጩ በንግድ ውድድር ላይ የሚያስከትለው ተጽኖ የለም በሚል የሚቀርብ ክርክር ተቀባይነት የሌለው ስለመሆኑ				

ፍትሐብሔር ሥነ-ሥርዓት

የሰ/መ/ቁ፡-200929

ቀን፡- 30/02/2014 ዓ.ም

ዳኞች፡- ብርሃኑ አመነው

ተሾመ ሽፈራው

ሀብታሙ እርቅይሁን

ብርሃኑ መንግስቱ

ነፃነት ተገኝ

አመልካች፡- ሕዳሴ ቴሌኮም አ/ማ

ተጠሪ፡- 1. አቶ ገዛኸኝ ለማ

2. አቶ ሕዝቂያስ ታፈሰ

መዝገቡ ተምርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሠጠ፡፡

ፍርድ

የሰበር አቤቱታው የቀረበው የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በሠጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሞበታል በሚል ነው፡፡ የክርክሩን አመጣጥ ከስር ፍርድ ቤት የመዝገብ ግልባጭ እንደተረዳነው አመልካች የስር ከሳሽ፣ ተጠሪዎች ተከሳሾች ሆነው ተከራክረዋል፡፡ አመልካች ያቀረበው ክስ 1ኛ ተጠሪ የአመልካች የሽያጭ ሠራተኛ ሆነው ሲሰሩ በውስጥ ኦዲት በሚደረግበት ጊዜ ብር 204,250.00 በጉድለት ስለተገኘ ገንዘቡን እንዲከፍሉ፤ 2ኛ ተጠሪም የ1ኛ ተጠሪ ዋስና ተያዥ በመሆናቸው እስከ 100,000.00 በአንድነትና ነጠላ ኃላፊነት እንዲከፍሉ የሚል ነው፡፡ 1ኛ ተጠሪ የሠጡት መልስ ገቢና ወጪውን ያልለየ፣ ከመቼ እስከመቼ የተደረገ ኦዲት ስለመሆኑ ግልጽ አይደለም፡፡ በውጭ ኦዲተር ኦዲት ይደረግልኝ ብለዋል፡፡ 2ኛ ተጠሪ በበኩላቸው ጉድለት የለም፣ ዋስ የሆንኩት 1ኛ ተጠሪ የመስመር ሠራተኛ እያለ ነው፤ ልጠየቅ አይገባም በማለት ተከራክረዋል፡፡

የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 58351 ግራ ቀኙን አከራክሮና በተፈቀደለት የሂሳብ ባለሙያ ድጋሚ ኦዲቱ እንዲሰራ በማድረግ ክስ የቀረበበትን ገንዘብ 1ኛ ተጠሪ እንዲከፍሉና 2ኛ ተጠሪ እስከ ብር 100,000.00 ድረስ በአንድነት እንዲከፍሉ ወስኗል፡፡ ተጠሪዎች ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ያቀረቡትን ይግባኝ ተቀብሎ በድጋሚ ኦዲቱ እንዲሰራ ካዘዘ በኋላ 1ኛ ተጠሪ ብር 204,250.00 ገንዘብ ማጉደላቸውን የቀረበው ማስረጃ ያሳያል፡፡ ነገር ግን ይህንኑ ገንዘብ 1ኛ ተጠሪ ባቀረቡት GSM Mobile Prepaid Card certificate ገቢ ስለመሆኑ ማስረጃ ያቀረቡ ቢሆንም በትክክል ገንዘቡ ገቢ ስለመሆኑ የሚረጋገጠው ቅጽ 7 (ውስጣዊ ደረሰኝ) ያላቀረቡ መሆኑን በመግለጽ ኦዲት

የሰራው ተቋም ገልጿል። 1ኛ ተጠሪ ገንዘቡ ገቢ ስለመሆኑ ቅጽ 7 ደረሰኝ ከአመልካች ተቋም ማግኘታቸውን በመግለጽ በተጨማሪ ማስረጃነት እንዲያያዝላቸው የጠየቁ ሲሆን አመልካች አዲስ ማስረጃ ሊያያዝ አይገባም፤ ይያያዝ ቢባል እንኳን የሽያጭ ገንዘቡ ወደባንክ ገቢ ከሆነው ስሊፕ ጋር ያልቀረበ በመሆኑ ፍርድ ቤቱን ለማሳሳት የቀረበ ነው ሲል አስተያየቱን አቅርቧል። የቀረበው ማስረጃ የአመልካች ማሕተም ያረፈበት፣ የአመልካች ሠነድ አለመሆኑ ያልተካደ በመሆኑና ማስረጃው ትክክለኛ ፍትሕ ለመስጠት የሚያግዝ በመሆኑ በፍብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 345 መሠረት ፍርድ ቤቱ ተቀብሎ በማያያዝ በጉድለት ተገኘ የተባለው ብር 204,250.00 ለአመልካች በቅጽ 7 (የውስጥ ደረሰኝ) ገቢ የተደረገ ስለመሆኑ ስለተረጋገጠ 1ኛ ተጠሪ ያጎደሉት ገንዘብ የለም በማለት የሥር ፍርድ ቤትን ውሳኔ በመሻር ክሱን ውድቅ አድርጓል። የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የአመልካችን የይግባኝ አቤቱታ ባለመቀበል ሠርሟል።

ይህ የሰበር አቤቱታ የቀረበው በዚህ ውሳኔ ነው። የአመልካች የሰበር አቤቱታ ይዘትም የገንዘብ ጉድለቱ በኦዲት ምርመራ ተረጋግጧል። ከሥነ-ሥርዓት ውጭ አዲስ ማስረጃ መቀበሉ ተገቢ አይደለም። ማስረጃው የገቢ ሠነድ ማስረጃ አይደለም። የውስጥ ደረሰኝ አይደለም፤ ቢሆን እንኳን ከባንክ ስሊፕ ጋር ያልቀረበ ስለሆነ ውጤት ሊኖረው አይችልም የሚል ሲሆን የሰበር አጣሪ ችሎት ጉዳዩን ተመልክቶ ማስረጃው የተያያዘበት አግባብነትና ማስረጃው ገንዘብ ገቢ ማድረጋቸውን የሚያሳይ መሆን አለመሆኑን ለመመርመር ተጠሪዎች መልስ እንዲያቀርብ በማዘዙ ተጠሪዎች ያቀረቡት መልስ የቅጽ 7 ሰነድ ከሥራ ተሰናብቼ ስለነበር ማግኘት ባለመቻሌ ያልቀረበ ሲሆን በኋላ ግን 1ኛ ተጠሪ የአመልካች ኃላፊን አስፈቅዶ ሠነዶችን ፈትሾ ያገኘው ነው። ሠነዱ የገቢ ደረሰኝ ሲሆን የገቢ ደረሰኝ አለመሆኑ በሥር ፍርድ ቤት ያልተካደ ነው። ማስረጃው ተመዝኖ የተሰጠው ውሳኔ ሊፀና ይገባል ብለዋል።

የክርክሩ ሂደት በአጭሩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን እኛም ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤቱ የክርክር አመራር ተገቢ መሆን አለመሆኑን እና የማስረጃ ምዘና መርህን መሠረት አድርጎ መወሰን አለመወሰኑን? በጭብጥነት በመያዝ መዝገቡን መርምረናል።

እንደመረመርነው አመልካች ያቀረበው ክስ 1ኛ ተጠሪ የአመልካች የሽያጭ ሠራተኛ ሆነው ሲሰሩ በውስጥ ኦዲት በሚደረግበት ጊዜ ብር 204,250.00 በጉድለት ስለተገኘ ገንዘቡን እንዲከፍሉ፤ 2ኛ ተጠሪም የ1ኛ ተጠሪ ዋስና ተያዥ በመሆናቸው እስከ 100,000.00 በአንድነትና ነጠላ ኃላፊነት እንዲከፍሉ የሚል ሲሆን ተጠሪዎች በበኩላቸው ገንዘቡ አልጎደለም፤ የኦዲት አሰራሩ ተገቢነት የለውም፣ ድጋሚ ኦዲት ይደረግልን ለክሱ ልንጠየቅ አይገባም በማለት ተከራክረዋል። ፍርድ ቤት የቀረበለትን የፍትሐ ብሔር ክርክር ጉዳዩን ለማስረዳት በሕግ ተቀባይነት ባለውና ለጉዳዩ አግባብነት ባለው ማስረጃ በማረጋገጥ ማን የተሻለ እንዳስረዳ የመወሰን ኃላፊነት አለበት። ክርክርን ለማስረዳት ማስረጃ የሚቀርብበት ሥርዓት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 223 መሠረት የሰው ማስረጃ ዝርዝር እና በፅጁ

የሚገኝ የፅሁፍ ማስረጃን የሚቀርብበት ሲሆን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 145 መሰረት ደግሞ በተከራካሪ ዕጅ የሌሉ ወይም ለማቅረብ ከፍተኛ ወጭ የሚጠይቁ ማስረጃዎች በፍርድ ቤት እገዛ የሚቀርቡበት ነው፡፡ የሠነድ ማስረጃ በፍብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 137 መሠረት ክሱ እስከሚሰማበት ጊዜ ድረስ ማቅረብ የሚቻል ሲሆን በእነዚህ ሂደቶች ማስረጃው ያልቀረበው ተከራካሪው ባለማወቁ ወይም አዲስ የተገኘ ማስረጃ ከሆነ ደግሞ በፍብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 256 አግባብ ማስረጃው እንዲቀርብ ለፍርድ ቤት ጥያቄ ሊቀርብ ይችላል፡፡ በዚህ አግባብ ማስረጃ እንዲቀርብ የሚጠየቀው ውሳኔ ከመሰጠቱ በፊት ሊሆን ይገባል፡፡ ውሳኔ ከተሰጠ በኋላ በይግባኝ ደረጃ በፍብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 327(3) እና 345 መሠረት በልዩ ሁኔታ ማስረጃ የሚስተናገድበት ሥርዓትም ተዘርግቷል፡፡

ተጠሪ ክሱን ለማስረዳት የኦዲት ውጤት ያቀረበ ሲሆን ፍርድ ቤት የማስረጃውን ትክክለኛነት ማጣራት ከፈለገ በፍብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 264 በተሠጠው ስልጣንና ኃላፊነት ድጋሚ ኦዲት እንዲሰራ በማዘዝ ክርክሩን መወሰን ይችላል፡፡ በዚህም አግባብ ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት የኦዲት ሥራው በድጋሚ እንዲከናወን አዟል፡፡ የቀረበው የኦዲት ውጤት 1ኛ ተጠሪ የገንዘብ ጉድለት ያለባቸው መሆኑን ያሳያል፡፡ ነገር ግን ይህንኑ ገንዘብ 1ኛ ተጠሪ ባቀረቡት GSM Mobile Prepaid Card certificate ገቢ ስለመሆኑ ማስረጃ ያቀረቡ ቢሆንም በትክክል ገንዘቡ ገቢ ስለመሆኑ የሚረጋገጠው ቅጽ 7 (ውስጣዊ ደረሰኝ) ያላቀረቡ መሆኑን ኦዲት የሰራው ተቋም መግለጹ ተከትሎ 1ኛ ተጠሪ ገንዘቡ ገቢ ስለመሆኑ ቅጽ 7 ደረሰኝ ከአመልካች ተቋም ማግኘታቸውን በመጥቀስ በተጨማሪ ማስረጃነት እንዲያያዝላቸው የጠየቁ ሲሆን ፍርድ ቤቱ አመልካች ክርክር እንዲያቀርብበት ካደረገ በኋላ የቀረበው ማስረጃ የአመልካች ማሕተም ያረፈበት፣ የአመልካች ሠነድ አለመሆኑ ያልተካደ በመሆኑና ማስረጃው ትክክለኛ ፍትሕ ለመስጠት የሚያግዝ በመሆኑ በፍብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 345 መሠረት ተቀብሎ በማያያዝ በጉድለት ተገኘ የተባለው ብር 204,250.00 ለአመልካች በቅጽ 7 (የውስጥ ደረሰኝ) ገቢ የተደረገ ስለመሆኑ ስለተረጋገጠ 1ኛ ተጠሪ ያጎደሉት ገንዘብ የለም ሲል ድምዳሜ ላይ ደርሷል፡፡ የፍብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 345(1)(ለ) እና 327(3) ላይ ይግባኝ ሰሚ ፍር ቤት ትክክለኛ ፍትሕ ለመስጠት የሚረዳ ተጨማሪ ማስረጃ ማያያዝ የሚችል ስለመሆኑ የተመለከተ ሲሆን የሥር ፍርድ ቤትም በዚህ ድንጋጌ ማዕቀፍ ማስረጃውን በመቀበሉ የፈጸመው የሥነ-ሥርዓት ሕግ ጥሰት የለም ብለናል፡፡

ለቀረበው ክስ የግራ ቀኙን ማስረጃ ፍርድ ቤቱ ከተቀበለ በኋላ በፍትሐ ብሔር ክርክር የምንከተለው የማስረዳት ደረጃ ከሁለቱ ወገን የተሻለ ያስረዳው ማን ነው (preponderance of evidence) የሚለውን በመመርመር እና የማስረጃ ተገቢነት፣ የማስረጃው ተቀባይነትን ደንቦችን መከተል እና ለማስረጃው የሚሰጠውን ክብደት (weight of evidence) በመለየት የመወሰን ኃላፊነት ማስረጃ ለመስማትና ለመመዘን ኃላፊነት ያለባቸው ፍርድ ቤቶች ዋና ተግባር ነው፡፡ የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በኢፌዲሪ ሕገ-መንግሥት አንቀጽ 80(3) በመጨረሻ ውሳኔ ላይ በተፈጸመ መሠረታዊ የሕግ ስህተት እንጂ ማስረጃው ተመዝኖ የተደረሠበትን የፍሬ ነገር ድምዳሜ ላይ እንዲመለከት

ሥልጣን አልተሠጠውም፡፡ የሥር ከፍተኛ ፍርድ ቤት ግራቀኙ ያቀረቡትን ማስረጃ መዝኖ 1ኛ ተጠሪ ገንዘብ ስለማጉደላቸው አልተረጋገጠም በሚል የደረሰበት የፍሬ ነገር ድምዳሜና በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የጸናው ውሳኔ ላይ የተፈጸመ የማስረጃ ምዘና መርሕ ስህተት ያልተገኘበት ስለሆነ የተፈጸመ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የለም ብለናል፡፡

ውሳኔ

1. የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 193074 ጥቅምት 16 ቀን 2013 ዓ/ም እና የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 14397 ጥቅምት 14 ቀን 2012 የሠጡት ውሳኔ በፍብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348(1) መሰረት ፀንቷል፡፡

2. በዚህ ችሎት ለወጣ ወጭና ኪሣራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

ትዕዛዝ

- የውሳኔው ግልባጭ ለስር ፍርድ ቤቶች ይተላለፍ፡፡
- መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ አምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ሄ/መ

የሰ.መ.ቁ.181649

መስከረም 26 ቀን 2013 ዓ.ም

ዳኞች፡-....1. ተፈሪ ገብሩ (ዶ/ር)

2. ቀነዓ ቂጣታ

3. ፈይሳ ወርቁ

4. ደጀኔ አያንሳ

5. ብርቅነሽ እሱባለዉ

አመልካች፡- አቶ ደጋረገ ሙሉ - የቀረበ የለም

ተጠሪ፡- ወ/ሮ ዉብናት ላቀ - የቀረበ የለም

ይህ መዝገብ ተመርምሮ የሚከተለዉ ፍርድ ተሰጥቷል።

ፍርድ

ይህ የባልና ሚስት የንብረት ክፍፍል ክርክር የተጀመረዉ በአማራ ክልል በሜጫ ወረዳ ፍ/ቤት ሲሆን፣ የአሁን አመልካች የሥር ተጠሪ፣ የአሁን ተጠሪ የሥር አመልካች ሆኖ ሲከራከሩ ነበር። ጉዳዩ ለዚህ ችሎት ሊቀርብ የቻለዉ የአሁን አመልካች የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ.ቁ.74190 ግንቦት 13 ቀን 2011 ዓ.ም የሰጠዉ ዉሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ እንዲታረምልኝ በማለት በማመልከታቸዉ ነዉ።

የአሁን ተጠሪ በሥር በወረዳዉ ፍ/ቤት ባቀረበችዉ ክስ ከአሁን አመልካች ጋር ያለን ጋብቻ እንዲፈርስ፣ በጋራ ያፈራናቸዉ ንብረቶች እንድንካፈል በማለት ዘርዝራ በማቅረብ እንዲወሰንላት ዳኝነት ጠይቃለች።

የአሁን አመልካች በዚህ ክስ ባቀረቡት መልስ ተጠሪዋ ባቀረበችዉ የንብረት ጥያቄ ላይ ተገቢ ነዉ ያለዉን ክርክር ያቀረበ ሲሆን፣ በራሱ በኩል ባቀረበዉ የተከሳሽ ክሳሽነት ክስ ከተጠሪ ጋር ልንካፈል ይገባል የሚላቸዉን ንብረቶች በመዘርዘር በመጠየቅ፣ የሰራተኛ እዳ አራት ኩንታል በቆሎ አንድ ኩንታል ዳጉሳ፣ አንድ ኩንታል ጓያ አለብን ልንከፍል ይገባል በማለት ጠይቋል። የአሁን ተጠሪ በዚህ በተከሳሽ ክሳሽነት ክስ ላይ መልስ ያቀረበች ሲሆን፣ የሰራተኛ የጋራ እዳ አለብን በማለት የቀረበዉም ሐሰት ነዉ፣ ይህ ተቀጠረ የተባለዉ ልጅ የአሁን አመልካች የግል ልጅ ነዉ የእኔም ሶስት ልጆች የግል ነበረኝ፣ የግል ከብቶች ነበራቸዉ፣ እነዚህ ልጆች አብረዉ ከእኛ ጋር ያደጉ ሲሆን ለሰሩበት ልንከፍላቸዉ አልተስማማንም አልቀጠርናቸዉም፣ የአሁን አመልካች ልጅ እንደ ልጅ ከቤት ነበረ እንጂ የተቀጠረ አይደለም።

ከዚህ በኋላ የወረዳዉ ፍ/ቤት የሰዉ ምስክሮች በመስማት በሰጠዉ ዉሳኔ የአሁን አመልካች በተከሳሽ ክሳሽነት የጋራ ዕዳ በማለት ያቀረበዉ የሰራተኛ እዳ 6 [ስድስት] ማዳበሪያ እህል በጋራ ሊከፍሉ ይገባል፣ የባልና ሚስት ንብረቶች ላይ ተገቢ ነዉ ያለዉን ዉሳኔ ሰጥቷል። የአሁን ተጠሪ

በዚህ ዉሳኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለባህር ዳርና አካባቢዋ ከፍተኛ ፍ/ቤት ያቀረበችዉ ሲሆን ፍ/ቤቱም ግራ ቀኙን በማከራከር በሰጠዉ ዉሳኔ የባልና ሚሰት ንብረት በተመለከተ በተወሰኑ ንብረቶች ላይ የሥር ፍ/ቤት ጉዳዩን ድጋሚ አጣርቶ እንዲወስን የመለሰ ሲሆን፣ የሰራተኛ ዕዳ የተባለዉን የሥር ዉሳኔ በማጽናት ወስኗል።

የአሁን ተጠሪ አሁንም በዚህ ዉሳኔ ቅር ተሰኝታ የሰበር አቤቱታ ለአማራ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ያቀረበች ሲሆን ችሎቱም ግራ ቀኙን በማከራከር በሰጠዉ ዉሳኔ ለአራሽ ሠራተኛ አበል የተባለዉን 6 [ስድስት] ማዳበሪያ እህልን በተመለከተ የእርሻ ሥራ ሰራሁ የሚለዉ ግርማዉ ደጋረገ የተባለዉ ሰዉ ቀርቦ ሳይጠየቅ የአሁን አመልካች መብት የለዉም እና ስለ ግርማዉ ደጋረጋ ዉክልና ባልያዘበት ሁኔታ የአሁን ተጠሪ ለአራሽ አበል ከሆነዉ 6 [ስድስት] ማደበሪያ እህል ዉስጥ እዳ በመሆን ድርሻዋን ትክፈል በማለት በዚህ ረገድ የሥር ፍ/ቤቶችን ዉሳኔ በመሻር የአሁን ተጠሪ ይህን ዕዳ ልትከፍል አይገባም፣ የጋራ ንብረቶችን በተመለከተ ተገቢ ነዉ ያለዉን ዉሳኔ በመስጠት የሥር ፍ/ቤቶችን ዉሳኔ በማሻሻል ወስኗል። የአሁን የሰበር አቤቱታ የቀረበዉ በዚህ ዉሳኔ ቅር በመሰኘት ለማስለወጥ ነዉ።

የአሁን አመልካች በ6/10/2011 ዓ.ም በተጻፈ የሰበር አቤቱታ፣ የሥር ፍ/ቤት የሰራተኛ ደመወዝ 6 ማዳባሪያ ሰብል እዳ ያለብን ስለመሆኑ በግራ ቀኝ ምስክሮቻችን ተጣርቶና ተረጋግጦ እያለ ተጠሪም ይህን አምናበት የሰራተኛ ደመወዝ ሰብሉን የከፈለች ሆኖ እያለ የሥር ፍ/ቤቱ ግን የሰራተኛ ደመወዝን እዳ ያለብንን ባለገንዘቡ ከሶ ይጠይቅ በማለት ለሌላ ወጭ በሚዳርግ መልኩ በምስክሮቻችን የተረጋገጠዉን እዳ ዉድቅ ማድረጉ የህግ ስህተት ስለሆነ እንዲሻርልኝ በማለት በሌሎች ጉዳዮችም ላይ ቅሬታዉን አቅርበዋል።

የሰበር አጣሪ ችሎት ጉዳዩን በማየት ፣የሥር የክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰጠዉ ዉሳኔ ተጠሪ ለእርሻ ሰራተኛ የተከፈለ እዳን በድርሻዋ ለአመልካች ልከፍላት አይገባም በማለት የመወሰኑን አግባብነት፣ ለመመርመር ሲባል የሰበር አቤቱታዉ ያስቀርባል በማለት ተጠሪ መልስ እንድትሰጥ ባዘዘዉ መሰረት በ6/2/2012 ዓ.ም በተጻፈ መልስ፣ የአማራ ክልል ጠቅላይ ሰበር ሰሚ ችሎት በዚህ ጉዳይ የአሁን ተጠሪ የሰራተኛ ደመወዝ የተባለዉን በድርሻዋ ለአሁን አመልካች መክፈል አይገባም በማለት የሰጠዉ ዉሳኔ ተገቢና ሕጋዊ ስለሆነ እንዲጸናልኝ በማለት በዝርዝር ክርክሯን አቅርባለች። የአሁን አመልካች የሰበር አቤቱታዉን በማጠናከር የመለሰ መልስ አቅርበዋል።

የጉዳዩ አመጣጥ ከፍ ሲል የተመለከተዉ ሲሆን ይህ ችሎት የግራ ቀኙ ክርክር አግባብነት ካላቸዉ የህግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ እንደሁም የሰበር አቤቱታዉ ያስቀርባል ሲባል ከተያዘዉ ጭብጥ አንጻር እንደሚከተለዉ መርምሮታል። እንደመረመርነዉ የአሁን አመልካች የእርሻ ሥራን ለሰራልን ለአቶ ግርማዉ ደጋረጋ ሊከፈል የሚገባዉን ደመወዝ የአሁን ተጠሪ ድርሻዋን ልትከፍል ይገባል በማለት ዳኝነት ለመጠየቅ መብትና ጥቅም አለዉ ወይስ የለዉም? የሚለዉ ነጥብ

መታያት ያለበት ጉዳይ መሆኑን ተገንዝበናል። እንግዲህ አቶ ግርማዉ ደጋረጋ የአሁን አመልካች ልጅ መሆኑን ከግራ ቀኙ እና ከሥር ፍ/ቤት የዉሳኔ ግልባጭ መገንዘብ ይቻላል። አቶ ግርማዉ ደጋረጋ በግራ ቀኙ ተቀጥረዉ የእርሻ ሥራ የሰራላቸዉ ከሆነ እና ሊከፍሉት የሚገባዉ የሥራ ዋጋ ወይም ደመወዝ ካለና መብት አለኝ የሚል ከሆነ አግባብነት ባለዉ የህግ ድንጋጌ መሰረት በማድረግ ፣በሕግ አግባብ ስልጣን ባለዉ ፍ/ቤት ክስ አቅርቦ ከመጠየቅ የሚከለክላቸዉ ነገር አልነበረም። የአሁን አመልካች ግን ይህን ግለሰብ ወክለዉ በዚህ ጉዳይ ዳኝነት የመጠየቅና እንዲወሰንልኝ ብሎ ለመጠየቅ በሕግ አግባብ የዉክልና ስልጣን የተሰጣቸዉ ወይም ከሕግ የመነጫ መብት ያላቸዉ መሆኑን የሚያሳይ ነገር የለም። ይህ ከሆነ ደግሞ አንድ ከሳሽ ለክስ ምክንያት በሆነዉ ነገር ወይም ክሱ በተመሰረተበት ነገር ሀብት ላይ ጥቅም ወይም መብት ያለዉ መሆኑን ካላረጋገጠ ክስ አቅርቦ ዳኝነት ለመጠየቅ እንደማይፈቀድለት የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.33 [2] ሥር ተመለክቷል። በዚህ አግባብ የተያዘዉ ጉዳይ ሲታይ የአሁን አመልካች አቶ ግርማዉ ደጋረጋ የእርሻ ሥራ ስለሰራልን በዚህ ምክንያት ልንከፍለዉ የሚገባዉን ደመወዝ የአሁን ተጠሪ ድርሻዋን እንድትከፍል በማለት ስለ ግርማዉ ደጋረጋ ክስ አቅርቦ ዳኝነት ጠይቆ እንዲወሰንለት የሚጠይቅበት የሕግ አግባብ የለም። ስለሆነም የአሁን አመልካች ለሰራተኛ የሚከፍል እዳ ቢኖር እንኳን የአሁን ተጠሪ ድርሻዋን ለገንዘብ ጠያቅዉ እንጂ ለአመልካች የምትከፍልበት አግባብ የለም፣ የሥር የወረዳዉ ፍ/ቤት እና የሥር የከፍተኛዉ ፍ/ቤት አመልካች በዚህ ጉዳይ መብትና ጥቅም የለዉም ብሎ የአመልካች የዳኝነት ጥያቄ ዉድቅ ማድረግ ሲገባቸዉ የሰጡት ዉሳኔ፣ የሥር የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመሻር የአሁን አመልካች ስለ ግርማዉ ደጋረጋ ዳኝነት እንዲወሰንለት ለመጠየቅ መብትና ጥቅም የለዉም በማለት በማረም የሰጠዉ ዉሳኔ በሕጉ አግባብ ነዉ ብለናል።

ሲጠቃለል የሥር የክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የአሁን አመልካች በእርሻ ሥራ ተቀጥሮ አገልግሏል በማለት የጠቀሰዉን አቶ ግርማዉ ደጋረጋ መብት በተመለከተ ይህ ግለሰብ ራሱ ሳይጠይቅ ስድስት ማዳበሪያ እህል እዳ አለብን ከዚህ ዉስጥ ተጠሪ ድርሻዋን ለአመልካች ልትከፍል አይገባም በማለት የሰጠዉ ዉሳኔ በሕግ አግባብ የተሰጠ እና መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ያልተፈጸመበት ስለሆነ የሚከተለዉ ተወስኗል።

<u>ዉ ሳ ኔ</u>

1. የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ.ቁ.74190 ግንቦት 13 ቀን 2011 ዓ.ም የሰጠዉ ዉሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት ያልተፈጸመበት ስለሆነ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.348 [1] መሰረት በአብላጫ ድምጽ ጸንቷል።
2. የዚህ ዉሳኔ ግልባጭ ለሥር ፍ/ቤቶች ይድረስ።
3. ግራ ቀኙ በዚህ ችሎት የደረሰባቸዉን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸዉን ይቻሉ።

4. ይህ ችሎት በ27/12/2011 ዓ.ም የሰጠዉ የአፈጻጸም የእግድ ትዕዛዝ በዚህ ዉሳኔ ተነስቷል። ይጻፍ።

መዝገቡ ተዘግቷል።

የማይነበብ የአራት ዳኞች ፊርማ አለበት

ስሜ በተራ ቁጥር 3ኛ ላይ የምገኘው ዳኛ የልዩነት ሀሳቤን እንደሚከተለው አስቀምጫለሁ

በስር ፍ/ቤት በተደረገው ክርክር በአሁን አመልካችና ተጠሪ መካከል የባልና ሚስት ንብረት ክርክር በተመለከተ የአሁን አመልካች የጋብቻ ፍቺ ተከትሎ በባልና ሚስት የጋራ ንብረት ላይ የጋራ የባልና ሚስት ለሰራተኛ የሚከፈል እዳ ያለ በመሆኑ የጋራ እዳ ተብሎ ይወሰንልኝ ሲል ጠይቋል። የአሁን ተጠሪም አመልካች ለሰራተኛ የሚከፈል የባልና ሚስት የጋራ እዳ ነው ሲል ያቀረበው እዳ የቀጠርነው ሰራተኛ የለም በሀሰት የቀረበ ነው፣ የባልና ሚስት የጋራ እዳ አይደለም ስትል ተከራክራለች። የስር የወረዳ ፍ/ቤትም የባልና ሚስት የጋራ እዳ በተመለከተ የግራ ቀኙን ማስረጃ ሰምቶ ለሰራተኛ የሚከፈል የባልና ሚስት የጋራ እዳ መኖሩን በራሱ በማስረጃ አጣርቶ የጋራ እዳ ነው ሲል ወስኗል። የከፍተኛ ፍ/ቤትም አጽንቶታል። የአሁን ተጠሪ ለክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አቤቱታ አቅርባ የአሁን አመልካች ለሰራተኛ የሚከፈል የባልና ሚስት የጋራ እዳ መሆን አለበት ሲል ያቀረበው ክርክር ተከፋዩ (ገንዘብ ጠያቂው) ወይም ባለመብት የተባለው ሰው ከባልና ሚስት ገንዘብ አለኝ ብሎ ሳይጠይቅ (ክስ ሳያቀርብ ወይም ጣልቃ ገብቶ ሳይከራከር) የባልና ሚስት የጋራ እዳ ነው ተብሎ መወሰኑ ስህተት ነው ሲል የስር ፍ/ቤት ውሳኔ በመሻር ወስኗል።

የባልና ሚስት የንብረት ክርክር በተመለከተ የክርክር ሂደቱ የቤተሰብ ህጉ በሚደነግገው መሰረት ግራ ቀኙ በዝርዝር በሚያቀርቡት የግል፣ የጋራ ንብረት እና የባልና ሚስት የጋራ እዳ የሆነውን ለይተው ስያመለክቱ ፍ/ቤቱ የህግ ግምት እንዳለ ሆኖ፣ ግራ ቀኙ በሚያቀርቡት ማስረጃ የባልና ሚስት የጋራ ንብረት የሆነው፣ የየግል ንብረታቸውን የሆነውንና የጋራ የባልና ሚስት እዳ የሆነውን በባለሙያ፣ በሽማግሌዎች ወይም በራሱ አጣርቶ የሚወስን ሲሆን፣ የባልና የሚስት የጋራ እዳ ነው ተብሎ የተወሰኑ የጋራ እዳዎችም ከባልና ሚስት የጋራ ንብረት ለባለመብቱ የሚከፈል ይሆናል። ባልና ሚስት በንብረት ላይ ክርክር በሚያደረጉበት ጊዜ ከባልና ሚስቱ ገንዘብ አለኝ የሚል ሰው አንዳንዴ በክርክር ውስጥ ጣልቃ ገብቶ ከባልና ሚስት የጋራ ንብረታቸው ገንዘብ እንዳለው ገልጾ የባልና ሚስት የጋራ እዳ ነው ተብሎ እንዲወሰንልት የሚጠይቅበት ጊዜ ያለ ሲሆን፣ ባልና ሚስት በንብረት ላይ ክርክር በሚያደረጉበት ጊዜ ከሁለቱ አንዳቸው የባልና ሚስት የጋራ እዳ እንዳለ ከማስረጃ ጋር አስደግፈው ስያመለክቱ ፍ/ቤት በግራ ቀኙ ሲታመን በእምነታቸው መሰረት የባልና የሚስት የጋራ እዳ መሆኑን የሚወስን ሲሆን በተካደ ጊዜ

በማስረጃ አጣርቶ የባልና ሚስት የጋራ እዳ መሆኑ ከተረጋገጠ የባልና ሚስት የጋራ እዳ ነው ሲል ይወስናል፡፡ በዚሁ ሁኔታ ሲሰራበትም ቆይቷል፡፡ ይሁንና የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የባልና ሚስት ንብረት ተርጣቶ የጋራ የባልና ሚስት እዳ መሆኑ ከተረጋገጠ በዚሁ መሰረት መወሰን ሲቻል ባለመብቱ በክሱ ውስጥ ገብቶ ባለመጠየቁ ጠያቂ የለም በሚል የባልና ሚስት የጋራ እዳ የለም ሲል ውሳኔ መስጠቱ የጋብቻ ፍቺ ውጤት የባልና ሚስት የንብረት ክርክር የንብረት ማጣራት ስርዓት ያልተከተለ በመሆኑ ስህተት የተፈጸመበት ነው፡፡ በክልሎችም ይሁን በፌደራል የቤተሰብ ህግ የባልና ሚስት የፍቺ ውጤት የባልና ሚስት የንብረት ክርክር የአማራ ብ/ክ/መ. የቤተሰብ ህግ አዋጅ ቁጥር 79/95 አንቀጽ 100 እና የተሻሻለው የፌ/የቤተሰብ ህግ አንቀጽ 89 ከባልና ሚስት አንደኛው ወይም ሁለቱም በጋራ በፍርድ የተረጋገጠባቸው ወይም ሁለቱም ያመኑት እዳ መኖሩ የታወቀ እንደሆነ ይኸው እዳ የባልና ሚስት ሀብት ከመከፋፈሉ በፊት ተቀንሶ የሚከፈል መሆኑን ይደነግጋል፡፡ ይሄውም አሰራሩ የተሻሻለው ፌ/የቤተሰብ ህግ አንቀጽ 83፣ 85 እና ተከታዮቹ በተደነገገው መሰረት የባልና ሚስት ንብረት በባለሙያ፣ በሽማግሌዎች፣ በፍ/ቤት በራሱ ወይም በባልና ሚስት ስምምነት በማጣራት ሲሆን ተጣርቶ በተረጋገጠው መሰረት እዳው የሚወሰን እንጂ ባለመብቱ ጣልቃ ገብቶ ካልተከራከረ በቀር እዳ የለም ተብሎ መወሰኑ የክርክር አመራር ስርዓት ጉድለት ያለበት መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል እላለሁ፡፡

የማይነበብ የአንድ ዳኛ ፊርማ አለበት

ስ/ጥ

የሰ/መ/ቁ. 200023

ጥቅምት 29 ቀን 2014 ዓ/ም

ዳኞች፡- ብርሃኑ አመነው

ተሾመ ሽፈራው

ሀብታሙ እርቅይሁን

ብርሃኑ መንግስቱ

ነፃነት ተገኝ

አመልካች፡- አንሲፍ ኮንስትራክሽ - ጠበቃ ሁሴን ይመር - ቀረቡ

ተጠሪ፡- አቶ ጥላሁን አበበ - አልቀረቡም

መዝገቡ ተምርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሠጠ፡፡

ፍርድ

የሰበር አቤቱታው የቀረበው የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በሠጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሞበታል በሚል ነው፡፡ የክርክሩን አመጣጥ ከስር ፍርድ ቤት የመዝገብ ግልባጭ እንደተረዳነው አመልካች በሥር ፍርድ ቤት ተከሳሽ፤ ተጠሪ ደግሞ ከሳሽ ነበሩ፡፡ ተጠሪ የሥራ ውላቸው አላግባብ ተቋርጧል በማለት ክስ አቅርበው አመልካች መጥሪያ ደርሶት አልቀረበም በሚል በሌለበት የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ለተጠሪ ክፍያዎችን እንዲከፍል ተወስኗል፡፡ አመልካች ሐምሌ 13 ቀን 2012 ዓ/ም በተጻፈ ማመልከቻ በ08/07/2012 ዓ/ም የተሰጠውን ውሳኔ ያወቅነው የአፈጻጸም መጥሪያ በደረሰን ጊዜ ነው፡፡ የተጠሪ ክስና መጥሪያ አልደረሰንም፡፡ ስለሆነም ውሳኔው ተነስቶ ክርክሩ አመልካች ባለበት እንደገና እንዲሰማ እንዲታዘዝልን በማለት በፍብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 78 መሠረት አቅርቧል፡፡ ተጠሪ ያቀረቡት መልስ አመልካች መጥሪያ ደርሶታል፡፡ መጥሪያውን አልቀበልም በማለቱ የቃለ መሃላ ማመልከቻ ማረጋገጫ ቀርቦ በሌለበት ታይቷል፡፡ አቤቱታው ተቀባይነት የለውም ብለዋል፡፡

የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የአመልካችን ማመልከቻ መርምሮ አመልካች መልስ የማቅረብ መብቱ ታልፎ በሌለበት ውሳኔ የተሠጠው የአመልካች ድርጅት የሰው ሀብት ክፍል ኃላፊ መጥሪያውን አልቀበልም ማለቱ በተጠሪ ምስክሮች ተረጋግጧል፡፡ መጥሪያ ለአመልካች የደረሰው ስለመሆኑ ፍርድ ቤቱ ስለተገነዘበ በሌለበት የተሰጠው ውሳኔ ሊነሳ አይገባም በማለት ወስኗል፡፡ አመልካች ለፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ያቀረበውን ይግባኝ ባለመቀበል ሠርዟል፡፡

ይህ የሰበር አቤቱታ የቀረበው በዚህ ውሳኔ ነው፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ ይዘትም አመልካች የንግድ ድርጅት ሲሆን ተጠሪ በፍብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 97(ሀ) ለተመለከቱት ሠዎች መጥሪያው መድረሱን

አላረጋገጡም፡፡ መጥሪያውን አልቀበለም ካለ ምትክ መጥሪያ ሊወጣ ይገባ ነበር፡፡ መዝገቡ ተዝግቶ ሲንቀሳቀስ ድጋሚ መጥሪያ ሊሰጥ ሲገባ መዝገቡ ተንቀሳቅሶ ክርክሩ አመልካች በሌለበት መቀጠሉ የሥነ-ሥርዓት ሕጉን የተከተለ አይደለም የሚል ነው፡፡ የሰበር አጣሪ ችሎት ጉዳዩን ተመልክቶ የአመልካች ጥያቄ በፍብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 78 መሠረት መስተናገዱ ተገቢነቱን ለመመርመር ለሰበር ችሎት ያስቀርባል በማለት ተጠሪ መልስ እንዲያቀርቡ አዟል፡፡ ተጠሪ የሠጡት መልስ የአመልካች አቤቱታ በሌሉበት የተሠጠው ውሳኔ ሊነሳ ይገባል የሚል ሲሆን ማስረጃ ተሰምቶ መጥሪያ መድረሱ ተረጋግጦ የተወሰነ ስለሆነ ውሳኔው ላይ የተፈጸመ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የለም ብለዋል፡፡ አመልካች የመልስ መልስ በማቅረብ የሠበር አቤቱታውን በማጠናከር ተከራክሯል፡፡

የክርክሩ ሂደት በአጭሩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን እኛም በፍብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 78 መሠረት የቀረበው ማመልከቻ ውድቅ መደረጉ የሥነ-ሥርዓት ሕጉን የተከተለ ስለመሆን አለመሆኑ? በጭብጥነት በመያዝ መዝገቡን መርምረናል፡፡

እንደመረመርነው አመልካች በፍብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 78 መሠረት ያቀረበው ማመልከቻ ውሳኔ መሰጠቱን ያወቅነው የአፈጻጸም መጥሪያ በደረሰን ጊዜ ነው፡፡ የተጠሪዎች ክስና መጥሪያ አልደረሰንም፡፡ ውሳኔው ተነስቶ ክርክሩ አመልካች ባለበት እንደገና እንዲሰማ እንዲታዘዝልን የሚል ነው፡፡ ክርክሩን በፍትሐ ብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕጉ መሰረት መምራት እና መቆጣጠር የፍርድ ቤቱ ኃላፊነት ሲሆን በተገቢው ሁኔታ ካልተመራ የሥነ-ሥርዓት ሕጉን ዓላማዎች የሆኑትን እንደ አንጻራዊ እውነትን የመፈለግ፣ ሥነ-ሥርዓታዊ ፍትህ፣ ክርክርን ውጤታማ፣ ወጭና ጊዜ ቆጣቢ በሆነ አግባብ መምራት የመሳሰሉትን ማሳካት ስለማይቻል የተከራካሪዎችን መብት ይነካል፡፡ የሕግ ሥርዓት ሂደት ሙግት ከፍርድ ሊቀድም ይገባል የሚለውን መርህ የሚከተል ሲሆን በፍትሐ ብሔር ሆነ በወንጀል ክርክር ሂደቶች ያለ መብት ነው፡፡ ከተከሳሽ አኳያ በነፃና ገለልተኛ የዳኝነት አካል የመዳኘት፣ ክሱን የማወቅ መብት፣ የመደመጥ መብት (መከላከያ ክርክር ማቅረብ፣ የከሳሽን ማስረጃ የማወቅና በማስረጃው ላይ ክርክር ማቅረብና ምስክሮችን የመጠየቅ መብት እና የራሱን ማስረጃ የማቅረብ መብትን ያካትታል፡፡)፣ የሚሰጠው ውሳኔ በሕግና በምክንያት ላይ የተመሠረተ ብቻ እንዲሆን እና ሌሎች ተያያዥ መብቶችን ያካተተ ሰፊ መብት ነው፡፡ በፍትሐ ብሔር ክርክር ተከሳሽ በከሳሽ የቀረበበትን ክስ እንዲያውቅ ማድረግ መሰረታዊ ሂደት ነው፡፡ ክሱን ከማወቅ ባሻገር የመደመጥ መብቱን ማክበር ሂደቱን ሙሉ ያደርገዋል፡፡

መልስ የማቅረብ መብት በሥነ-ስርዓታዊ የሕግ ሥርዓት ሂደት ውስጥ ያለ መብት በመሆኑ የሥነ-ስርዓታዊ የሕግ ሥርዓት ሂደት የያዛቸውን ዝርዝር ፍሬ ነገሮች መመልከቱ ተገቢ ነው፡፡ ሥነ-ስርዓታዊ የሕግ ሥርዓት ሂደት የራሱ ክፍሎች አሉት፡፡ በመጀመሪያ በልዩ ሁኔታ ተከሳሽ ጉዳዩ በሌለበት ቢታይም በመርህ ደረጃ ተከሳሹ በውሳኔ አሰጣጥ ሂደቱ ላይ የመሳተፍ መብት አለው የሚለው ነው፡፡ ክሱን እንዲያውቀው መደረግ አለበት፡፡ የቅድሚያ ማወቅ መብት ለተከሳሹ ጉዳዩ መድረሱን በሚገባ

ማረጋገጥና ለተከሳሹ የደረሰውም ለመከላከል በሚያስችል መልኩ የክሱና የሁኔታው ዝርዝር ነገር ስለመሆኑ የሚያካትት ነው፡፡ ተከሳሹ ክስ እንደቀረበበት ካላወቀ በፍርድ አሰጣጡ ሂደት ሊሳተፍ አይችልም፤ የመደመጥ መብት ካልተከበረ፤ ተከሳሹ ክርክሩንና ማስረጃውን እንዳያቀርብ ያደርገዋል እንዲሁም የዳኝነት አካሉ ክርክሩን ከግራ ቀኙ ተከራካሪ ወገኖች ካላደመጠ ደግሞ ለእውነቱ የቀረበና ውጤታማ ፍርድ መስጠት አይችልም፡፡ ፍርድ ቤቶች የተከሳሽን መልስ የማቅረብ መብት ከማለፋቸው በፊት ተገቢውን ጥንቃቄ እንዲያደርጉ ሕጉ ኃላፊነት ጥሎባቸዋል፡፡ መልስ የማቅረብ መብቱ ታልፎ ጉዳዩ በሌለበት የተወሰነ ተከራካሪ መብቱን የሚያስከብርበት ሥርዓት መቀረጹም የመደመጥ መብቱ አካል ነው፡፡

ፍርድ ቤቶች መጥሪያ ሲልኩ ተከሳሽ የሆነው ወገን የተፈጥሮ ሰው ወይም የንግድ ድርጅት መሆን አለመሆኑን በመለየት በሥነ-ሥርዓት ሕጉ በተዘረጋው ሥርዓት አግባብ መጥሪያው ወጪ መሆኑንና መድረሱን በማረጋገጥ የመደመጥ መብት መከበሩን የመከታተልና የመቆጣጠር ኃላፊነት አለባቸው፡፡ በተያዘው ጉዳይ አመልካች በንግድ ሕጉ መሠረት የተመዘገበ የንግድ ማሕበር/ድርጅት አይደለም፤ አመልካች ነጋዴ ቢሆንም የንግድ ድርጅት ባለመሆኑ ከመነሻውም ክሱ በንግድ ሥሙ ቀርቦ ክርክሩ መመራቱ ተገቢ አይደለም፡፡ የንግድ ድርጅት ባለመሆኑ በፍብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 97 የተመለከተውን የመጥሪያ አደራረስ ሥርዓት ሊከተል አይችልም፡፡ ነጋዴ ሥራውን ሊሰራለት የሚችል ሠራተኛ መቅጠር የሚችል ቢሆንም ሠራተኛው ነጋዴውን ወክሎ መጥሪያ ለመቀበል ሥልጣን ያለው መሆኑ እስካልተረጋጠ ድረስ የሥነ-ሥርዓት ሕጉ ዓላማ የሆኑትን አንጻራዊ እውነት የመፈለግና ፍትሐዊነትን በሚያሳካ መልኩ የመደመጥ መብትን በተሟላ አግባብ በሚያስከብር ሁኔታ ለሕጉ ውጤት ሊሰጠው ስለሚገባ መጥሪያው ሊደርስ የሚገባው በአካል የተፈጥሮ ሰው ለሆነው ለነጋዴው ነው፡፡ በተያዘው ጉዳይ ተጠሪ መጥሪያውን ለመስጠት የሞከሩት ለአመልካች ሠራተኛ ሲሆን ሠራተኛው የሠው ኃይል ክፍል ኃላፊ ቢሆንም መጥሪያ ለመቀበል ውክልና እስከሌላቸው ድረስ መጥሪያውን አልቀበልም ማለታቸው ሕጋዊ ተግባር ነው፡፡ ስለሆነም የአመልካች ሠራተኛ መጥሪያውን አልቀበልም ብለዋል በሚል አመልካች ክርክሩ በሌለበት መታየቱ ሆነ በፍብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 78 መሠረት ያቀረበው ማመልከቻ ውደቅ መደረጉ በሥነ-ሥርዓት ሕጉ የተዘረጋውን የመደመጥ መብት ያላከበረና መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

ውሳኔ

1. የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 257931 ታህሳስ 14 ቀን 2013 ዓ/ም እና የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 109523 ሕዳር 22 ቀን 2013 ዓ/ም የሠጡት ውሳኔ በፍብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348(1) መሰረት ተሽሯል፡፡

2. የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 109523 መጋቢት 08 ቀን 2012 ዓ/ም የሠጠው ውሳኔ ተነስቷል፡፡

3. የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ተጠሪ ላቀረቡት ክስ አመልካች የጽሁፍ መልስ እንዲያቀርብ በማድረግ ክርክሩን በሕግ መሠረት በመምራት እንዲወስን ጉዳዩን በፍብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 341(1) መሠረት መልሠናል፡፡

4. በዚህ ችሎት ለወጣ ወጭና ኪሣራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

ትዕዛዝ

- የውሳኔው ግልባጭ ለስር ፍርድ ቤቶች ይተላለፍ፡፡ የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በውሳኔው መሠረት እንዲፈጽም አዘናል፡፡ ይጻፍ
- አፈጻጸሙ ላይ የተሠጠው እግድ ተነስቷል፡፡ ይጻፍ
- መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

አ/ን

የሰ/መ/ቁጥር 201028

ጥቅምት 05 ቀን 2014 ዓ/ም

ዳኞች፡- ብርሀኑ አመነው

ተሾመ ሽፈራው

ሀብታሙ እርቅይሁን

ብርሀኑ መንግስቱ

ነፃነት ተገኝ

አመልካች፡- የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት ሶማሌ ሪጅን - አልቀረቡም

ተጠሪዎች፡- አቶ አህመድ እስማኤል የሱፍ - አልቀረቡም

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍርድ

ጉዳዩ የይግባኝ ማስፈቀጃን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ በተጀመረበት በሶማሌ ክልል መንግስት የፋፈን ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት የአሁን አመልካች ተከሳሽ ተጠሪ ደግሞ ከሳሽ በመሆን ተከራክረው ፍርድ ቤቱ በ18/06/2012 ዓ.ም. ውሳኔ ሰጥቷል፡፡ አመልካች በዚህ ውሳኔ ላይ የይግባኝ ቅሬታ ለማቅረብ ጊዜ ያለፈበት መሆኑን ጠቅሶ ለማቅረብ እንዲፈቀድለት ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በ22/11/2012 ዓ.ም. የተጻፈ አቤቱታ አቅርቦ የአመልካች የይግባኝ ማስፈቀጃ አቤቱታ ተቀባይነት አግኝቶ የይግባኝ ቅሬታውን እንዲያቀርብ ተፈቅዶለታል፡፡ አመልካችም የይግባኝ መዝገብ አስከፍቶ የይግባኝ ክርክሩ ቀጥሎ እያለ ፍርድ ቤቱ ተጠሪ የይግባኝ ማቅረቢያ ጊዜ አልፏል በማለት ያቀረቡትን ተቃውሞ በመቀበል የአመልካች የይግባኝ ቅሬታ የይግባኝ ማቅረቢያ 60 ቀን ካለፈ በኋላ የቀረበ ነው በማለት የይግባኝ መዝገቡን ዘግቶታል፡፡

አመልካች በ10/05/2013 ዓ.ም. የተጻፈ የሰበር ቅሬታ ያቀረበው የሱማሌ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የይግባኝ ቅሬታውን የማቅረቢያ ጊዜ ያለፈበት ነው በማለት መዝገቡን መዝጋቱን በመቃወም ለማሳረም ነው፡፡ የቅሬታው ይዘት ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የይግባኝ ማስፈቀጃ አቅርቦ ይግባኙ እንዲከፈት ተፈቅዶልኛል፡፡ የይግባኝ ፋይል ተከፍቶ ወደክርክር ከተገባ በኋላ ይግባኙ ሊከፈት ይገባል ያለው ፍርድ ቤት የይግባኝ ጊዜው አልፏል በማለት መዝገቡን መዝጋቱ በአንድ ጉዳይ ሁለት የተለያየ ውሳኔ በመስጠት መሰረታዊ የህግ ስህተት መፈጸሙን ያመለክታል፡፡ የይግባኝ ማቅረቢያ ጊዜ ሊያልፍ የቻለውም የውሳኔ ግልባጭ ዘግይቶ ስለደረሰን ነው፡፡ የውሳኔ ግልባጭ በደረሰን

በ8 ቀን ውስጥ ለጠቅላይ ፍርድ ቤቱ ይግባኙን አዘጋጅተን ቀርበናል። በመሆኑም በፍርድ ቤቱ ምክንያት የባከነው ጊዜ በይግባኝ ማቅረቢያ ጊዜ ውስጥ ሊካተት ስለማይገባ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ትእዛዝ ይታረምልኝ በማለት ጠይቋል።

የሰበር አጣሪ ችሎትም የአመልካችን የሰበር ቅሬታ መርምሮ አመልካች ያቀረበው የይግባኝ ማስፈቀጃ ተቀባይነት አግኝቶ ወደክርክር ከተገባ በኋላ የይግባኙን መዘጋት አግባብነት ከፍ/ስ/ስ/ህ/ቁጥር 326/1 አተገባበር አንጻር ለማጣራት ያስቀርባል በማለት ተጠሪ መልስ እንዲያቀርቡ አዟል።

ተጠሪም በ30/06/2013 ዓ.ም. ጽፈው ባቀረቡት መልስ አመልካች የይግባኝ ማስፈቀጃ አላቀረበም። ፍርድ ቤቱም በቀረበው ማስፈቀጃ ላይ ተጠሪን አስተያየት እንድሰጥ አላደረገም። አመልካች በ10 ቀን ውስጥ ይግባኙን እንዲያቀርብ የተሰጠ ትእዛዝም የለም። አመልካች የይግባኝ ማቅረቢያ ጊዜው ያለፈበት በበቂ ምክንያት ከሆነም የሰበር ቅሬታ ከማቅረብ ይልቅ ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የይግባኝ ማስፈቀጃ ማቅረብ ነበረበት። በመሆኑም የአመልካች የሰበር ቅሬታ ውድቅ ሊደረግ ይገባል በማለት ተከራክሯል።

አመልካችም በ13/07/2013 ዓ.ም. የተጻፈ የመልስ መልስ በማቅረብ የሰበር ቅሬታውን አጠናክሯል።

ከስር ጀምሮ የጉዳዩ አመጣጥ እና የግራ ቀኝ ክርክር ይዘት አጠር ባለ መልኩ ከላይ የተገለፀውን ሲመስል ይህ ችሎትም መዝገቡን ለማስቀረብ በሰበር አጣሪ የተያዘውን ጭብጥ ከግራ ቀኝ ክርክር እና ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸዉ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ መዝገቡን እንደሚከተለዉ መርምሮታል።

እንደመረመረዉም የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የአመልካች የይግባኝ አቤቱታ የቀረበዉ የይግባኝ ማቅረቢያ ጊዜዉ ካለፈ በኋላ ነዉ በማለት ዉድቅ ማድረጉን ለመገንዘብ ተችሏል። በሌላ በኩል ጠቅላይ ፍርድ ቤቱ እራሱ የይግባኝ ማስፈቀጃ አቤቱታ ቀርቦለት ይግባኙ እንዲከፈት የፈቀደ መሆኑን አመልካች ገልፆ ይከራከራል። ተጠሪ በበኩላቸው የይግባኝ ማስፈቀጃ አቤቱታ አመልካች አለማቅረቡን እና አመልካች ይግባኙን እንዲያቀርብ ያልተፈቀደ መሆኑን በመግለጽ ክርክር አቅርበዋል። የሰበር አጣሪ ችሎት አመልካች የይግባኝ ማስፈቀጃ አቅርቦ የተሰጠውን ትዕዛዝ ግልባጭ ከዚህ መዝገብ ጋር አያይዟል። ትዕዛዙን መርምረን እንደተረዳነዉ የይግባኝ ማቅረቢያ ጊዜ ያለፈ መሆኑን ጠቅሶ የይግባኝ ማስፈቀጃ ያቀረበበት ምክንያት ተቀባይነት እንዳገኘ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 05-1-161-12 በ01/12/2012 ዓ.ም. በዋለዉ ችሎት ትእዛዝ በመስጠት አመልካች ይግባኙን እንዲያቀርብ ፈቅዷል። ይህን ካደረገ በኋላ እንደገና ተመልሶ ተጠሪ ይግባኙ ጊዜው ካለፈ በኋላ የቀረበ ነው የሚል መቃወሚያ ማንሳታቸውን ተከትሎ በ25/02/2013 ዓ.ም በዋለዉ ችሎት የአመልካች የይግባኝ አቤቱታ የቀረበው የማቅረቢያ ጊዜ ካለፈ በኋላ ነዉ በማለት አቤቱታዉን ዉድቅ ማድረጉንም ከትእዛዙ ለመገንዘብ ተችሏል።

በመሠረቱ ከፍትሐብሔር ጉዳዮች አመራር ሥርዓት ጋር በተያያዘ ፍርድ ቤቱ የሚሰጣቸዉ ትዕዛዞች እና ዉሳኔዎች የሚከለሱባቸዉ ሥርዓቶች በመሠረታዊነት ሁለት ሲሆኑ አንድም ፍርዱን/ዉሳኔዉን/ትዕዛዙን በሰጠዉ ፍርድ ቤት በእራሱ (review by the court of rendition) ሲሆን ሁለተኛዉ በይግባኝ ሥርዓት ነዉ፡፡ ፍርድ ቤት እራሱ የሰጠዉን ፍርድ/ዉሳኔ/ትዕዛዝ እራሱ የሚከልስባቸዉ ሁኔታዎችም አንደኛ የዳግም ዳኝነት ጥያቄ ሲቀርብ (አንቀጽ 6)፣ ሁለተኛ የሥ/ሥርዓት ግድፈት የተፈጸመ ሲሆን (አንቀጽ 207-211) እና ሦስተኛ የመቃወም አቤቱታ ሲቀርብ (አንቀጽ 358) ስለመሆኑ መገንዘብ ያስፈልጋል፡፡ የፍትሐብሔር ክርክሮች በዘፈቀደ ሳይሆን በስርዓት መመራት እንዳለባቸዉም የሚታወቅ ነዉ፡፡ የትኛዉ ጉዳይ በማን፣ እንዴት እና መቼ መፈጸም (መከናወን) እንደሚገባዉ በፍ/ብ/ሥ/ሥርዓት ህጉ በተለያዩ አንቀፆች ላይ የተመለከቱት ድንጋጌዎችም ይህንኑ ያስገነዝባሉ፡፡ ይህም ማለት ክርክሮች በሥርዓት እንጂ በዘፈቀደ ሊመሩ አይገባም በሚል ሃሳብ መነሻነት ፍርድ ቤቶች በፍትሐብሔር ጉዳዮች አመራር ረገድ የሚሰጧቸዉ ዉሳኔዎች/ትዕዛዞች ለጉዳዩ ተፈፃሚነት ያላቸዉን የሥ/ሥርዓት ህጉን ድንጋጌዎች እና መርሆዎችን መሠረት ያደረጉ ስለመሆኑ የማረጋገጥ ኃላፊነት እንዳለባቸዉም እሙን ነዉ፡፡

በተያዘዉ ጉዳይ ላይ ከይግባኝ ማቅረቢያ ጊዜ ጋር በተያያዘ የሚቀርበዉ ክርክር በባህሪዉ ፍርድ ቤት በእራሱ የእራሱን ዉሳኔ/ትዕዛዝ ሊከልስ ከሚችልባቸዉ ሁኔታዎች ዉስጥ የሚካተት አይደለም፡፡ ስለሆነም የይግባኝ ማቅረቢያ ጊዜ አላለፈበትም የሚል ትዕዛዝ ከሰጠ በኋላ እንደገና ይህንኑ ትዕዛዝ እራሱ በመከለስ የማቅረቢያ ጊዜዉ አላለፈም በማለት የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሊወስን የሚችልበት የህግ ምክንያት የለም፡፡ ከዚህ ጋር በተያያዘ ተጠሪ አመልካች የይግባኝ ማስፈቀጃ ሲያቀርብ አስተያየት እንድሰጥ አልተደረገም በሚል ያቀረቡትን ክርክር ስንመለከት በእርግጥ አመልካች ይግባኝ እንዲያቀርቡ በተፈቀደበት ትእዛዝ ላይ ተጠሪ በአመልካች የይግባኝ ማስፈቀጃ አቤቱታ ላይ አስተያየት እንዲሰጡ ስለመደረጉ አያሳይም፡፡ የይግባኝ ማስፈቀጃ ሲቀርብ ፍርድ ቤቱ የፈቃድ ጥያቄ ማመልከቻው ተቀባይነት ያገኛል ብሎ ሲያስብ መልስ ሰጪ ወይም ተጠሪ የሆነ ወገን አስተያየት እንዲሰጥ ማድረግ እንደሚገባው በፍ/ስ/ስ/ህ/ቁጥር 325/3 ላይ ተመልክቷል፡፡ በዚህ መልኩ ተጠሪ አስተያየት እንዲሰጡ አለመደረጉ የስነ ስርዓት ግድፈት የተፈጸመበት መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ ስህተቱ ሊታረም የሚችለው ተጠሪ ደረጃውን ጠብቀው ይግባኝ በማቅረብ እንጂ በዚህ ደረጃ ስህተቱ የሚታረምበት የህግ አግባብ የሌለ በመሆኑ ተጠሪ በዚህ ረገድ ያቀረቡትን ክርክር አልተቀበልነውም፡፡ በመሆኑም የሶማሌ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በዚህ ረገድ የሰጠዉ ዉሳኔ መሠረታዊ የክርክር አመራር ሥርዓት ግድፈት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም የሚገባዉ ሆኖ ስለተገኘ ተከታዩ ተወስኗል፡፡

ውሳኔ

1. የሶማሌ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁ. 05-1-161/12 በቀን 25/02/2013 ዓ.ም በዋለዉ ችሎት የሰጠው ትእዛዝ በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ 348(1) መሠረት ተሽሯል፡፡

2. የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ተዘግቶ የነበረዉን መዝገብ በማንቀሳቀስ ከዋናዉ ጉዳይ ጋር በተያያዘ የግራ ቀኙን ክርክር ሰምቶ የመሰለዉን እንዲወስን መዝገቡ በፍ/ብ/ሥ/ሥርዓት ህጉ አንቀጽ 341(1) መሠረት ተመልሶለታል፡፡

3. በዚህ ችሎት የተደረገው ክርክር ያስከተለውን ወጪ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

ማ/አ **የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት**

የሰ/መ/ቁ. 226569

ቀን፡- ሚያዚያ 26 ቀን 2015 ዓ/ም

ዳኞች፡- እትመት አሰፋ

ደጀኔ አያንሳ

ብርቅነሽ እሱባለው

ሀብታሙ እርቅይሁን

ብርሃኑ መንግስቱ

አመልካች፡- አቶ ይስማው ድረስ

ተጠሪ፡- 1. አቶ ባህሩ ዓለሙ } በVC ቀረቡ

2. ወ/ሮ መሀሌ አዱኛ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሠጠ፡፡

ፍ ር ድ

የሰበር አቤቱታው የቀረበው የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሞበታል በሚል ነው፡፡ የክርክሩን አመጣጥ ከስር ፍርድ ቤት የመዝገብ ግልባጭ እንደተረዳነው አመልካች በስር ፍርድ ቤት ከሳሽ፤ ተጠሪዎች ተከሳሾች ሆነው ተከራክረዋል፡፡ ጉዳዩ የተጀመረው በእስቴ ወረዳ ፍርድ ቤት ሲሆን አመልካች በ15/07/2013 ዓ/ም ባቀረቡት ክስ በ1989 ዓ/ም እስቴ ወረዳ ልጫ ቀበሌ በዛሬው ስነ-ህይወት ከተማ መጠኑ አንድ ቃዳ መሬት ተሰጥቼ ደብተር አሰርቼ የያዝኩትን መሬት በምስራቅ በኩል ተጠሪዎች በግምት 500 ካሬ ሜትር በ1994 ዓ/ም በኪራይ ቤት አማካኝተው ቤቱን ከሰሩ በኋላ በመሬቱ ላይ በድብቅ ደብተር በማሰራት መሬቱን ስለያዘብኝ የሠሩትን ቤት አፍርሰው መሬቱን እንዲለቁልኝ በማለት ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡

ተጠሪዎች በ29/07/2013 ዓ/ም ባቀረቡት የመከላከያ መልስ በአመልካች ደብተር የተጠቀሰውን መሬት አልያዝንም፤ ከሃያ ዓመት በፊት ከባህር ዳር መንገድ ዳር በህገ-ወጥ መንገድ ሠርተን የያዝነው ይዞታ ስለነበር ከተማው ሲጠና እና በመሀንዲስ ሲሸነሸን 369 ካሬ ሜትር ጸድቆልን የያዝነው ነው፡፡ በ2011 ዓ/ም በድንበር ግፊ ተጣልተን ድንበራችንን ሲሚዛ አድርገን ገደብ 5000 ብር አስቀምጠን ታርቀን እያለ ክስ መመስረቱ አግባብ አይደለም፡፡ ቦታው ወደ ከተማ ገብቶ ሲሸነሸን በገጠሩ እና በከተማው ህዝብ የልጫ ስነ-ህይወት ከተማ ማዘጋጃ ቤት አስገምግሞ የማንም ሳይሆን የእኛ ይዞታ መሆኑ ተረጋግጦ አመልካች አብሮ ገምግሞ ነው ካርታ የተሠራልን፡፡ አመልካችም ምንአልባት ቦታው የእሱ ከሆነ መጠየቅ ያለበት የሰጠበትን አካል እንጂ እኛን ስላልሆነ ክሱ ውድቅ እንዲደረግልን፤ ከፈለገም ቦታውን

እና ቤቱን ያጸደቀው የልጫ ስነ-ህይወት ከተማ ማዘጋጃ ቤት ዋቢ ይለፍልን በማለት የመከላከያ መልሳቸውን አቅርበዋል።

የእስቴ ወረዳ ፍርድ ቤቱም ማስረጃ በመስማት መሬቱን አመልካች በ1989 ዓ/ም ከተመራው መሬት ላይ በ1994 ዓ/ም ለተጠሪ 600 ብር ባዶውን እንደሸጠላቸው፤ የተጠሪን ቤት የሠሩት ያለ አመልካች ተቃውሞ መሆኑን፤ ሙሉው ቦታ ላይ ቤት እንደሠሩበት ተረጋግጧል። ባዶ ቦታ ደግሞ እንደማይሸጥ እና እንደማይለወጥ የህገ-መንግስቱ ቀጥር 40/3 እና የክልሉ የመሬት አዋጅ ቁጥር 252/2009 ቁጥር 5/1 የሚደነግጉ በመሆኑ የባዶ ቦታ ሽያጭ ውል ህገ ወጥ ውል ነው፤ ሕገ-ወጥ ውል ፈርሶ ተዋዋይ ወገኖች ወደ ነበሩበት ሊመለሱ ወይም በፍ/ብ/ህግ ቁጥር 1817 መሠረት ውሉ ጉድለት ቢኖርበትም ውሉ የሚረጋበት ሁኔታ ሊኖር እንደሚችል ይደነግጋል። ድንጋጌውም ውሉ በመፍረሱ ምክንያት አንደኛው ተዋዋይ ወገን ያልተገባ ጥቅም እንዲያገኝ አንደኛው ተዋዋይ ወገን ደግሞ ውሉ በመፍረሱ ወይም በመሰረዙ ምክንያት የከፋ እና የማይተካ ጉዳት እንዳይደርስበት ለማጣጣም ያለመ ነው። አሁን በተያዘው ጉዳይ ላይም ተጠሪዎች ባዶ ቦታ ገዝተው ቤቱ የሠሩበት መሆኑ ቢረጋገጥም ሙሉ ቦታው ላይም ቤት እንደሰሩበት ስለተረጋገጠና ቤቱ ይፍረስ ቢባል ተጠሪዎች ላይ ከፍተኛ ጉዳት የሚያስከትል በመሆኑ የሽያጭ ውሉ ሊጸና ይገባል፤ አመልካችም ተጠሪዎች ቤቱን አፍርሰው ቦታውን እንዲለቁት ሊጠየቅ አይገባም በማለት ወስኗል።

የደቡብ ጎንደር ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት የአመልካችን የይግባኝ አቤቱታ ባለመቀበል ሰርዘዋል። አመልካች በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት የሰበር አቤቱታቸውን ለአማራ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ያቀረቡ ሲሆን ፍርድ ቤቱም የውሉ መፍረስ ውጤት ወደ ነበሩበት መመለስ በመሆኑ ግራ ቀኙ ያልተገባ ጥቅም የማያስገኝ እና በአንደኛው ወገን ላይ ከፍ ያለ ጉዳት የማይደርስ መሆኑ ሲረጋገጥ የሚፈጸም ሲሆን በተያዘው ጉዳይ የሽያጭ ውሉ የተከናወነው በ1994 ዓ/ም ሆኖ ተጠሪዎች ቤት ሠርተው እየኖሩበት ያለ በመሆኑ እና ወደ ነበሩበት ይመለሱ ቢባል ቤት ማፍረስ እና አንስቶ መልቀቅ በተጠሪዎች ላይ ከፍተኛ ጉዳት የሚያደርስ በመሆኑ ሌላ ማጣራት የሚያስፈልገው ፍሬ ነገር ስለሆነ እና ጉዳዩም ዳኝነት ያልተጠየቀበት ነጥብ በመሆኑ የስር ፍርድ ቤቶች ወሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለው ሆኖ አላገኘነውም በማለት ውሳኔውን አጽንቷል።

ይሕ የሠበር አቤቱታ የቀረበው በዚህ ውሳኔ ነው። አመልካች በቀን 04/09/2014 ዓ/ም በጻፉት የሰበር አቤቱታ ይዞታው በ1989 ዓ/ም፤ በ1996/97 በተደረገው የመሬት ቆጠራ እና ምዝገባ ወቅት የአመልካች ሆኖ የተመዘገበ መሆኑ፤ ተጠሪዎች በተጭበረበረ መንገድ የወሰዱት ደብተር በመ/ቁ ገ/ጠ/አስ/አጠ/5105/38 በ12/20/2010 ዓ/ም የተሰረዘ መሆኑ በወረዳ ፍርድ ቤት ተረጋግጦ፤ በወረዳ ፍርድ ቤት በተደረገው የማጣራት ሂደት ተጠሪዎች መሬቱን የያዙት በግዢ እንደሆነ ተረጋግጦ እያለ ይህንን በሚቃረን መልኩ የወረዳ ፍርድ ቤት ህገ-ወጥ ውል ቢሆንም ወደነበረበት ቢመለስ በተጠሪዎች

ላይ የከፋ ጉዳት ሊደርስ ስለሚችል የጸና ውል ነው ማለቱ የአመልካችን መብት የሚጎዳ ስለሆነ የተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ ተሽሮ ትክክለኛ ውሳኔ እንዲሰጠኝ የሚል ነው።

የሠበር አጣሪ ችሎት ጉዳዩን ተመልክቶ የስር ፍርድ ቤቶች በአመልካች እና ተጠሪዎች መካከል የተፈጸመው የመሬት ሽያጭ ውል ህገ-ወጥ ቢሆንም ውሉ ፈርሶ ወደ ነበሩበት እንዲመለስ ማድረግ በአንደኛው ወገን ላይ ከፍ ያለ ጉዳት የማያደርስ ከሆነ ብቻ ነው፤ በተያዘው ጉዳይ ላይ በተጠሪ ላይ ከፍ ያለ ጉዳት የሚያደርስ ስለሆነ ውሉ ሊፈርስ አይገባም ተብሎ የተወሰነበት አግባብነት መጣራት ያለበት መሆኑ ስለታመነበት ጉዳዩን ለመመርመር ተጠሪዎች የመከላከያ መልሳቸውን ይዘው እንዲቀርቡ ትዕዛዝ ሰጥቷል። ተጠሪዎች በ15/05/2015 ዓ/ም በተጻፈ የመከላከያ መልስ ክርክራችን ድንበር ገፍኸኝ ስለሆነ መጣራት ያለበት ተጠሪዎች የአመልካችን ይዞታ ገፍተው ቤት ሠርተዋል ወይስ አልሠሩም የሚለው ነው መሆን ያለበት። ይዞታው በምንም መልኩ ይያዝ ይዞታውን ከ1994 ዓ/ም ጀምሮ የያዘው መሆኑ በህዝብ የተረጋገጠ እና የይዞታ ደብተሬን አስረክቤ ካርታ እና ፕላን የተሰጠኝ በመሆኑ፤ በተሰጠኝ መሬት ከአመልካች ጋር በድንበር ግፊ ተስማምተን ድንበራችን ለይተን አመልካችም ይዞታው የእኔ መሆኑን አረጋግጦ ማንም ሳይቃወመኝ በ396 ካሬ ሜትር ላይ ሙሉውን ቤት ሠርቼ ቤተሰቦቼን የማስተዳድርበት ቤት መሆኑ በበቂ ማስረጃ የተረጋገጠ እና ድንበራችንን ለይተን የተስማማን ለመሆኑ ያመነ በመሆኑ፤ የአመልካች እና የተጠሪ አዋሳኝ የተለያየ እና አንዳችን ለአንዳችን ድንበር ያልገፋን ለመሆኑ በተሰጠን ካርታ ማዘጋጃ ቤት አረጋግጦ ማስረጃ የሰጠ በመሆኑ የአመልካች አቤቱታ ውድቅ እንዲደረግልን። ተጠሪ በስር መልሴ ላይ የአመልካች አዋሳኝ እና የተጠሪ አዋሳኝ የተለያየ እና የየራሳችንን ካርታ የያዝን ሲሆን በመዘጋጃ የተሰጠኝን ካርታ በማስረጃነት አያይዤ አቅርቤያለሁ። ተጠሪ በይዞታው ላይ ከ1994 ዓ/ም ጀምሮ ቤት የሠራሁት አመልካች ሳይቃወመኝ በመሆኑ እና 20 ቤተሰብ አባሌን በዚህ ቦታ የማስተዳድር እና ከ22 ዓመት በላይ የያዝኩትን ከዚህም በላይ ቤት እና ቦታው የእኔ ለመሆኑ ተረጋግጦ በ1996 ዓ/ም አረንጓዴ ደብተር ሲሰጥ አመልካችም አብሮ ያስተቸ ለመሆኑ በምስክር አረጋግጫለሁ። አመልካች ብለቅ ከፍ ያለ ጉዳት የሚያስከትል እና በአስተዳደር አካል የተሰጠን ካርታ ፍርድ ቤት ሊሰርዘው የሚችልበት አግባብ የሌለ እና እንዲሰረዝም ዳኝነት ያልተጠየቀ በመሆኑ የስር ፍርድ ቤት ውሳኔን ሊጸና ይገባል ብለዋል። አመልካች በ13/06/2015 ዓ/ም በሰጡት የመልስ መልስ የሰበር አቤቱታቸውን አጠናክረው ተከራክረዋል።

የክርክሩ ሂደት በአጭሩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን እኛም የሥር ፍርድ ቤት ውሳኔ ላይ የተፈጸመ መሠረታዊ የሕግ ስህተት መኖር አለመኖሩን እንደሚከተለው መርምረናል።

እንደመረመርነው አመልካች በ15/07/2013 ዓ/ም ባቀረቡት ክስ በ1989 ዓ/ም እስቴ ወረዳ ልጫ ቀበሌ በዛሬው ስነ-ህይወት ከተማ መጠኑ አንድ ቃዳ መሬት ተሰጥቼ ደብተር አሰርቼ የያዝኩትን መሬት

በምስራቅ በኩል ተጠሪዎች በግምት 500 ካሬ ሜትር በ1994 ዓ/ም በኪራይ ቤት አማካኝተው ቤቱን ከሰሩ በኋላ በመሬቱ ላይ በድብቅ ደብተር በማሰራት መሬቱን ስለያዘብኝ የሠሩትን ቤት አፍርሰው መሬቱን እንዲለቁልኝ በማለት ዳኝነት የጠየቁ ሲሆን ተጠሪዎች በበኩላቸው በሕገ-ወጥ መንገድ ይዞታው ላይ ቤት ሰርተን በመያዝ በኋላም በማዘጋጃ ቤቱ ሕጋዊ ተደርጎ የተመዘገብልን ንብረታችን ነው በማለት ተከራክረዋል፡፡ ክርክሩን በፍትሐ ብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕጉ መሰረት መምራት እና መቆጣጠር የፍርድ ቤቱ ኃላፊነት ሲሆን በተገቢው ሁኔታ ካልተመራ የሥነ-ሥርዓት ሕጉን ዓላማዎች የሆኑትን እንደ አንጻራዊ እውነትን የመፈለግ፣ ሥነ-ሥርዓታዊ ፍትህ፣ ክርክርን ውጤታማ፣ ወጭና ጊዜ ቆጣቢ በሆነ አግባብ መምራት የመሳሰሉትን ማሳካት ስለማይቻል የተከራካሪዎችን መብት ይነካል፡፡ ክርክር የሚወሰነው በተጠየቀው ዳኝነት አግባብ እንደሆነ የፍብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 182(2) ላይ ተመልክቷል፡፡ ፍርድ ቤቱም ከቀረበው ዳኝነት አኳያ ከግራ ቀኙ ክርክር በመነሳት በፍብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 246 እና ተከታዮቹ መሠረት በተነሱት ጉዳዮች ጭብጥ መስርቶ ውሳኔ የመስጠት ኃላፊነት ያለበት ስለመሆኑ በሰበር መዝገብ ቁጥር 164842 ሆነ በሌሎች በርካታ መዝገቦች ላይ አስገዳጅ ትርጉም የተሰጠበት ነው፡፡

በፍ/ሕ/ቁ. 2001 የተመለከተው የአንድን ነገር መኖር ገልጾ የተከራከረ ወገን የጠቀሰው ፍሬ ነገር መኖሩን ሆነ ትክክለኛነቱን የማስረዳት ኃላፊነት አለበት (the one who alleges shall prove it) የሚለው የማስረጃ አቀራረብ መርህን ፍርድ ቤቶች ተከትለው ሊወሰኑ ይገባል፡፡ በክርክር ሂደት ፍሬ ነገሮችን ማረጋገጥ የሚቻልባቸው ዘዴዎች ማስረጃ፣ በፍርድ ቤት በሚሠጥ የእምነት ቃል፣ ፍርድ ቤት በራሱ ግንዛቤ ሊወስድባቸው የሚችሉ ጉዳዮች፣ የሕግ ግምት እና የመሓላ ቃል ናቸው፡፡ በፍትሐ ብሔር ክርክር የምንከተለው የማስረዳት ደረጃ ከሁለቱ ወገን የተሻለ ያስረዳው ማን ነው (preponderance of evidence) የሚለውን በመመርመር በመሆኑ አመልካቾች ግዴታቸውን ከተወጡ በኋላ የተጠሪ ማስረጃን በመስማት ማመዛዘን ይገባል፡፡ የማስረጃ ተገቢነት (relevancy test)፣ የማስረጃው ተቀባይነትን (admissibility) ደንቦችን መከተል እና ለማስረጃው የሚሰጠውን ክብደት (weight of evidence) በመለየት የመወሰን ኃላፊነት ማስረጃ ለመስማትና ለመመዘን ኃላፊነት ያለባቸው ፍርድ ቤቶች ዋና ተግባር ነው፡፡

ፍርድ ቤት ጭብጥ ሊይዝ ሆነ በማስረጃ ሊያጣራ የሚገባው በግራ ቀኙ ተከራካሪዎች የተነሳን ፍሬ ነገር መሠረት በማድረግ ሊሆን ይገባል፡፡ በተያዘው ጉዳይ የሥር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ የተመሰረተው ተጠሪዎች ይዞታውን በሽያጭ ውል ያገኙት መሆን አለመሆኑ እና የሽያጭ ውሉ ሕገ-ወጥ መሆን ያለውን ሕጋዊ ውጤትን በመመርመር ነው፡፡ አመልካች በክስ አቤቱታቸው ላይ በኪራይ አማካኝተው ያዙብኝ ከማለት ባለፈ በሥር ፍርድ ቤት ይዞታው በሽያጭ ውል የተላለፈ ነው በማለት በሥር ፍርድ ቤት አልተከራከሩም፡፡ ተጠሪዎችም ሰነድ አልባ ይዞታ በመያዝ በኋላም ሕጋዊ ባለይዞታ ሆነናል ከማለት ባለፈ ከአመልካች ጋር በሽያጭ ውል ግንኙነት ያገኘነው ንብረት ነው በማለት አልተከራከሩም፡፡ ስለሽያጭ ውል የተጠቀሰው በምስክሮችና ማስረጃ በሰጠው አካል ነው፡፡ ምስክር ሆነ ማስረጃ

የሚቀርበው ተከራካሪዎች ያቀረቡትን ፍሬ ነገር መኖር አለመኖር ወይም ትክክለኛነት ለማረጋገጥ እንጂ አዲስ ክርክር ለማቅረብ/ለመቀበል አይደለም፡፡ በግራ ቀኙ ተከራካሪዎች ያልተነሳን ፍሬ ነገር መሠረት በማድረግ የሥር ፍርድ ቤቶች ጭብጥ በመያዘ መወሰናቸው መሠረታዊ የሆነ የክርክር አመራር ግድፈት የተፈጸመበት ነው፡፡ ክሱ የቀረበው ውልን መሠረት በማድረግ ሳይሆን ንብረትን መብትን ለማስከበር በመፋለም ቅርጽ ሆኖ እያለ በቀረበው ክስ እና በተጠሪዎች ክርክር መሠረት ንብረቱ ላይ ባለመብት የሆነው ሰው ማን ነው የሚለውን መሠረት አድርገው መወሰን ሲገባቸው ባልተነሳና ከተጠየቀው ዳኝነት ውጭ በሆነ ጭብጥ ላይ የተሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ ስለሆነም ተከታዩ ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

ው ሳ ኔ

1. የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 107537 ሚያዚያ 28 ቀን 2014 ዓ/ም፣ የደቡብ ጎንደር ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 79170 ሰኔ 30 ቀን 2013 ዓ/ም እና የእስቴ ወረዳ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 0118766 ሰኔ 21 ቀን 2013 ዓ/ም የሠጡት ውሳኔ በፍብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348(1) መሰረት ተሽሯል፡፡

2. የእስቴ ወረዳ ፍርድ ቤት የዘጋውን መዝብ በማንቀሳቀስ አመልካች ባቀረቡት ዳኝነትና በተጠሪዎች ክርክር መሠረት ይዞታው/ንብረቱ የማን ነው የሚለውን ጭብጥ በመያዝ በማስረጃ አጣርቶ የመሰለውን እንዲወሰን ጉዳዩን በፍብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 343(1) መሠረት መልሠናል፡፡

3. በዚህ ችሎት ለወጣ ወጭና ኪሣራ ግራቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

ት ዕ ዛ ዝ

- የውሳኔው ግልባጭ ለስር ፍርድ ቤቶች ይተላለፍ፡፡ የእስቴ ወረዳ ፍርድ ቤት በውሳኔው መሠረት እንዲፈጸም አዘናል፡፡ ይጻፍ
- ጥር 18 ቀን 2015 ዓ/ም የተሰጠው እግድ ተነስቷል፡፡ ይጻፍ
- መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ፍ/ገ

የሰበር መዝገብ ቁጥር 206183

ጥቅምት 30 ቀን 2014 ዓ/ም

ዳኞች፡- ተፈሪ ገብሩ (ዶ/ር)

ቀነዓ ቂጣታ

ፈይሳ ወርቁ

ደጀኔ አያንሳ

ብርቅነሽ እሱባለው

አመልካች፡- ወ/ሮ ማኔ ጫፋ ቀርቧል

ወ/ሮ እራሼ ጫፋ

ተጠሪ፡- አቶ ተስፋዬ ቡንዳሬ - ቀርቧል

ለምርመራ ተቀጥሮ የነበረው መዝገብ ተመርምሮ ቀጣዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍርድ

አመልካቾች የቦሌ ሶሬ ወረዳ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 56/13 ታህሳስ 22 ቀን 2013 ዓ/ም በዋለው ችሎት አስቀድሞ የሰጠውን የዕግድ ትዕዛዝ ማሻሻሉን በመቃወም ያቀረቡትን ይግባኝ የወላይታ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 49541 ጥር 21 ቀን 2013 ዓ/ም በዋለው ችሎት መሰረዙ፣ የደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ወላይታ ምድብ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 34697 ሚያዚያ 8 ቀን 2013 ዓ/ም በዋለው ችሎት የሥር ፍርድ ቤት ውሳኔን ማፀናቱ እንዲሁም የሰበር አጣሪ ችሎቱ በሰበር መዝገብ ቁጥር 35530 ሚያዚያ 8 ቀን 2013 ዓ/ም በዋለው ችሎት በሥር ሶስቱም ፍርድ ቤቶች የተፈፀመ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የለም በማለት የአመልካቾችን የሰበር አቤቱታ መሰረዙ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ነው በማለት በሰበር ለማሳረም የሰበር አቤቱታ ስላቀረቡ መዝገቡ ለችሎት ቀርቧል፡፡

ጉዳዩ አመልካቾች የውርስ ይጣራ ክስ አቅርበው በግራ ቀኙ መካከል ክርክሩ ቀጥሎ እያለ አመልካቾች ተጠሪ የውርስ ንብረቶቹን ለሶስተኛ ወገን እያስተላለፈ ነው በማለት ካሳገዱ በኋላ ተጠሪ የዕግድ ይነሳልኝ አቤቱታ አቅርቦ አመልካቾችም መልስ እና ከጉርሞ ማዘጋጃ ቤት አስቀድሞ የተሰጠውን ዕግድ በተመለከተ የተሻረ ደብዳቤ ያቀረቡ ሲሆን የቦሌ ሶሬ ወረዳ ፍርድ ቤት ወቅቱ የመንግስት ግብር የሚከፈልበት በመሆኑና የተጠሪ ገቢ ምንጭም ከእርሻ የሚገኝ መሆኑን በመረዳት እንዲሁም አንድ ባህር ዛፍ ለማገዶ እንድጠቀም አስፈላጊ መሆኑን በማመን ከታገዱት 9ንብረቶች ውስጥ ጫት፣ ጌሾ፣

ማንነ፣ ካሽሚር፤ ቡና፣ እንስት፣ ለማገዶነት የሚያገለግል አንድ ባህር ዛፍ እንዲሁም በክርከሩ መሬት ውስጥ ያልተጠቀሱ ሁለት የንግድ ቤቶች እና በክሱ ውስጥ ያልተጠቀሱ ሁለት ሰርቪስ ቤቶች ላይ የተሰጠው ዕግድ ለጊዜው ተነስቶ በሌሎች ንብረቶች ላይ የተሰጠው የዕግድ ትዕዛዝ እንዲቆይ ትእዛዝ የሰጠ ሲሆን ከጉርሞ ማዘጋጃ ቤት ተጠሪ ፍርድ ቤቱ የሰጠውን ዕገዳ ጥሷል በማለት የተፃፈው ደብዳቤ እውነትነት የለውም በማለት ሳይቀበለው ቀርቷል። አመልካቾች ይህን ትዕዛዝ በመቃወም ያቀረቡትን የይግባኝ አቤቱታ የወላይታ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰረዘው ሲሆን የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ወላይታ ምድብ ችሎት ግራ ቀኙን አከራክሮ የወላይታ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠውን ትዕዛዝ ሲያፀና የደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር አጣሪ ችሎት የሶስቱም ፍርድ ቤቶች ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት አይደለም በማለት የአመልካቾች የሰበር አቤቱታ ለሰበር ሰሚ ችሎቱ አያስቀርብም በማለት መዝገቡን ዘግቷል።

አመልካቾች በየደረጃው ያሉት የሥር የደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ፍርድ ቤቶች የሰጡትን ውሳኔ እና ትእዛዝ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ተፈፅሞበታል በማለት በሰበር ለማሰረም ሚያዚያ 12 ቀን 2013 ዓ/ም ያቀረቡት የሰበር አቤቱታ ይዘት፡- የውርስ ማጣራት ክስ ቀርቦ ጉዳዩ ተጣርቶ ውሳኔ እስክያገኝ ድረስ በውርስ ይዞታው ላይ ያሉ ቋሚ አትክልቶች ታግዶ እና ተከብሮ እንዲቆዩ አቤቱታ አቅርበው የወረዳው ፍርድ ቤት ለጉርሞ ኮይሻ ማዘጋጃ ቤት ታግዶ እና ተከብሮ እንዲቆዩ ትዕዛዝ ከሰጠ በኋላ ተጠሪ ዕገዳውን በመጣስ ታግዶ ያሉ ንብረቶችን እየተጠቀመ መሆኑን አመልካቾች አቤቱታ አቅርበው ተጠሪ የታገዱ እንጨቶችን ነቃቅሎ በመጣል እንዲሁም ቡና እና ጫት እየተጠቀመ መሆኑን ከጉርሞ ኮይሻ ማዘጋጃ ቤት መግለጫ ቀርቦ እያለ ዕግዱ በመጣሱ የቦሌ ሶሬ ወረዳ ፍርድ ቤት እርምጃ መወሰድ ሲገባው ዕገዳውን በከፊል ማንሳቱ የወራሾችን መብት የሚነካ እና የውርስ ንብረት ተጠሪ እንዲያጠፋ የሚያደርግ ነው በማለት ያቀረቡት የይግባኝ እና ሰበር ቅሬታ ተቀባይነት በማጣቱ ጠቅላላ ግምቱ 1,93,000.00(አንድ ሚልዮን ዘጠና ሶስት) ሺ ብር የሚሆን ንብረት እንዲጠፋ መደረጉ መሰረታዊ የሕግ ስህተት በመሆኑ ጉዳዩ ተጣርቶ ውሳኔ እስከሚያገኝ ድርስ የዕግድ ትዕዛዙ ፀንቶ እንዲቆይ እንድታዘዝላቸው ጠይቀዋል።

የአመልካቾችን የሰበር አቤቱታ የመረመረው የሰበር አጣሪ ችሎቱ፡- የሥር ፍርድ ቤት በግራ ቀኙ መካከል ባለው የውርስ ንብረት ክርክር ጉዳይ የእግድ ትዕዛዝ ከተሰጠ በኋላ በተጠሪ የዕግድ ይነሳልኝ አቤቱታ የንግድ ቤቶች እና በሌሎችም ንብረቶች ላይ የተሰጠው የእግድ ትዕዛዝ የማንሳቱን አግባብነት ለመመርምር ለሰበር ሰሚ ችሎቱ ይቅረብ በማለቱ ተጠሪ በሰጠው መልስ፡- ዕገዳ ለመጣሱ ከጉርሞ ኮይሻ ማዘጋጃ ቤት የተሰጠ መግለጫ ባለመኖሩ እንዲሁም ዕገዳ የተነሳላቸው ንብረቶች የተጠሪ የግል ንብረቶች በመሆናቸው በላይ ጫት እና ጌሾ በየሶስት ወሩ ከልተለቀመ ተጠሪ በየጊዜው ማግኘት ያለበትን ጥቅም በመሳጣት ሊተካ የማይችል ጉዳት የሚደርስበት በመሆኑ እና ቡናም ከመታገዱ በፊት አፍርቶ ፍሬው በመሬት ላይ ረግፎ እየተበላሸ ስለነበረ ተጠሪም በርካታ ቤተሰብ የሚያስተዳድር

አማራጭ የገቢ ምንጭ የሌለው አርሶ አደር በመሆኑ ለዕለት ኑሮው አስፈላጊ በሆኑት እና በክርክሩ ውስጥ በሌሉ ንብረቶች ላይ ዕግዱ መነሳቱ አግባብ ነው በማለት ተከራክረዋል፡፡ የአመልካቾች መልስ መልስም ቀርቧል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ እና ግራ ቀኙ በዚህ ችሎት ያደረጉት የጽሁፍ ክርክር ከላይ የተመለከተው ሲሆን በሥር ፍርድ ቤቶች የተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት መሆን አለመሆኑን ችሎቱ አግባብነት ካለው የህግ ድንጋጌ አንፃር እንደሚከተለው መርምሮታል፡፡ በክርክር ሂደት ተከሳሽ ንብረት በማሸሽ ወይንም ለሌላ ሰው በማስተላለፍ የክርክሩን ሂደት ውጤት አልባ በማድረግ ከሳሽ ላይ የማይተካ ጉዳት ሊያደርስ የሚችልበትን ሁኔታ ለማስቀረት ከፍርድ በፊት ንብረት እንደምከበር ወይም ዕግድ እንደምሰጥ የፍትሐ ብሔር ሥነ ሥርዓት ሕጉ ከቁጥር 147 እና ተከታይ ድንጋጌዎች ያመለክታሉ፡፡ ከፍርድ በፊት ንብረት እንዲያዝ ወይንም እንዲታገድ የሚሰጠው ትዕዛዝ የተከሳሽን የንብረት መብት ከማገድ አልፎ በኢኮኖሚ እንቅስቃሴ ላይም አሉታዊ ተፅኖ ሊያስከትል ስለሚችል የሚሰጠው ትዕዛዝ እነዚህን ተነፃፃሪ መብቶች ያማከለ መሆን አለበት፡፡ ንብረት ማስከበር የክርክሩ ሂደት ተጠናቆ ለሚሰጠው ፍርድ ማስፈፀሚያነት ይውል ዘንድ ንብረት ተይዞ በፍርድ ቤት ቁጥጥር ሥር ባለበት ሁኔታ በማቆየት ከሳሽ በፍርድ የሚያገኘው መብት ተጠቃሚ እንዲሆን ማስቻል ነው፡፡ ንብረት የሚከበረው ወይንም የሚታገደው ተከሣሽ ንብረቱን በማሸሽ ወይንም ለሌላ ሰው በማስተላፍ አፈፃፀሙን በማሰናከል እና በማዘግየት የከሳሽን ጥቅም ለመጉዳት ለመዘጋጀቱ በቂ ምክንያት መኖሩ በፍርድ ቤት ተረጋጦ በከሳሽ ላይ ሊደርስ የሚችለው ጉዳት ለማስቀረት ወይንም ለመከላከል የሚሰጥ ትዕዛዝ ነው፡፡

በተያዘው ጉዳይ ለክርክሩ ምክንያት የሆኑን ንብረቶች ተጠሪ ለሶስተኛ ወገን እያስተላለፈ ነው በማለት አመልካቾች ያቀረቡት አቤቱታ ተቀባይነት አግኝቶ ዕግድ ከተሰጠ በኋላ ተጠሪ የዕግድ ይነሳልኝ አቤቱታ አቅርቦ አመልካቾችም መልስ እና አስቀድሞ የተሰጠው የእግድ ትዕዛዝ መጣሱን ይገልፃል ያሉትን ማስረጃ ከጉርሞ ማዘጋጃ ቤት በማቅረብ የተከራከሩ ሲሆን፤ የቦሌ ሶሬ ወረዳ ፍርድ ቤት የተጠሪን ገቢ ምንጭ ከግምት ውስጥ በማስገባት ለዕለት ኑሮ አስፈላጊ በሆኑት አንድ የባህርዛፍ እንጨት፣ ጫት፣ ጌሾ፣ ማንጎ፣ ካሽሚር፤ ቡና እና እንሰት ላይ አስቀድሞ የሰጠውን የዕግድ ትእዛዝ ማሻሻሉ እንዲሁም በየደረጃው ያሉ ፍርድ ቤቶችም እነዚህን ንብረቶች በሚመለከት የተሰጠውን የዕግድ ትዕዛዝ መሻሻሉን በመቃወም አመልካቾች ያቀረቡትን የይግባኝ እና ሰበር አቤቱታ መሰረዛቸው የሚነቀፍ ሆኖ አልተገኘም፡፡ ይሁን እንጂ ለክርክሩ ምክንያት የሆኑትን ንብረቶች ተጠሪ ለሶስተኛ ወገን ለማስተላለፍ መዘጋጀቱ በአመልካቾች የቀረበው አቤቱታ ተቀባይነት አግኝቶ ታምኖበት የዕግድ ትእዛዝ ከተሰጠባቸው ንብረቶች ውስጥ ሁለት የንግድ ቤቶች እና ሁለት ሰርቪስ ቤቶች ላይ ክርክሩ ቀጥሎ ባለበት እና በንብረቶቹ ላይ ትክክለኛ ባለመብት ማን እንደሆነ ሳይጣራ በክሱ ውስጥ እና በክርክሩ መሬት ውስጥ አልተጠቀሱም በማለት በእነዚህ ንብረቶች ላይ የተሰጠው ዕገዳ መነሳቱ ተጠሪ ንብረቶቹን ለ3ኛ ወገን በማስተላለፍ በአመልካቾች ላይ ጉዳት ሊያደርስ ስለሚችል የሚነቀፍ ሆኖ እያለ ጉዳዩን በይግባኝ እና በሰበር ያዩት

ፍርድ ቤቶችም ይህን ትዕዛዝ ማጽናታቸው መሰረታዊ የሕግ ስህተት የፈፀመበት በመሆኑ ቀጣዩ ተወስኗል፡፡

ውሳኔ

1. የደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር አጣሪ ችሎት በሰበር መዝገብ ቁጥር 35530 ሚያዚያ 8 ቀን 2013 ዓ/ም በዋለው ችሎት የሰጠው ትዕዛዝ፣ ይግባኝ ሰሚው የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ወላይታ ምድብ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 34697 ሚያዚያ 8 ቀን 2013 ዓ/ም በዋለው ችሎት የሰጠው ውሳኔ፣ የወላይታ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 49541 ጥር 21 ቀን 2013 ዓ/ም በዋለው ችሎት የሰጠው ትዕዛዝ እና የቦሌ ሶሬ ወረዳ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 56/13 ታህሳስ 22 ቀን 2013 ዓ/ም በዋለው ችሎት አስቀድሞ የሰጠውን የዕግድ ትዕዛዝ በማሻሻል የሰጠው ትእዛዝ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 348(1) መሰረት **ተሻሽሏል**፡፡
2. ጫት፣ ጌሾ፣ ማንጎ፣ ካሽሚር፤ ቡና፣ እንሰት፣ ለማገዶነት የሚያገለግል አንድ ባህር ዛፍ እንጨት ላይ ተሰጥቶ የነበረውን የዕግድ ትዕዛዝ በማሻሻል የቦሌ ሶሬ ወረዳ ፍርድ ቤት ታህሳስ 22 ቀን 2013 ዓ/ም በዋለው ችሎት የሰጠው ትዕዛዝ እና በየደረጃው ያሉት ፍርድ ቤቶች ያፀኑት ውሳኔ ***ፀንቷል***፡፡
3. ሁለቱ የንግድ ቤቶች እና ሁለት ሰርቪስ ቤቶችን አስመልክቶ የተሰጠው የትዕዛዝ ክፍል ***ተሸሯል***፡፡
4. በተራ ቁጥር "3" ሥር የተጠቀሱት ንብረቶች ጉዳዩ እልባት እስክያገኝ ድረስ ባሉበት ሁኔታ ታግዶ እንዲቆዩ ብለናል፡፡
5. የዚህ ውሳኔ ግልባጭ ለሥር ፍ/ቤቶች ይድረስ፡፡
6. በሰበር ክርክሩ የደረሰውን ውጪ እና ኪሳራ ግራ ቀኙ የግላቸውን ይቻሉ፡፡
7. በዚህ መዝገብ ላይ ተሰጥቶ የነበረው የዕግድ ትዕዛዝ ተነስቷል፡፡
8. ውሳኔው ህዳር 1 ቀን 2014 ዓ/ም በችሎት ተነቧል፡፡

መዝገቡ ውሳኔ አግኝቶ ስለተዘጋ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

አ/ኃ

የሰ/መ/ቁጥር - 223405

ጥር 29 ቀን 2015 ዓ.ም

ዳኞች፡- ተፈሪ ገብሩ (ዶ/ር)

እንዳሻዉ አዳነ

ተሾመ ሽፈራዉ

መላኩ ካሳዬ

ነፃነት ተገኝ

አመልካች፡- ራዕይ በሲዳሞ ተራ ልማትና ንግድ አ/ማህበር - ስለ ራዕይ ገበየሁ ይርዳው ጠበቃ - ቀረቡ

ተጠሪ፡- ወ/ሮ ነኢማ ጫሞላ - ጠበቃ መኮንን ደምሴ ቀርበዋል፡፡

መዝገቡ ተምርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የተጀመረዉ በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ሲሆን ተጠሪ በአመልካች ላይ ያቀረቡትን ክስ መነሻ ያደረገ ነዉ፡፡ የተጠሪ ክስ ይዘትም በአጭሩ ሰኔ 11 ቀን 2000 ዓ.ም ተደርጎ በሰነዶች ምዝገባና ማረጋገጫ ጽ/ቤት በተረጋገጠ የሽያጭ ዉል በአዲስ ከተማ ክ/ከተማ ዉስጥ የሚገኘዉን ቁጥሩ 593/2 የሆነ የንግድ ቤት አቶ ሀብቱ ብርሃኑ ከሚባል ግለሰብ ገዝቼ በቤቱ ላይ ሐምሌ 25 ቀን 2000 ዓ.ም የንግድ ፍቃድ በማዉጣት ጳጉሜ 3 ቀን 2000 ዓ.ም ከቀበሌ ተከራይቼ የንግድ ስራ ሳከናዉን ቆይቻለሁ፡፡ መንግስት በመልሶ ማልማት እንቅስቃሴ መርካቶ ዉስጥ በሕግ አግባብ ሱቅ በመያዝ የሚነግዱ የንግድ ማህበረሰብ አባላት ቦታቸዉ ያለበትን ስፍራ በሊዝ ገዝተዉ ህንፃ በመገንባት የገበያ ማዕከል ባለቤት እንዲሆኑ መፍቀዱን ተከትሎ የክ/ከተማዉ አስተዳደር ባደረገዉ ጥናት ተጠሪ በቤቱ ህጋዊ ተገልጋይ መሆኔ ተረጋግጦ የማህበሩ አባል ሆኜ በማህበሩ መተዳደሪያ ደንብ መሠረት ታዝገፎ ብር 10,000.00 ከፍያለሁ፡፡ አመልካች እያስገነባ ላለዉ ህንፃ የድርሻዬን መዋጮ እንዲከፍሉ በታዘዙት መሠረት ከ2001 ዓ.ም ጀምሮ ከብር 800,000.00 በላይ መዋጮ በመክፈል ኃላፊነቴን መወጣቴን ተከትሎም አመልካች ሚያዝያ 17 ቀን 2010 ዓ.ም ባደረገዉ ስብሰባ የብር 200,000 ዋጋ ያለዉ 200 አክስዮን ባለድርሻ አድርጎ ተቀብሎኝ የገበያ ማዕከሉ ግንባታ በተጠናቀቀበት ወቅት በዕጣ ቁጥራቸዉ 14 እና 114 የሆኑ ሱቆችን ሰጥቶኛል፡፡ ይሁንና በሱቁ እየተገለገልኩ እያለ አመልካች ሱቆቹን ወ/ሮ ሙሃባ ቡሴር ለተባሉ ግለሰብ እንዲሰጥ ታዝዣለሁ በማለት በፖሊስ ኃይል የእኔ እንዲወሰድ አድርጓል፡፡ በዚህም በንግድ ስራዬ ማግኘት እችል የነበረዉን በወር ብር 26,000.00 አሳጥቶኛል፡፡ ስለሆነም አመልካች ሱቆቹን እንዲመልስ፣ ወደ ስራ እስክገባ ድረስ ለማጣዉ ገቢ ኃላፊ እንዲሆን ይወሰንልኝ፤ ይህ ከታለፈ የአክስዩን ባለድርሻ ባደረጋቸዉ መጠን የትርፍ ተካፋይ እንዲያደርገኝ ይወሰንልኝ የሚል ነዉ፡፡

አመልካች በበኩሉ ጉዳዩ አስቀድሞ ዉሳኔ የተሰጠበት ነዉ፣ ተጠሪም መብትና ጥቅም የላቸዉም የሚል የመጀመሪያ መቃወሚያ በማስቆም በፍሬ ነገር ረገድ ለክሱ በሰጠዉ መልስ ህንፃዉ የተገነባዉ ልዩ ቦታዉ ሲዳሞ ተራ ተብሎ በሚጠራዉ አካባቢ ንግድ ቤት ኖሮአቸዉ በሕጋዊ መንገድ ሲነግዱ የነበሩ የንግድ ማህበረሰብ አባላት በማህበር ተደራጅተዉ በመልሶ ማልማት ቦታዉን በሊዝ እንዲያለሙ መንግስት በፈቀደዉ ልዩ መመሪያ መሠረት ሲሆን ተጠሪ የማህበሩ አባል ሆነዉ የተመዘገቡት ሚያዝያ 17 ቀን 2009 ዓ.ም አባል የሆኑት ማህበሩ በኃላ/የተ/የግ/ማህበር ደረጃ በ1998 ዓ.ም ሲቋቋም ህንፃዉ በተገነባበት ቦታ ህጋዊ የንግድ ድርጅት ከነበራቸዉ አቶ ሀብቱ ብርሃኑ እና ወ/ሮ ዉድነሽ መሸሻ ላይ ገዝተዉ ስም ሳያዛዉሩ በዚሁ ቤት አባል ሆነዉ የተመዘገቡት ወ/ሮ ሙሃባ ቡሴር ሰዒድ በማህበሩ ዉስጥ የነበራቸዉን የአክስዮን ድርሻ ሰኔ 11 ቀን 2000 ዓ.ም ሸጠዉላቸዉ በእርሳቸዉ ምትክ እንጂ ከመጀመሪያዉ በቦታዉ ላይ የራሳቸዉ ህጋዊ ንግድ ቤት ኖሯቸዉ አይደለም፡፡ አመልካች ተጠሪን ሚያዝያ 17 ቀን 2009 ዓ.ም በአባልነት ሊቀበል የቻለዉ በ2000 ዓ.ም የተደረገዉ የሽያጭ ዉል፣ በማህበሩ ያላቸዉ መብት ለተጠሪ እንዲተላለፍ ወ/ሮ ሙሀባ ቡሴር ለማህበሩ ማመልከቻ በማቅረባቸዉ እና የስም ማዛወሪያ 10,000.00 መክፈላቸዉን የሚያሳይ ሰነድ በማቅረባቸዉ ይህንኑ ከማህበሩ መተዳደሪያ ደንብ አንቀጽ 9/23 በማገናዘብ ቢሆንም፣ ተጠሪን በማህበሩ የተኩት ወ/ሮ ሙሀባ ቡሰሬ ተጠሪ የተተኩበትን ሚያዝያ 17 ቀን 2009 ዓ.ም ቃለ ጉባኤ በሰነዶች ማረጋገጫና ምዝገባ ጽ/ቤት በማሳገድ በፌ/የመጀ/ደ/ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 68918 ላይ በአመልካች ላይ ክስ አቅርበዉ ተጠሪ ወደ ክርክሩ ጣልቃ ገብተዉ ክርክር ከተደረገ በኃላ ከወ/ሮ ሙሀባ ወደ ተጠሪ የተዛወረዉ የአክስዮን ድርሻ መብት የለም የሚል ዉሳኔ ተሰጥቷል፤ ግራ ቀኝ በየፊናቸዉ ይግባኝ አቅርበዉ በየደረጃዉ ጸንቷል፤ ሰበር በሰ/መ/ቁጥር 193366 ላይ በትዕዛዝ አጽንቶታል፡፡ ስለሆነም ተጠሪ የአክስዮን አባልነት መብት የላቸዉም፡፡ አንድ የንግድ ቤት በሁለት ሰዎች እንዲመዘገብ ማድረግ የአመልካች ማህበር የተቋቋመበትን ዓላማ የሚቃረን በመሆኑ አመልካች ተጠሪን የማህበሩ አባል አድርጎ የመመዝገብ ግዴታ የለበትም፡፡ በመሆኑም ተጠሪ ወ/ሮ ሙሀባ ቡሴርን በመተካት የከፈሉትን ብር 800,000.00 ከወ/ሮ ሙሃባ ቡሴር መጠየቅ ከሚችሉ በቀር በፍርድ ያጡትን የአክስዮን መብት ለማግኘት ያቀረቡት ክስ ተቀባይነት የለዉም በማለት ተከርክሯል፡፡

ጉዳዩ በመጀመሪያ የቀረበለት የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትም ከግራ ቀኝ በዚህ መልኩ የቀረበዉን ክርክር ከሰማ በኃላ ከሁለት ሱቆች ጋር በተያያዘ ተጠሪ ያቀረቡት የካሳ ይገባኛል ጥያቄ በብይን ዉድቅ ያደረገ ሲሆን፣ ተጠሪ ያቀረቡትን የአክስዩን ድርሻ መብት አስመልክቶ የቀረበዉን ዳኝነት በመቀበል በ200 የአክስዮን ድርሻ የሚገኘዉ መብት የሱቅ ድልድልም ሆነ ሌሎች መብቶች ሁሉ ለተጠሪ ይከበርላቸዉ በማለት ወስኗል፡፡ ለዉሳኔዉ መሠረት ያደረገዉ ምክንያትም በአጭሩ አመልካች ለህንፃ ግንባታ በሊዝ ከመንግስት ሲተዳደር በተረከበዉ ቦታ ላይ በህጋዊ መንገድ የንግድ ስራ ሲያከናዉኑ የንግድ ማህበረሰብ አባላት የቅድሚያ መብት በመስጠት ባለ አክስዮን አድርጎ የመመዝገብ

ግዴታ አመልካች በመንግስት መመሪያ ግዴታ የተጣለበት መሆኑን፤ በክ/ከተማ ደረጃ በተደረገ ማጣራት ተጠሪ የቤ/ቁጥር 593/2 የሆነዉን የንግድ ቤት ከመንግስት ተከራይተዉ የንግድ ፍቃድ አወጥተዉ የንግድ ስራ ሲሰሩ እንደነበረ እንዲሁም አመልካች ወደ አክሲዮን ማህበር ከመቀየሩ በፊት መዋጮ 800,000.00 መክፈላቸዉን የሚያረጋግጥ ማስረጃ ተጠሪ ማቅረባቸዉን፤ በአመልካች ማህበር ቦርድ ሚያዝያ 17 ቀን 2009 ዓ.ም ተይዞ ግንቦት 26 ቀን 2009 ዓ.ም የተመዘገበዉ ቃለ ጉባኤ ህጉን ስላልተከተለ እንዲሰረዝ እና ወ/ሮ መ·ሃባ ቡሴር ለተጠሪ በሽያጭ አላስተላለፉም በማለት የሰጠዉ ዉሳኔ ተጠሪ ሌሎችን መስፈርቶች አሟልተዉ እስከተገኙ ድረስ የተከራዩት ሱቅ ፈርሶ ይዞታዉ 2003 እስኪረከብ ድረስ ይዘዉ ሲገለገሉበት የነበረ በመሆኑ የህግ ጥበቃ የተሰጣቸዉን የባለ አክስዮንነት መብት የሚያሳጣቸዉ አይደለም የሚል ነዉ፡፡ አመልካች በዚህ ዉሳኔ ባለመስማማት ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ ያቀረበ ቢሆንም ይግባኙ በፍ/ብ/ሥ/ሥርዓት ህጉ አንቀጽ 337 መሠረት ተሰርዟል፡፡

ይህ የሰበር አቤቱታ የቀረበዉም በዚሁ ዉሳኔ ቅር በመሰኘት ለማስለወጥ ሲሆን፣ አመልካች መጋቢት 14 ቀን 2014 ዓ.ም በተፃፈ የሰበር አቤቱታ በስር የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ተሰጥቶ በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በትዕዛዝ የጸናዉ ዉሳኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነዉ የሚልባቸዉን ምክንያቶች በመዘርዘር ታርሞ ይወሰንለት ዘንድ ዳኝነት ጠይቋል፡፡ የሰበር አቤቱታዉ መሠረታዊ ይዘትም በአጭሩ ማህበሩ በ1998 ዓ.ም ሲቋቋም በአባልነት የተመዘገቡት በቦታዉ ላይ ህጋዊ ንግድ ቤት የነበራቸዉ፣ ህንፃዉ በተገነባበት ቦታ ላይ የንግድ ቤት ባለቤት ሆነዉ በህጋዊ መንገድ ሲነግዱ ለነበሩ የንግዱ ማህበረሰብ አባላት በማህበሩ ዉስጥ እንዲካተቱ ቅድሚያ መብት እንዲያገኙ በመንግስት በተወሰነ አስገዳጅ መመሪያ ነዉ፤ በወቅቱ በንግድ ቤቱ ሲሰሩ የነበሩት ወ/ሮ መ·ሀባ ናቸዉ፡፡ ተጠሪ ሚያዝያ 17 ቀን 2009 ዓ.ም በተያዘ ቃለ ጉባኤ የማህበሩ አባል ሆነዉ የተመዘገቡት በንግድ ሱቅ ቁጥር 593/02 የንግድ ስራ ሲሰሩ የማህበሩ መስራች አባል ከሆኑት ወ/ሮ መ·ሀባ ቡሴር ላይ የአባልነት መብትና ሱቅ ሰኔ 11 ቀን 2000 ዓ.ም በተደረገ የሽያጭ ዉል ተላልፎልኛል በማለት ነዉ፡፡ ይሁንና ወ/ሮ መ·ሀባ ቡሴር ለተጠሪ አልሸጥኩም የሚል ክርክር አቅርበዉ ለተጠሪ የተሰጠዉ የአክስዮን ድርሻ እንዲመለስ፤ ተጠሪ የተከራዩትንም ሱቅ ለመ·ሀባ እንዲመልሱ በሚል በፍርድ ቤት በተሰጠ ዉሳኔ ተጠሪ የአባልነት መብታቸዉን አጥተዋል፡፡ የተጠሪ የአባልነት መብት በዚህ ሁኔታ ቀሪ ሆኖ እያለ አመልካች ተጠሪን አባል አድርጎ ሊመዘግብ የሚችልበት ህጋዊ ምክንያት የለም የሚል ነዉ፡፡

የአመልካች የሰበር አቤቱታዉ በአጣሪ ችሎት ተመርምሮም የአሁን ተጠሪ የክርክሩ ተሳታፊ በሆኑበት መዝገብ ቁጥር 68918 ላይ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ተጠሪ የባለአክስዮንነት መብት እንደሌላቸዉ ተወስኖ እያለ የስር ፍርድ ቤት የሰጠዉ ዉሳኔ ለተጠሪ የአክስዮን ድርሻ የወሰነበትን አግባብ ግራ ቀኝ በተገኙበት አጣርቶ ለመወሰን ሲባል ያስቀርባል ተብሏል፡፡ በዚህም መሠረት ተጠሪ ሚያዝያ 21 ቀን 2014 ዓ.ም በተፃፈ መልስ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 68918 ላይ ለሰጠዉ ዉሳኔ መሠረት ያደረገዉ ጭብጥ ለዚህ ክርክር መነሻ በሆነዉ መዝገብ ላይ

ከሚያዝ ጭብጥ ጋር የማይገናኝ በመሆኑ በድጋሚ የቀረበዉን ዳኝነት በመቀበል የተሰጠ ዉሳኔ ነዉ በሚል አመልካች የሚያቀርበዉ ክርክር ተቀባይነት የለዉም፡፡ ተጠሪ ባቀረቡት ክስ የአባልነት መብታቸዉ ይከበርላቸዉ ዘንድ ዳኝነት ያቀረቡት በአንድ በኩል አመልካች ሚያዝያ 17 ቀን 2009 ዓ.ም በያዘዉ ቃለ ጉባኤ አባል አድርጎ መዝግቧቸዉ የነበረ በመሆኑ በሌላ በኩል ተጠሪ በማህበሩ ፈቃድና ጥሪ የሱቅ ቦታ ለአመልካች ግንባታ በመዋሉ የአክስዮን ባለ ድርሻ ይሆን ዘንድ ተገቢዉን መስፈርት ያሟሉ ስለመሆኑ በማህበሩ እና በመንግስት በመረጋገጡ ተጠሪ የአባልነት ክፍያ ከመፈጸም በተጨማሪ የህንፃዉ ግንባታ እንዲጠናቀቅ ከጅምሩ አንስተዉ ተገቢዉም መዋጮ ማድረጋቸዉ ህጋዊ አባልና ባለድርሻ የሚያደርገኝ ነዉ፡፡ በመሆኑም እንደማንኛዉም የአክስዮን አባል መፈጸም የሚገባኝን ግዴታና የመንግስት መመሪያ ማሟላቴን በማረጋገጥ የስር ፍርድ ቤት የሰጠዉ ዉሳኔ ተገቢ በመሆኑ ሊጸና ይገባል በማለት ተከራክረዋል፡፡ አመልካች ግንቦት 05 ቀን 2014 ዓ.ም በተፃፈ የመልስ መልስ የሰበር አቤቱታዉን በማጠናከር ተከራክሯል፡፡

ከስር ጀምሮ የጉዳዩ አመጣጥ እና የግራ ቀኝ ክርክር ይዘት አጠር አጠር ባለ መልኩ ሲታይ ከፍ ሲል የተመለከተዉን ሲመስል፣ ይህ ችሎትም የሰበር አቤቱታዉን ለማስቀረብ በአጣሪ ችሎት የተያዘዉን ጭብጥ ከግራ ቀኝ ክርክር እና ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸዉ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ መዝገቡን እንደሚከተለዉ መርምሮታል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ እንደሚቻለዉ ተጠሪ በስር ፍርድ ቤት ባቀረቡት ክስ ለጠየቁት ዳኝነት መሠረት ያደረጉት አቶ ሀብቱ ብርሃኑ ከሚባል ግለሰብ ገዝተዉ የንግድ ፍቃድ አዉጥተዉ ሲሰሩበት በነበረዉ የንግድ ቤት መነሻነት የአመልካች አክሲዮን ማህበር አባል በመሆን እንደማንኛዉም አባል የሚጠበቅባቸዉን ግዴታ የተወጡ ሆነዉ ሳለ የአመልካች ማህበር ከገነባዉ የገበያ ማዕከል ህንፃ ዉስጥ ተሰጥቶአቸዉ ሲገለገሉበት የነበረዉን ሱቅ በአመልካች እንዲለቁ መደረጉ ያላግባብ መሆኑን ሲሆን፤ አመልካች በበኩሉ ተጠሪ በእርግጥም የአመልካች አክስዮን ማህበር አባል መሆናቸዉን፣ በአባልነታቸዉ ምክንያት የተሰጣቸዉን ሱቅ እንዲለቁ ያደረጋቸዉ መሆኑን ሳይክድ የተጠሪ የዳኝነት ጥያቄ ዉድቅ ይሆን ዘንድ አጥብቆ የሚከራከረዉ ተጠሪ የባለአክስዮንነት ድርሻ እንዲኖራቸዉ ምክንያት የሆነዉን ሱቅ የገዙት ከወ/ሮ ሙሃባ ቡሴር ሲሆን፣ ወ/ሮ ሙሃባ ቡሴር በአመልካች ላይ ባቀረቡት ክስ መነሻነት ተጠሪ ወደ ክርክሩ ጣልቃ እንዲገቡ ተደርጎ በተደረገ ክርክር የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 68918 ላይ ከወ/ሮ ሙሃባ ቡሴር ወደ ተጠሪ የተዛወረ የአክስዮን ድርሻ የሌላቸዉ መሆኑን ጠቅሶ አመልካች ተጠሪ የያዙትን ሱቅ ለወ/ሮ ሙሃባ ቡሴር ሊያስረክብ ይገባል የሚል ዉሳኔ መስጠቱንና ዉሳኔዉም ተጠሪ የአክሲዮን ድርሻ የሚያሳጣቸዉ መሆኑን በመጥቀስ መሆኑን ነዉ፡፡

በእርግጥም ወ/ሮ ሙሃባ ቡሴር በአሁን አመልካች ላይ ባቀረቡት ክስ በአመልካች አክስዮን ማህበር ዉስጥ በ48ኛ ተራ ቁጥር ላይ ተመዝግበዉ ለማህበሩ ብር 200,000.00 ገቢ ያደረጉ ቢሆንም ምክንያቱን

በማያውቁት ሁኔታ አመልካች ሱቁን ሊያስረክባቸዉ አለመቻሉን ጠቅሰዉ በአክሲዮኑ መሠረት ሱቆቹን እንዲያስረክባቸዉ የጠየቁትን ዳኝነት ተከትሎ ተጠሪም በክርክሩ ጣልቃ በመግባት ክርክር ከተደረገ በኋላ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 68918 ላይ ሚያዝያ 30 ቀን 2011 ዓ.ም በዋለዉ ችሎት የአክስዮን መብት ከወ/ሮ መ·ሃባ ቡሴር ወደ ተጠሪ በህግ አግባብ ያልተዛወረ መሆኑን በመጥቀስ ዉሳኔዉ እስከተሰጠበት ቀን ድረስ የተሰሩ ስራዎችንና ለአመልካች ተከፍለዋል የተባሉ ክፍያዎችን ጨምሮ ስለ ሌሎች ኃላፊነቶች ወ/ሮ መ·ሃባ ቡሴር እና ተጠሪ በህግ አግባብ የሚጠያየቁ መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ በህጉ መስፈርት መሠረት የባለ አክስዮንነት መብት የወ/ሮ መ·ሃባ ቡሴር ነዉ በማለት ወስኗል፤ በዚህ ዉሳኔ ላይ ይግባኝ የቀረበለት የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 239302 ላይ ከፍ ሲል የተመለከተዉን የስር ፍርድ ቤት ዉሳኔ ያጸና ሲሆን በተጨማሪም ተጠሪ በአመልካች ማህበር ባለአክስዮን የሆኑበትን ሚያዝያ 27 ቀን 2009 ዓ.ም የተያዘዉ ቃለ ጉባኤ እንዲሁም በተጠሪ እና በመ·ሃባ ቡሴር መካከል ሰኔ 11 ቀን 2000 ዓ.ም የተደረገን የንግድ ድርጅት ሽያጭ ዉል እንዲፈርስ ወስኗል፤ ይህ ዉሳኔም በሰበር አጣሪ ችሎት በሰ/መ/ቁጥር 193366 ላይ በትዕዛዝ የጸና ስለመሆኑ ከመዝገቡ ለመገንዘብ ተችሏል፡፡

የአመልካች አክስዮን ማህበር መጀመሪያ በ1998 ዓ.ም በኃ/የተ/የግ/ማህበርነት ሊቋቋም የቻለዉ ማህበሩ ህንፃ በገነባበት ቦታ ላይ የንግድ ቤት ባለቤት ሆነዉ በህጋዊ መንገድ ሲነግዱ ለነበሩ የንግድ ማህበረሰብ አባላት በማህበሩ ዉስጥ እንዲካተቱ የቅድሚያ መብት እንዲሰጥ በመንግስት በተቀመጠ አስገዳጅ መመሪያ ስለመሆኑ፣ ተጠሪ በአመልካች ማህበር የአክስዮን አባል ሆነዉ ሊመዘገቡ የቻሉትም አክስዮን ማህበሩ በ1998 ዓ.ም ኃላ/የተ/የግ/ማህበር ሆኖ ሲቋቋም ለአመልካች በመልሶ ማልማት ተፈቅዶለት ህንፃ በገነባበት ቦታ ላይ በንግድ ሱቅ ቁጥር 593/02 የንግድ ስራ ሲሰሩ የማህበሩ መስራች አባል ከሆኑት ወ/ሮ መ·ሀባ ቡሴር ላይ የአባልነት መብትና ሱቁን ሰኔ 11 ቀን 2000 ዓ.ም በመግዛታቸዉ እንጂ ማህበሩ በ1998 ዓ.ም ሲቋቋም የንግድ መስሪያ ቦታ ስለነበራቸዉ አለመሆኑ ተጠሪ ክደዉ አይከራከሩም፡፡ ይህም የሚያሳየዉ ተጠሪ በአመልካች ማህበር የአክስዮን ድርሻ እንዲያገኙ ምክንያት የሆነዉ እንደ ሌሎች የማህበሩ የአክስዮን አባላት ማህበሩ ሲመሰረት የአመልካች ህንፃ በተገነባበት ቦታ ላይ የንግድ ቤት ተከራይተዉ ስለነበሩ ሳይሆን፣በወቅቱ በቦታዉ የንግድ ቤት ተከራይተዉ የነበሩት ወ/ሮ መ·ሀባ ቡሴር በሽያጭ ሲላስተላለፉላቸዉ መሆኑን ነዉ፡፡ ከዚህም ተጠሪ የንግድ ቤቱን ከወ/ሮ መ·ሀባ ቡሴር በግዥ ባያገኙ ኖሮ ከአመልካች ማህበር የባለአክዮንነት መብት ማግኘት የማይችሉ መሆኑን መገንዘብ ይቻላል፡፡

ይሁንና ተጠሪ የአመልካች አክስዮን ማህበር አባል ሆነዉ እንዲመዘገቡ ምክንያት የሆነዉ የሽያጭ ዉል እንዲሁም የአክስዮን አባልነት ዕዉቅና ያገኘበት ዉሳኔ (ቃለ ጉባኤ) ከፍ ሲል በተመለከቱት ግልጽ ዉሳኔዎች ተሽረዋል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ የአክስዮን ድርሻ መብት ለቀድሞ ባለቤታ ለወ/ሮ መ·ሀባ ቡሴር እንዲመለስ ተወስኗል፡፡ ከዚህ ሁሉ መገንዘብ የሚቻለዉ ተጠሪ ከአመልካች የነበራቸዉን

የአክስዮን ድርሻ መብት በፍርድ ሃይል ማጣታቸዉን ነዉ። በአመልካች ማህበር የአክስዮን ድርሻ መብት ለማግኘት ማህበሩ ህንፃዉን ባስገነባበት ቦታ ላይ ቀደም ሲል የነበሩት ሱቆች ህጋዊ ተከራይ ሆኖ መገኘት እንደ ቅድመ ሁኔታ የሚታይ ከመሆኑ አኳያ፣ ተጠሪ የአክስዩን መብት እንዲያገኙ ምክንያት የሆነዉ ዉል ተሽሮ እንዲሁም የአክስዮን አባልነት መብት ከወ/ሮ መ·ሀባ ቡሴር ወደ እርሳቸዉ የተዛወረበት ሁኔታም በህጋዊ መንገድ አለመሆኑ ተረጋግጦ የአክስዮን አባልነት መብት ያገኙበት ቃለጉባኤ እንዲፈርስ ተወስኖ ባለበት ሁኔታ፣ ተጠሪ ለህንፃዉ ግንባታ መዋጮ ማዋጣታቸዉ መረጋገጡ ተጠሪ ከአመልካች ማህበር የአክስዮን ድርሻ እንዲኖራቸዉ ምክንያት አይሆንም። ለሁሉም ግልጽ እንደሚሆነዉ ፍርድ ቤት በህግ የተረጋገጠን መብት ከማስከበር/ከማክበር በዘለለ እራሱ መብት ሊፈጥር አይችልም።

በሌላ በኩል በፍርድ ቤት የሚሰጥ ማንኛዉም ዉሳኔ ስርዓቱን ጠብቆ እስካልተለወጠ ወይም እስካልተሻሻለ ድረስ ተፈፃሚ ሆኖ ሊቀጥል የሚገባ ስለመሆኑ በፍትሐብሔር ፍትሕ አስተዳደር ተቀባይነት ካገኙ መርሆዎች ዉስጥ አንዱ እንደሆነ ይታወቃል። ይህ ካልሆነ እና ፍርድ ቤቶች ዉሳኔ ያሳረፉባቸዉን ጉዳዮች በማንኛዉም ጊዜ እና ሁኔታ እንዲሁም በማንኛዉም አካል በዘፈቀደ እንዲሻር ወይም እንዲለወጥ መፍቀድ የፍርድ ቤቶች ዉሳኔ ተገማች እንዳይሆኑ የማድረግ ዉጤት የሚያስከትል ከመሆኑም በላይ ዜጎች በፍርድ ቤት ላይ አመኔታ እንዳይኖራቸዉ ብሎም የህግ የበላይነት እንዲሸረሸር ምክንያት ይሆናል። በፍ/ብ/ሥ/ሥርዓት ህጋችን አንቀጽ 5 ላይ በፍርድ ያለቀ ጉዳይ በድጋሚ እንዳይቀርብ የሚከለክለዉ ድንጋጌ እንዲሁም ሥነ-ሥርዓቱን ጠብቆ እንዲታረም ያልተደረገ ዉሳኔ ተፈፃሚነቱ መቀጠል እንዳለበት በአንቀጽ 212 ላይ የተመለከተዉ ድንጋጌም የፍርድ ቤት ዉሳኔ በዘፈቀደ ሊሻሻል ወይም ሊለወጥ አይገባም የሚለዉ መርህ በእኛ አገር የፍትሐብሔር ፍትሕ አስተዳደር ተቀባይነት ስለማግኘቱ ማሳያዎች ናቸዉ። ክርክሮች ተገቢዉን ሥርዓት ጠብቀው የቀረቡ መሆን አለመሆናቸዉን የመቆጣጠር፣ የክርክር አመራር ሥርዓቱም ተቀባይነት ያገኙ የፍትሐብሔር ፍትሕ አስተዳደር መርሆዎችን ያገናዘበ እና የተከራካሪ ወገኖችን የመደመጥ መብት ከግምት ዉስጥ ባስገባ መልኩ የመምራት ኃላፊነት በዋነኝነት የፍርድ ቤት ስለመሆኑም የሚታወቅ ነዉ።

ከዚህ አንፃር የተያዘዉን ጉዳይ ስንመለከት ተጠሪ በሌላ መዝገብ ላይ ተከራክረዉ ያጡትን መብት በሌላ የፍርድ መዝገብ ለማስከበር ያቀረቡትን ዳኝነት ዉድቅ ማድረግ ሲገባዉ፣ ተጠሪ ለግንባታዉ አስፈላጊ የሆነዉን መዋጮ መክፈላቸዉ እና በአክስዮን መዝገብ መግባታቸዉ መረጋገጡን ብቻ መሠረት በማድረግ የባለአክስዮንነት መብት እንዲከበርላቸዉ በሚል በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ተሰጥቶ በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በትዕዛዝ የጸናዉ ዉሳኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ ተገኝቷል። ተከታዩም ተወስኗል።

ው ሳ ኔ

1. የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 288979 ላይ ሰኔ 17 ቀን 2013 ዓ.ም በዋለዉ ችሎት እንዲሁም የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 275508 ላይ የካቲት 25 ቀን 2014 ዓ.ም በዋለዉ ችሎት የሰጠዉ ትዕዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥርዓት ህጉ አንቀጽ 348(1) መሠረት ተሽረዋል፡፡
2. ተጠሪ ከአመልካች ማህበር የአክስዮን ድርሻ የላቸዉም ተብሎ ተወስኗል፡፡
3. በዚህ ችሎት የተደረገዉ ክርክር ያስከተለዉን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኝ የየራሳቸዉን ይቻሉ፡፡
4. ይህ ችሎት ነሐሴ 25 ቀን 2014 ዓ.ም በዋለዉ ችሎት የሰጠዉ እግድ ተነስቷል፡፡

ትዕዛዝ

- ከስር የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የቀረበዉ መዝገብ ቁጥር 288979 በመጣበት አካኋያ ለፍርድ ቤቱ ይመለስ፡፡
- መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ት/በ

የሰ/መ/ቁ 221679

ጥቅምት 1 ቀን 2015 ዓ/ም

ዳኞች፡- ተፈሪ ገብሩ (ዶ/ር)

ቀነአ ቂጣታ

ፈይሳ ወርቁ

ደጀኔ አያንሳ

ብርቅነሽ እሱባለው

አመልካች፡- አቶ አብዱሰላም ፋራህ	አልቀረቡም
ተጠሪ፡- አቶ አደም ኡመር	

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል።

ፍ ር ድ

የሰበር አቤቱታው የቀረበው አመልካች ክስ ያቀረበበትና የሚች አባቱ የውርስ ሀብት መሆኑን የገለጸው የእርሻ ይዞታ አስቀድሞ ክስ መስርቶበትና ጉዳዩ በሽምግልና ያለቀ መሆኑ ተረጋግጦ ውሳኔ የተሰጠበት በመሆኑ ክሱ በፍርድ ባለቀ ጉዳይ ላይ የቀረበ ነው ተብሎ ውድቅ መደረጉን በመቃወም ነው።

ከመዝገቡ መረዳት እንደሚቻለው በፌ/መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት (ድሬዳዋ ምድብ ችሎት) የአሁን አመልካች በቀን 16/03/2013 ዓ.ም ባቀረቡት የውርስ ይጣራልኝ አቤቱታ ወላጅ አባታቸው አቶ ፋራህ ዱአሌ በቀን 01/01/1996 ዓ.ም ከዚህ አለም በሞት የተለዩ መሆኑን፤ አባታቸው ያፈሩት እና አሁን ድረስ በከሳሽ እጅ የሚገኝ በድሬዳዋ ከተማ አስተዳደር ጎል አደግ ገጠር ቀበሌ ክልል ውስጥ የሚገኝ ስፋቱ 10 ካ/ሜ የሆነ የእርሻ ቦታ ያለ መሆኑን ጠቅሰው ይኸው የአባታቸው የውርስ ሀብት የውርስ አጣሪ ተሹሞ እና ተጣርቶ የወራሽነት ድርሻቸው ለሚመለከተው አካል በመሸኛ እንዲተላለፍላቸው ጠይቀዋል።

ፍ/ቤቱም የውርስ አጣሪ በመሾም የውርስ ሀብቱ በመጣራት ሂደት ላይ እያለ ጣ/ገብ (የአሁን ተጠሪ) ወደ ክርክሩ ጣልቃ ገብተው ባቀረቡት አቤቱታ በመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያነት ክስ የቀረበበት ንብረት ከዚህ ቀደም ፍ/ቤቱ በቀን 07/02/2012 ዓ.ም በሰጠው ብይን ከሳሽ በጉዳዩ ላይ ክስ የማቅረብ መብትና ጥቅም የሌለው መሆኑን እንዲሁም ጉዳዩ አስቀድሞ በሽምግልና ታይቶ ያለቀ መሆኑን በማረጋገጥ መዝገቡን የዘጋው በመሆኑ አስቀድሞ በፍርድ ባለቀ ጉዳይ ላይ ከሳሽ አቤቱታ ሊያቀርብ አይገባም እንዲባል፤ ይህን የእርሻ ይዞታ ከሳሽም ሆነ አባቱ ይዘውትም ሆነ ተጠቅመውበት

የማያውቁ መሆኑን በአንጻሩ ከደርግ ጊዜ ጀምሮ ይዞ የሚጠቀምበት እራሱ እንደሆነ፤ የገጠር ይዞታ ማረጋገጫ የተሰጠው በ2010 ዓ.ም መሆኑን ጠቅሶ ከሳሽ በዚህ የእርሻ ይዞታ ላይ የውርስ ማጣራት አቤቱታ ሊያቀርብ የሚችልበት አንዳችም መብትና ጥቅም የለውም፤ እንዲሁም የእርሻ ይዞታውን ከመሬት ላራሹ ጊዜ ጀምሮ ይዞ እያስተዳደረ እና እየተጠቀመበት በመሆኑ አቤቱታው በይርጋ ቀሪ ነው በማለት ተከራክሯል፡፡

ጉዳዩ በዚህ መልኩ የቀረበለት የስር ፍርድ ቤት ክርክሩንና ማስረጃ ከሰማ በኋላ ከግራ ቀኙ ክርክርና አስቀድሞ በፍርድ ካለቀው መዝገብ (መ/ቁ 75415) ለመገንዘብ እንደተቻለው በሁለቱም መዝገቦች ለተነሳው ክርክር የስረ ነገር መነሻው ከሳሽ የሚች አባቱ የውርስ ሀብት መሆኑን የገለጸው በድሬዳዋ ከተማ አስተዳደር ጎለአደግ ገጠር ቀበሌ ማህበር የሚገኝ የእርሻ ይዞታ ነው፤ ይህም በሁለቱም መዝገቦች የቀረበው የስረ ነገር ክርክር ጭብጥ የሚች ፋራህ ዱአሌ የውርስ ሀብትን የሚመለከት እንደመሆኑ መጠን በዚህ መዝገብ የተጀመረው የውርስ ሀብት ማጣራት በመ/ቁ 75415 ተከፍቶ እልባት ካገኘው ለክርክር መነሻ የሆነው የውርስ ሀብት ይለቀቅልኝ ክስ ጋር የተለያዩ ናቸው ሊባል የሚችል ሆኖ አልተገኘም፤ በሌላ በኩል ከሳሽ በመ/ቁ 75415 የነበረው ክርክር በብይን ሊዘጋ የቻለው መብትና ጥቅም የለውም በሚል እና አሁን ደግሞ መብትና ጥቅሙን አረጋግጦ የመጣ በመሆኑ አሁን ያቀረበው የውርስ ማጣራት አቤቱታ ለማቅረብ የሚከለክለው ህጋዊ ምክንያት የሌለ መሆኑን ገልጾ ቢከራከርም ፍ/ቤቱ ከቀደመው መዝገብ ለማረጋገጥ እንደተቻለው በቀድሞው መዝገብ ፍ/ቤቱ በብይን ላይ እንዳሰፈረው ከሳሽ ወራሽ መሆኑን ሳያረጋግጥ ክስ የመሰረተ እና ይህም ሁኔታ በጉዳዩ ላይ መብትና ጥቅም የሌለው መሆኑን እንደሚያሳይ የጠቀሰ ቢሆንም በዋነኛነት ክሱን በብይን ሊዘጋው የቻለው ግን ጉዳዩ በሽምግልና ታይቶ የተቋጨ መሆኑን በመጥቀስ ነው፤ ከዚህ አንጻር ከሳሽ የቀድሞ መዝገብ ሊዘጋ የቻለው መብትና ጥቅም የለህም ተብሎ ነው በማለት ያቀረበው መከራከሪያ ተገቢነት ያለው ሆኖ አልተገኘም፡፡ በመሆኑም ከሳሽ አሁን ክስ የመሰረተበትን እና የሚች አባቱ የውርስ ሀብት መሆኑን የገለጸው የእርሻ ይዞታ አስቀድሞ በመ/ቁ 75415 በጣ/ገብ ላይ ክስ መስርቶበትና ጉዳዩ በሽምግልና ያለቀ መሆኑ ተረጋግጦ ውሳኔ ተሰጥቶበት ያለቀ በመሆኑ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 5(1) መሰረት አስቀድሞ በፍርድ ባለቀ ጉዳይ ያቀረበው ክስ ተቀባይነት የለውም በማለት ብይን ሰጥቷል፡፡

በዚህ ቅር በመሰኘት አመልካች ይግባኝ ለከፍተኛው ፍ/ቤት ቢያቀርቡም ብይኑ የሚነቀፍ አይደለም ተብሎ ይግባኙ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 337 መሰረት ተሰርዟል፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበው በዚህ ነው፡፡

አመልካች በቀን 14/06/2014 ዓ/ም ባቀረቡት የሰበር ማመልከቻ በስር ፍ/ቤት አስቀድሞ በመ/ቁ 75415 የተካሄደው ክርክር አመልካች በተጠሪ እና ሌሎች የክፍሉ ቀበሌ አመራር አካላት ላይ የመፋለም ክስ ለማቅረብ የተረጋገጠ መብት እና ጥቅም የለህም እንዲሁም ጉዳዩ አስቀድሞ በሽምግልና

ያለቀ ነው በማለት ክሴን ውድቅ በማድረግ በብይን መዝገቡ የተዘጋበት ነው። ይሁን እንጂ የሟች አባቴ ሚስት እና ወራሽ የሆኑ ሌሎች ልጆች ጭምር ያሉበት እንደመሆኑ መጠን አስቀድሞ በተደረገው ክርክር በወራሽነቴ ሳይሆን በራሴ የባለቤትነት ክስ ማቅረቤ ከዚያ በኋላ መብትና ጥቅሜን ለማረጋገጥ ውርሱ እንዲጣራ የመጠየቅ መብቴን የማያጣብብ ከመሆኑም ሌላ በእኔ ስም የተደረገ የሽምግልና ውሳኔ የለም እንጂ አለ ቢባል እንኳ በራሴ ላይ ብቻ ውጤቱ ከሚወሰን ባሻገር የአባቴ የውርስ ሀብትና ወራሾች ላይ የሚያመጣው አንዳችም ውጤት በሌለበት ሁኔታ የስር ፍ/ቤት የመፋለም እና የውርስ ህጎችን በአግባቡ መለየት ሳይችል ቀርቶ መከራከሪያዬን ወደ ጎን በመተው የሰጠው ብይን አግባብነት የሌለው ነው። የውርስ ማጣራት ውጤቱ ከማስረጃነት በዘለለ የሚያመጣው አንዳችም አስገዳጅነት የሌለው ሆኖ ሳለ ተጠሪ በዚህ ሂደት ላይ ጣልቃ ገብተው ለመከራከር የሚያበቃ በቂ ምክንያት በሌለበት ሁኔታ ከጅምሩ ጣልቃ እንዲገቡ የተደረገበት ሂደት አግባብነት የሌለው ከመሆኑም በተጨማሪ በእጄ በሚገኘው ይዞታ ላይ ምንም አይነት የፍሬ ነገር ማጣራት እና ማረጋገጥ ሳይኖር እንዲሁም በስሜም ሆነ በአባቴ ስም የተደረገ አግባብነት ያለው የሽምግልና ሂደት እና ውሳኔ ሳይኖር ተጠሪ በደፈናው የእኔን መብት በመጋፋት ባለመብት እንዲሆኑ የሚያስችላቸው ሁኔታ መፈጠሩ መሰረታዊ የህግ ስህተት በመሆኑ የስር ፍ/ቤቶች ብይንና ትዕዛዝ ተሽሮ የውርስ ማጣራቱ እንዲቀጥል ውሳኔ እንዲሰጥልኝ በማለት ቅሬታቸውን አቅርበዋል።

የሰበር አጣሪ ችሎትም በዚህ ጉዳይ በመፋለም ቀርቦ የነበረው ክስን አሁን በውርስ የቀረበው ክስ አንድ አይነት ክርክርና ጭብጥ እንዳለው ተቆጥሮ ድጋሚ የቀረበ ነው መባሉ ከፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ 5 ድንጋጌ አንጻር አግባብነቱን ለማጣራት በሚል ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ እና ተጠሪ መልስ እንዲሰጡበት ተደርጓል።

ተጠሪ በቀን 17/10/2014 ዓ.ም ባቀረቡት መልስ አመልካች ከአሁን በፊት በፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት በመ/ቁ 75415 በውርስ የተላለፈልኝን መሬት ተጠሪ ስለያዘብኝ ለቆ እንዲያስረክበኝ በማለት ዳኝነት ጠይቆ በብይን ውድቅ ተደርጎ እያለ ይህ የጸና የፍ/ቤት ውሳኔ ባልተሻረበት በዚሁ ሀብትና ንብረት ላይ የውርስ ሀብት ተጣርቶ እንዲተላለፍለት የጠየቀው ዳኝነት ቀድሞ በፍርድ ያለቀ ነው መባሉ አግባብ ነው፤ አመልካች ቀድሞውኑም በስረ ነገር ደረጃ ያቀረቡት መከራከሪያና የጠየቁት ዳኝነት ከሟች አባቴ በውርስ የተላለፈልኝ የውርስ ሀብት እያሉ ዳግም ይህንኑ የውርስ ሀብት ይጣራልኝ የሚሉበት ህጋዊ ምክንያት አይኖርም። በመ/ቁ 75415 የተሰጠው ብይን መብትና ጥቅም መሰረት ያደረገ ሳይሆን በአመልካችና በተጠሪ መካከል ይህን የእርሻ መሬት በተመለከተ ጉዳያቸው ከፍ/ቤት ውጭ በአማራጭ መግት መፍቻ በሽምግልና ታይቶ በስምምነት የተቋጨ በመሆኑ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 244(2)(ረ) መሰረት ክስ ሊቀርብ አይገባም በማለት የተሰጠ ነው። ይህ ብይን ጸንቶ ባለበት አመልካች በዚሁ የውርስ ሀብት ላይ የጠየቀው የውርስ ሀብት ይጣራልኝ ጉዳይ በሽምግልና ያለቀ መሆኑ ተረጋግጦ

በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 5(1) እና 245(2) መሰረት መሰረዙ አግባብ በመሆኑ የስር ፍ/ቤቶች ውሳኔ ሊጸና ይገባል በማለት ተከራክረዋል። መዝገቡ ለምርመራ የተቀጠረውም በዚህ ሁኔታ ነው።

የክርክሩ አመጣጥ ከላይ ባጭሩ የተገለፀው ሲሆን በበኩላችን የስር ፍርድ ቤቶች የአመልካችን ክርክር ውድቅ ያደረጉት በአግባቡ ነው ወይስ አይደለም የሚለውን ጭብጥ በመያዝ ጉዳዩን መርምረናል።

ጉዳዩን እንደመረመርነው በመ/ቁ 75415 የአሁን አመልካች ተጠሪን ጨምሮ በሶስት ሰዎች ላይ ባቀረቡት ክስ መሬቱ ለአሁን ተጠሪ መተላለፉ አላግባብ ነው ተብሎ አከራካሪው መሬት እንዲመለስላቸው፣ ለተጠሪ የተሰጠው ማስረጃ እንዲሰረዝ እንዲሁም ተጠሪ በመሬቱ ላይ የወሰደው የካሳ ገንዘብ ብር 30000.00 (ሰላሳ ሺህ) እንዲመለስላቸው ዳኝነት ጠይቀው ነበር። ተከሳሾችም በዚህ ጉዳይ በሽምግልና ገብተን ዕርቅ የፈፀምን እና በስምምነት የተቋጨ በመሆኑ ዳግመኛ ልንከሰስ አይገባም የሚሉና ሌሎች መቃወሚያዎች አቅርበዋል። ፍርድ ቤቱም የግራ ቀኙን ክርክር መርምሮ በ07/02/2012 ዓ.ም በሰጠው ብይን በደረሰበት መደምደሚያ ጉዳዩ አስቀድሞ በሽምግልና ያለቀ መሆኑ ስለተረጋገጠ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 244(2)(ረ) መሰረት ዳግመኛ ክስ ሊቀርብበት አይገባም በማለት ክሱን ውደቅ አድርጓል።

ከዚህ በኋላ አመልካች ይህንኑ የእርሻ ቦታ ጠቅሰው ይኸው የአባታቸው የውርስ ሀብት በመሆኑ የውርስ አጣሪ ተሹሞና ተጣርቶ የወራሽነት ድርሻቸው ተለይቶ ለሚመለከተው አካል በመሸኛ እንዲተላለፍላቸው እንዲወሰን ዳኝነት ጠይቀዋል።

ክርክሩንና ፍሬ ነገሩን ለማጣራት በህግ ስልጣን የተሰጣቸው የስር ፍርድ ቤቶች ግራቀኙ ያደረጉትንና በዕርቅ የተቋጨበትን ስምምነት መሰረት በማድረግ አስቀድሞ የተሰጠውን ብይን ይዘት መርምረው አመልካች አሁን ያቀረቡት በመሬቱ ላይ የውርስ ሀብት ይጣራልኝ ጥያቄ አስቀድሞ በዕርቅ ስምምነት ዕልባት ያገኘ መሆኑንና ይኸው በበላይ ፍርድ ቤት ያልተለወጠ መሆኑን በፍሬ ነገር ደረጃ በማረጋገጥ ውሳኔ ሰጥተዋል።

እንደሚታወቀው አንድ ፍርድ ቤት የሰጠው ውሣኔ በሕግ በተደነገገው ሥርዓት መሠረት በይግባኝ ሥርዓት ወይም በሰበር ካልታረመ በጉዳዩ ላይ የመጨረሻና አስገዳጅነት ያለው ስለመሆኑ ከፍ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 5/1/ ግልጽ ድንጋጌ መገንዘብ ይቻላል። አመልካች በዕርቅ ስምምነታቸው መሰረት ክርክሩ እንዲቋጭ መደረጉ አግባብ አልነበረም የሚሉ ቢሆን እንኳ ይግባኝ በማቅረብ አላስለወጡም ወይም አላሻሩም።

ስለሆነም በዕርቅ በስምምነታቸው መሰረት እልባት ያገኘው ጉዳይ ባልተሻረበት ወይም ባለተለወጠበት ሁኔታ አመልካች በስምምነት አልቋል ተብሎ ውሳኔ ባረፈበት ንብረት ላይ ውርስ

እንዲጣራ በሚል ያቀረቡት የዳኝነት ጥያቄና ክርክር የፍርድ ቤቱን ውሣኔ/ትዕዛዝ አስገዳጅነትና ተፈፃሚነት መርህንና የፍ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 5/1/ የሚጥስ ነው፡፡ ስለሆነም የስር ፍርድ ቤቶች ይህን ምክንያትና መሠረታዊ የዳኝነት ሥራ አካሄድ መርሆች መሠረት በማድረግ የአመልካችን ክርክር ውድቅ ማድረጋቸው የሚነቀፍ ሆኖ አላገኘነውም፡፡ ስለሆነም የተላለፈው ብይንና ትዕዛዝ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የለበትም በማለት ተከታዩን ወስነናል፡፡

ው ሣ ኔ

1. የፌደራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ 81125 በቀን 17/09/2013 ዓ.ም የሰጠው ብይን እንዲሁም የፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ 18326 በቀን 15/03/2014 ዓ.ም ያሳለፈው ትዕዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 348(1) መሰረት ፀንቷል፡፡
2. ግራ ቀኙ በዚህ ፍርድ ቤት ያወጡትን ወጭና ኪሣራ የየራሣቸውን ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሰ/ጥ

የሰ/መ/ቁ. 185154

ቀን፡- ግንቦት 27 ቀን 2013 ዓ/ም

ዳኞች፡- ብርሃኑ አመነው

ተሾመ ሽፈራው

ሀብታሙ እርቅይሁን

ብርሃኑ መንግሥቱ

ነፃነት ተገኝ

አመልካች፡- ወ/ሮ አበባየሁ ብርሌ

ተጠሪ፡- 1. አቶ መሉዓለም ፈንታ

2. ወ/ሮ እናታለም ፈንታ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሠጠ፡፡

ፍርድ

የሰበር አቤቱታው የቀረበው የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር አጣሪ ችሎት በሠጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈጽሞበታል በሚል ነው፡፡ የክርክሩን አመጣጥ ከስር ፍርድ ቤት የመዝገብ ግልባጭ እንደተረዳነው አመልካች የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 50544 ግንቦት 22 ቀን 2011 ዓ/ም በሠጠው ውሳኔ የሰበር አቤቱታ ሰኔ 26 ቀን 2011 ዓ/ም በተጻፈ በመዝገብ ቁጥር 90087 ያቀረበ ቢሆንም ፍርድ ቤቱ ጥቅምት 04 ቀን 2012 ዓ/ም በዋለው ችሎት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በከፊል በሠጠበት ጉዳይ ውሳኔ ከተሰጠ ከሦስት ወር ከ4 ቀን በኋላ የቀረበና ጊዜው ያለፈበት ነው በማለት መዝገቡን ዘግቷል፡፡ አመልካች በመዝገብ ቁጥር 92606 ያቀረቡትን የሠበር ማስፈቀጃ አቤቱታ ፍርድ ቤት በቂ ምክንያት ያልቀረበ በመሆኑና የዘገየውም በአመልካች ቸልተኝነት ስለሆነ በማለት ጥቅምት 10 ቀን 2012 ዓ/ም ውደቅ አድርጓል፡፡

የሠበር አቤቱታ የቀረበው በዚህ ውሳኔ ነው፡፡ የአመልካች የሠበር አቤቱታ ይዘትም ይግባኝ ሰሚ ችሎት ይግባኙ መልሰ ሰጭን ያስቀርባል ሲል በከፊል ያጸናው ስለመሆኑ አላውቅም፡፡ ከተሰጠው መጥሪያ ላይም በከፊል የጸና ስለመሆኑ አይገልጽም፡፡ በፍርድ ቤቱ ችግር እንጂ በአመልካች ቸልተኝነት ባለመሆኑ የሠበር አቤቱታ እንዳቀርብ ሊፈቀድልኝ ይገባል የሚል ሲሆን የሠበር አጣሪ ችሎት ጉዳዩን ተመልክቶ ይግባኝ ሰሚ ችሎት ውሳኔ ላይ አመልካች አጠቃለው የሠበር አቤቱታ ሲያቀርቡ ቀደም ሲል በከፊል የተሰረዘ ቅሬታ ላይ ጊዜው አልፎበታል መባሉ ተገቢነቱን ለማጣራት ለሰበር ሰሚ ችሎት

ያስቀርባል በማለት ተጠሪዎች መልስ እንዲያቀርቡ አዟል። ተጠሪዎች መጥሪያ ደርሷቸው ባለመቅረባቸው ጉዳዩ በሌለበት ታይቷል።

የክርክሩ ሂደት በአጭሩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን እኛም አመልካች ያቀረቡት የሠበር አቤቱታ ጊዜው ያለፈበት ነው ወይስ አይደለም? የሚለውን በጭብጥነት በመያዝ መዝገቡን መርምረናል።

እንደመረመርነው በተሻሻለው የአማራ ክልል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 223/2007 አንቀጽ 17(4) መሠረት የሠበር አቤቱታ ማቅረቢያ ጊዜ 90 ቀናት ነው። በዚህ ጊዜ ውስጥ ካልቀረበ የሠበር አቤቱታው ጊዜ ያለፈበትና የማይመረመር ነው። አመልካች የሠበር አቤቱታ ያቀረበበትን የመጨረሻ ፍርድ የሠጠው የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ግንቦት 22 ቀን 2011 ዓ/ም ነው። አመልካች የሠበር አቤቱታ ያቀረቡት ደግሞ ሠኔ 26 ቀን 2011 ዓ/ም ነው። ይሕም 90 ቀናት ከመድረሱ በፊት መቅረቡን ያረጋግጣል። የሠበር አጣሪ ችሎቱ የአመልካች የሠበር አቤቱታ ጊዜ ያለፈበት ነው ያለው ይግባኝ ሰሚ ችሎቱ መልስ ሰጭዎችን ያስቀርባል ያለው በተከሳሽ ከሳሽነት ክሱ ሲሆን የአመልካችን ክሰ በተመለከተ ውሳኔው በከፊል አጽንቷል፤ በከፊል የጸናው መጋቢት 12 ቀን 2011 ዓ/ም በመሆኑ የ90 ቀናት የሠበር አቤቱታ ማቅረቢያ ጊዜ አልፎበታል በሚል ነው።

የፍትሐ ብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕጉ ክርክር ቀልጣፋ፣ ውጤታማና ወጭና ጊዜ ቆጣቢ እንዲሁም ፍተሐዊ በሆነ ሁኔታ እንዲመራ ዓላማ አድርጎ የተቀረጸ ነው። በፍብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 234(1(ረ) መሠረት ክስ የቀረበበት ተከሳሽ የሆነ ወገንም በከሳሹ ላይ የተከሳሽ ከሳሽነት ክስ እንዲያቀረብ የፈቀደበት ምክንያትም ወጭና ጊዜ ቆጣቢ በሆነ አግባብ እንዲመራ ካለው ሃሳብ ነው። ክርክሩ በአንድ ላይ ሲመራ የቆየ ክስ ሆነ የተከሳሽ ከሳሽነት ክስ የቀረበበት ክርክር በይግባኝ ሆነ በሰበር አቤቱታ በሚቀርብበት ጊዜ አንድ ላይ ተጠቃሎ ቢቀርብ በአንድ ጉዳይ ብዙ ፋይል እንዳይከፍት የሚያደርግና የፍርድ ቤቱን ሆነ የተከራካሪዎችን ጊዜ የሚቆጥብ ነው። በክርክር ሂደት ክርክሩ ተጠቃሎ ከመወሰኑ በፊት በግልጽ በከፊል የተወሰነ ካለና ከቀጠለው ክርክር ጋር ተያያዥነት የሌለው እስከሆነ ድረስ መብቱን ለማስከበር በጉዳዩ ላይ ይግባኝ ማቅረብ የፈለገ ተከራካሪን የሚከለክል የሥነ-ሥርዓት ሕግ ድንጋጌ የለም። በሌላ በኩል ተከራካሪው ክርክሩን አጠቃሎ ይግባኝ ወይም የሠበር አቤቱታ ከማቅረብ ግን ሊከለከል አይገባውም። በተያዘው ጉዳይም ይግባኝ ሰሚ ችሎት በከፊል የአመልካችን የይግባኝ ቅሬታ የሠረዘ ቢሆንም በከፊል የቀጠለው ክርክር ላይ ተጠቃሎ ውሳኔ የተሰጠው ግንቦት 22 ቀን 2011 ዓ/ም በመሆኑ አመልካች ክርክሩ ተጠቃሎ ከተቋጨ በኋላ የሠበር አቤቱታ 90 ቀናት ሳያልፍ አቅርበው እያለ የሰበር አጣሪ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 90087 ጥቅምት 04 ቀን 2012 ዓ/ም ጊዜው ያለፈበት አቤቱታ ነው በማለት መዝገቡን መዘጋቱ የአመልካችን ፍትሕ የማግኘት መብት አላግባብ የከለከለና መሠረታዊ የሆነ የክርክር አመራር ግድፈት ያለበት ሆኖ ስላገኘነው ሊታረም የሚገባ ነው ብለናል።

በሌላ በኩል አመልካች መብታቸውን ለማስከበር የሠበር ማስፈቀጃ አቤቱታ በመዝገብ ቁጥር 92606 ያቀረቡ ሲሆን ምንም እንኳን ከላይ እንደተመለከትነው የሰበር አቤቱታ ማቅረቢያ ጊዜው ያላለፈበት ቢሆንም በይግባኝ ሰሚ ችሎት በከፊል የተሰረዘ ቅሬታ ቢኖርም አመልካች አጠቃለው የሠበር አቤቱታ ያቀረቡት በሥነ-ሥርዓት ሕጉ ክርክሮች ተጠቃለው ቀልጣፋ፣ ወጭና ጊዜ ቆጣቢ በሆነ አግባብ እንዲመሩ ያሰበውን ዓላማ ከግብ ለማድረስ በሚያስችል መልኩና ከአንድ ጉዳይ ለሚመነጭ የተለያየ ፋይል እንዳይከፈት ለመከላከል ሆኖ እያለ፤ በሕጉ የተዘረጋወን ሥርዓት የተከተለን ተከራካሪ የሠበር አቤቱታ አቀራረብ ላይ ቸልተኝነት አለበት ተብሎ የሠበር ማስፈቀጃ አቤቱታው ውድቅ መደረጉ ስህተት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

ውሳኔ

1. የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር አጣሪ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 90087 ጥቅምት 04 ቀን 2012 ዓ/ም እና በመዝገብ ቁጥር 92606 ጥቅምት 10 ቀን 2012 ዓ/ም የሠጠው ውሳኔ በፍብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348(1) መሠረት ተሽሯል፡፡

2. የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር አጣሪ ችሎት አመልካች በመዝገብ ቁጥር 90087 ያቀረቡትን የሠበር አቤቱታ ተቀብሎ በመመርመር የመሠለውን እንዲወስን ጉዳዩን በፍብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 341(1) መሠረት መልሠናል፡፡

3. አመልካች በዚህ ችሎት ያወጡትን ወጭና ኪሣራ የራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

ትዕዛዝ

- ውሳኔው ለሥር ፍርድ ቤት ይተላለፍ፡፡ የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር አጣሪ ችሎት በውሳኔው መሠረት እንዲፈጽም አዘናል፡፡ ይጻፍ
- መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሠ/ኃ

የሰ.መ.ቁ. 242542

ጥቅምት 26 ቀን 2016 ዓ.ም

ዳኞች፡- እትመት አሠፋ

ደጀኔ አያንሳ

ኑረዲን ከድር

መላኩ ካሣዬ

ሐብታሙ እርቅ ይሁን

አመልካቾች፡- 1. ወ/ሮ ሳፊያ በከር } ቀርበዋል

2. ወ/ሮ አሚና በከር }

ተጠሪ፡- አቶ አብዲ መሐመድ - አልቀረቡም

መዝገቡ ለምርመራ የተቀጠረ ነው። በዚሁ አግባብ መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል።

ፍርድ

የሰበር አቤቱታው የቀረበው አመልካቾች የካቲት 06 ቀን 2015 ዓ.ም ጽፈው ባቀረቡት የሰበር አቤቱታ በኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የጎሮ ጉቱ ወረዳ ፍርድ ቤት በመ.ቁ 36558 ሚያዝያ 21 ቀን 2014 ዓ.ም የአመልካቾች ክስ ድጋሚ የቀረበ በመሆኑ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 5 መሠረት ተቀባይነት የለውም በማለት የሰጠው ብይን፤ ይህንኑ ብይን በማጽናት በየደረጃው ያሉ የሥር የክልሉ ፍርድ ቤቶች የሰጡት ውሳኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስሕተት የተፈጸመበት በመሆኑ በሰበር ታይቶ ሊታረም ይገባል በማለት አቤቱታ በማቅረባቸው ነው።

ጉዳዩ የእርሻ መሬት ውርስን በሚመለከት የቀረበን ክርክር የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው በኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የጎሮ ጉቱ ወረዳ ፍርድ ቤት ነው። በስር ፍርድ ቤት በተደረገው ክርክር የአሁን አመልካቾች ከሳሾች፤ የአሁን ተጠሪ ደግሞ ተከሳሽ በመሆን ተከራክረዋል። አመልካቾች በስር ፍርድ ቤት ያቀረቡት ክስ ይዘት በአጭሩ፡- የሚች ወንድማችን አቶ አሕመድ በከር ወራሾች መሆናችን ተረጋግጧል፤ ስለሆነም ተጠሪ አዋሳኙ በክሱ የተገለጸውን ይዞታ እንዲያካፍለን ይወሰንልን በማለት ዳኝነት ጠይቀዋል። ተጠሪ በሰጡት መልስ ከዚህ ቀደም በመ.ቁ 34030 አከራካሪውን ይዞታ በተመለከተ ውሳኔ ተሰጥቶበታል፤ ስለሆነም የአመልካቾች ክስ ድጋሚ የቀረበ ክስ ነው ተብሎ ውድቅ ሊደረግ ይገባል በማለት የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ አቅርበዋል።

ጉዳዩ የቀረበለት ፍርድ ቤትም በተጠሪ የቀረበውን የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ አመልካቾች ካቀረቡት ክስ እና በመ.ቁ 34030 ከተሰጠው ውሳኔ ጋር በማገናዘብ መርምሮ አመልካቾች አከራካሪውን ይዞታ

በሚመለከት ከዚህ ቀደም በመ.ቁ 34030 ክስ አቅርበው ጉዳዩ የቀረበለት ፍርድ ቤት ውሳኔ ሰጥቶበታል፤ ስለሆነም ይህንኑ ይዞታ በሚለከት በድጋሚ ያቀረቡት ክስ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 5 መሠረት ተቀባይነት የለውም በማለት በብይን ውድቅ አድርጎታል፡፡ ይህም ብይን በየደረጃው ባሉ የሥር የክልሉ ፍርድ ቤቶች ጸንቷል፡፡

የሰበር አቤቱታው የቀረበው ይህን ውሳኔ በመቃወም ሲሆን ይዘቱም፡- አመልካቾች በስር ፍርድ ቤት ክስ ያቀረብነው የወራሽነት መብታችን ተጠብቆ የሟች ወንድማችንን የውርስ ይዞታ እንድንካፈል ነው፤ ስለሆነም ክርክሩ ተገቢነት ባለው ማስረጃ ሳይጣራ የአመልካቾች ክስ ድጋሚ የቀረበ በመሆኑ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 5 መሠረት ተቀባይነት የለውም በማለት የተሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስሕተት የተፈጸመበት በመሆኑ በሰበር ታይቶ ሊታረም ይገባል የሚል ነው፡፡

የአመልካቾች የሰበር አቤቱታ በሰበር አጣሪው ችሎት ተመርምሮ 1ኛ አመልካች ከዚህ በፊት በወረዳ ፍርድ ቤት በመ.ቁ 34030 ያቀረቡት ዳኝነት ተጠሪ በጉልበት የያዘውን የጫት ይዞታ እንዲመልስ የሚል ሲሆን አሁን የጠየቁት ዳኝነት ደግሞ የሟች ወንድማችን ውርስ ይዞታ ያስረክበን የሚል ከመሆኑ አኳያ ከዚህ ቀደም የመጨረሻ ውሳኔ ያገኘ ነው በሚል የመወሰኑን አግባብነት ለመመርመር የሚል ማስቀረቢያ ጭብጥ ተይዞ ተጠሪ መልስ እንዲሰጡበት ተደርጎ ጉዳዩ ለዚህ ችሎት ቀርቧል፡፡

ተጠሪ መጋቢት 12 ቀን 2015 ዓ.ም የሰጡት መልስ ይዘት በአጭሩ፡- በመ.ቁ 34030 1ኛ አመልካች አከራካሪውን ይዞታ ለመውረስ መብት የላትም በማለት ተወስኗል፤ 2ኛ አመልካችም ይህን ውሳኔ በመቃወም በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 358 መሠረት መቃወሚያ አቅርባ አከራካሪውን ይዞታ ለመውረስም ሆነ ለመጠየቅ መብት የላትም በሚል ተወስኗል፤ ይህ ውሳኔ በይግባኝ አልተሻረም፤ ስለሆነም የስር ፍርድ ቤቶች አመልካቾች ያቀረቡት ክስ ድጋሚ የቀረበ በመሆኑ ተቀባይነት የለውም በማለት የሰጡት ውሳኔ ተገቢ ስለሆነ ሊጸና ይገባል የሚል ነው፡፡

አመልካቾችም በሰጡት የመልስ መልስ በመ.ቁ 34030 በቀረበው ክስ መጠየቅ ይገባው የነበረው ዳኝነት የውርስ ንብረት ይከፋፈል የሚል መሆን ሲገባው በጸሐፊ ስሕተት ተጠሪ አከራካሪውን የጫት ይዞታ በጉልበት ስለያዘብኝ ይልቀቅልኝ በሚል ዳኝነት ተጠይቆ ለተጠሪ ተወስኖለታል፤ ይህ ውሳኔ አመልካቾች የውርስ ድርሻችንን ክስ አቅርበን ከመጠየቅ አያግደንም በማለት የሰበር አቤቱታቸውን በማጠናከር የመልስ መልስ ሰጥተዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ በአጭሩ ከላይ የተገለጸውን ይመስላል፡፡ ይህ ችሎትም በሰበር አጣሪው ችሎት ያስቀርባል ሲባል የተያዘውን ነጥብ ከግራ ቀኙ ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸው ሕጎች ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለው መርምሮታል፡፡

ከክርክሩ ሒደት መገንዘብ እንደቻልነው ተጠሪ ከዚህ ቀደም በመ.ቁ 34030 በአሁን 1ኛ አመልካች ላይ ባቀረቡት ክስ 1ኛ አመልካች ከሕግ ውጪ የያዘችውን አከራካሪውን ይዞታ እንድትለቅ ይወሰንልኝ በማለት ዳኝነት ጠይቀው 1ኛ አመልካች በጉዳዩ ላይ መልስ ሰጥተው ጥቅምት 08 ቀን 2014 ዓ.ም 1ኛ አመልካች ይዞታውን እንዲለቁ ውሳኔ የተሰጠ መሆኑን፤ 2ኛ አመልካችን ይህን ውሳኔ በመቃወም በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 358 መሠረት መቃወሚያ አቅርበው ውሳኔው ሳይለወጥ የቀረ መሆኑን፤ አመልካቾች አሁን ለዚህ የሰበር አቤቱታ መነሻ በሆነው የስር መዝገብ ባቀረቡት ክስ የጠየቁት ዳኝነት ቀደም ሲል በመ.ቁ 34030 ውሳኔ ያረፈበትን ይዞታ የሚመለከት መሆኑን፤ ከዚህ ቀደም በመ.ቁ 34030 በተደረገው ክርክር እና አሁን ለዚህ ሰበር አቤቱታ በሆነው ጉዳይ የክሱ መሠረት የሆነው ጉዳይ በክሱ የተገለጸው አከራካሪው የጫት ይዞታ መሆኑን ነው፡፡

በመሠረቱ በሌላ በልዩ ሕግ ካልተገደበ በቀር የፍትሐብሔር ክርክር የሚመራው በፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ሕጉ ነው፡፡ የዚሁ ሕግ ዋና ዓላማም የሰው ልጆች ፍትሐ ብሔራዊ ከሆኑ መሰረታዊ የስረ ነገር ሕግጋት እና ዉሎች ያገኟቸዉ መብቶችና ጥቅሞች እንዲሁም የገቧቸዉ ግዴታዎች እና ኃላፊነቶች ጊዜን ጉልበትን እና ወጪን ቆጣቢ በሆነ መንገድ በተግባር እንዲተረጎሙ በማድረግ ፍትሐዊ የሆነ ውሳኔ መስጠት ነው፡፡ የሥነ ሥርዓት ሕጉ ይህንን ግብ ለማሳካት ከዘረጋቸዉ ሥነ ሥርዓቶች መካከል አንዱ የመጨረሻ ውሳኔ ስላገኙ የሚደነግገው ክፍል ነው፡፡

የመጨረሻ ውሳኔ ስላገኙ ጉዳዮች የሚደነግገው የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 5 በንዑስ ቁጥር (1) ላይ በሕግ ስልጣን የተሰጠው ማንኛውም ፍርድ ቤት ክርክሩን ተቀብሎ የመጨረሻ የፍርድ ውሳኔ ከሰጠ በኋላ ቀድሞ በፍርድ የተወሰነው ክርክር ሥረ ነገር እና የተያዘው ጭብጥ አንድ ዓይነት ከሆነ በክርክሩ ላይ የነበሩት ወይም ከተከራካሪዎቹ መብት ያገኙ ሶስተኛ ወገኖች በዚያው ነገር ሁለተኛ ክስ ወይም ማናቸውንም ዓይነት ሌላ ክርክር ለማቅረብ አይችሉም በማለት ይደነግጋል፡፡ በዚህ አግባብ የሚቀርበው መቃወሚያም የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ የሚቀርብበትን ሥርዓት አስመልክቶ በተደነገገው የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 244 ድንጋጌ ላይ በመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያነት የሚቀርቡ ናቸው ተብለው ከተዘረዘሩት ውስጥ አንዱ ነው፡፡

በሕግ ሥልጣን በተሰጠው ማናቸውም ፍርድ ቤት ታይቶ የመጨረሻ ውሳኔ ያገኘ ጉዳይ ድጋሚ ክስ ሊቀርብበት አይገባም በማለት የተደነገገበት ዋና ዓላማ አንድ ተከራካሪ ወገን በተመሳሳይ ጉዳይ ላይ በተለያየ ጊዜ ክስ እየቀረበበት ጊዜውን እንዳያባክን፤ ተጨማሪ ወጪ እንዳያወጣ እና እንዳይሸማቀቅ ለማድረግ፤ አንድ ፍርድ ቤት የሰጠው ውሳኔ በበላይ ፍርድ ቤት እስካልተሻረ ድረስ በሕብረተሰቡ ዘንድ ተቀባይነት እንዲኖረው ለማድረግ፤ ክርክሮች በአጭር ጊዜ ውስጥ መቋጫ እንዲኖራቸው ለማድረግ፤ ሕጉ ላልተፈለገበት ዓላማ እንዳይውል በመከላከል የፍትሕ አስተዳደር ሥርዓቱ ተገማች እና ፍትሐዊ እንዲሆን ለማድረግ ስለመሆኑ በዘርፉ ከዳበረው ሥነ ሕግ መገንዘብ ይቻላል፡፡ ስለሆነም አንድ ጉዳይ

ስልጣን ባለው ፍርድ ቤት ታይቶ ውሳኔ ያገኘ መሆኑ ከተረጋጠ አዲስ የቀረበውን ክስ በድጋሚ አይቶ ውሳኔ መስጠት ከላይ የተመለከተውን የሥነ ሥርዓት ሕጉን አይነተኛ ዓላማ የማያሳካ እና በተመሳሳይ ጉዳይ ላይ የተጣረሰ ውሳኔ ሊሰጥ የሚችልበትን ዕድል የሚፈጥር በመሆኑ ፍርድ ቤቶች ሕጉን በጥብቅ ሊተገብሩት ይገባል፡፡

በያዝነው ጉዳይ አመልካች እና ተጠሪ የሚከራከሩበት የጫት ይዞታ ከዚህ ቀደም ተጠሪ በመ.ቁ 34030 1ኛ አመልካች ከሕግ ውጪ ይዛብኛለች በማለት ክስ አቅርበው 1ኛ አመልካች መልስ እንዲሰጡት ተደርጎ ይዞታውን እንዲለቁ ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡ የአሁን 2ኛ አመልካችም የክርክሩ ተካፋይ ሳልሆነ የተሰጠው ውሳኔ መብቴን ይነካል በማለት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 358 መሠረት መቃወሚያ አቅርበው ውሳኔው ሳይለወጥ ቀርቷል፡፡ አመልካቾች አሁን ለዚህ የሰበር አቤቱታ መነሻ በሆነው የስር መዝገብ ባቀረቡት ክስ የጠየቁት ዳኝነት ቀደም ሲል በመ.ቁ 34030 ውሳኔ ያረፈበትን ያንኑ ይዞታ የሚመለከት ነው፤ ይህም ከዚህ ቀደም በመ.ቁ 34030 በተደረገው ክርክር እና አሁን ለዚህ ሰበር አቤቱታ በሆነው ጉዳይ በተደረገው ክርክር የክሱ መሠረት የሆነው ይዞታ ተመሳሳይ ይዞታ መሆኑን እና ተከራካሪዎችም ተመሳሳይ መሆናቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ አመልካቾች ቀደም ሲል በነበረው ክርክር ይዞታው የእኛ ነው በሚል በተከሳሽነት ዘንግ የተከራከሩ ሲሆን አሁን ባቀረቡት ክስ ላይ በውርስ የሚገባን ይዞታ ነው በሚል መብቱን ያገኙበትን መንገድ በመለወጥ የተከራከሩ ቢሆንም በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 5/2 መሠረት በቀድሞ ክርክር የመከላከያ ክርክር አካል ሊሆን የሚገባው ጉዳይ አብሮ እንዳለቀ የሚቆጠር ስለመሆኑ ከተመለከተው አንፃር ስንመለከተው የውርስ ነው የሚለው ክርክር በቀድሞ መዝገብ ላይ ክርክሩን አንስተው ሊከራከሩበት የሚችሉት ጉዳይ ከመሆኑ አንጻር የወረዳው ፍርድ ቤት የአመልካቾች ክስ ድጋሚ የቀረበ ነው በማለት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 5 መሠረት በብይን ውድቅ ማድረጉ በአግባቡ ነው ከሚባል በቀር የተፈጸመ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስሕተት አላገኘንበትም፡፡ በዚህም ምክንያት ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

ውሳኔ

1. በኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የጎሮ ጉቱ ወረዳ ፍርድ ቤት በመ.ቁ 36558 ሚያዝያ 21 ቀን 2014 ዓ.ም የሰጠው ብይን፤ ይህንኑ ብይን በማጽናት የምሥራቅ ሐረርጌ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ.ቁ 100352 ሠኔ 29 ቀን 2014 የሰጠው ውሳኔ፤ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ.ቁ 401664 ሕዳር 21 ቀን 2015 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ፤ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ.ቁ 420536 ጥር 30 ቀን 2015 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 348/1 መሠረት ጸንቷል፡፡
2. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡

- መዝገቡ ውሳኔ ስላገኘ ተዘግቷል፡፡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፌርማ አለበት

ፅ/ወ

የሰ/መ/ቁጥር 198033

ጥቅምት 5 ቀን 2014 ዓ/ም

ዳኞች፡- ብርሀኑ አመነው

ተሾመ ሽፈራው

ሀብታሙ እርቅይሁን

ብርሀኑ መንግስቱ

ነፃነት ተገኝ

አመልካች፡- የሸ ኃ/የተ/የግ/ማህበር - አልቀረቡም

ተጠሪ፡- የኢትዮጵያ መኪና መገጣጠሚ ኩባንያ (አምቼ) - ጠበቃ በላይ ከተማ - ቀርቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍርድ

ክርክሩ የመኪና ሽያጭ ውልን መሰረት ያደረገ ሲሆን ጉዳዩ በተጀመረበት የፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት አመልካች ተከሳሽ ተጠሪ ደግሞ ከሳሽ በመሆን ተከራክረዋል፡፡

ተጠሪ መጋቢት 11 ቀን 2010 ዓ.ም ፅፎ ባቀረበው ክስ ከግንቦት 2004 ዓ.ም እስከ ህዳር 2007 ዓ.ም በተለያዩ ጊዜያት በተደረጉ 4 ውሎች ቲ 38 ኤች ሲ ካብ መኪናዎች፣ ኤቪኮ ኤቲ 720 ቲኤች መኪናዎች እንዲሁም ፌንግሺን ሀይቦድ ሰሚ ትሬለሮችን ተጠሪ ለአመልካች በድምሩ በብር 100,850,000 (አንድ መቶ ሚሊዮን ስምንት መቶ ሀምሳ ሺ) ሸጧል፡፡ እስከ ጥር 22 ቀን 2010 ዓ.ም ድረስ ወለድና ቅጣትን ጨምሮ አመልካች ከሚፈለግበት ጠቅላላ ገንዘብ ብር 111,420,995.00 (አንድ መቶ አስራ አንድ ሺ አራት መቶ ሀያ ሺ ዘጠኝ መቶ ዘጠና አምስት) ላይ ብር 80,116,620.00(ሰማንያ ሚሊዮን አንድ መቶ አስራ ስድስት ሺ ስድስት መቶ ሀያ) ክፍያ የፈጸመ ሲሆን ቀሪ ክፍያውን ብር 31,306,375 (ሰላሳ አንድ ሚሊዮን ሶስት መቶ ስድስት ሺ ሶስት መቶ ሰባ አምስት) እንዲከፍል ይወሰንልኝ በማለት ዳኝነት ጠይቋል፡፡

አመልካች ግንቦት 8 ቀን 2010 ዓ.ም ዕፎ ባቀረበው መልስ ከተጠሪ ጋር የመኪና ሽያጭ ውል ማድረጉን ሳይክድ በውሎቹ የተመለከተውን ዋጋ በቅድመ ክፍያ እና በየወሩ በደረሰኝ የከፈልን ሲሆን አሁንም እየከፈልን እንገኛለን፡፡ ተጠሪ እ.አ.አ. መጋቢት 18 ቀን 2016 ዓ.ም በቁጥር 114/2016 ለአመልካች በፃፈው ደብዳቤ እስከ የካቲት 21 ቀን 2008 ዓ.ም ድረስ ያልተከፈለው ቀሪ እዳ ብር 18,703,775.55 መሆኑን ገልጿል፡፡ ከዚህ ጊዜ በኋላ አመልካች ብር 3,132,965.31 የከፈለ ሲሆን ወ/ሮ ሮዛ ለአመልካች መክፈል የነበረባቸውን ብር 3,866,707 ከተጠሪ ለገዛናቸው መኪኖች እዳ መክፈያ እንዲሆን ጥቅምት 18 ቀን 2010 ዓ.ም በተዋዋልነው መሰረት ክፍያውን ለተጠሪ ፈፅመዋል፡፡ አመልካች ከተጠሪ ለገዛቸው 33 ተሽከርካሪዎች ከእያንዳንዱ ተሽከርካሪ የተሽከርካሪውን ዋጋ 3% ኮሚሽን ተጠሪ ለአመልካች ሊከፍል ወይም ከእዳው ተቀናሽ ሊደረግ የተስማማንበት ብር 2,917,500፣ ተሽከርካሪዎቹን ከውጪ ሀገር ለማስመጣት የሚያስችል የውጭ ምንዛሬ ለማግኘት በባንክ የኤልሲ ሂሳብ ሲከፈት ለአመልካች የሚከፈል 6% ኮሚሽን ብር 877,799፣ አመልካች ለገዛቸው እያንዳንዱ መኪና ከዋጋው ላይ 2% ዊዝሆልዲንግ ብር 2,017,000፣ ለእያንዳንዱ መኪና ብር 100,000 የሚያወጣ መለዋወጫ ሊታሰብልን ስምምነት የተደረገበት የ26 መኪኖች ብር 2,600,000 ተቀናሽ አልተደረገም፡፡ ከላይ የተዘረዘሩት ተቀናሾች በድምሩ ብር 15,411,971.34 በደረሰኝ ከከፈልነው ብር 82,146,244.79 ጋር ተደምሮ የሚመጣው ብር 97,558,215.79 ከጠቅላላ ዋጋው ብር 100,650,000 ላይ ተቀናሽ ሲደረግ ልንከፍል የሚገባው ቀሪ ክፍያ ብር 3,291,784.21 ብቻ ነው በማለት ተከራክሯል፡፡

ፍርድ ቤቱም የግራ ቀኙን ክርክር እና ማስረጃ ሰምቶ አመልካች እስከ የካቲት 21 ቀን 2008 ዓ.ም ያልተከፈለ ቀሪ እዳ ብር 18,703,775.55 መሆኑን ተጠሪ ገልጿል በማለት የሚከራከር ቢሆንም የደብዳቤው ይዘት የተጠቀሰው ገንዘቡ ካልተከፈለው የመኪና እዳ ጋር የሚገናኝ ስለመሆኑ አያመላክትም፤ ብር 3,132,965.31 ስለመክፈሉም ያቀረበው ማስረጃ የለም፡፡ አመልካች በጠየቀው መሰረት ቀሪ እዳው በገለልተኛ ባለሞያ እንዲጣራ ታዞ ሶልያና ኪሮስ የተመሰከረላቸው የሂሳብ አዋቂዎች እና ኦዲተሮች በሪፖርታቸው የአመልካች ክርክር በማስረጃ እንዳልተደገፈ ያሳወቀ በመሆኑ ይህ ገንዘብ በአመልካች እንዳልተከፈለ ፍ/ቤቱ ተገንዝቧል፡፡ ወ/ሮ ሮዛ ዲፋብር የከፈሉት ብር 3,866,707 ለአመልካች እዳ የተከፈለ ስለመሆኑ የቀረበ ማስረጃ የለም ሪፖርቱም ይህን ያረጋግጣል፡፡ ሰኔ 11 ቀን 2008 በተደረገው ስምምነት ተጠሪ 3% ኮሚሽን እንደሚከፍል የተገለፀ ቢሆንም ከአመልካች እዳ ላይ ተቀናሽ የሚደረግ ስለመሆኑ አልተገለፀም፡፡ ተጠሪ ክሱን ሲያቀርብ 2% ዊዝሆልዲንግ ተቀናሽ አድርጓል፡፡ በመኪና ውሎቹ ተጠሪ ለሁሉም መኪኖች ብር 100,000 የሚገመት የመለዋወጫ እቃ እንደሚሰጥ የተስማሙ ቢሆንም ለእያንዳንዱ መኪና ብር 100,000 የሚገመት የመለዋወጫ እቃ እንደሚሰጥ የተስማሙ ስለመሆኑ የቀረበ ማስረጃ የለም፡፡ በፍ/ሕ/ቁጥር 1890(2) መሰረት ውል እንዲፈጸም እና መቀጮ እንዲከፈል በአንድነት መጠየቅ የማይቻል ስለሆነ ተጠሪ መቀጮ እንዲከፈለው መጠየቁ አግባብ አይደለም፡፡ በመሆኑም በቀረበው የሂሳብ ሪፖርት መሰረት እንዳልተከፈለ የተረጋገጠው

እዳ ብር 22,880,231.14፣ በውሉ መሰረት ያልተከፈለና የዘገየ ወለድ ብር 1,077,812፣ ክፍያ ከተቋረጠ በኋላ ያለው ወለድ ብር 2,809,444 በድምሩ ብር 26,767,487.14 ከጥር 24 ቀን 2010 ዓ.ም ጀምሮ ገንዘቡ ተከፍሎ እስኪያልቅ ከሚታሰብ 9% ወለድ ጋር አመልካች ለተጠሪ ይክፈል በማለት ወስኗል፡፡

አመልካች ይህን ውሳኔ በመቃወም ለፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የይግባኝ ቅሬታ ያቀረበ ሲሆን በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 337 መሰረት በአብላጫ ድምፅ ቅሬታው ተሰርዟል፡፡

አመልካች ህዳር 2013 ዓ.ም የተፃፈ የሰበር አቤቱታውን ያቀረበው ይህን የስር ፍ/ቤቶች ውሳኔ በመቃወም ለማሳረም ነው፡፡ የአቤቱታው ይዘት ባጭሩ አመልካች ብር 18,703,775 ያለበት መሆኑን ገልፆ ተጠሪ የፃፈውን ደብዳቤ አመልካች በማስረጃነት አቅርቧል፤ ተጠሪም ይህን ማስረጃ በማስተባበል ያቀረበው ክርክር የለም፤ አስፈላጊ ከሆነም በጉዳዩ ላይ የሰው ምስክር ሊሰማ እየተገባ ለክርክሩ መነሻ ለሆነው እዳ የተፃፈ ስለመሆኑ አያስረዳም በሚል የስር ፍ/ቤት ውድቅ ማድረጉ፤ በወ/ሮ ሮዛ ዲፉቤሪ የተከፈለው ብር 3,866,707 ከአመልካች እዳ ጋር ያለው ግንኙነት በግለሰቧ ምስክርነት አለመጣራቱ፣ አመልካች ከተጠሪ ለገዛቸው ተሽከርካሪዎች ሊከፈል የሚገባው ኮሚሽን ብር 2,917,500 ከጠቅላላ እዳው እንዲቻቻልኝ ያቀረብኩት ጥያቄ ውድቅ መደረጉ፣ በውሎቹ በቅድመ ክፍያነት መከፈሉ የተገለፀው በድምሩ ብር 5,350,000 ከአመልካች እዳ ላይ ተቀናሽ አለመደረጉ፣ ለእያንዳንዱ መኪና ግዢ የመለዋወጫ እቃ ብር 100,000 ተቀናሽ ሳይደረግ መወሰኑ፤ በሒሳብ አጣሪ ሪፖርት ተቀናሽ መደረጉ የተገለፀው ብር 5,350,000 ከእዳው ላይ የተቀነሰበት ምክንያት አለመጣራቱ፣ ክፍያ ከተቋረጠ በኋላ የዘገየ ወለድ ውስጥ የተካተተን ወለድ ሁለት ግዜ እንድንከፍል መወሰኑ መሰረታዊ ስህተት ተፈፅሞበታል የሚል ነው፡፡

የሰበር አቤቱታው ተመርምሮ ከዱቤ የመኪና ሽያጩ ጋር በተያያዘ በቀረበው የሂሳብ ምርመራ ሪፖርት መሰረት ከአመልካች እዳ ተቀናሽ መደረግ የነበረበት የቅድመ ክፍያ ብር 5,350,000 በተመለከተ በቂ ማስረጃ አልቀረበበትም ተብሎ በኦዲተር ውድቅ የመደረጉን፤ አስቀድሞ ተቀናሽ መደረግ አለመደረጉን እና ተያያዥ ነጥቦች ለማጣራት ያስቀርባል በመባሉ ተጠሪ መልሱን እንዲያቀርብ ትዕዛዝ ተሰጥቷል፡፡

ተጠሪ ህዳር 28 ቀን 2013 ዓ.ም የተፃፈ መልሱን አቅርቧል፡፡ የመልሱ ይዘት ባጭሩ ያልተከፈለውን እዳ እንዲመረምር የታዘዘው ገለልተኛ የሂሳብ ባለሞያ አመልካች ክፍያ ስለመፈፀሙ ያቀረባቸው ማስረጃዎች ከእዳው ጋር እንደማይገናኙ እና ወለድ ሳይታሰብ ቀሪ እዳው ብር 22,880,231.14 መሆኑን አረጋግጧል፡፡ አመልካች ሪፖርቱን በመቃወም እንዲሁም ተጠሪ ወለድ አለመካተቱን ገልፆ ለፍ/ቤቱ ባቀረበው ቅሬታ መሰረት እንደገና እንዲጣራ ታዞ ቅጣት እና ወለድን ጨምሮ እዳው ብር 29,055,279.88 መሆኑ የተረጋገጠ ሲሆን ፍ/ቤቱ መቀጮውን ቀንሶ ብር 26,767,487 እንዲከፈል መወሰኑ ተገቢ ነው፡፡ አመልካች ብር 18,703,775 እዳ እንዳለበት ተጠሪ ገልፆ የፃፈው ደብዳቤ እስከ የካቲት 21 ቀን 2008 ዓ.ም ያለውን ቀሪ ሂሳብ እና ወለድ የሚመለከት ሲሆን ክስ የቀረበበት ሒሳብ

የተሰላው እስከ ጥር 2010 ዓ.ም ያለውን ወለድ ጨምሮ ስለሆነ የአመልካች ቅሬታ ተገቢነት የለውም። ወ/ሮ ሮዛ ዲፋብሪ የተዋዋሉት ከአመልካች ጋር ሲሆን በሰነድ መከፈሉን የሚያረጋግጥ ማስረጃ አልቀረበም፤ የኮሚሽን ክፍያውም በ2000 ዓ.ም ተፈርሞ በ2001 ዓ.ም ያበቃ ውል እንጂ ለክርክሩ መነሻ የሆነውን ከ2004 እስከ 2007 ዓ.ም የተደረገን ውል የሚመለከት አይደለም፤ አመልካች በውሉ ላይ ተቀናሽ የተደረገ ብር 5,350,000 ከእዳው ተቀናሽ አለመደረጉን ጠቅሶ የሚከራከር ቢሆንም ተጠሪ ክሱን የመሰረተው አመልካች የከፈላቸውን እያንዳንዱን ገንዘብ ተቀናሽ በማድረግ ሲሆን ሂሳብ አጣሪውም ይህ ገንዘብ ለመከፈሉ የቀረበ ማስረጃ የሌለ መሆኑን ጠቅሶ ውድቅ አድርጎታል። ወለድም ሆነ የዘገየ ወለድ የታሰበው ውሉን መሰረት አድርጎ በመሆኑ አቤቱታው ተገቢነት የለውም በማለት ተከራክሯል።

አመልካችም የካቲት 26 ቀን 2013 ዓ.ም በተፃፈ የመልስ መልስ የሰበር አቤቱታውን በማጠናከር ተከራክሯል።

የክርክሩ አመጣጥ ባጭሩ ከላይ የተመለከተው ሲሆን ጉዳዩ ያስቀርባል ሲባል የተያዘወን ጭብጥ በስር ፍ/ቤት ከተደረጉ ክርክሮች፣ በማስረጃ ከተረጋገጡ ፍሬ ነገሮች እንዲሁም ለጉዳዩ ተገቢነት ካላቸው የሕግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለው መርምረነዋል።

እንደመረመርነውም አመልካች በዋናነት የሚከራከረው የአመልካች እዳ ብር 18,703,775 መሆኑን ተጠሪ ገልፆ የፃፈው ደብዳቤ ከእዳው ጋር የሚገናኝ አይደለም መባሉ፣ በወ/ሮ ሮዛ ዲፋቬሪ የተከፈለው ብር 3,866,707 ከአመልካች እዳ ጋር ያለው ግንኙነት በግለሰቧ ምስክርነት አለመጣራቱ፣ አመልካች ከተጠሪ ለገዛቸው ተሽከርካሪዎች ሊከፈል የሚገባው ኮሚሽን ብር 2,917,500 ከጠቅላላ እዳው እንዲቻቻል አለመወሰኑ፣ የቅድመ ክፍያ ብር 5,350,000 እንዲሁም ለእያንዳንዱ መኪና ግዢ የመለዋወጫ እቃ ብር 100,000 ተቀናሽ አለመደረጉ እና ወለድ 2 ጊዜ እንዲከፍል መወሰኑ አግባብ አይደለም በማለት ነው። ተጠሪ በበኩሉ አመልካች ብር 18,703,775 እዳ እንዳለበት የተፃፈው ደብዳቤ እስከ የካቲት 21 ቀን 2008 ዓ.ም ያለውን ቀሪ ሂሳብ እና ወለድ የሚመለከት እንጂ ክስ እስከ ቀረበበት ጥር 2010 ዓ.ም ያለውን ወለድና ዋና ገንዘብን አያካትትም፤ የኮሚሽን ክፍያውም ለክርክሩ መነሻ የሆነውን ውል የሚመለከት አይደለም፤ ወ/ሮ ሮዛ ዲፋብሪ ለአመልካች እዳ ክፍያ የፈጸሙ ስለመሆኑ የቀረበ የሰነድ ማስረጃ የለም፤ ክሱም የቅድመ ክፍያ ብር 5,350,000 ተቀናሽ ተደርጎ የቀረበ ሲሆን ሂሳብ አጣሪውም ይህ ገንዘብ ለመከፈሉ የቀረበ ማስረጃ አለመኖሩን ስላረጋገጠ እና ወለዱም ውሉን መሰረት አድርጎ የተሰላ ስለሆነ የስር ፍ/ቤቶች ውሳኔ ተገቢ መሆኑን ገልፆ ተከራክሯል።

ፍርድ ቤቶች በተከራካሪዎች የሚቀርቡ ክርክሮችን ለጉዳዩ ተገቢነት ባለው ማስረጃ ማጣራት ያለባቸው ስለመሆኑ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 136፣ 145፣ 257-259 እና ሌሎች የስነ ስርዓት ሕጉ ድንጋጌዎች ላይ ተመላክቷል።

በመጀመሪያ ተጠሪው የአመልካች ቀሪ እዳ ብር 18,703,775 ብቻ መሆኑን ገልፆ የፃፈው ደብዳቤ ለክርክሩ መነሻ ከሆነው እዳ ጋር ግንኙነት የለውም ተብሎ የመወሰኑን አግባብነት መመልከቱ ተገቢ ነው፡፡ ተጠሪ ከአመልካች ጋር በተደረጉ 4 የተለያዩ የመኪና ሽያጭ ውሎች ዋጋቸው ብር 100,850,000 የሆነ መኪኖችን በዱቤ መሸጡን፤ አመልካች እስከ ጥር 22 ቀን 2010 ዓ.ም ባለው ጊዜ ወለድ እና ቅጣትን ጨምሮ ከሚፈለግበት ብር 111,420,620 ውስጥ ያልከፈለው ቀሪ ክፍያ ብር 31,306,375 መሆኑን እና ይህን ገንዘብ እንዲከፍል እንዲወሰንለት ዳኝነት ጠይቋል፡፡ ጉዳዩን በመጀመሪያ የተመለከተው የስር ከፍተኛ ፍ/ቤት አመልካች ብር 18,703,775 እዳ ያለበት መሆኑን ገልፆ ተጠሪ የካቲት 21 ቀን 2008 ዓ.ም የፃፈው ደብዳቤ በዱቤ ከተገዙት መኪኖች እዳ ክፍያ ጋር የሚገናኝ ስለመሆኑ ይዘቱ አያመለክትም በማለት የአመልካችን ክርክር ሳይቀበለው ቀርቷል፡፡ ነገር ግን ተጠሪ ይህን ደብዳቤ ስለመፃፉ በስር ፍ/ቤቶች ክዶ ያቀረበው መከራከሪያ ካለመኖሩም በላይ ለዚህ ሰበር ችሎት በሰጠው መልስ በደብዳቤ የተገለጸው እዳ እስከ የካቲት 21 ቀን 2008 ዓ.ም. ብቻ ያለውን የሚመለከት እንጂ ከዚህ ጊዜ በኋላ ያለውን ዋና እዳ እና ወለድ የሚመለከት አይደለም በማለት ተከራክሯል፡፡ ይህ የተጠሪ ክርክር በአመልካች የተጠቀሰው ደብዳቤ ከእዳው ጋር በተያያዘ የተጻፈ መሆኑን ማመኑን የሚያሳይ ሆኖ እያለ የስር ከፍተኛ ፍርድ ቤት የደብዳቤው ይዘት ከእዳው ጋር ተያያዥነት ያለው አይደለም ማለቱ ተገቢ አይደለም፡፡ በሌላ በኩል ተጠሪ ደብዳቤው ከእዳው ጋር ተያያዥነት ያለው መሆኑን ቢያምንም ክስ እስከቀረበበት ጊዜ ከአመልካች የሚፈለገውን እዳ የሚያሳይ አለመሆኑን ገልጾ የሚከራከር በመሆኑ፡ አመልካች በበኩሉ ቀሪ እዳውን ይህን የገንዘብ መጠን መሰረት በማድረግ ሌሎች ክፍያዎች ተቀናሽ ተደርገው ሊከፍለው የሚገባ የገንዘብ መጠን ብር 3,291,784.21 ብቻ መሆኑን ጠቅሶ የሚከራከር በመሆኑ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 259 መሰረት አመልካች ይህን የማስረዳት ግዴታ አለበት፡፡ ነገር ግን አመልካች እዳው በደብዳቤው ላይ የተገለፀው ብቻ ስለመሆኑ እንዲሁም ቀሪ ክፍያው ይህን መሰረት በማድረግ ሊሰላ የሚገባ ስለመሆኑ አላስረዳም፡፡ በተጨማሪም የአመልካች ትክክለኛ እዳ ምን ያህል ነው የሚለው በአግባቡ መጣራት ያለመጣራቱን በቀጣይ የምንመለከተው ሁኖ በግራ ቀኙ መካከል በተደረገው የዱቤ የመኪና ሽያጭ ውል አመልካች ቀሪ እዳ በገለልተኛ የሂሳብ ባለሞያ እንዲጣራ ተደርጎ ቀሪ እዳ ያለበት መሆኑ እስከ ተረጋገጠ ድረስ የቀሪ እዳ ስሌቱ የግድ በደብዳቤው የተገለፀውን የገንዘብ መጠን መሰረት ተደርጎ ሊሰላ ይገባል የሚባልበት የሕግ አግባብ የለም፡፡ ስለሆነም ምንም እንኳ የስር ፍ/ቤት ደብዳቤው ለክርክሩ መነሻ ከሆነው የዱቤ የመኪና ሽያጭ ውል ጋር ግንኙነት ያለው ስለመሆኑ የደብዳቤው ይዘት አያመላክትም በማለት የደረሰበት ድምዳሜ ተገቢ ባይሆንም ከላይ በተገለፀው ምክንያት በውጤት ደረጃ መሰረታዊ ልዩነት የሚያመጣ ባለመሆኑ አመልካች በዚህ ረገድ ያቀረበውን ቅሬታ አልተቀበልነውም፡፡

በመቀጠልም አመልካች ከወ/ሮ ሮዛ ዲፋቬሪ ጋር ባለው ግንኙነት ሊከፈለው የሚገባውን ብር 3,866,707 ለተጠሪ እንዲከፍል ተስማምቶ ግለሰቧ ገንዘቡን ለተጠሪ ስለመክፈላቸው በምስክርነት

ቀርበው እንዲጣራ ያለመደረጉን አግባብነት ስንመለከት ተጠሪ ድርጅቱ ሰነድን መሰረት አድርጎ የሚሰራ መሆኑን ገልፆ ግለሰቧ የተጠቀሰውን ገንዘብ ስለመክፈላቸው የሚያረጋግጥ ሰነድ አልቀረበም በማለት ተከራክሯል፡፡ በስር ፍ/ቤቶች አመልካች ግለሰቧ ይህን ክፍያ ለተጠሪ የከፈሉ ስለመሆኑ ያቀረበው የሰነድ ማስረጃ የለም፤ የሒሳብ ባለሞያ ሪፖርቱም ይህ ገንዘብ ለተጠሪ ስለመከፈሉ ሳይሆን ግለሰቧ ከአምቼ ጋር የብድር ውል ግንኙነት የነበራቸው መሆኑን የሚያመላክት መሆኑን ይግባኝ ሰሚው ጠቅላይ ፍ/ቤት አረጋግጧል፡፡ በአንፃሩ አመልካች ይህን ገንዘብ ግለሰቧ ለተጠሪ እንድትከፍል ስለመስማማታቸው ማስረጃ ስለመቅረቡ በይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤቱ የተረጋገጠ ሲሆን አመልካችም ግለሰቧ በምስክርነት ቀርበው ቃላቸው እንዲሰጡ ጠይቆ የነበረ መሆኑን ጠቅሶ የሚያቀርበውን መከራከሪያ ተጠሪ ክዶ የሚያቀርበው መከራከሪያ የለም፡፡ ይልቁንም ተጠሪ የሚከራከረው ድርጅቱ ሰነድን መሰረት አድርጎ የሚሰራ በመሆኑ ጉዳዩ በሰው ምስክርነት የሚረጋገጥ አይደለም በማለት ነው፡፡ በመሰረቱ ድርጅቱ ሰነድን መሰረት አድርጎ የሚሰራ መሆን አለመሆኑ፣ ግለሰቧ ከአመልካች ወይም ከተጠሪ ድርጅት ጋር ያላቸው ግንኙነት፣ የድርጅቱን አሰራር መሰረት አድርገው ወይም ከድርጅቱ አሰራር ውጪ ክፍያ መፈፀም አለመፈጸማቸው ከሕግ አንፃር የሚኖረውን ውጤት መመዘን የሚቻለው ግለሰቧ ከሚሰጡት የምስክርነት ቃል ጋር አብሮ መመዘን ሲቻል ነው፡፡ ከዚህ በተቃራኒ የስር ፍ/ቤት የግለሰቧን የምስክርነት ቃል ሳይሰማና ከህግ አንፃር የሚኖረውን ውጤት ሳይመዝን ገንዘቡ ለአመልካች እዳ ስለመክፈሉ ማስረጃ አልቀረበም በማለት መወሰኑ፣ ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤቱም ይህን አለማረሙ የአመልካችን ከወ/ሮ ሮዛ ዲፈብሪጋ የመዋዋል መብት የሚያጠብ እና መሰረታዊ የክርክር አመራር ስነ ስርዓት ጥሰት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል፡፡

መፍትሔ ማግኘት ያለበት 3ኛው ጉዳይ አመልካች የቅድመ ክፍያ ብር 5,350,000 ተቀናሽ አለመደረጉን በመቃወም የሚያቀርበው መከራከሪያ ተገቢነት ሲሆን ለዚህ ክርክር እልባት ለመስጠት ጉዳዩን በመጀመሪያ በተመለከተው ከፍተኛ ፍ/ቤቱ ተጠሪ ያቀረበውን ክስ፣ የአመልካችን መልስ እንዲሁም በሒሳብ ባለሞያ የቀረበውን ሪፖርት መመልከቱ ተገቢ ነው፡፡ በግራ ቀኙ መካከል 4 የዱቤ የመኪና ሽያጭ ውል መደረጉ አከራካሪ አይደለም፡፡ ተጠሪ ባቀረበው ክስ የመጀመሪያውን ውል አስመልክቶ አመልካቹ 5,000,000 እንዲከፍል መስማማታቸውን በኋላም ቅድመ ክፍያውን ወደ 16,000,000 ማሳደጋቸውን ፤ በ2ኛ ውል አመልካች ሊከፍል ከሚገባው 2.4 ሚሊዮን ቅድመ ክፍያ ብር 1.5 ሚሊዮን ብቻ መክፈሉን፤ በ3ኛው ውል አመልካች ብር 12,250,000 ቅድመ ክፍያ ፈፅሞ ሌላ የሚቀርበት መሆኑን፣ በ4ኛ ውል አመልካች ብር 2,350,000 ቅድመ ክፍያ መክፈሉን እና ቀሪ ክፍያ ያለበት መሆኑን ገልፆ ተከራክሯል፡፡ በአንፃሩ አመልካች መልስ ሲሰጥ ተጠሪው የተከፈለ ቅድመ ክፍያ በሚል ከጠቀሳቸው ውስጥ ያልተካተተ የቅድመ ክፍያ አለ ሲል በግልፅ ያነሳው መከራከሪያ ባይኖርም የተለያዩ ክፍያዎች ተቀናሽ ተደርገው ሊከፍል የሚገባው ብር 3,920,124.68 ብቻ መሆኑን ገልፆ ተከራክሯል፡፡ በተጨማሪም ጉዳዩን በመጀመሪያ የተመለከተው ፍ/ቤት የግራ ቀኙን ክርክር መሰረት

በማድረግ ጉዳዩ በገለልተኛ የሂሳብ አጣሪ ባለሞያ ተመርምሮ አመልካች ያለበት ቀሪ እዳ እንዲለይ ትዕዛዝ ሲሰጥ አመልካች ተቀናሽ እንዲደረግ የሂሳብ ባለሞያዎቹን ከጠየቀበት 6 ዝርዝሮች መካከል አንዱ ከፈልኩት የሚለውን የቅድመ ክፍያ ብር 5,350,000 ነው፡፡ ይህም በሂሳብ ሪፖርቱ ገጽ 3 ላይ የሰፈረ ሲሆን ባለሞያዎቹም በዚህ ጉዳይ በቂ ማስረጃ ያልተገኘበት ተቀናሽ የተደረገ በሚል ገልፀውታል፡፡ በሌላ በኩል ግንቦት 7 ቀን 2011 ዓ.ም ለፍ/ቤቱ በላኩት ማብራሪያ በቂ ማስረጃ ያልተገኘበት መሆኑን ጠቅሰው ተቀናሽ አለመደረጉን አሳውቀዋል፡፡ ተጠሪ መቀነስ የሚገባቸው ቅድመ ክፍያዎች ተቀናሽ መደረጋቸውን፣ አመልካች በበኩሉ አከራካሪ የሆነው የገንዘብ መጠን ተቀናሽ ያልተደረገ እና ተቀናሽ ሊደረግ የሚገባ መሆኑን ገልጾ የሚከራከር በመሆኑ እና የሂሳብ ባለሞያዎቹም በአንድ በኩል ተቀናሽ መደረጉን በሌላ በኩል በቂ ማስረጃ ባለመገኘቱ ተቀናሽ አለመደረጉን አሻሚ በሆነ መልኩ በመግለፃቸው ከውሳኔ በፊት በጉዳዩ ላይ ተጨማሪ ማጣራት ሊደረግ እና እውነቱ ነጥሮ ሊወጣ ይገባ ነበር፡፡ በዚህ ረገድ ተገቢው ማጣራት እንዲደረግ ሳይደረግ የተሰጠው ውሳኔ የፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 257 እና ተከታዮቹን ድንጋጌዎች የሚቃረን መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነው፡፡

በአራተኛ ደረጃ አመልካች የኮሚሽን ገንዘብ ብር 2,917,500 ተቀናሽ ያለመደረጉ ገልፆ የሚያቀርበውን መከራከሪያ ስንመለከት ተጠሪ ይህ የኮሚሽን ክፍያ ስምምነት ለክርክሩ መነሻ የሆኑትን ውሎች የሚመለከት አይደለም በሚል የተከራከረ ቢሆንም ማስረጃን የመመዘን ስልጣን ያለው የስር ፍ/ቤት በውሉ ላይም ለእያንዳንዱ መኪና ዋጋ ላይ 3 በመቶ ኮሚሽን የሚታሰብ መሆኑ መገለፁን አረጋግጧል፡፡ ነገር ግን ከፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 236 እና ተከታዮቹ ድንጋጌዎች አንፃር ተቀናሽ እንዲደረግ ወይም እንዲቻቻል የሚጠይቀው ገንዘብ መቅረብ ያለበት ለመጀመሪያ ክስ መልስ በሚሰጥበት የመጀመሪያ ጊዜ መሆን ያለበት ሲሆን አንደኛው ከሳሽ ተከሳሽ ሌላኛው የተከሳሽ ከሳሽ ሁኖ እንደቀረበ ይቆጠራል፡፤ ፍ/ቤቱም በዋናው ክስ እና በመቻቻል ጥያቄው ውሳኔ የሚሰጥ መሆኑ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 236(3) ላይ ተመላክቷል፡፡ ከዚህ አንፃር የመቻቻል ጥያቄው የተከሳሽ ከሳሽነት ክስ በሚመራበት አግባብ ሊቀርብ የሚገባ መሆኑን የሚያመላክት ሲሆን አመልካች በዚህ ስርዓት አላቀረበም፡፡ በተጨማሪም በውሉ መሰረት ከሶ የመጠየቅ መብቱ የተጠበቀለት በመሆኑ በጉዳዩ ላይ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል የሚያስብል ሁኖ አላገኘነውም፡፡

በመጨረሻም አመልካች ወለድ ሁለት ግዜ ታስቧል በማለት የሚያቀርበውን መከራከሪያ ስንመለከት የመጀመሪያው ክፍያው እስከተቋረጠበት ጊዜ ድረስ ውሉን መሰረት በማድረግ የተሰላ እና ሳይከፈል የዘገየ በወለድ ብር 1,077,812 መሆኑ ሁለተኛው የታሰበው ክፍያው ከተቋረጠ በኋላ ያለው ሁኖ ብር 2,809,444 መሆኑ ስለተረጋገጠ በዚህ ረገድ የተፈፀመ መሰረታዊ ሕግ ስህተት የለም በማለት ተከታዩን ወስነናል፡፡

ውሳኔ

1. ፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁጥር 210446 ሚያዝያ 5 ቀን 2012 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ እንዲሁም የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 193846 ጥቅምት 16 ቀን 2013 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጠው ትእዛዝ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሰረት ተሻሽሏል፡፡
2. የፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ቁጥሩ 210446 የሆነውን መዝገብ በማንቀሳቀስ፡-
   2.1. ወ/ሮ ሮዛ ዲፋብሪን በማስቀረብ ከአመልካች ጋር ባላቸው ግንኙነት ለአመልካች ሊከፍሉት የሚገባውን ብር 3,866,707 ከተጠሪ ላለበት እዳ እንዲከፈል ተስማምተው መክፍል አለመክፈላቸውን በተመለከተ የምስክርነት ቃላቸውን እንዲሰጡ በማድረግ በሕግ የሚኖረውን ውጤት ከሌሎች አግባብነት ካላቸው ማስረጃዎች ጋር አገናዝቦ በመመርመር እንዲወስን፤
   2.2. የስር ፍ/ቤቶች በሂሳብ አጣሪው ተጣርቶ የቀረበው የእዳ መጠን መሰረት በማድረግ ብር 26,767,487.14 አመልካች ለተጠሪ እንዲከፍል ከተወሰነው የገንዘብ መጠን ላይ አመልካች ተቀናሽ አለመደረጉን በመግለፅ የሚከራከረው የቅድመ ክፍያ ብር 5,350,000 ሊቀነስ ይገባል ወይስ አይገባም የሚለውን ግራ ቀኙ የሚያቀርቡትን ማስረጃ መሰረት በማድረግ የሂሳብ አጣሪ ባለሞያዎቹ በድጋሚ አጣርተው ተገቢውን ውጤት እንዲያቀርቡ በማድረግ እንዲወስን መዝገቡን በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 343 /1/መሰረት መልሰንለታል፡፡ ይፃፍ ፡፡

3. ከላይ በውሳኔ ተራ ቁጥር 2.1 እና 2.2 ላይ ከተጠቀሱት ነጥቦች ውጪ በስር ፍርድ ቤቶች የተሰጠው ውሳኔ እና ትእዛዝ እንደተጠበቀ ነው፡፡
4. በዚህ ችሎት የተደረገው ክርክር ያስከተለውን ወጪ እና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡

ትእዛዝ

በዚህ መዝገብ በ11/03/2013 ዓ.ም. በዋለው ችሎት በፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት አፈጻጸም መዝገብ ቁጥር 252656 ላይ የተሰጠው የእግድ ትእዛዝ ተነስቷል፡፡ ይጻፍ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ማ/አ

የሰበር መዝገብ ቁጥር - 237965

ቀን - 26/07/2016 ዓ.ም

ዳኞች - ሱልጣን አባተማም

ገበየሁ ፈለቀ

አለማየሁ ሹናራ

አብርሃ መሰለ

ተናኜ ጥላሁን

አመልካች - ም/ኢንስፔክተር በሱፍቃድ እስጢፋኖስ - አልቀረቡም

ተጠሪ - ወ/ሮ ትዕግስት እስጢፋኖስ - አልቀረቡም

መዝገቡ የተቀጠረው ለምርመራ ስለሆነ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍርድ

ጉዳዩ የተጀመረው በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ሲሆን አመልካች ተከሳሽ ተጠሪ ከሳሽ በመሆን ተከራክረዋል፡፡ ተጠሪ በአመልካች ላይ ያቀረቡት ክስ ይዘቱ በአጭሩ በካርታ ቁጥር ቦሌ10/97/724/00 ተመዝግቦ የሚገኝ በቦሌ ክፍለ ከተማ ወረዳ 13 የቦታ ስፋቱ 73.5 ካሬ ሜትር የሆነውን የግል መኖሪያ ቤቱን ተከሳሽ ወንድሜ ስለሆነ ትዳር ሲይዝ እንዳይቸገር ብዬ ለጊዜው እንዲኖርበት ሰጥቼ 6 አመት ከኖረ በኋላ እንዲያስረክበኝ ስጠይቀው ለማስረከብ ፍቃደኛ ስላልሆነ ለቆ እንዲያስረክበኝ እንዲወስን የሚል ነው፡፡ አመልካች ለክሱ በሰጠው መልስ ለክርክሩ መነሻ የሆነው ቤት ካርታው በከሳሽ ስም ቢሆንም የሚች እናታችን የወ/ሮ ዘውድነሽ መኮንን የውርስ ሀብት እንጂ የከሳሽ አይደለም፡፡ ከሳሽ ታላቅ እህታችን በመሆናቸው የሁላችንም የውርስ ሀብት የሆነውን ቤት ከህግ አግባብ ውጭ በራሳቸው ስም አስመዝግበዋል፡፡ ለከሳሽ ውክልና ከሰጠናቸው በኋላ ከቅን ልቦና ውጭ በስማቸው ከማስመዝግብ ውጭ የግላቸው አይደለም በማለት መልስ ሰጥተዋል፡፡

የስር ፍርድ ቤትም ተከሳሽ ቤቱን ለከሳሽ ሊያስረክብ ይገባል ወይስ አይገባም የሚለውን ጭብጥ በመያዝ መርምሮ ለክርክሩ መነሻ ለሆነው ቤት ካርታ የተሰጠው በከሳሽ ስም መሆኑን፣ ቤቱን ከሳሽ ከአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ቦሌ ክፍለ ከተማ የቤት ማስተላለፍ ፅ/ቤት ጋር ባደረጉት የቤት ሽያጭ ውል መሰረት ያገኙ መሆኑን የሚያስረዳ የሰነድ ማስረጃ የቀረበ በመሆኑ ተከሳሽ ቤቱን ለከሳሽ እንዲያስረክብ ሲል ወስኗል፡፡ አመልካች በዚህ ውሳኔ ላይ ቅር በመሰኘት ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ ያቀረቡ ሲሆን የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 287033 በቀን 20/03/2015 አ.ም በዋለው ችሎት የስር ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሳኔ በማፅናት ወስኗል፡፡ የአሁን ሰበር አቤቱታ የቀረበው በዚህ

ውሳኔ ላይ አመልካች ቅር በመሰኘት ነው፡፡ የአመልካች ቅሬታ በአጭሩ የፌድራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ አንቀፅ 145 መሰረት እንዲቀርቡልኝ የጠየቋቸውን ማስረጃዎች ሳያስቀርብ ውሳኔ መስጠቱ መሰረታዊ የህግ ስህተት ነው፡፡ እንዲሁም የስር ፍርድ ቤት ፍሬ ነገሩን በሰው ምስክሮች ማረጋገጥ ሲገባው ማስረጃ ሳይሰማ መወሰኑ መሰረታዊ የህግ ስህተት ስለሆነ እንዲሻርልኝ የሚል ነው፡፡

ይህ ችሎትም አመልካች በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ አንቀፅ 145 መሰረት እንዲቀርብላቸው የጠየቁትን ማስረጃ ፍርድ ቤቱ ሳያስቀርብ እና ማስረጃ አሟጦ ሳይሰማ የወሰነበት አግባብነት ከማስረጃ ምዘና መርህ አንፃር ለማጣራት ያስቀርባል በመባሉ ተጠሪ የበኩላቸውን መልስ አቅርበዋል፡፡ ፍሬ ቃሉ በአጭሩ የስር ፍርድ ቤት ከተለያዩ መንግስታዊ ተቋማት የሰነድ ማስረጃ አሰባስቦ ቤቱ የተጠሪ መሆኑን አረጋግጦ የሰጠው ፍርድ የሚነቀፍ አለመሆኑን፣ የስር ፍርድ ቤት ግራ ቀኙ ከሚመለከታቸው ፅ/ቤቶች ማስረጃ እንዲያቀርቡ ትዕዛዝ ሰጥቶ አመልካች ማስረጃ አላቀረቡም፤ በቀጠሮ ቀን እራሳቸውም አልቀረቡም፡፡ ስለዚህ የስር ፍርድ ቤት የሰጠው ፍርድ በማስረጃ በሚገባ አጣርቶ የሰጠው ውሳኔ በመሆኑ እንዲፀናልኝ የሚል መልስ ሰጥተዋል፡፡ አመልካች የመልስ መልሱን አቅርቦ ከመዝገቡ ጋር ተያይዟል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ በተገለፀው መሰረት የተጠቃለለ በመሆኑ እኛም ያስቀርባል ከተባለው ነጥብ አንፃር እንደሚከተለው መርምረናል፡፡ መርምረን እንድተረዳነው፡ -

በስር ፍርድ ቤት ተጠሪ በአመልካች ላይ ያቀረቡት ክስ በአጭሩ በቦሌ ክፍለ ከተማ ወረዳ 13 የቦታ ስፋቱ 73.5 ካሬ ሜትር የሆነው የግል መኖሪያ ቤቱን ተከሳሽ ወንድሜ በመሆኑ ትዳር ሲመሰርት እንዳይቸገር ብዬ ለጊዜው እንዲኖርበት የሰጠሁትን እንዲመልስ ጠይቄ ለመልቀቅ ፍቃደኛ ስላልሆነ እንዲያስረክበኝ የሚል ክስ ሲሆን የአሁን አመልካች ለክሱ በሰጠው መልስ ለክርክሩ መነሻ የሆነው ቤት የከሳሽ ሳይሆን የእናታችን የወ/ሮ ዘውድነሽ መኮንን ቤት በመሆኑ የውርስ ንብረት ነው እንጂ የከሳሽ የግል ቤት አይደለም፡፡ ከሳሽ ታላቅ እህታችን በመሆናቸው ቤቱን እንዲያስተዳድሩ ውክልና ሰጥተን የቤቱ ስመ ሀብትነቱን ወደ ራሳቸው ስም አዞሩ እንጅ የውርስ ንብረት ነው በማለት መከላከያ መልስ ከማስረጃ ዝርዝር ጋር አቅርበዋል፡፡ በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ አንቀፅ 145 መሰረት የሰነድ ማስረጃ ከመንግስታዊ ተቋም በፍርድ ቤት በኩል እንዲቀርብ አመልክተዋል፡፡ የስር ፍርድ ቤትም የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ገቢዎች ቢሮ የቦሌ ክፍለ ከተማ አነስተኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ፅ/ቤት በመጠየቅ ከተላከው ማስረጃ እና ማህደሩን በማስቀረብ መርምሮ ተከሳሽ ቤቱ በውርስ የተገኘ ነው ከማለት ውጭ በውርስ ስለመገኘቱ በምትክነት የተሰጠ ስለመሆኑ እናታቸው ለተከሳሽ እና ለልጆቻቸው ያወረሱ ስለመሆኑ እና ቤቱ የከሳሽ አለመሆኑን ተቃራኒ ማስረጃ በማቅረብ አላስረዱም በማለት ለክርክሩ መነሻ የሆነው ቤት አመልካች (ተከሳሽ) ለተጠሪ (ከሳሽ) እንዲያስረክቡ ሲል ወስኗል፡፡ የአመልካች ቅሬታ በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ አንቀፅ 145 መሰረት እንዲቀርብ የጠየቁት ሰነድ ማስረጃ እና ከመከላከያ መልሶቹ ጋር አያይዘ

ያቀረብኳቸው የሰው ምስክሮች ቃል ሳይሰማ መወሰኑ መሰረታዊ የህግ ስህተት ነው በማለት ተከራክሯል። በመሰረቱ የግራ ቀኙ ተከራካሪ ወገኖች ለክርክር ይጠቅመናል በማለት በክሳሽነት ወይም በተከሳሽነት ጊዜ የሚያቀርቡትን ማስረጃ አሟጦ የማሰማት መብት በህገ መንግስቱ አንቀፅ 20(4) በግልፅ ተደንግጎ ይገኛል። አመልካች በዚህ ድንጋጌ መሰረት ለክሱ መልስ በሰጡበት ወቅት በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ አንቀፅ 234(1)(መ) መሰረት ከመከላከያ መልሳቸው ጋር የሰው ማስረጃ ዝርዝር አያይዘው ያቀረቡ ስለመሆናቸው አመልካች ካቀረቡት መልስ ጋር ተያይዞ የማስረጃ ዝርዝር አብሮ የቀረበ መሆኑ አከራካሪ አይደለም። የስር ፍርድ ቤት ለጉዳዩ አግባብነት ያላቸው የመንግስት መስሪያ ቤት መግለጫ እንዲልክ ካደረገ በኋላ ማህደሩንም በማስቀረብ አይቶ ለክርክሩ መነሻ የሆነው ቤት በተጠሪ ስም ተመዝግቦ የሚገኝ መሆኑ ተረጋግጧል። አመልካች ቤቱ የውርስ ቤት ስለመሆኑ በማስረጃ አላስረዱም በማለት ቤቱን እንዲለቁ የወሰነው የአመልካች የሰው ማስረጃም ሆነ በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ አንቀፅ 145 መሰረት በፍርድ ቤት በኩል እንዲቀርብ የጠየቀውን ማስረጃ ሳይቀርብ እና ሳይሰማ መሆኑን መዝገቡ ያስረዳል። የስር ፍርድ ቤት የአመልካች ማስረጃ ሳይሰማ ያለፈበት ምክንያት ምን እንደሆነ በመዝገቡ ውስጥ በግልፅ አልጠቀሱም። በአመልካች በኩል የተቆጠረው ማስረጃ ሳይሰማ እና ያልሰማበት ምክንያት ካለ ምክንያቱን በግልፅ መዝገብ ውስጥ ሳይገልፅ ቤቱ የውርስ ቤት ስለመሆኑ አመልካች በተቃራኒ ማስረጃ አላስረዳም ማለቱ ማስረጃ የማሰማት ህገ መንግስታዊ መብትን የሚጥስ ውሳኔ ሆኖ አግኝተነዋል። ሲጠቃለል አመልካች ለክሱ መልስ በሚሰጡበት ጊዜ የመከላከያ ማስረጃ ዝርዝር አያይዘው አቅርበው እያለ የስር ፍርድ ቤት የአመልካች ማስረጃን ያልሰማበትን ምክንያት ካለ በመዝገብ ውስጥ በግልፅ ሳይጠቅስ አመልካች በተቃራኒ ማስረጃ አላስረዱም ማለቱ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት በመሆኑ ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል።

ውሳኔ

1. የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ቦሌ ምድብ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 133958 በቀን 09/05/2014 ዓ.ም የሰጠው ፍርድ እና የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 287033 በቀን 20/03/2015 ዓ.ም ያፀናው ፍርድ በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ አንቀፅ 348(1) መሰረት ተሽሯል።
2. የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የተዘጋውን መዝገብ በማንቀሳቀስ ከአመልካች በኩል የተዘረዘሩ የሰው ምስክሮች እና በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ አንቀፅ 145 መሰረት እንዲቀርቡ የጠየቁትን የሰነድ ማስረጃ በማስቀረብ እንዲሁም ለትክክለኛ ፍትህ አሰጣጥ አስፈላጊ ከሆነ ተጠሪ ቤቱን ከመንግስት የገዙበትን ሁኔታ ጭምር በማስረጃ በማጣራት እንዲወስን በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ አንቀፅ 343(1) መሰረት መልሰናል።
3. በዚህ ችሎት ግራ ቀኙ ያወጡትን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸውን ይቻቻሉ ብለናል።

ትዕዛዝ

- መዝገቡ ውሳኔ ያገኘ ስለሆነ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ ብለናል።

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፌርማ አለበት

ፍ/ደ

የሰ/መ/ቁ. 232079

መጋቢት 25 ቀን 2016 ዓ.ም

ዳኞች፡- ተፈሪ ገብሩ (ዶ/ር)

እንዳሻው አዳነ

ተሾመ ሽፈራው

ዋዚሞ ዋሲራ

ሰናይት አድነው

አመልካች - ሕብረት ኢንሹራንስ አ/ማህበር

ተጠሪ - አቶ አብነት ሉሉ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል።

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የመድን ዋስትና ውልን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ በተጀመረበት በግልግል ዳኝነት ጉባኤ ተጠሪ በአመልካች ላይ ባቀረቡት ክስ በአመልካች የመድን ዋስትና ሽፋን የተሰጠው የሰሌዳ ቁጥር 3-90277 ኢት/227791 የሆነው የተጠሪ የደረቅ ጭነት ተሽከርካሪ ከነተሳቢው ጥቅምት 25 ቀን 2012 ዓ.ም በሱማሌ ክልል ሀረሬ ወንዝ በመሻገር ላይ እያለ በድልድይ መንሸራተት ምክንያት ተገልብጦ ወንዝ ውስጥ በመውደቁ የብር 2,000,000.00 ጉዳት ደርሶብኛል፤ አደጋ መድረሱን ለአመልካች አሳውቄ ካሳ እንዲከፍለኝ ጠይቄው ተሽርካሪውን አስነስቶ ወደ ሪከቨሪ ክፍል ውስጥ በማስገባት የሚጠገን መሆኑን ነግሮኝ ለ3 ወር አቆይቶታል፤ ሆኖም ግን ተሽከርካሪውን እንደማያስጠግንና ወጪውንም እንደማይሸፍን ስላሳወቀኝ በራሴ ወጪ በዱቤ አስጠግኛለሁ፤ ስለዚህ አመልካች ለማስጠገኛ የወጣ ወጪ ብር 2,000,000.00፤ ለሶስት ወር አቆይቶ ሳያስጠግን በመመለሱ የ3 ወር የተቋረጠ ገቢ ብር 600,000.00 እንዲሁም የተሽከርካሪ ማስጫኛ (ለክሬን) ዋጋ ብሎ አመልካች የተቀበለኝን ብር 38,000.00 ከህጋዊ ወለድ ጋር እንዲከፍለኝ ይወሰንልኝ በማለት የጠየቀዉን ዳኝነት መነሻ ያደረገ ነዉ።

አመልካች በበኩሉ በሰጠዉ መልስ በተጠሪ ተሸከርካሪ ላይ ለደረሰው አደጋ ምክንያት ጎርፍ በመሆኑ በመድን ውል አንቀጽ II(12) እና በንግድ ሕግ አንቀጽ 663(1) እና 665(1) መሰረት ኃላፊነት የለብኝም፤ አሽከርካሪው የሀረሬ ወንዝ በጎርፍ መሙላቱን እያየና ሊያሳልፍ እንደማይችል እያወቀ ተገቢውን ጥንቃቄ ባለማድረግ የደረሰ አደጋ ስለሆነና ይህም በመድን ውል አንቀጽ 6 ስር ተጠሪ ወይም አሽርካሪው ከአደጋ ወይም ከሲሳራ የመጠበቅ ግዴታ ስላልተወጣ ኃላፊነት የለብኝም፤ የዶሎ አዶ ወረዳ ፖሊስ ጽ/ቤት የአደጋውን ምክንያት ድልድይ በከፊል መናድ ነው ቢልም በአደጋው ቦታ ድልድይ የለም፤ በመሆኑም በማግለያ ድንጋጌ መሰረት ኃላፊነት የለብኝም፤ ለተሸከርካሪ ጥገና ብር 2,000,000.00 ወጪ አድርጌያለሁ በማለት የቀረበዉም የማስረጃ ድጋፍ የለውም፤ ከተሰጠው መጠን 50% በላይ ለጥገና ወጪ የሚያስፈልግ ከሆነ ካሳ ሊከፈል የሚገባው በጠቅላላ ውድመት ስለሆነ የካሳ ጥያቄው ተቀባይነት የለውም፤ ተሸከርካሪውን ለማስጠገን የእጅ ዋጋ ብር 58,000.00 እና የመለዋወጫ ዕቃ ብር 822,756.76 በሰርቬር አስገምቼ በዋጋ ማቅረቢያ ሰብስቤ ስላረጋገጥኩ ሊከፈለው የሚገባው ይህ ነው፤ በመድን ውል II (2) እና VI(2) መሰረት ተጠሪ ላይ ለደረሰ የተቋረጠ ገቢ ወይም ተሸከርካሪውን ባለመጠቀም ለሚደርስ ኪሳራ ኃላፊነት የለብኝም፤ ኃላፊነት አለብህ ከተባልኩኝ ልከፍል የሚገባው ብር 822,756.76 ብቻ ነው ተብሎ ይወሰንልኝ በማለት ተከራክሯል፡፡

ጉዳዩ የቀረበለት የግልግል ዳኝነት ጉባኤውም ከግራ ቀኝ በዚህ መልኩ የቀረበዉን ክርክር እና ማስረጃ ከመረመረ በኋላ አደጋው የደረሰው ተሸከርካሪው በአሽከርካሪው ቸልተኝነት ሳቢያ በውኃ ወደተሸፈነው የሀረሬ ወንዝ ሲነዳ ለተሸከርካሪዎች መተላለፊያ የተዘረጋው መሸጋገሪያ መንገድ በመናዱና ተሸከርካሪው መንገድ በመሳቱ እንጂ በድንገተኛ ደራሽ ጎርፍ አለመሆኑን በማስረጃነት የቀረበው ቪዲዮ ጭምር የሚያሳይ መሆኑን ጠቅሶ በተጠሪ ተሸከርካሪ ላይ ለደረሰ ጉዳት አመልካች ካሳ የመክፈል ኃላፊነት አለበት ከሚል ድምዳሜ ላይ በመድረስ የኃላፊነት መጠንን አስመልክቶ ተጠሪ ለጥገና ወጪ እንዲከፈለው የጠየቀው ብር 2,000,000.00 ቢሆንም ይህ ጥያቄዉ እምነት በሚጣልበት ማስረጃ ተደግፎ ያልቀረበ ሲሆን በአንፃሩ አመልካች በራሱ ባለሙያ ለጋቢና ያስገመተዉን ብር 906,800.00 እንዲሁም በተጠሪ ማስረጃ የተረጋገጠዉ 161,000.00 ጨምሮ በድምሩ ብር 1067800 የሚመጣ ሲሆን ከዚህ ዉስጥ የአደጋ መነሻ ብር 53,390.00 ተቀንሶ ለመኪናዉ ጥገና የመለዋወጫ ዕቃ ብር 1,014,410.00 እንዲሁም ለተጎዳዉ መኪና ማጓጓዣ ተጠሪ ያወጣዉን ብር 38,000.00 ክስ ከቀረበበት ቀን ጀምሮ ከሚታሰብ 9% ወለድ ጋር አመልካች ለተጠሪ እንዲከፍል ካለ በኋላ ተጠሪ የገቢዉን መጠን የሚያሳይ ማስረጃ እንዲያቀርብ ታዞ አለማቅረቡን ጠቅሶ በአደጋዉ ምክንያት የተቋረጠ ጥቅም እንዲከፈለዉ ተጠሪ ያቀረቡትን ዳኝነት ዉድቅ በማድረግ ወስኗል፡፡

ግራ ቀኝ በዚህ ዉሳኔ ላይ ቅር በመሰኘት በየግላቸው በመዝገብ ቁጥር 206497 እና 206501 ላይ ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ያቀረቡ ሲሆን፣ ፍርድ ቤቱም የግራ ቀኙን የይግባኝ መዝገቦች አጣምሮ ካከራከረ በኋላ የግልግል ጉባኤው ኃላፊነትን በተመለከተ የሰጠውን የውሳኔ ክፍል

በማፅናት በሌላ በኩል ጉባኤው ጉዳት ለደረሰበት ተሸከርካሪ ማስጠገኛ እና የመለዋወጫ ዕቃዎችን ዋጋ መጠን እንዲሁም የተቋረጠ ጥቅም ዳኝነት ጥያቄን አስመልክቶ የተሰጠውን የውሳኔ ክፍል በመሻር በድጋሚ አጣርቶ ተገቢውን ውሳኔ እንዲሰጥ ጉዳዩን በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.343(1) መሰረት ለጉባኤው በመመለስ በአብላጫ ድምጽ ወስኗል፡፡ ለዚህ ፍርድ መነሻ የሆነው የአመልካች የሰበር አቤቱታም የግልግል ጉባኤው እና የጠቅላይ ፍ/ቤት የሰጠውን ውሳኔን በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡

አመልካች ሐምሌ 28 ቀን 2014 ዓ.ም በተፃፈ የሰበር አቤቱታ በግልግል ዳኝነት ጉባኤው እና በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ተፈጽመዋል ያሏቸውን ስህተቶች በመዘርዘር በዚህ ችሎት እንዲታረሙለት ዳኝነት ጠይቋል፡፡ የአቤቱታው ይዘትም በአጭሩ የአደጋው ቦታ በጎርፍ ውሃ መሸፈኑን፣ አሽከርካሪው ውሃ እስከሚጎድል መጠበቅ ሲገባው ሌሎች ከኋላው ያሉት አሽከርካሪዎች ውሃው እስኪጎድል እየተጠባበቁ የተጠሪ ተሸከርካሪ ሹፌር ግን በድፍረት በውሃ ወደተሸፈነው በመግባት መንገዱን መለየት ባለመቻሉ አደጋው የደረሰ ስለመሆኑ የግልግል ጉባኤውም ሆነ የፌ/ጠ/ፍ/ቤት አረጋግጠዉ ነገር ግን የመድን ውሉን የማግለያ ድንጋጌ ያለአግባብ በመተርጎም በተጠሪ ተሸከርካሪ ላይ አደጋ የደረሰው ድንገተኛ ደራሽ በሆነ ጎርፍ ሳይሆን በአሽከርካሪው ቸልተኝነት ምክንያት ነው በማለት የሰጡት ዉሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት ነው፤ በአደጋው ቦታ ድልድይ አለመኖሩን በቪዲዮ፣ በፎቶግራፍ እና በምስክር ተረጋግጦ እያለ የዶሎ ኦዳ ወረዳ ትራፊክ ፖሊስ ጽ/ቤት ተገቢውን የሙያ ደንብ ሳይከተል የአደጋ ምክንያት የድልድዩ ድንገተኛ በከፊል መናድ ነው ሲል የሰጠውን ሪፖርት የግልግል ጉባኤው እና የስር ፍርድ ቤት ተገቢ ነው ሲሉ የሰጡት ወሳኔ ሰበር ሰሚ ችሎት በመ.ቁ 43453 ላይ የሰጠውን አስገዳጅ የህግ ትርጉም የሚቃረን ነው፤ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት አመልካች የተቋረጠ ገቢ ሊከፍል ይገባል ማለቱ እና መጠኑም በርትዕም እንዲወሰን ለጉባኤው መመለሱም መሰረታዊ ስህተት ነው የሚል ነዉ፡፡

የሰበር አቤቱታዉም በአጣሪ ችሎት ተመርምሮ ያስቀርባል በመባሉም ተጠሪ በተደረገለት ጥሪ መሠረት ጥር 15 ቀን 2015 ዓ.ም በተፃፈ መልሳቸው ማስረጃን የሚመለከት ክርክር ለሰበር ሊቀርብ አይችልም፡፡ የስር የግልግል ዳኝነት ጉባኤ እንዲሁም የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አደጋዉ የደረሰዉ በጎርፍ ሳይሆን በሾፌሩ ጥፋት ምክንያት ነዉ ከሚል መደምደሚያ ላይ የደረሱ ሲሆን ለሾፌሩ ጥፋት ደግሞ አመልካች ኃላፊነት ያለበት ከመሆኑ አኳያ ውሳኔዉ ስህተት ስለሌለበት አቤቱታው ውድቅ እንዲደረግልኝ በማለት ተከራክሯል፡፡ አመልካች የሰበር አቤቱታውን በማጠናከር የመልስ መልስ ሰጥቷል፡፡

ከስር ጀምሮ የጉዳዩ አመጣጥ እና የግራ ቀኙ ክርክር ይዘት አጠር አጠር ባለ መልኩ ሲታይ ከፍ ሲል የተመለከተዉን ሲመስል ይህ ችሎትም ለሰበር አቤቱታዉ ምክንያት የሆነዉን ዉሳኔ ከግራ ቀኝ ክርክር እና ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸዉ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ መዝገቡን እንደሚከተለዉ

መርምሮታል፡፡ እንደመረመረውም ተጠሪ በስር ፍርድ ቤት ባቀረበው ክስ ለጠየቀው ዳኝነት መሠረት ያደረገው በአመልካች የመድን ሽፋን የተሰጠው ተሽከርካሪው በደረሰበት አደጋ ምክንያት ለጥገና እና ለመለዋወጫ የወጣውን ወጪ እንዲሁም ለተቋረጠ ጥቅም ካሳ ለመክፈል አመልካች ኃላፊነት ያለበት መሆኑን ሲሆን፣ አመልካች በበኩሉ ጉዳት ለደረሰበት የተጠሪ ተሽከርካሪ የመድን ሽፋን መስጠቱን ሳይክድ ኃላፊነት የለብኝም በማለት አጥብቆ የሚከራከረው አደጋው የደረሰው በጎርፍ ምክንያት መሆኑን እና በጎርፍ ምክንያት ለደረሰው አደጋ ደግሞ በመድን ዉሉ የማግለያ ድንጋጌ መሠረት ኃላፊነት የሌለበት መሆኑን በመጥቀስ ነው፡፡

በርግጥ በጎርፍ ምክንያት በተሽከርካሪው ላይ ለሚደርስ አደጋ አመልካች ካሳ የመክፈል ኃላፊነት እንደሌለበት በመድን ዉሉ የማግለያ አንቀጽ II (12) ላይ የተመለከተ ስለመሆኑ ግራ ቀኝ የሚታማመኑበት ነው፡፡ አከራካሪው ነጥብ አደጋው የደረሰው በርግጥ በጎርፍ ምክንያት ነው ወይስ አይደለም? የሚለው ነጥብ ነው፡፡ ጉዳዩን በመጀመሪያ የተመለከተው የግልግል ዳኝነት ጉባኤውን ይህንኑ በጭብጥነት በመያዝ “ጎርፍ” ለሚለው ቃል በተለያዩ መዝገበ ቃላት የሚሰጡ ትርጉሞችን በዋቢነት በመጥቀስ የጎርፍ ዉሃ መጠኑ ከፍተኛ እንደሆነ፣ ድንገተኛ እና ከመደበኛ ቦታው በመዉጣት ሰፊ ቦታን በመሸፈን እና መስመርን በመጣስ የመፍሰስ ባህሪ ያለው መሆኑን ደምድሞ በተያዘው ጉዳይ በሀረሬ ወንዝ ላይ ዉሃው ሲፈስ የነበረው የፍሳሽ መስመሩን ይዞ መሆኑን፣ መኪናው ወደ ወንዙ የገባውና የመገልበጥ አደጋ የደረሰበት ዉሃው መስመሩን ይዞ እየሄደ እንጂ በድንገት በመጣ ደራሽ ዉሃ አለመሆኑን፣ የዉሃው መጠንም ሰዎች ከተገለበጠው መኪና ወጥተው በቀላሉ ሲንዘቡበት እንደነበረ እና አደጋው የደረሰውም የተጠሪ ተሽከርካሪ ሹፌር መኪናውን ወደ ዉሃው በመንዳቱ እንጂ ዉሃው ዉስጥ ከገባ በኋላ በመጣ ዉሃ ምክንያት አለመሆኑን ከድምዳሜ ላይ ደርሷል፡፡ በዚህ ድምዳሜ ላይ ሲደርስ በዋነኝነት ዋቢ ያደረገውም የቀረበለትን የቪዲዮ ማስረጃ ስለመሆኑ የዉሳኔው ይዘት ያሳያል፡፡ ጉዳዩን በይግባኝ የተመለከተው የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤትም ይህን የፍሬ ነገር ድምዳሜ ተቀብሎታል፡፡ ሁለቱም የዳኝነት ሰጪ አካላት በዚህ የፍሬ ነገር ድምዳሜ ላይ ሲደርሱ ከማስረጃ አቀባበል እና የምዘና መርህ ጋር በተያያዘ የፈጸሙት ስህተት ስለመኖሩ ዉሳኔዎቹ አያሳዩም፡፡ የማግለያ ድንጋጌው ከላይ በተመለከተው ሁኔታ በመድን ዉሉ የተመለከተበት ምክንያትም አስቀድሞ መገመት በማይቻል፣ ድንገተኛ እና ከቁጥጥር ዉጪ በሆነ ሁኔታ ለሚደርስ አደጋ አመልካች ኃላፊነት ሊኖርበት አይገባም በሚል መነሻ እንደሆነ ይታመናል፡፡ በመሆኑም አደጋው የደረሰው በድንገት በደረሰ ጎርፍ ምክንያት ሳይሆን አሽከርካሪው መስመሩን ይዞ በሚሄድ እና ሰዉም ሊሻገርበት ወደሚችል ዉሃ መኪናውን በመንዳቱ ምክንያት የተረጋገጠ ከመሆኑ አኳያ በመድን ዉሉ ላይ የተመለከተው የማግለያ ድንጋጌ ለተያዘው ጉዳይ ተፈፃሚነት የለውም፡፡ በመሆኑም አመልካች በዚህ ረገድ ያቀረበውን ክርክር ውድቅ በማድረግ በግልግል ዳኝነት ጉባኤው ተሰጥቶ በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በጸናው ዉሳኔ ላይ

የተፈጸመ በዚህ ችሎት ሊታረም የሚችል መሠረታዊ የህግ ስህተት ባለመኖሩ ከዚህ ጋር በተያያዘ አመልካች የሚያቀርበውን ክርክር ይህ ችሎት አልተቀበለውም፡፡

በመቀጠል መታየት ያለበት ነጥብ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ለመኪናው ጥገና እና መለዋወጫ የወጣውን ወጪ እንዲሁም የተቋረጠ ጥቅምን አስመልክቶ በድጋሚ ተጣርቶ እንዲወሰን ጉዳዩን ወደ ግልግል ዳኝነት ጉባኤው የመለሰበትን አግባብነት ነው፡፡ ከላይ በተደጋጋሚ እንደተገለጸው ክርክሩ የተጀመረው በግልግል ዳኝነት ጉባኤ ላይ ነው፡፡ የግልግል ዳኝነት ከመደበኛ ፍርድ ቤት ወጪ ዳኝነት ከሚታዩባቸው አማራጭ የሙግት መፍቻ መንገዶች ውስጥ አንዱ ስለመሆኑ የሚታወቅ ነው፡፡ አለመግባባቶችን በግልግል ዳኝነት መፍታት በተከራካሪ ወገኖች መካከል ያለው አለመግባባት በአነስተኛ ወጪ እና በአጭር ጊዜ እልባት እንዲያገኝ ማድረግ የሚያስችል እንዲሁም የፍርድ ቤቶችን የስራ ጫና እንዲቀንስ በማድረግ ረገድ ከፍተኛ ጠቀሜታ እንዳለው የሚታወቅ ነው፡፡ ስለሆነም በተቻለ መጠን በግልግል ዳኝነት የሚሰጥ ውሳኔ የመጨረሻ ሆኖ ተፈፃሚ ሊሆን የሚችልበትን ሥርዓት ማበጀት እና ተግባራዊ የማድረጉ አስፈላጊነት አያጠያይቅም፡፡ የግልግል ዳኝነትንና የእርቅ ሥርዓትን ለመደንገግ የወጣ አዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀጽ 49 በግልግል ዳኝነት ውሳኔ ላይ ይግባኝ ማቅረብ የሚቻልበትን ሁኔታ የገደበውም በዚሁ መነሻነት እንደሆነ ይታመናል፡፡ የፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ህጉም በግልግል ዳኝነት ውሳኔ ላይ ይግባኝ ማቅረብ የሚቻለው የተወሰኑ ሁኔታዎች ሲሟሉ ብቻ መሆኑን በመደንገግ በይግባኝ አቀራረብ ላይ ገደብ ያስቀምጣል፡፡ በዚህም መሠረት በግልግል ዳኝነት ውሳኔ ላይ ይግባኝ ማቅረብ የሚቻለው ውሳኔው የተለያየ ወይም አንዱ ክፍል ከሌላው ጋር የማይገናኝ ወይም የማይስማማ ወይም ግልጽ ያልሆነ ወይም የሚያጠራጥር ወይም በቀጥታ በህግና በፍሬ ነገሩ ረገድ የተሳሳተ ሲሆን፤ ጉባኤው የቀረበለትን ዳኝነት ሳይወስን ከቀረ፤ ክርክሩ በሚሰማበት ጊዜ ከሥነ ሥርዓት ውጪ የሆነ ነገር የተፈጸመ እንደሆነ እንዲሁም ከዳኞች አንዱ አባል የሥነ ምግባር ግድፈት ወይም የአድሎአዊነት ተግባር ያሳየ ሲሆን ብቻ ስለመሆኑ በህጉ አንቀጽ 351 ላይ ከተመለከቱት ድንጋጌዎች መገንዘብ ይቻላል፡፡ ከዚህ ሁሉ የምንገነዘበው በመደበኛ ፍርድ ቤት ከሚሰጥ ውሳኔ በተለየ ሁኔታ በግልግል ዳኝነት በተሰጠ ውሳኔ ላይ ይግባኝ የሚቀርበው በዘፈቀደ ሳይሆን በተወሰኑ ሁኔታዎች ላይ ብቻ መሆኑን ነው፡፡

በተያዘው ጉዳይ፣ ከፍ ሲል እንደተመለከተው፣ የግልግል ዳኝነት ጉባኤው ጉዳት የደረሰበትን ተሸከርካሪ ለማስጠገን እና የመለዋወጫ ዕቃዎችን ለመግዛት ሊወጣ የሚችለውን ወጪ መጠን የወሰነው አመልካች በዚህ ረገድ ያቀረባቸው ማስረጃዎች እምነት የሚጣልባቸው አለመሆኑና በአንዳንዱ በአመልካች በእራሱ ባለሙያዎች ተገምቶ የቀረበው አሳማኝ ሆኖ መገኘቱን በመጥቀስ ነው፡፡ የተቋረጠ ጥቅምን አስመልክቶ ለሰጠው ውሳኔ መሠረት ያደረገውም የገቢ መጠንን አስመልክቶ ከህብረት ባንክ እንዲያቀርብ የታዘዘውን ማስረጃ ተጠሪ ማቅረብ አለመቻሉን በግልጽ በማመላከት ነው፡፡ የግልግል ዳኝነት ጉባኤው በዚህ አግባብ ውሳኔ ሲሰጥ በፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ህጉ አንቀጽ 351 ስር ከተመለከቱት እና

ለይግባኝ ምክንያት ሊሆኑ ከሚችሉ ስህተቶች አንዱንም የፈጸመ ስለመሆኑ ዉሳኔዉ አያሳይም፡፡ ከዚህ አንፃር ሲታይ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የግልግል ዳኝነት ጉባኤዉ የሰጠዉን ዉሳኔ በመሻር በድጋሚ አጣርቶ ለተጠሪ የሚገባዉን የካሳ መጠን እንዲወስን ጉዳዩን ወደ ግልግል ዳኝነት ጉባኤዉ በመመለስ የሰጠዉ ዉሳኔ የፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ህጉን አንቀጽ 351 ድንጋጌን ያላገናዘበ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

በአጠቃላይ የአመልካችን ኃላፊነት አስመልክቶ በግልግል ዳኝነት ጉባኤ የተሰጠዉን ዉሳኔ በማጽናት የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰጠዉ ዉሳኔ ተገቢ ቢሆንም ለተጠሪ ሊከፈል የሚገባዉን ካሳ እና መጠኑን አስመልክቶ የሰጠዉ ዉሳኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ተከታዩ ዉሳኔ ተሰጥቷል፡፡

<u>ዉሳኔ</u>

1. የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 206497 እና 206501 ላይ ሚያዝያ 28 ቀን 2014 ዓ.ም በዋለዉ ችሎት ኃላፊነትን አስመልክቶ የግልግል ዳኝነት ጉባኤዉን ዉሳኔ በማጽናት የሰጠዉ የዉሳኔ ክፍል ጸንቷል፤ በፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ህጉ አንቀጽ 343(1) መሠረት ጉዳዩን ወደ ግልግል ዳኝነት በመመለስ የሰጠዉ የዉሳኔ ክፍል ተሽሯል፡፡
2. የግልግል ዳኝነት ጉባኤዉ የካቲት 20 ቀን 2013 ዓ.ም በዋለዉ ችሎት የሰጠዉ ዉሳኔ ጸንቷል፡፡
3. በዚህ ችሎት የተደረገዉ ክርክር ያስከተለዉን ወጪ እና ኪሳራ ግራ ቀኝ የየራሳቸዉን ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ፍ/ደ

የሰ/መ/ቁ፡- 202581

ቀን፡- 26/02/2014 ዓ.ም

ዳኞች፡- ብርሃኑ አመነዉ

ተሾመ ሽፈራዉ

ሀብታሙ እርቅይሁን

ብርሃኑ መንግሥቱ

ነጻነት ተገኝ

አመልካች፡- ወ/ሮ ረሂማ አብዱላሂ

ተጠሪዎች፡- 1.ከዲር ዮሱፍ በከር

2. ሰይዳ ረመዳን

መዝገቡ ተመርምሮ ከዚህ የሚከተለዉ የፍርድ ዉሳኔ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የጋራ የሆነ የእርሻ መሬት በሽያጭ ለማስተላለፍ የተደረገ ነዉ የተባለዉ ዉል ቀሪ እንዲደረግና ይዞታዉን ለማስለቀቅ እንዲሁም አላባ ለማስከፈል የቀረበ ክስ የመዳኘት ሥልጣን የሚመለከት ነዉ፡፡ አመልካች በተጠሪዎችና በስር 1ኛ ተከሳሽ አቶ ሙስጠፋ ዩሱፍ ላይ በሐረሪ ክልል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመሰረቱት ክስ ከስር 1ኛ ተከሳሽ ጋር ለ30 ዓመታት በትዳር ተሳስረን አብረን ስንኖር በሐረር ክልል በድሬ ጠያራ ወረዳ በአቦከር ሙጢ ቀበሌ ገበሬ ማኅበር ዉስጥ ያለንን አንድ ጥማድ ከግማሽ የሆነ አዋሳኙ በክሱ የተጠቀሰዉን የእርሻ መሬት ያለእኔ ፈቃድ በሕገ-ወጥ መንገድ ለአሁን ተጠሪዎች በሽያጭ አስተላልፈዋል፡፡ በዚህ ምክንያት በአመት 20 ኩንታል ማሽላ በማምረት ማግኘት የምንችለዉን በኩንታል በብር 1200.00 ሂሳብ ብር 24,000.00 አሳጥተዉኛል፡፡እየተቃወምኩ በመሬቱ ላይ ተጠሪዎች ቤት ሰርተዉበታል፡፡ስለሆነም ዉሉ ሕገ-ወጥ ስለሆነ እንዲፈርስና የገነቡትን ቤት አፍርሰዉ ይዞታዬን እንዲለቁ ይወሰንልኝ በማለት ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡

የስር 1ኛ ተከሳሽ ለክሱ በሰጡት መልስ ለክርክሩ መነሻ የሆነዉን መሬት ከአመልካች ጋር በጋራ የያዙት መሬት እንደሆነና ያለአመልካች ፈቃድ በማንኛዉም ሁኔታ ማስተላለፍ እንደሌለብኝ ባለማወቅ ለተጠሪዎች በማስተላለፌ ተጠሪዎች በእርሻ መሬታችን ላይ ቤት ሊሰሩበት ስለቻሉ በአመልካች ጥያቄ መሰረት ቢወሰን አልቃወምም የሚል ይዘት ያለዉ መልስ ሰጥተዋል፡፡2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች በሰጡት መልስ መኖሪያ ቤት ለመግዛት እየፈለጉ ባሉበት የስር 1ኛ ተከሳሽ በመሬቱ የመጠቀም መብታቸዉን ለማስተላለፍ ፈልገዉ የመጠቀም መብታቸዉን ብር 100,100.00 ሸጠዉልናል፡፡ የመሬት ባለቤትነት

ለመወሰድ በሂደት ላይ እንገኛለን፡፡መራቱ በዚህ አግባብ እንደተላለፈልንና ቤት ስንሰራም አመልካች እያወቁ አልተቃወሙንም በማለት ክሱ ዉድቅ እንዲደረግላቸዉ በመጠየቅ ተከራክረዋል፡፡

ፍርድ ቤቱም በመ/ቁጥር 17912 ላይ የግራ ቀኙን ክርክርና ምስክሮች ሰምቶና መርምሮ በቀን 26/01/2012 ዓ/ም በሰጠው ውሳኔ የስር 1ኛ ተከሳሽ ያለተጠሪ ፈቃድ ባልና ሚስት ሆነዉ ከአመልካች ጋር በጋራ ባለይዞታ የሆኑበትን የመሬት ይዞታ ለተጠሪዎች በሽያጭ በማስተላለፍ ያደረጉት ዉል የፌዴራል ቤተሰብ ሕግ አንቀጽ 68ን የሚቃረን በመሆኑ በዚሁ ሕግ አንቀጽ 69 መሰረት ዉሉ ፈርሶ ተጠሪዎች የገነቡትን ግንባታ በራሳቸዉ ወጪ አፍርሰዉ መሬቱን ለቀዉ እንዲወጡና ወደነበሩበት እንዲመለሱ ሲል ወስኗል፡፡

ተጠሪዎች በዚህ ዉሳኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለሐረሪ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት አቅርበዉ ፍርድ ቤቱ በመ/ቁጥር 04953 ላይ ግራ ቀኙን አከራክሮ በቀን 22/10/2012 ዓ/ም በሰጠዉ ዉሳኔ አመልካች ክስ የመሰረቱት ፍርድ ቤቱ በአዋጅ ቁጥር 25/1988 መሰረት ጉዳዩን ለመዳኘት ሥልጣን አለዉ በማለት ቢሆንም ግራ ቀኝ የኦሮሚያ ክልል ነዋሪዎች በመሆናቸዉ፣ዉሉ የተደረገበት የመሬት ይዞታ የሚገኘዉ በሐረሪ ክልል ዉስጥ የሚገኝ በመሆኑ ጉዳዩን የፌዴራል ጉዳይ የሚያደርግ ምክንያት በሌለበት እንደፌዴራል ጉዳይ ተቀብሎ መዳኘቱ ስህተት ነዉ፡፡እንዲሁም አመልካች ክስ ሲመሰርቱ በግምት ብር 24,000.00 ምርት የሚገኝበት መሬት እንደሆነ ጠቅሰዉ ያቀረቡት ክስ ስለሆነ የክልሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በዚህ ልክ የሚገመት ክስ በመጀመሪያ ደረጃ ዳኝነት ሥልጣን ተቀብሎ ለመዳኘት የሚያስችል ስልጣን ሳይኖረዉ የሰጠዉ ዉሳኔ ነዉ በማለት የስር ፍርድ ቤትን ዉሳኔ ሽሯል፡፡በዚህ ዉሳኔ ቅር በመሰኘት አመልካች የሰበር አቤቱታቸዉን ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ቢያቀርቡም በመ/ቁጥር 00124 ላይ በቀን 24/03/2013ዓ/ም በሰጠዉ ትእዛዝ አቤቱታቸዉን ሰርዞባቸዋል፡፡

አመልካች በቀን 07/10/2013 ዓ/ም የተጻፈ የሰበር አቤቱታ ያቀረቡት ግራ ቀኝ በተለያዩ ክልሎች ነዋሪ መሆናችን ስለተረጋገጠ የስር የክልሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ጉዳዩን እንደ ፌዴራል ጉዳይ በመቁጠር ዉሳኔ መስጠቱ ተገቢ ሆኖ ሳለ ተጠሪዎችም ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን የመዳኘት ስልጣን እንደሌለዉ ገልጸዉ ያቀረቡት መቃወሚያ ሳይኖር ዉሳኔዉ በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት መሻሩ በአዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀጽ 5/2 ስር የተደነገገዉንና በሰ/መ/ቁጥር 144613 ላይ የተሰጠዉን ዉሳኔ የሚቃረን በመሆኑ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ነዉ፡፡እንዲሁም የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ያቀረብኩትን የሰበር አቤቱታ ምርምሮ ለሰበር እንዲቀርብ አዞ ግራ ቀኝ የጽሁፍ ክርክር አቅርበን ለዉሳኔ በተቀጠረበት ቀን ጉዳዩ ለሰበር አያስቀርብም በማለት ዉሳኔ የሰጠበት አግባብ በፍ/ብ/ስ/ስ/ሕግ ቁጥር 337 እና ከቁጥር 339-348 ስር ስለዉሳኔ አሰጣጥ የተደነገገዉን ሥነ ሥርዓት የተከተለ ባለመሆኑ ሊታረም የሚገባዉ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ነዉ በማለት አቤቱታቸዉን አቅርበዋል፡፡

የሰበር አጣሪ ችሎት አቤቱታውን መርምሮ የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ጉዳዩን ለማጣራት ያስቀርባል ብሎ ግራ ቀኙን ካከራከረ በኋላ ወደኋላ ተመልሶ አያስቀርብም በማለት ዉሳኔ የሰጠበት አግባብ ተጠሪዎች ባሉበት እንዲመረመር ትዕዛዝ በመስጠቱ ተጠሪዎች በቀን 05/11/2013 ዓ/ም የተፃፈ መልስ በማቅረብ ግራ ቀኝ በአንድ ክልል ዉስጥ ነዋሪ ስለሆንና ለክርክሩ መነሻ የሆነዉ መሬትም በሐረሪ ክልል የሐረሪ ከተማ አካል ሆኖ የሚገኝ በመሆኑ ጉዳዩን የመዳኘት ሥልጣን ያለዉ የከተማ ነክ ፍርድ ቤት በመሆኑ የስር የክልሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ጉዳዩን በፌዴራል ዳኝነት ሥልጣን ተቀብሎ መዳኘቱ ስህተት ነዉ ተብሎ በመሻሩ የተፈጸመ ስህተት የለም በማለት መልሳቸዉን ሰጥተዋል፡፡

ከዚህ በላይ አጠር ባለ መልኩ የተመለከተዉ የግራ ቀኝ ክርክርና በስር ፍርድ ቤቶች የተሰጡ ዉሳኔዎች ይዘት ሲሆን እኛም የሰበር አጣሪ ችሎት ጉዳዩ ለሰበር ችሎት ያስቀርባል ሲል ከያዘዉ ጭብጥ በተጨማሪ የክልሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ጉዳዩን እንደፌዴራል ጉዳይ ቆጥሮ በዉክልና ሥልጣን አከራክሮ መወሰኑ ተገቢ አይደለም ተብሎ በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ዉሳኔዉ በመሻሩ የተፈጸመ መሰረታዊ የሕግ ስህተት መኖር አለመኖሩን አግባብነት ካለዉ ሕግ ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለዉ መርምረናል፡፡

እንደመረመርነውም አመልካችና ተጠሪዎች ነዋሪነታቸዉ በአንድ ክልል ዉስጥ እንደሆነ ጉዳዩን በይግባኝ ያየዉ የሐረሪ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ያረጋገጠዉ ፍሬ ነገር ነዉ፡፡የክሱ ስረ ነገር እና በአመልካች የተጠየቀዉ ዳኝነት አመልካች ያለፈቃደ የጋራ ባለይዞታ የሆንኩበትን የእርሻ መሬት ባለቤቱ ለተጠሪዎች በሽያጭ ለማስተላለፍ የተደረገዉ ዉል ቀሪ ሆኖ ተጠሪዎች እየተቃወምኩ የሰራሁትን ቤት አፍርሰዉ መሬቱን እንዲለቁ ይወሰንልኝ የሚል እንደሆነ ከክርክሩ ተገንዝበናል፡፡እንዲሁም ለክሱ መሰረት የሆነዉ ዉልም የተደረገዉም ሆነ ተሸጠ የተባለዉ መሬት የሚገኘዉ በሐረሪ ክልል ዉስጥ መሆኑ አከራካሪ አይደለም፡፡የሐረሪ ክልል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ዘንድ ክሱ ሲቀርብ በሥራ ላይ በነበረዉ በፌዴራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀጽ 5/2 መሰረት መደበኛ ነዋሪነታቸዉ በተለያዩ ክልሎች ዉስጥ በሆኑ ሰዎች መካከል የሚነሱ ክርክሮችን የመዳኘት ሥልጣን የፌዴራል ፍርድ ቤቶች እንደሆነ በተደነገገዉ መሰረት የሐረሪ ክልል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የግራ ቀኙ መደበኛ የመኖሪያ አድራሻ በተለያዩ ክልሎች ዉስጥ መሆኑ ከተረጋገጠና ክርክር ያስነሳዉ ንብረት ግምት በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ሥልጣን ሥር የሚወድቅ መሆኑ ካረጋገጠ በኢ.ፌ.ዲ.ሪ. ሕገ መንግስት አንቀጽ 80/4 መሰረት በዉክልና ጉዳዩን ተቀብሎ የመዳኘት ሥልጣን ይኖረዋል፡፡ሆኖም በተያዘዉ ጉዳይ የግራ ቀኙ መደበኛ አድራሻ በአንድ ክልል ዉስጥ መሆኑ ከመረጋገጡም በላይ ለክርክሩ መነሻ የሆነዉ ዉል የተደረገዉና እንዲፈጸም የታቀደዉ መሬቱ በሚገኝበት ሐረሪ ክልል ዉስጥ በመሆኑ ጉዳዩን የፌዴራል ጉዳይ የሚያደርግ ምክንያት የለም፡፡ስለሆነም የሐረሪ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የክልሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ጉዳዩን እንደፌዴራል ጉዳይ በመቁጠር በመጀመሪያ ደረጃ ዳኝነት ሥልጣን አከራክሮ መወሰኑ ተገቢ አይደለም በማለት መሻሩና ጉዳዩ የክልል ጉዳይ ነዉ ሲል የሰጠዉ ዉሳኔ ሕግን መሰረት ያደረገ ነዉ ከሚባል በስተቀር በዚህ ችሎት ደረጃ ሊታረም የሚችል ስህተት የተፈጸመበት አይደለም፡፡

በሌላ በኩል የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ከላይ በተመለከተዉ መሰረት በሰጠዉ ዉሳኔ ቅር በመሰኘት አመልካች ያቀረቡትን የሰበር አቤቱታ መርምሮ ተጠሪዎችን ያስቀርባል በማለት ተጠሪዎች መልስ እንዲሰጡ ካደረገ በኋላ የፍ/ብ/ስ/ስ/ሕግ ቁጥር 337ን በመጥቀስ የክልሉ ሰበር የአመልካችን የሰበር አቤቱታ መሰረዙን ከቀረበዉ ክርክር ተገንዝበናል፡፡ እስካሁን የሰበር ችሎት ክርክሮችን የሚመራበት የተለየ ሥነ ሥርዓት ሕግ ባለመኖሩ በሥነ ሥርዓት ሕጎች ለመደበኛ ክስና ለይግባኝ ክርክሮች አመራር የተቀመጡ ድንጋጌዎችን ለሰበር በሚሆን መልኩ አመሳስሎ ተግባራዊ የማድረግ የዳበረ የሰበር ችሎቶች አሰራር መኖሩ ግልጽ ነዉ፡፡በዚህ አግባብ የክልልም ሆነ የፌዴራል የሰበር ሰሚ ችሎቶች የሥነ ሥርዓት ሕጉን ድንጋጌዎች ሲጠቀሙ በሥነ ሥርዓት ሕጎች የተዘረጋዉን የክርክር ሂደቶች አፈጻጸም ቅደም ተከተል በተቻለ መጠን በጥንቃቄ ተግባራዊ ማድረግ ይጠበቅባቸዋል፡፡ለፍትሐ ብሔር ይግባኝ ክርክር አመራር በፍትሐ ብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 337 እና 338/1 መሰረት የይግባኝ ማመልከቻዉንና የመጀመሪያዉ ደረጃ ፍርድ ቤት ፍርድ የሰጠበትን መዝገብ ግልባጭ በመመርምርና ይግባኝ ባይን በመስማት መልስ ሰጭ ቀርቦ እንዲከራከር ይግባኝ ሰሚዉ ፍርድ ቤት ትእዛዝ ከሰጠ የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ እንዲሁም ሕግን መርምሮ እንደነገሩ ሁኔታ በፍ/ብ/ስ/ስ/ሕግ ቁጥር 341፣343/1 እና 348/1 መሰረት ዉሳኔ ሊሰጥ ይገባል እንጂ ወደኋላ ተመልሶ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 337ን በመጥቀስ የይግባኝ ማመልከቻዉ በመሰረዝ መወሰን የሚችልበት ሥነ ሥርዓት አግባብ የለም፡፡በተመሳሳይ ለይግባኝ ክርክር አመራር የተቀመጠዉን ሥነ ሥርዓት በመጠቀም የሰበር ክርክር ሲመራም የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ ተጠሪ የሆነ ወገን መልስ አቅርቦ እንዲከራከር ከተደረገ በኋላ በስር ፍርድ ቤት የመጨረሻ ዉሳኔ ላይ የተፈጸመ መሰረታዊ የሕግ ስህተት መኖር አለመኖሩ ተመርምሮ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል ከተባለ እንዲታረም ካልሆነም የስር ፍርድ ቤት ዉሳኔ እንዲጸና ከሚወሰን በስተቀር ሂደቱን ወደኋላ በመመለስ የፍ/ብሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 337 ተጠቅሶ በሰበር ችሎት እንዲመረመር የሚያስችል መሰረታዊ የሕግ ስህተት የለም ተብሎ የሰበር አቤቱታዉ የሚሰረዝበት አግባብ የለም፡፡

በያዝነዉ ጉዳይ የሐረሪ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ጉዳዩ በሰበር ችሎት እንዲመረመር ትእዛዝ ሰጥቶ ተጠሪዎች መልስ ሰጥተዉ ከተከራከሩ በኋላ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 337ን በመጥቀስ የአመልካችን የሰበር አቤቱታ በመሰረዝ ትእዛዝ የሰጠበት መንገድ ሊታረም የሚገባዉ የክርክር አመራር ጉድለት ነዉ፡፡ሆኖም በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 337 መሰረት የይግባኝ ማመልከቻም ሆነ የሰበር አቤቱታን በመሰረዝ የሚሰጠዉ ዉሳኔ ከዉጤት አንጻር ሲታይ የስር ፍርድ ቤትን ዉሳኔ የማጽናት ያክል ሕጋዊ ዉጤት ያለዉ ነዉ፡፡በመሆኑም ከመነሻዉም ክርክሩ የፌዴራል ጉዳይ ባልሆነበት እንደፌዴራል ጉዳይ ተቆጥሮ የተወሰነበት የክርክር አመራር ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑና ጉዳዩ የክልል ጉዳይ ስለሆነ እንደአዲስ ክስ ቀርቦበት ሥልጣን ባለዉ በሐረሪ ክልል ፍርድ ቤት ታይቶ ሊወሰን የሚገባ ከመሆኑ

አንጻር በማየት ከዚህ አኳያ በክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ዘንድ የተፈጠረዉን የክርክር አመራር ጉድለት አልፈነዋል፡፡ስለሆነም ተከታዩን ወስነናል፡፡

ዉ ሳ ኔ

1. የሐረሪ ክልል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 17912 ላይ በቀን 26/01/2012 ዓ/ም የሰጠውን ውሳኔ የሐረሪ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 04953 ላይ በቀን 22/10/2012ዓ/ም በሰጠዉ ዉሳኔ በመሻር የወሰነዉና የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ በመ/ቁጥር 00124 ላይ በቀን 24/03/2013ዓ/ም የሰጠዉ ትእዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 348/1 መሰረት ፀንተዋል፡፡
2. ይህ ዉሳኔ አመልካች ሥልጣን ባለዉ የክልሉ ፍርድ ቤት ክስ ከማቅረብ አያግዳቸዉም፡፡
3. ግራ ቀኝ በዚህ ችሎት ደረጃ ያወጡትን ወጭ የየራሳቸዉን እንዲችሉ ብለናል፡፡

ትዕዛዝ

1. የዉሳኔዉ ግልባጭ ለስር ፍርድ ቤት ይተላለፍ፡፡ ለግራ ቀኙም ግልባጩ ይሰጣቸዉ፡፡
2. በመዝገቡ ላይ የተሰጠ የዕግድ ትእዛዝ ካለ ተነስቷል፤ይጻፍ፡፡
3. መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ሄ/መ

የሰ.መ.ቁ.222041

ጥቅምት 04 ቀን 2015 ዓ.ም

ዳኞች፡- እትመት አሠፋ

ፀሐይ መንክር

ኑረዲን ከድር

መላኩ ካሣዬ

እስቲበል አንዱዓለም

አመልካች፡- አማን ባርጌቾ -- ጠበቃ ታረቀኝ አበራ -- ቀረቡ

ተጠሪ፡- ነጃት ባርጌቾ -- ቀረቡ

መዝገቡ ለምርመራ የተቀጠረ ነው፡፡ በመሆኑም መርምረን ተከታዩን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍርድ

የሰበር አቤቱታው ሊቀርብ የቻለው አመልካች የካቲት 24 ቀን 2014 ዓ.ም ጽፈው ባቀረቡት የሰበር አቤቱታ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ.ቁ 241972 ነሐሴ 12 ቀን 2014 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ፤ ይህንኑ ውሳኔ በማጽናት የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ.ቁ 215793 የካቲት 15 ቀን 2014 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ መሠረታዊ የሕግ ስሕተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል በማለት አቤቱታ በማቅረባቸው ነው፡፡

ጉዳዩ የቤት ክርክርን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ነው፡፡ በሥር ፍ/ቤት በተደረገው ክርክር የአሁን ተጠሪ ከሳሽ፤ የአሁን አመልካች ደግሞ ተከሳሽ በመሆን ተከራክረዋል፡፡ የአሁን ተጠሪ በሥር ፍ/ቤት ያቀረቡት ክስ ይዘት በአጭሩ፡- ተጠሪው በቦሌ ክፍለ ከተማ ቡልቡላ ወረዳ 12 ልዩ ስሙ መንደር 3 የሚገኝ ሰነድ አልባ ቤት አመልካች ከአረብ አገር በላኩለት ገንዘብ ገዝቶልኛል፤ ከውጪ ሐገር ስመለስ የተለያዩ ዕቃዎችን በመያዝ በቤቱ ውስጥ ለአንድ ዓመት ኖሬበታለሁ፤ ሆኖም በመካከላችን በተፈጠረው አለመግባባበት ምንም ዓይነት ንብረት ሳልይዝ ከቤቱ አስወጥቶኛል፤ ስለሆነም አመልካቹ ቤቱን እና ዕቃውን እንዲያስረክበኝ ይወሰንልኝ በማለት ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡

የአሁን አመልካች በሰጡት መልስ ተጠሪ በማስረጃነት ያቀረቡት የባለቤትነት ማስረጃ ሐሰተኛ ነው፤ ክስ ለማቅረብ የሚያስችል መብት እና ጥቅም የላቸውም በማለት የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ያቀረቡ ሲሆን በፍሬ ነገሩ ላይ ደግሞ ተጠሪ በተለያየ ጊዜ ከአረብ አገር የላከችውን ገንዘብ በአደራ አስቀምጬ ስትመጣ እኔ ጋ በማረፍ ገንዘቡን በፈለገችበት ጊዜ ስትወስድ ቆይታለች፤ ያልወሰደችው ብር 80000

/ሰማንያ ሺህ / አላት፤ ቤቱ በተጠሪ ስም አልተገዛም፤ ቤቱ የተገዛው ተጠሪ አረብ አገር ከመሄዷ በፊት ነው፤ ቤቱ የተገዛው በግል ገንዘቤ ነው፤ ቁሳቁስ እና ጌጥ ከፊሉ አለ፤ ከፊሉ ግን የተጋነነ እና በሀሰት የቀረበ ነው፤ ተጠሪ ቤቱን አስመልክቶ ከዚህ ቀደም በቦሌ ምድብ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ.ቁ 100305 ክስ አቅርባ በእርቅ ተስማምተን ተዘግቷል፤ ስለሆነም ክሱ ውድቅ ሊደረግ ይገባል በማለት ተከራክረዋል፡፡

ጉዳዩ የቀረበለት ፍ/ቤት በታመኑት ጉዳዮች ላይ አስቀድሞ ውሳኔ የሰጠ ሲሆን በተካዱ ላይ ደግሞ የግራ ቀኙን ምስክሮች ከሰማ በኋላ ተጠሪ ቀሪ ንብረቶች በአመልካች እጅ የሚገኝ መሆናቸውን አላረጋገጠችም፤ ቤቱን በሚመለከት ግን ከአመልካች በተሻለ ማስረጃ አስረድታለች፤ ስለሆነም አመልካች የተጠሪ ንብረት መሆናቸውን በዝርዝር ያመናቸውን የቤት ዕቃዎች እና አልባሳት እንዲሁም ክስ የቀረበበትን ቤት ያስረክባት በማለት ወስኗል፡፡

አመልካች ይህን ውሳኔ በመቃወም ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የይግባኝ አቤቱታ ያቀረቡ ቢሆንም በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 337 መሠረት አቤቱታቸው ተሰርዟል፡፡

አመልካች ይህን ውሳኔ በመቃወም የካቲት 24 ቀን 2014 ዓ.ም የተጻፈ የሰበር አቤቱታ ያቀረቡ ሲሆን ይዘቱም፡- ተጠሪ ከዚህ ቀደም በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍድ ቤት ቦሌ ምድብ ችሎት በመ.ቁ 100305 በቤቱ ጉዳይ ክስ መስርተው ጉዳዩ በሽምግልና አልቋል ብለው መዝገቡን ያዘጉ በመሆኑ በድጋሚ ሊከሱ አይገባም በማለት ያቀረብኩት መቃወሚያ መታለፉ አግባብ አይደለም፤ ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤትም በስር ፍርድ ቤት መቃወሚያው አልቀረበም በማለት በራሱ አነሳሽነት ይግባኙን የዘጋው ቢሆንም መቃወሚያው በስር ፍርድ ቤት ቀርቧል፤ አመልካች ተጠሪ በውጪ አገር ትልክ የነበረውን ገንዘብ ማስቀመጡ ቤቱ የተጠሪ መሆኑን የሚያመለክት አይደለም፤ ቤቱ የተገዛው በአመልካች ስም እንጂ በተጠሪ ስም አይደለም፤ ተጠሪ ልትጠይቀኝ ከተገባ ገንዘቡን እንጂ ቤቱን አይደለም፤ ስለሆነም ይህ ታልፎ በስር ፍርድ ቤት የተሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስሕተት የተፈጸመበት በመሆኑ በሰበር ታይቶ ሊታረም ይገባል የሚል ነው፡፡

የሰበር አጣሪው ችሎት የአመልካችን የሰበር አቤቱታ መርምሮ አመልካች ጉዳዩ በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ.ቁ 100305 በስምምነት ተቋጭቶ ያለቀና የተዘጋ ነው በማለት ያቀረቡት የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ የታለፈበትን አግባብነት ለመመርመር የሚል ማስቀረቢያ ጭብጥ በመያዝ ተጠሪ መልስ እንዲሰጡበት ተደርጎ ጉዳዩ ለዚህ ችሎት ቀርቧል፡፡

ተጠሪ ሚያዝያ 25 ቀን 2014 ዓ.ም የሰጡት መልስ ይዘት በአጭሩ፡- ጉዳዩ በድጋሚ ሊታይ አይገባውም ነበር የሚለው መቃወሚያ እንደ አዲስ ማቅረብ የሥነ ሥርዓት ሕጉ አይፈቅድም፤ ማንሳት በነበረባቸው ጊዜ ባለማቅረባቸው ምክንያት የስር ፍርድ ቤት ይህን መቃወሚያ እንደ መጀመሪያ ደረጃ

መቃወሚያ ባለመቁጠር አልፎ ውሳኔ መስጠቱ ተገቢ ነው፤ ከዚህ በፊት የተከፈተው ፋይል ሊዘጋ የቻለው አመልካች እና በሀይማኖታችን ትልቅ ቦታ የምሰጣቸው የሀይማኖት አባቶች መዝገቡን ካላዘጋሽ እንረግምሻለን ብለው ጫና ስለፈጠሩብኝ መሆኑን ገልጫለሁ፤ ስለሆነም በስር ፍርድ ቤት የተሰጠው ውሳኔ ሊጸና ይገባል የሚል ነው፡፡ አመልካችም የሰበር አቤቱታቸውን በማጠናከር የመልስ መልስ ሰጥተዋል፡፡

የግራ ቀኙ ክርክር እና በየደረጃው ባሉ ፍርድ ቤቶች የተሰጠው ውሳኔ በአጭሩ ከላይ የተገለጸው ነው፡፡ ይህ ችሎትም በሰበር አጣሪው ችሎት ሊጣራ ይገባዋል ተብሎ የተያዘውን ነጥብ ከግራ ቀኙ ክርክር፤ ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸው ሕጎች ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለው መርምሮታል፡፡

ከክርክሩ ሒደት መገንዘብ የተቻለው አመልካች ለቀረበባቸው ክስ መልስ ሲሰጡ ተጠሪ በማስረጃነት ያቀረቡት የባለቤትነት ማስረጃ ሐሰተኛ ነው፤ ክስ ለማቅረብ የሚያስችል መብት እና ጥቅም የላቸውም በማለት የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ያቀረቡ መሆኑን እና በፍሬ ነገሩ ላይ በሰጡት መልስ ደግሞ ቤቱን አስመልክቶ ከዚህ ቀደም በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ቦሌ ምድብ ችሎት በመ.ቁ 100305 ክስ አቅርባ በእርቅ በስምምነት የተዘጋ መሆኑን እና ሌሎችንም መከራከሪያ ሐሳቦች በማቅረብ የተከራከሩ መሆኑን ነው፡፡ ይህም አመልካች በመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያው ላይ ባይገልጹትም በፍሬ ነገር ክርክራቸው ላይ ጉዳዩ ከዚህ በፊት በፍርድ ቤት ታይቶ እልባት ያገኘ መሆኑን በመግለጽ መከራከራቸውን የሚያሳይ ነው፡፡

በመሠረቱ ማስረጃ ተቀብሎ ከመመርመሩ ወይም ምስክሮችን ከመስማቱ አስቀድሞ ፍርድ ቤቱ በመጀመሪያ ደረጃ ለቀረበለት እና ማናቸውም ተከራካሪ ወገን ላቀረበው መቃወሚያ ውሳኔ መስጠት ያለበት ስለመሆኑ፤ የነገርን ጭብጥ መያዝ የሚቻለውም የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ እንዳለ ከተወሰነ በኋላ ስለመሆኑ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 244/1 እና 246/1 ድንጋጌዎች ላይ በግልጽ ተመልክቷል፡፡

በያዝነው ጉዳይ የሥር ከፍተኛው ፍርድ ቤት አመልካች ተጠሪዋ ክስ ለማቅረብ የሚያስችል መብት ወይም ጥቅም የላቸውም በማለት ያቀረቡትን የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ መርምሮ ሕዳር 17 ቀን 2013 ዓ.ም በሰጠው ብይን ውድቅ ያደረገው ቢሆንም አመልካች ተጠሪ ቤቱን አስመልክቶ ከዚህ ቀደም በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ቦሌ ምድብ ችሎት በመ.ቁ 100305 ክስ አቅርባብኝ በእርቅ ተስማምተን ተዘግቷል በማለት ያቀረቡትን ክርክር በዝምታ አልፎታል፡፡ አመልካች ቤቱን በሚመለከት ከዚህ በፊት ተጠሪ ክስ አቅርባብኝ በስምምነት ተዘግቷል በማለት ያቀረቡትን ክርክር በመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያው ላይ ባይገልጹትም በፍሬ ነገር ክርክራቸው ላይ ቤቱን አስመልክቶ ከዚህ ቀደም በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ቦሌ ምድብ ችሎት በመ.ቁ 100305 ተጠሪዋ ክስ አቅርባ በእርቅ በስምምነት ተዘግቷል በማለት በግልጽ እስከተከራከሩ ጊዜ ድረስ ይህ ክርክራቸው እንደ መጀመሪያ ደረጃ

መቃወሚያ ተቆጥሮ በቅድሚያ አልባት ሊሰጠው የሚገባ ነው፡፡ ስለሆነም ጉዳዩ የቀረበለት የስር ከፍተኛው ፍርድ ቤት ይህን ሳያደርግ ቤቱን አስመልክቶ በዋናው ጉዳይ ላይ የሰጠው ውሳኔ ከላይ የተመለከቱትን የፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ሕጉን ድንጋጌዎች ያላገናዘበ እና መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስሕተት የተፈጸመበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በዚህም ምክንያት ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

ውሳኔ

1. የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ.ቁ 241972 ነሐሴ 12 ቀን 2014 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ፤ ይህንኑ ውሳኔ በማጽናት የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ.ቁ 215793 የካቲት 15 ቀን 2014 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 348/1 መሠረት ተሻሽሏል፡፡
2. ከላይ በፍርድ ሐተታው ላይ በተገለጸው ምክንያት የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ.ቁ 241972 ነሐሴ 12 ቀን 2014 ዓ.ም ቤቱን አስመልክቶ የሰጠው የውሳኔ ክፍል፤ ይህንኑ ውሳኔ በማጽናት የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ.ቁ 215793 የካቲት 15 ቀን 2014 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ ተሽሯል፡፡ ከዚህ ውጪ ያለው የውሳኔ ክፍል አልተነካም፡፡
3. የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በውሳኔ የዘጋውን መዝገብ በማንቀሳቀስ ቤቱን አስመልክቶ ከዚህ ቀደም በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ቦሌ ምድብ ችሎት በመ.ቁ 100305 ተጠሪዋ ክስ አቅርባ በእርቅ በስምምነት ተዘግቷል በማለት በፍሬ ነገር ክርክሩ ላይ የሰጡት መልስ የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ይዘት ያለው መሆኑን ተረድቶ በቅድሚያ በዚሁ ነጥብ ላይ ተገቢውን ብይን እንዲሰጥበት፤ የሚሰጠው ብይን ክርክሩን የማያስቆም ከሆነ በፍሬ ነገሩ ላይ ተገቢውን ውሳኔ እንዲሰጥበት በማለት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 341/1 መሠረት ጉዳዩን መልሰንለታል፡፡
4. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪ ግራ ቀኙ የየራሣቸውን ይቻሉ፡፡
5. መጋቢት 29 ቀን 2014 ዓ.ም በመዝገቡ የተሰጠው የዕግድ ትዕዛዝ ተነስቷል፡፡ ይጻፍ

ትዕዛዝ

- የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የመ.ቁ 241972 የሆነው መዝገብ ወደመጣበት ይመለስ፡፡
- መዝገቡ ውሳኔ ስላገኘ ተዘግቷል፡፡ ይመለስ

አ/መ

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

የሰበር መዝገብ ቁጥር 246384

መጋቢት 25 **ቀን** 2016 **ዓ.ም**

ዳኞች፡- እትመት አሠፋ

ደጀኔ አያንሳ

ኑረዲን ከድር

መላኩ ካሳዬ

ሀብታሙ እርቅይሁን

አመልካች፡- አቶ ተባረክ ዘሩ - ቀርቧል

ተጠሪ፡- ወ/ሮ ጨዋነሽ በርቱ - አልቀረቡም

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍርድ

ጉዳዩ የባልና ሚስት ንብረት ክርክር የሚመለከት ሆኖ ክሱ በቀረበበት የኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት በፊንፊኔ ዙርያ ኦሮሚያ ልዩ ዞን ቡራዩ ከተማ ወረዳ ፍርድ ቤት አመልካች ተከሳሽ፣ ተጠሪ ደግሞ በከሳሽነት ተከራክረዋል፡፡ የክርክሩ አመጣጥ በአጭሩ፡- አመልካች የፍቺ ውሳኔን ተከትሎ ባቀረቡት የንብረት ዝርዝር ቡራዩ ከተማ አስተዳደር በመልካ ገፈርሳ ቀበሌ ውስጥ የሚገኝ በ90 ካ.ሜ ቦታ ላይ ያረፈ በግራ ቀኙ የተፈራ አዋሳኞቹ በክሱ ላይ የተመለከተው 650,000.00(ስድስት መቶ ሃምሳ ሺህ) ብር የሚያወጣ መኖሪያ ቤት ተሸጦ ግማሽ ደርሻቸው እንዲወሰንላቸው ጠይቀዋል፡፡

ተጠሪ በበኩላቸው ባቀረቡት መልስ ለክርክሩ መነሻ የሆነው መኖሪያ ቤት የባልና ሚስት ንብረት ሳይሆን የእህታቸው የወ/ሮ አመለወርቅ በርቱ መሆኑን ፣ ንብረቱ የግራ ቀኙ የጋራ ለመሆኑ የቀረበ ማስረጃ አለመኖሩን ፣ ጥር 2 ቀን 2014 ዓ.ም በተደረገ የሽያጭ ውል አቶ ፈቃዱ በረዳ ከሚባል ሰው 430,000.00(አራት መቶ ሰላሳ ሺህ) ብር መግዛቱ ፣ አመልካች አከራካሪውን ቤት ለመግዛት የሚያስችል አቅም የሌለው በመሆኑ ፍርድ ቤቱ ቤቱ የባልና ሚስት የጋራ ንብረት አለመሆኑን ተረድቶ የአመልካችን አቤቱታ ውድቅ እንዲያደርግ ጠይቀዋል፡፡ ክርክሩ በተሰማበት ወቅት ለክርክሩ መነሻ የሆነው መኖሪያ ቤት በተጠሪ ስም መግዛቱንና በስማቸው መመዝገቡን ፣ በተጠሪ በኩል የቀረበው ማስረጃ የውሸት የመንደር ውል መሆኑን፣ ትክክለኛው ቤቱ የተገዛበት ውል አቶ ፈቃዱ በረዳ እጅ ስለሚገኝ ማቅረብ እንደሚቻል ተከራክረዋል፡፡ ተጠሪ በበኩላቸው ለክርክሩ

ምክንያት የሆነው ቤት እህታቸው ወ/ሮ አመለወርቅ በርቱ ከውጪ በላኩት ገንዘብ መገዛቱን፣ በእህታቸው ፈቃድ በቤቱ ውስጥ የሚኖሩ በመሆኑ በቤቱ ላይ መብት እንደሌላቸው ተከራካረዋል፡፡

ፍርድ ቤቱም የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኋላ አከራካሪው ቤት የግራ ቀኙ የጋራ ንብረት ነው ወይስ በተጠሪ እህት ስም የተገዛ ነው? የሚል ጭብጥ ይዞ የተከራካሪዎችን ማስረጃ ሰምቶ መዝገቡን እንደመረመረው በአመልካች በኩል የቀረቡት ሶስት ምስክሮች ግራ ቀኙ በአከራካሪው ቤት ውስጥ መኖራቸውን እንጂ ቤቱ የማን እንደሆነ አናውቅም ያሉ ሲሆን የቤቱ ሻጭ የሆኑት አንደኛው ምስክር ግን ቤቱን የሸጡት ለተጠሪ መሆኑን ፣ ውሉም በተጠሪ ስም መፃፉን ፣ ውልንም ለተጠሪ የሰጡ መሆኑን ገልፀዋል፡፡ በተጠሪ በኩል የቀረቡት ምስክሮች ቤቱ የተገዛው ለተጠሪ እህት ወ/ሮ አመለወርቅ በርቱ ተብሎ መሆኑን አስረደተዋል፡፡ አመልካች ቤቱ የተገዛው በተጠሪ ስም መሆኑን ገልፆ የተከራከረ ቢሆንም ጥር 2 ቀን 2014 ዓ.ም በተፃፈው የሽያጭ ውል የውል ተቀባይ አቶ ዓለሙ በርቱ መሆኑን የሚያመልክት ሲሆን አመልካች ቤቱ በተጠሪ ስም መገዛቱን የሚያመለክት ማስረጃ ማቅረብ አልቻለም፡፡ ተጠሪ አከራካሪው ቤት የተገዛበት ገንዘብ ከአቶ ገታሜ ኢንጋኒ ወደ እሷ አካውንት የተላለፈ መሆኑን ገልፃ የተከራከረች ሲሆን የሽያጭ ውሉ በተደረገበት ጥር 2 ቀን 2014 ዓ.ም 400,000.00(አራት መቶ ሺህ) ብር ከአቶ ገታሜ ኢንጋኒ ወደ ተጠሪ አካውንት መተላለፉን የሚያመለክት ማስረጃ ቀርቧል፡፡ አመልካች አከራካሪው ቤት በተጠሪ ስም መገዛቱን እንጂ እንዴት እንደተገዛ ማስረዳት ያልቻለ ሲሆን በአንፃሩ ተጠሪ ቤቱ የተገዛበት ገንዘብ በምን አግባብ ወደ አካውንቷ እንደተላለፈ አስረድታለች፡፡ አከራካሪውን ቤት ባልና ሚስት ያፈሩ መሆኑን የሚያረጋግጥ ማስረጃ አልቀረበም፡፡ በቡራዩ ከተማ አስተዳደር መልካ ገፈርሳ ቀበሌ በ90 ካሬ ሜትር ቦታ ላይ ያረፈው ቤት ግራ ቀኙ በትዳር ውስጥ እያሉ በጋራ ያፈሩት ንብረት ሳይሆን የተጠሪ እህት የሆኑት ወ/ሮ አመለወርቅ በርቱ በወንድሟ አቶ ፍቃዱ በርቱ ስም ጥር 2 ቀን 2014 ዓ.ም በተደረገ የሽያጭ ስምምነት ከአቶ ፍቃዱ በረዳ የተገዛ ስለሆነ ተከራካሪዎቹ በቤቱ ላይ ምንም መብት የላቸውም በማለት በፍትሐ ብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 33(2) መሰረት አመልካች ያቀረቡትን የቤቱ ግማሽ ድርሻ ይገባኛል ጥያቄን ውድቅ አድርጓል፡፡

አመልካች በዚህ ውሳኔ ቅር ተሰኝተው ያቀረቡትን የይግባኝ አቤቱታ የፊንፊኔ ዙሪያ ኦሮሚያ ልዩ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በፍትሐ ብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 337 መሰረት መሰረዙን ተከትሎ ለሁለተኛ ጊዜ አመልካች ያቀረቡትን የይግባኝ አቤቱታ የመረመረው ይግባኝ ሰሚው የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ግራ ቀኙን አከራክሮ በሰጠው ውሳኔ ሻጩ አከራካሪውን ቤት ለተጠሪ ሽጦ ገንዘቡንም በባንክ ያስተላለፈችለት መሆኑን፣ የሽያጭ ውሉንም ለተጠሪ የሰጠ መሆኑን መስክሯል፡፡ አመልካች እና ተጠሪ ክርክር በተነሳበት ቤት ውስጥ በአንድ ላይ እንደሚኖሩ በተጠሪ ባልተካደበት እና የቀረበው የሽያጭ ውልም ቤቱ በአቶ ዓለሙ በርቱ ስም እንጂ በወ/ሮ አመለወርቅ ስም የተገዛ መሆኑን የማያመለክት ሆኖ እያለ፣ አቶ ዓለሙ በርቱ ለወ/ሮ አመለወርቅ በርቱ ቤት

መግዛት የሚያስችለው ውክልና ሳያቀርብ እንዲሁም ወ/ሮ አመለወርቅ በርቱ በፍትሐ ብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 41 መሠረት ወደ ክርክሩ ጣልቃ ገብተው ያልተከራካሩ ሲሆን አከራካሪው ቤት በተጠሪ ስም መግዛቱ እና የሽያጭ ገንዘብም በተጠሪ ስም ለመከፈሉ ማስረጃ ስለቀረበ አከራካሪው ቤት ግራ ቀኙ በትዳር ውስጥ እያለ የተፈራ መሆኑ ተረጋግጧል በሚል የቡራዩ ወረዳ ፍርድ ቤት ውሳኔን በመሻር ቤቱ የባልና ሚስቱ የጋራ ንብረት ነው በማለት እኩል እንዲካፈሉ ወስኗል፡፡

ይግባኝ ሰሚው የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሞበታል በማለት ተጠሪ ባቀረቡት የሰበር ቅሬታ ጉዳዩን የተመለከተው የኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚው ችሎት የሰበር አቤቱታው ያስቀርባል በማለት የግራ ቀኙን ክርክር ሰምቶ በሰጠው ውሳኔ ይግባኝ ሰሚው የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ቤቱ የተገዛበት ገንዘብ ምንጭ ሳይሆን ግራ ቀኙ በቤቱ ውስጥ ይኖሩ የነበረ መሆኑና ቤቱ የተገዛው በሌላ ሰው ስም ቢሆንም ቤቱን ለመግዛት የሚያስችል የውክልና ማስረጃ አልቀረበም በማለት ቤቱ የጋራ ነው ሲል የደረሰበት ድምዳሜ ገንዘቡ በባለትዳሮቹ ልፋት የተገኘ ነው አይደለም የሚለውን ጭብጥ ሳይመረምር ውሳኔ የሰጠ ሲሆን በተቃራኒው የቡራዩ ከተማ ወረዳ ፍርድ ቤት ገንዘቡ የ3ኛ ወገን መሆኑን ማረጋገጡን ፤ አመልካች ቤቱ የተገዛበት ገንዘብ የተገኘው ግራ ቀኙ አቶ ገታሜ እንጋኒ ጋር ስንቆጥቡ የነበረ ነው በማለት ያቀረበው ክርክር አዲስ በመሆኑ በፍትሐ ብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 329 መሰረት ተቀባይነት የሌለው መሆኑን ጠቅሶ ይግባኝ ሰሚው የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት አከራካሪው ቤት የጋራ ነው ሲል የሰጠውን ውሳኔ በመሻር የቡራዩ ከተማ ወረዳ ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሳኔ አጽንቷል፡፡

የሰበር ቅሬታው የቀረበው የቡራዩ ከተማ ወረዳ ፍርድ ቤት ውሳኔ ፤ የፊንፊኔ ዙሪያ ኦሮሚያ ልዩ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠውን ትዕዛዝ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በማጽናቱ መሠረታዊ የህግ ስህተት ተፈጽሟል በማለት በሰበር ለማስለወጥ ሆኖ የሰበር ቅሬታው በአጭሩ፡- በትዳር ውስጥ የተገዛ ቤት የኔ ነው ባይ 3ኛ ወገን ቀርቦ ባልተከራከረበት ተጠሪ አከራካሪው ቤት የ3ኛ ወገን ነው የሚል ክርክር ለማቅረብ የሚያስችል መብት ሳይኖራት ባቀረበችው ክርክር መነሻነት ለክርክሩ ምክንያት የሆነው ቤት የጋራ ንብረት አይደለም ተብሎ መወሰኑ የሰበር ሰሚ ችሎት በሰበር መዝገብ ቁጥር 33411 የሰጠውን አስገዳጅ ውሳኔን ይቃረናል፡፡ ተጠሪ የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚው ችሎት የአራካሪውን ቤት ግማሽ ባለድርሻ ናቸው በማለት የሰጠውን ውሳኔ ለመቃወም የሚያስችላቸው መብት ሳይኖራቸው ያቀረቡት አቤቱታ የፍትሐ ብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 327 እና አዋጅ ቁጥር 216/2011 አንቀጽ 27 ድንጋጌን የሚቃረን ሆኖ እያለ ይህንን በመተላለፍ የተሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ነው፡፡ የአከራካሪው ቤት ሻጭ ቀርቦ በሰጠው የምስክርነት ቃል ቤቱን የሸጠው ለተጠሪ መሆኑን፣

የቤቱ ሽያጭ ገንዘብ የተከፈለው ከአዋሽ ባንክ ወጪ ሆኖ በተጠሪ በኩል መሆኑንና የውል ሰነዱም ያለው በተጠሪ እጅ መሆኑን ያስረዳ ሲሆን ወ/ሮ አመለወርቅ በርቱ ለግሸር የዋለውን ገንዘብ ለተጠሪ መላኳ እንዲሁም አቶ አለሙ በርቱ በወ/ሮ አመለወርቅ በርቱ ስም ቤት እንዲገዛ የተወከለበት ማስረጃ ባልቀረበበት አከራካሪው ቤት የወ/ሮ አመለወርቅ በርቱ የግል ንብረት ነው ተብሎ መወሰኑ እና የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ማስረጃ የመዘዘን ስልጣን ሳይኖረው ማስረጃን መዝኖ ውሳኔ መስጠቱ መሠረታዊ ህግ ስህተት የተፈጸመበት መሆኑን ጠቅሰው የሰበር ሰሚ ችሎት ውሳኔ ተሽሮ የይግባኝ ሰሚ ችሎቱ ውሳኔ እንዲፀናላቸው ጠይቀዋል፡፡

የሰበር አጣሪ ችሎቱ በአዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀጽ 28(1) እንዲሁም በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ሥነ ሥርዓት መመሪያ ቁጥር 17/2015 ቁጥር 6(1) መሠረት ለሰበር ሰሚው ችሎት የተመራው የሰበር አቤቱታ በሰበር ሰሚ ችሎቱ ተመርምሮ የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚው ችሎት ለክርክሩ መነሻ ምክንያት የሆነው የ3ኛ ወገን(የተጠሪ እህት) ሳይሆን የግራ ቀኙ የጋራ ንብረት ነው በማለት የሰጠው ውሳኔ የተጠሪን መብት ሊነካ የሚችልበት ሁኔታ በሌለበት ተጠሪ ቤቱ የ3ኛ ወገን ነው ተብሎ ሊወሰን ይገባል በማለት ያቀረቡት የሰበር አቤቱታ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚው ችሎት ተቀብሎ መወሰኑ ሥነ ሥርዓታዊ መሆን አለመሆኑ ለማጣራት ያስቀርባል በማለት ተጠሪ ለሰበር ቅሬታው በሰጡት መልስ የቡራዩ ከተማ ወረዳ ፍርድ ቤት አከራካሪውን ቤት አስመልክቶ የሰጠው ውሳኔ የፊንፊኔ ዙሪያ ኦሮሚያ ልዩ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ማጽናቱን ተከትሎ ጉዳዩን የተመለከተው የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚው ችሎት ባቀረቡት የይግባኝ አቤቱታ የሥር ፍርድ ቤቶች ውሳኔን በመሻሩ ተጠሪ ባቀረቡት የሰበር አቤቱታ የይግባኝ ሰሚው የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ውሳኔ መሻሩ የሥነ ሥርዓት ሕጉን የተከተለ ነው ከሚባል በቀር የሚነቀፍ አይደለም፡፡ አመልካችና ተጠሪ ለክርክር መነሻ የሆነውን ቤት ለመግዛት አቅም የሌላቸው መሆኑን ፤ ለቤቱ መግዣ የዋለው ገንዘብ ተጠሪ ወደ ሻጭ የሂሳብ ቁጥር ያስተላለፍኩት ወንድሜ አቶ ዓለሙ በርቱ የአዋሽ ባንክ አካውንት ስላልነበረው መሆኑን ፤ ከእህቱ ወ/ሮ አመለወርቅ በርቱ የተላከው ገንዘብ በተጠሪ አካውንት ገብቶ ለሻጭ መተላለፉ በተጠሪ ምስክሮች መረጋገጡን ፤ ወ/ሮ አመለወርቅ በርቱ ግራ ቀኙ በአከራካሪው ቤት ውስጥ እንዲኖሩ በመፍቀዷ ምክንያት አመልካች እንደጋራ ንብረት መጠየቁ ያልተገባ ብልጽግና ለማግኘት መሆኑን፤ የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ውሳኔ በቀጥታ የተጠሪ መብት የሚነካ ባይሆንም የባልና ሚስት ንብረት አይደለም በማለት ተጠሪ ያቀረብኩት ክርክር ተቀባይነት ማግኘቱ ሥነ ሥርዓታዊ አይደለም ቢባል እንኳን የሥር ፍርድ ቤቶች ወ/ሮ አመለወርቅ በርቱን የክርክሩ ተካፋይ ማድረግ የነበረባቸው ቢሆንም የተጋቢዎች ያልሆነውን ቤት የጋራ ንብረት አይደለም ብሎ መወሰናቸው የሚነቀፍ አለመሆኑን ፤ ቤቱ የባልና ሚስት የጋራ ነው ተብሎ ቢወሰን ተጠሪ ከሌላ ሶስተኛ ወገን ለወሰድኩት ንብረት ተጠያቂ መሆናቸውን በመግልጽ የቡራዩ ከተማ

ወረዳ ፍርድ ቤት ውሳኔ እንዲጸና ፣ ውሳኔው ሥነ ሥርዓታዊ አይደለም የሚባል ከሆነም መዝገቡ ወደ ሥር ፍርድ ቤት ተመልሶ ለክርክሩ 3ኛ ወገን የሆኑት እህታቸው ወ/ሮ አመለወርቅ በርቱ ወደ ክርክሩ ጣልቃ ገብተው ጉዳዩ በአዲስ መልክ ታይቶ ውሳኔ እንዲያገኝ ጠይቀዋል፡፡ አመልካችም የሰበር አቤቱታቸውን በማጠናከር የመልስ መልስ አቅርበዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ እና መሰረታዊ የክርክሩ ይዘት በአሮጡ ከላይ የተመለከተውን ሲመስል ችሎቱም በሰበር ችሎቱ ሊጣራ ይገባዋል ተብሎ የተያዘውን ነጥብ ከግራ ቀኙ ክርክር፤ ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸው ሕጎች ጋር በማገናዘብ መርምሯል፡፡

በፍትሐ ብሔር ሥና ሥርዓት ሕጉ ቁጥር 39 ድንጋጌ መሠረት በክሱ ውስጥ መጣመር የሚገባው ሰው አለመጣመር ወይንም መከሰስ የማይገባውን ሰው በማጣማር የቀረበ ክስ ውድቅ የማያደረገው ሲሆን ፣ በክሱ ውስጥ ተሳታፊ መሆን የሚገባቸዉ ወገኖች መቅረትን በሚመለከት ወይንም ተካፋይ መሆን የሚገባቸው ወገኖች ተሳታፊ ሆኖ ሲገኙ ክርክሩ ከመጀመሩ በፊት ተቃውም መቅረብ ያለበት መሆኑን ይደነግጋል። ከባለ ጉዳዮቹ የሚቀርብ ክርክርን መሠረት በማድረግ ፍርድ ቤት በራሱ ተነሳሽነት ለውሳኔ አሰጣጥ አስፈላጊ የሆነን ሰው አባሪ ሆኖ በክርክሩ እንዲገባ ማድረግ እንደሚችል የፍትሐ ብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 40(2) ይደነግጋል። በፍርድ ቤት ትዕዛዝ የክርክር ተካፋይ የሚሆኑ ሰዎች ለክርክሩ የግድ አስፈላጊ የሆኑ (indispensable party) ባልተሳተፉበት ክርክር መብት እና ጥቅማቸው ወይንም ግዴታቸውን የሚነካ ተካፋይ ባልሆኑበት ክርክር የሚሰጠው ፍርድ ወይንም ውሳኔ ውጤት የማይኖረው ሰዎች ሲሆኑ ነው። በክሱ በተከሳሽነት ተካፋይ መሆን የሚገባውን ከሳሽ ያላጣመረው ቢሆንም ለቀረበዉ ክስ የመከላከያ መልስ እንዲሰጥበት በፍርድ ቤት ሊታዘዝ የሚገባ መሆኑ የፍትሐ ብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 39(1) እና 40(2) ድንጋጌ ያስገነዝበናል።

ባለሀብትነት በሕግ ወይንም ባለጉዳዮች በሚያደርጓቸው ሕጋዊያን ተግባሮች የሚተላለፍ ሲሆን የማይንቀሳቀሱ ንብረቶች ባለሀብትነት ሲተላለፍ በማይንቀሳቀስ ንብረት መዝገብ ማስመዝገብ አስፈላጊ መሆኑን የፍትሐብሔር ሕጉ ቁጥር 1184 እና 1185 ያስገነዝበናል። በዚህ መልክ ሀብትነቱ ለሌላ ሰው ሲተላለፍ ሀብትነት ቀሪ እንደሚሆን ከፍትሐ ብሔር ሕጉ ቁጥር 1189 ድንጋጌ መረዳት ይቻላል። የባለሀብትነት ምስክር ወረቀት የሚሰጠው በፍ/ሕ/ሕግ ቁጥር 1553-1636 ድንጋጌዎች መሠረት ነው።

በተያዘው ጉዳይ ቡራዩ ከተማ አስተዳደር በመልካ ገፈርሳ ቀበሌ ውስጥ የሚገኝ በ90 ካ.ሜ ቦታ ላይ ያረፈው ቤት በስማቸው ተገዝቷል በማለት የቀረበው ሰነድ የመንደር ውል በመሆኑ የተጠሪ እህት የሆኑት ወ/ሮ አመለወርቅ በርቱ በክርክሩ በግድ መሳታፍ የሚገባቸውን (indispensable

party) ስላልሆኑ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 39(1) እና 40(2) መሠረት ወደ ክርክሩ መግባት የሚገባቸው አይደሉም።

አመልካች እና ተጠሪ ክርክር በተነሳበት ቤት ውስጥ በአንድ ላይ የሚኖሩ መሆኑ በተጠሪ አለመካዱ ፤ የቀረበው የሽያጭ ውልም ቤቱ በአቶ ዓለሙ በርቱ ስም እንጂ በወ/ሮ አመለወርቅ ስም መገዛቱን የማያመለክት መሆኑን ፤ አቶ ዓለሙ በርቱ ለወ/ሮ አመለወርቅ በርቱ ቤት መግዛት የሚያስችል ውክልና አለመቅረቡ ፤ አከራካሪው ቤት በተጠሪ ስም መገዛቱ እና የሽያጭ ገንዘብም በተጠሪ ስም መከፈሉንና የቤት ሽያጭ ውሉም ለተጠሪ መስጠቱን የቤቱ ሻጭ የሆኑት ግልሰብ በሰጡት የምስክርነት ቃል መረጋገጡን መሠረት አድርጎ ይግባኝ ሰሚው የኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሳኔ የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ማስረጃ የመዘዘን ስልጣን ሳይኖረው ማስረጃን መዝኖ ይግባኝ ሰሚው ችሎት የሰጠውን ውሳኔ መሻሩ በሰበር መዝገብ ቁጥር 41526(በቅጽ 9 እንደታተመው) የተሰጠውን አስገዳጅ ውሳኔን እንዲሁም የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ- መንግስት አንቀጽ 80(3/ለ) እና የኦሮሚያ ክልል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 216/2011 አንቀጽ 25(2/ረ) እና አንቀጽ 26/2 ድንጋጌዎችን የሚቃረን መሠረታዊ ህግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ቀጣዩ ተወስኗል።

ዉሳኔ

1. የኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚው ችሎት መዝገብ ቁጥር 421866 ሚያዝያ 17 ቀን 2015 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጠው ውሳኔ እና ትዕዛዝ ፤ በፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ሥነ - ሥርዓት መመሪያ ቁጥር 17/2015 ቁጥር 9(1/ለ) መሠረት **ተሽሯል**።

2. ይግባኝ ሰሚው የኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት መዝገብ ቁጥር 411341 ጥር 23 ቀን 2015 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጠው ውሳኔ እና ትዕዛዝ ፤ በፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ሥነ - ሥርዓት መመሪያ ቁጥር 17/2015 ቁጥር 9(1/ሀ) መሠረት **ፀንቷል**።

3. በዚህ ችሎት የተደረገዉ ክርክር ያስከተለውን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የራሳቸውን ይቻሉ ብለናል።

4. ውሳኔው ሚያዝያ 9 ቀን 2016 ዓ.ም በችሎት ተነቧል።

መዝገቡ ውሳኔ አግኝቶ ስለተዘጋ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ።

ፍ/ደ የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

የሠ/መ/ቁጥር 249817

መጋቢት 25 ቀን 2016 ዓ/ም

ዳኞች፡- ብርሃኑ አመነው

በዕዉቀት በላይ

ቀነዓ ቂጣታ

ብርሃኑ መንግሥቱ

ማርታ ተካ

አመልካች፡- ወ/ሮ ላዋይ መሃሪ - አልቀረቡም

ተጠሪ፡- አቶ ባወቀ አምባዉ - አልቀረቡም

መዝገቡ ለዛሬ የተቀጠረዉ መርምሮ ተገቢዉን ትእዛዝ ለመስጠት በመሆኑ ተመርምሮ ተከታዩ ዉሳኔ ተሰጥቷል፡፡

ዉሳኔ

ተጠሪ በአመልካች ላይ በአማራ ክልል በምዕራብ ጎጃም ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ክስ የመሰረቱት በመካከላችን የነበረዉ የሽያጭ ዉል በፍርድ ቤት እንዲፈርስ ስለተወሰነ አመልካች በሽያጭ ዉሉ የተቀበሉት ነዉ ያሉትን ብር 112,500.00 እና በይዞታዉ ላይ ያፈሩት ንብረት ግምት ነዉ ያሉትን ጨምሮ በድምሩ ብር 3,017,500.00 አመልካች እንዲከፍሉ እንዲወሰንላቸዉ ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡

አመልካች ክስ የቀረበበት ጉዳይ አስቀድሞ በዋድ አዲስዓለም ንዑስ ወረዳ ፍርድ ቤት በተደረገ ክርክር በመ/ቁጥር 01455 ላይ በተሰጠ የመጨረሻ ዉሳኔ እልባት ባገኘ ጉዳይ ላይ ለሁለተኛ ጊዜ የቀረበ ክስ ስለሆነ ዉድቅ ይደረግልኝ የሚል እና ሌሎች መከራከሪያዎችን በማቅረብ ተከራክረዋል፡፡

ፍርድ ቤቱም ግራ ቀኙን በመ/ቁጥር 82160 ላይ በማከራከር እንዲሁም አስቀድሞ በግራ ቀኙ መካከል ክርክር ተደርጎበት የነበረዉን መዝገብ አስቀርቦ በመመርመር ተጠሪ ክስ የመሰረቱት አስቀድሞ በመ/ቁጥር 01455 ላይ ክርክር ተደርጎ ዉሳኔ የተሰጠበትን ቤትና አትክልት በተመለከተ በመሆኑ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 244(2/ለ) እና 245/2 መሰረት ክሱ ተቀባይነት የለዉም በማለት ዉድቅ አድርጓል፡፡ተጠሪ በዉሳኔዉ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለአማራ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት አቅርበዉ ፍርድ ቤቱም ግራ ቀኙን በመ/ቁጥር 60780 ላይ አከራክሮ በሰጠዉ ዉሳኔ አስቀድሞ በግራ ቀኙ መካከል በመ/ቁጥር 01455 ላይ ክርክር ተደርጎ በተሰጠ ዉሳኔ ላይ ተጠሪ ቤቱን በማፍረስ አትክልቶቹን በመቁረጥ እንዲያነሱ ስለተወሰነ ለእነዚህ ንብረቶች ግምት እንዲከፈላቸዉ ያቀረቡት ክስ ለሁለተኛ ጊዜ የቀረበ በመሆኑ የስር ፍርድ ቤት ከዚህ አኳያ የተጠየቀዉን ዳኝነት ዉድቅ በማድረግ የሰጠዉ ብይን

የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 5/1ን የተከተለ ነዉ በማለት በማጽናት ተጠሪ በፈረሰዉ የሽያጭ ዉል መነሻ አመልካች የተቀበሉትን ገንዘብ ለማስከፈል ያቀረቡት ክስና የጠየቁት ዳኝነት ግን አስቀድሞ ዉሳኔ የተሰጠበት ባለመሆኑ የስር ፍርድ ቤት ከዚህ ዳኝነት ጥያቄ ጋር በተያያዘ የሰጠዉ ብይን ስህተት ነዉ በማለት ሽሯል፡፡ይህንን ተከትሎም የስር ከፍተኛ ፍርድ ቤት መዝገቡን አንቀሳቅሶ የሽያጩን ገንዘብ በተመለከተ ግራ ቀኙን አከራክሮና አጣርቶ ተገቢ ነዉ ያለዉን ዉሳኔ ይስጥበት በማለት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 341/1 መሰረት ጉዳዩን መልሶለታል፡፡

በመቀጠል አመልካች የሰበር አቤቱታቸዉን ለአማራ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ቢያቀርቡም ችሎቱ በመ/ቁጥር 03-125708 ላይ በቀን 06/10/2015ዓ/ም በሰጠዉ ትዕዛዝ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የስር ፍርድ ቤት ግራ ቀኙን አከራክሮ እንዲወስን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 341 መሰረት ጉዳዩን ለስር ፍርድ ቤት በመመለስ የሰጠዉ ዉሳኔ የመጨረሻ ፍርድ ባለመሆኑ በሰበር ሊታይ የሚችል አይደለም በማለት አቤቱታቸዉን ዉድቅ አድርጓል፡፡

አመልካች በቀን 27/10/2015 ዓ/ም የተጻፈ የሰበር አቤቱታ ያቀረቡት ከላይ በተመለከተዉ መሰረት በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ እና ሰበር ሰሚ ችሎቶች የተሰጠዉ ዉሳኔ እና ትእዛዝ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ነዉ ያስባላቸዉን ምክንያት በመዘርዘር ነዉ፡፡ ሰበር አጣሪ ችሎት በአመልካች የሰበር አቤቱታ ላይ የተጠቀሱትን ምክንያቶች በመቀበል የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አመልካች ያቀረቡትን መቃወሚያ በከፊል ዉድቅ በማድረግ ጉዳዩን ለስር ፍርድ ቤት በመመለስ በሰጠዉ ዉሳኔ ላይ የተፈጸመ ስህተት መኖር አለመኖሩ እንዲመረመር በሚል ጉዳዩን ለሰበር ሰሚ ችሎት አስተላልፏል፡፡

ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት ጉዳዩን በኢፌዲሪ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 80(1/ሀ) ፣ በፌዴራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀጽ 4(1/ሀ፣ለ እና ሸ)፣ 2/5 እና አንቀጽ 10(1/ሐ እና መ) እንዲሁም በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 320 ስር ከተደነገጉት መመዘኛዎች አንጻር መርምሯል፡፡በኢፌዲሪ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 80(3/ሀ) እና በፌዴራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀጽ 2(4/ሀ፣ለ እና ሸ)፣10(1/ሐ እና መ) መሰረት በክልል ጉዳይ ላይ በተሰጠ ዉሳኔ ላይ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል በሚል ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የሰበር አቤቱታ ሊቀርብ የሚችለዉ በዚሁ አዋጅ አንቀጽ 2/5 ስር እንደተመለከተዉ በጉዳዩ ላይ የመጨረሻ ዉሳኔ ከተሰጠበት ብቻ ነዉ፡፡ በኢፌዲሪ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 80(3/ለ) ስር እንደተመለከተዉ በክልል ጉዳዮች ላይ በክልሉ ፍርድ ቤቶች በተሰጠ የመጨረሻ ዉሳኔ ላይ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል በሚል የሚቀርብ አቤቱታ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ተቀብሎ በሰበር ችሎት የማየትና የማረም ሥልጣን ተሰጥቶታል፡፡

በተጨማሪም የመጨረሻ ዉሳኔ ምንነት የበለጠ ለመገንዘብ በፍትሐ ብሔር ሥነ ሥርዓት ሕጉ ቁጥር 320 ስር የተዘረጋዉን ሥነ ሥርዓታዊ ደንቦች መመልከት ያስፈልጋል፡፡ይህ ደንብ እንደአግባብነቱ

በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በወጣዉ የሰበር ሥነ ሥርዓት መመሪያ ቁጥር 17/2015 አንቀጽ 20/1 መሰረት ለሰበር ክርክርም ተፈጻሚነት አለዉ፡፡በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 320/1 መሰረት ይግባኝ ወይም የሰበር አቤቱታ ማቅረብ የሚቻለዉ በመጨረሻዉ ዉሳኔ ላይ ሲሆን አንድ ዉሳኔ የመጨረሻ ዉሳኔ ነዉ የሚባለዉ ደግሞ በዚሁ ሕግ በቁጥር 320(3 እና 4) ጣምራ ንባብ መሰረት ማንም ሰዉ እንዲታሰር ወይም በማረፊያ ቤት ተይዞ እንዲቆይ የተሰጠ ትእዛዝ ካልሆነ በስተቀር እንዲሁም ከሥረ ነገሩ ፍርድ በፊት አንድ ተከራካሪ ወገን በእጁ ያለዉን ንብረት ለሌላዉ ወገን እንዲያዘዉር የተሰጠ ዉሳኔ ካልሆነ በስተቀር በሥረ ነገሩ ላይ የመጨረሻ ፍርድ ከመሰጠቱ በፊት ጊዜያዊ አገልግሎት ባለዉ ትዕዛዝ ላይም ሆነ በሥረ ነገሩ ላይ የመጨረሻ ፍርድ ከመሰጠቱ በፊት በመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያነት በሚቀርብ መከራከሪያ ላይ በሚሰጥ ዉሳኔ ላይ ብቻ ይግባኝ ማቅረብ አይቻልም፡፡

በያዝነዉ ጉዳይ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የስር የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠዉን ዉሳኔ በከፊል በማጽናት በከፊል ደግሞ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 341/1 መሰረት ለስር ከፍተኛ ፍርድ ቤት መልሷል፡፡በዚህ መልኩ ከተሰጠዉ ዉሳኔ የጸናዉ ክፍል ለአመልካች የሚጠቅም በመሆኑ ለክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት አመልካች የሰበር አቤቱታ የሚያቀርቡበት ስርዓት የለም፡፡አመልካች ለክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት የሰበር አቤቱታ ሊያቀርቡ የሚችሉት የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 341/1 መሰረት በሰጠዉ ዉሳኔ ላይ ሲሆን በዚህ መልኩ ያቀረቡትን የሰበር አቤቱታ የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ገና የመጨረሻ ዉሳኔ ባልተሰጠበት ጉዳይ ላይ የቀረበ የሰበር አቤቱታ ነዉ በማለት ሰርዞታል፡፡ለዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት አመልካች የሰበር አቤቱታ ያቀረቡትም የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት በዚህ መልኩ በሰጠዉ ትእዛዝ ላይ ጭምር ነዉ፡፡

የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎትም ሆነ ሰበር ሰሚ ችሎት የሰጡት ዉሳኔ እና ትእዛዝ አመልካች ክስ የቀረበበትን ገንዘብ ለተጠሪ ሊከፍሉ ይገባል በማለት የመጨረሻ ዉሳኔ የሰጡበት አይደለም፡፡ ዉሳኔዉ ከዉጤት አንጻር ሲታይ አመልካች ያቀረቡት የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ዉድቅ ተደርጎ የተወሰነበት ነዉ፡፡ ጉዳዩ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 341/1 መሰረት ከተመለሰ በኋላ የመጨረሻ ዉሳኔ ሲያገኝ አመልካች በመጨረሻዉ ዉሳኔ ካልተስማሙ አቅርበዉ የነበረዉ የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ዉድቅ መደረጉን በተመለከተ ጭምር በሥነ ሥርዓት ሕጉ እና አግባብ ባለዉ ሌላ ሕግ መሰረት ይግባኝና የሰበር አቤቱታ ማቅረብ የሚችሉበት መብት አላቸዉ፡፡ በተገለጸዉ መሰረት በጉዳዩ ላይ በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎትም ሆነ በይግባኝ ሰሚዉ ችሎት በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 80(3/ለ) ፣ በአዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀጽ 2/5 እንዲሁም በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 320/3 ስር በተደነገገዉ መሰረት የመጨረሻ ዉሳኔ ስላልተሰጠ በዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት ታይቶ ሊመረመር የሚችል የመጨረሻ ዉሳኔ የለም፡፡ በመሆኑም የአመልካች የሰበር አቤቱታ በሰበር ችሎቱ ለመታየት ብቁ ስላልሆነ ተጠሪን መጥራት ሳያስፈልግ ተሰርሏል፡፡ በዚህ መዝገብ ላይ የተሰጠዉ የዕግድ ትእዛዝ ተነስቷል፡፡ይጻፍ፡፡መዝገቡ ተዘግቷል፤ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የሰ/መ/ቁጥር 225462

ጥቅምት 29 ቀን 2015 ዓ/ም

ዳኞች፡- ብርሀኑ አመነው

ተሾመ ሽፈራው

ሀብታሙ እርቅይሁን

ብርሀኑ መንግስቱ

ነፃነት ተገኝ

አመልካቾች፡- 1ኛ. የክርስቶስ አካል ቤተክርስቲያን - መጋቢ ተስፋልደት ሲሳይ - ቀርበዋል

2ኛ. መጋቢ ተስፋልደት ሲሳይ - ቀርበዋል

ተጠሪ፡- ወ/ሮ አልማዝ ባዩ - ጠበቃ መኮንን ይማም - ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍርድ

ጉዳዩ በቤት ኪራይ ውል መነሻ ያልተከፈለ የኪራይ ገንዘብ ለማስከፈል እና ቤት ለመረከብ የቀረበ ክርክርን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ በተጀመረበት በፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት አመልካቾች ተከሳሾች ተጠሪ ደግሞ ከሳሽ በመሆን ተከራክረዋል፡፡

ተጠሪ በህዳር 04 ቀን 2013 ዓ.ም ጽፈው ባቀረቡት ክስ በንፋስ ስልክ ላፍቶ ክፍለ ከተማ ወረዳ 03 የቤት ቁጥር 479 ሙሉ ጊቢውን በቆርቆሮ ብቻ ከተሰራ መለስተኛ አዳራሽ፤ አንድ ክፍል ቆርቆሮ ቤት እና በቆርቆሮ የተሰራ የጥበቃ ቤት አመልካቾች በወር ብር 12,000 በመክፈል ከጥቅምት 25 ቀን 2011 ዓ.ም እስከ ነሐሴ 25 ቀን 2012 ዓ.ም ድረስ ለመጠቀም ተስማምተው የኪራይ ውል አድርገናል፡፡ ነገር ግን አመልካቾች ከሚያዝያ 25 ቀን 2012 ዓ.ም ጀምሮ የኪራይ ገንዘብ በከፊል ያልከፈሉ ሲሆን ከሐምሌ እስከ ነሐሴ 2012 ዓ.ም ያለውን ደግሞ ሙሉ የኪራይ ገንዘብ አልከፈሉም፡፡ በመሆኑም አመልካቾች የሚቀርባቸውን ውዝፍ የኪራይ ገንዘብ በድምሩ 64,000 ከፍለው ቤቱን እንዲያስረክቡ እና እስኪያስረክቡ ላለው ጊዜ በወር 12,000 ብር የኪራይ ገንዘብ እንዲከፍሉ ይወሰንልኝ በማለት ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡

አመልካቾች በየካቲት 03 ቀን 2012 ዓ.ም ጽፈው ባቀረቡት መልስ የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ አቅርበው ውድቅ የተደረገ ሲሆን ፍሬ ነገሩን በተመለከተ ከተጠሪ ጋር የኪራይ ውል ብንፈጽምም ቤቱ ከነሙሉ ይዞታው በተጠሪ እጅ ነው የሚገኘው፡፡ አመልካቾች ቤት እና ይዞታውን አልተረከብንም፡፡ የኪራይ ገንዘብ እና ቤት እንዲለቀቅለት የሚጠይቅ ወገን በመጀመሪያ የቤቱ እና የይዞታው ሕጋዊ ባለቤት መሆኑን የሚያሳይ ማስረጃ ማቅረብ ይጠበቅበታል፡፡ 1ኛ አመልካች የራሴን ቤት ኪራይ ከፍዬ የምለቅበት ምክንያት የለም፡፡ በመሆኑም ክሱ ውድቅ ይደረግልን በማለት ተከራክረዋል፡፡

ጉዳዩን በመጀመሪያ የተመለከተው ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ምስክሮች ከሰማ በኋላ አመልካቾች ነሐሴ 25 ቀን 2011 ዓ.ም በተፈጸመ የቤት ኪራይ ውል መነሻነት እስከተወሰነ ጊዜ የኪራይ ክፍያ እየከፈሉ የነበረ መሆኑን አልካዱም፡፡ በኪራይ ውሉ ላይም በግልጽ አመልካቾች ቤቱን መከራየታቸው ተመልክቶ እያለ እና የኪራይ ገንዘብ እየከፈሉ በቆዩበት ቤቱን አልተረከብንም በማለት የሚያቀርቡት ክርክር ተቀባይነት የለውም፡፡ በመሆኑም አመልካቾች ሳይከፍሉ የቀሩትን የኪራይ ገንዘብ ብር 56,000 ሊከፍሉ እና ቤቱን ለቀው ሊያስረክቡ ይገባል፡፡ እንዲሁም አመልካቾች ቤቱን እስኪያስረክቡ ያለውን የኪራይ ገንዘብ ተጠሪ የመጠየቅ መብታቸው የተጠበቀ ነው በማለት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡ አመልካቾች በዚህ ውሳኔ ላይ የይግባኝ ቅሬታ ለፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርበው ፍርድ ቤቱ ግራ ቀኙን ካከራከረ በኋላ በውሉ ላይ የተጠቀሰው ካርታ በተጠሪ ስም የተመዘገበ መሆኑን እና በይግባኝ ባዮች ቁጥጥር ስር የሚገኙት በቆርቆሮ የተሰሩ ቤቶች በተጠሪ ስም በተመዘገበው ካርታ ላይ በተጠቀሰው 135.5 ካሬ ሜትር ይዞታ ውስጥ እንደሚገኙ በክፍሉ አስተዳደር ተጣርቶ የቀረበ በመሆኑ አመልካቾች የኪራይ ገንዘብ ከፍለው ቤቱን ሊለቁ ይገባል በመባሉ የተፈጸመ የፍሬ ነገርም ሆነ የህግ ስህተት የለም በማለት የስር ፍርድ ቤትን ውሳኔ አጽንቷል፡፡

አመልካቾች በሚያዝያ 13 ቀን 2014 ዓ.ም የተጻፈ የሰበር ቅሬታ ያቀረቡት የስር ፍርድ ቤቶችን በውሳኔ በመቃወም ለማሳረም ሲሆን የቅሬታው ይዘት ባጭሩ 2ኛ አመልካች የ1ኛ አመልካች አገልጋይ ነኝ፡፡ 1ኛ አመልካች ደግሞ የራሷ ሕጋዊ ሰውነት ያላት የእምነት ተቋም ናት፡፡ 2ኛ አመልካች 1ኛ አመልካችን ወክዬ ባደረኩት ሕጋዊ ተግባር በግሌ በኃላፊነት ልጠየቅ አይገባም፡፡ የቤት ኪራይ ውል ያደረግን ቢሆንም ቤቱን እስከዛሬ ድረስ አልተረከብንም፡፡ 1ኛ አመልካች አሁን የሚጠቀምበት ይዞታ የተጠሪ አይደለም፡፡ አመልካቾች ከሚመለከተው አካል የይዞታ ማስረጃ ለማግኘት በሂደት ላይ ነን፡፡ በስር ፍርድ ቤቶች የይዞታ ክርክር አቅርበን ተገቢው ማጣራት ከተደረገ በኋላ የደረሰቡት ድምዳሜ ተገቢ ስላልሆነ ሊታረም ይገባል በማለት ጠይቀዋል፡፡

የአመልካቾች የሰበር ቅሬታ በሰበር አጣሪ ችሎት ተመርምሮ የከፍተኛ ፍርድ ቤት የክርክር መነሻ የሆነውን እና አመልካቾች እንዲያስረክቡ የተወሰነውን ቤትና ቦታ መጠን በካሬ ተለይቶ የተወሰነ ስለመሆን አለመሆኑ በጭብጥነት በመያዝ በአስተዳደሩ ተጣርቶ እንዲቀርብ ትእዛዝ ተሰጥቶ የወረዳው

አስተዳደርም የቦታውን ትክክለኛ ይዘት እና ስፋት ለማወቅ የሚያስችል መሳሪያ የሌላቸው መሆኑን በመጥቀስ በክፍለ ከተማው መሬት ልማትና አስተዳደር ጽህፈት ቤት በኩል ተጣርቶ እንዲቀርብ የሚል መግለጫ ሰጥተዋል፡፡ ይህንን መግለጫ ውድቅ በማድረግ ውሳኔ የተሰጠበትን እና 1ኛ አመልካችም ህጋዊ ሰውነት ያለው ሆኖ እያለ 2ኛ አመልካች ተከሳሽ ተደርጎ ውሳኔ የተሰጠበትን አግባብነት ለማጣራት ያስቀርባል በማለት ተጠሪ መልስ እንዲያቀርቡ ትእዛዝ ተሰጥቷል፡፡

ተጠሪ በሰኔ 10 ቀን 2014 ዓ.ም ጽፈው ባቀረቡት መልስ ቤቱ በተጠሪ ስም የተመዘገበ የግል ቤቱ መሆኑ በስር ፍርድ ቤት በማስረጃ የተረጋገጠ ፍሬ ነገር ነው፡፡ ለክሱ መነሻ የሆነው የኪራይ ውል በመሆኑ ውሳኔው የኪራይ ግንኙነትን የሚመለከት ብቻ መሆኑ ተገቢ ነው፡፡ በስር ፍርድ ቤቶች በማስረጃ ተጣርቶ በተሰጠ ውሳኔ የተፈጸመ መሰረታዊ የህግ ስህተት ስለሌለ ቅሬታው ውድቅ ሊደረግ ይገባል በማለት ተከራክረዋል፡፡

አመልካቾችም በሐምሌ 1 ቀን 2014 ዓ.ም የተጻፈ የመልስ መልስ በማቅረብ የሰበር ቅሬታቸውን አጠናክረዋል፡፡

የክርክሩ አመጣጥ ከላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም 2ኛ አመልካች መከሰሳቸው ተገቢ ነው ወይስ አይደለም? እና አመልካቾች የኪራይ ገንዘብ ከፍለው ለክርክሩ መሰረት የሆነውን ቤት ሊያስረክቡ ይገባል ወይስ አይገባም? የሚሉትን ነጥቦች በጭብጥነት በመያዝ የግራ ቀኙን ክርክር በስር ፍርድ ቤቶች ከተረጋገጠው ፍሬ ነገር እንዲሁም ከተገቢው የህግ ድንጋጌ ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለው መርምረናል፡፡

በመጀመሪያም 2ኛ አመልካች ከ1ኛ አመልካች ጋር በአንድነት መከሰሳቸው ተገቢ ነው ወይስ አይደለም? የሚለውን ጭብጥ ስንመለከት 2ኛ አመልካች 1ኛ አመልካችን በመወከል ባከናወንኩት ሕጋዊ ተግባር በግሌ ልከሰስ አይገባም በማለት ተከራክረዋል፡፡ ከሳሽ ከተከሳሽ ላይ የሚጠይቀውን ጥቅም ወይም መብት በማረጋገጥ አቤቱታ ካላቀረበ በቀር በማናቸውም ሰው ላይ ክስ ሊያቀርብ እንደማይችል በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 33/3 ላይ ተመልክቷል፡፡ 1ኛ አመልካች የራሷ የህግ ሰውነት ያላት የእምነት ተቋም መሆኗ በስር ፍርድ ቤቶች የተረጋገጠ ፍሬ ነገር ነው፡፡ ህጋዊ ሰውነት ያለው አካል ሕጋዊ ተግባራትን የሚያከናውነው ህጋዊ ውክልና ባለው የተፈጥሮ ሰው መሆኑ ግልጽ ነው፡፡ 2ኛ አመልካችም የ1ኛ አመልካች አገልጋይ በመሆናቸው 1ኛ አመልካችን ወክለው ህጋዊ ተግባራትን የሚያከናውኑ ስለመሆኑ አከራካሪ ፍሬ ነገር አይደለም፡፡ ለክርክሩ መሰረት የሆነውን የኪራይ ውልም ከተጠሪ ጋር 1ኛ አመልካችን ወክለው የፈጸሙት 2ኛ አመልካች ናቸው፡፡ ውክልና ማለት ደግሞ ተወካዩ በወካዩ ስም ሆኖ ህጋዊ ተግባራትን ለማከናወን የሚያስችል ስልጣን ሲሆን ተወካዩ ከውክልና ስልጣኑ ሳያልፍ የሚያከናውናቸው ተግባራት ተጠያቂነትን የሚያስከትሉ ከሆነ ተጠያቂ የሚሆነው ወካዩ ስለመሆኑ ከፍ/ሕ/ቁጥር 2199 እና ከተከታዮቹ ድንጋጌዎች መገንዘብ ይቻላል፡፡ በዚህም መሰረት 2ኛ አመልካች

1ኛ አመልካችን ወክለው ከተጠሪ ጋር ለክርክሩ መሰረት የሆነውን የኪራይ ውል ያደረጉ ቢሆንም በኪራይ ውሉ መሰረት የኪራዩ ገንዘብ ባለመከፈሉ እንዲሁም የውሉ ጊዜ ሲያበቃ ቤቱ ባለመለቀቁ ተጠያቂ ልትሆን የምትችለው 1ኛ አመልካች ናት፡፡ 2ኛ አመልካች የ1ኛ አመልካች ሕጋዊ ወኪል በመሆናቸው 1ኛ አመልካች በምትከሰስበት ጉዳይ 2ኛ አመልካችም በግል የሚከሰሱበት ህጋዊ ምክንያት የለም፡፡ በመሆኑም ጉዳዩ የተጀመረበት ፍርድ ቤት 2ኛ አመልካች ልከሰስ አይገባም የሚል መቃወሚያ ሲያቀርቡ ከላይ በተገለጸው ምክንያት በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 33/3 መሰረት 2ኛ አመልካች ሊከሰሱ አይገባም በሚል ክርክሩ ውጪ ማድረግ ሲገባው 2ኛ አመልካችንም ለክሱ ተጠያቂ ማድረጉ እንዲሁም ጉዳዩን በይግባኝ የተመለከተው ፍርድ ቤትም የስር ፍርድ ቤትን ስህተት ማረም ሲገባው ለጉዳዩ አግባብነት የሌለውን የውክልና ድንጋጌ በመጥቀስ 2ኛ አመልካችን ከ1ኛ አመልካች ጋር ለክሱ ኃላፊ ማድረጉ መሰረታዊ የህግ ስህተት በመሆኑ ሊታረም ይባል ብለናል፡፡

በመቀጠል ያልተከፈለ የኪራይ ገንዘብ እንዲከፈል እና ለክርክሩ መሰረት የሆነውን ቤት ተጠሪ ሊረከቡ ይገባል ተብሎ የመወሰኑን አግባብነት ስንመለከት ተጠሪ ያልተከፈለ የኪራይ ገንዘብ እንዲከፈል እና ለክርክሩ መሰረት የሆነው ቤት እንዲለቀቅ እንዲወሰንላቸው የጠየቁት በ1ኛ አመልካች እና በተጠሪ መካከል በነሐሴ 25 ቀን 2011 ዓ.ም በተደረገ የኪራይ ውል መሰረት አልተፈጸመልኝም በሚል ነው፡፡ 1ኛ አመልካችም ይህ ውል መደረጉን ሳትክድ በኪራይ ውል ላይ የተጠቀሰውን ቤት ከተጠሪ ስላልተረከብኩ የኪራይ ገንዘብ ልከፍል አይገባም፡፡ እንዲሁም እየተጠቀምኩ ያለሁት በራሴ ቤት ስለሆነ ለተጠሪ ላስረክብ አይገባም በማለት ተከራክራለች፡፡ በመሆኑም ለግራ ቀኙ ክርክር እልባት ለመስጠት በመጀመሪያ መጣራት ያለበት ነጥብ 1ኛ አመልካች በኪራይ ውሉ ላይ የተጠቀሱትን ቤቶች ከተጠሪ ተረክባለች ወይስ አልተረከበችም የሚለው ይሆናል፡፡ ጉዳዩ የተጀመረበት ፍርድ ቤትም የግራ ቀኙን ምስክሮች ከሰማ በኋላ 1ኛ አመልካች የኪራይ ውል ፈጽማ የኪራይ ገንዘብ እየከፈለች ከቆየች በኋላ ቤቶቹን አልተረከብኩም በማለት የምታነሳው ክርክር ተቀባይነት የለውም የሚል ድምዳሜ ላይ ደርሷል፡፡ ይግባኝ ሰሚው ከፍተኛ ፍርድ ቤት በበኩሉ 1ኛ አመልካች በኪራይ ውሉ ላይ የተጠቀሱትን ቤቶች ከተጠሪ ተረክባለች ወይስ አልተረከበችም የሚለውን ለማጣራት አሁን በ1ኛ አመልካች ይዞታ ስር የሚገኙት ቤቶች በተጠሪ ካርታ ውስጥ የሚገኙ ስለመሆን አለመሆኑ በሚመለከተው የመንግስት አካል ተጣርቶ እንዲቀርብለት ትእዛዝ ሰጥቶ በ1ኛ አመልካች ይዞታ ስር የሚገኙት ቤቶች በተጠሪ ካርታ በተጠቀሰው ይዞታ ውስጥ የሚገኙ መሆናቸው ተረጋግጦ እንደቀረበለት የውሳኔው ግልባጭ ያሳያል፡፡ ለክርክሩ መሰረት የሆነው የኪራይ ውል ቢሆንም 1ኛ አመልካች በኪራይ ውል ላይ የተጠቀሱትን ቤቶች አልተረከብኩም፤ የምጠቀመውም በተጠሪ ቤቶች አይደለም በሚል ስለተከራከረች በኪራይ ውሉ ላይ የተገለጹት ቤቶች በተጠሪ ህጋዊ ይዞታ ውስጥ የሚገኙ ስለመሆን አለመሆኑ ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ተጣርቶ እንዲቀርብ በማዘዝ እና ተጣርቶ የቀረበለትን ማስረጃ በመመዘን 1ኛ አመልካች በኪራይ

ውሉ ላይ የተጠቀሱትን ቤቶች ከተጠሪ አልተረከብኩም የምትለውን ክርክር ውድቅ በማድረግ የስር ፍርድ ቤትን ድምዳሜ ተቀብሏል፡፡

እንደሚታወቀው ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት በሕገ-መንግስቱ አንቀጽ 80/3/ሀ እና በአዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀጽ 10 የተሰጠው የዳኝነት ስልጣን መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመባቸውን የመጨረሻ ውሳኔዎች ማረም ነው፡፡ በዚህ ሥልጣኑ ተከራካሪ ወገኖች ማስረጃ ለመቀበል፣ ለመስማትና ለመመዘን ሥልጣን ለተሰጣቸዉ የስር ፍርድ ቤቶች ያቀረቡትን ማስረጃዎች የመመዘን ጉዳይ ዉስጥ በመግባት ማስረጃዎችን በመመርመርና በመመዘን አከራካሪ የሆነዉ የፍሬ ነገር ጭብጥ መኖር አለመኖሩን ለማረጋገጥ የሚያስችል ሥልጣን ሰበር ችሎቱ አልተሰጠዉም ማለት ነው፡፡ ሆኖም የማስረጃ አቀራረብን፣ አግባብነትን፣ ተቀባይነትን እና ማስረጃ አቅርቦ አንድን ፍሬ ነገር የማስረዳት ሸክም መርህ (Production, relevancy, admissibility and burden of proof of evidence)እንዲሁም የማስረጃ ምዘናን ወይም የማስረዳት ደረጃን (standard of proof or weight of evidence) የሚመለከቱ መሰረታዊ መርሆዎች ተጥሶ የተሰጠ የመጨረሻ ዉሳኔ ሲኖር መሰረታዊ የሕግ ስህተት ስለሚሆን በሰበር ሰሚ ችሎት የሚታረም ይሆናል፡፡ በተያዘው ጉዳይ 1ኛ አመልካች በኪራይ ውል ላይ የተጠቀሰውን ቤት የተረከበች መሆን አለመሆኑን ማስረጃን የመመዘን ስልጣን ያላቸው የስር ፍርድ ቤቶች የቀረቡትን ማስረጃዎች መዝነው 1ኛ አመልካች በኪራይ ውሉ ላይ የተጠቀሱትን ቤቶች ተረክባለች የሚል ድምዳሜ ላይ ደርሰዋል፡፡ የስር ፍርድ ቤቶች ለቀረቡት ማስረጃዎች ተገቢውን ዋጋ ባለመስጠት ወይም መሰረታዊ የማስረጃ ምዘና መርህ ጥሰት መፈጸማቸውን የክርክሩ ሂደት አያሳይም፡፡ በመሆኑም የስር ፍርድ ቤቶች 1ኛ አመልካች በኪራይ ውሉ መሰረት ቤቶቹን ተረክባለች በማለት የደረሱበትን የፍሬ ነገር ድምዳሜ ይህ ችሎት እንዳለ የሚቀበለው ይሆናል፡፡

1ኛ አመልካች በኪራይ ውሉ መሰረት ቤቶቹን ተረክባለች ከተባለ በኪራይ ውሉ ላይ የተጠቀሰውን የኪራይ ገንዘብ የመክፈል እና የውሉ ጊዜ ሲያልቅ አከራይ ለሆኑት ተጠሪ ቤቶቹን የማስረከብ የውል ግዴታ አለባት፡፡ በመሆኑም የስር ፍርድ ቤቶች 2ኛ አመልካችን ለክሱ ኃላፊ ማድረጋቸው ሊታረም የሚገባው ቢሆንም ከ1ኛ አመልካች አንጻር የሰጡት ውሳኔ ግራ ቀኙ ያደረጉትን የኪራይ ውል እና የቀረቡትን ማስረጃዎች መሰረት ያደረገ ነው ከሚባል በስተቀር በዚህ ችሎት ሊታረም የሚችል መሰረታዊ የህግ ስህተት ያልተፈጸመበት በመሆኑ የሚከተለውን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

ውሳኔ

1ኛ. በፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 168970 በሚያዝያ 15 ቀን 2013 ዓ.ም የሰጠው ብይን፤ በነሐሴ 14 ቀን 2013 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ እና የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት

በመዝገብ ቁጥር 277732 በመጋቢት 07 ቀን የሰጠው ውሳኔ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348/1 መሰረት ተሻሽሏል፡፡

2ኛ. 2ኛ አመልካች በግል መከሰሳቸው ተገቢ አይደለም ብለናል፡፡

3ኛ. 1ኛ አመልካች ያልተከፈለ የኪራይ ገንዘብ ከፍላ ለክርክሩ መሰረት የሆነውን ቤት እንድታስረክብ በስር ፍርድ ቤቶች የተሰጠው የውሳኔ ክፍል ጸንቷል፡፡

4ኛ. በዚህ ፍርድ ቤት የተደረገው ክርክር ያስከተለውን ወጪ እና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡

ትእዛዝ

1ኛ.በዚህ መዝገብ በሚያዝያ 19 ቀን 2014 ዓ.ም በዋለው ችሎት የተሰጠው የእግድ ትእዛዝ ተነስቷል፡፡ይጻፍ፡፡

2ኛ. የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የመዝገብ ቁጥር 277732 ተመላሽ ይደረግ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

ውል

የሰ/መ/ቁ. 217867

ጥቅምት 04 ቀን 2015 ዓ.ም

ዳኞች፡- ብርሀኑ አመነው

ተሾመ ሽፈራው

ሀብታሙ እርቅይሁን

ብርሀኑ መንግስቱ

ነፃነት ተገኝ

አመልካች- ኤቦካ ኮንስትራክሽን ኃ/የተ/የግ/ማህበር - ጠበቃ ገ/ክርስቶስ ለማ - ቀርበዋል

ተጠራ- በአ/አበባ ከተማ አስተዳደር የቁጠባ ቤቶች ልማት ኢንተርፕራይዝ ነ/ፈጅ ታሪኳ ጌታቸው - ቀርበዋል

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የግንባታ ውልን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ በተጀመረበት በፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት አመልካች በተጠሪ ላይ ባቀረበው ክስ ተጠሪ በሰንጋ ተራና ክራውን ሳይቶች ለሚያስገነባቸው የጋራ መኖሪያ ቤቶች ላይ የቆሻሻ ማስወገጃ /Garbage Chute/ ከነገጠማ ስራው ለመገንባት ከተጠሪ ጋር በቀን ሚያዝያ 10 ቀን 2008 ዓ.ም ባደረግነዉ ውል አመልካች በተጠቀሱት ሳይቶቸ ላይ ለሚገኙ 19 ህንፃዎች የቆሻሻ ማስወገጃ ሊገጥም፤ ተጠሪም ለዚሁ ስራ ለአመልካች ብር 13,690,000.60 ሊከፍል ተስማምተናል፡፡ በዚሁም መሠረት አመልካች በክራውን ሳይት በሚገኙ 12 ህንፃዎች ላይ የገጠማ ስራውን ያጠናቀቅኩ ሲሆን ተጠሪ ለዚሁ ስራ ብር 8,520,000.00 እንዲከፍለኝና የተሰራውን ስራ እንዲረከብ በተደጋጋሚ ብጠይቅም ፍቃደኛ አልሆነም፡፡ ስለሆነም ስራውን እንዲረከብና ገንዘቡን ከሚያዝያ 10 ቀን 2010 ዓ.ም ጀምሮ ከሚታሰብ ህጋዊ ወለድ ጋር እንዲከፍል ይወሰንልኝ በማለት የጠየቀዉን ዳኝነት መነሻ ያደረገ ነዉ፡፡

ተጠሪ በበኩሉ ለቀረበበት ክስ በሰጠው መልስ በውሉ አንቀጽ 4(2) ስር በተመለከተው የውሉ አካልና አባሪ በሆነው የጨረታ ሰነድ (Specification) መሠረት አመልካች የቆሻሻ ማስወገጃውን ገጥሞ ለማስረከብ ግዴታ ገብቷል፡፡ ስራውንም ሲሰራ መጠቀም ያለበት ግብዓት ብሪትሽ ስታንዳርድ ቢኤስ 1703 እና ቢኤስ 5906 ደረጃውን የጠበቀ 304 የማይዝግ /Stainless Steel/ ሆኖ ውፍረቱ 1.5 ሚሊ ሜትር መሆን እንዳለበት ቢቀመጥም አመልካች ግን ስራውን የሰራው ከውሉ ውጪ ውፍረቱ 1 ሚሊ ሜትር እና ጋልቫናይዝድ በሆነ ወጥ ላሜራ ነው፡፡ በወቅቱም አመልካች በላከው የስራ እቅድ ላይ በሰጠነው አስተያየት ስራውን ለመስራት የሚጠቀመውን ግብዓት በተመለከተ ከውላችን ውጪ በመሆኑ

እንደማንቀበለው በመግለፅ እቅዱን ውድቅ ማድረጋችንን አመልካች ለመጠቀም ካቀደው ግብዓት የምዘና ውጤት ጋር በደብዳቤም ጭምር ገልፀንለታል፤ ስለሆነም አመልካች በውላችን መሠረት ላልሰራው ስራ የአገልግሎት ክፍያ እንዲከፈለው ለመጠየቅ የሚያስችል የህግም ሆነ የውል መሠረት የለውም በማለት ተከራክሯል፡፡

ጉዳዩ የቀረበለት የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤትም የግራ ቀኙን ክርክር እና ማስረጃ ከመረመረ፣ እንዲሁም ስለጉዳዩ ተጨማሪ ማጣራት እንዳደረገ ከገለፀ በኋላ በወቅቱ ከድሣይን ዝግጅት ጋር በተያያዘ በተፈጠረ ክፍተት ምክንያት በውሉ ላይ የተመለከተውና ለቆሻሻ ማስወገጃ ገጠማ የሚውለው ግብዓት በቀላሉ በገበያ ላይ የሚገኝ ስለመሆኑ ሳይጣራ ውል የተገባ መሆኑን እና በቀን መስከረም 23 ቀን 2009 ዓ.ም በተፃፈ ደብዳቤ አመልካች ላቀረበው የግብዓት ለውጥ እቅድ (Specification) ተጠሪ መልስ አለመስጠቱ በዕቅዱ እንደተስማማ የሚያስቆጥረዉ መሆኑን፤ ስለሆነም ምንም አንኳን አመልካች በህንፃዎቹ ላይ የቆሻሻ ማስወገጃ ለመግጠም የተጠቀመው ግብዓት በውሉ ላይ የተመለከተውን የማይዝግ፣ ውፍረቱም 1.5 ሚሊ ሜትር ባይሆንም ለተጠሪ በላከዉ የግብአት ለዉጥ መሠረት ስራውን በሌላ ግብዓት ያከናወነ በመሆኑ ተጠሪ ለተሰራዉ ስራ ዋጋዉን የመክፈል ኃላፊነት አለበት፡፡ የኃላፊነት መጠኑንም አስመልክቶ አመልካች የቆሻሻ ማስወገጃውን ለመግጠም በተጠቀመው ጋልቫናይዝድ ላሜራ ብረት ዋጋ ስሌት ብር 6,739,786.00 መሆኑ የተረጋገጠ መሆኑን ጠቅሶ ይህንኑ ገንዘብ ከቀን ከሚያዝያ 10 ቀን 2010 ዓ.ም ጀምሮ ከሚታሰብ 9% ወለድ ጋር ተጠሪ ለአመልካች ይክፈል በማለት ወስኗል፡፡ ተጠሪ በዚህ ውሳኔ ባለመስማማት ይግባኙን ለፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት አቅርቦ ግራ ቀኙ ከተከራከሩበት በኋላ አመልካች ስራውን በጋልቫናይዝድ ብረት እንደሚሰራ ያሳወቀበት እቅድ የውል ድርድር ሀሳብ ማስታወቂያ አይደለም፤ የውል ድርድር ሀሳብ ማስታወቂያ ነው እንኳን ቢባል ተጠሪ አመልካች በውሉ ላይ የተጠቀሰውን ግብዓት ለውጦ የተጠቀመው ግብዓት በውሉ ላይ ከተገለፀው ግብዓት ጋር ተመሳሳይና ደረጃውን የጠበቀ ስለመሆኑ በተስማሚነት ምዘና ድርጅት አስፈትሾ ውጤቱን እንዳወቀ ህዳር 05፣ ህዳር 16 እና ጥቅምት 21 ቀን 2009 ዓ.ም በፃፋቸው ደብዳቤዎች ስራው በውሉ መሠረት ተስተካክሎ መሠራት እንዳለበት፤ ይህ ካልሆነ ግን ክፍያውን መፈፀም እንደማይችል ገልፆና በማስረጃም ጭምር አስደግፎ ተከራክሮ እያለ የስር ከፍተኛ ፍርድ ቤት ተጠሪ የአመልካችን እቅድ ባለመቃወሙ በዝምታ እንደተቀበለ ይቆጠራል ከሚል መደምደሚያ ላይ በመድረስ ስራው የተሰራው በተጠሪ ፍቃድና ይሁንታ ነው ሲል የሰጠው ውሳኔ የቀረበውን ክርክርና ማስረጃ መሠረት ያደረገ ነው ማለት አይቻልም፤ አመልካች ከውል ዉጪ ራሱ በፈቀደው የሰራውን ስራ ተጠሪ ተገዶ እንዲረከብም ሆነ ክፍያውን ለመፈፀም ሊገደድ የሚችልበት የውልም ሆነ የህግ ግዴታ የለበትም በማለት የከፍተኛ ፍርድ ቤቱን ውሳኔ ሽሮታል፡፡ ለዚህ ፍርድ መነሻ የሆነው የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡

አመልካች ታህሳስ 12 ቀን 2014 ዓ.ም ጽፎ ባቀረበው የሰበር አቤቱታ በስር ፍርድ ቤቶች ተፈጽመዋል ያላቸውን ስህተቶች በመዘርዘር በዚህ ችሎት እንዲታረሙለት ጠይቋል፡፡ የአቤቱታው ይዘትም በአጭሩ ስራው የሚሰራበትን እቃ በገበያ ላይ አለማግኘታችንን ጠቅሰን በሌላ ተመሳሳይ እቃ እንደምንሰራ ለተጠሪ ያሳወቅን ሲሆን ተጠሪ በተገቢው ጊዜ ውስጥ ምላሽ አለመስጠቱ በህግ አግባብ ጥያቄያችንን እንደተቀበለው ይቆጠራል፤ ቀድሞ የተደረገን ውልም መለወጥ እንደሚቻል በህግ በግልጽ ተደንግጓል፤ ተጠሪም በአመልካች እየተሰራ የነበረውን ስራ የራሱን ባለሞያዎች በመላክ የመስክ ላይ የስራ ጉብኝትና የጥራት ቁጥጥር ሲያደረግ ያቀረበው ተቃውሞ አልነበረም፤ የስር ከፍተኛ ፍርድ ቤትም ይህንኑ በመገንዘብ የተሰራው ስራና ዋጋ ገለልተኛ በሆነው የከተማና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር በኩል ተጣርቶ እንዲቀርብለት ካደረገ በኋላ የሰጠው ውሳኔ ተሸሮ ተጠሪ በቤቱ ላይ የተሰራውን ስራ ጨምሮ ቤቶቹን ለሚመለከታቸው አካላት አስተላልፎ እያለ ለተጠሪ ክፍያ ሊከፈለው አይገባም፤ የሰራውን ስራ ከቤቶቹ ላይ አላቆ መውሰድ ይችላል ተብሎ መወሰኑ መሠረታዊ የህግ ስህተት ስለሆነ ሊታረም ይገባዋል የሚል ነው፡፡

ጉዳዩም በሰበር አጣሪ ችሎት ተመርመሮ አመልካች ስራውን የሰራው በውሉ ላይ በተቀመጠው ስታንዳርድ መሰረት ባይሆንም የተሰራው ስራ በገለልተኛ ተቋም ባለሞያ ተረጋግጦ የቀረበውን የገንዘብ መጠን ተጠሪ ሊከፍል የሚገባ መሆን አለመሆኑን ግራ ቀኝ በተገኙበት አጣርቶ ለመወሰን ሲባል ያስቀርባል ተብሏል፡፡ በዚሁም መሠረት ተጠሪ የካቲት 21 ቀን 2014 ዓ.ም ጽፎ ባቀረበው መልስ አመልካች ስራውን በተመሳሳይ እቃ ነው የሰራሁት ቢልም በውሉ ላይ የተገለፀውና አመልካች ስራውን የሰራበት እቃ ተመሳሳይ አይደሉም፤ በተመሳሳይ እቃ ስራውን መስራቱን የሚገልጽ መከራከሪያም በስር ፍርድ ቤት አላቀረበም፤ የስር ከፍተኛ ፍርድ ቤት ለአመልካች ገንዘብ እንዲከፈለው የወሰነው አመልካች ስራውን በጋልቫናይዝድ ሜታል ለመስራት ጥያቄ ሲያቀርብ ተጠሪ በዝምታ እሺታውን ገልጿል በሚል ምክንያት ነው፤ ሆኖም ግን ፍርድ ቤቱ ተጠሪ አመልካች ያቀረበውን ጥያቄ ውድቅ ያደረገበት፣ በክርክር ሂደትም ያነሳው እና በማስረጃት ያቀረበውን ጳጉሜን 02 ቀን 2008 ዓ.ም፣ ጥቅምት 21፣ ህዳር 05 እና ህዳር 16 ቀን 2009 ዓ.ም የተፃፉ እና ሌሎች በርካታ ደብዳቤዎችን ሳይመለከትና ሳይመረምር ነው፤ አመልካች ስራውን በሌላ እቃ እንደሚሰራ በቀን 23/12/2008 ዓ.ም በተፃፈ ደብዳቤ አሳውቂያለሁ ቢልም ደብዳቤው በፍትሐብሔር ህግ ቁጥር 1684 መሠረት የቀረበ አለመሆኑን ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት አረጋግጧል፤ አመልካች ለተጠሪ የላከው ደብዳቤ የስራ እቅድ እንጂ የውል ማሻሻያ አይደለም፤ አመልካች ስራውን የሰራበት ጋልቫናይዝድ ላሜራም ጥራቱ በኢትዮጵያ የተስማሚነት ምዘና ድርጅት የተረጋገጠ አይደለም፤ የስር ከፍተኛ ፍርድ ቤትም ተጠሪ ስራው እንዲሰራለት ከተስማማበት የእቃ አይነት ውጪ ለተሰራ ስራ በገለልተኛ አካል አስገምቶ እንዲከፍል መወሰኑ ስህተት ነበር በማለት የአመልካች አቤቱታ ውድቅ እንዲደረግለት ጠይቆ ተከራክሯል፡፡ አመልካችም የሰበር አቤቱታውን በማጠናከር የመልስ መልስ ሰጥቶ ተከራክሯል፡፡

ከስር ጀምሮ የጉዳዩ አመጣጥ እና የግራ ቀኙ ክርክር ይዘት አጠር አጠር ባለ መልኩ ሲታይ ከፍ ሲል የተመለከተዉን ሲመስል ይህ ችሎትም የሰበር አቤቱታዉን ለማስቀረብ የተያዘውን ጭብጥ ከግራ ቀኝ ክርክር እና ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸዉ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ መዝገቡን እንደሚከተለዉ መርምሮታል፡፡ እንደመረመረዉም አመልካች በስር ፍርድ ቤት ባቀረበዉ ክስ ለጠየቀዉ ዳኝነት መሠረት ያደረገዉ ተጠሪ በሚያስገነባቸዉ ህንፃዎች የቆሻሻ ማስወገጃ ለመግጠም አመልካች በዉል በገባዉ ግዴታ መሠረት በክራውን ሳይት በሚገኙ 12 ህንፃዎች ላይ የገጠማ ስራውን ያጠናቀቀ ቢሆንም ተጠሪ ለዚሁ ስራ ዋጋ ብር 8,520,000.00 ለመክፈል ፍቃደኛ አለመሆኑን ሲሆን፣ ተጠሪ በበኩሉ በግራ ቀኝ መካከል ለክርክሩ መነሻ የሆነዉ ዉል መኖሩን ሳይክድ ኃላፊነት የለብኝም በማለት የሚከራከረዉ በዉሉ መሠረት አመልካች የቆሻሻ ማስወገጃ ስራዉን ለመስራት ጥቅም ላይ ሊያዉል የሚገባዉ በብሪትሽ ስታንዳርድ ቢ3 1703 እና ቢኤስኤስ 906 ደረጃዉ 304 ሆኖ ዝገት የማይነካዉ እና ዉፍረቱም 1.5 ሚ/ሜ የሆነ ብረት መሆን ሲገባዉ ከዉል ስምምነቱ ዉጪ ከፍተኛ የሆነ የዋጋ እና የጥራት ልዩነት ባለዉ ጋልቫናይዝድ ሜታል ሺት ባለ 1 ሚ/ሜ ብረት የተጠቀመ መሆኑን በመጥቀስ ስለመሆኑ ለመገንዘብ ተችሏል፡፡ አመልካች የቆሻሻ ማስወገጃ ስራዉን ለመስራት ጥቅም ላይ ያዋለዉ ብረት በዉሉ ላይ የተመለከተዉ ዓይነት አለመሆኑ በስር ከፍተኛ ፍርድ ቤት የተረጋገጠ ከመሆኑም በላይ አመልካችም ይህን ፍሬ ነገር አይክድም፡፡ አመልካች ይህን ሳይክድ ስራዉ የተሰራበትን ገንዘብ ተጠሪ የመክፈል ኃላፊነት አለበት በማለት አጥብቆ የሚከራከረዉ ተጠሪ ስራዉ በተለዋጭ ማቴሪያል እንደሚሠራ ጭምር የተሰጠዉን የስራ ዕቅድ አለመቃወሙ የማቴሪያል ለዉጡን ተስማምቶ መቀበሉን ስለሚያሳይ እና ስራዉም በተለወጠዉ ማቴሪያል ተሰርቶ የተጠናቀቀ መሆኑን በመጥቀስ ነዉ፡፡

ከፍ ሲል እንደተገለጸዉ፣ ጉዳዩን በመጀመሪያ የተመለከተዉ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ተጠሪ ለተሰራዉ ስራ ዋጋዉን የመክፈል ኃላፊነት አለበት በሚል ድምዳሜ ላይ ሲደርስ የጠቀሰዉ መሠረታዊ ምክንያት በዉሉ ላይ የተመለከተዉ ዓይነት ብረት በገበያ ላይ የሌለ መሆኑን ተከትሎ አመልካች ነሐሴ 23 ቀን 2008 ዓ.ም እና መስከረም 23 ቀን 2009 ዓ.ም ለተጠሪ በላከዉ የስራ ዕቅድ በህንፃዉ ላይ ለሚገጠመዉ የቆሻሻ ማስወገጃ ዕቃ በዉሉ ላይ የተመለከተዉ ሳይሆን ጋልቫናይዝድ ስቲል ሽት መሆኑ እና ብረቱም በኢትዮጵያ ተስማሚነት እና ምዘና ድርጅት ተረጋግጦ ናሙናዉም ተልኮለት ተጠሪ እንዲጎበኘዉ መጠየቁን እና ተጠሪ ይህን ዕቅድ አስመልክቶ ምንም ዓይነት ተቃዉሞ አለማቅረቡ ዕቅዱን እና ስራዉ በተለወጠዉ ዕቃ የሚሰራ መሆኑን እንደተቀበለ ያሳያል የሚል ስለመሆኑ የዉሳኔዉ ይዘት ያስገነዝባል፡፡ ይሁንና የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በበኩሉ ተጠሪ አመልካች በዕቅዱ ላይ የጠቀሰዉ እና ለስራዉ የተጠቀመበትን ዕቃ በተስማሚነት ምዘና ድርጅት አስፈትሾ ዉጤቱን ካወቀ በኋላ ጥቅምት 21 ቀን 2009 ዓ.ም፣ ህዳር 05 ቀን 2009 ዓ.ም፣ ህዳር 16 ቀን 2009 ዓ.ም እንዲሁም ከዚህ ጊዜ በኋላ ለአመልካች በተጻፉት ደብዳቤዎች ስራዉ በዉሉ መሠረት ተስተካክሎ መሰራት እንዳለበት እና ይህ ካልሆነ አመልካች ክፍያዉን የማይፈጽም መሆኑን ለአመልካች መግለጹ ተረጋግጧል በሚል ድምዳሜ ላይ ደርሷል፡፡ አመልካች በዚህ ችሎት ባቀረበዉ ክርክር ስራዉን በዉሉ ላይ የተመለከተዉን

ማቴሪያል ከገበያ ላይ ማግኘት ባለመቻሉ በጋልቫናይዝድ ስቲል ሺት ማቴሪያል እንደሚሰራ ዝርዝር ዕቅድ አዘጋጅቶ ለተጠሪ ያሳወቀ መሆኑን እና ተጠሪ ለዚህ ምላሽ አለመስጠቱ የተሻሻለዉን ዉል በዝምታ መቀበሉን የሚያሳይ ነዉ በማለት አጥብቆ የሚከራከር ቢሆንም አመልካች ለስራዉ የተጠቀመዉ እና በዕቅዱ ያካተተዉን ማቴሪያል በተስማሚነት እና ምዘና ኤጀንሲ ካስመረመረ በኋላ አመልካች ይህን አስተካክሎ ስራዉን በዉሉ በተመለከተዉ መሠረት እንዲያከናዉን ካልሆነ ግን ክፍያ እንደማይፈጽምለት በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ዉሳኔ ላይ በተመለከቱት ቀናቶች የተፃፈን ደብዳቤ አስመልክቶ በግልጽ ክዶ አይከራከርም፡፡

እንግዲህ ከዚህ ሁሉ መገንዘብ የሚቻለዉ አመልካች ተጠሪ ለሚያስገነባቸዉ የቆሻሻ ማስወገጃ በማይዝግ ብረት ወይም ስቴንለስ ሜታል ሺት ለመስራት በዉሉ ግዴታ የገባ ቢሆንም በተጨባጭ ስራዉን የሰራዉ በዓይነትም(በጥራትም) ሆነ በዋጋ በዉሉ ላይ ከተመለከተዉ በሚያንሰዉ ጋልቫናይዝድ ብረት ስራዉን ማከናወኑ መረጋገጡን ነዉ፡፡ በመሠረቱ ዉል ተዋዋይ ወገኖች የእራሳቸዉን ጉዳይ በእራሳቸዉ ለመወሰን ያላቸዉን ነፃነት ተጠቅመው የሚደርጉት ስምምነት ሲሆን፣ ዉሉ በህግ የተመለከቱትን አስፈላጊዉን መስፈርቶች ተሟልቶ እስከተደረገ ድረስ አንደኛዉ ወገን በዉሉ የገባዉን ግዴታ በዉሉ ላይ በተመለከተዉ ጊዜ እና ሁኔታ ለሌላኛዉ ወገን የመወጣት ኃላፊነት አለበት፡፡ ዉል የህግ ደረጃ የተሰጠዉ ተግባር እንደሆነ በፍትሐብሔር ህጉ አንቀጽ 1731 ላይ የተመለከተዉም በዚሁ መሠረተ ሃሳብ መነሻነት እንደሆነ ይታመናል፡፡ ከተዋዋይ ወገኖች አንደኛዉ ወገን ግዴታዉን እንዲወጣ ሌላኛዉን ወገን ማስገደድ የሚችለዉም በቅድሚያ በበኩሉ የሚጠበቅበትን ግዴታ የተወጣ እንደሆነ ወይም ለመወጣት ዝግጁ መሆኑን ካረጋገጠ ብቻ ስለመሆኑም በፍትሐብሔር ህጉ አንቀጽ 1757 እና 1771 ላይ ከተመለከቱት ድንጋጌዎች መገንዘብ ይቻላል፡፡ ከዚህ አንፃር የተያዘዉን ገዳይ ስንመለከት አመልካች ለክርክሩ መነሻ የሆነዉን የቆሻሻ ማስወገጃ ገጠማ ስራ ለመስራት በዉሉ የተስማማዉ ስቴንለስ ሜታል ሺት በሆነ ዕቃ ሆኖ እያለ ነገር ግን በዋጋም ሆነ በጥራት በዉሉ ከተመለከተዉ በታች በሆነዉ ጋልቫናይዝድ ሜታል ሺት በሆነ ዕቃ መስራቱ በዉሉ መሠረት የሚጠበቅበትን ግዴታ አለመወጣቱን የሚያሳይ ነዉ፡፡ አመልካች በዉሉ ላይ ከተመለከተዉ ዉጪ በሆነ ሌላ ዕቃ ስራዉን ያከናወነዉ ይህንኑ ጠቅሶ ተጠሪ እንዲያዉቅ በዕቀድ አካቶ ከላከለት በኋላ ተጠሪ መልስ ባለመስጠቱ እና ይህም የተሻሻለዉን ዉል ተጠሪ እንደተቀበለዉ የሚቆጠር መሆኑን በመጥቀስ የሚከራከር ቢሆንም፣ የስራ ዕቅድ ዉሉን መሠረት በማድረግ አፈፃፀሙን አስመልክቶ ስራዉን በሚሰራዉ አካል የሚዘጋጅ የድርጊት መርሃ ግብር እንጂ በፍትሐብሔር ህጉ አንቀጽ 1684(2) ላይ በተመለከተዉ አግባብ እንደ የዉል ማሻሻያ ሃሳብ የማይወሰድ መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ እንደ የዉል ማሻሻያ ሃሳብ (offer for amendment of contract) የሚቆጠር ነዉ ቢባል እንኳ ተጠሪ አመልካች ባቀረበዉ ዕቅድ ላይ የጠቀሰዉ ጋልቫናይዝድ ሜታል ሺት በተስማሚነት እና ምዘና ኤጀንሲ ካስመረመረ በኋላ አመልካች ስራዉን በዉሉ መሠረት እንዲያከናዉን መጠየቁ እና ይህ ካልሆነ ክፍያዉን ለመፈጸም እንደማይገደድ ማሳወቁ አመልካች በዉሉ ላይ ከተመለከተዉ ዉጪ ስራዉን በሌላ ዕቃ እንዳይሰራ መቃወሙን የሚያሳይ ነዉ፡፡ ስለሆነም ተጠሪ

አመልካች የላከዉን ዕቅድ በዝምታ ተቀብሎታል ለማለት የሚቻል አይደለም፡፡ በመሆኑም አመልካች ወዶ እና ፈቅዶ ባደረገዉ ዉል ላይ በተመለከተዉ መሠረት የቆሻሻ ማስወገጃ ስራዉን በስቴንለስ ሜታል ሺት የመስራት ግዴታ እያለበት በእራሱ ጊዜ በመለወጥ በጋልቫናይዝደ ሜታል ሺት ዕቃ መስራቱ በዉሉ መሠረት የሚጠበቅበትን ግዴታ መጣሱን ወይም አለመወጣቱን የሚያሳይ በመሆኑ ተጠሪ ለተሰራዉ ስራ ኃላፊ ሊሆን የሚችልበት ህጋዊ ምክንያት የለም፡፡

ከዚህ አንፃር ሲታይ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠዉን ዉሳኔ በመሻር በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሰጠዉ ዉሳኔ በአግባቡ ነዉ ከሚባል በስተቀር በዚህ ችሎት ሊታረም የሚችል መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ ስላልተገኘ ተከታዩ ዉሳኔ ተሰጥቷል፡፡

<u>ዉሳኔ</u>

1. የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በይ/መ/ቁጥር 190735 ላይ መስከረም 28 ቀን 2014 ዓ.ም በዋለዉ ችሎት የሰጠዉ ዉሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥርዓት ህጉ አንቀጽ 348(1) መሠረት ጸንቷል፡፡
2. በዚህ ችሎት የተደረገዉ ክርክር ያስከተለዉን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኝ የየራሳቸዉን ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

አ/ኃ

የሰ/መ/ቁ. 195919

ቀን፡- ጥቅምት 01 ቀን 2014 ዓ/ም

ዳኞች፡- ብርሃኑ አመነው

ተሾመ ሽፈራው

ሀብታሙ እርቅይሁን

ብርሃኑ መንግስቱ

ነፃነት ተገኝ

አመልካች ፡- 1. ወ/ሮ ጌጤ ዶሪ

2. ወ/ሮ አበራሽ ዶሪ

3. ወ/ሮ ባዩ ዶሪ

4. ወ/ሮ ዘሪቱ ዶሪ

ተጠሪ፡- 1. አቶ ዶሪ ሻሎ

2. አቶ ዓለሙ ጉጆ

መዝገቡ ተምርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሠጠ፡፡

ፍርድ

የሰበር አቤቱታው የቀረበው የደቡብ ብ/ብ/ሕ/ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት የሠጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሞበታል በሚል ነው፡፡ የክርክሩን አመጣጥ ከስር ፍርድ ቤት የመዝገብ ግልባጭ እንደተረዳነው አመልካቾች በስር ፍርድ ቤት ከሳሾች ሲሆኑ ተጠሪዎች ተከሳሾች ነበር፡፡ አመልካቾች ያቀረቡት ክስ ወላጅ እናታችን ወ/ሮ ማሬ በዳኔ በ21/08/1990 ዓ/ም የሞቱ ሲሆን አመልካቾች የሚች ልጆችና ወራሾች ነን፤ በይርጋ ጨፌ ወረዳ በአዳሜ ቀበሌ አስተዳደር ክልል ሥር ከአባታችን ከ1ኛ ተጠሪ ጋር በጋራ ያፈሩት ቤት አላቸው፡፡ ንብረቱን ወራሾች በማናውቀው ሁኔታ በ15/05/2010 ዓ/ም በተጻፈ ውል 1ኛ ተጠሪ ለ2ኛ ተጠሪ በሽያጭ መኖሪያ ቤቱን ከነይዞታው አስተላልፏል፡፡ በፍ/ሕ/ቁ. 1715(2) መሠረት ውሉ ፈርሶ ንብረቱን ለወራሾች እንዲመልሱ እንዲወሰንልን ሲሉ ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡

1ኛ ተጠሪ የሠጡት መልስ ይዘት ውሉ የተደረገው በ21/09/2009 ዓ/ም ነው፡፡ የተሸጠውም 20 በ17 ሜትር ቦታ ላይ ያረፈ መኖሪያ ቤት ነው፡፡ የሽያጭ ውሉ ከባለቤቱ ወ/ሮ ምትኬ ደሮ እና ከሌሎች ሦስት ወራሾች ጋር በብር 50,000.00 የተደረገ ነው፡፡ 2ኛ ተጠሪም ንብረቱን ከገዛ በኋላ ማሻሻያ ሥራ

ሰርቶበታል፡፡ የእናታቸው ድርሻ ከተሸጠ ውርሱ ተጣርቶና ድርሻ ተለይቶ ሊቀርብ ሲገባ በዚህ አግባብ ያልቀረበ ክስ ተቀባይነት የለውም የሚል ነው፡፡ 2ኛ ተጠሪ በበኩላቸው ንብረቱን ገዝቻለሁ፡፡ የኔ ባይ ከመጣ ለመከራከርና ለማስቀረት ተዋዋዮች ግዴታ ገብተዋል፡፡ ንብረቱን የማደስና የማሻሻያ ሥራ ሰርቻለሁ፡፡ አመልካቾች ድርሻቸውን ከሻጮች ይጠየቁ እንጂ ውሉ ሊፈርስ አይገባም ብለዋል፡፡ የይርጋ ጨፌ ወረዳ ፍርድ ቤት ግራ ቀኙን አከራክሮ የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 41857 እና 47378 ላይ በቅጽ 10 እንደታተመ በሠጠው ትርጉም መሠረት ጠንቃቃ ገዥ ያደረገው የሽያጭ ውል ሊፈርስ አይገባም፡፡ ወራሾች ድርሻቸውን ከሽያጭ ገንዘቡ ከሻጮች ሊቀበሉ ይገባል በማለት ወስኗል፡፡ በየደረጃው የሚገኙ ፍርድ ቤቶች ውሳኔውን አጽንተዋል፡፡

ይህ የሰበር አቤቱታ የቀረበው በዚህ ውሳኔ ነው፡፡ የአመልካቾች የሰበር አቤቱታ ይዘትም በተጠቀሱት የሰበር ችሎት ውሳኔዎች ወራሾች ብቸኛ ወራሽ ነን በማለት ንብረቱን በስማቸው አዛውረው ያደረጉትን ሽያጭ የሚመለከት ነው፤ በተያዘው ጉዳይ የንብረቱ ሻጭ ወራሾች ሳይሆኑ 1ኛ ተጠሪ ናቸው፡፡ የንብረቱ ሥመ-ሀብትም አልተዛወረም፤ በጋራ ስናስተዳድረው የነበረን ንብረት ነው 1ኛ ተጠሪ የሸጡት፡፡ በውል አዋዋይ ፊት የተደረገ ውል አይደለም፤ ውሉም ሕገ-ወጥ በመሆኑ ሊፈርስ ይገባል የሚል ነው፡፡ የሰበር አጣሪ ችሎት ጉዳዩን መርምሮ የሠበር ውሳኔዎች ተጠቅሰው ውሉ ሊፈርስ አይገባም መባሉ ሕጋዊነቱን ለመመርመር ተጠሪዎች መልስ እንዲያቀርቡ አዟል፡፡ 1ኛ ተጠሪ ያቀረቡት መልስ ይዘትም በሥር ፍርድ ቤቱ የተጠቀሰው የሠበር ውሳኔ ለጉዳዩ ተፈጻሚነት ያለው ነው፡፡ አመልካቾች ንብረቱ ሲሸጥ ያውቃሉ፡፡ ውሳኔው ተገቢ ነው የሚል ነው፡፡ 2ኛ ተጠሪ ደግሞ አመልካቾች ውሉ ሲፈጸም እያወቁና ንብረቱ ማሻሻያ ሥራ ሲሰራበት እያዩ ቆይተው ያቀረቡት ክስ ተገቢነት የለውም፡፡ የተሸጠው ቤት እንጂ ቦታ አይደለም፤ ውሉ ሕጋዊ ስለሆነ ሊፈርስ አይገባም፡፡ የስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ ሊጸና ይገባል ብለዋል፡፡ አመልካቾች የመልስ መልስ በማቅረብ የሠበር አቤቱታቸውን በማጠናከር ተከራክረዋል፡፡

የክርክሩ ሂደት በአጭሩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን እኛም የግራ ቀኙን ክርክር፣ በሰበር አጣሪ ችሎት የተያዘው ጭብጥ፣ በሥር ፍርድ ቤቶች ከተረጋገጡት ፍሬ ነገሮችና ከሕጉ ጋር በማገናዘብ መዝገቡን መርምረናል፡፡

እንደመረመርነው አመልካቾች ያቀረቡት ክስ ወላጅ እናታችን ሟች ወ/ሮ ማሬ በዳኔ ልጆችና ወራሾች ነን፤ በይርጋ ጨፌ ወረዳ በአዳሜ ቀበሌ አስተዳደር ክልል ሥር ከአባታችን ከ1ኛ ተጠሪ ጋር በጋራ ያፈሩት ቤት አላቸው፡፡ ንብረቱን ወራሾች በማናውቀው ሁኔታ በ15/05/2010 ዓ/ም በተጻፈ ውል 1ኛ ተጠሪ ለ2ኛ ተጠሪ በሽያጭ መኖሪያ ቤቱን ከነይዞታው አስተላልፏል፤ ውሉ ፈርሶ ንብረቱን ለወራሾች እንዲመልሱ እንዲወሰንልን የሚል ነው፡፡ 1ኛ ተጠሪ 20 በ17 ሜትር ቦታ ላይ ያረፈ መኖሪያ ቤት ለ2ኛ ተጠሪ መሸጣቸውን ገልጸው ውርሱ ተጣርቶና ድርሻ ተለይቶ ያልቀረበ ክስ ተቀባይነት የለውም

ብለዋል። 2ኛ ተጠሪ በበኩላቸው ንብረቱን ገዝቻለሁ። ንብረቱን የማደስና የማሻሻያ ሥራ ሰርቻለሁ። አመልካቾች ድርሻቸውን ከሻጮች ይጠየቁ እንጂ ውሉ ሊፈርስ አይገባም ሲሉ ተከራክረዋል።

ውል ሊመሠረት የሚገባው ችሎታ ባላቸው፣ በተዋዋዮች ነጻ ፈቃድ፣ የሚቻልና ሕጋዊ በሆነ ዓላማና ጉዳይ ላይ በሕግ የተመለከተውን የውል አጻጻፍ ፎርም ተከትሎ ሊሆን እንደሚገባ በፍ/ሕ/ቁ. 1678 ላይ ተመልክቷል። ውሉ የአመሠራረት ጉድለት ካለበት ተዋዋዮች/መብት ያገኙ ሰዎች ሥምምነቱ ፈራሽ እንዲሆን በፍ/ሕ/ቁ. 1808 አግባብ ክስ ሊያቀርቡ ይችላሉ። አመልካቾችም በዚህ አግባብ ውል ሰጭ የሆኑት አባታቸው በሙሉ ንብረቱ ላይ ውሉን ለመፈጸም መብት የላቸውም፣ በንብረቱ የሚች እናታችን ግማሽ ድርሻ ላይ ወራሾች ሳንፈቅድና ሳንስማማ የተደረገው ውል ፈራሽ እንዲሆን ተከራክረዋል። ተጠሪዎች የንብረቱ ግማሽ ባለድርሻ ወራሾች የሆኑት አመልካቾች አይደሉም የሚል ግልጽ ክርክር የላቸውም። የሥር ፍርድ ቤትም አመልካቾች በንብረቱ ላይ ድርሻ ያላቸው መሆኑን በማረጋገጥ ከሽያጭ ገንዘቡ 1ኛ ተጠሪ ድርሻቸውን እንዲከፍሏቸው ወስኗል። አመልካቾች የሰበር አቤቱታ ያቀረቡትም ከሽያጭ ገንዘቡ ሳይሆን ውሉ ፈርሶ ንብረቱን መረከብ አለብን በሚል ነው።

2ኛ ተጠሪ በዚህ ችሎት ደረጃ የሚከራከሩት አመልካቾች ውሉ ሲፈጸም እያወቁና ንብረቱ ማሻሻያ ሥራ ሲሰራበት እያዩ ቆይተው አሁን ያቀረቡት ክስ ተገቢነት የለውም በማለት ነው። ከዚህ ክርክር በመነሳት 2ኛ ተጠሪ መብቱ የተላለፈላቸው ጥበቃ ሊደረግለት በሚገባ ግብይት መሆን አለመሆኑን መመልከት ተገቢ ነው። 2ኛ ተጠሪ ግዥ ሲፈጽሙ አንድ ጠንቃቃ ገዥ በሕግ ሆነ በአሠራር ሊያደርገው የሚገባውን ጥንቃቄ የማድረግ ኃላፊነት አለባቸው። የማይንቀሳቀስ ንብረት ላይ ሕግ የተለየ ጥበቃ ስለሚያደርግ የሀብትነት ሠነድ ስለሚወጣበት፤ ሠነዱ ስለሚገኝበት የሥራ ክፍል፣ ውሉ ስለሚፈጸምበት እና ንብረቱ ስለሚተላለፍበት ሥርዓት የተገለጸውን መከተል ግዴታ ይጥላል። ሽያጭ ውል የሚፈጸምበት ንብረት ላይ በሕግ መብት ያላቸው ሰዎች እነማን እንደሆኑ፣ ቦታው ላይ ቤት ያረፈበትና ስለቤቱ የሚመለከቱ ሠነዶች በቤቱ ባለሀብት ሥም በማይንቀሳቀስ ሀብት ምዝገባ ክፍል መገኘቱና ውሉ የፍ/ሕ/ቁ. 2878 በሚያዘው አግባብ ንብረቱ በሚገኝበት ሥፍራ ባለው የማይንቀሳቀስ ንብረት ምዝገባ ክፍል እንዲመዘገብ ይጠበቃል። 2ኛ ተጠሪ ውሉን የፈጸሙት ከ1ኛ ተጠሪ ጋር ሲሆን የንብረቱ ግማሽ ባለድርሻ ወራሾች የሆኑት አመልካቾች በሽያጭ ውሉ አለመሳተፋቸው ከትክክለኛው ባለመብት ያልገዙ መሆኑን ያሳያል። አመልካቾች የሽያጭ ሂደቱን በጊዜው ያውቁ ነበር የሚለው የ2ኛ ተጠሪ ክርክርም ሌሎች ወራሾች እንዳሉ እያወቁ ተገቢውን ጥንቃቄ ሳያደርጉ የገዙት መሆኑን ያስገነዝባል። ውሉም በማይንቀሳቀስ ሀብት ምዝገባ ክፍል የተመዘገበ አይደለም። ስለሆነም የተደረገው የሽያጭ ውል ተገቢውን ሕግና አሠራር ተከትሎ የተፈጸመ ባለመሆኑ ውሉ ፈራሽ ሊሆን ይገባል ብለናል።

በሥር ፍርድ ቤት የተጠቀሱት የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 41857 እና 47378 የሠጣቸው ውሳኔዎችና አስገዳጅ ትርጉሞች የሽያጭ ውሉ ጥበቃ እንዲደረግለት የሚያዘው ንብረቱ በሻጭ ስም ተዛውሮ የነበረና ገዥው ተገቢው ጥንቃቄ አድርጎ በሕግ በተመለከተው ሥርዓት ለተፈጸመ ግብይት ነው፡፡ በተያዘው ጉዳይ 2ኛ ተጠሪ ተገቢው ጥንቃቄ አድርገው የፈጸሙት የሽያጭ ውል ባልሆነበት ሁኔታ ውሉ ሊፈርስ አይገባም ተብሎ መወሰኑ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

ውሳኔ

1. የደቡብ ብ/ብ/ሕ/ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት በመዝገብ ቁጥር 76667 የካቲት 24 ቀን 2012 ዓ/ም፣ የጌዴኦ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 15110 ታህሳስ 03 ቀን 2012 ዓ/ም እና የይርጋ ጨፌ ወረዳ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 012032 መስከረም 06 ቀን 2012 ዓ/ም የሠጡት ውሳኔ በፍብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348(1) መሰረት ተሽሯል፡፡

2. በይርጋ ጨፌ ወረዳ በአዳሜ ቀበሌ አስተዳደር ክልል ሥር የሚገኘው ቤት በተጠሪዎች መካከል የተደረገው የሽያጭ ውል ፈራሽ ነው በማለት ወስነናል፡፡ 2ኛ ተጠሪ ንብረቱን ለአመልካቾችና ለ1ኛ ተጠሪ እንዲያስረክቡ ተወስኗል፡፡

3. 2ኛ ተጠሪ የሽያጭ ገንዘቡንና ለማሻሻያ ሥራ ያወጡት ወጪን በተመለከተ 1ኛ ተጠሪን ከመጠየቅ ይሕ ውሳኔ አያግድም፡፡

4. በዚህ ችሎት ለወጣ ወጭና ኪሣራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

ትዕዛዝ

- የውሳኔው ግልባጭ ለስር ፍርድ ቤቶች ይተላለፍ፡፡ የይርጋ ጨፌ ወረዳ ፍርድ ቤት በውሳኔው መሠረት እንዲያስፈጽም አዘናል፡፡ ይጻፍ
- በዚህ ችሎት የካቲት 17 ቀን 2013 ዓ/ም የተሰጠው እግድ ተነስቷል፡፡ ይጻፍ
- መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ማ/አ

የሰ/መ/ቁ፡-196963

ቀን፡- 04/02/2014 ዓ.ም

ዳኞች፡- ብርሃኑ አመነው

ተሾመ ሽፈራው

ሀብታሙ እርቅይሁን

ብርሃኑ መንግስቱ

ነፃነት ተገኝ

አመልካች፡- አቶ ደሣለኝ ሲሳይ

ተጠሪ፡- 1. ወ/ሮ ድማም ተክሉ } አልቀረቡም

2. አቶ መንግስቱ አዘነ

መዝገቡ ተመርምሮ ከዚህ የሚከተለዉ የፍርድ ዉሳኔ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

የሰበር አቤቱታ የቀረበው የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት የሠጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ነው በሚል ነው፡፡ አመልካች በሥር ፍርድ ቤት ጣልቃ ገብ ሲሆኑ 1ኛ ተጠሪ ከሳሽ እና 2ኛ ተጠሪ ተከሳሽ ሆነው ተከራክረዋል፡፡ 1ኛ ተጠሪ በ2ኛ ተጠሪ ላይ በመሰረቱት ክስ ከባለቤቱ አቶ አዘነ በየነ ጋር የባንክና የዕቁብ ዕዳ ስለነበረብን በቡራዩ ከተማ ዉስጥ የነበረንን ቤት በቀን 24/08/1999 ዓ/ም በተደረገ ዉል ሽጠን በሱሉልታ ከተማ ቁምቡራ በተባለ ቦታ በካርታ ቁጥር ሱል/243/2005 ሆኖ የሚታወቀዉን ቤት የአሁን 2ኛ ተጠሪ ልጃችን ስለሆነ በስሙ ከአቶ ዳዊት አለሙ ላይ ገዝተናል፡፡ ይሁን እንጂ ባለቤቴ በሞት ሲለይ አመልካች ቤቱን ስለያዘብኝ ቤቱንና ሰነዱን እንዲያስረክበኝ ይወሰንልኝ በማለት ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡ 2ኛ ተጠሪ ለክሱ በሰጡት መልስ ለክርክሩ መነሻ የሆነዉን ቤት በራሴ ገንዘብ የገዛሁት እንጂ የ1ኛ ተጠሪ አይደለም ብለዋል፡፡ አመልካች በክርክሩ በፍ/ብ/ስ/ስ/ሕግ ቁጥር 41 መሰረት ጣልቃ በመግባት ለክርክሩ መነሻ የሆነዉን ቤት በቀን 28/01/2011ዓ/ም በተደረገ ዉል በብር 443,594.25 ከ2ኛ ተጠሪ ላይ ገዝቼ በስሜ የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ ቁጥር ሱል/562/11 ከቀን 06/02/2011 ዓ/ም ጀምሮ አስመዝግቤ የያዝኩት ነው፡፡ ክርክር ያስነሳውን ቤት በግዥ ያገኘሁት ስለሆነ ሊከራከሩበት አይገባም ብለዋል፡፡ 1ኛ ተጠሪ ለጣልቃ-ገብ ማመልከቻ ባቀረቡት መልስ ቤቱን አመልካች የገዛው ክስ ካቀረብኩና እግድ እንዲሰጥ ከጠየቅሁ በኋላ ነው፡፡ 2ኛ ተጠሪም ፍርድ ቤት ሳይቀርብ ነው የሸጠው፤ አመልካች መብት የሌለው መሆኑን እያወቀ የገዛው ስለሆነ ክርክሩ ተቀባይነት የለውም በማለት ተከራክረዋል፡፡ 2ኛ ተጠሪ በበኩላቸው ንብረቱን ለአመልካች መሸጣቸውን በመግለጽ መልስ አቅርበዋል፡፡

ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ በመስማት ለክርክሩ መነሻ የሆነዉን ቤት የ2ኛ ተጠሪ አባት(የ1ኛ ተጠሪ ባለቤት) በ2ኛ ተጠሪ ስም ለራሳቸዉ ጥቅም በገንዘባቸዉ የገዙ ስለመሆኑ ምስክሮቻቸዉ አላስረዱም፡፡ ቤቱ የተገዛዉ በ2ኛ ተጠሪ ስም በመሆኑና ተመዝግቦ የሚገኘዉም በ2ኛ ተጠሪ ስም ስለሆነ በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 1195 መሰረት 2ኛ ተጠሪ የቤቱ ባለቤት እንደሆኑ ይገመታል፡፡ 1ኛ ተጠሪ በቤቱ ላይ መብት ለማግኘት ቤቱ በ1ኛ ተጠሪ እና በባለቤታቸዉ ገንዘብ በአሁን 2ኛ ተጠሪ ስም መገዛቱን በማስረጃ በማረጋገጥ ግምቱን ማስተባበል ይጠበቅባቸዋል፡፡ ከዚህ አንጻር ማስረጃዉ ሲመረመር የቤቱ ባለቤት 2ኛ ተጠሪ እንደሆኑ የሚያስቆጥረዉን ግምት በማስረጃ አላስተባበሉም በማለት ክሱን ዉድቅ በማድረግ ወስኗል፡፡

ጉዳዩን በይግባኝ የተመለከተው የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ግራ ቀኙን አከራክሮ ሚዛን በሚደፋ ሁኔታ ማስረጃዎቹ የሚያሳዩት 1ኛ ተጠሪ ከባለቤታቸዉ ጋር የነበራቸዉን እዳ ለመሰወር በማሳብ የነበራቸዉን ቤት ሸጠዉ በ2ኛ ተጠሪ ስም ለክርክሩ መነሻ የሆነዉን ቤት መግዛታቸዉን ነዉ፡፡ በሕብረተሰቡ ዉስጥ ባለዉ ተጨባጭ ሁኔታ አባት በልጁ ስም ቤትም ሆነ ሌላ ንብረት የሚገዛ መሆኑ የተለመደ ነዉ፡፡ በእነዚህ ሁሉ ምክንያቶች 1ኛ ተጠሪ በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 1195 መሰረት ቤቱ በ2ኛ ተጠሪ ስም ሊመዘገብ የቻለበትን ምክንያት በማስረዳት ግምቱን አስተባብለዋል፡፡ አመልካች ንብረቱ በቅን ልቦና ከ2ኛ ተጠሪ አልገዙትም፤ 1ኛ ተጠሪ በ2ኛ ተጠሪ ላይ ክስ የመሰረቱት በቀን 23/01/2011 ዓ/ም ሲሆን 2ኛ ተጠሪ ደግሞ አከራካሪዉን ቤት ለአመልካች በሽያጭ ያስተላለፉት በቀን 28/01/2011 ዓ/ም ክሱ ከተመሰረተ ከ5 ቀን በኋላ እንደሆነ የቀረበዉ ማስረጃ ስለሚያሳይና አስቀድሞ ከብር አንድ ሚሊዮን በላይ በሆነ ገንዘብ የተገዛዉን ቤት 2ኛ ተጠሪ ለአመልካች በብር 445,000.00 እንደሸጡ በመግለጽ መከራከራቸዉ ሲታይ በአመልካች እና በ2ኛ ተጠሪ መካከል በድብቅ ግንኙነት መኖሩን ያሳያል፡፡ ስለሆነም ክርክር ያስነሳዉን ንብረት 1ኛ ተጠሪ በሞት ከተለዩት ባለቤታቸዉ አቶ አዘነ በየነ ጋር ያፈሩት ንብረት ነዉ በማለት የስር ፍርድ ቤትን ዉሳኔ በመሻር አመልካች ቤቱን ለመግዛት ለ2ኛ ተጠሪ የከፈሉትን ገንዘብ ከ2ኛ ተጠሪ ላይ ከማስመለስ ዉሳኔዉ እንደማያግድ ገልጾ ወስኗል፡፡ አመልካች ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ያቀረቡትን የሠበር አቤቱታ ባለመቀበል ሠርዟል፡፡

የሰበር አቤቱታ የቀረበው በዚህ ውሳኔ ላይ ነው፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ ይዘትም 2ኛ ተጠሪ በስሙ ካርታ መያዙን፣ የሊዝ ውል መዋዋሉን አይቼ በውል አዋዋይ ፊት በተደረገ ውል ገዝቼና ስመ-ሀብት አዛውሬ የያዝኩት ንብረት ነው፡፡ የ2ኛ ተጠሪ አባት በሕይወት እያለ 2ኛ ተጠሪ የሊዝ ውል ተዋዋሎ ያዛወረውን ድብቅ ግንኙነት መባሉ ተገቢ አይደለም፡፡ ንብረቱን በምገዛበት ጊዜ በፍርድ ቤት እግድ አልተሰጠበትም፡፡ የቤቱ ዋጋ ብር 445,000.00 የተባለው የመሐንዲስ ዋጋ ግምት ነው፤ ቤቱን የሸጠልኝ በብር 1,200,000.00 ነው፡፡ ተጠሪዎች ያላቸውን ግንኙነት አላውቅም፤ በንብረቱ ላይ ያለኝ መብት ሊከበር ይገባል የሚል ነዉ፡፡ የሰበር አጣሪ ችሎት አቤቱታውን መርምሮ ለክርክሩ መነሻ የሆነዉ ቤት 2ኛ ተጠሪ በስሙ የሚገኘውን ለአመልካች በሽያጭ አስተላልፈው ባለበት ሁኔታ ቤቱን እንዲለቁ

የመወሰኑ አግባብነትን ተጠሪዎች ባሉበት እንዲጣራ ጉዳዩ ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ ትዕዛዝ ሰጥቷል። 1ኛ ተጠሪ ያቀረቡት መልስ ንብረቱ ላይ ክስ ካቀረብኩ በኋላ እገድ እንዲሰጥበት ጥያቄ አቅርቤ በእግድ ማመልከቻው ላይ 2ኛ ተጠሪ አስተያየት እንዲሰጡበት ትዕዛዝ ተሰጥቶ፤ 2ኛ ተጠሪ ትዕዛዙን አልቀበልም ካሉ በኋላ በ5 ቀናት ውስጥ ባላቸው ግንኙነት፣ 2ኛ ተጠሪን ለመርዳት በዝቀተኛ ዋጋ የተሸጠው ንብረቱን ለማሸሽ ነው። በማጭበርበርና ከቅን ልቦና ውጭ የተደረገ ሽያጭ ስለሆነ የአመልካች ክርክር ተቀባይነት የለውም ብለዋል። 2ኛ ተጠሪ በበኩላቸው ንብረቱ የራሴ ነው፤ ውል ለመዋዋል ሥልጣን ባለው አካል ፊት የባንክ ዕዳ እና የፍርድ ቤት እግድ እንደሌለው ተረጋግጦ ለአመልካች በሽያጭ ውል የተላለፈና በስሙ አዛውሮ ባለሀብት የሆነበት ንብረት ነው ብለዋል። አመልካች የመልስ መልስ በማቅረብ የሠበር አቤቱታቸውን በማጠናከር ተከራክረዋል።

የግራ ቀኝ ክርክር ከላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም የግራ ቀኙን ክርክር፣ የሰበር አጣሪ ችሎት የያዘዉን ማስቀረቢያ ነጥብ መሰረት በማድረግ ዉሳኔው ላይ የተፈጸመ መሰረታዊ የሕግ ስህተት መኖር አለመኖሩን አግባብነት ካለዉ ሕግ ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለዉ መርምረናል።

እንደመረመርነው 1ኛ ተጠሪ ያቀረቡት ክስ በሱሉልታ ከተማ ቁምቡሬ በተባለ ቦታ በካርታ ቁጥር ሱል/243/2005 በ2ኛ ተጠሪ ስም ያለው ንብረት የ1ኛ ተጠሪና የሚኝ ባለቤቱ ስለሆነ ቤቱን ከነሰነዱ 2ኛ ተጠሪ ሊያስረክበኝ ይገባል በሚል ባቀረቡት ክርክር መነሻነት የተጠሪዎች ክርክር እስከ ፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ደርሶ በመዝገብ ቁጥር 196173 ሐምሌ 26 ቀን 2013 ዓ/ም በሠጠው ውሳኔ ንብረቱ በ2ኛ ተጠሪ ስም የተገዛ ቢሆንም የተገዛበት ገንዘብና ባለቤትነቱ የ1ኛ ተጠሪና የባለቤታቸው ስለመሆኑ በመረጋገጡ ለ2ኛ ተጠሪ በሕግ የተሰጣቸው የባለሀብትነት ግምት ስለመስተባበሉ በሥር የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በማስረጃ ተረጋግጦ ንብረቱ የ1ኛ ተጠሪና የባለቤታቸው ተብሎ የተሠጠውን ውሳኔ አጽንቷል። በዚህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ላይ አመልካች በክርክር ያልተሳተፉ በመሆኑ ንብረቱን ከ2ኛ ተጠሪ መግዛታቸው ውጤቱ በጭብጥነት ተይዞ አልተመረመረም። በዚህም ምክንያት አመልካች አሁን በተያዘው መዝገብ ላይ የሠበር አቤቱታቸውን ያቀረቡ በመሆኑ በተጠሪዎች ክርክር ንብረቱን ገዝቻለሁ በሚል ያቀረቡት የጣልቃ ገብነት ማመልከቻና ሕጋዊ ውጤቱን በቀጣይነት እንመለከታለን።

በፍብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 41 መሠረት ጣልቃ የሚገባ ተከራካሪ ክርክሩ መብቱን የሚነካው እና በጉዳዩ ላይ የተረጋገጠ መብት ያለው መሆኑን ማሳየት አለበት። አመልካችም ጣልቃ የገቡት ክርክር ያስነሳውን ንብረት 2ኛ ተጠሪ በስማቸው ካርታ አውጥተው የያዙትን መስከረም 28 ቀን 2011 ዓ/ም በተደረገ ውል ገዝቼዋለሁ። ውሉም ሥልጣን ባለው አካል የተመዘገበና ስመ-ሀብቱ ተላልፎ የባለቤትነት ማረጋገጫ ያወጣሁበት ነው። ስለዚህ የ1ኛ ተጠሪ ክስ ተቀባይነት የለውም በማለት ነው። 1ኛ ተጠሪ የሚከራከሩት አመልካች ቤቱን የገዛው ክስ ካቀረብኩና እግድ እንዲሰጥ ከጠየቅሁ በኋላ ነው። 2ኛ ተጠሪም ፍርድ

ቤት ሳይቀርብ ነው የሸጠው፤ አመልካች መብት የሌለው መሆኑን እያወቀ የገዛው ስለሆነ ክርክሩ ተቀባይነት የለውም በሚል ነው፡፡ ከክርክሩ የተረዳነው 2ኛ ተጠሪ ቤቱን በስማቸው ከገዙ በኋላ ለአመልካች ውል ለመዋዋል ሥልጣን ባለው አካል ሽያጭ ውል በማድረግ ባለሀብትነት መብትን አስተላልፈዋል፡፡

አመልካች መብቱ የተላለፈላቸው ጥበቃ ሊደረግለት በሚገባ ግብይት መሆን አለመሆኑን መመልከት ተገቢ ነው፡፡ አመልካች ግዥ ሲፈጽሙ አንድ ጠንቃቃ ገዥ በሕግ ሆነ በአሠራር ሊያደርገው የሚገባውን ጥንቃቄ የማድረግ ኃላፊነት አለባቸው፡፡ የማይንቀሳቀስ ንብረት ላይ ሕግ የተለየ ጥበቃ ስለሚያደርግ የሀብትነት ሠነድ ስለሚወጣበት፤ ሠነዱ ስለሚገኝበት የሥራ ክፍል፣ ውሉ ስለሚፈጸምበት እና ንብረቱ ስለሚተላለፍበት ሥርዓት የተገለጸውን መከተል ግዴታ ይጥላል፡፡ ሽያጭ ውል ሊፈጸምበት በሚችል የከተማ ክልል ውስጥ ያለ፣ ቦታው ላይ ቤት ያረፈበትና ስለቤቱ የሚመለከቱ ሠነዶች በቤቱ ባለሀብት ሥም በማይንቀሳቀስ ሀብት ምዘገባ ክፍል መገኘቱና ውሉን የፍ/ሕ/ቁ. 1723(1) በሚያዘው አግባብ ውል ለማዋዋል ሥልጣን ባለው አካል ፊት ማድረግ ይጠበቃል፡፡

አመልካች ውሉን የፈጸሙት 2ኛ ተጠሪ ቤቱን ገዝተው ሕጋዊ ሠነድ በቤቱ ላይ ካወጡበት በኋላ ሕጋዊ ባለቤት እንዳለው በማረጋገጥ በውል አዋዋይ ፊት መሆኑ ሲታይ ግብይቱ ሕግን መሠረት ያደረገ በመሆኑ የሕግ ጥበቃ ሊደረግለት የሚገባ ነው፡፡ አመልካች ውሉን የማይንቀሳቀስ ሀብት መዝገብ እንዲጸፍ በማድረግ ካርታ ያወጡበት በመሆኑ በፍ/ሕ/ቁ. 2878 እንደተመለከተው ውሉ ሦስተኛ ወገኖችን ላይም ውጤት ያለው ነው፡፡ ሕግን መሠረት ላደረገ ግብይት ፍርድ ቤት ሕጋዊ ጥበቃ በመስጠት ገበያው በሕግ እንዲመራ ሆነ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴው ጤናማ በሆነ ሁኔታ እንዲመራ የማድረግ ኃላፊነት አለበት፡፡ ንብረቱ በ2ኛ ተጠሪ ስም ከመመዝገቡ እና ወደ አመልካች በሽያጭ ውል በሠነድ ከመዛወሩ በፊት መብቱ የማን ነው የሚለውን አመልካች የማጣራት ኃላፊነት በሕግ የለባቸውም፡፡ ንብረቱ ላይ በፍርድ ቤት እግድ ከመሰጠቱ በፊት የተዛወረ ከመሆኑ አኳያ አመልካች ክስ ካቀረቡ በኋላ ሽያጭ ውሉ መደረጉ ሆነ የተሸጠበት ዋጋ የተደረገውን ግብይት ቀሪና ውጤት አልባ አያደርገውም፡፡ ምንም እንኳን 1ኛ ተጠሪ በንብረቱ ላይ መብት ያላቸው ስለመሆኑ በፍርድ የተረጋገጠላቸው ቢሆንም ይህ መብታቸው ከመረጋገጡ በፊት 2ኛ ተጠሪ በስማቸው የነበረውን ንብረት ለሦስተኛ ወገን ለሆኑት ለአመልካች ያስተላለፉ በመሆኑ፤ ከሦስተኛ ወገን መብት አኳያ ንብረቱን 1ኛ ተጠሪ ሊረከቡ አይችሉም ብለናል፡፡ ሥለሆነም ክርክር ያስነሳው ንብረት ሕጋዊ ባለመብት አመልካች በመሆናቸው 1ኛ ተጠሪ ንብረት ለመረከብ ያቀረቡት ክስ ውድቅ ሊደረግ ሲገባ ይሕ ታልፎ የተሠጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

ውሳኔ

1. የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሠበር ችሎት በመዝገብ ቁጥር 333206 ነሀሴ 07 ቀን 2012 ዓ/ም እና የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 322981 ሚያዚያ 20 ቀን 2012 ዓ/ም የሠጡት ውሳኔ በፍብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348(1) መሰረት ተሻሽሏል፡፡

2. በፊንፊኔ ዙሪያ ኦሮሚያ ልዩ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 33894 ጥር 27 ቀን 2012 ዓ/ም የሠጠው ውሳኔ በውጤት ደረጃ ጸንቷል፡፡

3. 1ኛ ተጠሪ የሽያጭ ገንዘቡን ከ2ኛ ተጠሪ ለመጠየቅ ሆነ ወይም በሕግ አለኝ የሚሉትን መብት ክስ አቅርበው ከመከራከር ይሕ ውሳኔ አያግድም ብለናል፡፡

4. በዚህ ችሎት ለወጣ ወጭና ኪሣራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

ትዕዛዝ

- የውሳኔው ግልባጭ ለሥር ፍርድ ቤቶች ይተላለፍ፡፡
- መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

ዜ/መ

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

የሰ/መ/ቁ፡-197008

ቀን፡- 05/02/2014 ዓ.ም

ዳኞች፡- ብርሀኑ አመነው

ተሾመ ሽፈራው

ሀብታሙ እርቅይሁን

ብርሀኑ መንግስቱ

ነፃነት ተገኝ

አመልካች፡- አዲት ሰርቪስ ኮርፖሬሽን - ጠበቃ መኮንን ይማም - ቀረቡ

ተጠሪ፡- ፀጋ ረታ አስመጪ ኃላ/የተ/የግ/ማህበር - አልቀረቡም

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍርድ

ክርክሩ የሽያጭ ውልን መነሻ ያደረገ ሲሆን ጉዳዩ በተጀመረበት የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት አመልካች ከሳሽ ተጠሪ ተከሳሽ በመሆን ተከራክረዋል፡፡

አመልካች የካቲት 4 ቀን 2011 ዓ.ም ባቀረበው ክስ አመልካች የኮምፒዩተር እቃዎችን ለመግዛት ባወጣው ጨረታ ተጠሪ አሸንፎ እቃዎቹን አቅርቦ ክፍያ የተቀበለ ቢሆንም እቃዎቹን ከሰርቨሩ ጋር የሚያገናኙ ኬብሎችን ባለማቅረቡ ምክንያት እቃዎቹ የተፈለገውን አገልግሎት መስጠት አልቻሉም፡፡ በመሆኑም ኬብሎቹን እንዲያቀርብ ወይም በወቅቱ የገበያ ዋጋ የእቃዎቹን ግምት ብር 182,900 ወጪና ኪሳራን ጨምሮ እንዲከፍል ይወሰንልኝ በማለት ዳኝነት ጠይቋል፡፡

ተጠሪ የካቲት 29 ቀን 2011 ዓ.ም በተፃፈ መልስ አመልካች እቃዎቹ ጉድለት ያለባቸው መሆኑን ካወቀበት ጊዜ ጀምሮ በ1 አመት ውስጥ ክስ ስላላቀረበ ክሱ በይርጋ ቀሪ ሆኗል የሚል የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ አቅርቧል፡፡

ፍርድ ቤቱም በመቃወሚያው ላይ ግራ ቀኙን አከራክሮ ግንኙነታቸው የሽያጭ ውልን መሰረት ያደረገ ስለሆነ ለጉዳዩ ተፈፃሚነት ያለው ስለውሎች በጠቅላላው የተደነገገው የፍ/ሕ/ቁጥር 1845 ሳይሆን የሽያጭ ውልን የሚመለከተው የፍ/ሕ/ቁጥር 2298(1) ነው፡፡ በዚህ ድንጋጌ መሰረትም በሻጩ አጭበርባሪነት ካልሆነ በቀር ገዢው ጉድለቱን ካወቀበት ጊዜ ጀምሮ በ1 ዓመት ጊዜ ውስጥ ክስ ማቅረብ አለበት፡፡ አመልካች የተጠሪ አጭበርባሪነት ያለበት ስለመሆኑ በክሱ ያልገለፀ ሲሆን ተጠሪው የእቃዎቹን ጉድለት እንዲያስተካክል ያሳወቀው ጥቅምት 7 ቀን 2009 ዓ.ም እንዲሁም ለተረከባቸው እቃዎች ክፍያ

የፈጸመው ጥቅምት 25 ቀን 2009 ዓ.ም በመሆኑ ክሱ የቀረበው ሁለት ኣመት ካለፈው በኂላ የካቲት 4 ቀን 2011 ዓ.ም ነው፡፡ የተጠሪ ሰራተኛ ሰኔ 10 ቀን 2009 ዓ.ም UPS 5kg ለቼክ አፕ መውሰዱ ጉድለቱን በግልፅ አምኗል አያስብልም፡፡ አምኗል ቢባል እንኳ ከዚህ ጊዜ ጀምሮ በ1 ዓመት ውስጥ ክሱ ስላልቀረበ በይርጋ ይታገዳል በማለት ብይን ሰጥቷል፡፡

አመልካች ውሳኔውን በመቃወም ይግባኙን ለፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ያቀረበ ቢሆንም የስር ፍ/ቤት ውሳኔን በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሰረት በማፅናቱ ጥቅምት 13 ቀን 2013 ዓ.ም የተፃፈ የሰበር አቤቱታውን አቅርቧል፡፡ የአቤቱታው ይዘት ባጭሩ አመልካች በክሱ ላይ ፍሬ ነገርን ከመግለፅ በዘለለ ተጠሪው መቃወሚያ ሊያቀርብ ይችላል ብሎ በማሰብ በክስ መስማት ወቅት ሊያቀርብ የሚችለውን መከራከሪያ አስቀድሞ ማቅረብ ግዴታ በሌለበት ተጠሪው የማታለል እና የማጭበርበር ተግባር ስለመፈፀሙ አመልካች በክሱ አልገለፀም መባሉ ተገቢ አይደለም፡፡ ተጠሪ እቃዎቹን አስተካክላለው ብሎ መውሰዱን አልካደም፡፡ የወሰደውም እቃውን ባስረከበ በአንድ ዓመት ውስጥ ሲሆን እቃውን በእምነት በመውሰድ በተግባር የማታለል እና የማጭበርበር ተግባር የፈፀመ ሲሆን እቃዎቹን አስተካክሎ የሚያቀርብበት ጊዜም ስላልተወሰነ እና እቃዎቹን አስተካክሎ እንዲያስረክብ በተደጋጋሚ በአመልካች ሲጠየቅ ከዛሬ ነገር አስተካክዬ እመልሳለው ማለቱ ስላልተካደ አስፈላጊ ከሆነም ምስክሮቻችንን በመስማት ሊጣራ ሲገባ ክሱ በይርጋ ይታገዳል መባሉ ተገቢ አይደለም፡፡ ውሉ የሽያጭ ብቻ ሳይሆን የጥገና ማደስና መለዋወጫ ማቅረብ መሆኑ በሰነድ ተረጋግጦ እያለ ሽያጭ ብቻ ነው ተብሎ የሽያጭ ሕግ የይርጋ ድንጋጌ ተግባራዊ መደረጉ እንዲሁም እቃው በተጠሪ እጅ ያለ በመሆኑ አመልካች በማንኛውም ጊዜ ንብረቱን መጠየቅ የሚችል ሁኖ እያለ ክሱ በይርጋ ይታገዳል መባሉ የፍ/ሕ/ቁጥር 1206 እና የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 63600 ቅፅ 10 የሰጠውን ውሳኔ የሚቃረን መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ነው የሚል ነው፡፡

አቤቱታው በአጣሪ ችሎቱ ተመርምሮ ተጠሪ የእቃውን ጉድለት አምኖ መልሶ መቀበሉን ለክሱ በሰጠው መልስ አምኖ እያለ ክሱ በአንድ አመት ይርጋ ይታገዳል ተብሎ የመወሰኑን አግባብነት ከፍ/ሕ/ቁጥር 2298(1) እና አግባብነት ካላቸው የሕግ ድንጋጌዎች ጋር አገናዝቦ ለመመርመር ያስቀርባል በመባሉ ተጠሪ መልሱን እንዲያቀርብ ታዟል፡፡

ተጠሪም ጥር 10 ቀን 2013 ዓ.ም የተፃፈ መልስ አቅርቧል፡፡ የመልሱ ይዘት ባጭሩ ተጠሪ ለክሱ በአማራጭ በሰጠው መልስ አመልካች የመለሳቸውን እቃዎች አስመልክቶ ክትትል አላደረገም በሚል መቀመጡ አማራጭ ክርክር ከሚሆን በቀር በፍ/ሕ/ቁጥር 1851(ሀ) መሰረት እዳውን አምኗል አያስብልም፡፡ እቃው ጉድለት አለበት በሚል ማሳወቅም ሆነ ጉድለት አለ በሚል እቃ መመለሱ መታመኑ በውጤት ደረጃ አንድ ስለሆነ በፍ/ሕ/ቁጥር 2298(1) መሰረት አመልካች በአንድ አመት ጊዜ ውስጥ ክስ ስላላቀረበ ክሱ በይርጋ ይታገዳል መባሉ ተገቢ መሆኑን የሚገልፅ ነው፡፡

አመልካች የካቲት 1 ቀን 2013 ዓ.ም የተፃፈ የመልስ መልሱን ያቀረበ ሲሆን የሰበር አቤቱታውን በማጠናከር ተከራክሯል፡፡

የክርክሩ አመጣጥ ባጭሩ ከላይ የተመለከተው ሲሆን የአመልካች ክስ በይርጋ ይታገዳል ተብሎ የመወሰኑን አግባብነት በስር ፍ/ቤት ከተደረጉ ክርክሮች፣ በማስረጃ ከተረጋገጡ ፍሬ ነገሮች እንዲሁም ለጉዳዩ ተገቢነት ካላቸው የሕግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለው መርምረነዋል፡፡

እንደመረመርነውም አመልካች በዋናነት የሚከራከረው ተጠሪው ክርክር ያስነሳውን እቃ መልሶ መረከቡ እና በተለያዩ ጊዜያትም ከዛሬ ነገ አስተካክዬ አስረክባለው እያለ እንደነበር ባልተካደበት አስፈላጊ ከሆነም ምስክር ሊሰማ ሲገባ እንዲሁም ውሉ ሽያጭ ብቻ ሳይሆን የጥገና እና የመለዋወጫ እቃ አቅርቦት ጭምር ሆኖ እያለ ክሱ በአንድ አመት ይርጋ ይታገዳል መባሉ ተገቢ አይደለም በማለት ነው፡፡ ተጠሪ በበኩሉ እቃውን መልሶ መቀበሉን በአማራጭ ክርክር ማቅረቡ እዳውን አምኗል የማያስብል እና አመልካች ጉድለት አለበት በሚል ማሳወቁም ሆነ እቃውን መመለሱ በውጤት ደረጃ ልዩነት ስለሌለው ክሱ በፍ/ሕ/ቁጥር 2298(1) መሰረት በይርጋ ይታገዳል ተብሎ መወሰኑ ተገቢ መሆኑን ገልፆ ተከራክሯል፡፡

ገዢው ክስ ማቅረቡን የከለከለው የሻጩ አጭበርባሪነት ካልሆነ በቀር እቃው እንደ ውሉ ትክክል አለመሆኑን ወይም ጉድለት ያለበት መሆኑን ካስታወቀበት ቀን አንስቶ እስከ አንድ አመት ውስጥ ክስ ያላቀረበ እንደሆነ እቃው ጉድለት አለበት ወይም እንደ ውሉ የቀረበ አይደለም በማለት ክስ ማቅረብ የማይችል መሆኑ በፍ/ሕ/ቁጥር 2298(1) ላይ ተመላክቷል፡፡ ይህም ማለት አንድ ገዢ የገዛው እቃ ላይ ጉድለት ያለበት ከሆነ ጉድለቱ ለሻጩ ባሳወቀ በአንድ አመት ውስጥ ጉድለቱ እንዲስተካከልለት ክስ ካላቀረበ ክሱ በይርጋ ይታገዳል፡፡ ነገር ግን ገዢው በዚህ አንድ አመት ውስጥ ክስ እንዳያቀርብ የሻጩ አጭበርባሪነት ከልክሎት ከሆነ ገዢው ጉድለት መኖሩን ካሳወቀ ከአንድ አመት በኋላም ቢሆን ጉድለቱ እንዲስተካከልለት ክስ ማቅረብ ይችላል፡፡ በሌላ አባባል የሻጩ የማጭበርበር ድርጊት የአንድ አመቱን የይርጋ ጊዜ ገደብ የሚያቋርጥ ምክንያት ይሆናል፡፡ የዚህ ድንጋጌ አላማ ሻጩ በፈጸመው የማጭበርበር ተግባር የወንጀል ድርጊት በመሆኑ በአንድ አመት ውስጥ ክስ አልቀረበም በሚል በወንጀል ድርጊቱ ተጠቃሚ እንዳይሆን ለመከላከል ነው፡፡ ይህ ማለት ግን የማጭበርበር ድርጊት ከተፈጸመ ምንም አይነት የክስ ማቅረቢያ የጊዜ ገደብ አይኖረውም ማለት አይደለም፡፡ የማጭበርበር ድርጊቱ እንደ ይርጋ ማቋረጫ ጊዜ ተወስዶ የአንድ አመቱ የይርጋ ጊዜ የማጭበርበር ድርጊቱ ከተፈጸመ ጊዜ ጀምሮ እንደአዲስ መቁጠር የሚጀምር ይሆናል፡፡ ከዚህ ጋር ተያይዞ ሌላው መታየት ያለበት የሻጩ አጭበርባሪነት የሚለው አገላለጽ ምን አይነት እና መቼ የሚፈጸም የሻጩን ድርጊት የሚያመለክት ነው? የሚለው ሊሆን ይገባል፡፡ በፍ/ህ/ቁጥር 2297 ሻጩ የሸጠውን ነገር ጉድለቶች ያሉበት መሆኑን ገዢው እንዳያውቃቸው በተንኮል ደብቋቸው ከሆነ ሻጩን ከሀላፊነት የሚያድኑ የውል ቃሎች ቢኖሩ ሻጩ

ከተጠያቂነት ማምለጥ እንደማይችል ያመለክታል፡፡ ይህም ማለት ሻጩ ለገዢ በሸጣቸው ነገሮች ላይ ጉድለት መኖሩን እያወቀ በተንኮል በሽያጭ ወቅት ምንም አይነት ጉድለት እንደሌለባቸው አስመስሎ ከሸጠ ወይም ከሽያጭ በኋላም ቢሆን ጉድለቱ እንዳይታወቅ ለማድረግ ሻጩ የማጭበርበር ድርጊት የፈጸመ በመሆኑ ተጠያቂ የማያደርገው የውል ቃል እንኳን ቢኖር ውሉ ተፈጻሚ እንደማይሆን እና ሻጩ በኃላፊነት እንደሚጠየቅ የሚያመለክት ነው፡፡ የፍ/ህ/ቁጥር 2298/1 የፍ/ሕ/ቁጥር 2297 ተከታይ እንደመሆኑ ተጣምረው ሲነበቡ ሻጩ እቃውን ወይም የሚሸጠውን ነገር ለገዢ በሚሸጥበት ወይም በሚያስረክብበት ወቅት እቃው ጉድለት ያለበት መሆኑን እያወቀ ጉድለት እንደሌለ አድርጎ ወይም ጉድለቱ እንዳይታወቅ አድርጎ በማጭበርበር ለገዢ መሸጡ ወይም ማስረከቡ ከተረጋገጠ ክስ የማቅረቢያ ጊዜው በአንድ አመት ይርጋ የማይገደብ መሆኑን የሚያስገነዝብ ነው፡፡ በተቃራኒው ሻጩ በሽያጭ ወይም በርክክብ ወቅት የፈጸመው የማጭበርበር ድርጊት ከሌለ ጉድለቱን ገዢው ለሻጭ ባሳወቀ በአንድ አመት ውስጥ ክስ ካላቀረበ ክሱ በይርጋ ይታገዳል ማለት ነው፡፡

በተያዘው ጉደይ አመልካች ተጠሪው ከዛሬ ነገ እቃውን እጠግናለው በማለት የማጭበርበር ተግባር ስለፈጸመ ክሱ በይርጋ ተቋርጧል መባሉ ተገቢ አይደለም በማለት የሚከራከር ቢሆንም ከላይ እንደተገለጸው በፍ/ሕ/ቁጥር 2298(1) የተገለፀው የማጭበርበር ተግባር እቃውን ከሚመለከት ዝርዝር መግለጫ ወይም በግብይቱ ጊዜ እቃው ጉድለት ያለበት መሆኑ እየታወቀ ይህን በመደበቅ ከተፈጸመ ተግባር ጋር የሚገናኝ ነው፡፡ ተጠሪ ከዛሬ ነገ እቃውን አስተካክላለሁ እያለ ቆይቶ ቢሆን እንኳን ተጠሪ የዋቢነት ሃላፊነቱን አለመወጣቱን የሚያሳይ እንጂ በግዢ ወቅት በእቃው ላይ ያለው ጉድለት በአመልካች እንዳይታወቅ የማጭበርበር ድርጊት መፈጸሙን የሚያመለክት አይደለም፡፡ ከግብይቱ በኋላ የተጠሪ ሰራተኛ ሰኔ 10 ቀን 2009 ዓ.ም UPS 5kg ለቼክአፕ መውሰዱ ጉድለቱን በግልፅ አምኗል የሚያስብል ካለመሆኑም በላይ ተጠሪ ጉድለቱን ለማስተካከል እቃውን ተቀብሏል ቢባል እንኳ በዚህ አግባብ ባለማስተካከሉ አመልካች ተጠሪ እቃውን ለማስተካከል ከተቀበለበት ጊዜ ጀምሮ በሕግ በተገለፀው አንድ አመት ጊዜ ውስጥ ክስ በመመስረት ዳኝነት ሊጠይቅ ይገባ ነበር፡፡ ከዚህ ጋር ተያይዞ አመልካች ተጠሪው ከዛሬ ነገ እቃውን አስተካክላለው በማለት ያጭበረበረኝ ስለመሆኑ ምስክሮቼ መሰማት ነበረባቸው በማለት የሚከራከር ቢሆንም በፍትሐብሄር ክርክር ማስረጃ የሚሰማው እና ፍሬ ነገር እንዲነጥር የሚደረገው ለጉዳዩ አወሳሰን የግድ አስፈላጊ ሲሆን ብቻ ስለመሆኑ ከፍ/ሥ/ሥ/ሕግ ድንጋጌዎች መገንዘብ ይቻላል፡፡ ስለሆነም አመልካች ምስክሮቼ ሊሰሙ ይገባ ነበር በማለት የሚያቀርበው ቅሬታ ተገቢነት የለውም፡፡

በመጨረሻም አመልካች ለክሱ መነሻ ያደረገው የገዛዋቸው እቃዎች በውሉ መሰረት ተሟልተው የቀረቡ ባለመሆኑ ተገቢውን አገልግሎት መስጠት አልቻሉም የሚል ሁኖ እያለ እና ውላችን የጥገና እና የመለዋወጫ አቅርቦትን ስለሚጨምር የፍ/ሕ/ቁጥር 2298 ለጉዳዩ ተፈጻሚነት የለውም በማለት የሚያነሳው መከራከሪያ ተገቢነት ስንመለከት አመልካች በስር ፍርድ ቤት ባቀረበው ክስ ተጠሪው ጥገና

እንዲያደርግልኝ ይወሰንልኝ የሚል ግልጽ ዳኝነት አልጠየቀም፡፡ አመልካች በስር ፍርድ ቤት ከመለዋወጫ እና ጥገና ውል ጋር የተያያዘ ክስ ባላቀረበበት የተጠቀሰው የይርጋ ድንጋጌ ተፈጻሚ ሊሆን አይገባም በሚል የሚያቀርበው መከራከሪያ ተቀባይነት ያለው አይደለም፡፡ አመልካች በስር ፍርድ ቤት ክስ ያቀረበው የሽያጭ ውልን መሰረት አድርጎ በተሸጠው እቃ ላይ አለ የሚለው ጉድለት በገንዘብ ወይንም በአይነት እንዲስተካከልለት በመሆኑ ለጉዳዩ የፍ/ሕ/ቁጥር 2298/1 ተፈጻሚነት ይኖረዋል፡፡

በመሆኑም አመልካች ተጠሪ እቃውን እንዲያስተካክል ያሳወቀው ጥቅምት 7 ቀን 2009 ዓ.ም መሆኑ እና ክሱ የቀረበው የካቲት 1 ቀን 2011 ዓ.ም መሆኑ ተረጋግጦ በይርጋ ይታገዳል ተብሎ በስር ፍ/ቤቶች በተሰጠው ብይን ላይ እና ብይኑን በማጽናት በተሰጠው ውሳኔ ላይ የተፈፀመ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የለም በማለት ተከታዩን ወስነናል፡፡

ውሳኔ

1. የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በክ/መ/ቁጥር 65181 ግንቦት 16 ቀን 2011 ዓ.ም የሰጠው ብይን እንዲሁም የፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በክ/መ/ቁ 239590 ሐምሌ 22 ቀን 2012 ዓ.ም በዋለው ችሎት ሰጠው ውሳኔ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሰረት ፀንቷል፡፡
2. በዚህ ችሎት የተደረገው ክርክር ያስከተለውን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የራሳቸውን ይቻሉ፡፡
3. አመልካች ለተጠሪ እንዲስተካከል ሰጥቻለሁ የሚለውን እቃ በተመለከተ ባለበት ሁኔታ ለማስመለስ ክስ ከማቅረብ ይህ ውሳኔ አያግደውም፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

ሄ/መ

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

የሰ/መ/ቁ. 171678

ታህሳስ 22 ቀን 2012 ዓ/ም

ዳኞች፡- ሠለሞን አረዳ

ብርሃኑ አመነው

ተሾመ ሽፈራው

ሀብታሙ እርቅይሁን

ነፃነት ተገኝ

አመልካች፡- ኒው ክሬሽን ኢንተርናሽናል ቤተክርስቲያን - ጠበቃ-ገ/እግዚያብሄር ሙናቸው - ቀረቡ

ተጠሪ፡- ጭላሎ ኢንተርፕራይዝ ኃ/የተ/የግል ማህበር - ጠበቃ - ስራ አስኪያጅ አሰፋ ደገፉ - ቀረቡ

መዝገቡ ተምርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሠጠ፡፡

ፍርድ

የሰበር አቤቱታው የቀረበው የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በሠጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሞበታል በሚል ነው፡፡ የክርክሩን አመጣጥ ከስር ፍርድ ቤት የመዝገብ ግልባጭ እንደተረዳነው አመልካች የስር ጣልቃ ገብ ሲሆን ተጠሪ ከሳሽ ነበር፡፡ በዚህ ፍርድ ቤት ተከራካሪ ያልሆኑት አቶ መኩሪያ ታፈሰ እና ወ/ሮ ሣራ ኖርድ የስር ተከሳሾች ናቸው፡፡ ተጠሪ ያቀረበው ክስ በአዲስ አበባ ከተማ ቂርቆስ ክፍለ ከተማ ወረዳ 9 የቤት ቁጥር 485 የሆነና በ3252 ካሬ ሜትር ላይ የሚገኝ መኖሪያ ቤት በብር 19,000,000.00 (አስራ ዘጠኝ ሚሊዮን ብር) ተከሳሾች መጋቢት 01 ቀን 2007 ዓ/ም ለተጠሪ ሽጠዋል፡፡ ገንዘቡን ተቀብለው የውል ግዴታቸውን ስላልፈጸሙ ቤቱንና ቤቱን የተመለከተ ሠነድ እንዲያስረክቡ፣ የሥም ማዛወሪያ ክፍያ እና አስፈላጊ ሌላ ግዴታ እንዲፈጽሙ እና የውሉን መቀጫ ብር 500,000.00 (አምስት መቶ ሺህ ብር) እንዲከፍሉ ዳኝነት ጠይቋል፡፡

ተከሳሾች ያቀረቡት መልስ ውሉ በውል አዋዋይ ፊት አልተደረገም፡፡ ተጠሪ አዋክቦ ውሉን ቢያስፈርመንም ቤት ሆነ ሠነድ አልተረከበም፡፡ ከውሉ ገንዘብ ውስጥ ብር 5,500,000.00 በቼክ ለመክፈል የሠጠ ቢሆንም ቼኩ ስንቅ የለውም የተባለ ስለሆነ ተጠሪ የውል ግዴታውን አልተወጣም፡፡ ውሉም የፈረሰ ስለመሆኑ በጽሁፍና በፖስታ ቤት አማካኝነት ቢላክለትም ፈቃደኛ አልሆነም፡፡ ውሉ ስለፈረሰ ቤቱን ለ3ኛ ወገን በቀድሞ ዋጋ ሽጠን አስረክበናል፡፡ ተጠሪ የውል ግዴታውን ስላልተወጣ ውሉ ይፈጸም ማለት አይችልም ሲሉ አቅርበዋል፡፡

አመልካች በክርክሩ ጣልቃ በመግባት ክርክር ያስነሳውን ቤት ሚያዚያ 11 ቀን 2007 ዓ/ም ከተከሳሾች ገዝተናል፡፡ የተጠሪ ውልም በፍ/ሕ/ቁ. 2878 መሠረት በማይንቀሳቀስ ንብረት መዝገብ ላይ

ስላልተመዘገበ አመልካች ላይ ውጤት የለውም፡፡ ተጠሪ የውል ግዴታውን ስላልተወጣና ቤትና ሠነድ ስላልተረከበ ውሉ ፈራሽ ነው፡፡ ቤቱን ተረክበን ከፍተኛ ወጪ በማውጣት የማሻሻያ ተግባር እያከናወን እንገኛለን፡፡ ተጠሪ ለተከሳሾች የሠጠው ቼክ በቂ ስንቅ የለውም የተባለው በስህተት ነው በማለት ባንኩ የጻፈው ማስረጃ ባላቸው ድብቅ ግንኙነት የተፈጸመ ስለሆነ ተቀባይነት የለውም ይባልልን ብለዋል፡፡

ተጠሪ ለአመልካች ክርክር የሠጠው መልስ ክፍያውን ሚያዚያ 12 ቀን 2007 ዓ/ም የተፈጸመ በማስመሰል ያቀረቡት ተቀባይነት የለውም፡፡ ሲፒኦ ይዘው ሲሄዱ ሚያዚያ 13 ቀን 2007 ዓ/ም በፍርድ ቤት እግድ ምክንያት ሲፒኦውን ይዘው ተመልሰዋል፡፡ አመልካች ቤቱን ለቤተ አምልኮ እንፈልገዋለን ልቀቅልን ብለዋል፡፡ ለተከሳሾች የተሠጠው ቼክ በቂ ስንቅ የለውም ብሎ ባንኩ የጻፈውን ደብዳቤ አብረው ከተከሳሾች ጋርም መወስዳቸው ቤቱ ለተጠሪ መተላለፉን እያወቁ የገዙት መሆኑን ያሳያል፡፡ ቼኩ በቂ ስንቅ እያለው ተከሳሾች አለመውሰዳቸው ለመጠቃቀም ፍላጎት ስላላቸው ብቻ ነው፡፡ ብር 5,500,000.00 አልተከፈለም ቢባል እንኳን ውል ለማፍረስ በቂ ምክንያት አይደለም፡፡ በተናጠል ውሉን ለማፍረስ የሚያስችል ስምምነት የለንም፡፡ ቤቱ ሚያዚያ 12 ቀን 2007 ዓ/ም እንዲታገድ ስለታዘዘ በአመልካች እጅ ሊገባ አይችልም ብሏል፡፡

የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ማስረጃ ሰምቶ የተጠሪ ውል ያልተመዘገበ ቢሆንም በተለመደው አሠራር አመልካች ይህንኑ ቤት ከመግዛቱ በፊት እዚህ ቤት ላይ ያለውን የመብት ጥያቄ ሳያጣራ ይህን ሁሉ ገንዘብ አውጥቶ የሸያጭ ውል ይፈጽማል ብሎ መገመት አይቻልም፡፡ የተጠሪ ምስክሮች የአመልካች አባላትና ኮሚቴ ይህንን ቤትና ቦታ ለአመልካች ቤተ አምልኮነት መፈለጋቸውን በመግለጽ እንዲተውለት በአካልም ሆነ በስልክ መጠየቃቸውንና ተጠሪ ግን ለመተው ፈቃደኛ አለመሆኑን መግለጹን የመሠከሩ ሲሆን የአመልካች ምስክሮችም ተከሳሾች ቤቱን ለሌላ ሠው የሸጡት መሆኑን ነገር ግን የሚጠብቁት ነገር እንዳለ የገለጹላቸው መሆኑን፣ ውሉ ከተፈጸመ በኋላ ሚያዚያ 12 ቀን 2007 ዓ/ም ውልና ማስረጃ ሲሄዱ ቤቱ መታገዱን ካወቁ በኋላ ተጠሪን ለምን እንዳሳገደውና እንዲተውላቸው መጠየቃቸውን መግለጻቸው አመልካች በሚያዚያ 11 ቀን 2007 ዓ/ም የፈጸመችው ውል ባለማወቅና በቅን ልቦና ሳይሆን ተጠሪ ቤቱን መጋቢት 01 ቀን 2007 ዓ/ም መግዛቱን እያወቀች የፈጸመችው መሆኑን ተረድተናል፡፡

የተጠሪ ውል ያልተመዘገበ ነው ለተባለው የአመልካችም ውል ያልተመዘገበ ነው፡፡ የፍ/ሕ/ቁ. 2878 ለ3ኛ ወገኖች ማሳወቅ ዓላማ ያለው ሲሆን 3ኛ ወገኖች ውሉን ያውቁት እንደነበር ማረጋገጥ እስከተቻለ ድረስ አለመመዝገቡ የሚያመጣው ለውጥ የለም፡፡ አመልካች የሚጠበቅባትን ጥንቃቄ ሳታደርግና ከተጠሪ ጋር ቀድሞ የተደረገ ውል መኖሩን እያወቀች በመደረብ የፈጸመችው ውል ስለሆነ ተጠሪ እና ተከሳሾች የፈጸሙት የሽያጭ ውል ስላልተመዘገበ ብቻ አመልካች ላይ ተፈጻሚነት አይኖረውም ማለት አይቻልም፡፡

ከተከሳሾች አንጻር የተጠሪን ውል አልካዱም። ብር 5,500,000.00 ለተከሳሾች ከተጠሪ የተሠጠው ቼክ በቂ ስንቅ እንደነበረው ተረጋግጧል። ባይኖረው እንኳን አብዛኛው የውሉ ግዴታ የተፈጸመ በመሆኑ ውል ለማፍረስ በቂ ምክንያት አይደለም። ስለሆነም ክስ የቀረበበትን ቤትና የቤቱን ሠነድ ተከሳሾች ለተጠሪ እንዲያስረክቡ እና ተጠሪ ያልተመነዘረውን ቼክ ገንዘብ ብር 5,500,000.00 እንዲከፍል ወስኗል። መቀጮ እንዲከፈል የተጠየቀውን ዳኝነት ውደቅ አድርጓል። የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አመልካች ያቀረበችውን ይግባኝ ባለመቀበል ቅሬታውን ሰርዟል።

ይህ የሰበር አቤቱታ የቀረበው በዚህ ውሳኔ ነው። የአመልካች የሰበር አቤቱታ ይዘትም ቤቱን ተጠሪ ስለመግዛቱ ከክርክሩ በፊት ማወቃችን የሚያስረዳ ማስረጃ አልቀረበም። 3ኛ ወገንን በውል ለመቃወም በፍ/ሕ/ቁ. 1723 እና በፍ/ሕ/ቁ. 2878 መሠረት የተመዘገበ መሆን አለበት። ቤትና ሠነድ ከተያዘ ቅን ልቦና እንዳለ ሊወሰድ ይገባል። የማስፋፊያ ስራ ወጪ አውጥተንበታል። የተጠሪ ምስክሮች የድርጅቱ ባለቤትና ድርሻ ያላቸው ልጃቸው ናቸው። ከውል አዋዋይ አካል ውጭ የተደረገ ተመሳሳይ ውል ሲገኝ ገንዘብ አከፋፈል፣ ቤትና ሠነድ ርክክብ እና እድሳት ወጪ ጋር ተገናዝቦ መታየት አለበት የሚል ነው።

የሰበር አጣሪ ችሎት አመልካች ቤቱንና አስፈላጊ ሠነድ የተረከቡ መሆኑን እየገለጹ ባለበት ሁኔታ የተሻለ መብት ያለው ማነው የሚለውን ከፍ/ሕ/ቁ. 1161 እና ከሰበር መዝገብ ቁጥሮች 39568 እና 60720 አንጻር ለማጣራት ተጠሪ መልስ እንዲያቀርብ በማዘዙ ተጠሪ ያቀረበው መልስ የተጠሪን ውል አላውቅም ቢሉም ማስረጃ ተሰምቶ ውሉን እንደሚያውቁ ተረጋግጧል። ቤቱንም እስከ ግንቦት 04 ቀን 2007 ዓ/ም ድረስ በሻጭ እጅ እንደነበር በሚመለከተው ጽ/ቤት ተረጋግጧል። በአፈጻጸም የተረከብኩት ከተከሳሾች ነው። የውሉን ክፍያ ለሻጭ አልከፈሉም። ሠነድም አልረተከቡም፤ ቢረከቡ ኖሮ በማስረጃነት ያቀርቡት ነበር። ቤቱ በእጃቸው ስላልነበረ እድሳት አድርጊያለሁ የሚሉት ተቀባይነት የለውም። ውሳኔው ሊፀና ይገባል በማለት ተከራክሯል። አመልካች የመልስ መልስ በማቅረብ የሰበር አቤቱታዋን በማጠናከር ተከራክራለች።

የክርክሩ ሂደት በአጭሩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን እኛም ክርክሩ የሥነ-ሥርዓት ሕጉን ተከትሎ የተመራ መሆን አለመሆኑን በጭብጥነት በመያዝ መዝገቡን መርምረናል።

እንደመረመርነው ተጠሪ ክርክር ያስነሳውን ቤት በስር ፍርድ ቤት ተከሳሾች ከነበሩት ከአቶ መኩሪያ ታፈሰ እና ወ/ሮ ሣራ ኖርድ መጋቢት 01 ቀን 2007 ዓ/ም በተጻፈ ውል የገዛ ሲሆን እንደ ውሉ ባለመፈጸሙ ሻጮች የሆኑት የስር ተከሳሾች በውሉ መሠረት ቤቱን እና የቤቱን ሠነዶች ሆነ ሌላ አስፈላጊ ተግባር እንዲፈጽሙ ክስ አቅርቧል። ውሉ የፍ/ሕ/ቁ. 1723 በሚያዘው አግባብ በውል አዋዋይ ፊት ያልተደረገ ቢሆንም የስር ተከሳሶች ውል መኖሩን ያመኑ በመሆኑ በተጠሪ እና በተከሳሾች መካከል ሕጋዊ የሆነ የፀና ውል አለ ማለት ይቻላል። የፀና ውል ካለ ደግሞ ሻጭ በውል የገባውን ግዴታ፤ በፍ/ሕ/ቁ. 1731(1) እንደተደነገገው ውል በተዋዋዮች መካከል እንደሕግ የሚቆጠር ስለሆነ እና ውል

እንዲፈጸም የተጠየቀው የማይንቀሳቀስ ንብረት በመሆኑ ተጠሪ ልዩ ፍላጎት ንብረቱ ላይ እንዳለው ግምት ስለሚወሰድ፤ የመፈጸም ግዴታ አለበት፡፡ በዚህ አግባብም የሥር ፍርድ ቤት ተከሳሾች የነበሩት ውሉን እንዲፈጽሙ የተወሰነ መሆኑን ተረድተናል፡፡

በሌላ በኩል አመልካች ይህንኑ ቤት ሚያዚያ 11 ቀን 2007 ዓ/ም በተጻፈ ውል ከስር ተከሳሾች ገዝታለች፡፡ የተጠሪ ውል ይፈጸምልኝ ክርክር መብቴን ይነካል በማለትም በፍብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 41 መሠረት ጣልቃ ገብታ ተከራክራለች፡፡ በመሆኑም ግራ ቀኙ ተከራካሪዎች ቤቱን ከገዙ በቤቱ ላይ የተሻለ መብት ያለው ማን ነው? የሚለው በጭብጥነት ተይዞ እልባት ሊሠጠው የሚገባ ይሆናል፡፡ አመልካች ሆነ ተጠሪ ያደረጉት የማይንቀሳቀስ ንብረት ግዥ ውል የፍ/ሕ/ቁ. 1723 በተመለከተው አግባብ በውል አዋዋይ ፊት ያልተደረገ እና በፍ/ሕ/ቁ. 2878 አግባብ በማይንቀሳቀስ ንብረት መዝገብ የተመዘገበ አይደለም፡፡

በፍብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 41 መሠረት ጣልቃ የሚገባ ተከራካሪ ክርክሩ መብቱን የሚነካው እና በጉዳዩ ላይ የተረጋገጠ መብት ያለው መሆኑን ማሳየት አለበት፡፡ በሌላ በኩል አመልካች የምትከራከረው ተጠሪ ለመረከብ ዳኝነት የጠየቀበትን ቤት የተመለከተ ሠነድ ሆነ ቤቱን ተረክቤያለሁ በማለት ነው፡፡ እንዲህ ከሆነ ተጠሪ በሦስተኛ ወገን እጅ ያለ ንብረትን ተዋዋዮች ተገደው እንዲፈጽሙ መጠየቅ ይችላል ወይስ አይችልም? የሚለውን ጭብጥ ምላሽ መስጠት ያስፈልጋል፡፡

የሥር ፍርድ ቤቶች እነዚህን ክርክሮች በፍብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 246 እና ተከታይ ድንጋጌዎች መሠረት በጭብጥነት በመያዝ አጣርተው የመወሰን ኃላፊነት አለባቸው፡፡ አመልካች ቤቱን እና አስፈላጊ ሠነዶችን ሚያዚያ 12 ቀን 2007 ዓ/ም በሠነድ የተረከበችና የማሻሻያ ግንባታ የጀመረች መሆኑን በመግለጽ የተከራከረች ሲሆን የሥር ተከሳሾችም ቤቱን ለአመልካች አስረክበናል ብለዋል፡፡ ተጠሪ በበኩሉ ክስ ካቀረበበት ሚያዚያ 12 ቀን 2007 ዓ/ም በኋላ ግንቦት 04 ቀን 2007 ዓ/ም በስር ፍርድ ቤት በተደረገ ማጣራት ቤቱ በስር ተከሻሾች እጅ እንደነበር በፍትሕ ጽ/ቤት በኩል ተረጋግጧል፤ በአፈጻጸም ሂደትም የተረከብኩት ከተከሳሾች ነው በማለት ተከራክሯል፡፡

የፍትሐ ብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕጉ የተከራካሪዎች በእኩል የመደመጥ መብት እንዲከበር እና እውነትን የመፈለግ ዓላማ ያለው በመሆኑ እና ዓላማው እንዲሳካ የማድረግም ኃላፊነት የፍርድ ቤቱ ነው፡፡ ስለሆነም የቀረበውን የፍሬ ነገር ክርክር ተከራካሪዎች ባቀረቧቸው የሠው ሆነ የሠነድ ማስረጃዎች በማጣራት እና በተጨማሪም በፍብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 264 መሰረት ለክርክሩ አወሳሰን ጠቃሚ የሆነ ማስረጃ ፍርድ ቤቱ የማስቀረብ ስልጣን እና ኃላፊነት ያለበት በመሆኑ ጉዳዩ ተጣርቶ ተመዝኖ ሊወሰን ይገባ ነበር፡፡ የሥር ፍርድ ቤት አመልካች ቤቱን ስትገዛ ተጠሪ ቤቱን አስቀድሞ መግዛቱን እያወቀች ውሉን የፈጸመች መሆኑ ውሉ መብት አይሰጣትም በማለት ድምዳሜ የደረሠ ቢሆንም አመልካች እና ተጠሪ ሁለቱም በአንድ ንብረት ላይ ያደረጉት የማይንቀሳቀስ ንብረት ግዥ ውል በፍ/ሕ/ቁ. 1723

በተመለከተው አግባብ በውል አዋዋይ ፊት ያልተደረገ እና በፍ/ሕ/ቁ. 2878 አግባብ በማይንቀሳቀስ ንብረት መዝገብ ያልተመዘገበ በመሆኑ ቤቱ በማን እጅ ይገኛል? ቤቱን የተመለከቱ ሠነዶችን ማን ይሂል? የሚሉትን አጣርቶ ማን የተሻለ መብት አለው? የሚለውን አብሮ በመመዘን መወሰን ሲገባው ማለፉ ስህተት ያለበት ነው፡፡ ክርክር ያስነሳው ቤት ሦስተኛ ወገን በሆነችው አመልካች እጅ ካለ ተጠሪ ተዋዋዮች ተገደው እንዲፈጽሙ መጠየቅ ይችላል ወይስ አይችልም? የሚለውን ጭብጥ በመያዝ መወሰን ሲገባው ማለፉ ውሳኔው ላይ መሠረታዊ የሆነ የክርክር አመራር ግድፈት የተፈጸመበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

ውሳኔ

1. የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 165867 ታህሳስ 25 ቀን 2011 ዓ/ም እና የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 162166 ጥቅምት 28 ቀን 2011 ዓ/ም የሠጡት ውሳኔ በፍብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348(1) መሰረት ተሽሯል፡፡

2. የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ክርክር ያስነሳው ቤትና ቤቱን የተመለከቱ ሠነዶችን በማን እጅ ይገኛል የሚለውን በማጣራት እና አስቀድሞ ከተሰማው ማስረጃ ጋር በመመዘን ማን የተሻለ መብት አለው? ክርክር ያስነሳው ቤት ሦስተኛ ወገን በሆነችው አመልካች እጅ ካለ ተጠሪ ተዋዋዮች ተገደው እንዲፈጽሙ መጠየቅ ይችላል ወይስ አይችልም? የሥር ተከሳሾች ውሉን ተገደው መፈጸም የማይችሉ ከሆነ ሕጋዊ ውጤቱ ምንድን ነው? የሚሉትን ጭብጦች በመመርመር የሥር ተከሳሾችንም ወደ ክርክሩ በማስገባት የመሠለውን እንዲወስን በፍብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 343(1) መሠረት ጉዳዩን መልሠናል፡፡

3. በዚህ ችሎት ለወጣ ወጭና ኪሣራ ግራቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

ትዕዛዝ

1. የውሳኔው ግልባጭ ለስር ፍርድ ቤቶች ይተላለፍ፡፡ የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በውሳኔው መሠረት እንዲፈጽም አዘናል፡፡ ይጻፍ

2. ሀምሌ 10 ቀን 2011 ዓ/ም በዚህ ችሎት የተሠጠው የእግድ ትዕዛዝ ተነስቷል፡፡ ይጻፍ

3. የሥር ፍርድ ቤት መዝገብ ይመለስ፡፡

4. መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ብ/ም

የሰ/መ/ቁ 227366

ቀን፡- 29/09/2015 ዓ.ም

ዳኞች፡- ብርሃኑ አመነው

ረታ ቶሎሳ

እንዳሻ አዳነ

ቀነዓ ቂጣታ

ኑረዲን ከድር

አመልካች፡- አቶ ሰለሞን ደቻሳ

ተጠሪ፡- አቶ አየለ አበቱ

መዝገቡ የተቀጠረው መርምሮ ፍርድ ለመስጠት ሲሆን በዚሁ መሰረት ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍርድ

መዝገቡ ተከፍቶ ሊቀርብ የቻለው አመልካች ግንቦት 17 ቀን 2014 ዓ.ም በተፃፈ የሰበር አቤቱታ የፌ/ከ/ፍ/ቤት በመ/ቁጥር 269209 በቀን 27/11/2013 ዓ.ም እና የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ/ቁጥር 213653 በቀን 11/08/2014 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የህግ ስሕተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል በማለት በማመልከታቸዉ ነው፡፡

ጉዳዩ ከቤት ሽያጭ ውል ጋር የተያያዘ ክርክርን የሚመለከት ሆኖ ክርክሩ የተጀመረው በፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት ሲሆን በስር ፍ/ቤት አመልካች ከሳሽ ተጠሪ ደግሞ ተከሳሽ ሆነው ተከራክረዋል፡፡

አመልካች በ27/11/2013 ዓ.ም ጽፈው ባቀረቡት ክስ አመልካች ከተጠሪ ጋር በቦሌ ክ/ከተማ ወረዳ 10 የቤት ቁጥር አዲስ ከሆነው ከክፍለ ከተማው ጋር ሊዝ ከተዋዋሉበት ይዞታ ላይ 440 ካ.ሜ የይዞታ መጠንና አምስት በብሎኬት የተገነቡ ቤቶች ያሉበትን እንዲሁም ከካርታ ውጪ በይዞታቸው የሚገኘውንና አንድ ክፍል ብሎኬት ቤትና የቆርቆሮ ቤት ያለበትን በግምት 300 ካ.ሜ.ወደፊት ወደ ይዞታቸው የሚካተትና ከይዞታቸው አስቆርጠው ለአመልካች የሚያስረክቡት ቤትና ይዞታ በብር 4,224,000.00(አራት ሚልዮን ሁለት መቶ ሃያ አራት ሺህ አምስት መቶ ብር) ሸጠውላቸዋል፡፡ለዚህም ነሐሴ 02 ቀን 2012 ዓ.ም የመኖሪያ ቤት ሽያጭ ውል መፈራረማቸውን፤ ከውሉ በፊት ብር 800,000፣የውሉ ቀን ብር 200,000 እንዲሁም ከውሉ በኃላ በተለያዩ ቀናት የገንዘብ መጠኑ ብር 624,000 ከፍያለሁ፣ ብር 37,189.90 ለአጥርና የበር ስራ ቀሪ ክፍያ በአመልካች የንግድ ባንክ አካውንት ገቢ አድርጊያለሁ፤ በተጨማሪም በሽያጭ በተስማሙበት ይዞታ ላይ አጥርና በሮች ላስገነቡበት ብር 342,000 በምስክር ፊት በጥሬ ገንዘብ መክፈላቸውን፤ ሆኖም ተጠሪ ነሐሴ 2 ቀን 2012 ዓ.ም በተደረገው የመኖሪ ቤት ሽያጭ ዉል መሠረት ለመፈጸም ፍቃደኛ ባለመሆናቸው ተጠሪ

ለአመልካች የሸጡትን ቤትና ይዞታ ለአመልካች እንዲያስተላልፉና ለስም ዝውውሩ አስፈላጊ የሆኑ ተግባሮችን እንዲፈጽሙ ውሳኔ እንዲሰጥላቸው ጠይቀዋል፡፡

ተጠሪ በቀን 15/08/2013 ዓ.ም በተጻፈ መልስ ነሐሴ 2 ቀን 2012 ዓ.ም የተደረገው ውል ላይ ውሉ ስልጣን ባለው አካል ፊት ግራ ቀኙ ቀርበው ለመፈጸም ቢስማሙም ሻጭ ከመነሻውም ለገዢ ሊያስተላለፉት በማይችሉት ጉዳይ ላይ ብቻ ሳይሆን መብታቸው ባልሆነ ሀብት ጭምር ላይም የተደረገ ውል በመሆኑ ውሉ ሊፈጸም የማይችል ነው፤ ውሉም ረቂቅ ውል በመሆኑ በዚህ ውል አማካኝነት ተጠሪ እንድፈጽም ልገደድ አይገባም፤ ውሉ የዉል አጻጻፍ ፎርምን፤ ያልተከተለ በመሆኑ ፈራሽ ነው፤ አመልካች ከካርታ ውጪ 300 ካ.ሜ ቤትና ይዞታ ለመረከብ ያቀረቡት ጥያቄ ተጠሪ በዚህ ቦታ ላይ የሚያዙበት መብት የሌለውና የመንግስት ይዞታ ነው፤ አመልካቸው ውለታ ፈጸምኩበት የሚሉት ቤትና ይዞታ ስመሀብት የሌለውና ሰነድ አልባ ነው፤ ተፈጸመ የተባለው የቤት ሽያጭ ውል በሙሉም ሆነ በከፊል የሻጭ ሀብት ባልሆነ ላይ በመሆኑ ሊፈጸም የሚችል ውል የለም ተብሎ ውሳኔ እንዲሰጥና ተዋዋዮች ወደነበሩበት ሊመለሱ የሚገባ መሆኑን፤ተጠሪ ውሉን በህግ አግባብ ተፈጻሚ ለማድረግ ባደረጉት ሂደት የቦሌ ክ/ከተማ መሬት አስተዳደር ጽ/ቤት ከካርታ ውጪ ውል የተፈጸመበት 300 ካ.ሜ መሬት በይዞታቸው እንደማይካተት ስላሳወቃቸው የውሉ ዓላማ ህገ ወጥ ሆኖ ከአቅማቸው በላይ ስለሆነ ፍ/ቤቱ ሊፈጸም የሚችል ውል የለም ብሎ እንዲወስንልን፤በአመልካች የቀረቡት የተለያዩ የሰነድ ማስረጃዎችም የሀሰት ሰነዶችና ውሉን ሊያስረዱ የሚችሉ ሰነዶች ስላልሆኑ ሰነዶቹ ውድቅ ይደረግልን በማለት ተከራክረዋል፡፡

ጉዳዩ በዚህ መልኩ የቀረበለት የፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤትም በበኩሉ የግራ ቀኙን ክርክር እና ማስረጃ መርምሮ አመልካች መብት አስገኝቶልኛል በማለት ያቀረቡት ዉል ስምምነት ሰነድ የሽያጭ ውል ሳይሆን የቀብድ ውል እና ወደፊት በውልና ማስረጃ ቀርበው ለመዋዋል ስምምነት ያደረጉበት እንጂ የሽያጭ ውል ባለመሆኑ እና ይህ አይነት ስምምነት ደግሞ በህግ ፊት ዋጋ ያለው ሆኖ ሊጸና የሚችል ስምምነት ነው ብሎ ውጤት ለመስጠት የሚቻል ባለመሆኑ አመልካች ይህን በህግ ፊት ሊፀና የማይችለውን ውል መነሻ በማድረግ ተጠሪ ቤትና ይዞታውን ያስረክቡኝ እንዲሁም ስመሀብት ያዙሩልኝ በማለት ያቀረቡት ክስ ተቀባይነት የለውም፤ተጠሪ ከአመልካች የተቀበሉትን ገንዘብ ክሱ ሲሰማ ባመኑት መሰረት ብር 1,724,000 ለአመልካች ሊከፍሉ ይገባል፤ ውጪና ኪሳራን በተመለከተ የየራሳቸዉን ይቻቻሉ ሲል ወስኗል፡፡

አመልካች በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ይግባኛቸውን ለፌደራሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አቅርበው ፍ/ቤቱም ግራቀኙን አስቀርቦ ካከራከረ በኃላ ተጠሪ ለአመልካች እንዲከፍሉ ውሳኔ ካረፈበት ገንዘብ ውጪ ለአጥርና የበር ስራ ብር 37,189.90 እና ብር 342,000 አመልካች ወጭ በማድረግ ለተጠሪ ከፍለዋል? አልከፈሉም? ተጠሪ ይህንን ገንዘብ ሊመልሱ ይገባል? አይገባም? በሚለው ጭብጥ

ላይ አከራክሮ ውሳኔ እንዲሰጥ ወደ ስር ፍ/ቤት መልሶ በሌሎች ጉዳዮች ላይ ግን የከፍተኛ ፍ/ቤት የሰጠውን ውሳኔ በማጽናት ወስኗል፡፡

አመልካች ግንቦት 17 ቀን 2014 ዓ.ም ጽፈው ያቀረቡት የሰበር አቤቱታም ይዜንኑን ውሳኔ በመቃወም የቀረበ ሲሆን ይዘቱም ባጭሩ፡- ተጠሪ ክደው የተከራከሩት በይዞታቸው አድርገው እየተጠቀሙበት የነበረውንና ህጋዊ ባለይዞታ ያልሆኑበትን 300 ካ.ሜ በተመለከተ እንጂ ከአመልካች ጋር ውል የፈጸሙበትን እና ህጋዊ ባለይዞታ የሆኑበትን 440 ካ.ሜ ይዞታ ባለመሆኑ የስር ፍ/ቤት ባመኑት መሰረት ለአመልካች ይህንን ይዞታ እንዲያስረክቡ ሊወስን ይገባ የነበረ መሆኑን፤ የስር ፍ/ቤት ውሉ የቀብድ ውል ነው በሚል በተከራካሪ ወገኖች ያልተነሳ ክርክርን በማንሳት ውሉ የቀብድ ውል ነው ሲል የደረሰበት ድምዳሜ ስህተት መሆኑን፤ ፍ/ቤቱ ውሉ የቀብድ ውል ነው ካለም በቀብድ ውል ድንጋጌ መሠረት አመልካች የከፈሉትን ገንዘብ አጠፌታ እንዲከፈላቸው ሊወስን ሲገባ ይህን አለመደረጉ ስህተት ነው የሚል ነው፡፡

የአመልካች የሰበር አቤቱታ በሰበር አጣሪው ችሎት ተመርምሮ የስር ፍ/ቤት በግራቀኙ መካከል የተደረገው ስምምነት የሽያጭ ውል ሳይሆን የቀብድ ውል ነው በማለት ድምዳሜ ላይ ከደረሰ በኃላ ተጠሪ በቀብድ ውል ምክንያት የተቀበሉትን ክፍያ አጠፌታ መክፈል አለባቸው? ወይስ የለባቸውም? የሚለውን ሳይወሰን ያለፈበትን አግባብነት ከፍህ/ቁ.1885 እና ተያያዥ ጉዳዮች ለማጣራት የሚል ማስቀረቢያ ጭብጥ በመያዝ ተጠሪ መልስ እንዲሰጥበት ታዞ ጉዳዩ ለዚህ ሰበር ችሎት እንዲቀርብ ተደርጓል፡፡

ተጠሪም በበኩሉ በተደረገለት ጥሪ መሰረት ቀርቦ ሐምሌ 19 ቀን 2014 ዓ.ም በተፃፈ ከሰበር አጣሪ ችሎት ማስቀረቢያ ጭብጥ አንፃር ያቀረበዉ መልስ ይዘት ዝርዝሩ ሲታይ፡- የፍ/ህ/ቁ 1885(2) ተፈጻሚ የሚሆነው ቀብድ የተቀበለው ወገን የተቀበለውን ቀብድ አጠፌታ በመክፈል ውል ለማፍረስ የፈለገ እንደሆነ እንጂ ውሉ ሕገ ወጥ በመሆኑ በሚፈርስ ውል ላይ አለመሆኑን፤ ተጠሪ ከአመልካች ጋር ተፈጸመ በተባለው ውል ላይ ያቀረቡት ተቃውሞ ውል አልተፈጸመም የሚል ሳይሆን ሽያጩ ከተከናወነበት 440 ካ.ሜ ይዞታቸው ላይ 300 ካ.ሜ ይዞታ የራሳቸው ያልሆነና የመንግስት መሬት ላይ በመሆኑ ውሉ ሕገ ወጥ እና ሊፈፀም የማይችል በመሆኑ በዚህ ምክንያት ሊፈርስ ይገባል የሚል ክርክር መሆኑን፤ የቦሌ ክ/ከተማ የመሬት ልማት ማኔጅመንትም ሆነ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር መሬት ልማት ጽ/ቤት በሽያጭ ውሉ ላይ የተካተተው 300 ካ.ሜ ይዞታ የመንግስት ይዞታ መሆኑን ማረጋገጣቸውን፤ ይህ ደግሞ የሕገ መንግስቱን አንቀጽ 40(3) በተቃረነ መልኩ የተፈጸመ ውል በመሆኑ ሊፈርስ ይገባል የሚል ድምዳሜ ላይ ሊያደርስ የሚገባ እንጂ ተጠሪ ውል አፍርሰዋል በሚል የቀብዱን አጠፌታ ሊከፍሉ ይገባል ተብሎ ድምዳሜ ላይ የሚያደርስ አለመሆኑን፤የፍ/ብ/ህ/ቁ.1885 ተፈጻሚ ሊሆን የሚገባው አመልካችና ተጠሪ በውሉ ላይ ህጋዊ ውል ስምምነት የፈጸሙ እንደሆነና ተጠሪ ግን

ውሉን ለማፍረስ የፈለገ እንደሆነና የቀብዱን አጠፊታ በመክፈል ውሉ እንዲፈርስለት የጠየቀ እንደሆነ እንጂ ዉሉ ራሱ ህገ-ወጥ በመሆኑ ምክንያት በፍ/ቤት ውሳኔ የፈረሰ እንደሆነ አይደለም የሚል ነው፡፡

አመልካች የሰበር አቤቱታውን የሚያጠናክር ነሐሴ 10 ቀን 2014 ዓ.ም የተጻፈ የመልስ መልስ አቅርቦ ከመዝገቡ ጋር እንዲያያዝ ተደርጓል፡፡

ከስር ጀምሮ በግራ ቀኙ የቀረበዉ ክርክር፣በስር ፍ/በቶች የተሰጠ ዉሳኔና እንዲሁም ባጠቃላይ የጉዳዩ አመጣጥ እና ይዘት ከፍ ሲል ባጭሩ የተመለከተዉን ሲመስል ይህ ችሎትም ጉዳዩ ያስቀርባል ሲባል በሰበር አጠሪ ችሎቱ ያስቀርባል ሲባል ከተያዘዉ ጭብጥ አንፃር በስር ፍ/ቤቶቹ ዉሳኔ ላይ የተፈፀመ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት መኖር አለመኖሩን ከግራ ቀኙ ክርክር እና ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸዉ ህጉ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ በሚከተለዉ መልኩ መርምረናል፡፡

በመጀመሪያ ደረጃ በጭብጥነት ወደተያዘዉ ዋና ጉዳይ በቀጥታ ከመግባታችን በፊት ለመነሻ ያህል ቤትን ጨምሮ ባጠቃላይ የማይንቀሳቀሱ ንብረቶች ባለቤትነት መብትን በዉል ለማቋቋምም ሆነ ከአንዱ ወደ ሌላ ለማስተላለፍ የሚደረጉ ዉሎችን በተመለከተ ህጉ በዚህ ረገድ የወሰደዉን አቋም በትክክል የተመለከትን እንደሆነ ስለ ዉሎች አመሰራረት አጠቃላይ ጉዳይን የሚገዛዉ ፍትሐብሄር ህጉ ክፍል አንቀፅ 1723(1) ድንጋጌ ስር የማይንቀሳቀስ ንብረቶች ባለቤትነት ወይም በአንድ በማይንቀሳቀስ ንብረት ላይ የአላባ ጥቅም ወይም የመያዣ ወይም የሌላ አገልግሎት መብት ለማቋቋም ወይም ለማስተላለፍ የሚደረጉት ውሎች ሁሉ በፅሁፍ እና በሚገባ አካታን በፍ/ቤት መዝገብ ወይም ውል ለመዋዋል ስልጣን በተሰጠው ፊት መሆን እንዳለባቸው አስገዳጅነት ባለው መልኩ መደንገጉን መገንዘብ ይቻላል፡፡

ከዚህ አንፃር ወደተያዘው ጉዳይ ስንመለስም አመልካች ለክሱ ምክንያት ያደረገው እና በማስረጃነትም ከክሱ ጋር አያይዞ ያቀረበው ውል ስምምነት ሰነድ ርዕሱ የመኖሪያ ቤት ቀብድ ውል ስምምነት የሚል ሆኖ ይዘቱም ግራ ቀኙ ተዋዋይ ወገኖች ውሉን በውል እና ማስረጃ ፅ/ቤት ለወደፊት ቀርበው ሲዋዋሉ ሻጭ ቀሪውን ገንዘብ በመቀበል ቤትና ይዞታውን ለገዢ ለማስረከብ መስማማታቸውን እንጂ ከፍ ሲል በተጠቀሰዉ ውል በሰፈረው ግራ ቀኙ ሃሳብ መሰረት ግራ ቀኙ ውልና ማስረጃ ቀርበው የተደረገ ቤት ሽያጭ ውል ስምምነት አመለኖሩንና እንዲሁም ይህ ከፍ ሲል በተገለፀው አካታን በግራ ቀኙ መካከል ተደርጓል የተባለው የመኖሪያ ቤት ቀብድ ውል ስምምነትም ቢሆን የተጠሪ ባልሆነና ከካርታ ውጪ ያለ 300 ካ.ሜ መንግስት ይዞታ ጭምር ላይ የተደረገ መሆኑን የስር /ቤቶች ውሳኔ ግልባጭ በግልፅ ያስረዳሉ፡፡

እንግዲህ አመልካች ይህ ላቀረቡት ዳኝነት ጥያቄያቸው እና ክርክራቸው መሰረት ያደረጉት ውሉ ይዘት ይህ ከሆነ ከዚህ በቀላሉ መገንዘብ እንደሚቻለዉ ግራ ቀኙ የቤት ሽያጭ ውል ገና ለወደፊቱ ዉል እና ማስረጃ ምዝገባ እና ማረጋገጫ ፅ/ቤት ቀርበዉ ለመፈፀም ሲሆን ሆኖም ይህን ባለመፈፀማቸዉ ምክንያት የግራ ቀኙ ሃሳብ በጅማሮ እና ረቂቅ ደረጃ የቀረ መሆኑን ብቻ ሳይሆን ይህ ረቂቅ የተባለው

ውል ሰነድም ቢሆን የተጠሪ (ሻጭ) ባልሆነና መብቱን ለሌላ ማስተላለፍ በማይችለው 300 ካ.ሜ ካርታ ውጪ ባለ ይዞታ ላይ ጭምር የተደረገ ከመሆኑ ጋር ጉዳዩ በአንድ ላይ ተዳምሮና ተገናዝቦ ሲታይ ዉሉ ከአመሰራረት ጋር በተያያዘ ተደራራቢ የህግ ክፍተት ያለበትና በጥቅሉ የህጉን መሰፈርት በጠበቀ እና በተሟላ መልኩ የተቋቋመ ባለመሆኑ ዉሉ በዚህ ምክንያት የህግ ጥበቃ ሊደረግለት የሚገባ አይደለም(የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1723(1)፣ 1678(ለ)፣1715(1)፣2266፣2879 እና ሌሎችንም ይመለከታል)፡፡

ስለሆነም ተጠሪ ውሉን መሰረት በማድረግ ቤትና ይዞታውን እንዲያስረክብ እንዲሁም ስመ ሀብቱን ወደ አመልካች ለማዞር ሊገደድ አይችልም ሲሉ የስር ፍ/ቤቶች የደረሱበት መደምደሚያም ሆነ በዚህ ረገድ የሰጡት ውሳኔ ክፍል ህጉን መሰረት ያደረገ በመሆኑ የሚነቀፍ አይደለም፡፡በመሆኑም አመልካች በዚህ ረገድ ያቀረቡት ሰበር ቅሬታ እና ክርክር በዚህ ምክንያት ተቀባይነት ያለዉ አይደለም፡፡

በመቀጠል የዚህን ሰበር ችሎት ምላሽ ይሻል በሚል በሰበር አጣሪ ችሎቱ በጭብጥነት ወደተያዘዉ ዋና ሰበር ክርክር ነጥብ ወደ ሆነዉ ተጠሪ የተቀበሉትን ቀበድ አጠፌታ ሊከፍሉ ይገባል? ወይስ ይገባም? የሚለውን ስንመለከት ደግሞ በመሰረቱ አንዱ ተዋዋይ ወገን ለሌላኛው ተዋዋይ ወገን ቀብድ መስጠቱ በማያከራክር ሁኔታ ውል መደረጉን አረጋጋጭ እንደሆነ በፍ/ብ/ህ/ቁ.1883 ስር በህጉ የተደነገገዉ ሲሆን በአንፃሩ ደግሞ ይህ በህግ የተቋቋመዉን ዉል ሌላ ተቃራኒ ስምምነት ከሌለ በቀር ቀብድ የተቀበለ ተዋዋይ ወገን ይህንኑን የተቀበለዉን ቀብድ አጠፌታ በመክፈል ዉሉን ለማፍረስ እንደሚችል እንዲሁ በፍ/ብ/ህ/ቁ.1885(2) ስር የተደነገገ ሲሆን ከእነዚህ ከተጠቃሹ ህጉ ድንጋጌዎች ይዘትና አቀራረፅም መገንዘብ የሚቻለው በቅድሚያ በተዋዋይ ወገኖች መካከል በህግ አግባብ የተቋቋመ ውል ኖሮ ነገር ግን ሻጩ ወይም ቀብዱን የተቀበለው ወገን ይህ በመካከላቸዉ በህጉ አግባብ የተቋቋመዉን እና የፀናውን ውል በራሱ ፍቃድ ማፍረስ ከፈለገ የተቀበለውን ቀብድ አጠፌታ ለሌላኛው ወገን መልሶ በመክፈል ውሉን በነፃነት ማፍረስ የሚችል መሆኑን ሲሆን በያዝነው ጉዳይ ግን ሲጀመር በግራ ቀኙ መካከል በሃሳብ ደረጃ እና ጅማሮ የቀረ ረቂቅ እንጂ በህጉ አግባብ የተደረገ ቤት ሽያጭ ውል በሌለበት ሁኔታ ተጠሪ ረቂቅ ውሉን መሰረት በማድረግ የተቀበለውን ገንዘብ አጠፌታ ሊከፍል የሚገደድበት የህግ አግባብ ካለመኖሩም ባሻገር ስር ፍ/ቤት በዚህ ረገድ የቀረበ ዳኝነትም ሆነ ክርክር በሌለበት ሁኔታ ይህ ከስነ-ስርዓት ህጉ አንፃርም ሲታይ ተቀባይነት ያለዉ አይደለም(የፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ.182 ይመለከታል)፡፡

ስለሆነም አመልካች በዚህ ረገድ የጠቀሳቸው ቀብድን የሚመለከቱ ፍትሐብሔር ህጉ አንቀፅ.1883 እና 1885 ድንጋጌዎች ለተያዘው ሰበር ክርክር ጉዳይ አግባብነት ስለሌላቸዉ ተጠሪ የተቀበለዉን ገንዘብ አጠፌታ እንዲከፍል ሊያስገድዱ የሚችሉ አይደሉም፡፡

ሲጠቃለል ለዚህ ሰበር ችሎት ክርክር ምክንያት የሆነው ዉል በህግ አግባብ የተቋቋመ ሳይሆን ይልቁንም ቀድሞም ቢሆን በህግ አግባብ ያልተቋቋመ፣ በህግ ፊት የማይፀና እና በተዋዋይ ወገኖች ላይ መብትና ግዴታን የማይፈጥር ፈራሽ ከመሆኑ አኳያ ግራ ቀኙ በፍ/ብ/ህ/ቁ.1815 (1) ስር

እንደተመለከተው ውለታው ከመደረጉ በፊት እንደነበሩበት ሁኔታ እንዲመለሱ በማደረግ ማለትም ተጠሪ በዉሉ መነሻ ከአመልካች የተቀበለውን ገንዘብ ብቻ ለአመልካች እንዲመልስ ይደረጋል እንጂ አጠፋታ ባለመሆኑ በዚህ ረገድ በስር ፍ/ቤቶች የተደረሰዉ መደምደሚያ ሀሳብም ሆነ የተሰጠው ውሳኔ ክፍል በአግባቡ ነው ሊባል ከሚችል በቀር የሚነቀፍና መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት አይደለም በማለት ተከታዩ ተወስኗል፡፡

<u>ዉሳኔ</u>

1.የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት በኮ/መ/ቁ.213653 በ11/8/2014 ዓ.ም በዋለዉ ችሎት፤ የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍ/ቤት ይሄንን ጉዳይ በተመለከተ በኮ/መ/ቁ.269209 በ27/11/2013 ዓ.ም የሰጠዉን ፍርድ፤በማሻሻል የሰጠዉ ፍርድ በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ.348(1) መሰረት ፀንቷል፡፡

2.ግራ ቀኙ የዚህን ሰበር ችሎት ክርክር ወጪና ኪሳራ የየራሳቸዉን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ወደ መ/ቤት ይመለስ፡፡

የማይነብብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ብ/ም

ንብረት

የሰ/መ/ቁ. 197753

ቀን፡- የካቲት 24 ቀን 2014 ዓ/ም

ዳኞች፡- ብርሃኑ አመነው

ተሾመ ሽፈራው

ሀብታሙ እርቅይሁን

ብርሃኑ መንግሥቱ

ነፃነት ተገኝ

አመልካች፡- አቶ ሙሉጌታ ሩጋ - ቀረቡ

ተጠሪ፡- ወ/ሮ ፍሬሕይወት ተፈራ - ጠበቃ መሰረት አያሌው - ቀረቡ

መዝገቡ ተምርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሠጠ፡፡

ፍርድ

የሰበር አቤቱታው የቀረበው የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በሠጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈጽሞበታል በሚል ነው፡፡ የክርክሩን አመጣጥ ከስር ፍርድ ቤት የመዝገብ ግልባጭ እንደተረዳነው አመልካች የስር ተከሳሽ ሲሆኑ ተጠሪ ከሳሽ ነበሩ፡፡ ተጠሪ ሕዳር 05 ቀን 2009 ዓ/ም በተጻፈ የክስ ማመልከቻ ከአመልካች ጋር የነበረን ጋብቻ በፍቺ ፈርሶ የጋራ ንብረታችን የሆነ በአዲስ አበባ ከተማ ቦሌ ክፍለ ከተማ ወረዳ 01 የቤት ቁጥር 3099 መኖሪያ ቤት እንድንካፈል ውሳኔ አርፎበታል፡፡ ተጠሪ በኢትዮጵያ የማልኖር በመሆኑ ፍርዱን ማስፈጸምና ድርሻችን መካፈል አልቻልንም፡፡ አመልካች በጋራ ንብረቱን በመያዝ ከኪራይ የሚገኘውን ገቢ ለብቻቸው እየተጠቀሙበት በመሆኑ ክስ አቅርቤ እስከ ሐምሌ 06 ቀን 2001 ዓ/ም ድረስ ያለውን የኪራይ ገንዘብ እንዲያካፈሉ ተወስኗል፡፡ አመልካች ከነሀሴ 06 ቀን 2001 ዓ/ም ጀምሮ ክስ እስከቀረበበት ጊዜ ድረስ የጋራ ንብረቱን እያከራዩ ያገኙትን ገቢ ያላካፈሉኝ በመሆኑ የተጠሪን ድርሻ ብር 500,000.00 ከወለድ ጋር እንዲከፍሉ እንዲወሰንላቸው ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡ አመልካች ያቀረቡት መልስ ክሱ በይርጋ የታገደ ነው፡፡ በክሱ የተመለከተው ቤት የጋራ ንብረታችን ነው፡፡ ነገር ግን ቤቱ ያልተከፈለው ተጠሪ ባለመፈለጋቸው ነው፡፡ ከነሀሴ 06 ቀን 2001 ዓ/ም ጀምሮ ቤቱን አላካራየሁም፡፡ በአሁኑ ሰዓት ሁለት ክፍሎች ብቻ በወር በብር 3,000.00 ተከራይተዋል፡፡ በአንድ ወቅት ውጭ ሀገር ስለነበርኩኝ ቤቱን ዘግቼ ማንም ሳይከራይ ቆይቷል፡፡ ያገኘሁት ምንም ብልጽግና የሌለ በመሆኑ ክሱ ውድቅ ሊደረግ ይገባል በማለት ተከራክረዋል፡፡ አመልካች ባቀረቡት የተከሳሽ ክሳሽነት ክስ ለጋራ ንብረቱ ዕድሳት የወጣ ወጪ ብር 53,000.00 በመሆኑ ግማሽ ድርሻ ብር 26,500.00 እና የተጠሪ አባት የሚከራይ ቤት ይዘው ለአንድ ዓመት ስለኖሩ

በኪራይ ገንዘብ ታስቦ ድርሻዬ ብር 30,000.00 ተጠሪ እንዲከፍሉ በማለት ዳኝነት የጠየቁ ሲሆን ተጠሪ ባቀረቡት መልስ ቤቱ ስለመታደሱ የቀረበ ማስረጃ የለም፡፡ አመልካች በቤቱ ውስጥ ስለሚኖሩ በእኔ ምትክ አባቴ በቤቱ በነጻ መኖራቸው ተገቢ ነው፤ ኪራይ ገንዘብ ልከፍል አይገባም ብለዋል፡፡

የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 54271 የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያውን ውድቅ በማድረግ የግራ ቀኙን ማስረጃ ሰምቶ አመልካች የጋራ ሀበቱን በማከራየት ገቢ ያገኙ በመሆኑ የተጠሪ ደርሻ ብር 367,500.00 እንዲከፍሉና ቤቱ ላይ ለዕድሳት የወጣ ወጪ ብር 26,500.00 ተጠሪ ለአመልካች ሊከፍሉ ይገባል በማለት ወስኗል፡፡ አመልካች ያቀረቡትን ይግባኝ ተቀብሎ ያከራከረው የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 226240 ክሱ ያላግባብ መበልጸግን መሠረት አድርጎ የቀረበ በመሆኑ ለጉዳዩ ተፈጻሚነት ያለው የይርጋ ድንጋጌ በፍ/ሕ/ቁ. 2143(1) የተመለከተው የሁለት ዓመት ይርጋ ጊዜ ስለሆነ ከነሀሴ 06 ቀን 2001 ዓ/ም እስከ ሕዳር 05 ቀን 2007 ዓ/ም ድረስ ያለው የገንዘብ ዳኝነት በይርጋ የታገደ ነው፡፡ በይርጋ ላልታገደው ጊዜ አመልካች ብር 100,000.00 ለተጠሪ ሊከፍሉ ይገባል በማለት የሥር ፍርድ ቤት ውሳኔን አሻሽሎ ወስኗል፡፡ የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በበኩሉ ተጠሪ ያቀረቡት ክስ ከጋራ ሀብት የተሰበሰበ ገቢ ድርሻ ገንዘብ እንጂ ያላግባብ መበልጸግን መሠረት ያደረገ ባለመሆኑ የሁለት ዓመት ይርጋ ጊዜ መሠረት አድርጎ መወሰኑ ተገቢ አይደለም በማለት የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤትን ውሳኔ በመሻር የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ውሳኔን አጽንቷል፡፡

ይህ የሠበር አቤቱታ የቀረበው በዚህ ውሳኔ ነው፡፡ የአመልካች የሠበር አቤቱታ ይዘትም የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ያቀረብነውን መስቀለኛ ተቃውሞ በገምታ ማለፉ ተገቢ አይደለም፡፡ ክሱ የቀረበው አመልካች ያላግባብ በልጽጓል በሚል ነው፤ ከተጠሪ ጋር የውል ሆነ የሕግ ግንኙነት የለንም፡፡ ቤቱ ስለመከራየቱ ማስረጃ ላልቀረበበት ጊዜ በሙሉ ክፍያው መታሰቡ ስህተት ያለበት ነው፡፡ ከኪራይ ገንዘቡ ጋር የተያያዘ ማስረጃ እንዲቀርብ ጠይቀን ሳይቀርብና አመልካች እንዳይመሰክሩ ተደርጎ የተሰጠው ውሳኔ ተገቢ አይደለም የሚል ሲሆን የሰበር አጣሪ ችሎት ጉዳዩን ተመልክቶ አመልካች ንብረቱን በተጠሪ ፈቃድ የያዝኩት ነው በማለት ያቀረቡት ክርክር ውደቅ ተደርጎ የኪራይ ገንዘብ ይክፈሉ ተብሎ መወሰኑ ተገቢነቱን ለማጣራት ተጠሪ መልስ እንዲያቀርቡ ያዘዘ ሲሆን ተጠሪ የሰጡት መልስ በፍቺ ውሳኔ ቤቱ ላይ ክፍፍል እስኪደረግ እንጂ ለዘለቄታው አመልካች እንዲገለገሉበት ፈቃድ አልሰጠሁም፡፡ ከአመልካች ጋር የጋራ ባለሀብት ነን፤ ያላግባብ መበልጸግ ክስ የሚቀርበው ምንም መብት ሳይኖረው በያዘ ሰው ላይ ነው፤ ክሱ ያላግባብ መበልጸግን መሠረት አድርጎ የቀረበ አይደለም፡፡ የአመልካች መስቀለኛ ተቃውሞ በስር ውድቅ ተደርጓል፡፡ አመልካች በሥር ፍርድ ቤት በምስክርነት ቃላቸውን ሰጥተዋል፡፡ ውሳኔው ላይ የተፈጸመ ስህተት የለም ብለዋል፡፡ አመልካች ባቀረቡት የመልስ መልስ አመልካች ቃላቸውን የሰጡ መሆኑን ገልጸው ነገር ግን በጠበቃቸው ጥያቄ እንዳይጠየቁ ተደርጓል በማለትና የሰበር አቤቱታቸውን በማጠናከር ተከራክረዋል፡፡

የክርክሩ ሂደት በአጭሩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን እኛም የግራ ቀኙን ክርክር፣ የሠበር አጣሪ ችሎት የያዘው ጭብጥ፣ በሥር ፍርድ ቤት ከተረጋገጡ ፍሬ ነገሮችና ከሕጉ በማገናዘብ መዝገቡን መርምረናል።

እንደመረመርነው ተጠሪ ሕዳር 05 ቀን 2009 ዓ/ም በተጻፈ የክስ ማመልከቻ ከአመልካች ጋር በአዲስ አበባ ከተማ ቦሌ ክፍለ ከተማ ወረዳ 01 የቤት ቁጥር 3099 የጋራ መኖሪያ ቤት አለን። የጋራ ንብረቱን አመልካች እያከራዩ ያገኙትን ገቢ ያላካፈሉኝ በመሆኑ የተጠሪን ድርሻ ብር 500,000.00 ከወለድ ጋር እንዲከፍሉ የሚል ዳኝነት ጠይቀዋል። አመልካች የይርጋ መቃወሚያ ያቀረቡ ሲሆን በፍሬ ጉዳዩ ንብረቱ የጋራ ሀብት መሆኑን አምነው ተከራክረዋል። የፍትሐብሔር ጉዳይ የቀረበለት ፍርድ ቤት በቀዳሚነት እንዲያከናውን ከሚጠበቁበት ተግባራት ዉስጥ አንዱ እና መሠረታዊዉ ለቀረበለት ጉዳይ ተፈፃሚነት ያለዉ የህግ ክፍል የመለየት ተግባር (identification of applicable law) ነዉ። አስቀድሞ ይህን ማድረግ የቀረበዉ ክስ የክስ ምክንያት ያለዉ መሆን አለመሆኑ፣ ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን ለማየት ስልጣን ያለዉ መሆን አለመሆኑን እና ሌሎች የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያዎች ካሉ አስቀድሞ በመለየት መርምሮ ተገቢዉን ዉሳኔ ለመስጠት የሚያችለዉ ሲሆን፣ ጉዳዩ ወደ ሙሉ የክርክር ሂደት (full scale trial) የሚገባ ከሆነም በጉዳዩ ላይ ትክክለኛ ዉሳኔ ለመስጠት የሚያስችለዉን ጭብጥ ይዞ ክርክሩን በመምራት ለጉዳዩ ተፈፃሚነት ያለዉን ድንጋጌ በአግባቡ ለይቶ ፍትሐዊ ዉሳኔ ለመስጠት ያስችላል። በአጠቃላይ አስቀድሞ በጉዳይ ተፈፃሚነት ያለዉን የህግ ክፍል መለየት ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን ከክርክር አመራር ሥርዓት ጋር በተያያዘ በሥ/ሥርዓት ህጉ የተመለከቱትን ደንቦች እና ድንጋጌዎች መሠረት ባደረገ መልኩ ክርክሩን ይመራ ዘንድ ያስችለዋል። የክርክር አመራርን አስመልክቶ በህጉ በተመለከቱት ድንጋጌዎች መሠረት ጉዳዩን መምራት፣ የክርክር አመራሩ ፍትሐዊ እና ሚዛናዊ እንዲሆን በማድረግ የተከራካሪ ወገኖችን የመሰማት መብት እንዲከበር በማድረግ ሥነ ሥርዓታዊ ፍትሕ እንዲረጋገጥ የሚያስችል ከመሆኑም በላይ፤ ለጉዳዩ ትክክለኛ ጭብጥ በመያዝ፣ ተቀባይነት እና አግባብነት ያለዉን ማስረጃ ለይቶ በማስቀረብ እና በመመርመር ወሳኝ የሆኑ ፍሬ ነገሮች ነጥሮ እንዲወጡ በማድረግ ብሎም ለጉዳዩ ተፈፃሚነት ያለዉን የህግ ድንጋጌ ለይቶ ተፈፃሚ ለማድረግ የሚያስችል በመሆኑ በጉዳዩ ላይ ፍትሐዊ ዉሳኔ እንዲሰጥ ያስችላል።

በክስ አቤቱታ ላይ የሚገለጹ ነገሮችን አስመልክቶ በፍ/ብ/ሥ/ሥርዓት ህጉ አንቀጽ 222 ላይ ከሳሽ ለክሱ ምክንያት የሆኑትን ነገሮች እንዲሁም ተከሳሽ ለክሱ ምክንያት በሆነዉ ነገር ላይ በኃላፊነት የሚጠየቅበትን ሁኔታ ከሳሽ በግልጽ በክሱ ማካተት እንዳለበት፤ እንዲሁም የሚጠየቀዉ ዳኝነት በግልጽ መመልከት እንዳለበት በአንቀጽ 224 በአስገዳጅ መልክ ከደነገገባቸዉ ምክንያቶች ዉስጥ አንዱ ክስ የቀረበለት ፍርድ ቤት ለጉዳዩ ተፈፃሚነት ያለዉን የህግ ክፍል አስቀድሞ እንዲለይ ለማስቻል እንደሆነ ይታመናል። ክርክሩን በፍትሐ ብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕጉ መሰረት መምራት እና መቆጣጠር የፍርድ ቤቱ ኃላፊነት ሲሆን በተገቢው ሁኔታ ካልተመራ የሥነ-ሥርዓት ሕጉን ዓላማዎች የሆኑትን እንደ

አንጻራዊ እውነትን የመፈለግ፣ ሥነ-ሥርዓታዊ ፍትህ፣ ክርክርን ውጤታማ፣ ወጭና ጊዜ ቆጣቢ በሆነ አግባብ መምራት የመሳሰሉትን ማሳካት ስለማይቻል የተከራካሪዎችን መሠረታዊ መብት ይነካል። ክርክር የሚወሰነው በተጠየቀው ዳኝነት አግባብ እንደሆነ የፍብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 182(2) ላይ ተመልክቷል። ፍርድ ቤቱም ከቀረበው ዳኝነት አኳያ ከግራ ቀኙ ክርክር በመነሳት በፍብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 246 እና ተከታዮቹ መሠረት በተነሱት ጉዳዮች ጭብጥ መስርቶ ውሳኔ የመስጠት ኃላፊነት አለበት።

ከዚህ አንፃር የተያዘውን ጉዳይ ስንመለከት፣ ከፍ ሲል እንደተገለጸዉ፣ ተጠሪ ለክሱ መሰረት ያደረጉት የጋራ ሀብት ላይ የተገኘ ገቢ ያካፍለኝ የሚል በመሆኑ ክስ የቀረበው የፍ/ሕ/ቁ. 1257 እና ተከታይ ድንጋጌዎችን መሠረት ያደረገ በመሆኑ ለቀረበው የይርጋ መቃወሚያ ሆነ ለሥረ-ነገሩ ክርክር ተፈጻሚነት ያለው ይኸው የሕግ ክፍል ነው። የሥር ከፍተኛ ፍርድ ቤት ክሱ ያላግባብ መበልጸግን መሠረት ያደረገ ነው በማለት የፍ/ሕ/ቁ. 2143(1) የይርጋ ድንጋጌን ተፈጻሚ አድርጓል። ያላግባብ መበልጸግ በፍ/ሕ/ቁ. 2162 እንደተመለከተው በንብረቱ መብት የሌለው ሰው አላግባብ ንብረቱን በመያዝ ሲበለጽግ ኃላፊነት የሚከተልበት መሆኑን የሚደነግግ ነው። በተያዘው ጉዳይ አመልካች የንብረቱ የጋራ ባለሀብት እንጂ መብት ሳይኖራቸው ንብረቱን የያዙ ሰው ባለመሆናቸው ያላግባብ መበልጸግን መሠረት ተደርጎ ጉዳዩ ሊዳኝ የሚገባው አይደለም። በተጨማሪም የሥር ከፍተኛ ፍርድ ቤት ለይርጋው ተፈጻሚ ያደረገው የፍ/ሕ/ቁ. 2143(1) መሠረት ተደርጎ በሰበር መዝገብ ቁጥር 34406 የተሰጠው ትርጉም ሲሆን ይሕ ትርጉም በሰበር መዝገብ ቁጥር 78629 (በቅጽ 22 እንደታተመ) የተለወጠና ያላግባብ መበልጸገን መሠረት አድርጎ የቀረበ ክስ ቢሆን እንኳን ይርጋ ጊዜው በፍ/ሕ/ቁ. 1845 የተመለከተው የ10 ዓመት ጊዜ በመሆኑ ውሳኔ ስህተት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል።

ተጠሪ ያቀረቡት ከጋራ ሀብት የተገኘ የኪራይ ገንዘብ ያካፍሉኝ ክስ ሲሆን በፍ/ሕ/ቁ. 1170(2) እንደተመለከተው የንብረት ፍሬ ማለት ሀብቱ በየጊዜው የሚሰጠው አበልና ነገሩም እንደተመደበበት ጉዳይ ከዚህ ላይ ለመውሰድ ልማድ በሚፈቅደው መሠረት የሚገኝ ሁሉ ሲሆን አመልካችና ተጠሪ ያላቸው የጋራ የማይንቀሳቀስ ንብረት ተከራይቶ የሚገኘው ገቢ በድንጋጌው ማዕቀፍ ውስጥ የሚወድቅ ነው። በፍ/ሕ/ቁ. 1264(1) መሠረት ካልተከፋፈለው የጋራ ንብረት ላይ የሚገኘው ፍሬ፣ ጥቅም ያልተከፋፈለ እንደሆነና በንዑስ ቁጥር ሁለት ላይ እንደተደነገገው እያንዳንዱ የጋራ ባለሀብት በማንኛውም ጊዜ ክፍያ እንዲደረግ መጠየቅ ይችላል። ተጠሪም ያቀረቡት ክስ የጋራ ሀብቱ ላይ ከነሀሴ 06 ቀን 2001 ዓ/ም ጀምሮ ክስ እስከቀረበበት ሕዳር 05 ቀን 2009 ዓ/ም ጊዜ ድረስ በኪራይ የተገኘውን ገቢ አመልካች ሊያካፍሉኝ ይገባል የሚል በመሆኑና የጋራ ሀብት ላይ የሚገኝ ፍሬ ከጋራ ባለሀብቱ አንዱ ወገን ክፍያ እንዲደረግ ሲጠይቅ የሚከፋፈል በመሆኑ ክሱ በይርጋ ሊታገድ የሚገባው አይደለም ብለናል።

የክሱን ሥረ ነገር በተመለከተ አመልካች የጋራ ሀብት መሆኑን አምነው የሚከራከሩ በመሆኑ የጋራ ሀብቱ ገቢ አስገኝቷል ወይስ አላስገኝም? ገቢ ካስገኘስ ምን ያህል ነው? የሚለውን በፍ/ሕ/ቁ. 2001(1) እና በፍብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 259 እና 260 መሠረት የአንድን ፍሬ ነገር መኖር ጠቅሶ የሚከራከር ወገን ፍሬ ነገሩ ስለመኖሩ የማስረዳት ግዴታ ስላለበት የተጠሪ ግዴታ ነው፡፡ ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ማስረጃ በመስማትና በመመዘን የጋራ ሀብቱን በማከራየት የተገኘው የተጠሪ ድርሻ ብር 367,500.00 ስለመሆኑ ድምዳሜ ላይ ደርሷል፡፡ የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በኢፌዲሪ ሕገ-መንግሥቱ አንቀጽ 80(3) ሆነ የፌደራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀጽ 10 ላይ በመጨረሻ ውሳኔ ላይ በተፈጸመ መሠረታዊ የሕግ ስህተት እንጂ ማስረጃው ተመዝኖ የተደረሠበትን የፍሬ ነገር ድምዳሜ ላይ እንዲመለከት ሥልጣን አልተሠጠውም፡፡ በሥር ፍርድ ቤት የማስረጃ ምዘና ሂደት የተፈጸመ የማስረጃ ሕግና ማስረጃ ምዘና መርሕ ጥሰት መኖሩን የክርክሩ ሂደት አያሳይም፡፡ ስለሆነም በዚህ ረገድ አመልካች ያቀረቡትን የሠበር አቤቱታ አልተቀበልነውም፡፡

በሌላ በኩል አመልካች ገቢ ቢኖር እንኳን የማካፈል ኃላፊነት የለብኝም በማለት የሚከራከሩ ሲሆን የሚጠቅሱት ምክንያት ደግሞ ተጠሪ በባልና ሚስት የንብረት ክፍፍል ክርክር ጊዜ ንብረቱን አመልካች እንዲገለገሉበት ፈቅደዋል በማለት ነው፡፡ የባልና ሚስት ክርክር የተደረገበት የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የመዝገብ ቁጥር 18591 ላይ የተሰጠው ውሳኔ እንደተመለከትነው ተጠሪ የንብረት ክፍፍሉ ቢቆይና አመልካች ቢገለገሉበት ተቃውሞ የሌላቸው ስለመሆኑ በክርክሩ ሂደት የገለጹ ሲሆን ፍርድ ቤቱ ንብረቱን ግራቀኙ በዓይነት እንዲካፈሉ ወይም በጋራ እንዲገለገሉበት መወሰኑ ሲታይ የፍርድ ቤቱ ውሳኔ አመልካች ንብረቱን ለዘለቄታው በግል እንዲገለገሉበት ፈቃድ የማይሰጥ በመሆኑ ክርክሩ ተቀባይነት የለውም ብለናል፡፡ በአጠቃላይ የጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የከፍተኛ ፍርድ ቤት ውሳኔን በመሻር የሥር ፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ውሳኔን ማጽናቱ ላይ የተፈፈጸመ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ አላገኘነውም፡፡

ውሳኔ

1. የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 182937 ነሀሴ 13 ቀን 2012 ዓ/ም የሠጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥርዓት ሕጉ አንቀጽ 348(1) መሠረት ፀንቷል፡፡

2. በዚህ ችሎት ለወጣ ወጭና ኪሣራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

ትዕዛዝ

- የውሳኔው ግልባጭ ለስር ፍርድ ቤቶች ይተላለፍ፡፡
- አፈጻጸሙ ላይ የተሰጠ እግድ ካለ ተነስቷል፡፡ ይጻፍ

- መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ሄ/መ

የሰ/መ/ቁጥር 220031

ጥቅምት 03 ቀን 2015 ዓ/ም

ዳኞች፡- እትመት አሰፋ

ፀሐይ መንክር

ኑረዲን ከድር

መላኩ ካሣዬ

እስቲበል አንዱዓለም

አመልካች፡- አቶ ሸፋ ኢብራሂም፡- ጠበቃ አብዱራዚት ረሽድ - ቀረቡ

ተጠሪ፡- በሻዱ ቱፋ ዋንታሎ፡- አልቀረቡም

መዝገቡ የተቀጠረው ለምርመራ ሲሆን በዚሁ አግባብ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍርድ

ለዚህ የሰበር ክርክር መነሻ የሆነው ጉዳይ ሊቀርብ የቻለው አመልካች ጥር 20 ቀን 2014 ዓ.ም በተፃፈ ማመልከቻ የፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁ.281388 በቀን 20/04/2014 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስሕተት የተፈፀመበት መሆኑን ገልፀው በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት ያቀረቡትን አቤቱታ መነሻ ያደረገ ሲሆን አመልካች በፌደራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት 1ኛ ተከሳሽ የነበሩ ሲሆን ተጠሪ ከሳሽ ነበሩ፡፡

የአሁን ተጠሪ በስር ፍርድ ቤት በአሁን አመልካች እና በስር 2ኛ፣3ኛ እና 4ኛ ተከሳሾች ላይ ባቀረቡት የሁከት ይወገድልኝ ክስ ተጠሪ በአዲስ አበባ ከተማ በቀድሞው አጠራር ዞን 2 ወረዳ 24 ቀበሌ 17 በአሁኑ አጠራር ኮ/ቀ/ክ/ከተማ ወረዳ 07 የቤት ቁጥር አዲስ ነዋሪ ሲሆን ይህንን ይዞታዬን ከ1969 ዓ.ም ጀምሮ ይገፉው በእርሻ ስራ እየተጠቀምኩበት የምገኝ አርሶ አደር ስሆን የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ካቢኔ በ2010 ዓ.ም ባወጣው መመሪያ መሰረት በወረዳው የገበሬዎች ኮሚቴ፣ በወረዳው ግብርና አርሶ አደር ልማት ጽ/ቤት እና በወረዳው ካቢኔ ይዞታዬ

ተለክቶ 3324 ካሜ የተጠሪ መሆኑ ተረጋግጦ ወደ ኮ/ቀ/ክ/ከተማ የመሬት ይዞታ አስ/ጽ/ቤት/ለስር 4ኛ ተከሳሽ/ ተልኮለት ካርታ ሰርቶ መስጠት ሲገባው ካሳ ሳይከፈለኝና ምትክ ቦታ ሳይሰጠኝ አመልካች እና ለስር 2ኛ ተከሳሽ በይዞታዬ ላይ ካርታ ሰርቶ ሰጥቷል፡፡ የስር 3ኛ ተከሳሽ የግንባታ ፈቃድ በመስጠት የአሁን አመልካች ይዞታዬን ነጥቀው በውስጡ የፅቃ ማስቀመጫ ስቶር እና አጥር በመስራት የሁከት ተግባር ጥር 28 ቀን 2013 ዓም የፈጠሩብኝ ስለሆነ የሁከት ተግባር እንዲወገድልኝ፤ካርታውና የግንባታ ፈቃዱ እንዲመክንልኝ እና የተሰራው ስቶርና አጥር እንዲፈርስ ይወሰንልኝ በማለት አመልክተዋል፡፡

አመልካች በሰጡት መልስም አከራካሪው ይዞታዬ የተሰጠኝ ከአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በልማት ተነሺ ስለሆንኩ ባለቤት እንደሌለው እና ይዞታው የመንግስት ባዶ ቦታ መሆኑ ተረጋግጦ ነው፡፡ስለሆነም ተጠሪ በዚህ ይዞታ ላይ የሚጠይቁት መብትና ጥቅም ካለ ይዞታውን የሰጠኝን የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደርን ከሚጠይቁ በስተቀር አመልካችን የሚጠይቁበት አግባብ የለም በማለት በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ.33(2) መሰረት መቃወሚያ ያቀረቡ ሲሆን ከዚህ በተጨማሪም ተጠሪ ይዞታውን በይዞታቸው ስር አድርገውት የማያውቁ ለእርሻ አገልግሎትም ውሎ የማያውቅ በመሆኑ የይዞታውን አዋሳኝ ሲገልፁም በደቡብ በኩል መንገድ ያዋስነዋል ብለው መግለፃቸው ይዞታውን ይዘው የማያውቁ መሆኑን ስለሚያሳይ፤አመልካች በይዞታው ላይ ካርታ ያለኝ በመሆኑ በይዞታው ላይ የተሻለ መብት እንዳለኝ ስለሚያሳይ አያስከስስም ተብሎ መዝገቡ በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ.231(1)(ሀ) መሰረት ሊዘጋ ይገባል፤ይዞታው ከተጠሪ እጅ ወጥቶ በአመልካች እና በስር 2ኛ ተከሳሽ እጅ የሚገኝ በመሆኑ ከእጃቸው በወጣ ንብረት ላይ የመፋለም ክስ ከሚያቀርቡ በስተቀር ጥያቄው በሁከት ይወገድልኝ ክስ ሊስተናገድ ስለማይገባ ክሱ ውድቅ ሊደረግ ይገባል በማለት መቃወሚያ ያቀረቡ ሲሆን በፍሬ ጉዳዩ ላይ በሰጡት መልስም አከራካሪው ይዞታ ከሀያ አመት በፊት በአዲስ አበባ ከተማ ውስጥ ከተያዙ የማህበር ይዞታዎች መካከል አንዱ ሲሆን በኋላም ለልማት ተነሺዎች መሰጠት ተጀምሮ በአዲስ ከተማ ክ/ከተማ ወረዳ 6 ውስጥ የሚገኘው መኖሪያ ቤቴ በመልሶ ማልማት ስለፈረሰ አስተዳደሩ ከስር 3ኛ እና 4ኛ ተከሳሾች ጋር በመነጋገር ቦታው ባዶ ቦታ መሆኑን ከ6 ወር በላይ አጥንቶ በምትክነት የሰጠኝ በመሆኑ በይዞታው ላይ ግንባታ ያከናወንኩትም ተገቢውን የግንባታ ፈቃድ በመውሰድ በከተማው መሪ ፕላን መሰረት ስለሆነ ክሱ ውድቅ ሊደረግ ይገባል በማለት ተከራክረዋል፡፡

የፌደራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የስር ተከሳሾች ያቀረቡትን ክርክር በመስማትና ከሚመለከተው አካል ተገቢው ማስረጃ እንዲቀርብ አድርጎ በሰጠው ውሳኔም የወረዳ አስተዳደሩ አርሶ አደር ኮሚቴ ተጠሪ ህጋዊ ባለይዞታ መሆናቸውን ከመግለፁ በተጨማሪ ለኮልፌ ቀራኒዮ ክ/ከ/መ/ባንክና ማስተላለፍ ፅ/ቤት ደብዳቤ የላከ እና ይዞታውን በሚመለከት መብት ሊፈጠርላቸው ሂደት ላይ ሆኖ እያለ፤ለተጠሪ ምትክ ቦታ ወይም የካሳ ክፍያ ሳያዘጋጅ ወይንም የተጀመረውን የስነ

ስርዓት ሂደት በመጠበቅ መብት ሳይፈጥርላቸው ለአመልካችና ለስር 2ኛ ተከሳሽ ማስተላለፉ ህገ ወጥ እና ሁከት ተግባር መሆኑን፤ የወረዳው አርሶ አደር ኮሚቴ ከፃፈው ደብዳቤ አንፃር 4ኛ ተከሳሽም ሆነ የሚመለከተው አካል አስተዳደራዊ ውሳኔ ሊሰጥበት ይገባል፤አመልካችንና የስር 2ኛ ተከሳሽን በተመለከተ ባቀረቡት ማስረጃ አማካኝነት መብት የተፈጠረላቸው በመሆኑ ህጋዊ መብታቸውን በመመሪያና ደንብ መሰረት በመጠበቅ አስተዳደራዊ ውሳኔ ሊሰጥበት ይገባል፤ስለሆነም አስተዳደራዊ ውሳኔ ሊሰጥበት በሚገባው ጉዳይ በቀረበው የሁከት ይወገድልኝ ክስ ባለይዞታው ማን እንደሆነ ሊወሰን የማይገባ በመሆኑ በይዞታው ላይ 4ኛ ተከሳሽ አስተዳደራዊ ውሳኔ ከሰጠ በኋላ በህጋዊ መንገድ የሚመለከተውን አካል የመጠየቅ መብታቸውን በመጠበቅ ፍርድ ሰጥቷል፡፡ይህ ውሳኔ ጉዳዩን በይግባኝ በተመለከተው የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ፀንቷል፡፡

አመልካች በዚህ ውሳኔ ቅር ተሰኝተው ባቀረቡት የሰበር አቤቱታም የስር ፍርድ ቤት በፍርድ ሀተታው ላይ በግልጽ አከራካሪው ይዞታ አስተዳደራዊ ውሳኔ ከሚሰጥበት በቀር ይዞታው የማነው የሚለው ሊወሰን እንደማይገባ ድምዳሜ ላይ ደርሷል፡፡እዚህ ድምዳሜ ላይ የደረሰውም የወረዳው አርሶ አደር ኮሚቴ ለተጠሪ ከፃፈላቸው የድጋፍ ደብዳቤ ውጭ ከአመልካች እኩል የሚቆም ማስረጃ ስለሌላቸውም መሆኑን በሀተታው ተካትቷል፡፡ነገር ግን ከዚህ ፍፁም ተቃራኒ በሆነ መንገድ የስር ፍርድ ቤት በሰጠው ትዕዛዝ ተራ ቁጥር 1 ላይ የከተማው አስተዳደር ተጠሪ በቦታው ላይ መብት እያላቸው ለአመልካች ማስተላለፉ የሁከት ተግባር ነው በማለት እርስ በእርሱ የሚጋጭ ተገቢነት የሌለው ውሳኔ ሰጥቶብናል፡፡ፍርድ ቤቱ ሁከት አለ ብሎ ሲያበቃ የስር 4ኛ ተከሳሽ ተጠሪን ጨምሮ ጉዳዩን በአስተዳደራዊ መንገድ መፍትሔ እንዲሰጥበት በመወሰን ጉዳዩን የበለጠ እርስ በእርሱ የሚጋጭ አድርጎብናል፡፡

ከመነሻው የስር ፍርድ ቤት ተጠሪ ገና ሙሉ በሙሉ መብት ስላልተቋቋመላቸው ቦታው የማነው የሚለውን ለመወሰን የማይቻል መሆኑን ካመነበት ሕጋዊ ካርታ ላለን ለአመልካች መወሰን ወይም በቂ ማስረጃ አልቀረበም ብሎ መዝጋት ይችላል፡፡የስር ፍርድ ቤት በተቃራኒው የሰጠው እርስ በእርሱ የሚጋጭ ውሳኔ የአመልካችን መብት በእጅጉ ጎድቶታል፡፡የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤትም ይህንን ጉዳይ በአግባቡ ሳይመረምረው ይግባኙ አያስቀርብም ማለቱ መሰረታዊ ሕግ ስሕተት ነው፡፡ስለሆነም የፌደራል መጀመሪያ ደረጃ የሰጠው ውሳኔ እና የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የስር ፍርድ ቤት ውሳኔን በማፅናት የሰጠው ብይን ባቀረብነው የሰበር አቤቱታ መሰረት ሙሉ በሙሉ እንዲሻርልን በማለት አመልክተዋል፡፡

የስር ፍርድ ቤት አከራካሪ የሆነውን ይዞታ በተመለከተ በአስተዳደራዊ መንገድ እንዲታይ ውሳኔ ከሰጠ በኋላ የተፈጠረው ሁከት ይቁም ሲል ውሳኔ መስጠቱ ህጋዊ መሆን አለመሆን ለማጣራት ጉዳዩ ለሰበር ችሎት ያስቀርባል ከተባለ በኋላ ተጠሪ በሰጡት መልስም የስር ፍርድ ቤት ጉዳዩ

በአስተዳደር ይታይ ያለው ከተፈጠረው የሁከት ተግባር አኳያ ሳይሆን አመልካች በአስተዳደር ጠይቆ እንዲወስድና ጉዳዪ በአስተዳደር እልባት የሚያገኝ ነው አለ እንጂ ተጠሪ በመመሪያ ቁጥር 20/2013 መሰረት እንዲሁም መመሪያውን ለማሻሻል በወጣው መመሪያ ቁጥር 1/2013 በቀን 01/02/2014 ዓ.ም ተሻሽሎ በወጣው መመሪያ አንቀጽ 9(16) አርሶ አደሩ በማንኛውም ጊዜ ያለ አግባብ መሬቱ ለሌላ ሰው ተላልፎብኛል ብሎ ቅሬታ ለሚመለከተው አካል ሲያቀርብና ተጣርቶ ውሳኔ ሲሰጠው ቀደም ሲል በአርሶ አደር መሬት ላይ የተሰጠው ካርታ መክኖ መሬቱ ለአርሶ አደሩ ይመለሳል ብሎ የወጣ መመሪያ በመፃረር የስር 3ኛ እና 4ኛ ተከሳሾች የተጠሪን ይዞታ ሳያሳውቁኝ ካሳና ምትክ ቦታ ሳይሰጡኝ ካርታ መስጠቱና አመልካች በተጠሪ ይዞታ ላይ ግንባታ ለመገንባት መንቀሳቀሱ የሁከት ተግባር ነው ተብሎ በስር ፍ/ቤት ከፍ/ብ/ሕ/ቁ.1140-1149(1) መሰረት መወሰኑ እና የከፍተኛው ፍርድ ቤትም ይህንን ማጽናቱ መሰረታዊ የሕግ ስሕተት የለበትም ተብሎ ውሳኔው እንዲፀናልኝ በማለት ተከራክረዋል፡፡

አመልካች የመልስ መልሳቸውን በማቅረብ ክርክራቸውን አጠናክረዋል፡፡

በአጠቃላይ የግራ ቀኙ ክርክር ከላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም የሰበር ክርክሩን ያስቀርባል ከተባለበት ነጥብ፣ከተገቢው ሕግና ከስር ፍርድ ቤት ክርክር አንፃር እንደሚከተለው መርምረናል፡፡የሁከት ይወገድልኝ ክስ እና የባለሃብትነት ክስ ሁለቱም ከንብረት መብት የሚመነጩ ቢሆኑም ከክርክሩ አድማስ እና በፍሬ ነገር ደረጃ ተከራካሪዎች ሊያረጋግጡት ከሚገባው መሰረታዊ ጭብጥ አኳያ የተለያየ መነሻ እና ውጤት ያላቸው ህጋዊ መብቶች ናቸው፡፡ የአንድ ንብረት ባለይዞታ የሆነ ሰው ንብረቱን በተመለከተ በህግ ከተረጋገጡለት መብቶች ውስጥ አንዱ በሀብቱ ላይ የተፈጠረው ህገ ወጥ ሁከት እንዲወገድለት የሁከት ይወገድልኝ ክስ ማቅረብ ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁጥር 1149(1) ይደነግጋል፡፡ በዚህ መልኩ ክስ የሚያቀርብ ሰው ማረጋገጥ የሚጠበቅበት ዋና ዋና ፍሬ ነገሮች ሁከት ተፈጠረበት የተባለውን ንብረት/ሀብት/ ባልተጭበረበረ መንገድ በእጁ አድርጎ በእውነት የሚያዝበት መሆኑን እና በዚሁ ይዞታው ላይ በተከሰሰው ሰው/አካል ህገ ወጥ በሆነ መንገድ ሁከት የተፈጠረበት መሆኑን ስለመሆኑ ከፍ/ብ/ህ/ቁ/1140፣ 1146 እና 1149 ድንጋጌዎች ጣምራ ንባብ መረዳት ይቻላል፡፡ በዚህ አግባብ በቀረበ ክስ ላይ ሁከት ተፈጥሯል ተብሎ ውሳኔ የሚሰጠውም የተከሰሰው ሰው የሌላ ሰው ይዞታ መያዙ አልያም በይዞታው ላይ ሁከት መፍጠሩ ሲረጋገጥ እና የሁከት ክስ የቀረበበት አካልም የሥራውን አደራረግ የሚፈቅድ ለእርሱ የሚናገርለት መብት መኖሩን በፍጥነት እና በማይታበል ዓይነት ሳያስረዳ ሲቀር ስለመሆኑ ከዚሁ ድንጋጌ ንዑስ ቁጥር 1 እና 3 ይዘት መረዳት ይቻላል፡፡

በአንፃሩ የባለሃብትነት መብት የማይንቀሳቀስ ንብረት ባለሃብት የሆነ ሰው ከንብረቱ ላይ መብት ሳይኖረው ከህግ አግባብ ውጭ ንብረቱን በእጁ ባደረገው ሰው ወይም ንብረቱን በያዘው አካል ላይ

ክስ በማቅረብ የሚያስመልስበት ህጋዊ መብት (Right to bring Petutary Action) ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ/1206 ድንጋጌ ያስገነዝባል፡፡ በዚህ ድንጋጌ መሰረት ክስ የሚያቀርብ ሰው ለክርክሩ ምክንያት የሆነውን ንብረት በእጁ አድርጎ በእውነት የሚያዝበት ስለመሆኑ ማረጋገጥ አይጠበቅበትም፡፡ ይልቁንም በንብረቱ ላይ በህግ የተቋቋመ የባለሃብትነት መብት ያለው መሆኑን፤ ይህንኑ ንብረቱን ምንም መብት ወይም የተሻለ መብት የሌለው ሰው/አካል/ የወሰደበት መሆኑን ማረጋገጥ ነው፡፡

አሁን በያዝነው ጉዳይ ተጠሪ በስር ፍርድ ቤት የሁከት ይወገድልኝ ክስ ያቀረቡ ሲሆን በዚህ ክሳቸውም በአከራካሪው ይዞታ ላይ የቀደመ የተረጋገጠ በአርሶ አደርነት ይዞታውን የመያዝ መብት እያላቸው አመልካች ይዞታቸውን ነጥቀው በውስጡ የዕቃ ማስቀመጫ ስቶር እና አጥር በመስራት የሁከት ተግባር የፈጠሩባቸው መሆኑን በመጥቀስ የሁከት ተግባሩ እንዲወገድላቸው፤ለአመልካች የተሰጠው ካርታና የግንባታ ፈቃዱ እንዲመክንላቸው መጠየቃቸውን የስር ፍርድ ቤት መዝገብ ያሳያል፡፡ከላይ እንደተመለከተው አመልካች የሁከት ይወገድልኝ ክስ በማቅረብ በይዞታው ላይ የተፈጠረው ሁከት እንዲወገድላቸው በህጉ አግባብ ሊጠይቁ የሚችሉት ሁከት ተፈጠረበት የተባለውን ንብረት/ሀብት/ ባልተጭበረበረ መንገድ በእጁ አድርጎ በእውነት የሚያዝበት መሆኑን በቅድሚያ ሲያረጋግጡ ቢሆንም አሁን በያዝነው ጉዳይ አመልካች አከራካሪውን ለአመልካች የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ የተሰጠበትን 90 ካሜ ይዞታ በእጃቸው አድርገው ሲጠቀሙበት የነበረ መሆኑን ማስረዳታቸውን የስር ፍርድ ቤት መዝገብ አያሳይም፡፡

የወረዳው አርሶ አደርና ከተማ ግብርና ልማት ፅ/ቤት በ20/08/2013 ዓ/ም ተጠሪ የልማት ተነሺ አርሶ አደር መሆናቸውንና መንደር 5 ከቶታል ጀርባ የሚገኘው ቦታ **<u>ቀደም ሲል</u>** በእርሻ እና በግጦሽ ሲጠቀሙበት የነበረ መሆኑን ከመግለፅ ውጪ አመልካች የይዞታ ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ያገኙበት ይዞታ በተጠሪ እጅ ሆኖ በእውነት የሚያዙበት ሆኖ በክሱ ላይ በተመለከተው ጊዜ አመልካች ይዞታውን በሀይል በመያዝ በህገ ወጥ መንገድ አጥር ያጠሩበትና መጋዘን የሰሩበት መሆኑን የተረጋገጠበት መሆኑን አያሳይም፡፡ ከዚህ ይልቅ በወረዳው የአርሶ አደር ኮሚቴዎች እና የወረዳው ዋና ስራ አስፈፃሚ በ08/10/2013 ዓ.ም የተያዘው ቃለ ጉባኤ ለአመልካች የተሰጣቸው ይዞታ ታጥሮ የሚገኝ መሆኑን የሚያመለክት መሆኑና በክፍለ ከተማው የመሬት ልማት ማኔጅመንት ፅ/ቤት የመሬት ይዞታ አስተዳደር ጽ/ቤት ባለሙያ ግራ ቀኙ በተገኙበት በማጣራቱ ሂደት የያዘው ቃለ ጉባኤ የአመልካች ይዞታ በአመልካች በቆርቆሮ ታጥሮ የተያዘ ይዞታ መሆኑን መግለፁ አከራካሪው ይዞታ በተጠሪ እጅ ያልነበረና ያልተያዘ መሆኑን ያሳያል፡፡

የሁከት ይወገድልኝ ክስ ለማቅረብ የሚያስችለውን በዚሁ ይዞታው ላይ በተከሰሰው ሰው/አካል ህገ ወጥ በሆነ መንገድ ሁከት የተፈጠረበት መሆኑን የማረጋገጥ ግዴታን በተመለከትም አመልካች

ለአከራካሪው ይዞታ ከተገቢው የአስተዳደር አካል የይዞታ ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት እና የግንባታ ፈቃድ በማግኘት ማከናወናቸው መረጋገጡም ሁለተኛው የህጉ መሰረታዊ መስፈርት ያልተሟላ መሆኑን ያሳያል፡፡

እነዚህ ዝርዝር ሁኔታዎች ደግሞ ከመነሻውም ተጠሪ ያቀረቡት ክስ በሁከት ይወገድልኝ የክርክር ስርዓት ቀርቦ ሊስተናገድ የማይገባው መሆኑን እያሳዩ የስር የፌደራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በተጠሪ የቀረበው የሁከት ይወገድልኝ ክስ ባለይዞታው ማን እንደሆነ መወሰንን የሚጋብዝ መሆኑን እያመለከተ ይህ ከሆነ ደግሞ የግራ ቀኙ ክርክር ባለሀብትነትን በመፋለም ክስ እልባት ሊያገኝ የሚገባው መሆኑን በማመልከት የቀረበውን የሁከት ይወገድልኝ ክስ ውድቅ ሊያደርገው ሲገባ ይዞታውን የስር 4ኛ ተከሳሽ ለአመልካች ማስተላለፉ የሁከት ተግባር ነው በማለት መወሰኑና ከዚህም በማለፍ በስር 4ኛ ተከሳሽ ላይ ከተጠየቀው ዳኝነት ውጪ በአመልካች ይዞታ ላይ አስተዳደራዊ ውሳኔ እንዲሰጥ መወሰኑ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት በመሆኑ ጉዳዩን በይግባኝ የተመለከተው የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤትም ይህንን ከክርክር አመራር ስነ-ስርዓት አንፃር በስር ፍርድ ቤት የተፈፀመን ግድፈት ሊያርም ሲገባ ማፅናቱ አግባብነት ያለው ሆኖ ስላልተገኘ የሚከተለው ተወስኗል፡፡

ውሳኔ

1. የፌደራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁ.290115 ጥቅምት 09 ቀን 2014 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጠው ፍርድ እና ይህንን ፍርድ በማፅናት የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ. 281388 በቀን 20/04/2014 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጠው ብይን በፍ/ስ/ስ/ሕ/ቁ.348(1) መሰረት ተሽሯል፡፡
2. ተጠሪ ያቀረቡት የዳኝነት ጥያቄ በሁከት ይወገድልኝ ክስ ክርክር አግባብ ሊስተናገድ የሚችል አይደለም ብለናል፡፡
3. ይህ ውሳኔ ተጠሪ በይዞታው ላይ አለኝ የሚሉትን መብት ባለቤትነትን የመፋለም ክስ በማቅረብ ከማረጋገጥ የሚያግዳቸው አይደለም ብለናል፡፡
4. የስር ፍርድ ቤት መዝገብ በመጣበት አኳኋን ይመለስ፡፡
5. ግራ ቀኙ በሰበር ክርክሩ ምክንያት ያወጡትን ወጪና ኪሳራ ይቻቻሉ፡፡

ጉዳዩ ውሳኔ ስላገኘ መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሠ/ኃ

የሰ.መ.ቁ.220882

ጥር 30 ቀን 2015 ዓ.ም

ዳኞች፡- እትመት አሠፋ

ደጀኔ አያንሳ

ብርቅነሽ እሱባለው

ሐብታሙ እርቅ ይሁን

ብርሃኑ መንግስቱ

አመልካች፡- ወ/ሮ እሌኒ መኮንን - ተወካይ አቶ ተፈሪ በየነ

ተጠሪ፡- አቶ ጢቆ ደግፌ - አልቀረቡም

መዝገቡ ለምርመራ የተቀጠረ ነው፡፡ በመሆኑም መርምረን ተከታዩን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍርድ

የሰበር አቤቱታው ሊቀርብ የቻለው አመልካች የካቲት 04 ቀን 2014 ዓ.ም ጽፈው ባቀረቡት የሰበር አቤቱታ በኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ.ቁ 377515 ሕዳር 28 ቀን 2014 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስሕተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል በማለት አቤቱታ በማቅረባቸው ነው፡፡

ጉዳዩ የከተማ ይዞታን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው በኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ቢሾፍቱ ከተማ ወረዳ ፍ/ቤት ነው፡፡ በሥር ፍ/ቤት በተደረገው ክርክር የአሁን ተጠሪ ከሳሽ፤ አቶ ዳኛቸው ቦጋለ የተባሉ ግለሰብ ተከሳሽ፤ የአሁን አመልካች ደግሞ ጣልቃ ገብ በመሆን ተከራክረዋል፡፡ የአሁን ተጠሪ በስር ፍርድ ቤት ያቀረቡት ክስ ይዘት በአጭሩ፡- አዋሳኙ በክሱ የተገለጸ በቢሾፍቱ ከተማ ጎርባ ቀበሌ ውስጥ የሚገኝ 1.5 ጥማድ መሬት ከደርግ ጊዜ ጀምሮ ግብር እየገበርኩ እራሴም አከራይቼም ስጠቀምበት የነበረ ነው፤ በተጠሪ እና በአመልካች መካከል የነበረው የመሬት ኪራይ ውል በ2008 ዓ.ም ተጠናቆ መሬቱን ለመጠቀም ስሄድ ተከሳሹ መብት ሳይኖረው ከልክሎኛል፤ በሕገ ወጥ መንገድም ይዞብኛል፤ ስለሆነም በሕገ ወጥ መንገድ የገነባውን ቤት እና አጥር አፍርሶ ይዞታውን እንዲያስረክብ ይወሰንልኝ በማለት ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡

የስር ተከሳሽ በሰጡት መልስ የያዝኩት መሬት የለም፤ ክስ የቀረበበት የመኖሪያ ቤት እና ቦታ በ1994 ዓ.ም አመልካች የገዛችው ሆኖ በጥበቃ ተቀጥሬ የምጠብቀው እንጂ በጉልበት የያዝኩት አይደለም ባለንብረቷን መጠየቅ ስለሚቻል ክሱ አይመለከተኝም በማለት መልስ ሰጥቷል፡፡

የአሁን አመልካች ባቀረቡት የጣልቃ ገብነት ክርክር 20 ቅጠል ቆርቆሮ መኖሪያ ቤት ያረፈበት 1250 ካ.ሜ የግል ይዞታዬ ነው፤ ቤት እና ይዞታውን በቀን 06/10/1994 ዓ.ም ከተጠሪ የገዛሁት ነው፤ መሬቱ የእርሻ መሬት ሳይሆን በአሁኑ ወቅት በቢሾፍቱ ከተማ ጎርባ ቀበሌ ውስጥ የሚገኝ መኖሪያ ቤት ነው፤ ክስ የቀረበበት ይዞታ ተጠሪ የሸጠልኝ ብቻ ሳይሆን ከሌሎች ሰዎች የገዛሁትን ንብረት እና ይዞታ በአሁኑ ወቅት አልምቼ የያዝኩትን በአንድ ላይ በማጠቃለል አቅርቦታል፤ ክሱን በተመለከተ 1250 ካ.ሜ አዋሳኙ በምስራቅ የአቶ አሊ አሰፋ እና ወ/ሮ መስታወት መርጋ ይዞታ፤ በሰሜን የህዝብ መንገድ፤ በምዕራብ የአቶ ዮሴፍ ገመቹ መኖሪያ ቤት፤ በደቡብ የአለምሸት ኃይለጊዮርጊስ መኖሪያ ቤት ያዋስኑታል፤ ሌላ ድንበር የለውም፤ ይህንን ደግሞ ሸጦልኛል፤ አቶ አሊ አሰፋ እና ወ/ሮ መስታወት መርጋ በፍርድ ቤት ተካሰው ንብረታቸውን ሸጠው እንዲካፈሉ በመታዘዙ በቀን 01/09/1994 ዓ.ም ንብረቱ በሚገኝበት ቀበሌ በኩል በ1000 ካ.ሜ ቦታ ላይ የሚገኘውን 30 ቅጠል ቆርቆሮ ቤት ሸጠውልኛል፤ በዚያው አጠገብ ሌላ ይዞታ አለኝ፤ በተንኮል አጠቃሎ አቅርቦታል፤ ከ1994 ዓ.ም ጀምሮ ቤት እና የዶሮ ቤት በመስራት የመንግስት ግብር የከፈልኩበት በቦታ መለያ ቁጥር 29766 በባለቤቱ አቶ ንጉሴ ዲንቃ ስም የተመዘገበ ነው፤ ክሱም በይርጋ ይታገዳል በማለት ተከራክረዋል፡፡

ተጠሪ እና የስር ተከሳሽ በአመልካች /በጣልቃ ገብ/ ክርክር ላይ መልስ እንዲሰጡበት ታዞ ባለመቅረባቸው መልስ ለማቅረብ ፍላጎት እንደሌላቸው ተቆጥሮ መብታቸው የታለፈ መሆኑን መዝገቡ ያመለክታል፡፡

ጉዳዩ የቀረበለት ፍ/ቤት የግራ ቀኙን ምስክሮች ከሰማ እና ከሚመለከተው የአስተዳደር አካል ስለጉዳዩ ተጣርቶ እንዲቀርብለት ካደረገ በኋላ ተከሳሽ ከጣል ቃገብ / ከአመልካች / ጋር በቀን 07/06/2008 ዓ.ም የጥበቃ ውል ፈጽመው ተቀጥሮ ሲሰራ መቆየቱ ስለተረጋገጠ ንብረቱን በኃይል ይዟል ተብሎ የሚያስከስሰው ነገር የለም፤ ክርክር ያስነሳው 1000 ካ.ሜ ይዞታ የባልና ሚስት ንብረት ሲሆን በፍርድ ቤት ትዕዛዝ እንዲካፈሉ በተደረገው መሠረት በቀን 01/09/1994 ዓ.ም ከአቶ አሊ አሰፋ እና መስታወት መርጋ በመግዛት ሕጋዊ አድርገዋል፤ በቀን 06/10/1994 ዓ.ም በተጠሪ እና በጣል ቃገብ / አመልካች / መካከል በተደረገው ውል በ 1250 ካ.ሜ ላይ የሚገኘውን መኖሪያ ቤት በማዳበሪያ ዕዳ በመያዙ ለአመልካች የተሸጠ ሲሆን ቀበሌው ይህንኑ ያረጋገጠው ጉዳይ ነው፤ የአመልካች ምስክሮች አመልካች ክርክር ያስነሳውን ቦታ በሕጋዊ መንገድ ከቤት ጋር ከገዛች በኋላ የተለያየ ተክል እና ባሕርዛፍ በመትከል ትልቅ የዶሮ እርባታ ቤት ሰርታበት ከ1994 ዓ.ም አንስቶ አየተጠቀመችበት የምትገኝ መሆኑን አረጋግጠዋል፤ ተጠሪ አከራካሪውን መሬት በኮንትራት ሰጥቻለሁ ያለ ቢሆንም ይህን የሚደግፍ ማስረጃ አላቀረበም፤ ከቀበሌው ጽ/ቤት በቀን 03/03/2013 ዓ.ም የተጻፈው ደብዳቤ እና ተያይዞ የቀረበው ቃለ ጉባኤ አከራካሪው መሬት ከ1994 ዓ.ም በፊት በአቶ አሊ አሰፋ እጅ የነበረ እና አሁን ደግሞ ባልና ሚስት ሸጠውት በወ/ሮ እሌኒ መኮንን / አመልካች / እጅ እንደሚገኝ፤ የተጠሪ መሬት በቤት ሽያጭ አማካኝነት በአመልካች እጅ የገባ መሆኑን እና ከ2000 ዓ.ም ጀምሮ አመልካች የምትገብርበት መሆኑን

በመግለጽ ምላሽ ልኳል፤ የተጠሪ ጠበቃ የኮንትራት ውሉን እንዲያቀርብ ፍርድ ቤቱ ቢፈቅድም ማቅረብ ስላልቻለ መብቱ ታልፏል፤ ተጠሪ የመኖሪያ ቤት ቦታውን በሕጋዊ መንገድ ለአመልካች ከሸጠ በኋላ ተከሳሹ እንዲጠብቅላት በውል ስምምነት ቀጥራ በሚጠብቀው ግለሰብ ላይ ያቀረበው ክስ መብት በሌለው ንብረት ላይ ያቀረበው ስለሆነ ተቀባይነት የለውም በማለት ውድቅ አድርጎታል፡፡

ተጠሪ ይህን ውሳኔ በመቃወም እቴነሽ መኮንን የተባሉ ግለሰብን መልስ ሰጪ አድርገው ለምስራቅ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት የይግባኝ አቤቱታ አቅርበዋል፡፡ ይግባኙ የቀረበለት ፍርድ ቤትም ግራ ቀኙን ካከራከረ በኋላ የመዝገቡ መልስ ሰጪ ምስክሮች የግዢ እና የሽያጭ ውሉን እንደሚያውቁ አሳማኝ በሆነ ሁኔታ አስረድተዋል፤ ከተለያዩ አካላት በትዕዛዝ ተጣርቶ የቀረበው ማስረጃም ይህንኑ የሚረጋግጥ ነው፤ ውሉ የተደረገው በ1994 ዓ.ም በመሆኑ እና በገጠር መሬት ላይ የተሰራውን ቤት የገዛ ሰው አፍርሶ ያነሳል ተብሎ የተደነገገው ደግሞ በ1999 በወጣው ሕግ በመሆኑ በሕገ ወጥ መንገድ የተደረገ ግዢ ነው ማለት አይቻልም፤ አሊ አሰፋ እና ከባለቤቱ የተገዛው በቀበሌ አስተዳደር እውቅና ስለመሆኑ ተረጋግጧል፤ የባለይዞታነት ማስረጃው በባለቤቷ ስም መኖሩ የግብር ክፍያው በሚስት ስም መሆኑ የባልና ሚስት ይዞታ የጋራ ስለሆነ እርስ በእርሱ አይስማማም በማለት የቀረበው ክርክር የሕግ ድጋፍ የለውም፤ አከራካሪው መሬት በክርክሩ እንደተገለጸው ሳይሆን 2752.50 ካ.ሜ መሆኑን እና መልስ ሰጪዋ ከተጠሪ እና አሊ ከተባለ ግለሰብ የገዛችው ድንበርተኛ መሆኑ የቢሾፍቱ ከተማ መሬት አስተዳደር ከሰጠው ምላሽ ተረጋግጧል፤ መልስ ሰጪ በሕጋዊ መንገድ ከገዛችው የመሬት ይዞታ ውጪ ያለው 462.50 ካ.ሜ መሆኑ ተረጋግጧል፤ መልስ ሰጪ ይህ መሬት የእርስዋ መሆኑን የሚያረጋግጥ ማስረጃ አላቀረበችም፤ ጠበቃዋ በፍርድ ቤቱ ባቀረበው ክርክርም ይዞታውን ከቤት ጋር ገዝተው በሕጋዊ መንገድ የያዙትን መሬት ብቻ የሚመለከት መሆኑን በመግለጽ የተከራከረ በመሆኑ 462.50 ካ.ሜ ይዞታ የመልስ ሰጪዋ አይደለም፤ ስለሆነም መልስ ሰጪ ከይግባኝ ባይ ከአሊ ገዝታ በሕጋዊ መንገድ የያዘችው መሬት ተያይዞ የሚገኝ መሆኑ የተረጋጠ በመሆኑ ለክርክሩ ምክንያት ከሆነው 2712.50 ካ.ሜ መሬት ውስጥ 462.50 ካ.ሜ ለተጠሪ እንድትለቅ ሲል የወረዳው ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሳኔ በማሻሻል ወስኗል፡፡

ተጠሪ በመቀጠል የአሁን አመልካችን በመልስ ሰጪነት በመሰየም ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የይግባኝ አቤቱታ ያቀረቡ ቢሆንም አቤቱታቸው ተቀባይነት አላገኘም፡፡

ተጠሪ በመቀጠል ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የአሁን አመልካችን በተጠሪነት በመሰየም የሰበር አቤቱታ አቅርበዋል፡፡ አቤቱታው የቀረበለት ፍርድ ቤትም ግራቀኙን ካከራከረ በኋላ በስር ፍርድ ቤቶች የተሰጠውን ውሳኔ አሻሽሎ አከራካሪውን ይዞታ ተጠሪ ከአቶ አሊ አሰፋ እና ከወ/ሮ መስታወት መርጋ የገዛችው መኖሪያ ቤት በ 1000 ካ.ሜ ላይ አርፎ የሚገኘው የሌሎች ሰዎች ይዞታ መሆኑ መረዳት ስለተቻለ ተጠሪ መጠየቅ አይችልም፤ በአመልካች እና በተጠሪ መካከል በ1994 ዓ.ም

ክርክር ባስነሳው ቤት ላይ የተፈጸመው የግር እና ሽያጭ ስምምነት የሕገ መንግስቱን እና የሕጉን ተጻራሪ መሆኑን ስለተረዳን የሚጸና ውል አይደለም። ስለሆነም አመልካች የያዘችውን ይዞታ እና ንብረት ለተጠሪ መልቀቅ አለባት በማለት አሻሽሎ የወሰነ ሲሆን አመልካች ከውልም ሆነ ከውል ውጪ የያዘችውን ይዞታ 462.50 ካ.ሜ በከፍተኛው ፍርድ ቤት የተወሰነውን ጨምሮ አዋሳኙን እና ስፋቱን በባለሙያ ለይቶ ካጣራ በኋላ ፍትሐዊ ውሳኔ እንዲሰጥበት በማለት ጉዳዩን ለወረዳው ፍርድ ቤት መልሶለታል።

አመልካች የካቲት 24 ቀን 2015 ዓ.ም ጽፈው ያቀረቡት የሰበር አቤቱታ ይህን ውሳኔ በመቃወም የቀረበ ሲሆን ይዘቱም፡- ጥያቄው የመሬት ኮንትራት ሰጥቼዋለሁ የሚል እንጂ አመልካች በቦታው ላይ ቀድሞ ገዝቼ የነበረውን ቤት እና አድሼ እና ጨምሬ የሰራሁትን ቤት አያጠቃልልም። ሊታይ ይገባቸው የነበሩት ነጥቦች ይዞታው የእርሻ ቦታ ነው ወይስ ቤት ያረፈበት ግቢ። በውል በኪራይ ተሰጥቷል ወይስ አልተሰጠም። ቤቱ የሚገኘው በከተማ ክልል ነው ወይስ በገጠር ክለል የሚሉት ሊሆኑ ይገባ ነበር። የእርሻ ቦታ መሆኑን እና ባዶ መሬት በውል በኮንትራት መስጠቱን የማስረዳት ሸክሙ የተጠሪ ሊሆን ይገባ ነበር። ይዞታውን ስትገዛ የገጠር መሬት ነበር በማለት ለ20 ዓመታት ከኖርኩበት ቤት እንድፈናቀል መደረጉ ግፍ ነው። ይዞታው የእርሻ ነው ቢባል እንኳን ከ12 ዓመት በኋላ የቀረበው ክስ በይርጋ ይታገዳል። ቤቱን የገዛሁት በ1994 ዓ.ም ሆኖ በኋላ በወጣው አዋጅ ቁጥር 130/1999 መታየቱ አግባብ አይደለም። ውሉ አልተመዘገበም የተባለ ቢሆንም በወቅቱ ተመዝግቦ ለ12 ዓመታት የባለይዞታነት ወረቀት ከቀበሌ እስከ ወረዳ ተሰጥቶኛል። አሁንም ለ8 ዓመታት በቢሾፍቱ ከተማ ተመዝግቦ ቤቶቹን ገንብቼ እና አሳድሼ ስጠቀም ነበር። ተጠሪ ለ20 ዓመታት አልተቃወመኝም። ፍርድ ቤቱ ለውሳኔው መሠረት ያደረጋቸው ሕጎች ለጉዳዩ አግባብነት የላቸውም። አግባብነት አላቸው ቢባል እንኳን መሬትን መሸጥ የሚከለክሉ እንጂ ቤቱን መሸጥ አይከለክሉም። አከራካሪው መሬት የእርሻ መሬት አይደለም። በአንድ ወቅት ሁሉም ከተማዎች የገጠር መሬት እንደነበሩ ይገመታል። ይዞታው የተጠሪ ነው ቢባል እንኳን በቀረው ቤት እና ይዞታ ላይ ካሳ ተሰጥቶታል። ውሉ ሕጋዊ አይደለም በማለት የተሰጠው ውሳኔ ባልተጠየቀ ዳኝነት የተሰጠ ውሳኔ ነው። ስለሆነም ይህ ታልፎ በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የተሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስሕተት የተፈጸመበት በመሆኑ በሰበር ታይቶ ሊታረም ይገባል የሚል ነው።

የሰበር አጣሪው ችሎት የአመልካችን የሰበር አቤቱታ መርምሮ የፍሬ ነገር ክርክርን በተመለከተ በማስረጃ አጣርተው የመወሰን ስልጣን የተሰጣቸው የስር ፍርድ ቤቶች የሰጡትን ውሳኔ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የመሻሩን አግባብነት ለመመርመር የሚል ማስቀረቢያ ጭብጥ በመያዝ ተጠሪ መልስ እንዲሰጡበት ተደርጎ ጉዳዩ ለዚህ ችሎት ቀርቧል።

ተጠሪ ግንቦት 26 ቀን 2014 ዓ.ም የሰጡት መልስ ይዘት በአጭሩ፡- አመልካች በቦታው ላይ መኖሪያ ቤት ሰርታ አልኖረችበትም፤ የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት የክልሉን የገጠር መሬት ሕግ መሠረት በማድረግ የአመልካችን ክስ ውድቅ ማድረጉ ተገቢ ነው፤ አመልካች በቦታው ላይ መኖሪያ ቤት ሰርታ አልኖረችም፤ አመልካች እንድትለቅ በተወሰነው ቦታ ላይ ምንም ቤት የለም፤ ቤተሰብ በባዶ መሬት ላይ እንደማይኖርም ታውቃለች፤ አመልካች ገዛሁ የምትለው ቤት በገጠር መሬት አስተዳደር ውስጥ የነበረ ነው፤ የገጠር መሬትን መግዛት አይቻልም፤ በ12 ዓመት ይርጋ ክሱ ውደቅ ሊደረግ ይገባል በማለት የቀረበው ክርክር በስር ፍርድ ቤት አልተነሳም፤ ፍርድ ቤቱ አመልካች አለኝ የምትለውን ውል ሕጋዊነት መርምሮ መወሰኑ ተገቢ ነው፤ አከራካሪው መሬት የእርሻ መሬት ስለመሆኑ አልተካደም፤ አሁን በከተማ ስር መሆኑ አርሼ እንዳልጠቀም የሚከለክለኝ አይደለም፤ መሬቱ በከተማ ስር ቢገባም አመልካች በሕገ ወጥ መንገድ ከያዘችብኝ መሬት ውጪ ሁሉም መሬት በእጄ ነው፤ እየተከራከርን ያለነው በ 1000 ካ.ሜ ይዞታ ላይ ሳይሆን በቀሪው ይዞታ ላይ ነው፤ 1000 ካ.ሜ ቦታ ላይ ያረፈውን ቤት ከእነ አቶ አሊ አሰፋ የገዛችው ስለሆነ አመልካች ቅሬታ የለኝም፤ የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት የሽያጭ ውሉን ሕጋዊነት መርምሮ መወሰኑ ወደ ፍሬ ነገር ገብቷል አያስብለውም፤ ስለሆነም ውሳኔው ሊጸና ይገባል የሚል ነው፡፡

አመልካችም የሰበር አቤቱታቸውን በማጠናከር የመልስ መልስ ሰጥተዋል፡፡

የግራ ቀኙ ክርክር እና በየደረጃው ባሉ ፍርድ ቤቶች የተሰጠው ውሳኔ በአጭሩ ከላይ የተገለጸው ነው፡፡ ይህ ችሎትም በሰበር አጣሪው ችሎት ሊጣራ ይገባዋል ተብሎ የተያዘውን ነጥብ ከግራ ቀኙ ክርክር፤ ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸው ሕጎች ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለው መርምሮታል፡፡

የገጠርም ሆነ የከተማ መሬት የማይሸጥ እና የማይለወጥ ሆኖ ባለቤትነቱም የሕዝብና የመንግስት መሆኑን የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ መንግስት አንቀጽ 40(3) ይደነግጋል፡፡ መንግስት የገጠርም ሆነ የከተማ መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም በሚመለከት ህግ የሚያወጣ መሆኑን ከሕገ መንግስቱ 51(5), 52(2) (መ) እና 55 (1) (ሀ) ድንጋጌዎች የሚያመለክቱ ሲሆን፤ ሕገ መንግስታዊ ድንጋጌዎቹን መሰረት በማድረግ በፌደራልም ሆነ በኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የገጠርና የከተማ መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም በሚመለከት በርካታ ሕጎች ወጥተው ሲሰራባቸው የቆዩ ሲሆን፤ የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም አዋጅ ቁጥር 456/1997 እና የኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም አዋጅ ቁጥር 130/1999 እና አዋጁን ለማስፈፀም የወጣው ደንብ ቁጥር 151/2005 እንዲሁም ፤ የከተማ ቦታን በሊዝ ስለመያዝ የወጣ አዋጅ ቁጥር 721/2004፣ የኦሮሚያ ክልል የከተማ ቦታን በሊዝ ለማስተዳደር የወጣው ደንብ ቁጥር 182/2005 እና መመሪያ ቁጥር 4/2008 በሥራ ያሉ ተጠቃሽ ሕጎች ናቸው፡፡ እነዚህ ሕጎች የገጠር እና

የከተማ መሬት የሚገኝበትን አግባብ ፣ የመሬት ተጠቃሚው ያለው መብት ወሰን ፣ እና ሌሎች ዝርዝር ነገሮችን የያዙ ናቸው፡፡ የገጠር መሬት የመጠቀም መብት በሕጋዊ መንገድ ያገኘ ሰው ከይዞታው ያለመፈናቀል መብት ያለው መሆኑን የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ መንግስት አንቀጽ 40(4) እና የኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም አዋጅ ቁጥር 130/1999 ቁጥር 6(1- 6) ይደነግጋሉ፡፡ ዜጎች የግል ንብረት የማፍራት መሠረታዊ መብት ያላቸው ሲሆን ባለሀብትነት ከሁሉም የንብረት መብቶች የሰፋ በሕግ ብቻ የሚገደብ መሆኑን የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ መንግስት አንቀጽ 40(1) እና የፍትሐ ብሔር ህጉ ቁጥር 1204 እና 1205 ያመለክታሉ፡፡

በተያዘው ጉዳይ ተጠሪ ለሥር የቢሾፍቱ ከተማ ወረዳ ፍርድ ቤት ያቀረበው ክስ በቢሾፍቱ ከተማ ጎርባ ቀበሌ የሚገኝ አዋሳኞቹ በክሱ ላይ የተጠቀሰውን ስፋቱ አንድ ተኩል ጥማድ የሆነው ለአሁን አመልካች አከራይቶ ሲጠቀምበት የነበረውንና የኪራይ ጊዜው በ2008 ዓ.ም ተጠናቆ በእጁ የገባውን የሥር ተከሳሽ በሕገ ወጥ መንገድ የገነባውን ቤት እና አጥር አፍርሶ እንዲለቅልኝ የሚል ነው፡፡ የሥር ተከሳሽም አዋሳኙ ተጠቅሶ ክስ የቀረበበት ይዞታ የአሁን አመልካች የገዙት መኖሪያ ቤት እና ቦታ ሆኖ የሥር ተከሳሹ የጥበቃ ሠራተኛ እንጂ ባለንብረት ባለመሆኑ፤ ባለንብረት የሆኑትን አመልካች መጠየቅ ሲገባው በእሱ ላይ ክስ መቅረቡ አግባብነት የለውም በማለት ተከራክሯል፡፡ የአሁን አመልካች በጣልቃ ገብነት አቤቱታቸው አከራካሪውን ይዞታ ሰኔ 6 ቀን 1994 ዓ.ም ከ17 ዓመት በፊት 20 ቅጠል ቆርቆሮ ቤት ያረፈበትን 1250 ካ.ሜ ከአመልካች የገዙት ሲሆን ቀሪውን 30 ቅጠል ቆርቆሮ ቤት ያረፈበትን 1000 ካ.ሜ ባልና ሚስት ከሆኑት አቶ አሊ አሰፋ እና ወ/ሮ መሠረት መርጋ የገዙት ሲሆን ፤ ክሱ በቀረበበት ጊዜ የገጠር ሳይሆን በቢሺፍቱ ከተማ ጎርባ ቀበሌ ውስጥ የሚገኝ ፤ ከ1994 ዓ.ም አንስቶ በእጃቸው ያለ እና ተጨማሪ ግንባታ ገንብተው ግብር የሚገብሩበት የግል ይዞታ እና ቤታቸው ላይ የቀረበው ክስ በይርጋ ቀሪ ነው በማለት ተከራክረዋል፡፡ ተጠሪ በጣልቃ ገብነት አቤቱታው ላይ መልስ እንዲሰጡ በተያዘው ቀጠሮ መጥሪያ ደረሷቸው ስላልቀረቡ መልስ የመስጠት መብታቸው ታልፏል፡፡

አመልካች አከራካሪውን ቤት እና ይዞታውን ከተጠሪ በግዥ ነው የገኘሁት በማለት ያቀረቡትን ክርክር ተጠሪ መቃወማቸውን መዝገቡ አያመለክትም፡፡ የቢሾፍቱ ከተማ ወረዳ ፍርድ ቤትም ተጠሪ ለአመልካች አሳልፎ በሸጠው ንብረት ላይ ክስ የማቅረብ መብት የለውም በማለት ክሱን ውድቅ አድርጎታል፡፡ ይግባኝ ሰሚው የምስራቅ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤትም ተጠሪ እንደ ክስ አቀራረባቸው ማስረዳት አለመቻላቸውን ውሳኔው ያትታል፡፡

በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ መንግስት አንቀጽ 40 (1) እና (2) እንዲሁም የፍትሐ ብሔር ሕግ ቁጥር 1204 ድንጋጌ መሰረት ባለሀብትነት መሠረታዊ እና ከሁሉ የሰፋ በህግ ከተመለከቱት ሥርዓቶች ውጪ ሊገደብ የማይችል መብት ነዉ፡፡ ባለሀብትነት ማስተላለፍያ መንገዶች የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1184

እና ተከታዮቹ ሥር ተደንግጓል። ባለሀብትነት ቀሪ ሊሆን የሚችልባቸው መንገዶችም የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1188 እና ተከታዮቹ ሥር ተመላክቷል።

እኛችን ባለው ጉዳይ በአመልካችም እንደታመነው ከአከራካሪው ይዞታ እና ንብረት ውስጥ 20 ቅጠል ቆርቆሮ ቤት ያረፈበትን ስፋቱ 1250 ካ.ሜ የሆነውን መሬት ከ17 ዓመት በፊት ሰኔ 6 ቀን 1994 ዓ.ም ከተጠሪ በግዥ የተላለፈላቸው መሆኑ ነው። የአከራካሪው ይዞታ እና ቤት ባለሀብት ማነው? የሚለው ጭብጥ ሲመረመር ተጠሪ በንብረቱ ላይ ያላቸው መብት ቀሪ መሆን፤ አመልካችም በአከራካሪው ንብረት ላይ በሕጉ አግባብ የተላለፈላቸው የባለሀብትነት መብት መኖሩን ለመመርመር በግራ ቀኙ መካከል የተደረገውን የግዥ ውል ማየቱ የግድ ይላል። ከውሉ ጋር አብሮ መታየታ ያለበት ውሉ ሲደረግ መሬቱ ሲሰጥ ከነበረው አገልግሎት አንፃር የገጠር ነው ወይም የከተማ? ክርክሩ ሊመራ የሚገባው በከተማ መሬት ሕግ ወይም የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም አዋጅ? የሚሉ ጥያቄዎች ምላሽ መስጠት ያሻል።

ምንም እንኳን ውሉ ሲደረግ መሬቱ የገጠር የነበረ ቢሆንም ክሱ በቀረበበት ጊዜ ይዞታው በቢሾፍቱ ከተማ አስተዳደር ሥር የሚገኝ ለከተማ አገልግሎት የዋለ መሆኑን ከክርክሩ መረዳት ተችሏል። የተጠሪ ክስ የነበረውም የከተማ ይዞታዬ ይለቀቅልኝ የሚል ነው። ይዞታው በቢሾፍቱ ከተማ አስተዳደር ሥር ከገባበት ጊዜ ጀምሮ መሬቱ የከተማ እንጂ የገጠር ባለመሆኑ ክርክሩ በገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ሕግ ሊታይ የሚችልበት አግባብ አይኖርም። የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚው ችሎትም መሬቱ በገጠር አስተዳደር ክልል ሥር እያለ የተደረገ የውል ሕጋዊነት መታየት ያለበት ክርክሩ በተነሳበት ጊዜ መሬቱ በሚተዳደርበት ሕግ መሆኑን በሰበር መዝገብ ቁጥር 210072 ላይ አስገዳጅ የሕግ ትርጉም ሰጥቶበታል።

አከራካሪው ይዞታ እና ቤት በአመልካች እና ተጠሪ መካከል ሰኔ 6 ቀን 1994 ዓ.ም በተደረገ የሽያጭ ውል ወደ አመልካች ተላልፎ አመልካች ያለ ምንም ተቃውሞ እየተጠቀሙበት ፤ ከ2000 ዓ.ም ጀምሮ ሲገብሩበት በቆዩበት ወቅት አግባብነት ያለውን የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ሕግን በመተላለፍ አላግባብ የያዙትን የገጠር መሬት እንዲለቁ የቀረበ ክርክር በሌለበት፤ መሬቱ አስቀድሞ ይሰጥ የነበረው አገልግሎት ተቀይሮ ለከተማ አገልግሎት በቢሾፍቱ ከተማ አስተዳደር ሥር ከገባ በኋላ ፤ ከገጠር መሬት ይዞታ ያለመፈናቀል ሕገ መንግስታዊ ጥበቃው ለአርሶ አደሩ ሆኖ ክስ በቀረበ ጊዜ ከገጠር መሬት ይዞታ ላይ የተፈናቀለ አርሶ አደር በሌለበት ውል ሲደረግ የነበረው ሁኔታ ተቀይሮ ባለበት የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ሕጉን አላግባብ በመለጠጥ እና የከተማ መሬት ሕግ ተፈፃሚነት ወሰን በሚያጣብብ መልኩ የተሰጠው ውሳኔ የሚነቅፍ ነው።

የከተማ መሬት መሠረቱ የገጠር መሬት ቢሆንም ፤ ጉዳዩ መታየት ያለበት ክሱ በቀረበ ጊዜ በሥራ ላይ ያለው የከተማ መሬትን ለማስተዳደር የወጣው ሕግ ወይስ ውሉ በተፈፀመ ጊዜ የነበረው የገጠር መሬት አስተዳደር እና አጠቃቀም ህግ ?

የሚል ሆኖ መሬቱ ከተማ አስተዳደር ሥር ከገባ በኋላ ለቀረበ ክስ መሬቱ በገጠር ቀበሌ ሥር በሚገኝበት ጊዜ የተደረገውን የገጠር ቤት ሽያጭ ውል መሠረት በማድረግ የተጠሪ ባለሀብትነት በፍትሐ ብሔር ሕጉ ቁጥር 1189 መሠረት ቀሪ ሆኖ ፤ በፍትሐ ብሔር ሕጉ ቁጥር 1184, 1189, 2875 እና ተከታይ ድንጋጌዎች መሠረት በግዥ የተላለፈላቸውን ለክርክሩ መነሻ የሆነውን ቤት እና ይዞታ አመልካች እንዲለቁ የተሰጠው ውሳኔ በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ መንግስት አንቀጽ 40(1) እና የፍትሐ ብሔር ህጉ ቁጥር 1204 እና 1205 መሠረታዊ ንብረት የማፍራት መብታቸውን የሚገድብ የፌደራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 1234/2013 ቁጥር 2(4) (ሀ) እና (ሸ) የሚጣረስ መሠረታዊ የሕግ ስህተት በመሆኑ ቀጣዩ ተወስኗል፡፡

<u>ው ሳ ኔ</u>

1. በኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰበር መዝገብ ቁጥር 377515 ሕዳር 28 ቀን 2014 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 348(1) መሠረት **ተሽሯል**፡፡
2. የምስራቅ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 62039 ግንቦት 17 ቀን 2013 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ ፤ይህንኑ ውሳኔ በማጽናት የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 371724 ሠኔ 23 ቀን 2013 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 348(1) መሠረት **ፀንቷል**፡፡
3. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪ ግራ ቀኙ የየራሣቸውን ይቻሉ፡፡
4. ሰኔ 22 ቀን 2014 ዓ.ም በመዝገቡ የተሰጠው የዕግድ ትዕዛዝ ተነስቷል፡፡ ይጻፍ
5. ውሳኔው የካቲት 6 ቀን 2014 ዓ.ም በችሎት ተነቧል፡፡
   - መዝገቡ ውሳኔ ስላገኘ ተዘግቷል፡፡ ይመለስ

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ት/በ

ሰበር መ/ቁ 154712

ህዳር 28 ቀን 2011 ዓ.ም

ዳኞች፡- ብርሃኑ አመነው

በዕዉቀት በላይ

እንዳሻዉ አዳነ

ሃይሉ ነጋሽ

እትመት አሰፋ

አመልካች፡- አቶ ረጋሳ መልካሙ

ተጠሪዎች፡- 1ኛ/ ካየሶ ክርባ

2ኛ/ አቶ ብርሀኑ ተስፋዬ

መዝገቡ ለምርመራ የተቀጠረ በመሆኑ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍርድ፡፡

በዚህ መዝገብ የቀረበዉ ጉዳይ ከይዞታ አጠቃቀም ጋር በተያያዘ በንብረት ላይ የደረሰ ጉዳት መከላከል የሚመለከት ነዉ፡፡የጉዳዩ አመጣጥ ሲታይ በስር ፍርድ ቤት ከሳሽ የአሁኑ አመልካች ሲሆን የክሱ ይዘት ባጭሩ አመልካችና ተጠሪ በይዞታቸዉ በድንበር የሚዋሰኑ ሆኖ በምስራቅ በኩል ተጠሪዎች የተከሉት ባሕርዛፍ ቅርንጫፍና ስሩ በአመልካች ጫት፣ቡና እና እንሰት ተክሎች ላይ ጉዳት ያደረሰ ስለሆነ ዛፉን እንዲያነሱ እንዲወሰን የሚል ሲሆን በተጠሪዎች በኩል የቀረበዉ መልስ በመካከላቸዉ የእግር መንገድ ስላለ በአመልካች ንብረት ላይ የደረሰ ጉዳት አለመኖሩንና ባህርዛፍ ከተተከለ ረጅም ጊዜ ስለሆነ ክሱ ያለአግባብ የቀረበ ነዉ በማለት ተከራክረዋል፡፡ክርክሩን በመጀመሪያ የዳኝነት ስልጣን የተመለከተዉ የአለታ ጩኮ ወረዳ ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ምስክር ከሰማ በኋላ የተጠሪዎች ባህርዛፍ የአመልካች ተክሎች ላይ ጉዳት አድርሷል ወይስ አላደረሰም? የሚለዉን የወረዳዉ ግብርና ባለሙያ አጣርቶ መግለጫ እንዲያቀርብ ትእዛዝ በመስጠት ባለሙያዉ ባቀረበዉ መግለጫ የተጠሪዎች ባህርዛፍ በአመልካች ንብረት ላይ ጉዳት እንዳደረሰና ለወደፊትም ትልቅ ጉዳት እንደሚያደርስ ስለገለጸ ፍርድ ቤቱም ይሕንኑ መሰረት በማድረግ በፍ/ብ/ህግ አንቀጽ 1212/1 ና 2/መሰረት ተጠሪዎች ባህርዛፉን ቆርጠዉ እንዲያነሱ ዉሳኔ ሰጥቷል፡፡ተጠሪዎች በዚህ ዉሳኔ ቅር ተሰኝተዉ ለሲዳማ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ አቅርበዉ ፍርድ ቤቱም ግራቀኙን ካከራከረ በኋላ በአንድ በኩል የተጠሪዎች ምስክሮች ባህርዛፉ ጉዳት አላደረሰም በሚል ተከላክለዋል በሚል በሌላ በኩል ደግሞ በሲዳማ ባህል በረጅም ጊዜ ደጆ ስለሆነ ዛፉ አይቆረጥም በማለት የስር ፍርድ ቤት ዉሳኔን ሽሯል፡፡አመልካች በበኩሉ ይህንኑ በመቃወም ለደቡብ ብ/ብ/ህ/ክልል ጠ/ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት እና ሰበር ሰሚ ችሎት አቤቱታ ያቀረበ ቢሆንም ተቀባይነት አላገኘም፡፡

ለዚህ ሰበር ችሎት አቤቱታ የቀረበዉ በዚህ ላይ ሲሆን የአመልካች የሰበር አቤቱታ ይዘት ባጭሩ ተጠሪዎች በወሰን ላይ 40 ሜትር ርዝመት ላይ የተከሉት ባህርዛፍ የአመልካች መተዳደሪያ ቡና፣እንሰት እና ጫት በስር እና በቅርንጫፍ ጉዳት ማድረሱ እንዲቆርጡለት በሽማግሌ ጠይቆ እንቢ በማለታቸዉ ክስ ስለመመስረቱና በስር ፍርድ ቤት ጉዳት ስለመድረሱ በባለሙያ ጭምር መረጋገጡን ገልጾ የበላይ ፍርድ ቤቶች ዉሳኔ ተገቢ ባለመሆኑ እንዲታረም የሚል ነዉ፡፡የአመልካች የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ የተጠሪዎች ባህርዛፍ በአመልካች ንብረት ላይ ጉዳት ማድረሱ በማስረጃ ተረጋግጦ እያለ በራሳቸዉ ይዞታ ላይ ነዉ በሚል ወረዳ ፍርድ ቤት ዉሳኔ የመሻሩን አግባብነት ከፍ/ብ/ህግ አንቀጽ 1212 አንጻር ለመመርመር በሚል ጭብጥ ተይዞ ተጠሪዎች መልስ እንዲሰጡ ተደርጓል፡፡በተጠሪዎች በኩል የቀረበዉ መልስ ባጭሩ በሁለቱ መካከል ትልቅ የመኪና መንገድ ያለበት ስለሆነ በአመልካች ንብረት ላይ የደረሰ ጉዳት የለም በሚል የስር ፍርድ ቤት ዉሳኔ እንዲጸና ጠይቀዋል፡፡አመልካችም የመልስ መልስ ሰጥቷል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥና የክርክሩ ይዘት ከላይ ባጭሩ የተገለጸ ሲሆን እኛም አቤቱታዉ ለሰበር ያስቀርባል ሲባል የተያዘዉን ጭብጥ መሰረት በማድርግ አግባብነት ካለዉ ህግ ጋር በማገናዘብ መርምረናል፡፡መዝገቡን መርምረን እንደተገነዘብነዉ አመልካችና ተጠሪዎች በሚዋሰኑበት አቅጣጫ ተጠሪዎች ባህርዛፍ ተክል ያላቸዉ ስለመሆኑ አላከራከረም፡፡አመልካች በበኩሉ ከተጠሪዎች በሚዋሰንበት አቅጣጫ ተጠሪዎች ወሰን ላይ የተከሉት ባህርዛፍ አመልካች የሚጠቀምበት ጫት፣ቡና እንሰት የመሳሰሉት ተክሎች በዚህ የተጠሪዎች ባህርዛፍ ስርና ቅርንጫፍ ጉዳት ስለደረሰበት እንዲቆርጡለት ዳኝነት ጠይቀል፡፡በእርግጥ አመልካችም ሆነ ተጠሪዎች በየራሳቸዉ ይዞታ ላይ መሆናቸዉ አላከራከረም፡፡ነገር ግን ተጠሪዎች በራሳቸዉ ይዞታ ላይ የተከሉት ባህርዛፍ በስሩ እና በቅርንጫፍ ወደ አመልካች ይዞታ አልፎ በአመልካች ንብረት ላይ ጉዳት ቢያደርስ ህጉ የሰጠዉ መፍትሄ ምንድነዉ? የሚለዉ መታየት አለበት፡፡በፍ/ብ/ህግ አንቀጽ 1212 ላይ እንደተደነገገዉ ማንኛዉም ሰዉ ወደ መሬቱ ላይ ተዘርግተዉ የገቡትን የጎረቤቱን ዛፎችና ቅርንጫፎች በአንድ ወር ጊዜ ዉስጥ እንዲቆርጥ በዳኛ ማስገደድ ይችላል፡፡ከዚህ ባሻገር ከወሰኑ መስመር አልፎ በመሬቱ ዉስጥ የሚሄዱትን ሊቆርጥ እንደሚችል ተመልክቷል፡፡ከዚህ መገንዘብ የሚቻለዉ አንድ ባለንብረት ንብረቱን የመገልገል መብቱ የሌላኛዉን ወገን ጥቅም እንዳይጎዳ በህግ የተጣለ ወሰን ያለበት ስለመሆኑ ነዉ፡፡ይኸዉም ተጠሪዎች በራሳቸዉ ይዞታ ላይ በማናቸዉም ሁኔታ ዛፍ በመትከል ጭምር የመገልገል መብት ያላቸዉ መሆኑ በሌላ በኩል እነሱ የሚጠቀሙበት ዛፍ ቅርንጫፍ ወይም ስሩ የጎረቤት ንብረት ላይ ጉዳት እንዳያደርስ እና ጉዳት የደረሰበት ሰዉ የሚኖረዉ መፍትሄ ህጉ በግልጽ የደነገገ ስለመሆኑ ነዉ፡፡በመሆኑም በዚህ አግባብ ጥበቃ የተደረገለት ተጎጂ ወገን አንድም በራሱ ጉዳቱን የማስወገድ አሊያም በፍርድ ሃይል ጉዳቱ እንዲወገድ ዳኝነት የመጠየቅ መብት በሕግ የተጠበቀ መሆኑን እንገነዘባለን፡፡

በተያዘዉ ጉዳይ ተጠሪዎች የሚከራከሩት በመካከላቸዉ ትልቅ መንገድ ስላለ ባህርዛፎቹ በአመልካች ንብረት ላይ ጉዳት አላደረሱም በማለት ነዉ።የተጠሪዎች ባህርዛፍ በቅርንጫፉም ሆነ በስሩ በአመልካች ንብረት ላይ ጉዳት አድርሷል ወይስ አላደረሰም የሚለዉ የፍሬነገር ክርክር በማስረጃ ነጥሮ የሚታወቅ ከመሆኑ አኳያ የወረዳዉ ፍርድ ቤት የግራቀኙ ምስክሮች ብቻ መሰረት አድርጎ ፍትሃዊ ዉሳኔ መስጠት ባለመቻሉ የወረዳዉ የተፈጥሮ ሀብት ጥበቃ ጽ/ቤት ባለሙያ ጉዳዩን አጣርቶ መግለጫ እንዲሰጥ አድርጎ ባለሙያዉም በተጠሪዎች ባህርዛፍ ቅርንጫፍና ስር የአመልካች ንብረት ላይ ጉዳት ስለመድረሱ ገልጧል።የወረዳዉ ፍርድ ቤት ይህንኑ መሰረት በማድረግ ተጠሪዎች ባህርዛፉን እንዲቆርጡ ዉሳኔ ሰጥቷል።የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የምስክሮችን ቃል መሰረት በማድረግ የስር ፍርድ ቤት ዉሳኔ መሻሩን መዝገቡ ያሥረዳል።ከመዝገቡ ይዘት መገንዘብ እንደሚቻለዉ የግራቀኙ ምስክሮች ቃል ገለልተኛነት እና ተአማኝነት ጥያቄ ዉስጥ በመግባቱ የወረዳዉ ፍርድ ቤት ጉዳዩ በገለልተኛ ባለሙያ እንዲጣራ አድርጓል።ይግባኝ ሰሚዉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ግን ይህንን የባለሙያ መግለጫ ላለመቀበል የሰጠዉ ግልጽና ህጋዊ ምክንያት ስለመኖሩ አልተገለጸም። ስለሆነም ምንም እንኳን በመካከላቸዉ መንገድ መኖሩ ቢገለጽም ባህርዛፎቹ በቅርንጫፎቻቸዉና በስሮቻቸዉ በአመልካች ንብረት ላይ ጉዳት ስለማድረሳቸዉ በወረዳ ፍርድ ቤት በባለሙያ ታይቶ የተረጋገጠ እዉነታ ነዉ።በመሆኑም ይህንን በባለሙያ ጭምር የተረጋገጠ ፍሬ ነገር የሚያሥለዉጥ ማስረጃ ባልቀረበበት ሁኔታ የሲዳማ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት የወረዳዉን ፍርድ ቤት ዉሳኔ በመሻር ዉሳኔ መስጠቱም ሆነ የበላይ ፍርድ ቤቶች ይህንኑ ማጽናታቸዉ ህጉንና የተረጋገጠዉን ፍሬ ነገር ባለማገናዘብ የተሰጠ ፍርድ በመሆኑ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ አግኝተናል።በዚሁ አግባብ ተከታዩን ዉሳኔ ሰጥተናል።

<u>ዉሳኔ</u>

1. የሲዳማ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ/43103 ላይ በ14/03/2010 ዓ.ም የሰጠዉ ፍርድ እና ይህንኑ በማጽናት የደቡብ ብ/ብ/ህ/ክ/መ/ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት እና ሰበር ሰሚ ችሎት እንደቅደም ተከተላቸዉ በመ/ቁ/71766 እና መ/ቁ 71861 ላይ የሰጡት ትእዛዝ በፍ/ብ/ስ/ስ/ህግ ቁ/348/1/መሰረት ተሽሯል።
2. የአለታ ጩኮ ወረዳ ፍርድ ቤት በመ/ቁ/21358 ላይ በ12/10/09 ዓ.ም የሰጠዉ ፍርድ ጸንቷል።ይጻፍ።
3. በዚህ ፍ/ቤት ለተደረገዉ ክርክር ግራቀኙ የየራሳቸዉን ወጪና ኪሳራ ይቻሉ ብለናል።

መዝገቡ ተዘግቷል ይመለስ።

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ቤ/ፍ

ው-ርስ

የሰ.መ.ቁ.178714

ሚያዝያ 28/2012 ዓ.ም

ዳኞች፡- እትመት አሰፋ

ጳውሎስ ኦርሺሶ

ፀሐይ መንክር

መላኩ ካሳዬ

እስቲበል አንዱዓለም

አመልካች፡- ወ/ሮ ፋጡማ አልቃድር

ተጠሪዎች፡- 1. **ወ/ሮ ፋጡማ ሲራጅ**

2. **ወ/ሮ ሶፊያ የተመኝ**

3. **አቶ እንድሪስ አህመድ**

4. **ወ/ሮ ፅሐይ የተመኝ፡-** *መሞታቸው ተረጋግጦ ለወራሾች ጥሪ ቢደረግም የቀረበ ባለመኖሩ በሌለበት የታየ*

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍርድ

በዚህ መዝገብ ላይ የቀረበው ጉዳይ የውርስ ሀብት በሆነ ይዞታ ላይ በአንደኛው ወራሽ ያለተቃውሞ የተሰራ ቤትን በተመለከተ ቤቱን የሰራው እና ሎሎች ወራሾች በተሰራው ቤት ላይ ስላላቸው የመብት አድማስ የሚመለከት ነው፡፡

የሰበር አቤቱታው የቀረበው የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ/03-90267 ላይ መጋቢት 20/2011 ዓ.ም በዋለው ችሎት በአሁን አመልካች የቀረበለትን የሰበር አቤቱታ ውድቅ በማድረግ የሰጠውን የመጨረሻ ትዕዛዝ በመቃወም ነው፡፡

የክርክሩ አመጣጥ እንዲህ ነው፡፡ የአሁን አመልካች በአሁን 1ኛ ተጠሪ ላይ በሰሜን ጎንደር መስተዳድር ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ሰኔ 23/2002 ዓ.ም ፅፈው ባቀረቡት ክስ ቦታ እና አዋሳኙ በክሱ ዝርዝር ውስጥ የተጠቀሰውን እና ግምቱ ብር 100,000(አንድ መቶ ሺህ) የሆነ በካርታ ቁጥር 0398/2007 የተመዘገበ ቤት እና ግምቱ ብር 720(ሰባት መቶ ሃያ) የሆነ የባህር ዛፍ ፍልጥ የያዙባቸው መሆኑን በመግለፅ በፍርድ ታይል ተገደው እንዲለቁላቸው እና ለተጠቀሙበትም ኪራዩ በብር 50 ታስቦ እንዲከፈላቸው ዳኝነት ይጠይቃሉ፡፡

የአሁን 1ኛ ተጠሪ ለዚሁ ክስ ሐምሌ 26/2002 ዓ.ም በሰጡት መልስ የአመልካች ወንድም ሚስት በመሆናቸው ክስ የቀረበበትን ቤት ከሌሎች ወራሾች እጅ በአደራ ጠባቂነት ከመቀበላቸው ውጭ በቤቱ ላይ መብት የሌላቸው መሆኑን እና የቀረበው ግምትም የተጋነነ መሆኑን በመግለፅ "ልጠየቅ አይገባም" ብለዋል፡፡

በዚሁ መሀል የአሁን ከ2ኛ እስከ 4ኛ ያሉ ተጠሪዎች በጣልቃ ገብነት ቀረበው የክርክሩ አካል በመሆን ጥቅምት 29/2003 ዓ.ም የተፃፈ መልስ ሰጥተዋል፡፡ የመልሳቸው ይዘትም ክስ የቀረበበት ቤት የሟች እናታቸው ወ/ሮ ምናሉ ውቡ መሆኑን፤ ቤቱን በአደራ ለ1ኛ ተጠሪ የሰጧቸው እራሳቸው መሆኑን፤ ንብረቱ የጋራ የውርስ ሀብት ሆኖ እያለ የአሁን አመልካች ብቸኛ ወራሽ አስምስለው ካርታ ያወጡ መሆኑን በመግለፅ "ንብረቱን እኩል ከምንካፈል በቀር ልንለቅ አይገባም" በማለት ተከራክረዋል፡፡

ጉዳዩ የቀረበለት ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ክርክር እና ማስረጃን ከሰማ በኋላ ተገቢ ነው ያለውን ውሳኔ መስጠቱን፤ በጉዳዩ ላይ እስከ ክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ድርስ ክርክር ተደርጎ ሰበር ሰሚ ችሎቱ በመ/ቁ/16162 ላይ የካቲት 12/2005 ዓ.ም ሊጣሩ የሚገባቸውን ነጥቦች ለይቶ ጉዳዩን ለከፍተኛው ፍርድ ቤት የመለሰ መሆኑን፤ ከፍተኛ ፍርድ ቤቱም በተያዘው ነጥብ ላይ ተገቢውን ማጣራት አድርጎ ሐምሌ 23/2007 ዓ.ም ውሳኔ መስጠቱን፤ በዚሁ ውሳኔ ላይ እስከ ክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ክርክር ተደርጎ ሰበር ችሎት በመ/ቁ/01-38878 ላይ ጥር 30/2008 ዓ.ም በዋለው ችሎት በድጋሚ "ሊጣሩ ይገባል" ያላቸውን ነጥቦች ለይቶ ጉዳዩን ለከፍተኛው ፍርድ ቤት የመለሰ መሆኑን፤ ከፍተኛው ፍርድ ቤትም በተያዘው ነጥብ ላይ "ተገቢ ነው" ያለው ማጣራት አድርጎ ታህሳስ 25/2010 ዓ.ም በዋለው ችሎት ውሳኔ መስጠቱን፤ ይኸው ውሳኔ እስከ ክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ቀርቦ ከላይ በተጠቀሰው የመዝገብ ቁጥር እና ቀን በዋለው ችሎት የፀና መሆኑን የመዝገቡ ታሪክ ያስረዳል፡፡

የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ታህሳስ 25/2010 ዓ.ም የሰጠው እና ለዚህ ሰበር ክርክር መነሻ የሆነው ውሳኔ ይዘት በአጭሩ በክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ/01-38878 ላይ እንዲጣራ ተብሎ በነጥብነት የተለየው 1ኛ/ ክርክር የተነሳበትን ቤት በተመለከተ የአሁን አመልካች ያቀረቡት ካርታ ህጋዊነት እንዲጣራ፤ 2ኛ/ ክርክር የተነሳበት ይዞታ የውርስ ሀብት ከሆነ ወራሾች በድርሻቸው ልክ እንዲከፋፈሉ በማድረግ የመሰለውን እንዲወስን የሚል መሆኑን፤ በዚሁ አግባብ ክስ የቀረበበትን ቤት በተመለከለተ የዞኑ ቤቶች ልማት ኮርፖሬሽን ከወረዳው መሪ ማዘጋጃ ቤት ጋር በመሆን አጣርተው እንዲያቀርቡለት ትዕዛዝ መሰጠቱን፤ በውጤቱም ቤቱ የተሰራበትን ቦታ ወ/ሮ ማንአለብሽ ውቡ የተባሉት በ1987 ዓ.ም በባህላዊ ግዢ ወ/ሮ ውብነሽ ከተባሉት ገዝተው እላዩ ላይ የነበረውን ቤት አድሰው እየኖሩበትና ግብርም በተከታታይ ሲከፍሉበት የነበረ መሆኑን፤ ይዞታውን

በምን አግባብ እንደያዙ የሚታወቅ ነገር ባይኖርም አሁን ክርክር የተነሳበትን ቤት አመልካች በ1993 ዓ.ም በራሳቸው ወጪ የሰሩ ለመሆኑ ማረጋገጡን፣ ካርታውን በተመለከተ በአመልካች እጅ ያለው እና ከአስተዳደር ክፍል በቀረበው መካከል ልዩነት ያለ መሆኑን፣ በዚህም አመልካች ካርታውን ያገኙበት መንገድ ከአስተዳደር ክፍሉ አሰራር እና ደንብ ውጭ በመሆኑ ህጋዊ እንዳልሆነ፣ አመልካች ቤት የሰሩበት ይዞታ የግራ ቀኙ እናት በመሆኑ የውርስ ሀብት መሆኑን በመግለፅ የአሁን ተጠሪዎች የቤቱን ግምት ለአሁን አመልካች ከፍለው የውርስ ሃብት የሆነውን ይዞታ ግራ ቀኙ እኩል እንዲካፈሉ የሚል ነው፡፡

በአሁን አመልካች አቤቱታ አቅራቢነት በዚሁ ውሳኔ ላይ እንደ ቅደም ተከተላቸው ይግባኝ እና የሰበር አቤቱታ የቀረበላቸው የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት መደበኛ ይግባኝ ሰሚ ችሎት እና ሰበር ሰሚ ችሎት የአመልካችን አቤቱታ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁጥር 337 መሰረት ውድቅ አድርገዋል፡፡ የአሁን የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ በመቃወም ነው፡፡

አመልካች ሰኔ 03/2011 ዓ.ም በተፃፈ የሰበር አቤቱታ በስር ፍርድ ቤት ውሳኔ ላይ “ተፈጽሟል” ያሉትን መሰረታዊ የህግ ስህተት ጠቅሰው በዚህ ችሎት እንዲታረምላቸው ጠይቀዋል፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ ከተመረመረ በኋላ አመልካች በባዶ ይዞታ ላይ ክርክር የተነሳበትን ቤት ሰርተው ካርታ ያወጡበት ለመሆኑ በተረጋገጠበት ሁኔታ ቀድሞ ቦታው የግራ ቀኙ አውራሽ ነበር በሚል ብቻ አመልካች ለሰሩት ቤት ግምት ተከፍሏቸው ቦታውን ይከፋፈሉ የመባሉ አግባብነት በፍ/ብ/ህ/ቁ/1179 እና ማንም ባልተቃወመበት በይዞታ ላይ ስለተሰራ ቤት ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት ቀደም ሲል ከሰጠው ትርጉም አንፃር ለዚህ ችሎት ቀርቦ እንዲጣራ በአጣሪ ችሎት በመታዘዙ ተጠሪዎች መልስ እንዲሰጡበት ተደርጓል፡፡

በዚሁ መሰረት 1ኛ ተጠሪ ለብቻቸው፣ 2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች በጋራ ጥቅምት 20/2012 የተፃፈ መልስ ሰጥተዋል፡፡ 4ኛ ተጠሪን በተመለከተ ከዚህ ዓለም በሞት የተለዩ ለመሆኑ በመረጋገጡ እና ወራሾች ካሉ ቀርበው እንዲከራከሩ ጥሪ የተደረገ ቢሆንም የቀረበ ባለመኖሩ የሰበር ክርክሩ በሌሉበት እንዲታይ ተደርጓል፡፡

1ኛ ተጠሪ በሰጡት መልስ በስር ፍርድ ቤት ባቀረቡት መልስ አግባብ ቤቱን ከሌሎች ወራሾች በአደራ የተረከቡ እንጂ የሚጠይቁት መብት አለመኖሩን በመግለፅ በተከራካሪነት “ልጠራ አይገባም” ብለዋል፡፡

ከማስቀረቢያ ነጥቡ አኳያ የ2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች መልስ ይዘት በአጭሩ ክርክር የተነሳበትን ቤት ወላጅ እናታቸው አሮጌ ቤት ገዝተው አፍርሰው የሰሩት እንጂ አመልካች የሰሩት እንዳልሆነ፣ አመልካች ያቀረቡት ካርታም ህጋዊ ካለመሆኑም በላይ በከተማው ውስጥ ባላቸው ሌላ ቤት ላይ

የተሰጠ እንጂ አሁን ክርክር የተነሳበትን ቤት የሚመለከት እንዳልሆነ፣ ወላጅ እናታቸው በሰሩት ቤት ላይ ግምቱን ለአመልካች ከፍለው እንዲካፈሉ በሚል የተሰጠው ውሳኔ አግባብ ባይሆንም አመልካች እህታቸው በመሆናቸው በተሰጠው ውሳኔ ተጎጂ ቢሆኑም በይሁንታ የተቀበሉ መሆኑን በመግለፅ የስር ፍርድ ቤት ውሳኔ እንዲፀና የሚጠይቅ ነው፡፡

አመልካች በሰጡት የመልስ መልስ ክርክር የተነሳበትን ቤት በባዶ ቦታ ላይ ተጠሪዎች ላይ ሳይቃወሟቸው በራሳቸው ወጪ ለመስራታቸው ተረጋግጦ እያለ ቤቱ የግል ሃብታቸው ነው ተብሎ መወሰን ሲገባው ግምቱ ተከፍሏቸው ከሌሎች ወራሾች ጋር እንዲካፈሉ መወሰኑ አግባብ አለመሆኑን በመግለፅ በቀረበው አቤቱታ መሰረት እንዲወሰንላቸው ሞግተዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ እና የክርክሩ ይዘት ጠቅለል ባለ መልኩ ከላይ የተመለከተውን ሲመስል ችሎቱም ጉዳዩ ለዚህ ችሎት ሲቀርብ ከተያዘው ነጥብ አኳያ የግራ ቀኙን ክርክር አግባብነት ካለው ህግ ጋር በማገናዘብ መርምሯል፡፡

ከክርክሩ አመጣር መረዳት እንደሚቻለው ክርክር የተነሳበት ቤት የተሰራበት ይዞታን በተመለከተ የውርስ ሀብት ነው ወይስ የአመልካች የግል ይዞታ ነው የሚለው ከአንዴም ሁለት ጊዜ እስከ ክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ድረስ ግራ ቀኙን ሲያከራክር የቆየ መሆኑን፣ በመጨረሻም ጉዳዩን በመጀመሪያ የዳኝነት ስልጣኑ የተመለከተው የክልሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በዚሁ ነጥብ ላይ የግራ ቀኙን ክርክር እና ማስረጃን ሰምቶ እንዲሁም ስለይዞታው ጉዳዩ ከሚመለከተው አስተዳደር ክፍል በትዕዛዝ ካጣራ በኋላ ቤቱ የተሰራበት ይዞታ መሰረቱ የግራ ቀኙ አውራሽ መሆኑን፣ በዚሁ ይዞታ ላይ ክርክር የተነሳበትን ቤት አመልካች የሰሩ ለመሆኑ በፍሬ ነገር ደረጃ ማረጋገጡን በፍርድ ሀተታው ላይ በግል አስፍሯል፡፡

እንግዲህ በኢ.ፌ.ዴ.ሪ. ህገ መንግስት አንቀፅ 80(3) እና በፌዴራል ፍርድ ቤቶች ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀፅ 10 መሰረት ለዚህ ሰበር ችሎት የተሰጠው የዳኝነት ስልጣን በማናቸውም የመጨረሻ ውሳኔው ላይ የተፈፀመ መሰረታዊ የህግ ስህተት ካለ ማረም እንጂ ማስረጃን የመመርመር እና የመመዘን ሥልጣን አይደለም፡፡ በመሆኑም የዚህ ሰበር ችሎት ተግባር የሚሆነው ሥልጣን ባላቸው ፍርድ ቤቶች የተረጋገጠውን ፍሬ ነገር በግብዓትነት በመውሰድ ፍሬ ነገሩ መሰረት ተደርጎ በተሰጠ የህግ ትርጉም ውስጥ የተፈፀመ መሰረታዊ ስህተት ካለ መፈተሽ ነው፡፡

አሁን በቀረበው ጉዳይ ማስረጃን በመመርመር እና በመመዘን ፍሬ ነገርን የማጥራት ስልጣን ባለው ፍርድ ቤት ክርክር የተነሳበት ይዞታ የውርስ ሃብት መሆኑን እና በዚሁ ይዞታ ላይ የአሁን አመልካች በራሳቸው ወጪ ክርክር የተነሳበትን ቤት ስለመስራታቸው በፍሬ ነገር ደረጃ

ተረጋግጧል፡፡ በፍሬ ነገር ደረጃ ይህ ተረጋግጦ ባለበት አመልካች “ይዞታው የእኔ ነው” በማለት የሚያቀርቡት ክርክር ማስረጃን መሰረት ያላደረገ በመሆኑ ችሎቱ አልተቀበለውም፡፡

“ቤቱ የተሰራበት ይዞታ የውርስ ሀብት ነው” ከተባለ ወራሾች በዚህ ይዞታ ላይ ያላቸውን መብት እና ስለ መብቱ አፈፃፀም ያለውን የህግ ማዕቀፍ ማየቱ ተገቢ ይሆናል፡፡ በዚሁ መሰረት የውርስ ሀብት አከፋፈል እስከሚፈፀም ድረስ በወራሾች መካከል ውርሱ ሳይነጣጠል የሚቆይ መሆኑን እና ወራሾቹ በዚህ ባልተከፋፈለ የውርስ ሀብት ላይ ያላቸው መብት በፍትሐ ብሔር ህጉ ስለ የጋራ ባለሃብትነት በሚመለከተው የህጉ ድንጋጌዎች የሚወሰን ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ/1060(1) እና (2) ድንጋጌ ያስገነዝባል፡፡ ስለ የጋራ ባለሃብትነት የሚደነግገው የፍትሐ ብሔር ህጉ አንቀፅ 8 ምዕራፍ አንድ ደግሞ በአንድ ሀብት ላይ የጋራ ባለሃብት የሆኑት ሰዎች መብት እና ግዴታ የሚወሰነው የጋራ ባለሃብቱ በተቋቋመበት ውል እና የህጉን ግልፅ ድንጋጌን እስካልተላለፈ ድረስ በጋራ ባለሃብቶቹ መካከል በሚደረግ የውል ስምምት መሰረት ስለመሆኑ፣ በዚህ መልኩ የተደረገ ስምምነት ከሌለ ወይም ስምምነት ቢኖርም ያልተሟላ እና ብቁ ባልሆነበት ጊዜ ደግሞ የእያንዳንዱ የጋራ ባለሃብት ድርሻ ሀብት እኩል እንደሆነ የሚገመት ስለመሆኑ እና የመብቱ አፈፃፀምም በዚሁ መልኩ የሚመራ ስለመሆኑ ከፍ/ብ/ህ/ቁ/1258፣ 1259 እና ተከታዮቹ ድንጋጌዎች መገንዘብ ይቻላል፡፡

በዚሁ አግባብ አሁን ክርክር የቀረበበት ቤት የተሰራበት ይዞታ የውርስ ሀብት በመሆኑ እና በወራሾች መካከል ያልተከፋፈለ በመሆኑ አመልካች እና ሌሎች ወራሾች በይዞታው ላይ እኩል መብት ከሚኖራቸው በቀር የአንዱ ወራሽ ድርሻ መጠን ተለይቶ “ይህ ያክል ነው” የሚባል አይሆንም፡፡ በእንደዚህ ዓይነት ይዞታ ላይ በአንዱ ወራሽ የሚደረግ የትኛውም ግንባታ በሌላ ሰው ይዞታ ላይ ስለሚደረግ ግንባታ በሚመለከተው የፍትሐ ብሄር ህጉ የሚመራ ይሆናል፡፡

የራሱ ባልሆነ ይዞታ ላይ ቤት/ህንፃ/ የሰራ ሰውን በተመለከተ የቤቱ ሰሪ ስለሚኖረው የመብት አድማስ በፍ/ብ/ህ/ቁ/1178 እና 1179 ስር ተደንግጓል፡፡ በዚሁ መሰረት የራሱ ባልሆነ ይዞታ ላይ ቤት የሰራ ሰው የሚኖረው መብት ቤቱ ሲሰራ ባለይዞታው በሚኖረው እውቀት እና ፈቃድ ላይ የተመሰረተ መሆኑን፣ ቤቱ ባለይዞታው እየተቃወመ ተሰርቶ ከሆነ ቤቱን የሰራው ሰው ምንም ዓይነት መብት በሰራው ቤት ላይ የሌለው መሆኑን፣ ሆኖም ቤቱ የተሰራው ያለተቃውሞ ከሆነ የሰራው ሰው የቤቱ ባለቤት የሚሆን ስለመሆኑ እንደቅደም ተከተላቸው ከፍ/ብ/ህ/ቁ/1178(1) እና 1179(1) ድንጋጌዎች ይዘት መገንዘብ ይቻላል፡፡

በተያዘው ጉዳይ አመልካች የወራሾች የጋራ በሆነ ይዞታ ላይ ክርክር የተነሳበትን ቤት በ1993 ዓ.ም በራሳቸው ወጪ የሰሩ ለመሆኑ የተረጋገጠ ጉዳይ ነው፡፡ በእርግጥ በዚህን ጊዜ የግራ ቀኙ አውራሽ በህይወት የነበሩ ለመሆኑ የታወቀ ነገር የለም፡፡ አውራሻቸው በህይወት ኖሩም አልኖሩም

አመልካች በይዞታው ላይ ቤቱን ሲሰሩ ከአውራሻቸውም ሆነ ከሌሎች ወራሾች ቤቱ እንዳይሰራ የቀረበ ተቃውሞ የነበረ ለመሆኑ የቀረበ ክርክርም ሆነ የተረጋገጠ ነገር የለም፡፡ ይህ ከሌለ አመልካች ያለተቃውሞ ቤቱን የሰሩ ለመሆኑ ግምት የሚያስወስድ በመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ/1179(1) በሚያዘው መሰረት ቤቱ የአመልካች የግል ሀብት ይሆናል፡፡ ቤቱ የአመልካች የግል ሀብት ከሆነ ሌሎች ወራሾች የቤቱን ዋጋ ከፍለው ከአመልካች ጋር የሚካፈሉበት የህግ አግባብ የለም፡፡ ጉዳዩ ይህ በሆነበት የክልሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ለአመልካች የቤቱ ግምት ተከፍሎ ከሌሎች ወራሾች ጋር እኩል እንዲካፈሉ በሚል መወሰኑ እና በየደረጃው ያሉት የክልሉ የበላይ ፍርድ ቤቶችም ይህንኑ ውሳኔ ማፅናታቸው የፍትሐ ብሄር ህግ ቁጥር 1179(1) ድንጋጌን መሰረት ያላደረገና መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በመሆኑም ተከታዩ ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

ውሳኔ

1. በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የሰሜን ጎንደር ዞን መስተዳድር ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ/01-04881 ላይ ታህሳስ 25/2010 ዓ.ም ተሰጥቶ በክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ/03-90267 ላይ መጋቢት 20/2011 ዓ.ም በዋለው ችሎት የፀደቀው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁጥር 348(1) መሰረት ተሻሽሏል፡፡
2. ክርክር የተነሳበትን ቤት አመልካች በራሳቸው ወጪ ያለምንም ተቃውሞ የጋራ በሆነ የውርስ ይዞታ ላይ የሰሩ በመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁጥር 1179(1) በሚፈቅደው መሰረት ቤቱ የአመልካች የግል ሀብት ነው፡፡
3. ክርክር የተነሳበት ቤት ከተገነባበት እና ቤቱ ካረፈበት ቦታ ውጭ ያለውን ይዞታ በተመለከተ አመልካች እና ከ2ኛ እስከ 4ኛ ያሉት ተጠሪዎች እኩል የወራሽነት መብት አላቸው በማለት ተወስኗል፡፡
4. ይህ ውሳኔ አመልካች በአፈፃፀም ወቅት የመውጫ እና መግቢያ መብት እንዲከበርላቸው የሚያቀርቡትን መብት ከመጠየቅ አያግዳቸውም፡፡

ትዕዛዝ

1. የዚህን ሰበር ችሎት ክርክር ወጪ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡
2. መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ይመለስ፡፡

የልዩነት ሀሳብ

እኔ ስሜ በተራ ቁጥር 3 ስር የተሰየምኩት የችሎቱ ዳኛ አብላጫው የችሎቱ ዳኞች ከሰጡት ውሳኔ በከፊል በሀሳብ ስለምለይ ሀሳቤን እንደሚከተለው እገልፃለሁ፡፡

በአመልካች እና በተጠሪዎች መካከል ያለው በውርስ ሊከፋፈል በሚገባው ይዞታ ላይ ወራሾች ሳይቃወሙ የተሰራ ቤት ቤቱን የገነባው ሰው ሃብት የሚያደርገው በመሆኑ በቀረበው ጉዳይም ክርክር ያስነሳው ቤት በውርስ ይዞታ ላይ **አመልካች ይዞታውን በምን አግባብ እንዳገኙ ያለመታወቁን የካርታው ሕጋዊነትም ያልተረጋገጠ ስለመሆኑ በስር ፍ/ቤት ውሳኔ ላይ የተገለፀው እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ቤቱን መገንባታቸው ምን በሚል እና ማን በሰጠው ማስረጃ እንደተረጋገጠ በስር ፍ/ቤት ውሳኔ ላይ ባይገልጽም** ሆኖም በማስረጃ ማረጋገጡን የስር ፍ/ቤት የገለፀ በመሆኑ በፍሬ ነገር ደረጃ ማስረጃን መዝኖ እና ፍሬ ነገርን አረጋግጦ የመወሰን ስልጣን ባለው የበታች ፍርድ ቤት የተረጋገጠ ነው ብለን ወስደን ይዞታው የውርስ ቢሆንም ቤቱን ግን አመልካች በግል ገንዘባቸው ተጠሪዎች ሳይቃወሟቸው የሰሩ በመሆኑ ቤቱ የአመልካች ነው ተብሎ መውሰኑ ተጠሪዎችም በቅሬታ ያላመጡ ሆነው በመገኘቱ ተገቢ ሆኖ ስላገኘሁት በአብላጫው ውሳኔ እስማማለሁ፡፡

ሆኖም ግን አመልካች በክርክራቸው የጠየቁት ቤት ከአርባ ዓመት በፊት አርቦች ይኖሩበት የነበረ እና አርቦች ለቀው ሲሄዱ እንጀራ እናታቸው ወ/ሮ ውብነሽ ተረክበው ይዘው እየተጠቀሙበት ያለ መሆኑን አንስተው ለዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት ያቀረቡት አቤቱታ የሚያሳይ ከመሆኑ አንፃር ተጠሪዎች በበኩላቸው ከስር ፍ/ቤት ጀምሮ ክርክር ያስነሳውን ቤት በ1987 እናታቸው በባህል የሽያጭ ውል መሠረት ገዝተው ከዓመት በኋላ አድሰው ይኖሩበት እንደነበረ የተከራከሩ በመሆኑ፣ የስር ፍ/ቤትም የሽያጭ ውል መኖሩን እና ቤቱን የተጠሪዎች እናት ገዝተው አድሰው ይኖሩበት እንደነበረ ግብርም እየገበሩበት መሆኑን ያረጋገጡ ስለመሆኑ በስር ፍርድ ቤት ውሳኔ ገጽ 4 ላይ የገለፀ ሆኖ ስላገኘሁት አመልካች አሁን ያለውን እና የሚከራከረውን ቤት በባዶ ቦታ ላይ ተጠሪ ሰርቷል በመባሉ ብቻ ቀድሞ የተገዛውና የታደሰ ቤት ስለመኖሩ አለመኖሩ ሳይረጋገጠና ቤት የነበረው ቦታ እንዴት ባዶ ሊሆን እንደቻለም ሳይጣራ በስር ፍርድ ቤት መወሰኑ ማስረጃ መዝኖ እና ፍሬ ነገርን በአግባቡ መዝኖ አውነት ላይ በመድረስ የመወሰን መሰረታዊ የህግ ስህተት የፈፀመ በመሆኑ ሊታረም የሚገባውና ተጣርቶም እንዲወሰን ወደ ስር ፍርድ ቤት ሊመለስ የሚገባው ሆኖ አግኝቼዋለሁ፡፡

ይህ ታልፎ አሁን እያከራከር ያለው ቤት የተሰራው በአመልካች ነው ተብሎ መወሰኑን የምንቀበለው፣ በመሆኑ ቀድሞ የተጠሪዎች እናት በግዥ አግኝተውት አድሰውት የነበረው ቤት የሌለ በመሆኑ የዚህን ቤት ግምት ግን አመልካች የድርሻቸውን አንስተው ቀሪውን ለተጠሪዎች ድርሻ ክፍፍል የመክፈል ሀላፊነትን የሚያስቀር ባለመሆኑ በግዥ የተጠሪዎች እናት ያገኙት ቤት እድሳት የተደረገበትን ገንዘብ ጨምሮ ተሰጥቶ እንደ ውርስ ሀብት ተቆጥሮ አመልካች ሊከፍሉ ይገባው የነበረ በመሆኑ የስር ፍርድ ቤት ይህን አልፎ መወሰኑ እና አብላጫው ድምጽ በሰጠው ውሳኔ ላይ አንስቶ ሳይወስን ማለፉ ስህተት ነው ብዬ ስለማምን በሀሳብ ተለይቻለሁ፡፡

የማይነበብ የአንድ ዳኛ ፊርማ አለበት

የሰበር መዝገብ ቁጥር 245258

መጋቢት 26 ቀን 2016 ዓ.ም

ዳኞች፡- እትመት አሠፋ

ደጀኔ አያንሳ

ኑረዲን ከድር

መላኩ ካሳዬ

ሀብታሙ እርቅይሁን

አመልካች፡-1ኛ. ሳምራዊት አረጋ

2ኛ. መቅደስ የሻው (ሞግዚት ሳምራዊት አረጋ) } ጠበቃ ደሳለኝ የኔአካል - ቀረቡ

ተጠሪ፡- ደረሰ ታደሰ - ቀርቧል

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍርድ

ጉዳዩ የውርስ ንብረት ክርክርን የሚመለከት ሆኖ ክሱ በቀረበበት በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ደቡብ ወሎ ዞን መስተዳድር በወግዲ ወረዳ ፍርድ ቤት አመልካቾች ከሳሽ ሲሆኑ ተጠሪ እና በሰበር ክርክሩ የሌሉት አብረሃም አሰፋ የተባሉት ግለሰብ በተከሳሽነት ተከራክረዋል፡፡ አመልካቾች የካቲት 16 ቀን 2014 ዓ.ም ያቀረቡት ክስ ይዘት በአጭሩ፡- ተጠሪ እና 2ኛ ተከሳሽ የነበሩት አብርሃም አሰፋ የተባሉት ግለሰብ አዋሳኙ እና መጠኑ በክሱ ላይ የተመለከተውን የሚች እናታቸው የሔነውን የእርሻ መሬት እና በ2013 ዓ.ም እና 2014 ዓ.ም የውርስ ይዞታ ከሆነው መሬት የተገኘውን የመሬት አላባ የውርስ ድርሻቸውን እንዲያካፍላቸው ፤ እንዲሁም የያዙብንን ከሚች እናታችን በኑዛዜ የተላለፈልንን 75 ቅጠል ቆርቆሮ ቤት ለቀው እንዲያስረክቡን በማለት ጠይቀዋል፡፡

ተከሳሾቹም መጋቢት 1 ቀን 2014 ዓ.ም በተፃፈ መልስ የሚች እናታችንን የእርሻ መሬት አልከለከልናቸውም ይውሰዱ ፤ ሚች እናታቸው ከእናቷ የወረሰችው መሬት ሚች በህይወት እያለች 75 ቅጠል ቆርቆሮ ቤት የሰራች ሲሆን ቀሪውን ይዞታ በሚጅ እና በሥር ተከሳሾች መካከል ተደርጎ በፍርድ ቤት በፀደቀ ስምምነት ለ1ኛ ተከሳሽ ቁመቱ 42 ሜትር ወርዱ 6 ሜትር ፤ ለ2ኛ ተከሳሽ ቁመቱ 25 ሜትር ወርዱ 8 ሜትር የሆነ ቦታ ለቤት መስሪያ በስምምነት ከተላለፈልን ውጭ በእጃችን የለም፡፡ እናታችን በሕይወት እያለች የተላለፈልን ይዞታ ልንጠየቅ አይገባም፡፡ አመልካቾች በኑዛዜ ተላልፎልናል የሚሉት ሽማግሌ ውሉን ካፀደቀው ወዲህ ስላላወቅነው ኑዛዜው

ይፍርስልን፡፡ የ2013 ዓ.ም አላባን በአውድማ ተካፍለው የወሰዱ ሲሆን የ2014 ዓ.ም እኩል አራሹ እጅ ስለሚገኝ እኛም አልወሰድንም በማለት ተከራከረዋል፡፡

ፍ/ቤቱም ግራ ቀኙ በተማመኑበት ጉዳይ ላይ ከፊል ፍርድ ሰጥቶ በአከራካሪዎቹ ጉዳዮች ላይ የአመልካቾችንና የሥር ተካሳሾችን ክርክር እና ማስረጃ ካዳመጠ በኋላ ለክርክር መነሻ የሆነው 75 ቅጠል ቆርቆሮ ቤት ሟች ለአመልካቾች በማስተላለፍ ያደረጉት ኑዛዜ የሥር ተከሳሾችን ከውርስ የነቀለበትን ምክንያት በግልጽ ስለማያመለክት ኑዛዜው ፈራሽ ሆኖ አመልካቾች በፍትሐ ብሔር ሕጉ ቁጥር 839/3 ድንጋጌ መሠረት በኑዛዜ ጠቅላላ ስጦታ እንደተደረገላቸው ተቆጥረው ከሥር ተከሳሾች ጋር በጋራ እንዲካፈሉ ወስኗል፡፡ አመልካቾች ኑዛዜው ፈርሶ አከራካሪውን 75 ቅጠል ቆርቆሮ ቤት ግራ ቀኙ እኩል ይካፈሉ በማለት የተላለፈውን ውሳኔ በመቃወም ባቀረቡት የይግባኝ አቤቱታ ጉዳዩን የተመለከተው የደቡብ ወሎ መስተዳድር ከፍተኛ ፍርድ ቤት የግራ ቀኙ እናት ካላቸው ንብረት አንፃር አንድ ቤት ለአመልካቾች መናዘዛቸው ከውርስ መንቀልን ማስከተል አለማስከቱን ለማጣራት ያስቀርባል በማለት የሥር ተካሳሾችን ክርክር ሰምቶ ሟች ወ/ሮ የሮም አሰፋ የካቲት 6 ቀን 2012 ዓ.ም በወግዲ ወረዳ ፍትህ ጽ/ቤት ባደረጉት ኑዛዜ አከራካሪውን 75 ቅጠል ቆርቆሮ ቤት በፍትሐ ብሔር ህጉ ቁጥር 882 መሠረት የተናዘዙ መሆኑ የተረጋገጠ ሲሆን የሥር ተከሳሾች በጽሑፍ መልሳቸውም ሆነ በቃል ክርክር ወቅት ኑዛዜው ከውርስ ይነቅለናል የሚል ክርክር አላቀረቡም፡፡ አቅርበዋል ቢባል እንኳን የሟችን ይዞታ መሬት ግራ ቀኙ እንዲካፈሉ ከመወሰኑም ባሻገር ሟች የሮም አሰፋ ለሥር ተከሳሾች የቤት መስሪያ ቦታ የሰጧቸው መሆኑ ተረጋግጦ የውርስ ንብረት አይደለም የሚል ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡ የቤት መስሪያ ቦታ የተሰጠው እና ኑዛዜ የተደረገው በተመሳሳይ አመት ከመሆኑ አንፃር የሟች ፍላጎት ሊፈፀም ስለሚገባው ኑዛዜ መሻር የለበትም፡፡ ኑዛዜው ፈርሶ ግራ ቀኙ እኩል ሊካፈሉ ይገባል ሲል የወግዲ ወረዳ ፍርድ ቤት የሰጠውን የውሳኔ ክፍል በአብላጫ ድምጽ በመሻር የተቀረውን የውሳኔ ክፍል በማጽናት ወስኗል፡፡

በዚህ ውሳኔ ቅር የተሰኙት ተጠሪ ባቀረቡት የይግባኝ አቤቱታ ጉዳዩን የተመለከተው ይግባኝ ሰሚው የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ግራ ቀኙን አከራክሮ በሰጠው ውሳኔ የሥር ተከሳሾች በሥር ፍርድ ቤት ኑዛዜው ፈራሽ ተደርጎ ቤቱ የጋራ እንዲባልላቸው ክርክር ያቀረቡ በመሆኑ ኑዛዜው በየትኛው ህጋዊ ምክንያት ፈራሽ ሊሆን ይችላል የሚለው ጭብጥ ፍርድ ቤት በራሱ የሚመረምረው ጉዳይ ሆኖ እያለ የደቡብ ወሎ መስተዳድር ከፍተኛ ፍርድ ቤት ተጠሪ ኑዛዜው ከውርስ ይነቅለኛል በሚል ያቀረቡት ክርክር የለም ማለቱ አግባብነት የለውም፡፡ በሌላ በኩል አመልካቾች ሟች ለሥር ተከሳሾች ከሰጠችው ንብረት ውጭ ሌላ ንብረት ለሥር ተከሳሾች የሰጠች ለመሆኑ ያቀረቡት ክርክርም ሆነ ማስረጃ የሌለ ሲሆን ሟች የቤት መስሪያ ቦታ ሰጥታለች ቢባል እንኳን በክርክር ሂደት በፍርድ ቤት ውሳኔ የተገኘ ከመሆኑ ጋር ተያይዞ ሟች ካላቸው ንብረት ላይ በፈቃዳቸው በኑዛዜ እንዳስተላለፉት የውርስ ድርሻ የሚቆጠር ባለመሆኑ ሟች የተጠሪን ድርሻ ለይታ በኑዛዜ

የሰጠች መሆኑ ባልተረጋገጠበት ወይም በፍትሐ ብሔር ሕጉ ቁጥር 1123/3 መሰረት ለተጠሪ በቂ ውርስ ሀብት ድርሻ መኖሩ ባልተረጋገጠበት ሁኔታ ኑዛዜው ተጠሪን አይነቅልም መባሉ ተገቢ አለመሆኑን ጠቅሶ የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሳኔ በመሻር የወረዳ ፍ/ቤት ውሳኔን አጽንቷል፡፡

በዚህ ውሳኔ ባለመስማማት አመልካቾች ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የሰበር አቤቱታ ያቀረቡ ሲሆን ችሎቱም በሥር ተከሳሾች ኑዛዜው ይነቅለናል የሚል ግልጽ መከራከሪያ ባልቀረበበት ፍርድ ቤት በራሱ ማንሳት ይችላል ከተባለ አመልካቾች ሚች ካላቸው ንብረት አኳያ ኑዛዜው የሚነቅል መሆን አለመሆኑን አንስቶ የመከራከር መብት ማጣበብ አለማጣበቡን ፣ ተጠሪ ኑዛዜው ፈራሽ ሊሆን ይገባል በማለቱ ምክንያት ብቻ አመልካች ኑዛዜው የማይፈርስበትን ማንኛውንም ምክንያት ፍርድ ቤቱ ሊያነሳብኝ ይችላል በሚል መላምት መልስ እንዲሰጥ በሚያደርግ መልኩ ፍርድ ቤት መንቀልን ማንሳት ይችላል የመባሉን አግባብነት ፣ ይህም የሚታለፍ ከሆነ ይነቅላል አይነቅልም የሚለው ጭብጥ ክርክር ተደርጎበት በማስረጃ ተጣርቶ መወሰን አልነበረበትም ወይ የሚለውን ለማጣራት ጉዳዩ ያስቀርባል በማለት ተጠሪ በሰበር አቤቱታው ላይ መልስ እንዲሰጡ በማድረግ ጉዳዩ እንደመረመረው፡- ተጠሪ በሚች የተደረገው ኑዛዜ ፈራሽ ተደርጎ ለክርክር መነሻ የሆነው ቤት የጋራ እንዲባል በማለት ያቀረቡት ክርክር ኑዛዜውን የተቃወሙ መሆኑን የሚያመለክት ነው፡፡ ተጠሪ የሚች ልጅ መሆናቸው አከራካሪ እስካልሆነ ድረስ ኑዛዜው ከውርስ በዝምታ የሚነቅል መሆን አለመሆኑ ከአጠቃላይ የኑዛዜ ሰነድ ሕጋዊነት ጋር ተያይዞ የሕግ ግምቱ በፍርድ ቤቶች በፊፃሚ ከሚሆን በቀር አንደኛው ወገን ስለኑዛዜው መንቀል አለመንቀል በግል ክርክር እንዲያቀርብ የሚገደድበት ምክንያት አይኖርም፡፡ ተጠሪ የቤት መስሪያ ቦታ ያገኙት በፍርድ ቤት በተደረገ ክርክር በውሳኔ እንጅ በሚች ፍላጎት በተደረገ ሥጦታ ካለመሆኑም በላይ በአመልካቾች በኩል ሚች በህይወት እያለች ለተጠሪ ድርሻ የሚሆን የቤት መስሪያ ቦታ በፈቀዷ ሰጥታዋለች የሚል ክርክር ያልቀረበ ሲሆን በዚህ አግባብ የተረጋገጠ ፍሬ ነገር የለም፡፡ በሚች ወ/ሮ የሮም አሰፋ የተደረገው ኑዛዜ ተጠሪን ከውርስ የሚነቅል በመሆኑ ፈራሽ ሆኖ ለክርክሩ መነሻ የሐነው 75 ቅጠል ቆርቆሮ ቤት ግራ ቀኙ እኩል እንዲካፈሉ የተሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት አይደለም በሚል የይግባኝ ሰሚ ችሎቱን ውሳኔ አጽንቷል፡፡

የሰበር አቤቱታው የቀረበው የወግዲ ወረዳው ፍርድ ቤት የሠጠውን ውሳኔ በማጽናት የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚው ችሎት እንዲሁም የሰበር ሰሚ ችሎቱ የሰጠውን ውሳኔ በመቃወም ሆኖ ቅሬታው በአጭሩ፡- ተጠሪ በወረዳ ፍርድ ቤትም ሆነ በዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ክርክር ከቀረበበት ቤትና ቦታ ልካፈል ይገባል ከማለት ውጪ ኑዛዜው ከውርስ ይነቅለኛል የሚል ክርክር ሳያቀርብ በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በሥር ፍርድ ቤት ያልተነሳን

መከራከሪያ ማቅረቡ የፍትሐ ብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 329 ድንጋጌን ይቃረናል በማለት ያቀረብነውን የሰበር አቤቱታ የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ተቀብሎ ችሎቱም በሥር ተከሳሾች ኑዛዜው ይነቅለኛል የሚል ግልጽ መከራከሪያ ባልቀረበበት ፍርድ ቤት በራሱ ማንሳት ይችላል ከተባለ አመልካቾች ሟች ካላቸው ንብረት አኳያ ኑዛዜው የሚነቅል መሆን አለመሆኑን አንስቶ የመከራከር መብት ማጣበብ አለማጣበቡን ፤ተጠሪ ኑዛዜው ፈራሽ ሊሆን ይገባል በማለቱ ምክንያት ብቻ አመልካች ኑዛዜው የማይፈርስበትን ማንኛውንም ምክንያት ፍርድ ቤቱ ሊያነሳብኝ ይችላል በሚል መላምት መልስ እንዲሰጥ በሚያደርግ መልኩ ፍርድ ቤት መንቀልን ማንሳት ይችላል የመባሉን አግባብነት፤ ይህም የሚታለፍ ከሆነ ይነቅላል አይነቅል የሚለው ጭብጥ ክርክር ተደርጎበት በማስረጃ ተጣርቶ መወሰን አልነበረበትም ወይ የሚለውን ለማጣራት ጉዳዩ ያስቀርባል ቢልም የያዛቸውን ጭብጦች በአግባቡ ሳይመረምር የሰጠው ውሳኔ ሕግን የተከተለ አይደለም፡፡ ለአመልካቾች የተላለፈው ቤት እና ቦታ ሟች ካላት በርካታ መሬት እና ቦታ ላይ አነስተኛ በመሆኑና ተጠሪ ከውርስ ሀብቱ ከ1/4ኛ ድርሻ በላይ ያገኘ በመሆኑ ለአመልካቾች የተደረገው ኑዛዜ ከውርስ የማይነቅለው አይደለም፡፡ ሟች እናታችን በህይወት እያለች የቤት መስሪያ ቦታ የሰጠችው ሲሆን ከእርሻ መሬቱም ድርሻውን አግኝቶ እያለ አከራካሪው ቤት የሟች ብቸኛ ንብረት እንደሆነ የሚያቀርበው ክርክር ተቀባይነት የለውም፡፡ ተጠሪ ኑዛዜው የማይፀናበትን ምክንያት በመጥቀስ በወረዳ ፍርድ ቤት ያቀረበው መከራከሪያ ሳይኖር የወግዲ ወረዳ ፍርድ ቤት እና ይግባኝ ሰሚው የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የደረሱበት ድምዳሜ የፍትሐ ብሔር ሥነ ሥርዓት ሕጉን ቁጥር 329 ድንጋጌን የሚቃረን ከመሆኑም በላይ ሟች ለተጠሪ ባደረገችው ስጦታ ያገኘውን የቤት መስሪያ ቦታ የውርስ ሀብት አካል አይደለም ካሉ በኋላ ሟች ባደረገችው ኑዛዜ ለአመልካቾች የተላለፈውን 75 ቅጠል ቆርቆሮ ቤት የውርስ ሀብት ነው በማለት ግራ ቀኙ እኩል እንድንካፈል መወሰኑ ኢፍትሀዊ ነው በማለት ሟች ያደረገችው ኑዛዜ ለፈርስ አይገባም ተብሎ እንዲወሰን ጠይቀዋል፡፡

በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ሥነ ሥርዓት መመሪያ ቁጥር 17/2015 ቁጥር 6(1) መሠረት ለሰበር ሰሚው ችሎቱ የተመራው አቤቱታ በሰበር ሰሚ ችሎቱ ተመርምሮ የግራ ቀኙ እናት ሟች ወ/ሮ የሮም አሰፋ ያደረጉት ኑዛዜ ተጠሪን ከውርስ ስለሚነቅል ሊፈርስ ይገባል ተብሎ መወሰኑ ተጠሪ ያቀረቡትን ክርክር መሠረት ያደረገ መሆን አለመሆኑን ለማጣራት የሰበር አቤቱታው ያስቀርባል ተብሎ ተጠሪ ተከታዩን ምላሽ ሰጥቷል፡፡

ተጠሪ ሐምሌ 10 ቀን 2015 ዓ.ም ጽፎ ባቀረቡት መልስ በወረዳ ፍርድ ቤት በነበረው ክርክር ተከሳሾች የነበሩት ተጠሪ እና ወንድማቸው የሆኑት 2ኛ ተከሳሽ ሟች እናታቸው በኑዛዜ በዝምታ የነቀለቻቸው መሆኑን በመጥቀስ ኑዛዜው እንዲፈርስ ስለመጠየቃቸው ፤ ሟች የግራ ቀኙ እናት ወ/ሮ የሮም አሰፋ በህይወት ዘመናቸው ያላቸው ሀብት አከራካሪው ባለ 75 ክዳን ቆርቆሮ ቤት ብቻ ያፈሩ ሲሆን አመልካቾች ሟች ከዚህ ውጭ ሌላ ተንቀሳቃሽም ሆነ የማይንቀሳቀስ ንብረት ያላቸው

ለመሆኑ በሥር ፍርድ ቤት ያቀረቡት ክርክር እና ማስረጃ ሳይኖር እና ተጠሪ በውርስ ያገኘሁት አንዳች ንብረት በሌለበት በደፈናው ከፍተኛ ግምት ያለው ንብረት እንደወርሰኩ በማስመሰል የቀረበው የሰበር አቤቱታ ተቀባይነት የለውም፡፡ አንድ ተናዛዥ ወደ ታች የሚቆጠር ተወላጅን ከውርስ ለመንቀል በኑዛዜው ውስጥ ምክንያት መጥቀስ ተገቢ መሆኑ በሕጉ ተመልክቶ እያለ ሟች የጠቀሱት ምክንያት አለመኖሩ ተረጋግጦ የተሰጠው ውሳኔ የሚነቀፍ አይደለም፡፡ ከሟች አያታቸው በጎጆ መውጫነት በሰጣቸው መሬት ላይ ከሟች እናታቸው ወ/ሮ የሮም አሰፋ ጋር ተካሰው ባደረጉት እርቅ ስምምነት መሰረት ያገኙት ቦታ የሟች አለመሆኑ እየታወቀ ከሟች እናታቸው በስጦታ ወይም በኑዛዜ እንደተሰጠ ከፍተኛ ግምት እንዳለው የውርስ ሀብት አድርጎ የሚቀርበው ቅሬታ አግባብነት የሌለው በመሆኑ ሟች ያደረጉት ኑዛዜ ከ1/4ኛ በላይ ጉዳት ከማድረስ አልፎ ሙሉ በሙሉ ከውርስ የነቀለኝ በመሆኑ ለሰበር አቤቱታው ምክንያት የሆነው ውሳኔ ሊፀና ይገባል በማለት ተከራክረዋል፡፡ አመልካቾች የሰበር አቤቱታውን በማጠናከር የመልስ መልስ አቅርበዋል፡፡

ከዚህ በላይ አጠር ባለ መልኩ የተመለከተዉ የግራ ቀኝ ክርክር እና በስር ፍርድ ቤቶች የተሰጡ ዉሳኔዎች ይዘት ሲሆን እኛም የሰበር አጣሪ ችሎት ጉዳዩ ለሰበር ችሎት ያስቀርባል ሲል የያዘዉን ጭብጥ እና በስር ፍርድ ቤቶች ዉሳኔ ላይ የተፈጸመ መሰረታዊ የሕግ ስህተት መኖር አለመኖሩን አግባብነት ካለዉ ሕግ ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለዉ መርምረናል፡፡

ኑዛዜ ተናዛዡ በህይወት እያለ ከእሱ ሞት በኋላ ንብረቱን በሙሉ ወይም በከፊል ለሚፈልጋቸው ሰዎች የሚያስተላልፍበት እና ከውርስ የሚነቀሉትን ሰዎች ለይቶ የሚያስቀምጥበት የቃል መግለጫ ወይንም ሰነድ መሆኑን ከፍትሐ ብሔር ሕጉ ቁጥር 857(1) ፣ 892 ፣ 909 ፣ 949 ድንጋጌዎች ጣምራ ንባብ መገንዘብ ይቻላል፡፡ አንድ ተናዛዥ ልጁን ወይንም ወደ ታች የሚቆጠር ተወላጅን ያለ በቂ እና አሳማኝ ምክንያት ከውርስ ከነቀለ ኑዛዜው ፈራሽ እንደሚሆን የፍትሐ ብሔር ሕጉ ቁጥር 938(1) ይደነግጋል፡፡ ኑዛዜ በሕጉ የተመለከቱ ፎርማሊቲዎችንና ሁኔታዎችን አሟላቶ እስከተገኘ ድረስ የተናዛዡ ፍላጎት ማሳያ በመሆኑ ሊከበር ስለሚገባ ፈራሽ መሆን አለበት የሚለው ተከራካሪ ወገን ሊፈረስ ይገባል የሚልበትን ምክንያት መግለጽ አለበት፡፡

በተያዘው ጉዳይ ሟች ወ/ሮ የሮም አሰፋ የካቲት 6 ቀን 2012 ዓ.ም በወግዲ ወረዳ ፍትህ ጽ/ቤት ባደረጉት ኑዛዜ አከራካሪውን 75 ቅጠል ቆርቆሮ ቤት በፍትሐ ብሔር ህጉ ቁጥር 882 መሠረት ለአመልካቾች የተናዘዙ መሆኑ የተረጋገጠ ሲሆን የሥር ተከሳሾች አከራካሪው 75 ቅጠል ቆርቆሮ ቤት አመልካቾች በኑዛዜ ተላልፎልናል የሚሉት ሽማግሌ ውሉን ካፀደቀው ወዲህ ስላላወቅነው ኑዛዜው ሊፈርስ ይገባል ከማለት ባለፈ በጽሑፍ መልሳቸውም ሆነ በቃል ክርክር ወቅት ኑዛዜው ከውርስ ይነቅለናል የሚል ክርክር ያላቀረቡ ሲሆን ፣ የወግዲ ወረዳ ፍርድ ቤት ኑዛዜው የሥር ተከሳሾች የተነቀሉበትን ምክንያት በግልጽ ስለማያመለክት ፈራሽ ሆኖ አመልካቾች በፍትሐ

ብሔር ሕጉ ቁጥር 839/3 ድንጋጌ መሠረት በኑዛዜ ጠቅላላ ስጦታ እንደተደረገላቸው ተቆጥረው ከሥር ተከሳሾች ጋር በጋራ እንዲካፈሉ የወሰነው የሥር ተካሳሾች ኑዛዜው ከውርስ የነቀለ በመሆኑ ሊፈርስ ይገባል የሚል ምክንያት ባላቀረቡበት ሲሆን ተከሳሾቹ በምክንያትነት የጠቀሱት ኑዛዜውን አለማወቃቸውን ሲሆን ኑዛዜን አለማወቅ ለኑዛዜ መፍረስ በምክንያትነት በሕጉ አልተመለከተም፡፡ የሥር ተከሳሾች ኑዛዜው ፈራሽ ሊሆን ይገባል በማለታቸው ብቻ ኑዛዜው ፈራሽ ሊሆን የሚችልበት ሕጋዊ ምክንያት ተለይቶ የክርክር ጭብጥ ባልሆነበት አመልካቾች ኑዛዜው የማይፈርስበትን ማንኛውንም ምክንያት ፍርድ ቤቱ ሊያነሳብን ይችላል በሚል ግምት ክርክር እንዲያቀርቡ ማድረግ አግባብነት የሌለው የክርክር አመራር ከመሆኑም በላይ አከራካሪውን 75 ቅጠል ቆርቆሮ ቤት ለአመልካቾች በኑዛዜ ማስተላለፍ የሚች ወ/ሮ የሮም አሰፋ ፍላጎት በመሆኑ ሊከበር ሲገባው የወግዲ ወረዳ ቤት ኑዛዜውን መሻሩ እንዲሁም ይግባኝ ሰሚው እና ሰበር ሰሚው የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤትም ይህንን ውሳኔ ማጽናታቸው መሠረታዊ የሕግ ስህተት በመሆኑ ተከታዩ ተወስኗል፡፡

ውሳኔ

1. የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ሰሚው ችሎት የካቲት 29 ቀን 2015 ዓ.ም በዋለው ችሎት በሰበር መዝገብ ቁጥር 0337389 የሰጠው ፍርድ ፣ ውሳኔ እና ትዕዛዝ ፣ይግባኝ ሰሚው የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት መዝገብ ቁጥር 0112605 ታህሳስ 27 ቀን 2015 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጠው ፍርድ ፣ ውሳኔ እና ትዕዛዝ እንዲሁም የወግዲ ወረዳ ፍርድ ቤት መዝገብ ቁጥር 42435 ሰኔ 27 ቀን 2014 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጠው ፍርድ ፣ ውሳኔ እና ትዕዛዝ በፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ሥነ - ሥርዓት መመሪያ ቁጥር 17/2015 ቁጥር 9(1/ለ) መሠረት **ተሽሯል**፡፡

2. የደቡብ ወሎ መስተዳድር ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ጥቅምት 22 ቀን 2015 ዓ.ም በዋለው ችሎት በሰበር መዝገብ ቁጥር 55960 የሰጠው ፍርድ እና ውሳኔ እና ትዕዛዝ የሰበር ሥነ - ሥርዓት መመሪያ ቁጥር 17/2015 ቁጥር 9(1/ሀ) መሠረት **ፀንቷል**፡፡

3. በዚህ ችሎት የተደረገው ክርክር ያስከተለውን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

4. በዚህ መዝገብ ላይ ግንቦት 7 ቀን 2015 ዓ.ም የተሰጠው የዕግድ ትዛዝ ተነስቷል፡፡

5. ውሳኔው ሚያዝያ 9 ቀን 2016 ዓ.ም በችሎት ተነቧል፡፡

መዝገቡ ውሳኔ አግኝቶ ስለተዘጋ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፌርማ አለበት

ፍ/ደ

የሰ/መ/ቁጥር 236850

ግንቦት 29 **ቀን** 2015 **ዓ/ም**

ዳኞች፡- *ተፈሪ ገብሩ(ዶ/ር)*

እንዳሻው አዳነ

ተሾመ ሽፈራው

መላኩ ካሳዬ

ነፃነት ተገኝ

አመልካቾች፡- 1ኛ.አቶ መስፍን ዱባለ ወልደየስ

2ኛ.ወ/ሪት ገነት ዱባለ ወልደየስ

3ኛ.አቶ ደረጀ ዱባለ ወልደየስ

ተጠሪ፡- ወ/ሮ አልማዝ ዱባለ ወልደየስ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍርድ

ጉዳዩ በውርስ ማጣራት ሂደት ላይ ኑዛዜ እንዲፈርስ የቀረበ ክርክርን የሚመለከት ሲሆን ለዚህ ሰበር ችሎት ቅሬታ የቀረበው የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 213337 **በጥቅምት** 29 **ቀን** 2015 **ዓ.ም በሰጠው ውሳኔ ላይ ነው፡፡ ጉዳዩ በተጀመረበት የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የአሁን አመልካቾች ጣልቃ ገብ ተጠሪ ደግሞ አመልካች ነበሩ፡፡**

ተጠሪ በጥቅምት 24 **ቀን** 2013 **ዓ.ም በተባለ አቤቱታ የሟቾች አቶ ዱባለ ወልደየስ እና የእናታችን የወ/ሮ ሶርሱ ልሳነወርቅ የውርስ ሀብት የውርስ አጣሪ ተሹሞ ይጣራልን በማለት አቤቱታ አቅርበው ፍርድ ቤቱ የውርስ ሀብት ተጣርቶ እንዲቀርብ ትዕዛዝ ሰጥቷል፡፡ በውርስ አጣሪ ሪፖርቱ ላይ አመልካቾች ባቀረቡት አስተያየት ሟች እናታችን ለተጠሪ ያደረጉት ኑዛዜ ይፍረስልን በሚል ጠይቀው ፍርድ ቤቱም ውርስ እንዲጣራ በተጠየቀበት መዝገብ ላይ የኑዛዜ ይፍረስልኝ ክርክር ሊታይ አይችልም፡፡ ነገር ግን ሟች እናታቸው ባደረጉት ኑዛዜ በየካ/ክ/ከተማ ወረዳ** 12 **የቤ/ቁ**180 **ላይ ያላቸውን ድርሻ ለተጠሪ ብቻ**

መናዘዛቸው ሌሎች ወራሾችን ከውርስ የሚነቅላቸው በመሆኑ የተደረገው ጠቅላላ ኑዛዜ ፈርሶ ተጠሪ ከሌሎች ወራሾች ጋር እኩል ይካፈሉ ሲል የውርስ አጣሪ ሪፓርቱን በማሻሻል ወስኗል፡፡

ተጠሪ ሚች እናታቸው ያደረጉት ኑዛዜ ሊፈርስ ይገባል መባሉን በመቃወም ለፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የይግባኝ ቅሬታ አቅርበው ፍርድ ቤቱ ግራ ቀኙን ካከራከረ በኋላ አመልካቾች ሚች እናታቸው በህይወት እያሉ የባልና ሚስት የጋራ ንብረት የሆነውን በየካ ክ/ከተማ ወረዳ 02 የቤት ቁጥር 180 በሆነው ይዞታ ውስጥ ባዶ ቦታ ሰጥተዋቸው በግል ገንዘባቸው ቤት የሰሩበት መሆኑን አልካዱም፡፡ ይህ ከሆነ ደግሞ አመልካቾች ሚች ወ/ሮ ሶርሱ ባደረጉት ኑዛዜ መነሻነት ከውርስ ሀብቱ ላይ ሊደርሳቸው ከሚገባው የሀብት ድርሻ ከ1/4 በላይ ጉዳት የደረሰባቸው ስለመሆኑ በማስረጃ ማረጋገጥ ይጠበቅባቸዋል፡፡ አመልካቾች ኑዛዜው ከ1/4ኛ በላይ ጉዳት የሚያደርስባቸው መሆኑን ባላስረዱበት ሁኔታ ኑዛዜው አመልካቾችን ከውርስ ነቅሏል ሊባል አይገባም፡፡ በመሆኑም የስር ፍርድ ቤት ሚች ወ/ሮ ሶርሱ ልሳነወርቅ ለተጠሪ ያደረጉት ኑዛዜ አመልካቾችን ከውርስ የነቀለ ነው ሲል የደረሰበት ድምዳሜም ሊታረም የሚገባው ነው በማለት የስር ፍርድ ቤትን ውሳኔ አሻሽሏል፡፡ አመልካቾች በዚህ ውሳኔ ላይ የይግባኝ ቅሬታ ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ያቀረቡ ቢሆንም ፍርድ ቤቱ ግራ ቀኙን አስቀርቦ ካከራከረ በኋላ የከፍተኛውን ፍርድ ቤት ውሳኔ አጽንቷል፡፡

አመልካቾች በህዳር 12 ቀን 2015 ዓ.ም ጽፈው ባቀረቡት የሰበር ቅሬታ ሚች ወ/ሮ ሶርሱ ልሳነወርቅ ፈቅደውልን በባዶ መሬት ላይ የሰራነው ቤት የውርስ ሀብት የሚባልበት አግባብ የለም፡፡ ባዶ መሬት የመንግስት ነው፡፡ በመንግስት ቦታ ላይ በግል ገንዘባችን ቤት ሰራን እንጂ የውርስ ሀብት የሆነ አንድም ቤት አልተሰጠንም፡፡ የሚቾች የውርስ ሀብት የሆነው ዋናው ቤት በመሆኑ በዚህ ቤት ላይ የተሰጠ ኑዛዜ ተወላጅን የነቀለ በመሆኑ ሊፈርስ ይገባል፡፡ ሚች ወ/ሮ ሶርሱ ልሳነወርቅ ያላቸው የውርስ ሀብት በየካ ክ/ከተማ ወረዳ 02 የቤ/ቁ 180 የሆነው ቤት ብቻ ሲሆን ይህንኑም ለተጠሪ ብቻ የተናዘዙ እና ኑዛዜው አመልካቾችን ከውርስ የሚነቅል በመሆኑ ፈርሶ የውርስ ሀብቱን ወራሾች እኩል ልንካፈል ይገባል፡፡ በመሆኑም የስር ከፍተኛ እና ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰጡት ውሳኔ ተሽሮ የስር የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ውሳኔ ይጽናልን በማለት ጠይቀዋል፡፡

የአመልካቾች ቅሬታ በሰበር አጣሪ ችሎት ተመርምሮ ሚች ወ/ሮ ሶርሱ ልሳነወርቅ በቤት ቁጥር 180 ላይ 50% ለአሁን ተጠሪ እንዲሆን የተናዘዙት ኑዛዜ አመልካቾችን ከውርስ የሚነቅል በመሆኑ ኑዛዜው ይሻርልን ሲሉ ያቀረቡት የዳኝነት ጥያቄን በተመለከተ አመልካቾች በሚች ወ/ሮ ሶርሱ ልሳነወርቅ ቦታ ተሰጥቷቸው ቤት ሰርተውበት እያለ እንዲሁም ከሚገባቸው ላይ ከ1/4 በታች ጉዳት ያልደረሰባቸው በመሆኑ ኑዛዜው ሊፈርስ አይገባም የመባሉን አግባብነት ከሰበር መ/ቁ 96628 አኳያ መጣራት ስላለበት ተጠሪ መልሳቸውን ይዘው እንዲቀርቡ ተጠይቀዋል፡፡

ተጠሪ በየካቲት 6 ቀን 2015 ዓ.ም ጽፈው ባቀረቡት መልስ አመልካቾች ሚች ያደረጉትን ኑዛዜ እንዲፈርስ በማለት ስልጣን ባለው ፍርድ ቤት ባልጠየቁበት ሁኔታ ሰበር አጣሪው እንደጠየቁ አድርጎ የደረሰበት ድምዳሜ በስር ፍርድ ቤቶች ከተደረገው ክርክርና ከተሰጠው ውሳኔ ውጭ ነው፡፡ የሰበር አጣሪው የጠቀሰው የሰ.መ.ቁ 96628 ለጉዳዩ አግባብነት የሌለው ነው፡፡ ሚች ወ/ሮ ሶርሳ ልሳነወርቅ አመልካቾችን ከውርስ ሀብት ላይ አልነቀሉም ይልቁንም በህይወት እያሉ ከይዞታቸው ላይ በመቀነስ ለእያንዳንዳቸው አመልካቾች ቤት መስሪያ ቦታ ሰጥተዋቸው ቤት ሰርተው እየተጠቀሙበት ይገኛሉ፡፡ ይህንን ሳይክዱ ሚች ከውርስ ነቅለውናል ሲሉ ያቀረቡት ክርክር ቅን ልቦና የጎደለው ነው፡፡ አመልካቾች ከሚች ወ/ሮ ሶርሱ ልሳነወርቅ ሊያገኙት ከሚገባው የውርስ ድርሻ ከሩብ (1/4) በላይ ጉዳት የደረሰባቸው መሆኑን በተጨባጭ ሁኔታ አላስረዱም፡፡ በመሆኑም የአመልካቾች አቤቱታ ተሰርዞ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት እንዲሁም የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰጡት ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት ያልተፈፀመበት ነው ተብሎ ይጽናልኝ ብለዋል፡፡

አመልካቾች በመጋቢት 05 ቀን 2015 ዓ.ም የተጻፈ የሰበር አቤቱታውን የሚያጠናክር የመልስ መልስ አቅርበዋል ፡፡

የክርክሩ አመጣጥ ከላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም ያስቀርባል ሲባል የተያዘውን ጭብጥ ከግራ ቀኙ ክርክር፤ በስር ፍርድ ቤት በማስረጃ ከተረጋገጠው ፍሬ ነገር እና ከተገቢው የህግ ድንጋጌ ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለው መርምረናል፡፡

እንደመረመርነው ተጠሪና የስር 2ኛ አመልካች የሚች እናት እና አባታቸው የውርስ ሐብት እንዲጣራ ሲጠይቁ የአሁን አመልካቾች ሚች እናታቸው ለ1ኛ ተጠሪ ያደረጉት ኑዛዜ ከውርስ ነቅሎናል በሚል እንዲፈርስ ጠይቀዋል፡፡ ጉዳዩን በመጀመሪያ የተመለከተው ፍርድ ቤት ኑዛዜው ተወላጅ የሆኑትን አመልካቾችን ከውርስ ሐብት የሚነቅል ነው በሚል እንዲፈርስ የወሰነ ቢሆንም ጉዳዩን በይግባኝ የተመለከቱት የፌደራል ከፍተኛ እና ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሚች እናታቸው በህይወት እያሉ ለአመልካቾች ባዶ መሬት ሰጥተዋቸው ቤት የሰሩ በመሆኑ ምክንያት በኑዛዜው ላይ የተጠቀሰውን ቤት 1/2ኛ ድርሻ ለተጠሪ ብቻ መናዘዛቸው አመልካቾች ከውርስ ተነቅለዋል የሚያስብል አይደለም በማለት የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትን ድምዳሜ ቀይረዋል፡፡ አመልካቾች በሚች እናታቸው ባዶ መሬት ተሰጥቷቸው ቤት የሰሩ መሆኑን አይክዱም፡፡ አጥብቀው የሚከራከሩት ባዶ መሬት የመንግስት ነው፡፡ በመሬቱ ላይ በግል ገንዘባችን ቤት መስራታችን የውርስ ድርሻ እንዳገኘን ሊያስቆጥር አይገባም በሚል ነው፡፡ በእርግጥ ባዶ መሬት የመንግስት እና የህዝብ ሐብት መሆኑ በሕገ-መንግስቱ እና በሌሎች ሕጎች የተገለጸ ጉዳይ ነው፡፡ ይህ ማለት ግለሰቦች በመሬት ላይ የሚኖራቸው መብት የመጠቀም እንጂ የባለቤትነት መብት አይደለም፡፡ በዚህም መሰረት የአመልካች እናት የራሳቸው ይዞታ የነበረን መሬት ለአመልካቾች መስጠታቸው ሚች በይዞታው ላይ የነበራቸውን የመጠቀም መብት ማስተላለፋቸውን የሚያሳይ ነው፡፡

ስለዚህ አመልካቾች በሚች እናታቸው ባዶ መሬት ተሰጥቷቸው ቤት መስራታቸውን ሳይክዱ ባዶ መሬት መሰጠቱ ንብረት እንደተሰጣቸው ተደርጎ ሊቆጠር እንደማይችል አድርገው የሚያቀርቡት ክርክር ተቀባይነት የለውም፡፡

የአመልካቾች እናት ባደረጉት ኑዛዜ ላይ ለአመልካቾች አስቀድሞ ስጦታ ያደረጉላቸው መሆኑን በመግለጽ አከራካሪውን ቤት ተጠሪ ብቻ እንዲወርሱ መናዘዛቸውን የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ውሳኔ ግልባጭ ያሳያል፡፡ አንድ ኑዛዜ አድራጊ ያለኑዛዜ ሊወርሱ የሚችሉ ተወላጆችን በኑዛዜ በግልጽ ምክንያት ጠቅሶ ከውርስ መንቀል እንደሚችል እና ምክንያቱ ከውርስ ለመንቀል የሚያበቃ መሆኑን ካልሆነ በስተቀር የምክንያቱን ትክክለኛነት መመርመር አስፈላጊ አለመሆኑን ከፍ/ሕ/ቁጥር 937 እና 938 ድንጋጌዎች መገንዘብ ይቻላል፡፡ በተያዘው ጉዳይ የአመልካቾች እናት አመልካቾችን በኑዛዜ ከውርስ ሐብት የነቀሉት ለአመልካቾች አስቀድሞ ስጦታ መስጠታቸውን በመግለጽ ነው፡፡ የኑዛዜ አድራጊው ለተወላጅ አስቀድሞ በስጦታ ንብረትን ማስተላለፉ የስጦታ ተጠቃሚን በኑዛዜ ከውርስ ሐብት ለመንቀል እንደበቂ ምክንያት ሊወሰድ የሚችል ነው፡፡ በመሆኑም አመልካቾች በሚች እናታቸው አስቀድሞ ስጦታ የተደረገላቸው መሆኑ ተገልጾ በኑዛዜ ከውርስ ሐብት በግልጽ መነቀላቸው ሕጉን የተከተለ በመሆኑ ኑዛዜው የሚፈርስበት ምክንያት የለም፡፡

ሲጠቃለል የአመልካቾች እናት ያደረጉት ኑዛዜ አመልካቾችን ከውርስ ሐብት የነቀለ ቢሆንም የተነቀሉበት ምክንያት በኑዛዜ የተጠቀሰ እና ይህ ምክንያትም ከውርስ ሐብት ለመንቀል የሚያበቃ በመሆኑ ጉዳዩን በይግባኝ የተመለከቱት የፌደራል ከፍተኛ እና ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሚች ያደረጉት ኑዛዜ ሊፈርስ አይገባም በሚል በሰጡት ውሳኔ የተፈጸመ መሰረታዊ የህግ ስህተት የለም፡፡ በመሆኑም ተከታዩ ተወስኗል፡፡

ውሳኔ

1ኛ. የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 258055 በነሐሴ 06 ቀን 2013 ዓ.ም እና የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 213237 በጥቅምት 29 ቀን 2014 ዓ.ም የሰጡት ውሳኔ በፍ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348/1 መሰረት ጸንቷል፡፡

2ኛ. በዚህ ፍርድ ቤት የተደረገው ክርክር ያስከተለውን ወጪ እና ኪሳራ ግራ ቀኝ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ፅ/ወ

የሰ/መ/ቁጥር 239453

ሐምሌ 26 ቀን 2015 ዓ/ም

ዳኞች፡- ተፈሪ ገብሩ(ዶ/ር)

እንዳሻው አዳነ

ተሾመ ሽፈራው

መላኩ ካሳዬ

ነፃነት ተገኝ

አመልካቾች፡-

1ኛ. አቶ መስፍን ባልቻ አሩሲ

2ኛ. አቶ ተሾመ ባልቻ አሩሲ

3ኛ. አቶ አለማየሁ ባልቻ አሩሲ

4ኛ. አቶ ግዛው ባልቻ አሩሲ

5ኛ.አቶ ብርሃኑ ባልቻ አሩሲ

ጌታቸው ታደሰ - ቀረቡ

6ኛ. አቶ ሚሊዮን ባልቻ አሩሲ

7ኛ. ብርክቲ ባልቻ አሩሲ

አመልካቾች/ጠ

ተጠሪዎች

1ኛ. አቶ ሙሉጌታ አለሙ - **የተጠሪዎች ጠበቃ መስፍን አለማየሁ - ቀረቡ**

2ኛ. አቶ ጌታቸው ወዳጆ

3ኛ. አቶ ደስታ ጌታቸው

4ኛ. ወ/ሮ ገነት ጌታቸው

5ኛ. አቶ ደበበ ጌታቸው

6ኛ. ወ/ሮ ካሰች አለሙ

7ኛ. አቶ ሳሙኤል ወርቁ

8ኛ. ወ/ሮ አስቱር ወርቁ

9ኛ. አቶ ጸጋዬ ወርቁ

10ኛ. ወ/ሮ መአዛ ወርቁ

11ኛ. አቶ በቀለ ኤደኤ

12ኛ. ወ/ሮ ጸሀይ ኤደኤ

13ኛ. አቶ ቀነኒ ኤደኤ

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍርድ

ጉዳዩ የውርስ ሐብትን ለማስለቀቅ በቀረበ ክስ ላይ የተነሳ የይርጋ ክርክርን የሚመለከት ነው፡፡ ለዚህ ሰበር ቅሬታ መነሻ የሆነው የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 294531 በህዳር 20 ቀን 2015 ዓ.ም የሰር ፌደራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በሰጠው ብይን ላይ የቀረበውን ቅሬታ የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ውድቅ በማድረግ የሰጠው ትእዛዝ ነው፡፡ ጉዳዩ በተጀመረበት በፌደራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት አመልካቾች ከሳሽ ተጠሪዎች ደግሞ ተከሳሽ ነበሩ፡፡

አመልካቾች በሐምሌ 26 ቀን 2013 ዓ.ም ጽፈው ባቀረቡት ክስ ወላጅ አባታችን በጥር 12 ቀን 1993 ዓ.ም ከዚህ አለም በሞት ተለይተዋል፡፡ አባታችን በመጋቢት 04 ቀን 1983 ዓ.ም በአፈጻጸም የተረከቡትን በቦሌ ክፍለ ከተማ ወረዳ 11 የሚገኝ ቤት እና የእርሻ መሬት ተጠሪዎች ባልታወቀ ምክንያት ስለያዙ በማንእጅ እንደሚገኝ ፍርድ ቤቱ አጣርቶ ተጠሪዎች ይዞታውን እንዲያስረክቡ ወይም ተጠሪዎች በይዞታው የተቀበሉት ካሳ እና ምትክ ቦታ ካለ እንዲመልሱ ይወሰንልን በማለት ጠይቀዋል፡፡ ተጠሪዎች በነሐሴ 07 ቀን 2013 ዓ.ም ጽፈው ባቀረቡት የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ የውርስ ሀብት ነው የተባለው ንብረት ከሚች እጅ ከወጣ ከ30 ዓመት በላይ የሆነው በመሆኑ ክሱ በይርጋ ይታገዳል በማለት ተከራክረዋል፡፡

ጉዳዩን በመጀመሪያ የተመለከተው ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ክርክር ሰምቶ ሚች እስከ ጥር 12 ቀን 1993 ዓ.ም ድረስ የውርስ ሀብት ነው በተባለው ንብረት የተገለገሉ ሲሆን ከዚህ ጊዜ ጀምሮ ክስ እስከቀረበበት ድረስ ያለው ጊዜ ሲቆጠር 20 ዓመት ይሆናል፡፡ የውርስ ሀብት ሕጋዊ ወራሽ ባልሆነ ሰው ተይዞብኛል የሚል ክስ ማቅረቢያ የይርጋ ጊዜ 10 ዓመት ነው፡፡ አመልካቾች አባታቸው ሲሞቱ ልጆች መሆናቸውን እና አባታቸው ሲሞቱ የመጨረሻው ልጅ እድሜ 8 ዓመት የነበረ መሆኑን በመግለጽ የተከራከሩ ቢሆንም የስምንት አመት ልጅ 18 ዓመት የሚሞላው ከ2003 ዓ.ም ጀምሮ ነው፡፡ ከ2003 ዓ.ም ጀምሮ ቢቆጠር እንኳን ክሱ የቀረበው ከ10 ዓመት በኋላ ስለሆነ ክሱ በይርጋ ይታገዳል በማለት የአመልካቾችን ክስ በብይን ውድቅ አድርጓል፡፡ አመልካቾች ይህንን ብይን በመቃወም የይግባኝ ቅሬታ ለፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ያቀረቡ ቢሆንም ከፍተኛ ፍርድ ቤቱ ሚች ሲሞቱ የአመልካቾች እድሜ ስንት እንደነበር የ8ኛ ክፍል የምስክር ወረቀት በማስቀረብ ካጣራ በኋላ የይግባኝ ቅሬታቸውን በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁጥር 337 መሰረት ውድቅ በማድረጉ የሚከተለውን የሰበር ቅሬታ አቅርበዋል፡፡

አመልካቾች በታህሳስ 25 ቀን 2015 ዓ.ም ጽፈው ባቀረቡት የሰበር ቅሬታ ይግባኝ ሰሚው ከፍተኛ ፍርድ ቤት የአመልካቾችን እድሜ ለማጣራት ማስረጃ ያስቀረበው ተጠሪዎች የእድሜ ክርክር ባላቀረቡበት ነው፡፡ አመልካቾች አባታችን በክርክር የረታበት ማስረጃ እጃችን ላይ ስላልነበር የውርስ

ሀብቱን ለመጠየቅ አልቻልንም፡፡ ንብረቱ የአባታችን መሆኑን ያወቅነው ክስ ከማቅረባችን ከአንድ ወር በፊት ነው፡፡ በመሆኑም ክሱ በይርጋ ይታገዳል መባሉ መሰረታዊ የህግ ስህተት ስለሆነ ይታረምልን በማለት ጠይቀዋል፡፡

የሰበር አጣሪ ችሎት የአመልካቾችን ቅሬታ መርምሮ ክሱ በ10 ዓመት ይርጋ ይቋረጣል መባሉ ተገቢ መሆን እለመሆኑን ለማጣራት ተጠሪዎች መልስ እንዲያቀርቡ ትእዛዝ ተሰጥቷል፡፡

ተጠሪዎች በመጋቢት 20 ቀን 2014 ዓ.ም ጽፈው ባቀረቡት መልስ በስር ፍርድ ቤት ክሱ በሚሰማበት ወቅት ሟች ሲሞቱ የመጨረሻው ልጅ እድሜ 8 ዓመት ነበር ይበሉ እንጂ የሟች የመጨረሻ ልጅ የተወለደው ከ1983 ዓ.ም በፊት ነው፡፡ ፍርድ ቤቱ እውነታውን ለማጣራት ከቂርቆስ ክፍለ ከተማ ወረዳ 4 ማህደር በማስቀረብ ማየት ይችላል፡፡ በመሆኑም በስር ፍርድ ቤቶች ክሱ በይርጋ ይታገዳል በመባሉ የተፈጸመ መሰረታዊ የህግ ስህተት የለም በማለት ተከራክረዋል፡፡

የክርክሩ አመጣጥ ከላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም ያስቀርባል ሲባል የተያዘውን ጭብጥ ከግራ ቀኙ ክርክር፤ በስር ፍርድ ቤቶች በማስረጃ ከተረጋገጠው ፍሬ ነገር እና ከተገቢው ሕግ ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለው መርምረናል፡፡

እንደመረመርነው ተጠሪዎች የአመልካቾች የውርስ ሐብት ይለቀቅልን ክስ በይርጋ ይታገዳል የሚሉት ለክርክሩ መሰረት የሆነውን ቤት እና የእርሻ መሬት አባት ከሞቱ ከ1993 ዓ.ም ጀምሮ ይዘነዋል በሚል ነው፡፡ ተጠሪዎች ይህንን ቤት እና የእርሻ መሬት ሟች ከዚህ አለም በሞት ከተለዩበት ከ1993 ዓ.ም ጀምሮ መያዛቸው በአመልካቾችም የታመነ ፍሬ ነገር መሆኑን ከስር ፍርድ ቤት ብይን መረዳት ይቻላል፡፡ ይሁን እንጂ አመልካቾች አባታቸው ሲሞቱ የመጨረሻው ልጅ እድሜ 8 ዓመት የነበረ በመሆኑ ክስ ለማቅረብ የሚያስችል እድሜ ላይ አልነበርም በማለት ክሱ በይርጋ እንደማይታገድ ገልጸው ተከራክረዋል፡፡ የውርስ ሐብት በያዘ ሰው ላይ ክስ ሲቀርብ ተፈጻሚነት የሚኖረው የይርጋ ድንጋጌ የፍ/ሕ/ቁጥር 1000 ሲሆን በዚህ ድንጋጌ የ3 ዓመት እና የ15 ዓመት የይርጋ ጊዜዎች ተመልክተዋል፡፡ ይህ በፍ/ሕ/ቁጥር 1000 ላይ የተመለከተው የይርጋ ድንጋጌ ተፈጻሚነት የሚኖረው ወራሽ በሆኑ ተከራካሪዎች መካከል መሆኑን ነገር ግን ወራሽ በሆኑ እና ባልሆኑ ወገኖች መካከል ክርክሩ የሚደረግ ከሆነ ተፈጻሚነት ያለው የፍ/ሕ/ቁጥር 1000 ድንጋጌ ሳይሆን በፍ/ሕ/ቁጥር 1845 ላይ የተመለከተው የ10 ዓመት የይርጋ ድንጋጌ መሆኑን የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰበር መዝገብ ቁጥር 52407(በቅጽ 11 የታተመ) እና በሌሎች መዝገቦች የህግ ትርጉም የሰጠበት ጉዳይ ነው፡፡ በተጨማሪም ሟች ሲሞት ወይም የውርስ ንብረቱ በተከሳሽ ሲያዝ ህጻናት የነበሩ የሟች ወራሾች በመብታቸው መስራት እና ንብረቱ እንዲለቀቅ ክስ ማቅረብ የሚችሉት እድሜቸው 18 ዓመት ሲሞላ ነው፡፡ የውርስ ንብረቱ ሲያዝ አካለ መጠን ላላደረሱ የሟች ልጆችም ተፈጻሚነት ያለው የይርጋ ጊዜ 10 ዓመት መሆኑን እና ይህ የ10 ዓመት ጊዜ መቆጠር የሚጀምረው እድሚአቸው 18 ዓመት ከሞላ ጊዜ

ጀምሮ መሆኑን የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 171038 በየካቲት 25 ቀን 2012 ዓ.ም በተሰጠ ውሳኔ(ያልታተመ) የህግ ትርጉም ሰጥቷል፡፡

በተያዘው ጉዳይ የተከራካሪዎች ማንነት ሲታይ አመልካቾች የሚች ወራሾች ሲሆኑ ተጠሪዎች ደግሞ የሚች ወራሾች አይደሉም፡፡ ይህም ክርክሩ የሚች ወራሽ በሆኑ እና ባልሆኑ ወገኖች መካከል የሚደረግ መሆኑን ስለሚያሳይ የስር ፍርድ ቤት ተፈጻሚነት ያለው የይርጋ ጊዜ 10 አመት ነው ማለቱ ተገቢ ነው፡፡ ይህ የ10 ዓመት ጊዜ ከመቼ ጀምሮ መቆጠር አለበት የሚለው ሲታይ ማስረጃ የመቀበል እና የመመዘን ስልጣን ያለው የስር ከፍተኛ ፍርድ ቤት የአመልካቾችን የትምህርት ማስረጃ በማስቀረብ አመልካቾች 18 ዓመት የሚሞላቸው መቼ እንደሆነ በማጣራት 18 ዓመት ከሞላቸው ጊዜ ጀምሮ ክስ እስካቀረቡት ያለው ጊዜ ሲቆጠር ከ10 ዓመት በላይ በመሆኑ የአመልካቾችን ክስ በይርጋ ውድቅ በማድረግ በስር ፍርድ ቤት የተሰጠውን ውሳኔ አጽንቷል፡፡ በመሆኑም የአመልካቾች ክስ በ10 ዓመት ይርጋ የታገደ ነው መባሉ የተጠቀሱትን የሰበር ሰሚ ችሎት ውሳኔዎች የተከተለ ነው ከሚባል በስተቀር መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ ስላልተገኘ ተከታዩ ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

<u>ውሳኔ</u>

1ኛ. የፌደራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 129052 በግንቦት 23 ቀን 2014 ዓ.ም እና የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 294531 በህዳር 20 ቀን 2015 ዓ.ም የሰጡት ብይን በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348/1 መሰረት ጸንቷል፡፡
2ኛ. በዚህ ፍርድ ቤት የነበረው ክርክር ያስከተለውን ወጪ ግራ ቀኙ የራሳቸውን ይቻቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ፅ/ወ

የሰ/መ/ቁጥር 231538

ሚያዝያ 25 ቀን 2015 ዓ/ም

ዳኞች፡- ተፈሪ ገብሩ(ዶ/ር)

እንዳሻው አዳነ

ተሾመ ሽፈራው

መላኩ ካሳዬ

ነፃነት ተገኝ

አመልካቾች፡-1. ወ/ሮ ተናኜ ታፈሰ ወርቅነህ
2. እየሩሳሌም ሙሉጌታ ታምሬ } አልቀረቡም
3. የስነ-ጥበብ ሙሉጌታ ታምሬ

ተጠሪዎች፡- 1. አቶ ቴዎድሮስ ታዬ አበጋዝ
2. ወ/ሪት ሊያ ሙሉጌታ ታምሬ } አልቀረቡም
3. ወ/ሮ ቤተልሔም ሙሉጌታ ታምሬ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍርድ

ጉዳዩ በውርስ ንብረት ክፍፍል ጥያቄ ወቅት አስቀድሞ ውርሱ ሲጣራ ተነስቶ ውሳኔ ያገኘ ክርክር በድጋሚ ሊነሳ የሚችል መሆን ያለመሆኑን የሚመለከት ነው፡፡ የሰበር ቅሬታ የቀረበው የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በሰኔ 17 ቀን 2014 ዓ.ም በመዝገብ ቁጥር 270120 የሰጠውን ውሳኔ በመቃወም ነው፡፡ ጉዳዩ በፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ሲጀመር የአሁን አመልካቾች ተከሳሾች ተጠሪዎች ደግሞ ከሳሽ ነበሩ፡፡

ተጠሪዎች በታህሳስ 21 ቀን 2014 በተፃፈ አቤቱታ ባቀረቡት ክስ ከ1-3ኛ ተጠሪዎች እንዲሁም በዚህ አቤቱታ ላይ ያልተካተተው አቶ ደረጀ ቀፀላ የሟች እናታችን የወ/ሮ እሌኒ ውድነህ ሕጋዊ ወራሾች ነን፡፡ እንዲሁም 2ኛ ተጠሪ፣ 3ኛ ተጠሪ፣ 2ኛ አመልካች እና 3ኛ አመልካች የሟች አባታችን አቶ ሙሉጌታ ታምሬ ህጋዊ ወራሾች መሆናችንን በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁ 23489 በተደረገ የውርስ ማጣራት አረጋግጠናል፡፡ ውርሱ ሲጣራ በቂርቆስ ክፍል ከተማ ወረዳ 04 የቤት ቁጥሩ 777 የሆነው የመኖሪያ ቤት የሟቾች ወ/ሮ እሌኒ ውድነህ እና የሟች አቶ ሙሉጌታ ታምሬ የጋራ ሀብትና በወራሾች መካከል እኩል የሚከፋፈል መሆኑ፤ በ1ኛ አመልካችና በሟች አቶ ሙሉጌታ ታምሬ የጋብቻ

ዘመን ለባንክ የተከፈለ ብር 25,540,50 የሁለቱ የጋራ ሀብት መሆኑን እና የገንዘቡ ግማሽ ለአቶ ሙሉጌታ ታምሬ ወራሾች የሚከፋፈል መሆኑን ሰርቪስ ቤቶቹንም በተመለከተ ቀደም ሲል ለነበሩት ሰርቪስ ቤቶች የወጣው ብር 3204.50 ግማሹ በሚች በወ/ሮ እሌኒ ወራሾች መካከል ግማሹ ደግም በሚች ሙሉጌታ ታምሬ ወራሾች መካከል የሚከፋፈል መሆኑ ተረጋግጦ የውርስ አጣሪ ሪፖርት የፀደቀ ቢሆንም የውርስ ንብረቱ በወራሾች መካከል ክፍፍል ሳይደረግበት በአመልካቾች እጅ ሆኖ ብቻቸውን እየተጠቀሙበት ይገኛሉ፡፡ በመሆኑም በቂርቆስ ክፍለ ከተማ ወረዳ 04 የቤት ቁጥር 777 የሆነ የመኖሪያ ቤት በወራሾች መካከል የድርሻ ክፍፍል ይደረግልን በማለት ጠይቀዋል፡፡

አመልካቾች ለተጠሪዎች አቤቱታ በጥር 29 ቀን 2012 ዓ.ም ጽፈው ባቀረቡት መልስ የውርስ ክፍፍሉ የተጠየቀው የውርስ አጣሪ ሪፖርቱን መሰረት በማድረግ ነው፡፡ የውርስ አጣሪ ሪፖርት ደግሞ እንደማስረጃ እንጂ እንደ ፍርድ ስለማይቆጠር አፈፃፀም ሊጠየቅበት አይችልም፡፡ የአጣሪ ሪፖርቱ ቢፀድቅም ስህተት አለበት፡፡ ክርክር የቀረበበት የቤት ቁጥር 777 ሚች አቶ ሙሉጌታ ታምሬ 1ኛ አመልካችን ከማግባታቸው በፊት የተመሩት ቢሆንም ከጋብቻ በኋላ 1ኛ አመልካች በቤቱ ላይ መሰረታዊ ለውጥ አድርገውበታል፡፡ ቤቱ የተሰራበትንም እዳ ከፍለዋል፡፡ በመሆኑም ቤቱ የ1ኛ አመልካች እና የሚች አቶ ሙሉጌታ ታምሬ የጋራ ሀብት ሊሆን ይገባል በማለት ተከራክረዋል፡፡

የስር የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትም የግራቀኙን ክርክር መርምሮ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ/ 5፤244(2)ለ እና 245 (ለ) ከተደነገገው አኳያ እንዲሁም የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰበር መዝገብ ቁጥር 40418 በውርስ ይጣራልኝ መዝገብ ቀርቦ እልባት የተሰጠው የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ በድጋሚ በውርስ አጣሪው ሪፖርት መሰረት እንካፈል በሚል ሌላ መዝገብ ላይ በመቃወሚያነት ሊቀርብ አይችልም በማለት የወሰነ በመሆኑ አመልካቾች በውርስ ማጣራቱ ቅሬታ ከነበራቸው ሪፖርቱ በይግባኝ እንዲስተካከል መጠየቅ ነበረባቸው፡፡ በቂርቆስ ክፍለ ከተማ ወረዳ 04 የቤት ቁጥር 777 የሆነውን ቤት በተመለከተ 1ኛ አመልካች የጋራ ነው ሲሉ ያቀረቡትን ክርክር አስቀድሞ በውርስ አጣሪ መዝገብ ላይ ተነስቶ እልባት የተሰጠበት በመሆኑ በድጋሚ መቅረቡ ተገቢነት የለውም፡፡ ቤቱ የሚች ወ/ሮ እሌኒ ውድነህ እና የሚች አቶ ሙሉጌታ ታምሬ እንጂ የ1ኛ አመልካችና የሚች አቶ ሙሉጌታ ታምሬ የጋራ ሀብት ስላልሆነ የሚች ወ/ሮ እሌኒ ወራሾች አቶ ቴዎድሮስ ታዬ፣ ደረጀ ቀፀላ፣ ሊያ ሙሉጌታ፣ ቤተልሄም ሙሉጌታ 50% እኩል እንዲካፈሉ ቀሪውን 50% ደግሞ የሚች አቶ ሙሉጌታ ታምሬ ድርሻ ስለሆነ ወራሾቹ ሊያ ሙሉጌታ፣ ቤተልሄም ሙሉጌታ፣ እየሩሳሌም ሙሉጌታ እና ስነ-ጥበብ ሙሉጌታ እኩል እንዲካፈሉ እና ሌሎችን ንብረቶችም በውርስ አጣሪ ሪፖርት መሰረት እንዲከፋፈሉ ወስኗል፡፡

አመልካቾች ውሳኔውን ተከትሎ ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የይግባኝ ቅሬታ አቅርበው ፍርድ ቤቱ ግራቀኙን አስቀርቦ ካከራከረ በኋላ አጽንቷል፡፡

አመልካቾች በሀምሌ 20 ቀን 2014 ዓ.ም ባቀረቡት የሰበር ቅሬታ የውርስ አጣሪ ሪፖርት እንደ አንድ ማስረጃ የሚያገለግል ሆኖ እያለ የስር ፍርድ ቤቶች እንደ ውሳኔ በመውሰድ በፍ/ብ/ሥ/ስ/ህ/ቁ/5 መሰረት በድጋሚ ክርክር የሚቀርብበት አይደለም በማለት መወሰናቸው፤ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰበር መዝገብ ቁጥር 95681 መጋቢት 2 ቀን 2007 ዓ.ም በሰጠው አስገዳጅ ትርጉም የውርስ አጣሪ ሪፖርት ከማስረጃነት ዋጋ ውጭ ሌላ ዋጋ የሌለው እና በፍ/ብ/ስ/ስ/ሕ/ቁ 358 መሰረት መቃወሚያ ሊቀርብበት እንደማይችል ወስኗል፤ የውርስ ማጣራት እና የውርስ ሀብት ክፍፍል ጭብጥና ፍሬ ነገር የተለያዩ ናቸው፤ የውርስ ማጣራት እንደ ውሳኔ ቢቆጠር ኖሮ በቀጥታ አፈፃፀም ይከፈትበታል እንጂ ለክስ የማስረጃነት ውጤት ባልኖረው ነበር፤ የውርስ ማጣራት ሪፖርቱ በመደበኛው ፍርድ ቤት ውሳኔ የተሰጠበትና በድጋሚ ክርክር የማይቀርብበት ነው ከተባለም የስር ፍርድ ቤት ከመጀመሪያው ክሱን መቀበል ወይም ውሳኔ መስጠት አልነበረበትም፤ በአንድ ተከራካሪ ወገን የተቆጠረ ማስረጃ የማይሰማው ህጋዊ ምክንያት ሲኖር ብቻ በመሆኑ ምስክሮችን ሳናሰማ የተሰጠ ፍርድ የአመልካቾችን ማስረጃ የማሰማት መብታችንን ያላከበረ ነው፤ ክርክር የቀረበበት በቂርቆስ ክፍለ ከተማ ወረዳ 4 የቤት ቁጥር 777 የሆነው ቤት የቦታ ምሪት የተካሄደው 1ኛ አመልካችና አቶ ሙሉጌታ ታምሬ ከመጋባታቸው በፊት ቢሆንም ቤቱ የአሁኑን ቅርፅ የያዘው እና የተጠናቀቀው ከጋብቻቸው በኋላ ነው፤ የተሰራውም ከባንክ በተገኘ ብድር ሲሆን እዳው ከነወለዱ ብር 25,540,18 የተከፈለው በ1ኛ አመልካች ነው፤ በቤቱ ግንባታ ላይ የተጠሪዎች እናት ኢኮኖሚያዊ አስተዋጽኦ አላደረጉም፤ በንብረት መፈራት ምንም አስተዋፅኦ ያላደረገ ተጋቢ ንብረት እንዲካፈል ማድረግ በህገ-መንግስቱ አንቀፅ 40 (1) ስር የተቀመጠውን የንብረት ባለቤትነት መብት የሚጥስ መሆኑን አስገዳጅ የህግ ትርጉም ሰጥቶበታል፤ በመሆኑም የስር ፍርድ ቤት ውሳኔዎችን በመሻር የውርስ አጣሪ ሪፖርት በፍርድ ቤት ቢፀድቅም ባይፀድቅም እንደ ማስረጃ ተቃውሞ ቀርቦበት በተቃራኒ ማስረጃ ሊስተባበል የሚችል ነው ተብሎ ይወሰንልን፡፡ እንዲሁም የስር ፍርድ ቤት ያቀረብነውን ክርክር እና ማስረጃ መርምሮ በህግ መሰረት እንደገና ውሳኔ እንዲሰጥ ጉዳዩ ይመለስልን በማለት አቅርበዋል፡፡

የሰበር አጣሪ ችሎትም የአመልካችን ቅሬታ መርምሮ በፍርድ ቤት የፀደቀ የውርስ አጣሪ ሪፖርት ላይ በክፍፍል ጊዜ የሚነሳ ክርክር በፍ/ብ/ህ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ/5 ድንጋጌ መሰረት በድጋሚ የቀረበ ስለሆነ ተቀባይነት ያለው አይደለም የተባለበትን አግባብ በሰበር መዝገብ ቁጥር 95681፤169570 ከተሰጡት ውሳኔዎች አንፃር ተገቢነቱ መጣራት ያለበት በመሆኑ ተጠሪዎች መልስ እንዲቀርቡ ትእዛዝ ሰጥቷል፡፡

ተጠሪዎች በህዳር 28 ቀን 2015 ዓ.ም ጽፈው ባቀረቡት መልስ አመልካቾች በውርስ አጣሪ ሂደቱ ላይ አንድ አይነት መከራከሪያና አንድ አይነት ማስረጃ በማቅረብ እልባት ያገኘውን ጉዳይ እንደገና እንዲታይ ክርክር አቅርበዋል፡፡ የስር ፍርድ ቤት በውርስ ማጣራት ሂደቱ ላይ ክርክር ያደረጉት አንድ አይነት ተከራካሪዎች መሆናቸውን አሁንም ይዘው የቀረቡት ክርክር አንድ አይነት መሆኑን በመጥቀስ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ/5 ላይ የተመለከቱ መርሆዎችን የሚጥስ ነው በማለት ውሳኔ መስጠቱ ተገቢ ነው፡፡

የስር ፍርድ ቤት ድምዳሜ ላይ ከመድረሱ በፊት ዋናውን ውርስ የተጣራበት መዝገብ አስቀርቦ በክርክሩ የተነሳውን ፍሬ ነገርና ማስረጃ አንድ አይነት መሆኑን በሚገባ በማገናዘብ የሰጠው ውሳኔ ተገቢነት ያለው ነው። በስር ፍርድ ቤት ያቀረብነው አቤቱታ በፍርድ ቤት የፀደቀውን የውርስ አጣሪ ሪፖርት እንዲሁም የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ/.1020 እና ተከታዮቹን ድንጋጌዎች መሰረት የውርስ ሀብት ክፍፍል እንዲደረግልን እንጂ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 378 መሰረት ፍርድ እንዲፈፀምልን አይደለም። አመልካቾች በስር ፍርድ ቤት ምስክር ያልተሰማላቸው በውርስ ክፍፍሉ ክርክር ላይ ያነሷቸውን መከራከሪያዎች በሙሉ ከዚህ ቀደም በተመሳሳይ ሁኔታ በማቅረባቸው የተለወጠ አዲስ ነገር የሌለ መሆኑን ከግንዛቤ በማስገባት ነው። በመሆኑም ችሎቱ የአመልካቾችን የሰበር አቤቱታ ውድቅ አድርጎ ያሰናብተን በማለት ጠይቀዋል።

አመልካቾችም የሰበር አቤቱታቸውን የሚያጠናክር የመልስ መልስ በታህሳስ 24 ቀን 2015 ዓ.ም የተጻፈ አቅርበዋል።

የክርክሩ አመጣጥ ከላይ የተመለከተው ሲሆን አኛም ያስቀርባል ሲባል የተያዘውን ጭብጥ ከግራቀኙ ክርክር፤ በስር ፍርድ ቤት ከተረጋገጠው ፍሬ ነገር እና ከተገቢው የህግ ድንጋጌ ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለው መርምረናል።

እንደመረመርነው የተጠሪዎች እናት እና ተጠሪዎችን ጨምሮ ከ2ኛ እና 3ኛ አመልካቾች አባት የውርስ ሐብት ሲጣራ የአሁን 1ኛ አመልካች የክርክሩ ተሳታፊ ሆነው ለክርክሩ መሰረት የሆነው ቤት የተጠሪዎች እናት የውርስ ሐብት ድርሻ የለበትም። ቤቱ የ1ኛ አመልካች እና የሟች ሙሉጌታ ታምሬ የባል እና ሚስት ንብረት ነው የሚል ክርክር አቅርበው ውርሱ በተጣራበት መዝገብ ላይ ይህ ክርክር በጭብጥነት ተይዞ እና ማስረጃ ተሰምቶ የውርስ ሐብት ነው በሚል ተረጋግጦ የውርስ አጣሪ ሪፖርት በማጽደቅ ውሳኔ መሰጠቱ በአመልካቾች የተካደ አይደለም። አመልካቾች አጥብቀው የሚከራከሩት የውርስ አጣሪ ሪፖርት አፈጻጸም የሚጠየቅበት ሳይሆን እንደማስረጃ የሚያገለግል እና በሌላ ማስረጃ ሊስተባበል የሚችል ነው የሚል ነው። በመጀመሪያ ደረጃ ተጠሪዎች ያቀረቡት ጥያቄ በውርስ አጣሪ ሪፖርት መሰረት የውርስ ሐብት የክፍፍል ውሳኔ እንዲሰጥ እንጂ ቀጥታ በውርስ አጣሪ ሪፖርት መሰረት ያቀረቡት የአፈጻጸም ጥያቄ የለም። ስለዚህ የውርስ አጣሪ ሪፖርትን መሰረት አድርገው ተጠሪዎች አፈጻጸም እንደጠየቁ በማድረግ አፈጻጸም ሊጠይቁ አይችሉም የሚለው የአመልካቾች ክርክር ተገቢነት ያለው አይደለም።

ሌላው የአመልካቾች የውርስ አጣሪ ሪፖርት ከማስረጃ ያለፈ ውጤት የለውም የሚለው ክርክርም ቢሆን የውርስ አጣሪ ሪፖርት የጸደቀበት ውሳኔ ይዘት ማለትም በውርስ ማጣራቱ ሂደት ተሳታፊ የነበሩ ወገኖች ያነሷቸው ክርክሮች እና ክርክሮቹ በማስረጃ ተጣርተው ድምዳሜ የተደረሰባቸው መሆን ያለመሆኑ የሚወስነው ይሆናል። ይህም ማለት በውርስ ማጣራት ሂደት ተሳታፊ የነበሩ ወገኖች

የተለያዩ ክርክሮችን አንስተው ውርሱ በተጣራበት መዝገብ ክርክሮቹ በጭብጥነት ተይዘው እና ማስረጃ ተሰምቶ ድምዳሜ ላይ ከተደረሰ የውርስ አጣሪ ሪፖርቱ የጸደቀበት ውሳኔ ከማስረጃ ያለፈ ውጤት ይኖረዋል። ከዚህ ጋር በተያያዘ ቀደም ሲል በፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰበር መዝገብ ቁጥር 40418 እና በሌሎች መዝገቦች የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ ነው። በሌላ በኩል የውርስ አጣሪ ሪፖርት ላይ ተሳታፊ ያልነበረ እና ክርክሩን ያላቀረበ ወገን ደግሞ በውርስ አጣሪ ሪፖርቱ ላይ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 358 መሰረት መቃወሚያ ማቅረብ ሳይጠበቅበት በክፍፍል ወቅት ክርክሩን ማቅረብ ስለማይከለከል በዚህ ጊዜ የውርስ አጣሪ ሪፖርቱ የማስረጃ ዋጋ ብቻ ይኖረዋል። በመሆኑም በውርስ ማጣራት ሂደት ተሳታፊ የነበሩ ወገኖች በውርስ ማጣራት መዝገብ ላይ በክፍፍል ወቅት ሊነሳ የሚችል ክርክር ሁሉ አስቀድመው አንስተው ክርክራቸው በማስረጃ ተጣርቶ ውሳኔ ከተሰጠ ይህ የውርስ አጣሪ ሪፖርት የጸደቀበት ውሳኔ ክርክር ተደርጎ ድምዳሜ ላይ ከተደረሰባቸው ነጥቦች አንጻር የመጨረሻ ውጤት ይኖረዋል ማለት ነው።

በዚህ መሰረትም አመልካቾች ለክርክሩ መሰረት የሆነው ቤት የ1ኛ አመልካች እና የሟች ሙሉጌታ ታምሬ የባል እና ሚስት ንብረት ነው በሚል የሚያቀርቡት ክርክር አስቀድሞ በፍርድ ያለቀ እና የፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 5 መስፈርትን ያሟላል ወይስ አያሟላም? የሚለውን ስንመለከት በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 5(1) ላይ እንደተመለከተው በሕግ ሥልጣን የተሠጠው ማናቸውም ፍርድ ቤት ክርክሩን ተቀብሎ የመጨረሻ ፍርድ ከሠጠ በኋላ ቀድሞ በፍርድ የተወሰነው ክርክር ሥረ-ነገርና የተያዘው ጭብጥ አንድ ዓይነት ከሆነ በክርክሩ ላይ የነበሩት ወይም ከተከራካሪዎቹ መብት ያገኙ ሦስተኛ ወገኖች በዚያው ነገር ሁለተኛ ክስ ማቅረብ አይችሉም። ይህም ማለት በድንጋጌው መሠረት ጉዳዩ አስቀድሞ በፍርድ አልቋል ለማለት የተዘረዘሩት አራት መስፈርቶች በአንድነት መሟላት አለባቸው። የመጀመሪያው መስፈርት ጉዳዩን የተመለከተው በሕግ ሥልጣን የተሠጠው ማናቸውም ፍርድ ቤት መሆኑ ነው። በሕግ ሥልጣን የተሰጠው የሚለው አስቀድሞ ጉዳዩ የታየው በሕግ ዳኝነት ለመስጠት ሥልጣን ያለው ፍርድ ቤት ወይም ዳኝነት ነክ አካል መሆኑን ለማመላከት ነው። ሁለተኛው መስፈርት አስቀድሞ በፍርድ ቤት የተሠጠው የመጨረሻ ፍርድ መሆን አለበት የሚለው ነው። ፍርድ ቤቱ ክርክሩን አይቶ ጉዳዩ ላይ የመጨረሻ እልባት ወይም ውጤት የሠጠበት መሆን እንዳለበት የሚያስረዳ መስፈርት ነው። ሦስተኛው መስፈርት አስቀድሞ ፍርድ ያረፈበት ጉዳይ ሥረ-ነገሩና ጭብጡ አሁን ከተያዘው ጉዳይ ጋር አንድ ዓይነት መሆን አለበት የሚለው ነው። የክርክሩ መነሻ ጉዳይ አንድ መሆኑ ብቻ ሳይሆን ፍርድ ቤቱ በጭብጥነት የመረመረው ጉዳይ አሁን በተያዘው ክርክርም በጭብጥነት ተይዞ የሚመረመር ከሆነ ውጤቱ አስቀድሞ ፍርድ ያረፈበት ይሆናል። ሥረ-ነገሩ ተመሳሳይ ሆኖ ነገር ግን የሚያዘው ወይም የተያዘው ጭብጥ የተለያየ ከሆነ በተያዘው ጭብጥ ላይ የቀደመ ፍርድ ባለመኖሩ ጉዳዩ በፍርድ እንዳለቀ ሳይቆጠር ክርክሩ ቀጥሎ ፍርድ ሊያርፍበት የሚችል ጉዳይ ነው። በሕጉ ላይ የተቀመጠው አራተኛው መስፈርት የተከራካሪዎች ወይም ከተከራካሪዎች መብት ያገኙ ሦስተኛ ወገኖች ተመሳሳይ መሆን እና

በእነርሱ መካከል ያለ ክርክር መሆኑ ነው፡፡ የዚህ መስፈርት መነሻ ፍርድ የአስገዳጅነት ሀይል ሆነ ውጤት የሚኖረው በተከራካሪዎች መካከል ብቻ ነው የሚል ነው፡፡ ከተከራካሪዎች ውጭ ፍርዱን በመያዝ መብት ማቋቋም ሆነ ማስፈጸም አይቻልም፡፡ ፍርድ ቤት ጉዳዩን የሚመረምረው ሆነ ፍርድ የሚሠጠው ከተከራካሪዎች መካከል የተሻለ መብት ያለው ማን ነው ከሚለው ነጥብ አኳያ ብቻ ነው፡፡ በጉዳዩ ላይ ያላቸው መብት በፍርድ ቤቱ ሳይመረመር እና የመደመጥ ሆነ የመከላከል መብታቸው ሳይከበር ተከራካሪ ያልሆኑ ወገኖች ላይ ፍርዱ አስገዳጅነት አለው ሊባል አይችልም፡፡ የተከራካሪዎች ተመሳሳይነት የሚለው ከተከራካሪዎች በሕግ ሆነ በውል መብት የተላለፈላቸውን ሦስተኛ ወገኖች የመብታቸው ምንጭ የቀድሞው ክርክር ላይ ተከራካሪ በሆኑት ወገኖች ልክ በመሆኑ በእነዚህ ወገኖች ላይም ጉዳዩ አስቀድሞ በፍርድ እንዳለቀ የሚያስቆጥር ነው፡፡

ወደተያዘው ጉዳይ ስንመለስ በውርስ ማጣራት መዝገብ ላይ አመልካቾች ለክርክሩ መሰረት የሆነው ቤት የ1ኛ አመልካች እና የሟች ሙሉጌታ ታምሬ የባል እና ሚስት የጋራ ንብረት ነው የሚል ክርክር አቅርበው ይህ ክርክር በማስረጃ ተጣርቶ ተቀባይነት አለማግኘቱን የስር ፍርድ ቤት ለቅሬታ መነሻ በሆነው ውሳኔ ላይ አስፍሯል፡፡ በአመልካቾችም የተካደ አይደለም፡፡ ይህም ማለት አመልካቾች በውርስ ሀብት ክፍፍል ወቅት እያነሱ ያሉት ክርክር አስቀድሞ ውርሱ ሲጣራ በጭብጥነት ተይዞ ውሳኔ ያገኘ ጉዳይ ነው፡፡ ስለሆነም የስር ፍርድ ቤት አመልካች ለክርክሩ መሰረት የሆነው ቤት ላይ የተጠሪዎች እናት ድርሻ የላቸውም በሚል ክርክር ያቀረቡት ለቀረበባቸው የክፍፍል ክስ መልስ ሲሰጡ በመሆኑ ከውሳኔ በፊት ክሱን በብይን ውድቅ የሚያደርግበት እድል ባይኖረውም በውሳኔ ወቅት በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 5(1) መሠረት ጉዳዩ አስቀድሞ በፍርድ ያለቀ ነው በማለት የአመልካቾችን ክርክር ውድቅ ማድረጉ እና ይኼው በይግባኝ መጽናቱ ሕጉን የተከተለ በመሆኑ የሚከተለውን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

<u>ውሳኔ</u>

1. የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ቂርቆስ ምድብ ችሎት በየካቲት 18 ቀን 2013 ዓ.ም በመዝገብ ቁጥር 75947 እንዲሁም የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በሰኔ 17 ቀን 2014 ዓ.ም በመዝገብ ቁጥር 270120 የሰጡት ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ/348(1) መሰረት ጸንቷል፡፡
2. በዚህ ፍርድ ቤት የነበረው ክርክር ያስከተለውን ወጪ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

መ/ዐ

የሰ.መ.ቁ 243484

መጋቢት 30 ቀን 2016 ዓ.ም

ዳኞች፡- እትመት አሠፋ

ደጀኔ አያንሳ

ኑረዲን ከድር

መላኩ ካሣዬ

ሐብታሙ እርቅ ይሁን

አመልካቾች፡- 1. ወ/ሮ ነጻነት ደምሴ
2. ወ/ት የኔዘር ፍቃዱ
3. አቶ አብርሃም ከተማ
} ጠበቃ ሁሴን መሀመድ - ቀረቡ

ተጠሪ፡- ሲሳይ ታደሰ - ወኪል ህይወት ዱላ - ቀረቡ

መዝገቡ ለምርመራ የተቀጠረ ነው በመሆኑም መርምረን ተከታዩን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍርድ

የሰበር አቤቱታው ሊቀርብ የቻለው አመልካቾች መጋቢት 01 ቀን 2015 ዓ.ም ጽፈው ባቀረቡት የሰበር አቤቱታ የፌደራል መጀመርያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ.ቁ 91042 ታህሳስ 26 ቀን 2015 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ፤ ይህንኑ ውሳኔ በማጽናት የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ.ቁ 300152 የካቲት 27 ቀን 2015 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ በሰበር ታይቶ ሊታረም ይገባል በማለት አቤቱታ በማቅረባቸው ነው፡፡

ጉዳዩ ኑዛዜ ይፍረስልኝ በሚል የቀረበን ክርክር የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው በፌደራል መጀመርያ ደረጃ ፍርድ ቤት ነው፡፡ በስር ፍርድ ቤት በተደረገው ክርክር የአሁን ተጠሪ ከሳሽ፤ የአሁን አመልካቾች ደግሞ ተጠሪዎች በመሆን ተከራክረዋል፡፡

ተጠሪ በስር ፍርድ ቤት ያቀረቡት አቤቱታ ክስ ይዘት በአጭሩ፡- አክስቴ የሆነችው ሟች ወ/ሮ ደብራቱ ወልደሃና በቂርቆስ ክፍለ ከተማ ወረዳ 07 የቤት ቁጥር 003 ውስጥ ስትኖር ልጅ ሳትወልድ ከዚህ አለም በሞት ተለይታለች፤ የወ/ሮ ደብራቱ ወልደሃና ወንድም የሆነው ሟች አባቴ አቶ ታደሰ ወልደሃና የሞተው ከአክስቴ ቀድሞ ነው፤ የአባቴ ተተኪ ወራሽ መሆኔን አረጋግጫለሁ፤ ሌላ አክስቴ የሆነችው ወ/ሮ አማከለች ወልደሃና ቤቱን እያስተዳደረችልኝ በጋራ ከኪራይ የሚገኘውን ገንዘብ እየሰጠችኝ ስንጠቀም ቆይተን ጥር 06 ቀን 2014 ዓ.ም ከዚህ ዓለም በሞት ተለይታለች፤ የውርስ ማጣራትም ሆነ

የድርሻ ክፍፍል ያልተጠየቀበት በክሱ ላይ የተገለጸውን ቤት የውርስ ድርሻ ክፍፍል እንዲደረግበት በፌደራል መጀመርያ ደረጃ ፍርድ ቤት ቂርቆስ ምድብ ችሎት ጠይቁ እየታየ ባለበት አመልካቾች ሚች አማከለች ወልደሃና በልጅ ልጅነት ስላሳደገችን ኑዛዜ ተደርጎልናል በማለት ጣልቃ ገብተዋል፤ ወ/ሮ አማከለች ወልደሃና የራስዋ ባልሆነ የአክስቱ ሚች ደብሪቱ ወልደ ሃና የነበረ ከሚች አማከለች ወልደሃና ጋር በጋራ እየተጠቀምንበት የነበረ ንብረት ላይ ያደረገችው ኑዛዜ ነው፤ ከንብረቱ ላይ ሚች አማከለች ወልደሃና በሕይወት እያለች ድርሻዬን እንድትሰጠኝ በተደጋጋሚ ብጠይቃትም ስታመላልሰኝ ቆይታ ድርሻዬን ሳትሰጠኝ ከዚህ አለም በሞት ተለይታለች፤ የውርስ ሀብት የሆነውን ንብረት ውርስ ሳይጣራ እና ሳታሳውቀኝ ስመ-ሀብቱን ወደራስዋ በማዞር የእሷ ብቻ ባልሆነ ንብረት ላይ ኑዛዜ ማድረጓን አረጋግጫለሁ፤ ሚች አማከለች ወልደሃና በህመሟና በመሞቷ ምክንያት ከመስከረም 2014 ዓ.ም ጀምሮ ይከፈለኝ የነበረው ኪራይ ስላልተከፈኝ በሌላ መዝገብ ክስ መስርቻለሁ፤ ተጠሪ የውርስ ሀብት ድርሻዬን እየተጠቀምኩኝ ስለሆነ ሚች ወ/ሮ አማከለች ወልደሃና ለአመልካቾች የተናዘዙት ኑዛዜ እንዲሻርልኝ እና 1/2ኛ ድርሻዬ እንዲሰጠኝ እና ለአመልካቾች የተሰጠው ካርታ እንዲመክን ይወሰንልኝ በማለት ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡

አመልካቾች በሰጡት መልስ የመጀመርያ ደረጃ መቃወሚያ ያቀረቡ ሲሆን በብይን ውድቅ ተደርጓል፤ በፍሬ ነገሩ ላይ ደግሞ አከራካሪው ቤት ከጅምሩ የወ/ሮ አባይነሽ አበጋዝ የነበረ ነው፤ ወ/ሮ አባይነሽ አበጋዝ ለወ/ሮ ደብሪቱ ወልደ ሃና በአዲስ አበባ አውራጃ ፍርድ ቤት ቀርበው በግልጽ ኑዛዜ አውርሰዋል፤ የአመልካቾች አውራሽ ወ/ሮ አማከለች ወልደሃናም ይህንን ንብረት ከሕዳር 3 ቀን 1992 ዓ.ም ጀምሮ ሲያስተዳድሩ ቆይተው ወራሽነታቸውን ሐምሌ 30 ቀን 1993 ዓ.ም አረጋግጠዋል፤ ወ/ሮ አማከለች ወልደሃና የካቲት 30 ቀን 2009 ዓ.ም በሰነዶች ማረጋገጫ ቀርበው ንብረቱን ለአመልካቾች አውርሰዋል፤ የተጠሪ የተተኪ ወራሽነት ማረጋገጫ የኑዛዜ ወራሽነትን አያረጋግጥም፤ ተጠሪ የኪራይ ገንዘብ እንዲሰጣቸው የጠየቁት በምን አግባብ እንደሆነ አልገለጹም፤ የኪራይ ገንዘብ ተከፍሏቸውም አያውቅም፤ ተጠሪ ክስ ባቀረበበት ጉዳይ ላይ መብት ስለሌላቸው ክሱ ውድቅ ሊደረግ ይገባል በማለት ተከራክረዋል፡፡

ጉዳዩ የቀረበለት ፍርድ ቤትም የግራ ቀኙን ክርክር እና ማስጃ ከመረመረ በኋላ ወ/ሮ አማከለች ወልደሃና ያደረጉት ኑዛዜ በውልና ማስረጃ ጽ/ቤት የተደረገ እና ምንም እንከን የሌለበት ነው፤ ለአመልካቾች በኑዛዜ የተላለፈው አከራካሪው ቤት ቀደም ሲል የወ/ሮ ደብሪቱ ወልደሃና የነበረ ነው፤ ወ/ሮ አማከለች ወልደሃና ሐምሌ 30 ቀን 1993 ዓ.ም ባገኙት የወራሽነት ማስረጃ አከራካሪውን ቤት ከወ/ሮ ደብሪቱ ወልደሃና በውርስ ያገኙት መሆኑን ያሳያል፤ ወ/ሮ ደብሪቱ ወልደሃና የተጠሪ አክስት ተጠሪም ተተኪ ወራሽ መሆናቸውን በመ.ቁ 39486 በቀን 13/05/2014 ዓ.ም የተሰጠው እና በማስረጃነት የቀረበው የፍርድ ቤት ውሳኔ ያሳያል፤ ይህ ማስረጃ ያልተሰረዘ እና ወራሽነታቸውን

የሚያረጋግጥ ነው፤ ሟች ወ/ሮ አማከለች ወልደሃና ለአመልካቾች ያደረጉት ኑዛዜ በራሳቸው ድርሻ ላይ ብቻ ሳይሆን በተጠሪም ድርሻ ላይ በመሆኑ ኑዛዜው ፈራሽ ሊሆን ይገባል ሲል ወስኗል፡፡

አመልካቾች ይህንን ውሳኔ በመቃወም ለፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የይግባኝ አቤቱታ ያቀረቡ ቢሆንም በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 337 መሠረት ይግባኛቸው ተሰርዟል፡፡

አመልካቾች መጋቢት 01 ቀን 2015 ዓ.ም ጽፈው ያቀረቡት የሰበር አቤቱታ ይህን ውሳኔ በመቃወም የቀረበ ሲሆን ይዘቱም፡- የስር ፍርድ ቤት ያልተሰረዘ ማስረጃ ተቀባይነት የለውም ማለት አይቻልም በማለት የሰጠው ውሳኔ የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በሰ.መ.ቁ 82679 እና 226490 የሰጠውን አስገዳጅ የሕግ ትርጉም የሚቃረን ነው፤ የኑዛዜ አውራሻችን የንብረቱን ስመ ሀብት ወደ ራሷ በማዞር እስከዕለተ ሞቷ ድረስ ለ 22 አመታት ስትጠቀምበት እንደነበር ተረጋግጧል፤ ተጠሪ ከአዲስ አበባ ከተማ ፍርድ ቤት ያገኙት የወራሽነት ማስረጃ የድርሻ ባለቤትነትን የማያሳይ ከመሆኑም በላይ በውርስ አጣሪ ተጣርቶ አልተረጋገጠም፤ የተጠሪ የወራሽነት ማስረጃ ለውርስ ማጣራት አቤቱታው እንደመነሻነት የሚያገለግል እንጂ የጋራ ወራሽነትን ለማስረዳት የሚውል አይደለም፤ ተጠሪ የጋራ ባለሃብት የሆነችበት የሕግ መሰረት በማስረጃ አላረጋገጠችም፤ ንብረቱ የአመልካቾች እና የተጠሪ የጋራ ሃብት ነው በማለት የተሰጠው ውሳኔ ማስረጃን በአግባቡ በመመዘን የተሰጠ አይደለም፤ ስለሆነም እነኚህ ሁኔታዎች ታልፈው ሟች ያደረጉት ኑዛዜ ሊፈርስ ይገባል በማለት በስር ፍርድ ቤት የተሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስሕተት የተፈጸመበት በመሆኑ በሰበር ታይቶ ሊታረም ይገባል የሚል ነው፡፡

የሰበር አጣሪው ችሎት የአመልካቾችን የሰበር አቤቱታ መርምሮ አመልካቾች የውርስ ንብረቱን ካርታ አውጥተው ከ20 ዓመታት በላይ ሲጠቀሙበት ከነበሩት ሰው በውርስ ሳያገኙ ተጠሪ የተተኪ ወራሽ ነኝ በማለት ያቀረቡት የወራሽነት ምስክር ወረቀት የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ከሰጣቸው አስገዳጅ ውሳኔዎች አንጻር መጣራት ያለበት መሆኑ ስለታመነበት ጉዳዩ ለዚህ ችሎት ቀርቧል፡፡

ተጠሪ ሚያዝያ 26 ቀን 2015 ዓ.ም ያቀረቡት መልስ ይዘት ባጭሩ፡- አከራካሪው ቤት ከአመልካቾች ጋር በጋራ ይዘን ስለማስተዳደራችን በመ.ቁ 91042 ጥቅምት 25/2015 ዓ.ም በተሰጠ ብይን ተረጋግጧል፤ ሟች ያደረጉት ኑዛዜ እንዲፈርስ የተወሰነው ከአመልካቾች አውራሽ ጋር በጋራ በመሆን አከራካሪውን ቤት ስለመያዛችን ተረጋግጦ ነው፤ አመልካቾች ካርታ ያወጡት በወራሽነት ማስረጃ እንጂ ውርሱ ከተጣራ በኋላ አይደለም፤ የስር ፍርድ ቤት ለውሳኔው መሰረት ያደረገው የተጠሪን የወራሽነት ማስረጃ ብቻ አይደለም፤ ስለሆነም ውሳኔው ሊጸና ይገባል የሚል ነው፡፡

አመልካች በሰጡት የመልስ መልስ ያቀረቡትን አቤቱታ በማጠናከር ተከራክረዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ባጭሩ ከላይ የተገለጸው ነው። ይህ ችሎትም ሊጣራ ይገባዋል ተብሎ የተያዘውን ነጥብ ከግራ ቀኙ ክርክር፤ ለሰበር አቤቱታ መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸው ህጎች ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለው መርምሮታል።

ከክርክሩ ሒደት መገንዘብ የቻልነው ጉዳዩ የቀረበለት የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት አከራካሪ የሆነው ቤት ቀደም ሲል የወ/ሮ ደብሪቱ ወልደሃና እንደነበር፤ ወ/ሮ አማከለች ወልደሃና ሐምሌ 30 ቀን 1993 ዓ.ም ባገኙት የወራሽነት ማስረጃ አከራካሪውን ቤት ከወ/ሮ ደብሪቱ ወልደሃና በውርስ እንዳገኙት፤ ወ/ሮ ደብሪቱ ወልደሃና የተጠሪ አክስት ተጠሪም ተተኪ ወራሽ መሆናቸውን የሚያሳይ በመ.ቁ 39486 በቀን 13/05/2014 ዓ.ም የተሰጠው የፍርድ ቤት ውሳኔ በማስረጃነት እንደቀረበ፤ ወ/ሮ አማከለች ወልደሃና ያደረጉት አከራካሪውን ቤት አስመልክቶ ለአመልካቾች ያደረጉት ኑዛዜ እንከን የሌለበት መሆኑን አረጋግጦ ተጠሪ በማስረጃነት ያቀረቡት የወራሽነት ማስረጃ ያልተሰረዘ በመሆኑ እና ሟች ወ/ሮ አማከለች ወልደሃና ለአመልካቾች ያደረጉት ኑዛዜ በራሳቸው ድርሻ ላይ ብቻ ሳይሆን በተጠሪም ድርሻ ላይ በመሆኑ ኑዛዜው ፈራሽ ሊሆን ይገባል ሲል ከሚል ድምዳሜ ላይ የደረሰ መሆኑን ነው።

አመልካቾች ለዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት ባቀረቡት ክርክር በስር ፍርድ ቤት የተሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስሕተት የተፈጸመበት ነው በማለት በዋነኝነት የሚከራከሩት የስር ፍርድ ቤት ለተጠሪ የተሰጠው የወራሽነት ማስረጃ ያልተሰረዘ በመሆኑ አመልካቾች የተጠሪን ወራሽነት አስመልክቶ የሚያቀርቡት ክርክር ተቀባይነት የለውም በማለት የሰጠው ውሳኔ የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በሰ.መ.ቁ 82679 እና 226490 የሰጠውን አስገዳጅ የሕግ ትርጉም የሚቃረን ነው በሚል ነው። ስለሆነም ተጠቃሾቹ ውሳኔዎች ለጉዳዩ አግባብነት ያላቸው መሆን አለመሆኑን እንደሚከተለው መርምረናል።

የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በሰ.መቁ 82679 እና በሌሎችም መዛግበት የሰጠው ውሳኔ በአንድ ወገን አቤቱታ አቅራቢነት የተሰጠ ማስረጃ በማስረጃነት በቀረበበት በማናቸውም ጊዜ ተዓማኒነት እና ክብደት ያለው ማስረጃ መሆኑን ለማሳየት ክርክር ሊቀርብበት እና ተቃራኒ ማስረጃ ተሰምቶ ውድቅ ሊደረግ እንደሚችል በመግለጽ በየትኛም እርከን ላይ ለሚገኙ ፍርድ ቤቶች አስገዳጅ የሆነ የሕግ ትርጉም ሰጥቶበታል። ስለሆነም የስር ፍርድ ቤት በተጠሪ በኩል የቀረበውን ማስረጃ ስላልተሰረዘ አመልካቾች የተጠሪን ወራሽነት በሚመለከት ያቀረቡት ክርክር ተቀባይነት የለውም ማለቱ ተጠቃሹን የሰበር ሰሚ ችሎት ውሳኔ የሚቃረን ሆኖ አግኝተነዋል። ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ አመልካቾች በተጠሪ በኩል የቀረበው የወራሽነት ማስረጃ በሚመለከት ወራሽነቷ የተረጋገጠበት እንጂ የሕግም ሆነ የኑዛዜ ወራሽ መሆናቸውን አያሳይም በማለት ከመከራከራቸው በቀር ተጠሪ የሟች ወራሽ አለመሆናቸውን ለማሳየት የሚያስችል ተቃራኒ ማስረጃ በማቅረብ የተከራከሩ መሆኑን የስር ውሳኔ አያሳይም። በአዲስ አበባ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ.ቁ 39486 ጥር 13 ቀን 2014 የተሰጠው ውሳኔ ደግሞ ተጠሪ የሟች ወ/ሮ ደብሪቱ ወልደሃና ወራሽ መሆናቸውን የሚያሳይ ነው። ስለሆነም አመልካቾች የተጠሪን ወራሽነት

በሚመለከት ለዚህ ችሎት ያቀረቡት ክርክር ተቀባይነት ያለው ሆኖ አልተገኘም፡፡ በመቀጠል ሟች ያደረጉት ኑዛዜ እንዲፈርስ በማለት በስር ፍርድ ቤት የተሰጠው ውሳኔ ተገቢ መሆን አለመሆኑን እንደሚከተለው መርምረናል፡፡

በኢትዮጵያ ውርስ ሕግ የሚች ውርስ ያለ ኑዛዜ፣ በኑዛዜና በከፊል ኑዛዜና በከፊል ያለ ኑዛዜ የሚፈፀም ስለመሆኑ፤ ሟች በኑዛዜ የሚያስተላልፈው ንብረትም የራሱን ንብረት ስለመሆኑ ከፍ/ብ/ሕ/ቁ 829 እና ተከታይ ድንጋጌዎች ይዘት መገንዘብ ይቻላል፡፡

በያዝነው ጉዳይ አከራካሪ የሆነው ቤት የወ/ሮ ደብሪቱ ወልደሃና እንደነበር እና ወ/ሮ አማከለች ወልደሃና ሐምሌ 30 ቀን 1993 ዓ.ም ባገኙት የወራሽነት ማስረጃ አከራካሪውን ቤት ከወ/ሮ ደብሪቱ ወልደሃና በውርስ እንዳገኙት፤ ተጠሪ በበኩላቸው የወ/ሮ ደብሪቱ ወልደሃና ተተኪ ወራሽ መሆናቸውን የሚያሳይ በመ.ቁ 39486 በቀን 13/05/2014 ዓ.ም የተሰጠው የፍርድ ቤት ውሳኔ በማስረጃነት ያቀረቡ ስለመሆኑ በስር ፍርድ ቤት የተረጋጠ ፍሬ ነገር ነው፡፡ ይህም ተጠሪ እና ሟች ወ/ሮ አማከለች ወልደሃና የአከራካሪው ቤት ወራሾች መሆናቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ ተጠሪ እና ሟች ወ/ሮ አማከለች ወልደሃና የአከራካሪው ቤት ወራሾች ከሆኑ ደግሞ ሟች ወ/ሮ አማካለች ወልደሃና ቤቱን በኑዛዜ ማስተላለፍ የሚችሉት በድርሻቸው ላይ ብቻ ነው፡፡ ሆኖም ሟች ወ/ሮ አማካለች ወልደሃና ባደረጉት ኑዛዜ አከራካሪውን ቤት ያስተላለፉት በድርሻቸው ላይ ብቻ ሳይሆን የተጠሪንም ድርሻ ጨምረው በመሆኑ ኑዛዜው ሊፈርስ የሚገባው ሙሉ በሙሉ ሳይሆን በተጠሪ ድርሻ ላይ ያደረጉት የኑዛዜ ክፍል ብቻ ነው፡፡ በመሆኑም የስር ፍርድ ቤቶች ሟች ወ/ሮ አማከለች ወልደሃና በቂርቆስ ክፍለ ከተማ ወረዳ 07 የቤት ቁጥሩ 003 የሆነውን ቤት አስመልክቶ የካቲት 30 ቀን 2009 ዓ.ም ያደረጉት ኑዛዜ ሙሉ በሙሉ እንዲፈርስ በማለት የሰጡት ውሳኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስሕተት የተፈጸመበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ በዚህም ምክንያት ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

ውሳኔ

1. የፌደራል መጀመርያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ.ቁ 91042 ታህሳስ 26 ቀን 2015 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ፤ ይህንኑ ውሳኔ በማጽናት የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ.ቁ 300152 የካቲት 27 ቀን 2015 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 348/1 መሠረት ተሻሽሏል፡፡
2. ሟች ወ/ሮ አማከለች ወልደሃና በቂርቆስ ክፍለ ከተማ ወረዳ 07 የቤት ቁጥሩ 003 የሆነውን ቤት አስመልክቶ የካቲት 30 ቀን 2009 ዓ.ም ያደረጉት ኑዛዜ በራሳቸው ድርሻ ላይ ብቻ የተደረገ ሳይሆን በተጠሪም ድርሻ ላይ ጭምር የተደረገ በመሆኑ የተጠሪን ድርሻ በሚመለከት የተደረገው የኑዛዜ ክፍል ብቻ ፈራሽ ሆኗል በማለት ወስነናል፡፡

3. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡

- መዝገቡ ውሳኔ ስላገኘ ተዘግቷል፡፡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ፍ/ደ

የሰበር መዝገብ ቁጥር 245055

መጋቢት 27 ቀን 2016 ዓ.ም

ዳኞች፡- እትመት አሰፋ

ደጇኔ አያንሳ

ኑረዲን ከድር

መላኩ ካሳዬ

ሐብታሙ እርቅይሁን

አመልካች፡- ወ/ሮ ኤልሳቤጥ እሸቱ - ቀርበዋል

ተጠሪዎች፡- 1ኛ. ወ/ሮ ማህደር እሸቱ - ቀርበዋል

2ኛ. አቶ ጌታሁን እሸቱ - አልቀረቡም

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍርድ

ጉዳዩ የኑዛዜ ይፍረስ ክርክርን የሚመለከት ሆኖ ክሱ በቀረበበት የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት አመልካች ከሳሽ ፣ ተጠሪዎች ደግሞ በተከሳሽነት ተከራክረዋል፡፡ የክርክሩ አመጣጥ በአጭሩ፡- አመልካች ሰኔ 10 ቀን 2014 ዓ.ም በተፃፈ የክስ አቤቱታ አባታቸው በ1975 ዓ.ም ስለሞቱ የሚች አያታቸው ወ/ሮ ደምሽ ትክሴ ተተኪ ወራሽ መሆናቸውን እና ሟቿ ከመሞታቸው ሁለት ቀን በፊት ጥር 25 ቀን 2010 ዓ.ም አድርገውታል በተባለው ኑዛዜ መነሻነት ተጠሪዎች የውርስ ሀብቱን እንደከለከሏቸው በመግለፅ ፣ ሟች አድርገውታል የተባለው ኑዛዜ ከ1/4ኛ በላይ ጉዳት ያደረሰባቸው በመሆኑ ፈራሽ ተብሎ ያለኑዛዜ ወራሽ ናቸው ተብሎ እንዲወሰን ጠይቀዋል፡፡

ተጠሪዎች ለክሱ በሰጡት መልስ የኑዛዜ ይፍረስልኝ ጥያቄው በወቅቱ ስላልቀረበ በፍትሐ ብሔር ሕጉ ቁጥር 973 መሠረት በይርጋ ይታገዳል የሚል መቃወሚያ አቅርበዋል፡፡ ፍ/ቤቱም መቃወሚያውን እንደመረመረው በፍትሐ ብሔር ሕጉ ቁጥር 973/3 እና 974/1 ድንጋጌ መሠረት

ኑዛዜ እንዲፈርስ መቃወሚያ ማቅረብ የሚቻለው መቃወሚያ አቅራቢው የኑዛዜውን ይዘት ባወቀ ወይንም ውርስ አጣሪው የውርስ ሀብት ድልድል ባሳወቀ በ3(ሶስት) ወር ጊዜ ውስጥ ሲሆን ፤ ኑዛዜው ተነቦ እንደሆነ አልያም ኑዛዜ አድራጊው በሞተ 5(አምስት) ዓመት ውስጥ መሆን አለበት፡፡ ስለሆነም የ5(አምስት) ዓመት የይርጋ ድንጋጌ የሚመለከተው የኑዛዜውን ይዘት ያላወቀውን ወራሽን ነው፡፡ አመልካች የሚቃወሙት ኑዛዜ መኖሩን ከሰኔ ወር 2010 ዓ.ም አንስቶ የሚያውቁ መሆኑን በክሳቸው ስለገለጹ የ5(አምስት) ዓመት ይርጋው እሳቸውን የማይመለከት ከመሆኑም በላይ የፍትሐ ብሔር ሕጉ ቁጥር 1123/3 ድንጋጌም ለጉዳዩ አግባብነት የሌለው በመሆኑ ኑዛዜ መኖሩን ካወቁ ከ4 አመት በኋላ አመልካች ያቀረቡት ክስ በይርጋ የሚታገድ ነው በማለት ክሱን ውደቅ በማድረግ መዝገቡን ዘግቶታል፡፡ አመልካች በዚህ ብይን ቅር ተሰኝተው ይግባኝ ለፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ያቀረቡ ቢሆንም ፍርድ ቤቱ ይግባኙን ባለመቀበል በፍትሐ ብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 337 መሰረት ሰርዞታል፡፡

የሰበር ቅሬታው የቀረበው የፌደራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የሰጠውን ብይን በመቃወም አመልካች ያቀረቡት የይግባኝ አቤቱታ በይግባኝ ሰሚው የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት መጽናቱን በመቃወም በሰበር ለማስለወጥ ነው፡፡

የሰበር ቅሬታው በአጭሩ፡- የፍትሐ ብሔር ሕጉ ቁጥር 973 ድንጋጌ ተፈፃሚነት የሚኖረው ኑዛዜው በአካል ወይም በተወካይ ሲነበብ ለነበሩ ሲሆን የፍትሐ ብሔር ሕጉ ቁጥር 974 ድንጋጌ ደግሞ በኑዛዜው መነበብ ሥነ ሥርዓት ያልነበሩ ወይም ያልተወከሉ ሰዎችን የሚመለከት ለመሆኑ በሰበር መዝገብ ቁጥር 82585(በቅጽ 15 እንደታተመው) አስገዳጅ ውሳኔን ሰጥቷል፡፡ አመልካች ሟች አያታቸውን ደምሽ ትክሴ ጥር 25 ቀን 2010 ዓ.ም ያደረገችው ኑዛዜ ሚያዝያ 22 ቀን 2010 ዓ.ም ሲነበብ በአካል ያልነበርኩ መሆኑ በተጠሪዎች ያልተካደ ከመሆኑም በላይ በሥር ፍርድ ቤት ተረጋግጧል፡፡ አመልካች ኑዛዜ መኖሩን ያወቅኩት የውርስ ሀብት ተጣርቶ ድርሻዬን እንዲያካፍሉኝ በተጠሪዎች ላይ በመዝገብ ቁጥር 140168 ሳቀርብ ሆኖ ፍርድ ቤቱም ኑዛዜው ላይ የሚቀርበው ክርክር ታይቶ ውሳኔ ካገኘ በኋላ መዝገቡን የማንቀሳቀስ መብት ጠብቆ መዝገቡን ዘግቷል፡፡ በአዲስ አበባ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ኑዛዜውን በመቃወም ያቀረብኩት አቤቱታ ታይቶ ውሳኔ ካገኘ በኋላ ጉዳዩ የቀረበለት ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት መጣራት አላባቸው የሚላቸውን ጭብጦች ይዞ ጉዳዩ ወደ አዲስ አበባ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ቤት ግንቦት 10 ቀን 2013 ዓ.ም በመመለሱ ለሰበር ቅሬታው መሠረት የሆነው ክስ በፍትሐ ብሔር ሕግ ቁጥር 974 ድንጋጌ መሠረት የይርጋ ጊዜው 5(አምስት) መሆን ሲገባው ከ4(አራት ዓመት) በኋላ የቀረበ ክስ ነው ተብሎ በክርክር ሂደት ላይ የነበርኩ መሆኑ እየታወቀ በይርጋ ቀሪ መሆኑ መሠረታዊ የሕግ ስህተት በመሆኑ ስህተቱ ሊታረም ይገባል በማለት ተከራክረዋል፡፡

በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ሥነ ሥርዓት መመሪያ ቁጥር 17/2015 ቁጥር 6(1) መሠረት ለሰበር ሰሚው ችሎቱ የተመራው አቤቱታ በሰበር ሰሚ ችሎቱ ተመርምሮ አመልካች ኑዛዜ መደረጉን(መኖሩን) እንደማያውቁ በፍሬ ነገር ደረጃ ከመረጋገጡ አንፃር በሥር ፍርድ ቤት የተወሰደው የይርጋ እርዝማኔ ተገቢነት እንዲሁም አመልካች በኑዛዜው በተደረገው ክፍፍል ጉዳት አድርሶብኛል በማለት የሚከራከሩ በመሆኑ ያቀረቡት ክስ በይርጋ የሚታገድ መሆን አለመሆኑን ለማጣራት መዝገቡ ያስቀርባል ተብሎ ተጠሪዎች ተከታዩን ምላሽ ሰጥቷል፡፡

ተጠሪዎች ለሰበር አቤቱታው ህዳር 14 ቀን 2016 ዓ.ም የተጻፈ 3(ሶስት) ገጽ መልስ ያቀረቡ ሲሆን የክርክራቸው ይዘት፡- አመልካች የ1ኛ ተጠሪን የኑዛዜ ወራሽነት በመቃወም በመዝገብ ቁጥር 15281 አቤቱታ ያቀረቡት በሰኔ ወር 2010 ዓ.ም ሳይሆን በሚያዝያ 29 ቀን 2011 ዓ.ም ነው፡፡ ሟች ያደረጉት ኑዛዜ ሚያዝያ 22 ቀን 2010 ዓ.ም ስለሚነበብ(ስለሚፈስ) አመልካች እንዲገኙ በተደጋጋሚ ተደውሎላቸው እና ተነግሯቸው ለመቅረብ ፈቃደኛ ስላልሆኑ በፍትሐ ብሔር ህጉ 973/1 እና 974/3 ድንጋጌ መሠረት ቀሪ ሆኗል፡፡ አመልካች የሟች የልጅ ልጅ ተተኪ ወራሽ እንጂ ልጅ ስላልሆኑ በኑዛዜ ድርሻ ላይ መቃወሚያ ማቅረብ የሚችሉ ባለመሆኑ በግራ ቀኙ መካከል የይርጋ ክርክር በመካከላችን ሊነሳ የሚችልበት ሕግ አግባብ የለም፡፡ በይዞታ ውስጥ ከሟች የግል ንብረቶች በተጨማሪ በ1ኛ ተጠሪ የተሰሩ የንግድ ሱቆች ያሉ ሲሆን ቀሪውን ንብረት ሟች ለአራት የኑዛዜ ወራሾች ተናዘዋል፡፡ ለኑዛዜ ተቀባዮች የተሰጠው ንብረት ዋጋ መጠን ተለይቶ ጉዳት መኖር አለመኖሩ ባልታወቀበት አመልካች ጉዳት ድርሶብኛል በማለት በደፈናው የሚያቀርቡት ክርክር የህግ መሠረት ስለሌለው አመልካች ያቀረቡት አቤቱታ ውድቅ በማድረግ ውሳኔ እንዲሰጣቸው ጠይቀዋል፡፡

አመልካችም የሰበር አቤቱታቸውን በማጠናከር የመልስ መልስ አቅርበዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ እና መሰረታዊ የክርክሩ ይዘት በአጭሩ ከላይ የተመለከተውን ሲመስል ችሎቱም በሰበር ችሎቱ ሊጣራ ይገባዋል ተብሎ የተያዘውን ነጥብ ከግራ ቀኙ ክርክር፤ ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸው ሕጎች ጋር በማገናዘብ መርምሯል፡፡

በፍትሐብሔር ሕጉ ቁጥር 1807/ረ/ ድንጋጌ መሠረት ይርጋ ግዴታዎችን ቀሪ ከሚያደርጉ ምክንያቶች ውስጥ አንዱ ነዉ። ድንጋጌው የውል ህግን የሚመለከት ቢሆንም “**ግዴታዎች**” ማለቱ የውል ግዴታን ብቻ ላለመሆኑ አመላካች ሲሆን ከቁጥር 1677(1) ድንጋጌ አንፃርም ሲታይ ሌሎች ግዴታዎችንም ይጨምራል። ይርጋ *የመብት* ጥያቄ በህጉ በተቀመጠው ጊዜ ውስጥ ባለመቅረቡ በጊዜ ማለፍ ቀሪ የሚሆንበት ፣ ተጠያቂነትን በማስቀረት ያልነበረ መብትን የሚያጎናጽፍ ነው። ይርጋ ዳተኛ መብት ጠያቂዎችን መብት የሚያሳጣ በአንፃሩ ባለዕዳዉ ሁልጊዜ ያለበትን ዕዳ እያሰበ በስጋት እንዳይኖር ነፃ የሚያወጣ ነው። በጊዜ ማለፍ ምክንያት ኃላፊነት ወርዶልኛል

የሚለው ሰው ኃላፊነት እንዳለበት የማይክድ በክርክሩ በተከሳሽነት የሚሰየመው ሰው ነው፡፡ ሕጉ ይህን መብት አንስቶ የመከራከር ዕድል ለባለዕዳው የተሰጠ ሆኖ መከራከሪያውን ማንሳት የሚችለው በመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ መልክ ነው፡፡ የይርጋ መቃወሚያ ተጠቃሚ የሆነ ሰው በፍ/ሥ/ሥ ሕጉ ቁጥር 244(2) (ሠ) መሠረት በመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያነት ለማንሳት መብት ያለው ቢሆንም ይህን መብቱን መተው እንደሚችል የፍትሐብሔር ህግ ቁጥር 1856 ያስገነዝበናል። ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 244(2)(ሠ) እንዲሁም ከቁጥር 245 ድንጋጌዎች መረዳት እንደሚቻለውም ክሱ በይርጋ የታገደ መሆኑን የሚገልጽ መቃወሚያ ሲቀርብ የቀረበውን የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ፍርድ ቤቱ ተቀብሎ ሊላው ተከራካሪ ወገን በጉዳዩ ላይ የሚያቀርበውን ክርክር ከሰማ በኋላ ውሳኔ ለመስጠት ተገቢ መስሎ የሚገምተው ማስረጃ እንዲቀርብለት በማድረግ መቃወሚያው በተገቢና በቂ ማስረጃ መደገፉን በመመርመር ተገቢ መስሎ የታየውን ብይን ሊሰጥ ይገባል፡፡ በመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ክርክር የይርጋ መከራከሪ መብቱን ያልተጠቀመ ተከሳሽ መብቱን እንደተወው ስለሚገመት ዳኞች ክርክሩን ማንሳት ስለማይችሉ ፍሬ ነገሩን መርምረው ውሳኔ ይሰጣሉ፡፡ የፍትሐብሔር ሕጉ ቁጥር 1851 ይርጋ የሚቋረጥባቸውን ምክንያቶች ይዘረዝራል፡፡ ይርጋ ከተቋረጠ እንደ አዲስ የሚቆጠር መሆኑን ከቁጥር 1852 ድንጋጌ መረዳት ይቻላል፡፡

ኑዛዜን በመቃወም የሚቀርበው ማናቸውም መቃወሚያ መታየት ያለበት አግባብነት ካለቸው የውርስ ሕግ ድንጋጌዎች አንፃር ነው፡፡ አንድ ኑዛዜ ፈራሽ ነው በሚል ስለሚቀርብ መግለጫ እና ክስ እንዲሁም መግለጫ እና ክሱ ሊቀርብ ስለሚገባበት የጊዜ ገደብ በፍትሐ ብሔር ሕግ ቁጥር 973 እና 974 ተደንግጎ ይገኛል፡፡ የፍትሐ ብሔር ሕግ ቁጥር 973 ድንጋጌ ኑዛዜው ፈራሽ ነው የሚል መቃወሚያ ያላቸው ኑዛዜው ሲነገር /ሲፈስ/ የነበሩትን ሰዎች የሚመለከት ነው፡፡ ይህም ኑዛዜው ሲነበብ የነበሩ ወይም የተወከሉ ሰዎች ኑዛዜው አይፀናም ወይም በኑዛዜው የተነገረ ቃል አይፀናም የሚሉትንና የመሳሰሉትን የሚቃወሙ ቢሆን ይህን ማድረግ ያለባቸው ኑዛዜው ከተነበበበት አንስቶ እስከ አስራ አምስት ቀን ድረስ እንደሆነ ያመለክታል፡፡ የፍትሐ ብሔር ሕግ ቁጥር 973 (1) ድንጋጌ ክስን ሳይሆን መግለጫን የሚመለከት ነው፡፡ የንብረት ድልድል የማያውቅ ወራሽ መግለጫ የማቅረብ ግዴታ የለበትም፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ክስን የማቅረብ ሃላፊ መግለጫው በጽሐፍ ካልሆነና ለአጣሪው ወይም ለዳኞች ወይም በውርስ ላይ የተነሣውን ነገር ለመጨረስ ለተመረጡት የሽምግልና ዳኞች እንዲደርስ ካልተደረገ በቀር እንደማይፀና /መቃወሚያ አለ ለማለት እንደማይቻል/ በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 973/2/ ተደንግጓል፡፡ በመጨረሻም መግለጫው ከተሰጠበት ቀን አንስቶ እስከ ሦስት ወር ድረስ ክስ ካልቀረበ መብቱ ከነጭራሹ እንደሚቀር በንኡስ ቁጥር /3/ ተመልክቷል፡፡ ኑዛዜ መኖሩን ማወቅ እና በኑዛዜው የተደረገውን ክፍፍል ይዘት ማወቅ ልዩነት ያለው መሆኑን ልብ ማለት ይገባል፡፡ ኑዛዜው ሲነበብ(ሲፈስ) በአካል ወይም በተወካይ ላልተሳተፉ ወይንም በሌሉበት ኑዛዜ የፈሰሰ ሰዎች በፍትሐ ብሔር ሕጉ ቁጥር 973

የተመለከተው ጊዜ መቆጠር የሚጀምረው የውርስ አጣሪው ስለ ክፍያ ፣ ድልድል አመዳደብ ሃሳብ ከነገራቸው ቀን አንስቶ መሆኑን የፍትሐ ብሔር ሕግ ቁጥር 974(1) ድንጋጌ ያመለክታል፡፡ አንድ ሰው ኑዛዜው መነበቡን (መፍሰሱን) ያውቃል ለማለት በአካል ወይንም በተወካይ ኑዛዜው ሲነበብ ወይም ሲፈስ መገኘት አልያም ስለ ክፍያ ፣ ድልድል አመዳደብ ሃሳብ በአጣሪው የተነገረው እንደሆነ መሆኑን ከፍትሐ ብሔር ሕጉ ቁጥር 973 እና 974(1) ድንጋጌዎች ጣምራ ንባብ መገንዘብ ይቻላል፡፡ ኑዛዜ ከፈሰሰበት ወይም ሟቹ ከሞተበት ከአምስት ዓመት በኋላ ስለኑዛዜው መጽናት፤ ስለክፍያው አመዳደብ አጣሪው ያቀረበውን ሃሳብ መቃወሚያ ሊቀርብበት እንደማይገባ ፍፁም(absolute) ይርጋ በፍትሐ ብሔር ሕጉ ቁጥር 974(2) ሥር ተመልክቷል፡፡ ኑዛዜ ሲነበብ(ሲፈስ) በአካል ያልነበሩ ፣ ያልተወከሉ አልያም ስለ ክፍያ ፣ ድልድል አመዳደብ ሃሳብ በአጣሪው ያልተነገራቸው ሰዎችን የሚመለከተው ይርጋ በፍትሐ ብሔር ሕጉ ቁጥር 974(2) ሥር የተመለከተው ፍፁም(absolute) ይርጋ መሆኑን ይህን ሰበር ሰሚ ችሎት በሰበር መዝገብ ቁጥር 217691(ያልታተመ) ሰኔ 30 ቀን 2014 ዓ.ም አስገዳጅ ውሳኔን ሰጥቷል፡፡

በተያዘው ጉዳይ አመልካች ኑዛዜው ሲነበብ(ሲፈስ) በአካል ወይንም በተወካይ ያልተገኙ ፣ ስለ ክፍያ፤ ድልድል አመዳደብ ሃሳብ በአጣሪው ያልተነገራቸው ነገር ግን ያለኑዛዜ የውርስ ድርሻቸውን ለመካፈል በ2010 ዓ.ም ክስ ሲያቀርቡ ተጠሪዎች የኑዛዜ ወራሽነት ማስረጃ መውሰዳቸውን ሰምቶ ኑዛዜው እንዲሰረዝላቸው ክስ ያቀረቡ መሆኑን ከክርክሩ ሂደት መረዳት ተችሏል፡፡ አመልካች የኑዛዜውን መኖር በ2010 ዓ.ም ሰምተው እያለ ከ4(አራት) ዓመት በኋላ ሰኔ 10 ቀን 2014 ዓ.ም የቀረበው ክስ በ3(ሶስት) ወር የይርጋ ቀሪ ነው በማለት የአመልካችን የክሰ አቤቱታ በይርጋ ውድቅ ማድረጋቸው የፍትሐ ብሔር ሕጉን ቁጥር 973 እና 974(1) ድንጋጌዎች እንዲሁም በሰበር መዝገብ ቁጥር 217691 የሰጠውን አስገዳጅ የህግ ትርጉም የተላለፈ ነው፡፡ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ከአምስት ያላነሱ ዳኞች በተሰየሙበት ችሎት የሚሰጠው አስገዳጅ የህግ ትርጉምን በመተላለፍ የሚሰጥ ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት ስለመሆኑ የፌዴራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀጽ 2(4(ሸ)) ይደነግጋል፡፡

በመሆኑም አመልካች ኑዛዜዉ ሲነበብ ያልነበሩ ስለሆኑ በጉዳዩ ላይ ተፈጻሚነት ያለው ይርጋ የፍ/ብ/ሕ/ቁ.974 (2) ሥር የተመለከተው የአምስት አመት ሲሆን ሟች ከመሞታቸው ሁለት ቀን በፊት ጥር 25 ቀን 2010 ዓ.ም ያደረጉት ኑዛዜ እንዲፈርስላቸው ሰኔ 10 ቀን 2014 ዓ.ም ያቀረቡት ክስ በፍ/ብ/ሕ/ቁ.974 (2) ሥር የተመለከተው የአምስት ዓመት የጊዜ ገደብ ከማለፉ በፊት ሆኖ እያለ በፍ/ብ/ሕ/ቁ.973 (2) እና 974 (1) መሰረት በ3 ወር ይርጋ የሚታገድ ነዉ በማለት የሥር ፍርድ ቤቶች ያሳለፉት ውሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ነው ብለናል፡፡

ውሳኔ

1. ይግባኝ ሰሚው የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት መዝገብ ቁጥር 297333 ጥር 24 ቀን 2015 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጠው ብይን ፣ እንዲሁም የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 183641 ህዳር 3 ቀን 2015 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጠው ብይን በፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ሥነ - ሥርዓት መመሪያ ቁጥር 17/2015 ቁጥር 9(1/ሀ) መሠረት ተሽሯል፡፡

2. አመልካች ያቀረቡት የኑዛዜ ይፍረስልኝ አቤቱታ በይርጋ ቀሪ የሚሆን አይደለም በማለት ተወስኗል፡፡

3. የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በብይን የዘጋውን የመዝገብ ቁጥር 183641 አንቀሳቅሶ የፍሬ ነገር ክርክሩ አይቶ ውሳኔ እንዲሰጥ መዝገቡ በፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ሥነ - ሥርዓት መመሪያ ቁጥር 17/2015 ቁጥር 9/2 መሠረት ተመልሶለታል፡፡

4. ውሳኔው ሚያዝያ 16 ቀን 2016 ዓ.ም በችሎት ተነቧል፡፡

መዝገቡ ውሳኔ አግኝቶ ስለተዘጋ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ፍ/ደ

የሰበር መዝገብ ቁጥር 132787

ታህሳስ 24 ቀን 2009 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ፀጋይ አስማማው

ሙስጠፋ አህመድ

አብርሃ መሰለ

አብዬ ካሣሁን

እትመት አሰፋ

አመልካች፡- ወጣት አቡ ተሊሉ - ጠበቃ ፍጹም ሐሞተ - ቀረቡ

ተጠሪ፡- የለም

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ውሳኔ ተሰጥቶአል፡፡

ፍ ር ድ

አመልካች አቤቱታቸውን ለዚህ ችሎት ያቀረቡት በ1998 ዓ.ም. በሞት የተለዩትን አባታቸውን አቶ ተሊሉ ደብሬን ተክተው በ1997 ዓ.ም. በሞት የተለዩትን አያታቸውን /የአባታቸውን እናት/ ወ/ሮ ቦንቱ ዱላን የሚወርሱ ስለመሆኑ ተረጋግጦ የወራሽነት ማስረጃ እንዲሰጣቸው ያቀረቡትን አቤቱታ የተመለከተው የአዲስ አበባ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የአመልካች አባት የሞቱት እናታቸው ከሞቱ ከአንድ ዓመት በኋላ በመሆኑ አመልካች ያቀረቡት የተተኪ ወራሽነት ጥያቄ ተቀባይነት የለውም በማለት በመዝገብ ቁጥር 07905 በ17/12/2008 ዓ.ም. የሰጠው እና በከተማው ፍርድ ቤቶች ይግባኝ ሰሚ እና ሰበር ችሎቶች እንደቅደም ተከተሉ በመዝገብ ቁጥር 25804 በ03/01/2009 ዓ.ም. በመዝገብ ቁጥር 25845 በ12/01/2009 ዓ.ም. በትዕዛዝ የጸናው ትዕዛዝ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል ነው፡፡የሰበር አቤቱታው ተመርምሮ የአመልካቹ አያት የሞቱት ከወላጅ አባቱ በፊት መሆኑ በተረጋገጠበት ሁኔታ የተተኪ ወራሽነት ጥያቄው ውድቅ የመደረጉን አግባብነት ለማጣራት እንዲቻል ጉዳይ ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ የተደረገ ሲሆን እኛም አቤቱታ የቀረበበት ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት መሆን አለመሆኑን ለጉዳዩ ከተያዘው ነጥብ አንጻር መርምረናል፡፡

በዚህም መሰረት እናታቸው ማለትም የአመልካቹ አያት በሞቱበት ጊዜ ልጃቸው ማለትም የአመልካቹ አባት በሕይወት የነበሩ ስለመሆኑ አመልካቹ ለስር የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ባቀረቡት አቤቱታ ላይ ገልጸዋል፡፡አመልካች ለስር ፍርድ ቤት አቤቱታ ያቀረቡት የወራሽነት ደረጃቸው ተገልጾ የምስክር ወረቀት እንዲሰጣቸው በመጠየቅ ነው፡፡በአቤቱታቸው ላይ በተጠሪነት የተሰየመ ተከራካሪ ባለመኖሩ የአመልካቹ አባት በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 839 እስከ 840 በተመለከቱት ድንጋጌዎች መሰረት ለውርስ አይገቡም የተባሉ

ስለመሆኑ ወይም በዚሁ ሕግ በቁጥር 854 (1) ድንጋጌ መሰረት ውርሱን አልፈልግም ያሉ ስለመሆኑ የቀረበ ተቃራኒ ክርክር የለም፡፡እንዲህ ከሆነ ደግሞ ጉዳዩ ይመለከተኛል በሚል ሌላ ተከራካሪ ወገን የሚቀርብ ተቃራኒ ክርክር እና ማስረጃ ካለ የዚህ ዓይነቱ ክርክር እና ማስረጃ እስከሚቀርብበት ጊዜ ድረስ የአመልካች አባት ለውርስ አይገቡም ያልተባሉ ስለመሆኑ እና ውርሱን አልፈልግም ያላሉ ስለመሆኑ ግምት የሚወሰድበት ይሆናል፡፡እናታቸው በሞቱበት ጊዜ የአመልካች አባት በሕይወት የነበሩ ከሆነ እና ለውርስ አይገቡም ያልተባሉ ከሆነ ደግሞ በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 830 ድንጋጌ ስር የተመለከቱትን መስፈርቶች የሚያሟሉ በመሆኑ እናታቸውን የመውረስ መብት ይኖራቸዋል፡፡

አንድ ሰው የሞተ እንደሆነ በሞተበት ጊዜ ዋናው መኖሪያ ስፍራ በሆነበት ቦታ የሚቹ ውርስ የሚከፈት ስለመሆኑ እና በሚቹ ሞት ምክንያት የሚቋረጡ ካልሆኑ በቀር በውርሱ ውስጥ የሚገኙት የሚቹ መብቶች እና ግዴታዎች ለወራሾቹ እና የኑዛዜ ባለስጦታዎች የሚተላለፉ ስለመሆኑ በዚሁ ሕግ በቁጥር 826 የተመለከተ ሲሆን ለአንድ ውርስ ወራሽ የሆነ አንድ ሰው ውርሱ ከተከፈተ በኋላ የሞተ እንደሆነ የወራሽነቱ መብቶች ለእርሱ ወራሾች የሚተላለፉ ስለመሆኑም በቁጥር 833 ተደንግጎ ይገኛል፡፡የአመልካች አባት በሕይወት እያሉ የሚች እናታቸው ውርስ አልተከፈተም የሚባል ከሆነም አለመከፈቱ ከላይ በተጠቀሰው ድንጋጌ የሕግ ጥበቃ ባገኘው የወራሽነት መብት መተላለፍ ረገድ የሚያስከትለው ለውጥ አይኖርም፡፡

የስር ፍርድ ቤቶች እንደገለጹት አመልካች አባታቸውን ተክተው ከአባታቸው በፊት የሞቱትን አያታቸውን የመውረስ መብት የማይኖራቸው አባታቸው በሕይወት እያሉ የመውረስ መብታቸውን ተግባራዊ በማድረግ የእናታቸውን ውርስ ተካፍለዋል የሚባል ከሆነ ነው፡፡የአመልካች አባት በሕይወት እያሉ የእናታቸውን ውርስ የተካፈሉ መሆን አለመሆኑ እና ተያያዥ ፍሬ ነገሮች ደግሞ አመልካች በቆጠሯቸው ምስክሮች ተጣርተው ተገቢው ውሳኔ የሚሰጥባቸው ከሚሆን በቀር የአመልካች አባት የሞቱት እናታቸው ከሞቱ ከአንድ ዓመት በኋላ መሆኑ መገለጹ ብቻውን የአመልካቹን የወራሽነት ማስረጃ ይሰጠኝ ጥያቄ ከወዲሁ ውድቅ ለማድረግ የሚያስችል አይደለም፡፡ በመሆኑም የስር የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ጉዳዩን በማስረጃ ሳያጣራ የወራሽነት ደረጃቸው ተገልጾ የወራሽነት የምስክር ወረቀት እንዲሰጣቸው አመልካቹ ያቀረቡትን አቤቱታ ከወዲሁ ውድቅ በማድረግ የሰጠው እና በከተማው የበላይ ፍርድ ቤቶች ተቀባይነት ያገኘው ትዕዛዝ ከላይ የተጠቀሱትን የውርስ ሕግ ድንጋጌዎች መሰረት ያደረገ ባለመሆኑ ሕጋዊ ተቀባይነት ሊሰጠው የሚቸል ሆኖ አልተገኘም፡፡

ሲጠቃለል አቤቱታ የቀረበበት ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት እና ሊታረም የሚገባው በመሆኑ የሚከተለው ውሳኔ ተሰጥቶአል፡፡

ው ሳ ኔ

1. በአዲስ አበባ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 07905 በ17/12/2008 ዓ.ም. ተሰጥቶ በከተማው ፍርድ ቤቶች ይግባኝ ሰሚ እና ሰበር ችሎቶች እንደቅደም ተከተሉ በመዝገብ ቁጥር 25804 በ03/01/2009 ዓ.ም. እና በመዝገብ ቁጥር 25845 በ12/01/2009 ዓ.ም. በትዕዛዝ የጸናው ትዕዛዝ በፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 348 (1) መሰረት ተሽሮአል፡፡
2. ከላይ በፍርዱ ክፍል በተገለጸው መሰረት አመልካቹ ያቀረቡትን አቤቱታ አስተናግዶ በማስረጃ ካጣራ በኋላ ተገቢውን ውሳኔ ይሰጥበት ዘንድ ጉዳዩ ለአዲስ አበባ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት እንዲመለስ በፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 341 (1) መሰረት ወስነናል፡፡
3. የውሳኔው ቅጂ ተገቢውን መፈጸም ያስችለው ዘንድ ለአዲስ አበባ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት፣እንዲያውቁት ደግሞ ለከተማው ፍርድ ቤቶች ይግባኝ ሰሚ እና ሰበር ችሎቶች ይላክ፡፡
4. ውሳኔ ያገኘ ስለሆነ መዝገቡ ተዘግቶአል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፌርማ አለበት

እ/ጋ

ቤተሰብ

የሰ/መ/ቁ. 130957

ታህሳስ 24 ቀን 2009 ዓ.ም

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

መስጠፉ አህመድ

አብርሃ መሰለ

አብዬ ካሳሁን

እትመት አሰፋ

አመልካች፡- ወ/ሮ አንሻ ሰይድ

ተጠሪዎች፡- 1. ሸህ ሁሴን አደም

2. ወ/ሮ ፋጡማ ሰይድ

3. ወ/ሮ ዘይባ ኢብራሂም

መዝገቡን መርምረን የሚከተውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳይ የቀረበው አመልካች የስር ፍርድ ቤቶች የሰጡት ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት ያቀረቡትን የሰበር አቤቱታ አጣርቶ ለመወሰን ነው፡፡

ክርክሩ በመጀመሪያ የታየው በኮምቦልቻ ከተማ አስተዳደር ወረዳ ፍርድ ቤት ነው፡፡ በወረዳ ፍርድ ቤት አመልካች ከሳሽ 1ኛ ተጠሪ ተከሳሽ 2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች ደግሞ ጣልቃ ገብ በመሆን ተከራክረዋል፡፡

አመልካች ከ1ኛ ተጠሪ ጋር በ1991 ዓ.ም ጋብቻ መስርተን ስንኖር 2 ልጆች የወለደን እና የጋራ ሀብት በኮምቦልቻ ከተማ ቀበሌ 01 ክልል ውስጥ የሚገኝ በ175 ካ/ሜትር ቦታ ላይ ያረፈ መኖሪያ ቤት አፍርተናል፡፡ ስለሆነም ጋብቻው እንዲፈርስ፤ የልጅ ቀለብ እንዲቆረጥ የጋራ ሀብት የሆነውን ቤት የድርሻዬን እንዲያካፍለኝ እንዲሁም የልጅ ቀለብ እንዲሰጠኝ በማለት ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡ 1ኛ ተጠሪ ለክሱ የሰጡት መልስ ከአመልካች ጋር ጋብቻ የፈፀመን ቢሆንም ለ3 ወር ያክል አንድ ላይ አብረን አልኖርንም በ1996 ዓ.ም በሀገር ባህል ተለያይተናል፡፡ በ1993 ዓ.ም ፋጡማ ሰይድ የምትባል አግብቼ ሶስት ልጆች ወልጄ እገኛለሁ፡፡ ቤቱም የሰራሁትም ከአመልካች ጋር ተለያይቼ 2ኛ ተጠሪን ከአገባሁ በኋላ ነው፡፡ ልጆችን በተመለከተ መሀመድ ሁሴን ልጄ ሲሆን ሱመያ ሁሴን ግን ልጄ አይደለችም በማለት ተከራክረዋል፡፡

የስር ጣልቃ ገቦች የአሁን 2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች በኩል የተሰጠ መልስ ደግሞ የ1ኛ ተጠሪ ሚስቶች እኛ እንጂ አመልካች አይደለችም፡፡ ቤቱም የተሰራው በእኛ ጥረት እንጂ አመልካች ለቤቱ ግንባታ ውስጥ ተሳትፎ የላትም በማለት ተከራክረዋል፡፡

ጉዳዩን በመጀመሪያ የተመለከተው ፍርድ ቤትም የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማና ማስረጃ ከመዘነ በኋላ 2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች የ1ኛ ተጠሪ ሚስቶች ናቸው፤ ቤቱ በተጠሪዎች የተሰራ በመሆኑ አመልካች ልትካፈል አይገባም ስለሆነም ግማሹ የ1ኛ ተጠሪ ሲሆን ግማሹን ደግሞ ጣልቃ ገቦች ለሁለት እኩል ይካፈሉ በማለት ወስኗል፡፡

አመልካች ይህንን ውሳኔ በመቃወም ለደቡብ ወሎ ዞን አስተዳደር ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ ያቀረቡ ቢሆንም ተቀባይነት አላገኘም፡፡ በመቀጠል አመልካች አቤቱታቸው ለክልሉ ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ቅሬታ አቅርበዋል፡፡ ፍርድ ቤቱም የግራ ቀኙ ክርክር ከሰማና ከመረመረ በኋላ የስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ በማሻሻል አመልካች በአከራካሪው ቤት የመካፈል መብት አላት በማለት በ1ኛ ተጠሪ ግማሽ ድርሻ ላይ አመልካች ግማሽ ድርሻ አላት፤ቀሪው የስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ ይፀናል ሲል ወስኗል፡፡

የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ የስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡ አመልካች ሐምሌ 25 ቀን 2008 ዓ.ም በፃፉት አቤቱታ በስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስሕተት ተፈጽሟል የሚሉባቸውን ምክንያቶችን ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ በሰበር ችሎቱ ሊታይ ይገባዋል በመባሉ ተጠሪዎች መልስ እንዲሰጡበት በታዘዘው መሰረት መስከረም 27 ቀን 2009 ዓ.ም የተፃፈ መልስ አቅርበዋል፡፡ አመልካችም አቤቱታቸው በማጠናከር የመልስ መልስ በመስጠት ተከራክረዋል፡፡ የጉዳዩ አመጣጥ ባጭሩ ከላይ እንደተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የሰበር አቤቱታ ከቀረበበት ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው የሕግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡

አመልካች በ1991 ዓ.ም ከሁሉም በፊት ከ1ኛ ተጠሪ ትዳር የመሰረቱ ሲሆን የነበረው ጋብቻ በፍቺ የፈረሰው በቀን 21/3/2008 ዓ.ም ነው፡፡ ሌሎቹ 2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች ጋብቻ የፈፀሙት ከአመልካች በኋላ ሲሆን 2ኛ ተጠሪ በ1993 ዓ.ም 3ኛ ተጠሪ ደግሞ በ2000 ዓ.ም ነው፡፡ ለክርክር ምክንያት የሆነው ቤት የተሰራው በ2002 ዓ.ም መሆኑን በስር ፍርድ ቤቶች ተረጋግጧል፡፡ ይህ ማለት ቤቱ የተሰራው በጋብቻ ወቅት መሆኑን ነው፡፡ በተጠሪዎች በኩል አመልካች ሚስት አይደለችም፤ለቤቱ ግንባታ አስተዋፅኦ አላደረገችም በማለት ያቀረቡት ክርክር የፍሬ ጉዳዩ የማጣራትና ማስረጃ የመመዘን ስልጣን የተሰጣቸው ያረጋገጡትን በዚህ ደረጃ መነሳቱ ተቀባይነት የለውም፡፡

በጋብቻ ውስጥ የተፈራ ንብረት የባልና ሚስቱ ወይም የተጋቢዎቹ የጋራ ሀብት ሆኖ የሚገመት ስለመሆኑ የቤተሰብ ህጉ ያስገነዝባል፡፡ የጋራ ሀብት የሚያሰኘው በተጋቢዎች ከጋራ ጥረት ወይም

በአንደኛው ተጋቢ የግል ንብረትም የተፈራ ሲሆን እንደሚችልና በአንደኛው ተጋቢ ስም ተመዝግቦ ቢሆንም እንኳ በጋብቻ ውስጥ የተፈራ መሆኑ ከተረጋጋጠ እና በተለየ ሁኔታ ህጉ ባስቀመጠው አግባብ አንደኛው ተጋቢ የግል መሆኑን ካላስረዳ ጭምር መሆኑን የአብክመ ቤተሰብ ህግአንቀጽ 73/1/ እና 74/1/ ድንጋጌዎች መገንዘብ ይቻላል፡፡ በጋብቻ ወቅት የተፈራ መሆኑ ከመረጋገጡ በተጨማሪ ቤቱ በሚሰራበት ወቅት የሁለም ተሳትፎ የነበራቸው መሆኑን ከስር መዝገብ ተገንዝበናል፡፡ በዚህ ሁኔታ የተፈራ ንብረት እኩል መብት እያላቸው የአንደኛው ድርሻ ከሌላው ወገን ድርሻ በተለየ ሁኔታ የተረጋገጠ ሳይኖር የሚያንስበት ህጋዊ የሆነ ምክንያት የለም፡፡ በአመልካች በኩል ቤቱ አመልካችና 1ኛ ተጠሪ እኩል እንድኾፈል ተደርጎ 2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች ከ1ኛ ተጠሪ ድርሻ እንዲካፈሉ በማለት ያቀረቡት አቤቱታ ተቀባይነት የለውም ብለናል፡፡ ከላይ እንደተገለፀው አከራካሪው ቤት የተፈራው የሁሉም ጋብቻ ፀንቶ በነበረበትና የሁሉም ተሳትፎ የነበራቸው መሆኑን በስር ፍርድ ቤቶች ተረጋግጧል፡፡ ስለሆነም እኩል መብት ያላቸው በመሆኑ ክፍፍሉ በተመለከተ እያንዳንዳቸው ከቤቱ $^{1}/_{4}$ኛ ድርሻ አላቸው፡፡ የወረዳ ፍርድ ቤት ግማሹ የ1ኛ ተጠሪ ሲሆን ግማሹ ደግሞ 2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች እኩል እንዲካፈሉ በማለት የሰጠውን ውሳኔ የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት በማሻሻል በ1ኛ ተጠሪ ግማሽ ድርሻ ላይ አመልካች ግማሽ ድርሻ አላት በማለት የተሰጠው ውሳኔ በውጤት ደረጃ አመልካችና ተጠሪዎች እኩል እንዲካፈሉ የሚያደርግ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

በመሆኑም በክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት አመልካች ከ1ኛ ተጠሪ ድርሻ ላይ ግማሽ ድርሻ አላት ተብሎ መወሰኑ በውጤት ደረጃ ሲታይ መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ሆኖ አልተገኘም፡፡ ስለሆነም ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

<u>ውሳኔ</u>

1. የአብክመ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ. 03-13288 ግንቦት 3 ቀን 2008 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ ውጤቱ በፍ/ብ/ስ/ስ/ሕ/ቁ.348/1/ መሰረት ፀንቷል፡፡
2. አዋሳኝ ተጠቅሶ ክስ በቀረበበት ቤት ላይ አመልካች እና ተጠሪዎች እኩል እንዲካፈሉ ብለናል፡፡
3. በሌሎች ጉዳይ የተሰጠው ውሳኔ ክፍል አልተነካም፡፡
4. በዚህ ችሎት ለተደረገው ወጭ እና ኪሳራ የግራ ቀኙን ተከራካሪ ወገኖች የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የሰ/መ/ቁ.199906

ጥቅምት 5 ቀን 2014 ዓ/ም

ዳኞች፡- ተፈሪ ገብሩ (ዶ/ር)

ቀነአ ቂጣታ

ፈይሳ ወርቁ

ደጀኔ አያንሳ

ብርቅነሽ እሱባለው

አመልካች፡- ከበደ ተፈራ - አልቀረቡም

ተጠሪዎች፡- 1ኛ. መሬማ እሸቱ
2ኛ. ጸጋ ተፈራ
3ኛ. የማነ ገ/ክርስቶስ
} የ2ኛ ተጠሪ ወኪል ታደሰ ሁሴን እና 3ኛ ተጠሪ ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

የሰበር አቤቱታው የቀረበው አመልካች በቀን 16/04/2013 ዓ.ም በተጻፈ አቤቱታ የደሴ ከተማ ነክ ጉዳዮች የመ/ደ/ፍ/ቤት በመ/ቁ 29169 በቀን 08/07/2012 ዓ.ም፤ የደሴ ከተማ ነክ ጉዳዮች ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት በመ/ቁ 1407 በቀን 17/02/2013 ዓ.ም እንዲሁም የአ/ብ/ክ/መ ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ በመ/ቁ 0330451 በቀን 02/04/2013 ዓ.ም የሰጡት ውሳኔና ትዕዛዝ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ይታረምልኝ በማለት ስለጠየቁ ነው፡፡ ክርክሩ በደሴ ከተማ ነክ ጉዳዮች የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ሲጀመር የአሁን አመልካች መልስ ሰጭ፤ የአሁን ተጠሪዎች ደግሞ አመልካች ነበሩ፡፡

ከመዝገቡ መረዳት እንደሚቻለው የአሁን ተጠሪዎች ባቀረቡት ክስ የሚች አቶ ተፈራ መልካ ወራሽ መሆናቸውን ገልፀው ተከሳሽ (የአሁን አመልካች) የእኔ የሚለው ቤተሰብ እና አሳዳጊ ስላልነበረው ከህጻንነቱ ጀምሮ ሚች አቶ ተፈራ መልካ በበጎ አድራጊነት መንፈስ ተቀብሎ በቤት ውስጥ ከልጆቹ ጋር ስላሳደገው ብቻ እስካሁን ድረስ በአካባቢው ሰው ከበደ ተፈራ እየተባለ የሚጠራ ቢሆንም የሚች ልጅ አይደለም፤ ከአብራኩም አይወለድም፤ የተጠሪው ትክክለኛ ስሙ ከበደ ዳምጠው ነው፤ ስለሆነም ተከሳሽ ከፍ/ቤቱ በመ/ቁ 29169 የወሰደው የወራሽነት ሰርተፍኬት ማስረጃ እንዲሰረዝልን በማለት ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡

የአሁን አመልካች በበኩላቸው በቀን 11/06/2012 ዓ.ም በሰጡት መልስ ከሚች አብራክ የተወለደ ልጅ አይደለም የሚለው አቤቱታ እውነት ነው፤ የሚካድም አይደለም፤ ይሁን እንጂ ከሚች በመወለድ የተገኘሁ ልጅ ነኝ የሚል አቤቱታ አቅርቤ የስጋ ልጅነት ማስረጃ አላወጣሁም፤በዚህ ረገድ የቀረበው ክስ ሀሰት ነው፤ ከሳሾች በክሳቸው ላይ በግልጽ እንዳመኑት ከክሱ ጋር ተያይዞ የቀረበው የህጋዊ የጉዲፈቻ ውል መሰረት ሚች ከመንግስት ጋር ባደረጉት ስምምነት ከሆስፒታል ተቀብለው በህግ ልጅነት ያሳደጉኝ የጉዲፈቻ ልጅ ነኝ፡፡ በህጋዊ መንገድ የሚች የጉዲፈቻ ልጅ መሆኔ ከታመነ በፍ/ህ/ቁ 836 ድንጋጌ መሰረት ህጋዊ ልጅ (የጉዲፈቻ) ልጅ የአሳዳጊው ህጋዊ ወራሽ እንደሆነ እና በውርስ ድርሻ ክፍፍልም ላይ ምንም አይነት ልዩነት እንደማይደረግበት የተደነገገ በመሆኑ እንደ ሚች ተወላጅ የሚቆጠር ነው እንዲባልልኝ እና የወራሽነት ምስክር ወረቀቱ ሊሻር አይገባም ተብሎ እንዲወሰንልኝ በማለት ተከራክረዋል፡፡

ጉዳዩ በዚህ መልኩ የቀረበለት የስር ፍርድ ቤት ክርክሩንና ማስረጃ ከሰማ በኋላ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡ በሰጠው ውሳኔ በግራ ቀኙ የጋራ ማስረጃ ይሆናል የተባለው የሰነድ ማስረጃ ሲታይ ለሚች አቶ ተፈራ መልካ በቁጥር 61/58 በቀን ህዳር 7/1958 ዓ.ም በደሴ ማዘጋጃ ቤት በኩል የተጻፈ ሲሆን እናቱ የሞተችበትና ሌላም የቅርብ ዘመድ አጥቶ ለጊዜው በሆስፒታል የሚገኘውን ከበደ ዳምጠው የተባለውን ልጅ ወስደው ለማሳደግ ፈቃደኛ ስለሆኑ ለሌሎች በጎ አድራጊዎች ተቀዳሚ ምሳሌ ያሳዩ መሆኑን እና ልጁንም በማዘጋጃ ቤቱ አማካኝነት መረከባቸውን ማስረጃ ይሆን ዘንድ ይህን ደብዳቤ ከምስጋና ጋር እናቀርብልዎታለን የሚል ነው፡፡ ይህ በበጎ አድራጊነታቸው ለሚች ተፈራ መልካ የተሰጣቸው የምስጋና ደብዳቤ ከፍ/ህጉ እና ከክልሉ የቤተሰብ ህግ እንዲሁም በፌደራል የቤተሰብ ህግ የጉዲፈቻ ልጅነት የህግ ድንጋጌዎች አንጻር ሲታይ የጉዲፈቻ ልጅነት ሊያስገኙ የሚችሉ የህጉን ሁኔታዎች የማያሟላ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ ስለሆነም ተከሳሽ በፍ/ህ/ቁ 836 መሰረት የሚች የህግ ልጅ እና ወራሽ ለመሆን የሚያስችለው በፍ/ቤት የጸደቀ የጉዲፈቻ ልጅነት የውል ስምምነት ማስረጃ በሌለበት ሁኔታ ከዚሁ ፍ/ቤት ህጋዊ ልጅ ነኝ በማለት በመ/ቁ 29169/012 በቀን 21/02/2012 ዓ.ም የተሰጠው የወራሽነት ሰርተፍኬት ማስረጃ ተገቢ ሆኖ አልተገኘም፡፡ ጉዳዩን በምስክር ማረጋገጥ የማይቻል በመሆኑም ምስክር መሰማቱ አስፈላጊ አይደለም፡፡ ስለሆነም ተከሳሽ የወሰደው የወራሽነት ሰርተፍኬት ማስረጃ አላግባብ ሆኖ ስለተገኘ በፍ/ህ/ቁ 998(1) መሰረት ተሰርዟል፤ ማስረጃውን ሊመልስ ይገባል በማለት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት አመልካች ቅሬታቸውን ለደሴ ከተማ ነክ ጉዳዮች ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት እንዲሁም ለአ/ብ/ክ/መ ጠ/ፍ/ቤት ሰበር አጣሪ ችሎት ቢያቀርቡም ተቀባይነት የሰበር አቤቱታው ለዚህ ፍርድ ቤት የቀረበው በዚህ ነው፡፡

አመልካች በቀን 16/04/2013 ዓ/ም ባቀረቡት ማመልከቻ በስር መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በግልጽ የተጠየቀው ዳኝነት አመልካች የሚች በበጎ አድራጎት መንፈስ ያሳደገው ልጅ ሆኖ ሳለ ተወላጅ ልጅ እንደሆነ አድርጎ ያወጣው የወራሽነት ማስረጃ ይሰረዝልን የሚል ሲሆን በእኔ በኩል የተሰጠው መልስም እርግጥ ነው አመልካች የሚች ተወላጅ ልጅ አይደለሁም እኔም የሚች ተወላጅ ልጅ ነኝ ብዬ ማስረጃ አላወጣሁም ያወጣሁት ማስረጃ የሚች የጉዲፈቻ ልጅ ስለሆንኩ በፍ/ሀ/ቁ 836 መሰረት የሚች ወራሽ ነኝ በሚል ነው፤ የጉዲፈቻ ልጅ መሆኔንም ራሳቸው ባቀረቡት ክስና የሰነድ ማስረጃ አምነው የቀረቡ በመሆኑ የጉዲፈቻ ልጅ እንደ ተወላጅ ልጅ ሊወርስ አይገባም የሚለው ክርክር የህግ መሰረት የሌለው በመሆኑ ውድቅ ይደረግልኝ የሚል ሆኖ ፍ/ቤቱ የሰጠው ውሳኔ በተጠሪዎች ከተጠየቀው ዳኝነትና በሰበር አመልካች ከቀረበው መልስ አንጻር ከክርክሩ አውድ ውጭ በተያዘ ጭብጥ ላይ ተመስርቶ ተከራካሪዎች ባላነሱት መከራከሪያ ተመስርቶ የተሰጠ ውሳኔ ነው፣ የስር ፍ/ቤት በቁጥር 61/58 በቀን ህዳር 17/1958 ዓ.ም ተያይዞ የቀረበውን ማስረጃ በተመለከተ የጉዲፈቻ ማስረጃ ሳሆን የምስጋና ወረቀት ነው ሲል የደረሰበት ድምዳሜና ውድቅ ያደረገበት አግባብ በወቅቱ የነበረውን የመንግስት አሰራር ግምት ውስጥ ያላስገባና የማስረጃውን ይዘትም በአግባቡ ያልመረመረበት ነው፤ በመሰረቱ በህግ በልዩ ሁኔታ በተለየ ማስረጃ እንዲረጋገጥ በህግ የተደነገገ ካልሆነ በቀር አንድ ፍሬ ጉዳይ ልጅነትን ጨምሮ በማናቸውም ማስረጃ ሊረጋገጥ እንደሚችል የፌ/ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ችሎት በቅጽ 10 በመ/ቁ 42569 እና 42648 አስገዳጅ ውሳኔ ሰጥቶበታል፤ ፍ/ቤቱ በጠቅላላው ማስረጃው በፍ/ቤት ስላልጸደቀ አመልካች የሚች የጉዲፈቻ ልጅ አይደለም ሲል የደረሰበት ድምዳሜ በ1958 ዓ.ም የነበረውን አሰራር ግምት ውስጥ ያላስገባና የማስረጃ ምዝገባንና ማጽደቅ አላማ ያላገናዘበ ነው፤ይህንን ማስረጃ የሰጠው አካል ደግሞ በወቅቱ የወሳኝ ኩነት መ/ቤት ባልነበረበት ጊዜ ይህንን ተቋም በመወከል በወቅቱ በነበረው አሰራር መሰረት የሚመለከተው አካል የሰጠው ማስረጃ ነው፤ በመሆኑም የስር ፍ/ቤቶች ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነው ተብሎ እንዲሻርና አመልካች የሚች ተፈራ መልካ የጉዲፈቻ ልጅነት በተጠሪዎች ታምኖ የቀረበና በቀረበው ማስረጃ የተረጋገጠ በመሆኑ አመልካቹ በስር ፍ/ቤት ያገኘው የወራሽነት ማስረጃ ህጋዊ በመሆኑ ሊሰረዝ አይገባም ተብሎ እንዲወሰንልን በማለት ቅሬታቸውን አቅርበዋል፡፡

ቅሬታው በሰበር አጣሪ ችሎት ተመርምሮ የአሁን አመልካች የጉዲፈቻ ልጅ አይደለም ተብሎ በስር ፍ/ቤት የተወሰነበትን አግባብነት ህዳር 27/1958 ዓ.ም ከማዘጋጃ ቤት ከተጻፈው ሰነድ እና አግባብነት ካላቸው የፍትሐብሔር ሕግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ለመመርመር ሲባል ጉዳዩ ለዚህ ሰበር ችሎት እንዲቀርብ እና ተጠሪዎች መልስ እንዲሰጡበት ተደርጓል፡፡

1ኛ እና 2ኛ ተጠሪዎች በቀን 09/06/2013 ዓ.ም ባቀረቡት መልስ አመልካች በአቤቱታው እንደጠቀሰው ሚች ተፈራ መልካ አመልካችን በ1958 ዓ.ም ከተወለደበት ሆስፒታል ወስደው አሳድገውታል፡፡ ይህ የሆነው በወቅቱ የአመልካች እናት በወሊድ ምክንያት በመሞታቸው ሚች ተፈራ

መልካ ለጽድቅ (ለሞራል) ሲሉ ህጻኑን በነጻ ፈቃዳቸው ወስደው አሳድገዋል፡፡ ይህን በማድረጋቸውም የደሴ ከተማ ማዘጋጃ ቤት የምስጋና ወረቀት በህዳ 27/1958 ኣ.ም በስማቸው አዘጋጅቶ ሰጥቷቸዋል፡፡ ይህ ሰነድ በፍ/ህግ ሆነ በተሻሻለው የፌደራል ቤተሰብ ህግ ሲመዘን የጉዲፈቻ ልጅነት መፈጠርን (መመስረትን) የማረጋገጥ (የማስረዳት) ብቃት የለውም፡፡ ህጉ በግልጽ በጽሁፍ የተደረገ እና በፍ/ቤት (በዳኞች) የጸደቀ የጉዲፈቻ ልጅ ውል (ስምምነት) ከሌለ በቀር የጉዲፈቻ ልጅ ዝምድና አይመሰርትም በማለት ደንግጎ እያለ ከማዘጋጃ ቤት በተሰጠ ተራ የምስጋና ወረቀት የጉዲፈቻ ልጅ ዝምድና ተመስርቷል አያሰኝም፡፡ ሟች አመልካችን ከመልካም ስራ አንጻር አሳድጎ ለቁም ነገር ከማብቃት ባለፈ የጉዲፈቻ ልጅ ሊያደርጉት ባለመፈለጋቸው ስምምነቱን ሳያደርጉ አልፈዋል፤ ከመሞታቸውም በፊትም ባደረጉት የጸደቀ ኑዛዜ አመልካችን የጉዲፈቻ ልጅ ስለሆነ ካለን ንብረት ይካፈል በማለት ኑዛዜ አላደረጉለትም፡፡ ይህ የሚያስረዳው ሟች የአመልካችን የጉዲፈቻ ልጅነት እስከሞቱበት እለት ያላመኑበት (ያልተቀበሉት) መሆኑን ነው፡፡ ተጠሪዎች ለስር ፍ/ቤት ባቀረቡት የተቃውሞ ክስ ወይም አቤቱታ ላይ አመልካች የሟች የጉዲፈቻ ልጅ ነው በማለት አልተከራከሩም፤ አምነው መልስ አልሰጡም፡፡ ስለሆነም የሰበር ችሎቱ የግራ ቀኙን ክርክር ከስር ፍ/ቤት መዝገብ ጋር በማጣራት የተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የለበትም በማለት እንዲያጸናልን በማለት ተከራክረዋል፡፡ 3ኛ ተጠሪ በበኩላቸው በስር ፍ/ቤቶች የተሰጠው ውሳኔ ህግና ማስረጃን መሰረት ያደረገ መሆኑን በመግለጽ የ1ኛ እና 2ኛ ተጠሪን መልስ በማጠናከር አቅርበዋል፡፡ አመልካችም የመልስ መልስ ሰጥተዋል፡፡

ከፍ ሲል በአጭሩ የገለጽነው የጉዳዩን አመጣጥ ነው፡፡ በበኩላችን የግራ ቀኙን ክርክር ቅሬታ ከቀረበበት ውሳኔ እና ከተገቢው የህጉ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ የተፈጸመ የህግ ስህተት መኖር አለመኖሩን መርምረናል፡፡

እንደመረመርነው ተጠሪዎች ባቀረቡት አቤቱታ ሟች አቶ ተፈራ መልካ በበጎ አድራጊነት መንፈስ ተቀብሎ አመልካችን ስላሳደገው ብቻ ልጅ ሳይሆን ከስር ፍ/ቤቱ የወሰደው የወራሽነት ማስረጃ እንዲሰረዝልን በማለት የጠየቁ ሲሆን አመልካች በበኩላቸው ከሟች አብራክ የተወለዱ ልጅ አለመሆናቸው እንደማያከራክር ገልፀው ከክሱ ጋር ተያይዞ በቀረበው የህጋዊ የጉዲፈቻ ውል መሰረት ሟች ከመንግስት ጋር ባደረጉት ስምምነት ከሆስፒታል ተቀብለው በህግ ልጅነት ያሳደጉኝ የጉዲፈቻ ልጅ ነኝ በማለት ተከራክረዋል፡፡ የስር ፍርድ ቤት ግራቀኙ የጠቀሱትን በቁጥር 61/58 በቀን ህዳር 7/1958 ዓ.ም ከደሴ ማዘጋጃ ቤት የተሰፈውን ማስረጃ ይዘት መርምሮ ማስረጃው በበጎ አድራጊነታቸው ለሟች ተፈራ መልካ የተሰጣቸው የምስጋና ደብዳቤ መሆኑንና ከፍ/ህጉ እና ከክልሉ የቤተሰብ ህግ እንዲሁም በፌደራል የቤተሰብ ህግ አንጻር የጉዲፈቻ ልጅነት ሊያስገኙ የሚችሉ የህጉን ሁኔታዎች የማያሟላ መሆኑን በማረጋገጥ አመልካች ልጅ ነኝ በማለት የወሰዱት ማስረጃ እንዲሰረዝ ወስኗል፡፡

የአመልካች ዋና ቅሬታ የጉዲፈቻ ልጅ መሆኔን ተጠሪዎች ራሳቸው ባቀረቡት ክስና የሰነድ ማስረጃ አምነዋል፤ የስር ፍ/ቤት የሰጠው ውሳኔም በተጠሪዎች ከተጠየቀው ዳኝነትና ከክርክሩ አውድ ውጭ በተያዘ ጭብጥ ላይ የተመሰረተ ነው፤ የስር ፍ/ቤት በቁጥር 61/58 በቀን ህዳር 17/1958 ዓ.ም ተያይዞ የቀረበው ማስረጃ የጉዲፈቻ ማስረጃ ሳይሆን የምስጋና ወረቀት ነው ሲል የደረሰበት ድምዳሜም በወቅቱ (1958 ዓ.ም) የነበረውን አሰራር ግምት ውስጥ ያላስገባ ነው የሚል ነው፡፡

እንደሚታወቀው የ1952 ዓ.ም የፍትሐ ብሔር ህግ በተለይ በቁጥር 2/1952 ዓ.ም የነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከመስከረም 1 ቀን 1953 ዓ.ም ጀምሮ የጸና ሆኖ በስራ ላይ ውሏል፡፡ ይኸው የፍትሐ ብሔር ህግ በቁጥር 804(1) ስር እንደደነገገው የጉዲፈቻ ውል በፍርድ ቤት ካልተረጋገጠ (ዳኞች ካላጸኑት) በስተቀር ውጤት የሌለው፤ አይጸናምም፡፡ ከዚህም ሌላ አሁን ሥራ ላይ ያሉት የአማራ የቤተሰብ ህግ አዋጅ ቁጥር 79/95 እና የፌዴራሉ የቤተሰብ ህግ አዋጅ ቁጥር 213/1992 አንቀጽ 194 እና 205 በተመሳሳይ ጉዲፈቻ ስምምነት ተደርጎበት ፍርድ ቤት ካላፀደቀው በስተቀር ውጤት አይኖረውም በማለት ይደነግጋሉ፡፡

ከፍ ሲል ከተጠቀሰው የህጉ ድንጋጌዎች መገንዘብ የሚቻለው የጉዲፈቻ ልጅነት አለ ይባል ዘንድ የጉዲፈቻ ስምምነት መኖርና ይኸው ስምምነት ለፍርድ ቤት ቀርቦ በዳኞች መጽደቅ እንደሚኖርበት፤ ይህ ካልሆነ ግን በህጉ እይታ ውጤት ያለው የጉዲፈቻ ልጅነት አለ ለማለት እንደማይቻል ነው፡፡ ከዚህም ሌላ መሰል ጉዳይ የህግ ጉዳይ በመሆኑ ፍርድ ቤቱ በራሱ አንስቶ ሊወስንበት አይችልም የሚባል አይደለም፡፡

በተያዘው ጉዳይ ከፍሲል እንደተገለፀው የጉዲፈቻ ልጅ ነኝ በማለት ክርክር ያቀረቡት አመልካች ራሳቸው ናቸው፡፡ ይህን ክርክራቸውን ደግሞ ህጉ በሚጠይቀው አግባብ ማስረዳት ይጠበቅባቸዋል፡፡ በማስረጃነት የጠቀሱት በቁጥር 61/58 በቀን ህዳር 17/1958 ዓ.ም ከማዘጋጃ ቤት ለሚች ተፃፈ የተባለው ሰነድ የጉዲፈቻ ስምምነት መደረጉንና ስምምነቱ ፍርድ ቤት ቀርቦ ተቀባይነት ማግኘቱን እንደማያስረዳ አመልካቹም የሚክዱት አይደለም፡፡ በስር ፍርድ ቤትም በፍሬ ነገር ደረጃ ተረጋግጧል፡፡ ይህ ሆኖ እያለ አመልካች የጉዲፈቻ ልጅ መሆኔ በተጠሪዎች ታምኖልኛል፤ የስር ፍ/ቤት የሰጠው ውሳኔም ከክርክሩ አውድ ውጭ ነው፤ በፍርድ ቤት የፀደቀ የጉዲፈቻ ስምምነት እንዲኖር መጠየቁና የማዘጋጃ ቤቱ በ1958 የጻፈው ደብዳቤ ውድቅ መደረጉ በወቅቱ የነበረውን አሰራር ግምት ውስጥ ያላስገባ ነው በሚል የሚያቀርቡት ክርክር ግራ ቀኙ በስር ፍርድ ቤት ያደረጉትን ክርክር፤ ጉዳዩ የሚመራበትን ስርዓት እና የፀና ጉዲፈቻ ይኖር ዘንድ ሥራ ላይ የነበረው ህግ በግልጽ የሚደነግገውን መሰረት ያደረገ ባለመሆኑ መከራከሪያቸው ተቀባይነት የለውም ብለናል፡፡

በአጠቃላይ አመልካች የሚች አቶ ተፈራ መልካ ልጅ እና ወራሽ ለመሆን የሚያስችላቸው በፍ/ቤት የጸደቀ የጉዲፈቻ ስምምነት ማስረጃ በሌለበት ሁኔታ ህጋዊ ልጅ ነኝ በማለት ከፍርድ ቤት

የወሰዱት የወራሽነት ማስረጃ ተሰርዞ የወሰዱትን ማስረጃ ሊመልሱ ይገባል ተብሎ በስር ፍርድ ቤት መወሰኑ እና ይኸው ውሳኔ በበላይ ፍርድ ቤቶች ተቀባይነት ማግኘቱ ህጉን መሰረት ያደረገ ነው ከሚባል በቀር የሚነቀፍ ባለመሆኑ ተከታዩን ወስነናል፡፡

ው ሣ ኔ

1. የደሴ ከተማ ነክ ጉዳዮች የመ/ደ/ፍ/ቤት በመ/ቁ 29169 በቀን 08/07/2012 ዓ.ም፤ የደሴ ከተማ ነክ ጉዳዮች ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት በመ/ቁ 1407 በቀን 17/02/2013 ዓ.ም እንዲሁም የአ/ብ/ክ/መ ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ በመ/ቁ 0330451 በቀን 02/04/2013 ዓ.ም የሰጡት ውሳኔና ትዕዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 348(1) መሰረት ፀንቷል፡፡

2. በስር ፍርድ ቤት የተጀመረው ክርክር እንዲታገድ በዚህ ፍርድ ቤት ታህሳስ 23/2013 ዓ.ም የተሰጠው የዕግድ ትዕዛዝ ተነስቷል፡፡ ይፃፍ፡፡

3. የሰበር ክርክሩ ያስከተለውን ወጭና ኪሣራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

ማ/አ የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

የሰበር መዝገብ ቁጥር 221097

ጥቅምት 1 ቀን 2015 ዓ/ም

ዳኞች፡- ተፈሪ ገብሩ (ዶ/ር)

ቀነዓ ቂጣታ

ፈይሳ ወርቁ

ደጀኔ አያንሳ

ብርቅነሽ እሱባለው

አመልካች፡- አቶ ሙሉጌታ ዘውዱ፡- ከጠበቃ ሲሳይ ወርቅነህ ጋር ቀርቧል

ተጠሪዎች፡- 1ኛ. ወ/ሮ ሄለን ደረሰ፡- ከጠበቃ የኋላወርቅ ተከተለው ጋር ቀርቧል

2ኛ. ወ/ሮ ፍቅርተ ደረሰ፡- ጠበቃ መስፍን ጫኔ - ቀርቧል

3ኛ. በየካ ክፍለ ከተማ ወረዳ 8 አስተዳደር ወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ ቅ/ጽ/ቤት

4ኛ. በየካ ክፍለ ከተማ ወረዳ 8 ቤቶች አስተዳደር ጽ/ቤት } አልቀረቡም

ለምርመራ ተቀጥሮ የነበረው መዝገብ ተመርምሮ ቀጣዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍርድ

አከራካሪው ሱቅ በሥጦታ የተገኘ ሳይሆን ከ4ኛ ተጠሪ አመልካች እና 1ኛ ተጠሪ በኪራይ ያገኙት ሆኖእያለ፤ የስጦታ ውል ተብሎ የቀረበው ሰነድም በቤቱ ማኅደር ውስጥ የሌለ ፤ ውሉም በሕግ የተመለከተውን ፎርም የማያሟላ በሰነዶች ማረጋገጫ እና ምዝገባ ጽ/ቤት ያልተደረገ በተንኮል የተዘጋጀ የመንደር ውል በመሆኑ ዋጋ የሌለው መሆኑን ፤ ዋጋ አለው ቢባል እንኳን አመልካች እና 1ኛ ተጠሪ በጋብቻ ውስጥ እያሉ የባልና ሚስት የጋራ በሆነ ንብረት ላይ 1ኛ ተጠሪ ለብቻቸው ያደረጉት የስጦታ ውሉ የማይፀና መሆኑና የስጦታ ውሉም ለ1ኛ ተጠሪ በግል የተደረገላቸው መሆኑን ስለማይገልጽ በሕጉ የጋራ ንብረት እንደሆነ ይገመታል በማለት አመልካች ያቀረቡት ክርክር በጭብጥነት ሳይመረመር ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ውሳኔን መሻሩ የቤተሰብ ሕጉን አንቀጽ 63 እና የሕገ - መንግስቱን አንቀጽ 34(1) የሚቃረንና 1ኛ ተጠሪ ጋብቻ ከመፈፀማቸው በፊት ያወጡትን ያላገባ የምስክር ወረቀት በሀሰተኛ የቃለ - መሐላ አቤቱታ በማሳደስ የፈፀሙት ድርጊት ሕገ - ወጥነትን የሚያበረታታ መሆኑን፤ የሥጦታ ውሉ በአራት ምስክሮች ፊት ባለመነበቡ፤ ውሉን የፈረሙት ምስክሮችም ሁለት ብቻ በመሆናቸው እና ወ/ሮ ሃና ታደሰ የሥጦታ ውሉን በፈረሙበት ጊዜ በቤቱ ላይ መብት የነበራቸው መሆኑን የሚያረጋግጥ ማስረጃ ባለመቅረቡ ውሉ ፈራሽ ነው በማለት አመልካች ያቀረቡት ክርክር ታልፎ ሱቁ የ1ኛ ተጠሪ የግል ንብረት ነው ተብሎ መወሰኑ ፤ 2ኛ ተጠሪም ጋብቻ የፈፀመችው እህታቸው የሆነችው 1ኛ ተጠሪ ጋብቻ ፈጽማም እንደማታውቅ ያላገባ የምስክር ወረቀት አውጥታ ሱቁን ስትሸጥላቸው የቅን ልቦና ገዥ ናቸው ተብለው የአዲስ አበባ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ

ፍርድ ቤት የሰጠው ውሳኔ በይግባኝ ሰሚው ችሎት መሻሩ እና የሰበር ሰሚ ችሎቱም ውሳኔውን ማጽናቱ መሠረታዊ የሕግ ስህተት በመሆኑ ስህተቱ ታርሞ የአዲስ አበባ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የሰጠው ውሳኔ እንዲፀናላቸው አመልካች የካቲት 8 ቀን 2014 ዓ/ም ባቀረቡት የሰበር አቤቱታ መነሻነት መዝገቡ ለችሎት ቀርቧል፡፡

ጉዳዩ የባልና ሚስት የጋብቻ ፍቺን ተከትሎ የቀረበ የንብረት ክርክርን የሚመለከት ሲሆን፤ ለሰበር አቤቱታ ምክንያት የሆነውን የመንግስት ሱቅ አመልካች እና 1ኛ ተጠሪ በትዳር ውስጥ እያሉ በኪራይ የተገኘ ነው በማለት አመልካች ከሌሎች የባልና ሚስት ንብረቶች ጋር ያቀረቡትን የክፍፍል ጥያቄ የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ጉዳዩን የማየት ሥልጣን የፍርድ ቤት አይደለም በማለቱ አመልካች በተጠሪዎች ላይ በአዲስ አበባ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የካ ምድብ ችሎት ባቀረቡት ክስ፤ በየካ ክፍለ ከተማ ወረዳ 8 ቁጥሩ 249/124 የሆነው የቀበሌ ንግድ ሱቅ አመልካች እና 1ኛ ተጠሪ ጋር የተከራዩ ቢሆንም የግራ ቀኙ ጋብቻ ታህሳስ 29 ቀን 2006 ዓ/ም በፍቺ ውሳኔ መፍረሱን ገልፀው 1ኛ ተጠሪ 3ኛ ተጠሪን በማሳሳት ታህሳስ 4 ቀን 2011 ዓ/ም ያላገባ የምስክር ወረቀት በመውሰድ የጋራቸው የሆነውን የቀበሌ ንግድ ሱቅ ለ2ኛ ተጠሪ በሰነዶች እና ምዝገባ ጽ/ቤት በተደረገ የሽያጭ ውል ያስተላለፉ በመሆኑ፤ 4ኛ ተጠሪ የኪራይ ውሉን እንዲሁም 3ኛ ተጠሪም ያለአግባብ የሰጠውን ያላገባ የምስክር ወረቀት እንዲሰርዝ አቤቱታ ቢያቀርቡም ባለመሰረዙ፤ በተጭበረበረ መንገድ የወጣው ያላገባ የምስክር ወረቀት እንዲሁም 1ኛ እና 2ኛ ተጠሪዎች ያደረጉት ጋራ ንብረት ሽያጭ ውል ተሰርዞ 3ኛ ተጠሪ ሱቁን አካፍሎ ከአመልካች እና 1ኛ ተጠሪ ጋር የኪራይ ውል እንዲያደርግ ከወጪ እና ኪሳራ ጋር እንዲወሰንላቸው ጠይቀዋል፡፡

1ኛ ተጠሪም በመልሳቸው አመልካች ያቀረቡት ክስ አስተዳደራዊ ጉዳይ በመሆኑ ፍርድ ቤት ጉዳዩን ለማየት ሥልጣን የሌለው መሆኑን፤ ክሱ በይርጋ የሚታገድ መሆኑ እና ጉዳዩ ውሳኔ ያገኘ መሆኑን በመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያነት አንስተው በፍሬ ነገር ክርክራቸውም የቀበሌ ንግድ ቤቱ የወ/ሮ ሎሚናት ወ/ዓዲቅ የነበረ ሲሆን እሳቸው የ1ኛ ተጠሪ እህት ለነበሩት ወ/ሮ ሃና ታደሰ አስተላልፈው ከወ/ሮ ሃና ታደሰ በስጦታ ያገኙት የግል ንብረት በመሆኑና 1ኛ ተጠሪ ከአመልካች ጋር የነበራቸው ትዳር ታህሳስ 4 ቀን 2011 ዓ/ም ከፈረሰ በኋላ ያላገባ የምስክር ወረቀት አውጥተው ከ2ኛ ተጠሪ ጋር ያደረጉት ሕጋዊ የሱቅ ሽያጭ ውል የሚፈርስበት ምክንያት ባለመኖሩ አመልካች ያቀረቡት ክስ ውድቅ ሊሆን ይገባል በማለት ተከራክረዋል፡፡ 2ኛ ተጠሪም ከ1ኛ ተጠሪ ጋር ተመሳሳይ ይዘት ያለው መቃወሚያን በማስቀድም በፍሬ ነገር መልሳቸው ሱቁን የገዙት 1ኛ ተጠሪ ትዳር የሌላት መሆኑ ተረጋግጦ በመሆኑ ታህሳስ 8 ቀን 2011 ዓ/ም የተደረገው የሽያጭ ውል የሚፈርስበት ምክንያት የለም የሚል ክርክር አቅርበዋል፡፡ በአመልካች እና 1ኛ ተጠሪ መካከል የነበረው ትዳር ህዳር 25 ቀን 2011 ዓ/ም ከመፍረሱ በፊት 2ኛ ተጠሪ ህዳር 19 ቀን 2011 ዓ/ም ያላገባ የምስክር ወረቀት እንዲሰጣቸው በቃለ መሃላ የተደገፈ አቤቱታ አቅርበው ትዳራቸው ከፈረሰ በኋላ ታህሳስ 4 ቀን 2011 ዓ/ም

የወሰዱትን ምስክር ወረቀት እንዲመልሱ በደብዳቤ የተገለፀላቸው መሆኑ ፤ ክርክር ያስነሳው የቀበሌ ንግድ ቤት የኪራይ ውሉ በ1ኛ ተጠሪ ስም ብቻ በመሆኑና ያላገባ የምስክር ወረቀት በማቅረባቸው በመመሪያ ቁጥር 4/2009 አንቀጽ 24 መሠረት የተከራይነት መብቱ ለ2ኛ ተጠሪ የተላለፈ በመሆኑ 3ኛ እና 4ኛ ተጠሪዎች መመሪያው ከሚፈቅደው ውጭ የሰጡት አገልግሎት ባለመኖሩ እና ሥራቸውን በአግባቡ ስለሰሩ ልንከሰስ አይገባም በማለት መልስ ሰጥተዋል፡፡

ፍርድ ቤቱም የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያውን ውድቅ በማድረግ ፤ የግራ ቀኙን ክርክር እና ማስረጃ ሰምቶ መዝገቡን እንደመረምረው 1ኛ ተጠሪ በትዳር ውስጥ እያለች የቀበሌ ንግድ ቤት በስጦታ ውል አግኝታ በትዳር ውስጥ እያለች የኪራይ ውል የተዋዋለች መሆኑ፤ የግራ ቀኙ ትዳር ከመፍረሱ ስድስት ቀን አስቀድሞ ያላገባ የምስክር ወረቀት ለማግኘት የቃለ መሃላ አቤቱታ አቅርባ ታህሳስ 4 ቀን 2011 ዓ/ም ያላገባ የምስክር ወረቀት የወሰደች መሆኑ የተረጋገጠ ፍሬ ነገር መሆኑን ገልጾ ፤ 1ኛ ተጠሪ የፍቺ ውሳኔ ከመሰጠቱ ስድስት ቀን አስቀድሞ ያላገባ የምስክር ወረቀት ለማግኘት ማመልከቻ አቅርባ ከሕግ ውጭ የወሰደችውን ያለላባ የምስክር ወረቀት በመጠቀም ታህሳስ 8 ቀን 2011 ዓ/ም በተደረገ የሽያጭ ውል ለ2ኛ ተጠሪ ሱቁን ማስተላለፏን ከቀረበው የሰነድ ማስረጃ ግንዛቤ መወሰዱን ግልፃ ፤ 3ኛ ተጠሪ ታህሳስ 4 ቀን 2011 ዓ/ም ለ1ኛ ተጠሪ የሰጠው ያላገባ የምስክር ወረቀት ሕጉን ጠብቆ የተሰጠ ባለመሆኑ እንዲሰረዝ፤ 1ኛ ተጠሪ የኪራይ ውሉን የተዋዋለችው በ2008 ዓ/ም ከአመልካች ጋር በትዳር ውስጥ እያለች ሆኖ የአመልካች እና 1ኛ ተጠሪ ትዳር የፈረሰው ህዳር 25 ቀን 2011 ዓ/ም በመሆኑ በመመሪያ ቁጥር 5/2011 አንቀጽ 40(1) መሠረት የአመልካችና 1ኛ ተጠሪ ትዳር ከፈረሰ በኋላ ክርክር የተነሳበት ቁጥሩ 249/124 የሆነው የቀበሌ ንግድ ሱቅ ለአመልካች እና ለ1ኛ ተጠሪ የሚካፈል በመሆኑ ከሕጉ ወጭ የሆነውን ያላገባ የምስክር ወረቀት መሠረት በማድረግ በ1ኛ ተጠሪ እና 2ኛ ተጠሪ መካከል የተደረገው ውል ህጋዊ ባለመሆኑ 4ኛ ተጠሪ ክርክር የተነሳበትን የቀበሌ ንግድ ቤት ለአመልካች እና 1ኛ ተጠሪ አካፍሎ የኪራይ ውል ሊይዝ ይገባል በማለት ወስኗል፡፡

ይህን ውሳኔ በመቃወም 1ኛ ተጠሪ የንግድ መደብሩ የባልና ሚስቱ የጋራ ሳይሆን የግል ንብረታቸው ለመሆኑ በማስረጃ ተረጋግጦ እያለ የንግድ መደብሩ የሽያጭ ውል ሕጋዊ አይደለም መባሉ፤ 2ኛ ተጠሪ ሱቁን የገዙት በአመልካች እና 1ኛ ተጠሪ መካከል የነበረው ጋብቻ መፍረሱንና የሽያጭ ውሉ በተፈጸመበት ጊዜ ጋብቻ የሌላትና ያላገባ የምስክር ወረቀት ያወጣች መሆኑ እንዲሁም የንግድ መደብሩን 1ኛ ተጠሪ በግል ከእናቷ የተሰጣት መሆኑን በማረጋገጥ ከአንድ ጠንቃቃ እና ምክንያታዊ ገዥ የሚጠበቀውን ጥንቃቄ በማድረግ በቅን ልቦና በሰነዶች ማረጋገጫ ምዝገባ ጽ/ቤት የተደረገው የመደብር ግዥ ውል እንዲፈረስ መወሰኑ አግባብ አይደለም በማለት 1ኛ እና 2ኛ ተጠሪዎች በተለያየ መዝገብ ያቀረቡትን የይግባኝ ቅሬታ አጣምሮ የተመለከተው የአዲስ አበባ ከተማ ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ሁለተኛ ይግባኝ ሰሚው ችሎት፤ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ለውሳኔ መሠረት ያደረገው አመልካች እና 1ኛ ተጠሪ በትዳር ውስጥ በነበሩበት ጊዜ ክርክር የተነሳበት የቀበሌ ንግድ ቤት በ2008

ዓ/ም 1ኛ ተጠሪ የኪራይ ውል የተዋዋሉ በመሆኑ እና ትዳራቸውም የፈረሰው ህዳር 25 ቀን 2011 ዓ/ም በመሆኑ በመመሪያ ቁጥር 5/2011 አንቀጽ 40(1) መሠረት ትዳር በፍቺ ውሳኔ ሲፈርስ ቤቱ እንደሚከፋፈል ስለሚደነግግ በሚል ቢሆንም፤ የንግድ መደብሩን አመልካች እና 1ኛ ተጠሪ በውል ከ3ኛ ተጠሪ ያገኙት ሳይሆን የ1ኛ ተጠሪ እህት የሆኑት ወ/ሮ ሃና ታደሰ ሲጠቀሙበት ቆይተው 1ኛ ተጠሪ በትዳር ውስጥ እያሉ አመልካችን ሳይጨምር በግላቸው በስጦታ ያገኙ መሆኑን ታህሳስ 8 ቀን 2011 ዓ/ም የተደረገ የንግድ ድርጅት የስጦታ ውሉ እንደሚያመለክት እና አመልካች እና 1ኛ ተጠሪ የነበራቸው ትዳር ህዳር 25 ቀን 2011 ዓ/ም ከፈረሰ በኋላ ታህሳስ 8 ቀን 2011 ዓ/ም የንግድ መደብር ሽያጭ ውል በ1ኛ እና 2ኛ ተጠሪዎች መካከል መደረጉን ገልፆ፤ አመልካች ከ1ኛ ተጠሪ ጋር የንግድ መደብሩ ያገኙ መሆኑን ባላስረዱበት የአመልካች እና 1ኛ ተጠሪ ትዳር ከፈረሰ በኋላ የተደረገው የሽያጭ ውል ፈርሶ የንግድ ቤቱን እንዲካፈሉ የሥር ፍርድ ቤት የደረሰበት ድምዳሜ አግባብ አለመሆኑን፤ እንዲሁም 1ኛ ተጠሪ በግል በስጦታ ያገኙት መደብር በትዳር ውስጥ ሆነውም ይሁን ከፍቺ በኋላ በግላቸው እንዳያስተላልፉ የሚከለክላቸው ሕግ ካለመኖሩም በላይ የሽጭ ውሉ የሕግ ጥሰት የተፈፀመበት ነው ቢባል እንኳን 2ኛ ተጠሪ ካላቸው የዝምድና ቅርበት አኳያ በአመልካች እና 1ኛ ተጠሪ መካከል የጋብቻ ፍቺ ማድረጋቸውን ተረድተው ግዥ መፈፀማቸው አንድ ጠንቃቃ ገዥ መፈፀም ያለበትን ጥንቃቄ ማድረጋቸውን ያሳያል በማለት የሥር ፍርድ ቤት ውሳኔን ሽሯል፡፡

አመልካች በውሳኔው ባለመስማማት ባቀረቡት የሰበር አቤቱታ አከራካሪው የንግድ መደብር ለ2ኛ ተጠሪ ከመተላለፉ በፊት የ1ኛ ተጠሪ የግል ንብረት ወይንም የአመልካች እና የ1ኛ ተጠሪ የጋራ ንብረት መሆን አለመሆኑን በጭብጥነት ይዞ የቤቱን ማህዳር በማስቀረብ የመረመረው የከተማው ሰበር ሰሚ ችሎት፡- ለክርክሩ ምክንያት የሆነው ንግድ ቤት የቀድሞ ተከራይ ወ/ሮ ሎሚናት ወ/ዓዲቅ ወ/ጊዮርጊስ መመሪያ ቁጥር 4/2009 ከመውጣቱ በፊት ቤቱን በሽያጭ ለወ/ሮ ሃና ታደሰ አስተላልፈው ከህዳር 4 ቀን 2004 ዓ/ም ጀምሮ በወ/ሮ ሃና ታደሰ በስማቸው የኪራይ ውል ተዋውለው ቤቱን ሲጠቀሙበት ከቆዩ በኋላ ታህሳስ 1 ቀን 2008 ዓ/ም በተፃፈ የንግድ ስጦታ ውል የንግድ ቤቱ (መደብሩ) ለ1ኛ ተጠሪ ብቻ ተላልፎላቸው የኪራይ ውል ተዋውለው ቤቱን ይዘው ሲጠቀሙበት ከቆዩ በኋላ ታህሳስ 8 ቀን 2011 ዓ/ም በተደረገ የንግድ መደብር ሽያጭ ውል ለ2ኛ ተጠሪ ተላልፎ 4ኛ ተጠሪም በወቅቱ በሥራ ላይ በነበረው መመሪያ ቁጥር 4/2009 መሠረት የንግድ ቤቱን የኪራይ ውል ከ1ኛ ተጠሪ ስም ወደ 2ኛ ተጠሪ ስም አዙሮ 2ኛ ተጠሪ እየተጠቀሙበት የሚገኙ መሆኑ መረጋገጡን ጠቅሶ ፤ ለክርክሩ ምክንያት የሆነውን የንግድ ቤት አመልካች እና 1ኛ ተጠሪ የተከራዩት ሳይሆን 1ኛ ተጠሪ በስጦታ ያገኙት የንግድ መደብር መሆኑን፤ አመልካች የንግድ መደብሩን ከ1ኛ ተጠሪ ጋር በጋራ ያገኙ ለመሆኑ ያቀረቡት ክርክርም ሆነ ማስረጃ ባለመኖሩ የንግድ መደብሩ ወደ 2ኛ ተጠሪ ከመተላለፉ በፊት የአመልካች እና የ1ኛ ተጠሪ የጋራ ንብረት ሳይሆን የ1ኛ ተጠሪ የግል ንብረት በመሆኑ፤ 1ኛ ተጠሪ በግል በስጦታ ያገኙትን የንግድ መደብር በጋብቻ ውስጥ ሆነውም ይሁን ከፍቺ በኋላ በህጉ አግባብ በሽያጭ

ማስተለላፍን የማይከለከሉ በመሆኑ የይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት ውሳኔ የሚነቀፍ አይደለም በማለት ወስኗል፡፡

አመልካች የሥር የአዲስ አበባ ከተማ የሰበር ሰሚው እና ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤቶች ውሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሞበታል በማለት ያቀረቡትን በፍርዱ መግቢያ ላይ የተመለከተውን የሰበር አቤቱታ የመረመረው የሰበር አጣሪ ችሎቱ ግራ ቀኙን እያከራከረ ያለው የንግድ ሱቅ አመልካች እና 1ኛ ተጠሪ በጋብቻ ውስጥ እያሉ 1ኛ ተጠሪ ከቀበሌ መከራየታቸው ፤ 1ኛ ተጠሪ ከአመልካች ጋር በትዳር ውስጥ እያሉ 3ኛ ተጠሪን በማሳሳት ያላገባ የምስክር ወረቀት ወስደው አከራካሪውን ሱቅ እህታቸው ለሆኑት 2ኛ ተጠሪ በሽያጭ ማስተላለፋቸውን አረጋግጦ አመልካች እና 1ኛ ተጠሪ እንዲከፋፈሉ በማለት የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የሰጠው ውሳኔ በበላይ ፍርድ ቤቶች የመሻሩን አግባብነት መጣራት አለበት በማለቱ የፍርድ ቤቱ መጥሪ ለተጠሪዎች ድርሶ መልስ ሰጥተዋል፡፡ 1ኛ ተጠሪ በመልሳቸው አከራካሪውን የንግድ መደብር ከመንግስት የተከራዩት ሳይሆን በስጦታ ያገኙት የግል ሀብታቸው መሆኑ በማስረጃ የተረጋገጠ ሲሆን፤ ሱቁን (መደብሩን) ከቀበሌ ተከራይቷል የሚለው የአመልካች ክርክር በማስረጃ አለመረጋገጡን ፤ በወ/ሮ ሃና ታደሰ እና 1ኛ ተጠሪ መካከል የተደረገው የስጦታ ውል በሕጉ የተመለከተውን ፎርማሊት የሚያሟላ ባለመሆኑ አይፀናም የሚለው የአመልካች ክርክር በሥር ፍርድ ቤት ያልተነሳ በመሆኑ በሰበር ደረጃ መነሳቱ ሥነ ሥርዓታዊ አለመሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ ክርክሩ የንግድ መደብር ሽያጭ ውል በመሆኑና በንግድ መደብር ላይ የሚደረገው የስጦታ ውል በጽሑፍ ከመደረጉ በቀር ሌላ የተለየ ፍርማሊትን ስለማይጠይቅ እና የፍትሐ ብሔር ሕጉ ድንጋጌዎችም ለጉዳዩ አግባብነት የሌላቸው መሆኑን ፤ የአመልካች እና 1ኛ ተጠሪ ጋብቻ ህዳር 25 ቀን 2011 ዓ/ም ከፈረሰ በኋላ 1ኛ ተጠሪ ታህሳስ 4 ቀን 2011 ዓ/ም ያላገባ የምስክር ወረቀት ማስረጃ ወስደው ታህሳስ 8 ቀን 2011 ዓ/ም የሽያጭ ውል የፈፀሙ ሲሆን ፤ በቃላ መሃላ የተወሰደ ያላገባ ምስክር ወረቀት ካለመኖሩም በላይ ተወስዷል ቢባል እንኳን ማስረጃውን ከማሰረዝ ባለፈ የግል ንብረታቸው ላይ ተደረገው የሽያጭ ውል ፈርሶ በንብረቱ ላይ ምንም መብት የሌለው ሰው ንብረቱን እንዲካፈል የማደረግ ውጤት የሌለው መሆኑን፤ አመልካች የንግድ መደብሩ በጋራ ተሰጥቶናል የሚል ክርክር በሥር ፍርድ አለመቅረቡ እንደተጠበቀ ሆኖ መደብሩ የ1ኛ ተጠሪ የግል ንብረት መሆኑ፤ የክራይ ውሉም በ1ኛ ተጠሪ ስም ብቻ በመሆኑ የንግድ መደብር ሽያጭ እና የተከራይነት መብቱ ሊተላለፍ የሚችል መሆኑ ተረጋግጦ የተሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያልተፈፀመበት ነው በማለት ለሰበር ቅሬታው መነሻ የሆነው ውሳኔ እንዲፀናላቸው ጠይቀዋል፡፡

2ኛ ተጠሪ ለሰበር አቤቱታው በሰጡት መልስ፡- አመልካች 2ኛ ተጠሪ የንግድ መደብሩን ሲገዙ ተገቢውን ጥንቃቄ አለማድረጋቸውን፤ የንግድ መደብሩ ከአመልካች ጋር በጋራ የተሰጣቸው መሆኑ፤ የስጦታ ውሉን ህጋዊነትና ፎርማሊትን በተመለከተ እንዲሁም የስጦታ ውሉ ለዚህ ክርክር ተብሎ በተንኮል የተዘጋጀ ነው የሚለው ክርክር በሥር ፍርድ ቤት ስላልተነሳ በፍትሐ ብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር

329(1) መሠረት ውድቅ እንዲሆን ፤ የንግድ መደብሩ ግዥ የተፈፀሙት መደብሩን 1ኛ ተጠሪ በስጦታ ያገኙት የግል ንብረታቸው መሆኑን የስጦታ ውሉን በማየት የአመልካች እና 1ኛ ተጠሪ ጋብቻ ህዳር 25 ቀን 2011 ዓ/ም ከፈረሰ በኋላ 1ኛ ተጠሪ ያቀረቡትን ያላገባ ማስረጃ አይተው ታህሳስ 4 ቀን 2011 ዓ/ም በሰነዶችና ማረጋገጫና ምዝገባ ጽ/ቤት በመገኘት ተገቢውን ጥንቃቄ ያደረጉ የቅን ልቦና ገዥ መሆናቸውን አረጋግጦ የንግድ መደብሩ የሚከናወንበት ቤት ባለቤት መንግስት በመሆኑ የተከራይነት መብቱ በንግድ መደብሩ ላይ የሚካሄደውን ግብይት የሚከተል በመሆኑ የተሰጠው ውሳኔ የፍትሐ ብሔር ሕግ ቁጥር 1162(1) ፤ የንግድ ሕጉ ቁጥር 124, 151 (1) (ሀ) እና 152 ድንጋጌዎችንና በሰበር መዝገብ ቁጥር 34568 ላይ የተሰጠውን አስገዳጅ የሕግ ትርጉም መሠረት ያደረገ ነው ከሚባል በቀር የሚነቀፍ ባለመሆኑ ለሰበር ቅሬታው መሠረት የሆነው ውሳኔ ሊፀና ይገባል በማለት ተከራክረዋል፡፡

3ኛ እና 4ኛ ተጠሪዎች በጋራ በሰጡት መልስ ለ1ኛ ተጠሪ ያላገባ የምስክር ወረቀት የተሰጣቸው በቤተሰብ ቅጽ ላይ ያላገቡ በመሆኑና እሳቸውም ያላገቡ መሆኑን በቃለ መሃላ በማረጋገጣቸው ለጉዳዩ አግባብነት ካለው መመሪያ አንፃር ሕገ ወጥ ተግባር ያልፈፀሙ መሆኑንና አመልካች ቅሬታቸውን ካቀረቡ በኋላ 1ኛ ተጠሪ የወሰዱትን ያላገባ የምስክር ወረቀት እንዲመልሱ የጠየቁ ሲሆን ፤ የቤቱ የኪራይ ውሉ በ1ኛ ተጠሪ ስም በመሆኑና 1ኛ ተጠሪ ያቀረቡት ያላገባ ምስክር ወረቀት ታይቶ በወቅቱ በሥራ ላይ ያለው መመሪያ በሚፈቅደው መሠረት 1ኛ ተጠሪ በተከራዩት የመንግስት ንግድ ቤት ውስጥ የሚገኘውን የንግድ መደብር በፌደራል ሰነዶች ማረጋገጫና ምዝገባ ኤጀንስ ጽ/ቤት ለ2ኛ ተጠሪ የንግድ መደብሩን የሸጡላቸው ስለሆነ መመሪያው ከሚፈቅደው ውጭ 3ኛ እና 4ኛ ተጠሪዎች ለ1ኛ ተጠሪ የሰጡት አገልግሎት የሌለ በመሆኑ የሥር ፍርድ ቤት ውሳኔ የሚነቀፍበት አግባብ የለውም በማለት ተከራክረዋል፡፡ አመልካችም የሰበር አቤቱታቸውን በማጠናከር የመልስ መልስ ሰጥተዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ከላይ የተመለከተውን ሲመስል ለሰበር ቅሬታው ምክንያት የሆነው ውሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት መሆን አለመሆኑን ከፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት አመልካች እና 1ኛ ተጠሪ የተከራከሩበትን መዝገብ በትዕዛዝ በማስመጣት እንደሚከተለው መርምሮታል፡፡

የባልና ሚስት ንብረት ክርክር በተደረገበት የመዝገብ ቁጥር 68570 ጥቅምት 2 ቀን 2012 ዓ/ም በተሰጠው ውሳኔ አከራካሪው የቤት ቁጥር 249/124 የ3ኛ ወገን በመሆኑ የቀረበው የክፍፍል ጥያቄ የሕግ መሠረት የሌለው ከመሆኑም በላይ ተከራይ የመሆን ጥያቄም መቅረብ ያለበት ለፍርድ ቤት ሳይሆን ጉዳዩን ለሚመለከተው የከተማ አስተዳደር ጽ/ቤት በመሆኑ አከራካሪውን ቤት አስመልክቶ ክፍፍልም ሆነ ኪራዩን በሚመለከት አስተዳደራዊ በሆነ ጉዳይ ላይ ፍርድ ቤት ውሳኔ እንዲሰጥ አመልካች ያቀረቡት አቤቱታ የሕግ መሠረት የለውም በማለት የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ አመልካች አከራካሪውን ቤት በተመለከተ ያቀረቡትን ክስ ውድቅ ካደረገው በኋላ አመልካች አዲስ ክስ

ለአዲስ አበባ ከተማ ፍርድ ቤት አቅርበው ለሰበር ክርክሩ ምክንት የሆነው ውሳኔ የተሰጠ መሆኑን ለመረዳት ተችሏል፡፡

የንግድ መደብር የንግድ ሥራዎችን ለማከናወን የሚያገለግሉ የሚንቀሳቀሱ ንብረቶችን ሁሉ የሚመለከት መሆኑን ፤ በሽያጭም ሆነ በሌላ በማንኛውም ውል ሊተላለፍ እንደሚችል ፤ ሽያጩን በሚመለከት የፍትሐ ብሔር ሕጉ ቁጥር 2266 እስከ 2367 ያሉት ድንጋጌዎች ተፈፃሚነት ያላቸው መሆኑን የቀድሞው የንግድ ሕግ ቁጥር 124 ,150 እና 151 ድንጋጌዎች መመልከት ይቻላል፡፡ በተያዘው ጉዳይ በ1ኛ ተጠሪ እና 2ኛ ተጠሪ መካከል የተደረገው የንግድ መደብር ሽያጭ መሆኑ፤ መደብሩን 1ኛ ተጠሪ ከአመልካች ጋር በትዳር ውስጥ እያሉ በግላቸው በስጦታ አግኝተው በቀበሌ ንግድ ቤቱ ላይ ከ4ኛ ተጠሪ ጋር ውል ገብተው ሲጠቀሙበት ቆይተው የአመልካች እና 1ኛ ተጠሪ ጋብቻ ህዳር 25 ቀን 2011 ዓ/ም ከፈረሰ በኋላ ታህሳስ 8 ቀን 2011 ዓ/ም በተደረገ የንግድ መደብር ሽያጭ ውል ለ2ኛ ተጠሪ ተላልፎ 4ኛ ተጠሪም በወቅቱ በሥራ ላይ በነበረው መመሪያ ቁጥር 4/2009 መሠረት የንግድ ቤቱን የኪራይ ውል ከ1ኛ ተጠሪ ስም ወደ 2ኛ ተጠሪ ስም አዙሮ 2ኛ ተጠሪ እየተጠቀሙበት እንደሚገኙ በፍሬ ነገር ደረጃ መረጋገጡን የሥር ፍርድ ቤት የሰጠው ፍርድ ያመለክታል፡፡ አመልካች በአዲስ አበባ ከተማ ፍርድ ቤት ክስ ያቀረቡት የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ጉዳዩ አስተዳደራዊ በመሆኑ በፍርድ ቤት ሊታይ የሚችል አይደለም በማለት ውሳኔ ከሰጠ በኋላ በመሆኑ ጉዳዩ ዳግም መታየት የለበትም በማለት ያቀረበው መቃወሚያ ታልፎ ወደ ፍሬ ነገር ክርክር መገባቱ አግባብ ባይሆንም ከዚህ አንፃር ተጠሪዎች በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 340 መሠረት የቀረበ አቤቱታ ባለመኖሩ በሰበር ሰሚ ችሎቱ የሚታይ አይደለም፡፡ 1ኛ ተጠሪ ከአመልካች ጋር በትዳር ውስጥ እያሉ በግላቸው በስጦታ ያገኙት የንግድ መደብር ባለሀብት የሆኑበትን ንብረት ለ2ኛ ተጠሪ ማስተላለፋቸው የተሻሻለውን የቤተሰብ ሕግ አዋጅ ቁጥር 213/1992 አንቀጽ 57 ፤ የፍትሐ ብሔር ሕጉን ቁጥር 1204 ፤ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የቤቶች ልማት አስተዳደር ቢሮ የመንግስት ቤቶች አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 4/2009 ቁጥር 24(ረ) እና የንግድ ሕጉን ለጉዳዩ አግባብነት ያላቸውን ድንጋጌዎች መሠረት ያደረገ ነው ከሚባል በቀር አመልካች ካቀረቡት ቅሬታ አንፃር ሲታይ የሥር ፍርድ ቤት ውሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሞበታል ለማለት ስላልተቻለ ቀጣዩ ተወስኗል፡፡

<u>ውሳኔ</u>

1. የአዲስ አበባ ከተማ ሰበር ሰሚው ችሎት በመዝገብ ቁጥር 34766 ጥር 23 ቀን 2014 ዓ/ም በዋለው ችሎት ሁለተኛ ይግባኝ ሰሚው ችሎት በመዝገብ ቁጥር 33797 መስከረም 27 ቀን 2014 ዓ/ም በዋለው ችሎት የሰጠውን ውሳኔ በማጽናት የሰጠው ውሳኔ በፍ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 348(1) መሠረት ***ፀንቷል*** ::
2. በሰበር ክርክሩ የደረሰውን ወጪ እና ኪሳራ ግራ ቀኙ የግላቸውን ይቻሉ፡፡

3. የሥር ፍርድ ቤት መዝገብ በመጣበት አካኝ ይመለስ፡፡

መዝገቡ ውሳኔ ስላገኘ ተዘግቷል።

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሠ/ኃ

የሰ/መ/ቁ 196971

ጥቅምት 22 **ቀን** 2014 **ዓ/ም**

ዳኞች፡- *መዓዛ አሸናፊ*

ተፈሪ ገብሩ (ዶ/ር)

ቀነአ ቂጣታ

ፈይሳ ወርቁ

ብርቅነሽ እሱባለው

አመልካች፡- ወ/ሮ *ሠርካለም* አበበ -- ቀረቡ

ተጠሪ፡- አቶ አፈወርቅ ቅጣው -- አልቀረቡም

መዝገቡን ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች በቀን 12/02/2013 ዓ.ም በተጻፈ ማመልከቻ የፌደራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ 100989 በቀን 18/10/2011 ዓ.ም እንዲሁም የፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ 243618 በቀን 24/11/2012 ዓ.ም የሰጡት ብይንና ትዕዛዝ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ይታረምልኝ በማለት ስለጠየቁ ነው፡፡

ከመዝገቡ መረዳት እንደሚቻለው በስር የፌ/መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የአሁን አመልካች ባቀረቡት አቤቱታ ከተጠሪ ጋር ጋብቻ ፈጽመን በነበረበት ወቅት ጥር 5/2004 ዓ.ም ከጋራ ገንዘባችን በተጠሪ ስም ብር 160,000.00 (አንድ መቶ ስልሳ ሺህ) ወጪ በማድረግ በ250 አክስዮኖች የተከፋፈለ ብር 250,000.00 (ሁለት መቶ ሀምሳ ሺህ) ካፒታል ያለውን ተጠሪና ወንድማቸው አቶ ቃለአብ ቅጣው መስራች አባላት የሆኑበትን ኮንሶሉሹን አስመጪ ኃ/የተ/የግ/ማህበር በኋላ ስሙ ኮንሶሉሽን ንግድ ኃ/የተ/የግ/ማህበር የሆነ ማህበር አቋቁመናል፤ የማህበሩ ካፒታል ወዲያውኑ ባልና ሚስት ሆነን በጋራ ካፈራነው ሀብት በጥሬ ገንዘብ የተከፈለ ሲሆን መዋጮው ሙሉ በሙሉ የተከፈለ ስለመሆኑ በኮንሶሉሽን ንግድ ኃ/የተ/የግ/ማህበር መመስረቻ ጽሁፍ ተረጋግጧል፤ በተጠሪ ስም የተመዘገበው አክስዮን ብዛቱም

እያንዳንዳቸው ብር 1000.00 (አንድ ሺህ) ዋጋ ያላቸው 11,350 (አስራ አንድ ሺህ ሶስት መቶ ሀምሳ) አክስዮኖች ሆነዋል። በመካከላችን የነበረው ጋብቻ በመፍረሱ ምክንያት ይህ በጋራ ገንዘብ መዋጮ የተቋቋመው ኮንሶሉሽን ንግድ ኃ/የተ/የግ/ማህበር አክስዮኖች የሚያስገኘው መብትና ጥቅም እንዲሁም ገንዘብና ንብረት የጋራ በመሆናቸው አክስዮኖቹና አክስዮኖቹ የሚያስገኙት እና ያስገኙት ትርፍ ለአመልካች እና ለተጠሪ እኩል ሊካፈል ይገባል በማለት ጠይቀዋል።

ተጠሪ በሰጡት መልስ ባቀረቡት የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ በመካከላችን የነበረው ትዳር በፍ/ቤት የፈረሰው ሐምሌ 9/2004 ዓ.ም ሲሆን አመልካች የጋራ ሀብት ክፍፍል ጥያቄ በታህሳስ 7/2006 ዓ.ም አቅርበው በዚህ መነሻነት የጋራ ሀብት ክፍፍል ውሳኔ ተሰጥቷል። አመልካች የክፍፍል ጥያቄውን ሲያቀርቡ የአሁኑንም አብረው ማቅረብ ነበረባቸው። አሁን ክፍፍል የጠየቁበትን ማህበር ከምስረታው ጀምሮ ያውቁታል ይህንም ባቀረቡት ክስ ላይ ስመ· ኮንሶሉሽን ንግድ ኃ/የተ/የግ/ማህበር አቋቁምን በማለት አረጋግጠዋል። ስለሆነም በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 216 መሰረት ቀንሰው ያስቀሩትን መብት እንደገና ሊከሱበት አይችሉም በማለት ተከራክረዋል።

ጉዳዩ በዚህ መልኩ የቀረበለት የስር ፍርድ ቤት የመቃወሚያ ክርክሩን ከሰማ በኋላ አመልካች የባልና ሚስት የጋራ ንብረት ተጠሪ ያካፍሉኝ ብለው ታህሳስ 7/2006 ዓ.ም አቤቱታ ሲያቀርቡ ኮንሶሉሽን ንግድ ኃ/የተ/የግ/ማህበር የሆነውን ንብረት አብረው ማቅረብ እየቻሉ ሆን ብለው ቀንሰው ካስቀሩ በኋላ አሁን ይህን ንብረት ተጠሪ ግማሽ ድርሻዬን ያካፍሉኝ በማለት ያቀረቡት አቤቱታ የህግ ድጋፍ የለውም በማለት ብይን ሰጥቷል።

በዚህ ብይን ቅር በመሰኘት አመልካች ይግባኝ ለከፍተኛው ፍ/ቤት ቢያቀርቡም ጉድለት የለበትም ተብሎ ይግባኙ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 337 መሰረት ተሰርሟል። የሰበር አቤቱታው የቀረበው በዚህ ነው።

አመልካች በቀን 12/02/2013 ዓ/ም ባቀረቡት የሰበር ማመልከቻ በስር ፍ/ቤት በአሁን አመልካች የቀረበው አቤቱታ የፍቺ ውሳኔ ከተሰጠ በኋላ የሚቀርብ የፍቺ ውጤት የሆነው የባልና ሚስት ሀብት እንዲጣራ እና ንብረት ክፍፍል እንዲደረግ ነው እንጂ በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 216 እንደተመለከተው የቀረበ አይደለም። ንብረቱ በተጠሪ ቁጥጥር ሆነ እንጂ የአመልካችም ንብረት ነው። በዚህም ግዜ የጋራ ንብረቱ በእጁ ያለ ሰው (ባል ወይም ሚስት) ንብረቱ መኖሩንና የማጣራቱ አካል እንዲሆን ማሳወቅ አለበት፣ ይህ ካልሆነ ንብረት መሸሸግና አላግባብ መበልጸግን ያስከትላል። ከተጋቢዎች አንደኛው የጋራ ንብረት እንድንካፈል በማለት አቤቱታ ሲያቀርብ ፍርድ ቤቱ በተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አንቀጽ 85 እና ተከታይ ድንጋጌዎች መሰረት የባልና ሚስት ሀብት እንዲጣራ ከማድረግ በስተቀር እንደ ክስ ተቆጥሮ መሰል መቃወሚያ የሚቀርብበት አይደለም።የፍቺ ወጤት የሆነ ንብረት ክፍፍልን በመቃወሚያ ማስቆም ህጉ አይፈቅድም። ሀብት የሚጣራው ከተጋቢዎች አንደኛው በሚያቀርበው የንብረት ዝርዝር ተመስርቶ ሲሆን ይህ ሂደትም የሀብት ማጣራት ሂደት እንጂ በፍ/ሥ/ሥ/ህግ አራተኛው መጽሀፍ ምዕራፍ 1

(ከ215-240) የተመለከተው ክስ አይደለም፡፡ ንብረት የሚጣራውም በየቦታው ያሉና በየግዜው የሚገኙ ንብረቶች ማሰባሰብ እና ለባለቤቶቹ ማለትም ለባልና ሚስት ለማካፈል ነው፡፡ በመሆኑም የስር ፍ/ቤት ውሳኔ የህግ ስህተት የተፈፀመበት በመሆኑ እንዲሻርና የጋራ ንብረት የሆኑ በተጠሪ ስም የተመዘገቡ አክስዮኖች ካስገኙት ትርፍና ወደ ካፒታል ማሳደጊያ ያልዋለው ትርፍ የግራ ቀኞችን የጋራ ሀብት በመሆናቸው በቤተሰብ ህጉ መሰረት እኩል እንድንካፈል ይወሰንልኝ በማለት ቅሬታቸውን አቅርበዋል፡፡

ቅሬታው በሰበር አጣሪ ችሎቱ ተመርምሮ በአመልካችና ተጠሪ መካከል የነበረው ጋብቻ በፍቺ መፍረሱን ተከትሎ በመካሄድ ላይ በሚገኘው የንብረት ክፍፍል አመልካች በተጠሪ ስም ተመዝግቦ የሚገኝ የሶሉሽን ንግድ አክስዮኖችና አክስዮኖቹ ያስገኟቸው ጥቅሞች የጋራ ሀብት መሆናቸውን በመጥቀስ የድርሻቸው ተካፍሎ እንዲሰጣቸው ያቀረቡት አቤቱታ ያለ ፍርድ ቤት ፈቃድ ቀንሰው ያስቀሩት መብትና ጥያቄ ነው በሚል ውድቅ የተደረገበት አግባብነት ከፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 216 አንጻር ለማጣራት በሚል ጉዳዩ ለሰበር ችሎት እንዲቀርብና ተጠሪ መልስ እንዲሰጡበት ተደርጓል፡፡

ተጠሪ በቀን 08/08/2013 ዓ.ም ባቀረቡት መልስ የአመልካች የሰበር አቤቱታ የመጨረሻ ውሳኔ በተሰጠ በ90 ቀናት ውስጥ ያልቀረበ በመሆኑ ውድቅ ሊደረግ ይገባል፡፡ የአመልካች ተጨማሪ ሀብት ክፍፍል ጥያቄ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 216 መሰረት የሚገዛ ነው፤ የሥነ ሥርአት ህጉ በስራ ላይ እንዲውል ከታወጀበት ጀምሮ ለሚቀርቡ ክሶችና በክርክር ላይ ላሉትም ክሶች ተፈጻሚነት እንዳለው የህጉን የአፈጻጸም ወሰን በወሰነው አንቀጽ 1 ላይ ተደንግጓል፡፡ አመልካች ያቀረቡት አቤቱታ ደግሞ ይግባኝ ወይም የሰበር ወይም የአፈጻጸም አቤቱታ ሳይሆን ለመጀመሪያ ግዜ የቀረበ የክፍፍል ክስ በመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 216 ተፈጻሚነት አለው፡፡ በሌላ በኩል በተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አንቀጽ 108 ላይ በግልጽ እንደተመለከተው በቤተሰብ ህጉ የተመለከቱ የሥነ ሥርአት ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው በዚህ ህግ ውስጥ በተመለከቱት ጉዳዮች ላይ ለሚነሱ ክርክሮች የፍ/ሥ/ሥ/ህጎች ተፈጻሚነት ይኖራቸዋል በማለት ይደነግጋል፤ በቤተሰብ ህጉ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 216 ተፈጻሚነትን የሚያስቀር የሥነ ሥርአት ድንጋጌም የለም፡፡ ስለዚህ የፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 216 ለቤተሰብ ጉዳዮች ክርክርም ተፈጻሚነት አለው፡፡ አመልካች ክፍፍል ሲጠይቁ አብረው መጠየቅ የሚችሉትን ነገር ያለ ፍርድ ቤት ፈቃድ ቀንሰው ያስቀሩትን የመብት ጥያቄ አሁን ነጥለው አቤቱታ ሊያቀርቡበት ስለማይችሉ አቤቱታቸው በስር ፍ/ቤቶች በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 216 መሰረት ውድቅ መደረጉ ተገቢ ነው፡፡ ከዚህም ሌላ አመልካች እና ተጠሪ በትዳር እያሉ የነበረው የአክስዮን መጠን 160 ስለሆነ የአመልካች አቤቱታ በፍ/ብሥ/ሥ/ህ/ቁ 216 መሰረት ተቀባይነት የለውም እንጂ አለው የሚባል ከሆነ የድርሻ መጠናቸው የ160 አክስዮኖች ግማሽ 80 አክስዮኖች ብቻ ናቸው፡፡ ከትዳር መፍረስ በኋላ ተጠሪ የግል ገንዘባቸውን በመጨመር ያሳደጉት አክስዮን አመልካችን አይመለከትም፤ አመልካች ይገባቸዋል ከተባለ በማህበሩ ውስጥ የሚገባቸው አክስዮን 80 አክስዮን ስለሆነ የእነዚህን አክስዮኖች ዋጋ ተጠሪ ሊከፍሏቸው ይችላሉ፤ በቤተሰብ በተያዘ ኃ/የተ/የግ/ማህበር ውስጥ ግን አመልካች የማህበሩ አባል የሚሆኑበት ምክንያት የለም፤ የንግድ ህግ

ቁጥር 523 እና የማህበሩ መተዳደሪያ ደንብ አንቀጽ 9.2 አይፈቅድም፡፡ ስለሆነም 80 አክስዮኖች ያስገኙት ትርፍም ሆነ ወደፊት ትርፍ ካስገኘ ከማህበሩ ተጣርቶ በሚቀርበው መጠን መሰረት ሊከፈላቸው ይችላል፡፡ አመልካች በትዳር ዘመን ያላፈሩትን እና የሌለውን 11,350 አክስዮኖች ልካፈል፣ ትርፍም በዚሁ መጠን ይከፈለኝ በማለት ያቀረቡት አቤቱታ ውድቅ እንዲደረግና የስር ፍ/ቤቶች ውሳኔ እንዲጸናልኝ በማለት ተከራክረዋል፡፡ አመልካችም በመልስ መልሳቸው የስር ክርክራቸውን በማጠናከር ተከራክረዋል፡፡

ከፍ ሲል ባጭሩ የገለጽነው የጉዳዩን አመጣጥ ሲሆን በበኩላችን ለሰበር ችሎቱ የተያዘውን ጭብጥ ከግራ ቀኙ ክርክር እንዲሁም ከተገቢው የህጉ ድንጋጌ በማያያዝ ቅሬታ በቀረበበት ውሳኔ የተፈጸመ የህግ ስህተት መኖር አለመኖሩን መርምረናል፡፡ ለውሳኔ አሰጣጥ እንዲረዳንም የፌዴራሉ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የኮ/መ/ቁ 100989 የሆነውን መዝገብ አስቀርበን ተመልክተናል፡፡

እንደመረመርነው ተጠሪ ባቀረቡት መልስ የአመልካች የሰበር አቤቱታ የመጨረሻ ውሳኔ በተሰጠ በ90 ቀናት ውስጥ ያልቀረበ በመሆኑ ውድቅ ሊደረግ ይገባል በሚል ቀዳሚ መከራከሪያ ያቀረቡ ቢሆንም ከመዝገቡ መረዳት እንደሚቻለው የፌ/ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኙን መርምሮ የመጨረሻ ውሳኔ (ትዕዛዝ) የሰጠው ሀምሌ 23/2012 ዓ.ም ሲሆን የሰበር አቤቱታው የቀረበውና የዳኝነቱ ተከፍሎ የሰበር ፋይል የተከፈተው ጥቅምት 12/2013 ዓ.ም ነው፡፡ ስለሆነም የሰበር አቤቱታው በጉዳዩ ላይ የመጨረሻ ውሳኔ በተሰጠ በ90 ቀናት ውስጥ የቀረበ በመሆኑ በዚህ ረገድ የቀረበው መከራከሪያ ተቀባይነት ያለው አይደለም፡፡

ለሰበር ችሎቱ ወደተያዘው ጭብጥ ስንመለስ ክሳሽ ሊከስበት ሲችል ሆነ ብሎ በመቀነስ ባስቀረው ሀብት ምክንያት እንደገና ሌላ ክስ ማቅረብ የማይችል ስለመሆኑ እና ከሳሽ ያቀረበው ክስ በአንድ ጉዳይ ላይ የተመሰረተ ሆኖ የሚጠይቀው ዳኝነት ግን ከአንድ በላይ ሲሆን ፍርድ ቤቱ ሳይፈቅድለት ሊጠይቅ ይገባው ከነበረው ዳኝነት ውስጥ በከፊል ራሱ ቀንሶ ባስቀረው መብት እንደገና ሊከስበት የማይችል ስለመሆኑ ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 216 (3) (4) መረዳት ይቻላል፡፡ ይኸው የስነ ስርዓት ህጉ ድንጋጌ እንደአግባብነቱ በቤተሰብ ክርክሮችም ተፈፃሚነት አይኖረውም የሚባልበት የህግ ምክንያት የለም፡፡ ይሁን እንጂ ጉዳዩን በቤተሰብ ህጉ ስለጋብቻ ንብረት ማጣራት ከተደነገጉት ድንጋጌዎች እና በተለይም ከግራ ቀኙ ክርክር ይዘት አንፃር መመልከቱ ተገቢ ይሆናል፡፡

በተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አዋጅ ቁጥር 213/1992 ከአንቀጽ 85 ጀምሮ ያሉ ድንጋጌዎች የባልና ሚስትን ሀብት ስለማጣራት ይደነግጋሉ፡፡ የባልና ሚስትን ሀብት የማጣራቱም ሆነ የክፍፍሉ ተግባር የሚመራበት የህጉ መሰረታዊ መርህ የባልና ሚስት የጋራ ሀብት ለሁለቱም እኩል የሚከፋፈል በመሆኑ ላይ የተመሰረተ መሆኑን ከድንጋጌዎቹ መገንዘብ ይቻላል፡፡ ግራ ቀኙ በሚያደርጉት ስምምነትና

በህጉ አግባብ የግል ሀብት መልሶ የሚወሰድ መሆኑ እንዲሁም የካሳና የእዳ ጉዳዮች የባልና ሚስት ሀብት ከመከፈሉ በፊት ተቀንሶ የሚከፈል መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ ከዚህ በመለስ ግን የባልና ሚስት የጋራ ሀብት ለሁለቱም እኩል እንዲከፈል የሚደረግ መሆኑ የህጉ መሰረታዊ መርህ ነው።

ከዚህም ሌላ ከቤተሰብ ህጉ አንቀጽ 108 እና 109 ግልጽ ድንጋጌዎች መገንዘብ እንደሚቻለውም የፍትሐብሄር ሥነ ሥርዓት ህጉ ድንጋጌዎች ተፈፃሚነት የሚኖራቸው በቤተሰብ ህጉ ባልተመለከቱ የሥነ ሥርዓት ጉዳዮች ላይ ብቻ ነው። በባልና ሚስት የጋብቻ ንብረት ክርክር ብቻም ሳይሆን ጋብቻው የፈረሰው በሞት ቢሆን እንኳ በህይወት ባለው ተጋቢ እና በሟች ወራሾች መካከል የንብረት ክፍፍልን በተመለከተ ክርክር የተነሳ እንደሆነ የባልና ሚስትን ሀብት ስለማጣራት በቤተሰብ ህጉ በምዕራፍ 5 የተደነገጉት ድንጋጌዎች ተፈፃሚ እንደሚሆኑ ተመልክቷል። ከእነዚህ ድንጋጌዎች መገንዘብ የሚቻለውም የጋብቻ ንብረት ማጣራትና ክፍፍል ጉዳይ የቤተሰብ ህጉን ድንጋጌዎች በጥብቅ ተከትሎ ሊፈፀም የሚገባ ስለመሆኑ ነው።

በተያዘው ጉዳይ በግራቀኙ መካከል የነበረው ጋብቻ በፍቺ ቀሪ ሆኖ የፍች ውጤት በሆነው የጋብቻ ንብረት ክፍፍል ጉዳይ ረዥም ጊዜ የወሰደና የተለያየ መልክ የያዘ ክርክር በመካሔድ ላይ የሚገኝ መሆኑ ግራ ቀኙን የሚያከራክር አይደለም። አስቀርበን የተመለከትነው የፌዴራሉ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የከ/መ/ቁ 100989 የጋብቻ ንብረት ክርክሩ በሂደት ላይ መሆኑን የሚያሳይ ነው። የአመልካች ቀዳሚ የዳኝነት ጥያቄም የጋብቻ ንብረት ተጣርቶ ድርሻቸው እንዲከፈል ሲሆን በተለይም የማህበር ድርሻ የመብት ጥያቄን በተመለከተ በተለያዩ ፍርድ ቤቶች የዕግድ ትዕዛዝ ሲሰጥበት የቆየና የማጣራቱ አካል ሆኖ መኖሩን ከመዝገቡ መረዳት ይቻላል።

በመሆኑም የስር ፍርድ ቤቶች አመልካች ኮንሶሊሽን ንግድ ኃ/የተ/የግ/ማህበር የሆነውን ንብረት ጉዳይ አብረው ማቅረብ እየቻሉ ቀንሰው አስቀርተዋል ስለሆነም አቤቱታቸው ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 216 አንፃር ተቀባይነት የለውም በማለት የደረሱበት መደምደሚያ እና ያሳለፉት ብይንና ትዕዛዝ ግራ ቀኙ እያደረጉት ያለውን የንብረት ክርክር እና የጋብቻ ንብረትን ስለማጣራት በቤተሰብ ህጉ የተዘረጋው ስርዓት ስርዓት የተከተለ ሆኖ አላገኘነውም።

በሌላ በኩል ተጠሪ ባቀረቡት መልስ የአመልካች የድርሻ መጠን የ160 አክስዮኖች ግማሽ 80 አክስዮኖች ብቻ መሆኑን፤ ከትዳር መፍረስ በኋላ ተጠሪ የግል ገንዘባቸውን በመጨመር ያሳደጉት አክስዮን መኖሩን፤ በቤተሰብ አባላት በተያዘ ኃ/የተ/የግ/ማህበር ውስጥ አመልካች አባል ሊሆኑ እንደማይገባ፤ እንዲሁም አመልካች በትዳር ዘመን ያላፈሩትን እና የሌለውን 11,350 አክስዮኖች ልካፈል፣ ትርፍም በዚሁ መጠን ይከፈለኝ በማለት ያቀረቡት ክርክር ተቀባይነት ሊኖረው እንደማይገባ ተከራክረዋል። ነገር ግን በተጠሪ የተጠቀሱት እነዚህ መከራከሪያዎች ከመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ

በኋላ የሚታዩ ፍሬ ጉዳዩን የተመለከቱ በመሆናቸውና በዚህ ረገድ በስር ፍርድ ቤቶች ተሰጠ ውሳኔ ባለመኖሩ ከወዲሁ የምንመለከተው አይሆንም ::

በአጠቃላይ በስር ፍርድ ቤቶች የተሰጠው ብይንና ትዕዛዝ ለጉዳዩ አግባብነት ያላቸውን ህጎች እና የግራ ቀኙን ክርክር ሂደት ያላገናዘበ በመሆኑ ተቀባይነት ያለው አይደለም በማለት ተከታዩን ወስነናል::

<u>ው ሳ ኔ</u>

1. የፌደራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ 100989 በቀን 18/10/2011 ዓ.ም እንዲሁም የፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ 243618 በቀን 24/11/2012 ዓ.ም የሰጡት ብይንና ትዕዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 348 (1) መሰረት ተሽሯል::

2. የፌደራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን የፍሬ ነገር ክርክር ተመልክቶ ተገቢውን እንዲወስን ጉዳዩን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 341(1) መሰረት መልሰናል:: ይጻፍ::

3. የሰበር ክርክሩ ያስከተለውን ወጪና ኪሳራ ይቻቻሉ::

4. እግድ ተነስቷል ይጻፍ:: የሥር ፍ/ቤት መዝገብ ይመለስ::

መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መ/ቤት ይመለስ::

አ/መ የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

የሰ.መ.ቁ.203715

ጥር 23 ቀን 2014 ዓ.ም

ዳኞች፡....1. ተፈሪ ገብሩ (ዶ/ር)

2. ቀነዓ ቂጣታ

3. ፈይሳ ወርቁ

4. ደጀኔ አያንሳ

5. ብርቅነሽ እሱባለዉ

አመልካች፡.....ወ/ሮ ፀሐይ አስራት- ጠበቃ ታዬ ግ/መድን - ቀርበዋል፡፡

ተጠሪ፡.....አቶ አሰፋ ማሞ - ከጠበቃ ልኡል አያሌው ጋር - ቀርበዋል፡፡

ይህ መዝገብ ተመርምሮ የሚከተለዉ ፍርድ ተሰጥቷል።

ፍርድ

ይህ የባልና ሚስት ክርክር የተጀመረዉ በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የአሁን አመልካች የሥር ከሳሽ፣ የአሁን ተጠሪ የሥር ተከሳሽ ሆኖ ሲከራከሩ ነበር። ጉዳዩ ለዚህ ችሎት ሊቀርብ የቻለዉ የአሁን አመልካች የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ.244466 መስከረም 7 ቀን 2013 ዓ.ም የሰጠዉ ዉሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ እንዲታረምልኝ በማለት በማመልከታቸዉ ነዉ።

የጉዳዩ አመጣጥ ሲታይ የአሁን አመልካች በሥር ፍ/ቤት ባቀረበችዉ ክስ ከተከሳሽ ጋር የነበረን ጋብቻ የፈረሰ በመሆኑ የፍቺ ውጤት የሆነዉ፣ በቀድሞ በቦሌ ክ/ከተማ ወረዳ 10 (አሁን ወረዳ 11) ዉስጥ የሚገኙ 1ኛ. የካርታ ቁጥር ቦሌ11/16/1/6/47615/00 የሆነዉ ቤትና ከዚህ ቤት የሚገኝ የቤት ኪራይ ገቢ፣ 2ኛ. የቤት ቁጥር አዲስ ሰነድ አልባ አምስት ክፍል ቤትና ከዚህ ቤት የሚገኝ የቤት ኪራይ ገቢ፣ 3ኛ. በ500 ካ.ሜ ቦታ ላይ የተከልነው 400 እግር ባህር ዛፍ ከነይዞታው፤ በኢትዮጵያ ንግድ ባንክና በዳሽን ባንክ በተጠሪ ስም ያለ ገንዘብ፤ የተለያዩ የቤት እቃዎችን ፤የመቃብር ፋካና እድሮችን በጋራ ያፈራን በመሆኑ ድርሻዬን እንዲያካፍለኝ በማለት ዳኝነት ጠይቋል፡፡

ተከሳሽ በዚህ ክስ ላይ ባቀረበዉ መልስ እኔና ከሳሽ በጋብቻ ስንኖር ከምግብ ያለፈ በጋራ ሰርተን ያጠራቀምነው ገንዘብ የለም፤ የካርታ ቁጥር ቦሌ11/16/1/6/47615/00 የሆነውን ቤት የጋራ ያልሆነና ከእናቴ በውርስ ያገኘሁት ቤትና ቦታ መንግስት ለልማት በመዉሰዱ በተሰጠ ምትክ ቦታና የካሳ

ገንዘብ የተሰራ በመሆኑ የጋራ ሀብት ሳይሆን የግል ንብረቴ ነዉ፤ ሌሎቹም ከሳሽ የጠየቀቻቸው ንብረቶችም ከዉርስ ሀብት የተገኘና የሌሉ በመሆናቸው የግል ሀብት ናቸው ፤የመቃብር ፋካና እድሮቹን ትካፈል በማለት ተከራክሯል፡፡

ከዚህ በኋላ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ግራ ቀኙን በማከራከር፣ የሰዉ ምስክሮችን በመስማት፣ ከሚመለከተዉ የከተማዉ አስተዳደር ጽ/ቤት ተጣርቶ እንዲቀርብ በማድረግና የሰነድ ማስረጃ በመመርመር በሰጠዉ ዉሳኔ በተከሳሽ ስም የካርታ ቁጥር ቦሌ11/16/1/6/47615/00 የተሰራለት ቤት ግራ ቀኙ ጋብቻ ፈጽመዉ እየኖሩ በነበረበት ጊዜ የተሰራ መሆኑን በግራ ቀኙ የሰዉ ምስክሮች የተረጋገጠ መሆኑና በተከሳሽም ያልተካደ ነዉ፤ በመሆኑም ይህ ቤት የግራ ቀኙ የጋራ ንብረት ነዉ፤ ከዚህ ቤት የሚገኘዉን የቤት ኪራይ ገቢ ብር 40000 (አርባ ሺህ) ግማሹ 20000 (ሀያ ሺህ) የከሳሽ ነዉ፤ በቦሌ ክ/ከተማ ወረዳ 10 የቤት ቁጥር አዲስ የሆነዉ ሰነድ አልባ ቤት 5 ክፍል መኖሩ ስላልተረጋገጠ የከሳሽ የዳኝነት ጥያቄ ዉድቅ ነዉ፤ በቦሌ ክ/ከተማ ወረዳ 10 ዉስጥ በ500 ካ.ሜ ባዶ ቦታ ላይ የተተከለ ቁጥቋጦ በብዛት በቁጥር 17 ጉቶ በቁጥር 23 ያገኘ እና በጠቅላላዉ 40 የተቆጠረ ዛፍ ጉቶ እና ቁጥቋጦና ይዞታ የግራ ቀኙ የጋራ ንብረት ነዉ፤ የቤት ቁሳቁሶች እና በባንክ አለ የተባለዉን ገንዘብ አጣርቶ ተገቢ ነዉ ያለዉን ዉሳኔ በመስጠት፤ የጋራ ንብረት ነዉ የተባሉትን ንብረቶችን የክፍፍል ሥርዓቱንም በማመልከት ወስኗል፡፡

የሥር ተከሳሽ በዚህ ዉሳኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ያቀረበ ሲሆን ፍ/ቤቱም ግራ ቀኙን በማከራከር በቦሌ ክ/ከተማ በወረዳ 11 ዉስጥ የሚገኘዉ የካርታ ቁጥር ቦሌ11/16/1/6/47615/00 የሆነዉ ያለዉና የተሰራዉ ቤት መንግስት ለልማት በወሰደዉ ቤትና ይዞታ ምትክ በተሰጠዉ ይዞታና በካሳ በተገኘ ገንዘብ የተሰራ መሆኑን ተከሳሽ ባቀረበዉ ማስረጃ በተሻለ ሁኔታ በማስረዳቱና የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ.መ.ቁ.65708 (ቅጽ 17) ጥር 2 ቀን 2004 ዓ.ም በሰጠዉ አስገዳጅ የህግ ትርጉም ዉሳኔ ከባልና ሚስት የጋራ ንብረት ክፍፍል ጋር በተገናኘ በአንደኛዉ ተጋቢ በዉርስ የተገኙ ንብረቶች ለልማት በሚል በመፍረሳቸዉ የተገኘ የካሳ ክፍያ በግብይት እንደተገኘ ተቆጥሮ የግል ስለመሆኑ በፍ/ቤት አልተረጋገጠም በሚል እንደ የጋራ ሀብት ሊቆጠር የማይችል መሆኑን ዉሳኔ ያሳለፈ በመሆኑ በዚህ ጉዳይ ላይ ተፈጻሚነት ያለዉ ስለሆነ፤ ይህ ቤትና ይዞታ የተከሳሽ የግል ንብረት ነዉ፤ ከዚህ ቤት ከፍቺ በኋላ የሚገኘዉም የቤት ኪራይ ገንዘብ የተከሳሽ የግል ንብረት ነዉ በማለት የሥር ፍ/ቤትን ዉሳኔ በማሻሻል ወስኗል፡፡ የሥር ከሳሽ በዚህ ዉሳኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ያቀረበች ቢሆንም ፍ/ቤቱ ይግባኙን በትዕዛዝ ዉድቅ በማድረግ የሥር ፍ/ቤትን ዉሳኔ በማጽናት ወስኗል፡፡ የአሁን የሰበር አቤቱታ የቀረበዉ በዚህ ዉሳኔ ቅር በመሰኘት ለማስለወጥ ነዉ፡፡

የአሁን አመልካች በ1/7/2013 ዓ.ም በተጻፈ የሰበር አቤቱታ፡ አሁን ክርክር ያስነሳው የካርታ ቁጥር ቦሌ11/16/1/6/47615/00 በ500 ካ.ሜ ይዞታ ላይ የነበረዉ ጎጆ ቤት በትዳር ውስጥ በማፍረስ አመልካች ጠላ በመሸጥና ብሎኬት በመሸከም የጉልበት አስተዋፀኦ በማድረግ፣ በብሎኬት 7 ክፍል ቤት በጋራ መስራታችን በማስረጃ ተረጋግጦ ባለበት፤ ይህም ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ.መ.ቁ.65708 ጥር 2 ቀን 2004 ዓ.ም የሰጠዉ አስገዳጅ የህግ ትርጉም ለዚህ ጉዳይ አስገዳጅ ሊሆን የማይችል ሆኖ ሳለ፤ ይህን ቤት በጋብቻ ዉስጥ በጋራ የሰራንና ያፈራነዉ በመሆኑ በተሻሻለዉ የቤተሰብ ሕግ አዋጅ ቁጥር 213/1992 አንቀጽ 63 (1) መሰረት የጋራ ሀብት ሆኖ እያለ፤ እንዲሁም ክርክር የተነሳበት ቤት በጋብቻ ውላችን የጋራ ሀብት መሆኑን የተስማመንበትና እየተጠቀምንበት ያለን የጋራ ሀብት በመሆኑ፤ የሥር የከፍተኛ ፍ/ቤት እና የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት የሰጡት ዉሳኔ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ እንዲሻርልኝ፣ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የሰጠዉ ዉሳኔ እንዲጸናልኝ ወጪና ኪሳራ ከጠበቃ አበል ጋር እንዲወሰንልኝ በማለት አመልክታለች፡፡

የሰበር አጣሪ ችሎትም ጉዳዩን በማየት ፣የክርክሩ መነሻ የሆነውና በቦሌ ክ/ከተማ ወረዳ 11 የካርታ ቁጥር ቦሌ11/16/1/6/47615/00 የሆነው ቤት ተከራካሪ ወገኖቹ በጋብቻ ውስጥ እያሉ የተሰራ ስለመሆኑ በተገለፀበት ቤቱ የግል ንብረት ነው በሚል የተወሰነበት አግባብነት፣ ለማጣራት ለሰበር አቤቱታዉ ያስቀርባል በማለት ተጠሪ መልስ እንዲሰጥ ባዘዘዉ መሰረት ግንቦት 30 ቀን 2013 ዓ.ም የተጻፈ መልስ አቅርቧል፡፡ የመልሱም ይዘት በአጭሩ፡ ተጠሪ ከመንግስት የተረከበዉ ይዞታ ባዶ ቦታና በወቅቱ የተሰራ ምንም ዓይነት ቤት አልተሰራም፤ በጋብቻ ውላችን የጋራ እንዳይሆኑ የተስማማንበትና በውርስና ስጦታ ያገኘሁት ቤትና ቦታ ለልማት በመወሰዱ በተገኘ ምትክ ቦታና ካሳ ገንዘብ የተሰራ ቤት በመሆኑና ይህንንም በፍ/ቤት የግል ይባልልኝ ማቅረብ የሚያስፈልገው ባለመሆኑ፤ አመልካች ያቀረበችዉ የሰበር አቤቱታ የተዛባ በመሆኑ፣ የሥር የከፍተኛና የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ያስተላለፉት ውሳኔ ምንም ዓይነት መሰረታዊ የህግ ስህተት የሌለዉ ስለሆነ እንዲጸናልኝ፣ ወጪና ኪሳራ ዝርዝር የማቅረብ መብት እንዲጠበቅልኝ በማለት ተከራክሯል፡፡ አመልካችም የሰበር አቤቱታዉን በማጠናከር የመልስ መልስ አቅርቧል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ከፍ ሲል የተመለከተዉ ሲሆን ይህ ችሎት የግራ ቀኙን ክርክር አግባብነት ካላቸዉ የህግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ እንዲሁም የሰበር አቤቱታዉ ያስቀርባል ሲባል ከተያዘዉ ጭብጥ አንጻር እንደሚከተለዉ መርምሮታል፡፡ እንደመረመርነዉ አከራካሪዉ በቦሌ ክ/ከተማ ወረዳ 11 የካርታ ቁጥር ቦሌ11/16/1/6/47615/00 የተመዘገበዉ የመኖሪያ ቤት የአሁን አመልካች እና የተጠሪ የጋራ ሀብት ነዉ ወይስ የተጠሪ የግል ሀብት ነዉ? የሚለዉ ነጥብ መታየት ያለበት ጉዳይ ነዉ፡፡ አመልካች ባቀረበችዉ ክርክር ይህን ቤት በጋራ ገንዘባችን በትዳር ዉስጥ የሰራንና ያፈራን ስለሆነ የጋራ ሀብታችን ነዉ በማለት የተከራከረች ሲሆን፤ ተጠሪ በበኩሉ ቤቱን

የሰራሁት መንግስት በዉርስ ያገኙትን ቤትና ቦታ ለልማት ወስዶ በሰጠኝ ምትክ ቦታና በከፊለኝ የካሳ ገንዘብ በመሆኑ ቤቱ የግል ሀብቴ ነዉ በማለት ተከራክሯል፡፡ በዚህ መሰረት በሥር ፍ/ቤት በማስረጃ የተረጋገጠዉ ፍሬ ነገር ሲታይ አመልካች እና ተጠሪ በ1999 ዓ.ም ዉስጥ ጋብቻ ፈጽመዉ ጋብቻቸዉ በፍቺ ዉሳኔ በ8/2/2011 ዓ.ም እስከፈረሰበት ድረስ በትዳር አብረዉ ሲኖሩ እንደነበሩ እና ግራ ቀኙ በትዳር አብረዉ ሲኖሩ ይህን ለክርክር መነሻ የሆነዉን የመኖሪያ ቤት በ2009 ዓ.ም ዉስጥ የሰሩትና ያፈሩት መሆናቸዉን ነዉ፡፡ ይህ ማለት አመልካች እና ተጠሪ በትዳር አብረዉ እያለ ቤቱን መስራታቸዉንና ማፍራታቸዉን የሚያስገነዝብ ነዉ፡፡

እንደሚታወቀዉ የፌዴራሉ የተሻሻለዉ የቤተሰብ ሕግ አዋጅ ቁጥር 213/1992 አንቀጽ 62 (1) መሰረት ባልና ሚስት በትዳር ዉስጥ በጋራ ያፈሩአቸዉ ንብረቶች የጋራ ሀብቶቻቸዉ እንደሚሆኑ እና ይህም አንደኛዉ ተገቢ የግል ሀብቱ መሆኑን አግባብነት ባለዉ ማስረጃ ካላስረዳ በቀር ንብረቱ በአንደኛዉ ተገቢ ስም ተመዝግቦ የሚገኝ ቢሆንም የጋራ ሀብት እንደሆነ እንደሚቆጠር በዚህ ሕግ አንቀጽ 63 (1) ሥር ተመልክቷል፡፡ በዚህ አግባብ አሁን የተያዘዉ ጉዳይ ሲታይ ለክርክር መነሻ የሆነዉ ግራ ቀኙ በትዳር አብረዉ እየኖሩ የሰሩትና ያፈሩት መሆናቸዉን በሥር ፍ/ቤት በማስረጃ የተረጋገጠ ሲሆን፣ ተጠሪ በበኩሉ ግን ቤቱን ከመንግስት በተከፈለዉ የካሳ ገንዘብ እንደሰራ ገልጾ የተከራከረ ቢሆንም ተጠሪ የካሳ ገንዘብን ለቤቱ ሥራ ያዋለ መሆኑን በፌዴራሉ የቤተሰብ ሕግ አንቀጽ 58 መሰረት የካሳ ገንዘቡን ለቤቱ ሥራ አዉሎ ያፈራዉ መሆኑን ጠቅሶ ቤቱ የግል ሀብት እንዲባልልኝ በማለት ለፍ/ቤት አቤቱታ አቅርቦና ፍ/ቤቱ ቤቱ የተጠሪ የግል ሀብት መሆኑን ተብሎ ያጸደቀበት አግባብ የለም፡፡ ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ.መ.ቁ.65708 ጥር 2 ቀን 2004 ዓ.ም (ቅጽ 13) የሰጠዉ አስገዳጅ የህግ ትርጉም በባንክ የተቀመጠ በመንግስት የተከፈለ የካሳ ገንዘብ የሚመለከት ስለሆነ አሁን ከተያዘዉ ክርክር ጋር ተመሳሳይ የህግ ጭብጥ የሌለዉ ስለሆነ በዚህ ጉዳይ ላይ ተፈጻሚነት የለዉም፡፡ በመሆኑም ተጠሪ አከራካሪዉ ቤት የግል ሀብቱ መሆኑን በሕግ አግባብ ማረጋገጡን የሥር ፍ/ቤት የዉሳኔ ግልባጭ የሚያመለክተዉ ነገር የለም፡፡ ስለሆነም ለክርክር መነሻ የሆነዉ በቦሌ ክ/ከተማ ወረዳ 11 የካርታ ቁጥር ቦሌ11/16/1/6/47615/00 በተጠሪ ስም ተመዝግቦ የሚገኘዉ የመኖሪያ ቤት ግራ ቀኙ በትዳር አብረዉ እየኖሩ ያፈሩት መሆናቸዉ የተረጋገጠ በመሆኑ፣ ቤቱ የአመልካች እና የተጠሪ የጋራ ሀብት ነዉ እንጂ የተጠሪ የግል ሀብት አይደለም ብለናል፡፡ የሥር የከፍተኛ ፍ/ቤት የግራ ቀኙን ክርክር በዚህ አግባብ በመረዳት አከራካሪዉ ቤት የግራ ቀኙ የጋራ ሀብት መሆኑን መወሰን ሲገባዉ የተጠሪ የግል ሀብት ነዉ በማለት መወሰኑ እና የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይህን ዉሳኔ ማረም ሲገባዉ በትዕዛዝ በማጽናት መወሰኑ የህግ ድጋፍ የለዉም ብለናል፡፡

ሲጠቃለል የሥር የከፍተኛ ፍ/ቤት እና የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት አከራከሪዉ ቤት የግራ ቀኙ የጋራ ሀብት ሆኖ ሳለ፣ የተጠሪ የግል ሀብት ነዉ በማለት መወሰናቸዉ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ ተከታዩን ወስነናል፡፡

<u>ዉሳኔ</u>

1. የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ.244466 መስከረም 7 ቀን 2013 ዓ.ም የሰጠዉ ዉሳኔ እና የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ.ቁ.197833 የካቲት 4 ቀን 2013 ዓ.ም የሰጠዉ ትዕዛዝ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸባቸዉ ስለሆነ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.348 (1) መሰረት ተሽሯል፡፡
2. የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ.ቁ.73234 ሐምሌ 19 ቀን 2013 ዓ.ም የሰጠዉ ዉሳኔ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ያልተፈጸመበት ስለሆነ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.348 (1) መሰረት ጸንቷል፡፡
3. የዚህ ዉሳኔ ግልባጭ ለሥር ፍ/ቤቶች ይድረስ፡፡
4. ግራ ቀኙ በዚህ ችሎት የደረሰባቸዉን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸዉን ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ሄ/መ

የሰ/መ/ቁ. 234422

ሚያዚያ 30 ቀን 2015 ዓ.ም

ዳኞች፡- ተፈሪ ገብሩ (ዶ/ር)

እንዳሻዉ አዳነ

ተሾመ ሽፈራው

መላኩ ካሳዬ

ነፃነት ተገኝ

አመልካቾች፡- 1ኛ ወ/ሮ ሙሉ ጥበቡ

2ኛ ወ/ሮ ኤልሳ ጥበቡ } ጠበቃ መድን መሀሪ - ቀርበዋል

3ኛ አቶ ኪሮስ ጥበቡ

4ኛ አቶ ፀጋዬ ጥበቡ

ተጠሪዎች፡- 1ኛ ወ/ሮ አዜብ አሰፋ አበራ

2ኛ አቶ አብርሃም ጥበቡ } ጠበቃ ግርማ ወልደአረጋን - ቀርበዋል

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ይህ ጉዳይ የተጀመረዉ በፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ሲሆን፣ አመልካቾች በተጠሪዎች ላይ ባቀረቡት ክስ 1ኛ ተጠሪ የ2ኛ ተጠሪ እናት ሲሆኑ 2ኛ ተጠሪ የተሰጣቸውን ውክልና በመጠቀም 1ኛ ተጠሪ የአቶ ጥበቡ ገ/ማርያም ልጅ በማስመሰል እንዲሁም እራሳቸውንም የአቶ ጥበቡ ገ/ማርያም እና የወ/ሮ ምህረት አለማየሁ ልጅ ሳይሆኑ ልጅ በመምሰል የውርስ ሰርትፍኬት መዉሰዳቸዉን ጠቅሰዉ ተጠሪዎች ልጅ አይደሉም ተብሎ እንዲወሰንላቸዉ የጠየቁትን ዳኝነት መነሻ ያደረገ ነዉ፡፡ ተጠሪዎች በሰጡት መልስ ከአቶ ጥበቡ ገ/ማርያም እና ከወ/ሮ ምህረት አለማየሁ በፀና ጋብቻ ውስጥ የተወለዱ መሆኑን ጠቅሰዉ አመልካቾች በቀጥታ የመካድ ክስ ማቅረብ እንደማይችሉ እና የመካድ ክስ ማቅረብ የሚቻለዉ ፍርድ ቤት ሲፈቅድ ሆኖ ልጁ በተወለደ በ180 ቀናት ውስጥ ካልቀረበ በይርጋ እንደሚታገድ ጠቅሰዉ ተከራክረዋል፡፡

ጉዳዩ የቀረበለት የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትም ከግራ ቀኝ በዚህ መልኩ የቀረበዉን ክርክር ከሰማ በኋላ ግራ ቀኝ ሚያዝያ 27 ቀን 2007 ዓ.ም የቤተሰብ ሽምግልና በማድረግ አመልካቾች እና ተጠሪዎች የመቶ አለቃ ገ/ማርያም ልጆች መሆናቸው እና ከወ/ሮ ምህረት አለማየሁ መወለዳቸዉን አረጋግጠዋል፤ በተጨማሪም አመልካቾች 2ኛ ተጠሪን ወንድማችን ነዉ በማለት ለስጋ ዘመድ ብቻ

የሚሰጠዉን ዉክልና መስጠታቸዉ ተጠሪዎች በጋብቻ ዉስጥ መወለዳቸዉን ያመላክታል ካለ በኋላ የተጠሪዎች የመካድ ክስ በተሻሻለው የቤተሰብ ሕግ አንቀጽ 178(1)፤176(1) እና በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 244 (2)መ መሰረት በይርጋ ይታገዳል በማለት ውድቅ አድርጎታል፡፡ አመልካቾች በዚህ ባለመስማማት ይግባኛቸውን ለፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርበው ይግባኝ የቀረበለት ፍርድ ቤትም ግራ ቀኙን ካከራከረ በኋላ የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍድ ቤት የሰጠውን ብይን በማጽናት ወስኗል፡፡ ለዚህ ፍርድ መነሻ የሆነው የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡

አመልካቾች መስከረም 09 ቀን 2015 ዓ.ም ጽፈው ባቀረቡት የሰበር አቤቱታ በስር ፍርድ ቤቶች ተፈጽመዋል ያሏቸውን ስህተቶች በመዘርዘር በዚህ ችሎት እንዲታረሙላቸው ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡ የአቤቱታቸው ይዘትም በአጭሩ የስር ፍርድ ቤት ክርክር ሳይደረግበት አመልካቾች የማያውቁትንና ስለሰነዱ ሁኔታ ባላመኑበት ሁኔታ ለጉዳዩ አግባብነት የሌለውን ሰነድ ክክስ መስማት በፊት ተቀብሎ ሚያዝያ 27 ቀን 2007 እና ሚያዝያ 29 ቀን 2007 የተሰጠ ውክልና ሰነድ በመቀበል በተለይ 1ኛ ተጠሪ እስከ ዛሬ ድረስ ወ/ሮ አዜብ አሰፋ አበራ እየተባሉ የሚታወቁ እንጂ የአቶ ጥበቡ ገ/ማርያም ጋር ግንኙነት ያላቸው ስለመሆኑ ምንም አይነት ባልቀረበበት ተጠሪዎች ልጆች ናቸዉ ማለቱ ስህተት ነዉ፡፡ የመካድ ክስ ለማቅረብ የፍርድ ቤት ፈቃድ የሚያስፈልገው በሕግ አባት የተባለን ሰው የሚመለከት እንጂ ለኛ ጉዳይ ተገቢነት የለውም፡፡ እስከ ዛሬ ድረስ 1ኛ ተጠሪ ወ/ሮ አዜብ አሰፋ አበራ እየተባሉ የሚጠሩ እንጂ የአቶ ጥበቡ ገ/ማርያም ልጅ መሆናቸውን የሚገልጽ እና አመልካቾች የምናውቀው ሁኔታ ስለሌለ በይርጋ ሊቋረጥ የሚችልበት ምክንያት የለም፡፡ ተጠሪዎች በጋብቻ የተወለድን ነን በማለት ያነሱት ክርክር የህግ ግምት ሊወሰድ የሚገባው በቅድሚያ በጋብቻ ውስጥ ስለመወለዳቸው በፍሬ ነገር አልተረጋገጠም፡፡ 1ኛ እና 2ኛ ተጠሪዎች እናት እና ልጅ ሲሆኑ ከአባታችን ጋር ምንም አይነት የስጋ ዝምድና የላቸዉም፤ በማስረጃ ተጣርቶ መወሰን ሲገባው የስር ፍ/ቤቶች አግባብነት የሌለውን አንቀጽ በተሳሳተ ሁኔታ በመተርጎም የሰጡት ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት ነዉ የሚል ነዉ፡፡

ጉዳዩም በሰበር አጣሪ ችሎት ተመርምሮም የስር ፍርድ ቤቶች የጠቀሱት የቤተሰብ ህግ አንቀጾች ለዚህ ጉዳይ ተገቢ አንቀጾች መሆን አለመሆናቸዉን ግራ ቀኝ በተገኙበት አጣርቶ ለመወሰን ሲባል ያስቀርባል ተብሏል፡፡ በዚሁም መሠረት ተጠሪዎች ታህሳስ 07 ቀን 2015 ዓ.ም ባቀረቡት መልስ ተጠሪዎች እና አመልካቾች የአንድ እናት አባት ልጆች እህትና ወንድማማቾች ነን፤ አመልካቾች እና ተጠሪዎች ወላጆታችን በፀና ጋብቻ ውስጥ እያሉ ተወልደናል፤ አብረን አንድ ቤት በወላጆቻችን እቅፍ ውስጥ አድገናል፤ አመልካቾች ከ1ኛ ተጠሪ ጋር ሆነው ለ2ኛ ተጠሪ ወንድማቸው ለሆንኩት አቶ አብርሃም ጥበቡ በሰነዶች ምዝገባና ማረጋገጫ ጽ/ቤት መታወቂያቸውን ይዘው በአካል ቀርበው 2ተኛ ተጠሪ ወንድማችን ነው ጉዳያችንም አንድ ዓይነት ነው የውርስ ሃብታችን አንዲጣራ እንዲያደርግል ንብረታችን ተረክቦ እንዲያስተዳድርልን ወራሽነታችን እንዲያረጋግጥልን የሚል ውክልና ሚያዝያ 29

ቀን 2007 ዓ.ም ሲሰጡኝ እህት እና ወንድም መሆናችንን ያውቁ ነበር፤ አመልካቾች እና ተጠሪዎች አውራሾቻችን ካረፉ በኃላ በንብረት ላይ ፀብ እንዳይነሳ ሁላችንም ተወላጆች በተገኘንበት የቤተ ዘመድ ጉባኤ ሰብስቦን ንብረቱን 2ተኛ ተጠሪ ወንድማቸው እንዳስተዳደር ሚያዚያ 27 ቀን 2007 ዓ.ም በተፃፈው ቃለ-ጉባኤ ከተፈራረምንበት ግዜ አንስቶ ልጆች መሆናችንን ያውቁ ነበር፤ በፀና ጋብቻ ውስጥ የተወለዱ ልጆችን ለመካድ የሚቻለው የልጆቹን መወለድ ካወቀበት ወይም ማወቅ ከነበረበት ግዜ አንስቶ በ180 ቀናት ውስጥ የፍ/ቤቱን ፈቃድ አግኝተው መሆን እንዳለበት በተሻሻለው የቤተሰብ ሕግ አዋጅ ቁጥር 213/92 አንቀጽ 171(1) በግልጽ ተደንግጓል። በመሆኑም የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የተሸሻለው የቤተሰብ ሕግ አዋጅ ቁጥር 213/92 አንቀጽ 176(1) እና የፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 244 2(መ) ጠቅሶ ዉሳኔ መስጠቱ እንዲሁም ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤትም ይህንኑ በማጽናት የሰጠው ዉሳኔ መሰረታዊ የህግ የተፈፀመበት አይደለም በማለት ተከራክረዋል።

ከስር ጀምሮ የጉዳዩ አመጣጥ እና የግራ ቀኙ ክርክር ይዘት አጠር አጠር ባለ መልኩ ሲታይ ከፍ ሲል የተመለከተውን ሲመስል ይህ ችሎትም የሠበር አቤቱታዉን ለማስቀረብ በሰበር አጣሪ የተያዘውን ጭብጥ፣ ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና ከተገቢው የህጉ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ በሚከተለው መልኩ መርምሮታል። እንደመረመረዉም አመልካቾች በስር ፍርድ ቤት ባቀረቡት ክስ ለጠየቁት ዳኝነት መነሻ ያደረጉት ተጠሪዎች የአቶ ጥበቡ ገ/ማርያም እና የወ/ሮ ምህረት አለማየሁ ልጆች ሳይሆኑ ልጆች ነን በማለት የውርስ ሰርተፍኬት መዉሰዳቸዉን በመጥቀስ ሲሆን፣ ተጠሪዎች በበኩላቸዉ ክሱ በይርጋ ይታገዳል የሚል ክርክር በማስቀደም የሚኞች ልጆች መሆናቸዉን ጠቅሰዉ የፍሬ ነገር ክርክር ማቅረባቸዉን ለመገንዘብ ተችሏል። የስር የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትም ሆነ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ክሱ በይርጋ ይታገዳል በማለት ሲወስኑ መሠረት ያደረጉት ክሱ የመካድ ክስን የሚመለከት ነዉ በሚል ሃሳብ ስለመሆኑ ከየዉሳኔዎቹ ይዘት መገንዘብ ይቻላል። ስለሆነም ፍርድ ቤቶች ክሱ በይርጋ ይታገዳል ሲሉ የደረሱበት ድምዳሜ የአመልካቾችን የክስ ምክንያት መሠረት ያደረገ መሆን ያለመሆኑ ጉዳይ የዚህን ችሎት ምላሽ የሚያሻዉ ሆኖ ተገኝቷል።

የፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ህጉ የመጀመሪያ መቃወሚያዎች ሁሉ ተጠቃለዉ መቅረብ እንዳለባቸዉ ይደነግጋል (የህጉ አንቀጽ 244/3/ ይመለከቷል)። እንዲሁም ፍርድ ቤቱ ክስ ከሰማ በኃላ ግራ ቀኝ የተለያዩበትን የህግ እና/ወይም የፍሬ ነገር ነጥብ መሠረት በማድረግ ጭብጥ መስርቶ ወደሚቀጥለዉ የክርክር ሂደት ከመግባቱ በፊት በመጀመሪያ መቃወሚያ ላይ ብይን መስጠት እንዳለበት በህጉ አንቀጽ 245 (2) እና 246 (1) ላይ ከተመለከቱት ድንጋጌዎች መገንዘብ ይቻላል። የሥነ ሥርዓት ህጉ በዚህ ሁኔታ ሲደነግግ ማሳካት የፈለጋቸዉ የተለያዩ ዓላማዎች እንዳሉት የሚታወቅ ሲሆን ከዚህም ዉስጥ አንዱ እና መሠረታዊዉ የቀረበዉ ክስ በመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ዉድቅ የሚደረግ ከሆነ ከፍሬ ነገር ጋር በተያያዘ የግራ ቀኝን ክርክር እንዲሁም ማስረጃዎችን ለመስማት የሚባክነዉን የፍርድ ቤቱ እና የተከራካሪ ወገኖችን ወጪ፣ ጊዜ እና ድካም ለማስቀረት፣ ጉዳዩም በአጭር ጊዜ ዉስጥ መቋጫ

እንዲያገኝ በሚል ዓላማ እንደሆነ ይታመናል። በሌላ በኩል እንደነገሩ ሁኔታ በመጀመሪያ መቃወሚያ ላይ ዉሳኔ ለመስጠት ማስረጃን መስማት እና መመርመር አስፈላጊ ሊሆን የሚችልበት ሁኔታ መኖሩ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ በዋናዉ ጉዳይ ላይ ክርክር እና ማስረጃ ቀርቦበት እልባት ሊሰጥበት የሚገባዉ የክርክር ጭብጥ የመጀመሪያ መቃወሚያን ለመወሰን የክርክር ነጥብ ሊሆን የሚችልበት ሁኔታ የለም። ይልቁንም የፍሬ ነገር ክርክር የሚመረመረዉ ክሱ በመጀመሪያ መቃወሚያ ዉድቅ የማይደረግ ከሆነ ብቻ ስለመሆኑ እሙን ነዉ።

በመጀመሪያ መቃወሚያነት የሚነሱ እና ፍርድ ቤቱ የፍሬ ነገር ክርክርን አስመልክቶ ጭብጥ መስርቶ ወደሚቀጥለዉ የክርክር ሂደት ከመግባቱ በፊት መርምሮ ዉሳኔ እንዲሰጥበት ምክንያት ከሚሆኑት ዉስጥ አንዱ ይርጋ ስለመሆኑ የሚታወቅ ነዉ። ይርጋ መብትን ለማስከበር የሚቀርብ ክስን (limitation of action) ቀሪ የሚያደርግ ሲሆን፣ የሚነሳዉም ለክርክሩ መነሻ በሆነዉ ንብረት ወይም ጉዳይ ላይ ካለዉ መብት አኳያ ሳይሆን ከሳሽ የሆነዉ ወገን መብቱን ለማስከበር በምን ያህል ጊዜ ክሱን ማቅረብ እንዳለበት የሚመለከትና በህግ ተለይቶ የተመለከተዉ የክስ ማቅረቢያ ጊዜ ካለፈ ክስ የማቅረብ መብትን ቀሪ የማድረግ ዉጤት ያለዉ ነዉ። ይህም ከሳሽ የሆነዉ ወገን ክስ የሚያቀርብበት ጉዳይ ላይ መብት ቢኖረዉም በጊዜዉ ክሱን ባለማቅረቡ ብቻ ለክሱ መሠረት ካደረገዉ ጉዳይ ጋር በተያያዘ ያለዉን መብት ሊያጣ የሚችልበት ሁኔታ መኖሩን ታሳቢ ያደረገ ነዉ። ሕግ አዉጪዉ ለተለያዩ የመብት ዓይነቶች የተለያየ የይርጋ ደንብ የሚያስቀምጥ በመሆኑ አንድ ክስ በይርጋ የሚታገድ መሆን አለመሆኑን በመወሰን ረገድ ጉዳዩ የቀረበለት ፍርድ ቤት ከሳሽ በክሱ የጠቀሰዉን የክስ ምክንያት ለጉዳዩ አግባብነት ካለዉ የይርጋ ደንብ አንፃር የመመርመር ኃላፊነት እንዳለበት መገንዘቡም ተገቢ ነዉ።

ወደ ተያዘዉ ጉዳይ ስንመለስ፣ ከላይ እንደተገለጸዉ፣ የስር ፍርድ ቤቶች የአመልካቾችን ክስ ዉድቅ ያደረጉት ጉዳዩ የመካድ ክስን የሚመለከት ነዉ በሚል ሃሳብ ነዉ። በመሠረቱ የመካድ ክስ የሚቀርበዉ የልጅ አባት ነዉ ተብሎ በህግ ግምት የሚወሰድበት ሰዉ የልጁ አባት አለመሆኑን ፍርድ ቤት እንዲወስንለት የሚቀርብ ዳኝነት ስለመሆኑ በተሻሻለዉ የፌዴራል የቤተሰብ ህጉ አዋጅ ቁጥር 213/92 አንቀጽ 126 እና 167 ላይ ከተመለከቱት ድንጋጌዎች የምንገነዘበዉ ነዉ። ከመካድ ክስ ጋር በተያያዘ በቤተሰብ ህጉ ከተመለከቱት ድንጋጌዎች (አንቀጽ 167 እስከ 178 ይመለከቷል) በአጠቃላይ የምንገነዘበዉ፣ ልጁ የተጸነሰዉ ወይም የተወለደዉ የልጁ አባት በተባለዉ ሰዉ እና በልጁ እናት መካከል በህግ በታወቀ ግንኙነት (ማለትም ባልና ሚስት ወይም እንደባልና ሚስት) አብረዉ የመኖር ግንኙነት በነበረበት ወቅት ከሆነ እና በዚህም ምክንያት በህግ የልጁ አባት ነዉ ተብሎ ግምት የሚወሰድበት ሰዉ ወይም በህጉ መብት የተሰጠዉ ሌላ ሰዉ፣ የልጁ አባት ሊሆን የማይችልበትን ምክንያት አስመልክቶ በቤተሰብ ህጉ ተለይቶ ከተቀመጡት ምክንያቶች ዉስጥ አንዱን በመጥቀስ በህጉ በተመለከተዉ የጊዜ ገደብ ዉስጥ (አንቀጽ 176 ይመለከቷል) ክስ አቅርቦ ካላስወሰነ በስተቀር የአባትነት ግምቱ በማንኛዉም ጊዜ እና ሁኔታ በዘፈቀደ ሊስተባበል የማይችል መሆኑን ነዉ። ስለሆነም የመካድ ክስ የሚያቀርብ ሰዉ

በህግ የልጁ አባት እንደሆነ ግምት የሚወሰድበት ሰዉ ወይም በህግ ይህን ክስ የማቅረብ መብት የተሰጣቸዉ ሆኖ፣ ክሱ የመካድ ክስ ነዉ ለማለት የሚቻለዉም ከሳሹ የመካድ ክስ የቀረበበት ልጅ የተወለደዉ አባት ነዉ ተብሎ የህግ ግምት የተወሰደበት ሰዉ እናቱ በጋብቻ ወይም እንደባልና ሚስት አብረዉ ሲኖሩ በነበረበት ወቅት መሆኑን ተቀብሎ ነገር ግን በሌላ ምክንያት ልጁ በህግ አባቱ ነዉ የተባለዉ ሰዉ ልጅ አለመሆኑን በመጥቀስ የቀረበ ክስ ሲሆን ነዉ፡፡

ይሁንና በተያዘዉ ጉዳይ አመልካቾች ክስ ሲያቀርቡ ተጠሪዎች በጋብቻ ዉስጥ የተወለዱ መሆኑን አልጠቀሱም፡፡ ክሳቸዉ ተጠሪዎች የሚች ወላጆቻቸዉ የአቶ ጥበቡ ገብረማርያም እና የወ/ሮ ምህረት አለማየሁ ነን በማለት የወራሽነት ማረጋገጫ ማስረጃ መያዛቸዉን በመጥቀስ ነዉ፡፡ ምንም እንኳ በክሳቸዉ የጠየቁት ዳኝነት ተጠሪዎች የሚች ወላጆቻቸዉ አቶ ጥበቡ ገብረማርያም እና የወ/ሮ ምህረት አለማየሁ ልጆች አይደሉም ተብሎ ይወሰንልን የሚል ቢሆንም፣ ክሱ ተጠሪዎች በጋብቻ ዉስጥ የተወለዱ ስለመሆኑ ዕዉቅና ባልሰጠበት ሁኔታ የአመልካቾች ክስ የመካድ ክስ ነዉ ለማለት አይቻልም፡፡ በመሆኑም የስር ፍርድ ቤቶች ተጠሪዎች በጋብቻ ዉስጥ የተወለዱ መሆን አለመሆኑ እና በጋብቻ ዉስጥ ተወልደዋል ከተባለ ህጋዊ ዉጤቱ ምንድን ነዉ የሚለዉ ነጥብ ይርጋን አስመልክቶ የቀረበዉ ክርክር ዉድቅ ከተደረገ በኋላ ግራ ቀኝ በሚያቀርቧቸዉ ክርክሮች እና ማስረጃዎች መሠረት ተጣርቶ ዉሳኔ ሊሰጥበት የሚገባ የስረ ነገር ጭብጥ ነዉ፡፡ ከዚህ ዉጪ፣ የአመልካቾች የክስ ይዘት ሲታይ የመካድ ክስ ባልሆነበት ሁኔታ፣ ተጠሪዎች በጋብቻ ዉስጥ የተወለዱ መሆናቸዉን የሚሳይ ማስረጃ መቅረቡ (በእርግጥ ቀርቧል ወይስ አልቀረበም የሚለዉ ነጥብ እንደተጠበቀ ሆኖ) የቀረበዉ ክስ ልጅነትን እንደ መካድ ክስ ተወስዶ ክሱ በይርጋ ቀሪ ለማድረግ ምክንያት ሊሆን አይችልም፡፡

ከዚህ ሁሉ አንፃር ሲታይ የአመልካቾች ክስ በቤተሰብ ህጉ አንቀጽ 176 መሠረት በይርጋ ይታገዳል በማለት በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ተሰጥቶ በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የጸናዉ ዉሳኔ፣ የአመልካቾችን ክስ መሠረታዊ ባህርይ እና ይዘቱን ያገናዘበ ባለመሆኑ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡ ስለሆነም ተከታዩ ተወስኗል፡፡

ዉሳኔ

1. የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 135974 ላይ መጋቢት 12 ቀን 2014 ዓ.ም በዋለዉ ችሎት የሰጠዉ ብይን እንዲሁም የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 289961 ላይ ነሐሴ 12 ቀን 2014 ዓ.ም በዋለዉ ችሎት የሰጠዉ ዉሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥርዓት ህጉ አንቀጽ 348(1) መሠረት ተሽረዋል፡፡
2. የአመልካቾች ክስ በይርጋ አልታገደም ተብሎ ተወስኗል፡፡

3. የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ተዘግቶ የነበረዉን መዝገብ በማንቀሳቀስ፣ ተጠሪዎች ከሚች አቶ ጥበቡ ገብረማርያም እና ከሚች ወ/ሮ ምህረት አለማየሁ የተወለዱ መሆን አለመሆናቸዉን አስመልክቶ ግራ ቀኝ በሚያቀርቡት ክርክር እና ማስረጃ ላይ በመንተራስ መርምሮ አግባብ ነዉ የሚለዉን ዉሳኔ እንዲሰጥ ጉዳዩ በፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ህጉ አንቀጽ 341(1) መሠረት ተመልሶለታል፡፡

4. በዚህ ችሎት የተደረገዉ ክርክር ያስከተለዉን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኝ የየራሳቸዉን ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

መ/ዐ

የመ.ቁ.238021

ሐምሌ 25/2015 ዓ.ም

ዳኞች፡- ተፈሪ ገብሩ(ዶ/ር)

እንዳሻው አዳነ

ተሾመ ሽፈራው

መላኩ ካሳዬ

ነፃነት ተገኝ

አመልካች፡- ወ/ሪት አብነት ሐብታሙ ካሴ - ጠ አቶ ውቤ አለነ - ቀረቡ

ተጠሪ፡ - ህፃን ናፍቆት ሐብታሙ ካሴ - ጠ አቶ ዘላለም ሙሉነህ - ቀርበዋል

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍርድ

ጉዳዩ ልጅን ለመካድ በሚል የቀረበ ክስን መነሻ አድርጎ የተነሳ ክርክርን የሚመለከት ነው፡፡ ለዚህ ሰበር ሰሚ ችሎቱ የቀረበውም የአሁን ተጠሪ በህግ እውቅና ከሚሰጠው ግኑኝነት ውጭ የተወለደች ስለመሆኑ ተመልክቶ እያለ አመልካች ያቀረቡት ክስ እንደመካድ ክስ ተቆጥሮ ክሱን ለማቅረብ የፍርድ ቤት ፈቃድ ያስፈልጋል በሚል ውድቅ የተደረገበትን አግባብ መርምሮ ለመወሰን ነው፡፡

ክርክሩ የተጀመረው የአሁን አመልካች ጥር 30/2014 ዓ.ም ፅፈው በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በአሁን ተጠሪ ላይ ባቀረቡት ክስ ነው፡፡ የክሱም ጭብጥ የአሁን ተጠሪ ሞግዚትና አሳዳጊ(እናት) የሆኑት ወ/ሮ ትዕግስት ጣሰው ከአመልካች ወላጅ አባታቸው አቶ ሀብታሙ ካሴ ጋር በጋብቻም ሆነ ከጋብቻ ውጭ እንደ ባልና ሚስት አብሮ የመኖር ግኑኝነት ሳይኖራቸው ሚች አባታቸው ከሞቱ 6 ወር በኋላ የተወለዱትን የአሁን ተጠሪን ከሚቹ የወለዱ መሆኑን ጠቅሰው ከፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የወራሽነት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ወስደው የሚች ውርስ እንዲጣራላቸው ለፍርድ ቤት አቤቱታ በማቅረባቸው ስለጉዳዩ ያወቁ መሆኑን፣ ይህንኑ ተከትሎ የወራሽነት ማስረጃውን ለሰጠው ፍርድ ቤት የመቃወም አቤቱታ ያቀረቡ ቢሆንም ፍርድ ቤቱ ተገቢ የመካድ ክስ ቀርቦ ተጠሪ የሚቹ ልጅ አለመሆናቸው ባልተወሰነበት የመቃወም አቤቱታው ሊቀርብ እንደማይችል በመጥቀስ ይኸው እስኪረጋገጥ ድረስ በሚል መዝገቡ የተዘጋ መሆኑን፣ የተጠሪ ሞግዚትና አሳዳጊ(እናት) ከሚች ጋር በህግ የታወቀ ግኑኝነት ሳይኖራቸው እንዲሁም ሚች የአሁን ተጠሪ ልጇ ናቸው በሚል አባትነታቸውን አምነው ባልተቀበሉበት ተወልጃለሁ መባሉ አግባብ አለመሆኑን እና አመልካችም የሚክዱት መሆኑን በመጥቀስ የDNA ምርመራ ተደርጎ ተጠሪ የሚች ልጅ አይደለችም ተብሎ እንዲወሰን ዳኝነት የሚጠይቅ ነው፡፡

በዚሁ ክስ ላይ መልስ እንዲሰጥ በታዘዘው መሰረት የአሁን ተጠሪ ሞግዚትና አሳዳጊ(እናት) በሰጡት መልስ ከሚች አቶ ሀብታሙ ካሴ ጋር በጋብቻ አልያም ከጋብቻ ውጭ እንደባልና ሚስት አብሮ የመኖር ግኑኝነት ያልነበራቸው ቢሆንም ከ3 ዓመት በላይ የቆየ የፍርቅ ግኑኝነት የነበራቸው እና ተጠሪም በዚሁ ግኑኝነት ውስጥ የተወለደች መሆኑን፤ ይኸው ለመሆኑም የሰው እና የሰነድ ማስረጃዎችን አቅርበው በማረጋገጥ የወራሽነት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀቱ የተሰጣቸው መሆኑን፤ የቀረበው ማስረጃ በቂ አይደለም የሚባል ከሆነ ከሚቹ አስከሬን ላይ ናሙና ተወስዶ የተጠየቀው ምርመራ ቢከናወን የማይቃወሙ መሆኑን በመግለፅ ተከራክረዋል፡፡

ጉዳዩ የቀረበለት ፍርድ ቤትም የግራ ቀኙ ክርክር ከመረመረ በኋላ በሰጠው ውሳኔ በተሻሻለው የቤተሰብ ህግ የመካድ ክስ ማቅረብ የሚችለው በህግ ግምት "አባት ነህ" የተባለው ሰው ብቻ መሆኑን፤ የአሁን ተጠሪ ከጋብቻ እና ጋብቻ ሳይኖር እንደ ባልና ሚስት አብሮ ከመኖር ግኑኝነት ውጭ በሆነ ሁኔታ ውስጥ የተወለደች ስለመሆኑ ክርክሩ የሚያሳይ በመሆኑ የአመልካች አባት(ሚች) በህግ ግምት የተጠሪ አባት ነው የሚባል ሰው ባለመሆኑ የመካድ ክስ ለማቅረብ የሚቻልበት የህግ መሰረት የሌለ መሆኑን፤ የመካድ ክሱ ሊቀርብ ይችላል የሚባል ቢሆን እንኳን ክሱን ለማቅረብ የፍርድ ቤት ፈቃድ የሚያስፈልግ በመሆኑ አመልካች ፈቃድ ሳያገኙ የመካድ ክስ ማቅረባቸው ከህግ አግባብ ውጭ ነው በማለት ክሱ ውድቅ አድርጓል፡፡ አመልካች ይህንኑ በመቃወም ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የይግባኝ አቤቱታ ያቀረቡ ቢሆንም ፍርድ ቤት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህግ ቁጥር 337 መሰረት ይግባኙን ዘግቷል፡፡

የአሁን የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ በመቃወም ነው፡፡ አመልካች ህዳር 29/2015 ዓ.ም በተፃፈ የሰበር አቤቱታ በስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ እና ትዕዛዝ ላይ ተፈፅሟል ያሉትን መሰረታዊ የህግ ስህተት ጠቅሰው በዚህ ችሎት እንዲታረምላቸው ጠይቀዋል፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ ከላይ በዚህ ፍርድ መግቢያ ላይ የተመለከለተውን ነጥብ ተጠሪ በተገኙበት አጣርቶ ለመወሰን ሲባል ያስቀርባል ተብሎ ግራ ቀኙ በጽሁፍ እንዲከራከሩ ተደርጓል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ እና መሰረታዊ የክርክሩ ይዘት ጠቅለል ባለ መልኩ ከላይ የተመለከተውን ሲመስል ችሎቱም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው የስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ እና ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸው ሕጎች ጋር በማገናዘብ መርምሯል፡፡

በመሰረቱ አባትነትን ከማረጋገጥ ጋር በተያያዘ "የአንድ ህፃን አባት ማነው?" ለሚለው ጥያቄ የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አዋጅ ቁጥር 213/1992 ሶስት አበይት ማረጋገጫ መንገዶችን ዘርግቷል፡፡ እነዚህም አንደኛው "የልጁ አባት እገሌ ነው" በሚል ህጉ በራሱ የሚወስደው ግምት ነው፡፡ ሁለተኛው "የልጁ አባት እኔ ነኝ" በሚል በገዛ ፈቃድ ልጅነትን በመቀበል በሚደረግ

መተማማኛ ሲሆን ሶስተኛ እና የመጨረሻው ደግሞ “የልጁ አባት እገሌ ነው” በሚል ፍርድ ቤት በሚሰጠው ውሳኔ ስለመሆኑ ከአንቀፅ 126 እና ተከታዮቹ ድንጋጌዎች ይዘት መገንዘብ ይቻላል፡፡

የቤተሰብ ህጉ አባትነትን አስምልክቶ የዚህ ዓይነት የህግ ግምት የሚወስደው ልጁ በሚፀነስበት ወይም በሚወለድበት ጊዜ በልጁ እናት እና በአንድ ወንድ መካከል በህግ የታወቀ ግኑኝነት መኖሩ ሲረጋገጥ እንደሆነ፤ በዚህ መልኩ በህግ እውቅና የተሰጠው ግኑኝነትም ጋብቻ እና ጋብቻ ሳይኖር እንደባልና ሚስት አብሮ የመኖር ግኑኝነት ብቻ ስለመሆኑ የቤተሰብ ህጉ አንቀፅ 126 እና 130 ድንጋጌዎች ይዘት ያስገነዝባሉ፡፡ ከእነዚህ ሁለቱ ግኑኝነቶች ውጭ በሆነ ሁኔታ በእናቲቱ እና በአንድ ወንድ መካከል በተደረገ የግብረ ስጋ ግኑኝነት የተወለደ ልጅን ጉዳይ አስመልክቶ አባትነቱ ሊረጋገጥ የሚችለው በተቀሩት ሁለቱ ማረጋገጫ መንገዶች ይሆናል ማለት ነው፡፡

በእርግጥ በአባት በኩል ያለውን መወለድ ለማረጋገጥ የቤተሰብ ህጉ እነዚህን ሶስት አማራጭ መንገዶችን ያስቀመጠ ቢሆንም በቀጥታም ሆነ በፍርድ ቤት ፈቃድ የመካድ ክስ ለማቅረብ የተፈቀደው በህግ ግምት “አባት ነህ” ለተባለው ሰው ብቻ ስለመሆኑ ከቤተሰብ ህጉ አንቀፅ 168፣ 170 እና 174 ድንጋጌዎች ጣምራ ንባብ መገንዘብ ይቻላል፡፡ በሌላ አነጋገር አባትነትን ፈቅዶ የተቀበለ እና በፍርድ ቤት ውሳኔ “አባት ነህ” የተባለው ሰው ወይም ከዚሁ ሰው መብቱ የተላለፈለት ሰው የመካድ ክስ ለማቅረብ ህግ አይፈቅድለትም ማለት ነው፡፡

አሁን በቀረበው ጉዳይ አመልካች ለአሁኑ ክርክር ምክንያት የሆነውን ክስ ያቀረቡት የተጠሪን የወራሽነት ማስረጃ በመቃወም ያቀረቡት አቤቱታ ውድቅ ተደርጎ የመካድ ክስ እንዲቀርብ ማስረጃውን በሰጠው ፍርድ ቤት በመታዘዙ ምክንያት መሆኑን በክሰ አቤቱታቸው ገልፀዋል፡፡ ክሱ ልጅን ለመካድ እንደቀረበ የተመለከተ ቢሆንም ዝርዝር ይዘቱ የአሁን ተጠሪ በህግ በታወቀ ግኑኝነት ውስጥ ያልተወለደች እንዲሁም ሟች ልጅነትዋን አምኖ ያልተቀበለ በመሆኑ የሟቹ ልጅ ናት ልትባል አይገባም የሚል መሆኑን ያስገነዝባል፡፡ ተጠሪ በህግ ጥበቃ በሚደረግለት ግኑኝነት ውስጥ ያልተወለደች ስለመሆኑ የተጠሪ ሞግዚትና አሳዳጊ(እናት) በራሳቸው የተቀበሉት ጉዳይ ነው፡፡ ይህ ከሆነ ደግሞ የተጠሪ አባት ናቸው የተባሉት ግለሰብ የአባትነት ጉዳይ በህግ ግምት የሚወሰድበት ባለመሆኑ የተጠሪን መወለድ ለመቃወም የሚቀርብ ክስ አባትነትን ስለመካድ በሚቀርበው አኳኋን ሊሆን ይገባል የሚባልበት የህግ መሰረት የለም፡፡

የተጠሪን ተወላጅነት ለመቃወም የመካድ ክስ ማቅረብ የማያስፈልግ ከሆነ ደግሞ የፍርድ ቤት ፈቃድ የሚጠየቅበት ህጋዊ ምክንያት አይኖርም፡፡ ከላይ እንደተመለከተው አመልካች ያቀረቡት ክስ አርእስቱ ልጅን ከመካድ ክስ ጋር የተያያዘ መሆኑን የሚጠቁም ቢሆንም ዝርዝር ይዘቱ በመካደ ክስ የማይስተናገድ መሆኑን ያረጋግጣል፡፡ በፍትሓ ብሔር ሥነ ሥርዓት ህጉም ቢሆን ከባለጉዳዮች የሚጠበቀው ለዳኝነት ጥያቄያቸው መሰረት የሆነው ፍሬ ነገር በግልፅ መጥቀስ ብቻ

ሲሆን ከተጠቀሰው ፍሬ ነገር አኳያ ዳኝነቱ በየትኛው የህግ ማዕቀፍ እንደሚዳኝ የመለየት እና የቀረበውን ክርክር ከዚሁ አኳያ አቃንቶ ሙግቱን የመምራት ኃላፊነቱ የፍርድ ቤቱ ይሆናል።

ከዚህ አኳያ የአሁን ተጠሪ የተወለደችው አባትነት በህግ ግምት ከሚረጋገጥበት እና በህግም እውቅና ከሚሰጠው ግኑኝነት ውጭ በመሆኑ የተነሳ አመልካች ያቀረቡት ክሰ በመካድ ክስ የሚስተናገድ እንዳልሆነ ክሱ የቀረበለት የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በራሱ የተቀበለው ስለመሆኑ በውሳኔው ገልጿል። ፍርድ ቤቱ ይህንን ከተቀበለ ከቀረበው ክርክር አኳያ ዳኝነቱን በማቃናት፤ አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘም ክሱ ተሻሽሎ እንዲቀርብ በማድረግ የግራ ቀኙን ክርክር እና ማስረጃን መርምሮ መወሰን ሲገባው ክሱን ለማቅረብ በህግ ያልተመለከተን ቅድመ ሁኔታ ጠቅሶ ውድቅ ማድረጉ፤ እንዲሁም ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት ጉዳዩን ከዚሁ አኳያ ማረም ሲገባው በትዕዛዝ ማፅናቱ የክርክሩን ይዘት እና ከዚሁ በተጓዳኝ ያለውን የህግ ማዕቀፍ መሰረት ያላደረገ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ ተገኝቷል። በመሆኑም ተከታዩ ውሳኔ ተሰጥቷል።

ውሳኔ

1. የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁ/138158 ላይ ግንቦት 05/2014 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ እና ይህንኑ በማፅናት የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ/294567 ላይ ጥቅምት 21/2015 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጠው ትዕዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁጥር 348(1) መሰረት ተሽረዋል።
2. የአሁን ተጠሪ ከሚች አቶ ሐብታሙ ካሴ ተወልዳለች የተባለው በቤተሰብ ህጉ አባትነትን በህግ ግምት ለማረጋገጥ እውቅና ከተሰጠው የወንድ እና ሴት ግኑኝነት ውጭ በሆነ ፆታዊ ግኑኝነት ውስጥ ስለመሆኑ የተገለፀ በመሆኑ ጉዳዩ ልጅን በመካድ ክስ የሚስተናገድ አይደለም፤ ተወላጅነቷንም ለመቃወም የፍርድ ቤት ፈቃድ አያስፈልገውም።
3. የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በውሳኔ የዘጋውን መዝገብ በማንቀሳቀስ ከሚች አቶ ሐብታሙ ካሴ አስከሬን ላይ ናሙና ተወስዶ ከተጠሪ ደም ጋር በማመሳከር የዘር ባህሪ ወሳኝ ቅንጣት (DNA) ምርመራ እንዲደረግ በማዘዝ የሚገኘውን ውጤት በግራ ቀኙ ከቀረቡት ማስረጃዎች ጋር አገናዝቦ በመመርመር ሚች አቶ ሐብታሙ ካሴ የተጠሪ አባት ነው? ወይስ አይደለም? በሚለው ነጥብ ላይ እንዲወስን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህግ ቁጥር 341(1) መሰረት ጉዳዩ ይመለስለት።

ትዕዛዝ

1. የዚህን ሰበር ሰሚ ችሎት ክርክር ወጪ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ።

2. በዚህ መዝገብ ላይ የተሰጠ የእግድ ትዕዛዝ ካለ ተነስቷል፡፡ ይፃፍ፡፡

3. መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአራት ዳኞች ፊርማ አለበት

<u>የልዩነት ሃሳብ</u>

እኔ በተራ ቁጥር ሦስት ላይ የተሰየምኩት ዳኛ የአመልካችን ክስ ውድቅ በማድረግ በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ተሰጥቶ በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በትዕዛዝ በጸናው ውሳኔ የተፈጸመ በዚህ ችሎት ሊታረም የሚችል መሠረታዊ የህግ ስህተት የለም የሚል ሃሳብ ስላለኝ ከአብላጫው ድምጽ በሃሳብ ተለይቻለሁ፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ እንደሚቻለው አመልካች በስር ፍርድ ቤት ባቀረቡት ክስ የጠየቁት ዳኝነት ተጠሪ የሚች ልጅ አይደለም ተብሎ ይወሰንልኝ የሚል ነው፡፡ ይህ የአመልካች ዳኝነትም የመካድ ክስን የሚመለከት ነው፡፡ አመልካች ለዚህ ዳኝነታቸው መሠረት ያደረጉትም ሚች አቶ ሀብታሙ ካሴ ከመሞታቸው በፊት የተጠሪ ሞግዚትና አሳዳጊ (እናት) ከሆኑት ከወ/ሮ ትግስት ጣሰው ጋር በጋብቻም ሆነ ከጋብቻ ውጪ እንደባልና ሚስት ሆነው አብረው ኖረው አያውቁም የሚል ስለመሆኑ የስር ፍርድ ቤት ውሳኔ ግልባጭ ያሳያል፡፡ ይህ የአመልካች የክስ ምክንያትም ሆነ የዳኝነት ጥያቄ ግልጽ እና የማያሻማ፣ በጉዳዩ ላይ ፍትሐዊ ውሳኔ ለመስጠትም አስቸጋሪ ባለመሆኑ በፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ህጉ አንቀጽ 91(1) ላይ በተመለከተው አግባብ ፍርድ ቤቱ በእራሱ አነሳሽነት አመልካች የክስ አቤቱታቸውን እንዲያሻሽሉ ትዕዛዝ እንዲሰጥ የሚጋብዝ አይደለም፡፡ ይልቁንም ለተጠየቀው ዳኝነት ከተጠቀሰው ምክንያት አንፃር የፍርድ ቤቱ ሚና አመልካች ለጠየቁት የልጅነት መካድ ዳኝነት የጠቀሱት ግልጽ ምክንያት በህግ አግባብ ተቀባይነት ያለው መሆን አለመሆኑን ነው፡፡

በመሠረቱ የመካድ ክስ የሚቀርበው የልጅ አባት ነው ተብሎ በህግ ግምት የሚወሰድበት ሰው የልጁ አባት አለመሆኑን ፍርድ ቤት እንዲወስንለት የሚቀርብ ዳኝነት ስለመሆኑ በተሻሻለው የፌዴራል የቤተሰብ ህጉ አዋጅ ቁጥር 213/92 አንቀጽ 126 እና 167 ላይ ከተመለከቱት ድንጋጌዎች የምንገነዘበው ነው፡፡ በቤተሰብ ህጉ ከአንቀጽ 167 እስከ 178 ከተመለከቱት ድንጋጌዎች መገንዘብ እንደሚቻለው፣ የመካድ ክስ የሚያቀርብ ሰው የመካድ ክስ የቀረበበት ልጅ የተጸነሰው ወይም የተወለደው የልጁ አባት በተባለው ሰው እና በልጁ እናት መካከል በህግ በታወቀ ግንኙነት (ማለትም ባልና ሚስት ወይም እንደባልና ሚስት) አብረው የመኖር ግንኙነት በነበረበት ወቅት መሆኑን እንዲሁም በህግ ግምት የልጅ አባት ነው የተባለው ሰው የልጁ አባት ሊሆን የማይችልበትን ምክንያት አስመልክቶ በቤተሰብ ህጉ ተለይቶ ከተቀመጡት ምክንያቶች ውስጥ አንዱን እንዲጠቅስ ይጠበቃል፡፡ ስለሆነም ከሳሽ ያቀረበውን የመካድ ክስ ከመቀበሉ በፊት፣ ፍርድ ቤቱ ከሳሽ በክሱ የጠቀሰው ምክንያት ሲታይ የመካድ ክስ ዳኝነትን ሊያሰጥ የሚችል መሆን አለመሆኑን በቤተሰብ ህጉ ላይ ከተመለከቱት አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች

ጋር በማገናዘብ የመመርመር ኃላፊነት አለበት፡፡ በዚህ መሠረት መርምሮም ከሳሽ ለጠየቀዉ የመካድ ክስ መሠረት ያደረገዉ ምክንያት የተጠየቀዉን የልጅነት መካድ ዳኝነት ሊያሰጥ የሚችል መሆኑን የተረዳ እንደሆነ ልጁ በህግ ግምት የልጅ አባት ነዉ የተባለዉ አባት ሊሆን የማይችልበት ሁኔታ መኖር አለመኖሩን ከግራ ቀኝ ክርክር አንፃር መርምሮ እና አጣርቶ ዉሳኔ መስጠት ያለበት ሲሆን፣ ከሳሹ በክሱ የጠቀሰዉ ምክንያት የልጅነት መካድ ዳኝነት የማያሰጥ መሆኑን የተረዳ እንደሆነ ተከሳሽን መጥራት ሳያስፈልገዉ በፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ህጉ አንቀጽ 231(1/ሀ) መሠረት ክሱን ዉድቅ ሊያደርግ ይገባል፡፡

ከዚህ አንፃር የተያዘዉን ጉዳይ ስንመለከት አመልካች ያቀረቡት የመካድ ክስ ቢሆንም፣ ከላይ እንደተጠቀሰዉ፣ በክስ ምክንያታቸዉ ተጠሪ የተወለዱት በሚች እና በተጠሪ እናት ወ/ሮ ትግስት ጣሰዉ መካከል በህግ የታወቀ ግንኙነት ባልነበረበት ወቅት መሆኑን ገልጸዋል፡፡ ይህ የአመልካች የክስ ምክንያት ደግሞ ከፍ ሲል በጠቀስኩት ምክንያት የልጅነት መካድ ዳኝነት የሚያሰጥ አይደለም፡፡ በመሆኑም ተጠሪን መጥራት ሳያስፈልገዉ ፍርድ ቤቱ የአመልካችን ክስ በፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ህጉ አንቀጽ 231(1/ሀ) መሠረት ዉድቅ ማድረግ ነበረበት፡፡ የስር ፍርድ ቤት፣ ምንም እንኳን ክሱን በዚህ አግባብ ባይሰርዝም፣ ግራ ቀኝን ካከራከረ በኋላ አመልካች የመካድ ክስ ለማቅረብ የሚያስችል የህግ መሠረት የሌላቸዉ መሆኑን ጠቅሶ ክሱን ዉድቅ አድርጎታል፡፡ ይህ የፍርድ ቤቱ ዉሳኔ የልጅነት መካድ ክስ የሚቀርብበትንና ፍርድ ቤቱም ተቀብሎ ሊወስን የሚችልበትን ሁኔታ አስመልክቶ ከፍ ሲል የተመለከቱትን የቤተሰብ ህጉን ድንጋጌዎች ያገናዘበ ሆኖ አግኝቸዋለሁ፡፡

በሌላ በኩል የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ስልጣን መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመባቸዉን ዉሳኔዎች በማረም ላይ የተገደበ ስለመሆኑ በኢፌዲሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 80(3/ሀ) ላይ ከተመለከተዉ ድንጋጌ መገንዘብ ይቻላል፡፡ የፌዴራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀጽ 10 ላይ የተመለከተዉ ድንጋጌም ይህንኑ የሚያሳይ ሲሆን፣ አዋጁ በአንቀጽ 2(4) ላይ መሠረታዊ የህግ ስህተትን አስመልክቶ ትርጓሜ ይሰጣል፡፡ በዚህም መሠረት አንድ ዉሳኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነዉ ለማለት የሚቻለዉ በአዋጁ አንቀጽ 2(4/ ሀ-ሸ) ከተመለከቱት ሁኔታዎች ዉስጥ አንዱን በመጣስ የተሰጠ ዉሳኔ ሆኖ ዉሳኔዉም ፍትሕን የሚያዛባ ጉልህ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ ሲገኝ ስለመሆኑ ከድንጋጌዎቹ ይዘት መገንዘብ ይቻላል፡፡ ከዚህ አንፃር ሲታይ የፌዴራል የአመልካችን ዳኝነት ዉድቅ በማድረግ በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ተሰጥቶ በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በትዕዛዝ በጸናዉ ዉሳኔ ላይ የተፈጸመ በዚህ ችሎት ሊታረም የሚችል መሠረታዊ የህግ ስህተት የለም፡፡

አብላጫዉ ድምጽ የስር ፍርድ ቤቶችን ዉሳኔ ሲሽር የጠቀሰዉ መሠረታዊ ምክንያት ፍርድ ቤቱ ዳኝነቱን በማቃናት አስፈላጊ ከሆነም አመልካች ክሳቸዉን እንዲያሻሽሉ በማድረግ ማስረጃን ሰምቶ

መወሰን ነበረበት በማለት ነዉ። ይሁንና በአገራችን የፍትሐብሔር ክርክር አመራር ረገድ የፍርድ ቤቶች ሚና ግራ ቀኝ ተከራካሪዎች ያቀረቧቸዉን ክርክሮች እና ማስረጃዎች መሠረት ያደረገ ዉሳኔ ከመስጠት ዉጪ በእራሱ አነሳሽነት የግራ ቀኙን ክርክር እና ማስረጃ ሊያቃና የሚችልበት ሁኔታ የለም፤ ሊኖረዉም አይገባም። በርግጥ ፍርድ ቤት በእራሱ አነሳሽነት ክስ ወይም መልስ ተሻሽሎ እንዲቀርብ ማድረግ የሚችል ሲሆን፣ ይህም የሚሆነዉ የቀረበዉ ክስ ወይም መልስ ግልጽ ካልሆነ እና ፍትሐዊ ዉሳኔ ለመስጠት አስቸጋሪ መስሎ ከታየዉ ስለመሆኑ በህጉ አንቀጽ 91(1) ላይ ከተመለከተዉ ድንጋጌ ይዘትና መንፈስ መገንዘብ ይቻላል። በመሆኑም በተያዘዉ ጉዳይ፣ የአመልካች የክስ ምክንያትም ሆነ የተጠየቀዉ ዳኝነት ግልጽ ከመሆኑ አኳያ ፍርድ ቤቱ አመልካች ክሳቸዉን እንዲያሻሽሉ በማድረግ ክርክሩ እንዲቃና ሊያደርግ የሚችልበት ምክንያት የለም። በዚህ ሁሉ ምክንያት ከሌሎች የስራ ባልደረቦቼ በሃሳብ ተለይቻለሁ።

የማይነበብ የአንድ ዳኛ ፊርማ አለበት

ፅ/ወ

የዳኝነት ስልጣን

የሰ/መ/ቁ፡-196411

ቀን፡- ሰኔ 23 ቀን 2013 ዓ.ም

ዳኞች፡- ብርሃኑ አመነው

ተሾመ ሽፈራው

ሀብታሙ እርቅይሁን

ብርሃኑ መንግስቱ

ነፃነት ተገኝ

አመልካች ፡- 1. ወ/ሪት መሠረት አማረ

2. አቶ ፍጹም አማረ

3. አቶ ተወልደ አማረ - ቀረቡ

4. ወ/ሪት ገነት አማረ

5. ወ/ሪት ራሔል አማረ

6. አቶ ሚካኤል አማረ

7. ወ/ሪት ሳባ አብርሃም

8. አቶ ዘላለም አማረ

9. አቶ ነፃነት አብርሃም

10. ወ/ሮ ምጽላል አባይ

ተጠሪ፡- አቶ ክብሮም አሮን - ጠበቃ ሙሉቀን ልመንህ - ቀረቡ

መዝገቡ ተምርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሠጠ፡፡

ፍርድ

የሰበር አቤቱታው የቀረበው የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሠጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሞበታል በሚል ነው፡፡ የክርክሩን አመጣጥ ከሥር ፍርድ ቤት የመዝገብ ግልባጭ እንደተረዳነው አመልካቾች በሥር ፍርድ ቤት ተከሳሾችና የተከሳሽ ከሳሽነት ክስ አቅራቢዎች ሲሆን ተጠሪ ከሳሽ ነበሩ፡፡ ተጠሪ ያቀረቡት ክስ በአዲስ አበባ ከተማ ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክፍለ ከተማ ወረዳ 09 የቤት ቁጥር 202 የሆነ ቤት አመልካቾች እንዲያስረክቡ እንዲወሰንላቸው ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡ አመልካቾች ለክሱ መልስ ካቀረቡ በኋላ በዚህ ችሎት ደረጃ አከራካሪ ሆኖ የቀረበው የተከሳሽ ከሳሽነት ክስ አቅርበዋል፡፡ የክሱ ይዘትም የአመልካቾች ወላጆች የጋራ ንብረት በሆነው በኤርትራ ሀገር አሰብ ከተማ የሚገኘው የቤት ቁጥሩ ሲ/385 እና ተጠሪ ክስ ያቀረበቡት ቤት ጋር መስከረም 02 ቀን 1991 ዓ/ም የቤት ልውውጥ ውል የተደረገ በመሆኑ ውሉ እንዲፈርስ እንዲወሰን፣ ኤርትራ አሰብ ከተማ የሚገኘውን ቤት ተጠሪ እንዲያስረክቡ እና ተጠሪ ክስ ያቀረቡበትን ቤት ከተረከብን በኋላ ለዕድሳት ያወጣነውን ብር 50,000.00 ተጠሪ እንዲተኩልን እንዲወሰንልን የሚል ነው፡፡ ተጠሪ ለቀረበው የተከሳሽ ከሳሽነት ክስ ባቀረቡት መልስ ኤርትራ ሀገር የሚገኝ ቤት በዚህ ሀገር ፍርድ ቤት ሊታይ አይችልም የሚሉና ሌሎች ክርክሮችን አቅርበዋል፡፡

የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት አመልካቾች ባቀረቡት የተከሳሽ ከሳሽነት ክስ ላይ የቀረበውን የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያውን በመመርመር ክሱ በኢትዮጵያ ውስጥ የተደረገ ውል ይፍረስልኝ የሚል ነው፡፡ የውሉ መሠረት ኤርትራ አገር የሚገኝ ቤትን የሚመለከት ሲሆን ተጠሪም ኤርትራዊ እንደመሆናቸው ጉዳዩ የግለሰብ ዓለምአቀፍ ሕግ ጥያቄ የሚያስነሳ በመሆኑ ፍርድ ቤት ሊመለከተው ይችላል፡፡ ነገር ግን የውሉ መነሻ የሆነው ቤት ኤርትራ አገር የሚገኝ በመሆኑ ክሱ ሊቀርብ የሚገባው ንብረቱ ባለበት አገር ሊሆን ይገባል፡፡ በሌላ በኩል አመልካቾች ክሱ በቀረበበት ጉዳይ መብትና ጥቅም ያላቸው መሆኑን አራጋግጠው ክሱን አላቀረቡም፡፡ እንዲሁም የውል ይፍረስልኝ ክሱ በ10 ዓመት ጊዜ ስላልቀረበ ክሱ በይርጋ ቀሪ ነው በማለት ወስኗል፡፡ አመልካቾች ይግባኙን ለፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት አቅርበው ፍርድ ቤቱ ግራቀኙን በፍብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 25 መሠረት የማይንቀሳቀስ ንብረትን የሚመለከት ክርክር የሚቀርበው ንብረቱ በሚገኝበት ቦታ በመሆኑ የሥር ፍርድ ቤት ሥልጣን የለኝም ማለቱ ተገቢ ነው፡፡ ነገር ግን ጉዳዩን ለመመልከት ሥልጣን የለኝም ካለ በኋላ አመልካቾች መብትና ጥቅም የላቸውም፤ ክሱ በይርጋ ቀሪ ነው ማለቱ ተገቢ ባለመሆኑ ሊታረም ይገባል በማለት ውሳኔው አሻሽሎ ወስኗል፡፡

ይህ የሰበር አቤቱታ የቀረበው በዚህ ውሳኔ ነው፡፡ የአመልካቾች የሰበር አቤቱታ ይዘትም ክስ ያቀረብነው አዲስ አበባ የተደረገ ውል እንዲፈርስ ነው፣ ውሉ ሲፈርስ ወደነበርንበት ስለምንመለስ በውሉ የተገኘው አዲስ አበባ የሚገኘውን ቤት ልናስረክብና አሰብ ከተማ የሚገኘው ቤት ተጠሪ ሊያስረክቡን እንጂ በቀጥታ አሰብ ከተማ ያለው ቤት ላይ ክስ አላቀረብንም፡፡ ውል ይፍረስልኝ ክስ በፍብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 24 መሠረት የሚታይ ነው፡፡ የግለሠብ ዓለምቀአፍ ሕግን የሚመለከት አይደለም፤ ይመለከታል ቢባል እንኳን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ጉዳዩን ለመመልከት ሥልጣን አለው የሚል ሲሆን የሰበር አጣሪ ችሎት ጉዳዩን ተመልክቶ ኢትዮጵያ ውስጥ የተደረገው የቤት ልውውጥ ውል እንዲፈርስ የቀረበው ክስ ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን ለመመልከት ሥልጣን የለኝም ማለቱ ሕጋዊነቱን ለማጣራት ተጠሪ መልስ እንዲያቀርቡ አሏል፡፡ ተጠሪ ያቀረቡት መልስ ለክሱ መሠረት ያረጉት ውል ሰበር ችሎት በመዝብ ቁጥር 154915 ውሳኔ የሠጠበት ነው፡፡ የሥር ከፍተኛ ፍርድ ቤት ሥልጣን ያለው መሆኑን ተቀብሎ መብትና ጥቅም ያላቸው መሆን አለመሆኑን እና የይርጋ ክርክሩን መርምሮ ውሳኔ ሰጥቶበታል፡፡ በሀሰት የተዘጋጀ ውል ነው፡፡ ክሱ ላይ መብትና ጥቅም የላቸውም፤ የሠበር አቤቱታው ተቀባይነት የለውም ተብሎ ውደቅ ሊደረግ ይገባል ብለዋል፡፡ አመልካቾች የመልስ መልስ በማቅረብ የሠበር አቤቱታቸውን በማጠናከር ተከራክረዋል፡፡

የክርክሩ ሂደት በአጭሩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን እኛም አመልካቾች ያቀረቡት የተከሳሽ ከሳሽነት ክስን የሥር ፍርድ ቤቶች የመመልከት ሥልጣን የለንም በማለት መወሰናቸው ሕጋዊ መሆን አለመሆኑን? በጭብጥነት በመያዝ መዝገቡን መርምረናል፡፡

እንደመረመርነው አመልካቾች በተጠሪ ላይ ያቀረቡት ተከሳሽነት ክሳሽነት ክስ የአመልካቾች ወላጆች የጋራ ንብረት በሆነው በኤርትራ ሀገር አሰብ ከተማ የሚገኘው የቤት ቁጥሩ ሲ/385 እና ተጠሪ ክስ ያቀረበቡት ቤት ጋር መስከረም 02 ቀን 1991 ዓ/ም የቤት ልውውጥ ውል የተደረገ በመሆኑ ውሉ እንዲፈርስ እንዲወሰን፣ ኤርትራ አሰብ ከተማ የሚገኘውን ቤት ተጠሪ እንዲያስረክቡ እና ተጠሪ ክስ ያቀረቡበትን ቤት ከተረከብን በኋላ ለዕድሳት ያወጣነውን ብር 50,000.00 ተጠሪ እንዲተኩልን እንዲወሰንልን የሚል ነው፡፡ አሁን አከራካሪ ሆነው የኢትዮጵያ ፍርድ ቤት ክሱን የማየት ብሔራዊ የዳኝነት ሥልጣን አለው ወይስ የለውም የሚለውን የሚመለከት ነው፡፡

ክርክሩን በፍትሐ ብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕጉ መሰረት መምራት እና መቆጣጠር የፍርድ ቤቱ ኃላፊነት ሲሆን በዚህ ሂደት ከሚመረምራቸው ጉዳዮች መካከል ጉዳዩ ላይ ለመወሰን ሥልጣን ያለው መሆን አለመሆኑ ዋነኛው ነው፡፡ የፍርድ ቤት ሥልጣን ብሔራዊ የመዳኘት ሥልጣን (judicial jurisdiction)፣ የሥረ-ነገር ሥልጣን እና የግዛት ሥልጣን በሚል የተከፋፈለ ነው፡፡ ብሔራዊ የመዳኘት ሥልጣን ከሀገሮች ሉዓላዊነት፣ የሚሠጠው ፍርድ በሌሎች ሀገሮች ዕውቅና ሊሠጠውና ሊፈጸም የሚችል መሆን አለመሆኑ እና ከተከሳሽ መብት ጋር የተያያዘ መሠረቱ ዓለምአቀፍ ሕግና የታወቁ የሕግ መርሆዎች ሆኖ የአንድ ሀገር ፍርድ ቤት ጉዳዩን ለመመልከት ከተከሳሹ ወይም የክርክሩ ምክንያት የሆነው ተግባር ከተፈጸመበት ወይም አከራካሪ የሆነው ንብረት ከሚገኝበት ቦታ ጋር በቂ የሆነ ግንኙነት ያለው ሆኖ ሲገኝ ወይም ተከሳሽ የሆነው ወገን በሀገሪቱ ፍርድ ቤቶች ለመዳኘት ያለው ፈቃድ ላይ መሠረት በማድረግ የሚወሰን ነው፡፡

በተያዘው ጉዳይ አመልካቾች ኢትዮጵያ ውስጥ የተደረገ ውል እንዲፈርስ ዳኝነት መጠየቃቸው የክርክሩ ምክንያት የሆነው ተግባር ከተፈጸመበት ቦታ ጋር በቂ ግንኙነት መኖሩን ስለሚያሳይ ኢትዮጵያ ፍርድ ቤቶች ጉዳዩን ለማየት ሥልጣን ያገኛሉ፡፡ አመልካቾች ውል ይፍረስ የሚል ዳኝነት ያቀረቡ በመሆኑ ኤርትራ አሰብ ከተማ የሚገኘው ቤት ላይ በቀጥታ የመፋለም ክስ እንዳቀረበቡት ሊቆጠር የሚገባው አይደለም፡፡ ነገር ግን ውሉ ከፈረሰ ወደነበሩበት መመለስ ስለሚኖራባቸው በተከራካሪዎች መካከል የሚመላለሱት ንብረት ውስጥ አንደኛው በአዲስ አበባ ከተማ የሚገኘውን ቤት በመሆኑ የኢትዮጵያ ፍርድ ቤቶች ጉዳዩን ለማየት ተጨማሪ ሕጋዊ ምክንያት ያገኛሉ፡፡ ተጠሪ በዜግነት ኤርትራዊ መሆናቸው የተገለጸ ሲሆን በሥር ፍርድ ቤት የብሔራዊ ዳኝነት ሥልጣን የለውም በማለት የተቃወሙ ስለመሆኑ ከውሳኔው ይዘት የተረዳን ሲሆን በዚህ ችሎት ደረጃ ፍርድ ቤት ሥልጣን ያለው መሆኑን ተረድቶ በሌሎች መቃወሚያዎች ተመስርቶ ነው ክሱን ውደቅ ያደረገው በማለት በክሱ ሥረ-ነገር ላይ ክርክር ማቅረባቸው በፍርድ ቤቱ ለመዳኘት ፈቃድ እንደሠጡ ሊወሰድ ይችላል፡፡ ስለሆነም በአመልካቾች የቀረበው ክስ ክሱ ከቀረበበት ሀገር ጋር በቂ ግንኙነት ያለው በመሆኑ የኢትዮጵያ ፍርድ ቤቶች ጉዳዩን ለማየት የብሔራዊ ዳኝነት ሥልጣን አላቸው ብለናል፡፡ የሥር ከፍተኛ ፍርድ ቤት አንዱን ዳኝነት ነጥሎ በማየት ኤርትራ ሀገር በሚገኝ ቤት ላይ ለቀረበ ዳኝነት ሥልጣን የለኝም ማለቱ ዋናው የክሱ መሠረት

በኢትዮጵያ የተደረገ ውል ይፍረስልኝ መሆኑን ያላገናዘበ እና ተገቢነት የሌለው ነው። ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤቱም ኤርትራ ሀገር የሚገኘው ቤት ላይ የመፋለም ክስ እንደቀረበበት አድርጎ በመውሰድ ለግዛት ክልል ተፈጻሚነት ያለውን የፍብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 25 ድንጋጌ መሠረት ፍርድ ቤቱ ሥልጣን የለውም ማለቱ ሕጋዊነት የለውም ብለናል፤ ውሳኔው መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል።

ውሳኔ

1. የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 180811 ሐምሌ 20 ቀን 2012 ዓ/ም፤ የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 220803 ሠኔ 21 ቀን 2011 ዓ/ም አመልካቾች ያቀረቡትን የተከሳሽነት ከሳሽነት ክስ አስመልክቶ የሠጠውን ውሳኔ በማሻሻል የሠጠው ውሳኔ በፍብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348(1) መሰረት ተሻሽሏል።

2. የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ጉዳዩን የማየት ሥልጣን የለውም በማለት የሠጠው ውሳኔ ክፍል ተሽሯል። ቀሪው የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ውሳኔ ፀንቷል።

3. የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የቀረበውን የተከሳሽ ከሳሽነት ክስ መመልከቱን በመቀጠል ተጠሪ ያቀረቧቸውን ሌሎች መቃወሚያዎች በመመርመርና ክሱ በመቃወሚያው መሠረት ውድቅ የማይደረግ ከሆነ በሥረ-ነገሩ ተመልክቶ እንዲወሰን ጉዳዩን በፍብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 341(1) መሠረት መልሠናል።

4. በዚህ ችሎት ለወጣ ወጭና ኪሣራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል።

ትዕዛዝ

- የውሳኔው ግልባጭ ለሥር ፍርድ ቤቶች ይተላለፍ። የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በውሳኔው መሠረት እንዲፈጽም አዘናል። ይጻፍ
- ክርክሩ እንዲታገድ የተሠጠው እግድ ተነስቷል። ይጻፍ
- መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ።

ሄ/መ የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት።

የሠ/መ.ቁጥር 244107

ሰኔ 24 ቀን 2016 ዓ/ም

ዳኞች፡- ብርሀኑ አመነው

በእውቀት በላይ

ቀነአ ቂጣታ

ብርሃኑ መንግሥቱ

ማርታ ተካ

አመልካቾች፡- 1. ዮሀንስ ተስፋዬ
2. ኢዮብ ተስፋዬ
3. አክሊሉ ተስፋዬ
4. ኤልዳና ተስፋዬ

ተወካይ ሐረገወይን ሲርና - ቀረቡ

ተጠሪ፡- የአዲስ ከተማ ክፍለ ከተማ ወረዳ 08 ቤቶች አስተዳደር ፅ/ቤት

መዝገቡ ተመርምሮ ከዚህ የሚከተለዉ የፍርድ ዉሳኔ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የዳኝነት ሥልጣን የሚመለከት ነዉ፡፡ ክርክሩ የተጀመረዉ በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ሲሆን አመልካቾች በተጠሪ ላይ የመሠረቱት ክስ በአዲስ አበባ ከተማ በቀድሞው ወረዳ 5 ቀበሌ 6 በአሁኑ አዲስ ከተማ ወረዳ 08 በብሎክ ቁጥር 4 በፓርሴል ቁጥር 34 በቤት ቁጥር 108 የሚታወቅ የድርጅት ቤት አመልካቾች አለን፡፡ይህ ቤት ሴት አያታችን የቤቱ ባለቤት የነበሩት አቶ ማኮ ጮረና ሀምሌ 12 ቀን 1944 ዓ.ም በአደረጉት ኑዛዜ መሰረት አስተላልፈዉልናል፡፡ ኑዛዜውም በቀድሞ የአዲስ አበባ 8ኛ ወረዳ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 486/45 በ21/12/1945 ዓ.ም በተሰጠ ውሳኔ ፀድቆ ተመዝግቧል፡፡ይህን ቤት አያታችን አዋጅ ቁጥር 47/1967 እስከታወጀበት ጊዜ ድረስ ለ22 ዓመታት የማይንቀሳቀስ ንብረት ባለቤት በመሆን ከእጃቸው ሳይወጣ ሲጠቀሙበት ቆይተዋል፡፡አዋጅ ቁጥር 47/67 ሥራ ላይ በሚውልበት ጊዜም አያታችን ለክሱ መነሻ የሆነውን ቤት በመምረጣቸው ለዚሁ ቤታቸው የከተማ ልማት እና ቤት ሚኒስቴር በቁጥር 5/07886 መስከረም 11 ቀን 1974 ዓ.ም የከተማ ባለቤትነት ደብተር ሰጧቸዋል፡፡አዋጅ ቁጥር 47/1967 በሥራ ላይ ከዋለበት ከ1968 ዓ.ም ጀምሮ እስከ 2008 ዓ.ም ለ40 ዓመታት በቤት ቁጥር 108 ለመንግስት የቤት ግብር እና የአፈር ግብር ሲከፈልበት ቆይቷል፡፡ከሴት አያታችን ሞት በኋላም ለአባታችን በውርስ ተላልፎለት እስከለተ ሞቱ ድረስ ሲያስተዳድረው ቆይቷል፡፡አባታችን ከሞተ በኋላም አመልካቾች ወራሽነታችንን አረጋግጠን የአዲስ ከተማ ክፍለ ከተማ የይዞታ አስተዳደር የሽግግር ጊዜ መስተንግዶ ማስተባበሪያ ፕሮጀክት በእነ ዮሀንስ ተስፋዬ (አራት ሰዎች) የሚል ተነባባሪ የቤት ባለቤትነት ማረጋገጫ ካርታ ሰጥቶናል፡፡አባታችን ለክሱ መነሻ

የሆነውን ቤት በመከፋፈል ለእነ ሀሚድ መሀመድ(6 ሰዎች) አከራይተው ሲጠቀሙበት ነበር፡፡ይሁንና አዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር መንግስት ከሚያስተዳድራቸው ቤቶች ጋር በተያያዘ ያወጣውን መመሪያ ቁጥር 4/2004 ተከትሎ እነ ሀሚድ ከቀበሌው መስተዳድር ጋር የጥቅም ግንኙነት በመፍጠር ቤቱ የመንግስት ስለሆነ ኪራይ አንከፍልም ብለው አባታችንም በፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የቤት ኪራይ ከፍለው ቤቱን ለቀው ይውጡ የሚል ክስ አቅርበዉ ክሱ ውድቅ የተደረገበት ሲሆን ከፍተኛ ፍርድ ቤቱ ደግሞ የስር ፍርድ ቤትን ውሳኔ በመሻር እያንዳንዳቸው ተከራዮች ያለባቸውን ውዝፍ ቤት ኪራይ ከፍለው ቤቱንም ያስረክቡ ሲል ውሳኔ ሰጥቷል፡፡ተጠሪም ውሳኔ ከተሰጠ በኋላ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 358 መሰረት መቃወሚያ አቅርቦ ለክሱ መነሻ የሆነው ቤት ቁጥር 108 የሚባል የለም ቤቱ በቤት ቁጥር 101 የሚታወቅ የመንግስት ቤት ነው በማለት ለአባታችን የተወሰነውን ውሳኔ አሸሯል፡፡ይሁንና በግራ ቀናችን መካከል የፍትሐ ብሄር ሕግ ቁጥር 1206 ድንጋጌን መሰረት አድርጎ የቀረበ የመፋለም ክስ ስለሌለ አሁን ያቀረብነው ክስ አዲስ ነው፡፡ለክሱ መነሻ የሆነው ቤት ቁጥር 108 የአመልካቾች የግል ንብረት ሆኖ ሳለ ተጠሪ ይህንን ቤት ሳይወርስ ወይም በመንግስት በጀት ሳይሠራ መንግስታዊ ስልጣኑን በመጠቀም የፈጠራ መረጃ አደራጅቶ ቤቱ የመንግስት ነው በማለት ያቀረበው ክርክር ተቀባይነት የለውም፤ ቤቱ የአመልካቾች የግል ሀብት ተብሎ ተጠሪ ለክሱ ምክንያት የሆነው ቤት ቁጥር 108 ተከራዮችን በማስወጣት እንዲያስረክበን ይወሰንልን በማለት ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡

ተጠሪም የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያዎችን በማስቀደም ባቀረበዉ መልስ አመልካቾች ከዚህ በፊት በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ክስ አቅርበው ይህ ቤት የአመልካቾች እንዳልሆነ እና ካርታውንም ያገኙት የቤት ቁጥር 101/2 የተባለውን የመንግስት ቤት ወደ ግል ቤትነት ቀይረው መሆኑ ተረጋግጦ ለክርክሩ ምክንያት የሆነው ቤት የመንግስት ነው በሚል ውሳኔ ተሰጥቶ ይህም ውሳኔ እስከ ፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ድረስ ፀንቷል፡፡አመልካቾች በድጋሚ ድጋሚ ዳኝነት አቅርበው ፍርድ ቤቱ ውድቅ ያደረገባቸው ሲሆን በድጋሚ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አላግባብ ካርታችን መክኗል በሚል ክስ መስርተው ውድቅ ተደርጎባቸዋል፡፡ስለሆነም በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 5 እና 244(2/ለ) መሰረት ውሳኔ ያገኘ ስለሆነ ክሱ ዉድቅ ሊሆን ይገባል፡፡በአዲስ ከተማ ክፍለ ከተማ ወረዳ 08 የቤት ቁጥሩ 101/2 የሆነው ቤት ተጠሪ በአዋጅ ቁጥር 64/2011 እና በመመሪያ ቁጥር 5/2011 ዓ.ም የሚያስተዳድረው የመንግስት ቤት ነው፡፡ የከተማ አስተዳደሩ ከሚያስተዳድረው ቤት ጋር በተያያዘ የሚነሱ ክርክሮችን በተመለከተ በቻርተር አዋጅ ቁጥር 361/1995 አንቀፅ 41(1/ረ) እና በፌደራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀጽ 5(1/ደ) መሰረት ጉዳዩን የመዳኘት ሥልጣን የአዲስ አበባ ከተማ ፍርድ ቤቶች ስለሆነ ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን የመዳኘት ሥልጣን የለዉም በማለት ተቃዉሟል፡፡እንዲሁም ሌሎች መከራከሪያዎችንም በማቅረብ ተከራክሯል፡፡

ፍርድ ቤቱም በመ/ቁጥር 102923 ላይ በቀን 04/05/2015 ዓ/ም በሰጠዉ ብይን ክስ የቀረበዉ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ይዞ እያስተዳደረ ባለው ቤት ላይ በመሆኑ በአዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀጽ

5(1/ደ) ስር በተደነገገዉ መሠረት ጉዳዩን የመዳኘት ሥልጣን የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ፍርድ ቤቶች ነዉ በማለት የክሱን መዝገብ በመዝጋት አመልካቾች ሥልጣን ያለዉ ፍርድ ቤት ክሳቸዉን ማቅረብ ይችላሉ ሲል ወስኗል፡፡ አመልካቾች በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ያቀረቡ ቢሆንም በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 337 መሠረት ተጠሪን ሳያስቀርብ ይግባኙን ሠርዘዋቸዋል፡፡

አመልካቾች መጋቢት 1 ቀን 2015 ዓ.ም አቤቱታቸውን ያቀረቡት ከላይ በተጠቀሰው መንገድ በተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ተፈፅሟል በማለት ሲሆን የአቤቱታቸውም አጭር ይዘት፡-የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በያዘው ቤት ባለቤትነትን የመፋለም ክስ እንዲሁም በቤቱ ባለቤትነት ላይ ክርክር እስከቀረበበት ድረስ የአዲስ አበባ ከተማ ነክ ፍርድ ቤት የስረ ነገር ስልጣን የለውም ሲል የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁጥር 32376 ላይ አስገዳጅ የሕግ ትርጉም ሰጥቶበታል፡፡በዚህ መሰረት የፈደራል ፍርድ ቤቶች ጉዳዩን የማየት የሥረ ነገር ስልጣን እያላቸው ሥልጣኑ የአዲስ አበባ ከተማ ፍርድ ቤቶች ናቸው በማለት የስር ፍርድ ቤቶች ሥልጣን የለንም በማለት የሠጡት ብይን መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ስለሆነ ተሽሮ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በፍሬ ነገሩ ላይ ግራ ቀኙን አከራክሮ ተገቢውን ውሳኔ እንዲሰጥ ጉዳዩ ሊመለስለት ይገባል በማለት ተከራክረዋል፡፡

የሰበር ሰሚ ችሎት አቤቱታዉን መርምሮ አመልካቾች በተጠሪ ላይ የመሰረቱት ክስ የቤት ባለቤትነት መብት መፋለምን የሚመለከት ሆኖ እያለ የስር የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ጉዳዩን የመዳኘት ስልጣን የለኝም በማለት ክሱን ውድቅ አድርጎ መወሰኑ እና ይህንን ውሳኔ በመቃወም ያቀረቡትን ይግባኝ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት መሰረዙ አግባብ መሆን አለመሆኑን በሰ/መ/ቁጥር 32376 ከተሰጠው የሕግ ትርጉም እና በፌደራል ፍ/ቤች አዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀፅ 5(1/ደ) አኳያ እንዲመረመር ተጠሪ መልስ እንዲሰጥ አዝዟል፡፡

ተጠሪ ሐምሌ 25 ቀን 2015 ዓ.ም ጽፎ ባቀረበዉ መልስ በአዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀጽ 5(1/ደ) ስር ጉዳዩን የመዳኘት ሥልጣን ለአዲስ አበባ ከተማ ፍርድ ቤት ስልተሰጠ ይህ አዋጅ ከጸና በኋላ በተጠቀሰዉ የሰበር መዝገብ ላይ የተሰጠዉ የሕግ ትርጉም ተፈጻሚነት አይኖረዉም፡፡ስለሆነም በስር ፍርድ ቤቶች በተሰጠ ዉሳኔ የተፈጸመ ስህተት የለም በማለት ተከራክሯል፡፡ አመልካቾችም የመልስ መልሳቸውን በማቅረብ ተከራክረዋል፡፡

ከላይ አጠር ባለ መልኩ የተገለጸዉ የግራ ቀኙን ክርክርና በስር ፍርድ ቤቶች የተሰጠ ዉሳኔ ይዘት የሚመለከት ሲሆን እኛም የተያዘዉን ጭብጥ መሠረት በማድረግ በዚህ ችሎት ደረጃ ሊታረም የሚችል መሠረታዊ የሕግ ስህተት መፈጸም አለመፈጸሙን አግባብነት ካለዉ ሕግ ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለዉ መርምረናል፡፡

እንደመረመርነውም በፌዴራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 1234/2013 ላይ በዋናነት የፌዴራል ፍርድ ቤቶች የዳኝነት ሥልጣን በጠቅላላዉ የተደነገገ ሲሆን በአንቀጽ 5(1/ደ) ስር ደግሞ ለአዲስ አበባ እና ድሬዳዋ ከተሞች ፍርድ ቤቶች በቻርተር አዋጆቻቸዉ የተሰጣቸዉ የዳኝነት ሥልጣን እንደተጠበቀ ሆኖ የከተሞቹ አስተዳደሮች ከሚያስተዳድሩት ቤት ጋር በተያያዘ በሚነሳ የይዞታ ወይም የባለቤትነት ወይም ሌላ ማንኛዉም ክርክር የመዳኘት ሥልጣን የከተሞቹ አስተዳደሮች ፍርድ ቤቶች እንደሆነ ተደንግጓል። ይህም በፌዴራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ላይ በልዩ ሁኔታ ስለአዲስ አበባ እና ድሬዳዋ ከተሞች ፍርድ ቤቶች የሥረ ነገር ዳኝነት ሥልጣን መደንገጉን የሚያሳይ ነዉ።በዚህ መልኩ የተደነገገዉ አስቀድሞ በተሻሻለዉ የአዲስ አበባ ከተማ ቻርተር አዋጅ ቁጥር 361/1995 አንቀጽ 41(1/ረ) እና በድሬዳዋ ከተማ አስተዳደር ቻርተር አዋጅ ቁጥር 416/1996 አንቀጽ 33(1/ረ) ስር እንደ ቅደም ተከተላቸዉ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ከሚያስተዳድራቸዉ የመንግሥት ቤቶች እና የድሬዳዋ ከተማ አስተዳደር የሚያስተዳድራቸዉ ሆኖ ለንግድ፣ለመኖሪያ ወይም ለሌላ አገልግሎት በመስጠት ላይ ካሉ የመንግሥት ቤቶች ጋር በተያያዘ የሚነሱ ጉዳዮችን(ክሶችን) የመዳኘት ሥልጣን የከተሞቹ ፍርድ ቤቶች ሥልጣን ነዉ በሚል ደንግገዋል።በእነዚህ አዋጆች የተደነገገዉን ግልጽ በሚያደርግ አኳኋን ከቤቶቹ ጋር በተያያዘ የሚነሳ የይዞታ እና የባለቤትነት መብቶች የመፋለም ክሶች (The petitory action and the possessory action) ወይም ሌላ ማንኛዉም ክርክር በሚል ሰፋ ባለ አኳኋን መደንገጉን የሚያሳይ ነዉ።

እንዲሁም የአዋጁን አንቀጽ 5(1/ደ)ን ከአዋጁ አንቀጽ 5(1/ሰ) እና በአዋጅ ቁጥር 361/1995 አንቀጽ 41(1/ረ) እና በአዋጅ ቁጥር 416/1996 አንቀጽ 33(1/ረ) ስር ከተደነገገዉ ጋር አገናዝበን የተመለከትን እንደሆነ የፌዴራል ፍርድ ቤቶች ዳኝነት ሥልጣን የሚሆነዉ የአዲስ አበባ እና የድሬዳዋ ከተሞች አስተዳደሮች የሚያስተዳድሯቸዉንና ለንግድ፣ለመኖሪያ ወይም ለሌላ አገልግሎት በመስጠት ላይ ካሉ የመንግሥት ቤቶች ዉጭ በሆኑት የፌዴራል መንግሥቱን ንብረቶች በተመለከተ የሚነሱ ጉዳዮች ማለትም ከፌዴራል ሦስቱም የመንግሥት አካላት እና ከፌዴራል የልማት ድርጅቶች ንብረቶች ጋር በተያያዘ የሚቀርቡ ማናቸዉም ክሶች በተመለከተ እንደሆነ ነዉ።ከዚህ ጋር በተያያዘም የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁጥር 244174 ላይ በቀን 28/09/2016ዓ/ም(ያልታተመ) አስገዳጅ የሕግ ትርጉም ሰጥቷል።

በሌላ በኩል የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አዋጅ ቁጥር 361/1995 አንቀጽ 41(1/ረ) ስር የተደነገገዉን በሰ/መ/ቁጥር 32376 (ቅጽ 5) ላይ በሰጠዉ ዉሳኔ በመተርጎም የአዲስ አበባ ከተማ ነክ ፍርድ ቤቶች የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በሚያስተዳድራቸዉ ቤቶች ላይ ባለቤትነት በማፋለም የሚቀርብ ክስ ለመዳኘት ሥልጣን የላቸዉም የሚል አስገዳጅ የሕግ ትርጉም ሰጥቷል።ይህ የሕግ ትርጉም የተሰጠዉ የፌዴራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 1234/2013 ከመጽናቱ በፊት መሆኑ ግልጽ ነዉ።ሆኖም ከላይ እንደተገለጸዉ በአዋጅ ቁጥር 1234/2013 ከጸናበት ከጥር 13 ቀን 2013 ዓ/ም ጀምሮ

በዚህ አዋጅ አንቀጽ 5(1/ደ) ስር በተደነገገዉ መሠረት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በሚያስተዳድራቸዉ ቤቶች ላይ የባለቤትነት መብት በማፋለም የሚቀርብ ክስ የመዳኘት ሥልጣን የአዲስ አበባ ከተማ ፍርድ ቤቶች በመሆኑ አዋጅ ቁጥር 1234/2013 ከጸናበት ቀን ጀምሮ በሰ/መ/ቁጥር 32276 ላይ የተሰጠዉ የሕግ ትርጉም ተፈጻሚነቱ ቀሪ ሆኗል፡፡

በተያዘዉ ጉዳይ አመልካቾች ክስ የመሰረቱት በክሱ ላይ የተጠቀሰዉ ቤት የሥራና ቤት ሚኒስቴር ለአያታቸዉ (ለአዉራሻቸዉ) የፈቀደላቸዉ እና በስማቸዉ የተመዘገበ በኋላም በዉርስ ወደአባታቸዉ ተላልፎ ሲተዳደር የቆየዉን ተጠሪ ከሕግ አግባብ ዉጭ በመያዝ እያስተዳደር እንደሚገኝ በመግለጽ መብት ሳይኖረዉ ይዞ እያከራየ ያለዉ ተጠሪ ተከራዮችን አስለቅቆ እንዲያስረክባቸዉ ዳኝነት በመጠየቅ ያቀረቡት ክስ ነዉ፡፡ይህም ክሱ የከተማ አስተዳደሩ እያስተዳደረ የሚገኘዉን ቤት ባለቤትነት መብት በመፋለም እንደቀረበ የሚያሳይ ነዉ፡፡ በመሆኑም በአዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀጽ 5(1/ደ) መሰረት ክሱን ተቀብሎ የመዳኘት ሥልጣን ያላቸዉ የአዲስ አበባ ከተማ ፍርድ ቤቶች ናቸዉ፡፡ስለሆነም የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የተጠሪን የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ በመቀበል ጉዳዩን የመዳኘት ሥልጣን የለኝም በማለት የሰጠዉ ዉሳኔም ሆነ ይህንን ዉሳኔ በመቃወም አመልካቾች ያቀረቡትን ይግባኝ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመሠረዝ የሰጠዉ ብይን በሕግ የተደነገገዉን የዳኝነት ሥልጣን ክፍፍል መሠረት ያደረገ ነዉ ከሚባል በስተቀር በዚህ ችሎት ደረጃ ሊታረም የሚችል ስህተት የተፈጸመበት ባለመሆኑ ተከታዩን ወስነናል፡፡

ዉ ሳ ኔ

1. የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 102923 ላይ በቀን 04/05/2015 ዓ/ም የሰጠዉ ብይን እና የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 300134 ላይ በቀን 16/06/2015ዓ/ም የሰጠዉ ብይን በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ሥነ ሥርዓት መመሪያ ቁጥር 17/2015 አንቀጽ 9/1 መሰረት ጸንተዋል፡፡
2. የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በሚያስተዳድራቸዉ ቤቶች ላይ የባለቤትነት መብት በማፋለም የሚቀርብ ክስ የመዳኘት ሥልጣን የአዲስ አበባ ከተማ ፍርድ ቤቶች ሥልጣን ነዉ፡፡
3. ግራ ቀኝ በዚህ ችሎት ያወጡትን ወጭ የየራሳቸዉን እንዲችሉ ተወስኗል፡፡

ት እ ዛ ዝ

1. የዉሳኔዉ ግልባጭ ለሥር ፍርድ ቤቶች ይተላለፍ፡፡ ግራ ቀኙ ሲጠይቁም ግልባጩ ይሰጣቸዉ፡፡
2. ዉሳኔዉ በቀን 11/11/2016 ዓ/ም ተነበበ፡፡
3. መዝገቡ ተዘግቷል፤ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፌርማ አለበት

ብ/ም

የሰበር መዝገብ ቁጥር 221715

ጥቅምት 29 ቀን 2015 ዓ/ም

ዳኞች፡- ተፈሪ ገብሩ (ዶ/ር)

ቀነዓ ቂጣታ

ፈይሳ ወርቁ

ሰናይት አድነው

ደጀኔ አያንሳ

አመልካች፡- ሚ/ር ይቤዝን አውግስቲን አሌክስ ፌሬዝ

ተጠሪ፡- ሚስ ማርካዬት ጉርክሊን ሱዛን ግራሲያ

ለምርመራ ተቀጥሮ የነበረው መዝገብ ተመርምሮ ቀጣዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍርድ

የግራ ቀኙ ጋብቻ የፈረሰው ፈረንሳይ ሀገር ባለ ፍርድ ቤት የሀገርቱን ሕግ መሠረት አድርጎ በተላለፈ ውሳኔ መሆኑ ያላከራከረ በመሆኑ የፍቺ ውጤት የሆነው የንብረት ክርክርም መታየት ያለበት በዚያው ሀገር ፍርድ ቤት ሆኖ እያለ የሥር ፍርድ ቤት ጉዳዩ የማየት የሥረ ነገር ሥልጣን ሳይኖረው አከራካሪው የብድር ገንዘብ የጋራ መሆኑን አመልካች ያልተቀበሉትን እንደታመነ ወስዶ፤ የፈረንሳይ ሕግ ከኢትዮጵያ ሕግ ጋር እንደማይቃረን በጥናት ድርሸበታለሁኝ በማለት ከኢትዮጵያ ውጭ የሚገኝ አበዳሪ ድርጅት የሰጠውን ብድር መጠየቅ የሚቻለው ድርጅቱ በሚኖርበት ሀገር ባለ ፍርድ ቤት ሆኖ ሳለ፤ ለአመልካች ሳይሆን አበዳሪ ለሆነው ድርጅት እንድከፈል የተወሰነውንና የብድር ዕዳው መከፈሉ እርግጠኛ ያልሆነውን ገንዘብ ብድሩን ለማስመለስ ለግልግል ዳኝነት የተከፈለ፤ የጠበቃ አበል እና ሌሎች ወጪዎች ተቀናሽ ሳይደረግ የብድር ገንዘቡን እኩሌታ ተጠሪ እንዲካፈሉ መወሰኑ አግባብ ባለመሆኑ ተጠሪ የጋራ ሃብት አላቸው የሚባል ከሆነም ሊጋሩ የሚገባው ዕዳዎቹን ለማስመለስ የተከፈሉ ወጪዎች ተቀንሶ ተራፊውን ገንዘብ በመሆኑ የሥር ፍርድ ቤት ውሳኔ መሻር አለበት በማለት አመልካች የካቲት 17 ቀን 2014 ዓ/ም የሰበር አቤቱታ ስላቀረቡ መዝገቡ ለሰበር ሰሚ ችሎቱ ቀርቧል፡፡

ጉዳዩ የጋብቻ በፍርድ ቤት ውሳኔ መፍረስን ተከትሎ የቀረበ የባልና ሚስት የንብረት ክርክር ሲሆን ክርክሩን በመጀመሪያ ደረጃ ሥልጣን በተመለከተው የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ተጠሪ በከሳሽነት ፤ አመልካች ደግሞ በተከሳሽነት ተከራክረዋል፡፡ ተጠሪ ያቀረቡት ክስ ይዘት፡- ግራ ቀኙ ፈረንሳያዊያን በመሆናቸው በዚያው ሀገር በ1969 ዓ/ም ጋብቻቸውን መስርተው ሲኖሩ መስማማት ባለመቻላቸው

ትዳራቸው በፈረንሳይ ሀገር በፍርድ ቤት በተሰጠ የፍቺ ውሳኔ መፍረሱን ተከትሎ ግራ ቀኙ በትዳር ውስጥ እያሉ አመልካች ብቸኛ ባለድርሻ በመሆን ባቋቋሙት ቲኢ.ኤፍ.ዜድ.ኢ የሚባል ድርጅት ከተጠሪ እውቅና ውጪ ለዋይ. ጅ.ኤፍ ሰርቪስስ ኃ/የተ/የግ/ ማህበር ታህሳስ 25 ቀን 2015 ዓ/ም እ.አ.አ ብር 6,300,000.00 (ስድስት ሚልዮን ሶስት መቶ ሺ) እና የካቲት 19 ቀን 2015 ዓ/ም እ.አ.አ 265,000.00(ሁለት መቶ ስልሳ አምስት ሺ) ብር ፤ እንዲሁም ለሰመር ቱር ኤንድ ትራቭል ኃ/የተ//የግ/ ማህበር 2,700,000.00 (ሁለት ሚልዮን ሰባት መቶ ሺ) ማበደራቸውን የፍቺ ውሳኔ ከተሰጠ በኋላ እንዳወቁ ገልፀው፤ ከላይ የተጠቀሱት ተበዳሪ ተቋማት የወሰዱትን የብድር ገንዘብ እንዲከፍሉ ጠይቆ ፈቃደኛ ባለመሆናቸው አመልካች የብድር ገንዘቡን ለማስመለስ በተቋማቱ ላይ ያቀረቡት ክስ ውሳኔ አግኝቶ የአፈፃፀም ፋይል በፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ተከፍቶ ጉዳዩ በመታየት ላይ ስለሚገኝ ይህ ግራ ቀኙ በትዳር ውስጥ እያሉ በብድር የተሰጠው ገንዘብ ከነወለዱ በተሻሻለው የቤተሰብ ሕግ አዋጅ ቁጥር 213/1992 መሠረት የጋራ የባልና ሚስት ሀብት ነው ተብሎ እንዲወሰን ጠይቀዋል፡፡

አመልካችም በተጠሪ ለቀረበው ክስ የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያን በማስቀደም በፍሬ ነገሩ ላይ በሰጡት መልስ ግራ ቀኙ የነበራቸው ትዳር በፍርድ ቤት የፍቺ ውሳኔ መፍረሱን፤ አመልካች የአበዳሪው ድርጅት ብቸኛ ባለድርሻ መሆናቸው እና አበዳሪው ድርጅትም ለዋይ. ጅ.ኤፍ ሰርቪስስ ኃ/የተ//የግ/ ማሕበር እና ለሰመር ቱር ኤንድ ትራቭል ኃ/የተ//የግ/ ማህበር ብደር መስጠቱን አምነው በብድር የተሰጠውን ገንዘብ በአበዳሪ ድርጅቱ ላይ ያፈሰሰው ችልድረን ኦፍ ዘ ሰን የሚባል በጎ አድራጎት ድርጅት ሆኖ ብድሩ የሚመለስበት ዝርዝርም የፍቺ ውሳኔውን በሰጠው ፈረንሳይ ፍርድ ቤት መዝገብ ተያይዞ የሚገኝ እና ክርክሩ ታይቶ የተወሰነ ሆኖ ሳለ እንደ አዲስ መቅረቡ ተገቢ አለመሆኑን፤ አፈፃፀም ላይ በደረሰው ክርክር ተጠሪ በምስክርነት ቀርበው እያለ ጉዳዩን እንደማያውቁት እና ፍቺውን በሰጠው ፍርድ ቤትም ጉዳዩ እንደማይታወቅ ያቀረቡት ክርክር ተቀባይነት የለውም፡፡ ተጠሪ የጠየቁት ገንዘብ እሳቸውን የማይመከለት፤ አበዳሪው ድርጅት እና አመልካች ባላቸው የኢንቨስትመንት ግንኙነት ለ3ኛ ወገን መመለስ ያለበት፤ ፈረንሳይ ሀገር በሚገኘው የንብረት ክፍፍሉን ለሚመለከተው ፍርድ ቤት መግለጫ ቀርቦ በዚያው ፍርድ ቤት ውሳኔ ማግኘት ያለበት በመሆኑ ተጠሪ ገንዘቡን የመጠየቅ መብት የላቸውም ተብሎ እንዲወሰን ጠይቀዋል፡፡ ክሱ በተሰማበት ወቅት አመልካች ጉዳዩ መዳኘት ያለበት በፈረንሳይ ሀገር ሕግ መሆን እንዳለበት የተከራከሩ ሲሆን፤ ተጠሪ በበኩላቸው ተበዳሪዎቹ ተቋማት ኢትዮያዊያን ሆኖእያለ አበዳሪው የፈረንሳይ ሀገር ዜጋ በመሆኑ ብቻ በፈረንሳይ ህግ ሊዳኙ እንደማይገባ ተከራክረዋል፡፡

ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ ሥልጣን የተመለከተው የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ጉዳዩ መዳኘት ያለበት በኢትዮጵያ ወይንስ በፈረንሳይ ሕግ ?፤ አመልካች ለተበዳሪዎቹ ተቋማት ያበደሩትን ገንዘብ ግራ ቀኙ መካፈል አለባቸው ወይስ የለባቸውም? የሚሉ ጭብጦችን ይዞ ጉዳዩ እንደሚከተለው መርምሮታል፡፡ አመልካች ብቸኛ ባለድርሻ በመሆን ያቋቋሙት ቲኢ.ኤፍ.ዜድ.ኢ የተሰኘ ድርጅት ለዋይ. ጅ.ኤፍ ሰርቪስስ

ኃ/የተ//የግ/ማህበር እዲሁም ለሰመር ቱር ኤንድ ትራቭል ኃ/የተ//የግ/ ማኅበር በክሱ ላይ የተመለከተውን ገንዘብ ማበደሩ በማስረጃ ተረጋግጧል፡፡ የተጠሪ የዳኝነት ጥያቄ በግራ ቀኙ ጋብቻ ውስጥ የተፈራና አመልካች በክሱ ውስጥ ለተመለከቱት ድርጅቶች ያበደሩት ገንዘብ የጋራ እንዲባልላቸው የጋብቻ ፍቺ ውጤትን የሚመለከት ሆኖ የተከራካሪዎቹ ጋብቻ የተመሰረተው በፈረንሳይ ሀገር መሆኑ፤ የፍቺ ውሳኔውም የፈረንሳይ ሕግን መሠረት አድርጎ በዚያው ሀገር ስለተሰጠ የፍቺ ውጤት የሆነው የንብረት ክርክርም መታየት የሚገባው በፈረንሳይ ሕግ መሆኑ ግልጽ ቢሆንም በፈረንሳይ ሀገር ሕግ እና በኢትዮጵያ የቤተሰብ ሕግ መካከል ግጭት አለመኖሩን ፍርድ ቤቱ ባደረገው ጥናት ተረጋግጧል፡፡ በፈረንሳይ ሀገር ሕግም በጋብቻ ውስጥ የተፈራ የባልና ሚስት ንብረት እኩል እንደሚካፈል በሕጉ የተመላከተ ሲሆን አመልካች ገንዘቡ በጋብቻ ውስጥ እንዳልተፈራ፤ የግላቸው እንደሆነ ወይንም ከፍቺ በኋላ የተፈራ ነው የሚል ክርክር ስላላቀረቡ እና ለክርክሩ ምክንያት የሆነው ገንዘብ አበዳሪ ችልድረን ኦ ዘ ሰን ሳይሆን አመልካች ብቸኛ ባለድርሻ በመሆን ያቋቋሙት ድርጅት መሆኑን በብድር ውሉ ላይ በግልጽ የተመለከተውንና ለአመልካች እንዲከፈል የግልግል ዳኝነት ውሳኔ አርፎበት በአፈፃፀም ክርክር ላይ የሚገኘው 9,265,000.00 (ዘጠኝ ሚልዮን ሁለት መቶ ስልሳ አምስት ሺ) ግማሽ ብር 4,632,500.00 (አራት ሚልዮን ስድስት መቶ ሰላሳ ሁለት ሺ አምስት መቶ) አመልካች ለተጠሪ እንዲከፍሉ ወስኗል፡፡

የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚው ችሎት የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ውሳኔ ጉድለት አልተገኘበትም በማለት የይግባኝ አቤቱታውን በመሰረዙ አመልካች ያቀረቡትን በፍርዱ መግቢያ ላይ የተመለከተውን የሰበር አቤቱታ የመረመረው የሰበር አጣሪ ችሎቱ፡- ግራ ቀኙ የፈረንሳይ ሀገር ዜግነት ያላቸው እና የፍቺ ውሳኔውም የተሰጠው በዚያው ሀገር ከመሆኑ አንፃር የሥር ፍርድ ቤት ጉዳዩን ለማየት የሥረ ነገር ሥልጣን ያለው መሆን / አለመሆኑን ፤ ሥልጣን ነበረው ቢባል እንኳን በፍሬ ነገሩ ላይ የሰጠው ውሳኔ አግባብነት ተጠሪ ባሉበት መጣራት አለበት በማለቱ ተጠሪ በሰጡት መልስ፡- የውጭ ሀገር ዜግነት ባላቸው ተከራካሪዎች መካከል የሚነሱ ክርክሮችን የማየት ሥልጣን በአዋጅ ቁጥር 25/88 ሆነ በአዋጅ ቁጥር 1234/2013 የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመሆኑ ከሥልጠ አንፃር የቀረበው አቤቱታ ተቀባይነት የለውም፡፡ የአመልካች አድራሻ አዲስ አበባ በመሆኑና ክሱ በአድራሻቸው መቅረቡ አግባብ መሆኑን፤ ዋይ. ጆ.ኤፍ ሰርቪስስ ኃ/የተ//የግ/ ማህበር እና ለሰመር ቱር ኤንድ ትራቭል ኃ/የተ//የግ/ ማኅበር በኢትዮጵያ የንግድ ሕግ የተቋቋሙ ኢትዮጵያዊያን ተቋማት አመልካች ከተጠሪ ደብቀው በኢትዮጵያ ፍርድ ቤቶች ክሰው በማስፈረድ ባለመበት ሆነው ጉዳዩ በአፈፃፀም ላይ እያለ ንብረቱ በሚገኝበት ሀገር ክስ መቅረቡ የሚነቀፍ አለመሆኑን፤ አመልካች ጉዳዩ በፈረንሳይ ሕግ ይታይልኝ ከማለት ውጪ የፈረንሳይ ሕግ የባልና ሚስት ንብረትን አስመልክቶ ከኢትዮጵያ የቤተሰብ ሕግ እንደሚቃረን ያቀረቡት አቤቱታ ካለመኖሩም በላይ የሥር ፍርድ ቤት የሁለቱ ሀገራት ሕጎች እንደማይቃረኑ አረጋግጦ የሰጠው ውሳኔ የሚነቀፍ አይደለም፡፡ የአመልካች አበዳሪው ድርጅት የግል

ድርጅት መሆኑን አውቀው በራሳቸው ስም ከሳሽ ሆኖ ጉዳዩ ውሳኔ አግኝቶ እያለ ተጠሪ ከሳሽ ሲሆኑ ጉዳዩ መልኩን ቀይሮ ክሱ በአረብ ኢምሬት መቅረብ አለበት በማለት ያቀረቡት ቅሬታ ተቀባይነት የሌለው በመሆኑ የአመልካች አቤቱታ ውድቅ ሆኖ የሥር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ ፀንቶ፤ የጠበቃ እና ሌሎች ወጪዎችን አመልካች እንዲተኩላቸው ጠይቀዋል። አመልካችም ነሃሴ 2 ቀን 2014 ዓ/ም በተፃፈ የመልስ መልስ ክርክራቸው የብሔራዊ የዳኝነት ሥልጣንን የሚመለከት እንጂ በፌደራል ፍርድ ቤቶች መካከል ስላለው ሥልጣን ባለመሆኑ ተጠሪ የጠቀሱት ሕግ ለጉዳዩ አግባብነት የሌለው መሆኑን ፤የአመልካች አድራሻ አዲስ አበባ ሊሆን የቻለው በየአመቱ በሚታደስ ጊዜያዊ የመኖሪያ ፈቃድ በመሆኑ መሠረታዊ የሕግ ክርክሩን ሊቀይር አለመቻሉን ፤ ድርጅቱ ኃ/የተ/የግ/ማኅበር ሆኖ የአንድ ሰው ኩባኒያ እንጅ የግል (ሶል ፕሮፕራይተር) አለመሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ የግል ድርጅት ነው ቢባል እንኳን ድርጅቱ ፈርሶ የሂሳብ ማጣራት ሳይደረግ ለድርጅቱ የተከፈለውን ገንዘብ ባልና ሚስት ሊከፋፈሉ የሚችሉበት የሕግ አግባብ የለም በማለት የሰበር አቤቱታቸውን በማጠናከር ተከራክረዋል።

የጉዳዩ አመጣጥ ከላይ የተመለከተውን ሲመለከት ለሰበር ቅሬታው ምክንያት የሆነው ውሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት መሆን አለመሆኑን የሰበር አቤቱታው ያስቀርባ ሲባል የተያዘውን ጭብጥ ለጉዳዩ አግባነት ካለው ሕግ አንፃር እንደሚከተለው ተመርምሯል።

የፍርድ ቤቶች ሥልጣን ከሶስት መሰረታዊ ጉዳዮች አንፃር የሚታይ መሆኑ ይታወቃል። ይኸውም ብሔራዊ የዳኝነት ስልጣን (judicial jurisdiction)፤ የስረ ነገር የዳኝነት ስልጣን (material jurisdiction) እና የግዛት ክልል ሥልጣን (local jurisdiction) ናቸው። የስረ ነገር እና የግዛት ክልል የዳኝነት ስልጣን የሚወሰነው በሀገራዊ (ብሔራዊ) ሕጎች (domestic or national laws) ሲሆን በዋናነት በስነ ስርዓት ሕጎች አልያም በመሰረታዊ ሕጎች (substantive laws) ተደንግጎ ይገኛል። ብሔራዊ የዳኝነት ስልጣን (judicial jurisdiction) የሥልጣን ምንጭ ዓለም ዓቀፍ የግለሰብ ሕግ (private International law) ፣ በሀገሮች መካከል በሚደረግ ሁለትዮሽ ወይንም ሶስትዮሽ ስምምነቶች ፤ ዓለም ዓቀፍ ተቀባይነትን ያገኙ ሕጉች ወይንም ልማዶች ሊሆን ይችላል። በኢትዮጵያም ዓለም ዓቀፍ የግለሰብ ሕግ (private International law) የዳበሩ ልምዶች እና ተቀባይነት ያላቸው መርሆዎች መሠረት ተደርጎ ለጉዳዮች እልባት ሲሰጥ ቆይቷል። ከእነዚህ የዳበሩ ልምዶችና በዘርፉ የተደረጉ ጥናቶች እንደሚያመለክቱት የአንድ ሀገር ፍርድ ቤት በጉዳዩ ላይ ብሔራዊ የዳኝነት ሥልጣን አለው ወይስ የለውም ለማለት መሠረት ተደርጎ የሚወሰደው ከተከሳሽ ጋር ያለው ግንኙነት መለኪያ አንዱ ሲሆን፤ ይኸውም ከተከሳሽ ሰው ወይንም (action impersonal) የሕግ ይሁን የተፈጥሮ ሰው ዘግነቱ ወይንም መደበኛ መኖሪያው ከፍርድ ቤቱ ጋር ያለው ቁርኝት፤ ለክሱ ምክንያት የሆነው ድርጊት (Act) ውል፤ ከውል ውጪ የተፈፀመበት ከሀገር ጋር ያለው ቁርኝት፤ ለክሱ ምክንያት የሆነው ንብረት (property) ተንቀሳቃሽ ይሁን የማይንቀሳቀስ የሚገኝበት አልያም የተከሳሽ ፈቃድ (consent) መኖር ወይንም አለመኖር መለኪያዎች ተደርጎ ይወሰዳሉ። ከዚህ ባለፈም በጉዳዩ ላይ ያለው ብሔራዊ ጥቅምና

ፖ/ሊስ (National interest or public policy) መኖሩ ሲረጋገጥ ክሱ የቀረበበት ሀገር ብሔራዊ የዳኝነት ሥልጣን አለው ሊባል ይችላል፡፡

ከዚህ አንፃር ወደተያዘው ጉዳይ ስንመልስ የተጠሪ የዳኝነት ጥያቄ ዜግነታቸውም ሆነ መደበኛ ነዋሪነታቸው ፈረንሳይ ሀገር በሆኑት በግራ ቀኙ ጋብቻ ውስጥ በፈረንሳይ ሀገር የተፈሩ ኢትዮጵያዊያን ለሆኑ የንግድ ድርጅቶች በብድር ተሰጥቶ ብድሩን ለማስመለስ አመልካች በፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ባቀረቡት ክስ የብድሩ ገንዘቡ ለአመልካች እንዲከፈል ውሳኔ ተሰጥቶ፤ አመልካች የብድር ገንዘቡ እንዲመለስላቸው በፍርድ ባለመብት የሆኑበትን ፍርድ ለማስፈፀም የአፈፃፀም አቤቱታ የቀረበበት ገንዘብ የጋራ እንዲባልላቸው የጋብቻ ፍቺ ውጤትን የሚመለከት የባልና ሚስት ንብረት ክርክር መሆኑን ከመዝገቡ ለመረዳት ተችሏል፡፡ ከላይ በማብራሪያው ውስጥ እንደተመለከተው ለክሱ ምክንያት የሆነው ንብረት መገኛ መሆን ለብሔራዊ የዳኝነት ሥልጣን መኖር አንዱ ምክንያት ሲሆን፤ የብድር ገንዘቡ ተመላሽ እንዲሆን ውሳኔ የተሰጠው ወይንም አመልካች በገንዘቡ ላይ መብት ያላቸው መሆኑ የተረጋገጠው በኢትዮጵያ ውስጥ ከመሆኑም ባሻገር አመልካች በፍርድ ያገኙት መብት እውን የሚሆነው የፍርድ አፈፃፀሙ የፍርድ ባለዕዳ የሆኑት ኢትዮጵያዊያን የንግድ ድርጅቶች በኢትዮጵያ ውስጥ ባፈሩት ንብረቶች ላይ በመሆኑ የኢትዮጵያ ፍርድ ቤቶች ጉዳዩን የማየት ብሔራዊ የዳኝነት ሥልጣን አላቸው፡፡

በፌደራል ፍርድ ቤት በአዋጅ ቁጥር 1234/2013 ቁጥር 5(1) (በ) መሠረት የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የተጠየቀውን ዳኝነት አይቶ ውሳኔ ለመስጠት የሚያስችለው የስረ - ነገር ስልጣን (material jurisdiction) ያለው በመሆኑ ውሳኔው ስህተት ነው ለማለት ስላልተቻለ ከዚህ አንፃር የቀረበው የሰበር ቅሬታ የሕግ ድጋፍ ያለው ሆኖ ስላተገኘ ተቀባይነት አላገኘም፡፡ አመልካች በፈረንሳይ እና በኢትዮጵያ የቤተሰብ ሕግ መካከል የሕግ ግጭት ስላለ በተሻሻለው የፌደራል የቤተሰብ ሕግ መዳኘት የለብኝም የሚል ክርክር በሥር ፍርድ ቤት ሳያነሱ በሰበር ደረጃ አዲስ ክርክር መቅረቡ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 329 ድንጋጌ መሠረት ተቀባይነት ያለው አይደለም፡፡

ሲጠቃለል የገንዘቡ አበዳሪ አመልካች ብቸኛ ባለድርሻ በመሆን ያቋቋሙት ድርጅት መሆኑን፤ አመልካችም ገንዘቡ በጋብቻ ውስጥ ያልተፈራ የግላቸው መሆኑን ወይንም ከፍቺ በኋላ የተፈራ ነው የሚል ክርክር ስላላቀረቡ ለክርክሩ ምክንያት የሆነው ገንዘብ የግራ ቀኙ የጋራ በመሆኑ እኩል ሊካፈሉ ይገባል በማለት የስር ፍርድ ቤት የደረሰበት የፍሬ ነገር መደምደሚያን አይቶ የመቀየር ሥልጣን በአዋጅ ቁጥር 1234/2013 ቁጥር 10(1) ለፌደራል ጠይቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት የተሰጠ ሥልጣን ባለመሆኑና የሥር ፍርድ ቤት ውሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሞበታል ለማለት ስላልተቻለ ቀጣዩ ተወስኗል፡፡

ውሳኔ

1. የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚው ችሎት በመዝገብ ቁጥር 210935 ህዳር 17 ቀን 2014 ዓ/ም በዋለው ችሎት የሰጠው ትዕዛዝ ፤ እንዲሁም የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 242425 ግንቦት 12 ቀን 2013 ዓ/ም በዋለው የሰጠው ፍርድ ፤ ውሳኔ እና ትዕዛዝ በፍ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 348(1) መሠረት ***ፀንቷል*** ።
2. በሰበር ክርክሩ የደረሰውን ወጪ እና ኪሳራ ግራ ቀኙ የግላቸውን ይቻሉ።
3. ውሳኔው ጥቅምት 30 ቀን 2015 ዓ/ም በችሎት ተነቧል።

መዝገቡ ውሳኔ ስላገኘ ተዘግቷል።

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሠ/ኃ

የሰበር መ/ቁ. 212543

ጥር 24 ቀን 2015 ዓ.ም

ዳኞች፡- ብርሃኑ አመነው

በእውቀት በላይ

ቀነዓ ቂጣታ

ሌሊሴ ደሳለኝ

ኑረዲን ከድር

አመልካች፡ ካንትሪ ክለብ ዴቬሎፕርስ ሪል ስቴት ኃላ.የተ.የግ.ማህበር - ታማኝ በየነ - ቀረቡ

ተጠሪ፡ ወ/ሮ እናኑ ዘለቀ - ጠበቃ በላይ መሸሻ ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

መዝገቡ ለዚህ ችሎት የቀረበው የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ 228731 በቀን 06/04/2013 ዓ.ም በሰጠው ፍርድ ላይ ይግባኝ የቀረበለት የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁ 201266 በቀን 29/10/2013 ዓ.ም ይግባኙን በመሰረዝ የስር ፍርድ ቤት ዉሳኔ በማጽናቱ ዉሳኔዉ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ እንዲታረም በማለት አመልካች ባቀረበው አቤቱታ መነሻ ነው፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ በአጭሩ ሲታይ በስር ፍ/ቤት ከሳሽ ተጠሪ ሲሆኑ አመልካች ተከሳሽ በመሆን ተከራክረዋል፡፡ተጠሪ ባቀረቡት ክስ በአመልካችና በተጠሪ መካከል ጥቅምት 02 ቀን 2001ዓ.ም በተደረገ ቤትን ገንብቶ የማስረከብ ውል አመልካች ከመንግስት በሊዝ ከተረከበው ቦታ በቦታ ቁጥር A-936 የቤት አይነት 1/ በመነሻ/1001.7 ካ.ሜ በሆነ የግቢ ስፋት የስምምነቱ አካል በሆኑት የቦታ ፕላን፣ የቤት ፕላን፣ የስራ ዝርዝር እና የግንባታ እቃዎች ዝርዝር የኤሌክትሪክ፣ውሃና የስልክ መስመር እንዲሁም ዋና ዋና የውስጥ ለውስጥ አስፋልት መንገዶችን ጨምሮ ቤት ገንብቶ በ18 ወራት ውስጥ አጠናቆ ለማስረከብ ተጠሪ ለቤቱ እና ተጓዳኝ አገልግሎቶች ግንባታ ባጠጉ ጨምሮ የሚስፈልገውን ብር 2,894,285.50 (ሁለት ሚሊዮን ስምንት መቶ ዘጠና አራት ሺህ ሁለት መቶ ሰማኒያ አምስት ከ50/100) ለመክፈል ተዋውለዋል፡፡አመልካች ግንባታውን ለማጠናቀቅና ለማስረከብ የውጭ ምንዛሪ እጥረትና የኮንስትራክሽን ግብዓት ላይ የዋጋ ንረት የገጠማቸው እና የዋጋ ጭማሪ ማስተካከያ እንዲደረግላቸው እና ቤቶቹ ከሚያዚያ 2003 ዓ.ም ጀምሮ እስከ ታህሳስ 2004 ዓ.ም ለማስረከብ በተደረገ ስምምነት መሰረት የዋናው ክፍያ እና የጭማሪ ዋጋ ማስተካከያ እንዲሁም ከ2000 ዓ.ም እስከ 2007 ዓ.ም ላለው ስምንት አመት ጊዜ ውስጥ የሚከፈል የሊዝ ክፍያን ጨምሮ ተጠሪ አጠቃላይ ብር

3,426,248.47 (ሶስት ሚሊዮን አራት መቶ ሃያ ስድስት ሺ ሁለት መቶ አርባ ስምንት ከ47/100) የከፈሉ ሲሆን በውሉ መሰረት አመልካች ቤቱን ገንብቶ እንዲያስረክባቸው፣በወቅቱ ግንባታውን ገንብቶ ባለማጠናቀቁ የውሉ 10% ብር 342,624.85 (ሶስት መቶ አርባ ሁለት ሺህ ስድስት መቶ ሃያ አራት ከ85/100) መቀጮ እንዲከፍላቸው፣ቤቱን በወቅቱ ገንብቶ ባለማጠናቀቁ ከቤቱ በኪራይ ያገኙ የነበረውን በወር ብር 10,000 (አስር ሺህ) ከታህሳስ 2004 ዓ.ም ጀምሮ ክሱ እስከ ቀረበበት ቀን ድረስ 87 ወራት ብር 870,000 (ስምንት መቶ ሰባ ሺህ ብር) እና ወጪና ኪሳራ እንዲከፈላቸው ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡

አመልካች በጽሁፍ በሰጠው መልስ ተጠሪ ክስ ያቀረቡበት ጅምር ቤት የሚገኘው በኦሮሚያ ክልላዊ መንግስት ለገጣፎ ለገዳዲ ከተማ አስተዳደር ውስጥ ስለሆነ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 25 መሰረት ፍ/ቤቱ ስልጣን የለውም በማለት የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ያቀረበ ሲሆን በፍሬ ነገር ረገድ በሰጠው መልስ በውሉ አንቀጽ 14.4 እና 14.5 መሰረት አመልካች በውሉ በተመለከተው ጊዜ ውስጥ ቤቱን ገንብቶ ማስረከብ ያልቻለ እንደሆነ ለተጠሪው የተቀመጠው መፍትሔ (remedy) አመልካች ውሉን ተገዶ እንዲፈጽምለት መጠየቅ ሳይሆን የከፈለው ገንዘብ እንዲመለስለት እና ለደረሰበት ጉዳት ኪሳራ መጠየቅ ብቻ በመሆኑ ተጠሪ ያቀረቡት ክስ ውሉን ሳይረዱት ነው፡፡ተጠሪ የሪል ስቴት ቤት ሌላ ቦታ እንደማይገኝ አድርገው ውሉ በግድ ይፈጸምልኝ በማለት ያቀረቡት ክርክር አግባብ አይደለም፡፡በፍ/ብ/ህ/ቁ 2876 የአንድ ተዋዋይ ግዴታ የሌለን ቤት ገንብቶ የማስረከብ በሆነ ጊዜ ውሉ ህንፃ ስራ ውል እንጂ የሽያጭ ውል ሊባል እንደማይቻል በግልጽ ተደንግጓል፡፡አመልካችና ተጠሪ የቤት ግንባታ ውልን በተፈራረምንበት ወቅት ምንም የተገነባ ነገር የሌለበት ቦታ አዲስ ቤትን ገንብቶ የማስረከብ ውል ነው፡፡ስለዚህ እየተገነባ ያለው ቤት ውል በምንዋዋልበት ወቅት ያልነበረ እና ውላችንም ግንባታ እንጂ የሽያጭ ውል ስላልሆነ ከሳሽ የፍ/ብሔር ህጉ አንቀጽ 2892(1/2) ድንጋጌ ያለቦታው በመጥቀስ ያቀረቡት ክስ ውድቅ ሊደረግ ይገባል፡፡አመልካች ውሉን ተገዶ ቢፈጽም የውል ፈፃሚውን ነፃነት ስለሚጎዳ በተጠሪ ላይ ጉዳት የደረሰ እንደሆነ ይህንኑ ከመጠየቅ በቀር ውሉን አመልካች ተገዶ የሚፈጽምበት ምክንያት የለም፡፡የተጠሪ የውል ይፈፀምልኝ ክስ የፌዴራሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ችሎት በመ/ቁ 35472 በፍ/ብ/ህ/ቁ 1776 ላይ ከሰጠው አስገዳጅ ህግ ትርጉም አንፃር አንዱንም መስፈርት ስለማያሟላ ክሱ ውድቅ ይደረግ፤አመልካች የቤቱን ግንባታ በ18 ወራት ውስጥ እንዳላጠናቀቀ ሁሉ ተጠሪም በበኩላቸው የሚፈለጉባቸውን ክፍያ በውሉ መሰረት አልከፈሉም የከፈሉትም ቢሆን በውሉ አንቀጽ 7 በተቀመጠው ሁኔታ ሳይሆን ቆራርጠው በመክፈላቸው የተጠሪ ቤት ግንባታ በተደጋጋሚ ተቋርጧል፡፡ተጠሪ የሚፈለግባቸውን ክፍያ ሳይፈጽሙ እና ግዴታቸውን በወቅቱ ሳይወጡ ወይም ለመወጣት ዝግጁ የነበሩ መሆኑን ሳያስረዱ አመልካች ውሉን ተገዶ እንዲፈጽም ያቀረቡት ክስ የፍ/ብ/ህ/ቁ 1757 የሚቃረን ስለሆነ 10% ኪሳራ ይከፈለኝ ሲሉ ያቀረቡት መከራከሪያ የህግ መሰረት የለውም፡፡ተጠሪ ቤቱ የዘገየበት ኪሳራ ይከፈለኝ ማለታቸው ተቀባይነት የለውም ኪሳራ መጠየቅ ይችላሉ እንኳን ቢባል የኪሳራውን መጠን በተመለከተ ተጠሪ በክሳቸው ላይ የጠቀሱትን ቤቱ ቢከራይ ኖሮ ያስገኝ የነበረውን ገቢ ለመጠየቅ

አይችሉም፡፡በፍ/ብ/ህ/ቁ 1889 እና 2090 በተደነገገው መሰረት ተዋዋይ ወገኖች ስለሚከፈለው ኪሳራ አስቀድመው በውላቸው መወሰን እንደሚችሉ በተደነገገው መሰረት የቤቱ ግንባታ ከውሉ የጊዜ ገደብ በላይ ለዘገየበት ጊዜ ለቤት አሰሪው መከፈል የሚገባው ኪሳራ 0.1% በየቀኑ ተሰልቶ 10% እስኪደርስ መሆኑ በግንባታ ውሉ አንቀጽ 14.5 ተመላክቶ ይገኛል፡፡ስለሆነም ተጠሪ ከውሉ ላይ ከተቀመጠው ጣሪያ በላይ ኪሳራ ሊጠይቁ አይችሉም፡፡ተጠሪ በወር ብር 10,000 (አስር ሺህ) ሂሳብ ተሰልቶ እንዲከፈላቸው የጠየቁት የቤት ኪራይ መጠን ቤቱ የሚገኘው አካባቢ ገና በመልማት ላይ ያለና ከመሀል ከተማ የራቀ በመሆኑ የተጋነነ እና የአካባቢውን ሁኔታ ያላገናዘበ በመሆኑ በአሁኑ ወቅት ቤቱ ቢከራይ ከብር 5000 (አምስት ሺህ) በላይ ሊከራይ የማይችል በመሆኑ ተጠሪ የጠየቁትን ዳኝነት ውድቅ በማለት ተከራክረዋል፡፡

ጉዳዩ የቀረበለት ከፍተኛ ፍ/ቤት የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ በብይን ዉድቅ በማድረግ በፍሬ ነገሩ ላይ የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ ሰምቶ አመልካች የግንባታ ስራውን በውሉ መሰረት ማጠናቀቅ በነበረበት ጊዜ ውስጥ ባለማጠናቀቁ እና የግንባታ ጊዜው ተራዝሞ ባለበት ሁኔታ በውሉ ተገድጄ የግንባታ ስራን የምፈጽምበት ግዴታ ቀሪ አድርጌያለሁ ሲል አመልካቹ ያቀረበዉን መከራከሪያን ውድቅ በማድረግ፣በፍ/ብ/ህ/ቁ 1776(1) እና በሰበር መ/ቁ 35472 ላይ የህግ ትርጉም መሰረት አመልካች በህግ የሰውነት መብትና ግዴታ ያገኘ በመሆኑ ነፃነቱን ስለሚነካ ተገድጄ አልፈጽምም ያለውን በተመለከተ ነፃነቱን የሚነካ የህግ ምክንያት የለም፤ቀሪ የቤቱ ስራ የአመልካችን ልዩ ሙያና ችሎታ የሚጠይቅ ቴክኒካል የሆኑ ስራዎች ስለሆኑ በውል መሰረት ተገደው ሊፈጽም ይገባል፡፡ተጠሪ የጠየቁት መቀጮ 10% ከፍ/ብ/ህ/ቁ 1790 መሰረት በአንድ በኩል ተገዶ ውል ይፈፀምልኝ በሌላ በኩል የውሉን መቀጮ ይክፈለኝ በማለት መጠየቅ አይችሉም፡፡አመልካች በውሉ መሰረት ባለመፈፀሙ ተጠሪ ከቤቱ ማግኘት የነበረባቸውን ጥቅም ያጡ ስለሆነ የቤቱን ኪራይ በወር ብር 5000 (አምስት ሺህ) ሂሳብ ከታህሳስ 2004 ዓ.ም ጀምሮ የ87 ወራት በድምሩ ብር 435,000 (አራት መቶ ሰላሳ አምስት ሺህ) ከመጋቢት 30 ቀን 2011 ዓ.ም ጀምሮ እዳው ተከፍሎ እስኪያልቅ ድረስ ከሚታሰብ 9% ወለድ ጋር ለተጠሪ እንዲከፍሉ በማለት ወስኗል፡፡ አመልካች በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ለፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ በመ/ቁ 201266 ያቀረበ ሲሆን ፍ/ቤቱ በቀን 29/10/2013 ዓ.ም ይግባኙን በመሰረዝ መዝገቡን ዘግቶታል፡፡ ይህ አቤቱታ የቀረበው ይህንኑ በሰበር ለማሳረም ነው፡፡

የአመልካች ጠበቃ በቀን 06/12/2013 ዓ.ም ጽፈው ያቀረቡት አቤቱታ አጭር ይዘቱ፡ የስር ፍ/ቤት የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 22 እና 24 በመጥቀስ ውሉ የተደረገው በአዲስ አበባ በመሆኑ እና የአመልካች ዋና መስሪያ ቤት አዲስ አበባ በመሆኑ የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ጉዳዩን በውክልና ማየት የሚችል ቢሆንም ከፍተኛው ፍ/ቤት አዲስ አበባ ውስጥ ስለሚገኝ ሁለቱም ተደራሽ ስለሆኑ የፌ/ጠ/ፍ/ቤት ሰበር በመ/ቁ 15904 ጉዳዩን የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ማየት አይችልም ብሎ ቢወስንም ውሳኔው ያልታተመ በመሆኑና ከዚህ በፊት በተቃራኒው የተሰጠ ውሳኔ ጠቅሶ ስላልሻረ አስገዳጅነት የለውም

በማለት የሰጠው ውሳኔ ከአዋጁ ድንጋጌ ውጪ ራሱን ቅድመ ሁኔታ በመፍጠር በተመሳሳይ ጉዳይ ላይ ፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ችሎት የሰጠው አስገዳጅ የህግ ትርጉም ውድቅ ያደረገበት ሁኔታ መሰረታዊ የህግ ስህተት አለበት፡፡በህገ መንግስቱ አንቀጽ 80(2) መሰረት ክልሎች በግዛታቸው ውስጥ የሚነሱ የፌዴራል ጉዳዮችን የማየት ስልጣን ተሰጥቷቸዋል፤እንዲሁም በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 25 መሰረት የግዛት ስልጣን ያለው የኦሮሚያ ክልል ፍ/ቤት እንጂ ፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት አይደለም፣አመልካችና ተጠሪ ባደረግነው ውል አንቀጽ 14.4 እና 14.5 መረዳት የሚቻለው ቤት ሰሪ በውሉ በተመለከተው ጊዜ ውስጥ ቤቱን ገንብቶ ማስረከብ ካልቻለ ለቤት አሰሪው የተቀመጠው መፍትሔ ቤት ሰሪው ውሉን ተገዶ እንዲፈጽም መጠየቅ ሳይሆን የከፈለው ገንዘብ እንዲመለስለት እና እስከ 10 በመቶ ድረስ ኪሳራ እንዲከፈለው ለመጠየቅ መሆኑን ስምምነት ተደርጓል፡፡ የውሉን ተገዶ መፈፀም አማራጭ በውል ቀሪ አድርገናል የሚለውን ክርክራችን በማለፍ አመልካች ተገዶ ውሉን መፈፀም አለበት በማለት የተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ነው፡፡ በፍ/ብ/ህ/ቁ 1771 እና 1779 መሰረት ተጠሪ ግዴታቸውን ሳይወጡ ክፍያዎችን አቆራርጠው በመክፈላቸውና በማዘግየታቸው ቤቱ ግንባታ የዘገየ ሆኖ ሳለ እንዲሁም አመልካችና ተጠሪ የተስማማንበት የኪሳራ መጠን በውላችን ላይ ተመልክቶ እያለ የስር ፍ/ቤት ከህግ ውጪ የቤት ኪራይ እንድከፍል የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ ህግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ዉሳኔዉ እንዲታረም በማለት አመልክተዋል፡፡

የአመልካች አቤቱታ በሰበር አጣሪ ተመርምሮ የስር ፍርድ ቤት የክርክር መነሻ የሆነውና በተከራካሪ ወገኖች መካከል በኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ልዩ ስሙ ለገጣፎ ተብሎ በሚታወቅ ቦታ የቤት ግንባታና ማስረከብ ውል በሚመለከት የቀረበውን አቤቱታ ተቀብሎ ለማየት የግዛት ዳኝነት ሥልጣን ያላቸው መሆን አለመሆን፣ ውሉንም ተገደው ስለመፈፀም አማራጭ ቀሪ ያደረጉ ስለመሆናቸው በውላቸው ተገልፆ እያለ አመልካች ተገዶ እንዲፈጽም፣ ኪሳራ ጭምር እንዲከፍል የተወሰነበት አግባብ ከህገ መንግስቱ አንቀጽ 80(2)፣ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 25፣ ከፍ/ብ/ህ/ቁ 1776 እና ተከታይ ድንጋጌዎች እንደዚሁም ጥቅምት 2 ቀን 2001 ዓ.ም ከተደረገው የቤት ግንባታና ማስረከብ ውል አንቀጽ 14.4 እና 14.5 አንፃር ለማጣራት መዝገቡ ያስቀርባል ተብሎ ተጠሪ መልስ እንዲሰጥበት ታዟል፡፡

ተጠሪ በቀን ጽፎ ባቀረቡት መልስ የስር ፍ/ቤት ግዛት ስልጣን የለውም በማለት በቀረበው መቃወሚያ ላይ ፍ/ቤቱ ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 10(2) እና በሰ/መ/ቁ 109393 ቅጽ 19 ከተሰጠው ሰበር ውሳኔ አንፃር ፍትህን የሚያጓድል ባልሆነበት ይግባኝ ሊቀርብ አይገባም፤ አመልካች ከዚህ ቀደም የሰበር አመልካች ሆኖ በሰበር መ/ቁ 159041 ህዳር 28 ቀን 2011 ዓ.ም ከፍ/ቤቶች የግዛት ክልል ስልጣን አንፃር ያስወሰነውን ፍርድ የህገ-መንግስት አጣሪ ጉባዔ መጋቢት 25 ቀን 2011 ዓ.ም በመ/ቁ 1937/09 በዋለው ችሎት ሽሮታል፣የፌዴሬሽን ምክር ቤት ህገ-መንግስቱን ለመተርጎም ባለው ስልጣን ተጠቅሞ የሚሰጠው ውሳኔ የመጨረሻ ሆኖ መፈፀም እንደሚገባው በሰበር መ/ቁ 43511 ቅጽ 11 ላይ አስገዳጅና ገዢ ትርጉም ሰጥቶበታል፤ክስ የቀረበበት ቤት ገንብቶ የማስረከብ ውል የተያዘው አዲስ አበባ በመሆኑና

የአመልካች ዋና መስሪያ ቤት አዲስ አበባ በመሆኑ፣የተጠሪ መኖሪያ አድራሻ ካናዳ ቶሮንቶ በመሆኑ በፌዴራል ፍ/ቤቶች ማቋቋሚያ አዋጅ 1234/13 አንቀጽ 5(1)(ሸ) እንዲሁም የሰበር መ/ቁ 36460 ቅጽ 8 እና ሰበር መ/ቁ 144613 ቅጽ 23 መሰረት የፌዴራል ፍ/ቤቶች የስረ ነገርና ግዛት ክልል ስልጣን ያላቸው ስለመሆኑ አስገዳጅ ውሳኔ ተሰጥቶበታል፤ውሉ የማይንቀሳቀስ ንብረትን የሚመለከት ነው ቢባል እንኳን ክሱ ግንባታው በሚገኝበት ላስቻለው ባለስልጣን ፍ/ቤት ወይም የአመልካች ዋና መስሪያ ቤት በሚገኝበት አዲስ አበባ በሚያስችለው ስልጣን ባለው ፍ/ቤት በአማራጭ ለማቅረብ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 25(2) መሰረት እንዲሟሉ የሚጠበቁበት ሁለት መስፈርቶች የተሟሉ በመሆናቸው ተጠሪ ክሱን ለፌዴራል ፍ/ቤት ማቅረቡ ህጋዊ መሰረት ያለው ነው፤በተመሳሳይ ሁኔታ ቤት ገንብቶ የማስረከብ ውል በፌዴራል ፍርድ ቤቶች በአመልካች ላይ ክስ ቀርቦበት እንደ ውሳኔው ሲፈጸም ለመቆየቱ ማሳያ ይሆን ዘንድ ሰበር መ/ቁ 100541 ዉሳኔ ይገኛል፤በሌላ በኩል በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 22(1) ላይ በድርጅቱ ዋና መስሪያ ቤት ወይም ቅርንጫፍ መ/ቤት ባለበት ክስ ማቅረብ እንደሚቻል በግልጽ ደንግጓል፤አመልካች በገባው የመጀመሪያ ውል መሰረት ቤቱን አጠናቆ ለማስረከብ በዋጋ ንረት ምክንያት አለመቻሉን ቤቱን አጠናቆ የቤት ማስረከቢያ ጊዜ ማራዘሚያ ስምምነት በመደረጉ ምክንያት አመልካቹ ጠቅሶ እየተከራከረበት ያለው የውሉ አንቀጽ 14.4 ተፈፃሚነት የለውም፡፡አንቀጹ ተፈፃሚነት ሊያገኝ የሚችለው ብቸኛ ሁኔታ ተዋዋዮች የግንባታ ጊዜውን በስምምነት ማራዘም ሳይችሉ ቀርተው ቢሆን ኖሮ ብቻ ነው፤ የቤት ማስረከቢያ ጊዜው መራዘሙን ተከትሎ አመልካች ለተጠሪ ቤት ሰርቶ ሊያስረክብ በገባው ግዴታ መሰረት ቤቱን ገንብቶ የባለቤትነት ማረጋገጫ ካርታ በካርታ ቁጥር L/X/L/D/7459/07 በቀን 15/08/07 ዓ.ም አሰርቶ መስጠቱ፣የሊዝ ክፍያ መጠናቀቁ በስር ፍ/ቤት የተረጋገጠ ጉዳይ ነው፡፡አመልካቹ በተሰጠው ተጨማሪ ጊዜ ቤቱን አጠናቆ ለማስረከብ ባለመቻሉ ይህን ክስ በስር ፍ/ቤት ስናቀርብና ሲፈረድበት የቤቱ አብዛኛው ስራ የተጠናቀቀ በመሆኑና የቀሩትን ማጠቃለያ ስራዎች በጋራ ለመለየት እንዲቻል የግራ ቀኙን ባለሙያዎች ይዘው ያልተጠናቀቁና እንደውሉ ሊሟሉ የሚገባቸው 16 የሚሆኑ በዓይነትና በስም ዝርዝር ግራ ቀኙ ተማምነውበት ተፈርሞ አመልካቹ በቀን 20/12/2013 ዓ.ም በቁጥር ሲሲዲ/693/13 በተፃፈ ደብዳቤ በጋራ ተለይቶ የተፈረመውን ቀሪ ስራ አባሪ በማድረግ እነዚህ ጉድለቶችን እስከ የካቲት 15 ቀን 2014 ዓ.ም ድረስ አስተካክሎ ሊያስረክብ ማረጋገጫ መስጠቱ እንደውሉ ተገዳጅ መሆኑን ራሱ አምኖ የተቀበለ እና ቤት ሰርቶ የማስረከብ ውሉ ቀሪ ያልተደረገም መሆኑን ነው፡፡ አመልካች የውሉን አንቀጽ 14.4 እና 14.5 በመጥቀስ የጉዳት ኪሳራው ውሳኔ ተገቢነት የለውም በማለት ያቀረበው ክርክር አንቀጾችን ሙሉ በሙሉ በእጅጉ የሚጣረስ ነው፡፡እነዚህ አንቀፆች ግንባታ ውሉ በስምምነት ተራዝሞ ውሉ ቀሪ ባልተደረገበት ሁኔታ ከግንባታ መዘግየት ጋር ለሚደርስ ጉዳት ተፈፃሚነት የማይኖራቸው በመሆኑ የስር ፍ/ቤት የሰጠው ውሳኔ የሚነቀፍ አይደለም በማለት ተከራክረዋል፡፡አመልካች አቤቱታውን በማጠናከር የመልስ መልስ አቅርቧል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ እና ክርክሩ በአጭሩ ከላይ የተገለፀውን የሚመስል ሲሆን እኛም የግራ ቀኙን ክርክር እና አቤቱታ የቀረበበት ውሳኔ በሰበር አጣሪ ችሎት የተያዘዉን ጭብጥ መሰረት በማድረግ አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ መዝገቡን መርምረናል፡፡

<u>የመጀመሪያዉ ጭብጥ የዳኝነት ስልጣን የሚመለከት ነዉ</u>

በሰበር አጣሪ ችሎት የተያዘዉ የመጀመሪያ ጭብጥ የክርክር መነሻ የሆነውና በተከራካሪ ወገኖች መካከል የተደረገዉ ዉል በኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ልዩ ስሙ ለገጣፎ ተብሎ በሚታወቅ ቦታ ቤት ገንብቶ ማስረከብ ውል በሚመለከት የቀረበውን ክስ የፌዴራል ፍርድ ቤት ተቀብሎ ለማየት የግዛት ዳኝነት ሥልጣን ያለው መሆን አለመሆኑን የሚመለከት ነዉ፡፡

በመሰረቱ የፍርድ ቤቶች የዳኝነት ስልጣን በሶስት መሰረታዊ ጉዳዮች ተከፍሎ የሚታይ መሆኑ ይታወቃል፡፡ይኸዉም ብሔራዊ የዳኝነት ስልጣን (judicial jurisdiction)፣ የስረ ነገር የዳኝነት ስልጣን (material jurisdiction) እና የግዛት ክልል የዳኝነት ስልጣን(local jurisdiction) ተብሎ የሚከፈል ሲሆን የመጀመሪያዉ የዳኝነት ስልጣን ምንጭ ዓለም አቀፍ የግለሰብ ህግ ወይም ስምምነቶች ወይም ተቀባይነት ያገኙ መርሆዎችን በመከተል ሊወሰን ይችላል፡፡የአንድ ፍርድ ቤት የስረ ነገር እና/ወይም የግዛት ክልል ስልጣን ምንጩ ብሔራዊ ህጎች ሲሆኑ በዋናነት የስነ ስርዓት እና እንደ አግባብነቱ በመሰረታዊ ህጎችም ተደንግጎ እናገኛለን፡፡በተለይም የፌዴራል ስርዓት በሚከተሉ ሀገሮች የዳኝነት አካል አወቃቀር እና የስልጣን ክፍፍል በዋናነት በህገ መንግስት የሚወሰን ስለመሆኑ የበርካታ ሀገሮች ልምድ ያሣያል፡፡

የሀገራችን የፍርድ ቤቶች አወቃቀር ስንመለከት የፌዴራል መንግስት አወቃቀር ስርዓት በ1987 ዓ.ም በወጣዉ ህገ መንግስት መሰረት ስርዓቱ ፌዴራላዊ መሆኑን ተከትሎ ፍርድ ቤቶችም የፌዴራል እና የክልል ፍርድ ቤቶች ተብለዉ ትይዩ የሆኑ ሁለት ፍርድ ቤቶች የተዋቀሩ ስለመሆኑና የፌዴራል ፍርድ ቤቶች በፌደራል ጉዳይ ላይ እንዲሁም የክልል ፍርድ ቤቶች በክልል ጉዳይ የዳኝነት ስልጣን የተሰጣቸዉ መሆኑን ከህገ መንግስቱ ድንጋጌዎች መገንዘብ ይቻላል፡፡የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 78 እና 80(1/2) ይመለከታል፡፡ከዚህ የስልጣን ክፍፍል መርህ መገንዘብ የሚቻለዉ ክልሎች በክልላዊ ጉዳይ ላይ ሉዓላዊ ስልጣን ያላቸዉ መሆኑን ነዉ፡፡ከዚህም በተጨማሪ የፌዴራል ጉዳዮችን የሚመለከት የፌዴራል ፍርድ ቤት ባልተቋቋመባቸዉ ክልሎች ዉስጥ የክልል ፍርድ ቤቶች በህገ መንግስቱ በተሰጠ ዉክልና መሰረት የፌዴራል ጉዳዮችን የመዳኘት ስልጣን በጣምራነት እንደተሰጣቸዉ የህገ መንግስቱ አንቀጽ 80(2/4) ድንጋጌ በግልጽ ያሳያል፡፡በመሆኑም በክልል የሚነሱ የፌደራል ፍርድ ቤት ስልጣን የሆኑ ጉዳዮች በሌላ ህግ በግልጽ ካልተመለከተ በስተቀር በክልል ፍርድ ቤት ዳኝነት የሚታዩ መሆናቸዉን እንገነዘባለን፡፡ስለሆነም የክልል ፍርድ ቤቶች በጣምራ ስልጣናቸዉ በክልል ግዛት ወሰን የተነሱ የፌዴራል ጉዳዮችን የማየት ስልጣን ስላላቸዉ ጉዳዩ ወደ ፌዴራል ፍርድ ቤት ስልጣን ስር

የሚወድቅ አይደለም ማለት ነዉ፡፡በሌላ አገላለጽ ጉዳይ በህጉ ፣በተከራካሪዎቹ ወይም በንብረቱ ምክንያት የፌዴራል ጉዳይ ቢሆንም በክልል ግዛት ስር የሚገኝ ከሆነ የክልል ፍርድ ቤቶች እንዲያዩት በህገ መንግስት ዉክልና ተሰጥቷቸዋል፡፡ከዚህም የተነሳ የክልል ፍርድ ቤቶች በግዛታቸዉ ባሉ ሰዎች ወይም ንብረቶች ጋር በተያያዘ የሚነሳ የፌዴራል ጉዳይን ዉክልናቸዉ እስካልተነሳ ድረስ የመመልከት ስልጣን አላቸዉ፡፡ከዚህም በተጨማሪ በህገ መንግስት ለፌዴራል እና ለክልል ፍርድ ቤቶች ጣምራ ስልጣን መሰጠቱ ተከራካሪ ወገኖች ወደ ፈለጉት ፍርድ ቤት እንዲወስዱ (forum shopping) የሚፈቅድ እንዳይሆን ጥንቃቄ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡

በተያዘዉ ጉዳይ ተከራካሪ ወገኖች በተለያየ ክልል ነዋሪ መሆናቸዉን እና አመልካቹ በፌዴራል መንግስት የተመዘገበ ድርጅት መሆኑን ተከትሎ ጉዳዩ የፌዴራል ጉዳይ ስለመሆኑ ክርክር አልቀረበበትም፡፡ይሁንና የከሳሽ የዳኝነት ጥያቄ በዉሉ መሰረት እንዲፈጽም የሚል በመሆኑ የግዛት ስልጣን የሚወሰነዉ በፍ/ብ/ስ/ስህግ ቁጥር 24 መሰረት ነዉ በሚል የሥር ፍርድ ቤት የዳኝነት ስልጣን ላይ የቀረበዉን መቃወሚያ ዉድቅ ያደረገ ሲሆን አመልካች በበኩሉ ጉዳዩ የማይንቀሳቀስ ንብረት ለመረከብ የቀረበ ነዉ በሚል በፍ/ብ/ስ/ስ/ህግ ቁጥር 25 መሰረት ንብረቱ ያለበት ፍርድ ቤት የግዛት ስልጣን አለዉ በሚል ተከራክሯል፡፡በክርክሩ እንደተገለጸዉ ክሱ ዉልን መሰረት ያደረገ ሲሆን የተጠየቀዉ ዳኝነት የቤቱን ግንባታ አጠናቆ እንዲያስረክብ የሚል ነዉ፡፡የዉል ግንኙነት መብትና ግዴታ የሚፈጥረዉ አንድም በተዋዋዩ ሰዉ(right in personum) ላይ ወይም በሆነ ንብረት (right in rem)ላይ ሊሆን ይችላል፡፡በዉሉ የተፈጠረዉ መብት በሰዉ ላይ ግዴታን የሚፈጥር ሲሆን ክሱ የሚቀርብበትን ፍርድ ቤት በመምረጥ ረገድ የፍ/ብ/ስ/ስ/ህጉ አንቀጽ 24(1) ለከሳሽ ወገን የተተወ መሆኑ አከራካሪ አይደለም፡፡ነገር ግን ጉዳዩ መነሻ ዉል ቢሆንም በተለይም የማይንቀሳቀስ ንብረት የሚመለከት ሲሆን የግዛት ዳኝነት ስልጣኑ የሚለየዉ በፍ/ብ/ስ/ስ/ህግ ቁጥር 25 ስር በተደነገገዉ አግባብ እንደሆነ ከድንጋጌዉ ይዘት ማየት ይቻላል፡፡ በዚህም ጉዳይ ክሱ ቤቱን ለመረከብ የቀረበ እንደመሆኑ በፍ/ብ/ህግ ቁጥር 25(1/ሐ) እንደተመለከተዉ ጉዳዩ በንብረቱ ላይ ያለዉን መብት ለማስወሰን የቀረበ መሆኑን ያሣያል፡፡ይህ ከሆነ ደግሞ ክሱ መቅረብ የሚገባዉ ንብረቱ የሚገኝበት ግዛት ክልል ባለዉ ፍርድ ቤት ነዉ፡፡በዚህ ረገድ በተመሳሳይ ሁኔታ አመልካቹ ተከራካሪ በሆነበት ጉዳይ ላይ ክርክሩ የግዛት ስልጣንና የስረ ነገር ልጣን አጣምሮ የያዘ መሆኑን፤ጉዳዩ ለተከራካሪ ወገኖች አመቺነት በሚል ምክንያት ለተከራካሪ ወገኖች ምርጫ የሚተዉ አለመሆኑን በመግለጽ ክሱ ንብረቱ በሚገኝበት ግዛት ክልል ፍርድ ቤት መቅረብ አለበት በሚል አስገዳጅ የህግ ትርጉም ተሰጥቶበታል፡፡ሰበር መ/ቁ/ 159041 ይመለከታል፡፡ሰበር ችሎቱ የሰጠዉ የህግ ትርጉም በተመሳሳይ ጉዳዮች ላይ አስገዳጅነት እንዳለዉ በአዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀጽ 26(3) ስር ተደንግጓል፡፡ስለዚህም የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ላይ የሰጠዉ ብይን የሰበር ችሎቱን ዉሳኔ ያላገናዘበ በመሆኑ ሊታረም ይገባል፡፡

በሌላ በኩል ተጠሪ በበኩሉ ከዚህ ቀደም ተመሳሳይ ክርክር (ጉዳዩ) በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ተወስኖ አመልካቹም አቤቱታ እስከ ህገ መንገስት አጣሪ ጉባኤ አቅርቦ የሰበር ችሎቱ ዉሳኔ ተሸሯል በማለት የጠቀሳቸዉን ዉሳኔዎች ይዘት መርምረናል፡፡በተለይም የተጠቀሰዉ የህገ መንገስት አጣሪ ጉባኤ መ/ቁ 1937/09 የሰጠዉ ዉሳኔ ሲሆን በይዘቱ ሲታይ በፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት መታየቱ የህገ መንግስት ትርጉም የሚያስፈልገዉ አይደለም ተብሎ የአመልካቹ አቤቱታ ዉድቅ መደረጉን የሚያሳይ እንጂ ሰበር ችሎቱ በመ/ቁ/159041 ላይ እና በሌሎችም ተመሳሳይ ክርክሮች ላይ የሰጠዉን አስገዳጅ ዉሳኔ በግልጽ የሻረዉ መሆኑን አያሣይም፡፡እንደሚታወቀዉ የህገ መንግስት ትርጉም አስገዳጅ ዉሳኔ ተብሎ የሚወሰደዉ ጉዳዩ ለፌዴሬሽን ም/ቤት ቀርቦ ህገ መንግስታዊ ትርጉም የተሰጠበት ሲሆን ነዉ፡፡(አዋጅ ቁጥር 251/1993 አንቀጽ 11 እንዲሁም አዋጅ ቁጥር 1261/2013 አንቀጽ 22(1)ይመለከታል)፡፡በዚህ ጉዳይ የተሰጠ ህገመንግስታዊ ትርጉም ስለመኖሩ የቀረበ አስረጂ ባለመኖሩ በተጠሪ በኩል የቀረበዉን ክርክር አልተቀበልንም፡፡ ከዚህም ባሻገር ሰበር ችሎቱ በመ/ቁ/100541 ላይ የሰጠዉ ዉሳኔ ይዘት ሲታይ የፍሬ ነገር ክርክሩን በሚመለከት እንጂ የዳኝነት ስልጣን በሚመለከት ጭብጥ ተይዞ አቋም የተወሰደበት ባለመሆኑ ለተያዘዉ ክርክር ነጥብ አግባብነት የለዉም፡፡በዚህ ሁሉ ምክንያት የስር ፍርድ ቤት በአመልካች የቀረበዉን የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ዉድቅ ማድረጉ ስህተት ነዉ ብለናል፡፡ጉዳዩ በዚህ ጭብጥ የተቋጨ ስለሆነ ተከታዮቹን የፍሬ ነገር ጭብጦችን መመርመር አላስፈለገም፡፡

ሲጠቃለል ጉዳዩ ከተከራካሪ ወገኖች ማንነት እና አድራሻ አኳያ ሲታይ የስረ ነገር የዳኝነት ስልጣን የፌዴራል ፍርድ ቤቶች መሆኑ አከራካሪ ባይሆንም የማይንቀሳቀስ ንብረት ለመረከብ የቀረበ ክስ በመሆኑና ንብረቱ የሚገኘዉ ኦሮሚያ ክልል ስለመሆኑ ክርክር ያልቀረበበት በመሆኑ በህገ መንግስቱ የተሰጠ ዉክልና ስልጣንና ንብረቱ የሚገኝበት ቦታ አንጻር በተመሳሳይ ጉዳይ የግዛትም ሆነ የስረ ነገር ስልጣን በተመለከተ ሰበር ችሎቱ ቀደም ሲል በመ/ቁ/ 159041 በሰጠዉ አስገዳጅ ዉሳኔ መሰረት መታየት ሲገባዉ የዉል ጉዳይ ነዉ በሚል ምክንያት የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ተቀብሎ በስረ ነገሩ ላይ አከራክሮ የሰጠዉ ዉሳኔም ሆነ ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት ሳያርመዉ ማለፉ የሰበር ችሎቱን አስገዳጅ ዉሳኔ የሚቃረን ስለሆነ በፌዴራል ፍርድ ቤቶች 1234/2013 አንቀጽ 2(4/ሸ) እና 10(1/ለ) መሰረት ሊታረም የሚገባዉ ሆኖ አግንተናል፡፡በዚሁ አግባብ ተከታዩን ዉሳኔ ሰጥተናል፡፡

<u>ዉ ሳ ኔ</u>

1ኛ/የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ/ 228731 ላይ በቀን 06/04/2013 ዓ.ም የሰጠዉን ፍርድ በማጽናት የፌዴራል ጠ/ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁ/ 201266 ላይ በቀን 29/10/2013 ዓ.ም የሰጠዉ ትእዛዝ ተሸሯል፡፡

2ኛ/ይህ ፍርድ ተጠሪ ስልጣን ባለዉ ፍርድ ቤት ክስ የማቅረብ መብቱን የሚከለክል አይደለም፡፡

3ኛ/ በዚህ ፍርድ ቤት የተደረገዉ ክርክር ያስከተለዉን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የራሳቸዉን ይቻሉ ብለናል፡፡

ፍርዱ በአዳሪ ሲሰራ ቆይቶ በቀን13/06/2015 ዓ.ም ግራ ቀኙ በተገኙበት ተነበበ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል ይመለስ፡፡

የሰበር መዝገብ ቁጥር 223548

ጥር 25 ቀን 2015 ዓ.ም

ዳኞች፡-...

1. እትመት አሰፋ
2. ደጀኔ አያንሳ
3. ብርቅነሽ እሱባለው
4. ሀብታሙ እርቅይሁን
5. ብርሃኑ መንግስቱ

አመልካቾች፡.....1ኛ. አቶ በላይ ዘለቀ

2ኛ. ወ/ሮ ብዙነሽ ዘለቀ 1ኛ አመልካች እና 2ኛ ተወካይ - ቀርቧል

ተጠሪ፡..... የቴፒ ከተማ ማዘጋጃ ቤት - አልቀረቡም

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል።

ፍርድ

መዝገቡ ለሰበር ሰሚ ችሎቱ ሊቀርብ የቻለው የሸካ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ቴፒ ምድብ ችሎት በአዋጅ ቁጥር 1161/2011 ቁጥር 19 እና 20 መሠረት ለአቤቱታ ሰሚ እና ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ ያልቀረበውን የካሳ ይከፈለን እና ምትክ መሬት ይሰጠን ጥያቄን ተቀብሎ የማስተናገድ የሥረ ነገር ሥልጣን የሌለው በመሆኑና ክሱም በይርጋ የሚታገድ ነው በማለት የሰጠው ብይን፤ እንዲሁም ይህን ብይን በመቃወም የቀረበውን የይግባኝ እና የሰበር አቤቱታ በተመለከቱት የሥር ፍርድ ቤቶች አቤቱታው ተቀባይነት ማጣቱ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ነው በማለት በሰበር ታይቶ እንዲታረምላቸው አመልካቾች መጋቢት 15 ቀን 2014 ዓ/ም ባቀረቡት የሰበር አቤቱታ መነሻነት ነው፡፡

ጉዳዩ የካሳ ክፍያ እና በተወሰደ መሬት ምትክ መሬት መጠየቅን የሚመለከት ሆኖ ክሱ በቀረበበት በሸካ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ቴፒ ምድብ ችሎት አመልካች በከሳሽነት ተጠሪ ደግሞ በተከሳሽነት

የተከራከሩ ሲሆን፣ አመልካቾች ያቀረቡት ክስ በአጭሩ፡- አዋሳኞቹ በክሱ ላይ የተመለከቱት በሁለት አከባቢዎች የሚገኝ አጠቃላይ ስፋቱ 2,500.00(ሁለት ሺህ አምት መቶ) የሆነ ቦታ ላይ የሚገኘውን 5,000.00 (አምስት ሺህ) እግር ቡና ተገቢውን ከሳ ሳይከፍል እና ምትክ ቦታ ሳይሰጥ ተጠሪ አትክልቱን ነቃቅሎ በማንሳት መሬቱን ለባለሥልጣናት እና ለሌሎች ግለሰቦች ስለሰጠ የንብረት ግምቱን 800,000.00 (ስምንት መቶ ሽህ) ብር ከፍሎ ምትክ ቦታ እንዲሰጣቸው እንዲወሰንላቸው ጠይቀዋል፡፡ ተጠሪም ለክሱ በሰጠው መልስ አመልካቾች ይዞታቸው ያለአግባብ ከተወሰደባቸው በአዋጅ ቁጥር 1161/2011 መሠረት ቅሬታቸውን ለይግባኝ ሰሚው አካል ማቅረብ ሲገባቸው ያቀረቡት ሂደቱን ያልጠበቀውን ክስ ፍርድ ቤት ተቀብሎ የማየት የሥረ ነገር ሥልጣን ያለውም፡፡ አመልካቾች ይዞታቸው ተወሰደብን የሚሉት ከ24 — 26/01/2002 ባለው ጊዜ ውስጥ ሆኖ ከ10 ዓመት በኋላ የቀረበው ክስ በይርጋ ይታገዳል፡፡ ይዞታው የራሳቸው ለመሆኑ አመልካቾች ያቀረቡት የሰነድ ማስረጃ ስለሌለ በፍትሐ ብሔር ሥነ ሥርዓት ሕጉ ቁጥር 33(2) መሠረት ክስ ለማቅረብ መብት እና ጥቅም የሌላቸው በመሆኑ ፍርድ ቤቱ ከክሱ እንዲያሰናብታቸው በመጠየቅ በፍሬ ነገር ክርክሩ ላይም ዝርዝር ምላሽ አቅርበዋል፡፡ አመልካቾች በመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያው ላይ ባቀረቡት ክርክር ቅሬታውን ተቀብሎ የሚያስተናግድ ኮሚቴ አለመኖሩን ፤ ከ10/07/2001 እስከ 2005 ዓ/ም ድረስ የከተማ ቦታዎች እንዳይሸነሸኑ የክልሉ መንግስት ዕግድ ሰጥቶ ባለበት ይዞታቸው ተሸንሽኖ ለግለሰቦች ስለተሰጠ የይርጋ ጊዜው መቆጠር ያለበት ከ2005 ዓ.ም ጀምሮ በመሆኑ ያቀረቡት ክስ በይርጋ የማይታገድ መሆኑን፤ የይዞታው ባለቤት ለመሆናቸው ግብር የከፈሉበት ደረሰኝ ስላላቸው ክስ ለማቅረብ መብትና ጥቅም አለን በማለት ተከራክረዋል፡፡

የሸካ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ቴፒ ምድብ ችሎትም ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን የማየት የሥረ ነገር ሥልጣን ያለው መሆን አለመሆኑንና ክሱ በይርጋ መታገድ አለመታገዱን በጭብጥነት ይዞ እንደመረመረው፡- ጉዳዩ በአዋጅ ቁጥር 1161/2011 ቁጥር 19 እና 20 ድንጋጌ መሠረት ለቅሬታ እና ይግባኝ ሰሚ ኮሚቴ ሳይቀርብ ፍርድ ቤት በቀጥታ ጉዳዩን ተቀብሎ የማስተናግድ የሥረ ነገር ሥልጣን የሌለው በመሆኑና አመልካቾች ለተወሰደባቸው መሬት ካሳ እና ምትክ መሬት እንዲሰጣቸው ያቀረቡት ክስ በይርጋ የሚታገድ ነው በማለት መዝገቡን በብይን የዘጋ ሲሆን ፤ ይግባኝ ሰሚው የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት አመልካቾች ያቀረቡትን የይግባኝ አቤቱታ በፍትሐ ብሔር ሥነ ሥርዓት ሕጉ ቁጥር 337 መሠረት በመሰረዙ እና የሰበር አጣሪ ችሎቱም የሥር ፍርድ ቤቶች የሰጡት ብይንና ትዕዛዝ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት አይደለም በማለት አመልካቾች ያቀረቡትን የሰበር አቤቱታ ሳይቀበል ቀርቷል፡፡

አመልካቾች በየደረጃ ያሉት ጉዳዩን የተመለከቱት ፍርድ ቤቶች የሰጡት ብይንና ትዕዛዝ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሞበታል በማለት ያቀረቡት የሰበር አቤቱታ በአጭሩ ተጠሪ ይዞታቸውን የተሸነሸነው በክልሉ መንግስት የተጣለ ዕገዳ እያለ መሆኑን፤ አዋጅ ቁጥር 1161/2011

የወጣው በ2011 ሆኖ አመልካቾች ይዞታቸውን የተነጠቁት ከዚያ በፊት በመሆኑና ቅሬታ ለመስማት የተቋቋመ አካል በሌለበት አዋጅ ቁጥር 1161/2011ን መሠረት አድርጎ የቀረበው አቤቱታ ተቀባይነት ማግኘቱ አግባብነት የለውም፡፡ ይዞታው የተወሰደው አዋጅ ቁጥር 1161/2011 ከመውጣቱ በፊት ስለሆነ ጉዳዩ በመደበኛ የፍትሐ ብሔር ሕግ የሚታይ ሆኖ ሳለ የሥር ፍርድ ቤቶች ሥልጣን የለንም ማለታቸው ተገቢ አይደለም፡፡ የይርጋ ጊዜው መቆጠር ያለበት የዕግድ ትዕዛዙ ከተነሳበት ጊዜ አንስቶ በመሆኑና በከፍተኛ እና ጠቅላይ ፍርድ ቤቶች በ2006 ዓ.ም በክርክር ላይ መቆየታቸው ይርጋውን የሚያቋርጥ ምክንያት ሆኖ እያለ ክሱ በይርጋ ቀሪ ነው መባሉ ስህተት በመሆኑ የሥር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ ተሽሮ ጉዳዩ ወደ ሥር ፍርድ ቤት ተመልሶ የፍሬ ነገር ክርክሩ ታይቶ ውሳኔ እንዲያገኝ ጠይቀዋል፡፡

የሰበር አቤቱታውን የመረመረው የሰበር ሰሚ ችሎቱ የሥር ፍርድ ቤት ጉዳዩን የማየት የሥረ ነገር ሥልጣን የለኝም ካለ በኋላ የቀረበው ክስ በይርጋ ይታገዳል በማለት የሰጠው ውሳኔ የሕግ መሠረት ያለው መሆን አለመሆኑን ለማጣራት ተጠሪ በጽሑፍ መልስ እንዲሰጥ በሰጠው ትዕዛዝ መሠረት ተጠሪ የፍርድ ቤት መጥሪያ የደረሰው ለመሆኑ ማረጋገጫ ስለቀረበ እና ቀርቦ መልስ ስላልሰጠ መልስ የመስጠት መብቱ ታልፏል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ከፍ ሲል የተመለከተው ሲሆን ችሎቱም ለሰበር አቤቱታው መሠረት የሆነው ውሳኔ መሠረታዊ ሕግ ስህተት የተፈፀመበት መሆን አለመሆኑን ለክርክሩ አግባብነት ካለው የሕግ ድንጋጌ አንፃር እንደሚከተለው መርምሮታል፡፡

ማንኛውም ሰው በፍርድ ሊቋጭ በሚችል ጉዳይ ለፍርድ ቤት ወይንም ሌላ በሕግ ለተቋቋመ የዳኝነት አካል በማቅረብ ፍትሕ የማግኘት መሠረታዊ መብት እንዳለው የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ መንግስት አንቀጽ 37 ይደነግጋል፡፡ በዋነኛነት የዳኝነት ሥልጣን የፍርድ ቤቶች መሆኑን እና ለሌሎች ተቋማትም በሕግ የዳኝነት ሥልጣን ሊሰጥ እንደሚችል ከህገ መንግስቱ አንቀጽ 37 እና 79(1) ጣምራ ንባብ መገንዘብ ይቻላል፡፡ በሕግ በግልጽ የዳኝነት ሥልጣን ለሌላ አካል እስካልተሰጠ ድረስ በፍርድ እልባት ሊያገኙ የሚችሉ ጉዳዮችን ተቀብሎ የመዳኘት ሥልጣን የፍርድ ቤት ነው፡፡

ለማንኛውም ኢትዩጵያዊ ዜጋ የግል ንብረት ባለቤት የመሆን መብት በኢ.ፌ.ዴ.ሪ ሕገ መንግስት አንቀጽ 40(1) ተከብሯል፡፡ ኢትዩጵያዊ ዜጋ በጉልበቱ ወይንም በገንዘቡ በመሬት ላይ ለሚገነባው ቋሚ ንብረት ወይንም ለሚያደርገው ቋሚ መሻሻል ሙሉ መብት ያለው መሆኑን፤ ይህ መብትም የመሸጥ፤ የመለወጥ፤ የማውረስ ፤ የመሬት ተጠቃሚነቱ ሲቋረጥ ንብረቱን የማንሳት፤ ባለቤትነቱን የማዛወር ወይንም የካሳ ክፍያ የመጠየቅ መብትንም እንደሚያካትት እና አፈፃፀሙ በሕግ እንደሚወሰን አንቀጽ 40(7) ያመለክታል፡፡ በንዑስ አንቀጽ 8 ድንጋጌ መሠረት የግል ንብረት

መብት እንደተጠበቀ ሆኖ መንግስት ለሕዝብ ጥቅም ተመጣጣኝ ካሳ በቅድሚያ በመክፈል የግል ንብረትን ሊወስድ ይችላል፡፡ ሕግ መንግስቱን መሠረት አድርጎ ለሕዝብ ጥቅም ሲባል የመሬት ይዞታ የሚለቀቅበት፣ ካሣ የሚከፈልበት እና ተነሺዎች መልሶ የሚቋቋሙበትን ሁኔታ ለመሰወን የወጣው አዋጅ ቁጥር 1161/2011 ቁጥር 11 ድንጋጌ መሠረት ለህዝብ ጥቅም ሲባል ወይንም የተሻለ ልማት ሊካሄድበት ይገባል ተብሎ ሲታመን አግባብ ባለው የመንግስት አካል ውሳኔ ሲተላለፍ በአዋጁ መሠረት ቅድሚያ ለተነሽ ባለው የንብረትና ይዞታ መብት መሠረት የንብረት እና የልማት ተነሽ ካሳ ከፍሎ መሬቱን የማስለቀቅ ሥልጣንን ለከተማ አስተዳደር ወይንም ለወረዳ አስተዳደር ይሰጣል፡፡ የሚከፈለው ካሣም በመሬቱ ላይ ለሚገኘው ንብረት እና በመሬቱ ላይ ለተደረገው ቋሚ መሻሻል እንደሆነ ከአዋጁ ቁጥር 12 ድንጋጌ መረዳት ይቻላል፡፡ በቋሚነት ለሚነሳ የከተማ መሬት ባለይዞታ ልማት ተነሽ ካሰ እና ምትክ ቦታ የሚሰጥበት አግባብ በቁጥር 13(4) ሥር ተመላክቷል፡፡ አዋጁን መሠረት አድርጎ በሚሰጥ ውሳኔ ላይ የሚቀርብ አቤቱታን እና ይግባኝ የሚመለከት አካል መቋቋም ያለበት መሆኑን ከቁጥር 18 ድንጋጌ መረዳት ይቻላል፡፡ አዋጁ አቤቱታ እና ይግባኝ የሚቀርብበትን ሥርዓት መዘርጋቱንም የቁጥር 19 እና 20 ድንጋጌ ያመለክታል፡፡

በተያዘው ጉዳይ የአመልካቾች የዳኝነት ጥያቄ ለተወሰደባቸው ይዞታ ምትክ መሬት እንዲሰጣቸው እና በይዞታቸው ላይ ላፈሩት ንብረት ካሳ እንዲከፈላቸው ሲሆን ፣ ጉዳዩ መታየት ያለበት የመሬት ይዞታቸው በተወሰደባቸው ወቅት በሥራ ላይ በነበረው ሕግ ወይስ ክሱ በቀረበበት ጊዜ ያለውን ሕግ መሠረት አድርጎ መሆኑ ፣ ለጉዳዩ አግባብነት ባለው ሕግ መሠረት የአመልካቾችን የዳኝነት ጥያቄ ተቀብሎ ሊያስተናግድ የሚችል በህግ ሥልጣን የተሰጠው አካል መኖር አለመኖሩ ፣ ጉዳዩን አይቶ ውሳኔ ሊሰጥ የሚችል በሕግ አግባብ የተቋቋመ አካል የሌለ ከሆነ ፍርድ ቤት ጉዳዩን አይቶ መወሰን መቻል አለመቻሉ እና ሌሎች ተያያዥነት ያላቸው ጭብጦች በፍትሐ ብሔር ሥነ ሥርዓት ሕጉ ቁጥር 246 ፣ 247 እና 248 ድንጋጌዎች መሠረት ሳይመረመሩ የተሰጠው ውሳኔ የአመልካቾችን ፍትሕ የማግኘት መብት የሚገድብ ነው፡፡

በሌላ በኩል የሥር ፍርድ ቤት ጉዳዩን የማየት የሥረ ነገር ሥልጣን የለኝም ካለ በፍትሐ ብሔር ሥነ ሥዓት ሕጉ ቁጥር 9(1) እና 231 (1) (ለ) መሠረት የክስ አቤቱታው ተቀባይነት የለውም በማለት መዝገቡን ዘግቶ ተከራካሪዎቹን ማሰናበት ሲገባው ተጠሪ በፍትሐ ብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 244(2) (መ) መሠረት ያቀረበውን መቃወሚያ ተቀብሎ በቁጥር 245 መሠረት መርምሮ ክሱ በይርጋ ይታገዳል ማለቱ የሥነ ሥርዓት ጉድለት ነው፡፡

ሲጠቃለል ከላይ በዝርዝር በተጠቀሰው ምክንያት ለሰበር አቤቱታው ምክንያት የሆነው ብይን እና ትዕዛዝ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት በመሆኑ ተከታዩ ተወስኗል፡፡

ውሳኔ

1. የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ሕዝቦች ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር አጣሪው ችሎት በሰበር በመዝገብ ቁጥር 10097 ታህሳስ 21 ቀን 2014 ዓ/ም በዋለው ችሎት የሰጠው ትዕዛዝ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348 (1) መሰረት ተሽሯል፡፡
2. የሸካ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ቴፒ ምድብ ችሎት በፍርድ ሀተታው ውስጥ በተመለከተው መሠረት ጉዳዩን አይቶ ተገቢ ነው ያለውን ውሳኔ እንዲሰጥ መዝገቡ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 341(1) መሠረት ተመልሶለታል፡፡
3. የዚህ ውሳኔ ግልባጭ ለሥር ፍ/ቤቶች ይድረስ፡፡
4. ግራ ቀኞቸው የሰበር ክርክሩ ያስከተለው ወጪና ኪሳራ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ውሳኔ አግኝቶ ስለተዘጋ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

መ/ዐ

የሰ.መ.ቁ.200482

ህዳር 27 ቀን 2014 ዓ.ም

ዳኞች፡.....1. ተፈሪ ገብሩ (ዶ/ር)

2. ቀነዓ ቂጣታ

3. ፈይሳ ወርቁ

4. ደጀኔ አያንሳ

5. ብርቅነሽ እሱባለዉ

አመልካች፡-.....ወ/ሮ ሐቢባ ሸምሱ ስሩር - ቀርበዋል

ተጠሪ፡-.....አቶ ቴዎድሮስ ገብሩ ብዛ - ቀርበዋል

ይህ መዝገብ ተመርምሮ የሚከተለዉ ፍርድ ተሰጥቷል።

ፍርድ

ይህ የፍቺ ክርክር የተጀመረዉ በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ሲሆን፣ የአሁን አመልካች እና የአሁን ተጠሪ ሆኖ ሲከራከሩ ነበር። ጉዳዩ ለዚህ ችሎት ሊቀርብ የቻለዉ የአሁን አመልካች የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ.251802 ጥር 26 ቀን 2012 ዓ.ም የሰጠዉ ዉሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ እንዲታረምልን በማለት በማመልከታቸዉ ነዉ።

የጉዳዩ አመጣጥ ሲታይ የአሁን አመልካች በሥር ፍ/ቤት ባቀረበችዉ ክስ ከተጠሪ ጋር ግንቦት 12 ቀን 2001 ዓ.ም በግብጽ ሀገር ጋብቻ ፈጽመን አብረን ሲንኖር ህጻን ሊና ቴዎድሮስ የተባለችዉን ልጅ የወለድን ቢሆንም ከ2008 ዓ.ም ጀምሮ ግንኙነታችን ተቋርጦ በጋብቻ መቀጠል ስላልቻልን ጋብቻችን እንዲፈርስልን በማለት ዳኝነት ጠይቃለች፡፡

የአሁን ተጠሪ በዚህ ክስ ላይ ባቀረበዉ መልስ ከአመልካች ጋር ጋብቻ አልፈጸምንም፣ በጋብቻ ሰነዱ ላይም አልፈረምኩም፣ አመልካች ጋብቻ እንደሌላቸዉ ስለመሆኑ ማስረጃ ተሰጥቷል፣ በግብጽ አገር ጋብቻ የሚፈጸመዉ በፍ/ቤት ነዉ፣ ከአመልካች ጋር በነበረን የግብረ ስጋ ግንኙነት የተጠቀሰችዉን ልጅ ከመዉለዳችን ዉጭ በጋብቻም ሆነ ጋብቻ ሳይፈጽም እንደባልና ሚስት አለመኖራቸዉን ገልጸዉ ጋብቻ በሌለበት የቀረበዉ ክስ ተቀባይነት የለዉም በማለት ተከራክሯል፡፡

ከዚህ በኋላ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ግራ ቀኙን በመስማት፣ ከሚመለከተዉ አካል በማጣራትና የቀረበዉን የሰነድ ማስረጃ በመመርመር ባሳለፈዉ ዉሳኔ በአመልካች እና በተጠሪ መካከል በግብጽ አገር ጋብቻ ስለመፈጸማቸዉ አግባብነት ባለዉ ማስረጃ ባለመረጋገጡ አመልካች የጋብቻ ፍቺ እንዲወሰን ያቀረበችዉ የዳኝነት ጥያቄ ተቀባይነት የለዉም፣ በአመልካች እና በተጠሪ መካከል የተፈጸመ ጋብቻ የለም፣ የሚሰጥ ፍቺ የለም በማለት ወስኗል፡፡ ይህ ጉዳይ በይግበኝ

የቀረበለት የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ.254606 በ20/4/2013 ዓ.ም በዋለዉ ችሎት ግራ ቀኙን በማከራከር የሥር ፍ/ቤትን ዉሳኔ በማጽናት ወስኗል፡፡ የአሁን የሰበር አቤቱታ የቀረበዉ በዚህ ዉሳኔ ቅር በመሰኘት ለማለወጥ ነዉ፡፡

የአሁን አመልካች ታህሳስ 26 ቀን 2013 ዓ.ም በተጻፈ የሰበር አቤቱታ፡ አመልካች እና ተጠሪ መንግስትን ተቃዉመን ከአገር ተሰደን ለብዙ ጊዜ እንደባልና ሚስት አብረን ሲንኖር ዕድሜዋ 10 ዓመት የሆናትን ልጅ ሊና ቴዎድሮስ የተወለደች ሲሆን በግብጽ አገር የጋብቻ ዉል ያደረግን ሲሆን እኛ በግብጽ አገር በስደት የሚንኖርና ሕጋዊ ነዋሪዎች ባልሆንበት በአገሪቱ በሕጋዊ መንገድ እንደሚኖር ዜጋ የጋብቻ ዉሉ በፍ/ቤት አልተመዘገበም በማለት የጋብቻ ዉል የለም በማለት የሰጠዉ ዉሳኔ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነዉ፡፡ አመልካች ይህን ክርክር ለማስረዳት የሰዉ ምስክሮችን ቆጥረን እያለ የሥር ፍ/ቤቶች ምስክሮቹን ሊቀበሉን አልቻሉም፣ ተጠሪ የጋራ ሀብት ነዉ በማለት በአመልካች ስም ለኮንዶሚኒየም የተቆጠበዉን ገንዘብ ማሳገዱ ጋብቻ መኖሩን እያመነ መሆኑን የሚያሳይ ሆኖ ሳለ የሥር ፍ/ቤቶች ጋብቻ የለም በማለት የሰጡት ዉሳኔ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ እንዲታረምልኝ በማለት በዝርዝር አመልክታለች፡፡

ይህ ችሎት የሰበር አቤቱታዉ ያስቀርባል በማለት ተጠሪ መልስ እንዲሰጥ ባዘዘዉ መሰረት ሚያዚያ 21 ቀን 2013 ዓ.ም በተጻፈ መልስ፡ አመልካች እና ተጠሪ በግብጽ አገር በስደተኞች ካምፕ ጋብቻ ስለመኖሩ የጋብቻ ሰነድ መፈረሙ ተረጋግጧል ይበሉ እንጂ ሰነዱ ወደ ኢትዮጵያ ሲገባ በኢፌዴሪ የዉጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ሕጋዊነቱ ተረጋግጦ የገባ ስላልሆነ ሕጋዊ ሆኖ የቀረበ ሰነድ አይደለም ተቀባይነት የለዉም፣ የሥር ፍ/ቤት ከግራ ቀኙ ክርክር አንጻር የሰዉ ምስክሮችን መስማት እንደማያስፈልግ ስላመነበት ማለፉ ትክክል ነዉ፣ አመልካች ከተጠሪ ጋር እንደባልና ሚስት አብረን ኖረናል ያሉት በሥር ፍ/ቤት ያልተነሰ ክርክር ስለሆነ ተቀባይነት የለዉም፣ ለኮንዶሚኒየም የተቆጠበዉን ገንዘብ ያሳገድኩት የጋራ ሀብት ነዉ በሚል ሳይሆን በዚህ ክርክር ምክንያት ለሚደርስብኝ ወጪና ኪሳራ የሚወሰንልኝ ከሆነ ይህን ገንዘብ ለመዉሰድ እንዲችል ነዉ፡፡ ስለሆነም የሥር ፍ/ቤት ዉሳኔ በአግባቡና ሕጋዊ ስለሆነ የቀረበዉ አቤቱታ ዉድቅ እንዲሆንልኝ ወጪና ኪሳራ እንዲወሰንልኝ በማለት በዝርዝር ተከራክሯል፡፡ አመልካች የሰበር አቤቱታዋን በማጠናከር የመልስ መልስ አቅርባለች፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ከፍ ሲል የተመለከተዉ ሲሆን ይህ ችሎት የግራ ቀኙን ክርክር አግባብነት ካላቸዉ የህግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ መርምሮታል፡፡ እንደመረመርነዉ በዚህ ጉዳይ ምላሽ የሚሻዉ ፣ይህ ጉዳይ የግለሰብ ዓለም አቀፍ ሕግን የሚመለከት ነዉ ወይስ አይደለም? ጉዳዩ የግለሰብ ዓለም አቀፍ ህግን የሚመለከት ከሆነ ክርክሩን ለማየት የሥረ-ነገር የዳኝነት ያለዉ

የትኛዉ ፍ/ቤት ነዉ? የሚሉት ነጥቦች መሆናቸዉን ተገንዝበናል፡፡ በዚህ መሰረት አመልካች ካቀረበችዉ ክርክር እና የሥር ፍ/ቤቶች በዉሳኔያቸዉ እንዳመለከቱት አመልካች ከተጠሪ ጋር ጋብቻ ፈጽመናል የሚትለዉ በግብጽ አገር በስደተኞች ካምፕ መሆኑን ጠቅሳ የተባበሩት መንግስታት የስደተኞች ከፍተኛ ኮሚሽን ጋብቻቸዉን በምስክሮች ፊት አስፈጽሟል ያለችበትን የጋብቻ የምስክር ወረቀት የሰጠ መሆኑን እና ተጠሪም ይህን ሰነድ መፈረሙን በፌዴራል ፖሊስ ኮሚሽን የፎረንሲክ ምርመራ ክፍል መረጋገጡን ነዉ፡፡ ተጠሪ ግን ከአመልካች ጋር በግብጽ አገር ጋብቻ አለመፈጸቸዉን፣ በግብጽ አገር ተጋቢዎች ጋብቻ መፈጸም ያለባቸዉ በፍ/ቤት መሆኑን፣ የተባለዉ የጋብቻ ሰነድ አግባብነት ባለዉ ሕግ መሰረት በኢትዮጵያ የዉጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ተረጋግጦ ወደ አገር ያልገባ መሆኑንና ተቀባይነት ሊኖራዉ እንደማይገባ ገልጸ መከራከሩን መዝገቡ ያሳያል፡፡ በግራ ቀኙ መካከል ከሚነሳዉ የፍሬ ነገር እና የህግ ክርክር አንጻር ጉዳዩ የግለሰብ ዓለም አቀፍ ሕግን [Private International Law] የሚመለከት ነዉ ወይስ አይደለም? የሚለዉ ነጥብ መታየት ያለበት ጉዳይ ነዉ፡፡

እንደሚታወቀዉ የግለሰብ ዓለም አቀፍ ሕግ የዉጭ አካል ተካፋይ የሆነበትን የህግ ክርክር የሚመለከቱ መርሆዎችና ደንቦችን የሚያካተት ነዉ፡፡ የግለሰብ ዓለም አቀፍ ሕግ ወይም የሕግ ግጭት [Conflict of laws] የሚመለከተዉ በተያዘዉ የህግ ክርክር የትኛዉ ሕግ ተፈጻሚነት እንዳላዉ እና የትኛዉ ፍ/ቤት ጉዳዩን ለማየት ስልጣን እንዳለዉ የሚወስኑ የህግ መርሆችን ነዉ፡፡ የፌዴራል ፍ/ቤቶች አዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀጽ 5 (1፣ ሀ) እና 11 (1፣ ሀ) መሰረት የግለሰብ ዓለም አቀፍ ሕግን በሚመለከቱ የፍትሕ ብሔር ጉዳዮችን ለማየት የመጀመሪያ ደረጃ የዳኝነት ስልጣን ያለዉ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት መሆኑን ይደነግጋል፡፡

በዚህ አግባብ አሁን የተያዘዉ ጉዳይ ሲታይ አመልካች ባቀረበችዉ ክርክር ከተጠሪ ጋር ጋብቻ ፈጽመናል ያለችዉ በግብጽ አገር በሚገኘዉ በተባበሩት መንግስታት የስደተኞች ካምፕ በከፍተኛ ኮሚሽንና በምስክሮች ፊት መሆኑን ገልጻ ተከራክራለች፡፡ ይሁን እንጂ አመልካች ከተጠሪ ጋር አድርገናል የሚትለዉ ጋብቻ እንዲፈርስላት ክስ አቅርባ ዳኝነት የጠየቀችዉ በኢትዮጵያ ፍ/ቤት መሆኑን ማየት ይቻላል፡፡ በዚህ መሰረት ከግራ ቀኙ ክርክር አንጻር በአመልካች እና በተጠሪ መካከል በግብጽ አገር በሚገኘዉ በተባበሩት መንግስታት የስደተኞች ካምፕ አመልካች ተፈጽሟል የሚትለዉ ጋብቻ በተመለከተ ሕጋዊ ጋብቻ ተፈጽሟል ለማለት የትኛዉ ሕግ ተፈጻሚነት ይኖረዋል? የሚለዉ ነጥብ ምላሽ የሚያስፈልገዉ ጉዳይ ሆኖ እናገኛለን፡፡ እንዲሁም በግራ ቀኙ መካከል በግብጽ አገር በሚገኘዉ የተባበሩት መንግስታት የስደተኞች ካምፕ ተፈጽሟል የተባለዉ ጋብቻ፣ በሕግ አግባብ የተፈጸመ ጋብቻ ነዉ የሚባል ከሆነና ጋብቻቸዉ በፍቺ ዉሳኔ እንዲፈርስ የሚወሰን እንደሆነ የፍቺ ዉጤት በምን አግባብ ይታያል? የሚለዉ ነጥብ ሊነሳ እንደሚችል ሌላዉ ጉዳይ ነዉ፡፡ ይህ ከሆነ ደግሞ የግራ ቀኙን የጋብቻ ይፍረስልን ክርክር በተመለከተ ተፈጻሚነት

ያለዉ ሕግ የትኛዉ ነዉ? የሚለዉን ነጥብ መወሰንን ይጠይቃል ማለት ነዉ፡፡ ይህ ከሆነ ደግሞ የግራ ቀኙ ክርክር የግለሰብ ዓለም አቀፍ ሕግን የሚመለከት ጥያቄ የሚያስነሳ ሆኖ እናገኛለን፡፡ ይህ ጉዳይ የግለሰብ ዓለም አቀፍ ሕግን የሚመለከት ከሆነ ደግሞ በኢትዮጵያ ዉስጥ የትኛዉ ፍ/ቤት ጉዳዩን ለማየት የሥረ-ነገር የዳኝነት ስልጣን አለዉ? የሚለዉ አግባብነት ካለዉ ሕግ አንጻር ታይቶ ምላሽ ሊሰጥበት የሚገባዉ ጉዳይ ነዉ፡፡ በዚህ መሰረት በአዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀጽ 5 (1፣ ሀ) እና 11 (1፣ ሀ) መሰረት የግለሰብ ዓለም አቀፍ ሕግን የሚመለከቱ የፍትሕ ብሔር ጉዳዮችን የማየት የመጀመሪያ ደረጃ የሥረ-ነገር የዳኝነት ስልጣን ያለዉ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት መሆኑን ይደነጋገል፡፡ ስለሆነም ፍ/ቤት አንድን ጉዳይ ለማየት የሥረ-ነገር የዳኝነት ስልጣን አለዉ ወይስ የለዉም? የሚለዉን አስመልክቶ ተከራካሪ ወገኖች ከዚህ አንጻር የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ባያነሱም ፍ/ቤት በራሱ ተነሳሽነት በማንሳት ተገቢ ነዉ ያለዉን ዉሳኔ ሊሰጥበት እንዲሚገባዉ ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.9 (1)፣ 231 (1፣ ለ)፣ 244 (3) እና 245 (2) ድንጋጌዎች ይዘትና ዓላማ መረዳት ይቻላል፡፡ በመሆኑም የሥር ፍ/ቤቶች ይህ ጉዳይ የግለሰብ ዓለም አቀፍ ሕግ ጥያቄን የሚያስነሳ መሆኑን እና ጉዳዩን ለማየት የመጀመሪያ ደረጃ የሥረ-ነገር የዳኝነት ስልጣን ያለዉ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት መሆኑን በመገንዘብ የአሁን አመልካች ያቀረበችዉን ክስ ዉድቅ በማድረግ ስልጣን ላለዉ ፍ/ቤት ጉዳዩን ማቅረብ እንደሚትችል በማመልከት መወሰን ሲገባቸዉ ይህን ባለማድረግ ያሳለፉት ዉሳኔ ከፍ ሲል ከተጠቀሱት ሕጎች አንጻር ተቀባይነት የለዉም ብለናል፡፡

ሲጠቃለል የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ይህን ጉዳይ ለማየት የሥረ-ነገር የዳኝነት ስልጣን ሳይኖረዉ ጉዳዩን አይቶ ያሳለፈዉ ዉሳኔ እና የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ይህን ዉሳኔ ማረም ሲገባዉ በማጽናት የሰጠዉ ዉሳኔ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ የሚከተለዉ ተወስኗል፡፡

<u>ዉሳኔ</u>

1. የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ.ቁ.251802 ጥር 26 ቀን 2012 ዓ.ም የሰጠዉ ዉሳኔ እና የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ.254606 በ20/4/2013 ዓ.ም የሰጠዉ ዉሳኔ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመባቸዉ ስለሆኑ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.348 (1) መሰረት ተሽሯል፡፡
2. ይህ ጉዳይ የግለሰብ ዓለም አቀፍ ሕግን የሚመለከት ስለሆነ ጉዳዩን ለማየት የመጀመሪያ ደረጃ የሥረ-ነገር የዳኝነት ስልጣን ያለዉ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት እንጂ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት አይደለም ብለናል፡፡

3. ግራ ቀኛቸዉ ይህን ጉዳይ ስልጣን ላለዉ ፍ/ቤት ከማቅረብ ይህ ዉሳኔ የሚከለክላቸዉ አይሆንም ብለናል፡፡
4. የዚህ ዉሳኔ ግልባጭ ለሥር ፍ/ቤቶች ይድረስ፡፡
5. ግራ ቀኙ በዚህ ችሎት የደረሰባቸዉን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸዉን ይቻሉ፡፡
6. ይህ ዉሳኔ ታህሳስ 1 ቀን 2014 ዓ.ም ተነቧል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡

ማ/አ **የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት**

ንግድና ኢንሹራንስ

የሰ/መ/ቁጥር 194093

ጥቅምት 29 ቀን 2014 ዓ/ም

ዳኞች፡- ብርሀኑ አመነው

ተሾመ ሽፈራው

ሀብታሙ እርቅይሁን

ብርሀኑ መንግስቱ

ነፃነት ተገኝ

አመልካች፡- 1ኛ. አቶ ሐይማኖት አበራ - ቀረቡ

2ኛ. አባይ ባንክ አክስዮን ማሕበር- ነ/ፈ ለምለም ሙለታ - ቀረቡ

ተጠሪ፡- ፀሀይ ኢንሹራንስ ኩባንያ - ጠበቃ ምንተስኖት ታዬ - ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍርድ

ክርክሩ የመድን ሽፋን ውልን መነሻ ያደረገ ሲሆን ጉዳዩ በተጀመረበት የፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት አመልካቾች እንደየቅደም ተከተላቸው 1ኛ እና 2ኛ ከሳሽ ተጠሪ ደግሞ ተከሳሽ በመሆን ተከራክረዋል፡፡

አመልካቾች ነሐሴ 21 ቀን 2010 ዓ.ም በተፃፈ ክስ ተጠሪ ንብረትነቱ የ1ኛ አመልካች የሆነ የሰሌዳ ቁጥሩ 3-91089-ኢት ሲኖ ትራክ ከባድ የጭነት ተሽከርካሪ ለሚደርስበት ጉዳት ከሐምሌ 1 ቀን 2010 ዓ.ም እስከ ሰኔ 28 ቀን 2011 ዓ.ም የሚቆይ ለብር 2,800,000 የመድን ሽፈን ሰጥቷል፡፡ ተሽከርካሪው በምእራብ ጎጃም ዞን ቡሬ ከተማ ቀበሌ 03 ውስጥ ከአሽከርካሪው የጥንቃቄ ጉድለት በደረሰበት አደጋ ሙሉ ለሙሉ የወደመ ቢሆንም ተጠሪ ካሳ ለመክፈል ፍቃደኛ አልሆነም፡፡ 1ኛ አመልካች ከ2ኛ አመልካች ጋር ሐምሌ 26 ቀን 2009 ዓ.ም በተደረገ የብድር ውል መነሻነት ለወሰደው ብር 875,000 ተሽከርካሪውን በዋስትና አስይዟል፡፡ በመሆኑም ተጠሪ 5% የአደጋ መነሻ ዋጋ ተቀናሽ አድርጎ 1ኛ አመልካች ለ2ኛ አመልካች ሊከፍል የሚገባውን ብር 784,738.47 ከጥር 26 ቀን 2010 ዓ.ም ጀምሮ ተጠናቆ እስኪከፈል በ15.5% እና 3% ቅጣት ለ2ኛ አመልካች እንዲከፍል፤ ቀሪውን ለ1ኛ አመልካች እንዲከፍል እንዲሁም ካሳው በጊዜው ባለመከፈሉ የተቋረጠ ገቢን ውሳኔ እስከሚሰጥበት ቀን ድረስ 1ኛ አመልካች የመጠየቅ መብቱ እንዲጠበቅለት እንዲሁም ወጪ እና ኪሳራ እንዲወሰንላቸው ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡

ተጠሪ ህዳር 3 ቀን 2011 ዓ.ም ፅፎ ባቀረበው መልስ አደጋው የደረሰው ተሸከርካሪው ከተፈቀደለት የመጫን አቅም በላይ አንድ ሰው በትርፍነት ጭኖ ሲጓዝ ስለሆነ በመድን ውሉ፣ በሕግ እንዲሁም በሰ/መ/ቁጥር 90793 እና 146235 በተሰጠው ገዢ ውሳኔ መሰረት ካሳ የመክፈል ኃላፊነት የለብኝም፤ ካሳ የመክፈል ኃላፊነት አለብሕ ቢባል እንኳ በመድን ውሉ መሰረት ለተቋረጠ ገቢ ኃላፊነት የለብኝም፤ ተሸከርካሪውም ሙሉ ውድመት የደረሰበት ስለሆነ አመልካቾች ተሸከርካሪውን ከእዳ እና እገዳ ነፃ ሳያደርጉ ካሳ ሊጠይቁ አይችሉም በማለት ተከራክሯል፡፡

ፍርድ ቤቱ የግራ ቀኙን ክርክር ሰምቶ 1ኛ አመልካች ተሸከርካሪው በሊብሬው ከተገለጸው በላይ አንድ ሰው በትርፍነት ጭኖ የነበረ መሆኑን ሳይክድ የመጫን አቅሙ ከፍተኛ ስለሆነ አንድ ሰው ትርፍ በመጫኑ ምክንያት አደጋው ሊደርስ አይችልም በሚል የሚከራከር ቢሆንም በውላቸው ክፍል 2 አጠቃላይ በውሉ የተገለሉ ጉዳዮች ቁጥር 2.4 ላይ በሚመለከተው ባለስልጣን በሚሰጠው የባለቤትነት ማረጋገጫ ሊብሬ ላይ ከተገለጸ ሰው በላይ ትርፍ ጭኖ ጉዳት ከደረሰ ተጠሪ ካሳ እንደማይከፍል ተገልጿል፤ ይህ ስምምነትም በፍ/ሕ/ቁጥ 1731 መሰረት በተዋዋዮቹ መካከል እንደ ሕግ የሚቆጠር በመሆኑና ግልጽ ህግን በመተላለፍ የተፈጸመ ስለሆነ ተጠሪ ካሳ ለመክፈል አይገደድም በማለት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

አመልካቾች ውሳኔውን በመቃወም ለፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ይግባኛቸውን ያቀረቡ ቢሆንም በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሰረት የስር ፍ/ቤትን ውሳኔ አፅንቶታል፡፡

አመልካቾች መጋቢት 7 ቀን 2012 ዓ.ም የተፃፈ የሰበር አቤቱታቸውን ያቀረቡት ይህን የስር ፍ/ቤቶች ውሳኔ በመቃወም ለማሳረም ነው፡፡ የአቤቱታቸው ይዘት ባጭሩ በ1ኛ አመልካች እና በተጠሪ መካከል በተደረገው የመድን ሽፋን ውል ክፍል 2 አንቀፅ 2.4 ተጠሪው ካሳ የማይከፍለው አደጋው የደረሰው ተሸከርካሪው ትርፍ በመጫኑ ምክንያት የተከሰተ እንደሆነ ብቻ ነው፡፡ ተጠሪም አደጋው የደረሰው ትርፍ በመጫኑ ምክንያት መሆኑን ጠቅሶ ያቀረበው ክርክርም ሆነ ማስረጃ የለም፤ አደጋውን የመረመረው የቡራ ከተማ አስተዳደር ፖሊስ ፅ/ቤት በቁጥር ወ/ም/2771/31/41 መጋቢት 20 ቀን 2010 ዓ.ም ለተጠሪ በፃፈው ደብዳቤም የአደጋው ምክንያት የአሽከርካሪው የጥንቃቄ ጉድለት መሆኑን አረጋግጦ እያለ የግራ ቀኙን ስምምነት በሚቃረን ሁኔታ አንድ ሰው ትርፍ በመጫኑ ብቻ ካሳ ሊከፍል አይገባም ተብሎ የተሰጠው ውሳኔ የፍ/ሕ/ቁጥር 1731 እና የን/ሕ/ቁጥር 664(1,2) ድንጋጌን ይቃረናል፡፡ በተጨማሪም የስር ፍ/ቤቶች ለጉዳዩ ተገቢነት የሌላቸውን ለሕዝብ ማመላለሻ ተሸከርካሪዎች የተሰጠ የመድን ሽፋን ውልን መሳሻ አድርጎ በተሳሳ ክርክር ላይ በሰ/መ/ቁጥር 90793 እንዲሁም 146235 የተሰጠን ውሳኔ መሰረት በማድረግ የካሳ ክፍያ ጥያቄውን ውድቅ ማድረጋቸው ተገቢ አይደለም፡፡ አደጋው የደረሰው ተሸከርካሪው ከተፈቀደለት 300 ኩንታል የመጫን አቅም በታች ጭኖ ሲጓጓዝ ሲሆን አሽከርካሪው ትርፍ በመጫን በፈጸመው ጥፋት ጉዳት እና ኪሳራ ቢከሰት መድን ሰጪው በሰጠው

የመድን ሽፈን መሰረት ካሳ ሊከፍል የሚገባ ስለመሆኑ የሚደነግገውን የን/ሕ/ቁጥር 664(1,2) በሚቃረን መልኩ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ተፈፅሞበታል የሚል ነው፡፡

አቤቱታው በሰበር አጣሪ ችሎቱ ተመርምሮ ለክርክሩ መነሻ በሆነው ተሽከርካሪ ላይ ለደረሰው አደጋ ዋና መንስኤ የአሽከርካሪው የጥንቃቄ ጉድለት መሆኑ በተገለጸበት እና ተሽከርካሪው ከተፈቀደለት ሰው በላይ ትርፍ መጫኑ ለአደጋው መንስኤ መሆኑ ባልተረጋገጠበት ተጠሪው ካሳ የመክፈል ኃላፊነት የለበትም ተብሎ የተወሰነበት አግባብ ከኢንሹራንስ ፖሊሲው ፣ አግባብነት ካላቸው ህጎች እና ከሰበር ውሳኔዎች አንፃር ለማጣራት ያስቀርባል በመባሉ ተጠሪ መልሱን እንዲያቀርብ ታዟል፡፡

ተጠሪ በበኩሉ ህዳር 9 ቀን 2013 ዓ.ም የተፃፈ መልሱን አቅርቧል፡፡ የመልሱ ይዘት ባጭሩ የመድን ውሉ አጠቃላይ የማግለያ ድንጋጌዎች ትርፍ መጫንን ጨምሮ ሌሎች ህገወጥ ተግባራት በሚፈፀሙበት ጊዜ ተግባራዊ እንዳይሆን በማሰብ የተቀረፀ ነው፡፡ በፍ/ሕ/ቁጥር 1678(ለ) መሰረትም ውል ህጋዊ ተግባራትን ለማከናወን የሚደረግ ስለሆነና በሊብሬው 1 ሰውና 153 ኩንታል እንዲጭን ከተፈቀደው በላይ ሹፌሩን ጨምሮ 3 ሰው ጭኖ እንዲሁም በትራንስፖርት ህግ የተመለከተውን የመጫን አቅም በመተላለፍ የተፈፀመ ተግባር ሲሆን ይህም በፍ/ሕ/ቁጥር 2035 መሰረት ጥፋት በመሆኑ ህግን በመተላለፍ ለደረሰ አደጋ ተጠሪ ኃላፊነት የለብኝም፡፡ በመድን ውሉ ክፍል 2 አንቀፅ 2.4 ላይም ተሽከርካሪው በሊብሬው ከተገለፀው የመጫን አቅም በላይ ጭኖ ሲሽከረከር ለሚደርስ አደጋ ተጠሪ ካሳ እንደማይከፈል ስለተገለፀ ትርፍ መጫኑ ለአደጋው መንስኤ መሆን አለመሆኑ ከግምት ውስጥ ሳይገባ ትርፍ ጭኖ ለደረሰ አደጋ ተጠሪ ካሳ ለመክፈል አይገደድም፡፡ ይህንንም በማጠናከር በሰ/መ/ቁጥር 90793 እና 146235 አስገዳጅ የሕግ ትርጉም ስለተሰጠ እና ትርፍ መጫኑ ስላልተካደ ቅሬታው ተገቢነት የለውም፡፡ ተጠሪ ካሳ የመክፍል ኃላፊነት አለበት ቢባል እንኳ ለተቋረጠ ገቢ ኃላፊነት የሌለበት መሆኑ በውሉ ማግለያ ክፍል 1(ሀ) ተገልጿል፡፡ የብድር ውሉም በአመልካቾች መካከል የተደረገ በመሆኑ በባንክ ማበደሪያ መሰረት ወለድና ቅጣት እንዲከፍል የመጠየቅ መብት የላቸውም በማለት ተከራክሯል፡፡

አመልካቾች ህዳር 23 ቀን 2013 ዓ.ም የተፃፈ የመልስ መልሳቸውን ያቀረቡ ሲሆን የሰበር አቤቱታቸውን በማጠናከር ተከራክረዋል፡፡

የክርክሩ አመጣጥ ባጭሩ ከላይ የተመለከተው ሲሆን ጉዳዩ ለሰበር ሰሚ ችሎቱ ያስቀርባል ሲባል የተያዘውን ጭብጥ በስር ፍ/ቤቶች ከተደረጉ ክርክሮች፣ በማስረጃ ከተረጋገጡ ፍሬ ነገሮች እንዲሁም ለጉዳዩ ተገቢነት ካላቸው የሕግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለው መርምረነዋል፡፡

እንደመረመርነውም አመልካቾች በዋናነት የሚከራከሩት አደጋው በአሽከርካሪው የጥንቃቄ ጉድለት የደረሰ እንጂ ትርፍ በመጫኑ ምክንያት የደረሰ አይደለም፤ በ1ኛ አመልካች እና በተጠሪ መካከል ባለው የመድን ሽፋን ውል መሰረት ተጠሪ የ1ኛ አመልካችን የካሳ ክፍያ ጥያቄ ውድቅ ሊያደርግ የሚችለው አደጋው

ተሽከርካሪው ትርፍ በመጫኑ ምክንያት የደረሰ ሲሆን ብቻ በመሆኑ የስር ፍ/ቤቶች ለጉዳዩ ተገቢነት የሌላቸውን የሰበር ሰሚ ችሎት ውሳኔዎች በመጥቀስ የአመልካቾችን የዳኝነት ጥያቄ ውድቅ ማድረጋቸው ተገቢ አይደለም በማለት ነው፡፡ ተጠሪ በበኩሉ በውሉ መሰረት ተሽከርካሪው በሊብሬው ከተገለጸው 153 ኩንታል እና 1 ሰው የመጫን አቅም ውጪ ትርፍ ጭኖ ሲሽከረከር ለደረሰበት አደጋ ካሳ የመክፍል ኃላፊነት የለብኝም፤ አደጋው የደረሰው ተሽከርካሪው ሹፌሩን ጨምሮ 3 ሰው በመጫን ሲሽከረከር በመሆኑና ይህም ህገ ወጥ ተግባር ስለሆነ ለአደጋው መንስኤ መሆን አለመሆኑን ማስረዳት አይጠበቅብኝም፡፡ በመሆኑም የስር ፍ/ቤቶች ውሳኔ ተገቢ ነው በማለት ተከራክሯል፡፡

ተጠሪ የመድን ሽፋን የሠጠው ንብረትነቱ የ1ኛ አመልካች የሆነ የሰሌዳ ቁጥሩ 3-91089-ኢት ተሽከርካሪ የመድን ሽፋን በተሰጠበት ጊዜ ውስጥ አደጋ የደረሰበት መሆኑ እና በተሽከርካሪው ሊብሬ ላይ የመጫን አቅሙን በሚመለከት 153 ኩንታልና አንድ ሰው ተብሎ የተገለፀ መሆኑ አላከራከረም፡፡ ከክርክሩ መረዳት እንደቻለነው ተጠሪ ተሽከርካሪው በሊብሬው ከተገለፀው የመጫን አቅም በላይ አንድ ሰው በትርፍነት ጭኖ ሲጓዝ አደጋው የደረሰ ስለሆነ ካሳ ልከፍል አይገባም በማለት የሚከራከር በመሆኑ የውሉ ድንጋጌ እና ውጤቱን መመልከቱ አስፈላጊ ነው፡፡ የመድን ውሉ ክፍል 2 ጠቅላላ ማግለያዎች 2.4 ስር “Loss, damage or liability caused by overloading or strain or if the number of persons exceed the seating capacity of the vehicle described in the schedule as specified in the ownership booklet issued by the licensing authority.” ከዚህ የውል ድንጋጌ መገንዘብ የሚቻለው የተሽከርካሪው ትርፍ መጫን የደረቅ ጭነትን እንዲሁም በጋቢናው የተጫነን የተሳፋሪ መጠን በሚመለከት 2 የተለያዩ ውጤቶች ያለው መሆኑን ነው፡፡ የመጀመሪያው የደረቅ ጭነትን አስመልክቶ አደጋው በሚደርስበት ጊዜ ተሽከርካራው በሊብሬው ከተገለፀው በላይ ትርፍ መጫኑ እንዲሁም አደጋው ትርፍ በመጫኑ ምክንያት የደረሰ መሆኑ ያለው የምክንያትና የውጤት ግንኙነትን ማረጋገጥ የካሳ ክፍያ ጥያቄውን ውድቅ ለማድረግ በቅድመ ሁኔታነት መታየት ያለበት መሆኑ ነው፡፡ 2ኛው የተሽከርካሪው ሰው የመጫን አቅምን የሚመለከት ሲሆን ተሽከርካሪው በሊብሬው ከተገለፀው ቁጥር በላይ ጭኖ ሲሽከረከር አደጋው የደረሰ መሆኑ ከተረጋገጠ በአደጋው እና በትርፍ መጫኑ መካከል ያለውን የምክንያት እና የውጤት ግንኙነት ማረጋገጥ ሳያስፈልግ የካሳ ክፍያው ውድቅ የሚደረግበት አግባብ ነው፡፡

ውሎች በተዋዋዮች መካከል ሊኖር የሚገባውን የቅንነት እና የመተማመን ግንኙነት እንዲሁም በጉዳዩ ውስጥ ያለውን ልማዳዊ አሰራር መሰረት በማድረግ በቅን ልቦና ሊተረጎሙ የሚገባ ስለመሆኑ በፍ/ሕ/ቁጥ 1732 ላይ ተመላክቷል፡፡ በመሆኑም በተያዘው ጉዳይ የስር ፍርድ ቤቶች ተሽከርካሪው በሊብሬው ከተገለፀው በላይ አንድ ሰው በትርፍነት ጭኗል በሚል የአመልካቾችን የካሳ ክፍያ የዳኝት ጥያቄ ውድቅ ማድረጋቸው የውሉን ይዘት በዘርፉ ያለውን ልማዳዊ አሰራር ከግምት ውስጥ ያስገባ መሆን አለመሆኑ ሊመረመር የሚገባው ነው፡፡ በሀገራችን ለጭነት ተሽከርካሪዎች የሚሰጠው

የባለቤትነት ማረጋገጫ ደብተር (ሊብሬ) ላይ በገቢና እንዲጭኑ የተፈቀደላቸውን የሰው ብዛት በሚመለከት አሽከርካሪውን የሚጨምር እንዳልሆነ ይታወቃል፡፡ ተጠሪም አሽከርካሪውን ይጨምራል በማለት የሚያቀርበው መከራከሪያ የለም፡፡ በዘርፉ በዳበረው አሰራርም የጭነት ተሽከርካሪዎች በአብዛኛው ያለረዳት ሹፌር የማይንቀሳቀሱ መሆኑ ይታወቃል፡፡ በሊብሬውም አንድ ሰው ተብሎ የተገለፀው በዘርፉ ከዳበረው ልማድ ጋር ተገናዝቦ ሲተረጎም ሹፌሩን እና ረዳት ሹፌሩን የማይጨምር መሆኑን ያስገነዝባል፡፡ በመሆኑም የስር ፍ/ቤቶች በዘርፉ ያለውን ልማዳዊ አሰራር በፍ/ሕ/ቁጥር 1732 መሰረት ከግምት ውስጥ ሳያስገቡ ለጉዳዩ ተገቢነት የሌለውን የሕዝብ ጭነት ተሽከርካሪን በሚመለከት የተሰጡ የሰበር ሰሚ ችሎት ውሳኔዎችን በመጥቀስ ተጠሪ ለአመልካቾች የካሳ ክፍያ ጥያቄ ኃላፊነተ የለበትም በማለት የደረሱበት ድምዳሜ ተገቢነት የለውም፡፡

በመሆኑም ከላይ በተጠቀሰው ምክንያት ተጠሪ በ1ኛ አመልካች ተሽከርካሪ ላይ ለደረሰው ጉዳት ካሳ የመክፈል ኃላፊነት ያለበት በመሆኑ የካሳ መጠንን በተመለከተ እንዲሁም 2ኛ አመልካች የጠየቀውን ዳኝነት በተመለከተ የሚከተለው ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

ውሳኔ

1. ፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 220462 በቀን 20/05/2011 ዓ.ም እንዲሁም የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በይ/መ/ቁጥር 173213 የካቲት 2 ቀን 2012 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሠጡት ውሳኔ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሰረት ተሽሯል፡፡
2. የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የተዘጋውን መዝገብ ቁጥር 220462 አንቀሳቅሶ ተጠሪ ለአንደኛ አመልካች ተሽከርካሪ ሊከፍል የሚገባው የካሳ መጠን ምን ያክል ነው? 2ኛ አመልካች በጠየቀው ዳኝነት መሰረት ለ1ኛ አመልካች ከሚከፈለው የካሳ ገንዘብ ላይ ምን ያክል የብድር ገንዘብ ሊከፈለው ይገባል፡፡ 2ኛ አመልካች ከካሳው ገንዘብ ላይ የብድር ገንዘቡ ከተከፈለው በኋላ ለ1ኛ አመልካች የሚከፈል ተራፊ ገንዘብ አለ የለም? የሚሉትን ነጥቦች በግራ ቀኙ ማስረጃ እንዲሁም አስፈላጊ ከሆነ ተጨማሪ ማስረጃ በማስቀረብ ተገቢውን እንዲወስን በፍ/ስ/ስ/ህ/ቁጥር 143/1 መሰረት ጉዳዩ ተመልሶለታል፡፡
3. በዚህ ችሎት የተደረገው ክርክር ያስከተለውን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የራሳቸውን ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

አ/ኃ

የሰ/መ/ቁጥር 202174

ጥቅምት 29 ቀን 2014 ዓ/ም

ዳኞች፡- ብርሀኑ አመነው

ተሾመ ሽፈራው

ሀብታሙ እርቅይሁን

ብርሀኑ መንግስቱ

ነፃነት ተገኝ

አመልካች፡- ብርሀን ኢንሹራንስ ኩባንያ አክሲዮን ማህበር - ነገረ ፈጅ ዳንኤል ደፋር - ቀረቡ

ተጠሪ፡- አቶ ዝናቡ ጌታነህ - ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍርድ

ክርክሩ የመድን ውልን መሰረት ያደረገ ሲሆን ጉዳዩ በመጀመሪያ በታየበት የግልግል ጉባኤ ተጠሪ ከሳሽ አመልካች ተከሳሽ በመሆን ተከራክረዋል፡፡

ተጠሪ ነሐሴ 29 ቀን 2011 ዓ.ም ባቀረበው ክስ የሰሌዳ ቁጥሩ 03-78476-ኢት ዋና መኪና እና የሰሌዳ ቁጥሩ 3-23823-ኢት ተሳቢ ንብረትነቱ የተጠሪ የሆነ ተሽከርካሪ ለሚደርስበትም ሆነ ለሚያደርሰው ጉዳት አመልካች ከነሐሴ 21 ቀን 2010 ዓ.ም - ነሐሴ 14 ቀን 2011 ዓ.ም የሚቆይ የመድን ሽፋን ሰጥቷል፡፡ ተሽከርካሪዎቹ በአዊ አስተዳደር ዞን ባንጃ ወረዳ ልዩ ስሙ ጎመርታ በሚባል ቦታ ተገልብጠው ከፍተኛ ጉዳት የደረሰባቸው ሲሆን አመልካች ጉዳቱ የደረሰው ተሽከርካሪዎቹ ከአቅም በላይ በመጫናቸው ነው በሚል የካሳ ክፍያ ጥያቄውን ውድቅ አድርጓል፡፡ ተሽከርካሪዎቹ 420 ኩንታል የጫኑት የትራንስፖርት ባለስልጣን ባቀረበው ሀገራዊ ግዳጅ ሲሆን ከአቅም በላይ አልጫኑም፡፡ በመሆኑም አመልካች ተሽከርካሪዎቹን ጠግኖ እንዲያስረክበኝ ወይም የዋናውን መኪና ግምት ብር 3,400,000 እና የተሳቢውን ብር 1,100,000 በድምሩ ብር 4,500,000 ከወጪና ኪሳራ ጭምር እንዲከፍል ይወሰንልኝ በማለት ዳኝነት ጠይቋል፡፡

አመልካች መስከረም 9 ቀን 2012 ዓ.ም ባቀረበው መልስ ሽፋን የተሰጠው ዋና ተሽከርካሪ የመጫን አቅም 155 እንዲሁም ተሳቢው 255 ኩንታል በድምሩ 380 ኩንታል ሲሆን አደጋው የደረሰው ተሽከርካሪዎቹ 40 ኩንታል ትርፍ ጭነው ሲጓዙ ስለሆነ በንግድ ህጉ ቁጥር 663(1)፣ 665(1) እና በመድን ውሉ ቁጥር መ(መ) መሰረት ኃላፊነት የለብኝም፡፡ የተሽከርካሪው የመጫን አቅም ተሽከርካሪውን በሰራው ኢንጂነር ወይም አምራች ድርጅት የሚወሰን በመሆኑ የማዳበሪያ እጥረት በማጋጠሙ ወይም

ባለስልጣን በሚፅፈው ደብዳቤ አይሻሻልም፡፡ በተጨማሪም በንግድ ህጉ ቁጥር 675(1)፣ 678፣ በፍ/ሕ/ቁጥር 2090 እና 2091 መሰረት ተጠሪ የጉዳቱን መጠን ገምቶ ባላቀረበበት ሁኔታ የካሳውን ጣሪያ ሊጠይቅ አይችልም፤ የጉዳት መነሻም 7.5% ተቀናሽ ሊደረግ ይገባል፤ ለተቋረጠ ጥቅም ኃላፊነት የለብኝም በማለት ተከራክሯል፡፡

የግልግል ጉባኤውም የግራ ቀኙን ክርክር እና ማስረጃ ሰምቶ ግራ ቀኙ የድርጅቱ አምራች የሆነው አምቼ በወሰነው የመጫን አቅም እንጂ በተሸከርካሪው ሊብሬ በተገለጸው የመጫን አቅም ላይ አልተካካዱም፡፡ የትራንስፖርት ባለስልጣኑ በውስጥ የተፃፃፈባቸውን ሰነዶች ጨምሮ አምራቹ ድርጅት የላካቸውን ሰነዶች በፖስታ አሸጎ ልኳል፡፡ ከአምቼ የቀረበው ማስረጃ ዋናው ተሸከርካሪ ሲመረት 245 ኩንታል እንዲሁም ተሳቢው 280 ኩንታል ለመጫን እንዲችል ተደርጎ መሰራቱን የሚገልፅ ሲሆን የፌደራል ትራንስፖርት ባለስልጣንም በቁጥር ኮ/70/1/ማጉባ/717/001/06/11 የካቲት 11 ቀን 2011 ዓ.ም በፃፈው ደብዳቤ ማዳበሪያ የሚያጓጉዙ ተሸከርካሪዎች የመጫን አቅማቸውን አሟጦ መጠቀም እንዲቻል ተጨማሪ 50 ኩንታል እንዲጭኑ መደረጉን ገልጿል፡፡ ይህም የተሸከርካሪው የመጫን አቅም በሊብሬው ላይ ከተገለፀው በላይ መሆኑን የሚያመላክት በመሆኑ ተሸከርካሪው ከመጫን አቅሙ በላይ ጭኗል ለማለት አይቻልም፡፡ በመድን ውሉ ክፍል 2 መ ላይም ስልጣን ባለው ፈቃድ ሰጪ አካል በመኪናው ባለቤትነት ደብተር ላይ እንደተጠቀሰው በውሉ ሰንጠረዥ የተገለፀውን የመጫን አቅም አልፎ መጫን በሚል የተገለፀው የሰው ቁጥርን እንጂ ትርፍ ጭነትን የሚመለከት አይደለም፡፡ በመድን ውሉ ላይ የተገለፀው ከመጠን በላይ መጫን (Over Loading) በሊብሬው ላይ የተገለፀውን የሚመለከት ቢሆን በሊብሬው ላይ ከተገለፀው በላይ ሰው መጫን ካሳ እንደማያስከፍል በተገለፀው አግባብ ይገለፅ ነበር፡፡ የውሉ ድንጋጌ ትርፍ መጫንን በሚመለከት በሊብሬው የተገለፀውን ወይም በአምራቹ የተወሰነውን የመጫን አቅም የሚያመላክት መሆኑ አሻሚ ነው፡፡ በተጨማሪም ተሸከርካሪው ከሊብሬው በላይ 40 ኩንታል መጫኑ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ አደጋውን ያደረሰ ስለመሆኑ የቀረበ ማስረጃ የለም፡፡ ስለሆነም አመልካች በተሸከርካሪው ላይ ለደረሰው ጉዳት ካሳ የመክፈል ኃላፊነት ስላለበት ተሸከርካሪቹን ጠግኖ ያስረክብ ወይም በውሉ የተገለፀውን ብር 4,500,000 ይክፈል፡፡ ግራ ቀኙ ጉዳያቸው በግልግል ጉባኤው እንዲታይ ሲስማሙ ክርክሩ የሚወስደውን ጊዜ በመቀበል ስለሆነ ተጠሪ የተቋረጠ ገቢ በወር ብር 100,000 ታስቦ እንዲከፈለው ያቀረበው ጥያቄ ተቀባይነት የለውም፡፡ የአደጋ መነሻ በውሉ መሰረት ከካሳው ላይ 7.5% ተቀናሽ ይደረግ በማለት በአብላጫ ድምፅ ወስኗል፡፡

አመልካች ውሳኔውን በመቃወም ይግባኙን ለፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አቅርቦ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 337 መሰረት በመሰረዙ የካቲት 2 ቀን 2013 ዓ.ም የተፃፈ የሰበር አቤቱታውን አቅርቧል፡፡

የአቤቱታው ይዘት ባጭሩ በግራ ቀኞችን መካከል በተደረገው የመድን ውል ጠቅላላ ማግለያዎች ፊደል መ ላይ ትርፍ መጫን የካሳ ክፍያ የማያስከፍል መሆኑን እና ይህም በሊብሬ ከተገለፀው የመጫን አቅም ጋር የሚገናዘብ መሆኑ ተገልጿል። የግልግል ጉባኤው አብላጫ ድምፅ ከተዋዋዮች ግልፅ ስምምነት ውጪ እንዲሁም የማግለያ ድንጋጌውን አተረጓጎም በተመለከተ በብሔራዊ ባንክ የኢንሹራንስ ሱፐርቪዥን ዳይሬክቶሬትን አስተያየት ወደ ጎን በመተው የሠጡት ውሳኔ የፍ/ሕ/ቁጥር 1733፣ 1735፣ 1737 ድንጋጌዎችን እንዲሁም ሰበር ሰሚ ችሎቱ በቅፅ 4 በመ/ቁጥር 15662 እና 14493 የሰጠውን አስገዳጅ የሕግ ትርጉም የሚቃረን ነው። የማግለያ ውሉ ሊብሬን አያጣቅስም፤ ከብሔራዊ ባንክ የመጣው ማብራሪያም ተገቢነት የለውም ቢባል እንኳ የተሽከርካሪ መለያ፣ መመርመሪያ እና መመዝገቢያ አዋጅ ቁጥር 681/2002 አንቀፅ 4 እና 7(1)(መ) መሰረት ማንኛውም የተሽከርካሪ ባለንብረት የባለቤትነት ማረጋገጫ ደብተር(ሊብሬ) ሊኖረው እንደሚገባ እና ሊብሬው ከሚይዛቸው ጉዳዮች መካከል አንዱ የመጫን አቅምን በመሆኑ የውሉን ክፍተት ከዚህ የሕግ ድንጋጌ ጋር በማገናዘብ ሊሞላ ሲገባ ከዚህ በተቃራኒ የተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ስለሆነ ሊታረም ይገባል የሚል ነው።

ጉዳዩ በሰበር አጣሪ ችሎቱ ተመርምሮ መኪናው በሊብሬው ላይ ከተመለከተው የመጫን አቅም በላይ መጫኑ ከመረጋገጡ አንፃር የሰበር አመልካች ለጉዳዩ ኃላፊነት አለብህ ተብሎ የተሰጠው ውሳኔ ውሉን መሰረት ያደረገ መሆን አለመሆኑን ለማጣራት ያስቀርባል በመባሉ ተጠሪ መልሳቸውን እንዲያቀርቡ ታዟል።

ተጠሪም መጋቢት 27 ቀን 2013 ዓ.ም የተፃፈ መልስ አቅርበዋል። የመልሱ ይዘት ባጭሩ በግልግል ጉባኤው በግራ ቀኙ መካከል የነበረው ክርክር ተሽከርካሪው ከአቅም በላይ ጭኖ ነበር ወይ? የሚለው ነበር፤ አመልካችም ትክክለኛውን የመጫን አቅም የሚወስነው አምራቹ ነው በሚል ተከራክሯል። የግልግል ጉባኤውም ከአምራቹ ኩባንያና ከፈቃድ ሰጪው ትራንስፖርት ባለስልጣን ማስረጃ ሰብስቦ አደጋ በደረሰበት ጊዜ ተሽከርካሪው ከጫነው ጭነት በላይ መጫን እንደሚችል አረጋግጦ የሠጠው ውሳኔ ተገቢ ነው። በመድን ውሉ ክፍል 2 መ ድንጋጌ መሰረት በጭነት መጠን ምክንያት የኢንሹራንስ ሽፋንን ማግለል የሚቻለው ተሽከርካሪው ከአቅም በላይ ወይም ተወጥሮ የተጫነ መሆኑ ሲረጋገጥ ነው። በዚህ ድንጋጌ ሊብሬ የተጠቀሰው ተሽከርካሪው መጫን ካለበት የሰው መጠን አንፃር ብቻ ነው። የተሽከርካሪዎችን የመጫን አቅም መወሰን ስልጣን ያለው የትራንስፖርት ባለስልጣን ሚያዝያ 24 ቀን 2011 ዓ.ም ለአመልካች በፃፈው ደብዳቤ በሊብሬ ከተገለፀው በላይ 50 ኩንታል ጨምሮ እንዲጭን የተፈቀደለት እና ይህም የትራንስፖርት አቅምን አሟጦ ለመጠቀም እንዲቻል መሆኑን ስለገለፀ የትራንስፖርት ህጉን በመጥቀስ አመልካች የሚያነሳው መከራከሪያ ተገቢነት የለውም። የብሔራዊ ባንክም የካሳ ክፍያ መከልከሉ ከቅን ልቦና ውጪ የተፈፀመ መሆኑን የገለፀ በመሆኑ አመልካች አንድን ሀረግ ብቻ መዞ ያቀረበው መከራከሪያ ተገቢነት የለውም በማለት ተከራክረዋል።

አመልካች በበኩሉ ሰኔ 9 ቀን 2013 ዓ.ም የተፃፈ የመልስ መልሱን ያቀረበ ሲሆን የሰበር አቤቱታውን በማጠናከር ተከራክሯል፡፡

የክርክሩ አመጣጥ ባጭሩ ከላይ የተመለከተው ሲሆን ጉዳዩ ለሰበር ሰሚ ችሎቱ ያስቀርባል ሲባል የተያዘውን ጭብጥ በስር ከተደረጉ ክርክሮች፣ በማስረጃ ከተረጋገጡ ፍሬ ነገሮች እንዲሁም ለጉዳዩ ተገቢነት ካላቸው የሕግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለው መርምረነዋል፡፡

እንደመረመርነውም አመልካች ንብረትነታቸው የተጠሪ ለሆነ የሰሌዳ ቁጥሩ 03-78476-ኢት ዋና መኪና እና የሰሌዳ ቁጥሩ 3-23823-ኢት ተሳቢ ተሽከርካሪ ለሚደርስባቸው አደጋም ሆነ በሌላ 3ኛ ወገን ንብረት ላይ ለሚያደርሱት ጉዳት ከነሐሴ 21 ቀን 2010 ዓ.ም - ነሐሴ 14 ቀን 2011 ዓ.ም የሚቆይ የመድን ሽፋን መስጠቱ፤ በዚህም ጊዜ ውስጥ ዋናው እና ተሳቢ ተሽከርካሪው በድምሩ 420 ኩንታል ማዳበሪያ ጭነው ሲጓዝ በደረሰባቸው አደጋ ከፍተኛ ጉዳት ማጋጠሙን፣ ተሽከርካሪው ትርፍ ጭኖ ሲጓጓዝ ለሚደርስበት አደጋ አመልካች ካሳ ለመክፍል የማይገደድ መሆኑ እንዲሁም በሊብሬው ላይ የተገለፀው የተሽከርካሪዎቹ የመጫን አቅም በድምሩ 380 ኩንታል መሆኑ ግራ ቀኙን አላከራከረም፡፡

ግራ ቀኙን የሚያራክረው የተሽከርካሪው ትርፍ መጫን የሚወሰንበት አግባብ ነው፡፡ አመልካች የተሽከርካሪው ትርፍ መጫን በሊብሬው የሚወሰን መሆኑን ገልጾ የሚከራከር ሲሆን በአንፃሩ ተጠሪ የመጫን አቅም በሊብሬ የሚወሰን መሆኑ በውሉ የተገለፀው የሰው የመጫን አቅምን በሚመለከት ስለሆነ በተያዘው ጉዳይ ትርፍ ጭኗል ወይስ አልጫነም የሚለውን ለመወሰን ከግምት ውስጥ መግባት ያለበት የተሽከርካሪው አምራች የወሰነው የመጫን አቅም መሆን አለበት በማለት ነው፡፡ በመሆኑም የውሉን ይዘት መመልከቱ ተገቢ ነው፡፡ የመድን ውሉ ክፍል 2 መ ላይ “The company shall not be liable to make payment in respect of; loss, damage or liability happen while the vehicle is overloaded or strained or if the number of persons exceeding the seating capacity of the vehicle described in the schedule as specified in the ownership booklet issued by the licensing authority”. በሚል ተገልጿል፡፡ ድንጋጌው መድን ሰጪው ካሳ ለመክፈል የማይገደድበትን ሁኔታዎች በሚመለከት ተሽከርካሪው ትርፍ ጭኖ ወይም በመወጠር ወይም ከተፈቀደለት ሰው በላይ ጭኖ ሲያሽከረክር አደጋው የደረሰ እንደሆነ መሆኑን ያመላክታል፡፡ የውሉ ድንጋጌ እነኚህን ካሳ የማያስከፍሉ አማራጮች “ወይም” በሚል ሐረግ በማገናኘት አንዱን ከአንዱ አስከትሎ የሚስቀምጣቸው በመሆኑ ትርፍ መጫን ወይም አለመጫን በውሉ ሰንጠረዥ ላይ በተገለፀው ስልጣን ባለው አካል በተሰጠ የባለቤትነት ማረጋገጫ ወይም ሊብሬ ይወሰናል የሚለው አገላለፅ ይህን ሐረግ ቀድመው በአማራጭ ለተጠቀሱት የጭነት መጠንን ወይም የሰው ቁጥርን የሚመለከቱ ናቸው፡፡በተዋዋዮች መካከል ያለው የውል ቃል ግልጽ በሆነበት ጊዜ ፍርድ ቤቶች ውሉን በመተርጎም ከተዋዋዮቹ ሀሳብ መራቅ የሌለባቸው መሆኑ በፍ/ሕ/ቁጥር 1733 ላይ ተመላክቷል፡፡ በመሆኑም ይህ

የውል ድንጋጌ በፍ/ሕ/ቁጥር 1731 መሰረት በተዋዋዮች መካከል ሕግ ሁኖ የሚያገለግል፤ የድንጋጌው ይዘትም ግልፅ ሁኖ እያለ ከውሉ ይዘት ውጪ በመውጣት የግልግል ጉባኤው አምራቹ የወሰነውን የጭነት መጠን መሰረት አድርጎ የሰጠው ትርጓሜ የፍ/ሕ/ቁ 1733 ድንጋጌን፣ የንግድ ሕግ ቁጥር 663 እንዲሁም በሀገራችን የተሽከርካሪ የጭነት መጠን የአየር ፀባይን፣ የመንገዶችን የጥራት ደረጃና የመልከዓ ምድር አቀማመጥን መሰረት አድርጎ በሊብሬ ወይም በባለቤትነት ማረጋገጫ የሚወሰንበትን ነባራዊ ሁኔታ ያላገናዘበ ነው፡፡

በተጨማሪም የግልግል ጉባኤው በአንድ በኩል በውሉ ላይ ትርፍ መጫን በሊብሬው በተገለፀው አግባብ እንዲወሰን የተገለፀው ከተሽከርካሪው የሰው ቁጥር የመጫን አቅም ጋር የሚገናኝ እንጂ ጭነትን የሚመለከት አይደለም በማለት ያሰፈረ ሲሆን በሌላ በኩል ውሉ በዚህ ረገድ የትኛውን ለማመላከት እንደሆነ ግልጽ አይደለም፤ አሻሚ ነው በሚል የደረሰበት መደምደሚያ እርስ በእርሱ የሚቃረንና የውል ስምምነቱን ያላገናዘበ ነው፡፡ የተሽከርካሪው ትርፍ መጫንም ለአደጋው መንስኤ ሁኗል ወይስ አልሆነም የሚለው በማስረጃ ሊረጋገጥ የሚገባው በውላቸው ላይ በግልጽ አደጋው ትርፍ በመጫኑ ምክንያት የደረሰ እንደሆነ (loss caused by overloading) ካሳ የማያስከፍል መሆኑ የምክንያት እና የውጤት ግንኙነትን በሚያመላክት ሁኔታ በውሉ በግልፅ የተቀመጠ ሲሆን ነው፡፡ ከዚህ በተቃራኒ ተሽከርካሪው በሊብሬው ከተገለፀው በላይ 40 ኩንታል ትርፍ ጭኖ እንደነበር ተረጋግጦ እያለ የግልግል ጉባኤው አደጋው ትርፍ በመጫኑ ምክንያት የደረሰ ስለመሆኑ አልተረጋገጠም በሚል በፍርዱ ማስፈሩ የውሉን ይዘት ያላገናዘበ ነው፡፡ ይግባኝ ሰሚው የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤትም የግልግል ጉባኤው የፈፀመውን ስህተት አለማረሙ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት በመሆኑ ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

ውሳኔ

1. በአመልካች እና ተጠሪ መካከል የተነሳውን ክርክር ለመዳኘት የተቋቋመው የግልግል ጉባኤ ጥር 16 ቀን 2012 ዓ.ም በአብላጫ ድምፅ የሰጠው ውሳኔ እንዲሁም የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በፍ/ይ/መ/ቁጥር 191117 ህዳር 4 ቀን 2013 ዓ.ም በዋለው ችሎት የግልግል ጉባኤውን ውሳኔ በማጽናት የሠጠው ትዕዛዝ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሰረት ተሽሯል፡፡
2. ንብረትነቱ የተጠሪ የሆነው የሰሌዳ ቁጥሩ 03-78476-ኢት ዋና መኪና እና የሰሌዳ ቁጥሩ 3-23823-ኢት ተሳቢ ተሽከርካሪ በሊብሬው ከተጠቀሰው 380 ኩንታል የመመጫን አቅም በላይ 40 ኩንታል በትርፍነት ጭኖ ሲጓዝ አደጋው የደረሰ በመሆኑ እና በሊብሬው ከተገለፀው የመጫን አቅም በላይ ጭኖ ሲጓጓዝ ለሚደርስበት አደጋ መድን ሰጪው ኃላፊነት የሌለበት መሆኑ በመድን ውሉ የማግለያ ድንጋጌ ክፍል 2 መ ላይ የተገለጸ በመሆኑ ለተጠሪ ካሳ ሊከፍል አይገባም በማለት ወስነናል፡፡

3. በዚህ ችሎት የተደረገው ክርክር ያስከተለውን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የራሳቸውን ይቻሉ።

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ።

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

የሰ.መ.ቁ 208270

ጥቅምት 26 **ቀን** 2014 **ዓ.ም**

ዳኞች፡- **እትመት አሠፋ**

ፀሐይ መንክር

ኑረዲን ከድር

መላኩ ካሣዬ

እስቲበል አንዱዓለም

አመልካች፡- ተካልኝ ጫላ ገቢሳ - አልቀረቡም

ተጠሪዎች፡- 1. ኦሮሚያ ኢንተርናሽናል ባንክ አ.ማ - ነ/ፈጅ - ዮናስ አይናለም - ቀረቡ

2. ቶሊና ያደሳ ርቂቱ - ጠ አገናኝ ውዴ - ቀረቡ

መዝገቡ ለምርመራ የተቀጠረ ነው። በመሆኑም መርምረን ተከታዩን ፍርድ ሰጥተናል።

ፍርድ

የሰበር አቤቱታው ሊቀርብ የቻለው አመልካች በቀን 2012 **ዓ.ም ጽፈው ባቀረቡት የሰበር አቤቱታ በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ.ቁ.** 285529 **በጥር** 03 **ቀን** 2013 **ዓ.ም የሰጠውን ውሳኔ በማጽናት፤ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ.ቁ.** 261287 **በግንቦት** 19 **ቀን** 2013 **ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስሕተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል በማለት አቤቱታ በማቅረቡ ነው።**

ጉዳዩ የሀብት ይወገድ ክስ ክርክርን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ነው። በሥር ፍ/ቤት በተደረገው ክርክር የአሁን አመልካች ከሳሽ፤ የአሁን ተጠሪዎች ደግሞ ተከሳሾች በመሆን ተከራክረዋል። የአሁን አመልካች በሥር ፍ/ቤት ያቀረቡት ክስ ይዘት በአጭሩ፡- በአዲስ አበባ ከተማ ኮልፌ ቀራኒዮ ክፍለ ከተማ ወረዳ 8 **የቤት ቁጥር** 660 **የግል ቤት ሲሆን በካርታ ቁጥር መ**8/ወ1101/400/10919/01 **በሴሪ ቁጥር** 050929 **ግንቦት** 18 **ቀን** 2006 **ዓ.ም ስፋት** 605 **ካ.ሜ የሆነውን ከ**1**ኛ ተጠሪ ጋር የብድር ውል አማካኝነት ገንዘብ ተበድሬ ካርታውን ያስያዝኩ**

ሲሆን አመልካች ከ1ኛ ተጠሪ ጋር በነበረን የብድር ውል አማካኝነት በኪሳራ ምክንያት ገንዘቡን በወቅቱ ባለመክፈሌ 1ኛ ተጠሪ በቤቱ ላይ ጨረታ እንደሚያወጣ አሳውቆኛል፤ 1ኛ ተጠሪ ከሚመራበት የጨረታ መመሪያ ውጪ የመጀመሪያ ዙር እና ሁለተኛ ዙር ጨረታ ማስታወቂያ ሳያወጣ የ3ኛ ዙር በማውጣት እና ከ2ኛ ተጠሪ ጋር በመመሳጠር ቤቱ ሊያወጣ የሚገባውን ዋጋ እንዳያገኝ እና ተጫራቾች በስፋት መጥተው እንዳይጫረቱ በማድረግ መብቱ እና ጥቅሜን የሚጎዳ ተግባር ፈጽሟል፤ 1ኛ ተጠሪ በሪፖርተር ጋዜጣ መጋቢት 9 ቀን 2012 ዓ.ም ለ2ኛ ግዜ የወጣ የጨረታ ማስታወቂያ በማለት የተጭበረበረ ጨረታ በማውጣት እና አመልካችን በማስለቀቅ ቤቱን ለ2ኛ ተጠሪ ለማስተላለፍ ጥረት ማድረጉን ስለደረስኩበት ይህንንም ጉዳይ ለ1ኛ ተጠሪም ሆነ የበላይ ኃላፊ ለሆነው የኦሮሚያ ኢንተርናሽናል ባንክ ለዋናው መስሪያ ቤት አሳውቄ ጉዳዩ እንዲስተካከልልኝ በመጠየቅ ላይ እያለሁ 2ኛ ጊዜ የወጣ ጨረታ ብሎ ቤቱን ለ2ኛ ተጠሪ እና ዘመዱ ለሆነ ሰውን በድምሩ ሁለት ሰዎችን ብቻ በማጫረት ሊጫረቱ የመጡትን አቶ ቶላ ገዳ የተባሉትን ግለሰብ እንዳይጫረቱ በማድረግ ቤቱ ሊያወጣ የሚችለውን ዋጋ ያሳጡኝ መሆኑን ለ1ኛ ተጠሪም ሆነ ለበላይ ኃላፊው አሳውቄ መፍትሄ እንደሚሰጠኝ በተነገረኝ መሰረት እየተከታተልኩ እገኛለሁ፤ ከሳሽ የጨረታው ሂደት አግባብነት የሌለው መሆኑን በቃለ ጉባኤ ላይ ሀሳቤን የገለፅኩ ሲሆን የጨረታው ሂደት ቤቱ ከሚያወጣው ዋጋ በታች መሆኑን ገልጬ ገንዘቡን መልሼ ቤቱን ልረከብ ብልም ከሳሽ ላቀረብኩት ቅሬታና አቤቱታ 1ኛ ተጠሪ ምንም አይነት ምላሽ ሳይሰጠኝ ከዛሬ ነገ አይተንልህ መፍትሄ እንሰጣለን እያለ ጉዳዩ ከሶስት ወር በላይ ከቆየ በኋላ ከ2ኛ ተጠሪ ጋር በመመሳጠር ቤት መልቀቅ አለብህ ብለው ከህግ ውጪ ቤቱን በኃይል ሊያስለቅቁኝ የሁከት ተግባር እየፈጸሙ መሆናቸውን በመግለጽ በይዞታዬ ላይ እየተፈጸመ ያለው የሁከት ተግባር ሊወገድ ይገባል በማለት ዳኝነት መጠየቁን የሚያሳይ ነው፡፡

የአሁን 1ኛ ተጠሪ በሰጠው መልስ፡- አመልካች ከ1ኛ ተጠሪ ላይ የወሰዱትን ብድር በውሉ መሰረት ያልመለሱ በመሆኑ በአዋጅ ቁጥር 97/90 መሰረት አመልካች በዋስትና ያስያዙት ቤት በጨረታ ተሸጦ እዳውን እንደሚሰበስብ ጨረታ ከማውጣቱ በፊት ለአመልካች አሳውቋል፤ ይህንንም አመልካች አልካደም፤ በአዋጅ ቁጥር 97/90 መሰረት 1ኛ ተጠሪ ወደ ፍርድ ቤት መሄድ ሳያስፈልገው ንብረቱን በጨረታ ሽጦ ስመሀብቱን ወደ ገዢው እንዲያዛውር ስልጣን ተሰጥቶታል፤ ይህም በፍርድ ቤት ሊፈርስ እንደማይችል በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ቅጽ 13 መ.ቁ. 68708 እና በቅጽ 14 መ.ቁ. 84353 አስገዳጅ የህግ ትርጉም ተሰጥቶበታል፤ 1ኛ ተጠሪ የጨረታ ማስታወቂያ በየካቲት 1 ቀን 2012 ዓ.ም ሲያስነግር 1ኛ እና 2ኛ የጨረታ ማስታወቂያ ሳያወጣ በስህተት ለ3ኛ ግዜ ተብሎ የወጣ ቢሆንም ወድያውኑ እንዲታረም በማድረግ አመልካች በተገኘበት ለመጀመሪያ ጊዜ ጨረታ ለማድረግ የተገኘን ቢሆንም በጨረታው ለመሳተፍ የቀረበ ተጫራች ባለመኖሩ ጨረታው ሳይካሄድ ቀርቷል፤ በዚህ መሰረት ጨረታው ለ2ኛ ግዜ በቀን 09/07/2012 ዓ.ም በሪፖርተር ጋዜጣ እንዲወጣ ተደርጎ በ2ኛ ጨረታ ሁለት ተጫራቾች ቀርበው አመልካች በታዛቢነት በተገኘንበት ጨረታው ተካሂዶ 2ኛ ተጠሪ

ባቀረቡት ዋጋ አሸናፊ ሆነዋል፤ በጨረታው መመሪያ መሰረት ጨረታው በሚካሄድበት ሰዓት የጨረታ ማስከበሪያ ሲፒኦ አሟልተው የቀረቡት ሁለት ተጫራቾች ብቻ ናቸው፤ መመሪያውን አሟልቶ የቀረበ ተጫራች በጨረታው እንዳይሳተፍ አልተደረገም፤ የቀረቡት ሁለቱ ተጫራቾች በመካከላቸው ዝምድና ስለመኖሩ 1ኛ ተጠሪ አያውቅም፤ የማወቅም ግዴታ የለበትም፤ አመልካችም 1ኛ ተጠሪ ዝምድና ያላቸው መሆኑን ያውቃል የሚል መቃወሚያም ሆነ ክርክር አልቀረበም፤ ከጨረታውም በፊትም ሆነ በኋላ 1ኛ ተጠሪ አመልካች እዳውን እንዲከፍል በተደጋጋሚ ቢያሳውቀውም ሊከፍል ባለመቻሉ የንብረቱ ስመሀብት ገዢ ወደ ሆኑት 2ኛ ተጠሪ ዞሯል፤ አመልካች በንብረቱ ላይ ከገዢው የተሻለ መብት ካለመኖሩም በተጨማሪ ምንም ዓይነት ህጋዊ መብት የለውም፤ 1ኛ ተጠሪ አመልካች ከመኖሪያ ቤቱ ለቆ ለ2ኛ ተጠሪ እንዲያስረክብ መጠየቁ የሁከት ተግባር አያስብለውም፤ ይልቁንም አመልካች ቤቱን እንዲያስረክቡ በቃል እና በጽሁፍ በተደጋጋሚ የተነገራቸው ቢሆንም ከነገ ዛሬ አስረክባለሁ እያሉ ሳያስረክቡ በኃይል ይዘውት ይገኛሉ፤ 1ኛ ተጠሪ ለ2ኛ ጊዜ የተጭበረበረ ጨረታ በማውጣት ሆን ብሎ አመልካችን በሚጎዳ መልኩ ለ2ኛ ተጠሪ ቤቱን ለማስተላለፍ እየጣረ ነው ብሎ ያቀረበው ክስ ከቅን ልቦና ውጪ የቀረበ ሀሰተኛ ክስ ነው፤ በስህተት የወጣውን የጨረታ ማስታወቂያ መስተካከሉን አመልካች እያወቁ 1ኛ ተጠሪ እንዲስተካከል በጋዜጣ ማስነገሩ የጨረታውን አወጣጥ ሂደት መሰረት አድርገው ያቀረቧቸው ዝርዝር ጉዳዮች ከእውነት የራቀ መሆኑን በመግለጽ የአመልካች የሁከት ይወገድልኝ ክስ ወድቅ ሊደረግ ይገባል በማለት ተከራክረዋል፡፡

የአሁን 2ኛ ተጠሪ በሰጡት መልስ የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ አመልካች ለክርክሩ መነሻ የሆነውን ቤት ግምት ተገምቶ ክስ ያላቀረበ በመሆኑ ክሱ ውድቅ ሊደረግ ይገባል ወይም ትክክለኛውን የዳኝነት ግምት ቀርቦ ሊከፍሉ ይገባል፤ በፎርክሎዠር ህግ መሰረት የሚከናወን የሀራጅ ጨረታ በፍርድ ቤት የሚሰረዝበት አግባብ የሌለ በመሆኑ ፍርድ ቤት ጉዳዩን ለማየት ስልጣን የለውም፤ ከሁለት ወራት በኋላ ጨረታው እንዲሰረዝ የቀረበ ክስ በመሆኑ በይርጋ ይታገዳል፤ በፍሬ ነገር ላይ ደግሞ ለ3ኛ ጊዜ በሚል የወጣው ጨረታ ማስታወቂያ በስህተት በመሆኑ ይህም በጋዜጣ እርማት ተደርጎ በመጀመሪያው የጨረታ ሂደት ላይ ተጫራች ባለመቅረቡ ምክንያት ጨረታ አልተደረገም፤ አመልካች ቤቱ በሚሸጥበት ወቅት 1ኛ ተጠሪ 1ኛ እና 2ኛ ጨረታ ሳያወጣ 3ኛ ጨረታ በማውጣት እና ከ2ኛ ተጠሪ ጋር በመመሳጠር የፈጠረው ህገ ወጥ ተግባር የለም፤ አመልካች በየጨረታ ሂደቱ በህጉ አግባብ ባለመፈጸሙ ጉዳት ደረሰብኝ የሚል ከሆነ በሻጭ ላይ የጉዳት ካሳ ብቻ መጠየቅ እንደሚችል በአዋጅ ቁጥር 97/90 አንቀጽ 7 እና በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አስገዳጅ የህግ ትርጉም የተሰጠበት መሆኑን በመግለጽ የአመልካች ክስ ውድቅ ሊደረግ ይገባል በማለት ተከራክሯል፡፡

ጉዳዩ የቀረበለት ፍርድ ቤት የቀረቡት የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያዎችን በብይን ውድቅ አድርጓል፡፡ በመቀጠልም ፍርድ ቤቱ 1ኛ ተጠሪ ያካሄደውን የጨረታ ሂደት የሚገልጽ ቃለ ጉባዔ እንዲቀርብ ካደረገ በኋላ አመልካች ይዞታውን በዋስትና አስይዘው ከ1ኛ ተጠሪ ገንዘብ የተበደሩ እና 2ኛ ተጠሪም በጨረታ

አሸንፈው ይዞታውን የገዙ ስለመሆኑ ተረጋግጧል፤ የብድር ገንዘብ አመላለስ በመያዣነት የተያዘ በኪሳራ የፈረሰ ማህበር ንብረት በሀራጁ ጨረታ የተሸጠ በመሆኑ ሽያጭ ሊፈርስ ይገባል በሚልም ሆነ በመያዣ የተያዘውን ንብረት በባንኩ በሀራጅ የተሸጠ በመሆኑ በባለእዳው በኩል ቢሸጥ የተሸለ ዋጋ ያስገኝ ስለነበር ሽያጭ ሊፈርስ ይገባል በሚል የሚቀርብ አቤቱታ ተቀባይነት የሌለው መሆኑን የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት መ.ቁ. 84353 እና መ.ቁ. 38708 መሰረት አስገዳጅ የህግ ትርጉም ተሰጥቶበታል፤ 1ኛ ተጠሪ በአሻሻጡ ሂደት ባንኩ ህግን ባለመከተል የፈጸመው ስህተት ቢኖር እና በባለእዳው ላይ ጉዳት ቢደርስ ግን ለዚህ ጉዳት ለባለ እዳው ካሳ የመክፈል ኃላፊነት ከሚኖርበት ውጪ ፍርድ ቤቶችም ሀራጁን ለማስቆም ስልጣን እንደሌለው በአዋጅ ቁጥር 97/90 እና 216/92 የተደነገገ በመሆኑ ተጠሪዎች በአመልካች ላይ የፈጸሙት የሁከት ተግባር የለም በማለት ውሳኔ ሰጥቷል። አመልካች ይህን ውሳኔ በመቃወም ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የይግባኝ አቤቱታ አቅርበዋል። ይግባኙ የቀረበለት ፍ/ቤትም የስር ፍርድ ቤትን ውሳኔ አጽንቶታል።

የሰበር አቤቱታው የቀረበው ይህን ውሳኔ በመቃወም መሠረታዊ የሕግ ስሕተት ተፈጽሞበታል በሚል ሲሆን ይዘቱም፡- አመልካች በስር ፍርድ ቤቶች ያነሳው የጨረታው ሂደት ህጋዊ አይደለም በሚል እንጂ በአዋጅ ቁጥር 97/90 የተሰጠውን ስልጣን በመቃወም አይደለም፤ አንደኛ ተጠሪ በየካቲት 1 ቀን 2012 ዓ/ም በስህተት ያወጣው የሀራጅ ማስታወቂያ ላይ እርማት ሲያወጣ ማስታወቂያው ዝርዝር ላይ የሚታረሙ ብቻ ተስተካክለው የቀደመው ሀራጅ በዚህ ቀን፣ወር እና ዓ/ም በማስታወስ የሚከናወን ሆኖ ሳለ 1ኛ ተጠሪ ይህንን ሳያደርግ በደፈናው ሌላ አይነት የሀራጅ ማስታወቂያ በሚመስል መልኩ ለ ሁለተኛ ጊዜ የወጣ በሚል መቀመጡ ቀድሞ በስህተት ከወጣው የጨረታ ማስታወቂያ ጋር የተለያየ የሚመስል እና የአመልካችን ንብረቱን ከፍሎ የማስቀረት መብቱን ወይም የኢ.ፌ.ድ.ሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 40 እንዳይጠቀም አድርጎታል፤ በሁለተኛ ጨረታ ከአሁን አመልካች ውጭ ቀደም ሲል በተበዳሪዎች ዝርዝር ውስጥ ያልነበሩ ተካተውበታል፤ የስር ፍርድ ቤቶች ተጠሪዎች በአዋጅ ቁጥር 97/90 እና 216/92 ላይ አበዳሪው ባንክ በዋስትና የያዘውን ንብረት ወደ ፍርድ ቤት መሄድ ሳያስፈልገው ንብረቱን በጨረታ ሻጩ ስመሀብቱን ወደ ገዢ የማዛወር ስልጣን ተሰቶኛል በሚል ያቀረቡትን ክርክር ያለመንቀፋቸው የአመልካችን በኢ.ፌ.ድ.ሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 37 ፍትህ የማግኘት መብቱን የሚቃረን ነው፤ አመልካች ስለ ህገወጥ የጨረታ ሂደት እያነሳ ባለበት የስር ፍርድ ቤቶች የጨረታውን ህግ እና ደንብ አስቀርቦ መመርመር ሲገባቸው የጨረታውን ቃለ ጉባኤ ብቻ መሰረት በማድረግ የሰጡት ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል የሚል ነው።

የአመልካች የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ የአሁን አመልካች የፍትህ ጥያቄ ባንክ ሀራጅ ማውጣት ስልጣን የለውም የሚል ሳይሆን በህግ አግባብ 1ኛ እና 2ኛ ጨረታ ሳይወጣ 3ኛ ጨረታ አውጥቶ ከህግ ውጪ ንብረቱን በአነስተኛ ዋጋ እየሸጠ ስለሆነ ሁከት ይወገድ የሚል ሆኖ ሳለ የስር ፍርድ ቤት በአዋጅ ቁጥር 97/90 ለባንክ የተሰጠውን ስልጣን ብቻ መሰረት በማድረግ ከህግ ውጪ የተደረገ ጨረታ አይፈርስም

በማለት የወሰነበትን አግባብ ከህገ መንግስቱ አንቀጽ 37 እና 40፣ ከአዋጅ ቁጥር 97/90፣ 216/92 እንዲሁም የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ. 136092 ከተሰጠው የህግ ትርጉም ጋር በማገናዘብ ለመመርመር ሲባል ጉዳዩ በዚህ ችሎት እንዲታይ ተደርጓል። ለተጠሪ ጥሪ ተደርጎም ግራ ቀኙ በጽሑፍ እንዲከራከሩ ተደርጓል።

የ1ኛ ተጠሪ መልስ ይዘት በአጭሩ፡-አመልካች ጨረታው ህጉን ተከትሎ ያልተፈጸመ በመሆኑ ጨረታው እንዲሰረዝ እና የሁከት ተግባር እንዲቆም በሚል ክስ ያቀረቡ ሲሆን 1ኛ ተጠሪም ጨረታው የማይፈርስበትም ምክንያቶች በመጥቀስ ተከራክሯል፤ አመልካች በጨረታው ምክንያት ጉዳት ደርሶብኛል በማለት የጉዳት መጠኑን ጠቅሰው ያቀረቡት የካሳ ጥያቄ በሌለበት የስር ፍ/ቤት የጨረታው ሂደት ውስጥ በመግባት ጨረታው በህጉ አግባብ ስለመካሄዱ አለመካሄዱ የሚመረምርበት እና ውሳኔ የሚሰጥበት የህግ መሰረት የለም፤ አመልካች ጉዳት ደርሶብኛል የሚሉ ከሆነ የጉዳት መጠኑን ጠቅሰው ክስ ከመመስረት ውጪ ጨረታው በፍ/ቤት የሚሰረዝበት የህግ መሰረት የለም፤ አመልካች በሰበር አቤቱታቸው የጠቀሱት የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በቅጽ 22 በመ/ቁ. 136092 የሰጠው አስገዳጅ ውሳኔ አሁን ክርክር ካስነሳው ጉዳይ ጋር የሚያያዝ አይደለም። በሁለተኛ ጨረታ ከአሁን አመልካች ውጭ ቀደም ሲል በተበዳሪዎች ዝርዝር ውስጥ ያልነበሩ ተካተውበታል በማለት ያቀረቡት ክርክር በስር ፍርድ ቤት ያልተነሳ እና ህጋዊ መሰረት የሌለው በመሆኑ የስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ ሊጸና ይገባል የሚል ነው።

የ2ኛ ተጠሪ መልስ ይዘት በአጭሩ፡- የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር አጣሪ ችሎት የተያዘው ጭብጥ አመልካች በስር ፍርድ ቤት ያቀረቡትን የክርክር ይዘት የስር ፍርድ ቤቶችን ውሳኔ ይዘት እንዲሁም ጨረታው ክሱ በቀረበበት ጊዜ የነበረበትን ሂደት በተሳሳተ ሁኔታ በመገንዘብ ነው፤ 1ኛ ተጠሪ በስህተት የወጣውን የጨረታ ጥሪ በጋዜጣ ላይ እርማት በማድረግ በዚሁ ጨረታ ላይ ተጫራች ባለመቅረቡ ምክንያት የቤቱ ሽያጭ ያልተከናወነ በመሆኑም በእርማት በመደረጉ ምክንያት የደረሰ ጉዳት የለም፤ በጨረታ ሂደቱ ላይ የተፈጠረ ስህተት ወይም የማጭበርበር ድርጊት አልነበረም፤ አመልካች በጨረታው ሂደት፣ እርማቱ ተገቢ አይደለም እንዲሁም እዳውን ከፍዬ ቤቱን ላስቀር በሚል አቤቱታ አቅርቤ አልተፈቀደልኝም የሚል ክርክር በስር ፍርድ ቤት በአመልካች አልተነሳም፤ በጨረታ የተሸጠው ቤት አመልካች ከ1ኛ ተጠሪ ለተበደሩት ብድር በመያዣነት የተያዘ ሆኖ ብድሩ ባለመክፈሉ ለጨረታ የቀረበ ስለመሆኑ አመልካች አልካደም በመሆኑም የስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ ሊጸና ይገባል የሚል ነው።

አመልካችም የሰበር አቤቱታቸውን በማጠናከር የመልስ መልስ ሰጥተዋል።

የጉዳዩ አመጣጥ በአጭሩ ከላይ የተገለጸው ነው። ይህ ችሎትም በሰበር አጣሪው ችሎት ሊጣራ ይገባዋል ተብሎ የተያዘውን ነጥብ ከግራ ቀኙ ክርክር፤ ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸው ሕጎች ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለው መርምሮታል።

ከክርክሩ ሒደት መገንዘብ የቻልነው አመልካች በስር ፍ/ቤት ሂደት የሚጎዳኝ ሆኖ የጨረታን ህግ እና ደንብ አስቀርቦ መመርመር ሲገባቸው የጨረታውን ቃለ ጉባኤ ብቻ መሰረት በማድረግ የሰጡት ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል በሚል የሚከራከሩ ሲሆን ተጠሪ በበኩሉ ፍ/ቤቱ ጉዳዩን ለማየት የመጀመሪያ ደረጃ የዳኝነት ሥልጣን የለውም የሚል መቃወሚያን በማንሳት መከራከሩን እና የስር ፍ/ቤቶችም መቃወሚያውን መሠረት በማድረግ ሥልጣን የለንም ሲሉ መወሰናቸውን ነው፡፡

በዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት በጭብጥነት ተይዞ ሊመረመር የሚገባው አጣሪው ከያዘው ጭብጥ በተጨማሪ አመልካች አጥብቀው እየተከራከሩ ያሉት አስቀድሞ በዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት ውሣኔ ያገኘ በመ/ቁ/ 136092 በሆነው መዝገበ የተወሰነ ውሣኔ እያለ በስር ፍ/ቤት የተሰጠው ውሣኔ ተገቢ አይደለም በሚል የተከራከሩ በመሆኑ የውሣኔውን አግባብነት አስቀድሞ በተመሳሳይ ጉዳይ ይኸው ሰበር ሰሚ ችሎት ከሰጣቸው የህግ ትርጉሞች አንፃር፣ እንዲሁም የቀረበው የሁከት ክስ ከመሆኑ አኳያ ተመርምሮ ስለመወሰን አለመወሰኑ ነው፡፡

አመልካች በስር ፍ/ቤት አቅርበውት የነበረው ክስ የሚመለክተው 1ኛ እና 2ኛ ዙር ጨረታ በጋዜጣ ሳያወጣ 3ኛ ዙር ጨረታ ብሎ በጋዜጣ ማውጣቱ ባንኩ ከሚመራበት የጨረታ መመሪያ ውጪ ከ2ኛ ተጠሪ ጋር በመመሳጠር በጨረታ የሚሸጠው ቤት ሊያወጣ የሚገባውን እንዳያገኝ እና ተጫራቾች በስፋት እንዳይቀርቡ በሪፖርተር ጋዜጣ ለ2ኛ ጊዜ የወጣ ጨረታ በሚል ጥቅሜን የሚጎዳ ተግባር በመፈፀም፣ እንዲሁም ከሳሽ የጨረታው ሂደት አግባብነት የሌለው መሆኑን በቃለ ጉባኤ ላይ ሀሳቤን የገለፅኩ ሲሆን የጨረታው ሂደት ቤቱ ከሚያወጣው ዋጋ በታች መሆኑን ገልጬ ገንዘቡን መልሼ ቤቱን ልረከብ ብልም ከሳሽ ላቀረብኩት ቅሬታና አቤቱታ 1ኛ ተጠሪ ምንም አይነት ምላሽ ሳይሰጠኝ ከዛሬ ነገ አይተንልህ መፍትሄ እንሰጣለን እያለ ጉዳዩ ከሶስት ወር በላይ ከቆየ በኋላ ከ2ኛ ተጠሪ ጋር በመመሳጠር ቤት መልቀቅ አለብህ ብለው ከህግ ውጪ ቤቱን በኃይል ሊያስለቅቁኝ የሁከት ተግባር እየፈጸሙ በመሆኑ የሁከት ተግባር ሊወገድ ይገባል በማለት ዳኝነት መጠየቁን የሚያሳይ ነው፡፡

በመሠረቱ በሰበር ሰሚ ችሎት የተሰጡ የህግ ትርጉም ተፈፃሚ ሊሆን የሚገባው በተመሳሳይ ጉዳይ ላይ የቀረበ ጉዳይን ለማስተናገድ ሲሆን፣ በአጣሪ በተያዘው ጭብጥ ላይ የተጠቀሰው የሰበር ውሣኔ በተጫራቾች መካከል በተደረገ የጨረታ አካሄድ ላይ የተሰጠ ውሣኔ እንጂ በባንክ በተያዘ እና በተከበረ ንብረት ላይ ባለዕዳው ዕዳውን መክፈል ባልቻለ ጊዜ በሚወጣ የጨረታ አካሄድ ላይ የቀረበ ቅሬታን አስመልክቶ የተሰጠ የህግ ትርጉም ባለመሆኑ በሰ/መ/ቁ/ 136092 ላይ የተሰጠው ትርጉም ከቀረበው ጉዳይ ጋር ተመሳሳይነት የሌለው በመሆኑ ተቀባይነት ሊያገኝ የሚገባው አይደለም፡፡

አዋጅ ቁጥር 97/90 እና 216/92ን አስመልክቶ ለቀረቡ መዛግብት ከዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት የተሰጡ ትርጉሞችን ስንመለከት፡- በሀራጁ ጨረታ የተሸጠ በመሆኑ ሽያጭ ሊፈርስ ይገባል በሚልም ሆነ

በመያዣ የተያዘውን ንብረት በባንኩ በሀራጅ የተሸጠ በመሆኑ በባለእዳው በኩል ቢሸጥ የተሻለ ዋጋ ያስገኝ ስለነበር ሽያጭ ሊፈርስ ይገባል በሚል የሚቀርብ አቤቱታ ተቀባይነት የሌለው መሆኑን የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት መ.ቁ. 84353 እና መ.ቁ. 38708 እንዲሁም በሌሎች መዛግብት አስገዳጅ የህግ ትርጉም ተሰጥቶበታል፡፡

ወደያዝነው ጉዳይ ስንመለስ ከላይ እንደተመለከተው የአመልካች የሁከት ይወገድልኝ ክስ መሠረት ያደረገው ባንኩ የጨረታ ህግን ሳይከተል ጨረታ በአግባቡ ሳያወጣ ንብረቱን ሊሸጥና ከንብረቱ ላገኝ የሚገባኝን ጥቅም ሊያሳጣኝ ነው የሚል በመሆኑ እንዲሁም በተያዘው ጉዳይ ጨረታው ወጥቶ ቤቱ ተሸጦ ለ2ኛ ተጠሪ ለማስተላለፍ አመልካች ቤቱን እንዲለቁ የተጠየቁ በመሆኑ በቤቱ ላይ የወጣውን ጨረታ የማሳገድ ሳይሆን በጨረታ የተሸጠውን ንብረት ወደገዢ እንዳይተላለፍ እና በውጤት ደረጃም እንዲታገድ የማድረግ ውጤት ያለው መሆኑን እንረዳለን፡፡ በመሆኑም አንድ በባንክ ዕዳ ምክንያት በጨረታ የተሸጠን ንብረት እንዲለቅ የሚጠየቅ ባለዕዳ በጨረታ ሂደቱ ላይ ጉድለት ያለበት የሚል ከሆነ ጉዳት መድረሱን አረጋግጦ ክስ ከሚያቀርብ በስተቀር ቤት እንድለቅ መጠየቁ የሁከት ተግባር ነው በሚል የሁከት ክስ ለማቅረብ የሚችልበት የህግም አግባብ የሌለ በመሆኑ የስር ፍ/ቤቶች ሁከት የለም ብለው መወሰናቸው ተገቢ እንጂ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ ባለመገኘቱ አቤቱታው ውድቅ ሆኖ ተከታዩ ተወስኗል፡፡

<u>ውሳኔ</u>

1. የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ.261287 ግንቦት 19 ቀን 2013 ዓ.ም. በዋለው ችሎት የሰጠው ፍርድ እና የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 285529 ጥር 03 ቀን 2013 ዓ.ም. በዋለው ችሎት የሰጠው ፍርድ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 348/1 መሠረት ፀንቷል፡፡
2. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪ ግራ ቀኙ የየራሣቸውን ይቻሉ፡፡
3. በ26/09/2013 ዓ.ም. በዋለው ችሎት ጨረታው ለጊዜው ታግዶ እንዲቆይ የተሰጠው የእግድ ትዕዛዝ ተነስቷል፡፡ ይጻፍ
4. የውሣኔው ትክክል ግልባጭ ለስር ፍ/ቤቶች ይድረስ፡፡

- <u>መዝገቡ ውሳኔ ስላገኘ ተዘግቷል፡፡ ይመለስ</u>

ማ/አ የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሰ/መ/ቁ/ 166392

ሚያዚያ 26 ቀን 2012 ዓ.ም

ዳኞች፡- ሰለሞን አረዳ

ብርሃኑ አመነዉ

ተሾመ ሽፈራዉ

ሐብታሙ እርቅይሁን

ብርሃኑ መንግስቱ

አመልካች፡- ሚ/ር ሳሚ ሳዲቅ ራቲብ

ተጠሪ፡- 1. አቶ ቴዎድሮስ ታደሰ ወላንሳ

2. አቢሲኒያ ስላዉተር ሰርቪስ ኃ/ የተ/የግ/ ኩባኒያ

መዝገቡ ያደረዉ ለምርመራ ሲሆን መዝገቡን መርምረን የሚከተለዉን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍርድ

ለዚህ ሰበር አቤቱታ ምክንያት የሆነዉ የፌ/ጠ/ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁ. 158393 በመስከረም 23 ቀን 2010 ዓ.ም በዋለዉ ችሎት የሰጠዉ ዉሳኔ ነዉ፡፡ አመልካች በህዳር 11 ቀን 2011 ዓ.ም ፅፈዉ ባቀረቡት አቤቱታ ላይ ዉሳኔዉ መሰረታዊ የህግ ስህተት ስላለበት ይታረምልን በማለት ያመለከቱ ሲሆን የሰበር አጣሪ ችሎትም አቤቱታዉን መርምሮ ያስቀርባል በማለት መዝገቡ ለችሎት ቀርቦ ግራ ቀኙ እንዲከራከሩበት ትዕዛዝ ሰጥቶ በፅሑፍ ክርክራቸዉን አቅርቦል፡፡

የጉዳዩን አመጣጥ ስንመለከት ክርክሩ በተጀመረበት በፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት የአሁን አመልካች ባቀረበዉ ክስ የአቢሲኒያ ስላዉተር ሰርቪስ ኃ/ የተ/የግ/ ኩባኒያ (የአሁን ሁለተኛ ተጠሪ) ዉስጥ የ50% አክሲዮን ድርሻ የነበረኝ ሲሆን ይህን ድርሻ በብር 35,000,000 (በሰላ አምስት ሚሊዬን ብር) ለአሁን 1ኛ ተጠሪና በስር ከ/ፍ/ቤት 2ኛ እና 3ኛ ተከሳሾች ለነበሩት ለአቶ ሶሻል በየነ ወዳጆ እና አቶ ኤፌሶን ታደሰ ወላንሳ የሸጥኩ ቢሆንም ምንም ባልተገነዘብኩት ሁኔታ የአክሲዮን ሽያጭ ሂሳቡ ብር 24,000,000 (ሀያ አራት ሚሊዬን ብር) ተብሎ ተጽፏል፡፡ የአክሲዮን ሽያጭ ዝዉዉሩ ከመፈፀሙ በፊት ከተጠሪዎች ጋር የወጪ ቀሪ የሒሳብ መተሳሰብ ተደራርጎ ማናቸዉም ወጪዎችና ዕዳዎች ሁሉ ከተቀናነሱ በኋላ ለአመልካች የሚደርሰዉ ንፁሁ የጥሬ ገንዘብ መጠን ብር 14,600,000 (አስራ አራት ሚሊዬን ስድስት መቶ ሺህ ብር) እንደሆነ ስምምነት ላይ ተደርሶ በወቅቱ ተጠሪዎች ይህን ገንዘብ ለመክፈል የሚያስችል ገንዘብ ስላልነበራቸዉ በተለያየ ጊዜያት የሚከፈሉ በጠቅላላዉ የብር 14,600,000 (አስራ አራት ሚሊዬን ስድስት መቶ ሺህ ብር) ዋጋ ያላቸዉ ሦስት ቼኮች ለአመልካች እንዲሰጣቸዉ

ተደርጓል። በ1ኛ ተጠሪ ተፈርሞ የወጡና ንብረትነታቸዉ የ2ኛ ተጠሪ የሆኑት ክርክር የተነሳባቸዉ ቼኮች ሀ) ቁ. ቢኤ 794575 የብር 4,500,000 (አራት ሚሊዬን አምስት መቶ ሺህ ብር) ዋጋ ያለዉ በየካቲት 3 ቀን 2007 ዓ.ም የሚከፈል፣ ለ) ቁ. ቢኤ 794576 የብር 4,500,000 (አራት ሚሊዬን አምስት መቶ ሺህ ብር) ዋጋ ያለዉ በመጋቢት 3 ቀን 2007 ዓ.ም የሚከፈል፣ ሐ) ቁ. ቢኤ 794578 የብር 5,600,000 (አምስት ሚሊዬን ስድስት መቶ ሺህ ብር) ዋጋ ያለዉ በሚያዚያ 2 ቀን 2007 ዓ.ም የሚመነዘር የኦሮሚያ ህብረት ሥራ ባንክ ሲሆኑ አመልካች ቼኮቹን በእጁ ይዞ ጫና እንዳይፈጥር በማሰብ በስምምነት የአመልካችና የ1ኛ ተጠሪ የጋራ ጓደኛ በሆኑት በአቶ ጌታቸዉ ተገኔ እጅ እንዲቀመጡ ተደርጓል። ቼኮቹ የሚመነዘሩበት ጊዜ በተደጋጋሚ በማለፉና ተጠሪዎችም ቃላቸዉን በየጊዜዉ በማጠፋቸዉና የማይፈፅሙ መሆኑ ሲታወቅ ቼኮቹ ከአቶ ጌታቸዉ ተገኔ እጅ ለአመልካች ተመልሷል። ቼኮቹ ለአመልካች መመለሳቸዉን ከተረዱ በኋላ 1ኛ ተጠሪ ብር 150,000 (መቶ ሃምሳ ሺህ ብር)) (በቼክ ቁ. ሲኦ 775082) እና ብር 2,000,000 (ሁለት ሚሊዬን) በሁለት ቼኮች (አንድ ሚሊዬን ብር በቼክ ቁ. ሲኦ 889783፣ ሌላ አንድ ሚሊዬን ብር በቼክ ቁ. ኦኤፍ 001225151) ክፍያ ፈፅሞ ቀሪዉን ገንዘብ ለመክፈል ጊዜ ሲጠይቁ ቆይታል። በተጨማሪም በፍ/ቤት ትዕዛዝ መሰረት ለአመልካች የዕዳ ገንዘብ ብር 1,000,000 (አንድ ሚሊዬን ብር) ከፍሏል። ባጠቃላይ 1ኛ ተጠሪ ለአመልካች ብር 3,150,000 (ሦስት ሚሊዬን አንድ መቶ ሃምሳ ሺህ ብር) ስለከፈለ እነዚህን የተጠቀሱትን ክፍያዎች ለመቀናነስ በማለት ከላይ በተራ ቁ. (ሐ) ላይ የተጠቀሰዉን የቼክ ቁጥር ለ1ኛ ተጠሪ ተመልሶ ክፍያዎቹ ከተቀናነሱ በኋላ ተጠሪ ለልዩነቱ ብር 2,450,000 (ሁለት ሚሊዬን አራት መቶ ሃምሳ ሺህ ብር) የቼክ ቁ. ሲዲ 889784 ለአመልካች ሰጥቷል። በጠቅላላዉ ተጠሪዎች ለአመልካች መክፈል ከሚገባቸዉ ብር 14,600,000 (አስራ አራት ሚሊዬን ስድስት መቶ ሺህ ብር) ላይ የብር 3,150,000 (ሦስት ሚሊዬን አንድ መቶ ሃምሳ ሺህ ብር) ክፍያ የፈፀሙ ሲሆን መክፈል ያለባቸዉ ቀሪ ገንዘብ ብር 11,450,000 (አስራ አንድ ሚሊዬን አራት መቶ ሃምሳ ሺህ ብር) ነዉ። አመልካችም ቀሪዉ ገንዘብ እንድከፈለዉ በተደጋጋሚ ቢጠየቅም ፈቃደኛ አልሆኑም። ሦስቱንም ቼኮች አመልካች ለከፋዩ ባንክ ቢያቀርብም በቼኮቹ ክፍያ እንዳይፈፀም 1ኛ ተጠሪ አሳግዷል። በመሆኑም ተጠሪዎች ባልተነጣጠለ ኃላፊነት እንዲከፍሉ ይወሰንልኝ በማለት ዳኝነት ጠይቋል። ተጠሪዎችም ለስር ከፍተኛ ፍ/ቤት ባቀረቡት መልስ በዋናነት ለዚህ ሰበር ችሎት ጽፈዉ ባቀረቡት መልስ ዉስጥ የተመለከቱትን የመከላከያ ነጥቦች (ከታች ባጭሩ እንደቀረበዉ) በመጥቀስ በሽያጭ ላስተላለፉት የአክሲዮን ድርሻቸዉ ሙሉ ዋጋ የተከፈላቸዉ ስለሆነ በቼኮቹ ላይ የተመለከተዉን ገንዘብ የመክፈል ኃላፊነት ስለሌለባቸዉ ክሱ ዉድቅ ተደርጎ ወጪና ኪሳራ የመጠየቅ መብታቸዉ ተጠብቆላቸዉ በነዛ እንዲያሰናብታቸዉ ጠይቆ እንደነበር የስር ከፍተኛ ፍ/ቤት መዝገብ ያሳያል። የስር ከፍተኛ ፍ/ቤትም ግራ ቀኙን ካከራከረ በኋላ በአንድ በኩል ቼኮቹ ክፍያ እንዳይፈፀምባቸዉ መታገዳቸዉን ያረጋገጠ ሲሆን በሌላ በኩል አመልካች ከተለያየ አካላት ለነበራቸዉ ዕዳዎች የተከፈለ ብር 13,576,274.40 (አስራ ሶስት ሚሊዬን አምስት መቶ ሰባ ስድስት ሺህ ሁለት መቶ ሰባ አራት ከ40/100፤ ከዚህ ዉስጥ ለወጋገን ባንክ

ብር 8,559,274.40 (ስምንት ሚሊዬን አምስት መቶ ሀምሳ ዘጠኝ ሺህ ሁለት መቶ ሰባ አራት ብር ከ40/100 ሳንቲም) እና አቶ ሽፈራ ለተባሉ ብር 5,017,000 (አምስት ሚሊዬን አስራ ሰባት ሺህ ብር) እንዲሁም አመልካች በተለያየ ጊዜ እየመነዘረ የወሰዳቸዉን ክፍያዎች ጨምሮ በጠቅላላዉ ብር 18,526,274.40 (አስራ ስምንት ሚሊዬን አምስት መቶ ሀያ ስድስት ሺህ ሁለት መቶ ሰባ አራት ብር ከ40/100 ሳንቲም) ስለሆነ 1ኛ ተጠሪ ለአመልካች መክፈል ያለበት ብር 1,113,725.60 (አንድ ሚሊዬን አንድ መቶ አስራ ሶስት ሺህ ሰባት መቶ ሀያ አምስት ብር ከ60/100) ብቻ ነዉ፤ በቼኮቹ ላይ የተመለከተዉን ገንዘብ የመክፈል ግዴታ የለበትም፤ 2ኛ ተጠሪ ኃላፊነት የለበትም በማለት ዉሳኔ ሰጥቷል። አመልካችም በዚህ ዉሳኔ ቅር በመሰኘት የይግባኝ ቅሬታ ለፌ/ጠ/ፍ/ ቤት አቅርቦ ፍ/ቤቱም ጉዳዩን ከመረመረ በኋላ በሰጠዉ ዉሳኔ የስር ከፍተኛ ፍ/ቤትን ዉሳኔ በሁለት ነጥቦች በማሻሻል ዉሳኔ ሰጥቷል። አንደኛ የስር ከፍተኛ ፍ/ቤት ከተጠሪ ለአመልካች መክፈል ስለነበረበት ቀሪ ገንዘብ ያደረገዉ ስሌትና የደረሰበት ድምዳሜ የተሳሳተ ነዉ በማለት ጠቅላላ የአክሲዮን ሽያጩ ዋጋ ብር 24,000,000 (ሀያ አራት ሚሊዬን ብር) ስለሆነ ተጠሪ በተለያየ ጊዜ ለአመልካች ከፍያለዉ ያላቸዉን 20,526,244.40 (ሀያ ሚሊዬን አምስት መቶ ሀያ ስድስት ሺህ ሁለት መቶ አርባ አራት ብር ከ40/100 ሳንቲም) በመቀነስ ቀሪ ገንዘቡ 3,447,756 (ሶስት ሚሊዬን አራት መቶ አርባ ሰባት ሺህ ሰባት መቶ ሀምሳ ስድስት ብር) እንዲከፍል በማለት ወስኗል። ሁለተኛ የስር ከፍተኛ ፍ/ቤት 2ኛ ተጠሪን ምንም ሳይል በዝምታ ከክሱ ያስወጣዉ አግባብ አይደለም በማለት 2ኛ ተጠሪም ከ1ኛ ተጠሪ ጋር በአንድነትና በነጠላ ተጠያቂ ነዉ በማለት ወስኗል።

ይህ የሰበር አቤቱታም ከላይ የተጠቀሱትን የስር ፍ/ቤቶችን ዉሳኔ ለማሳረም የቀረበ ማመልከቻ ነዉ። አመልካችም በሰበር አቤቱታቸዉ ላይ የስር ፍ/ቤቶች ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት ተፈፅሞባቸዋል ያለበትን ነጥቦች በመዘርዘር ተከራክሯል። ያቀረበዉም ክርክር ባጭሩ እንደሚከተለዉ ነዉ።

1ኛ ቼኮቹ ከተጠሪዎች ለአመልካች የተሰጡት አመልካች በ2ኛ ተጠሪ ዉስጥ ለነበራቸዉ የአክሲዮን ድርሻ ለሠነዶች ማረጋገጫና ምዝገባ ጽ/ቤት በሐምሌ 17 ቀን 2006 ቀርቦ ለፀደቀዉ ሽያጭ ዋጋ መክፈያ መሆኑ የተረጋገጠ ጉዳይ ነው። ተጠሪዎች ግን ቼኮቹ ለዋስትና ነው የሚል ክርክር ቢያቀርቡም በዚህ በኩል የተደረገ ስምምነት ስለመኖሩ ያቀረቡት ማስረጃም ሆነ ዉል የለም። የዋስትና ስምምነት በሰነድ በሚደረግ ስምምነት ብቻ የሚረጋገጥ ነዉ። ቼኮቹ የተሰጡት ለዋስትና ቢሆን ኖሮ የክፍያ ጊዜያቸዉ የተለያዩ ሦስት ቼኮችን መስጠት ባላስፈለገ ነበር። ለዋስትና የድምር ሂሳብ የሚያሳይ አንድ ቼክ በቂ ነበር። ለዋስትና ተሰጥቶል ቢባልም ለምን በክሱ መሰረት ለሆኑት ቼኮች ዋጋ መጠን ስለመሰጠታቸዉ መከራከሪያ አላቀረቡም። የስር ፍ/ቤትም ምንም የሠነድ ማስረጃ ባልቀረበበት በጉዳዩ ላይ ቀጥታ ተከሳሽ የሆኑትን ግለሰቦች ቃል ላይ ብቻ ተሞርክዞ ቼኮቹ ወደፊት ሂሳብ ለመተሳሰብ በማሰብ ለአመልካች እንደተሰጠ አድርጎ የተጠቀሰዉን ዉሳኔ መስጠቱ መሠረታዊ የህግ ስህተት ነዉ።

1ኛ ተጠሪ በመስኩ በቂ እዉቀትና ልምድ ያለዉ ሰዉ ሆኖ ሳለ ለወጋገን ባንክና ለአቶ ሽፈሬ ለተባለ ግለሰብ ተፈፀሙ የተባሉትን ክፍያዎች ለክርክሩ ምክንያት የሆኑት ቼኮች ከመሰጠታቸዉ በፊት በማያሻማ መልኩ የሚታወቁ ሆኖ እያለ ወደፊት ለመተሳሰብ ብሎ ከአስራ አንድ ሚሊዬን ብር በላይ ዋጋ ያላቸዉን ቼኮች ሰጠ መባሉ ተቀባይነት የለዉም። ለወጋገን ባንክ ተከፈለ የተባለዉ ክፍያም ቼኮቹ ከመሰጠታቸዉ አስቀድሞ በቀን 23/05/2006 ዓ.ም ሲሆን ክፍያዉም የተፈፀመዉ ሼባ ትራንስፖርት ኃ/የተ/የግ/ኩባንያ እንጂ በ1ኛ ተጠሪ አይደለም። ለአቶ ሽፈሬ የተከፈለዉ ክፍያ በተመለከተ በተጠሪና ግለሰቡ መካከል በተደረገ ስምምነት ሲሆን አመልካች በዚህ የስምምነት ሠነድ ላይ አልተስማሙም፤ አልፈረሙም፤ ሠነዱም ደግሞ የተፈረመዉ ለዚህ ክርክር ምክንያት የሆኑት ቼኮች ከመሰጠታቸዉ ከወራት በፊት ሆኖ እያለ የስር ፍ/ቤት በሠነዱ ላይ የተመለከተዉን ገንዘብ ከቼኮቹ ዋጋ ላይ ተቀናሽ ሊደረጉ ይገባል ማለቱ ስህተት ስለሆነ ሊታረም ይገባል።

2ኛ የስር ፍ/ቤት አስቀድሞ የተቀናነሱትን ክፍያዎች መልሶ በድጋሚ አመልካች ከያዙት ቼክ ዋጋ ላይ መቀነሱ ስህተት ነው። 1ኛ ተጠሪ በቼክ ቁጥሮች ሲኦ 889783፣ ሲኦ 775082፤ ሲኤፍ 001225151 እና 486969 በድምሩ ብር 4,950,000 (አራት ሚሊዬን ዘጠኝ መቶ ሀምሳ ሺህ ብር) ከፍያለሁ ብልም ለአመልካች የተከፈለዉ ጠቅላላ ብር 3,150,000 (ሦስት ሚሊዬን አንድ መቶ ሃምሳ ሺህ ብር) ዉጪ (በፍ/ቤት ትዕዛዝ መሰረት የተከፈለዉንና በቼክ ቁጥሮች ሲኦ 889783፣ ሲኦ 775082ና ሲኤፍ 001225151 የተከፈሉትን ክፍያዎች ጨምሮ) ከተጠሪ ለአመልካች የፈፀመዉ ሌላ ክፍያ የለም።

3ኛ የአመልካችና የተጠሪ የጋራ ምስክር ሆኖ የቀረቡት አቶ ጌታቸዉ ተገኔ ቼኮቹ ለአመልካች የተሰጡት አሰቀድሞ የነበሩት ሂሳቦች ተቀናንሰዉ ለአመልካች ሊከፈል የሚገባ ገንዘብ መጠን የተሰሩ ስለመሆናቸዉ የሰጡትን የምስክርነት ቃል ሳይቀበል የራሳቸዉ የተከሳሾችን የምስክር ቃል ክብደት በመስጠት ፍርድ መስጠቱ ስህተት ነው። በተጨማሪም የሁለት ቼኮችን ቁጥር (ቢኤ 79424- ብር 400,000 (አራት መቶ ሺህ ብር) የተከፈለበትና 486961 ገንዘብ መጠኑም ያልተገለፀ) በመጥቀስ በእነዚህ ቼኮች የተከፈለዉ ለክርክሩ መነሻ የሆኑት ቼኮች ከመሠጠታቸዉ በፊት መሆኑን ሠነዶቹ ራሳቸዉ የሚያረጋግጡ ሆኖ ሳለ ወደፊት ከተሰጠ ቼክ ላይ ታሳቢ መደረጉ ስህተት ነዉ።

ስለሆነም ለክርክሩ መነሻ በሆኑት በቼክ ቁ. ቢኤ 794575፣ ቢኤ 794576 እና ሲኦ 889784 ላይ የተመለከቱት ጠቅላላ ብር 11,450,000 (አስራ አንድ ሚሊዬን አራት መቶ ሃምሳ ሺህ ብር) ተጠሪዎች ለአመልካች እንዲከፍሉ እንዲወሰንለትና ለዚህ ክርክር የወጡትን ወጪዎችና ኪሳራዎችና ህጋዊ ወለድ ተጠሪ ለአመልካች እንዲተኩ እንዲወሰንለት ዳኝነት ጠይቋል።

ተጠሪዎች በጥር 23 ቀን 2011 ዓ.ም በጋራ ፅፈዉ ባቀረቡት መልስ 1ኛ የአመልካች የሰበር አቤቱታም ሆነ በሰበር አጣሪ ችሎት ያስቀርባል በማለት የተያዘዉ ጭብጥ የፍሬ ነገር ጉዳዮችን እንጂ

የህግ ስህተቶችን የሚመለከቱ አይደሉም። የሰበር ችሎቱ ደግሞ የሚመለከታቸዉ ጉዳዮች ወይም አቤቱታዎች በስር ፍ/ቤቶች ዉሳኔዎች ላይ የተፈፀሙትን መሰረታዊ የህግ ስህተቶችን በተመለከተ ብቻ ነዉ። በስር ፍ/ቤቶች ዉሳኔ የተፈፀመ ስህተት የለም እንጂ ቢኖርም እንኳን ስህተት የተባሉትና የቅሬታ ነጥቦች የፍሬ ነገር ጉዳዮችን የተመለከቱ ሆነዉ ባሉበት ሁኔታ ይህ የሰበር ችሎት የአመልካችን ማመልከቻ ተቀብሎ የመወሰን ስልጣን የለዉም።

2ኛ አመልካችና 1ኛ ተጠሪ የብር 35,000,000 (ሰላሳ አምስት ሚሊዬን ብር) የአክሲዮን ሽያጭ ስምምነት አላደረጉም፤ አመልካችም ይህን ያህል የሚያወጣ ድርሻም በኩባኒያዉ ዉስጥ አልነበራቸዉም። ለዚህም የቀረበ ማስረጃ የለም። በስር ፍ/ቤት አሻሽሎ ባቀረቡት የክስ ማመልከቻ አመልካች በ2ኛ ተጠሪ ዉስጥ የነበራቸዉ የአክሲዮን ብዛት 2454 የአንዱ የአክሲዮን ድርሻ ዋጋ ብር 10,000 (አስር ሺህ ብር) ሆኖ ጠቅላላ የሽያጭ ዋጋቸዉ 24,540,000 (ሀያ አራት ሚሊዬን አምስት መቶ አርባ ሺህ) ከሆነዉ ድርሻ ዉስጥ ለ1ኛ ተጠሪ የተሸጠዉ 1964 አክሲዮን ዋጋቸዉ ብር 19,640,000 (አስራ ዘጠኝ ሚሊዬን ስድስት መቶ ስልሳ አራት ሺህ ብር) ሆኖ የተቀሩት ደግሞ ለሌሎች ግለሰቦች መሆኑንና ይህም አመልካችን ጨምሮ ሌሎች የኩባንያዉ ባለድርሻዎችና አባላት በሐምሌ 17 ቀን 2006 ዓ.ም ባደረጉት ጉባኤና በተያዘዉ ቃለ-ጉባኤ ተረጋግጦ ለሠነዶች ማረጋገጫና ምዝገባ ቀርቦ የተመዘገበ ሲሆን ሠነዱም ለስር ፍ/ቤት በማስረጃነት ቀርቧል። በተጨማሪም ተጠሪ ለአመልካች የብር 14,600,000 (አስራ አራት ሚሊዬን ስድስት መቶ ሺህ ብር) የያዘ ቼክ ለአመልካች አልሰጠም፤ ስለመሰጠቱም የቀረበ ማስረጃ የለም፤ በአመልካችና በተጠሪ መካከል የተደረገ የሒሳብ መተሳሰብ የለም፤ ስለመደረጉም የቀረበዉ ማስረጃ የለም።

3ኛ አመልካች ለ1ኛ ተጠሪ ያስተላለፉትን የአክስዮን ሽያጭ አክፋፈልን በተመለከተ 2ኛ ተጠሪ እንደ ኩባንያ ከመመስረቱ በፊት አመልካች በግል ንግድነት ይዘዉት በነበረዉ በአመልካችና በተጠሪ መካከል የንግድ የግል ግንኙነት (personal relationship) ተመስርቶ የቆየ ሲሆን በዚህን ጊዜ አመልካች የድርጅቱን ፕላንትና ማሽነሪዎች አስይዘዉ ከወጋገን ባንክ አ.ማ ለተበደሩት ብር 8,559,274.40 (ስምንት ሚሊዬን አምስት መቶ ሃምሳ ዘጠኝ ሺህ ሁለት መቶ ሰባ አራት ከ40/100) ለመክፈል ባለመቻላቸዉ ባንኩም በመያዣነት የያዛቸዉን ንብረቶች በሀራጅ ለመሸጥ በሂደት ላይ ስለነበር አመልካች በ1ኛ ተጠሪና በሌሎች አስማሚ ግለሰቦች በጋራ ባደረጉት የማስማማት ሂደት 1ኛ ተጠሪ የአመልካችን የባንክ ዕዳ ሙሉ በሙሉ ከፍሎ ከዕዳዉ ነፃ የሆኑ ሲሆን ወደፊት 2ኛ ተጠሪ የሆነዉ ኩባንያ ሲመሰረት አመልካች ከሚያስተላልፉለት የአክሲዮን ድርሻዎች ሙሉ ወይም ከፊል ዋጋ መክፈያነትም ለባንኩና ከሌሎች ግለሰቦች የነበሩባቸዉና የተከፈሉላቸዉ የዕዳ ገንዘቦች በታሳቢነት እንዲያዝ አስማሚ ሽማግሌዎች በተገኙበት ግራ ቀኙ ተስማምቶ ነበር። 1ኛ ተጠሪ ለዋስትና ዓላማ ለአመልካች የሰጡት ቼኮች ብር 11,450,000 (አስራ አንድ ሚሊዬን አራት መቶ ሀምሳ ሺህ ብር) ነዉ። የተሰጡበትም አግባብ አመልካች በ2ኛ ተጠሪ ዉስጥ ከነበረዉ የአክሲዮን ድርሻዎች ዉስጥ የብር

19,640,000 (አስራ ዘጠኝ ሚሊዬን ስድስት መቶ አርባ ሺህ) ዋጋ ያላቸውን ድርሻዎችን ጁላይ 24/2014 (ሐምሌ 17 ቀን 2006) በተደረገ ቃለ ጉባኤ አማካኝነት ለ1ኛ ተጠሪ በማስተላለፋቸዉ ሲሆን ስምምነቱ ለሠነዶች ማረጋገጫና ምዝገባ ቀርቦ መፈረምና መረጋገጥ ስለነበረበት አመልካች ቀደም ባለዉ ጊዜያት ለነበሩባቸዉ የገንዘብ ዕዳዎች በ1ኛ ተጠሪ የተከፈሉላቸዉና በቼኮች የተከፈሏቸዉ መሆኑን አምነዉ ነበር። ነገር ግን አመልካች ያስተላለፉትን ድርሻ ዋጋ የሚያሟላ በልዩነት ሊኖር የሚችልን ክፍያ ሊሸፍን የሚችልና በ2ኛ ተጠሪ ኩባንያ ስም የወጡ ቼኮች በዋስትና ወይም ለክፍያ መተማመኛነት ካልተሰጠኝ ቃለ-ጉባኤዉ እንዲፈረምና እንዲረጋገጥ አላደርግም ስላሉ ሌሎች ሰዎች በጉዳዩ ገብተዉ እንዲያሸማግሏቸዉ ተደርጎ እነዚሁ ግለሰቦች በተገኙበት የተጠቀሰዉን የብር መጠን የያዙ ሦስት ፖስት ዴትድ ቼኮች በግራ ቀኙ መካከል የሂሳብ ሥራ እስከሚከናወን ድረስ ለባንኩ ቀርቦ ክፍያ እዲፈፀምባቸው ሳይሆን ለክፍያ መተማመኛና ለዋስትና ዓላማ ብቻ ተሰጥቷቸዉ ቼኮቹም አቶ ጌታቸው ተገኔ በተባሉ ግለሰብ እጅ በአደራ እንዲቀመጡ ተደርጓል። የፌ/ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ. 24435 የካቲት 4 ቀን 2000 ዓ.ም በዋለዉ ችሎት ቼክ ለዋስትና ያለ ምንም ፎርማሊቲ ሊሰጥ እንደሚችል በሰጠዉ አስገዳጅ ትርጉም መሰረት ተጠሪ ለአመልካች ሦስቱን ቼኮች መስጠታቸዉ ህገ-ወጥ ሊያሰኛቸዉና ቼክ በዋስትና ሊሰጥ ስለማይችል አመልካች በቼኮቹ ላይ የተመለከተዉ ገንዘብ ሊከፈለኝ ይገባል ለማለት አይችልም። የስር ከፍተኛ ፍ/ቤት በሰጠዉ ዉሳኔ ላይ 1ኛ ተጠሪ በሽያጭ ለተላለፉላቸዉ የብር 19,640,000 (አስራ ዘጠኝ ሚሊዬን ስድስት መቶ አርባ ሺህ ብር) አክሲዮን ድርሻ ዉስጥ ብር 18,526,274.40 (አስራ ስምንት ሚሊዬን አምስት መቶ ሀያ ስድስት ሺህ ሁለት መቶ ሰባ አራት ብር ከ40/100 ሳንቲም) ለአመልካች የከፈሉ ስለመሆኑ የተረጋገጠ ስለሆነ ሦስቱ ቼኮች የተሰጡበት የዋስትና ዓላማ የተሟላና ዋስትናዉ የወረደ በመሆኑ አመልካች በቼኮቹ ላይ የተመለከተዉን ብር 11,450,000 (አስራ አንድ ሚሊዬን አራት መቶ ሀምሳ ሺህ ብር) ይከፈለኝ በማለት በድጋሚ ያቀረቡት ጥያቄ ተቀባይነት የለዉም። ስለሆነም የስር ፍ/ቤቶች ዉሳኔ የሚነቀፍበትና የተፈፀመበት መሰረታዊ የህግ ስህተት የለም በማለትና በማፅናት ያለአግባብ የቀረበዉን የአመልካች አቤቱታና የክፍያ ጥያቄ ዉድቅ በማድረግ ከበቂ የወጪና ኪሳራ ክፍያ ጋር ተጠሪዎችን በነፃ እንዲያሰናብት ጠይቋል።

አመልካች በበኩሉ በየካቲት 4 ቀን 2011 ዓ.ም ባቀረበዉ የመልስ መልስ ላይ በዋናነት አቤቱታቸዉን አጠናክረዉ ተከራክረዋል። በተለይም ተጠሪዎች ከሰበር ችሎቱ ስልጣን አንፃር ላነሱት መቃወሚያ በሰጡት የመ/መልስ ላይ በአመልካችና በተጠሪዎች መካከል ያለዉ አለመግባባትና ለሰበር ሰሚዉ ችሎት ያደረሰን ጉዳይ ቼክ ከተሰጠ በኋላ ለክፍያ ሊከለከል የሚገባበት አግባብ፣ ቼክ ለክፍያ ከተሰጠ በኋላ ወይም ቼክ ከመሰጠቱ በፊት የተፈፀሙ ክፍያዎች ከቼኩ ዋጋ ላይ ይቀነሱ ወይም ይታሰቡ የሚለዉ መሰረታዊ የህግ ትርጉም የሚሻና የሰበር ሰሚዉ ፍ/ቤት ሥልጣን ስር የሚወድቅ ነዉ በማለት ተከራክረዋል። በተጨማሪም ቼክ ለዋስትና የሚሰጥበት አግባብ የህግ ትርጉም የሚያሻዉ ጉዳይ ነዉ። ለሰበር ችሎቱ የቀረበዉ ክርክር እና በአጣሪ ቼሎት የተያዘዉ ጭብጥ ለክርክሩ ምክንያት

የሆኑት ሦስት ቼኮች ለአመልካች ከመሰጠታቸዉ በፊት 1ኛ ተጠሪ ለአመልካች ከፍያለዉ ያላቸዉ ክፍያዎች ወደፊት እንዲከፍሉ ከሰጡዋቸዉ ቼኮች ዋጋ ላይ ሊቀነሱ ይገባል ወይም አይገባም የሚለዉን የህግ መርህ ላይ ጭምር ስለሆነና አመልካችም ከስር ፍ/ቤት ጀምሮ እያቀረበ ያለዉ ክርክር ስለሆነ ተጠሪዎች በዚህ ዙሪያ ያነሱት ክርክር የህግ መሰረት የለዉም በማለት ተከራክሯል።

የጉዳዩ አመጣጥ እና የግራ ቀኙ ክርክር ከላይ የተመለከተዉ ሲሆን ይህ ችሎትም መዝገቡን እንደሚከተለዉ መርምሮታል። እንደመረመረዉም የሰበር አጣሪ ችሎቱ ያስቀርባል በማለት ከተያዘዉ ጭብጥ በተጨማሪ በሰበር ችሎቱ ለተነሱት ክርክሮች እልባት ለመስጠት ከመሰረቱ ምላሽ ማግኘት ያለባቸዉ መሰረታዊ የህግ ክርክሮች (ጭብጦች)፡-

1. *ቼክ ለዋስትና/ ለመያዣነት በሚሰጥበት ጊዜ መሟላት ያለበት በህግ የተቀመጠ ፎርም አለ ወይስ የለም?*
2. *በቼክ ባለዕዳ የሆነ አዉጪ ባለዕዳ የሆነበትን ቼክ ለአምጪዉ ፈርሞ ከሰጠ ወይም ካወጣ በኋላ ቼኩ ከመስጠቱ አስቀድሞ በአምጪዉ ላይ የነበረዉንና ተለይቶ የሚታወቅ ዕዳን ከቼኩ ዋጋ ላይ ሊቀንስ የሚችልበት የህግ አግባብ አለ ወይ? ሂሳብ ከተሳሰቡ በኋላ ክርክር የተነሳበትን ቼክ ፈርሞ በሚሰጥበት ጊዜ አስቀድሞ ለአምጪዉ ላይ የነበሩትን ዕዳዎች ታሰቢ አላደረገም የሚለዉ ክርክር ተቀባይነት ሊኖረዉ ይችላል ወይ? የሚሉት ናቸዉ።*

ይህ ችሎት መዝገቡን መርምሮ እንደተረዳዉ በግራ ቀኙ መካከል የአክሲዮን ሽያጭ ስለመኖሩ፣ ለስር ፍ/ቤት የቀረበዉ የሽያጭ ዉል ሰነድ (በሰነዶች ማረጋገጫና ምዝገባ ቀርቦ የተረጋገጠዉ) የጠቅላላ የአክሲዮን ሽያጭ ዋጋ ብር 24,540,000 (ሀያ አራት ሚሊዬን አምስት መቶ አርባ ሺህ ብር) ስለመሆኑ፣ በአክሲዮን ሽያጩ ላይ የስም ዝዉዉር ከመደረጉ በፊት ከተጠሪዎች የ14,600,000 (አስራ አራት ሚሊዬን ስድስት መቶ ሺህ ብር) ዋጋ ያላቸዉና የተለያዩ የመክፈያ ጊዜ ያላቸዉ ሦስት ቼኮች (ቁጥራቸዉ ከላይ የተገለፀት) ለአመልካች ስለመሰጠታቸዉና እነዚህም ቼኮች የግራ ቀኙ የጋራ ጓደኛ በሆኑት በአቶ ጌታቸዉ ተገኔ እጅ ስለመቀመጣቸዉ፣ የተባሉት ቼኮች የመክፈያቸዉ ጊዜ በተደጋጋሚ ከማለፉ የተነሳ አቶ ጌታቸዉ ተገኔ ቼኮቹን ለአመልካች እንደመለሰ፣ ይህን ተከትሎ 1ኛ ተጠሪ በተለያየ ጊዜ የተወሰኑ ክፍያዎችን በጠቅላላዉ የብር 3,150,000 (ሶስት ሚሊዬን አንድ መቶ ሀምሳ ሺህ ብር) ለአመልካች እንደከፈለ፣ በኋላ ላይ የብር 2,450,000 (ሁለት ሚሊዬን አራት መቶ ሀምሳ ሺህ ብር) ዋጋ ያለዉ ቼክ ቁ. 889784 ከተጠሪ ለአመልካች እንደተሰጠና ጠቅላላ ዋጋቸዉ ብር 11,450,000 (አሥራ አንድ ሚሊዬን አራት መቶ ሀምሳ ሺህ ብር) የሆኑ ሦስት ቼኮች በአመልካች እጅ እያሉ ክፍያ እንዳይፈፀምባቸዉ በ1ኛ ተጠሪ ትዕዛዝ ስለመታገዳቸዉ ከግራ ቀኙ ክርክርና በዚህ ችሎት ትዕዛዝ መሰረት ቀርቦ ከታየዉ የስር ከፍተኛ ፍ/ቤት መዝገብ ለማረጋገጥ ተችሏል። በተጨማሪም ክርክር

የተነሳባቸዉን እነዚህን የ2ኛ ተጠሪ ንብረት የሆኑት ሦስት ቼኮች በ1ኛ ተጠሪ ፈራሚነት ለአመልካች ከመሰጠታቸዉ ቀደም ብሎ አመልካችና 1ኛ ተጠሪ የግል የንግድ ግንኙነት እንደነበራቸዉና የአመልካች የተለያዩ ዕዳዎች በ1ኛ ተጠሪና በ1ኛ ተጠሪ ድርጅት በኩል እንደተፈፀመለት፤ በዚህም ምክንያት የአመልካችና የአቶ ሽፈራ በነበረዉ 2ኛ ተጠሪ ድርጅት ዉስጥ 1ኛ ተጠሪ ድርሻ እንዲኖረዉና በስተመጨረሻም አመልካች የነበረዉን የ50% ድርሻ ሙሉ በሙሉ ከላይ በሰነድ በተረጋገጠዉ ጠቅላላ ዋጋ ለዚሁ 1ኛ ተጠሪ እና በሥር ፍ/ቤት 2ኛና 3ኛ ተከሳሽ ለነበሩት ከመሸጡ የተነሳ 1ኛ ተጠሪ በኩባንያዉ ዉስጥ የላቀ ድርሻ (ወደ 90%) እንዲኖረዉ ማስቻሉንም ከቀረበዉ መዝገብ ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

አሁን ክርክር ሆኖ የተነሳዉ መሰረታዊ ጉዳይ ሦስቱ ቼኮች ለአመልካች ከመሰጠታቸዉ በፊት በ1ኛ ተጠሪና በድርጅቱ አማካኝነት የአመልካች ዕዳዎችን ለመክፈል የተፈፀሙ ክፍያዎችና ለአመልካች የተሰጡ የሦስቱ ቼኮች ጠቅላላ ድምር ዋጋ መካከል ያለዉ ግንኙነት ነዉ፡፡ አመልካች የሚከራከረዉ ቀድሞ የነበሩት ዕዳዎችን በሙሉ ከተሳሰብን በኋላ ከጠቅላላዉ የሽያጭ ዋጋ ላይ ተቀናንሰዉ ቀሪዉ ብር 14,600,000 (አስራ አራት ሚሊዬን ስድስት መቶ ሺህ) ተጠሪዎች በወቅቱ ለመክፈል አቅም ስላልነበራቸዉ በ3 ቼኮች በተለያየ ጊዜ እንዲከፈሉ ተደርጎ ተሰጠኝ በማለት ነዉ፡፡ ይህ ማለት ደግሞ ሂሳብ መተሳሰብ ከተደረገ በኋላ ተጠሪዎች ለአመልካች መስጠት ከነበረበት ከጠቅላላዉ የአክሲዮን ሽያጭ ገንዘብ መጠን ላይ ወደ ብር 9,940,000 (ዘጠኝ ሚሊዬን ዘጠኝ መቶ አርባ ሺህ ብር) የሚሆን የገንዘብ መጠን ቀድሞ ለነበሩት ዕዳዎች ቅናሽ አድርጓል እንደ ማለት ነዉ፡፡

ተጠሪዎች በበኩላቸዉ እየተከራከሩ ያሉት ከአክሲዮን ሽያጩ ዉል በፊት ለአመልካች የተከፈሉ የዕዳ ገንዘብ ስለነበሩ ምንም የሂሳብ መተሳሰብም ሆነ የዕዳ መቀናነስ ሳይኖር እንዲሁ የብር 14,600,000 (አስራ አራት ሚሊዬን ስድስት መቶ ሺህ ብር) ዋጋ ያላቸዉ ሦስት ቼኮች ሂሳብ እስከሚሰራ ድረስ በማለት ለዋስትና ብቻ ለአመልካች ተሰጥቶታል የሚል ነው፡፡ ይህ ማለት ደግሞ ተጠሪዎች ምንም ሂሳብ ሳይሰራ (በቃልም ይሁን በምንም መልኩ) እንዲሁ (በዘፈቀደ ወይም ያለምንም መሰረት) የብር 9,940,000 (ዘጠኝ ሚሊዬን ዘጠኝ መቶ አርባ ሺህ ብር) የገንዘብ መጠን የብር 14,600,000 (አስራ አራት ሚሊዬን ስድስት መቶ ሺህ ብር) ዋጋ ያላቸዉንና የተለያየ የክፍያ ቀን ያላቸዉን ሦስት ቼኮች ለአመልካች ተሰጠ እንደማለት ነዉ፡፡ ይህን ለማድረጋቸዉ እንደምክንያት የጠቀሱት ደግሞ ቀደም ብሎ በመካከላቸዉ የነበረዉ “የንግድ የግል ግንኙነት” ነዉ የሚል ነዉ፡፡ አመልካች ግን ከሽያጭ ዉሉ በፊት የነበሩት ዕዳዎች በሙሉ የተፈፀሙት ቼኮቹ ከመዉጣታቸዉ ቢያንስ ከወራት በፊት መሆኑን በመግለፅ ቼኮቹ የተሰጡትም ቀድሞ የነበሩት ዕዳዎች በሙሉ ከተቀናነሱ በኋላ ነዉ በማለት ይከራከራል፡፡

በእርግጥም የተባሉት የዕዳ ክፍያዎች ከሽያጩና ከቼኮቹ መዉጣት በፊት ስለመሆኑ የስር ፍ/ቤቶች ዉሳኔና ለዚህ ችሎት የቀረበዉ የከፍተኛ ፍ/ቤት መዝገብ ያመለክታል፡፡ የአክሲዮን ሽያጩን

ጠቅላላ የገንዘብ መጠን፣ ከአመልካች የአክሲዮን ሽያጭ ገንዘብ ላይ የተደረገገዉን ቅናሽ፣ የቀድሞ የዕዳዎች ክፍያ ጊዜንና ለአመልካች በእጁ የተሰጡትን የሶስት ቼኮች ዋጋ በአንድ ላይ ወስደን ስንመለከት የሂሳብ መተሳሰብ በግራ ቀኙ መካከል ስለመኖሩና ቼኮቹም የሚያመለክቱት የተጣራ ንፁህ ክፍያ ስለመሆኑ አመልካች በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 259/1/ መሰረት ያለበትን የማስረዳት ሸክም በበቂ ሁኔታ መወጣቱን ያሳያሉ። በተጨማሪም የሁለቱ የጋራ ጓዋደኛ ስለመሆኑ በግራ ቀኙ የተገለፀዉና ክርክር የተነሳባቸዉን የብር 14,600,000 (አስራ አራት ሚሊዬን ስድስት መቶ ሺህ ብር) ዋጋ የነበራቸዉን ሶስት ቼኮችን በስምምነት በአደራ በእርሱ እጅ አስቀምጠዉት የነበረዉ የአቶ ጌታቸዉ ተገኔም የምስክርነት ቃል ይህንኑን ያጠናክራል። በተለይ ይህ ችሎት የስር ከፍተኛ ፍ/ቤትን አስቀርቦ ባደረገዉ ማጣራት ይህ ምስክር በሰጠዉ የምስክርነት ቃል ዉስጥ ሦስቱ ቼኮች ለአመልካች የተሰጡት ቀድሞ የነበሩት ዕዳዎች በሙሉ ከተቀናነሱ በኋላ የተጣራ ክፍያ ስለመሆኑ በማያጠራጥር ሁኔታ መስክረዋል። በተቃራኒዉ የተጠሪዎች የምስክርነት ቃል እርስ በርሱ የሚጣረስ እንደሆነ የቀረበዉ መዝገብ ያመለክታል። በማስረጃ ህግና የማስረጃ ምዘና መርሆዎች መሰረትም ቢታይ በጉዳዩ ዉስጥ በቀጥታ ጥቅም ካላቸዉ ባለጉዳዮች ምስክርነት ቃል ይልቅ የአቶ ጌታቸዉ ተገኔ ምስክር ቃል በግራ ቀኙ ዘንድ ከነበረዉ መልካም ግንኙነት፣ አሜኔታና ሁለቱን ለማግባባት ይጫወት ከነበረዉ ሚና አንፃር ሲታይ የሰጠዉ የምስክርነት ቃል ገለልተኛ፣ ተዓማኒና እዉነትነት ያለዉ ስለመሆኑ ጥርጣሬ ዉስጥ የሚገባ ጉዳይ አይደለም። ይህ ከሆነ ደግሞ የማቻቻል ጥያቄን ያነሱት ተጠሪዎች ለአመልካች ቀድሞ የተከፈሉት ክፍያዎች ከሂሳብ ዉስጥ አለመግባታቸዉን በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 259/2// መሰረት ግልፅና በቂ የሆነ ማስረጃ በማቅረብ ማስረዳት ይገባቸዉ ነበር።

ተጠሪዎች በሰ/መ/ቁ. 24435 ላይ የተሰጠዉን የሰበር ችሎት ዉሳኔን በመጥቀስ ቼክ ያለ ምንም ፎርማሊቲ ለዋስትና መስጠት እንደሚቻል በተሰጠዉ አስገዳጅ የህግ ትርጉም መሰረት ከአመልካች ጋር "የንግድ የግል ግንኙነት" ስለነበረን ቼኮቹን ለዋስትና (ለመያዣ) ተሰጥቶታል በማለትም ተከራክሯል። በተጨማሪም ተጠሪዎች በስር ከፍተኛ ፍ/ቤት ባደረጉት የቃል ክርክር ለ1ኛ ተጠሪና ለሌሎች ሁለት የአክሲዮን ገዢዎች ለተደረገዉ የአክሲዮን ሽያጭ ዋጋ መክፈያነት 4ኛ ተጠሪ ዋስ የመሆን መብቱን ተጠቅሞ ክርክር የተነሳባቸዉን ሦስቱን ቼኮች ለአመልካች ሰጠ እንጂ ለባንክ ቀርቦ ክፍያ እንዲፈፀምባቸዉ አይደለም በማለት ተከራክረዉ እንደነበርም ከቀረበዉ ከከፍተኛ ፍ/ቤቱ መዝገብ ማየት ተችሏል።

ነገር ግን ቼክ ያለምንም ፎርማሊት ለመያዣ ወይም ለዋስትና መስጠት ይቻላል በማለት የሰበር ችሎት ዉሳኔ ሰጥቷል የሚለዉን የተጠሪዎች ክርክር በሚመለከት የተጠቀሰዉ የሰበር ዉሳኔ ዕዳ ከፋይ (ተከሳሽ) በቼክ አምጪ (ከሳሽ) ላይ ዕዳዉን ላለመክፈል ወይም ከዕዳዉ ነፃ ለመሆን ከህግ አንፃር ማቅረብ ስለሚችላቸዉ የመቃወሚያ ዓይነቶችን የሚመለከት ነዉ። በተለይ የሰበር ችሎቱ የን/ህ/ቁ. 717 እና 850ን በመተርጎም ተከሳሽ ከከሳሽ ጋር ከህግ ወይም ከዉል የመነጨ ግንኙነት ከነበራቸዉ እና

ይህም ግንኙነት ዕዳዉን በሙሉ ወይም በከፊል ላለመክፈል ምክንያት የሚሰጠዉ ከሆነ በተጠቀሱት የን/ህጉ ቁጥሮች ድንጋጌ መሰረት መቃወሚያ ለማቅረብ ይችላል በማለት ወስኗል። በዉሳኔዉም ላይ የግል ግንኙነት የሚለዉ ሐረግ የዉል ወይም የህግ መሰረት የሌለዉና ከንግድ ህጉ ዓላማ ያፈነገጠ ዓይነት ተድርጎ ትርጉም ሊሰጠዉ እንደማይገባም አስምሮበታል። አንድ ዕዳ ከፋይ (ተከሳሽ) ከተጠቀሱት የንግድ ህጉ ድንጋጌዎች አንፃር የግል ግንኙነትን መሰረት በማድረግ በአምጪዉ (በባለገንዘቡ) ላይ መቃወሚያ ለማቅረብ በመጀመሪያ የግንኙነቱ መሰረት የሆነውን ዉል ወይም ህግ አቅርቦ ማስረዳት አስፈላጊ ስለመሆኑ የሰበር ችሎቱ አፅኖት የሰጠበት ነጥብ ነዉ።

ተጠሪዎች ካሉት በተቃራኒ የሰበር ችሎቱ በየትኛዉም የዉሳኔ ክፍሉ ወይም ገፅ ላይ ቼክ ያለ ምንም ፎርማሊቲ ለዋስትና ሊሰጥ ይችላል የሚልም ሆነ የግል ግንኙነትን መሰረት በማድረግ ሂሳብ መተሳሰብ ሳያስፈልግ ቼክን ለዋስትና (ለመያዣ) መስጠትና ይህንም ሂሳብ ወደፊት ከሚመነዘረዉ ከቼኩ ዋጋ ላይ ታሳቢ ማድረግ (መቀነስ) ይቻላል የሚል ዉሳኔ አልሰጠም። በመርህ ደረጃ አግባብነት ያለዉ የፍ/ብ/ህጉና የንግድ ህጉ ለቼክ የሰጡት ዋና ዓላማ ለመያዣነት እንዲያገለግል ነዉ ባይባልም እንደማንኛዉም ሊተላለፉ እንደሚችሉ ሰነዶች በመያዣነት ወይም በዋስትና ሊሰጥ እንደሚችልና ይህ በሚሆንበት ጊዜ ግን በንግድ ህጉና በፍ/ብ/ህጉ ላይ በተቀመጡት ግልፅ ድንጋጌዎች መመራት ይኖርበታል (የን/ህ/ቁ 950 ና ፍ/ብ/ህ/ቁ. 2866)። በተለይ የመያዣ ዉል ስምምነት በሚደረግ ጊዜ ዉሉ መከተል ስላለበት ፎርም በተመለከተም በግልፅ የተደነገገ ስለመሆኑ ከን/ህጉ ቁ. 952 እና የፍ/ብ/ህጉ ቁ. 2828 መመልከት ይቻላል።

የመያዣ ወይም የዋስትና ዉል ህጉ በፅሑፍ በሰነድ ካልተደረጉ በህግ ፊት ዋጋ የላቸዉም (ፈራሽ ናቸዉ) በማለት ከደነገጋቸዉ ጥቂት የዉል ዓይነቶች ዉስጥ አንዱ ስለመሆኑ ግልፅ ነዉ (የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1725(ሀ)፤ 1922(1-3)፣ 2828(1-2))። ሌላዉ ደግሞ የመያዣዉ ስምምነት ለምን ግዴታ እንደተደረገ፣ የግዴታዉ መጠን (ከፍተኛ የገንዘብ ወሰን) በጥንቃቄ ግልፅ መደረግ እንዳለበትና ስምምነቱ የተደረገበት ቀን በግልፅ ሊቀመጥ እንደሚገባ ህጉ የግድ ይላል (የፍ/ብ/ህ/አንቀጽ 2828 (1-2)፣ 2864-2866ና የን/ህ/ቁ. 952)። እነዚህ የህጉ አስገዳጅ ድንጋጌዎች ካልተሟሉ የመያዣ ስምምነት ዉል አለ ማለት አይቻልም። ተጠሪዎች ቼኮቹ ለአመልካች የተሰጡት ክፍያ እንዲፈፀምባቸዉ ሳይሆን ለዋስትና (ለመያዣ) ነዉ ይበሉ እንጂ ይህ ስለመሆኑ እነዚህ የህግ ድንጋጌዎች በሚጠይቁት መልኩ ያቀረቡት የመያዣ ዉል ሰነድ የለም። ነገር ግን የሰበር ችሎቱ በሰ/መ/ቁ. 123984 ላይ ቼክ ክፍያ የሚፈፀምበት ወይም የክፍያ ሰነድ እንጂ በራሱ (ብቻዉን) ዉል መኖሩን ለማረጋገጥ የሚዉል ሰነድ አይደለም በማለት አስገዳጅ ዉሳኔ ሰጥቷል። በሌላ አነጋገር ቼክ በመሰጠቱ ብቻ በሁለት ወገኖች ማለትም በአዉጪዉና በአምጪዉ መካከል ዉል (የዋስትናም ይሁን የመያዣ) አለ ለማለት የሚቻልበት የህግ አግባብ የለም ማለት ነዉ (የሰመ/ቁ. 123984 ቅፅ 21 ገፅ 309 - 310)። ባጭሩ ቼክ ያለ ምንም ፎርማሊቲ ለዋስትና (በመያዣ) መስጠት ይቻላል የሚለዉ የተጠሪዎች ክርክር አግባብነት ያላቸዉን

ግልፅ የህግ ድንጋጌዎችንና የተጠቀሰዉን የሰበር ዉሳኔን ያላገናዘበ ስለሆነ ተቀባይነት የለዉም ብለናል። በመሆኑም የስር ፍርድ ቤቶች ቼኮቹን 1ኛ ተጠሪ ለዋስትና (ለመያዣ) የሰጡት ነዉ በማለት የደረሱበት መደምደሚያ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነዉ ብለናል።

ከላይ እንደተገለፀዉ ቼክ በባህሪዉ የተወሰነ ገንዘብ ለመክፈል ሐተታ የሌለበት ትዕዛዝ የያዘ ሆኖ ለከፋዩ (payee) እንደ ቀረበ የሚከፈልበትና ሊተላለፍ የሚችል የገንዘብ መጠየቂያ ሰነድ እንደሆነ ግልፅ ነዉ (ን/ህ/ቁ. 850፣ 827፣ 732፣ 715)። ዋና ዓላማዉም አስተማማኝ፣ የተቀላጠፈና ዉጤታማ የሆነ የግብይት ሥርዓት እንዲኖር ማድረግ እንደሆነ ከቼክ መሰረታዊ ባህርያትና ቼክን መሰረት አድርጎ ለሚከሰቱ ክርክሮች በን/ህግ፣ በፍ/ሥ/ሥ/ህግና በወንጀል ህግ ዉስጥ ከተቀመጡት ድንጋጌዎች መረዳት ይቻላል። ይህ ቢሆንም ግን ለቼኩ መዉጣት ወይም መሰጠት ምክንያት የሆነዉ በከሳሽና በተከሳሽ መካከል የነበረዉ ዉል የግል ግንኙነት ከሆነና በዚህ ረገድ በሁለቱ መካከል ክርክር በሚፈጠርበት ጊዜ እንደኛዉ ወገን የሚያነሳዉን መቃወሚያ ወይም ክርክር መርምሮ ተገቢዉን ዉሳኔ ለመስጠት ክርክር የተነሳበትን ቼክ ለቼኩ መሰረት ከሆነዉ ዉል ወይም ግንኙነት ጋር ማገናዘብ አስፈላጊ ሊሆን ይችላል። ይህ በዋናነት የሚረዳዉ ቼክ የተሰጠዉ ወገን ቼኩ እንዲሰጠዉ ምክንያት የሆነዉ ግንኙነት የጣለበትን ግዴታ ስለመወጣቱና በቼኩ ላይ የተቀመጠዉን መብት ለመጠቀም የሚያስችለዉ ስለመሆኑ ለማረጋገጥና ለተነሳዉም ህጋዊ ተቃዉሞ በህጉ መሰረት እልባት ለመስጠት ነዉ።

አሁን በያዝነዉ ጉዳይ ክርክር ለተነሳባቸዉ ለሦስቱ ቼኮች መዉጣት (ለአመልካች መሰጠት) መሰረቱ የአመልካች በ2ኛ ተጠሪ ዉስጥ የነበረዉን የአክሲዮን ድርሻ መሸጡና ለአክሲዮኖቹም ጠቅላላ ዋጋ መክፈያነት ስለመሆኑ ተረጋግጧል። ባጭሩ ለቼኮቹ መዉጣት መነሻዉ የአክሲዮን ሽያጭ ዉል ሲሆን 4ኛ ተጠሪ በ1ኛ ተጠሪ ፈራሚነት ቼኮቹን የሰጠ ስለመሆኑ ከመጀመሪያ ጀምሮ ካለዉ የግራ ቀኝ ክርክር፣ ከስር ፍ/ቤቶች የዉሳኔ መዝገቦችና ከቀረበዉ የከፍተኛ ፍ/ቤቱ መዝገብ መረዳት ይቻላል። በተጨማሪም ችሎቱ በመጀመሪያ ለአመልካች በቼክ የተሰጠዉ የገንዘብ መጠን ብር 14,600,000 (አሥራ አራት ሚሊዬን ስድስት መቶ ሺህ ብር) ስለመሆኑ ለስር ከፍተኛ ፍ/ቤት ከቀረቡት የቼክ ሰነዶች ማረጋገጥ ተችሏል።

በዚህ ረገድ ከቼክ ህግ ድንጋጌዎች አባባፍ አንፃር ሊሰመርበት የሚገባዉ መርህ ቢኖር የአንድ ቼክ ምንጩ ምንም ይሁን ምን የሚፈጥረዉ መብትና ግዴታ የወደፊት እንጂ ወደኋላ ተመልሶ አለመሆኑን ነው። ይህ ማለት ቼክ የሚያሳየዉ በላዩ ላይ ከተገለፀዉ ቀን ጀምሮ ወደፊት ባሉት የስድስት ወራት የጊዜ ገደብ ዉስጥ መፈፀም ስላለበት የክፍያ መብትና ግዴታ ነው። ከዚህ አንፃር መታየት ያለበት መሰረታዊ ነገር አዉጪዉና አምጪዉ ቼኩ ከመዉጣቱ ቀደም ብሎ በመካከላቸዉ የነበረ ሌላ የግል ግንኙነት (other antecedent personal relations) አለ ቢባል ለቼኩ ገንዘብ ባለዕዳ የሆነዉ አዉጪ በቼኩ ላይ ባለገንዘብ ከሆነዉ አምጪ ላይ ቼኩን ከመስጠቱ በፊት የነበረዉን የዕዳ ገንዘብ ታሳቢ ሳያደርግ ወይም ሳይቀናንስ (ቼኩን ያወጣዉ እራሱ እስከሆነ ድረስ ማለት ነዉ) ቼኩን

ለአሁን ባለገንዘቡ ለቀድሞ ባለዕዳው ፈርሞ ይሰጣል ብሎ መገመት ከአንድ ምክንያታዊ ከሆነ የነጋዴ ባህሪ (reasonable business person) ወይም አስተሳሰብ ጋር በፍፁም ሊታረቅ የሚችል አይደለም። አድርጎ ቢገኝም በራሱ ፈቃድ ወይም ችልተኝነት እራሱን ለኪሳራ (risk) እንዳጋለጠ ይቆጠራል። በሁለቱ መካከል ያለው ቅርበት ይህን ሊፈጥር ይችላል እንኳን እንዳይባል በሽያጭ ገንዘቡም ጠቅላላ ዋጋም ሆነ በአክሲዮኖቹ የስም ዝውውር ወቅት በመካከላቸው አለመግባባት (ጭቅጭቆች) ተፈጥሮ እንደነበርና አስታራቂ ግለሰቦች በሁለቱ መካከል መግባት አስፈላጊ ሆኖ እንደነበር ከክርክራቸውም ሆነ ከስር ፍ/ቤቶች ውሳኔዎች ላይ በግልፅ መረዳት ይቻላል። እንደዚህ ዓይነት ሁኔታዎች ደግሞ የቼኩ ፈራሚ የሆነው 1ኛ ተጠሪ ከአመልካች ላይ የሚጠይቅ የዕዳ ገንዘብ ካለው ቆም ብሎ በጥንቃቄ እንዲያስብ ሊያደርጉት የሚችሉ ሁኔታዎች ስለመሆናቸው አያከራክርም። ከዚህ በተጨማሪም የሽያጭ ውሉ በሚፈፀምበትና ቼኮቹ በራሱ በ1ኛ ተጠሪ በሚፈረሙበት ጊዜ ለአመልካች ከፍያለው ያላቸው የተለያዩ የገንዘብ መጠኖች በግልፅ ተለይተው የሚታወቁ ስለመሆናቸውም ክርክር የለም። ወደፊት የተፈፀሙ ቢሆን እንኳን ተጠሪ ያቀረባቸው የማቻቻል መከራከሪያዎች ከላይ ከተጠቀሱት ድንጋጌዎች አኳያ ሚዛን ሊደፉ ይችሉ ነበር። እንዳንዱ ክፍያዎች እንዲያዉም የተፈጸሙት በ1ኛ ተጠሪ ሳይሆን 1ኛ ተጠሪ ባለአክሲዮን በሆነበት ኩባንያ ነው። ስለሆነም ከቼኮቹ መዉጣት አስቀድሞ ለአመልካች ዕዳዎች ተፈፅሟል የተባሉት ክፍያዎች ለአመልካች ከተሰጡት ቼኮች ላይ ታሳቢ ሊደረጉ/ሊቀናነሱ ይገባል መባሉ ምንም የህግ መሰረት የለዉም፤ ከላይ ከተጠቀሱት የቼክ ባህሪያትና የቼክ ህግ ድንጋጌዎች አንፃርም ሲታይ መሰረታዊ ስህተት ነው። በህጉ አግባብ መሆን የነበረበት ከቼኮቹ መዉጣት (ከአክሲዮን ሽያጩ ስምምነት) ቀን በኋላ የነበሩትን ክፍያዎች ታሰቢ ማድረግ ብቻ ነው።

ከላይ የተደረሰበት ውሳኔ እና የተሰጡት ዝርዝር ምክንያቶች እንደተጠበቁ ሆኖ ጉዳዩን ከሌላ አቅጣጫም መመልከት ይቻላል። የቀረበው አቤቱታ እንደሚያሳየው የአመልካች የዳኝነት ጥያቄ በአክሲዮን ሽያጭ ውሉ መሰረት ያልተከፈለው ቀሪ ገንዘብ መኖሩን በመጥቀስ ነው። ተጠሪዎች/1ኛ ተጠሪ የሽያጭ ውሉ መኖሩን ሳይክድ የተባለው ገንዘብ ተከፍሏል በማለት አዉንታዊ መንገድ (affirmatively) ተከራክሯል። ስለዚህ 1ኛ ተጠሪ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 259(1) በሚያዘዉ አግባብ መሰረት በክሱ ላይ የተመለከተዉን ቀሪ ገንዘብ ስለመክፈሉ በቅድሚያ የማስረዳት ሸክም/ ግዴታ አለበት። 1ኛ ተጠሪ ቀሪ ገንዘቡ ተከፍሏል ብሎ የሚከራከረው ለአመልካች የተሰጠው ቼክ በዋስትና ሆኖ ቀሪ ገንዘቡ በሌላ ዕዳ የተሰጠው መሆኑን በመግለጽ ቢሆንም ከላይ በተሰጠው ውሳኔ ላይ ተመለከተው ምክንያት ክርክሩ ተቀባይነት አላገኘም። በሌላ በኩል አመልካች ከክሱ ጋር አያይዞ ያቀረባቸው ቼኮች (ከላይ በተመለከተው መሰረት በዋስትና አለመሰጠታቸው ስለተረጋገጠ) በተጠሪዎች ላይ ያልተከፈለ ዕዳ ስለመኖሩ የሚያስረዱ መሆናቸዉን ያሳያሉ።

በዚሁ መሰረት ቼኮቹ ከተቆረጡ (ከወጡ) ቀን አንስቶ ባሉት ጊዜያት ውስጥ ለአመልካች በተጠሪዎች ስለተከፈሉት የገንዘብ መጠን በተመለከተ ችሎቱ የስር ከፍተኛ ፍ/ቤት መዝገብ አስቀርቦ

አጣርቷል። ባደረገውም ማጣራት በሐምሌ 17 ቀን 2006 ዓ.ም የአክሲዮን ሽያጭ ከተደረገ በኃላ ለአመልካች ስለተከፈሉት ክፍያዎች የሚያሳዩት የቼክ ቁጥሮች ሲኦ 889783፣ ኦፍ 001225151፣ ሲኦ 775082 እና ቢኤ 794240 እና የፍ/ቤት የአፈፃፀም ትዕዛዝ ሲሆኑ ጠቅላላ ድምራቸው ደግሞ ብር 3.55 ሚሊዬን መሆኑን መዝገቡ ያሳያል። ቁጥሩ ቢኤ 794240 ሰለሆነውና የብር 400 ሺህ ዋጋ ስላለውና በጥቅምት 10 ቀን 2007 ስለተመነዘረው ቼክ በተመለከተ ግን አመልካች ክርክር የተነሳባቸው ሦስቱ ቼኮች ከመሰጠታቸው በፊት የተፃፉና የተሰጡ ናቸው በማለት ተከራክሯል። ሆኖም ግን ክርክር የተነሳባቸው ቼኮች የአክሲዮን ሽያጭና ዝውውር በተደረገው ቀን የተሰጡ ናቸው ከተባለና ይህ ቼክ ደግሞ የተመነዘረው ከዚህን ቀን በኋላ ከሆነና የተከፈለበት ሌላ አሳማኝ ምክንያት ስለመኖሩ በአለመልካች በኩል የቀረበ ነገር ስለሌለ በዚህ ረገድ የአመልካችን ክርክር አልተቀበልነውም። ይህ ከሆነ ደግሞ ክርክር ከተነሳባቸው ቼኮች ዋጋ ላይ ለአመልካች መከፈል የነበረበት ቀሪ ገንዘብ ብር 11.05 ሚሊዬን ይሆናል ማለት ነዉ።

ባጠቃላይ ከላይ ከተዘረዘሩት ምክንያቶች የተነሳ በስር ፍ/ቤቶች ክርክር ከተነሳባቸው ሦስቱ ቼኮች መዉጣት (ከአክሲዮን ሽያጩ ስምምነት) ቀን ቀድሞ ብሎ የነበሩት የዕዳ ክፍያዎች ከቼኮቹ ዋጋ ላይ ሊታሰቡ (ሊቀነሱ) ይገባል በማለት የሰጡት ዉሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ነዉ ብለናል። ስለሆነም የሚከተለዉ ዉሳኔ ተሰጥቷል።

ዉሳኔ

ሀ) የፌ/ጠ/ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁ. 158393 በመስከረም 23 ቀን 2010 ዓ.ም በዋለዉ ችሎት የሰጠዉ ዉሳኔና የፌ/ከፍ/ፍ/ቤት በመ/ቁ. 162264 በመጋቢት 13 ቀን 2010 ዓ.ም በዋለዉ ችሎት የሰጠዉ ዉሳኔ በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 348(1) መሰረት ተሽሯል።

ለ) ተጠሪዎች ለአመልካች ብር 11,050,000 (አስራ አንድ ሚሊዬን ሀምሳ ሺህ ብር) በአንድነትና በነጠላ ክሱ በስር ከፍተኛ ፍ/ቤት ተሻሽሎ ከቀረበበት ቀን አንስቶ የሚታሰብ ህጋዊ ወለድ (9%) ጋር ይክፈሉ።

ሐ) ተጠሪዎች የጠበቃ አበል የብር 11,050,000 (አስራ አንድ ሚሊዮን ሀምሳ ሺህ ብር) 5% (አምስት ፐርሰንት) በአንድነትና በነጠላ ለአመልካች ይክፈሉ።

መ/ ሌሎች ወጪዎችና ኪሳራን ግራ ቀኙ ራሳቸዉን ይቻሉ።

ትዕዛዝ

- **የፌ/ከፍ/ፍ/ቤት መ/ቁ. 162264 ለፍ/ቤቱ ይመለስ።**
- ***መዝገቡ ተዘግቷል።***

የሰ.መ.ቁ.153867

ሐምሌ 27 ቀን 2010 ዓ.ም

ዳኞች፡ 1. ተክሊት ይመሰል

2. ተፈሪ ገብሩ (ዶ/ር)

3. ቀነዓ ቂጣታ

4. ተሾመ ሽፈራው

5. አብዬ ካሳሁን

አመልካች፡.....ዓባይ ባንክ አ.ማ - ነ/ፈጅ አቶ እንዳክመው ጌትነት - ቀርበዋል

ተጠሪ፡.....ዶ/ር ታርቆ አለነ - ቀርበዋል

ይህ መዝገብ ተመርምሮ የሚከተለዉ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ይህ ጉዳይ የተጀመረዉ በሰሜን ጎንደር መስተዳድር ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ሲሆን፣ የአሁን አመልካች ተከሳሽ፣ የአሁን ተጠሪ ደግሞ ከሳሽ ሆኖ ሲከራከሩ ነበር፡፡ ጉዳዩ ለዚህ ችሎት ሊቀርብ የቻለዉ የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ.ቁ.149867 በ05/04/2010 ዓ.ም የሰጠዉ ትዕዛዝ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ እንዲታረምልን በማለት አመልካች ያቀረበዉን የሰበር አቤቱታ መርምሮ ዉሳኔ ለመስጠት ነዉ፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ሲታይ ከሳሽ (የአሁን ተጠሪ ባቀረበዉ ክስ ከሳሽ እና ተከሳሽ ባንክ መካከል በተደረገዉ የብድር ዉል መሻሻት በጎንደር ከተማ አዘዞ ድማዛ ክ/ከተማ ኤም.ቲ.ማይ አቢሲኒያ ቲችንግ ኮሌጅ የሚገኘዉን ንብረትነቱ የከሳሽ የሆነዉን በመያዣነት የያዘዉን ተከሳሽ በሕጉ አግባብ ማስጠንቀቂያ ሳይሰጠኝ በጨረታ ሽጦ፣ በመያዣነት ያልያዘዉን ሆስፒታል አስረክብ እያለ ስለሆነ፣ ጨረታዉን ሲያወጣዉ ሕጉ የጣለበትን ስርዓት ስላልተከተለ ጨረታዉ ፈርሶ ሆስፒታሉን ከበቂ ኪሳራ ጋር ይከፈለን በማለት ክሷል፡፡

በዚህ ክስ ላይ ተከሳሽ ባቀረበዉ የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ እና አማራጭ መልስ፡ ፍ/ቤቱ ይህን ክርክር ለማየት ስልጣን የለዉም፣ በአዋጅ ቁጥር 97/90 መሰረት ፍ/ቤት በመያዣነት የተሸጠዉን ንብረት የሚመለከት የማየት ስልጣን የለዉም፣ ከሳሽ በብድር ዉሉ መሰረት ዕዳዉን በጊዜ ሳይከፍል በመቅረቱ ተከሳሽ ለከሳሽ ጨረታዉ ከመዉጣቱ በፊት የ30 ቀን ማስጠንቀቂያ በመስጠት በአዲስ ዘመን ጋዜጣ ጨረታ አዉጥቶ ጨረታዉ የፍትሓ ብሔር ስነ ስርዓት ሕጉን ተክትሎ የሸጠ በመሆኑ፣ ሆስፒታሉም የመያዣዉ አካል በመሆኑ በሕጉ አግባብ የተሸጠ ስለሆነ በከሳሽ የደረሰዉ ምንም ጥፋት የለም በማለት ተከራክሯል፡፡

ከዚህ በኋላ ፍ/ቤቱ የሰዉ ምስክሮች በመስማት እና የሰነድ ማስረጃ በመመዘን በሰጠዉ ዉሳኔ በከሳሽ እና በተከሳሽ መካከል በተደረገዉ የመያዣ ዉል በመያዣነት የተያዘዉ ኮሌጁ ቢሆንም ሆስፒታሉ

በመያዣነት የተያዛ ባይሆንም በመያዣ በተያዘዉ ንብረት ይዞታ ላይ የተሰራ መሆኑን በሰዉ ምስክሮች እና በክፍሉ ክ/ከተማ የተረጋገጠ በመሆኑ፣ ሆስፒታሉ በፍ/ብ/ሕ/ቁ.3066 መሰረት የመያዣ አካል ስለሆነ ተከሳሽ ይህን ሆስፒታል መሸጡ በመያዣነት ያልተያዘ ንብረት ሽጧል የሚያስብል አይደለም፣ ሆስፒታሉ በመያዣዉ ስለሚጠቃለል ይህን ንብረት መሸጥ ሕግን የተከተለ ነዉ፤ የጨረታ ሂደቱን በተመለከተ ተከሳሽ ለከሳሽ የ30 ቀን ማስጠንቀቂያ ሳይሰጠዉ ንብረቱ በጨረታ የተሸጠ ስለሆነ የጨረታዉ ሂደት የስነ ስርዓት ሕጉን እና አዋጅ ቁጥር 97/90 አንቀጽ 6 መሰረት ያላደረገ ነዉ፤ ነገር ግን ጨረታዉ ስርዓትን አልተከተለም በሚል ምክንያት እንዲሰረዝ የሚቀርብ ዳኝነት ፍ/ቤት የማየት ስልጣን የለዉም፣ ጨረታዉ በሥርዓት ባለመካሄዱ የንብረቱ ባለቤት ጉዳት የደረሰበት እንደሆነ ግን ካሳ መጠየቅ እንደሚችል በአዋጅ ቁጥር 97/90 ሥር ተመልክቷል፤ ከሳሽ በዚህ ምክንያት ጉዳት ደርሶብኛል የሚል ከሆነ ኪሳራ (ካሳ) በሌላ መዝገብ ዳኝነት ከፍሎ መጠየቅ ይችላል በማለት ወስኗል፡፡

የሥር ከሳሽ በዚህ ዉሳኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለአማራ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ያቀረበ ሲሆን ፍ/ቤት ግራ ቀኞቸዉን በማከራከር በሰጠዉ ዉሳኔ መልስ ሰጪዉ ጨረታዉን የፍትሓ ብሔር ሥነሥርዓት ሕጉ እና በአዋጅ ቁጥር 97/90 አንቀጽ 3 እና 6 መሰረት ያልተደረገ በመሆኑ፣ ጨረታዉ በሕጉ አግባብ ያልተፈጸመ በመሆኑ፣ መልስ ሰጪን ጨረታ ሰረዘነዋል ቀሪ አደርገነዋል፤ መልስ ሰጪዉ በመያዣነት የያዘዉን የይግባኝ ባይ ንብረት በሕጉ አግባብ በግለጽ ሁኔታ ጨረታ አዉጥቶ የመሸጥ መብት አለዉ በማለት የሥር ዉሳኔ በመሻር ወስኗል፡፡ የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የቀረበለትን ይግባኝ ማመልከቻ ዉድቅ በማድረግ የሥር ዉሳኔ በማጽናት ወስኗል፡፡ የአሁን የሰበር አቤቱታ የቀረበዉ በዚህ ዉሳኔ ቅር በመሰኘት ለማስለወጥ ነዉ፡፡

የአሁን አመልካች የካቲት 12 ቀን 2010 ዓ.ም በተጻፈ ስድስት ገጽ የሰበር አቤቱታ፡ የአሁን ተጠሪ ባቀረበዉ ክስ አመልካች በመያዣነት የያዘዉን ንብረት ሲሸጥ ጨረታዉ ሕጉን ያልተከተለ በመሆኑ ሐራጁ እንዲሰረዝልኝ/እንዲፈርስልኝ በማለት የጠየቀዉን ዳኝነት መደበኛዉ ፍ/ቤት የማየት ስልጣን የሌለዉ ሆኖ ሳለ፣ የሐራጅ ሽያጭ የተደረገዉ በፍትሓ ብሔር ሕጉ እና በአዋጅ ቁጥር 97/90 መሰረት የተፈጸመ ስለሆነ፣ የሥር ጠቅላይ ፍ/ቤት የሰጠዉ ዉሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ እንዲታረምልን በማለት በዝርዝር አመልክቷል፡፡

ይህ ችሎት የሰበር አቤቱታዉ ያስቀርባል በማለት ተጠሪ መልስ እንዲሰጥ ባዘዘዉ መሰረት ግንቦት 3 ቀን 2010 ዓ.ም የተጻፈ አራት ገጽ መልስ አቅርቧል፡፡ የመልሱም ይዘት በአጭሩ፡ በዚህ ጉዳይ የሥረ ጠቅላይ ፍ/ቤት የሰጠዉ ዉሳኔ በአግባቡ ስለሆነ አመልካች ያቀረበዉ ቅሬታ የሕግ ምክንያት የሌለዉ ስለሆነ ዉድቅ እንዲደረግልኝ በማለት በዝርዝር ተከራክሯል፡፡ የአሁን አመልካች የመልስ መልስ አቅርቧል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ከፍ ሲል የተመለከተዉ ሲሆን ይህ ችሎት የግራ ቀኞቸዉን ክርክር አግባብነት ካላቸዉ የህግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ እንዲሁም የአሁን አመልካች በመያዣነት የያዘዉን ንብረት በጨረታ የሸጠዉ ሕጉን ባልተከተለ ስርዓት በመሆኑ ጨረታዉ እንዲሰረዝልኝ በማለት የአሁን ተጠሪ የጠየቀዉን

ዳኝነት መደበኛዉ ፍ/ቤት የማየት ስልጣን አለዉ ወይስ የለዉም? የሚለዉን ነጥብ እንደጭብጥ በመያዝ እንደሚከተለዉ መርምሮታል፡፡ እንደመረመርነዉ በአመልካች እና በተጠሪ መካከል በነበረዉ የመያዣ ዉል መነሻነት የአሁን ተጠሪ ኤም.ቲ.ማይ አቢሲኒያ ቲችንግ ኮሌጅ በመያዣነት አመልካች እንዲይዝ በማድረግ ገንዘብ ከአመልካች ተበድሮ የነበረ መሆኑን የሥር ፍ/ቤት ዉሳኔ ያሳያል፡፡ ሌላዉ የአሁን ተጠሪ በመያዣነት በያዘዉ ኮልጅ ባረፈዉ ይዞታ ላይ ሆስፒታል የሰራ መሆኑን የሰዉ ምስክሮች እና በአዘዞ ድማዞ ክ/ከተማ የተረጋገጠ በመሆኑ፣ የሥር ከፍተኛ ፍ/ቤት ሆስፒታሉ በፍ/ብ/ሕ/ቁ.3066 መሰረት የመያዣ አካል እንደሆነ በፍሬ ነገር ደረጃ ያረጋገጠዉ ጉዳይ ነዉ፡፡ ስለሆነም ይህ ሆስፒታል የመያዣዉ አካል እንደሆነ ስለተረጋገጠ በዚህ ረገድ ይህ ችሎት በሥር ፍ/ቤት የተረጋገጠዉን ፍሬ ነገር የሚቀበለዉ ይሆናል፡፡

በሌላ በኩል መታየት ያለበት ጉዳይ አመልካች ያካሄደዉ የጨረታ ሂደትን የሚመለከት ነዉ፡፡ በዚህ ረገድ የሥር ፍ/ቤቶች ፍሬ ነገርን የማጣራትና ማስረጃ የመመዘን በተሰጣቸዉ ስልጣን የአሁን አመልካች በመያዣነት የያዘዉን የተጠሪን ንብረት በጨረታ ሲሸጥ የፍትሓ ብሔር ሥነ ሥርዓት ሕጉን እና በአዋጅ ቁጥር 97/90 አንቀጽ 3 እና 6 ሥር የተመለከተዉን ሂደት ያልተከተለ እንደነበር በማረጋገጥ ዉሳኔ ሰጥቷል፡፡ የአሁን አመልካች ይህን ነጥብ በተመለከተ የሥር የከፍተኛ ፍ/ቤት ዉሳኔ በመቃወም ይግባኝ ለአማራ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ያቀረበ መሆኑን የሚያመለክት ነገር ስለሌለ፣ በዚህ አግባብ ይግባኝ ባላቀረበበት ጉዳይ አመልካች ለዚህ ችሎት የሚያቀረበዉ ቅሬታ ተቀባይነት የለዉም፡፡ በመሆኑም የአሁን አመልካች በመያዣ የያዘዉን ንብረት የሸጠበት ሂደት የሕጉን ሂደት ያልተከተለ ነዉ ተብሎ በሥር ፍ/ቤት የተደረሰበት ድምዳሜ ይህ ችሎት ከሚቀበለዉ በስተቀር የሚያርምበት አግባብ የለም ብለናል፡፡

በመቀጠል መታየት ያለበት ጉዳይ የአመልካች ባንክ በመያዣ የያዛቸዉን ንብረት ለመሸጥ በአዋጅ ቁጥር 97/90 መሰረት ለሚፈጽመዉ የሐራጅ ሽያጭ እንዲፈርስልኝ በማለት የሚቀርበዉን የዳኝነት ጥያቄ መደበኛዉ ፍ/ቤት የማየት ስልጣን አለዉ ወይስ የለዉም? የሚለዉን ነጥብ ነዉ፡፡ ከፍ ሲል እንደተመለከተዉ ይህ ጉዳይ የአሁን አመልካች በመያዣያነት የያዘዉን የተጠሪን የማይንቀሳቀስ ንብረት በሐራጅ ከመሸጥ ጋር የሚያያዝ መሆኑ ግልጽ ነዉ፡፡ በመሆኑም ለዚህ ጉዳይ አግባብነት ያለዉ ሕግ ‹‹በባንክ በመያዣ ስለተያዘ ንብረት የወጣ አዋጅ ቁጥር 97/90›› እንደሆነ የሚያከራክር ጉዳይ አይደለም፡፡ በዚህ አዋጅ መሰረት ባንክ በመያዣነት የያዘዉን ንብረት ለመሸጥ ያለዉ ስልጣን፣ ከዚህ ሽያጭ ጋር በተያያዘ መደበኛ ፍ/ቤት ያለዉ ስልጣን፣ በዚህ አዋጅ አግባብ ለተፈጸመ የሐራጅ ሽያጭ ጋር በተያያዘ በምን አግባብ ለመደበኛ ፍ/ቤት ጉዳዩ ሊቀርብ እንደሚችል ሁኔታ መታየት ያለባቸዉ ነጥቦች ናቸዉ፡፡

የዚህ አዋጅ ዓላማ ከአዋጁ መግቢያ /preamble/ መገንዘብ የሚቻል ሲሆን፣ በመግቢያዉ እንደተመለከተዉ ባንኮች በመያዣ የያዙትን ንብረቶች ለመሸጥ መደበኛ ሥነ ሥርዓት ተክትሎ ለመደበኛ ፍ/ቤት ክስ አቅርቦ ለማስወሰንና ዉሳኔዉን ለማስፈጸም ረጅም ጊዜ በመዉሰዱ፤ ባንኮች ገንዘብ

አበድረዉ ወለድ በመሰብሰብ ገቢ የማግኘት ሥራቸዉ ላይ ከፍተኛ ተጽዕኖ በማሳደሩ፣ ባንኮች የሚሰጡትን ብድሮች በተቀላጠፈ መንገድ መሰብሰብ እንዲችሉ ምቹ ሁኔታ ለመፍጠር አዋጁ ማስፈለጉን ያስገነዝባል፡፡ ከዚህም በላይ በአዋጁ አንቀጽ 3 እና 4 እንደተመለከተዉ ባንኮች በመያዣነት የያዙአቸዉን ንብረቶች ተፈላጊዉ ዕዳ ያልተከፈለ እንደሆነ በድንጋጌዎቹ የተመለከተዉን ሥርዓት ተከትሎ ንብረቶቹን በሐራጅ የመሸጥ እና ለገዢዉ ባለቤትነቱን የማዛወር እና ሁለት ጊዜ ሐራጅ ወጥቶ ያልተሸጠ እንደሆነ ንብረቱን በመያዣ ስምምነቱ ላይ በተመለከተዉ ግምት መዉሰድ እንደሚችሉ እና ወደ ስመ ለማዛወር ስልጣኑ የባንኮች እንደሆነ ማየት ይቻላል፡፡ ባንክ ይህን የሐራጅ ሽያጭ ሲያካሄድ እንደአግባብነቱ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.394--449 ተፈጻሚ ማድረግ እንደሚችል በአዋጁ አንቀጽ 6 ሥር ተመልክቷል፡፡ ከዚህ ሁሉ መገንዘብ እንደሚቻለዉ ባንክ ለዕዳ በመያዣ የያዘዉን ንብረት በሐራጅ በመሸጥ ዋናዉን ገንዘብ እና ወለድ ለመሰብሰብ ለሚያካሄደዉ የሐራጅ ሽያጭ ሂደት ጋር በተያያዘ ስልጣኑ የባንኩ መሆኑን እና መደበኛ ፍ/ቤት ጉዳዩን ማየት እንደማይችል ነዉ፡፡ መደበኛ ፍ/ቤት ባንክ ያካሄደዉ የሐራጅ ሽያጭ በአግባብ ነዉ ወይስ አይደለም? የሐራጅ ሽያጩ ሊፈርስ ይገባል ወይስ አይገባም? የሚሉትን ነጥቦች አይቶ ለመወሰን ስልጣን እንደሌለዉ የሚያስገነዝብ ነዉ፡፡ መደበኛ ፍ/ቤቶች እነዚህን ነጥቦች በማየት የሐራጅ ሽያጩ የተካሄደዉ በአግባብ ነዉ ወይስ አይደለም? በዚህ ምክንያት ሽያጩ ሊፈርስ ይገባል ወይስ አይገባም? የሚሉትን በመመርመር የሚወስኑ ከሆኑ ከላይ የተመለከተዉን የአዋጁን ዓላማ ሙሉ በሙሉ ዋጋ ሚያሳጣ እና የአዋጁንም ተፈጻሚነት የሚገድብ እንደሆነ መገንዘብ ያስፈልጋል፡፡ በመሆኑም ሕግ አዉጭዉ ባንክ በመያዣ የያዘዉን ንብረት በሐራጅ በመሸጥ ያበደረዉን ገንዘብ መሰብሰብ እንዲችል በአዋጁ የተዘረጋዉን ሥርዓት መደበኛ ፍ/ቤቶች በማክበር ተፈጻሚ ማድረግ ይገባቸዋል እንጂ አዋጁ ለባንክ የሰጠዉን ስልጣን በመንጠቅ ጉዳዩን የማየት ስልጣን አለን በማለት የአዋጁን ዓላማ ዋጋ ማሳጣት የለባቸዉም፡፡ ስለሆነም መደበኛ ፍ/ቤት አንድ ባለዕዳ የሐራጅ ሽያጭ ያለ አግባብ የተደረገ ስለሆነ እንዲፈርስልኝ ወይም እንዲሰረዝልኝ በማለት የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.445 በመጥቀስ ያቀረበዉን ክስ በመቀበል ክርክር በማካሄድ ዉሳኔ በመስጠት አዋጁ የወጣበትን ዓላማ ዋጋ ማሳጣት የለበትም፡፡

በሌላ በኩል ባለዕዳዉ የሐራጅ ሽያጭ በአግባቡ አልተደረገም የሚል ከሆነ በዚህ ምክንያት የደረሰበትን ጉዳት ለይቶ ክስ ማቅረብ እንዳለበት አዋጁ ያሳያል፡፡ የአዋጁ አንቀጽ 7 ስለባንክ ተጠያቂነት ሲደነግግ ‹‹ባንክ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 6 የተጠቀሱትን አግባብ ያላቸዉን ድንጋጌዎች በመተላለፍ ሽያጩን በመፈጸሙ በባለዕዳዉ ላይ ለሚደርሰዉ ጉዳት በኃላፊነት ተጠያቂ ይሆናል›› በማለት ይደነግጋል፡፡ የእንግሊዝኛዉ ቅጅ Liability of of the Bank በማለት <<The Bank shall be liable for any damage it causes to the debtor in the process of selling by auction in violation of the relevant provisions of the civil procedure code specified under Article 6 of this Proclamation>> በማለት ይደነግጋል፡፡ ከዚህ ድንጋጌ መገንዘብ እንደሚቻለዉ አንድ ባለዕዳ ከሐራጅ ሽያጭ ጋር በተያያዘ ጉዳዩን ለመደበኛ ፍ/ቤት ማቅረብ የሚችለዉ የሐራጅ ሽያጩ ያለ አግባብ ከሕግ ዉጭ የተደረገ ነዉ የሚል ከሆነ፣ በዚህ

ምክንያት የደረሰበት ጉዳት ካለ አግባብነት ባለዉ ማስረጃ በማስደገፍ ክስ አቅርቦ ካሳ እንዲከፈለዉ ዳኝነት ከመጠየቅ ዉጭ የሐራጅ ሽያጩ እንዲፈርስ ወይም እንዲሰረዝለት የሚጠይቅበት የሕግ አግባብ የለም፡፡ በዚህ ድንጋጌ መሰረት ደረሰብኝ የሚለዉን ካሳ አግባብነት ባለዉ ማስረጃ በማስደገፍ ስልጣን ላለዉ መደበኛ ፍ/ቤት አቅርቦ ከመጠየቅ በስተቀር ሐራጁ እንዲፈርስ ክስ ማቅረብ አይችልም፡፡ በመሆኑም መደበኛ ፍ/ቤት በዚህ አዋጅ አግባብ የሚቀርብ ክስ የካሳን ጥያቄ የሚመለከት ካልሆነ በስተቀር ጨረታ እንዲፈርስ በማለት የሚቀርበዉን ክስ ተቀብሎ ግራ ቀኞቸዉን አከራክሮ ተገቢ የሆነ ዉሳኔ ለመስጠት ስልጣን የለዉም፡፡

ይህን አዋጅ መሰረት በማድረግ ባንክ ያካሄደዉ ሐራጅ እንዲፈርስ የሚል ክስ የቀረበ እንደሆነ፣ ፍ/ቤት የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.9 /1/ እና 231 መሰረት ክሱን ተቀባይነት የለዉም በማለት ለባለጉዳዩ መመለስ ይጠበቅበታል፡፡ ነገር ግን ፍ/ቤቱ ክሱን ተቀብሎም ቢሆን ጉዳዩን ለማየት የሥረ ነገር ስልጣን የሌለዉ በመሆኑ፣ በሌላ ተከራከሪ ወገን መቃወሚያ ቢቀርብም ባይቀርብም፣ ፍ/ቤቱ ይህን ጉዳይ ለማየት ስልጣን እንደሌለዉ በተገነዘበ ጊዜ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.244 /2/ /ሀ/ እና 245 /2/ መሰረት ክሱን ዉድቅ በማድረግ መዝገቡን መዝጋት አለበት፡፡

በዚህ መሰረት አሁን የተያዘዉ ጉዳይ ሲታይ የአሁን ተጠሪ አመልካች ያካሄደዉ ጨረታ ሂደቱን ያልተከተለ ስለሆነ ጨረታዉ እንዲፈርስልኝ በማለት በመደበኛ ፍ/ቤት ዳኝነት የማቅረብ መብት የለዉም፣ ተጠሪ ክስ ቢያቀርብም አመልካች ባቀረበዉ መቃወሚያ መሰረት ይህን ነጥብ በተመለከተ ግራ ቀኞቸዉን አከራክሮ ለመወሰን የሥረ ነገር ስልጣን የለኝም በማለት በዚህ ረገድ የተጠሪን የዳኝነት ጥያቄ ዉድቅ ማድረግ ሲገባዉ የሥር የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት የሰጠዉ ዉሳኔ እና የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይህን ዉሳኔ ሳያርመዉ በትዕዛዝ በማጽናት መወሰኑ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ነዉ፡፡

ሲጠቃለል የሥር የክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት እና የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት አመልካች በመያዣ የያዘዉን ንብረት በተመለከተ ያካሄዉ ጨረታ የሕጉን ሂደት ያልተከተለ ነዉ በማለት ጨረታዉ እንዲፈርስልኝ በማለት ተጠሪ ያቀረበዉን የዳኝነት ጥያቄ ተቀብሎ አይቶ ለመወሰን የሥረ ነገር ስልጣን ሳይኖራቸዉ፣ በዚህ ነጥብ ላይ ጉዳዩን በማየት ጨረታዉ ሊሰረዝ ይገባል፣ አመልካች በሕግ አግባብ ጨረታዉን በግልጽ እንዲያካሄድ መብት ተጠብቋል በማለት የሰጡት ዉሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ የሚከተለዉ ተወስኗል፡፡

<u>ዉ ሳ ኔ</u>

1. የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ.ቁ.01-00929 ጥቅምት 17 ቀን 2010 ዓ.ም የሰጠዉ ዉሳኔ እና ይህን ዉሳኔ በማጽናት የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ.ቁ.149867 በ5/4/2010 ዓ.ም የሰጠዉ ትዕዛዝ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመባቸዉ ስለሆነ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.348 /1/ መሰረት ተሽሯል፡፡

2. የሰሜን ጎንደር ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ.01-29474 በ2/5/2009 ዓ.ም የሰጠዉ ዉሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የሌለዉ ስለሆነ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.348 (1) መሰረት ጸንቷል፡፡
3. የአሁን ተጠሪ የአመልካች ባንክ ለዕዳ ምክንያት በመያዣነት የያዘዉን ንብረት በአዋጅ ቁጥር 97/90 መሰረት በሐራጅ ከመሸጥ ጋር በተያያዘ የሐራጅ ሽያጩ የሕጉን ሂደት ያልተከተለ ስለሆነ እንዲፈርስልኝ በማለት የጠየቀዉን ዳኝነት መደበኛ ፍ/ቤት ተቀብሎ አይቶ ለመወሰን ስልጣን የለዉም፡፡ የአሁን ተጠሪ በአመልካች በተደረገዉ የጨረታ ሂደት ምክንያት የደረሰባቸዉ ጉዳት ያለ እንደሆነ የአዋጅ ቁጥር 97/90 አንቀጽ 7 በሚደነግገዉ እና በሕጉ አግባብ በመደበኛ ፍ/ቤት ክስ በማቅረብ ካሳ ከመጠየቅ ይህ ዉሳኔ የሚከለክላቸዉ አይሆንም ብለናል፡፡
4. ግራ ቀኞቸዉ በዚህ ችሎት የደረሰባቸዉን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸዉን ይቻሉ፡፡
5. ሰኔ 18 ቀን 2010 ዓ.ም የተሰጠዉ እግድ በዚህ ዉሳኔ ተነስቷል፡፡ ይጻፍ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

መ/ይ

አፈ፻ፀም

የስ/መ/ቁ. 201128

ጥቅምት 03 ቀን 2014 ዓ.ም

ዳኞች፡- ብርሀኑ አመነው

ተሾመ ሽፈራው

ሀብታሙ እርቅይሁን

ብርሀኑ መንግስቱ

ነፃነት ተገኝ

አመልካች - ወ/ሮ መሠረት ኃይሉ - ጠበቃ ሰለሞን ረዳ

ተጠሪ - ወ/ሮ ቢቂልቱ በየነ - ቀርበዋል

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የፍርድ አፈፃፀምን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ በተጀመረበት በቡራዩ ከተማ ወረዳ ፍርድ ቤት ተጠሪ የፍርድ ባለመብት በመሆን የፍርድ ባለዕዳ በሆኑት በአመልካች እና ሌሎች ሁለት ግለሰቦች ላይ ባቀረቡት አቤቱታ የቡራዩ ከተማ ወረዳ ፍ/ቤት በመ/ቁጥር 64593 ላይ በቀን 10/08/2009 ዓ.ም በዋለዉ ችሎት በሰጠዉ ውሳኔ መሠረት እንዲፈፀምላቸው የጠየቁትን ዳኝነት መነሻ ያደረገ ነዉ፡፡

የአፈፃፀም አቤቱታዉ የቀረበለት ፍርድ ቤት አከራካሪው ይዞታ በገፈርሳ ቡራዩ ቀበሌ አስተዳደር አማካኝነት ተለክቶ እንዲቀርብለት ካደረገ በኋላ ስፋቱ 842.8 ካ.ሜ እንደሆነ፤ ተጠሪ ደግሞ በክሳቸው ላይ የጠቀሱት የይዞታ መጠን 660 ካ.ሜ ስለመሆኑ መገንዘቡን ጠቅሶ የፍርድ ባለእዳዎች በዚሁ መጠን ለአመልካች እንዲያስረክቡ፣ ከዚህ ውጪ የሚተርፍ ይዞታ ካለና ባለመብት ካልተገኘ የከተማው አስተዳደር ወደ መሬት ባንክ እንዲያስገባ በማለት ትዕዛዝ ሰጥቷል፡፡ ግራ ቀኙ በዚህ ዉሳኔ ቅር በመሰኘት ይግባኛቸውን ለዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ያቀረቡ ሲሆን ፍርድ ቤቱም የግራ ቀኙን የይግባኝ አቤቱታ በማጣመር ከመረመረ በኋላ ትርፍ ነው የተባለውን መሬት የቡራዩ ከተማ አስተዳደር መሬት ልማትና ማኔጅመንት ጽ/ቤት ይዉሰድ መባሉ ስህተት ነው፤ ተጠሪ በአራቱም አቅጣጫ አዋሳኝ ጠቅሰው ያቀረቡትን ክስ መጠኑ በባለሞያ እንዲጣራ ከማዘዝ ውጪ ትክክለኛውን መጠን አልጠቀሱም ሊባል አይገባም በማለት የወረዳ ፍርድ ቤቱ የሰጠውን ውሳኔ ሽሮታል፡፡ አመልካች በበኩላቸው በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት የይግባኝ እና የሰበር አቤቱታቸውን ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ እና ሰበር ሰሚ ችሎቶች በቅደም ተከተል ቢያቀርቡም ተቀባይት አላገኘም፡፡ ለዚህ ፍርድ መነሻ የሆነው የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡

አመልካች በቀን 12/05/2013 ዓ.ም ጽፈው ባቀረቡት 03 ገጽ የሰበር አቤቱታ በስር ፍርድ ቤቶች ተፈጽመዋል ያሏቸውን ስህተቶች በመዘርዘር በዚህ ችሎት እንዲታረሙላቸው ጠይቀዋል። የአቤቱታቸው ይዘትም በአጭሩ ክርክር ያስነሳውና ተጠሪ እንዲረከቡት የተወሰነላቸው ይዞታ መጠን 660 ካ.ሜ ሆኖ እያለ ከዚህ መጠን በላይ አመልካች በውርስ ያገኘሁትን ይዞታ በማጠቃለል በአፈፃፀም እንዲረከቡ መወሰኑ ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት ከዚህ በፊት በተመሳሳይ ጉዳይ ላይ የሰጠውን አስገዳጅ የህግ ትርጉም ያላገናዘበ እና መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባዋል የሚል ነው።

ጉዳዩም በሰበር አጣሪ ችሎት ተመርምሮ የአከራካሪው ይዞታ አፈፃፀም ፍርዱን የተከተለ ነው? ወይስ አይደለም? የሚለው ነጥብ ከፍትሐብሔር ስነ-ስርዓት ህግ አንፃር መጣራት ያለበት መሆኑ ስለታመነበት ለዚህ ሰበር ችሎት ቀርቧል። በዚሁም መሠረት ተጠሪ መልስ እንዲሰጡበት ተደርጎ በቀን 22/06/2013 ዓ.ም በተፃፈ መልሳቸው የቡራዩ ከተማ ወረዳ ፍርድ ለአፈፃፀሙ ምክንያት የሆነውን ውሳኔ ሲሰጥ ለክርክሩ ምክንያት የሆነውን መሬት ስፋት ያላጣራ ሲሆን በደፈናው የተጠሪ ይዞታ ላይ የተፈጠረው ሁከት ተወግዶ የፍርድ ባለእዳዎች የሰሩትን አጥር አፍርሰው ይዞታውን እንዲለቁ ወሰነ እንጂ የይዞታውን መጠን አልገለፀም፤ በስር ፍርድ ቤት ክስ ያቀረብኩበት ይዞታ መጠኑ 1300 ካ.ሜ የነበረ ሲሆን መንግስት በይዞታው ላይ መንገድ በማውጣቱ መጠኑ ቀንሷል፤ አመልካች በዚህ አካባቢ ምንም አይነት መሬት የላቸውም፤ የስር ከፍተኛ ፍርድ ቤት አዋሳኙ የተጠቀሰውን መሬት በአፈፃፀም እንድረከብ ትዕዛዝ መስጠቱ ስህተት ስለሌለው ሊፀና ይገባል በማለት ተከራክረለች። አመልካችም የሰበር አቤቱታቸውን በማጠናከር የመልስ መልስ ሰጥተው ተከራክረዋል።

ከስር ጀምሮ የጉዳዩ አመጣጥ እና የግራ ቀኝ ክርክር ይዘት አጠር አጠር ባለ መልኩ ሲታይ ከፍ ሲል የተመለከተዉን ሲመስል ይህ ችሎትም የአመልካችን የሠበር አቤቱታ በሰበር አጣሪ ከተያዘው ጭብጥ፣ ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና ከተገቢው የህጉ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ በሚከተለው መልኩ መርምሮታል። እንደመረመረዉም ለአፈፃፀሙ ምክንያት ለሆነዉ ዉሳኔ መነሻ የሆነዉን ክስ ተጠሪ ሲያቀርቡ አዋሳኛቸንም በአራት አቅጣጫ በመጥቀስ ሲሆን ለአፈፃፀሙ ምክንያት የሆነዉ ዉሳኔ ይዘትም አዋሳኙ ከተጠቀሰዉ ይዞታ ዉስጥ የሚገኘዉ ይዞታ የተጠሪ በመሆኑ አመልካችን ጨምሮ ሌሎች ተከሳሾች ሁከት አስወግዶ በቦታዉ ላይ ያጠሩትን አጥር ያፍርሱ የሚል ስለመሆኑ በፊንፊኔ ዙሪያ የኦሮሚያ ልዩ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ከሰጠዉ የፍርድ ሃተታ መገንዘብ ይቻላል። አመልካች ለክርክሩ መነሻ በሆነዉ ወይም ለአፈፃፀሙ መነሻ የሆነዉ ፍርድ ካረፈበት ይዞታ አጠገብ አዋሳኝ ይዞታ ያላቸዉ ስለመሆኑ የቀረበ ክርክር የለም። ለፍርድ አፈፃፀም ምክንያት የሆነዉ ዉሳኔም ይሄዉ ነዉ።

ፍርድ እንዲያስፈጽም አቤቱታ የቀረበለት ፍርድ ቤት እንደ ፍርዱ፣ ማለትም በፍርዱ ላይ በተመለከተዉ ላይ ሳይጨምር ወይም ሳይቀንስ፣ የማስፈጸም ኃላፊነት አለበት። በፍርድ ቤት የሚሰጥ

ዳኝነት ያላግባብ የተወሰደ ንብረት ወይም ሀብት እንዲመለስ ወይም ገንዘብ እንዲከፈል ሊሆን ይችላል። በዚህ መልኩ በሚሰጥ ውሳኔ የፍርድ ባለመብት ተጠቃሚ ሊሆን የሚችለው በተሰጠ ፍርድ መሠረት የተፈጸመለት እንደሆነ ነው። እያንዳንዱ ጉዳይ የሚፈጀው ጊዜ እንደ የጉዳዩ ዓይነትና ባህርይ ሊለያይ የሚችል ቢሆንም፣ ክስ ከቀረበበት ጀምሮ እስከ ውሳኔ ድረስ ያለው ሂደት የተወሰነ ጊዜ መውሰዱ አይቀሬ ነው። በዚህም ሂደት የፍርድ ቤት ብሎም የተከራካሪ ወገኖች ጊዜ ይባክናል፤ ወጪና ድካም ይኖራል። ስለሆነም ፍርድን እንደ ፍርዱ ማስፈጸም ይህን ሂደት በማለፍ የተሰጠ ፍርድ ፍሬ አልባ እንዳይሆን የማድረግ ውጤት ሊያስከትል የሚችል ከመሆኑም በላይ ፍርድ ቤቶች የሚሰጡት ፍርድ ተፈፃሚነቱ ተገማች እንዲሆን ያስችላል። የፍት/ብ/ሥነ ሥርዓት ህጋችን ሰባተኛ መጽሐፍ ከአንቀጽ 371 ጀምሮ ባሉት ድንጋጌዎቹ የፍርድ አፈፃፀም የሚመራበትን ሥነ-ሥርዓት ይደነግጋል። የፍርድ አፈፃፀም የቀረበለት ፍርድ ቤትም በዚህ የመጽሐፉ ክፍል የተዘረጋውን ስርዓት በመከተል ድንጋጌዎቹን እንደየአግባብነታቸው ተግባራዊ በማድረግ አፈፃፀሙን በመምራት እንደ ፍርዱ የማስፈጸም ግዴታ አለበት።

ከዚህ አንፃር የተያዘውን ጉዳይ ስንመለከት ለአፈፃፀሙ መነሻ ለሆነው ውሳኔ ምክንያት በሆነው ክስ ተጠሪ የጠቀሱት የይዞታ መጠን 660 ካ/ሜትር የሚል ቢሆንም የተሰጠው ውሳኔ በክሱ ላይ አዋሳኞቹ የተጠቀሰው ይዞታ የተጠሪ መሆኑን የሚያሳይ ከሆነ በአዋሳኙ የተመለከተው የይዞታ መጠን ከ660 ካ/ሜትር በላይ 842.8 ካ/ሜትር መሆኑ ቀሪው ይዞታ ማለትም 182 ካ/ሜትር ፍርድ ያላላረፈበት ነው ለማለት የሚያስችል አይደለም። በመሆኑም የወረዳው ፍርድ ቤት ጉዳዩን ከዚህ አንፃር ማየት ሲገባው ይዞታው ተለክቶ በታወቀው መጠን እና በተጠሪ ክስ ላይ በተጠቀሰው መጠን መካከል ልዩነት በመፈጠሩ ብቻ 182 ካ/ሜትር ቦታ ላይ ፍርድ አላረፈም በማለት መቀነሱ የፍርዱን ትክክለኛ ይዘት ያላገናዘበ ሲሆን፣ በአንፃሩ የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይህንኑ በማረም በፍርዱ ላይ አዋሳኙ የተጠቀሰው ይዞታ ለተጠሪ እንዲፈጸም በማለት ውሳኔ መስጠቱ እንዲሁም የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ እና ሰበር ሰሚ ችሎቶች ይህንኑ ውሳኔ በማጽናት የሰጡት ትዕዛዝ የፍርድ አፈፃፀም ሥርዓት መሠረታዊ መርህን ለአፈፃፀሙ ምክንያት ከሆነው ውሳኔ ጋር በማገናዘብ የተሰጠ እና በአግባቡ ነው ከሚባል በስተቀር በዚህ ችሎት ሊታረም የሚችል መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ አልተገኘም። ስለሆነም ተከታዩ ውሳኔ ተሰጥቷል።

<u>ውሳኔ</u>

1. በፊንፊኔ ዙሪያ የኦሮሚያ ልዩ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 39788 በቀን 16/04/2013 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጠው ውሳኔ፣ የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 325009 በቀን 27/04/2013 ዓ.ም በዋለው ችሎት እንዲሁም የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 334648 በቀን

03/05/2013 ዓ.ም በዋለዉ ችሎት የሰጡት ትዕዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥርዓት ህጉ አንቀጽ 348(1) መሠረት ጸንተዋል፡፡

2. የሰበር አጣሪ ችሎት በመ/ቁጥር 201128 በቀን 25/05/2013 ዓ.ም በዋለዉ ችሎት የሰጠዉ እግድ ተነስቷል፡፡
3. በዚህ ችሎት የተደረገዉ ክርክር ያስከተለዉን ወጪ እና ኪሳራ ግራ ቀኝ የየራሳቸዉን ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ

ዜ/መ

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

የሰ/መ/ቁ 251605

መጋቢት 23 ቀን 2016 ዓ.ም

ዳኞች፡- ተፈሪ ገብሩ (ዶ/ር)

እንዳሻው አዳነ

ተሾመ ሽፈራው

ዋዚሞ ዋሲራ

ሰናይት አድነው

አመልካች፡- ወ/ሮ ምህረት መኮንን - የቀረበ የለም

ተጠሪ፡- 1. ወ/ሮ ትርሲት መኮንን - ጠበቃ ዘላለም አበበ - ቀረበ

2. አቶ ታላቅ ሰው መንገሻ - ከጠበቃ ሀብተማሪያም ፀጋዬ ጋር - ቀረቡ

መዝገቡ የተቀጠረው መርምሮ ፍርድ ለመስጠት ነበር ተመርምሮ ተከታዩን ፍርድ ተሰጠ፡፡

ፍርድ

መዝገቡ የተቀጠረው ለሚያዝያ 30 ቀን 2016 ዓ.ም የነበረ ቢሆንም 2ኛ ተጠሪ ቀጠሮ ተሰብሮ ይታይልኝ በማለት መጋቢት 3 ቀን 2016 ዓ.ም በመጠየቃቸው ቀጠሮ ተሰብሮ ለዛሬ እንዲታይ ችሎቱ በማዘዙ ነው፡፡

ይህ የአፈጻጸም ክርክር የተጀመረው በፌደራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ሲሆን የአሁን 1ኛ ተጠሪ የፍርድ ባለመብት የአሁን አመልካች የፍርድ ባለእዳ በመሆን በተሰጠ ውሳኔ መነሻነት ለእዳው መክፈያ በሀራጅ እንዲሸጥ የተወሰነበትን ቤት የአሁን 2ኛ ተጠሪ በጨረታ ከመግዛታቸው ጋር ተያይዞ የአሁን 2ኛ ተጠሪ ጨረታ ያሸነፉበትን ገንዘብ ለመክፈል በሀራጅ ማስታወቂያ ላይ ከተገለጸው 15 ቀን ሌላ ተጨማሪ 15 ቀን ይፈቀድልኝ በማለት ለፍርድ ቤቱ ባቀረቡት አቤቱታ መነሻነት ግራ ቀኙ ተከራክረዋል፡፡

ጉዳዩ ለዚህ ችሎት ሊቀርብ የቻለው የፌደራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በሰጠው ውሳኔ አመልካች ቅር ተሰኝተው ለፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የይግባኝ ቅሬታ ያቀረቡት ቢሆንም ፍርድ ቤቱ በመ/ቁ 308038 በቀን 25/10/2015 ዓ.ም በዋለው ችሎት የስር መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የሰጠውን ትእዛዝ በማጽናት የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት አመልካች ሀምሌ 26 ቀን 2015 ዓ.ም የተጻፈ የሰበር አቤቱታ ስላቀረቡ ነው፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ሲታይ የአሁን አመልካች እና 1ኛ ተጠሪ ከወላጆቻቸው በውርስ ያገኙትን ቤት በፍርድ አፈጻጸም ዳይሬክቶሬት በሀራጅ ተሸጦ እንዲካፈሉ በተሰጠ የአፈጻጸም ትእዛዝ መነሻነት ቤቱ በሃራጅ እንዲሸጥ በጋዜጣ በወጣው ማስታወቂያ መሰረት የአሁን 2ኛ ተጠሪ ጨረታውን ተወዳድረው እና አሸንፈው እያለ መጋቢት 22 ቀን 2015 ዓ.ም በወጣው የጨረታ ማስታወቂያ መሰረት ጨረታውን በአሸነፉ በ15 ቀን ውስጥ ጨረታ ያሸነፉበትን ገንዘብ መክፈል እንዳለባቸው የተገለጸ ቢሆንም 2ኛ ተጠሪ 15 ቀን ሊያበቃ 1 ቀን ሲቀረው ሚያዝያ 5 ቀን 2015 ዓ.ም ባቀረቡት አቤቱታ በጨረታ ማስታወቂያ ላይ ጨረታውን ያሸነፈ ሰው በ15 ቀን ውስጥ ጨረታ ያሸነፈበትን ገንዘብ መክፈል እንዳለበት የተገለጸ ቢሆንም ባለቤቱ ለውሊድ ሆስፒታል ገብታ የነበረ በመሆኑ ገንዘቡ በተባለው ጊዜ መክፈል ስላልቻልኩ ተጨማሪ 15 ቀን ይፈቀድልኝ በማለት ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡

ጉዳዩ የቀረበለት የፌደራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትም 2ኛ ተጠሪ ባለቤታቸው ሚያዝያ 6 ቀን 2015 ዓ.ም ለወሊድ ሆስፒታል የነበሩ መሆናቸውን የሚያሳይ ማስረጃ ያቀረቡ ስለሆነ ይህ ምክንያት የሽያጩን ገንዘብ በተባለው 15 ቀን ውስጥ ገቢ ለማድረግ የሚከለክል በቂ ምክንያት ነው በማለት ደምድሞ ሚያዝያ 30 ቀን 2015 ዓ.ም በዋለው ችሎት ከዚህ ቀን ጀምሮ የሚታሰብ ተጨማሪ 15 ቀን ለመፍቀድ ትእዛዝ ሰጥቷል፡፡

በዚህ ውሳኔ ቅር የተሰኙት የአሁን አመልካች ለፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የይግባኝ ቅሬታቸውን ያቀረቡ ቢሆንም ፍርድ ቤቱ የስር መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሳኔ በማጽናቱ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

ይህ የሠበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንን ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡ የአመልካች የሠበር አቤቱታ ይዘት በአጭሩ በጨረታው ላይ የተገለጸው ለመክፈያ ጊዜ 15 ቀን ከመሆኑ በስተቀር ይህ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንን ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡ የዐመልካች የሠበር አቤቱታ ይዘት በአጭሩ በጨረታው ላይ የተገለጸው የመክፈያ ጊዜ 15 ቀን ከመሆኑ በስተቀር ይህ ጊዜ ሊራዘም የሚችልበት አግባብ ስለመሆኑ ባልተገለጸበት ሁኔታ የስር ፍርድ ቤቶች 2ኛ ተጠሪ በህጉ በተፈቀደው 15 ቀን ጊዜ ውስጥ ክፍያውን ጨርሰው ባለመክፈላቸው ድጋሚ ጨረታ እንዲወጣ ማዘዝ ሲገባቸው ተጨማሪ 15 ቀን ጊዜ መፍቀዳቸው የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህጉን የሚያሻሽል ከመሆኑም በተጨማሪ የኔን መብት የሚነካ ስለሆነ የስር ፍርድ ቤቶች የሰጡት ውሳኔ ተሽሮ ድጋሚ ጨረታ እንዲወጣ ተብሎ ይወሰንልኝ የሚል ነው፡፡

የአመልካችም አቤቱታ በሰበር አጣሪው ችሎት ተመርምሮ ክፍያው ለ15 ቀን እንዲራዘም የተወሰነበትን አግባብነት ተጠሪዎች ባሉበት ለመመርመር ሲባል መዘዝገቡ ለሰበር ሰሚ ችሎት ያስቀርባል ተብሎ ተጠሪ መልስ እንዲሰጡበት ታዟል፡፡

1ኛ ተጠሪ ህዳር 20 ቀን 2016 ዓ.ም የተፃፈ መልስ አቅርበዋል ይዘቱም በአጭሩ የስር ፍርድ ቤቶች የሰጡት ውሳኔ የሚነቀፍ ባለመሆኑ ሊጸና ይገባል ሲሉ 2ኛ ተጠሪ ህዳር 20 ቀን 2016 ዓ.ም በተጻፈ የሰጡት መልስ የመክፈያ ተጨማሪ ጊዜ በራሴ ጊዜ ያላራዘምኩኝ ይልቁኑስ በወቅቱ ያጋጠመኝን ምክንያት ከግምት በማስገባት በፍርድ ቤቶች የተፈቀደልኝ ከመሆኑም በተጨማሪ በተፈቀደልኝ 15 ቀን ጊዜው ውስጥ ሙሉ ክፍያ ከፍዬ የጨረስኩኝ ስለሆነ የስር ፍርድ ቤቶች የሰጡት ውሳኔ የሚነቀፍ እና መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት አይደለም፤ ስለሆነም ሊጸና ይገባል በማለት ክርክራቸውን ሲያቀርብ አመልካችም የሰበር አቤቱታቸውን በማጠናከር የመልስ መልስ አቅርበዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥና የክርክሩ ይዘት በአጭሩ ከላይ የተመለከተው ሲሆን ይህ ችሎትም አቤቱታ የቀረበበት ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት መሆን ያለመሆኑን ለክርክሩ ከተያዘው ጭብጥ እና ከተገቢው ህግ ጋር አገናዝበን መርምረናል፡፡

እንደመረመርነው በመሰረቱ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህግ ቁጥር 441 ላይ ለፍርድ አፈጻጸም ሲባል ንብረት በሀራጅ እንዲሸጥ ሲታዘዝ በሀራጅ የተሸጠው ንብረት ዋጋ በሙሉ የሚከፈለው ገዢው ንብረቱን መግዛቱ ከተረጋገጠበት ጊዜ ጀምሮ በ15 ቀን ውስጥ እንደሆነ ተደንግጎ ይገኛል፡፡ በተጨማሪም በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 442 ላይ እንደተመለከተው ከላይ በተገለጸው ጊዜ ውስጥ የንብረቱ ዋጋ ሳይከፈል የቀረ እንደሆነ ገዢው አስይዞት ከነበረው ገንዘብ ውስጥ ለሽያጩ ስርአት እና ለማናቸውም ጉዳይ ውጭ የተደረገው ገንዘብ ተቀንሶ የቀረው ገንዘብ ለመንግስት ገቢ እንዲሆን ፍርድ ቤቱ ለማዘዝ ይችላል ንብረቱም እንደገና እንዲሸጥ ትዕዛዝ ይሰጣል እንዲህ በሆነ ጊዜ ግዴታውን ሳይፈጽም የቀረው ገዢ በሽያጭ ገንዘቡ ወይም በተሸጠው ንብረት ላይ ምንም መብት አይኖረውም በማለት ደንግጎ ይገኛል፡፡ የጨረታ ማስታወቂያውም ክፍያው በ15 ቀን ውስጥ እንደሚከፈል የሚገልጽ መሆኑን ግራ ቀኙን አላከራከረም፡፡ አከራካሪው ጉዳይ በሥ/ሥ/ህጉ የተደነገገው እና በሃራጅ ማስታወቂያ ላይ የተገለጸው የ15 ቀን መክፈያ ጊዜ በዳኞች ትእዛዝ ሊሻሻል ይገባል አይገባም የሚለው ነው፡፡

ይህንን አከራካሪ ጭብጥ ለመወሰን የድንጋጌዎቹ ይዘት ህጉ ለወጣበት አላማ አንጻር ማየቱ ተገቢ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ በመሆኑም የድንጋጌዎቹን ይዘት ስንመለከት በፍ/ሥ/ሥ/ህግ ቁጥር 441 ላይ ለፍርድ አፈጻጸም ሲባል ንብረት በሀራጅ እንዲሸጥ ሲታዘዝ በሀራጅ የተሸጠው ንብረት ዋጋ በሙሉ የሚከፈለው ገዢው ንብረቱን መግዛቱ ከተረጋገጠበት ጊዜ ጀምሮ በ 15 ቀን ውስጥ ነው በማለት ሲደነግግ፡ በፍ/ሥ/ሥ/ህግ ቁጥር 442 ላይ እንደተመለከተው ከላይ በተገለጸው ጊዜ ውስጥ የንብረቱ ዋጋ ሳይከፈል የቀረ እንደሆነ ገዢው አስይዞት ከነበረው ገንዘብ ውስጥ ለሽያጩ ስርዓት እና ለማናቸውም ጉዳይ ወጭ የተደረገው ገንዘብ ተቀንሶ የቀረው ገንዘብ ለመንግስት ገቢ እንዲሆን ፍርድ ቤቱ ለማዘዝ ይችላል ንብረቱም አንደገና እንዲሸጥ ትእዛዝ ይሰጣል፤ እንዲህ በሆነ ጊዜ ግዴታውን ሳፈጽም የቀረው ገዢ በሽያጭ ገንዘቡ ወይም በተሸጠው ንብረት ላይ ምንም መብት አይኖረውም በማለት ደንግጎ ይገኛል፡፡

የድንጋጌዎቹ አገላለጽ በመጀመሪያ ደረጀ በ15 ቀን ውስጥ የሽያጩ ገንዘብ መከፈል እንዳለበት በአስገዳጅ ሁኔታ ሲደነግግ ቀጥሎ ያለው ድንጋጌ በ15 ቀን ውስጥ ክፍያው ያለመፈጸሙ ገዢው አስይዞት ከነበረው ገንዘብ ላይ ለሽያጩ ስርአት እና ለማናቸውም ጉዳይ ወጪ የተደረገ ገንዘብ ሊቀነስበት እንደሚገባ በአስገዳጅ ሁኔታ ደንግጎ የቀረው ገንዘብም ለመንግስት ገቢ እንዲሆን ፍርድ ቤቶች ለማዘዝ እንደሚችሉ ከደነገገ በኋላ ንብረቱም እንደገና እንዲሸጥ ትእዛዝ ይሰጣል በማለት በአስገዳጅነት በመግለጽ የተቀመጠው የህጉ ድንጋጌ ገዢ ጨረታ ያሸነፈበትን ገንዘብ በህጉ በተመለከተው ጊዜ ካልከፈለ ሌላ ሃላፊነት የሚጥልበት መሆኑን በአስገዳጅ ሁኔታ እና በጥብቅ የደነገገ መሆኑን ከድንጋጌው አገላለጽ መረዳት የሚቻል ጉዳይ ነው።

ህጉ በዚህ አግባብ መደንገጉም አላማው ንብረት በጨረታ ለመግዛት የሚመጣ ሰው ጨረታውን ቢያሸንፍ ክፍያውን ወዲያው ከፍሎ ንብረቱን መረከብ የሚችል ሰው መሆኑን በመገመት እና ወይም ጨረታውን ቢያሸነፍም ያሸነፈበትን ገንዘብ ለመክፈል የሚችል ሰው ጨረታውን አስቀድሞም አይወዳደርም ብሎ በማሰብ እና የተባለው ንብረት በተባለው ጊዜ ካልተሸጠ የሚያስከትለውን የገበያ ውጣ ውረድ ሃላፊነት ለመቀነስ በማሰብ የ 15 ቀን ጊዜውን በጥብቅ አገላለጽ የደነገገው።

ከዚህ የድንጋጌ አላማ ስንነሳ ጨረታ አሸናፊው በ15 ቀን ውስጥ ክፍያውን ካልከፈለ ንብረቱ እንዲሸጥ እና ገዢው ላይ ተጨማሪ ሃላፊነት በሚጥልበት ሁኔታ በጥብቅ ድንጋጌ የተቀመጠን ሥነ-ሰርአት ዳኞች እንደፈለጉ ሊለውጡት የሚችሉበት የህግ ምክንያት የለም።

ስለሆነም የስር ፍርድ ቤቶች የአሁን 2ኛ ተጠሪ በጨረታ ያሸነፉበትን ገንዘብ በ15 ቀን ውስጥ ያለመክፈላቸውን ካረጋገጡ በህጉ አግባብ በድጋሚ ጨረታ ንብረቱ እንዲሸጥ ማዘዝ ሲገባቸው ይህንን ካለማድረጋቸው በተጨማሪ 2ኛ ተጠሪ ንብረቱን በሀራጅ የገዙበትን ዋጋ ለመክፈል በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህግ ቁጥር 441 ላይ ከተመለከተው በተጨማሪ የ15 ቀን ጊዜ እንዲጨመርላቸው ያቀረቡት ጥያቄ የስነ ስርዓት ህጉን ያልተከተለና ሕጋዊ ዕውቅና እና ውጤት ሊሰጠው የሚገባው ባልሆነበት ሁኔታ 2ኛ ተጠሪ ያቀረቡትን የ15 ቀን ተጨማሪ ጊዜ በመፍቀድ የስር መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የሰጠውን ትዕዛዝ በማጽናት የስር ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠው ውሳኔ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 441፣ እና 442 ድንጋጌዎች ያላገናዘበና መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ አግኝተነዋል በመሆኑም ተከታዩ ውሳኔ ተሰጥቷል።

ውሳኔ

1. የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ.ቁ 308038 ሰኔ 25 ቀን 2015 ዓ.ም በዋለው ችሎት የፌደራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የሰጠውን ትዕዛዝ በማጽናት የሰጠው ውሳኔ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 348/1/ መሰረት ተሽሯል፡፡
2. ንብረቱ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 442 መሰረት በድጋሚ ጨረታ ሊሸጥ ይገባል ብለናል፡፡
3. የፌደራል መጀመሪያ ደራጅ ፍርድ ቤት መዝገቡን በማንቀሳቀስ ገዢው (2ኛ) ተጠሪ አስይዘውት ከነበረው ገንዘብ ውስጥ ለሽያጩ ስርአት እና ለማናቸውም ጉዳይ ውጪ የተደረገው ገንዘብ የሚቀነስበትን ሁኔታ እና ስለቀሪው ገንዘብ ተገቢውን ትዕዛዝ እንዲሰጥ እንዲሁም ንብረቱ እንደገና በ2ኛ ሀራጅ ሽያጭ እንዲሰጥ ተገቢውን ትዕዛዝ እንዲሰጥ ጉዳዩ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 343(1) መሰረት ተመልሶለታል፡፡
4. በዚህ ፍርድ ቤት ለተደረገው ክርክር ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡
5. በዚህ ችሎት ነሀሴ 5 ቀን 2015 ዓ.ም የተሰጠው እግድ ተነስቷል፡፡ ይጻፍ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ፍ/ደ

የስ/መ/ቁ. 184585

ታህሳስ 15 ቀን 2013 ዓ.ም

ዳኞች፡- ብርሀኑ አመነው

ተሾመ ሽፈራው

ሀብታሙ እርቅይሁን

ብርሀኑ መንግስቱ

ነፃነት ተገኝ

አመልካች፡- ታግሮ ቢዝነስ ኃ/የተ/የግ/ማህበር

ተጠሪዎች፡- 1. ወ/ሮ ማእበል ፍፁም

2. አቶ ጎይቶም ግደይ

3. አቶ ካሳሁን ማሞ

4. አቶ ምናለ ሀይለ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ለዚህ ፍርድ መነሻ የሆነዉ ጉዳይ 1ኛ ተጠሪ የፍርድ ባለእዳ፣ ከ 2ኛ - 4ኛ ተጠሪዎች የፍርድ ባለመብት በመሆን በሚከራከሩበት መዝገብ ላይ አመልካች ያቀረበዉን አቤቱታ ባለመቀበል የተሰጠ ዉሳኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነዉ የሚል አቤቱታ በመቅረቡ ነዉ፡፡ አመልካች በስር ፍርድ ቤት ያቀረበዉ አቤቱታ ይዘትም በአጭሩ ለፍርድ አፈፃፀም እንዲከበሩ ትዕዛዝ የተሰጠባቸው 154 ባለ 3 እግር ባጃጅ ተሽከርካሪዎች ንብረትነታቸው የፍርድ ባለዕዳ (የ1ኛ ተጠሪ) አለመሆኑንና የእግድ ትዕዛዙ ከመሰጠቱ በፊት ለ3ኛ ወገን በሽያጭ የተላለፉ ስለሆነ በይዞታዉ ስር የሌሉ ሆነዉ እያለ በግል የባንክ ሂሳቡ ላይ የተሰጠው የእግድ ትዕዛዝ ያላግባብ በመሆኑ ይነሳልኝ የሚል ነዉ፡፡

አመልካች ባቀረበው አቤቱታ ላይ 2ኛ ተጠሪ በሰጡት አስተያየት የአሁን አመልካች ተመሳሳይ አቤቱታ በፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት መዝገብ ቁጥር 161609 ላይ አቅርበው በቀን 14/02/2010 ዓ.ም በተሰጠው ትዕዛዝ ውድቅ መደረጉን በዚህም እስከ ፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ድረስ የባጃጆቹ ባለንብረት ማነው? የሚል ጭብጥ ተይዞ ባለንብረቱ የአሁን 1ኛ ተጠሪ መሆናቸው ተረጋግጦ ፍርድ የተሰጠ በመሆኑ አቤቱታው ተገቢነት የለውም በማለት ተከራክሯል፡፡

ጉዳዩን በመጀመሪያ የተመለከተዉ የስር ከፍተኛ ፍርድ ቤትም ከግራ ቀኝ በዚህ መልኩ የቀረበዉን ክርክር መርምሮ አመልካች 1ኛ ተጠሪን ተክቶ የተጠሪዋን እዳ እንዲፈፅም የተሰጠ ትዕዛዝ

የለም፡፡ አመልካች በእጁ ያሉትን 154 ባጃጅ ተሽከርካሪዎች ለፌደራል ፍርድ ቤቶች ፍርድ አፈፃፀም ዳይሬክቶሬት እንዲያስረክብ እና በሀራጅ ተሸጠው ለፍርድ ባለመብቶቹ እንዲከፈል ፍ/ቤቱ መጋቢት 13 እና ሚያዝያ 18 ቀን 2008 ዓ.ም ትእዛዝ የሰጠ ሲሆን ትዕዛዙ በፍርድ ቤቱም ሆነ በይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት አልተቀየረም፡፡ የባጃጅ ተሽከርካሪዎቹ የ1ኛ ተጠሪ ንብረት እንጂ የአመልካች እንዳልሆኑ እንዲሁም አመልካች ያቀረቡት የእግድ ይነሳልኝ ክርክር ንብረት ለማሸሽ መሆኑ ተረጋግጦ ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡ ውሳኔው እስከ ፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ድረስ ክርክር ተደርጎበት ጸንቷል፡፡ ፍርድ ቤቱም በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 378 እና ተከታዮቹ ድንጋጌዎች መሰረት ፍርዱን አመቺ በሆነ መንገድ እንዲፈፀም ማድረግ ይችላል፡፡ አመልካች ባጃጆቹን መሸጡን ገልፆ የሚከራከር በመሆኑ የእግድ ትዕዛዝ ከተሰጠበት የባጃጅ ተሽከርካሪዎች ሽያጭ በተገኘው ገንዘብ ላይ አፈፃፀሙ እንዲቀጥል መደረጉ ተገቢ ነው በማለት አቤቱታውን ውድቅ አድርጎ በአመልካች ስም በባንክ የተቀመጠው የሽያጭ ገንዘብ ተጠሪዎች ያስፈረዱትን ገንዘብ የማይሸፍን በመሆኑ በፍ/ስ/ሥ/ሕ/ቁጥር 403 በድርሻቸው መጠን ይከፋፈሉ በማለት ወስኗል፡፡

አመልካች በዚህ ውሳኔ ባለመስማማት ይግባኛቸውን ለፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አቅርበዋል፡፡ ፍ/ቤቱም ለክርክሩ ምክንያት የሆኑት ባጃጅ ተሽከርካሪዎች ከ1ኛ ተጠሪ ወደ አመልካች በሽያጭ ተዘዋውረዋል ከመባሉ በፊት የ1ኛ ተጠሪ ንብረት የነበሩ መሆኑ በአመልካችም ጭምር የታመነ ፍሬ ጉዳይ ነው፡፡ አመልካች ባጃጆቹን የእግድ ትዕዛዙ ከመሰጠቱ በፊት ለ3ኛ ወገን በሽያጭ ያስተላለፈ እና በይዞታው ስር የማይገኙ መሆኑን ጠቅሶ በባጃጆቹ ላይ የተሰጠው የእግድ ትዕዛዝ እንዲነሳ ባቀረበው አቤቱታ መነሻነት ከፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት እስከ ፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ድረስ በተደረገው ክርክር ንብረቶቹ የ1ኛ ተጠሪ እንጂ የአመልካች አለመሆናቸው ይልቁኑም የአመልካች ክርክር ከ1ኛ ተጠሪ ጋር በመመሳጠር ንብረቶቹን ለማሸሽ የቀረበ መሆኑ ተረጋግጦ የመጨረሻ ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡ አመልካች ባጃጆቹን እንዲያስረክብ ተጠይቆ ማስረከብ ስላልቻለ አፈፃፀሙ በሽያጭ ገንዘቡ ላይ እንዲቀጥል መወሰኑ በአግባቡ ነው በማለት የስር ከፍተኛ ፍርድ ቤት ውሳኔን አፅንቷል፡፡

ለዚህ ፍርድ መነሻ የሆነው የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ለማስለወጥ ነው፡፡ አመልካች በጠበቃው አማካኝነት ጥቅምት 10 ቀን 2012 ዓ.ም በተፃፈ 03 ገፅ የሰበር አቤቱታ በስር ፍርድ ቤቶች ተፈፅመዋል ያላቸውን ስህተቶች በመዘርዘር በዚህ ሰበር ችሎት እዲንታረሙለት ጠይቋል፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ ይዘትም በአጭሩ በግራ ቀኙ መካከል እስከ ፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ድረስ ክርክር የተደረገው በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 154 መሰረት የተሰጠው የእግድ ትዕዛዝ እንዲነሳ ብቻ ሁኖ እያለ የክርክሩ መነሻ የሆኑት 154 ባጃጆች የ1ኛ ተጠሪ ንብረት ናቸው ተብሎ ውሳኔ ተሰጥቷል በሚል ምክንያት በስር ፍርድ ቤቶች የተሰጠው ውሳኔ ተገቢ አይደለም፡፡ በተጨማሪም አመልካች የእግድ ይነሳልኝ አቤቱታው ተቀባይነት ባለማግኘቱ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 421 በመዝገብ

ቁጥር 227839 በባጃጆቹ ላይ ያለው መብት እንዲታወቅለት ክርክር አቅርቦ ጉዳዩ በመታየት ላይ እያለና ይህም ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 166908 የያዘውን ጭብጥ ለመወሰን የግድ አስፈላጊ በመሆኑ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 197 መሰረት መዝገቡ በቀጠሮ ማቆየት ሲገባው በዝምታ አልፎ የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ተፈፅሞበታል የሚል ነው፡፡

ጉዳዩ በሰበር አጣሪ ችሎቱ ተመርምሮ ያስቀርባል በመባሉ ተጠሪዎች መልሳቸውን እንዲያቀርቡ ትዕዛዝ ተሰጥቷል፡፡ 1ኛ ተጠሪ በጋዜጣ ጥሪ ተደርጎላቸው ባለመቅረባቸው መልስ የማቅረብ መብታቸው የታለፈ ሲሆን ከ2ኛ እስከ 4ኛ ያሉት ተጠሪዎች በተናጠል መልሳቸውን አቅርበዋል፡፡ የመልሳቸዉ የተጠቃለለ ይዘትም አመልካች በባጃጆቹ ላይ የተሰጠው እግድ እንዲነሳ ያቀረበው አቤቱታ የባጃጆቹ ባለንብረት ማነው? የሚል ጭብጥ ተይዞ ንብረቶቹ የ1ኛ ተጠሪ መሆናቸው ተረጋግጦ የእግድ ትዕዛዙ እንዲነሳ በአመልካች የቀረበው አቤቱታው ንብረት ለማሸሽ ነው በሚል እስከ ሰበር ሰሚ ችሎቱ በተደረገ ክርክር ውደቅ ተደርጓል፡፡ የስር ፍ/ቤቶች አመልካች የፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 418 መሰረት አመልካች ያቀረበውን አቤቱታ መርምረው አመልካች ንብረትነታቸው የ1ኛ ተጠሪ የሆኑ ባጃጅ ተሽከርካሪዎች በመሸጥ ያገኘው ገንዘብ ላይ አፈፃፀም እንዲቀጥል የተሰጠው ውሳኔ የፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 378 እና ተከታዮቹን ድንጋጌዎች መሰረት ያደረገ በመሆኑ በውሳኔዎቹ የተፈፀመ ሕግ ስህተት የለም በማለት ተከራክረዋል፡፡ አመልካችም የሰበር አቤቱታው በማጠናከር የመልስ መልስ ሰጥቶ ክርክሩ ተጠናቋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ እና የክርክሩ ይዘት አጠር ባለ መልኩ ከላይ የተገለፀውን ሲመስል ይህ ችሎትም የአመልካችን የሠበር አቤቱታ ከግራ ቀኝ ክርክር እና ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸዉ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ መዝገቡን እንደሚከተለዉ መርምሮታል፡፡ እንደመረመረዉም ባጃጆቹን አስመልክቶ የአሁን አመልካች የመፋለም ክስ አቅርቦ ጉዳዩ በሌላ መዝገብ በመታየት ላይ እያለ ባጃጆቹ የ1ኛ ተጠሪ (የፍርድ ባለ ዕዳ) መሆናቸዉ ተረጋግጧል የሚል ይዘት ያለዉ ምክንያት በመጥቀስ በስር ፍርድ ቤቶች የተሰጠዉ ዉሳኔ በአግባቡ መሆን አለመሆኑ የዚህን ችሎት ምላሽ የሚያሻዉ ጭብጥ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው በ1ኛ ተጠሪ እና ከ2ኛ-4ኛ ተጠሪዎች መካከል በነበረው የአፈፃፀም ክርክር ንብረትነታቸው የፍርድ ባለ እዳ (የ1ኛ ተጠሪ) ናቸው የተባሉት 154 ባለ ሶስት እግር ባጃጅ ተሽከርካሪዎች በአመልካች እጅ ስለሚገኙ ለፍርድ ማስፈፀሚያነት እንዲውሉ በስር ፍርድ ቤት ታግደዋል፡፡ አመልካች ትዕዛዙን በመቃወም እንዲነሳለት በፍ/ብ/ሥ/ሥርዓት ህጉ አንቀጽ 418 መሠረት አፈፃጸሙን ሲመለከት ለነበረዉ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 161753 የመቃወም አቤቱታ ያቀረበ ቢሆንም ተቀባይነት አላገኘም፡፡ ይህ ዉሳኔ በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 125912 እንዲሁም በሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 138823 የጸና ስለመሆኑ አላከራከረም፡፡ አመልካች በእነዚህ መዛግብት ላይ ለተሰጡት ዉሳኔዎች ምክንያት የሆነዉን አቤቱታ ያቀረበዉ በባጃጆቹ ላይ የቅድሚያ መብት አለኝ በሚል ሃሳብ ነዉ፡፡ የአመልካች የመቃወም አቤቱታ ዉድቅ የተደረገዉም

ክርክሩን ከዚሁ አንፃር በመመርመር ነዉ፡፡ በየደረጃዉ ባሉት ፍርድ ቤቶች የተሰጠዉ ዉሳኔም አመልካች በባጃጆቹ ላይ የቅድሚያ መብት የለዉም በሚል ምክንያት አቤቱታዉ ዉድቅ መደረጉን እንጂ ባጃጆቹ የፍርድ ባለዕዳዋ (የአሁን 1ኛ ተጠሪ) መሆናቸዉን የሚያሳዩ እንዳልሆኑ ከዉሳኔዎቹ ይዘት የምንገነዘበዉ ነዉ፡፡ በፍ/ብ/ሥ/ሥርዓት ህጉ አንቀጽ 418 መሠረት የሚቀርብ አቤቱታ በባህርዉ እንደሌሎች መደበኛ ክርክሮች የተሟላ ክርክር የማይደረግበት ከመሆኑ እና የክርክሩም አድማስ የመቃወም አመልካች ለአፈፃጸም እንዲዉል አግድ በተላለፈበት ንብረት ላይ የቅድሚያ መብት ያለዉ መሆን አለመሆኑ ላይ የተገደበ ከመሆኑ አንፃር ሲታይ፣ አመልካች በባጃጆቹ ላይ የቅድሚያ መብት የለዉም በሚል ቀደም ሲል በተሰጡት ዉሳኔዎች የተደረሰበት ድምዳሜ በምንም መልኩ ባጃጆቹ የፍርድ ባለ ዕዳ ናቸዉ በሚል እንደተወሰነ ሊተረጎም የሚገባዉ አይደለም፡፡ ስለሆነም የስር ከፍተኛ ፍርድ ቤት ከላይ በተጠቀሱት መዝገቦች ላይ ቀደም ሲል የተሰጡት ዉሳኔዎች ባጃጆቹ የፍርድ ባለዕዳ መሆናቸዉን የሚያረጋግጥ ነዉ በሚል የደረሰበት ድምዳሜ እና ይግባኝ ሰሚዉ ችሎትም ይህንኑ በመቀበል የሰጠዉ ዉሳኔ ለዉሳኔዉ ምክንያት የሆነዉን ክርክር ባህርይ ከዉሳኔዉ ትክክለኛ ይዘት ጋር ካለማገናዘብ የመነጨ ስህተት በመሆኑ ሊታረም የሚገባዉ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

በሌላ በኩል አመልካች በባጃጆቹ ላይ ያለዉን የባለቤትነት መብት ለማስከበር ሲባል በኮ/መ/ቁጥር 227839 ላይ ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ክስ አቅርቦ ጉዳይ በመታየት ላይ የሚገኝ ስለመሆኑ አላከራከረም፡፡ በፍ/ብ/ሥ/ሥርዓት ህጉ አንቀጽ 418 መሠረት ያቀረበዉ አቤቱታ ዉድቅ የተደረገበት ሰዉ በንብረቱ ላይ ያለዉን መብት ለማረጋገጥ አዲስ ክስ ማቅረብ እንደሚችል የህጉ አንቀጽ 421 ድንጋጌ ያስገነዝባል፡፡ አመልካች በባጃጆቹ ላይ የቅድሚያ መብት አለኝ በሚል ያቀረበዉ መቃወሚያ ዉድቅ በመደረጉ ምክንያት በባጃጆቹ ላይ ያለዉን መብት በፍርድ ለማረጋገጥ ክስ ያቀረበዉም በዚህ ድንጋጌ መሠረት ነዉ፡፡ ስለሆነም ባጃጆቹ በእርግጥ የፍርድ ባለ ዕዳ (1ኛ ተጠሪ) ናቸዉ? ወይስ የአመልካች? የሚለዉ ጉዳይ ክሱ በቀረበበት መዝገብ ላይ ታይቶ እልባት ሊሰጥበት የሚገባ ጉዳይ ነዉ፡፡ ለፍርድ አፈፃጸም የሚዉል የፍርድ ባለዕዳዉ እንጂ የሦስተኛ ወገን ንብረት ካለመሆኑ አንፃር ሲታይ፣ ባጃጆቹ የፍርድ ባለዕዳዋ ስለመሆናቸዉ እራሱ ገና በፍርድ ሂደት ተጣርቶ ዉሳኔ የሚያገኝ እንጂ አሁን ላይ ባልታወቀበት ሁኔታ ከባጃጆቹ ጋር በተያያዘ ምክንያት በአመልካች ስም በባንክ በተቀመጠዉ ገንዘብ ላይ አግዶሙ እንዲቀጥል ማድረግ በኮ/መ/ቁጥር 227839 ላይ በመካሄድ ላይ ያለዉን ክርክር ዉጤት አልባ የሚያደርግ ነዉ፡፡ በመሰማት ላይ ያለዉን ክርክር መወሰን የሚቻለዉ በሌላ መዝገብ ላይ በመታየት ላይ ያለ ጉዳይ ዉሳኔ ሲያገኝ መሆኑ የተረጋገጠ እንደሆነ ፍርድ ቤቱ የያዘዉን መዝገብ በቀጠሮ ማቆየት እንደሚችል በፍ/ብ/ሥ/ሥርዓ ህጉ አንቀጽ 197(2) ላይ ተመልክቷል፡፡ የዚህ ድንጋጌ ዓይነተኛ ዓላማ በአንድ ጉዳይ ላይ የተለያዩ ምናልባትም የሚጋጩ ዉሳኔዎች እንዳይሰጡ ወይም በአንድ መዝገብ ላይ የሚሰጥ ትዕዛዝ/ዉሳኔ በሌላ መዝገብ ላይ በመታየት ላይ ያለዉ ክርክር ዉጤት አልባ እንዳይሆን በማድረግ የሥነ ሥርዓታዊ ፍትሕ፣ የወጥነት እና የተገማችነት መርሆዎች እዉን እንዲሆኑ ለማስቻል

እንደሆነ ይታመናል፡፡ ይህ ድንጋጌ እላዩ ላዩን ሲታይ አፈፃጸምን ሳይሆን በዋና ጉዳይ ላይ የሚታይ ክርክርን የሚመለከት ቢመስልም፣ በአፈፃጸም መዝገብ ላይ የሚሰጥ ትዕዛዝ/ውሳኔ በሌላ መዝገብ ላይ እየታየ ያለዉን ክርክር ዋጋ የሚያሳጣዉ መሆኑ ከተረጋገጠ ይህ ድንጋጌ በአፈፃጸም ጉዳይ ላይ ተፈፃሚ ሊሆን የማይችልበት ምክንያት የለም፡፡ በመሆኑም ምንም እንኳ በፍ/ብ/ሥ/ሥርዓት ህጉ አንቀጽ 421 መሠረት በቀረበ ክስ መነሻነት የሚሰጥ ዉሳኔ እስከሚታወቅ ድረስ በፍ/ብ/ሥ/ሥርዓት ህጉ አንቀጽ 418 መሠረት የሚቀርብ የመቃወም አቤቱታን ዉድቅ በማድረግ የሚሰጥ ዉሳኔ እንደጸና የሚቆይ ስለመሆኑ በድንጋጌዉ የተመለከተ ቢሆንም፣ ለመቃወም አቤቱታዉ ምክንያት የሆነዉን ንብረት በተመለከተ የቀረበ ክስ ታይቶ ዉሳኔ እስከሚሰጥ ድረስ በአፈፃፀም መዝገብ ላይ ንብረቱን አስመልክቶ የሚሰጥ ዉሳኔ/ትዕዛዝ በሂደት ላይ ያለዉን ክርክር ዉጤት የሚጎዳ መሆኑ ከተረጋገጠ ንብረቱን አስመልክቶ የቀረበ ክስ እልባት እስኪሰጠዉ ድረስ ንብረቱን በተመለከተ የሚሰጥ/የተሰጠ የአፈፃፀም ትዕዛዝ ለጊዜዉ ታግዶ እንዲቆይ የማይደረግበት ምክንያት የለም፡፡

ስለሆነም የስር ከፍተኛ ፍርድ ቤት ጉዳዩን ከዚህ አንፃር በማየት በኮ/መ/ቁጥር 227839 ላይ በመታየት ላይ ያለዉ ክርክር ዉጤቱ እስኪታወቅ ድረስ ከአመልካች የግል የባንክ ሂሳብ ላይ ገንዘብ ወጪ ተደርጎ እንዳይከፈል በፍት/ብ/ሥ/ሥርዓት ህጉ አንቀጽ 197(2) መሠረት ማቆየት ሲገባዉ ይህን ባለማድረግ ይባስ ብሎም ባጃጆቹ የ1ኛ ተጠሪ መሆን አለመሆናቸዉ ገና በአመልካች በቀረበዉ ክስ መሠረት ታይቶ እና ተጣርቶ ዉሳኔ የሚሰጥበት ሆኖ እያለ ባጃጆቹ የፍርድ ባለዕዳዋ ናቸዉ በሚል ድምዳሜ ላይ በመድረስ የሰጠዉ ዉሳኔ ገና በሌላ መዝገብ ላይ በክርክር ላይ ባለዉ ጉዳይ ከወዲሁ ዉሳኔ በመስጠት የፍርድ ሂደቱን ዉጤት አልባ የማድረግ ዉጤት ያለዉ ሲሆን የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤትም ይህን ማረም ሲገባዉ የከፍተኛ ፍርድ ቤቱን ዉሳኔ በማጽናት የሰጡት ዉሳኔ መሠረታዊ የክርክር አመራር ግድፈት የተፈጸመበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡ ስለሆነም ተከታዩ ተወስኗል፡፡

<u>ውሳኔ</u>

1. የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ. 167153 በቀን 28/03/2011 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ እና የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በይ/መ/ቁ. 166908 በቀን 30/01/2012 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ. 348(1) መሠረት ተሽረዋል፡፡

2. ለዚህ ክርክር መነሻ የሆኑት 154 ባለ ሦስት እግር ባጃጆች የፍርድ የፍርድ ባለዕዳዋ (1ኛ ተጠሪ) መሆን አለመሆናቸዉ የሚወሰነዉ በኮ/መ/ቁጥር 227839 ላይ በመታየት ላይ ባለዉ መዝገብ ላይ ነዉ ብለናል፡፡

3. በኮ/መ/ቁጥር 227839 ላይ በመታየት ላይ ያለ ክርክር ዉሳኔ እስከሚያገኝ ድረስ በአመልካች ስም የተቀመጠዉ እና የታገደዉ ገንዘብ ለ2-4ኛ ተጠሪዎች ባስፈረዱት የገንዘብ መጠን መቶኛ

ስሌት መሠረት እንዲያከፋፍሉ ለወጋገን ባንክ፣ ለዘመን ባንክ፣ ለህብረት ባንክ፣ ለቡና ባንክ፣ ለንብ ባንክ፣ ለዳሽን ባንክ፣ ለአዋሽ ባንክ፣ ለኢትዮጵያ ንግድ ባንክ፣ ለብርሃን ኢንተርናሽናል ባንክ እና ለአንበሳ ኢንተርናሽናል ባንክ የተላለፈ ትዕዛዝ ሳይፈጸም እንዲቆይ ተወስኗል፡፡

4. በዚህ ችሎት የተደረገው ክርክር ያስከተለውን ወጪ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡

ትዕዛዝ

- በዚህ ችሎት ትዕዛዝ መሠረት ከፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የቀረበዉ መ/ቁጥር 167153 በመጣበት አኳኋን ለፍርድ ቤቱ ይመለስ
- በዉሳኔዉ መሠረት እንዲፈጽም የዚህ ፍርድ እና ዉሳኔ ግልባጭ ለስር ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይድረስ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአራት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሠ/ኃ

የልዩነት ሃሳብ

ሥሜ በተራ ቁጥር 3 ላይ የተሰየምኩት ዳኛ ከአብላጫው ሃሳብ የተለየሁበትን ምክንያት እንደሚከተለው አስፍሬያለሁ፡፡

በመርሕ ደረጃ የተሠጠ ፍርድ በተቻለ ፍጥነት መፈጸም አለበት፡፡ ፍርድ ካልተፈጸመ የሕግ የበላይነትን ማረጋገጥ ሆነ ዜጎች ፍርድ ቤቶች ላይ እምነት እንዲኖራቸው ማድረግ አይቻልም፡፡ ፍርድ በሚፈጸምበት ጊዜም የሦስተኛ ወገኖች መብት ላይ ጉዳት እንዳይደርስ ተገቢውን ጥንቃቄ መደረግ ያለበት ስለመሆኑ ከፍትሐ ብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕጉ አቀራረጽ የምንረዳው ነው፡፡ የፍርድ ባለመብቱን ሆነ የሦስተኛ ወገኑን መብትና ጥቅም ማስታረቅ የሕጉ ዓላማ ሲሆን ለፍርድ ቤቶች ደግሞ ኃላፊነታቸው ነው፡፡ በፍብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 418 — 421 በተመለከቱት ድንጋጌዎች ደግሞ የሁለቱ ተጻራሪ የሚመስሉ ፍላጎቶችን የምንዳኝበት ሥርዓት ተዘርግቷል፡፡ ለአፈጻጸም በተከበረው ንብረት መያዝ መብቱን ተነክቷል የሚል ወገን ክርክሩን ከማስረጃ ጋር ማቅረብ እንዲችል የተፈቀደ መሆኑ የመደመጥ መብትን ያከበረ መሆኑን ያሳያል፡፡ የመደመጥ መብቱ ቢከብርም አፈጻጸም ክርክር በመሆኑ ደግሞ በቀጥታ ክስ ዳኝነት እንደተጠየቀበት ንብረት ሙሉ የሙግት ሂደትን የሚያልፍ ሥርዓት አለመሆኑን መገንዘብ ያስፈልጋል፡፡ ይህ አጭር ሥርዓት የፍርድ ባለመብቱን ሆነ የሦስተኛ ወገኑን መብትና ጥቅም አቻችሎ ለመሄድ የተዘረጋ ሲሆን አፈጻጸም ችሎቱ በሚሰጠው ብይን ይግባኝ የማለት መብት ሁሉቱም

ወገኖች ያላቸው ከመሆኑም በላይ በፍብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 418 ያቀረበው መቃወሚያ ውደቅ የተደረገበት ወገን በፍብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 421 መሠረት ንብረቱ ላይ ያለውን መብት ለማስከበር አዲስ ክስ የማቅረብ መብቱ ተጠብቋል።

አፈጻጸሙ በተከበረው ንብረት ላይ እየቀጠለ ባለበት ሁኔታ በተያዘው ንብረት ላይ በፍብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 421 መሠረት አዲስ ክስ ቢቀርብ የአፈጻጸም ሂደቱ ውጤት ምን ይሆናል የሚለው የዚህን ችሎት ምላሽ የሚፈልግ ጭብጥ ነው። አብላጫው ሃሳብ ጉዳዩን የተመለከተው ከፍብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 197(2) አኳያ ነው። የፍብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 197(2) አተገባበር በመሰማት ላይ ያለውን ጉዳይ ለመወሰን በሌላ ችሎት ወይም ፍርድ ቤት የተያዘ ክርክር ከተወሰነ በኋላ እንደሆነ ክርክሩን በማቆየት በሌላ ፍርድ ቤት የተያዘው ጉዳይ ውሳኔ ከተሰጠ በኋላ የተሠጠውን ውሳኔ ተመልክተን ክርክሩን የምንመራበት መንገድ የሚፈጥር ነው። በተያዘው ጉዳይ የአፈጻጸም ችሎቱ ጉዳዩን ተመልክቶ ውሳኔ ሰጥቶበት ያደረ ነው። አፈጻጸም ችሎቱ ውሳኔ ከሰጠ በኋላ ሌላ ክስ መኖሩ ውሳኔውን እንደገና ተመልሶ የሚሰጥበት ሥርዓት የሚፈጥር አይደለም። ክርክሩ ታግዶ እንዲቆይ ሕጉ ቢፈልግ ኖሮ በፍብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 418 ክርክር ተደርጎ ውሳኔ ከተሠጠ በኋላ አዲስ ክስ እንዲቀርብ ዕድል አይሰጥም ነበር። የፍብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 418 እና 421 ዓላማም መብት የሌለው ሠው ለአፈጻጸሙ መሠናክል እንዳይሆን ለመከላከልና መብት ያለው ሠውም የንብረት መብቱን የሚያስጠብቅበት ዕድል እንዳያጣ ማድረግ ነው። በመሆኑም አንዱ ጉዳይ ቀድሞ በተወሰነበት ደረጃ አፈጻጸም ችሎቱ ሌላ ክርክር የሚጠብቅበት ሥርዓት ስለማይኖር የፍብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 197(2) ለጉዳዩ ተፈጻሚነት የለውም። ጉዳዩ የአፈጻጸም ክርክርን የማገድ ውጤት ካለው መመርመር ያለበት የአፈጻጸም ክርክሩን በሕጉ ለማገድ የተመለከቱ ሁኔታዎች ምንድን ናቸው የሚለው ነው። ከፍብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 332 — 335 እና በቁጥር 377 ላይ የአፈጻጸም ክርክር የሚታገድበት ሥርዓት ተዘርግቷል። በፍብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 421 መሠረት በተከበረ ንብረት ላይ አዲስ ክስ ማቅረብ በሕጉ የአፈጻጸም ክርክር እንዲታገድ ሆነ በተከበረው ንብረት ላይ አፈጻጸሙ እንዳይቀጥል የሚያደርግ በቂ ምክንያት አይደለም።

ከዚህ ጋር ተያይዞ መታየት ያለበት ነጥብ በአፈጻጸም ሂደት የተከበረው ንብረት መሸጥ እና በፍብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 421 መሠረት አዲስ ክስ ያቀረበው ሠው በክሱ መሠረት የፍርድ ባለመብት ቢሆን የንብረት መብቱን እንዴት ያስከብራል የሚለው ነው። ከላይ እንደተመለከተው ፍርድ በተቻለ መጠን መፈጸም ያለበት በመሆኑ በተከበረው ንብረት ላይ ክስ መቅረቡ አፈጻጸሙን ለማቆም ሕጋዊ ምክንያት ሊሆን አይገባም። በፍብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 421 የመጨረሻ ዓረፍተ ነገር ላይም አዲስ የቀረበው ክስ ውጤቱ እስኪታወቅ ድረስ አፈጻጸም ችሎቱ ንብረቱን አስመልክቶ የሠጠው ውሳኔ የጸና ነው ማለቱ፤ ክስ ማቅረብ ብቻውን በተከበረው ንብረት የአፈጻጸም ሂደት ላይ ምንም ተጽዕኖ እንደሌለው ያስገነዝባል። ይሕም በፍብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 419 መሠረት ውሳኔ ከተሰጠ በኋላ በተከበረው ንብረት ላይ ያለውን የአፈጻጸም ሂደት መቀጠል የሚቻል መሆኑን ያሳያል። ክስ መቅረቡ የአፈጻጸም ክርክሩን ያቋርጣል

የሚለው ከሕጉ ዓላማ ውጭ ነው፡፡ አመልካች ተከብረው በነበሩት ባጃጆች ላይ መብት የለውም ተብሎ በአፈጻጸም ክርክር ጥያቄው ውደቅ የተደረገ በመሆኑ ባጃጆች ላይ ያለውን መብት ለማረጋገጥ አዲስ ክስ ማቅረቡ አፈጻጸሙን የሚያስቆም አይደለም፡፡

መብታቸውን ለማስከበር ክስ የሚያቀርቡ ሦስተኛ ወገኖች በክርክሩ ረቺ ከሆኑ ንብረቱን የመከተል መብት ያላቸው በመሆኑ በአፈጻጸም ሂደት ገዥ ከሆነውም ሠውም ማስመለስ ይችላሉ፡፡ አፈጻጸም ችሎትም የሐራጅ ማስታወቂያ ሲያወጣ ንብረቱ ላይ የይገባኛል መብት ቀርቦበት የነበረ ስለመሆኑ በመግለጽ ገዥ የሚገዛውን ንብረት ሁኔታ እንዲያውቅና በማናቸውም ጊዜ ንብረቱ ላይ መብት ያለው ሠው ሊጠይቀው እንደሚችል አውቆ እንዲወስን ማድረግ ይገባል፡፡ ይሕም ክስ ማቅረብ አፈጻጸም ላይ መሠናክል እንዳይሆን የሚከላከል ሲሆን በሌላ በኩል ንብረት ላይ መብት ያላቸው ሠዎችን መብት ለማክበርም ዕድል ይሰጣል፡፡ ሥለሆነም አመልካች ያቀረበው ክስ ውጤቱ ያልታወቀ ስለሆነ ስለመብቱ አፈጻጸም ክርክር ሊያቀርብ አይገባም፡፡ በሌላ በኩል አሁን የተያዘው ክርክር የቀረበው የባጃጆቹ ሽያጭ ገንዘብ ነው የተባለ በመታገዱና አመልካች እግዱ እንዲነሳለት አመልክቶ ውድቅ የተደረገበት በመሆኑ ነው፡፡ ይሕ የእግድ ትዕዛዝ አስቀድሞ የነበረውን በፍብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 418 መሠረት የተደረገው ክርክር ውጤት በመሆኑ እግዱ አይነሳም መባሉ ላይ የተፈጸመ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የለም በማለት በሃሳብ ተለይቻለሁ፡፡

የማይነበብ የአንድ ዳኛ ፊርማ አለበት

ሠ/ኃ

የወንጀል ህግ

የሰ/መ/ቁጥር 237423

መጋቢት 26 ቀን 2016 ዓ/ም

ዳኞች፡- ብርሃኑ አመነው

በዕውቀት በላይ

ቀነዓ ቂጣታ

ብርሃኑ መንግስቱ

ማርታ ተካ

አመልካች፡- የጦሳ ነጋዴዎች አጠቃላይ ንግድ ሥራ አክሲዮን ማኅበር

ተጠሪ፡- የኢፌዲሪ ፍትህ ሚኒስቴር - ዐቃቤ ሕግ

ጉዳዩ በሰባት ዳኞች የተለየ የህግ ትርጉም ስለማያስፈልገው አመልካች ካቀረቡት ሰበር አቤቱታ አንጻር የግራቀኙን ክርክር መሰረት በማድረግ ተገቢውን ውሳኔ እንዲሰጥበት በተመራው መሰረት ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር ባለ መልኩ ሲታይ፡- ክርክሩ የተጀመረዉ በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት በደቡብ ወሎ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ሆኖ የአሁን ተጠሪ ተወካይ የነበረዉ የአማራ ብሔራዊ ክልል ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ በአሁን አመልካችና የአመልካች ሥራ አስኪያጅ እና ሠራተኛ በሆኑት ላይ ሁለት ክሶችን መስርቷል፡፡

አንደኛው ክስ በአመልካች ድርጅት ሥራ አስኪያጅ እና የጥበቃ ሠራተኛ ላይ ሲሆን በወንጀል ሕግ አንቀጽ 32(1/ሀ) እና በፌዴራል ታክስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 983/2008 አንቀጽ 120/1 ላይ የተደነገገዉን በመተላለፍ ያለደረሰኝ ግብይት በማከናወናቸው ያለደረሰኝ ግብይት በመፈጸም ወንጀል ተከሰዋል የሚል ሲሆን ሁለተኛው ክስ ደግሞ አመልካች በሆነው ድርጅት ላይ ሲሆን የክሱ ይዘትም አመልካች በወንጀል ሕግ አንቀጽ 34/1 እና በፌዴራል ታክስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 983/2008 አንቀጽ 120/1 ስር የተደነገገዉን በመተላለፍ ደረሰኝ የመስጠት ግዴታ እንዳለበት እያወቀ በቀን 10/03/2013 ዓ/ም ከምሽቱ በግምት 1፡00 ሰዓት በደሴ ከተማ ሆጤ ክፍለ ከተማ መናኸሪያ አካባቢ በሚገኘዉ ጦሳ ቁጥር 1 መኝታ ቤት ደንበኛ የሆኑት ግለሰብ ለተከራዩት አልጋ ደረሰኝ ባለመስጠቱ በፈጸመዉ ያለደረሰኝ ግብይት መፈጸም ወንጀል ተከሷል የሚሉ ናቸው፡፡

ለአመልካችና ለስር ተከሳሾች የክስ ማመልከቻዉ በጠበቃቸዉ በተወከሉበት እንዲደርሳቸዉ ተደርጎ ተነብቦላቸዉ አመልካች በጠበቃዉ አማካኝነት ባቀረበዉ የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ይህ የወንጀል ክስ ከመቅረቡ በፊት የገቢዎች ሚኒስቴር ኮምቦልቻ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት በዚሁ ጉዳይ በአመልካች ላይ

አስተዳደራዊ ክስ ስለወሰነብኝ በድጋሚ ልከሰስ አይገባም በማለት ቢቃወምም ፍርድ ቤቱም አመልካች አስተዳደራዊ ቅጣት መቀጣቱ የወንጀል ክስ እንዳይቀርብበት አያደርግም በማለት መቃወሚያዉን ዉድቅ ካደረገ በኋላ ተከሳሾች የእምነት ክህደት ቃላቸዉን እንዲሰጡ ጠይቋቸዉ ጥፋተኛ አይደለንም በማለት ክደዉ በመከራከራቸዉ ፍርድ ቤቱ የዐቃቤ ሕግ ምስክሮች ሰምቶ ምስክሮች የሰጡት ቃል እና የሰነድ ማስረጃዎችን መርምሮ አመልካች የተጨማሪ እሴት ታክስ(ተ.እ.ታ) ተመዝጋቢ መሆኑን የሰነድ ማስረጃ የሚያሳይ መሆኑን፤ የአመልካች የጥበቃ ሠራተኛ የመኝታ አገልግሎት ፈልጎ ለመጣዉ ለአመልካች ደንበኛ አልጋ በማስያዝ ብር 120.00 ተቀብሎ ደረሰኝ ሳይሰጥ ግብይት መፈጸሙ ተመስክሯል፣ደንበኛዉም አልጋ መያዛቸዉን የሚያሳይ የእንግዶች መመዝገቢያ ፎርም የቀረበ መሆኑን ጠቅሶ ዐቃቤ ሕግ እንደ ክስ አቀራረቡ ያስረዳ በመሆኑ አመልካችን ጨምሮ የስር ተከሳሾች እያንዳንዳቸው ክሱን እንዲከላከሉ ብይን ሰጥቷል፡፡

የስር ፍርድ ቤት የተከሳሾችን መከላከያ ምስክሮች ከሰማ በኋላ የግራ ቀኙን ምስክሮች ቃልና የሰነድ ማስረጃዎችን መርምሮ በመ/ቁጥር 20586 ላይ በቀን 24/06/2014ዓ/ም በሰጠዉ ፍርድ፡- የአመልካች ሥራ አስኪያጅ የነበሩት የስር 1ኛ ተከሳሽ ወንጀሉ በተፈጸመበት ጊዜ በህመም ምክንያት እረፍት ላይ መሆናቸዉን በማስረዳት ክሱን መከላከላቸዉን በመግለጽ በነጻ እንዲሰናበቱ ሲወስን፤ የስር 2ኛ ተከሳሽ የነበሩት ምንም እንኳን በድርጅቱ የሥራ ድርሻቸዉ ጥበቃ ቢሆንም አልጋ በማስያዝ ገንዘብ ለመቀበል ፈቅደዉ ለሰሩት ሥራ ደረሰኝ የመስጠት ሕጋዊ ግዴታ ያልተወጡ መሆኑን በዐቃቤ ህግ የተመሰከረባቸዉን በማስተባበል ስላልተከላከሉ ጥፋተኛ ናቸዉ በማለት የጥፋተኝነት ፍርድ ሰጥቷል እንዲሁም የአሁን አመልካችን በሚመለከትም ታክስ ከፋይ የሆነ ሕጋዊ ሰዉነት ያለዉ ድርጅት በመሆን የአገልግሎት ግብይት ሲፈጽም ደረሰኝ የመስጠት ሕጋዊ ኃላፊነት እያለበት ደረሰኝ ሳይሰጥ ግብይት መፈጸሙ በማስረጃ የተረጋገጠበትን በማስተባበል ስላልተከላከለ በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 34/1 እና በአዋጅ ቁጥር 983/2008 አንቀጽ 120/1 ስር ጥፋተኛ ነዉ በማለት ፍርድ በመስጠት የግራ ቀኙን የቅጣት አስተያየት በመመርመር አመልካች በብር 30,000.00 (ሰላሳ ሺህ ብር) የገንዘብ መቀጮ እንዲቀጣ ወስኗል፡፡

አመልካች ይህንኑ ዉሳኔ በመቃወም ለአማራ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ያቀረበው ይግባኝ አቀርቦ በመ/ቁጥር 0207905 ላይ በቀን 15/07/2014ዓ/ም በሰጠዉ ትእዛዝ ይግባኙን በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 195/1 መሰረት ሰርዞበታል፡፡ በመቀጠል የሰበር አቤቱታዉን ለአማራ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ቢያቀርብም ጉዳዩ የፌዴራል ጉዳይ በመሆኑ አቤቱታ የቀረበበትን የመጨረሻ ዉሳኔ በሰበር ለመመርመር ሥልጣን የለኝም በማለት በመ/ቁጥር 0335004 በቀን 16/02/2015ዓ/ም ወስኗል፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበውም ይህንኑ የበታች ፍርድ ቤቶች ውሳኔ በመቃወም ነው፡፡

አመልካች በጠበቃዉ አማካኝነት በቀን 19/03/2015 ዓ/ም የተዘጋጀ ለዚሁ ሰበር ችሎት ያቀረቡት ሰበር አቤቱታ ይዘቱ አጠር ባለ መልኩ ሲታይ፡- አመልካች ከዚህ ቀደም በዚሁ ጉዳይ አስተዳደራዊ ዉሳኔ ተላልፎበት በብር 15,000.00 ተቀጥቶ እያለ በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 23 እና በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 2/5 ስር የተደነገገዉን በሚቃረን አኳኋን በዚያዉ ድርጊት ለሁለተኛ ጊዜ ተከሶ መቀጣቱ ተገቢ አለመሆኑን፤ አመልካች ድርጅት ሕጋዊ ሰዉነት ያለዉ ግኡዝ በመሆኑ ሥራዉን የሚመራዉ፣ የሚያንቀሳቀስዉና የሚያስተዳድረዉ በቀጠራቸዉ ሠራተኞች አማካኝነት ሲሆን የድርጅቱ ሥራ አስኪያጅ የሆነው ስር 1ኛ ተከሳሽ ድርጊቱ በተፈጸመበት ጊዜ በቦታዉ አልነበረም ተብሎ ከወንጀሉ በነጻ ሲሰናበት አመልካች የሆነው ድርጅት ግን በማያዉቀዉና ባልፈጸመዉ ድርጊት ያለደረሰኝ ግብይት ፈጽመሃል ተብሎ ጥፋተኛ ተብሎ መቀጣቱ ተገቢ አለመሆኑ፤ አመልካች ወደ ድርጅቱ የሚመጡ እንግዶች ደረሰኝ ሳይቀበሉ ክፍያ እንዳይፈጽሙ ማስታወቂያ ግልጽ ቦታ በለጠፈበት ሁኔታ በወንጀል ተጠያቂ ሊሆን ስለማይገባ ፍርድ ቤቶች ዉሳኔ እንዲሻር በመጠየቅ ተከራክሯል፡፡

የሰበር አጣሪ ችሎቱም የአመልካችን ሰበር አቤቱታ መርምሮ፡- አመልካች ድርጅት ያለደረሰኝ ግብይት ፈጽሟል ተብሎ በአስተዳደር ብር 15,000.00 እንዲከፍል በተደረገበት ሁኔታ በወንጀል ተከሶ ጥፋተኛ ተብሎ በብር 30,000.00 የገንዘብ መቀጮ እንዲቀጣ የተወሰነበትን አግባብነት ከወንጀል ሕጉ አንቀጽ 2/5 እና ጥፋተኛ ከተባለበት አዋጅ ቁጥር 983/2008 አንቀጽ 120/1 ጋር ተገናዝቦ ተጠሪ ባለበት ለመመርመር ሲባል ተጠሪ መልስ እንዲሰጥበት ተደርጓል፡፡

ተጠሪ በቀን 05/07/2015 ዓ/ም ጽፎ የሰጠው መልስ ይዘቱ፡- አስተዳደራዊ ቅጣትና የወንጀል ቅጣት ራሳቸዉን ችለዉ የሚቆሙ ስለሆኑ በአመልካች ላይ የወንጀል ቅጣት መወሰኑ የሕገ መንግሥቱን አንቀጽ 23 እና የወንጀል ሕጉን አንቀጽ 2/5ን የወንጀል ክስንና ጥፋተኝነትን የሚመለከት እንጂ አስተዳደራዊ ቅጣትን የሚመለከት ባለመሆኑ ዉሳኔዉ እነዚህን ድንጋጌዎች የሚቃረን ስላልሆነ የሰበር አቤቱታዉ ዉድቅ ሊደረግ ይገባል በማለት ተከራክሯል፡፡ አመልካችም የሰበር አቤቱታውን በማጠናከር የመልስ መልስ በመስጠት ተከራክሯል፡፡

የግራ ቀኙ ክርክር ከተጠናቀቀ በኋላ ጉዳዩን በሚመረመርበት ጊዜ ተጨማሪ ጭብጥ መመስረት “አመልካች በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 34/1 እና በፌዴራል ታክስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 983/2008 አንቀጽ 120/1 ስር የተደነገገዉን በመተላለፍ ያለደረሰኝ ግብይት ፈጽሟል በሚል የተከሰሰዉና ጥፋተኛ ተብሎ የተቀጣዉ በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 34/1 አነጋገር መሰረት ሕጋዊ ሰዉነት የተሰጠዉ ድርጅት ያለደረሰኝ ግብይት ከፈጸመ በወንጀል ተጠያቂ እንደሚሆን በፌዴራል ታክስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 983/2008 በግልጽ መደንገጉ ተረጋግጦ ነዉ ወይስ አይደለም? የሚለዉን ከዚህ ቀደም በሰ/መ/ቁጥር 48850፣58008 ፣69899፣74237፣፣94913 እና በሌሎችም መዛግብት ላይ ከተሰጡ የሕግ ትርጉሞች

ጋር በማገናዘብ መመርመር ይቻል ዘንድ ለተጠሪ ደርሶት ተጨማሪ በተያዘው ጭብጥ ላይ ግራቀኙ በጽሁፍ ክርክራቸውን እንዲለዋወጡ ተደርጓል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን ይህ ችሎትም ጉዳዩ ለሰበር ችሎቱ ሲቀርብ በሰበር አጣሪው ከተያዘው ጭብጥ አንጻር በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡

አመልካች በጉዳዩ ላይ በድጋሚ ሊቀጣ አይገባም በሚል የሚከራከሩበት ምክንያት ድርጅቱ ከዚህ ቀደም በዚሁ ጉዳይ በአስተዳደራዊ ዉሳኔ በብር 15,000.00 ተቀጥቶ እያለ ለሁለተኛ ጊዜ በወንጀል ተከሶ ብር 50000(ሀምሳ ሺህ ብር) እንዲቀጣ መወሰኑ ተገቢነት የለውም በሚል ነው፡፡ አመልካች ከሆነው ድርጅት ክርክር መገንዘብ የሚቻለው አመልካች በአንድ ጉዳይ ሁለት ጊዜ ልቀጣ አይገባም በማለት በአንድ ወንጀል ድጋሚ ቅጣት የሚከለክለውን የኢ.ፌ.ድ.ሪ ሕገ መንግስት አንቀጽ 23 ድንጋጌንና በዚህ ረገድ ተቀባይነት ያለውን የወንጀል ሕግ አንቀጽ 2(5) ድንጋጌ ፅንሰ ሀሳብ መሰረት በማድረግ የሚከራከሩ መሆኑን ነው፡፡ ይህ ሰበር ችሎትም የተጠቀሰው የህገ መንግስት ድንጋጌ እና ወንጀል ሕግ ጽንስ ሀሳብ ለዚህ ጉዳይ አግባብነት ያለው መሆን አለመሆኑን ተመልክቷል፡፡ በዚህም መሰረት ማንኛውም ሰው በወንጀል ሕግና ሥነ ሥርዓት መሰረት ተከሶ የመጨረሻ በሆነ ውሳኔ ጥፋተኝነቱ በተረጋገጠበት ወይም በነፃ በተለቀቀበት ወንጀል እንደገና የማይከሰስ ወይም የማይቀጣ መሆኑን ከወንጀል ህጉ ጽንሰ ሃሳብ መገንዘብ የሚቻል ሲሆን በኢ.ፌ.ድ.ሪ ሕገ መንግስትም ይህንኑ በግልጽ ተመልክቶ ይገኛል፡፡ ከዚህም መረዳት እንደሚቻለው በአንድ ወንጀል ድጋሚ ቅጣት የተከለከለው የመጨረሻ ውሳኔ በሆነ ጥፋተኝነቱ በተረጋጠበት ወይም በነፃ በተለቀቀበት ወንጀል እንደሆነ መገንዘብ ያስፈልጋል፡፡

እንደሚታወቀው በወንጀል ሕጉ ምዕራፍ አንድ አንቀጽ 3 ይህ የወንጀል ሕግ ቢኖርም ቅጣት የሚደነግጉ ደንቦችና ልዩ ሕጎች የተጠበቁ ናቸው፤ በእነዚህ ደንቦችና ሕጎች ላይ በተለየ አኳሃን ካልተደነገገ በቀር የዚህ ሕግ መርሆዎች ለእነርሱም ተፈጻሚ ይሆናሉ በማለት ይደነግጋል፡፡

አመልካች በተከሰሱበት የታክስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 983/2008 በዚሁ አዋጅ ክፍል አስራ አምስት ምእራፍ አንድ ስር ስለ አስተዳደራዊ ቅጣቶችንና የወንጀል ሀላፊነቶችን የሚመለከቱ ጠቅላላ ድንጋጌዎች በተመለከተ አንድን ድርጊት መፈጸም ወይም አለመፈጸም አስተዳደራዊ ቅጣት እና የወንጀል ሀላፊነትን የሚያስከትል በሚሆንበት ጊዜ ጥፋቱን የፈጸመው ሰው አስተዳደራዊ ቅጣት መቀጣቱ የወንጀል ተጠያቂነቱን እንደማያስቀር በዚሁ አንቀጽ 100 ንኡስ አንቀጽ 1 ስር በግልጽ ተደንግጓል፡፡

በዚሁ አዋጅ ክፍል አስራ አምስት ምእራፍ ሁለት ስር ባሉት ድንጋጌዎች ስለ አስተዳደራዊ ቅጣቶችን የሚደነግጉ ሲሆን በምእራፍ ሦስት ስር ደግሞ ስለ ታክስ ወንጀሎች እና የሚስቀጡት ቅጣት መጠን በግልጽ ተለይተው ተደንግገው ይገኛሉ፡፡ አመልካች የሆነው ድርጅት የተከሰሰው ያለደረሰኝ ግብይት መፈፀም ወንጀል ተላልፏል በሚል ሲሆን በታክስ አስተዳደር አዋጁ አንቀጽ 108 ስር የታክስ ደረሰኝ

አለመስጠት በአስተዳደራዊ የገንዘብ ቅጣት እንደሚያስቀጣ የሚያስቀምጥ ሲሆን ከዚህም በተጨማሪ በአዋጁ አንቀጽ 120(1) ማንኛውም ደረሰኝ የመስጠት ግዴታ ያለበት ታክስ ከፋይ ያለደረሰኝ ግብይት ያከናወነ እንደሆነ ከብር 25,000 እስከ ብር 50,000 የገንዘብ መቀጫ እና ከሶስት እስከ አምስት ዓመት በሚደርስ ጽኑ እሥራት እንደሚያስቀጣ ተደንግጓል፡፡

ከዚህም መረዳት እንደሚቻለው ደረሰኝ የመስጠት ግዴታ ያለበት ታክስ ከፋይ የሆነ ድርጅት ያለደረሰኝ ግብይት ፈጽሞ በተገኘ ጊዜ በአዋጁ መሰረት በአስተዳደራዊ ውሳኔ ከሚያስከትለው ቅጣት በተጨማሪ የወንጀል ተጠያቂነት የሚያስከትል ስለመሆኑ በግልጽ በህጉ በተደነገገ ጊዜ በአስተዳደራዊ ውሳኔ መቀጣት የወንጀል ተጠያቂነት ሊያስቀር የሚችል ካለመሆኑም በላይ በአንድ ወንጀል ድጋሚ ቅጣት የመከልከልን ጥያቄ የሚያስነሳ ሊሆንም አይችልም፡፡ በአንድ ወንጀል ድጋሚ ቅጣት የመከልከል ጥያቄ ሊነሳ የሚችለው በፍርድ ቤት ጉዳዩ ታይቶ ተገቢ ነው የተባለው ውሳኔ በተሰጠበት ጉዳይ በድጋሚ በዚሁ ጉዳይ በወንጀል የተከሰሰ መሆኑ ሲረጋገጥ ነው፡፡ በመሆኑም ድርጅቱ በአስተዳደራዊ ውሳኔ ተቀጥቶ እያለ በድጋሚ በወንጀል ሊቀጣ አይገባም በሚል አመልካች ያነሱት የሕግ ክርክር ስለድጋሚ ቅጣት ክልከላ መርህ (principle of double jeopardy) የተቀመጡትን መመዘኛዎች የሚያሟላ ባለመሆኑ ተቀባይነት ያለው ሁኖ አላገኘነውም፡፡

ሌላው አመልካች በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 34/1 እና በፌዴራል ታክስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 983/2008 አንቀጽ 120/1 ስር የተደነገገዉን በመተላለፍ ያለደረሰኝ ግብይት ፈጽሟል በሚል የተከሰሰዉና ጥፋተኛ ተብሎ የተቀጣዉ በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 34/1 አነጋገር መሰረት ሕጋዊ ሰዉነት የተሰጠዉ ድርጅት ያለደረሰኝ ግብይት ከፈጸመ በወንጀል ተጠያቂ እንደሚሆን በፌዴራል ታክስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 983/2008 በግልጽ መደንገጉ ተረጋግጦ ነዉ ወይስ አይደለም? የሚለዉን ከዚህ በፊት በሰ/መ/ቁጥር 48850፣58008 ፣69899፣74237፣94913 እና በሌሎች መዝገቦች ከተሰጡት ውሳኔዎች አንጻር በሰባት ዳኛ እንዲታይ የተመራ ቢሆንም ተጨማሪ ተደርጎ በተያዘው ጭብጥ ላይ የተለየ ትርጉም መስጠት ያስፈልጋል ወይስ አያስፈልግም በሚለው ላይ በሰባት ዳኛ ታይቶ አመልካች የተከሰሱበት አዋጅ ቁጥር 983/2008 አንቀጽ 120/1 ያለደረሰኝ ግብይት መፈጸም ወንጀል ሕጋዊ ሰዉነት የተሰጠዉ ድርጅት ያለደረሰኝ ግብይት ፈጽሞ በተገኘ ጊዜ ድርጅቱ በወንጀል ተጠያቂ የሚያደርግ መሆኑን የዚሁ አዋጅ አንቀጽ 132/1 ድንጋጌ የህግ ሰውነት የተሰጠው ድርጅት የወንጀል ተጠያቂነት ለማስቀረት የተደነገገ ድንጋጌ አለመሆኑን ህጋዊ ሰውነት የተሰጠው ድርጅት ያለደረሰኝ ግብይት ፈጽሞ በተገኘ ጊዜ አዋጁን መሰረት በማድረግ በወንጀል ተጠያቂ ሊሆን እንደሚችል ተጠቅሶ ከዚህ በፊት በዚህ አግባብ የተሰጡ የሕግ ትርጉሞች ለመለወጥም ሆነ ለማሻሻል የሚያስችል ህጋዊ ምክንያት ባለመኖሩ የተለየ የሕግ ትርጉም አያስፈልገውም በማለት በዚሁ መዝገብ በሰባት ዳኛ በ29/6/2016ዓ.ም አብላጫ ድምጽ ፍርድ የተሰጠበት በመሆኑ ተጨማሪ ተደርጎ የተያዘው ጭብጥ በድጋሚ ማየቱ አስፈላጊ ሆኖ አላገኘነውም፡፡

ሲጠቃለል አመልካች የሆነው ድርጅት ያለደረሰኝ ግብይት የፈፀመ መሆኑ በሰውና ሰነድ ማስረጃ ተረጋግጦ በስር ፍርድ ቤቶች ጥፋተኛ ተብሎ በገንዘብ እንዲቀጣ መወሰኑ በፌደራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀጽ 2/4) እና አንቀጽ 10 (1) መሰረት መሰረታዊ የሕግ ስህተት መፈፀሙን የሚያሳይ ሆኖ ስላላገኘነው ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

ውሳኔ

1. የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የደቡብ ወሎ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ 20586፤ የካቲት 24 ቀን 2014ዓ.ም የሰጠው ፍርድ፤ ይህንኑ ፍርድ በማጽናት የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመ/ቁ 0207905፤ መጋቢት 15 ቀን 2014ዓ.ም የሰጠው ትእዛዝ በፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት የሰበር ስነ- ስርአት መመሪያ ቁጥር 17/2015 አንቀጽ 9/1 መሰረት ፀንቷል፡፡
2. በዚህ ፍ/ቤት ለተደረገዉ ክርክር ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸዉን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የሶስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ብ/ም

የመስማሚያ ሀሳብ

በተራ ቁጥር 2 እና 4 ላይ የተሰየምን ዳኞች በአብላጫ ድምጽ በቀን 26/07/2016ዓ/ም በዋለዉ ችሎት በተሰጠዉ የፍርድ ዉሳኔ ላይ የሚከተለዉን የመስማሚያ ሀሳብ አስፍረናል፡፡

አመልካች በታክስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 983/2008 አንቀጽ 120/1ን ተላለፏል ተብሎ በዚህኛዉ የወንጀል ክስ ተከሶ ጥፋተኛ ተብሎ ከመቀጣቱ በፊት በዚህ ክስ በተከሰሰበት ድርጊት ከዚህ ቀደም በሌላ የወንጀል ክስ ተከሶ ጥፋተኛ ተብሎ ስለመቀጣቱ ወይም በነጻ ስለመሰናበቱ በመግለጽ ያቀረበዉ ክርክር የለም፡፡የአመልካች ክርክር የወንጀል ክስ በቀረበብኝ ድርጊት አስተዳደራዊ ቅጣት ተቀጥቻለሁ የሚል ነዉ፡፡በአዋጅ ቁጥር 983/2008 አንቀጽ 100/1 ስር አስተዳደራዊ ቅጣት መቀጣት የወንጀል ተጠያቂነትን አያስቀርም በሚል ተደንግጓል፡፡በኢፌዲሪ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 23 ስር የተደነገገዉ መብት በአንድ የወንጀል ድርጊት ለሁለተኛ ጊዜ በወንጀል መከሰስንና ድጋሚ ቅጣትን የሚከለክል መብት የሚሰጥ እንጂ አስተዳደራዊ ቅጣት የተቀጣ ሰዉ በወንጀል ተጠያቂ አይሆንም የሚል አይደለም፡፡

በመሆኑም ከዚህ ጭብጥ አኳያ አመልካች ያቀረበዉ ክርክር ዉድቅ ተደርጎ በአብላጫ ድምጽ በቀን 26/07/2016ዓ/ም በዋለዉ ችሎት በተሰጠ ድምዳሜ እንስማማለን፡፡ሆኖም በቀን 29/06/2016 ዓ/ም በዋለዉ ችሎት ባሰፈርነዉ የልዩነት ሀሳብ ላይ አመልካች የተከሰሰበት የአዋጅ ቁጥር 983/2008 አንቀጽ 120/1 የሕግ ሰዉነት የተሰጠዉ ድርጅት በወንጀል ተጠያቂ እንደሚሆን የተደነገገበት ባለመሆኑ

አመልካች በዚህ ድንጋጌ ተከሶ ጥፋተኛ ተብሎ በገንዘብ እንዲቀጣ መወሰኑ ሊታረም የሚገባዉ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ስለሆነ የስር ፍርድ ቤቶች የሰጡት ዉሳኔ ተሽሮ አመልካች በተከሰሰበት ድርጊት የወንጀል ተጠያቂነት የለበትም ተብሎ ሊወሰን ይገባል በማለት በሀሳብ ስለተለየን ይህንኑ ከግምት በማስገባት የመስማማቲያ ሀሳባችንን አስፍረናል፡፡

የማይነበብ የሁለት ዳኞች ፊርማ አለበት

ብ/ም

አሥሪ እና ሰራተኛ

የሰ/መ/ቁ. 202393

ጥቅምት 03 ቀን 2014 ዓ.ም

ዳኞች፡- ብርሀኑ አመነው

ተሾመ ሽፈራው

ሀብታሙ እርቅይሁን

ብርሀኑ መንግስቱ

ነፃነት ተገኝ

አመልካች፡- የኢትዮጵያ ወንጌላዊት ቤተ-ክርስቲያን መካነ ኢየሱስ - ነገረ ፈጅ ጌታቸው ባጫ - ቀርበዋል

ተጠሪ፡- ወ/ሮ አይናበባ ተፈራ - አልቀረቡም

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የስራ ስንብትን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ በተጀመረበት በምዕራብ ሐረርጌ ጭሮ ወረዳ ፍርድ ቤት አመልካች ተከሳሽ፣ ተጠሪ ደግሞ ከሳሽ በመሆን ተከራክረዋል፡፡ ተጠሪ በቀን 15/03/2012 ዓ.ም ጽፈው ባቀረቡት ክርክር በአመልካች ድርጅት ውስጥ ከቀን 05/01/2010 ዓ.ም ጀምሮ በወር ብር 4,558.00 እየተከፈልኝ ስሰራ ቆይቻለሁ፡፡ በዚህ ጊዜ ውስጥም ስራዬን ህግን ተከትዬ ስሰራ ብቆይም የድርጅቱ ስራ አስኪያጅ በተደጋጋሚ የፋይንናስ ህግ በመጣስ ሀሰተኛ እና ስርዝ ድልዝ ያለበትን ሰነድ በማዘጋጀት ሂሳብ እንዲወራረድ ትዕዛዝ ሲሰጠኝ በህግ ስለሚያስጠይቀኝ ትዕዛዙን አልተቀበልኩም፡፡ በዚህም ምክንያት ትዕዛዝ አትቀበልም በማለት ከቀን 05/02/2012 ዓ.ም ጀምሮ ከስራ የተሰናበትኩ መሆኑን በሚገልጽ ደብዳቤ የስራ ዉሌን በህገ-ወጥ መንገድ አቋርጦታል፡፡ ስለሆነም ወደ ስራዬ እንድመለስ ወይም ከህገ ወጥ ስንብት ጋር የተያያዙ ልዩ ልዩ ክፍያዎችን በጠቅላላው ብር 78,110.20 እንዲከፈለኝ ይወሰንልኝ በማለት ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡

አመልካች በበኩሉ በቀን 02/04/2012 ዓ.ም በተፃፈ መልስ ከአመልካች ጋር የስራ ውል ግንኙነት የለኝም፤ ደመወዝ እየከፈልን አላሰራናትም፤ ቀጣሪዋ የኢትዮጵያ ወንጌላዊት ቤተ-ክርስቲያን መካነ ኢየሱስ የልማትና ማህበራዊ አገልግሎት ኮሚሽን ማዕከላዊ ኢትዮጵያ ሲኖዶስ ድሬዳዋ ቅርንጫፍ ነው በማለት የመጀመሪያ መቃወሚያ ያቀረበ ሲሆን በፍሬ ነገሩ ላይ በሰጠው መልስ ደግሞ በተጠሪ ላይ የፈፀምነው ምንም አይነት በደል የለም፤ ተጠሪ በሌላ መስሪያ ቤት ተቀጥራ የምትሰራ በመሆኑ በ15 ቀናት ውስጥ ከዚያ መስሪያ ቤት መልቀቂያ እንድታመጣ፣ ካላመጣች ግን ስራዋን በራሷ ፍቃድ እንደለቀቀች እንደሚቆጠር ከቀጠራት አካል ደብዳቤ ቢሰጣትም ባለማቅረቧ ከስራዋ ተሰናብታለች፤

ከዚህም ባለፈ ተጠሪዋ ህግ በመጣስ በተደጋጋሚ ጥፋት የምትፈጽምና የተሰጣትን የቃል ማስጠንቀቂያ የማታከብር በመሆኗ ከስራ የተሰናበተች በመሆኑ ክሱ ውድቅ ሊደረግ ይገባል በማለት ተከራክሯል፡፡

ጉዳዩ የቀረበለት የወረዳዉ ፍርድ ቤትም የግራ ቀኙን ክርክር እና ማስረጃ ከመረመረ በኋላ አመልካች ተጠሪን ያሰናበተዉ በህገ-ወጥ መንገድ ስለሆነ ከጥቅምት ወር 2012 ጀምሮ ያልተከፈላት ደመወዝ ተከፍሏት ወደ ስራ ትመለስ በማለት ወስኗል፡፡ አመልካች በዚህ ውሳኔ ባለመስማማት ይግባኙን ለዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርቦ ግራ ቀኙ ከተከራከሩበት በኋላ ተጠሪ ከስራ የተሰናበተችው በአመልካች ድርጅቱ ውስጥ የሚሰሩ ሰራተኞችን በመሳደቧና አምባገሮ በመፍጠሯ ስለመሆኑ በማስረጃ ተረጋግጧል፤ ይህም ስንብቱን ህጋዊ ያደርገዋል በማለት የወረዳ ፍርድ ቤቱ የሰጠውን ውሳኔ በአብላጫ ድምጽ ሽሮታል፡፡ ተጠሪ በበኩሏ በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት አቤቱታ ያቀረበች ሲሆን ችሎቱም ጉዳዩ ያስቀርባል በማለት ግራ ቀኙን ካከራከረ በኋላ አመልካች ተጠሪ የስነ-ምግባር ጥፋት መፈፀሟን በስነ-ምግባር ኮሚቴ ያልተረጋገጠ ከመሆኑም በላይ ስንብቱም የተፈጸመዉ የስነ ምግባር ጥሰት መፈጸሟን የሚሳይ ማስጠንቀቂያ በአመልካች ከተፃፈላት ከ30 ቀን በኋላ መሆኑ ስንብቱን ህገ ወጥ ያደርገዋል በማለት ከጥቅምት ወር 2012 ዓ.ም ጀምሮ የስድስት ወር ውዝፍ ደመወዝ በመክፈል አመልካች ተጠሪን ወደ ስራዋ ይመልሳት በማለት የከፍተኛ ፍርድ ቤቱን ውሳኔ ሽሮታል፡፡ ለዚህ ፍርድ መነሻ የሆነው የሰበር አቤቱታ በአመልካች የቀረበውም ይህንኑ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡

አመልካች በቀን 08/06/2013 ዓ.ም በተፃፈ 02 ገጽ የሰበር አቤቱታ በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት እና በወረዳ ፍርድ ቤቱ ተፈጽመዋል ያላቸውን ስህተቶች በመዘርዘር በዚህ ችሎት እንዲታረምለት ጠይቋል፡፡ የአቤቱታው ይዘትም የወረዳ ፍርድ ቤቱ እና የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ተጠሪ በተመሳሳይ ሰዓት ለሁለት መስሪያ ቤት እየሰራች ምንም አይነት ጥፋት እንዳልፈፀመች በመቁጠር ስንብቱን ህገ-ወጥ ነው ማለታቸው፤ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ተጠሪ የፈፀመችው ለሃላፊ ያለመታዘዝና በስራ ቦታ አምባገሮ መፍጠር ጥፋት ያለማስጠንቀቂያ ከስራ የሚያሰናብት ሆኖ እያለ ጉዳዩ በዲሲፕሊን ኮሚቴ መታየት ነበር ማለቱ መሠረታዊ የህግ ስህተት በመሆኑ ሊታረም ይገባል የሚል ነው፡፡

ጉዳዩም በሰበር አጣሪ ችሎት ተመርምሮ ተጠሪ በቋሚነት ሁለት ቦታ እንደምትሰራ አመልካች አስረድቶ እያለ እና ተጠሪም ይህንን ባልካደችበት ስንብቱ ህገ-ወጥ ነው ተብሎ የመወሰኑ አግባብነት መጣራት ያለበት መሆኑ ስለታመነበት ለዚህ ሰበር ችሎት ቀርቧል፡፡ በዚሁም መሠረት ተጠሪ መልስ እንድትሰጥበት ተደርጎ በቀን 24/07/2013 ዓ.ም ጽፋ ባቀረበችው መልስ በስር ፍርድ ቤቶች የተከራከርኩት አሁን የሰበር አቤቱታ ካቀረበው የኢትዮጵያ ወንጌላዊት ቤተ-ክርስቲያን መካነ እየሱስ ዋና ጽ/ቤት ጋር ሳይሆን የጭሮ (አሰበ ተፈሪ) መካነ እየሱስ ማህበረ ምዕመናን ጋር በመሆኑ በአሁን

አመልካች የቀረበው አቤቱታ ውድቅ ይደረግልኝ የሚል የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ያቀረበች ሲሆን በፍሬ ነገሩ ላይ በሰጡት መልስ ደግሞ በአመልካች ድርጅት ውስጥ በምሰራበት የስራ ሰዓት ውስጥ ሌላ ስራ አልሰራም፤ በሌላኛው መስሪያ ቤት ውስጥ የምሰራው የጽዳት ስራ በአመልካች ድርጅት ውስጥ ከምሰራበት የስራ ሰዓት ውጪ የምሰራው ስራ ነው፤ ለቅርብ አለቃ አትታዘዝም እና በስራ ቦታ አምባጓሮ ትፈጥራለች የተባለውም ሀሰት ነው በማለት ተከራክራለች፡፡ አመልካችም የሰበር አቤቱታውን በማጠናከር የመልስ መልስ ሰጥቶ ተከራክሯል፡፡

ከስር ጀምሮ የጉዳዩ አመጣጥ እና የግራ ቀኝ ክርክር ይዘት አጠር አጠር ባለ መልኩ ሲታይ ከፍ ሲል የተመለከተውን ሲመስል ይህ ችሎትም የአመልካችን የሠበር አቤቱታ በሰበር አጣሪ ከተያዘው ጭብጥ፣ ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና ከተገቢው የህጉ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡ እንደመረመረዉም ተጠሪ በሌላ መስሪያ ቤት ተቀጥራ መስራቷ በአመልካች ድርጅት የተሰጣትን ኃላፊነት በአግባቡ እንዳትወጣ ምክንያት ሆኗል የሚል ክርክር አመልካች የሌለዉ ሲሆን ተጠሪም የሌላ መስሪያ ቤት ሠራተኛ መሆኗን ሳትክድ በሌላ መስሪያ ቤት የምትሠራዉ የጽዳት ስራ በአመልካች ድርጅት ዉስጥ የምትሠራዉን የስራ ሰዓት የማይነካ መሆኑን ጠቅሳ የተከራከረች ሲሆን አመልካችም በሰጠዉ የመልስ መልስ ይህን በግልጽ ክዶ አይከራከርም፡፡ ተጠሪ በአመልካች ድርጅት ስትቀጠር የሌላ መስሪያ ቤት ሠራተኛ መሆን ያለመሆኑን ተጠይቃ እዉነታዉን ደብቃ በአመልካች ድርጅት መቀጠሯን የሚያሳይ ክርክር እና ማስረጃ ባልቀረበበት ሁኔታ ተጠሪ በሌላ ድርጅት ተቀጥራ መስራቷ ብቻዉን በአመልካች ላይ የማታለል ድርጊት ፈጽማለች ለማለት የሚያስችል ህጋዊ ምክንያትም የለም፡፡ በመሆኑም ተጠሪ ሌላ መስሪያ ቤት ሠራተኛ መሆኗን እንደ ጥፋት በመቁጠር ስንብቱ ህጋዊ ነዉ በማለት አመልካች የሚያቀርበዉን ክርክር ይህ ችሎት አልተቀበለዉም፡፡

ሌላዉ የአመልካች ክርክር ተጠሪ ከስራ የተሰናበተችዉ ለአለቃ ባለመታዘዝ እና በስራ ቦታ አምባጓሮ በመፍጠር የስነ ምግባር ጥሰት ትፈጽማለች የሚል ነዉ፡፡ ማስረጃን መዝኖ ፍሬ ነገርን የማጣራት ስልጣን የተሰጣቸዉ የወረዳዉ እና የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤቶች ተጠሪ የስነ ምግባር ጥሰት መፈጸሟን ያረጋገጡ ሲሆን ሁለቱ በተለያየ ድምዳሜ ላይ የደረሱት የስንብት እርምጃዉ በተጠሪ ላይ የተወሰደዉ በህጉ ላይ በተመለከተዉ ጊዜ ዉስጥ መሆን ያለመሆኑ ነዉ፡፡ የወረዳዉ ፍርድ ቤት እንዲሁም የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ስንብቱ ህገ ወጥ ነዉ በሚል ድምዳሜ ላይ የደረሱት አመልካች በአዋጅ ቁጥር 1156/2011 አንቀጽ 27(3) ላይ የተመለከተዉ የ30 ቀን ጊዜ ካለፈ በኋላ መሆኑን በመጥቀስ ሲሆን፣ ከፍተኛዉ ፍርድ ቤት በበኩሉ ስንብቱ ህጋዊ በማለት ለሰጠዉ ዉሳኔ መሠረት ያደረገዉ አመልካች ማስጠንቀቂያ በ30 ቀናት ዉስጥ ማድረስ አለበት የሚል ግዴታ በአዋጁ አልተጣለበትም የሚል ይዘት ምክንያት በመጥቀስ ነዉ፡፡ በበኩላችን እንደተመለከትነዉ አመልካች ተጠሪ የተለያዩ ጥፋቶችን መፈጸሟን ጠቅሶ ማስጠንቀቂያ የፃፈላት ነሐሴ 28 ቀን 2011 ዓ.ም ሲሆን ከስራ

ያሰናበታት ግን ጥቅምት 05 ቀን 2012 ዓ.ም ስለመሆኑ በስር ፍርድ ቤት ተረጋግጧል፡፡ አመልካች ለስንብቱ ምክንያት ናቸዉ የሚላቸዉን ጥፋቶች ማስጠንቀቂያ ከደረሳት በኋላ ስለመሆኑ ገልፃ አይከራከርም፡፡ ይህም የሚያሳየዉ አመልካች ተጠሪን ከስራ ሊያሰናብት የሚችል ጥፋት መኖሩን ካወቀ ከ30 ቀናት በኋላ ከስራ ያሰናበታት መሆኑን ነዉ፡፡ በአዋጅ ቁጥር 1156/2011 አንቀጽ 27(3) ላይ ከተመለከተዉ ድንጋጌ መገንዘብ የሚቻለዉ አሠሪዉ በሠራተኛዉ ጥፋት ምክንያት ማስጠንቀቂያ መስጠት ሳያስፈልገዉ የስራ ዉሉን ለማቋረጥ ያለዉ መብት ዉሉ የሚቋረጥበት ምክንያት መኖሩን ካወቀ ከሰላሳ የስራ ቀናት በኋላ በይርጋ የሚታገድ መሆኑን ነዉ፡፡ ይህም ማለት ምንም እንኳ ሠራተኛዉ የፈጸመዉ ድርጊት ከስራ የሚያሰናብተዉ ቢሆንም እንኳ አሠሪዉ ጥፋት መኖሩን ካወቀበት ጊዜ ጀምሮ በሰላሳ ቀናት ዉስጥ እርምጃ ካልወሰደ ከስራ የማሰናበት መብት ያጣል ማለት ነዉ፡፡ በመሆኑም ተጠሪ በአመልካች የተጠቀሱትን ጥፋቶች መፈጸሟ የተረጋገጠ ቢሆንም በአዋጁ በተመለከተዉ ከሰላሳ የስራ ቀናት በኋላ ከስራ ማሰናበቱ ስንብቱን ህገ ወጥ የሚያደርግ በመሆኑ በዚህ ረገድ የወረዳዉ እና የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የደረሱበት ድምዳሜ የሚነቀፍ ሆኖ አልተገኘም፡፡

ሌላዉ የአመልካች ክርክር ተጠሪ ወደ ስራ ልትመለስ አይገባም የሚል ነዉ፡፡ አንድ ሠራተኛ ከስራ የተሰናበተበት ሁኔታ ህገ ወጥ መሆኑ ከተረጋገጠ ዉጤቱን በመወሰን ረገድ በአንድ በኩል ሠራተኛዉን ወደ ስራዉ በመመለስ የሠራተኛዉን የስራ ዋስትና ማረጋገጥ፣ በሌላ በኩል ደግሞ በሠራተኛዉ ወደ ስራ መመለስ ምክንያት በአሠሪዉ ላይ ሊደርስ የሚችለዉን ጉዳት ግምት ዉስጥ በማስገባት በሁለቱም በኩል ያሉትን ተፃራሪ ጥቅሞችን ማስታረቅ በሚቻል መልኩ ሊሆን ይገባል፡፡ የስራ ክርክሮችን የሚወስነው አካል ከስራ ግንኙነቱ ጠባይ የተነሳ የስራ ግንኙነቱ ቢቀጥል <u>ከፍተኛ ችግር</u> (ሰረዝ የተጨመረበት) ያስከትላል ብሎ ካመነ ሰራተኛው ወደ ስራው መመለስ ቢፈልግ እንኳን ካሳ ተከፍሎት እንዲሰናበት ለመወሰን እንደሚችል በአሰሪና ሰራተኛ አዋጅ ቁጥር 1156/2011 እንቀፅ 43(3) ላይ የተመለከተዉ ድንጋጌም ይህንኑ የሚያስገነዝብ ነዉ፡፡ ከዚህ የአዋጁ ድንጋጌ አቀራረጽ መገንዘብ የሚቻለዉም ስራዉ በህገ-ወጥ መንገድ የተቋረጠበት ሠራተኛ ወደ ስራዉ ተመልሶ ለመስራት ፍላጎት ያለዉ መሆኑ ከተረጋገጠ፣ ክርክሩ የቀረበለት የስራ ክርክር ችሎት ሠራተኛዉ ወደ ስራዉ እንዲመለስ የመወሰን ግዴታ ያለበት ሲሆን ሠራተኛዉ ካሳ ተከፍሎት እንዲሰናበት መወሰን የሚችለዉ ወደ ስራዉ መመለሱ በአሠሪዉ ስራ ላይ ከፍተኛ ችግር የሚያስከትል መሆኑን የተረዳ እንደሆነ ብቻ መሆኑን ነዉ፡፡ ስለሆነም የስራ ክርክሩን የሚያይ ፍርድ ቤት ሠራተኛዉ ወደ ስራዉ ሊመለስ አይገባም በሚል ድምዳሜ ላይ ከመድረሱ በፊት የሠራተኛዉ ወደ ስራዉ መመለስ በአሠሪዉ ላይ ከፍተኛ ችግር የማድረስ ዉጤት የሚያስከትል መሆን አለመሆኑን በአግባቡ የማጤን እና የመመርመር ኃላፊነት ይኖርበታል፡፡

ከዚህ አንፃር የተያዘውን ጉዳይ ስንመለከት ተጠሪ በአመልካች ድርጅት በሠራተኝነት እንድትቀጥል መደረጉ በአመልካች ላይ ሊያደርስ የሚችል ጉዳት መኖሩ ፍርድ ቤቱን ሊያሳምን የሚችል ግልጽ ምክንያት በሌለበት ሁኔታ ሁለት ቦታ መስራቷን እንደ ምክንያት በመጥቀስ ወደ ስራ እንድትመለስ ሊወሰን አይገባም በማለት አመልካች የሚያቀርበዉ ክርክር ወደ ስራ ለመመለስ ሠራተኛዉ ፍላጎቱ ቢኖረዉም ወደ ስራ እንዳይመለስ ፍርድ ቤት ሊወስን የሚችልበትን ሁኔታ አስመልክቶ በአዋጁ የተመለከተዉን ድንጋጌ ያገናዘበ ባለመሆኑ አመልካች ይህን አስመልክቶ የሚያቀርበዉ ክርክርም ተቀባይነት ያለዉ ሆኖ አልተገኘም፡፡

በዚህ ሁሉ ምክንያት ተከታዩ ተወስኗል፡፡

<u>ዉሳኔ</u>

1. የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 334254 በቀን 18/05/2013 ዓ.ም በዋለዉ ችሎት የሰጠዉ ዉሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥርዓት ህጉ አንቀጽ 348(1) መሠረት ጸንቷል፡፡
2. የሰበር አጣሪ ችሎት በቀን 02/07/2013 ዓ.ም በዋለዉ ችሎት የሰጠዉ እግድ ተነስቷል፡፡
3. በዚህ ችሎት የተደረገዉ ክርክር ያስከተለዉን ወጪ እና ኪሳራ ግራ ቀኝ የየራሳቸዉን ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ማ/አ

የሰ/መ/ቁ፡- 200687

ቀን፡-30/02/2014 ዓ.ም

ዳኞች፡- ብርሃኑ አመነው

ተሾመ ሽፈራው

ሀብታሙ እርቅይሁን

ብርሃኑ መንግስቱ

ነፃነት ተገኝ

አመልካች፡- አይካ አዲስ ጨርቃ ጨርቅ ኢንቨስትመንት ግሩፕ ኃ/የተ/የግ/ማህበር - ጠበቃ ንጉሴ እሰየው - ቀረቡ

ተጠሪ፡- አቶ ኢብራሒም አይዶግዱ - አልቀረቡም

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍርድ

ጉዳዩ የስራ ዉል መቋረጥ የሚመለከት ነዉ፡፡ክርክሩ የተጀመረው ኦሮሚያ ክልል በፊንፊኔ ዙሪያ ኦሮሚያ ልዩ ዞን ሰበታ ከተማ ወረዳ ፍ/ቤት ሲሆን የአሁኑ ተጠሪ ከሳሽ በመሆን የአሁኑ አመልካች ተከሳሽ በመሆን ተከራክረዋል፡፡ከመዝገብ እንደሚታየዉ ተጠሪ በአመልካች ድርጅት ውስጥ የምግብ ባለሙያ ሁኜ በቀን 28/04/2000 ዓ.ም በወር 2500 ዶላር ደመወዝ ተቀጥሬ እየሰራሁ እያለ በቀን 22/08/2011 ዓ.ም ያለጥፋት ከህግ ውጪ ውልህን ጨርሰሀል በማለት ከስራዬ አሰናብቶኛል፣ስለዚህ ስንብቱ ህገ ወጥ ነዉ ተብሎ የአገልግሎት ክፍያ፣የካሳ ክፍያ፣ የማስጠንቀቂያ ጊዜ፣ ክፍያ የዘገየበት እና ለአውሮፕላን ቲኬት በአጠቃላይ 41,264.33 ዶላር ወይም በኢትዮጵያ ብር 1,190,477.44 ከ10% የጠበቃ አበል ጋር እንዲከፈልኝ እንዲወሰንልኝ በማለት ዳኝነት ጠይቋል፡፡አመልካች በበኩሉ በአመልካች እና በተጠሪ መካከል የተደረገው የስራ ስምምነት ለተወሰነ ጊዜ ለአንድ አመት የሚቆይ ሆኖ ውሉ እንደተጠናቀቀ ወዲያውኑ ሊቋረጥ እንደሚችል ተስማምተናል፣ተጠሪ ተቀጥሮ ሲሰራበት የቆየው የስራ መደብ ላይ የኢትዮጵያ ዜጋ በብቃት ሊሰሩ የሚችሉት ነው፡፡ለአንድ የውጪ ዜጋ ደግሞ ፈቃድ የሚሰጠው የሀገር ውስጥ ሰራተኞች ግንዛቤ እና ልምድ እስከሚያገኙ ብቻ ነው፡፡ስለዚህ የሀገር ውስጥ ዜጎች መስራት እየቻሉ የውጭ ዜጋ መስራት የለበትም፡፡ውላችን ለተወሰነ ጊዜ የተደረገ ሲሆን የውጭ ዜጋ ሆኖ ተጠሪ ላልተወሰነ ጊዜ መስራቱ ከህግ ውጪ በመሆኑ ውሉ የተቋረጠው በህግ አግባብ በመሆኑ የተጠየቀው ክፍያ ሊከፈለው አይገባም በማለት ተከራክረዋል፡፡

ፍ/ቤቱም የግራ ቀኝ ክርክርና ማስረጃ መርምሮ አመልካች እና ተጠሪ የተፈራረሙት የስራ ውል ከ23/04/2010 ዓ.ም ጀምሮ ለአንድ ዓመት ጸንቶ የሚቆይ መሆኑን የሚያሳይ ቢሆንም በአዋጅ ቁ/377/96 አንቀጽ 10 ስር ከተገለጹት ምክንያቶች ውስጥ በየትኛው ምክንያት ለተወሰነ ጊዜ እንደተደረገ የተገለጸ ነገር የለም፡፡ውሉ ለተወሰነ ጊዜ ስለተባለ ብቻ የህጉን መስፈርት አሟልቷል የሚያስብል አይደለም፣ተጠሪ ለተወሰነ ጊዜ የሚቆይ ስራ ሲሰራ እንደቆየ የሚያሳይ ማስረጃ አመልካች አላቀረበም፡፡ተጠሪ ተቀጥሮ ሲሰራበት የቆየው ስራ ደግሞ በባህሪው በቀጣይነት የሚሰራ ስራ በመሆኑ እና የፌ/ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ.43160 ላይ በሰጠው ዉሳኔ በአንቀጽ 10 ስር ተዘርዝረው ካሉት ስራዎች ውጭ ከሆነ ይህ ውል የተወሰነ ጊዜ ነው ቢባል እንኳን የተወሰነ ጊዜ ዉል ሊሆን አይችልም በማለት አስገዳጅ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡የውጭ ሀገር ዜጋ ስለሆነ ውሉ የተወሰነ ጊዜ ነው የሚል ህግ የለም፣ስለዚህ የስራ ውሉ ላልተወሰነ ጊዜ ነው፣አመልካች የውሉ ጊዜ ስለተጠናቀቀ በማለት ውሉን ማቋረጡ የህግ መሰረት የለውም፣ስንብቱ ከህግ ውጭ ነው በማለት የተጠየቁ ክፍያዎች ለተጠሪ እንዲከፈል በማለት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

አመልካች በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ለፊንፊኔ ዙሪያ ኦሮሚያ ልዩ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ ቢያቀርብም ፍ/ቤቱ ጉዳዩ አያስቀርብም በማለት በፍ/ስ/ስ/ህ/ቁ 337 መሰረት ይግባኙን ሰርዟል፡፡አመልካች ለኦሮሚያ ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አቤቱታ ያቀረበ ሲሆን ችሎቱም ጉዳዩ ያስቀርባል በማለት የግራ ቀኝ ክርክር ሰምቶ የስር ፍ/ቤት ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የለዉም በማለት አጽንቷል፡፡ለዚህ ሰበር ችሎት አቤቱታ የቀረበዉ በዚህ ላይ ነዉ፡፡

አመልካች ያቀረበው አቤቱታ ይዘት ባጭሩ፣ዉሉ ለተወሰነ ጊዜ ከውጭ ሀገር ዜጋ ጋር የተደረገ የቅጥር ውል የሚል ሲሆን ይህንን የሚያረጋግጥ በስር ፍ/ቤት ሰነዱ ቀርቦ እያለ እና በቅጥር ውሉ አንቀጽ 11(ሐ) መሰረት ከተዋዋይ ወገኖች መካከል አንዱ ወገን ውሉን በማንኛውም ጊዜ መቋረጥ እንደሚቻል ተመልክቷል፣በኢንቨስትመንት ደንብ ቁጥር 474/2012 አንቀጽ 19(1) መሰረት የውጭ ሀገር ዜጎችን የሚቀጥር ባለሀብት ለኢትዮጵያዊያን አስፈላጊውን የስራ ላይ ስልጠና እንዲሰጥ እና እውቀት እንዲተላለፍ በማድረግ የውጭ ዜጋ ተቀጣሪዎች በኢትዮጵያዊያን እንዲተኩ የማድረግ ግዴታ ያለበት ሲሆን በዚሁ መሰረት አመልካች የተጠሪ የስራ ውል በውላቸው መሰረት እንዲቋረጥ ማድረጉ ህጋዊ ስንብት ነው፡፡ተጠሪ በአመልካች ድርጅት ውስጥ ለ11 ዓመት የሰራው በጊዜያዊነት የስራ ቅጥር ውሉ እየታደሰ እና የስራ ፍቃዱም እንዲታደስ በማድረግ ነው፡፡ተጠሪ በቋሚነት መቀጠሩን የሚያረጋግጥ ማስረጃ አላቀረበም፡፡ስለዚህ ለዜጎች ቅድሚያ የሥራ ዕድል ለመስጠት ሲባል በህጋዊ መንገድ የተቋረጠ ዉል ላይ ብር 1,190,477.44 እንዲከፈል የተወሰነው መሰረታዊ የህግ ስህተት በመሆኑ ውሳኔው እንዲሻር በማለት አመልክተዋል፡፡

የአመልካች አቤቱታ በሰበር አጣሪ ችሎት ተመርምሮ በዚህ ጉዳይ ቅጥሩ ለተወሰነ ጊዜ መሆኑን የቅጥር ውሉ ላይ ከመመልከቱ አንፃር የስር ፍ/ቤት ላልተወሰነ ጊዜ የተደረገ የስራ ውል ነው በሚል መነሻ ስንብቱ ህገወጥ ነው ማለቱን አግባብነት ለማጣራት ጉዳዩ ለሰበር ሰሚ ችሎት ያስቀርባል ተብሎ ተጠሪ መልስ እንዲሰጥበት ታዟል፡፡

ተጠሪ ባቀረበው መልስ በውላችን መሰረት አመልካች በቅድሚያ የአንድ ወር ማስጠንቀቂያ ሳይሰጥ እንዲሁም የውሉ ቀን ሳይጠናቀቅ ውሉን ማቋረጡ ስንብቱን ህገ ወጥ ያደርጋል፡፡ በተጠሪ ድርጅት ላልተወሰነ ጊዜ ተቀጥሬ ለ11 ዓመታት ሲሰራ መቆየቴ በስር ፍ/ቤት ተረጋግጧል፡፡አንድ ሰራተኛ ለተወሰነ ወይስ ላልተወሰነ ጊዜ ነው የተቀጠረው ለማለት የሚቻለው ሰራተኛው የተቀጠረበት ስራ ባህሪይ እንጂ በውሉ ላይ ለጊዜያዊ ስራ ተቀጥሪዋል ስለተባለ ብቻ እንደማይሆን ሰበር ችሎቱ በመ/ቁ.43160 ላይ አስገዳጅ ውሳኔ ሰጥቷል፣ አመልካች ስራው እንዳልተጠናቀቀ እና በተጠሪ ስራ ቦታ ሌላ ሰው መቅጠሩ ተጠሪ ላልተወሰነ ስራ እንደተቀጠረ ያረጋግጣል፡፡ስለዚህ በድርጅቱ ለተከታታይ ለ11 ዓመት አገልግዬ ያለአገልግሎት ክፍያ፣ ያለማስጠንቀቂያ፣ የቲኬት ክፍያ እና ያለምንም ክፍያ ያሰናበተኝ ስለሆነ የስር ፍ/ቤቶች ስንብቱ ህገ ወጥ ነዉ በማለት የሰጡት ውሳኔ ስህተት የሌለበት በመሆኑ እንዲፀና በማለት ተከራክረዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ እና የግራ ቀኙ ክርክር አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተመለከትነው ሲሆን ጉዳዩ ለሰበር ያስቀርባል ከተባለበት ሞቡጥ አንጻር የስር ፍርድ ቤት ውሳኔ እና ክርክሩን አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ መርምረናል፡፡መዝገቡን መርምረን እንደተገነዘብነዉ በአመልካች እና በተጠሪ መካከል የነበረዉ የስራ ዉል የተቋረጠዉ በአመልካች አነሳሽነት መሆኑ አላከራከረም፡፡አመልካች አጥብቆ የምከራከረዉ ተጠሪ የዉጭ ሀገር ዜጋ በመሆኑና ዉሉም ለተወሰነ ጊዜ የተደረገ ስለሆነ ስንብቱ ህገ ወጥ ነዉ ሊባል አይገባም በማለት ነዉ፡፡

በመሰረቱ የስራ ዉል እንደማናቸዉም ዉል የግራ ቀኙን መብትና ግዴታ በሚመለከት በአሰሪዉ እና በሰራተኛዉ ነጻ ፈቃድና ስምምነት የሚደረግ ዉል ቢሆንም በህግ የተጠበቁ ዝቅተኛ የሥራ ሁኔታዎችን የሚቀንስ ወይም የሚቃረን ሊሆን አይችልም፡፡የአሰሪና ሰራተኛ አዋጅ ቁጥር1156/2011 አንቀጽ4 ድንጋጌ ስር የተመለከቱት ሁኔታዎች ይህንኑ ያስገነዝባሉ፡፡የስራ ዉል አይነት በተመለከለተ ለተወሰነ ወይም ላልተወሰነ ጊዜ ወይም ለተወሰነ ስራ ሊደረግ እንደሚችል የአዋጁ አንቀጽ 4/1/ ድንጋጌ ይዘት ያሣያል፡፡ከዚህም የምንገዘነበዉ የስራ ዉሉ ቆይታ በጊዜ ወይም እንደስራዉ ባህርይ በተዋዋዮች ሊወሰን የሚችል ስለመሆኑ ነዉ፡፡ይሁን እንጂ የሰራተኛዉን የስራ ዋስትና እና የመደራደር አቅም ዉስንነት ከግምት በማስገባት የስራ ዉሉን ቆይታ ጊዜ ወይም ባህርይ ለመወሰን የሚረዱ ሁኔታዎች በህግ ተደንግጎ እናገኛለን፡፡በዚህ ረገድ የአሰሪና ሰራተኛ አዋጁ አንቀጽ 9 እና 10 ድንጋጌዎች እንደሚያሣዩን በመርህ ደረጃ የስራ ዉል ላልተወሰነ

ጊዜ እንደተደረገ የሚገመት ሲሆን በተወሰኑ ሁኔታዎች እና ምክንያቶች ብቻ ለተወሰነ ጊዜ ወይም ለተወሰነ ስራ ተብሎ የሥራ ዉል ሊደረግ የሚችል መሆኑን ነዉ፡፡ስለዚህም አሰሪዉ እና ሰራተኛዉ ለተወሰነ ጊዜ ወይም ለተወሰነ ስራ በሚል መስማማት የሚችሉ ቢሆንም ጉዳዩ አከራካሪ ሆኖ ከቀረበ ዉሉ ከህጉ ጋር የሚጣጣም መሆን አለመሆኑ ሊመመርመር ይገባል፡፡በዚህ ረገድ ይህ ሰበር ችሎት ከዚህ ቀደም በተመሳሳይ ክርክር ዉሳኔ የሰጠባቸዉ ጉዳዮች ላይ እንዳመለካተዉ የሥራ ዉሉ ቆይታ ጊዜ አስመልክቶ ለተወሰነ ጊዜ ወይም ለተወሰነ ስራ በሚል መዋዋላቸዉ ብቻ ሳይሆን ዉሉ ከስራዉ ባህርይ ጋር ተገናዘቦ መታየት እንዳለበት ያስገነዝባል፡፡ሰበር መ/ቁ11924፣መ/ቁ/25765፣መ/ቁ.43160 እና ሌሎች መሰል መዝገቦችን ማየት ይቻላል፡፡

በተያዘዉ ጉዳይ በግራቀኙ መካከል የተደረገዉ ዉል ለተወሰነ ጊዜ የተደረገ መሆኑን እና በየጊዜዉ እየታደሰ መቆየቱንና ለመጨረሻ ጊዜም በ23/04/2010ዓ.ም ለአንድ ዓመት የተራዘመ መሆኑን ዉሉ የተቋረጠዉ በ22/08/2011ዓ.ም ስለመሆኑ የስር ፍርድ ቤት አረጋግጧል፡፡ፍርድ ቤቱም ዉሉ ለተወሰነ ጊዜ ነዉ ቢባልም የስራዉ ባሕርይ ሲታይ የድርጅቱ ቋሚ ወይም ቀጣይነት ያለዉ ስራ ነዉ በሚል ምክንያት ሰበር ችሎቱ በመ/ቁ/43160 ላይ የሰጠዉን ዉሳኔ ድጋፍ በማድረግ ላልተወሰነ ጊዜ እንደተደረገ ይቆጠራል በማለት ስንብቱ ህገ ወጥ ነዉ የሚል ድምዳሜ ላይ ደርሷል፡፡ከክርክሩ እንደሚታየዉ ተጠሪ ለ11ዓመት በቋሚነት አገልግያለዉ በሚል ምክንያት የሥራ ዉሉ ላልተወሰነ ጊዜ እንደተደረገ ይቆጠራል በማለት የሚከራከር ቢሆንም ዉሉ በየጊዜዉ እየታደሰ የቆየ መሆኑ በተጠሪም አልተካደም፡፡በእርግጥ የስራ ዉል ለተወሰነ ጊዜ ወይም ለተወሰነ ስራ የተደረገ ነዉ የሚያሠኘዉ የዉሉ ይዘት ብቻ ሳይሆን በአሰሪና ሰራተኛ አዋጅ አንቀጽ 10 ስር የተዘረዘሩት ምክንያቶች ወይም ሁኔታዎች መኖራቸዉ መረጋገጥ እንዳለበት የህጉ አገላለጽ እና ይህ ሰበር ችሎት በመ/ቁ 43160 እና ሌሎች መሰል መዝገቦች ላይ የሰጠዉ ዉሳኔ ያስገነዝባል፡፡ይሁንና የሰበር ችሎቱ ዉሳኔ በዚህ መዝገብ ከቀረበዉ ክርክር አኳያ ተፈጻሚነት አለዉ ወይ የሚለዉ ከጉዳዩ ባህርይ አንጻር መመርመር አለበት፡፡

ከመዝገቡ እንደሚታየዉ ተጠሪ የተቀጠረበት የሥራ መደብ የድርጅቱ ቋሚ ወይም ቀጣይነት ያለዉ ስራ አይደለም የሚል ክርክር የለዉም፡፡የአመልካች ዋነኛ መከራከሪያ ነጥብ ተጠሪ ለተወሰነ ጊዜ የተቀጠረዉ እና ዉሉ እየታደሰ የቆየዉ የዉጭ ሀገር ዜጋ በመሆኑ በቋሚነት ሊቀጠር አይችልም የሚል ነዉ፡፡ተጠሪ የዉጭ ሀገር ዜጋ መሆኑ አከራካሪ እስካልሆነ ድረስ የሥራ ዉሉን ዓይነት በመወሰን ረገድ የሚኖረዉ ዉጤት ከአሰሪና ሰራተኛ አዋጁ እና ሌሎች አግባብነት ካላቸዉ ህጎች ጋር ተገናዝቦ መታየት አለበት፡፡

የአሰሪና ሰራተኛ አዋጅ ቁጥር 377/96 የዉጭ አገር ሠራተኞች የሚቀጠሩበትን ሁኔታ የሚደነግግ ሲሆን በዚህም መሠረት የዉጭ አገር ዜጋ በማናቸዉም የስራ መስክ ተቀጥሮ ለመስራት የሚችለዉ

የሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳዮች ሚኒስቴር ወይም ክልል ሲሆን የክልል ሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳዮች ቢሮ የሚሰጠዉን የስራ ፍቃድ ሲያገኝ እና የስራ ፍቃድ የሚሰጠዉም በአንድ የስራ መስክ ለማገልገል እስከ ሦስት ዓመት ሲሆን በየዓመቱ መታደስ ያለበት ስለመሆኑ በአዋጁ አንቀጽ 174 ላይ ከተመለከተዉ ድንጋጌ መገንዘብ ይቻላል፡፡በዚህ ረገድ አዋጅ ቁጥር 1156/2011 ተመሳሳይ ይዘት ያለዉ መሆኑን ልብ ይለዋል፡፡የአዋጁን አንቀጽ 171/1/ሠ እና 176 መመልከት ይቻላል፡፡የዜጎችን የኑሮ ደረጃ ማሻሻልን አንዱ ዓላማዉ ያደረገዉ (መግቢያዉን መመልከት ይቻላል) የኢንቨስትመንት አዋጅ ቁጥር 769/2004 በአንቀጽ 37(2)፣ በዚህ አዋጅ የተተካዉ የኢንቨስትመንት አዋጅ ቁጥር 280/94 አንቀጽ 36(2) እንዲሁም አሁን በስራ ላይ ያለዉ የእንቨስትመንት አዋጅ ቁጥር 1180/2012 አንቀጽ 22(4) የዉጭ ዜጎችን የሚቀጥር ባለሀብት ለኢትዮጵያዉያን አስፈላጊዉ ስልጠና እንዲዘጋጅ እና እንዲሰጥ በማድረግ በተወሰነ ጊዜ ዉስጥ የዉጭ አገር ዜጋ ሠራተኞችን እንዲተኩ ማድረግ እንዳለበት ይደነግጋሉ፡፡ ቀደም ሲል በስራ ላይ የነበሩት ሁለቱ የእንቨስትመንት አዋጆችም ሆነ አሁን በስራ ላይ ያለዉ የእንቨስትመንት አዋጅ ዓላማዎች ናቸዉ ተብለዉ ከተዘረዘሩት ዉስጥ አንዱ ለኢትዮጵያዉያን ሰፊ እና ጥራት ያለዉ የስራ ዕድል መፍጠር እና ለአገሪቱ ዕድገት የሚያስፈልገዉን የዕዉቀት፣ ክህሎት እና ቴክኖሎጂ ሽግግር ማሳለጥ ስለመሆኑ በአዋጅ ቁጥር 280/94 አንቀጽ 4(6)፣ በአዋጅ ቁጥር 769/2004 እና አዋጅ ቁጥር 1180/2012 አንቀጽ 5 ላይ ከተመለከቱት ድንጋጌዎች መገንዘብ ይቻላል፡፡ ከዚህ ሁሉ መገንዘብ የሚቻለዉ በአገራችን የግል እንቨስትመንትን ማስፋፋት አስፈላጊ ከሆነባቸዉ ምክንያቶች ዉስጥ አንዱ መንግስት ማንኛዉም ኢትዮጵያዊ ዜጋ በአገሪቱ ዉስጥ በማንኛዉም የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ የመሰማራት እና ለመተዳደሪያ የመስራት መብት ለመተግበር በተለይም ሰፊ የሥራ እድል ለመፍጠር የሚያስችል ፖሊሲ መከተል እንዳለበት በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 41 /1/ እና 4) በተጣለበት ግዴታ መሠረት ለዜጎች የስራ ዕድል በመፍጠር ለዜጎች የስራ ዋስትና ማረጋገጥ መሆኑን ነዉ፡፡አንድ ዓላማ ያላቸዉ የተለያዩ ህጎች በሚኖርበት ጊዜ በተለያዩ የህግ ክፍሎች በሚገኙ ድንጋጌዎች ተደጋጋፊ ሆነዉ የጋራ ዓላማ የሚያሳኩበትን የህግ ትርጉም መሻት የህግ ባለሙያዎች ሊመርጡት የሚገባ የህግ አተረጓጎም ዘይቤን መከተል በህግ አተረጓጎም ዕዉቅና ከተሰጣቸዉ መርሆዎች አንዱ ሲሆን ይህ ሰበር ሰሚ ችሎትም በሰ/መ/ቁጥር 21448 ላይ በሰጠዉ የህግ ትርጉም ለዚህ መርህ ዕዉቅና ሰጥቶታል፡፡

ከዉጭ አገር ዜጎች የቅጥር ሁኔታ ጋር በተያያዘ በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 174 ላይ የተመለከተዉ ድንጋጌ ዓላማዉ ምን እንደሆነ በግልጽ የሚያመላክት ድንጋጌ ባይኖርም ከላይ ከተመለከቱት የእንቨስትመንት ህጎች ድንጋጌዎች እንዲሁም በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ህገ መንግስት መሠረት መንግስት ለእራሱ ዜጎች የስራ ዕድል ለማመቻቸት ካለበት ግዴታ አንፃር ሲታይ በአዋጁ አንቀጽ 174 ላይ የተመለከተዉ ድንጋጌ አጠቃላይ ዓላማ የግል ድርጅቶች የዉጭ አገር ዜጎችን

የሚቀጥሩት ለስራ ዕድል ፈጠራ ዓላማ ሳይሆን ለድርጅቱ ስራ አስፈላጊነታቸዉ ከታመነበት ብቻ መሆኑን ነዉ፡፡ከዚህም በተጨማሪ የዉጭ ሀገር ዜጋ በሀገር ዉስጥ ስራ እንዲቀጠር የሚፈለገዉ በዘርፉ በቂ ባለሙያ በሀገር ዉስጥ ሳይኖር ወይም የእዉቀትና ቴክኖሎጂ ሽግግር ለማድረግ ዓላማ በመያዝ ስለመሆኑ የኢንቨስትመንት አዋጅ እና አዋጁን ተከትሎ የወጣዉ ደንብ የሚያስገነዝቡን ጉዳይ ነዉ፡፡ደንብ ቁጥር 474/2012 አንቀጽ 19/1/ይመለከታል፡፡በሌላ በኩል ከላይ እንደተገለጸዉ፣ የስራ ቅጥር ዉል ጊዜ ጋር በተያያዘ በአዋጁ አንቀጽ 9 እና 10 ላይ የተመለከተዉ ድንጋጌ የዜጎችን የስራ ዋስትና የማረጋገጥ ዓላማ ያለዉ ነዉ፡፡የስራ ዋስትና ከስራ ዕድል ፈጠራ ጋር በተያያዘ የሚታይ በመሆኑም በዚህ መብት ተጠቃሚ የሚሆኑበትን እድል ይፈጥራል ተብሎ ይታሰባል፡፡

በመሆኑም የስራ ቅጥሩ በሚመለከተዉ አካል ይሁንታ የሚፈጸም መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ አንድ አሠሪ ከዉጭ አገር ሠራተኛ ጋር በሚያደርገዉ ዉል ዉሉ ጸንቶ የሚቆይበትን ጊዜ በተመለከተ ተስማምተዉ የሚያስቀምጡት የጊዜ ገደብ ህጋዊ ዉጤት ያለዉ በመሆኑ አሠሪዉ የዉሉ ጊዜ ሲያበቃ ዉሉን አቋርጦ ሠራተኛዉን የማሰናበት መብት ይኖረዋል፡፡በዚህ ረገድ በተመሳሳይ ክርክር ይህ ሰበር ችሎት በመ/ቁ/194630 ላይ (ያልታተመ) የሰጠዉ ዉሳኔም ተመሳሳይ አቋም የተወሰደበት መሆኑን ያሣያል፡፡

በመሆኑም በተያዘዉ ጉዳይ በአመልካች እና በተጠሪ መካከል የተደረገዉ የስራ ዉል በጊዜያዊ ቅጥር ላይ የተመሠረተ ሆኖ በየጊዜዉ እየታደሰ ተጠሪ ለአስራ አንድ ዓመታት በአመልካች ዘንድ ሲሰራ የቆየ መሆኑ ያላከራከረ ሲሆን፣ አመልካች ዉሉ ከተጠሪ ጋር እንዲቀጥል ተስማምቶ ዉሉ ታድሶ በመካከላቸዉ ግንኙነቱ እንዲቀጥል ለማድረግ የስራ ፈቃድ እንዲታደስ ያስፈልጋል፡፡ዉጪ ሀገር ዜጋ የስራ ፈቃድ የሚታደሰዉ በአሰሪዉ ጥያቄ መነሻ መሆኑን አዋጁ ያሳያል፡፡በአዋጁ አንቀጽ 174(2-4) ላይ በተመለከተዉ ድንጋጌ መሠረት የስራ እና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር (በክልል ሲሆን ቢሮ) የሚሰጠዉ የስራ ፍቃድ እና አድሳት ማንኛዉም የግል ድርጅት ያለሚኒስቴሩ (ቢሮዉ) ዕዉቅና እና ይሁንታ የዉጭ አገር ዜጎችን እንዳይቀጥር ለመከላከል ታስቦ የተቀረጸ ስለመሆኑ ከድንጋጌዉ መገንዘብ ይቻላል፡፡በመሆኑም አሠሪዉ ድርጅት ከዉጭ አገር ዜጋ ጋር በጊዜያዊነት ያደረገዉ የስራ ቅጥር ዉል ግንኙነት እንዲቀጥል የስራ ፈቃድ አስፈላጊ በመሆኑ ለሠራተኛዉ የስራ ፍቃድ በሚመለከተዉ አካል አለመታደሱም አመልካች የቅጥር ዉሉ እንዲያራዝም የሚያስፈልግበት ምክንያት አለመኖሩን የሚያሣይ ነዉ፡፡

በአጠቃላይ በየደረጃዉ ያሉት ፍርድ ቤቶች ጉዳዩን ከፍ ሲል በዝርዝር ከተመለከተዉ አንፃር በማየት ስንበቱ ህጋዊ ነዉ ማለት ሲገባቸዉ በአዋጁ አንቀጽ 9 እና 10 ላይ የተመለከቱት ድንጋጌዎች ለዉጭ አገር ዜጋ ሠራተኛም ጭምር ተፈፃሚ እንደሚሆኑ በመዉሰድ በግራ ቀኝ

መካከል ለተወሰነ ጊዜ የተደረገን የስራ ዉል ላልተወሰነ ጊዜ እንደተደረገ ይገመታል በሚል ሃሳብ አመልካች በዚህ ረገድ ያቀረበዉን ክርክር ዉድቅ በማድረግ ስንብቱ ህገ ወጥ ነዉ በማለት የሰጡት ዉሳኔ ለጉዳዩ አግባብነት ያላቸዉን ድንጋጌዎቹ ዓይነተኛ ዓላማ እና ተጠሪ የዉጭ ሀገር ዜጋ ከመሆኑ አኳያ በህጉ የተፈቀደለትን መሰረት በማድረግ ለተወሰነ ጊዜ ወይም ስራ ለመስራት ግራ ቀኙ ያደረጉት ስምምነት ተገኝ ሊሆኑ ይገባል የሚለዉን የዉል አጠቃላይ መርህ ያላገናዘበ በመሆኑ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡

ስንበቱ ህጋዊ ነዉ ከተባለ ለተጠሪ የሚከፈል ክፍያ አለ ወይ የሚለዉንም መርመርናል፡፡በዚህ ረገድ ከስር መዝገብ እንደሚታዉ ተጠሪ ስንበቱ ህገ ወጥ ነዉ በሚል ምክንያት የስንብት፣ካሳ፣የማስጠንቀቂያ ጊዜ እና ክፍያ የዘገየበት የሚል የጠየቃቸዉ ክፍያዎች ሲሆኑ በተጨማሪም ወደ ሀገር ቤት የሚመለስበት የትኬት ክፍያ ብር 431.053(አራት መቶ ሰላሳ አንድ ከዜሮ ሃምሳ ሶስት ሳንቲም ዶላር) አመልካቹ እንድከፍል ጠይቋል፡፡የሥር ፍርድ ቤትም ይህንኑ በመቀበል ዉሳኔ ሰጥቷል፡፡ከላይ እንደተመለከተዉ በዚህ ሰበር ችሎት ዉሳኔ መሰረት ስንበቱ ህጋዊ ነዉ ስለተባለ ህገ ወጥ ስንብት ነዉ ተብሎ በስር ፍርድ ቤት የተወሰኑት ክፍያዎች ተገቢነት የላቸዉም፡፡ይሁንና ዉሉ ሲቋረጥ ተጠሪ ወደ ሀገሩ የሚመለስበት የትኬት ወጪ በአመልካች እንደሚሸፈን የግራቀኙ ዉል አንቀጽ 9/d/ ላይ ተመላክቷል፡፡አመልካችም ይህን በሚመለከት በመካድ ያቀረበዉ ክርክር የለም፡፡ ስለዚህም የሥራ ውሉ ሲቋረጥ የመመለሻ ትኬት ወጪ በአመልካች የሚሸፈን ስለመሆኑ በስምምንቱ የተመለከተ በመሆኑ ይህንኑ በተጠሪ የዳኝነት ጥያቄ መሰረት አመልካች ሊከፍል ይገባል ብለናል፡፡ስለሆነም ተከታዩ ተወስኗል፡፡

<u>ዉሳኔ</u>

1ኛ/የሰበታ ወረዳ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 11361 በቀን 19/06/2012 ዓ.ም በዋለዉ ችሎት፣ የፌንፌኔ ዙሪያ የኦሮሚያ ልዩ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 39465 በቀን 29/07/2012 ዓ.ም በዋለዉ ችሎት እንዲሁም የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ.333832 በቀን 06/04/2013 ዓ.ም የሰጡት ውሳኔ በፍ/ብ/ስ/ህ/ቁ. 348(1) መሠረት ተሻሽሏል፡፡

2ኛ/ አመልካች ከተጠሪ ጋር ያደረገዉን የስራ ዉል ማቋረጡ በህጋዊ መንገድ በመሆኑ ለተጠሪ ሊከፍል የሚገባዉ ክፍያ ወደ ሀገሩ የመመለሻ ትኬት ወጪ ብቻ ነዉ ተብሏል፡፡በዚሁ መሰረት 431.053(አራት መቶ ሰላሳ አንድ ከዜሮ ሃምሳ ሶስት ሳንቲም ዶላር)በወቅቱ የባንክ ምንዛሪ ተለዉጦ አመልካች ለተጠሪ እንዲከፍል ብለናል፡፡በዚሁ ልክ የጠበቃ አበል 10% ጨምሮ ይክፈል ብለናል፡፡የስር ፍርድ ቤትም ይህንኑ አዉቆ እንዲያስፈጽም የዉሳኔ ግልባጭ ይተላለፍለት፡፡ይጻፍ

3ኛ/የሰበር አጣሪ ችሎት በቀን 04/05/2013 ዓ.ም በዋለዉ ችሎት የሰጠዉ እግድ ተነስቷል፡፡

4ኛ/በዚህ ችሎት የተደረገዉ ክርክር ያስከተለዉን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኝ የየራሳቸዉን ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፌርማ አለበት፡፡

ዒ/መ

የሰበር መ/ቁ/ 203557

ጥቅምት 30 ቀን 2014 ዓ.ም

ዳኞች፡- ብርሃኑ አመነው

ተሾመ ሽፈራው

ሀብታሙ እርቅይሁን

ብርሃኑ መንግስቱ

ነፃነት ተገኝ

አመልካች፡- 1ኛ/ አቶ መላኩ አብረሃ

2ኛ/ አቶ እርቅይሁን ባየ } አልተጠሩም

3ኛ/ አቶ መሃመድ አሊ

ተጠሪ፡- ኢትዮ ቴሌኮም ሰሜን ምስራቅ ርጅን - ነ/ፈጅ አቶ ዳንኤል ገ/አናንያ - ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍርድ

ጉዳዩ የስራ ክርክር የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው በአማራ ክልል ደቡብ ወሎ በደሴ ከተማ ወረዳ ፍ/ቤት የአሁን አመልካቾች ከሳሽ በመሆን የአሁኑ ተጠሪ ላይ ባቀረቡት ክስ በተጠሪ መ/ቤት ውስጥ በረዳት መስመር ሰራተኝነት 1ኛ አመልካች ሰኔ ወር 1991 ዓ.ም፣ 2ኛ አመልካች ጥቅምት ወር 1992 ዓ.ም፣ 3ኛ አመልካች ግንቦት ወር 1986 ዓ.ም ጀምሮ ተቀጥረን እያንዳንዳችን በወር ብር 3000 እየተከፈለን እያለ ተጠሪ የሰራተኞች ቅነሳ ምክንያት ሳይኖር በቀን 06/07/2011 ዓ.ም ከስራ እንደተቀነስን ገልጸ የስራ ውላችንን በህገ ወጥ መንገድ ያቋረጠ ስለሆነ ውዝፍ ደመወዛችን ተከፍሎ ወደ ስራ እንዲንመለስ ወይም በአዋጁ የተመለከቱት ክፍያዎች እንዲከፈለን ይወሰንልን በማለት ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡ተጠሪ በበኩሉ አመልካቾች በተጠሪ መ/ቤት ውስጥ ሲሰሩ የነበረው በቀን ሰራተኝነት ሲሆን ሲሰሩት የነበረው ስራ የመ/ቤቱ ቋሚ ስራ ሆኖ እየተቆራረጠ

ስራው በሚኖርበት ጊዜ ብቻ አልፎ አልፎ እየተጠሩ የሚሰሩ እንጂ የመስሪያ ቤቱ ሰራተኞች ባለመሆናቸው ከስራ መሰናበታቸው ህጋዊ ነው በማለት መከራከሩን መዝገቡ ያሣያል፡፡

ፍ/ቤቱም የግራ ቀኝ ክርክር እና የቀረበለትን ማስረጃ መርምሮ አመልካቾች ስራ ሲኖር ብቻ የሚሰሩ የቀን ሠራተኞች በመሆናቸው ከአሰሪና ሰራተኛ አዋጅ ቁጥር 1156/2011 ድንጋጌ አንፃር በተጠሪ ድርጅት በአንቀጽ 10 መሰረት ለተወሰነ ጊዜ ወይም ላልተወሰነ ጊዜ ወይም ለተወሰነ ሥራ የተቀጠሩ ሰራተኞች ናቸው ለማለት የማያስችል በመሆኑ አመልካቾች የተጠሪ ድርጅት ሰራተኞች ባለመሆናቸው በአዋጁ ሊያገኙ የሚገባቸው ክፍያ የለም በማለት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

አመልካቾች በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ለደቡብ ወሎ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ አቅርበዉ ፍ/ቤቱም ግራ ቀኙን አስቀርቦ ከመረመረ በኋላ አመልካቾች በተጠሪ ድርጅት በሚሰጣቸው የሥራ ትዕዛዝ የሚሰሩ እና ለሰሩበትም በየአስራ አምስት ቀን ክፍያ የሚከፈላቸው ስለመሆኑ በስር ፍ/ቤት በማስረጃ ተረጋግጧል፣ይህ ከሆነ ደግሞ በአዋጅ ቁ/1156/2011 አንቀጽ 4(1) መሰረት የስራ ውል ግንኙነት አለ በማለት የስር ፍ/ቤት ውሳኔ በመሻር የስራ ውል ግንኙነቱ ለተወሰነ ጊዜ ነው ወይስ ላልተወሰነ ስራ ነው? ውሉ የተቋረጠው በህግ አግባብ ነው ወይስ አይደለም? የሚለው ጭብጥ ላይ አከራክሮ ውሳኔ እንዲሰጥበት ለስር ፍ/ቤት በፍ/ስ/ስ/ህግ ቁ/ 343/1/ መሰረት መልሶታል፡፡

ተጠሪ በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ለክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ቅሬታ ያቀረበ ሲሆን ችሎቱም ቅሬታውን ተቀብሎ ካከራከረ በኋላ የስር ፍ/ቤት የሰማቸው ምስክሮችም ሆነ የተያያዙት ሰነዶች አመልካቾች ስራ ሲኖር ከያለበት በስልክ ተጠርተው የስልክ መስመር ለማስገባት ወይም ብልሽት ሲገጥም መስላልና ሌሎች እቃዎችን ተሸክመው መጥተው የሚሰሩ ሆኖ የስራ ሰዓት ላይ የሚያደርገው ቁጥጥርና ክትትል አለመኖሩን ለስር ፍ/ቤት የቀረበው ፔሮል 'Daily workers wage payment form' በሚል የተዘጋጀ መክፍያ እንጂ ለመደበኛ ሰራተኞች የሚዘጋጅ ፔሮል አለመሆኑን ያስረዳል፡፡ስለዚህ አመልካቾች ከተጠሪ ጋር ያላቸው የሥራ ውል ግንኙነት በአዋጅ ቁ/1156/2011 የሚሸፈን አይደለም፣ የስራ ውል ግንኙነት የላቸዉም በማለት የከፍተኛ ፍ/ቤት ውሳኔ በመሻር የወረዳ ፍ/ቤት ውሳኔ በአብላጫ ድምጽ አጽንቷል፡፡ለዚህ ሰበር ችሎት አቤቱታ ቀረበዉ በዚህ ላይ ነዉ፡፡

አመልካቾች ይህ ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት ተፈጽሞበታል በማለት ያቀረቡት አቤቱታ ይዘት ባጭሩ፣በስር ወረዳ ፍ/ቤት ተጠሪ ባቀረበው ክርክር አመልካቾች ሲሰሩት የነበረው ስራ አልፎ አልፎ የሚሰራ ስራ ማለትም የተከሳሽ ቋሚ ስራ ሆኖ ስራዉ በሚኖርበት ጊዜ ብቻ ለመስራት የተቀጠሩ ናቸው በማለት መልስ መስጠቱ ሲታይ ከመነሻው አመልካቾች ከተጠሪ ጋር በአዋጅ ቁ/1156/2011 አንቀጽ 10(1)(ሠ) ድንጋጌ ላይ የተመለከተውን የሥራ ውል ሁኔታ ለተወሰነ ጊዜ ወይም ለተወሰነ ስራ የተደረገ የስራ ውል መኖሩን አምኖ መልስ ሰጥቶ እያለ ሰበር ችሎቱ የስራ

ውል የለም በማለት የሰጠው ውሳኔ ሊታረም ይገባል፡፡በተጠሪ ድርጅት ከሚከፈለው ደመወዝ ላይ ግብር እየተቀነሰ እንዲሁም በስራ ሰዓት ሊያጋጥም ለሚችል አደጋ ተጠሪ የመድን ዋስትና እንዲኖረን ማድረጉ የተረጋገጠ ከመሆኑ አንፃር የስራ ውል ግንኙነት መኖሩን የሚያሳይ ነው፡፡የስር ፍ/ቤት ቁጥጥርና ክትትል የለም በማለት የሰጠው ድምዳሜ በማስረጃ ያልተረጋገጠ በመሆኑ የስራ ግንኙነቱ በአሰሪና ሰራተኛ አዋጅ 1156/2011 አይሸፈንም መባሉ የህግ ስህተት በመሆኑ ሊታረም ይገባል በማለት አመልክተዋል፡፡

የአመልካቾች አቤቱታ በሰበር አጣሪ ችሎት ተመርምሮ በዚህ ጉዳይ አመልካቾች ከተጠሪ ጋር የስራ ውል ግንኙነት የላቸውም መባሉን አግባብነት ከአዋጅ ቁጥር 1156/2011 አንቀጽ 10(1/ሠ) አንፃር ለማጣራት ጉዳዩ ያስቀርባል ተብሎ ተጠሪ መልስ እንዲሰጥበት ታዟል፡፡

ተጠሪ ድርጅት ባቀረበው መልስ አመልካቾች ሲሰሩበት የነበረው ስራ አልፎ አልፎ የሚሰራ ስራ ሆኖ የድርጅቱ ቋሚ ሥራ መደብ አይደለም፣ የስራ መደብ መጠሪያ የለውም፣ አመልካቾች ጋር የስራ ግንኙነት ስለሌለን ስራ ሲኖር ብቻ በፈቃዳቸው መጥተው የሚሰሩና ድርጅቱም ማስገደድና መቆጣጠር የማይችል፣ እነሱም ስራ በሌለ ጊዜ ለምን አልተጠራንም፣ለምን ደመወዝ አልተከፈለንም ማለት የማይችሉ በመሆኑ የስራ ውል ግንኙነት የለም፡፡የመስመር ዝርጋታ የሚሰሩ ቋሚ ባለሙያ ሰራተኞች አሉ፣ አመልካቾች የመስመር ስራ ሊሰሩ አይችሉም፣ አልሰሩም ከእውነት የራቀ አቤቱታ ነው፡፡ተጠሪ ድርጅት የመድን ዋስትና የሚሰጠው በማንኛውም ሁኔታ ለሚሰራው ሰራተኛ የቀንም ይሁን መደበኛ ሰራተኞች በስራ ምክንያት ለሚመጣ አደጋ ዋስትና መውሰዱ የሚጠበቅ ከህግ የመነጨ ግዴታ ሲሆን የስራ ውል አለ የሚያስብል አይደለም፡፡በአዋጁ አንቀጽ 4 መስፈርት አሟልቶ በቅጥር ላይ የተመሰረተ የስራ ግንኙነት መኖሩ ያልተረጋገጠ ስለሆነ የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የሰጠው ውሳኔ እንዲጸና በማለት ተከራክረዋል፡፡አመልካቾች አቤቱታቸውን የሚያጠናክር የመልስ መልስ አቅርበው ከመዝገቡ ጋር ተያይዟል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ እና የግራቀኙ ክርክር አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተመለከትነው ሲሆን ጉዳዩ ለሰበር ያስቀርባል ከተባለበት ጭብጥ አንጻር የስር ፍርድ ቤት ውሳኔ አግባብ ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ መርምረናል፡፡መዝገቡን መርምረን እንደተገነዘበነዉ አመልካቾች ከተጠሪ ጋር የነበረን የስራ ዉል ከህግ አግባብ ዉጭ በተጠሪ አነሳሽነት ተቋርጧል በሚል ወደ ስራ እንዲመልሳቸዉ ወይም ተገቢዉን ክፍያ እንዲከፍላቸዉ የጠየቁት የአሰሪና ሰራተኛ አዋጅን መሰረት በማድረግ ነዉ፡፡አመልካች በበኩሉ የስራ ግንኙነት እንደነበር ሳይክድ ግንኙነቱ ስራ ሲኖር ብቻ ሰርተዉ ክፍያ የሚከፈላቸዉ የቀን ሰራተኞች እንጂ በአሰሪና ሰራተኛ አዋጅ የሚሸፈን የስራ ግንኙነት ወይም ዉል የለንም በማለት ተከራክሯል፡፡ጉዳዩን በየደረጃዉ የመረመሩት የስር ፍርድ ቤቶች ማስረጃ አመዛዝነዉ ጉዳዩ በአሰሪና ሰራተኛ አዋጅ የሚሸፈን ነዉ ወይም አይደለም

በማለት የተለያየ አቋም ይዘዉ የሰጡትን ዉሳኔ በሰበር ስልጣኑ የመረመረዉ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ፍሬ ነገሩን መርምሮ አመልካቾች ከተጠሪ ጋር የነበራቸዉ የሥራ ግንኙነት አዋጁን መስፈርት የሚያሟላ አይደለም የሚል ድምዳሜ ላይ ደርሷል፡፡የዚህ ሰበር ችሎት ዉሳኔ የሚሻዉ አቢይ ነጥብ በአመልካቾች እና በተጠሪ መካከል በአሰሪና ሰራተኛ አዋጅ የሚሸፈን የስራ ዉል ግንኙነት የለም ተብሎ በሰበር ሰሚ ችሎት የተሰጠዉ ዉሳኔ ላይ የተፈጸመ የህግ ስህተት መኖር አለመኖሩን የሚመለከት ነዉ፡፡

ከመዝገቡ እንደሚታየዉ በአመልካቾችና እና በተጠሪ መካከል የስራ ዉል እንደነበር አላከራከረም፡፡አከራካሪዉ ጉዳይ ስራ ዉሉ በየትኛዉ ህግ ይሸፈናል የሚለዉ ነዉ፡፡አንድ ሰራተኛ ወይም የሥራ ዉል በየትኛዉ ህግ ይተዳደራል የሚለዉን ጥያቄ ለመመለስ ሰራተኛ ማነዉ የሚለዉን መመርመር ግድ ይላል፡፡ለዚህም የስራ ውል አመስራረትን አስመልክቶ በአሰሪና ሰራተኛ አዋጅ ቁጥር 1156/2011 ላይ የተደነገገውን በቀዳሚነት መመልከት ተገቢ ይሆናል፡፡በመሰረቱ በቅጥር ላይ የተመሰረተ የስራ ግንኙነት ሁሉ በአሰሪና ሰራተኛ አዋጅ የሚሸፈን አለመሆኑን የአዋጁ ተፈጻሚነት ወሰን የሚመለከተዉ አንቀጽ 3/2/ ድንጋጌ ያስገነዝባል፡፡በሌላ አገላለጽ በዚህ ድንጋጌ መሰረት በአዋጁ እንደማይሸፈኑ የተገለሉ የስራ ዉል አይነቶች ካልሆነ በስተቀር በአሰሪዉና በሰራተኛዉ መካከል ዉል መኖሩ ከተረጋገጠ ዉሉ የሚገዛዉ በዚሁ አዋጅ መሰረት እንደሆነ ይገመታል፡፡በአሰሪና ሰራተኛ መካከል የስራ ዉል የሚመሰረተዉ በአዋጁ አንቀጽ 4 ስር የተመለከቱት ሁኔታዎች ሲኖሩ ነዉ፡፡በአሰሪና ሰራተኛ አዋጁ አንቀጽ 4/1/ ላይ፣

« ማንኛዉም ግለሰብ ደመወዝ እየተከፈለው በአሰሪው መሪነት በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ ለተወሰነ ወይም ላልተወሰነ ጊዜ ወይም የተወሰነ ስራ ለአሰሪው ለመስራት ቢስማማ በሁለቱ መካከል የስራ ውል ይመሰረታል»በማለት ይደነግጋል፡፡ከዚህም መገንዘብ የሚቻለዉ የስራ ውል ማለት አንድ ሰዉ በአሰሪው የሚሰጠዉን ስራ ለመስራት እና ለሰራዉ ስራ ደግሞ ደመወዝ የሚከፈለዉ ሆኖ ዉሉ ቆይታ እንደስራዉ ዓይነት በጊዜ ወይም በስራዉ መጠን በጊዜ ወይም በሥራ ዐይነት በመወሰን የሚያደርጉት ስምምነት ነዉ፡፡በሌላ በኩል ደግሞ የስራ ውል እንዴት መደረግ እንዳለበት እና ዉሉ ሊይዛቸው ስለሚገባው ነገሮች በንኡስ ቁጥር 2 እና 3 ሥር ተመልክተዋል፡፡በዚህም መሰረት የስራ ውሉ ተዋዋይ ወገኖች የሚኖራቸው መብትና ግዴታ በማያጠራጥር አኳኋን በግልጽ ስምምነት መደረግ ያለበት ሲሆን ውሉም የስራውን አይነትና ቦታ፣ለስራው የሚከፈለውን ደመወዝ መጠን፣ የስሌቱን ዘዴ፣ የአከፋፈሉን ሁኔታና ጊዜ እና ውሉ ፀንቶ የሚቆይበትን ጊዜ መያዝ እንደሚኖርበት ተመልክቷል፡፡የስራ ውል በዚህ መልክ መደረግ የሚኖርበት ሲሆን በሕግ በተለየ አኳኋን ካልተደነገገ በቀር የተለየ ፎርም የሌለው ስለመሆኑ በአንቀጽ አምስት ስር ተመላክቷል፡፡ስለሆነም የስራ ውል የተለየ ፎርም እንዲኖረዉ ሕጉ ስላላስገደደ በማንኛውም አይነት ሁኔታ ሊቋቋም እንደሚችል መገንዘብ ይቻላል፡፡

ወደ ተያዘዉ ጉዳይ ስንመለስ በአመልካቾችና በተጠሪ መካከል የነበረዉ የስራ ግንኙነት ምን ይመስላል የሚለዉን ጉዳይ የመረመሩት የሥር ፍርድ ቤቶች ያረጋገጡት ፍሬ ነገር የስልክ መስመር ዝርጋታ ወይም ብልሽት ጥገና ስራ ሲኖር እየተጠሩ የጉልበት ስራ ማለትም ምሶሶ እና ሌሎች መገልገያ እቃዎችን ከቦታ ቦታ መሸከም፤ጉድጓድ መቆፈርና ሌሎች ተዛማጅ ስራዎችን ማከናወን፤በሰሩት ስራ ልክ በየሁለት ሳምንቱ ክፍያ የሚፈጸምላቸዉ ስለመሆኑና የሚሰሩትም ሆነ ክፍያ የሚፈጸምላቸዉ ስራ ሲኖር ብቻ መሆኑን የሚያሳይ ነዉ፡፡በዚህ ላይ በግራ ቀኙ መካከል መካካድ የለም፡፡ከላይ እንደተገለጸዉ በአሰሪና ሰራተኛ አዋጁ መሰረት በቅጥር ላይ የተመሰረተ የስራ ዉል በአሰሪና ሰራተኛ መካከል ተቋቁሟል ለማለት የሚቻለዉ ሰራተኛዉ ስራ መስራቱ እና ደመወዝ ወይም የሥራ ዋጋ መከፈሉ ብቻ ሳይሆን በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ በአሰሪዉ መሪነት የሚሰራ ሰራተኛ መሆኑም ጭምር መረጋገጥ እንዳለለበት ያሣያል፡፡በዚህ ረገድ ይግባኝ ሰሚዉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አሰሪዉ በሚሰጣቸዉ ስራ ልክ ሰርተዉ በዚህም ልክ የሚከፈላቸዉ ስለመሆኑ በማስረጃ የተረጋገጠዉን ፍሬ ነገር መሰረት በማድረግና ከህጉ ጋር በማዛመድ የአሰሪና ሰራተኛ ግንኙነት አላቸዉ ነገር ግን የዉሉ ዓይነት እና ዉሉ የተቋረጠበትን ምክንያት ህጋዊነት የሥር ፍርድ ቤት እንዲመረምር በሚል መልሶለታል፡፡

የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ይህን ዉሳኔ ለመሻር መሰረት ያደረገዉ አመልካቾች ስራ ሲኖር ብቻ የሚጠሩ ስለሆነ በአሰሪዉ በኩል ቁጥጥር የሚደረግባቸዉ አይደሉም፤ከስራ ለመቅረት ፈቃድ አይጠይቁም፤ረዳት የመስመር ሰራተኛ የሚባል የሥራ መደብ የለዉም፤መደበኛ ፔሮል የላቸዉም፤የበጀት ድጋፍ የለዉም እናም መመዘኛዉን አሟልተዉ በአሰሪዉ ስለመቀጠራቸዉ በምክሮቻቸዉ አላረጋገጡም፤በመቆጣጠር ረገድ ተጠሪ የነበረዉ ተግባር አልተረጋገጠም በማለት የቀን ሰራተኛ እንጂ የስራ ዉል ግንኙነት አላቸዉ የሚባል አይደለም በማለት ነዉ፡፡ከክርክሩ እንደተገነዘብነዉ ስራዉ የድርጅቱ ቋሚ ስራ መሆኑ አከረካሪ አለመሆኑን ነገር ግን አመልካቾች ስራዉን የሚሰሩት አልፎ አልፎ የመስመር ዝርጋታ ወይም ጥገና ሲኖር ብቻ በመሆኑ ቋሚ የስራ መደብ አለመኖሩ መሰረታዊ መመዘኛ ሆኖ መዉሰዱ ተገቢ አለመሆኑን ነዉ፡፡ሌላዉ አሰሪዉ ቁጥጥር እና ክትትል አያደርግም የሚለዉ የሰበር ችሎቱ ዉሳኔ ምክንያት አግባብነት ሲታይ ቁጥጥርና ክትትል የሚለዉ ልክ እንደመደበኛ ሰራተኛ በማየት ከሆነ ስህተት ነዉ፡፡ምክንያቱም በዚህ ጉዳይ የተረጋገጠዉ ፍሬ ነገር የሚያሳየን ስራዉ አልፎ አልፎ የሚሰራ ስራ በመሆኑና አመልካቾችም በአሰሪዉ የተሰጣቸዉን ስራ ሰርተዉ በሰሩት ስራ ልክ በየአሰራ አምስት ቀን ደመወዝ የሚከፈላቸዉ በመሆኑ አሰሪዉ የስራዉን ዓይነትና መጠን በመወሰንና በመምራት ረገድ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ቁጥጥር የሚያደርግ መሆኑን መገንዘብ ይቻላል፡፡ከዚህም በተጨማሪ ሰበር ችሎቱ ለዉሳኔ መሰረት ያደረጋቸዉ ምክንያቶች ረዳት የመስመር ሰራተኛ የሚባል የሥራ መደብ የለዉም፤መደበኛ ፔሮል የላቸዉም፤የበጀት ድጋፍ የለዉም የሚሉት በዋናነት የፍሬ ነገር ጉዳይ እና የማስረጃ ምዘና ላይ ተመሰረተ መሆኑን ነዉ፡፡

እንደሚታወቀዉ የሰበር ሰሚ ችሎት የተቋቋመበት ዋነኛ ዓላማ አንድ ወጥ የህግ አተረጓጎም እንዲኖር እና የዉሳኔዎችን ተገማችነት ለማረጋገጥ ነዉ፡፡በፌዴራልም ሆነ በክልል ፍርድ ቤቶች ሰበር ሰሚ ችሎት እንዲቋቋም ያስፈለገዉ በኢፌዲሪ ሕገ-መንግሥት አንቀጽ 80(3)(ሀ ና ለ) ላይ እንደተደነገገዉ በመጨረሻ ውሳኔ ላይ የተፈጸመ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ለማረም ነዉ፡፡ህገ መንግስቱን ተከትሎ የወጣዉ የፌደራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀጽ 10 እንዲሁም ይህንን አዋጅ የተካዉ አዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀጽ 4/1/ እና 10 ድንጋጌዎች የሰበር ስልጣን የሚመለከቱ ሲሆን ሰበር ችሎቱ ማስረጃ ማጣራትና መመዘን ሥልጣን እንደሌለው ያስገነዝባሉ፡፡የአማራ ክልል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 223/2007 አንቀጽ 17 ተመሳሳይ ዓላማ እና ይዘት እንዳለዉ ግልጽ ነዉ፡፡ስለዚህም የሰበር ችሎት ዋና ተግባር የፍርድ ቤቶች ዉሳኔ ተገማች እና ወጥ የህግ አተረጓጎም እና አተገባበር እንዲኖር ማድረግ በመሆኑ ማስረጃ የመመርመርና የመመዘን ጉዳይ ላይ ጥንቃቄ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡በእርግጥ ማስረጃ ለመስማትና ለመመዘን ሥልጣን የለውም ማለት ግን ከማስረጃ ጋር የተያያዘ ሞጉጥ የሠበር አቤቱታ አይመለከትም ማለት አይደለም፡፡ማስረጃ ለመመዘን ሥልጣን የተሠጠው ፍርድ ቤት ማስረጃ ሲቀበል የተከራካሪዎችን እኩል የመደመጥ መብት ካላከበረ፣ የማስረዳት ሸክም (burden of production) የማን ነው የሚለውን ካልለየ፣ የማስረጃ ተቀባይነትና ተገቢነት ላይ መከተል የሚገባውን ሥርዓት ካልተከተለ፣ በምዘና ጊዜ የሁሉንም ተከራካሪዎች ማስረጃ አብሮ ካልመዘነ፣ የተለየ የማስረዳት ደረጃ (standard of proof) የሚጠይቁ ጉዳዮችን በሚጠይቀው ደረጃ ልክ መረጋገጡን ካላሳየ እና በመሠረታዊ ሕግ ሆነ በሥነ-ሥርዓት ሕግ ያሉትን የማስረጃ ሕጎችና መርሆች ካላከበረ ጉዳዩ የማስረጃ ምዘና ሳይሆን የሕግ አተረጓጎም ስህተትና ፍርድ ቤት ያለበትን ኃላፊነት አለመወጣት ስለሚሆን የሰበር ሰሚ ችሎቱ የሚመለከተው ጉዳይ ይሆናል፡፡

በተያዘዉ ጉዳይ ከላይ እንደተገለጸዉ የስራ ዉል በጽሁፍ ወይም በቃል ሊደረግ ይችላል፡፡ዉል መኖሩን ለማስረዳት የሚቀርበዉ ማስረጃ ዓይነትም እንደነገሩ ሁኔታ ሰነድ ወይም ምስክር ሊሆን ይቻላል፡፡አመልካቾች ከተጠሪ ጋር የነበራቸዉ ግንኙነት አሰሪና ሰራተኛ ግንኙነት መሆኑን ለማስረዳት ያቀረቡት ማስረጃ የደመወዝ ክፍያ ፔሮል፣ በድርጅቱ የተሰጣቸዉ መታወቂያ እና የሰዉ ምስክር ሲሆን ተጠሪም በበኩሉ ማስተባበያ ክርክር እና ማስረጃ ማቅረቡን መዝገቡ ያሣያል፡፡እነዚህን ማስረጃዎች የመመርመር እና ፍሬ ነገር የማረጋገጥ ሃላፊነትና ስልጣን ያለዉ ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት ማስረጃዎቹን ይዘት መመርምሮና አመዛዝኖ ግንኙነታቸዉ የአሰሪና ሰራተኛ ግንኙነት መሆኑን አረጋግጧል፡፡አመልካቾች እንደ ክርክራቸዉ አቀራረብ በዚህ ልክ ካስረዱ ከተጠሪ የሚጠበቀዉ የስራ ዉሉ በአሰሪና ሰራተኛ ህግ የማይሸፈንበትን ምክንያት በአዋጅ አንቀጽ 3/2/ ስር ከተደነገጉት ማግለያ ሁኔታዎች በአንዱ ወይም በሌላዉ የሚጠቃለል መሆኑን ማስረዳት ነዉ፡፡ይህ ስለመሆኑ ደግሞ በተጠሪ በኩል የቀረበ ክርክርም ሆነ ማስረጃ ስለመቅረቡ መዝገቡ አያሣይም፡፡በመሆኑም በከፍተኛዉ ፍርድ ቤት ማስረጃ ተመዝኖ የተረጋገጠዉን ፍሬ ነገር

ጉዳይ ይህ ሰበር ችሎት የማይቀበልበት ምክንያት የለም፡፡ይህ ከሆነ ደግሞ ስራዉ አልፎ አልፎ የሚሰራ ስራ በመሆኑም ሆነ ደመወዝ በየአስራ አምስት ቀን መከፈሉ እንዲሁም ለስራዉ ቋሚ የስራ መደብ አለመኖሩ ብቻ ግንኙነታቸዉ በአሰሪና ሰራተኛ አዋጅ የሚሸፈን አይደለም ሊያሰኝ አይችልም፡፡

ሲጠቃለል በክርክሩ የተረጋገጠዉ ፍሬ ነገር አመልካቾች የሚሰሩት ስራ የተጠሪ ቋሚ ስራ መሆኑ፣ስራዉ አልፎ አልፎ የሚሰራ እና አመልካቾችም ስራዉ ሲኖር ተጠርተዉ ለሰሩት ስራ ደመወዝ በየአስራ አምስት ቀን የሚከፈላቸዉ መሆኑን ያሳያል፡፡ተጠሪ በበኩሉ አመልካቾች ቀን ሰራተኞች ናቸዉ ብሎ ቢከራከርም የሥራ ዉል መኖር የሚወሰነዉ በስራዉ ላይ እንጂ በቆይታዉ ጊዜ አለመሆኑን የህጉ ይዘት ያስገነዝባል፡፡ስለሆነም በአመልካቾች እና በተጠሪ መካከል ያለዉ የስራ ዉል በአሰሪና ሰራተኛ አዋጅ የሚሸፈን ነዉ በማለት ይግባኝ ሰሚዉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የደረሰበት ድምዳሜ በማስረጃ የተረጋገጠዉን ፍሬ ነገር እና ህጉን ያገናዘበ ሆኖ እያለ የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት የፍሬ ነገር ክርክር እና ማስረጃ ምዘና ጉዳይ ላይ ተመስርቶ ዉሳኔዉን መሻሩ በህግ ለሰበር ሰሚ ችሎት ከተሰጠዉ ስልጣን ዉጪ በመሆኑ ሊታረም የሚገባዉ ነዉ ብለናል፡፡በዚሁ አግባብ ተከታዩን ዉሳኔ ሰጥተናል፡፡

<u>ዉሳኔ</u>

1ኛ/አማራ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ 0330427 ላይ በቀን 14/05/2013ዓ.ም የሰጠዉ ዉሳኔ በፍ/ብ/ስ/ስ/ህግ ቁጥር 348/1/ መሰረት ተሽሯል፡፡

2ኛ/የደቡብ ወሎ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ/47249 ላይ በቀን 25/02/2013ዓ.ም የሰጠዉ ፍርድ ጸንቷል፡፡ይጻፍ

3ኛ/በዚህ ፍርድ ቤት ለተደረገዉ ክርክር ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸዉን ይቻሉ ብለናል፡፡

<u>መዝገቡ ተዘግቷል ይመለስ፡፡</u>

ማ/አ የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

የሠ/መ/ቁጥር 209295

የካቲት 30 ቀን 2014 ዓ/ም

ዳኞች፡- ብርሃኑ አመነው

ተሾመ ሽፈራው

ሀብታሙ እርቅይሁን

ብርሃኑ መንግሥቱ

ነጻነት ተገኝ

አመልካች፡- አቶ አፈወርቅ መንግስቱ

ተጠሪዎች፡- ወጋገን ባንክ አ.ማ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የስራ ስንብትን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ በተጀመረበት በፌደራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት አመልካች በተጠሪ ላይ ባቀረበው ክስ በተጠሪ ባንክ ውስጥ ከሐምሌ 20 ቀን 1996 ዓ.ም ጀምሮ በተለያዩ የስራ መደቦች ላይ፤ በኋላም ከስራ እስከ ተሰናበትኩበት ታህሳስ 24 ቀን 2011 ዓ.ም ድረስ የባንኩ የቱሉ ቦሎ ቅርንጫፍ ስራ አስኪያጅ ደረጃ 3 የስራ መደብ ላይ በወር ብር 23,750.00 እየተከፈለኝ በማገልገል ላይ እያለሁ እንደ አውሮፓውያን አቆጣጠር በሴፕቴምበር 06 ቀን 2018 በቅርንጫፉ በባለ መቶ እና በባለ ሃምሳ ብር ኖት እሽግ ውስጥ የባለ አስር ብር ኖት ተቀላቅሎ በመታሸጉ ምክያት ለተከሰተ የብር 469,000.00 ጉድለት ተጠያቂውም አንተ ነህ በማለት ተጠሪ በቀን 23/04/2011 ዓ.ም በተፃፈ ደብዳቤ ከስራዬ ያሰናበተኝ በመሆኑ ስንብቱ ህገ-ወጥ ነው ተብሎ ልዩ ልዩ ክፍያዎች እንዲከፈሉኝ ይወሰንልኝ በማለት የጠየቀውን ዳኝነት መነሻ ያደረገ ነው፡፡

ተጠሪ በበኩሉ በሰጠው መልስ የአመልካች የስራ ውል የተቋረጠው እንደ አውሮፓውያን አቆጣጠር ሴፕቴምበር 06 ቀን 2016 ዓ.ም በተደረገ ምርመራ በባንኩ ቱሉ ቦሎ ቅርንጫፍ በባለ መቶ እና ባለ ሃምሳ ብር ኖት እሽግ ውስጥ የባለ አስር ብር ኖት ተቀላቅሎ የብር 469,000.00 ጉድለት በመከሰቱ እና ጉደለቱ ከመከሰቱ በፊት የቅርንጫፉ ዋና ገንዘብ ያዥ እረፍት ሲወጡ እ.አ.አ. በኦገስት 31 ቀን 2018 ዓ.ም የተደረገው የገንዘብ ርክክብ የባንኩን መመሪያ በመጣሱ ሲሆን ይህም ጥፋት ያለማስጠንቀቂያ ከስራ ሊያሰናብት የሚችል የዲሲፕሊን ጥፋት በመሆኑ ነው፤ ጉዳዩም በዲሲፕሊን ኮሚቴ ታይቶ ከስራ እንዲሰናበት የተደረገ ስለሆነ ስንብቱ ህጋዊ ነው፤ ሊከፈለው የሚገባ ክፍያም የለም በማለት ተከራክሯል፡፡

ጉዳዩ የቀረበለት የስር መጀመሪያ ፍርድ ቤትም የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ ከመረመረ በኋላ ጉድለቱ የተፈጠረዉ በአመልካች ቸልተኝነት ስለመሆኑ ተጠሪ በማስረጃ ያላረጋገጠ በመሆኑ ስንብቱ ህገ-ወጥ ነዉ በማለት ካሳን ጨምሮ የተለያዩ ክፍያዎችን በጠቅላላዉ ብር 415,624.99 ተጠሪ ለአመልካች ይክፈለዉ በማለት ወስኗል። በዚህ ዉሳኔ ቅር የተሰኘዉን ተጠሪ ይግባኙን ለፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ያቀረበ ሲሆን ፍርድ ቤቱም በጉዳዩ ላይ ግራ ቀኙን ካራከር በኋላ ተጠሪ አመልካች የስራ መሪ መሆኑን በመጥቀስ ያቀረበዉን መቃወሚያ ዉድቅ በማድረግ ግራ ቀኙን አከራክሮ ዉሳኔ መስጠቱ የፌደራል ጠቅላይ ሰበር ሰሚ ችሎት በሰበር መዝገብ ቁጥር 92466 እና በሌሎች በርካታ መዛግብት ላይ የሰጠዉን አስገዳጅ የህግ ትርጉም ይቃረናል፤የስር መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ጉዳዩን የማየት ስልጣን የለዉም በማለት ዉሳኔዉን ሽሮታል። ለዚህ ፍርድ መነሻ የሆነዉ የሰበር አቤቱታ በአመልካች የቀረበዉም ይህንኑ በመቃወም ለማስለወጥ ነዉ።

አመልካች ሰኔ 11 ቀን 2013 ዓ.ም በተፃፈ የሰበር አቤቱታ በስር ፍርድ ቤት ተፈጽመዋል ያላቸዉን ስህተቶች በመዘርዘር በዚህ ችሎት እንዲታረምለት ጠይቋል። የአቤቱታዉ ይዘትም በአጭሩ በተጠሪ ባንክ የተቀጠርኩት በተራ ሰራተኛነት ሆኖ እያለ እና ከተቀጠርኩ በኋላም በመካከላችን የተሻሻለ የስራ ዉል ባልተፈፀመበት ተጠሪ የስራ መሪ እንደሆንኩ አስመስሎ ያቀረበዉ ክርክር ተቀባይነት አግኝቶ በዚሁ አግባብ ዉሳኔ መሰጠቱ፤ ተጠሪ ባንክ አስራ አንድ አባላት ባሉት የዳይሬክተሮች ቦርድ የሚመራ ሲሆን ባንኩን የሚያስተዳድሩት ለቦርዱ ተጠሪ የሆኑ አንድ ፕሬዝዳንት እና አምስት ምክትል ፕሬዝዳንቶች አሉት፤አመልካች የምሰራበት ቅርንጫፍ በአነስተኛ ደረጃ የተመደበ በመሆኑ እኔም ደረጃ ሶስት ስራ አስኪያጅ የስራ መደብ ተሰጥቶኝ በዚሁ የስራ መደብ ላይ ሳገለግል ቆይቻለሁ፤ ከአጠቃላይ የባንኩ መዋቅር የአልካች የስልጣን ደረጃ ከአራት መቶ ሰዎች በኋላ ሲሆን ይህም እንደ ክፍል ኃላፊ ስልጣን የሚቆጠር ነዉ፤ በስሬ የማስተዳድራቸዉ ሰራተኞች አስራ አምስት የማይሞሉ ሲሆን እነዚህን ሰራተኞች ከማስተዳደር ባለፈ ፖሊሲ የማዉጣት፤ የመፈፀም፤ ሰራተኛ የመቅጠር፤የማዘዋወር፤ የመመደብ፤ የማባረር፤ የማገድ፤ እርምጃ የመዉሰድ፤ የመቀነስ እና የመሳሰሉት ስልጣኖች እንደሌሉኝ እየታወቀ የስራ መሪ ነዉ ተብሎ መወሰኑ፤ የቅርንጫፍ ስራ አስኪያጅ የስራ አስኪያጅ የስራ መዘርዝር በእንግሊዝኛዉ እና በአማርኛዉ መካከል ያለዉን የትርጉም መዛባት አመልካች ማብራሪያ እንዲሰጥበት ጥያቄ አቅርቤ በዝምታ ታልፎ የስራ መሪ ነዉ ተብሎ የተሰጠዉ ዉሳኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት በመሆኑ ሊታረም ይገባዋል የሚል ነዉ።

ጉዳዩም በሰበር አጣሪ ችሎት ተመርምሮ አመልካች የስራ መሪ ነዉ? ወይስ አይደለም? የሚለዉ ነጥብ ከአዋጅ ቁጥር 1156/2011 እና በዚህ ሰበር ችሎት ከሰጡት የህግ ትርጓሜዎች አንፃር ተጠሪ ባለበት መጣራት ያለበት መሆኑ ታምኖበት ለዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት ቀርቧል። በዚሁም መሠረት ተጠሪ በተደረገለት ጥሪ መሠረት ህዳር 20 ቀን 2014 ዓ.ም ጽፎ ባቀረባዉ መልስ አመልካች በተጠሪ መስሪያ ቤት ዉስጥ የቅርንጫፍ ስራ አስኪያጅ መደብ ላይ ሲሰራ እንደነበረና ውሉም የተቋረጠው ስራ አስኪያጅ

ሆኖ ሲያገልግል የቆየ መሆኑ ከስር ፍ/ቤት ጀምሮ የተረጋገጠ ሲሆን እንደ ቅርንጫፍ ስራ አስኪያጅነቱ ደግሞ የቅርንጫፉን እቅድና ዓላማዎች ማዘጋጀትና የማስፈፀም፣ የቅርንጫፍ በጀት ማዘጋጀት እና አፈፃፀማቸው የመከታተል፣ በቅርንጫፍ ያሉ ሰራተኞች ውጤታማ እንዲሆኑ ማሰልጠን፣ በስሩ ያሉ ሰራተኞችን የስራ ውጤት መመላት፣ የሰራተኞችን የስነ-ምግባር ሁኔታ መከታተል፣ ቅርንጫፉን የሚመለከቱ ውሳኔዎችን በተመለከተ በተለያዩ ኮሚቴዎች ውስጥ በመሳተፍ ውሳኔ የማሳለፍ ኃላፊነት እንዳለበት በስራ መዘርዝሩ ላይ የተቀመጠ ሲሆን ከፍተኛ ፍርድ ቤቱም ይህንኑ በማረጋገጥ የሰጠው ውሳኔ ተገቢ በመሆኑ የአመልካች አቤቱታ ውድቅ ሊደረግ ይገባል በማለት ተከራክሯል፡፡ አመልካችም የሰበር አቤቱታውን በማጠናከር የመልስ መልስ ሰጥቶ ተከራክሯል፡፡

ከስር ጀምሮ የጉዳዩ አመጣጥ እና የግራ ቀኝ የክርክር ይዘት አጠር ባለ መልኩ ከላይ የተገለፀውን ሲመስል ይህ ችሎትም የሰበር አቤቱታውን ለማስቀረብ በሰበር አጣሪ ችሎት የተያዘውን ጭብጥ ከግራ ቀኙ ክርክር እና ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ መዝገቡን እንደሚከተለው መርምሮታል፡፡ እንደመረመረዉም የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት አመልካች የስራ መሪ ነው በሚል ድምዳሜ ላይ የደረሰው አመልካች በተጠሪ ባንክ የቅርንጫፍ ስራ አስኪያጅ በመሆኑ የሚያከናውናቸው ዋና ዋና ተግባራት የቅርንጫፍ ግብአቶችን ለማሳደግ ማሰባሰብ፣ እቅድና ፕሮግራሞችን ማዘጋጀት እና መተግበር፣ የቅርንጫፍን የኦፕሬሽን ፖሊሲ እና አስራሮች እንዲሁም ውጫዊ የደንብ መስፈርቶች ተገዥነት መቆጣጠር እንዲሁም አስፈላጊ ሲሆን የለውጥ ማሻሻያ ምክሮችን መስጠት፣ የቅርንጫፍ እቅድ እና ዓላማዎች ማዘጋጀት እና ተግባራቸውን መምራት፣ በስራቸው የሚገኙትን ሰራተኞች የስነ ምግባር ሆኔታዎች ማስተዳደር እና በቅርንጫፍ የውሳኔ አሰጣጥ ሂደት ላይ የተለያዩ ኮሚቴዎች አባል በመሆን መሳተፍ ስለመሆኑ ተረጋግጧል፡፡ አመልካች “በአማርኛው የቅርንጫፉ የኦፕሬሽን ፖሊሲ” በሚል የተገለፀው ትክክለኛ ትርጉም አይደለም በሚል የሚከራከር ቢሆንም በመሰረታዊነት የስራ ድርሻው ከላይ የተመለከተው ስለመሆኑ ክዶ አይከራከርም፡፡ የዚህን ችሎት ምላሽ የሚያሻው መሰረታዊ ነጥብ አመለካች እንደ ቅርንጫፍ ስራ አስኪያጅ እንዲያከናውን የሚጠበቁበት ከላይ የተመለከቱት ተግባራት በአሰሪና ሰራተኛ አዋጅ ቁጥር 1156/2011 አግባብ አመልካችን የስራ መሪ የሚያሰኝ መሆን አለመሆኑ ነው፡፡

በአዋጁ አንቀጽ 2(10) ላይ እንደተመለከተው የስራ መሪ ማለት በሕግ ወይም እንደ ድርጅቱ የስራ ጠባይ በአሰሪው በተሰጠው የውክልና ስልጣን መሰረት የስራ አመራር ፖሊሲዎችን የማውጣትና የማስፈፀም ስልጣን ያለው ወይም ሰራተኛን የመቅጠር፣ የማዘዋወር፣ የማገድ፣ ማሰናበት ወይም የመመደብ ተግባሮችን የመወሰን ስልጣን ያለው ግለሰብ ሲሆን እነዚህን የስራ አመራር ጉዳዮች አስመልክቶ የአሰሪውን ጥቅም ለመጠበቅ አሰሪው ሊወስድ ስለሚገባው እርምጃ በማንም ሳይመራ የራሱን ውሳኔ ሀሳብ የሚያቀርብ የህግ አገልግሎት ኃላፊንም ይጨምራል በማለት ትርጉም ሰጥቷል፡፡ ከዚህ መረዳት የሚቻለዉ አንድ ሠራተኛ የሥራ አመራር ፖሊሲዎችን የሚያወጣና የሚያስፈጽም

ወይም ሠራተኛን የሚቀጥር እና የማሰናበት ዕርምጃ የመወሰድ ተግባራትን የሚያከናውን የሥራ መሪ ሊባል የሚችል መሆኑን ነዉ። ሠራተኛዉ ከእነዚህ አንዱን ወይም ከዚያ በላይ ሥራዎችን የሚሠራ መሆኑ በማስረጃ መረጋገጥ ያለበት ሲሆን ተግባራቱ መኖራቸዉ ከተረጋገጠ ደግሞ በአሰሪዉ እና በሰራተኛዉ መካከል ያለዉ ግንኙነት በአሰሪና ሰራተኛ አዋጅ ጉዳይ የሚገዛበት አግባብ አይኖርም። ህግ አዉጪዉ ይህንን ልዩ ሁኔታ ወይም ማግለያ በአዋጁ ያስቀመጠበት መሰረታዊ ዓላማ የሠራ መሪ አሰሪዉን ወክሎ የድርጅቱን ፖሊሲ የሚያቅድና የሚያስፈጽም ነዉ ተብሎ ስለሚገመት ከሌላዉ ሰራተኛ መብት ጋር የጥቅም ግጭት እንዳይፈጠር በሚል መነሻ ሃሳብ እንደሆነ ይታወቃል። ስለዚህም አንድ ቀጣሪ የስራ መሪ ነዉ ተብሎ ሊፈረጅ የሚችለዉ በህጉ የሥራ የመሪ ተግባራት ተብለዉ የተዘረዘሩትን ስራዎች ለማከናዉን ስልጣን የተሰጠዉ መሆኑ መረጋገጥ አለበት።

በተያዘዉ ጉዳይ በአመልካች ድርጅት መዋቅር መሰረት ተጠሪ የ3ኛ ደረጃ ቅርንጫፍ ስራ አስኪያጅ ሆነዉ ሲሰራ እንደነበር አላከራከረም። በሌላ በኩል ተጠሪ ስራ አስኪያጅ የሚል ስያሜ መያዙ በራሱ የስራ መሪ የሚያሰኝ አለመሆኑን ከህጉ አነጋገር የምንገነዘበዉ ጉዳይ ሲሆን ዋናኛ መስፈርቱ የስራ መሪ የሚያሠኙ ጉዳዮችን በሚመለከት የመወሰን ስልጣንና ተግባር መኖሩ አለመኖሩ ላይ የሚመሰረት መሆኑን ነዉ። ሆኖም የአመልካች የስራ ድርሻ መሆናቸዉ የተረጋገጠዉ ከላይ የተመለከቱት ተግባራት አመልካች የተጠሪ ባንክ ፖሊሲ ጉዳዮች ላይ የማቀድ እና የመወሰን እንዲሁም ሰራተኛ የመቅጠርም ሆነ የማሰናበት ተግባራትን የሚያካትት አይደለም። ይልቁንም እነዚህ ተግባራት በበላይ አካላት የሚወሰኑ ሆኖ የአመልካች ኃላፊነት ከዚህ በመለስ ያሉ የእለት ከእለት አስተዳደራዊ ስራዎች ላይ የተገደበ ስለመሆኑ ለመገንዘብ ተችሏል። ይህም የሚያሳየዉ ተጠሪ በሚመራዉ ቅርንጫፍ ባንክ የእለት ስራዎችን መምራትና ሰራተኛ ማስተዳደር ስልጣን ቢኖረዉም ሠራተኞችን የመቅጠርና ማሰናበት ስራዉ በበላይ አካላት የሚሰራ መሆኑን ነዉ።

በአጠቃላይ አመልካች እንደ ቅርንጫፍ ስራ አስኪያጅ የተሰጠዉ ኃላፊነት የስራ መሪን አስመልክቶ በአዋጅ አንቀጽ2(10) ላይ የተመለከተዉን ትርጓሜ ያማያሟላ ሆኖ እያለ የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠዉ ዉሳኔ በማስረጃ የተረጋገጠዉን ፍሬ ነገር እንዲሁም ለጉዳዩ አግበብነት ያለዉን ድንጋጌ ይዘት ያላገናዘበ በመሆኑ በፌዴራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀጽ 2/4/እና 10 ድንጋጌ መሰረት በዚህ ችሎት ሊታረም የሚገባ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ ተገኝቷል። በዚሁ አግባብ ተከታዩን ዉሳኔ ተሰጥቷል።

<u>ዉሳኔ</u>

1. የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 249947 ግንቦት 18 ቀን 2013 ዓ/ም በዋለዉ ችሎት የሰጠዉ ዉሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348(1) መሰረት ተሽሯል።

2. የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ተዘግቶ የነበረዉን መዝገብ በማንቀሳቀስ አመልካች ከስራዉ የተሰናበተበትን አግባብ ህጋዊነት ከግራ ቀኝ ክርክር አንፃር በመመርመር የመሰለዉን ዉሳኔ እንዲሰጥ መዝገቡ በፍ/ብ/ሥ/ሥርዓት ህጉ አንቀጽ 341(1) መሠረት ተመልሶለታል፡፡
3. በዚህ ችሎት የተደረገዉ ክርክር ያስከተለዉን ወጭና ኪሣራ ግራ ቀኙ የየራሳቸዉን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ

አ/መ የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ከውል ውጪ ኃላፊነት

የሰ/መ/ቁ. 199777

ቀን፡- ጥቅምት 04 ቀን 2014 ዓ/ም

ዳኞች፡- ብርሃኑ አመነው

ተሾመ ሽፈራው

ሀብታሙ እርቅይሁን

ብርሃኑ መንግስቱ

ነፃነት ተገኝ

አመልካች፡- የኢትዮጵያ ኮንስትራክሽን ሥራዎች ኮርፖሬሽን - የርብ ግድብ መስኖ ልማት ፕሮጀክት - ነ/ፈጅ መካኒንት ደግነት - ቀረቡ

ተጠሪ፡- 1. ሕፃን አብርሃም ግዛቸው - ሞግዚት ግዛቸው ሞላ - ቀረቡ

2. የኢትዮጵያ መድን ድርጅት - አልቀረቡም

3. አቶ ደረጀ ከበደ - በሌለበት የሚታይ

መዝገቡ ተምርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሠጠ፡፡

ፍርድ

የሰበር መዝገቡ የቀረበው የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በሠጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሞበታል በሚል ነው፡፡ የክርክሩን አመጣጥ ከስር ፍርድ ቤት የመዝገብ ግልባጭ እንደተረዳነው አመልካች በሥር ፍርድ ቤት ተከሳሽ ሲሆን 1ኛ ተጠሪ ከሳሽ፣ 2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች ጣልቃ ገብ ነበሩ፡፡ 1ኛ ተጠሪ ግንቦት 11 ቀን 2009 ዓ/ም በተጻፈ ያቀረቡት ክስ ታህሳስ 17 ቀን 2007 ዓ/ም ሕፃን አብርሃም ግዛቸው ከአዲስ ዘመን ወደ ርብ ግድብ እየተጓዘ እያለ ንብረትነቱ የአመልካች የሆነ ኮድ 3-47221 ቶዮታ መኪና በ3ኛ ተጠሪ እየተሽከረከረ እግሩን በመግጨት ከጉልበቱ በታች ባደረሰበት ጉዳት እግሩ ከጥቅም ውጭ ሲሆን በሕክምና 30% ጉዳት መድረሱ ተረጋግጧል፡፡ ሕፃን አብርሃም ግዛቸው ጉዳቱ ሲደርስበት 5 ዓመቱ ሲሆን እስከ 62 ዓመት ድረስ ሊኖር ስለሚችል ሊያገኝ የሚችለውና በጉዳቱ የሚያጣው ጥቅም በቀን 30 ብር በወር 900 ሲሆን 900 ብር x 12 ወራት x 57 ዓመት ብር 615,600.00፣ የሞራል ካሣ ብር 1,000.00 እና የሕክምናና የትራንስፖርት ወጪ ብር በድምሩ ብር 617,502.00 አመልካች እንዲከፍል እንዲወስንላቸው ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡ አመልካች ያቀረበው መልስ ክሱ በፍ/ሕ/ቁ. 2143(1) መሠረት በይርጋ የታገደ ነው፡፡ ጥፋት ያጠፋው ሾፌር ነው መጠየቅ ያለበት፤ ባለንብረት ኃላፊነት የለበትም፡፡ የ5 ዓመት ሕፃን እስከ 18 ዓመት ድረስ ሥራ አይሰራም፡፡ ጉዳቱ በሂደትም ስለዳነ አሉታዊ ጉዳት አላስከተለም፡፡ 30% ቋሚ ጉዳት የተባለው

ያልተብራራ እና በተጎጂው ሕይወት ላይ የሚያስከትለው የመሥራት ችግር ያልተገለጸ ስለሆነ ክሱ ውድቅ ሊደረግ ይገባል። ለተሸከርካሪው 3ኛ ወገን ኃላፊነት ሽፋን የሠጠው 2ኛ ተጠሪ እና የተሸከርካሪው ሾፌር የነበረው 3ኛ ተጠሪ ወደ ክርክሩ ጣልቃ እንዲገቡ ጠይቋል። ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት 2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች ጣልቃ እንዲገቡ ያዘዘ ሲሆን 2ኛ ተጠሪ ቀርቦ አደጋውን አመልካች ያላሳወቀኝ በመሆኑ ኃላፊነት የለብኝም በማለት የተከራከረ ሲሆን 3ኛ ተጠሪ መጥሪያ ደርሷቸው ባለመቅረባቸው ጉዳዩ በሌሉበት ታይቷል።

የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ጉዳዩን መርምሮ የይርጋ መቃወሚያውን ውድቅ ካደረገ በኋላ 2ኛ ተጠሪ ኃላፊነትን ክዶ ተከራክሯል በማለት ከክርክሩ ውጭ አድርጓል። 3ኛ ተጠሪ ከፍጥነት ወሰን በላይ በማሽከርከር በጥፋቱ በ1ኛ ተጠሪ ላይ ጉዳት በማድረሱ እና አመልካች የተሸከርካሪው ባለንብረት በመሆኑ ለጉዳቱ ኃላፊ ናቸው። የኃላፊነት መጠኑን በተመለከተ 1ኛ ተጠሪ 30% ቋሚ ጉዳት የደረሰበት ስለመሆኑ በሕክምና ተረጋግጧል። ይሕም ለወደፊት ሕይወቱ ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ የሚያሳድር ነው። 1ኛ ተጠሪ ዕድሜው 5 ዓመት በመሆኑ አሁን በጉዳቱ ሳቢያ ሊያጣው የሚችል ነገር ባይኖርም ለወደፊት የሚያጣው ጥቅም መካስ እንዳለበት በፍ/ሕ/ቁ. 2092 የተመለከተ ስለሆነ ነገር ግን የሚቋረጠውን ጥቅም በእርግጠኝት ማወቅ ስለማይቻል በርትዕ ብር 250,000.00 ካሣ፣ የሞራል ካሣ ብር 1,000.00 እና የሕክምናና የትራንስፖርት ወጪ ብር 902.00 በድምሩ ብር 251,902.00 ከወጭና ኪሣራ ጋር አመልካች እና 3ኛ ተጠሪ በአንድነትና በነጠላ ኃላፊነት ለ1ኛ ተጠሪ እንዲከፍሉ ወስኗል። የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የአመልካችን ይግባኝ ባለመቀበል ሠርዟል።

ይህ የሰበር አቤቱታ የቀረበው በዚህ ውሳኔ ነው። የአመልካች የሰበር አቤቱታ ይዘትም ክሱ የቀረበው ጉዳቱ ከደረሰ ከሁለት ዓመት በላይ ስለሆነ በፍ/ሕ/ቁ. 2143(1) በይርጋ ቀሪ ሊሆን ይገባል። አመልካች የተሸከርካሪው ባለንብረት ስለሆነ የፍ/ሕ/ቁ. 2143(2) ተፈጻሚ አይደለም። 2ኛ ተጠሪ የ3ኛ ወገን ኃላፊነት የመድን ሽፋን የሠጠ ሆኖ እያለ ከክሱ ውጭ መደረጉ ተገቢ አይደለም። ጥፋቱ የ3ኛ ተጠሪ ሆኖ እያለ የኃላፊነት መጠኑ ሳይለይ በአንድነትና በነጠላ ኃላፊ ልንባል አይገባም። የማይሰራ ልጅ፣ ጉዳቱ ሳይረጋገጥ በርትዕ ካሣ መወሰኑ ስህተት ያለበት ነው የሚል ሲሆን የሰበር አጣሪ ችሎት ጉዳዩን ተመልክቶ 2ኛ ተጠሪ ከክሱ ውጭ መደረጉ ሕጋዊነቱን ለማጣራት ተጠሪዎች መልስ እንዲያቀርቡ በማዘዙ 1ኛ ተጠሪ ያቀረቡት መልስ ክሱ በጊዜው የክልሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ላይ ቀርቦ ነበር፣ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በይግባኝ ሥልጣን የለውም በማለት በመሻሩ እንደገና ሥልጣን ላለው ፍርድ ቤት ክሱ ሲቀርብ ነው የዘገየው፤ በይርጋ ሊታገድ አይገባም። ጉዳቱ በሆስፒታል ተረጋግጦ ቀርቦ የተወሰነ ነው። ውሳኔው ሊጸና ይገባል ብለዋል። 2ኛ ተጠሪ በበኩሉ ክሱ በይርጋ ቀሪ ቢሆን እንደሚስማማ በመግለጽ በይርጋ ቀሪ ካልሆነ ግን አመልካች አደጋውን በጊዜው ያላሳወቀው በመሆኑ ከክሱ ውጭ መደረጉ ተገቢ ነው በሏል። አመልካች የመልስ መልስ በማቅረብ የሠበር አቤቱታውን አጠናክሮ ተከራክሯል። 3ኛ ተጠሪ ተጠርተው ያልቀረቡ በመሆኑ ጉዳዩ በሌሉበት ታይቷል።

የክርክሩ ሂደት በአጭሩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን እኛም የግራ ቀኙን ክርክር፣ በሠበር አጣሪ ችሎት የተያዘው ጭብጥ፣ በሥር ፍርድ ቤት ከተረጋገጡ ፍሬ ነገሮች እና ከሕጉ ጋር በማገናዘብ መዝገቡን እንደሚከተለው መርምረናል፡፡

እንደመረመርነው 1ኛ ተጠሪ ግንቦት 11 ቀን 2009 ዓ/ም በተጻፈ ያቀረቡት ክስ ታህሳስ 17 ቀን 2007 ዓ/ም ሕፃን አብርሃም ግዛቸው ከአዲስ ዘመን ወደ ርብ ግድብ እየተጓዘ እያለ ንብረትነቱ የአመልካች የሆነ ኮድ 3-47221 ቶዮታ መኪና በ3ኛ ተጠሪ እየተሽከረከረ እግሩን በመግጨት ከጉልበቱ በታች ባደረሰበት ጉዳት እግሩ ከጥቅም ውጭ ሲሆን በሕክምና 30% ጉዳት መድረሱ ተረጋግጧል፡፡ የጉዳት ካሣ ብር በድምሩ ብር 617,502.00 አመልካች እንዲከፍላቸው እንዲወስንላቸው ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡ አመልካች በበኩሉ ክሱ በፍ/ሕ/ቁ. 2143(1) መሠረት በይርጋ የታገደ ነው በማለት የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ አቅርቧል፡፡ በፍ/ሕ/ቁ. 2143(1) መሠረት ጉዳት ከደረሰ በሁለት ዓመት ጊዜ ውስጥ ካልቀረበ የካሣ ክስ በይርጋ የታገደ እንደሚሆን አስቀምጧል፡፡ 1ኛ ተጠሪ ክሱን ያቀረበው ግንቦት 11 ቀን 2009 ዓ/ም ሲሆን ጉዳቱ የደረሠው ደግሞ ታህሳስ 17 ቀን 2007 ዓ/ም ነው፡፡ ይሕም ክስ የቀረበው በሕጉ ከተመለከተው የሁለት ዓመት የይርጋ ጊዜ ካለፈ በኋላ እንደሆነ ያስገነዝባል፡፡ በፍ/ሕ/ቁ. 2143(2) ላይ ጉዳቱ በወንጀል የሚያስቀጣ ከሆነ የይርጋ ዘመኑ በወንጀል ይርጋ ጊዜው ልክ ይሆናል በሚል ተደንግጓል፡፡ የሥር ፍርድ ቤት 3ኛ ተጠሪ ከፍጥነት ወሰን በላይ በማሽከርከር በጥፋቱ በ1ኛ ተጠሪ አካል ላይ በቋሚነት ጉዳት ማድረሱን አረጋግጧል፡፡ ይሕም ድርጊቱ በወንጀል ሕግ አንቀጽ 559(2) መሠረት በወንጀል ስለሚያስቀጣ እና የወንጀሉ ይርጋ በወ/ሕ/ቁ. 217(1)(ሠ) መሠረት አምስት ዓመት ነው፡፡ 1ኛ ተጠሪ ክሱን በአምስት ዓመት ጊዜ ውስጥ አቅርበዋል፡፡ የክሱ ምክንያት ከውል ውጭ ካሣ እንዲከፈል በመሆኑ የጉዳት አድራሹ ተሽከርካሪ ባለቤት ላይ ክሱ ሲቀርብ የፍ/ሕ/ቁ. 2143(2) ለጉዳዩ ተፈጻሚ ነው፡፡ በተጨማሪም ክሱ በጊዜው የክልሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ላይ ቀርቦ በይግባኝ ሥልጣን የለውም ተብሎ በመሻሩ እንደገና ሥልጣን ላለው ፍርድ ቤት ክሱ ሲቀርብ ነው የዘገየው በሚል 1ኛ ተጠሪ ያቀረበውን ክርክር አመልካች አልካደውም፡፡ ይሕም ይርጋ ጊዜውን የሚያቋርጥ በመሆኑ የጉዳት ካሣ ክሱ በይርጋ የታገደ አይደለም መባሉ ተገቢ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

የጉዳት ካሣውን በተመለከተ ግራ ቀኙ ባላቸው ከውል ውጭ ኃላፊነት የጉዳት ካሣ ክርክር የሥር ፍርድ ቤቶች የጉዳት ካሣውን ጉዳት አድራሹን መኪና ሲያሽከረክር የነበረውን 3ኛ ተጠሪና የተሽከርካሪው ባለንብረት የሆነው አመልካችን ኃላፊ በማድረግ የ1ኛ ተጠሪ ዘለቄታዊ የአካል ጉዳቱ 30% መሆኑን ግምት ውስጥ በማስገባት ተጠሪ ለወደፊት ይኖራሉ ተብሎ በተገመተው ዕድሜ ልክ በርትዕ ካሣ እንዲከፈላቸው ወስነዋል፡፡ 3ኛ ተጠሪ ከፍጥነት ወሰን በላይ በማሽከርከር በጥፋታቸው በፍ/ሕ/ቁ. 2027(1) እና 2028 መሠረት እና አመልካች የጉዳት አድራሹ ተሽከርካሪ ባለንብረት በመሆኑ በፍ/ሕ/ቁ. 2081(1) መሠረት ለጉዳቱ ኃላፊ መሆናቸው ተገቢ ነው፡፡ ካሣ በፍ/ሕ/ቁ. 2090(1) እንደተመለከተው ከደረሰው ጉዳት ጋር ተመዛዛኝ ወይም ተመጣጣኝ መሆን እንዳለበት መርህ የተቀመጠ ሲሆን በፍ/ሕ/ቁ.

2092 አግባብ ደግሞ ካሣው የተረጋገጠ ለወደፊት የሚደርስን ጉዳትም ማካተት እንዳለበት ተመልክቷል። የአካል ጉዳትን ወደ ገንዘብ መተመን አስቸጋሪ ቢሆንም በተጎጂው ወደፊት የመስራት አቅም ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ ካለው ለወደፊት የሚደርስ ጉዳት (future damage) መወሰን እንደሚገባ ሰበር ችሎቱ በሰ/መ/ቁ. 19338 ቅጽ 5 ላይ እና በሰ/መ/ቁ. 35034 ቅፅ 9 ላይ አስገዳጅ ትርጉም ሰጥቶበታል። ለወደፊት የሚደርስ ጉዳት ለመወሰን የደረሰው የአካል ጉዳት ዘላቂና የመስራት አቅም ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ ያለው ስለመሆኑ የሚረጋገጠው በዋነኛነት በህክምና ማስረጃ ነው። በተያዘው ጉዳይ 1ኛ ተጠሪ ከጉልበቱ በታች እግሩ ላይ ጉዳት የደረሰበት ሲሆን የአካል ጉዳቱም በህክምና 30% ስለመሆኑ በሥር ፍርድ ቤት የተረጋገጠ ፍሬ ነገር ነው። 1ኛ ተጠሪ ጉዳቱ ሲደርስበት ሥራ መስራት ያልጀመረ ሕጻን በመሆኑ አሁን ተቀጥሮ የሚሰራና ገቢ የሚያገኝ አይሆንም። በሌላ በኩል ሥራ ለመስራት በሚደርስበት ዕድሜ ላይ የደረሰበት ቋሚ የአካል ጉዳት በአጠቃላይ የመሥራት ኃይል በመቀነስ ለወደፊት የሚደርስ ጉዳት (future damage) እንደሚያስከትል የሚታወቅ ሲሆን ትክክለኛ ጉዳቱ ግን ለማወቅና ለመለየት ስለሚያስቸግር በፍ/ሕ/ቁ. 2102 እንደተመለከተው ጉዳት መድረሱ ተረጋግጦ ነገር ግን የጉዳት መጠኑን ማወቅ ካልተቻለ ካሣውን በርትዕ መወሰን ይችላል። በመሆኑም የሥር ፍርድ ቤቶች ካሣውን በርትዕ በመወሰን ለ1ኛ ተጠሪ ብር 250,000.00 ካሣ በርትዕ እንዲከፈል መወሰናቸው ላይ የተፈጸመ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የለም ብለናል።

አመልካች በፍብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 43 መሠረት የጉዳት ካሣ ኃላፊነቱን እንዲጋራው 2ኛ ተጠሪ የኢትዮጵያ መድን ድርጅት ጣልቃ ገብቶ እንዲከራከር ጠይቋል። 2ኛ ተጠሪ ቀርቦ አደጋውን አመልካች ያላሳወቀኝ በመሆኑ ኃላፊነት የለብኝም በማለት የተከራከረ ሲሆን ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው ፍርድ ቤት ጉዳዩን መርምሮ 2ኛ ተጠሪ ኃላፊነትን ክዶ ተከራክሯል በማለት ከክርክሩ ውጭ አድርጓል። በፍብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 43 መሠረት የተከሳሽን ኃላፊነት ሊጋሩ የሚችሉ ወገኖች ወደክርክሩ እንዲገቡ የሚደረገው ውጤታማ፣ ወጭና ጊዜ ቆጣቢ በሆነ አግባብ ክርክሩን አጠቃሎ ለመምራት እንዲያስችል ሲሆን ከውል ውጭ ኃላፊነት ተከትሎ ከሚመጣ ክርክር ጋር በተያያዘ ተጎጂው ካሣውን የሚጠይቅበት እድል የሚያሰፋ ነው። በተያዘው ጉዳይ ክርክሩ በዚህ ሰበር ችሎት ደረጃ ከደረሰ በኋላ መመለስ የተጎጂውን ካሣውን ሳያገኝ እንዲቆይ የሚያደርግ ሲሆን ከአመልካች መብት አኳያም ካሣውን በራሱ ከከፈለ ከ2ኛ ተጠሪ ጋር በገባው የሦስተኛ ወገን መድን ውሉ መሠረት 1ኛ ተጠሪ የከፈለውን ካሣና 2ኛ ተጠሪ ባለበት ኃላፊነት ልክ የውል ግዴታ መሠረት በማድረግ ለመጠየቅ ሕጋዊ መፍትሔ አለው። በመሆኑም የሥር ፍርድ ቤቶች ለ1ኛ ተጠሪ ሊከፈል የሚገባውን የጉዳት ካሣ አመልካች ከ3ኛ ተጠሪ ጋር እንዲከፍል በመወሰናቸው በዚህ ሰበር ችሎት ደረጃ የሚመረመር መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት አላገኘንበትም።

ውሳኔ

1. የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 194240 ጥቅምት 17 ቀን 2013 ዓ/ም እና የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 45936 ሐምሌ 20 ቀን 2012 ዓ/ም የሠጡት ውሳኔ በፍብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348(1) መሰረት ፀንቷል፡፡

2. በዚህ ችሎት ለወጣ ወጭና ኪሣራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

ትዕዛዝ

- የውሳኔው ግልባጭ ለሥር ፍርድ ቤቶች ይተላለፍ፡፡
- አፈጻጸሙ ላይ የተሠጠው እግድ ተነስቷል፡፡ ይጻፍ
- መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

ማ/አ የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

የወንጀል ሥነ ሥርዓት ህግ

የሰ/መ/ቁ/ 212950

ህዳር 30/2014 ዓ.ም

ዳኞች፡- ሰለሞን አረዳ

እትመት አሰፋ

ኑረዲን ከድር

መላኩ ካሳዬ

እስቲበል አንዱዓለም

አመልካች፡- አቶ ቶቼሮ ቶማ

ተጠሪ፡- የደቡብ ክልል ጠቅላይ ዐቃቤ ህግ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍርድ

ጉዳዩ የውንብድና ወንጀልን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩም የተጀመረው የአሁን ተጠሪ በአመልካች ላይ የወንጀል ህግ አንቀፅ 670 ድንጋጌን ጠቅሶ በወላይታ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ባቀረበው የወንጀል ክስ ነው፡፡ የክሱም ይዘት አመልካች የተጠቀሰውን የወንጀል ህግ ድንጋጌን በመተላለፍ የማይገባውን ብልፅግና ለራሱ አልያም ለሌላ ሰው ለማስገኘት አስቦ በክሱ ዝርዝር ውስጥ በተገለፀው ቀን፣ ቦታ እና ሰዓት የግል ተበዳይ ወደሆኑት ወ/ሮ አበበች ባደቦ የንግድ ቤት በመሄድ የተበዳይን ጉረሮ አንቆ በመያዝ አንገታቸው ላይ የነበረ የዋጋ ግምቱ ብር 50,000(ሃምሳ ሽህ) የሚያወጣ 20 ግራም የወርቅ ሀብል፣ እንዲሁም ባንኮኒ ውስጥ የነበረውን ብር 20,000(ሃያ ሺህ) ወስዶ በጓሮ በኩል ያመለጠ በመሆኑ የውንብድና ወንጀል ፈፅሟል የሚል ነው፡፡

አመልካች ለዚሁ ክስ በሰጠው መልስ ድርጊቱን እና ጥፋተኝነቱን ክዶ በመከራከሩ የዐቃቤ ህግ ምስክሮች ቀርበው እንዲሰሙ ከተደረገ በኋላ እንደክሱ አቀራረብ አስረድተዋል በሚል አመልካች ክሱን እንዲከላከል ታዟል፡፡ አመካችም አራት መከላከያ ምስክሮችን አሰምቷል፡፡ የመከላከያ ምስክሮቹም አመልካች እና የግል ተበዳይ ባል አና ሚስት የነበሩ መሆኑን፣ ክስ የቀረበበት ድርጊት ተፈፀመ ከተባለ በኋላ በዚያው ጉዳይ ሁለቱን ለማሸማገል ሽምግልና ተቀምጠው የነበረ መሆኑን፣ በዚሁ ጊዜ የግል ተበዳይን ስለድርጊቱ ሲጠይቋቸው አመልካች ንብረት ዘርፎኛል በሚል የከሰሷቸው ዘወትር ሰክሮ እየሄደ ስለሚረብሻቸው እንጂ የተወሰደባቸው ንብረት እንደሌላ የነገሯቸው መሆኑን ተናግረዋል፡፡ ጉዳዩን የያዘው ፍርድ ቤትም ለጉዳዩ አወሳሰን ይረዳኛል በማለት የሽማግሌዎቹ ሰብሳቢ የነበሩትን ፓስተር ታደሰ ታንቱ የተባሉትን ግለሰብ አስቀርቦ

ሰምቷል፡፡ ተጨማሪ ምስክሩም አመልካች እና የግል ተበዳይ ባልና ሚስት መሆኑቻውን፣ ክስ የቀረበበት ጉዳይ ተፈፀመ ከተባለ በኋላ የሁለቱን ጉዳይ በሽምግልና የተመለከቱ መሆኑን፣ በሽምግልናው ላይም የግል ተበዳይ በእርግጥም ዝርፊያ ተፈፅሞባቸው እንደሆን በሚል የጠየቋቸው መሆኑን፣ ተበዳይም አመልካች ዘወትር ሰክሮ ንግድ ቦታቸው እየሄደ ስለሚረብሻቸው ለመከላከል በሚል የከሰሷቸው እንጂ የተፈፀመባቸው ውንብድና እንደሌለ የነገሯቸው መሆኑን ገልፀዋል፡፡

ከዚህ በኋላ ፍርድ ቤቱ የግራ ቀኙ ክርክር መርምሮ እና የቀረቡትን ማስረጃዎች መዝኖ የዐቃቤ ህግ ክስ እና ማስረጃ ተስተባብሏል በሚል አመልካችን ከቀረበባቸው ክስ በነፃ አሰናብቷል፡፡ ይህንኑ ውሳኔ በይግባኝ የተመለከተው የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አመልካች በመከላከያ ማስረጃው ያስመሰከረውን ፍሬ ነገር አስምልክቶ በዋናው ክርክር ወቅት በመስቀልኛ ጥያቄ ያስተባበለው ነገር የለም፣ ከተበዳይ ጋር ተደርጓል የተባለውን የእርቅ ስምምነት አስምልክቶም በጽሑፍ የቀረበ የእርቅ ስምምነት የለም፣ የድርጊቱ አፈፃፀምም አመልካች ከግል ተበዳይ ጋር የነበረው ጋብቻ ከተቋረጠ በኋላ ጉልበቱን በመጠቀም ለማስቀጠል ፍላጎት ያለው መሆኑን የሚያሳይ በመሆኑ ድርጊቱ ከውንብድና ወንጀል ይልቅ በማስገደድ መጠቀም ወንጀልን የሚያቋቁም ነው በማለት ክስ የቀረበበትን አንቀፅ ወደ አንቀፅ 713 በመቀየር አመልካችን ጥፋተኛ ብሎት በ1 ዓመት ከ2 ወር ቀላል እስራት እና በብር 2,000(ሁለት ሺህ) የገንዘብ ቅጣት እንዲቀጣ ወስኗል፡፡ አመልካች ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ያቀረበው የሰበር አቤቱታ ተቀባይነት አላገኘም፡፡

የአሁን የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ በመቃወም ነው፡፡ አመልካች ነሓሴ 14/2013 ዓ.ም በተፃፈ የሰበር አቤቱታ በክልሉ የበላይ ፍርድ ቤቶች ውሳኔ ላይ ተፈፅሟል ያለውን መሰረታዊ የህግ ስህተት ጠቅሶ በዚህ ችሎት እንዲታረምለት ጠይቋል፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ ያስቀርባል በመባሉ ግራ ቀኙ በፅሁፍ እንዲከራከሩ ተደርጓል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ እና የክርክሩ ይዘት በአጭሩ ከላይ የተመለከተውን ሲመስል ችሎቱም አመልካች የዐቃቤ ህግ ክስ እና ማስረጃን አላስተባበለም በሚል በወንጀል ህግ አንቀፅ 713 ስር ጥፋተኛ ተብሎ የመቀጣቱን አግባብነት በወንጀል ጉዳት ተከሳሽ የሆነ ሰው በመከላከያ ማስረጃው ማስረዳት ከሚጠበቅበት የማስረዳት ደረጃ አኳያ መርምሯል፡፡

በወንጀል ጉዳይ ዐቃቤ ህግ ያቀረበውን ክስ አስረድቷል የሚባለው ባቀረባቸው ማስረጃዎች ክሱን በቂ እና አሳማኝ በሆነ መልኩ ሲያስረዳ እንደሆነ የወንጀል ህግ ሥነ ሥርዓት ቁጥር 141 ይደነግጋል፡፡ በወንጀል ክሱ ተከሳሽ የሆነው ሰውም የቀረበበትን ክስ አስምልክቶ ማስተባበያ ማስረጃ እንዲያቀርብ የሚታዘዘው ይኸው ሲረጋገጥ ስለመሆኑ ከወንጀል ህግ ሥነ ሥርዓት ቁጥር 141 እና 142 ድንጋጌዎች መገንዘብ ይቻላል፡፡ ከዚህ ጋር ተያይዞ አንድ ሊነሳ እና መልስ

ሊሰጠው የሚገባው ነጥብ “በወንጀል የተከሰሰ ሰው በመከላከያ ማስረጃው ማስረዳት/ማረጋገጥ/ የሚጠበቅበት የማስረዳት ደረጃ ምን ያክል ነው?” የሚለው ነው፡፡ በሌላ አገላለፅ በወንጀል ተከስሶ ክሱን እንድከላከል ከተነገረው ተከሳሽ የሚጠበቀው ዐቃቤ ህግ ባስረዳው ልክ በመከላከያ ማስረጃው በቂ እና አሳማኝ በሆነ መልኩ መረጋገጥ ነው ወይስ የዐቃቤ ህግ ማስረጃ ላይ ጥርጣሬ እንዲፈጠር ማድረግ ነው እንደማለት ነው፡፡

እንግዲህ ከላይ እንደተመለከተው በወንጀል የተከሰሰ ሰው መከላከያ ማስረጃ እንዲያቀርብ የሚታዘዘው በዐቃቤ ህግ ማስረጃ የተረጋገጠበትን ክስ እና ማስረጃን እንዲያስተባብል ነው፡፡ ማስተባበል ማለት ደግሞ የተከሳሹን የወንጀል ድርጊት እና ጥፋተኝነት አረጋግጠዋል በተባሉት ማስረጃዎች ላይ በአንድም ይሁን በሌላ መንገድ ጥርጣሬ እንዲፈጠር በማድረግ በማስረጃዎቹ የማስረዳት አቅም ላይ መተማመን እንዳይኖር ማድረግ ስለመሆኑ ከማስረጃ ህግ መሰረተ ሀሳብ እና በዚሁ ዙሪያ ከተደረጉ የምርምር ፅሁፎች የምንረዳው ጉዳይ ነው፡፡ ይህ ደግሞ ከተከሰሰው ሰው የሚጠበቀው በመከላከያ ማስረጃው በቂ እና አሳማኝ በሆነ መልኩ ማስረዳት ሳይሆን የዐቃቤ ህግ ማስረጃን አስመልክቶ ቀድሞ በተያዘው አቋም ላይ ጥርጣሬን መፍጠር ብቻ መሆኑን ያስገነዝባል፡፡

ወደተያዘው ጉዳይ ስንመለስ ዐቃቤ ህግ ክሱን ለማረጋገጥ ያቀረበው የሰው ምስክር ብቻ ነው፡፡ ቀርበው የተሰሙት የዐቃቤ ህግ ምስክሮችም እንደ ክሱ አቀራረብ አመልካች በግል ተበዳይ ላይ የውንብድና ወንጀል ሲፈጽም መመልከታቸውን ተናገረዋል፡፡ ሆኖም አመልካች ከተከሰሰበት የወንጅል ድርጊት ጋር በተያያዘ በአመልካች እና በየግል ተበዳይ መካከል ሽምግልና ተቀምጠው የነበሩት የአመልካች መከላከያ ምስክሮች እና በፍርድ ቤት ትዕዛዝ በማጣሪያ ምስክርነት የተሰሙት ሽማግሌዎቹ ሰብሳቢ የግል ተበዳይዋ በሽምግልናው ላይ አመልካችን በወንጀል የከሰሷችው ዘወትር ሰክሮ በመሄድ ስለሚረብሻቸው እንጂ የፈፀመባቸው የወንብድና ድርጊት እንደሌለ የነገሯቸው ስለመሆኑ ተናግረዋል፡፡ በእንዚህ አሸማጋይ ሽማግሌዎች ይህ ሁኔታ መረጋገጡ ቀድሞ በተሰሙት የዐቃቤ ህግ ምስክሮች የምስክርነት ቃል ላይ ጥርጣሬ እንዲኖር የሚያደርግ ነው፡፡

ጉዳዩ ይህ ሆኖ እያለ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በአመልካች እና የግል ተበዳይ መካከል ተደርጓል የተባለው የእርቅ ስምምነት በፅሁፍ አልቀረበም፣ እንዲሁም አመልካች በመከላከያ ማስረጃው ያረጋገጠውን ፍሬ ነገር በመስቀልኛ ጥያቄ አልጠየቀም በሚል ምክንያት የአመልካችን መከላከያ ማስረጃ ውድቅ ማድረጉ የቀረበው ጉዳዩ የወንጀል ክርክር መሆኑን እና በወንጀል ጉዳይ ተከሳሽ የሚጠበቅበትን የማስረዳት ደረጃ ያላገናዘበ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በመሆኑም ተከታዩ ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

ውሳኔ

1. የደቡብ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦች እና ህዝቦች ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁ/34748 ላይ ግንቦት 04/2013 ዓ.ም የተሰጠው ውሳኔ እና ይህንኑ ውሳኔን በማፅናት የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ/36060 ላይ ነሐሴ 04/2013 የሰጠው ትዕዛዝ በወንጀል ህግ ሥነ ሥርዓት ቁር 195(2(ለ(2))) መሰረት ተሽሯል፡፡

2. የወላይታ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ/46898 ላይ ታህሳስ 19/2013 ዓ.ም በዋለው ችሎት አመልካችን ከተከሰሰበት ወንጀል ነፃ በመልቀቅ የሰጠው ውሳኔ በወንጀል ህግ ሥነ ሥርዓት ቁጥር 195(2(ለ(2))) ፀንቷል፡፡

ትዕዛዝ

1. አመልካች በዚህ መዝገብ ላይ ከተከሰሰበት ወንጀል በነፃ የተሰናበተ በመሆኑ በሌላ ወንጀል የማይፈለግ መሆኑን አረጋግጦ በአስቸኳይ ከእስር እንዲለቀው ለሚገኝበት ማረሚያ ቤት ይፃፍ፡፡
2. መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ማ/አ

የሠ/መ/ቁጥር 252231

ጥቅምት 12 ቀን 2016 ዓ/ም

ዳኞች፡- ብርሃኑ አመነው

በዕዉቀት በላይ

ቀናዓ ቂጣታ

ብርሃኑ መንግሥቱ

ማርታ ተካ

አመልካች - አቶ አየለ ዳመና

ተጠሪ - የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ

መዝገቡ ተመርምሮ ከዚህ የሚከተለዉ የፍርድ ዉሳኔ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የአመልካች የዋስትና መብት ይከበርልኝ ጥያቄ ዉድቅ ተደርጎ በመወሰኑ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል በሚል ለማሳረም የቀረበ የሰበር አቤቱታ የሚመለከት ነዉ፡፡ አመልካች በተጠረጠሩበት ወንጀል ምርመራ እየተደረገ ቆይቶ በኦሮሚያ ክልል አርሲ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ዐቃቤ ሕግ በአመልካች ላይ በ15 ቀናት ዉስጥ ክስ እንዲመሰርት ጊዜ ሰጥቶ መዝገቡን መዝጋቱን፤በዚህ መልኩ በተሰጠዉ ጊዜ ዉስጥ በአመልካች ላይ የወንጀል ክስ አለመመስረቱን ምክንያት በማድረግ አመልካች ለፍርድ ቤቱ የዋስትና መብታቸዉ እንዲጠበቅላቸዉ ጠይቀዋል፡፡ፍርድ ቤቱም ዐቃቤ ሕግ መልስ እንዲሰጥ አዝዞ በሰጠዉ መልስ አመልካች በፈጸሙት የእምነት ማጉደል እና ከባድ ማታለል ወንጀል የተጠረጠሩና ድርጊቱም በተለያዩ 12 ሰዎች ላይ የተፈጸመ በመሆኑ፤በማታለል ብር 924,814 በባንክ ሂሳባቸዉ ማስገባታቸዉ የተደረሰበት በመሆኑ፤የኦዲት ሥራዉ ስላልተጠናቀቀ በተባለዉ ጊዜ ዉስጥ ክስ መመስረት አንችልም፡፡ስለሆነም አመልካች ከዚህ ቀደም ያቀረቡት የዋስትና ጥያቄ ዉድቅ ስለተደረገ በድጋሚ ያቀረቡት የዋስትና ጥያቄ ዉድቅ ይደረገልኝ በማለት ተከራክሯል፡፡

ፍርድ ቤቱም በመ/ቁጥር 121631 ላይ በቀን 10/11/2015ዓ/ም በሰጠዉ ትዕዛዝ አመልካች እምነት የማጉደል እና የማታለል ወንጀል ፈጽመዋል ተብሎ ከመጠርጠራቸዉ ጋር በተያያዘ ከዚህ በፊት የዋስትና መብት ጥያቄ አቅርቦ በቀን 23/09/2015 ዓ/ም ዉድቅ ከተደረገ በኋላ አሁን በድጋሚ የዋስትና መብት ጥያቄ ማንሳታቸዉ ተቀባይነት የለዉም፡፡ጉዳዩ ላይ አስቀድሞ የመጨረሻ ዉሳኔ ስለተሰጠበት በይግባኝ ካልተስተካከለ በስተቀር በድጋሚ ሊጠይቁ አይችሉም፡፡ በሌላ በኩል በአመልካች ላይ እየተደረገ ያለዉን ምርመራ በተመለከተ የኦዲት ሂደቱ ያልተጠናቀቀ መሆኑንና በሂደት ላይ መሆኑን በመግለጽ

ዐቃቤ ሕግ የቀረበዉ በቂ ምክንያት ስለሆነ ዐቃቤ ሕግ ክሱን በአጭር ጊዜ ዉስጥ እንዲመሰረት በማለት የአመልካችን የዋስትና መብት ጥያቄ ዉድቅ በማድረግ ወሰነ፡፡

አመልካች በዉሳኔዉ ቅር በመሰኘት በየደረጃዉ ይግባኝ እና የሰበር አቤቱታ ለኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ቢያቀርቡም ፍርድ ቤቱ አመልካች የተጠረጠሩበት ወንጀል በአዋጅ ቁጥር 881/2007 አንቀጽ 32/2 ስር የተደነገገዉን ተላልፈዋል በሚል በመሆኑ በአዋጅ ቁጥር 882/2007 አንቀጽ 3/1 መሰረት ለአመልካች የዋስትና መብት መከልከሉ በአግባቡ ነዉ በማለት ሠርዞባቸዋል፡፡

አመልካች በቀን 10/12/2015ዓ/ም የተጻፈ የሰበር አቤቱታ ያቀረቡት ከላይ በተመለከተዉ መሰረት በተሰጠ ዉሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል በሚል ሲሆን የአቤቱታቸዉ አጭር ይዘት፡- ዐቃቤ ሕግ በአመልካች ላይ በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 109 መሰረት በ15 ቀን ጊዜ ዉስጥ ክስ እንዲመሰርት ቢታዘዝም ክስ ባልመሰረተበት በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 19/6 ጥበቃ የተደረገልኝን የዋስትና መብት ተከልክያለሁ፡፡ የዋስትና መብት ጥያቄ አንድ ጊዜ ተጠይቆ በሌላ ጊዜ የተለየ ሁኔታ በተፈጠረ ጊዜ የዋስትና መብት መጠየቅ እንዳይቻል የሚከለክል ሕግ በሌለበት አመልካች አስቀድሞ የዋስትና ጥያቄ አቅርበዉ ዉድቅ ተደርጓል በሚል ምክንያት ዐቃቤ ሕግ በ15 ቀን ዉስጥ የወንጀል ክስ እንዲመሰርት በተሰጠዉ ጊዜ ክስ አለመመስረቱ ተረጋግጦ እያለ የስር ከፍተኛ ፍርድ ቤት የአመልካችን የዋስትና ጥያቄ ዉድቅ ማድረጉ ስህተት ነዉ፡፡በምርመራ መዝገቡ በቀረበዉ ማስረጃ መሰረት አመልካች ሊከሰስ የሚችለዉ በወንጀል ሕግ ቁጥር 676 እና 692 መሰረት ሆኖ እያለ በአዋጅ ቁጥር 881/2007 አንቀጽ 32 መሰረት ሊከሰስ ይችላል በሚል የዋስትና መብት ጥያቄዬ ዉድቅ መደረጉ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ነዉ፡፡አንድን ሰዉ በወንጀል ተጠርጥሯል በሚል ምክንያት ብቻ በአስር ላይ ማቆየት በራሱ የዜጎችን ሕገ መንግሥታዊ መብት የሚጥስ ነዉ ተብሎ የስር ፍርድ ቤቶች የሰጡት ዉሳኔ ተሽሮ የዋስትና መብቴ ይጠበቅልኝ በማለት ጠይቀዋል፡፡

የሰበር አጣሪ ችሎት አቤቱታዉን መርምሮ አመልካች በተጠረጠሩበት ወንጀል ክስ ሳይቀርብባቸዉ የሚከሰሱት ዋስትና ሊያስከለክል በሚችል ድንጋጌ ነዉ በሚል ምክንያት ብቻ የዋስ መብታቸዉ የተከለከለበትን አግባብ ተጠሪ ባለበት እንዲመረመር ትዕዛዝ በመስጠቱ ተጠሪ በቀን 07/01/2016ዓ/ም የተጻፈ መልስ በማቅረብ ተከራክሯል፡፡ የመልሱም አጭር ይዘት፡- አመልካች የአቢሲኒያ ባንክ ቦሩ ጃዊ ቅርንጫፍ ምክትል ሥራ አስኪያጅ ሆነዉ ሲሰሩ ከተለያዩ 13 የሚሆኑ የባንኩ ደንበኞች ላይ ብር 1,024,817.00 ስብስበዉ ወደ ደንበኞች ሂሳብ ቁጥር ሳያስገቡ ለራሳቸዉ ጥቅም በማዋላቸዉ በከባድ የእምነት ማጉደልና የማታለል የሙስና ወንጀል ተጠርጥረዋል፡፡ይህ ጉዳይ ከባንክ ጋር የተያያዘ ከመሆኑ አንጻር የስር ከፍተኛ ፍርድ ቤት ጉዳዩን ለማየት ሥልጣን የለዉም፡፡ክስ መመስረቻ ጊዜ እንዲሰጠን ሳንጠይቅ የስር ፍርድ ቤት በ15 ቀን ዉስጥ ክስ እንድንመሰርት ያዘዘዉ ሥልጣን ሳይኖረዉ ነዉ፡፡ይህ ጊዜ የተሰጠዉ የምርመራ መዝገቡ ለተጠሪ ከመላኩ በፊት ነዉ፡፡ጉዳዩ ተጨማሪ የማጣራት ሥራ

የሚያስፈልገዉ ነዉ።አመልካች አቢሲኒያ ባንክ ከመግባታቸዉ በፊት የዘመን ባንክ ሠራተኛ የነበሩ ቢሆንም ከዚህ ባንክ የተሰናበቱት በዲሲፕሊን ግድፈት ቢሆንም ከዚህ ባንክ ባልተጻፈ ማስረጃ በአቢሲኒያ ባንክ ስለተቀጠሩ በተጨማሪነት በሀሰተኛ ሰነድ በመገልገል የሙስና ወንጀል ለመክሰስ እየተጣራ ይገኛል። አመልካች በገቢ ደረሰኝ ላይ ሲያትሙ የነበረዉ ማህተም በባንኩ ለማን የተሰጠ እንደሆነ ከባንኩ ተጠይቆ ማስረጃ ተገኝቷል።በደረሰኞቹ ላይ ያለዉ ፊርማ በፎረንሲክ እንዲመረመር ተደርጎ ዉጤቱ እየተጠበቀ ይገኛል። ስለሆነም አመልካች በከባድ ማታለል፣በከባድ እምነት ማጉደልና ሀሰተኛ ሰነድን በማዘጋጀትና በመገልገል ተደራራቢ ወንጀሎች የተጠረጠሩ በመሆኑ የጉዳዩ ክብደት ከግምት ገብቶ የአመልካች የዋስትና ጥያቄ ዉድቅ በመደረጉ የተፈጸመ ስህተት የለም ተብሎ የስር ፍርድ ቤቶች ዉሳኔ ይጽናልኝ በማለት ተከራክሯል። አመልካችም የመልስ መልሳቸዉን በማቅረብ ተከራክረዋል።

ከዚህ በላይ አጠር ባለ መልኩ የተገለጸዉ የግራ ቀኙን ክርክርና በስር ፍርድ ቤቶች የተሰጡ ዉሳኔዎች ይዘት የሚመለከት ሲሆን እኛም ሰበር አጣሪ ችሎት የያዘዉን ጭብጥ ከግምት በማስገባት አመልካች የዋስትና መብት እንዲጠበቅላቸዉ ያቀረቡት ጥያቄ ዉድቅ ተደርጎ በመወሰኑ በዚህ ችሎት ደረጃ ሊታረም የሚችል መሰረታዊ የሕግ ስህተት መፈጸም አለመፈጸሙን አግባብነት ካለዉ ሕግ ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለዉ መርምረናል።

እንደመረመርነዉም አመልካች የዋስትና መብት ጥያቄ ያቀረቡት ስር ፍርድ ቤት ምርመራ ተጠናቋል በሚል ዐቃቤ ሕግ ክስ እንዲመሰርት በተሰጠዉ 15 ቀን ዉስጥ ክስ እንዳልመሰረተባቸዉ፣ በተጠረጠሩበት ወንጀል ክስ ሊቀርብባቸዉ የሚችለዉ በወንጀል ሕግ አንቀጽ 676 እና 692 መሰረት ስለሆነ የተጠረጠሩበት ወንጀል የዋስትና መብት የሚያስከለክል እንዳልሆነ እና ክስ ሳይመሰረትባቸዉ ከሕግ አግባብ ዉጭ በእስር ላይ እንደሚገኙ በመግለጽ ነዉ።በዚህ መልኩ ያቀረቡትን የዋስትና መብት ይጠበቅልኝ ጥያቄ የስር ፍርድ ቤቶች ዉድቅ በማድረጋቸዉ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል በማለት ተከራክረዋል። ተጠሪ ደግሞ አመልካች በእስር ላይ የሚገኙት በፌዴራል መንግሥት በተመዘገበዉ ባንክ (ሕዝባዊ ድርጅት) ላይ ከባድ የማታለል፣ ከባድ የእምነት ማጉደል እና ሀሰተኛ ሰነድ የማዘጋጀትና የመገልገል ተደራራቢ ወንጀሎችን ፈጽመዋል በሚል በመጠርጠራቸዉ እንደሆነ፣ ምርመራዉ ሳይጠናቀቅና የምርመራ መዝገብ ለዐቃቤ ሕግ ሳይተላለፍ ክስ መመስረቻ ተብሎ 15 ቀን መሰጠቱ ስህተት እንደሆነ፣ ይህንን ትእዛዝ የሰጠዉ ፍርድ ቤት ሥልጣን እንደሌለዉና ክስ መመስረቻ ጊዜ እንዲሰጠዉም እንዳልተጠየቀ በመግለጽ በአመልካች ላይ ተደራራቢ የወንጀል ክስ ሊቀርብባቸዉ የሚችለዉ የሙስና ወንጀሎችን ለመደንገግ በወጣዉ አዋጅ መሰረት በመሆኑ የዋስትና ጥያቄያቸዉ ዉድቅ መደረጉ በአግባቡ ነዉ ሲል ተከራክሯል።

በዚህ መልኩ ግራ ቀኙ ካሰሙት ክርክር እና ከስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ ግልባጭ እንደተረዳነዉ የስር የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ጉዳዩን ለመዳኘት ሥልጣን አለዉ ወይስ የለዉም የሚለዉን ቀጥለን የምንመለከተዉ ሆኖ ፍርድ ቤቱ በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 109/1 መሰረት ዐቃቤ ሕግ በ15 ቀናት ዉስጥ በአመልካች ላይ ክስ እንዲመሰርት የሰጠዉ ጊዜ አመልካች የዋስትና ጥያቄ ከማቅረባቸዉ በፊት እንደተጠናቀቀ የግራ ቀኙ ክርክር ያሳያል፡፡ የስር ከፍተኛ ፍርድ ቤት አስቀድሞ ለምርመራ ተጨማሪ ጊዜ ቀጠሮ መስጠት እንደማይገባ አምኖበት ተጠሪ በአመልካች ላይ ክስ እንዲመሰርት የ15 ቀናት ጊዜ ከተሰጠ በኋላ እና ይህ ጊዜ ካለቀ በኋላ አመልካች በቀን 06/11/2015ዓ/ም ለሁለተኛ ጊዜ የዋስትና ጥያቄ ማቅረብ አይችሉም በማለት የአመልካችን የዋስትና ጥያቄ ዉድቅ ሲያደርግ የወንጀል ምርመራ አለመጠናቀቁን መረዳቱን ገልጾ ተጠሪ *በአጭር ጊዜ ዉስጥ* በአመልካች ላይ ክስ እንዲመሰርት አዝዞ መዝገቡን መዝጋቱን የትዕዛዙ ይዘት ያሳያል፡፡በዚህ መልኩ በቀን 10/11/2015ዓ/ም ትዕዛዝ ተሰጥቶ የጊዜ ቀጠሮ መዝገብ ከተዘጋ በኋላ በዐቃቤ ሕግ መልስ ላይ እንደተመለከተዉ አመልካች ላይ እስካሁን ወይም ቢያንስ ዐቃቤ ሕግ ለዚህ ችሎት መልሱን እስካቀረበበት ቀን 07/01/2016ዓ/ም ድረስ የወንጀል ክስ አለመመስረቱን ተገንዝበናል፡፡

በኢፌዲሪ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 17/2 ስር ማንኛዉም ሰዉ በሕግ ከተደነገገዉ ሥርዓት ዉጭ ሊያዝ፣ክስ ሳይቀርብበት ወይም ሳይፈረድበት ሊታሰር እንደማይችል በመደንገግ ለነጻነት መብት ጥበቃ ተደርጓል፡፡ይህ መብት የሀገራችን የሕግ አካል በሆነዉ በተባበሩት መንግሥታት የሲቪልና የፖለቲካ መብቶች ቃል ኪዳን አንቀጽ 9/1 ላይ በግልጽ እዉቅና የተሰጠዉ መብት ነዉ፡፡በኢፌዲሪ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 19/6 ስር የተያዙ ሰዎች በሕግ በተደነገጉ ልዩ ሁኔታዎች ፍርድ ቤት የዋስትና መብት ጥያቄዎችን ላይቀበል የሚችልበት ወይም በገደብ መብታቸዉን የሚያስጠብቅበት ሁኔታ ሊኖር የሚችል መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ በመርህ ደረጃ በዋስ የመፈታት መብት እንዳላቸዉ ተደንግጓል፡፡

በተያዘዉ ጉዳይ በአመልካች ከባድ አታላይነትና ከባድ የእምነት የማጉደል ወንጀል ተፈጽሞበታል የተባለዉ አቢሲኒያ ባንክ አ.ማ በመሆኑ የሙስና ወንጀሎችን ለመደንገግ በወጣዉ አዋጅ ቁጥር 881/2007 አንቀጽ 2/4 ትርጓሜ መሰረት ወንጀሉ የተፈጸመዉ ሕዝባዊ ድርጅት ላይ ነዉ፡፡አመልካች የዚህ ባንክ ቅርንጫፍ ምክትል ሥራ አስኪያጅ እንደነበሩ ከተገለጸዉ ጋር ተደምሮ ሲታይ ዐቃቤ ሕግ በአመልካች ላይ የወንጀል ክስ የሚመሰርት ከሆነ አመልካች በአዋጅ ቁጥር 881/2007 ስር የተደነገገዉን ወንጀል ፈጽመዋል በሚል ሊሆን እንደሚችል ይገመታል፡፡ በተሻሻለዉ የፀረ ሙስና የሥነ ሥርዓትና የማስረጃ ሕግ አዋጅ ቁጥር 434/1997 አንቀጽ 7(1 እና 4) ስር እንደተመለከተዉ ከሙስና ወንጀል ጋር በተያያዘ የሚነሱ የመያዝ፣ የብርበራ፣የቀነ ቀጠሮ፣በማረፊያ ቤት የማቆየት፣የዋስትና፣የዕግድ እንዲሁም ከምርመራ ጋር የተያያዙ ሌሎች ተመሳሳይ ጉዳዮች የሚታዩት የሙስና ወንጀሎችን ክስ ለማየት ሥልጣን በተሰጠዉ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ነዉ፡፡እንዲሁም በኢፌዲሪ ሕገ መንግሥት አንቀጽ

80/2 ስር እንደተመለከተዉ በአዋጅ ቁጥር 322/1995 መሰረት የዉክልና ሥልጣናቸዉ ያልተነሳባቸዉ የክልሎች ጠቅላይ ፍርድ ቤቶች ይህ ሥልጣን ይኖራቸዋል፡፡

ከላይ በተመለከተዉ መሰረት በአዋጅ ቁጥር 434/1997 አንቀጽ 7/4 ስር የተደነገገዉ ቢኖርም ይህንን አዋጅ እንደገና ለማሻሻል በወጣዉ አዋጅ ቁጥር 882/2007 አንቀጽ 7/5 ስር እንደተደነገገዉ በአዋጁ የመያዣ፣ የብርበራ፣ የቀነ ቀጠሮ፣...የዋስትና መብት ጥያቄ የሚመለከቱ ሥነ ሥርዓታዊ ጉዳዮች የሙስና ወንጀሉን የማየት ሥልጣን ባለዉ ፍርድ ቤት እንዲታዩ መደረጉ የተከሳሹን መብት የሚያጣብብ ወይም ማስረጃ እንዲጠፋ ምክንያት የሚሆን ወይም ተገቢ ላልሆነ ወጪ የሚዳርግ መሆኑን አግባብ ያለዉ የሙስና ወንጀልን ለመመርመር እና/ወይም ለመክሰስ ሥልጣን የተሰጠዉ አካል ካመነበት እንደ ሁኔታዉ በአቅራቢያዉ በሚገኝ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት እንዲታይ ሊወስን ይችላል፡፡በያዝነዉ ጉዳይ በአመልካች ላይ የወንጀል ምርመራ ሲያደርግ የነበረዉ አካል ለስር ለዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አመልካችን አቅርቦ ለምርመራ የሚያስፈልገዉን ጊዜ ቀጠሮ ሲጠይቅ እንደነበርና በዚያዉ መዝገብ ላይ አመልካች የዋስትና መብታቸዉ እንዲጠበቅላቸዉ ጠይቀዋል፡፡በዚህ አግባብ የቀረበዉን የወንጀል ምርመራ ለማድረግ የሚያስፈልገዉን ጊዜ ቀጠሮ ጉዳይ እና የአመልካች የዋስትና መብት ጥያቄ አይቶ ለመወሰን የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በአዋጅ ቁጥር 434/1997(በአዋጅ ቁጥር 882/2007 እንደገና እንደተሻሻለዉ) በአንቀጽ 7/5 ስር በተደነገገዉ መሰረት ሥልጣን አለዉ ብለናል፡፡በመሆኑም ተጠሪ ጉዳዩ የታየዉ ሥልጣን በሌለዉ ፍርድ ቤት ነዉ በማለት ያቀረበዉ ክርክር ተቀባይነት የለዉም፡፡

እንዲሁም የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 109/1 መሰረት ዐቃቤ ሕግ በአመልካች ላይ በ15 ቀናት ዉስጥ ክስ እንዲመሰርት ትእዛዝ ሰጥቶ መዝገቡን ዘግቷል፡፡ተጠሪ በአመልካች ላይ የሚደረገዉ የወንጀል ምርመራ ሳይጠናቀቅ ክስ መመስረቻ ጊዜ ተሰጥቶ መዝገቡ መዘጋቱ ትክክል አይደለም የሚል ከሆነና በትእዛዙ ላይ ቅሬታ ካለዉ አግባብ ባለዉ ሕግ መሰረት ይግባኝ ጠይቆ ማሻርና በአመልካች ላይ ምርመራ ማድረጊያ ተጨማሪ ጊዜ እንዲሰጠዉ ማስፈቀድ ሲገባዉ ይህንን አላደረገም፡፡ክስ እንዲመሰርት የተሰጠዉ ጊዜ ካለቀ በኋላ እስካሁን በአመልካች ላይ ክስ ሳይመሰርት አመልካች በሕግ ከተደነገገዉ ሥርዓት ዉጭ በማረፊያ ቤት ታስረዉ እንዲቆዩ መደረጉ ተረጋግጧል፡፡ዐቃቤ ሕግ ወይም አመልካችን የያዘዉ የወንጀል መርማሪ አካል በዚህ አግባብ አመልካችን እስር ላይ እንዲያቆዩ የሚፈቅድላቸዉ ሕግ የለም፡፡

አመልካች የዋስትና መብታቸዉ ተጠብቆ ከእስር ለመለቀቅ ለሁለተኛ ጊዜ ማመልከቻ ያቀረቡት አዲስ የተፈጠረዉን ሁኔታ ማለትም ዐቃቤ ሕግ በተሰጠዉ 15 ቀናት ዉስጥ ክስ ያልመሰረተባቸዉ መሆኑን መሰረት በማድረግ ነዉ፡፡በመሆኑም የስር ከፍተኛ ፍርድ ቤት የአመልካችን የዋስትና ጥያቄ ተመልክቶ የዋስትና መብታቸዉ እንዳይጠበቅ የሚያደርግ ሕጋዊ ምክንያት መኖር አለመኖሩን መርመሮ መወሰን

ሲገባዉ አመልካች የዋስትና ጥያቄ አቅርበዉ አስቀድሞ በተሰጠ ትእዛዝ ዉድቅ መደረጉን በመግለጽ ይህን ትእዛዝ አመልካች በይግባኝ ሳያሸሩ ለሁለተኛ ጊዜ ጥያቄዉን ማቅረባቸዉ ተገቢ አይደለም በማለት ዉድቅ ማድረጉ የክርክሩን ልዩ ባህርይና የተፈጠረዉን አዲስ ሁኔታ መሰረት ያደረገ ባለመሆኑ መሰረታዊ የሆነ የክርክር አመራር ጉድለት ነዉ፡፡ በተጨማሪም የስር ከፍተኛ ፍርድ ቤት ዐቃቤ ሕግ ***በአጭር ጊዜ ዉስጥ በአመልካች ላይ ክስ ይመሰርት*** በማለት መዝገቡን መዝጋቱ የጊዜዉን አጭርነት ዐቃቤ ሕግ በመሰለዉ እንዲወስን በሚፈቅድ አኳኋን የመወሰን ሥልጣኑን ለዐቃቤ ሕግ አሳልፎ መስጠቱን እና አመልካች ላልተገደበ ጊዜ በእስር ላይ እንዲቆዩ ሊያደርግ የሚችል ትእዛዝ መስጠቱን ያሳያል፡፡ይህም የዳኝነት ሥራ አመራር የሚጠይቀዉን የገለልተኛነትና የዳኝነት ነጻነት መርሆዎችን የሚቃረንና ሕገ መንግሥታዊ ጥበቃ የተደረገለትን የአመልካችን የነጻነትና የዋስትና መብቶች የሚጥስ ነዉ፡፡ እንዲሁም ጉዳዩን በይግባኝና በሰበር ያየዉ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት እነዚህን ስህተቶች ማረም ሲገባዉ ያልተረጋገጠ መነሻ ይዞ አመልካች ዋስትና በሚያስከለክል የሙስና ወንጀል ሊከሰሱ ይችላሉ በማለት የአመልካችን ይግባኝና የሰበር አቤቱታዎች በትእዛዝ መሰረዙም ሊታረም የሚገባዉ ስህተት ነዉ፡፡

ሲጠቃለል በወንጀል በተጠረጠረ ሰዉ ላይ ምርመራ ማድረጊያ ጊዜ በፍርድ ቤት እየተሰጠ ቆይቶ በወንጀል መርማሪ እና/ወይም በዐቃቤ ሕግ የተጠየቀዉን ተጨማሪ የምርመራ ማከናወኛ ጊዜ ፍርድ ቤቱ ባለመፍቀድ እስከ 15 ቀን ድረስ ዐቃቤ ሕግ ክስ እንዲመሰረት በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 109/1 መሰረት የሰጠዉ ትእዛዝ ጸንቶ እያለ እና የተሰጠዉ ክስ መመስረቻ ጊዜ ከአለቀ በኋላ በተጠርጣሪዉ ላይ ክስ ሳይመሰረት ተጠርጣሪዉን በእስር ላይ ማቆየት በኢፌዲሪ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 17/2 እና በተባበሩት መንግሥታት የሲቪልና የፖለቲካ መብቶች ቃል ኪዳን አንቀጽ 9/1 የተከለከለዉን በሕግ ከተደነገገዉ ሥርዓት ዉጭ ወይም በዘፈቀደ አስሮ እንደማቆየት የሚቆጠር ነዉ፡፡ በወንጀል ምርመራ ሂደት የዋስትና መብት እንዲጠበቅለት ተጠርጣሪዉ ጥያቄ አቀርቦ ጥያቄዉ ተቀባይነት ከአጣ በኋላ የዋስትና ጥያቄ ለማቅረብ የሚያስችል አዲስ ሁኔታ ሲፈጠር ይህንኑ አዲስ ሁኔታ መሰረት በማድረግ ለዚያዉ ፍርድ ቤት ተጠርጣሪዉ የዋስትና መብት ጥያቄ በድጋሚ ለማቅረብ ሥነ ሥርዓታዊ መብት አለዉ ብለናል፡፡በዚህ አግባብ አዲስ ሁኔታ በመፈጠሩ ወይም ዐቃቤ ሕግ ክስ እንዲመሰረት የተሰጠዉ ጊዜ ክስ ሳይመሰረት በማለቁ ምክንያት የተያዘዉ (የታሰረዉ) ሰዉ በዋስትና ለመለቀቅ የሚያቀርበዉ ጥያቄ አግባብነት ካለዉ ሕግ አንጻር ሳይመረመር በደፈናዉ ጥያቄዉ ቀድሞ ተቀባይነት ያላገኘ ነዉ በሚል የተያዘዉ ሰዉ ክስ ሳይመሰረትበት ላልተወሰነ ጊዜ ታስሮ እንዲቆይ የሚያደርግ ትእዛዝ/ዉሳኔ መስጠት በፌዴራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀጽ 2(4/ሀ) እና 10(1/ሐ) ስር በተደነገገዉ መሰረት ሊታረም የሚገባዉ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ነዉ፡፡ ስለሆነም አመልካች ላይ የወንጀል ክስ እንዲመሰረት የተሰጠዉ የ15 ቀን ጊዜ ከአለቀ በኋላ አመልካች ላይ የወንጀል ክስ

ሳይመሰረትባቸዉ በእስር ላይ የሚገኙት በሕግ ከተደነገገዉ ሥርዓት ዉጭ በመሆኑ የአመልካች የዋስትና መብታቸዉ ተጠብቆ ከእስር ሊፈቱ ይገባል ብለናል፡፡ በመሆኑም ተከታዩን ወስነናል፡፡

ዉ ሳ ኔ

1. የአርሲ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 121631 ላይ በቀን 10/11/2015ዓ/ም የሰጠዉ ትእዛዝ፣ የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 433052 ላይ በቀን 20/11/2015ዓ/ም የሰጠዉ ትእዛዝ እና የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 436417 በቀን 02/12/2015ዓ/ም የሰጠዉ ትእዛዝ በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ሥነ ሥርዓት መመሪያ ቁጥር 17/2015 አንቀጽ 9/1 መሰረት ተሽረዋል፡፡
2. አመልካች ብር 50,000.00(ሃምሳ ሺህ ብር) በዋስትና አስይዘዉ ወይም ለዚህ በቂ የሆነ መያዣ ሲያቀርቡ ከእስር እንዲፈቱ ታዟል፡፡አመልካች በአዋጅ ቁጥር 434/1997 አንቀጽ 6/መ መሰረት ከአገር አንዳይወጡ ታግደዋል፡፡ይጻፍ፡፡በዚህ ትእዛዝ መሰረት አመልካች በዋስትና ከመለቀቃቸዉ በፊት ከአገር እንዳይወጡ የተሰጠዉ የዕግድ ትእዛዝ በሚመለከተዉ አካል ተመዝግቦ ዉጤቱ ሲገለጽ ከእስር እንዲለቀቁ ይጻፍ፡፡

ትዕዛዝ

1. የዉሳኔዉ ግልባጭ ለስር ፍርድ ቤት ይተላለፍ፡፡ ለግራ ቀኙም ግልባጩ ይሰጣቸዉ፡፡
2. መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ዕ/ወ

የሰ.መ.ቁ.188086

ሚያዝያ 28/2013 ዓ.ም

ዳኞች፡- እትመት አሰፋ

ፀሐይ መንክር

ኑረዲን ከድር

መላኩ ካሳዬ

እስቲበል አንዱዓለም

አመልካች፡- አቶ ግ/መድህን ብርሃነ

ተጠሪ፡- የትግራይ ክልል ፍትህ ቢሮ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍርድ

ጉዳዩ በሌለበት ታይቶ የተወሰነ የወንጀል ክስ እንዲነሳ ኤቤቱታ ቀርቦ ውድቅ በመደረጉ በቅጣት አወሳሰን ረገድ የቀረበ የሰበር ቅሬታን የሚመለከት ነው፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበው የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በወ/መ/ቁ/178997 ላይ መስከረም 30/2012 ዓ.ም በዋለው ችሎት የአመልካችን የይግባኝ ቅሬታ ውድቅ በማድረግ የሰጠውን የመጨረሻ ውሳኔን በመቃወም ነው፡፡

ክርክሩ የተጀመረው የአሁን ተጠሪ የወንጀል ህግ አንቀፅ 32(1(ሀ))፣ 27(2) እና 539(1(ሀ)) ድንጋጌን ጠቅሶ አመልካችን ጨምሮ በሶስት ተከሳሾች ላይ በትግራይ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ባቀረበው የወንጀል ክስ ነው፡፡ በቀረበው ክስ ላይ የአሁን አመልካች ሁለተኛ ተከሳሽ ነበር፡፡ የክሱም ጭብጥ ተከሳሾች ሰውን ለመግደል አስቀድመው በማሰብ አባሪ ተባባሪ ሆነው አቶ ክብሮም ፃድቃን የተባለውን የግል ተበዳይ የስር 3ኛ ተከሳሽ የነበረው ተበዳዩን እየመራ ከተቀጣጠሩበት ስፍራ ሲደርሱ አመልካች እና የስር 1ኛ ተከሳሽ በሽጉጥ ተኩሰው ሲመቱት ተበዳዩ እንደሞተ ሰው መስሎ ያሳለፉቸው እና በደረሰበት ጉዳት ምክንያት ተበዳዩ ላይ 100% የአካል ጉዳት የደረሰበት ለመሆኑ በህክምና ምርመራ የተረጋገጠ በመሆኑ ከባድ የግድያ ሙከራ ወንጀል ፈፅመዋል የሚል ነው፡፡

አመልካች እና የስር 3ኛ ተከሳሽ በአድራሻቸው ተፈልገው ባለመገኘታቸው እና በኢትዮጵያ ሄራልድ ጋዜጣም በተደረገላቸው ጥሪ መሰረት ባለመቅረባቸው ክሱ በሌለበት እንዲታይ

ተደርጓል፡፡ በዚሁ አግባብ የዐቃቤ ህግ ክስ እና ማስረጃ ከተሰማ በኋላ የስር 1ኛ ተከሳሽ ባቀረበው መከላከያ ማስረጃ የዐቃቤ ህግ ማስረጃን አላስተባበለም፣ አመልካች እና 3ኛ ተከሳሽ ቀርበው አልተከራከሩም በሚል በተከሰሱበት ወንጀል ጥፋተኛ ተብለዋል፡፡ ከቅጣት አንፃርም በተከሳሾቹ ላይ የወንጀል ሪኮርድ አለመቅረቡ እንዲሁም የስር 1ኛ ተከሳሽ የቤተሰብ አስተዳዳሪ መሆኑ በቅጣት ማቅለያነት ተይዞ እና የቅጣት ውሳኔው በቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቁጥር 01/2002 መሰረት ተሰልቶ 1ኛ ተከሳሽ በ15(አስራ አምስት) ዓመት ፅኑ እስራት፣ አመልካች እና ቀሪው ተከሳሽ እያንዳንዳቸው በ19(አስራ ዘጠኝ) ዓመት ፅኑ እስራት እንዲቀጡ ተወስኗል፡፡

ይህ ከሆነ በኋላ አመልካች እርሱ በሌለበት የተወሰነው የወንጀል ጥፋተኝነት እና የቅጣት ውሳኔ ተነስቶ ክሱ በድጋሚ ሊታይ ይገባል ያለበትን ምክንያት ጠቅሶ በወንጀል ህግ ሥነ ሥርዓት ቁጥር 197 መሰረት ፍርዱን ለሰጠው ፍርድ ቤት አቤቱታ አቅርቧል፡፡ ፍርድ ቤቱም በአቤቱታው ላይ የግራ ቀኙ ክርክር ከሰማ በኋላ የአመልካችን ጥያቄ ውድቅ አድርጓል፡፡ አመልካችም በቅጣት ማቅለያነት ሊያዙልኝ ሲገባ አልተያዙልኝም ያላቸውን ነጥቦች ዘርዝሮ ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ያቀረበ ቢሆንም አቤቱታው በወንጀል ህግ ሥነ ሥርዓት ቁር 195(1) መሰረት ተሰርዞበታል፡፡

የአሁን የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ በመቃወም ነው፡፡ አመልካች ታህሳስ 09/2012 ዓ.ም በተፃፈ የሰበር አቤቱታ በስር ፍርድ ቤት ተፈፅሟል ያላቸውን መሰረታዊ የህግ ስህተት ጠቅሶ በዚህ ችሎት እንዲታረምለት ጠይቋል፡፡ ፍሬ ቃሉም ጥፋተኛ የተባልኩበት የወንጀል ድርጊት በሙከራ ደረጃ የቀረ በመሆኑ፣ ከባድ የጤና እክል ያለብኝ እና የቤተሰብ አስተዳዳሪ መሆኔ እንዲሁም ከተበዳይ ጋር መታረቄን ገልጬ እያለሁ በቅጣት ማቅለያነት ተይዘውልኝ ቅጣቱ ቀልሎ ሊወሰን ሲገባ መታለፉ አግባብ ባለመሆኑ ሁኔታዎቹ ከግንዛቤ ገብተው ቅጣቱ ተሻሽሎ ሊወሰን ይገባል የሚል ነው፡፡

የአመልካች የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ አመልካች ጥፋተኛ ከተባለበት የወንጀል ህግ ድንጋጌ አንፃር የቅጣት ውሳኔው አግባብነት ከቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቁጥር 01/2002 አንፃር በዚህ ችሎት ቀርቦ እንዲመረመር በመታዘዙ ምክንያት ተጠሪ የፅሁፍ መልስ እንዲሰጥበት ተደርጓል፡፡

በዚሁ አግባብ ተጠሪ የካቲት 30/2012 ዓ.ም በተፃፈ መልስ ድርጊቱ በሙከራ ደረጃ መቅረቱ እንደ አንድ የቅጣት ማቅለያ ቢያዝ የማይቃወም መሆኑን፣ ቀሪዎቹ የቅጣት ማቅለያ ምክንያቶች ግን በስር ፍርድ ቤት ያልቀረቡ እና ክርክር ያልተደረገባቸው በመሆናቸው በዚህ ችሎት ሊቀርቡ አይችሉም በማለት ተከራክሯል፡፡ አመልካችም የሰበር አቤቱታውን የሚያጠናክር የመልስ መልስ በማቅረብ ሞግቷል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ እና የክርክሩ ይዘት አጠር ባለመልኩ ከላይ የተመለከተውን ሲመስል ይህ ችሎትም ጉዳዩ ለዚህ ችሎት ሲቀርብ ከተያዘው ነጥብ አኳያ የግራ ቀኙን ክርክር ለጉዳዩ አግባብነት ካለው ህግ ጋር በማገናዘብ መርምሯል፡፡

እንግዲህ ከክርክሩ አመጣጥ በግልፅ መረዳት እንደሚቻለው የአመልካች የሰበር አቤቱታ መነሻው በሌለሁበት የተላለፈብኝ የወንጀል ጥፋተኝነት ውሳኔ እንዲነሳ ያቀረብኩት አቤቱታ ውድቅ ቢደረግም በቅጣት ማቅለያነት መያዝ ሲኖርባቸው ያልተያዙ ምክንያቶች እንዲያዙልኝ ያቀረብኩት የይግባኝ አቤቱታ ውድቅ መደረጉ አግባብ አይደለም የሚል ስለመሆኑ መገንዘብ ይቻላል፡፡

በእርግጥ በሌለበት የተሰጠ የወንጀል ጥፋተኝነት ውሳኔ እንዲነሳለት አቤቱታ አቅርቦ ውድቅ የተደረገበት አመልካች በተሰጠው የቅጣት ውሳኔ ላይ ብቻ ይግባኝ ማለት የሚችል ስለመሆኑ የወንጀል ህግ ሥነ ሥርዓት ቁጥር 202(3) ይደነግጋል፡፡ ሆኖም “በወንጀል ህግ ሥነ ሥርዓት ቁጥር 202(3) ድንጋጌ ስር የተመለከተው የይግባኝ መብት የቅጣት ማቅለያ ምክንያቶችን አቅርቦ መከራከርን ያጠቃልላልን?” የሚለው ትኩረት ሊሰጠው የሚገባው ነጥብ ነው፡፡

በወንጀል ቅጣት አወሳሰን ውስጥ የሚቀርቡት የቅጣት ማክበጃ እና ማቅለያ ምክንያቶች ላይ የግራ ቀኙ መከራከሪያ ሊሰማ እንደሚገባ የወንጀል ህግ ሥነ ሥርዓት ቁጥር 149(3) ይደነግጋል፡፡ ይህ እንዲሆን የተፈለገውም የሚቀርበው የቅጣት አስተያየት የተያዘውን መነሻ የወንጀል ቅጣት ከፍ አልያም ዝቅ የማድረግ ውጤት ያለው በመሆኑ ምክንያት ስለትክክለኛነቱ በተገቢ አክኋን ለማጥራት እንደሆነ መገንዘብ ይቻላል፡፡ የሚቀርበው የቅጣት አስተያየትም የህግ ወይም የፍሬ ነገር ሊሆን ይችላል፡፡ የቅጣት አስተያየቱ የህግ ከሆነ እንደየሁኔታው በፍርድ ቤት ግምት የሚወሰድበት በመሆኑ ያን ያክል የግራ ቀኙን መገኘት እና ክርክር ማቅረብ ላይፈልግ ይችላል፡፡ ሆኖም አስተያየቱ የፍሬ ነገር ከሆነ የተባለው ምክንያት ስለመኖሩም ሆነ ስላለመኖሩ ግልፅ ጥያቄ እና ክርክር መቅረብ ያለበት በመሆኑ በቅጣት አወሳሰን ሂደት የተከራካሪ ወገኖችን መቅረብ/መገኘት/ የግድ የሚል ነው፡፡ ከዚህ አኳያ ተገቢውን መከራከሪያ ለማቅረብ ደግሞ ከመነሻውም የክርክሩ አካል መሆንን የሚጠይቅ በመሆኑ ጉዳዩ በሌለበት የተወሰነበት ተከሳሽ የፍሬ ነገር የቅጣት አስተያየት አቅርቦ የሚከራከርበት የህግ አግባብ የለም፡፡ እናም በወንጀል ህግ ሥነ ሥርዓት ቁጥር 202(3) ስር የተመለከተው በቅጣት ውሳኔ ላይ በይግባኝ የመከራከር መብት ተከሳሽ ባይኖርም በህግ ረገድ ፍርድ ቤት በራሱ ተነሳሽነት በቅጣት ማቅለያነት መያዝ ሲገባው ያልያዘውን አልያም በቅጣት ማክበጃነት መያዝ ሳይኖርበት በተሳሳተ የህግ አተረጓጎም የተያዘ የቅጣት ማክበጃ ምክንያትን ብቻ የሚመለከት ነው፡፡

አሁን በቀረበው ጉዳይ አመልካች በቅጣት ማቅለያነት ሊያዙልኝ ሲገባ አልተያዙልኝም ብሎ ከዘረዘራቸው ውስጥ የወንጀል ድርጊቱ በሙከራ ደረጃ ስለመቅረቱ ተጠቅሶ ከቀረበው ውጭ ያሉት

ምክንያቶች የፍሬ ነገር መከራከሪያዎች ናቸው፡፡ ይህ ከሆነ ደግሞ ቀድሞውኑ ጉዳዩን ለያዘው ፍርድ ቤት ሊቀርቡ እና ተገቢው ክርክር ሊደረግባቸው የሚገባቸው እንጂ ፍርድ ቤት በራሱ አስተያየት ሊያነሳቸው የሚችላቸው ጉዳዮች አይደሉም፡፡ አመልካች በዚህ መልኩ መከራከሪያውን እንዳያቀርብ ደግሞ ጉዳዩ በሌለበት የታየ በመሆኑ እና እድሉም ያልነበረ በመሆኑ ከጊዜ በኋላ በይግባኝ ደረጃ መከራከሪያ ሊቀርብባቸው የሚገባ አይደለም፡፡ በመሆኑም አመልካች ከዚህ አንፃር ያቀረበው መከራከሪያ ለአቤቱታው መሰረት ከሆነው የወንጀል ሀግ ሥነ ሥርዓት ቁጥር 202(3) ድንጋጌ ይዘትና መንፈስ ውጭ በመሆኑ ችሎቱ አልተቀበለውም፡፡

ሆኖም ድርጊቱ በሙከራ ደረጃ የመቅረቱ ጉዳይ በወንጀል ህግ አንቀፅ 27(3) እና 31 መሰረት ከቅጣት አወሳሰን ረገድ ፍርድ ቤት በራሱ አስተያየት ከግንዛቤ ሊያስገባው የሚችል የህግ ነጥብ ሆኖ እያለ የስር ፍርድ ቤት ከዚህ አንፃር ጉዳዩን ያለማየቱ ሊታረም የሚገባው መሰረታዊ የህግ ስህተት ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በዚሁ አግባብ የሙከራ ወንጀል ድርጊት በመሰረቱ ሊፈፀም ለነበረው ወንጀል በተቀመጠው ቅጣት መደብ የሚያስቀጣ ነው፡፡ ሆኖም የነገሩ ሁኔታዎች ታይተው እና ተመዝነው በወንጀል ህጉ አንቀፅ 179 ስር በተመለከተው መደበኛው የቅጣት ማቅለያ ምክንያት ቅጣቱ ሊቀል ወይም አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ቅጣትን መወሰን ጨርሶ ለመተው የሚቻል መሆኑን የወንጀል ህጉ አንቀፅ 27(3) እና 31 ድንጋጌ ያስገነዝባል፡፡ በዚሁ መሰረት በስር ፍርድ ቤት የተያዘው የእስራት ቅጣት እርከን በአንድ እርከን እንዲቀንስ ተደርጎ በእርከን 32 ስር መቀጣት እንዳለበት ታምኗል፡፡ በመሆኑም ተከታዩ ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

<u>ውሳኔ</u>

1. የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁ/178997 ላይ መስከረም 30/2012 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ እና የትግራይ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመ/ቁ/88512 ላይ ከአመልካች አኳያ የሰጠው የቅጣት ውሳኔ በወንጀል ህግ ሥነ ሥርዓት ቁጥር 195(2(መ)) እና 202(3) መሰረት ተሻሽሎ አመልካች በ15(አስራ አምስት) ዓመት ጽኑ እስራት እንድቀጣ ተወስኗል፡፡

2. የክልሉ ማረሚያ ቤት አስተዳደር በተሻሻለው ቅጣት መሰረት ተከታትሎ እንዲያስፈፅም ይዛፍ፡፡

3. መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ይመለስ፡፡

ልዩ ልዩ

የሰ/መ/ቁ. 115221

ቀን 25/08/2008 ዓ/ም

ዳኞች፡- 1. አልማው ወሌ

2. ዓሊ መሐመድ

3. ተኽሊት ይመሰል

4. እንደሻው አዳነ

5. ቀነዓ ቂጣታ

አመልካች፡- አቶ ግርማ ወ/ትንሳኤ - ቀረቡ

ተጠሪ፡- የልደታ ክፍል ከተማ ወረዳ 5 አስተዳደር - አልቀረበም

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል

ፍ ር ድ

1. ጉዳዩ የቀረበው የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት፣ ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሰበር ችሎት አመልካች ከተጠሪ በኪራይ ውል የያዘውን መኖሪያ ቤት እንድለቅ የሰጡት ውሳኔ አግባብነት ያላቸውን የህግ ማዕቀፎች መሰረት ያደረገ ነው ወይስ አይደለም? የሚለውን ጭብጥ በሰበር አጣርቶ ለመወሰን ነው፡፡ ጉዳዩ በመጀመሪያ የተያዘው በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ነው፡፡ በስር ፍርድ ቤት፣ አመልካች በልደታ ክፍለ ከተማ ወረዳ 5 የቤት ቁጥር የሆነውን የመንግስት ቤት ከተከሳሽ ጋር የካቲት 15 ቀን 2004 ዓ/ም በፈጸምኩት የኪራይ ውል ተከራይቼ በመኖር ላይ እገኛለሁ፣ ከሳሽ የተከራይነት ግዴታዬን እየተወጣሁ እያለሁ የኪራይ ውሉን ለማቋረጥ የሚስችል ህጋዊ ምክንያት በሌለበት ሁኔታ ህዳር 15 ቀን 2007 ዓ/ም በተጻፈ ደብዳቤ የተከራየሁትን ቤት በአምስት ቀን ውስጥ ለቅቄ እንድወጣ ማስጠንቀቂያ ሰጥቶኛል፡፡በመሆኑም በተከራያሁት ቤት የመኖር መብቱ እንዲከበርልኝና ተከሳሽ እየፈጠረ ያለው ሁከት ይወገድልኝ በማለት ክስ አቅርቧል፡፡
2. ተጠሪ በተከሳሽነት ቀርቦ የፍርድ ቤቱን የዳኝት ስልጣን አለመኖርና ከሳሽ ተከሳሽን ለመክሰስ የሚያስችለው ምክንያት የለም የሚል የክስ መቃወሚያ አቅርቧል፡፡ የስር ፍርድ ቤት የተጠሪን የመጀመሪያ የክስ መቃወሚያ ውድቅ አድርጎታል፡፡ ተጠሪ አመልካች የእናቱ ወ/ሮ እታገኘ ለገሰ የኮንደሚኒየም ቤት፣ በውርስ አግኝቶ እየተጠቀመ ነው፡፡ በመሆኑም ከሳሽ በውርስ ያገኘው ኮንደሚኒየም ቤት ያለው በመሆኑ ከመንግስት የተከራየውን ቤት ማስረከብ አለበት፡፡ ለዚህ ምክንያት የኪራይ ውሉን በማቋረጥ ቤቱን እንዲያስረክብ የወሰድኩት እርምጃ በአግባቡ ነው

በማለት ተክራክሯል፡፡ የስር ፍርድ ቤት ከሳሽ ከእናቱ ወረሰ የተባለው ኮንደሚኒየም ቤት ዘጠኝ የሚች ልጆች በጋራ የወረሱትና ከሳሽ ብቻውን ቤተሰቡን ይዞ ገብቶ ሊኖርበት የማይችል በመሆኑ፣ ተከሳሽ የከሳሽን የቤት ኪራይ ውል ያቋረጠው ከህግ አግባብ ውጭ ነው በማለት፣ ከሳሽ የተከራየውን ቤት ለተከሳሽ የማስረከብ ግዴታ የለበትም በማለት ወስኗል፡፡

3. ተጠሪ በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አቅርቧል፡፡ ይግባኝ ሰሚ ችሎት የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኋላ የስር ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሳኔ ሽሮ፣ አመልካች የተከራየውን ቤት ለተጠሪ ሊያስረክብ ይገባል በማለት ወስኗል፡፡ አመልካች የሰበር አቤቱታ ለአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት የሰበር ችሎት አቅርቧል፡፡ የከተማው አስተዳደር ሰበር ችሎት አመልካችን የሰበር አቤቱታ አልተቀበለውም፡፡
4. አመልካች ሰኔ 25 ቀን 2007 ዓ/ም በተጻፈ የሰበር አቤቱታ ሚች እናቱ የደረሳት ባለ አንድ መኝታ ቤት ኮንደሚኒየም ቤት ነው፡፡ ይህንን ቤት የሚች ዘጠኝ ወራሾች በውርስ አግኝተናል፡፡ የኮንደሚኒየም ቤቱን አመልካች ብቻዬን በውርስ አላገኘሁትም፡፡ የሌሎች ሰዎች የጋራ ሀብት በሆነ ኮንደሚኒየም ቤት ገብቼ ለመኖር የሚያስችለኝ መብት የለኝም፡፡ ስለዚህ የተጠሪ እርምጃ የከተማው አስተዳደር ያወጣውን መመሪያ የሚጻረርና የህግ መሰረት የሌለው በመሆኑ በሰበር ታይቶ እዲታረምልኝ በማለት አመልክቷል፡፡ ተጠሪ ሀምሌ 27 ቀን 2007 ዓ/ም በተጻፈ መልስ ተጠሪ የተከራየውን ቤት እንዲለቅ የተጠየቀው የከተማ አስተዳደር ባወጣው መመሪያ ቁጥር 3/2003 መሰረት ነው፡፡ ለዚህ ሰበር ችሎት የተያዘው ጭብጥ የፍሬ ጉዳይ እንጂ የህግ ጭብጥ አይደለም የሚል ይዘት ያለው ክርክር አቅርቧል፡፡ አመልካች ነሐሴ 28 ቀን 2007 ዓ/ም የተጻፈ የመልስ መልስ አቅርቧል፡፡
5. ጉዳዩን መርምረናል፤ የአመልካች ወላጅ እናት ኮንደሚኒየም ቤት የደረሳቸው ቢሆንም፣ የአመልካች እናት ከዚህ ዓለም በሞት በመለየታቸው በደረሳቸው ኮንደሚኒየም ቤት ላይ ያላቸው መብትና ጥቅም በፍታብሔር ህግ ቁጥር 826 ንዑስ አንቀጽ 2 መሰረት ለሚች ወራሾች የሚተላለፍ መሆኑ ግልጽ ነው፡፡ የአመልካች እናት ከአመልካች ሌላ ስምንት ወራሾች ያላቸው መሆኑ በስር ፍርድ ቤትና ግራ ቀኙ ባቀረቡት ክርክር ተረጋግጧል፡፡ አመልካች ከተጠሪ ጋር ኪራይ ውል ተዋውሎ እየኖር ባለበት ሁኔታ እናትህ ኮንደሚኒየም ስለደረሳቸውና ኮንደሚኒየም ቤት በውርስ ስላገኘህ የተከራየከውን ቤት ልትለቅ ይገባል በማለት ተጠሪ ያቀረበው ጥያቄ አመልካች በውርስ ከሌሎች ወራሾች ጋር ባገኘው ኮንደሚኒየም ቤት ላይ ያለው መብት በፍታብሔር ህግ ቁጥር 1060 ንዑስ አንቀጽ 2 እና በፍታብሔር ህግ ቁጥር 1266 እና ተከታይ ደንጋጌዎች መሰረት የጋራ ባለሀብትነት መብት መሆኑን ያገናዘበ ሆኖ አላገኘነውም፡፡
6. አመልካች የኮንደሚኒየም ቤቱ ብቸኛ ወራሽ ካልሆነ ከእናቱ ከሌሎች ጋር በወረሰው ኮንደሚኒየም ቤት ገብቶ ለመኖር የሚያስችለው መብት የለውም፡፡ ይህ ከሆነ ተጠሪ ከላይ

የጠቀሰናቸውን የህግ ደንጋጌዎችና የመመሪያ ቁጥር 3/2003 አንቀጽ 14 እና አንቀጽ 15 ንዑስ አንቀጽ 3 በሚቃረን ሁኔታ የኪራይ ውሉን በመሰረዝ አመልካች የተከራየውን ቤት እንድለቅ ያቀረበው ጥያቄ ህጋዊ ነው በማለት አዲስ አበባ አስተዳደር ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤትና ይግባኝ ሰሚ ችሎትና የሰበር ችሎት ተቀብለው አመልካች ቤቱን ለቅቆ እንዲወጣ የሰጡት ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ነው በማለት ወስነናል፡፡

ው ሳ ኔ

1. የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ሰኔ 16 ቀን 2007 ዓ/ም የሰጠው ውሳኔና የከተማው አስተዳደር የሰበር ችሎት በመዝገብ ቁጥር 23821 ሰኔ 19 ቀን 2007 ዓ/ም የሰጠው ትዕዛዝ ተሽሯል፡፡
2. የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 00020 መጋቢት 3 ቀን 2006 ዓ/ም የሰጠው ውሳኔ ፀንቷል፡፡
3. በዚህ ፍርድ ቤት የወጡትን ወጭና ኪሳራ ግራ ቀኙ ለየራሳቸው ይቻሉ፡፡ መዝገቡ ወደ መዝግብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሃ/ወ

የሰ/መ/ቁ 213917

ጥቅምት 29 ቀን 2015 ዓ/ም

ዳኞች፡- ተፈሪ ገብሩ (ዶ/ር)

ቀነአ ቂጣታ

ፈይሳ ወርቁ

ሰናይት አድነው

ደጀኔ አያንሳ

አመልካች፡- አቶ ነስሬ መሐመድ

ተጠሪ፡- ወ/ሮ ዘምዘም መሐመድ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ የቀረበው ጉዳይ የመጥፋት ውሳኔን እና የጋብቻ ንብረት ክርክርን የተመለከተ ነው፡፡ ክርክሩ የጀመረው በስር የቡታጀራ ከተማ መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ሲሆን የአሁን አመልካች ከሳሽ፣ ተጠሪ ተከሳሽ፣ በዚህ መዝገብ የሌሉት አማል ሁሴንና ወ/ሮ ፋጡማ ሀሰን ደግሞ ጣ/ገቦች ነበሩ፡፡

ከመዝገቡ መረዳት እንደሚቻለው የአሁን አመልካች ባቀረቡት ክስ ተጠሪ በመ/ቁ 07818 ባቀረበችው የመጥፋትና የፍቺ ውሳኔ ይሰጥልኝ አቤቱታ መነሻነት ፍርድ ቤቱ ከሳሽን ጠፍቷል ሲል ወስኖ አያይዞ በከሳሽና ተከሳሽ መሀከል የነበረው ጋብቻ ፈርሷል ሲል መወሰኑን ከምኖርበት ሳውዲ አረቢያ በተመለስኩበት ጊዜ ማወቅ ችያለሁ፡፡ ይሁን እንጂ ተከሳሽ ፍ/ቤቱን በማሳሳት የጋራ የሆኑ ንብረቶቻችን በግሏ አዙራ አላግባብ ለመበልጸግ በማሰብ ከሳሽ ሳላውቅ ጥሎኝ ጠፍቷል በማለት የተገለጸውን ፍርድ እንዲሰጥ ብታስደርግም ከሳሽና ተከሳሽ በ1992 ዓ.ም ተጋብተን 2 ልጆች ከወለድን በኋላ ኑሯችንን ለማሻሻል በጋራ ተመካክረን በ1997 ዓ.ም ወደ አረብ ሀገር ለስራ ተሰድጄ ስሄድ ተከሳሽ ሸኝታኝ ከሄድኩ በኋላም በስልክ እንደዋዋል ከመቆየታችንም በላይ በተለያዩ ግዜያት ለእሷና ለልጆቻችን ገንዘብ ስልክላት ቆይቻለሁ፡፡ ከዚህም ባሻገር ወደ አረብ ሀገር እንድትመጣ መንገድ አመቻችቼላት በነበራት አጋጣሚ የጋራ ቤታችንን የምትሰራበትን ገንዘብ ጨምሬ በመስጠት ወደ አገር ቤት አስቀድማ ተመልሳ ከእሷ ጋር ከመጋባታችን በፊት ከሳሽ በ1982 ዓ.ም አቶ መሀመድ ሁሴንና ፋጡማ ኢብሮ ከተባሉ ግለሰቦች ገዝቼው የነበረውንና ተሰርቶ ይገኝ የነበረውን በቡታጀራ ከተማ የሚገኝ መጠኑ 487.34 ካ/ሜ ቦታ ላይ የነበረውን 30 የቆርቆሮ ክዳን ቤት በማፍረስ በምትኩ ግምቱ ከብር

1,000,000.00 (አንድ ሚሊየን) በላይ የሆነ አንድ ባለ 90 ቆርቆሮ ክዳን ትልቅ መኖሪያ ቤት በጋራ ገንዘባችን ተሰርቶ ይገኛል፡፡ እንዲሁም በዚሁ ክ/ከተማ በተከሳሽ ስም ከቀበሌ ተከራይተን በጋራ ስንጠቀምበት የነበረ አንድ ክፍል ንግድ ቤት እና ከዚሁ ይዞታ ተያይዞ የሚገኝ በግምት 150 ካ/ሜ የሚሆን አስቀድሞ በሰነድ አልባ ይዞታነት ይዘነው የምንጠቀምበትን ተከሳሽ በስውር ወደ ራሷ ስም በማዞር ወደ ሌላ 3ኛ ወገን ለማዛወር ስትል ከሳሽ ደርሼ ያሳገድኩት ይዞታና በላዩ ላይ የሚገኙ 4 ክፍል ሰርቪስ ቤቶች የከሳሽና ተከሳሽ የባልና ሚስት ሀብት ነው፡፡ በመሆኑም በመ/ቁ 07818 የተሰጠው የመጥፋትና የፍቺ ውሳኔ ተሰርዞ የጋራ ሀብቶቻችን ወደነበሩበት እንዲመለሱ፤ ተከሳሽ በፍቺው የምትጸና ከሆነ የፍቺ ውጤት የሆኑትና ከሳሽ በጋራ ያፈራናቸውን ቤትና ቦታዎች እንዲሁም የቤት ቁሳቁሶች በንብረት አጣሪ ተለይተው እኩል እንድንካፈል ይወሰንልኝ በማለት ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡ ተከሳሽ የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያና የፍሬ ነገር መልስ ያቀረቡ ሲሆን ጣልቃ ገቦችም የበኩላቸውን ክርክር አቅርበዋል፡፡

ፍ/ቤቱም የግራ ቀኙን ክርክር እና ማስረጃ ከሰማ በኋላ በመ/ቁ 07818 በቀን 23/01/2004 ዓ.ም የተሰጠው የፍቺ ውሳኔ ሊሰረዝ አይገባም፡፡ ንብረትን በተመለከተ በይዞታው ላይ የነበረው 30 የቆርቆሮ ክዳን ቤት ፈርሶ ከውሳኔው በኋላ ተከሳሽ አሁን ያለውን ትልቁን ቤት የሰራች በመሆኑ በዚህ ቤት ላይ ከሳሽ መብት ባይኖረውም ተያይዞ ያለው ባዶ ይዞታ መሬት ተለክቶ 50% ለከሳሽ የቀረውን 50% ደግሞ ትልቁ ቤት ያረፈበትን አካቶ ተከሳሽ ሊሆን ይገባል በማለት ወስኗል፡፡ በ150 ካ/ሜ ላይ የተሰሩት ቤቶችና ይዞታ መሬት በተመለከተ የከሳሽና ተከሳሽ በጋብቻ ጊዜ ያፈሩት መሆኑ ስለተረጋገጠ የጋራ ሀብት ነው እኩል ሊካፈሉት ይገባል፡፡ በዚህ 150 ካ/ሜ ላይ የተሰሩት ቤቶችን በተመለከተ እነ አማል ሁሴን ከተከሳሽ ወኪል ወ/ሮ ሸምሲ መሀመድ ጋር ያደረጉት የሽያጭ ውል ስምምነት በፍ/ህ/ቁ 1723 እና 1815 መሰረት መፍረሱን በማረጋገጥ ወደ ነበሩበት ይመለሱ፡፡ ከሳሽ በተከሳሽ ላይ ተንቀሳቃሽ ንብረት በተመለከተ ያቀረቡት የዳኝነት ጥያቄ በማስረጃ ያልተደገፈ በመሆኑ ተቀባይነት የለውም በማለት ወስኗል፡፡

በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት አመልካች ይግባኝ ለቡታጅራ አካባቢ ከፍተኛ ፍ/ቤት እንዲሁም የሰበር አቤቱታ ለደቡብ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ቢያቀርቡም ተቀባይነት አላገኙም፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበው በዚህ ነው፡፡

አመልካች ባቀረቡት ማመልከቻ በመ/ቁ 07818 የተላለፈው የመጥፋትና የፍቺ ውሳኔ ተሰርዞ የአመልካችና ተጠሪ ጋብቻ ወደነበረበት እንዲመለስ እና በፍቺ ውጤቶች ላይ እንድንከራከር ተብሎ እንዲወሰንልኝ፤ በቡታጀራ ከተማ ቀበሌ 04 የሚገኘው 487.34 ካ/ሜ ይዞታና ባለ 90 ቅጠል ቆርቆሮ ቤትም የግል ሀብት ነው ተብሎ እንዲወሰንልኝ በማለት ቅሬታቸውን አቅርበዋል፡፡

ቅሬታው በሰበር አጣሪ ችሎት ተመርምሮ የስር ፍ/ቤት የሰጠው ውሳኔ የፍ/ብ/ህ/ቁ 170 እና ተከታዮቹን ድንጋጌዎች በተገቢው ያገናዘበ መሆን አለመሆኑን ለማጣራት በሚል ጉዳዩ ለዚህ ችሎት እንዲቀርብና ተጠሪ መልስ እንዲሰጡበት ተደርጓል፡፡

ተጠሪ ባቀረቡት መልስ አመልካችና ተጠሪ በ1992 ዓ.ም ጋብቻ የመሰረትን ሲሆን ልጆች እንደወለድን ተጠሪ አመልካችን በምንኖርበት የቀበሌ ኪራይ ቤት ውስጥ ጥሎኝ በ1997 ዓ.ም በመጥፋቱ ለረጅም አመታት ሳስፈልገው ብቆይም ያለበትን ላውቅ ባለመቻሌ ልጆቼን ብቻዬን ሳሳድግ ቆይቼ በ2003 ዓ.ም ለቡታጀራ ከተማ የመ/ደ/ፍ/ቤት የመጥፋት ውሳኔ እንዲሁም ጋብቻ ይፍረስልኝ አቤቱታ አቅርቤ ለ7 አመታት መጥፋቱ በመረጋገጡ የመጥፋት ውሳኔ ተሰጥቶ ጋብቻችን ፈርሷል፡፡ የመጥፋት ውሳኔ ከተሰጠ 6 አመት በኋላ ተመልሶ ከጠፋበት በመምጣት የጋራ ንብረት ታካፍለኝ ክስ ያቀረበ ሲሆን የጋራ ንብረቱ ነው ብሎ ያቀረበው በቡታጀራ ከተማ 04 ቀበሌ ውስጥ የሚገኘውና በ487 ካ/ሜ ቦታ ላይ የተሰራው ቤት የመጥፋት የፍቺ ውሳኔ ከተሰጠ ከ2 አመት በኋላ በተጠሪ የግል ጥረት የተፈራ ስለመሆኑ የራሱ የአመልካች ምስክሮች ጭምር አረጋግጠው መስክረውበታል፡፡ ይህም ሆኖ አመልካች ቦታውን ከመጥፋቱ በፊት የገዛሁት ነው የሚል የሀሰት የሽያጭ ውል አቅርቦ የነበረ በመሆኑ ቤቱ የተጠሪ ነው ተብሎ ተወስኖ ትርፉን ይዞታ እኩል ይካፈሉ ሲል ፍ/ቤቱ ወስኗል፡፡ አመልካች ለረጅም አመታት ልጆቹንና ትዳሩን ጥሎ ጠፍቶ የራሱን ህይወት ሲመራ የኖረ ለመሆኑ ባልካደበትና ጋብቻ በተጋቢዎች ነጻ ፈቃድ ላይ የሚመሰረትና አንዱ የትዳር አጋር ባልፈለገ ግዜ የሚፈርስ በመሆኑ የፍቺ ውሳኔ ተነስቶ ወደ ነበርንበት ጋብቻ እንመለስ ብሎ መጠየቅ የህግም ሆነ የሞራል መሰረት የለውም፡፡ የመጥፋት ውሳኔ መነሳትም ሆነ አለመነሳት በጋብቻችን መፍረስ ላይ የሚያመጣው የተለየ ህጋዊ ውጤት ስለሌለ ያቀረበው ጥያቄ የህግ መሰረት የለውም፤ የስር ፍ/ቤቶችም የፈጸሙት ምንም አይነት የህግ ስህተት የለም በማለት ተከራክረዋል፡፡ አመልካችም ክርክራቸውን በማጠናከር የመልስ መልስ አቅርበዋል፡፡

ከፍ ሲል በአጭሩ የገለጽነው የጉዳዩን አመጣጥ ነው፡፡ በበኩላችን የግራ ቀኙን ክርክር ቅሬታ ከቀረበበት ውሳኔ እና ከተገቢው የህጉ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ በውሳኔው የተፈጸመ የህግ ስህተት መኖር አለመኖሩን መርምረናል፡፡

እንደመረመርነው የአሁን አመልካች ቀዳሚ ቅሬታ የመጥፋትና የፍቺ ውሳኔ ተሰርዞ የአመልካችና ተጠሪ ጋብቻ ወደ ነበረበት እንዲመለስ የሚጠይቅ ነው፡፡ በፍ/ብ/ህ/ቁ 163(1) ስር እንደተመለከተው የጠፋ ሰው ጋብቻ የመጥፋቱ ማስታወቅ ፍርድ የመጨረሻ በሆነበት ቀን የሚፈርስ ሲሆን በአንዣሩ ጠፍቷል የማለት ማስታወቅ ውጤት መስጠቱ የሚቀረው ጠፋ የተባለው ሰው የመጣ እንደሆነ ስለመሆኑ በዚሁ ህግ አንቀጽ 170(1)(ሀ) ስር ተደንግጓል፡፡ ይህም ቢሆን ግን ጋብቻን በተመለከተ ወደ ነበረበት እንዲመለስ የማድረግ ውጤት ይኖረዋል ተብሎ የሚወሰድ አይደለም፡፡

ስለሆነም የፍቺ ውሳኔው ተነስቶ ከተጠሪ ፈቃድ ውጪ ወደ ነበሩበት ጋብቻ እንዲመለሱ የቀረበው ጥያቄ ተቀባይነት ያለው ሆኖ አላገኘነውም።

ንብረቱን በተመለከተም ጠፋ የተባለው ሰው በተመለሰ ጊዜ ንብረቶቹን በሚገኙበት አኳኋን፤ እንዲሁም የተሸጡትን ንብረቶች ዋጋና እነዚህንም ዋና ገንዘቦች በሥራ ላይ በማዋል የተገኙትን ንብረቶች ሁሉ መልሶ እንደሚወስድ፤ ይሁንና ንብረቶች የሚያስገኙትን ገቢ በተመለከተ ንብረቶቹ በይዞታ ተሰጥቷቸው እነዚህን ገቢዎች ላገኙ ሰዎች ገቢ እንደሆኑ እንደሚቀሩ በፍ/ብ/ህ/ቁ 171(1) እና (2) ስር ተመልክቷል።

በተያዘው ጉዳይ የስር ፍርድ ቤት የፍሬ ነገር ክርክርና ማስረጃውን መርምሮ መጠኑ 487.34 ካ/ሜ የሆነው ይዞታ ላይ የነበረው 30 ቅጠል ቆርቆሮ ቤት አለመኖሩንና አሁን ሰፍሮ የሚገኘው 90 ቅጠል ቆርቆሮ የለበሰ መኖሪያ ቤት መሆኑን፤ ይህም ቤት በተጠሪ ጥረት ብቻ የተፈራ መሆኑን በማረጋገጥ ይዞታውን አመልካችና ተጠሪ እኩል ይካፈሉ፤ ቤቱ የተጠሪዋ ስለሆነ በእኩሌታው ውስጥ መኖሪያ ቤቱ ያለበትን ይዞታ ተጠሪ እንድትወስድ ቀሪውን የእኩሌታ ድርሻ ደግሞ አመልካች እንዲወስዱ፤ እንዲሁም መጠኑ 150 ካ/ሜ የሆነውን ይዞታና ቤት ግን በጋራ የተፈራ መሆኑ ስለተረጋገጠ እኩል እንዲካፈሉ በማለት ወስኗል። የንብረት ክርክሩ በዚህ መልኩ መወሰኑ ደግሞ ከፍሲል የተጠቀሱትን የህጉን ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ የተከተለ ነው ከሚባል በቀር የሚነቀፍ ሆኖ አላገኘነውም። በአጠቃላይ ውሳኔው መሰረታዊ የህግ ስህተት ተፈጽሞበታል የሚሰኝ ሆኖ ስላላገኘነው ተከታዩን ወስነናል።

<u>ው ሳ ኔ</u>

1. የቡታጀራ ከተማ መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ 15544 በቀን 11/04/2011 ዓ.ም፤ የቡታጀራ አካባቢ ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ 12200 በቀን 28/05/2013 ዓ.ም እንዲሁም የደቡብ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ 16337 በቀን 24/10/2013 ዓ.ም የሰጡት ውሳኔና ትዕዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 348(1) መሰረት ፀንቷል።

2. የዕግድ ትዕዛዝ ተነስቷል። ይጻፍ።

3. በዚህ ፍ/ቤት ያወጡትን ወጭና ኪሳራ ግራ ቀኙ ይቻቻሉ።

መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ።

የማይነበብ የአራት ዳኞች ፊርማ አለበት

ስሜ በተራ ቁጥር 3ኛ ላይ የምገኘው ዳኛ የልዩነት ሀሳቤን እንደሚከተለው አስቀምጫለሁ

ለዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት ክርክር ምክንያት የሆነው ጉዳይ የአሁን ተጠሪ አመልካች አረብ ሀገር (ውጪ) ያለ መሆኑን እያወቀች የመጥፋት ውሳኔ አሰጥታበት የግል ቤቱን አፍርሳ ቤት የሰራች በመሆኑና የአሁን አመልካች ከውጪ ለስራ ከሄደበት መጥቶ አለመጥፋቱንና የአሁን ተጠሪም አብራ ውጪ ሀገር የነበረችና ያልጠፋ መሆኑን የምታውቅ እንደሆነ አስረድቶ ጋብቻቸው በመጥፋት ውሳኔ የፈረሰ በመሆኑ የግል ንብረቱ እንዲመለስለት ላቀረበው ዳኝነት ንብረትህን ልታገኝ አይገባም በሚል በስር ፍ/ቤቶች የተሰጠበትን ውሳኔ በመቃወም አቤቱታ በማቅረቡ ነው፡፡

የመጥፋት ውሳኔ ሲሰጥ የጠፋው ሰው ንብረት ሊተላለፍለት ለሚገባው ሰው ለወራሾቹ የሚተላለፍ በመሆኑ የአሁን አመልካች የመጥፋት ውሳኔ ሲሰጥበት ንብረቱ የሚተላለፈው ለአሁን አመልካች ወራሾች ለልጆቹ ነው፡፡ አሁን ለዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት ክርክር ምክንያት የሆነው ያከራከረው ቤት የአሁን አመልካች ከአሁን ተጠሪ ጋር ጋብቻ ሳይፈጽም በፊት የገዛው የግል ንብረቱ ስለመሆኑ በስር ፍ/ቤት በተደረገው ክርክር የተረጋገጠ ጉዳዩ ነው፡፡ የአሁን ተጠሪ በአሁን አመልካች ላይ የመጥፋት ውሳኔ ስታሰጥ በመሀላቸው ያለው ጋብቻ ይፈርሳል ጋብቻቸው ሲፈርስ በጋራ የፈሩት ንብረት የራሷን ድርሻ ትወስዳለች የጠፋው ሰው ድርሻ ደግሞ ለወራሾቹ ይሰጣል፡፡ የግል ንብረቱም እንዲሁ ለወራሾቹ የሚተላለፍ ይሆናል፡፡ የአሁን ተጠሪ እየተከራከረች ያለው በሚስትነት ደረጃ እንጂ ጠፋ የተባለው ሰው የአሁን አመልካች ልጆችን ወክላ ወይ በሞግዚት ደረጃ አይደለም፡፡ ልጆችም የአሁን አመልካች የመጥፋት ውሳኔ የተሰጠበት በመሆኑ ንብረቱ ተላልፎልናል የሚል ክርክር የላቸውም፡፡ የአሁን ተጠሪ በአሁን አመልካች ላይ የመጥፋት ውሳኔ ስታሰጥ ሆን ብላ በስራ ምክንያት አረብ ሀገር ያለ መሆኑን አያወቀች፣ አረብ አገር አብራ ኖራ ተመልሳ መጥታ፣ የመጥፋት ክስ አቅርባበት በሽምግልና ክሱን ትታ እንደገና በሌላ መዝገብ የመጥፋት ውሳኔ ያሰጠችበት ንብረቱን ለመውሰድ ያደረገችው ስለመሆኑ በስር ፍ/ቤት በተደረገው ክርክር የተረጋገጠ ጉዳይ ነው፡፡ የአሁን ተጠሪ ከአሁን አመልካች ጋር ጋብቻቸው በመጥፋት ውሳኔ ሲፈርስ የጠፋውን ሰው የግል ንብረት ልትይዝ የምትችልበት መንገድ የለም፡፡ ጋብቻቸው ከፈረሰና ንብረት ከተከፋፈሉ በኋላ በመሀላቸው የንብረት ግንኙነት እና የጋብቻ ግንኙነት የለም፡፡ ሁለት የተለያዩ ሰዎች ናቸው፡፡ በመሆኑም የጠፋውን ሰው የግል ንብረት የመያዝ መብቱ ሳይኖራት ይዛ ማንባታ የምትፈጽምበት የህግ መሰረት ምክንያትም የለም፡፡ የሌላ ሰው ንብረት በህገ ወጥ መንገድ ይዞ እንደመገኘት የሚወሰድ ነው፡፡ የአሁን ተጠሪ አመልካች ያልጠፋ እና አረብ አገር በስራ ምክንያት ያለ መሆኑን እያወቀች የመጥፋት ውሳኔ አሰጥታበት፣ የሱን የግል ንብረት መያዝ እንደማትችልና ጋብቻዋ ፈራሽ ሲሆን ለቃ ለሚመለከታቸው ወራሾቹ ማስተላለፍ ሲገባት መቃወም በማይችልበት ሁኔታ የግል ቤቱን አፍርሳ ቤት ሰርታበታለች፡፡

የኢፌዲሪ ህገ መንግስቱም ሆነ የንብረት ህግ እንድ ሰው የሌላ ሰው የግል ንብረት መሆኑን እያወቀ ሆነ ብሎ የግል ቤቱን አፍርሶ ቤት ከሰራበት የዚህ ቤት (ንብረት) ባለቤት ይሆናል በሚል

የተቀመጠ ድንጋጌ የለም፡፡ የሰበር ሰሚ ችሎት ትርጉምም የለም፡፡ ሰበር ሰሚ ችሎት በዚህ ሁኔታ የሰውን ቤት እያፈረሱ ቤት ከሰሩ የቤቱ ባለቤት ይሆናሉ ሲል የሚሰጥው ትርጉም ጉልበተኞች የሰው ቤት እያፈረሱ ቤት ከሰሩ የቤቱ ባለቤት የሚያደርግ ትርጉም የሚያስከትል በመሆኑ ውሳኔው ተገቢ ያልሆነና ሰዎች ንብረታቸውን ካለአግባብ እንዲነጠቁ የሚያደርግ ትርጉም የሚሆን ነው፡፡ የአሁን ተጠሪ አመልካች ያልጠፋ መሆኑን እያወቀች የመጥፋት ውሳኔ አሰጥታ የግል ንብረቱ መሆኑንም እያወቀች ቤቱን አፍርሳ ቤት ሰርታለች፡፡ የኢፌዴሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 40(7) ማንም ኢትዮጵያዊ በጉልበቱ ወይም በገንዘቡ በመሬት ላይ ለሚገነባው ቋሚ ንብረት ወይም ለሚያደርገው ቋሚ መሻሻል ሙሉ መብት አለው፡፡ ይህ መብት የመሸጥ የመለወጥ የማውረስ የመሬት ተጠቃሚነቱ ሲቋረጥ ንብረቱን የማንሳት ባለቤትነቱን የማዛወር ወይም የካሳ ክፍያ የመጠየቅ መብትን ያካትታል፡፡ ዝርዝር አፈጻጸሙ በህግ ይወሰናል ሲል ይደነግጋል፡፡ ይህ ድንጋጌ አንድ ሰው የሌላ ሰው የግል ንብረት መሆኑን እያወቀ የሰው የግል ንብረት ቤት አፍርሶ ቤት የሰራን ሰው የሚመለከት አይደለም፡፡ እንዲያውም ድንጋጌው የአሁን አመልካች በህጋዊ መንገድ ቤት በግዥ (በገንዘቡ) ያፈራው ንብረት በመሆኑ ይዞታውም ቢሆን ተጠቃሚነቱ በህጋዊ መንገድ እስካልተቋረጠ ድረስ የመሬቱም ባለይዞታነት የሚቀጥል የሚሆን ነው፡፡ የፍ/ብ/ህግ ቁጥር 1178 (1) ባለመሬቱ በግልፅ እየተቋወመው ማንም ሰው በሌላ ሰው መሬት ላይ ህንጻ የሰራ እንደሆነ በዚሁ ህንጻ ላይ አንዳችም መብት አይኖረውም ሲል ይደነግጋል፡፡ የፍ/ብ/ህግ ቁጥር 1178 (3) ከዚህ በላይ ባሉት በሁለቱ ንኡስ ቁጥሮች የተጻፉን ውሳኔዎች በማንኛውም ምክንያት ባለመሬቱ መቃወም ባልቻለበትም ጊዜ ተፈጻሚ ይሆናሉ ሲል ይደነግጋል፡፡ በመሆኑ የአሁን አመልካች መቃወም በማይችልበት ሁኔታ የአሁን ተጠሪ የአሁን አመልካችን ቤት አፍርሳ በይዞታው ላይ ቤት ሰርታ በመገኘቷ በዚህ ድንጋጌ መሰረት የዚህ ቤት ባለቤት የምትሆንበት የህግ መሰረት የሌለ በመሆኑ ቤቱን አፍርሳ እንድታነሳ ወይም ቤቱን ለቃ መሄድ የሚገባት ነው፡፡

እንዲሁም የፍ/ብ/ህግ ቁጥር 171(1) ጠፋ የተባለው ሰው በተመለሰ ጊዜ ንብረቶቹን በሚገኙበት አካኋን እንዲሁም የተሸጡትን ንብረቶች ዋጋና እነዚህንም ዋና ገንዘቦች በስራ ላይ በማዋል የተገኙትን ንብረቶች ሁሉ መልሶ ይወስዳል ሲል ደንግጎ ይገኛል፡፡ የአሁን አመልካች የመጥፋት ውሳኔ ከተሰጠበት በኋላ ሲመለስ ንብረቶቹን ሁሉ በሚገኙበት አካኋን ሊመለስለት ይገባል፡፡ የአሁን ተጠሪ የአመልካችን የግል መኖሪያ ቤት አፍርሳ የሰራችውን ቤት ባለቤት የምትሆንበት የህግ መሰረትም ሆነ ምክንያት የትኛው ነው? የለም፡፡ በመሆኑም የአሁን አመልካች የግል ንብረቱን ማግኘት ሲገባ ባልተገባ መንገድ ንብረቱን እንዲያጣ የተሰጠው ውሳኔ ሊታረም የሚገባው በመሆኑ የልዩነት ሀሳቤን አስቀምጫለሁ፡፡

አ/መ የማይነበብ የአንድ ዳኛ ፊርማ አለበት

የሰ/መ/ቁ 209040

የካቲት 30 ቀን 2014 ዓ/ም

ዳኞች፡- ተፈሪ ገብሩ (ዶ/ር)

ቀነአ ቂጣታ

ፈይሳ ወርቁ

ደጀኔ አያንሳ

ብርቅነሽ እሱባለው

አመልካች፡- አቶ አብርሃም ጌታሁን፡- ቀረቡ

ተጠሪ፡- አቶ ኃይለሥላሴ አስረስ፡- ከጠበቃ መለሰ ግርማይ ጋር ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ የተያዘው ክርክር ከንግድ ምልክት ጋር የተገናኘ ነው፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበውም አመልካች በቀን 08/10/2013 ዓ.ም በተጻፈ ማመልከቻ የፌደራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ 180219 በቀን 12/02/2012 ዓ.ም እንዲሁም የፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ 246897 በቀን 26/09/2013 ዓ.ም የሰጡት ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ይታረምልኝ በማለት ስለጠየቁ ነው፡፡ ክርክሩ በፌደራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ሲጀመር የአሁን ተጠሪ ከሳሽ አመልካች ደግሞ ተከሳሽ ነበሩ፡፡

ተጠሪ ባቀረቡት ክስ Sunland International Hotel የሚለውን ቃልና ምስል በንግድ ምልክትነት ያስመዘገብኩ ሲሆን ከ25/01/2009 ዓ.ም እስከ 25/01/2016 ዓ.ም ድረስ የሚቆይ የአዕምሯዊ ንብረት ጥበቃ ተሰጥቶኛል፡፡ ይሁን እንጂ ተከሳሽ ያለእኔ ፈቃድ እና እውቅና ያስመዘገብኩትን የንግድ ምልክት እየተጠቀመበት የሚገኙ በመሆኑ ተከሳሽ ይህን ድርጊታቸውን እንዲያቆሙ ይወሰንልኝ በማለት ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡

ተከሳሽ በሰጡት መልስ የምጠቀመው የንግድ ስም Sunland international Hotel የሚል ሳይሆን Sunland Hotel የሚል ነው፤ International የሚለው ቃል በተከሳሽ የንግድ ስም ውስጥ የለም፤ በጋዜጣ ላይ የወጣው የከሳሽ ንግድ ምልክት በኢታሊክስ አጻጻፍ *Sunland* የሚል ነው፤ ነገር ግን የተከሳሽ የንግድ ስም በካፒታል ሌተር SUNLAND HOTEL የሚል በመሆኑ ከከሳሽ የንግድ ምልክት ጋር ተቀራራቢ እንጂ ተመሳሳይ ነው ሊባል አይችልም፤ በጋዜጣ የወጣው የከሳሽ ንግድ ምልክት ምስል እና ከሳሽ ከክሱ ጋር አያይዞ በማስረጃነት ያቀረበው ምስል ተመሳሳይነት የሌላቸው

ናቸው፤ ከሳሽ የንግድ ምልክቱን በስማቸው ያስመዘገቡ ስለመሆኑ የምስክር ወረቀት አላቀረቡም፤ ይህን ባላቀረቡበት የንግድ ምልክቱ በ3ኛ ወገኖች ላይ ተፈጻሚነት አይኖረውም፡፡ ተከሳሽ sunland hotel የሚለውን የንግድ ስም ስልጣን ባለው በንግድ እና ኢንደስትሪ ጽ/ቤት አስመዝግቤያለሁ፡፡ አፅምሯዊ ንብረት የንግድ ምልክትን ምዝገባ የሚያካሂድ ሲሆን ንግድ እና ኢንደስትሪ ሚኒስቴር ደግሞ የንግድ ስም ለመመዝገብ ስልጣን የተሰጠው ነው፡፡ በዚህ ምክንያት አንዱ በአንዱ ላይ የበላይ ሊሆን የሚችልበት አግባብ የለም፡፡ አለ ቢባል እንኳ መብቱን ቀድሞ ያገኘው ማን ነው የሚለው ነጥብ መታየት አለበት፡፡ ተከሳሽ የንግድ ስም የምስክር ወረቀት ያገኘው በ10/05/2009 ዓ.ም ሲሆን ከሳሽ በዚህ ጊዜ የንግድ ምልክቱን በጋዜጣ ማስታወቂያ አሳውጆ ተቃዋሚ የሚቀርብ ከሆነ ሲጠባበቅ ነበር፤ የምስክር ወረቀት ሊያገኝ የሚችለውም ከዚህ ጊዜ በኋላ ነው፡፡ ከሳሽ የንግድ ምልክት አስመዝግቤያለሁ በማለት የሚከራከሩ ቢሆንም በንግድ ስሙ የከፈተው ሆቴል ወይም የሚያንቀሳቀሰው ንግድ የለም፡፡ በአንጻሩ ተከሳሽ ባስመዘገብኩት የንግድ ስም በስራ ላይ የምገኝ ሲሆን ተከሳሽ በንግድ ስሙ እንዳልጠቀም የምከለከል ከሆነ ያገኘሁትን መልካም ስም አጣለሁ፤ በመሆኑም ክሱ ውደቅ ሊደረግ ይገባል በማለት ተከራክረዋል፡፡

ጉዳዩ በዚህ መልኩ የቀረበለት የስር ፍርድ ቤት ክርክሩንና ማስረጃ ከሰማ በኋላ ተከሳሽ የሚጠቀመው የንግድ ምልክት ከከሳሽ የንግድ ምልክት ጋር ተመሳሳይ መሆኑ በማስረጃ ተረጋግጧል፤ ተከሳሽ የሚጠቀመው የንግድ ምልክት/ስም አማካይ የሆነ ተጠቃሚን ሊያሳስት የሚችል ሲሆን ከሳሽ እና ተከሳሽ ከሚሰጡት አገልግሎት አንጻር ተከሳሽ የሚጠቀመው የንግድ ምልክት ህብረተሰቡን የሚያሳክር ነው፤ ከሳሽ የንግድ ምልክታቸውን ያስመዘገቡት ለሆቴል አገልግሎት በመሆኑ ከዚህ አገልግሎት ጋር በተያያዘም የንግድ ምልክቱን ቃልም ሆነ ምስል መጠቀም የብቸኝነት መብት ያላቸው በመሆኑና ተከሳሽ በከሳሽ የንግድ ምልክት ላይ ጥሰት የፈፀሙ መሆኑ ስለተረጋገጠ ተከሳሽ ውሳኔ ከተሰጠበት ቀን ጀምሮ የከሳሽን የንግድ ምልክት እንዳይጠቀሙ፤ የሰቀሉትንም የንግድ ምልክት ከሆቴላቸው ላይ እንዲያነሱ በማለት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ተከሳሽ ለከፍተኛው ፍ/ቤት ይግባኝ አቅርበዋል፡፡ ፍርድ ቤቱ ክርክሩን መርምሮ በህግ ስልጣን ከተሰጠው ከኢትዮጵያ አእምሯዊ ንብረት ጽ/ቤት በተጻፈ ደብዳቤ ከሳሽ ከ25/01/2009 ዓ.ም እስከ 25/01/2016 ዓ.ም ድረስ ለንግድ ምልክቱ ጥበቃ የተሰጣቸው መሆኑ በማስረጃ ተረጋግጧል በማለት ቅሬታውን ውድቅ በማድረግ የስር ፍርድ ቤት ያሳለፈውን ውሳኔ አፅንቷል፡፡

የሰበር አቤቱታው የቀረበው በዚህ ነው፡፡ አመልካች በቀን 08/10/2013 ዓ/ም ባቀረቡት ማመልከቻ ተፈፀመ የሚሉትን የህግ ስህተት በመዘርዘር የስር ፍ/ቤቶች አመልካች በህጋዊ መንገድ

ያገኘሁትን የንግድ ስም እንዳልጠቀም የሰጡት ውሳኔ ስህተት የተፈፀመበት ነው ተብሎ እንዲታረም በማለት ቅሬታቸውን አቅርበዋል፡፡

ቅሬታው በሰበር አጣሪ ችሎት ተመርምሮ የስር ፍርድ ቤቶች አመልካች የተጠሪን ንግድ ምልክት ከሆቴሉ ላይ እንዲያነሱ የወሰኑበትን አግባብነት እንዲሁም የንግድ ምልክቱን ማን ቅድሚያ እንዳስመዘገበው የተጣራበትን አግባብ ለማጣራት በሚል ጉዳዩ ለሰበር ችሎት እንዲቀርብና ተጠሪ መልስ እንዲሰጡበት ተደርጓል፡፡

ተጠሪ ባቀረቡት መልስ ክርክራቸውን አጠናክረው የስር ፍርድ ቤቶች ተከሳሽ የንግድ ስሙን በማስመዝገብ ከቅን ልቦና ውጭ ሊጠቀሙት አይችሉም፤ ለክሱ ምክንያት በሆነው የንግድ ስምና ምልክት ከሳሽ የቀደምትነት መብት አላቸው በማለት የሰጡት ውሳኔ ተገቢነት ያለው በመሆኑ እንዲጸና ብለዋል፡፡ አመልካችም የመልስ መልስ አቅርበዋል፡፡

ከፍ ሲል በአጭሩ የገለጽነው የጉዳዩን አመጣጥ ነው፡፡ በበኩላችን የግራ ቀኙን ክርክር ቅሬታ ከቀረበበት ውሳኔ እና ከተገቢው የህጉ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ የተፈፀመ የህግ ስህተት መኖር አለመኖሩን መርምረናል፡፡

አንደመረመርነው የአመልካች መሰረታዊ መከራከሪያ ተጠሪ ለንግድ ምልክቱ የህግ ጥበቃ አግኝቼበታለሁ ባሉት የአእምሯዊ ንብረት ጥበቃ አዋጅ ቁጥር 501/98 መሰረት አመልካችን ለመቃወም የሚያስችል መብት የላቸውም፤ እንዲሁም ቀደምትነት ያለው የአመልካች የንግድ ስም ሆኖ እያለ በኋላ የተመዘገበው የተጠሪ የንግድ ምልክት በምዝገባ ቅደም ተከተል ሳይሆን የአእምሯዊ ንብረት ጽ/ቤት በጻፈው ደብዳቤ ቀደምትነት አለው መባሉ ስህተት ነው በሚል ነው፡፡

በንግድ ምልክት ምዝገባና ጥበቃ አዋጅ ቁጥር 501/1998 አንቀጽ 2(12) የተሰጠው ትርጉም እንደሚያመለክተው “የንግድ ምልክት” ማለት የአንድን ሰው ዕቃዎች ወይም አገልግሎቶች ከሌሎች ሰዎች ዕቃዎች ወይም አገልግሎቶች ለመለየት የሚያስችል የሚታይ ምስል ነው፡፡ ምልክቱ ቃላቶችን፣ ዲዛይኖችን፣ ፊደሎችን፣ ቁጥሮችን፣ ቀለሞችን ወይም የዕቃዎችን ወይም የመያዣዎቻቸውን ቅርጽ ወይም የእነዚህኑ ቅንጅት ሊይዝ ይችላል፡፡

ከዚህም ሌላ ምልክቱ በአዋጁ የተጠቀሱትን ሁኔታዎች የማያሟላ ከሆነ ተቀባይነት አይኖረውም፡፡ በአዋጁ የተጠቀሱት ሁኔታዎች ደግሞ በክፍል ሁለት ከአንቀጽ 5 እስከ 7 ድረስ ተዘርዝረዋል፡፡ ከድንጋጌዎቹ መረዳት እንደሚቻለው ማንኛውም የንግድ ምልክት የአንድን ሰው ዕቃዎች ከሌሎች ዕቃዎች በግልፅ ለመለየት የሚያስችል ከሆነ (capable of clearly distinguishing) ሊመዘገብ እንደሚችል፤ ነገር ግን ከአንድ አይነት ዕቃዎች ጋር የተያያዘ የሌላ ሰው ቀዳሚ የንግድ ምልክት ጋር አንድ አይነት የሆነ ወይም መሳከርን ሊያስከትል የሚችል ተመሳሳይነት ያለው ከሆነ (where it is

identical ……. Or if it so nearly resembles such a trademark as to be likely to deceive or cause confusion) ሊመዘገብ እንደማይገባ ተመልክቷል፡፡ (የአዋጁን አንቀጽ 5(1) እና 7(1) ይመለከታል)፡፡፡ በሌላ በኩል እነዚህን መመዘኛዎች አልፎ በባለስልጣኑ ምዝገባ የተደረገለት የንግድ ምልክት ጥበቃ ያገኛል፡፡

ከፍ ሲል ከተጠቀሱት የአዋጁ ድንጋጌዎች እና ከአዋጁ ጠቅላላ ይዘት እንዲሁም በዘርፉ ከዳበረው ዕውቀት መገንዘብ እንደሚቻለውም የአንድን በማመልከቻ በምዝገባ የገባ የንግድ ምልክት መሰረተዊ ባህሪ (essential feature) በመውሰድ ወይም የንግድ ምልክቱን እንዳለ ወስዶ በምልክቱ ላይ የተወሰነ ጭማሪ ወይም ለውጥ በማድረግ የቀረበ የንግድ ምልክት መሳከርን ሊያስከትል የሚችል ተመሳሳይነት ያለው ነው ሊባል ይችላል፡፡

በተያዘው ጉዳይ የስር ፍ/ቤት አመልካች የሚጠቀሙበት የንግድ ምልክት ተጠሪ በአዋጅ ቁጥር 501/98 ያገኙትን መብት እና ጥበቃ የሚጥስ መሆን አለመሆኑን በጭብጥነት ይዞ ከቀረበው ማስረጃ አንፃር በመመርመር የተጠሪ የንግድ ስምና ምልክት የሆነው Sunland International Hotel በተጠሪ ጠያቂነት የአዋጁን መስፈርት አሟልቶ ከ 25/01/2009 ዓ.ም እስከ 25/01/2016 ድረስ ለንግድ ምልክቱ ጥበቃ የተሰጣቸው መሆኑንና የንግድ ምልክቱም ለሆቴል አገልግሎት ምድብ 13 የተመዘገበ መሆኑን፤ እንዲሁም አመልካች በተጠሪ የንግድ ምልክት ላይ ጥሰት የፈፀሙ መሆኑን በፍሬ ነገር ደረጃ በማረጋገጥ ወስኗል፡፡

ይህ የፍሬ ነገር መደምደሚያ ተጠሪ በህጉ ስልጣን በተሰጠው አካል ዘንድ በመዝገብ ያስገቡት የንግድ ምልክት መሰረተዊ ባህሪ (essential feature) አመልካች በንግድ ሚ/ር በንግድ ምዝገባ አስመዝግቤዋለሁ በሚሉት የንግድ ምልክት የተወሰነ ለውጥ ተደርጎ መወሰዱን የሚያሳይ ነው፡፡

በአጠቃላይ የአመልካች የሚጠቀሙበት Sunland Hotel የሚለው ምልክት በተጠሪ በተገቢው ጽ/ቤት የተመዘገበውንና ጥበቃ ያገኘውን Sunland International Hotel የሚል የንግድ ምልክት መሰረታዊ ባህሪ በመያዝ የተወሰነ ለውጥ የሚያደርግ በመሆኑና የሁለቱ ንግድ ምልክቶች ተመሳሳይነት መሳከርን የሚፈጥር መሆኑ ፍሬ ነገርን ለማጣራትና ማስረጃን ለመመዘን ስልጣን ባለው የስር ፍርድ ቤት ተረጋግጦ አመልካች የተጠሪን የንግድ ምልክት እንዳይጠቀሙ፤ የሰቀሉትንም የንግድ ምልክት ከሆቴላቸው ላይ እንዲያነሱ ተብሎ በመወሰኑ የተፈፀመ የህግ ስህተት የለም ብለናል፡፡ ተከታዩንም ወስነናል፡፡

ው ሣ ኔ

1. የፌደራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ 180219 በቀን 12/02/2012 ዓ.ም እንዲሁም የፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ 246897 በቀን 26/09/2013 ዓ.ም የሰጡት ውሳኔ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ባለመሆኑ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 348(1) መሰረት ፀንቷል፡፡

2. በዚህ ፍርድ ቤት የተሰጠው የዕግድ ትዕዛዝ ተነስቷል፡፡ ይጻፍ፡፡

3. ለሰበር ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ የየራሣቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሠ/ኃ

የሰበር መ/ቁ/ 199697

ጥቅምት 5 ቀን 2014 ዓ.ም

ዳኞች፡- ብርሃኑ አመነው

ተሾመ ሽፈራው

ሀብታሙ እርቅይሁን

ብርሃኑ መንግስቱ

ነፃነት ተገኝ

አመልካች፡- አቶ ሰሃኔ አህመድ አብዲ - ጠበቃ ጌቱ ሶሬሳ - ቀረቡ

ተጠሪ፡- አቶ መሀመድ አብዲ መዶቤ - አልቀረቡም

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍርድ

ጉዳዩ የገጠር መሬት ክርክር የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው በሶማሌ ክልል በደቡብ ጅጅጋ ወረዳ ፍ/ቤት ላይ የአሁኑ አመልካች ከሳሽ በመሆን የአሁኑ ተጠሪ ተከሳሽ በመሆን የተከራከሩበት ነዉ፡፡አመልካች ያቀረበው ክስ ይዘት ባጭሩ በሸቤሌ ወረዳ በለድካ ቀበሌ የሚገኝ 200 ጋሻ መሬት ከአባቴ የወረስኩና ለመሬቱም በፍ/ብ/ህ/ቁ 1195 መሰረት በሃይለስላሴ ዘመን የይዞታ ካርታ ማረጋገጫ ቁጥር 015685 ያለኝ ሲሆን ቦታው በ4 ቤተሰብ ይዞታ ስር የሚገኝ ጫትና ማሽላ የሚመረትበት ሲሆን ያልታረሰ መሬት የቤተሰብ አባላት መኖሪያ መንደር እና ለእንስሳት ግጦሽ የሚውል ተጠሪ እንዲለቅልኝ ይወሰንልኝ የሚል ሲሆን ተጠሪ በበኩሉ በመካከላችን የቦታ ይገባኛል ጥያቄ ጉዳይ በሽማግሌዎች ለመዳኘትና ውሳኔያቸውን ለመቀበል በፊርማችን አረጋግጠን በቀን 30/07/2012ዓ.ም ተስማምተናል፡፡ቦታው የእኔ ከመሆኑም በላይ የሸቤሌ ወረዳ አስተዳደርም በቁጥር 534/012 በቀን 01/08/2012 ዓ.ም የሽማግሌዎቹን ውሳኔ ያፀደቀ ሲሆን የነሳ መሪው ጋራድ ኩልሚዬ በ03/08/2012 ዓ.ም እንዲሁም የሲን ቀበሌ አስተዳደርም በ06/08/2012 ዓ.ም ደብዳቤ የሽማግሌዎችን ውሳኔ ያፀደቁ ናቸዉ፡፡ስለዚህ በፍ/ስ/ስ/ህ/ቁ 244(1/ሀ) መሰረት ጉዳዩ በአዲስ መልክ መታየት የለበትም በማለት ክሱ ውድቅ እንዲሆን ሲል መከራከሩን መዝገቡ ያሣያል፡፡

ፍ/ቤቱም የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ውድቅ በማድረግ በፍሬ ነገር ላይ አከራክሮ የግራ ቀኝ የሰነድና የሰው ምስክሮች ቃል መርምሮ ለክሱ ምክንያት የሆነው ቦታ የተጠሪ ይዞታ ነው በማለት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

አመልካች በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ለፋፊን ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ አቅርቦ ፍ/ቤቱም ጉዳዩ ያስቀርባል በማለት መዝገቡን መርምሮ አመልካች ያቀረበው መሬት ባለቤትነት የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ አግባብ አልነበረም ምክንያቱም በአዋጅ ቁጥር 47/67 መሰረት የተሻረ እና ያለአግባብ የተዘጋጀ ነው፣መሬቱ ላይ የጫት ምርት አለኝ የሚለው ከእውነት የራቀ ነው፣ ስለዚህ የተጠሪ ማስረጃ አብላጫ ያለው ነው በማለት የስር ፍ/ቤት ውሳኔ አጽንቷል፡፡አመልካች ለክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ያቀረበዉን አቤቱታ ችሎቱ መርምሮ በውሳኔው ላይ መሰረታዊ የህግ ስህተት አልተፈፀመም በማለት አቤቱታው ውድቅ አድርጎታል፡፡

በዚህ ዉሳኔ ላይ መሰረታዊ የህግ ስህተት ተፈጽሞበታል እንዲታረምልኝ በማለት አመልካች ለዚህ ችሎት ያቀረበው አቤቱታ ይዘት ባጭሩ ሲታይ ማንኛውም ክርክር ሊወሰን የሚገባው በቀረበው ማሰረጃ እና በህጉ መሰረት ብቻ መሆኑን፣ይህ ታልፎ የሚሰጥ ውሳኔ ህጋዊ ሊሆን እንደማይችል፣የስር ፍ/ቤት ማስረጃዎቹ ምን እንዳስረዱ፣ የአመልካች ማስረጃዎች በምን ምክንያት ውድቅ እንደተደረጉ፣በአካባቢው ተገኝቶ ምን እንደተገነዘበ ለውሳኔ ያበቃዉ ማስረጃ የትኛው እንደሆነ ሳይጠቅስ እንዲሁም የተያዘው ጭብጥ ምን እንደሆነ እና የፍርድ ሐተታ ሳይቀመጥ የተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት ነው፣የተጠሪ ምስክሮች የተጠሪ ነው ብሎ አዋሳኝ ጠቅሶ የመሰከሩት የተለየ ቦታ ሆኖ እያለ መሬቱ የተጠሪ ነው በማለት የሰጠዉ ውሳኔ የስነ ስርዓት ደንብ የተከተለ አይደለም፣በአስተዳደር እና በሽማግሌዎች ለተጠሪ ተወስኗል ተብሎ የቀረበው ሰነድ ሰመተር ፋራህ እና ሂርሲ ፋራህ በሚባል ጎሳዎች መካከል የተነሳ ክርክር እንጂ በአመልካች እና በተጠሪ መካከል እንዳልሆነ ተጠቅሶ እያለ የፍ/ብ/ህ/1195 ጠቅሶ ውሳኔ ማሳለፉ እና የገጠር መሬት ህግና አዋጅ መሰረት በማድረግ ውሳኔ መሰጠት ሲገባ ይህንን ሳያደርግ ህግን እና መደበኛ የሙግት አመራር ሥነ ሥርዓት በመጣስ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት በመሆኑ ውሳኔው በመሻር ተጠሪ ያለአግባብ የወሰደው መሬት እንዲመልስ ይወሰንልኝ በማለት አመልክተዋል፡፡

የአመልካች አቤቱታ በሰበር አጣሪ ችሎት ተመርምሮ በዚህ ጉዳይ በስር ፍ/ቤቶች የተደረገው ክርክርና የተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የክርክር አመራር ስርዓትን እና የማስረጃ ምዘና መርህን የተከተለ መሆን አለመሆን ተጠሪ ባለበት ለማጣራት ጉዳዩ ያስቀርባል ተብሎ ተጠሪ መልስ እንዲሰጥበት ታዟል፡፡

ተጠሪ ባቀረበው መልስ በአዋጅ ቁ/456/1997 አንቀጽ 12 መሰረት ከእርሻ መሬት ጋር ተያይዞ የሚነሳ ግጭትና አለመግባባት በግራ ቀኝ በተመረጡ ሽማግሌዎች ታይቶ ውሳኔ ማግኘት እንዳለበት በሚገልጸዉ መሰረት ክርክር ያስነሳው መሬት ከአያታችን የተላለፈልን በእጁ የሚገኝ ይዞታ መሆኑ አረጋግጦ በሽማግሌዎች እና በጎሳ መሪ ጋራድ ኩልሚዬ እና የቀበሌው አስተዳደር ጽ/ቤት የሽማግሌዎች ውሳኔ በመደገፍ ያጸደቀ በመሆኑ አመልካች በስር ፍ/ቤት ይህንን ሃቅ

ማስተባበል ባለመቻሉ ተወስኖበታል፡፡አመልካች ስርዝ ድልዝ ያለበት በኃይለስላሴ ዘመን የተሰጠ ተአማኒነት የጎደለው ሰነድ አቅርቦ ቢከራከርም በቁጥር 31/67 በወጣው የመሬት አዋጅ መሰረት መሬት ለአራሹ ድንጋጌ መሰረት የተሰረዘና የተሻረ በመሆኑ ማስረጃው ተቀባይነት የለዉም፣የስር ፍ/ቤት ማስረጃዉን ውድቅ ማድረጉ ትክክለኛ ነው፡፡የስር ፍ/ቤት ጭብጥ በመመስረት መሬቱ የሚገኝበት የመስክ ምልከታ በማድረግ አጣርቶ የግራ ቀኝ ማስረጃ መርምሮ የሰጠው ውሳኔ የሚነቀፍበት የህግ ምክንያት የለም፣በየደረጃው ያሉ ፍ/ቤቶች ይህንኑ በማገናዘብ ውሳኔውን ያፀደቁ በመሆኑ የአመልካች አቤቱታ ውድቅ ተደርጎ ወጪና ኪሳራ ተወስኖልኛ በነፃ እንዲሰናበት በማለት ተከራክረዋል፡፡አመልካች አቤቱታቸውን የሚያጠናክር የመልስ መልስ አቅርበው ከመዝገቡ ጋር ተያይዟል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ እና የግራ ቀኙ ክርክር አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተመለከትነው ሲሆን ጉዳዩ ለሰበር ያስቀርባል ከተባለበት ጭብጥ አንጻር የስር ፍርድ ቤት ውሳኔ አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ መርምረናል፡፡መዝገቡን መርምረን እንደተገነዘብነዉ አመልካች ክስ ያቀረበበት የገጠር መሬት ተጠሪ ያለአግባብ ይዟል በሚል በፍርድ ሃይል ተገዶ እንዲለቅ ዳኝነት የጠየቀ ሲሆን ተጠሪ በበኩሉ ይዞታዉ በእጁ የገባዉ በዉርስ የተላለፈለት ስለመሆኑ እና ክስ የቀረበበት ይዞታ ላይ አመልካች መብት የሌለዉ መሆኑን መከራከሩን መዝገቡ ያሣያል፡፡ይሁንና ፍሬ ነገር የማጣራትና ማስረጃ የመመርመር ስልጣን በህግ የተሰጣቸዉ የሥር ፍርድ ቤቶች ጉዳዩ አስቀድሞ በግራ ቀኙ ስምምነት በተመረጡ ሽማግሌዎችና የጎሳ መሪ ታይቶ የተጠሪ ይዞታ ስለመሆኑ ተወስኖ በወረዳዉ መሬት አስተዳደር አካል የጸደቀ መሆኑን አረጋግጠዉ የአመልካችን ክስ ዉድቅ ስለማድረጋቸዉ ተገንዝበናል፡፡አመልካች አሁንም አጥብቆ የሚከራከረዉ የሥር ፍርድ ቤት ዉሳኔ የክርክር አመራር እና የማስረጃ ምዘና ስህተት ተፈጽሞበታል በማለት ነዉ፡፡በዋናነትም አከራካሪዉ ይዞታ የአመልካች ስለመሆኑ በሃይለስላሴ ዘመነ መንግስት የተሰጠ የግል ይዞታ ማረጋገጫ እያለኝ ለተጠሪ መወሰኑ የማስረጃ ምዘና ስህተት ነዉ በማለት ይከራከራል፡፡እኛም ይህንኑ መሰረት በማድረግ በስር ፍርድ ቤት ዉሳኔ ላይ የተፈጸመ መሰረታዊ የህግ ስህተት መኖር አለመኖሩን እንደሚከተለዉ መረምረናል፡፡

አንድ መብት ወይም ግዴታ አለ ብሎ የሚከራከር ወገን መብቱ ወይም ግዴታው ስለመኖሩ የማስረዳት ሸክም (one who alleges in the affirmative shall prove it) እንዳለበት የፍ/ብ/ስ/ስ/ህግ ቁጥር 258 እና 259 እና የፍ/ብ/ህግ ቁጥር 2001 ድንጋጌዎች ይዘት ያሳገነዝባል፡፡አከራካሪዉን ፍሬ ነገር ለማስረዳት ሊቀርብ የሚገባዉ ማስረጃ ዓይነት በሚመለከት ሰነድ/ጽኑፍ/፣ምስክር፣የህሊና ግምት፣በተከራካሪ ወገን እምነት ወይም በመሓላ ቃል ማስረዳት እንደሚቻል የፍ/ብ/ህግ አንቀጽ 2002 በግልጽ ይደነግጋል፡፡በፍትሓብሔር ክርክር ቅቡልነት ያለዉ የማስረጃ ምዘና መርህ ``standard of proof`` የክርክርሩን ፍሬ ነገር ማን በተሻለ ሁኔታ/ደረጃ/ በማስረጃ

አሰረድቷል``preponderance of evidence`` የሚል መሆኑም ልብ ይለዋል፡፡የክርክሩን ጭብጥ በመለየት እና ማስረጃ የማቅረብና የማስረዳት ግዴታን፣የቀረበዉን ማስረጃ አግባብነትና ተቀባይነት መለየት እና የማስረጃዉ ብቃት/ምዘና/ መርህን አስመልክቶ ቅቡልነት ያላቸዉን መርሆዎች ተከትሎ የክርክሩን ፍሬ ነገር ማጣራት እና ማስረጃ በመመዘን ሚዛናዊና ፍትሃዊ ድምዳሜ ላይ ለመድረስ በሚያስችል ሁኔታ ክርክሩን በአግባቡ መምራት የፍርድ ቤቱ ሃላፊነትና ተግባር ስለመሆኑ ስለፍትሐብሔር ክርክር አመራር ስርዓት የሚደነግገዉ የስነ ስርዓት ህግ የሚያስገነዝበን ጉዳይ ነዉ፡፡

በዚህ መዝገብ የቀረበዉ ጉዳይ ተጠሪ የያዘዉን መሬት ለአመልካች እንዲለቅ በሚል ዳኝነት በመጠየቁ ተጠሪ መብት ሳይኖረዉ የያዘዉ ስለመሆኑ የማስረዳት ሸክም አመልካቹ ነዉ፡፡ፍርድ ቤቱም በአከራካሪዉ መሬት ላይ የይዞታ መብት ያለዉ ማነዉ የሚል ጭብጥ በመያዝ የግራቀኙን ማስረጃ ከመስማት ባሻገር በአካልም ጭምር በቦታዉ ተግኝቶ ምልክታ ያደረገ ስለመሆኑ ዉሳኔዉ ያሣያል፡፡መሬቱ የአመልካች ስለመሆኑ ያስረዳልኛል በማለት ያቀረበዉ ሁነኛ ማስረጃ አዋጅ ቁጥር 31/67 ከመዉጣቱ በፊት የተሰጠዉ የይዞታ ማረጋገጫ ሰነድ ስለመሆኑ በስር ፍርድ ቤቶች የተረጋገጠ ነዉ፡፡አመልካች ያቀረበዉ የይዞታ ማረጋገጫ ተቀባይነት የለዉም የተባለዉ የገጠር መሬት የግል ሀብት መሆኑ በአዋጅ ቁጥር 31/67 የተሻረ መሆኑ ተጠቅሶ ነዉ፡፡የዉሳኔዉ ምክንያት ተገቢ መሆን አለመሆኑ የሚወሰነዉ በዚህ ዙሪያ ያለዉን ህግ በማጤን ነዉ፡፡የሀገራችን የመሬት ስሪት ስርዓት ከስርዓተ መንግስት ጋር እየተለዋወጠ የመጣ መሆኑን ማየት ይቻላል፡፡በዘዉዳዊዉ ስርዓት መሬት በአብዛኛዉ በከበርቴዎች እና መንግስት ይዞታ ስር የነበረ ሲሆን ከሞላ ጎደል የግል ሀብት ሆኖ ቆይቷል፡፡ይህንን ስርዓት የተካዉ ዋጅ ቁጥር 31/67 እና አዋጅ ቁጥር 47/67 በማወጅ የገጠር እና የከተማ መሬት የህዝብ እና የመንግስት ሀብት እንዲሆን አድርጓል፡፡ከእነዚህ አዋጆች በኋላ በወጣዉ በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ህገ መንግስት እንደተደነገገዉ የገጠርም ሆነ የከተማ መሬትና የተፈጥሮ ሀብት የመንግስት እና የህዝብ ሀብት ተደርጓል፡፡(የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 40/3/ ይመለከቷል)፡፡ይህም የመሬት ስሪት ለዉጥ መደረጉንና መሬት የግል ሀብት መሆኑ ሙሉ በሙሉ ቀሪ መሆኑን የሚያሳይ ነዉ፡፡ይህንኑ ተከትሎ ግለሰቦች የገጠር መሬትም ሆነ የከተማ መሬት የመጠቀም የይዞታ መብት እንጂ የባለቤትነት መብት እንደሌላቸዉ ከህገ መንግስቱ ድንጋጌዎች መገንዘብ ይቻላል፡፡የገጠር መሬት የመጠቀም የይዞታ መብት የሚገኘዉም በመንግስት በሚደረግ ድልድል፣በዉርስ ወይም በስጦታ ወይም የግል ባለሀብት ከሆነ ደግሞ በኢንቨስትመንት ዉል እንደሚሆን ህገ መንግስቱን ተከትሎ የወጣዉ የፌዴራል የገጠር መሬት አስተዳደር አዋጅ ቁ/456/97 አንቀጽ 5/3/ ይዘት ያስገነዝባል፡፡በዚህ ዙሪያ ሶማሌ ክልል ከዚህ የተለየ የገጠር መሬት አስተዳደር አዋጅ ስለመኖሩ በስር ፍርድ ቤት ዉሳኔ አልተገለጸም፡፡ስለሆነም በገጠር መሬት የመጠቀም የይዞታ መብት አለኝ የሚል ሰዉ ከእነዚህ በአንደኛዉ አግባብ ይዞታዉን ያገኘ ስለመሆኑ ማስረዳት ይጠበቅበታል፡፡

በዚህ ጉዳይ ለክርክር ምክንያት የሆነዉ መሬት ተጠሪ በዉርስ ያገኘዉ መሆኑን እና ጉዳዩ አስቀድሞ በግራ ቀኙ መካከል በተደረገ ስምምነት በሽማግሌዎች እና ጎሳ መሪ ታይቶ የተጠሪ ህጋዊ ይዞታ ነዉ ተብሎ ጉዳዩ በሚመለከተዉ አስተዳደር አካልም ተቀባይነት ያገኘ ስለመሆኑ ከስር ፍርድ ቤቶች ዉሳኔ ይዘት መገንዘብ ተችሏል፡፡በአዋጅ ቁጥር 456/97 አንቀጽ 12 እንደተደነገገዉ የገጠር መሬት በተመለከተ የሚነሳ አለመግባባት አስቀድሞ ግራ ቀኙ በሚያደርጉት ዉይይትና ስምምነት ወይም በመረጡት ሽማግሌዎች እንዲታይ በማድረግ ወይም በክልሉ የገጠር መሬት አስተዳደር ህግ በሚወሰነዉ መሰረት ሊታይ የሚቻል ሲሆን ከዚህ ሌላ አቤቱታዉን ለሚመለከተዉ ፍርድ ቤት ማቅረብ ይቻላል፡፡አለመግባባቱ አስቀድሞ በሽምግልና እንዲታይ መስማማት የሚቻል ቢሆንም የሽማግሌዎቹ ዉሳኔ የመጨረሻ እና አስገዳጅ እንደማይሆን የድንጋጌዉ ይዘት ያስገነዝባል፡፡ስለዚህም ዉሳኔዉ የመጨረሻ እንደሆነ አድርጎ ተጠሪ ያቀረበዉን መቃወሚያ የስር ፍርድ ቤቶች ዉድቅ ማድረጋቸዉ ስህተት የለዉም፡፡ነገር ግን ጉዳዩ ለፍርድ ቤት ሲቀርብ ፍርድ ቤቱ በሽማግሌዎቹ ዉሳኔ እና ማስረጃ ይዘት ሳይወሰን ሌሎች አግባብነት ያላቸዉን ማስረጃዎችን በመስማትና በመመርመር የበኩሉን ዉሳኔ መስጠት ይችላል፡፡ በዚህም ጉዳይ የተደረገዉም ይኸዉ ነዉ፡፡የስር ፍርድ ቤት የግራቀኙን ማስረጃ የመረመረ ስለመሆኑ የዉሳኔዉ ይዘት የሚያሳይ ሲሆን አመልካች ያቀረበዉ የገጠር መሬት ባለቤትነት ማረጋገጫ ሰነድ የተሰጠዉ አዋጅ ቁ/31/67 ከመዉጣቱ በፊት በመሆኑና የዚህ ሰነድ የማስረጃ ጠቀሜታ ወይም ብቃት ከአዋጅ ቁጥር 31/67 አንጻር በማየት ከሌሎች ማስረጃዎች ጋር በማገናዘብ እና በማመዛን የደረሰበት ድምዳሜ ላይ ማስረጃ ምዘና ስህተት ተፈጽሟል የሚያሰኝ ምክንያት አልተገኘም፡፡

ባጠቃላይ ክስ የቀረበበት መሬት ላይ የባለይዞታነት መብት ያለዉ ተጠሪ ወይስ አመልካች ነዉ? የሚለዉን ጭብጥ በመወሰን ረገድ ፍርድ ቤቱ የግራ ቀኙን የሰነድና የምስክሮችን ቃል በመመርመርና በማመዛዘን ተጠሪ በተሻለ ማስረጃ ማስረዳቱን አረጋግጦ ዉሳኔ የሰጠ መሆኑን መገንዘብ ተችሏል፡፡ስለሆነም ዉሳኔዉ የክርክሩን ጭብጥ በመለየት እና ማስረጃ የማቅረብና የማስረዳት ግዴታን፣የቀረበዉን ማስረጃ አግባብነትና ተቀባይነት በመለየት እና የማስረጃዉን ብቃት/ምዘና/ መርህን አስመልክቶ ቅቡልነት ያላቸዉን መርሆዎች ተከትሎ የተወሰነ ነዉ ከሚባል በስተቀር በኢፌዲሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 80/3/ሀ እና በፌዴራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀጽ 2/4/ ና 10 ድንጋጌዎች መሰረት ለሰበር ችሎቱ ከተሰጠዉ መሰረታዊ የህግ ስህተት የማረም ስልጣን አንጻር በዉሳኔዉ ሊታረም የሚገባ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነዉ የሚባልበት ምክንያት አላገኘንም፡፡በዚሁ አግባብ ተከታዩን ዉሳኔ ሰጥተናል፡፡

ዉሳኔ

1ኛ/በዚህ ጉዳይ የሶማሌ ክልል ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የስር ፍርድ ቤቶች የሰጡት ዉሳኔ የህግ ስህተት የለዉም በማለት በመ/ቁ/05-1-68/13 ላይ በ22/03/2013 ዓ.ም የሰጠዉ ዉሳኔ በፍ/ብ/ስ/ስ/ህግ ቁጥር 348/1/መሰረት ጸንቷል፡፡

2ኛ/በዚህ መዝገብ ላይ በ04/06/2013 ዓ.ም ተሰጥቶ የነበረዉ የእግድ ትእዛዝ ተነስቷል፡፡ይጻፍ፡፡

3ኛ/በዚህ ፍርድ ቤት ለተደረገዉ ክርክር ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸዉን ይቻሉ ብለናል፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ማ/አ

የሠ/መ/ቁጥር 225796

ጥቅምት 29 ቀን 2015 ዓ/ም

ዳኞች፡- ብርሃኑ አመነው

ተሾመ ሽፈራው

ሀብታሙ እርቅይሁን

ብርሃኑ መንግስቱ

ነፃነት ተገኝ

አመልካች፡- አቶ ይስሀቅ ጥጋቡ - ጠበቃ ጌታነው ሙንየ - ቀረቡ

ተጠሪዎች፡- 1. ወ/ሮ ሐመረ ጥዑመልሳን - ጠበቃ ምንይችል ተኮላ - ቀረቡ

2. አቶ አብርሃም ገለቱ - አልቀረቡም

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለዉ የፍርድ ዉሳኔ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የከተማ ቦታ የሊዝ መብት በሽያጭ የሚተላለፍበትን አግባብ የሚመለከት ነዉ፡፡ አመልካች በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በተጠሪዎች ላይ በመሰረቱት ክስ በአዲስ አበባ ከተማ ቦሌ ክፍለ ከተማ ወረዳ 10 ክልል ዉስጥ የሚገኝ የቤት ቁጥር አዲስ የካርታ ቁጥሩ ቦሌ10-1/100/3/7/30914 የሆነ ለቅይጥ አገልግሎት እንዲዉል በሊዝ ለ1ኛ ተጠሪ የተሰጣቸዉን 883 ካሬ ሜትር ቦታ በወኪላቸዉ 2ኛ ተጠሪ አማካኝነት በቀን 11/06/2013ዓ/ም በተደረገ ዉል በብር 4,500,000.00 አመልካች ገዝቻለሁ፡፡2ኛ ተጠሪ የሊዝ ክፍያ መፈጸም አልቻልኩም በማለታቸዉ አመልካች ግዥዉ የፈጸምኩበትን 50% ብር 2,250,000.00 ከፍያለሁ፡፡ቀሪዉን በሰነዶች ማረጋገጫና ምዝገባ ጽ/ቤት ቀርበን ሰነዶችን ስንረካከብ ለመክፈል ተስማምተናል፡፡በወቅቱ የሊዝ ይዞታዉ ለሰባት ዓመታት የሊዝ ክፍያ ስላልተከፈለበት ይዞታዉ ወደ መሬት ባንክ እና ማስተላለፍ ጽ/ቤት ገብቶ ስለነበር ዉሉን በሰነዶች ማረጋገጫና ምዝገባ ኤጅንሲ ቀርቦ ለመፈጸም አልተቻለም፡፡ይዞታዉን ከመሬት ባንክና ማስተላለፍ ጽ/ቤት ለማዉጣት አመልካች ብር 700,000.00 ለሊዝ ክፍያ በ1ኛ ተጠሪ ስም ለቦሌ ክፍለ ከተማ መሬት ባንክና ሊዝ ጽ/ቤት በዳሽን ባንክ በኩል ከፍያለሁ፡፡2ኛ ተጠሪ ከጽ/ቤቱ ደረሰኝ አስቆርጠዉ እንዲያመጡ ብጠይቃቸዉ ፈቃደኛ አልሆኑም፡፡እንዲሁም ብር 50,000.00 በ2ኛ ተጠሪ ስም ገቢ አድርጌያለሁ፡፡ በድምሩ ብር 3,000,000.00 ክፍያ ለተጠሪዎች ማስጠንቀቂያ ብሰጣቸዉም በሰነዶች ማረጋገጫና ምዝገባ ኤጀንሲ ቀርበዉ የሽያጭ ዉሉን ለመፈጸም ፈቃደኛ አልሆኑም፡፡ ስለሆነም በዉሉ የተመለከተዉን መቀጮ ብር 1,000,000.00 እንዲሁም በዉሉ መሰረት ባለመፈጸማቸዉ ለደረሰብኝ ጉዳት ካሳ ብር 250,000.00 ከፍለዉ የሊዝ መብት በሽያጭ የማስተላለፍ ዉሉን ተገደዉ እንዲፈጽሙ ይወሰንልኝ በማለት ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡

ተጠሪዎች ለክሱ በሰጡት መልስ 1ኛ ተጠሪ ዉሉን አላዉቅም፡፡የሊዝ መብቴን ለ3ኛ ወገን ለማስተላለፍ የሚያስችል ዉክልና አልሰጠሁም፡፡1ኛ ተጠሪ ከአመልካች ጋር የፈጸምኩት የሊዝ መብት ማስተላለፍ ዉል የለም፡፡አመልካች በሌላቸዉና ባልተፈጠረ መብት ላይ ተመርኩዘዉ ያለምንም ሕጋዊ መሰረት ያቀረቡት ክስ የሕግ መሰረት የሌለዉ በመሆኑ ተገድጄ የሊዝ መብቴን የማስተላልፍበት ምክንያት የለም፡፡የሊዝ መብት በማይንቀሳቀስ ይዞታ መነሻነት የሚገኝ በመሆኑ ይህንን መብት ለማስተላለፍ የሚደረግ ዉል በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 1723 እና 2878 መሰረት መደረግ ሲገባዉ በዚህ አግባብ የተደረገ ዉል አልቀረበም፡፡የሊዝ መብት የሚተላለፈዉ በአዋጅ ቁጥር 721/2004 አንቀጽ 24/2 መሰረት አግባብ ባለዉ አካል ቁጥጥር ተደርጎበት ግልጽ የሽያጭ ስርዓት ተከትሎ የሚደረግ በመሆኑ 1ኛ ተጠሪም ሆንኩ የመንግስት አካል በማያዉቀዉ ሁኔታ ተዘጋጅቶ በቀረበ የሽያጭ ዉል 1ኛ ተጠሪ የሊዝ መብቴን የማጣበት ምክንያት የለም፡፡ስለሆነም ዉል የለም ተብሎ ክሱ ዉድቅ ሊሆን ይገባል፡፡የዉል ግንኙነት ስለሌለኝ 1ኛ ተጠሪ በክሱ የተጠቀሰዉን መቀጮ እና ኪሳራ የምከፍለበት ምክንያት የለም፡፡ አመልካች ብር 700,000.00 በ1ኛ ተጠሪ ስም አልከፈሉም፡፡ለምን ዓላማ እንደከፈሉም ማስረጃዉ አያሳይም፡፡ይህ ክፍያ ከሊዝ ክፍያዉ ጋርም ግንኙነት የለዉም፡፡በመሆኑም በዚህም ረገድ ያቀረቡት ጥያቄ ዉድቅ ሊሆን ይገባል፡፡2ኛ ተጠሪ ከአመልካች ጋር የሊዝ መብት ለማስተላለፍ በክሱ የተጠቀሰዉን ዉል አልተዋዋልኩም፡፡ዉሉ ላይ አልፈረምኩም፡፡በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 1723 መሰረት የተደረገ ዉል በማስረጃነት አልቀረበም፡፡በመካከላችን የዉል ግንኙነት በሌለበት መቀጮና ኪሳራ ለአመልካች የሚከፈልበት ምክንያት የለም፡፡ዉል ሳይኖር አመልካች የሊዝ ክፍያ ሊከፍሉ ስለማይችሉ ብር 700,000.00 ከፍያለሁ ያሉት ተቀባይነት የለዉም ተብሎ ክሱ ዉድቅ እንዲደረግ በመጠየቅ ተከራክረዋል፡፡

ፍርድ ቤቱም በመ/ቁጥር 131175 ላይ የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃዎችን መርምሮ በቀን 06/04/2014ዓ/ም በሰጠዉ ዉሳኔ 1ኛ ተጠሪ በክሱ ካርታ ቁጥሩ የተጠቀሰዉን ቤት እንዲሸጡ በቀን 13/11/2020ዓ/ም ለ2ኛ ተጠሪ የዉክልና ሥልጣን መስጠታቸዉ ተረጋግጧል፡፡ለክሱ መነሻ የሆነዉ በቀን 11/06/2013ዓ/ም የተደረገዉ ዉል የ1ኛ ተጠሪን የሊዝ መብት በሽያጭ ለማስተላለፍ የተደረገ ነዉ፡፡2ኛ ተጠሪ የዉክልና ሥልጣናቸዉን በመጠቀም የ1ኛ ተጠሪን የሊዝ መብት ለአመልካች በዉል ማስተላለፋቸዉ ተረጋግጧል፡፡አመልካች ቀሪዉን 50% ክፍያ ዉል ለማዋዋል ሥልጣን በተሰጠዉ አካል ፊት ቀርበዉ ዋናዉን የሽያጭ ዉል ሲዋዋሉ እና ቤቱን የሚመለከቱ ልዩ ልዩ ሰነዶችን ርክክብ ሲፈጽሙ እንደሆነ ተስማምተዋል፡፡በሰ/መ/ቁጥር 99124 ላይ በተሰጠዉ አስገዳጅ የሕግ ትርጉም መሰረት ግራ ቀኝ ዉል ሥልጣን ባለዉ አካል ፊት ቀርበዉ ለመዋዋል የገቡትን ግዴታ ተፈጻሚ ማድረግ ካልቻሉ የተዘጋጀዉ ስምምነት ረቂቅ እንጂ ከጅምሩ ዉል አይደለም በማለት በወሰነዉ መሰረት በግራ ቀኙ መካከል ያለዉ ስምምነት ረቂቅ በመሆኑ ተጠሪዎች ተገደዉ ሊፈጽሙ አይገባም፡፡ዉሉ ረቂቅ በመሆኑ በክሱ የተጠየቀዉን መቀጮና ኪሳራም ተጠሪዎች ሊከፍሉ አይገባም፡፡ነገር ግን አመልካች ለተጠሪዎች የከፈሉትን ብር 2,250,000 እና ለ2ኛ ተጠሪ ገቢ ያደረጉትን ብር 50,000.00 በድምሩ ብር

2,300,000.00 ተጠሪዎች ባልተነጣጠለ ኃላፊነት ለአመልካች ሊከፍሉ ይገባል፡፡አመልካች ለሊዝ ክፍያ ብር 700,000.00 ከፈልኩኝ ያሉትን ገንዘብ ለሊዝ ክፍያ ስለመክፈላቸዉ ያላስረዱ በመሆኑ ከሚመለከተዉ ሌላ አካል መጠየቅ ይችላሉ እንጂ ተጠሪዎችን መጠየቅ አይችሉም በማለት ወስኗል፡፡

አመልካች በዉሳኔዉ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 283217 ላይ ቢያቀርቡም ፍርድ ቤቱ በቀን 07/07/2014ዓ/ም በሰጠዉ ትእዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 337 መሰረት ሰርዞባቸዋል፡፡

አመልካች በቀን 21/08/2014 ዓ/ም የተጻፈ የሰበር አቤቱታ ያቀረበዉ ከላይ በተገለጸዉ መሰረት በተሰጠ ዉሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል በሚል ሲሆን የአቤቱታዉ ይዘት በአጭሩ፡- 2ኛ ተጠሪ በ1ኛ ተጠሪ በተሰጣቸዉ የዉክልና ሥልጣን በጽሁፍ በተደረገ የሽያጭ ዉል የሊዝ ይዞታ ለአመልካች አስተላልፈዋል፡፡ዉሉ የማይንቀሳቀስ ንብረት ሽያጭ ዉል ሳይሆን የሊዝ መብትን በሽያጭ የማስተላለፍ ዉል ነዉ፡፡የሊዝ መብት በሽያጭ ማስተላለፍ በይዞታዉ ላይ ያለዉን መብት በሌላ አካል መተካት እንጂ የማይንቀሳቀስ ንብረት ሽያጭ የሊዝ መብትን በሽያጭ የማስተላለፍ ዉል ደግሞ በከተማ መሬት ሊዝ አዋጅ ቁጥር 721/2004 አንቀጽ 24፣ደንብ ቁጥር 49/2004 አንቀጽ 38 እና 39 እንዲሁም መመሪያ ቁጥር 93/2014 አንቀጽ 7.4 ከመንግስት አካል ጋር ዉል በመዋዋል የሚገኝ መብት ነዉ፡፡ከዚህ ዉጭ ዉሉ በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 1723 መሰረት እንዲፈጸም የሚያስገድድ ድንጋጌ የለም፡፡የሊዝ መብት ለማስተላለፍ የሚደረግ ዉል በተመለከተ ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁጥር 36294 ላይ የተሰጠዉ አስገዳጅ ትርጉም ተፈጻሚ ሊሆን ይገባል፡፡የስር ፍርድ ቤት በሕግ ፊት የሚጸና ዉል አለ ወይስ የለም የሚለዉን ከዚህ አኳያ ሳይመረምር በግራ ቀኙ መካከል የጸና ዉል የለም ሲል የደረሰበት ድምዳሜ ስህተት ነዉ፡፡ለክርክሩ መነሻ የሆነዉ ዉል ሥልጣን ባለዉ አካል ሊደረግ አይችልም ስላልተባለና ይህንን ማድረግም ግዴታ ስላልሆነ ለዚህ ጉዳይ አግባብነት የሌለዉን በሰ/መ/ቁጥር 99124 ላይ የተሰጠዉን ዉሳኔ በመጥቀስ ዉሉ እንደ ረቂቅ ይቆጠራል ሲል የሰጠዉ ዉሳኔ የሕጉን መንፈስ የተከተለ አይደለም፡፡2ኛ ተጠሪ በሽያጭ ዉሉ መሰረት ገንዘቡን መቀበላቸዉን ስለአመኑ ዉሉ መኖሩን ማመናቸዉን ያሳያል፡፡በዚህ መልኩ ዉሉ መኖሩን እስከአመኑ ድረስ የዉሉን ፎርማሊቲ በመከራከሪያነት በማንሳት የሚያቀርቡት ክርክር በሰ/መ/ቁጥር 36887 ላይ ከተሰጠዉ አስገዳጅ የሕግ ትርጉም አንጻር ተቀባይነት የለዉም፡፡አመልካች በ1ኛ ተጠሪ ስም ለሊዝ ክፍያ ብር 700,000.00 መክፈሉን በምስክሮች ለማስረዳት የቆጠርኩትን ምስክሮች ሳይሰማ በዚህ ረገድ የጠየቅሁትን ዳኝነት ዉድቅ በማድረግ የሰጠዉ ዉሳኔ በሰ/መ/ቁጥር 43845 ላይ የተሰጠዉን የሕግ ትርጉም የሚቃረን ነዉ፡፡ እንዲሁም የስር ፍርድ ቤት ወለድ ተጠሪዎች ገንዘቡን ከተቀበሉበት ጊዜ ጀምሮ እንዲከፍሉ አለመወሰኑ እና ወጪና ኪሳራ አመልካች ለዳኝነት በከፈልኩት እንዲሁም ለጠበቃ አበል በከፈልኩት ልክ አለመወሰኑ ስህተት ስለሆነ ይታረምልኝ በማለት አቤታቸዉን አቅርበዋል፡፡

የሰበር አጣሪ ችሎት አቤቱታውን መርምሮ 2ኛ ተጠሪ ከ1ኛ ተጠሪ በተሰጣቸዉ ዉክልና ከአመልካች ጋር በቀን 11/06/2013ዓ/ም የሊዝ ይዞታ መብትን በሽያጭ ለማስተላለፍ ዉል ተዋዉለዉ ብር 2,300,000.00 ከአመልካች የተቀበሉ መሆኑ በተገለጸበት ዉሉ ረቂቅና ያልተመዘገበ በመሆኑ ተጠሪዎች ይዞታዉን ለማስተላለፍ በዉል ሊገደዱ አይገባም በሚል የተወሰነበትን አግባብ በሰ/መ/ቁጥር 36887 ላይ ከተሰጠዉ የሕግ ትርጉም፣ከፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 1723/1 ከሊዝ አዋጅ ቁጥር 721/2004 አንቀጽ 24 እንዲሁም አዋጁን ተከትለዉ ከወጡ ደንብና መመሪያ አንጻር ተጠሪዎች ባሉበት እንዲመረመር ትእዛዝ በመስጠቱ ተጠሪዎች በቀን 09/10/2014ዓ/ም በተናጠል የተጻፈ መልስ አዘጋጅተዉ አቅርበዋል፡፡ የመልሳቸዉም ይዘት በአጭሩ፡- አመልካች በሰር ፍርድ ቤት የተሰጠዉን ዉሳኔ በማስፈጸም የተፈረደላቸዉን ገንዘብ ከተቀበሉ በኋላ ያቀረቡት የሰበር አቤቱታ ተቀባይነት ሊኖረዉ አይገባም፡፡አመልካች ዉል ነዉ በሚል ያቀረቡትን ሰነድ ተጠሪዎች የማናዉቀዉ እና የሊዝ መብት ለማስተላለፍ የተደረገ ዉል እንደሌለ በመግለጽ ተከራክረናል፡፡የሊዝ መብት ማስተላለፍ የሚቻለዉ በአዋጅ ቁጥር 721/2004 አንቀጽ 24፣ በደንብ ቁጥር 49/2004 እና በመመሪያ ቁጥር 11/2004 መሰረት ከሚመለከተዉ የመንግስት ተቋም ተገቢዉ ፈቃድ ሲገኝ ብቻ ነዉ፡፡ይህም የሚያሳየዉ በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 1723 ስር ከተደነገገዉ ፎርማሊቲ በተጨማሪ ተጨማሪ ቅድመ ሁኔታ መሟላት እንዳለበት ነዉ፡፡ዉል የለም እንጂ አለ ቢባል እንኳ ዉሉ የተደረገዉ የሊዝ መብትን ለማስተላለፍ በሚቻልበት ደረጃ ግንባታ ሳይከናወን ነዉ፡፡ስለሆነም የዉሉ ጉዳይ ሕጋዊ ካለመሆኑም በተጨማሪ ሊፈጸም የማይችል ነዉ፡፡ይህም ዉሉን ፈራሽ የሚያደርግ ነዉ፡፡የሊዝ መብትን ለማስተላለፍ የሚደረግ ዉል በማይንቀሳቀስ ይዞታ ላይ የሚደረግ ዉል እንደመሆኑ መጠን ከቤት ሽያጭ ዉል የተለየ አይደለም፡፡ስለሆነም ዉሉ በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 1723/1 መሰረት ሊደረግ ይገባል፡፡2ኛ ተጠሪ ከአመልካች ገንዘብ መቀበላቸዉ ብቻዉን የሊዝ መብትን ለማስተላለፍ ዉል ፈጽመዋል የሚያስብል አይደለም፡፡በሰ/መ/ቁጥር 36887 ላይ የተሰጠዉ አስገዳጅ የሕግ ትርጉም በትክክል በተደረገና ስለመደረጉም በተከራካሪ ወገኖች በታመነ ዉል ላይ ብቻ እንጂ ከጅምሩ ዉል የለም ተብሎ ክርክር በቀረበበት ጉዳይ ላይ ተፈጻሚነት የለዉም፡፡ዉሉ በተዋዋይ ወገኖች ያልታመነና በሰ/መ/ቁጥር 99124 ላይ በተሰጠዉ አስገዳጅ የሕግ ትርጉም መሰረት ሕጋዊ ዉጤት የሌለዉ በመሆኑ ምስክሮች አለመስማት በዉጤት ደረጃ የሚያመጣዉ ለዉጥ የለም፡፡እንዲሁም የስር ፍርድ ቤት ወለድ፣ ወጪና ኪሳራ ተጠሪዎች በአንድነትና በነጠላ ኃላፊነት እንድንከፍል መወሰኑ አመልካችን የሚጠቅም ከመሆኑም በተጨማሪ አመልካች አለአግባብ አጋነዉ በመጠየቅ ያወጡትን ወጪ ቀንሶ በመወሰኑ የተፈጸመ ስህተት የለም በማለት ተከራክረዋል፡፡ አመልካችም የመልስ መልሳቸዉን በማቅረብ ተከራክረዋል፡፡

ከዚህ በላይ አጠር ባለ መልኩ የተመለከተዉ የግራ ቀኙ ክርክርና በስር ፍርድ ቤት እና በይግባኝ ሰሚዉ ችሎት የተሰጡ ዉሳኔዎች ይዘት ሲሆን እኛም በግራ ቀኙ መካከል ሕጋዊ ዉጤት በሚኖረዉ አኳኋን

የተደረገ ውል የለም በሚል በተሰጠዉ ዉሳኔ የተፈጸመ መሰረታዊ የሕግ ስህተት መኖር አለመኖሩን አግባብነት ካለዉ ሕግ ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለዉ መርምረናል፡፡

እንደመረመርነዉም የክርክሩ ሥረ ነገር 2ኛ ተጠሪ በ1ኛ ተጠሪ በተሰጣቸዉ የዉክልና ሥልጣን በ1ኛ ተጠሪ ስም ተመዝግቦ የሚገኝ የከተማ ቦታ የሊዝ መብት ለአመልካች በሽያጭ ለማስተላለፍ ተደረገ የተባለዉን የሽያጭ ዉል መነሻ ያደረገ ነዉ፡፡ ተጠሪ በክሳቸዉ ላይ የሽያጭ ዉሉ በቀን 11/06/2013ዓ/ም እንደተደረገ እና የቤቱም ሽያጭ ዋጋ ብር 4,500,000.00 ሆኖ በዉሉ ደረሰኝነት የዋጋዉን 50% ብር 2,250,000.00 መክፈላቸዉን፣ብር 50,000.00 ለ2ኛ ተጠሪ ገቢ ማድረጋቸዉን እንዲሁም ብር 700,000.00 ለሊዝ ክፍያ እንዲዉል ለቦሌ ክፍለ ከተማ መሬት ባንክና ሊዝ ጽ/ቤት በ1ኛ ተጠሪ ስም በዳሸን ባንክ በኩል ገቢ ቢያደርጉም ተጠሪዎች በዉሉ መሰረት ሰነዶች ማረጋገጫና ምዝገባ ኤጀንሲ ዘንድ በመቅረብ ዉሉን ለመዋዋልና ተገቢዉን ሰነድ ለማስረከብ ፈቃደኛ እንዳልሆኑ በመግለጽ ተገደዉ እንዲፈጽሙና በዉሉ የተመለከተዉንና ክስ የቀረበበትን መቀጮና ኪሳራ እንዲከፍሉ እንዲወሰንላቸዉ ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡ ተጠሪዎች ከላይ በተመለከተዉ አግባብ አመልካች በክሱ የጠቀሱትን ዉል እንዳልተዋዋሉ በመግለጽ ክደዉ ከመከራከራቸዉም በተጨማሪ አመልካች በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 1723/1 መሰረት የተደረገ የሽያጭ ዉል በማስረጃት ያላቀረቡ መሆኑን ጭምር በመጥቀስ ተገደዉ እንዲፈጽሙ የሚያደርግ የጸና ዉል የለም ሲሉ ተከራክረዋል፡፡

በመርህ ደረጃ ተዋዋይ ወገኖች በፈለጉት አይነት ፎርም እና ሁኔታ ዉል ቢዋዋሉ ዉላቸዉ የሕግ ደረጃ ተሰጥቶት የሚያስገድዳቸዉ ይሆናል፡፡ ሕግ በልዩ ሁኔታ አንድ ዉል መደረግ ስላለበት የአጻጻፍ ስርዓትና (ፎርምና) ምዝገባ በተመለከተ የደነገገዉ ካለ ይሄዉ የአጻጻፍ ስርአት(ፎርም) ተፈጻሚ መሆን ይኖርበታል፡፡ የአንድን ዉል ጉዳይ መሰረት በማድረግ ዉሉ ልዩ የአጻጻፍ ሥርዓት ተከትሎ እንዲደረግ በሕግ የተደነገገ እንደሆነ ተዋዋይ ወገኖች ዉላቸዉን በሕግ በተወሰነዉ ፎርም መሰረት የማድረግ ግዴታ እንዳለባቸዉ እና ይህን ካላደረጉ ዉሉ ሕጋዊ ዉጤት እንደማያስከትል በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 1678፣1719 እና ተከታዮቹ ድንጋጌዎች ላይ የተመለከተዉ ያሳያል፡፡ልዩ የአጻጻፍ ሥርዓትን ተከትለዉ እንዲደረጉ በሕግ ከተለዩት የዉል ጉዳዮች ዉስጥ አንዱ የማይንቀሳቀስ ንብረትን ባለቤትነት ለማስተላለፍ የሚደረግ ዉል ነዉ፡፡በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 1130 ስር እንደተደነገገዉ የማይንቀሳቀሱ ንብረቶች የሚባሉት መሬትና ቤት ናቸዉ፡፡ በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 1723/1 መሰረት የማይንቀሳሰቀስ ንብረት ባለቤትነትን በሽያጭ ለማስተላለፍ የሚደረግ የሽያጭ ዉል በጽሁፍ ሆኖ ዉል ለማዋዋል በሕግ ሥልጣን በተሰጠዉ አካል ፊት መደረግና መረጋገጥ (መመዝገብ/ authentication) እንዳለበት ተደንግጓል፡፡ ይህንን አጻጻፍ ተከትሎ ያልተደረገ የቤት ሽያጭ ዉል እንደ ረቂቅ እንደሚቆጠርና ሕጋዊ ዉጤት እንደማያስከትል ከፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 1720/1 እና 1723/1 ጣምራ ንባብ መገንዘብ ይቻላል፡፡የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁጥር 21448 ላይ (በቀጽ 4 ላይ እንደታተመዉ) የሰጠዉ አስገዳጅ የሕግ ትርጉምም ይህንኑ የሚያሳይ ነዉ፡፡

በሌላ በኩል የማይንቀሳቀስ ንብረት ሽያጭ ውል መደረጉን ግራ ቀኙ የተማመኑ እንደሆነ ወይም ተዋዋዮች የሽያጭ ውል በመካከላቸዉ መኖሩን ያልተካካዱ እንደሆነ ዉሉ በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 1723/1 ስር በተደነገገዉ መሰረት በሕግ ውል ለማዋዋል ሥልጣን በተሰጠዉ አካል ፊት ተደርጎ ያልተረጋገጠ ቢሆንም እንኳን ዉሉ ሕጋዊ ዉጤት እንደሚኖረዉ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁጥር 36887 ላይ (ቅጽ 13 ላይ እንደታተመዉ) እና በሌለች መዛግብት ላይ አስገዳጅ የሕግ ትርጉም ሰጥቷል፡፡

አመልካች ለክርክሩ መነሻ የሆነዉ የሽያጭ ውል የተደረገዉ የከተማ ቦታ የሊዝ መብት ለማስተላለፍ በመሆኑ ዉሉ መደረግ ያለበት በሊዝ አዋጅ ቁጥር 721/2004 አንቀጽ 24 መሰረት በመሆኑ በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 1723/1 ስር የተደነገገዉ የአጻጻፍ ሥርዓት ተፈጻሚ ሊሆን አይገባም በማለት የተከራከሩ ሲሆን ተጠሪዎች ደግሞ የሊዝ መብትን ለማስተላለፍ የሚደረግ ዉል የማይንቀሳቀስ ንብረት በሽያጭ ከማስተላለፍ የተለየ ባለመሆኑ በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 1723/1 ስር የተደነገገዉን የአጻጻፍ ሥርዓት ተከትሎ መደረግ ብቻ ሳይሆን በአዋጅ ቁጥር 721/2004 አንቀጽ 24 ስር በተደነገገዉ መሰረት በሚመለከተዉ የመንግስት አካል ሊፈቀድ ይገባል በማለት ተከራክረዋል፡፡በአዋጅ ቁጥር 721/2004 አንቀጽ 18 እና 19 ስር እንደተደነገገዉ በሕጉ በተደነገገዉ አግባብ ሊራዘም የሚችል መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ በሊዝ የሚገኝ የከተማ ቦታ የመጠቀም መብት ጸንቶ የሚቆይበት ዘመን እንደ ቦታዉ አገልግሎት አይነት ከ15 ዓመት እስከ 99 ዓመት ድረስ ነዉ፡፡ በዚህ አግባብ የተገኘዉን የሊዝ መብት በአዋጁ አንቀጽ 24/1 ስር በተደነገገዉ መሰረት ማንኛዉም የሊዝ ባለይዞታ መብቱን ለማስተላለፍ ወይም በከፊለዉ የሊዝ ክፍያ መጠን በዋስትና ለማስያዝ ወይም በካፒታል አስተዋጽኦ ለመጠቀም እንደሚችል ተደንግጓል፡፡እንዲሁም ማንኛዉም የሊዝ ባለይዞታ ከዉርስ በስተቀር ግንባታ ከመጀመሩ በፊት ወይም የግንባታዉን ግማሽ ከማጠናቀቁ በፊት የሊዝ መብቱን ማስተላለፍ የሚችለዉ አግባብ ባለዉ አካል ቁጥጥር ተደርጎበት ግልጽ የሽያጭ ሥርዓትን በመከተል *(...shall be required to follow transparent procedures of sale to be supervised by the appropriate body.)* እንደሆነ በዚሁ አዋጅ አንቀጽ 24/2 ስር የተደነገገዉ ያሳያል፡፡በአዋጁ አንቀጽ 2/6 ስር በተመለከተዉ ትርጓሜ መሰረት አግባብ ያለዉ አካል ማለት የከተማ ቦታን ለማስተዳደርና ለማልማት ሥልጣን የተሰጠዉ የክልል ወይም የከተማ አስተዳደር አካል ነዉ፡፡ በሌላ አግባብ ስምምነት ካልተደረገ በስተቀር በመሬት የመጠቀም መብት...ሲተላለፍ በመሬቱ ላይ የተገነባዉ ሕንጻና ከሕንጻዉ ጋር የተያያዙ መገልገያዎች መብት አብሮ እንደሚተላለፍ...በአዋጁ አንቀጽ 24/6 ላይ ተመልክቷል፡፡

እንዲሁም የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ባወጣዉ የከተማ መሬት ሊዝ ደንብ ቁጥር 49/2004 ከአንቀጽ 38 እስከ 41 ስር ግንባታ ያልተጀመረበትን እና ግማሽ ግንባታ ያረፈበትን ቦታ የሊዝ መብት በሽያጭ ማስተላለፍ የሚቻልበት አግባብ በዝርዝር ተደንግጓል፡፡በሽያጭ የሚተላለፈዉ ግንባታ ያልተጀመረበት ቦታ ከሆነ የሊዝ መብት ሽያጩ ዋጋ የሚወሰነዉ አግባብ ባለዉ አካል እንደሆነና

ዋጋዉም ወቅታዊ የመሬት ሊዝ መብት መሸጫ ዋጋ እንደሚሆን፣ ባለመብቱ በዋጋዉ ካልተስማማ መሬቱ ለጨረታ እንደሚወጣና ለጨረታ እንዲወጣ ካልተስማም አግባብ ያለዉ አካል በአዋጁ አንቀጽ 24(3/ሀ) መሰረት ክፍያ በመፈጸም አግባብ ያለዉ አካል ክፍያ በመፈጸም ቦታዉን መልሶ እንደሚወስድ፣የሊዝ መብት የሽያጭ ዉል እና የስም ዝዉዉሩ የሚፈጸመዉ የሊዝ ክፍያ ለመፈጸም ገዥ ዉል ከተዋዋለ እና የሊዝ ቅድመ ክፍያ ከፈጸመ በኋላ እንደሆነ፤ግማሽ ግንባታ የተከናወነበት ሲሆን ደግሞ አግባብ ባለዉ አካል የመሬት ሊዝ መብት ዋጋ እና የግንባታ ዋጋ በሚል ተለይቶ ቀርቦ ባለመብቱ በዚህ አግባብ በቀረበዉ የመሬት ሊዝ መብት መሸጫ ዋጋ ሲስማማ እና የመሬት ሊዝ ዋጋዉን ገዥ አግባብ ላለዉ አካል ገቢ ሲያደርግ፣ የሊዝ ዉል መዋዋል ሲቻል እና የሊዝ ቅድመ ክፍያ ሲፈጸም ብቻ እንደሆነ ተመልክቷል፤የሊዝ መብት የተሸጠበት ገንዘብ ለሻጭ የሚከፈለዉ አግባብ ባለዉ አካል በኩል እንደሆነም በዚሁ ደንብ ተደንግጓል።(የደንቡ አንቀጽ 38 እና 39 ይመለከቷል።)

ከዚህ በላይ በዝርዝር እንደተገለጸዉ በሊዝ አዋጅ እና ደንብ ላይ ከተደነገገዉ መረዳት የሚቻለዉ የሊዝ መብት በሽያጭ የሚተላለፈዉ ግንባታ ያልተጀመረ ቦታ ከሆነ በሕግ በተመለከተዉ አግባብ የሊዝ ዘመኑ ሊራዘም የሚችል መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ የሊዝ ዘመኑ እስከሚያልቅ ድረስ በቦታዉ የመጠቀም መብት እንደሆነ፤የሊዝ መብት የተላለፈዉ በቦታዉ ላይ ግማሽ ግንባታ ከተከናወነ በኋላ ከሆነም የሚተላለፈዉ ለሊዝ ዘመኑ በቦታዉ የመጠቀም መብት ብቻ ሳይሆን በቦታዉ ላይ ከተሰራዉ ሕንጻ ጭምር በመሆኑ አመልካች የሊዝ መብት ማስተላለፍ የማይንቀሳቀስ ንብረት እንደማስተላለፍ የሚቆጠር አይደለም በማለት ያቀረቡት ክርክር የሕግ መሰረት ያለዉ አይደለም።እንዲሁም በሊዝ የተገኘ የከተማ ቦታ ግንባታ ሳይከናወን እና ግማሽ ግንባታ ተከናዉኖ በባለመብቱ ለሶስተኛ ወገን ሲተላለፍ ከላይ በተገለጸዉ አግባብ ባለመብቱና ገዥ በሚያደርጉት የሽያጭ ዉል ብቻ ግብይቱ የሚፈጸም ሳይሆን ከዋጋዉ ጀምሮ የዉል አፈጻጸሙ ጭምር አግባብ ባለዉ የመንግስት አካል ቁጥጥር የሚመራ ነዉ። በዚህ ሥርዓት ለማሳካት የታቀደዉ የፖሊሲ ምክንያቶችም የከተማም ሆነ የገጠር መሬት ባለቤትነት የሕዝብና የመንግስት በመሆኑና ዉስን የተፈጥሮ ሀብት በመሆኑ በአግባቡ ጥቅም ላይ እንዲዉል ማድረግ፣ በመሬቱ ላይ እሴት ሳይጨመር አየር በአየር የሊዝ መብት በማስተላለፍ አለአግባብ መበልጸግ እንዳይኖርና የኢኮኖሚ አለመረጋጋት የሚያባብስ ምክንያት እንዳይሆን ለመከላከል፣ በማይገባ አኳኋን ዋጋ በገበያ ብቻ በመመራት እየተወሰነ የመሬት ተጠቃሚነትና ምርታማነት እንዳይቀንስ ለመከላከል እና ሌሎች ማኅበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ምክንያቶችን ታሳቢ ያደረገ እንደሆነ ይታመናል።

በተያዘዉ ጉዳይ አመልካች ተጠሪዎች የሊዝ መብት በሽያጭ የማስተላለፍ ዉሉን ተገደዉ እንዲፈጽሙ ይወሰንልኝ በማለት ለጠየቁት ዳኝነት መሰረት ያደረጉትን ዉል ተጠሪዎች አልተዋዋልንም በማለት በግልጽ ክደዉ ተከራክረዋል።የሊዝ መብት ማስተላለፍ ማለት ደግሞ ከላይ እንደተገለጸዉ መብቱ የተመሰረተበትን የከተማ ቦታና በእላዩ ላይ የሰፈረ ሕንጻ(ግንባታ) ጭምር የሚመለከት ነዉ። ስለሆነም የሊዝ መብቱ የሚሸጥበትን ዋጋ ከመወሰን፣ መብቱን ለሦስተኛ ወገን ከማስተላለፍ አኳያ ሊሟሉ

የሚገባቸዉ ቅድመ ሁኔታዎች መሟላታቸዉን በማረጋገጥ የሊዝ ዉል ከገዥ ጋር ከመዋዋልና ስመ ሀብቱን ወደገዥ ከማስተላለፍ አንጻር የሚመለከተዉ የመንግስት አካል የሚኖረዉ ተሳትፎ እንደተጠበቀ ሆኖ በባለመብቱና በገዥ መካከል የሚደረገዉ ዉል ግልጽ የሽያጭ ሥርዓትን በመከተል *(...shall be required to follow transparent procedures of sale...)* መደረግ ይኖርበታል፡፡ ይህም ግልጽ የሽያጭ ሥርዓት በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 1723/1 ስር የማይንቀሳቀስ ንብረት በሽያጭ ለማስተላለፍ የተደነገገዉ ነዉ፡፡በዚህ መሰረት የሊዝ መብት በሽያጭ ለማስተላለፍ የሚደረገዉ ዉል አግባብ ባለዉ አካል ቁጥጥር ተደርጎበት በጽሁፍ መሆንና በሕግ ዉል ለማዋዋል ሥልጣን በተሰጠዉ አካል ፊት ተረጋግጦ የተመዘገበ መሆን ይኖርበታል፡፡ የማይንቀሳቀስ ንብረት ሽያጭ መደረጉን እና የሽያጭ ዉሉን ይዘት አስመልክቶ ተክዶ ክርክር በቀረበ ጊዜ እንዲህ አይነት ክርክር ለማስረዳት ሊቀርብ የሚገባዉ ማስረጃ ዉል ለማማዋል ሥልጣን በተሰጠዉ አካል ፊት ተደርጎ መመዝገቡን ወይም መረጋገጡን (Authentication) የሚያሳይ ዉል ሊሆን ይገባል እንጂ በምስክር ወይም በሌላ ማስረጃ ማስረዳት አይቻልም፡፡

ሲጠቃለል በያዝነዉ ጉዳይ አመልካች ከተጠሪዎች ጋር ተዋዋልኩኝ ያሉትን ዉል ተጠሪዎች ክደዉ የተከራከሩ በመሆኑ አመልካች በሚመለከተዉ የመንግስት አካል ቁጥጥር ተደርጎበት በዉል አዋዋይ ፊት የተደረገ የሊዝ መብት ሽያጭ ዉል በማስረጃነት በማቅረብ በሕግ አግባብ የተደረገ ዉል መኖሩን ማስረዳት አልቻሉም፡፡በመሆኑም የስር ፍርድ ቤት በሕግ ፊት ዉጤት ያለዉ ዉል በግራ ቀኙ መካከል አልተደረገም በሚል ተጠሪዎች ከአመልካች የተቀበሉትን ገንዘብ ሊመልሱ ይገባል ሲል የሰጠዉ ዉሳኔ ከዉጤት አንጻር ሲታይ በዚህ ችሎት ሊታረም የሚችል ስህተት የተፈጸመበት አይደለም፡፡እንዲሁም መቀጮና ወለድ በተጨማሪም ለሊዝ ተከፈለ የተባለዉ ብር 700,000.00 በሕግ አግባብ የተደረገ ዉል ሕጋዊ ዉጤት በመሆኑ በግራ ቀኙ መካከል ሕጋዊ ዉጤት ያለዉ ዉል የለም የሚል ድምዳሜ ላይ ተደርሶ ዉድቅ መደረጉ እና ተጠሪዎች የተቀበሉትን ብር 2,300,000.00 እና ከዚህ ጋር በተያያዘ ክሱ ያስከተለዉ ወጪ እንዲከፍሉ በመወሰኑ የተፈጸመ ስህተት የለም ብለናል፡፡

ዉ ሳ ኔ

1. የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 131175 ላይ በቀን 06/04/2014 ዓ/ም የሰጠዉ ዉሳኔ እና የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 283217 በቀን 07/07/2014 ዓ/ም የሠጠዉ ትእዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 348/1 መሰረት ጸንተዋል፡፡

2. በዚህ ችሎት ለወጣ ወጭና ኪሣራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

ት ዕ ዛ ዝ

1. የውሳኔው ግልባጭ ለግራ ቀኙ ይሰጣቸዉ፤ለሥር ፍርድ ቤቶችም ይተላለፍ፡፡

2. የፍርድ አፈጻጸም እንዲታገድ የተሰጠው ትእዛዝ ተነስቷል፡፡ ይጻፍ፡፡

3. መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሰ/ጥ

የሠ/መ/ቁጥር 238091

ግንቦት 30 ቀን 2016 ዓ/ም

ዳኞች፡- ብርሃኑ አመነዉ

በዕዉቀት በላይ

ቀነዓ ቂጣታ

ብርሃኑ መንግሥቱ

ማርታ ተካ

አመልካች - አቶ ካህሱ ወ/ትንሳይ - ቀረቡ

ተጠሪዎች - 1. በኮልፌ ቀራንዮ ክፍለ ከተማ የመሬት ልማት የመሬት ባንክ እና ማስተላለፍ ጽ/ቤት

2. በኮልፌ ቀራንዮ ክፍለ ከተማ ወረዳ 07 አስተዳደር ጽ/ቤት

3. አቶ ጀማል መሐመድ

4. አቶ ተማም ኢብራሂም } ጠበቃ ቦሬሳ በየነ - ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ከዚህ የሚከተለዉ የፍርድ ዉሳኔ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ አመልካች ክስ በተመሠረተበት የመሬት ይዞታ ላይ መብትና ጥቅም የላቸዉም ተብሎ ክሳቸዉ ዉድቅ በመደረጉ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል በሚል የቀረበ የሰበር አቤቱታ ተከትሎ የቀረበ ክርክር የሚመለከት ነዉ፡፡ አመልካች በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በተጠሪዎች ላይ የመሠረቱት ክስ ይዘት በአጭሩ - አመልካች በኮልፌ ቀራንዮ ክፍለ ከተማ ወረዳ 07 የቤት ቁጥር አዲስ በሆነውና አዋሳኙ በክሱ በተጠቀሰዉ 500 ካሬ ሜትር ላይ ያረፈ ይዞታዉ ገዝቼ ከ1986 ዓ.ም ጀምሮ በእጄ አድርጌ በእውነት እያዘዝኩበት ለመኖሪያነት ከዛም የንግድ ፍቃድ አውጥቼ በብሎኬት ማምረቻነት ግብር እየገበርኩኝ ስገለገልበት የቆየሁት ይዞታ አለኝ፡፡በ2ኛ ተጠሪ ስር የሚገኘው የደንብ ማስከበር ጽ/ቤት ይዞታዬን ሕገ-ወጥ ነው በማለት ለማፍረስ በመንቀሳቀሱ ሁከት እንዲወገድልኝ ክስ መስርቼ ዕግድ ተሰጥቶበት ሳለ የፍርድ ቤት ዕግድ ተላልፈው ቤቶቼን አፍርሰው ሕገ-ወጥ የሆነ ግንባታ እየሰሩ ይገኛሉ፡፡ አስቀድሞ በሌላ መዝገብ ላይ ሁከት እንዲወገድልኝ ክስ መስርቼ ፍርድ ቤቱም ይዞታው የአመልካች መሆኑን፣ በመመሪያ ቁጥር 18/2006 መስተናገድ እንደሚገባኝ እና የሁከት ተግባሩ ሊወገድ

እንደሚገባ በመግለፅ ፍርድ ሰጥቶ ተጠሪም ይግባኝ ብሎ ውሳኔው ፀንቶበታል።ሆኖም የአመልካች ይዞታና ቤቶቹም በ1997 ዓ/ም የአየር ካር በኮኦርድኔት ቁጥር 464454 እና 995675 የሚታዩ፣ማናቸዉም ተግባራት እንዳይፈጸምበት በፍርድ ቤት የታገደ እና በተለያዩ ፍርድ ቤቶች ውሳኔ ያረፈበትን ይዞታ ሆኖ እያለ 2ኛ ተጠሪ ለ3ኛ እና 4ኛ ተጠሪዎች ማህደር አደራጅቶ በመላክ 1ኛ ተጠሪም ለ3ኛ እና 4ኛ ተጠሪዎች በአመልካች ይዞታ ላይ ካርታ መስጠቱ ሕገ-ወጥ ተግባር ነዉ። በመሆኑም ተጠሪዎች ክስ የቀረበበትን ይዞታ እንዲለቁ እና 1ኛ እና 2ኛ ተጠሪዎች አመልካች በይዞታው ላይ ለመገልገል አስፈላጊ የሆኑ ተግባራትን እና መስተንግዶ በመስጠት እንዲፈፅሙ እንዲወሰንልኝ በማለት ዳኝነት ጠይቀዋል።

1ኛ እና 2ኛ ተጠሪዎች በሰጡት መልስ አመልካች በወረራ በያዙት መሬት ላይ ክስ ለማቅረብ የሚያስችል መብት እና ጥቅም የላቸውም የሚል የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ በማስቀደም ስረ ነገሩን በተመለከተ በሰጡት መልስ - ለክርክሩ መነሻ የሆነው ይዞታ በ1997 እና በ2003 ዓ.ም በተነሳው የመስመር ካርታ ላይ የማይታይ በመሆኑ በመመሪያ ቁጥር 18/2006 አንቀጽ 5/1 መሰረት በሰነድ አልባ ይዞታነት የሚስተናገድ አይደለም።ይህንንም እስከመጨረሻ ክርክር ተደርጎበት ውሳኔ ሳይሰጥ እና ቤቱ የቴሌ ማኅበር የመኖሪያ ቤቶች ግንባታ ሆኖ ሳለ በ1997 የአየር ካርታ ላይ ይታያል ስለተባለ ብቻ የአመልካች ይዞታ ነው ለማለት አይቻልም። በተጨማሪም መሬቱ በአሁን ወቅት ምንም አይነት ግንባታ የሌለው የመንግስት ባዶ መሬት ነው።ይዞታው ግንባታ የሌለዉ ባዶ እና በአመልካች ያልተያዘ በመሆኑ አመልካች ግንባታ አለው የሚል ክርክር አላቀረቡም።በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ልደታ ምድብ 14ኛ ፍትሐ ብሄር ችሎት የጠየቁት ዳኝነት ሁከት ይወገድልኝ ሆኖ ሳለ እንደባለይዞታነት ክርክር የአየር ካርታን መነሻ ተደርጎ የተሰጠው ውሳኔ በምንም መልኩ መብት የማይፈጥር መሆኑን ሰበር አስገዳጅ ትርጉም ሰጥቶበታል። 3ኛ እና 4ኛ ተጠሪዎች አርሶ አደር መሆናቸው በኮልፌ ቀራንዮ ክፍለ ከተማ ወረዳ 07 ተረጋግጦ ለ1ኛ ተጠሪ የተላከ በመሆኑ ከተላኩ ማስረጃዎች አንፃር ካርታ ተዘጋጅቶ እንዲሰጣቸው ተደርጓል። በመሆኑም ከመመሪያ ውጭ የሆነ ነገር ያልሰራን ስለሆነ እና የተላለፍነውም ምንም አይነት ዕግድ ባለመኖሩ ልንጠየቅ አይገባም።ይዞታው በአዋጅ ቁጥር 64/2011 መሰረት በኮድ 411 መሬት ባንክ ገብቶ የሚጠበቅ ይዞታ መሆኑ ተረጋግጦ ለባለመብቶቹ ካርታ ወጥቶበታል።በመሆኑም አመልካች በይዞታው ላይ ያላቸው መብት ከምን የመነጨ እንደሆነ ያላስረዱ በመሆኑ ክሱ ውድቅ ይደረግልን ሲሉ ተከራክረዋል።

3ኛ እና 4ኛ ተጠሪዎችም አመልካች በክሱ በተጠቀሰዉ ይዞታ ላይ የይዞታ ባለቤትነት ማረጋገጫ ማስረጃ ያላቀረቡ በመሆኑ ምንም አይነት መብትም ሆነ ጥቅም የላቸውም የሚል የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ በማስቀደም ባቀረቡት መልስ - አርሶ አደር እና የአርሶ አደር ልጅ በመሆናችን በኮልፌ ቀራንዮ ክፍለ ከተማ ወረዳ 07 አርሶ አደር ኮሚቴ ተረጋግጦ ከመሬት ባንክ ወጥቶ በሕጋዊ ካርታ

ተመዝግቦ ይዞታው ተሰጥቶናል፡፡ይዞታውን በእጃችን በማድረግ የመንግስት ግብር ስንከፍልበት ቆይተናል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ በይዞታው ላይ ግንባታ ለመፈፀም የግንባታ ፍቃድ አግኝተን ተገቢውን ሕጋዊ አካሄድ በመከተል ይዞታውን ስንገለገልበት ቆይተናል፡፡ይህ ይዞታ ከጥንት ጀምሮ በቤተሰብ ጭምር ስንጠቀምበት የነበረ ይዞታ እንጂ አመልካች እንደሚሉት በአመልካች ቁጥጥር ስር የነበረ ይዞታ አልነበረም፡፡አመልካች ከዚህ ቀደም በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ልደታ ምድብ 14ኛ ችሎት በ2ኛ ተጠሪ ላይ የሁከት ይወገድ ክስ ያቀረቡ ሲሆን ጉዳዩ አሁን በፌዴራል ሰበር ሰሚ ችሎት የሚገኝ ነው፡፡እኛ የክስ ሂደቱ አካል ካለመሆናችንም በላይ ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 27506 በሰጠው አስገዳጅ የሕግ ትርጉም የሁከት ይወገድልኝ ክስ የሚያዘው ጭብጥ ሁከት ተፈጥሯል አልተፈጠረም እንጂ ባለቤትነትን የማያጎናጽፍ እንደሆነ በግልፅ ተቀምጧል፡፡ስለሆነም በአመልካች እና በ2ኛ ተጠሪ መካከል እየተካሄደ ያለው የሁከት ክስ ላይ የሚሰጠው ማንኛውም አይነት ውሳኔ ከዚህ ክስ ጋር ምንም አይነት ግንኙነት የለውም ተብሎ ክሱ ውድቅ ይደረግልን በማለት ተከራክረዋል፡፡

ፍርድ ቤቱም አስቀድሞ የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያውን በብይን ውድቅ ካደረገ በኋላ ዋናውን ጉዳይ በተመለከተ በሰጠዉ ዉሳኔ - አመልካች ይዞታውን ከ1986 ዓ.ም ጀምሮ የያዙት መሆኑን እና ክስ በሚሰማበት ጊዜ ይዞታውን በአካባቢው ከሚገኙ አርሶ አደሮች መግዛታቸውን ከመግለፅ ውጪ ያቀረቡት የሰነድ ማስረጃ የለም፡፡ያቀረቧቸውም ማስረጃዎች አመልካች የቦታው ባለቤት መሆናቸውን የሚያረጋግጡ አይደሉም፡፡የማይንቀሳቀስ ንብረት ባለቤትነት የሰነድ ማስረጃ ከሌለ እንደ አግባብነቱ በሰው ማስረጃ ሊጣራ ይችላል፡፡ይህ የሚሆነው የንብረቱ ባለቤት ነኝ የሚለው አካል ንብረቱን ሕጉ እውቅና በሰጣቸው መንገድ ያገኘ መሆኑን ሲያረጋግጥ ነው፡፡አመልካች ይዞታውን ከአርሶ አደሮች የገዙ መሆኑን በቃል ክርክር ጊዜ ከመግለፅ ውጪ በክሳቸው የገለፁት ነገር የለም፡፡አመልካች ከክሳቸዉ ጋር አያይዘዉ ያቀረቧቸዉ ማስረጃዎች የአከራካሪዉ ይዞታ ባለቤት ለመሆናቸዉ የሚያስረዱ ማስረጃዎች አይደሉም፡፡ ይዞታዉ በ1997 ዓ/ም አየር ካርታ ላይ በማለት የቀረበዉ ማስረጃ በተመለከተ በ1997 ዓ/ም ኤር ካርታ በሚነሳበት ወቅት ይዞታዉ ያለ መሆኑን ከመግለጽ ዉጭ ይዞታዉ የአመልካች መሆኑን የሚያረጋግጥ አይደለም፡፡ እንዲሁም የወረዳ 7 አስተዳደር ጽ/ቤት የተጻፈ በማለት አመልካች ያቀረቡት ማስረጃ በይዞታዉ ላይ አመልካች ብሎኬት ማምረቻዉ እንዳላቸዉ መግለጽ ይዞታዉ ለአመልካች የግል ሀብታቸዉ ስለመሆኑ የሚያስረዳ ማስረጃ አይደለም፡፡ በተጨማሪም አመልካች በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 279873 ላይ ሁከት ይወገድልኝ የሚል ክስ መስርተዉ የተሰጠዉ ዉሳኔ በሰ/መ/ቁጥር 27506 ላይ በተሰጠዉ የሕግ ትርጉም መሰረት ባለቤትነትን በተመለከተ የተሰጠ ዉሳኔ እንኳን ቢሆን ተቀባይነት ስለማይኖረዉ ይህ ዉሳኔ በይዞታዉ ላይ የባለቤትነት መብት እንደሚሰጣቸዉ በመግለጽ ያቀረቡት ክርክር ተቀባይነት የለዉም፡፡ አመልካች ይዞታዉን ከአርሶ አደሮች በግዥ መግዛታቸዉን ከመግለጽ ዉጪ በውርስ፣ በስጦታ፣በምሪት እና በመሳሰሉት ሕጋዊ ኩነቶች ማግኘታቸውን በክሳቸው ያልገለፁ በመሆኑ ምስክር መስማት አስፈላጊ አይደለም፡፡ስለሆነም አመልካች

ለክርክር መነሻ በሆነው ይዞታ ላይ መብት እና ጥቅም ያላቸው መሆኑን የማስረዳት ሸክም ስላልተወጡ ተጠሪዎች የመከላከያ ግዴታ ዉስጥ የሚገቡ ባለመሆኑ ስለተጠሪዎች መተንተን ተገቢ አይደለም በማለት የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 33/2ን በመጥቀስ ክሱን ውድቅ በማድረግ ወስኗል፡፡

አመልካች በዚህ ዉሳኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርበዉ ፍርድ ቤቱም ግራ ቀኙን አከራክሮ በሰጠዉ ዉሳኔ ለክርክሩ መነሻ የሆነዉ የመሬት ይዞታ አመልካች ሕጉ እዉቅና በሰጠዉ መንገድ ይዞታዉን ማግኘታቸዉን ያላስረዱ ሲሆን በአንጻሩ ለ3ኛ እና 4ኛ ተጠሪዎች አርሶ አደርና የአርሶ አደር ልጅ መሆናቸዉ ተረጋግጦ ከመሬት ባንክ ወጥቶ አከራካሪዉ መሬት እንደተሰጣቸዉ ከቀረበዉ ማስረጃ ተረጋግጧል በማለት የስር ፍርድ ቤትን ዉሳኔ አፅንቷል፡፡

አመልካች በቀን 28/03/2015 ዓ/ም የተጻፈ የሰበር አቤቱታ ያቀረቡትም ከላይ በተሰጠዉ ዉሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል በሚል ሲሆን የአቤቱታቸዉ ይዘት በአጭሩ፡- የሥር ፍርድ ቤት አመልካች ክሱን የማቅረብ መብት እና ጥቅም እንዳላቸው ድምዳሜ ላይ በመድረስ መቃወሚያውን ውድቅ በማድረግ ብይን የሰጠ ቢሆንም ለጉዳዩ አወሳሰን አግባብነት ያለው ጭብጥ ሳይመሰረት፣ ክርክሩን በአግባቡ ሳይመራ፣ አስቀድሞ ብይን ዉድቅ ያደረገዉን የክርክር ነጥብ መሰረት በማድረግ አመልካች መብት የላቸዉም በማለት ዉሳኔ ሰጥቷል፡፡ ጉዳዩን አልመረመረም፡፡ ይህ ደግሞ በፍ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 241፣247 እና 248 የተደነገገዉን እና በዚህም ረገድ በሰ/መ/ቁጥር 47252 እና 37391 የሰጠዉን አስገዳጅ የሕግ ትርጉም የሚቃረን ነዉ፡፡እንዲሁም በተከራካሪ ወገኖች የተቆጠሩ አግባብነት እና ተቀባይነት ያላቸው ማስረጃዎች በአግባቡ በመስማት እና ከነሙሉ ይዘታቸው በመመዘን የክርክሩን ውጤት መወሰን ሲገባዉ የአመልካችን ምስክሮች በመስማት የማስረዳት ግዴታዬን በአግባቡ እንዲወጣ ሳያደርጉና ፍሬ ጉዳይ ሳያጣሩ የሰጡት ውሣኔ የአመልካች የመሰማት መብትን የነፈገ በመሆኑ በሰመ/ቁጥር 37105፣ 36848፣ 38683፣63014፣95026 እና በሌሎች መዛግብት ላይ የተሰጠዉን የሕግ ትርጉም የሚቃረን ነዉ፡፡በተጨማሪም በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 1195 እና 1196 እንደተደነገገው የይዞታ ማረጋገጫ ወረቀት የባለይዞታነት ግምት መስጫ ቢሆንም ይህ ግምት ግን ሊስተባበል የሚችል ከመሆኑም በተጨማሪ የማይንቀሳቀስ ንብረት ባለሀብትነት ካርታ በማቅረብ ብቻ የሚረጋገጥ ስላለመሆኑ በሰ/መ/ቁ 36320 ላይ አስገዳጅ የሕግ ትርጉም ሰጥቶበታል፡፡ 3ኛ እና 4ኛ ተጠሪዎች ካርታ እንደተሰራላቸው የተከራከሩ ቢሆንም ካርታዎቹ መምከናቸው አለመካዳቸውን እና በመጀመሪያ ደረጃ እና በከፍተኛ ፍርድ ቤቶች መረጋገጡን በተመለከተ በዝምታ መታለፉ ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት በተሰረዘ የባለሀብትነት ምስክር ወረቀት የሚገኝ የባለሀብትነት መብት ስላለመኖሩ በሰ/መ/ቁጥር 17712 እንዲሁም የማይንቀሳቀስ ንብረት ጋር በተያያዘ ሕጋዊ ባልሆነ መንገድ ስመ ሃብት ይዞ መገኘት የንብረቱ ባለቤት አድርጎ የማያስቆጥር ስለመሆኑ በሰ/መ/ቁጥር 47139 የሰጠውን

አስገዳጅ የሕግ ትርጉም የጣሰ በመሆኑ የሕግ መሰረት የለውም::አመልካች ከዚህ አንጻር ያቀረብኩትን ክርክር የሥር ፍርድ ቤት ከሚመለከተው አካል ሳያጣራ መወሰኑም ፍትህን ያጓደለ ነዉ፡፡

አመልካች በወቅቱ በነበረው አሰራር ከአርሶደሮች የግጦሽ መሬት በግዥ አግኝቼ ለረጅም ጊዜ በይዞታዬ ስር እንደሚገኝ እና አግባብ ባለው አካል ሳይፈቀድ የተያዙ ቦታዎችን ለማስተካከልና ለመከላከል በወጣ የአፈጻጸም መመሪያ ቁጥር 18/2006 መሠረት መስተንግዶ ማግኘት የሚገባኝ ሕጋዊ ይዞታ መሆኑ የሚያስረዱ ማስረጃዎችን አቅርቤያለሁ፡፡ ያቀረብኳቸዉ ማስረጃዎች ተጠሪዎች በማስረጃነት ካቀረቧቸው በ2013 እና ከዛ በኋላ ከተሰጡ ማስረጃዎች በተሻለ ይዞታው የአመልካች መሆናቸውን የሚያስረዱ ናቸው፡፡ይህ ሆኖ ሳለ ግን ከሚመለከታቸው አካላት መቅረብ የነበረባቸው እና አመልካች በራሳቸው ያቀረቧቸው ማስረጃዎች ተጠቃለው ሳይሰሙ እና ከተጠሪዎች ጋር ተነጻጽረው ሳይመዘኑ በንግድ ፈቃዱ እና የአየር ካርታው ላይ ብቻ በመመስረት የተሰጠዉ ዉሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስሕተት ነው፡፡እንደዚሁም በሁከት ይወገድልኝ ክርክሩ እና በተሰጠዉ ዉሳኔ ክርክር ያስነሳው ይዞታ የአመልካች እንደሆነ ፣ አመልካች ከ1986 ዓ.ም ጀምሮ ከ25 ዓመት በላይ ይዞታው ላይ ቤት ሰርቼ ስለመያዘ፣ በመመሪያ ቁጥር 18/2006 መሠረት መስተንግዶን ለማግኘት የሚያስችላቸው መሆኑ፤ ይዞታው በ1997 ዓ.ም የአየር ካርታ ላይ የሚታይ እና አመልካች ለረጅም ጊዜ ይዘውት ንግድ ፈቃድ አውጥተው የሚገለገሉበት ሕጋዊ ይዞታ መሆኑ የተረጋገጠ ሆኖ ሳለ ግን የሥር ፍርድ ቤቶች በሁከት ክርክሩ የተረጋገጡትን ፍሬ ነገሮች ለመጠቀም የሚከለክል ሕጋዊ ምክንያት ሳይኖር ውሳኔዉን የመሻር ውጤት ያለው የሚመስል ውሳኔ መሰጠቱ በሕገ-መንግሥቱ አንቀጽ 37 እና 40 የተደነገገዉን ፍትህ የማግኘትና የንብረት መብቶች የጣሰ ዉሳኔ በመሆኑ መሠረታዊ የሕግ ስሕተት የተፈጸመበት ነዉ ተብሎ ተሽሮ በአመልካች ክስ መሠረት እንዲወሰንልኝ አሊያም የስር ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ማስረጃዎች ሰምቶና መዝኖ እንዲወስን ለስር ፍርድ ቤት እንዲመለስ በማለት አመልክተዋል፡፡

የሰበር አጣሪ ችሎት አቤቱታዉን መርምሮ ለክርክር ምክንያት የሆነው ይዞታ በ1997 ዓ/ም አየር ካርታ ላይ የሚታይ ስለመሆኑ ከሚመለከተው አካል ተረጋግጦ ሪፖርት ቀርቦ ባለበት ሁኔታ ተጨማሪ ማጣራት ቢያስፈልግ እንኳን ማስረጃ ተሰምቶ ማጣራት ሲገባ ከሳሽ መብት እና ጥቅም መኖሩን ስላላስረዳ ክሱ ውድቅ ነው ተብሎ የተወሰነበትን አግባብ ከመመሪያ ቁጥር 18/2006፣ በሰ/መ/ቁጥር 37391፣37105 እና ተያያዥ የሕግ ትርጉሞች አንጻር ተጠሪዎች ባሉበት እንዲመረመር ትእዛዝ ተሰጥቶ ተጠሪዎች በሚከተለዉ መሠረት መልሳቸዉን ሠጥተዋል፡፡

1ኛ እና 2ኛ ተጠሪዎች በጋራ በቀን 25/05/2015 ዓ.ም ጽፈዉ ባቀረቡት መልስ - አመልካች ባቀረቡት ክስ ላይ የጠየቁት ዳኝነት 1ኛ እና 2ኛ ተጠዎች አመልካች በይዞታው ላይ ለመገልገል አስፈላጊውን ተግባርና መስተንግዶ እንዲሰጡኝ ይወሰንልኝ የሚል ነው፡፡ ከዚህ አንጻር የስር ፍርድ ቤት መዝገቡን የመረመረው አመልካች ይህን መብት ለመጠየቅ የሚያስችል መብት አላቸው ወይስ የላቸውም

የሚለውን ጭብጥ በመያዝ በፍሬ ጉዳይ ላይ ይህንን በማጣራት ውሳኔ የሰጠ በመሆኑ በዚህ ረገድ የቀረበው አቤቱታ አግባብነት የሌለው ነው፡፡በስር ፍርድ ቤት በተሰጠ ውሳኔ ይዞታው በ1997ዓ/ም ይታያል በሚል የተሰጠው ማስረጃ ሳይመዘንልኝ የሰጠው ውሳኔ ነው ያሉትን በተመለከተ በሰ/መ/ቁጥር 27506 በሰጠው አስገዳጅ የሕግ ትርጉም ሁከት ይወገድ በሚል የቀረበ ክስ ላይ ፍርድ ቤቱ ሊይዘው የሚገባው ጭብጥ ሁከት ተፈጥሯል አልተፈጠረም የሚል መሆን እንዳለበት አስገዳጅ የሕግ ትርጉም ሰጥቷል፡፡ ከዚህ ውጭ የሁከት ይወገድልኝ ክስ በምን አግባብ መብትን የሚፈጥር አይደለም፡፡ከዚህ አንጻር የስር ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሳኔ የሚነቀፍበት የሕግ አግባብ የለም፡፡አመልካች ይዞታውን ያገኙት ከአርሶ አደሮች ገዝተው መሆኑን በቃል ክርክር ጊዜ ከመግለጽ ውጭ በክሳቸው በምን መንገድ እንዳገኙት የገለጹት ነገር የለም፡፡ በሁከት ይወገድልኝ ክስ ጊዜ የሚቀርቡ ማስረጃዎች እና በመፋለም ጊዜ የሚቀርቡ ማስረጃዎች እና የሚያዙም ጭብጦች የተለያዩ ናችው፡፡ይህ በእንዲህ እንዳለ በሁከት ይወገድልኝ ወቅት የተሰጡ ማስረጃዎች ስህተት በመሆናቸው ለዚህ ለሰበር አቤቱታ ምክንያት በሆነው መዝገብ ላይ የቀረቡት ማስረጃዎች ታርመው የቀረቡ ናቸው፡፡የሥር ፍርድ ቤት ውሳኔ በሚሰጥበት ሰዓት ተጠሪዎች ያቀረቡትን ማስረጃ በተገቢው መንገድ መርምሯል፡፡መብት እና ጥቅም በፍሬ ጉዳይ ላይ የሚጣራ እንጂ በመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ላይ የሚጣራ ጉዳይ አይደለም፡፡ በዚህም ጉዳይ ላይ ሰበር አስገዳጅ የሕግ ትርጉም ሰጥቶበታል፡፡ የሁከት ይወገድልኝ ክስ ላይ በወቅቱ ቀርበው የነበሩ ማስረጃዎች ሀሰተኛ ስለነበሩ በወቅቱ ፍርድ ቤቱ እነዚህን ማስረጃዎች ምክንያት በማድረግ የወሰነው ውሳኔ ነው፡፡ ነገር ግን እነዚህ ማስረጃዎች በአሁን ሰዓት ጠርተው ወደ ፍርድ ቤቱ የቀረቡ በመሆኑ ነው ለክርክር ምክንያት በሆነው ይዞታ ላይ አመልካች መብት እና ጥቅም የላቸውም በማለት የወሰነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ የሰበር አመልካች ከነዚህ ማስረጃዎች ውጭ ለመፋለም ክስ የሚሆን ያቀረቡት ማስረጃ የለም፡፡ በተጨማሪ አመልካች ይዞታውን ለ28 ዓመት ይገዙው ነበር ቢሉም ይዞታው በ1988 እና በ1997 የአየር ካርታ ላይ አይታይም እንዲሁም በወቅቱ ለገነባሁት ይዞታ ከአስተዳደሩ እውቅና ተሰጥቶኛል ያሉትን በተመለከተ በወቅቱ የተሰጡ ማስረጃዎች ከሕግ አግባብ ውጭ በመሆናቸው እንዲታረሙ መደረጉ ተረጋግጦ በስር ፍርድ ቤት ውሳኔ የተሰጠ በመሆኑ የስር ፍርድ ቤት የሰጠው ውሳኔ ከሕግ አግባብ ውጭ ነው ማለት አይቻለም፡፡ በመሆኑም የስር ፍርድ ቤት የሰጠው ውሳኔ የሚነቀፍበት የፍሬ ነገርም ሆነ የሕግ መሰረት የሌለ በመሆኑ አቤቱታ ውድቅ እንዲያደርግልን ሲሉ ተከራክረዋል፡፡

3ኛ እና 4ኛ ተጠሪዎችም በጋራ በቀን 20/06/2015ዓ.ም ጽፈዉ ባቀረቡት መልስ - በአመልካች ለቀረበው የሰበር አቤቱታ ማስቀረቢያ ምክንያት የተደረገዉ የሰ/መ/ቁጥር 37105 የተሰጠ አስገዳጅ የሕግ ትርጉም በአሠሪና ሠራተኛ ክርክር የተሰጠ የሕግ ትርጉም ሲሆን በተያዘው ጉዳይ ግን የይዞታ ባለቤትነትን ለማረጋገጥ አስፈላጊ አይደለም በሚል ብቻ ሳይቀርብ እና ሳይመዘን የታለፈ የሰነድ ማሥረጃ ባለመኖሩ ተፈጻሚነት የለዉም፡፡ የ1997 ዓ.ም የአየር ካርታም ቢሆን በማሥረጃነት ቀርቦና

ተመርምሮ እንዲሁም በ2ኛ ተጠሪ ጭምር ይዞታው የማን እንደሆነ እና ባለቤትነትን እንደማያረጋግጥ ማብራሪያ ቀርቦበት ውድቅ የተደረገ እንጂ ሳይቀርብና ሳይመዘን የታለፈ ባለመሆኑ ከተጠቀሰው የሰበር ትርጉም ጋር የሚገናኝ አይደለም፡፡በተጨማሪም የይዞታ ባለቤትነት ከፍ/ሕ/ቁ.1195 እንዲሁም ሌሎች አግባብነት ያላቸው ደንቦች እና መመሪያዎች አንፃር በምስክር ብቻ የሚረጋገጥ ፍሬ ነገር ባለመሆኑ በሥር ፍርድ ቤት ምስክር ተቀባይነት የሚሰጠው ማሥረጃ አይደለም በሚል ሳይሰማ መታለፉ ከተጠቀሰው አስገዳጅ የሕግ ትርጉም ጋር የሚጋጭ አይደለም፡፡በተመሣሣይም ለሰበር አቤቱታው ማስቀረብ ምክንያት በሆነዉ በሰ/መ/ቁጥር 37391 የተሰጠ አስገዳጅ ውሣኔ በሥራ ክርክር ከጭብጥ አመሰራረት ጋር ተያይዞ የተሰጠ አስገዳጅ የሕግ ትርጉም ሲሆን በተያዘው ጉዳይ ከይዞታው ባለቤትነት ማንነት ማረጋገጥ ጋር በተገናኘ በሥር ፍርድ ቤት ሳይያዝ የታለፈ ጭብጥ ባለመኖሩ፣በፍሬ ነገር ማስረጃ ምዘና ነጥሮ እና ተመዝኖ የተወሰነ በመሆኑ የሰበር አቤቱታዉ ዉድቅ እንዲደረግልን ሲሉ ተከራክረዋል፡፡አመልካችም የመልስ መልሳቸውን በማቅረብ ተከራክረዋል፡፡

ከላይ አጠር ባለ መልኩ የተገለጸዉ የግራ ቀኙን ክርክርና በስር ፍርድ ቤቶች የተሰጡ ዉሳኔዎች ይዘት የሚመለከት ሲሆን ሰበር አጣሪ ችሎት የያዘዉን ጭብጥ ከግምት በማስገባት በስር ፍርድ ቤቶች በተሰጠው ውሳኔ በዚህ ችሎት ደረጃ ሊታረም የሚችል መሰረታዊ የሕግ ስህተት መፈጸም አለመፈጸሙን አግባብነት ካለዉ ሕግ ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለዉ መርምረናል፡፡

እንደመረመርነዉም በኢፌዲሪ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 40(1-3 እና 6) ስር የግል ንብረት ባለቤትነት መብት እንደሚከበር፤ የገጠርም ሆነ የከተማ መሬት ባለቤትነት የመንግሥትና የሕዝብ ብቻ እንደሆነና መሬት የማይሸጥ የማይለወጥ የኢትዮጵያ ሕዝቦች የጋራ ንብረት እንደሆነ፤ለግል ባለሀብቶች በሕግ በዝርዝር በሚደነገገዉ አግባብ በሚወሰን ክፍያ በመሬት የመጠቀም መብታቸዉ እንደሚከበርላቸዉ ተደንግጓል፡፡ ከዚህ ሕገ መንግሥት በፊት ወጥቶ በሥራ ላይ በሚገኘዉ አዋጅ ቁጥር 47/1967 አንቀጽ 3 እና 4 ስር ይህ አዋጅ ከጸናበት ከቀን 01/12/1967 ዓ.ም ጀምሮ የከተማ ቦታ የመንግሥት ንብረት መሆኑ፤ ማንኛዉም ሰዉ የከተማ ቦታ በግል ባለሀብትነት ለመያዝ እንደማይችል፤የከተማ ቦታ ሊሸጥ፣ ሊለወጥ... እንደማይችል እንዲሁም ከቀን 11/04/1967 ዓ/ም ጀምሮ ...በሽያጭ ወይም በሌላ መንገድ የከተማን መሬት ለማስተላለፍ የተደረገ ተግባር ወይም ዉል እንደተሻረ ተደንግጓል፡፡ከዚህ በኋላ የከተማ ቦታ በኪራይ ስለመያዝ ለመደንገግ በወጣዉ አዋጅ ቁጥር 80/1986፣አዋጅ ቁጥር 272/1994 እና የከተማ ቦታን በሊዝ ስለመያዝ ለመደንገግ የወጣዉ አዋጅ ቁጥር 721/2004 ላይ የከተማ መሬት አግባብ ባለዉ አካል በሚሰጥ ዉሳኔ በኪራይ ወይም በሊዝ እንደሚያዝ ተመልክቷል፡፡

የከተማ ቦታ በሊዝ ስለመያዝ ለመደንገግ በወጣዉ አዋጅ ቁጥር 721/2004 አንቀጽ 6(4 እና 5) ስር በተደነገገዉ መሠረት አዋጁ ከጸናበት ቀን ጀምሮ ባለዉ የአራት ዓመት ጊዜ ዉስጥ አግባብ ያለዉ አካል ሳይፈቅድ የተያዙ ይዞታዎችን ሥርዓት ለማስያዝ ክልሎችና የከተማ አስተዳደሮች የሚያወጧቸዉን

ደንቦች ተከትሎ ከከተሞች ፕላንና ከሽንሻኖ ስታንዳርድ አንጻር ተቀባይነት የሚያገኙ ይዞታዎች በሊዝ ሥሪት እንዲተዳደሩ እንደሚደረግ ተደንግጓል። ይህንን ተከትሎ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ደረጃ የሊዝ አዋጁን ማስፈጸሚያ ደንብ እና ልዩ ልዩ መመሪያዎች ወጥተው እየተተገበሩ ይገኛሉ። ከተያዘው ጉዳይ ጋር ተያይዞ ሊጠቀስ የሚችለው በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የወጣው *መመሪያ "አግባብ ባለው አካል ሳይፈቀድ የተያዙ ቦታዎችን ለማስተካከልና ለመከላከል የወጣው የአፈጻጸም መመሪያ ቁጥር 18/2006* ነው።በዚህ መመሪያ አንቀጽ 2/6 በተመለከተው ትርጓሜ እና በአንቀጽ 3 ስር በተደነገገው መሠረት አግባብ ያለው አካል ሳይፈቅድ የተያዘ ቦታ ነው የሚባለው በከተማ አስተዳደር መሬትን በይዞታነት እንዲፈቅድ ሥልጣን በተሰጠው አካል ሳይፈቀድ እስከ ሚያዝያ 1997 ዓ/ም በግለሰብ የተያዘ የከተማ ቦታ ነው። በዚሁ መመሪያ አንቀጽ 2/21 ከተመለከተው ትርጓሜ እና በተለይም በአንቀጽ 5.1.1. ላይ እንደተደነገገው አግባብ ያለው አካል ሳይፈቅድ የተያዘ ይዞታ ወደ ሕጋዊ ስርዓት ገብቶ በሊዝ እንዲተዳደር ይዞታውን ለያዘው ሰው ሊፈቀድ የሚችለው በቦታው ላይ ለመኖሪያ፣ለንግድ፣ለማህበራዊ ወይም ለማንኛውም ለሌላ አገልግሎት የተሠራ ሆኖ በ1997 ዓ.ም በተነሳው የመስመር ካርታ ላይ የሚታይ እና አሁንም አገለግሎት እየሰጠ የሚገኝ ቤት ሲኖር፣በመመሪያው አንቀጽ 5.1.2. መሠረት ቤቱ ከከተማው ፕላን ጋር የማይቃረን ሲሆን፣ በመመሪያው አንቀጽ 5.1.3. እንደተደነገገው በአንቀጽ 5.1.1. ስር የተደነገገው ቢኖርም ቤቱ በተለያዩ ምክንያቶች በ1997 የመስመር ካርታ ላይ የማይታይ ሆኖ ስለቤቱ መንግሥታዊ በሆነ ተቋም ከሚያዝያ 1997 ዓ/ም በፊት የተሰጠ የሰነድ ማቅረብ እና ቤቱ በወቅቱ ተገንብቶ በእጃቸው የሚገኝ እንደነበር በወረዳው አስተዳደር ተረጋግጦ ከቀረበ እና ከሽንሻኖ ማስተካከል ጋር የሚጣጣም መሆኑ ሲረጋገጥ ነው።

ከላይ ከተጠቀሱት ሕግጋት መሠረት አግባብ ያለው አካል ሳይፈቅድ የተያዘ ይዞታ ወደ ሕጋዊ ሥርዓት እንዲገባና በሊዝ ሥርዓት እንዲተዳደር ካልተደረገ በአዋጅ ቁጥር 721/2004 አንቀጽ 26/4 በተደነገገው መሰረት አግባብ ያለው አካል የማስለቀቂያ ትእዛዝ መስጠትና ካሣ መክፈል ሳያስፈልግ የ7 የሥራ ቀናት የጽሁፍ ማስጠንቀቂያ ብቻ ይዞታውን ለያዘው ሰው በአካል በመስጠት ወይም በቦታው በሠፈረው ንብረት ላይ በመለጠፍ የማስለቀቅ ሥልጣን አለው። በዚህ መልኩ ማስጠንቀቂያ የሚሰጥበትም ምክንያት ይዞታውን የያዘው ሰው ከዝርዝር ምክንያትና ማስረጃ ጋር አግባብ ላለው አካል አቤቱታ ማቅረብ እንዲችል፣ አግባብ ያለው አካል ጉዳዩን ከሚቀርበው አቤቱታና ማስረጃ አንጻር መርምሮ አስተዳደራዊ ውሳኔ እንዲሰጥበት እንዲሁም የይዞታውን የያዘው ሰው አቤቱታ የማያቀርብ ከሆነም በይዞታው ላይ ያሰፈረውን ንብረት በራሱ ወጪ ማንሳት እንዲችል ጊዜና እድል ለመስጠት እንደሆነ በዚሁ አዋጅ አንቀጽ 28(2 እና 3) ስር ከተደነገገው መረዳት ይቻላል። አግባብ ያለው አካል በአዋጁ አንቀጽ 26/4 መሰረት ማስጠንቀቂያ ሰጥቶ ከሆነ በዚሁ አዋጅ አንቀጽ 31/5 ስር በተደነገገው መሰረት በሕገ-ወጥ መንገድ የተያዘ የከተማ ቦታ እንዲለቀቅ በማድረጉ በቦታው ላይ ላለ ንብረት ካሳ ለመክፍል ኃላፊነት አይኖርበት። በአንጻሩ አግባብ ያለው አካል በሕግ የተጣለበትን ማስጠንቀቂያ የመስጠት ግዴታ ሳይወጣ

መሬቱ በሕገ-ወጥ መንገድ ተይዟል በሚል ብቻ በመሬቱ ላይ የሰፈረ ንብረት የሚያወድም ወይም በንብረቱ ላይ ጉዳት እንዲደርስበት የሚያደርግ ከሆነ በደረሰዉ ጉዳት ልክ ካሣ የመክፈል ኃላፊነት እንደሚኖርበት በሰ/መ/ቁጥር 236995 እና 241461(ያልታተሙ) ላይ የተሰጠዉ አስገዳጅ የሕግ ትርጉም ያሳያል፡፡

ከተያዘዉ ጉዳይ ጋር በተያያዘ የሥረ ነገር ሕጉ አቋም ከሞላ ጎደል ከላይ የተመለከተዉ ሆኖ በሌላ በኩል በልዩ ሕግ በተለየ አኳኋን ካልተደነገገ በስተቀር የፍትሐ ብሔር ክርክር መመራት ያለበት በፍትሐ ብሔር ሥነ ሥርዓት ሕጉ በተዘረጋዉ ሥርዓት መሰረት መሆኑ ይታወቃል፡፡ በዚህ መሰረት የፍትሐ ብሔር ክርክር የቀረበለት ፍርድ ቤት የክስ ማመልከቻዉን፣ የመከላከያ መልስ፣ በግራ ቀኙ የቀረቡትን ማስረጃዎች እንዲሁም በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 241 መሰረት ግራ ቀኙን በመመርመር ያጣራዉን መሰረት በማድረግ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 246 እና ተከታዮቹ ድንጋጌዎች መሰረት በተጠየቀዉ ዳኝነት ላይ ተገድቦ ተገቢዉን የሕግና የፍሬ ነገር ጭብጦችን መመስረት ይገባል፡፡ ተገቢዉን ጭብጥ ለመመስረት ምስክሮች አስቀርቦ መስማት ወይም የሰነድ ማስረጃ አስቀርቦ መመርመር ካስፈለገም ጭብጥ ከመመስረቱ በፊት ይህንኑ ተግባር መፈጸም እንደሚቻል በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 249 እና 250 ላይ ሥርዓት ተዘርግቷል፡፡ በዚህ አግባብ ተገቢዉ ጭብጥ ከተመሰረተ በኋላ በተለይም በማስረጃ ሊረጋገጥ የሚገባዉን የፍሬ ነገር ጭብጭ በግራ ቀኙ በቀረቡ ማስረጃዎች እና እንደ ነገሩ ሁኔታ ራሱ ፍርድ ቤቱ ባስቀረባቸዉ ማስረጃዎች በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 258 እና ተከታዮቹ ድንጋጌዎች መሰረት የተከራካሪ ወገኖችን ክርክር የመክፈት ቅደምተከተል ጠብቆ የግራ ቀኙን ሙግት በመስማት እና በማስረጃ በማጣራትና በማረጋገጥ እልባት መስጠት ይገባል፡፡ ከክሳሽ እና ከተከሳሽ የጽሁፍ ክርክር (pleadings) ጋር ተያይዞ በቀረበዉ እና በመጀመሪያ ክሱ እስከተሰማበት የክርክር ሂደት ደረጃ (First Hearing Stage) በቀረበዉ ማስረጃ ብቻ በመመርመር በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 255 መሰረት አከራካሪዉን ጉዳይ በፍርድ መወሰን ፍትህን የሚያጓድል ከሆነ በአከራካሪዉ ጉዳይ ላይ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 257 እና ተከታዮቹ ድንጋጌዎች መሠረት የግራ ቀኙ ተጨማሪ ሙግት እና ምስክሮች ሳይሰማ ዉሳኔ መስጠት የዳኝነት ሥራ አመራር ኃላፊነት በአግባቡ ተግባራዊ አለማድረግ እንደሆነ፤ክርክሩ ከጊዜ፣ከገንዘብና ከሰዉ ሀብት (judicial economy) አጠቃቀም አኳያ ዉጤታማ እንዳይሆን ከማድረግ አልፎ የተከራካሪ ወገኖችን ሥነ ሥርዓታዊ ፍትሕ (procedural justice) እንደሚያጓድል የተከራካሪ ወገኖችን የሥረ ነገር መብት(substantive right) እስከማሳጣት የሚያደርስ ጉዳት የሚያስከትል መሠረታዊ የሕግ ስህተት እንደሆነ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁጥር 37391(ቅጽ 8)፣189065፣234426፣241461 እና በሌሎች መዛግብት ላይ አስገዳጅ የሕግ ትርጉም ሰጥቷል፡፡

በተጨማሪም አሚጋች ፍርድ ቤት ተከራካሪ ወገኖች ከጽሁፍ ክርክራቸዉ ጋር እና የመጀመሪያዉ የክስ አሰማም ሥነ ሥርዓት እስከተፈጸመበት የክርክር ሂደት ደረጃ ድረስ ካቀረቧቸዉ ማስረጃዎች ዉጭ ሌሎች ትክክለኛ ፍርድ ለመስጠት የሚያስችሉ ምስክሮችን ወይም የሰነድ ማስረጃዎችን አስቀርቦ በመስማትና በመመርመር አንጻራዊ እዉነታን በማጣራት መወሰን እንዲችል በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 264 ስር ሥርዓት ተዘርግቷል፡፡ከዚህም ጋር በተያያዘም የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁጥር 22603 (ቅጽ 6)፣105956(ቅጽ 20) ፣በሰ/መ/ቁጥር 232290 እና 236995 (ያልታተሙ) ላይ የሕግ ትርጉም ሰጥቷል፡፡

ወደ ተያዘዉ ጉዳይ ስንመለስ አመልካች አስቀድሞ ከአሁን 2ኛ ተጠሪ ጋር ተከራክረዉ የተሰጠዉን ዉሳኔ በመጥቀስ ጭምር ለክርክሩ መነሻ የሆነዉን መሬት በ1986ዓ/ም በግዥ አግኝተዉ ከዚሁ ጊዜ ጀምሮ ቤት ሰርተዉ ይዘዉ እንደሚገኙ፤ቤቱም በ1997 ዓ/ም አየር ካርታ ላይ እንደሚታይ በመግለጽ ከሕግ-አግባብ ዉጭ ወደ 3ኛ እና 4ኛ ተጠሪዎች እንደተላለፈ በመግለጽ ሲከራከሩ 1ኛ እና 2ኛ ተጠሪዎች ደግሞ የመሬት ይዞታዉ የመንግሥት ባዶ መሬት መሆኑን በመግለጽ በይዞታዉ ላይ አመልካች መብት የላቸዉም፤ለ3ኛ እና 4ኛ ተጠሪዎች በአርሶ አደርነት የተላለፈ ነዉ በማለት ተከራክረዋል፡፡3ኛ እና 4ኛ ተጠሪዎችም በአርሶአደርነት በሕግ አግባብ የተሰጣቸዉ መሬት እንደሆነ በመግለጽ ተከራክረዋል፡፡በዚህ መልኩ ግራ ቀኙን በአከራካረዉ ጉዳይ ላይ ዉሳኔ ለመስጠት ሊያዙ የሚገባቸዉ ጭብጦች - 1ኛ እና 2ኛ ተጠሪዎች ለ3ኛ እና 4ኛ ተጠሪዎች መብት በመፍጠር በይዞታ ማረጋገጫ ካርታ መዝግበዉ የሠጡት የመሬት ይዞታ አመልካች አግባብ ባለዉ አካል ሳይፈቀድላቸዉ በመያዝ ቤት በመሥራት ይዘዉ የሚገኙት እና በአመልካች ስም እንዲመዘገብ ሕግ የሚፈቅድላቸዉ ነዉ ወይስ አይደለም? 1ኛ እና 2ኛ ተጠሪዎች ይህንን የመሬት ይዞታ ለ3ኛ እና 4ኛ ተጠሪዎች ማስተላለፋቸዉ ተገቢ ነዉ ወይ ? ለአመልካች መብት ሊፈጠርላቸዉ የሚገባ ነዉ የሚባል ከሆነ አከራካሪዉን የመሬት ይዞታ ተጠሪዎች ለአመልካች ሊለቁ ይገባል ወይስ አይገባም ? የሚሉ ናቸዉ፡፡የስር የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት እነዚህን ጭብጦች መመስረቱን የዉሳኔዉ ይዘት በግልጽ አያሳይም፡፡

እንዲሁም ግራ ቀኙ የሚከራከሩበትን የመሬት ይዞታ ላይ ተፈጠረ የተባለዉን የሁከት ተግባር ለማስወገድ ከዚህ ቀደም አመልካች በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 279873 ላይ በአሁን 2ኛ ተጠሪ ላይ የመሰረቱትን ክስ ፍርድ ቤቱ በማስረጃ አጣርቶ በቀን 04/09/2012ዓ/ም በሰጠዉ ዉሳኔ “...ለክርክሩ መነሻ በሆነዉ ይዞታ ላይ የሚገኘዉ ቤት በ1997ዓ/ም አየርና መስመር ካርታ ላይ እንደሚታይ የክፍለ ከተማዉ የመሬት አስተዳደር አካል አጣርቶ ምላሽ እንደላከለት በመግለጽ ቤቱ የግንባታ ፈቃድ ወጥቶበት የተሠራ ባይሆንም በመመሪያ ቁጥር 18/2006 አንቀጽ 5 መሠረት በሰነድ አልባ ይዞታዎች መስተንግዶ ማግኘት የሚችል ነዉ፡፡በመሆኑም 2ኛ ተጠሪ 500 ካሬ ሜትር ስፋት

ያለዉን ይዞታ አመልካች እንዲለቅ የሰጠዉ ትእዛዝ የሁከት ተግባር በመሆኑ በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 1149/1 መሰረት ሊወገድ ይገባል፡፡" በማለት መወሰኑን የዉሳኔዉ ይዘት ያሳያል፡፡የአሁን 2ኛ ተጠሪ በዚህ ዉሳኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርቦ ፍርድ ቤቱም በመ/ቁጥር 259154 ላይ አመልካችንና 2ኛ ተጠሪን አከራክሮ በቀን 16/11/2013ዓ /ም በሰጠዉ ዉሳኔ "...ምንም እንኳን የአሁን 2ኛ ተጠሪ በአየር ካርታ ላይ ይታያል የተባለዉና ለክርክሩ መነሻ የሆነዉ ቤት የቴሌ መኖሪያ ቤቶች ማኅበር ቤቶች በዕቃ ማስቀመጫነት ሲያገለግል የነበረ ቆርቆሮ በቆርቆሮ የሆነ ቤት ነዉ ቢልም በኮልፌ ቀራንዮ ክፍለ ከተማ የይዞታ አስተዳደር ሽግግር ጊዜ አግልግሎት ጽ/ቤት ሰነድ ማጣራትና የሽንሻኖ ማስተካከልና ካርታ ዝግጅት የሥራ ሂደት ጉዳዩን ከወረዳዉ ደንብ ማስከበር አገልግሎት ጽ/ቤት ጋር በጋራ በማጣራት ያላኩት ምላሽ ቤቱ በ1997 ዓ/ም አየር ካርታ ላይ የሚታይ እንደሆነ ያሳያል በማለት የአሁን 2ኛ ተጠሪ ያቀረበዉን የይግባኝ ቅሬታ ባለመቀበል ይዞታዉ በመመሪያ ቁጥር 18/2006 መሰረት ለመስተናገድ የሚችል ሆኖ እያለ 2ኛ ተጠሪ ቤቱ እንዲፈርስ ማስጠንቀቂያ መስጠቱ የሁከት ተግባር ነዉ ሲል የስር ፍርድ ቤት የሰጠዉ ዉሳኔ ተገቢ ነዉ ሲል በማጽናት መወሰኑን የዉሳኔዉ ይዘት ያሳያል፡፡ በዚህ አግባብ ለክርክሩ መነሻ የሆነዉ ይዞታ በመመሪያ ቁጥር 18/2006 መሰረት ሊስተናገድ የሚችል ይዞታ ሆኖ እያለ የአሁን 2ኛ ተጠሪ ቤቱ እንዲፈርስ ለአመልካች የሰጠዉ ማስጠንቀቂያ የሁከት ተግባር ነዉ በሚል በመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት እና በይግባኝ ሰሚዉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የተሰጠዉ ዉሳኔዎች እስካሁን ጸንተዉ የሚገኙ መሆናቸዉ አከራካሪ አይደለም፡፡ በፍርድ ቤት የተሰጠ ፍርድ፣ዉሳኔ ወይም ሌላ ትዕዛዝ በሥነ ሥርዓት ሕጉ በተመለከተዉ አግባብ ካልተለወጠ በስተቀር ሕጋዊ ዉጤት እንዳለዉ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 212 ከተደነገገዉ መገንዘብ ይቻላል፡፡ከዚህ ድንጋጌ አተገባበር ጋር በተያያዘም የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁጥር 67127፣85718 (ቅጽ12)፣ እና 191608 (ያልታተመ) ላይ የሕግ ትርጉም ሰጥቷል፡፡

ከላይ የተጠቀሱትን ዉሳኔዎች አመልካች በማስረጃነት ማቅረባቸዉን የስር ፍርድ ቤት ዉሳኔ ያሳያል፡፡በማስረጃነት አልቀረበም የሚል ክርክርም አልቀረበም፡፡በተጠቀሱት መዛግብት ላይ ክርክር ሲደረግ 2ኛ ተጠሪ በአንድ በኩል በ1997 አየር ካርታ ላይ የሚታየዉ በመሬቱ ላይ ያለዉ ቤት የቴሌ መኖሪያ ቤቶች ማኅበር ቤቶች በዕቃ ማስቀመጫነት የሚያገለግል እንጂ በአመልካች የተሠራ አይደለም እያለ እየተከራከረ በሌላ በኩል ደግሞ አመልካች ቤቱን አፍርሶ ይዞታዉን እንዲለቅ ማስጠንቀቂያ መጻፉ ተመልክቷል፡፡በዚህ መልኩ የቀረበዉ ክርክር ተቀባይነት አጥቶ በመሬቱ ላይ የተሰራዉ ቤት በአመልካች እንደተሠራ እና ቤቱ እንዲፈርስ ማስጠንቀቂያ መሰጠቱ የሁከት ተግባር ነዉ ተብሎ መወሰኑ 1ኛ እና 2ኛ ተጠሪዎች በተያዘዉ መዝገብ ላይ አከራካሪዉ መሬት ባዶ የመንግሥት መሬት ነዉ በሚል ለሚያቀርቡት ክርክር በማስረጃነት የሚኖረዉ ሕጋዊ ዉጤት ምን እንደሆነ በስር ፍርድ ቤቶች በአግባቡ አልተመዘነም፡፡በተጨማሪም በተጠቀሱት መዛግብት ላይ የተሰጠዉ የፍርድ ዉሳኔ ሁከት ሊወገድ ይገባል የሚል ብቻ ሳይሆን አመልካች ለይዞታዉ በመመሪያ ቁጥር 18/2006 መሰረት መስተንግዶ

ሊያገኝ የሚችል ነዉ በሚል ድምዳሜ ላይ የተደረሰበት በመሆኑ አመልካች "... ተጠሪዎች ክስ የቀረበበትን ይዞታ እንዲለቁ እና 1ኛ እና 2ኛ ተጠሪዎች አመልካች በይዞታው ላይ ለመገልገል አስፈላጊ የሆኑ ተግባራትን እና መስተንግዶ በመስጠት እንዲፈፅሙ እንዲወሰንልኝ፡፡" በማለት የጠየቁት ዳኝነት ከዚህ የፍርድ ዉሳኔ ይዘት አንጻር ጭምር ታይቶ ሊወሰን የሚገባ ሆኖ እያለ የሥር ፍርድ ቤቶች በማስረጃነት ለቀረበዉ ለዚህ ዉሳኔ ተገቢዉን ዋጋ በመስጠት አለመመዘናቸዉን ተገንዝበናል፡፡የስር ፍርድ ቤት ይህንን አቋም ለመያዝ በሰ/መ/ቁጥር 27506(ቅጽ 6) መሠረት እንዳደረገ የገለጸ ቢሆንም በተጠቀሰዉ መዝገብ ላይ ሁከት ለማስወገድ ዳኝነት ተጠይቆ እያለ ስለባለቤትነት መብት መወሰኑ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ነዉ ተብሎ የተወሰነ ሲሆን በያዝነዉ ጉዳይ ላይ 2ኛ ተጠሪ ከአመልካች ጋር ተከራክሮ በመ/ቁጥር 279873 እና 259154 የተሰጠዉ ዉሳኔ ሁከት ለማስወገድ ከተጠየቀዉ ዳኝነት በላይ አመልካችን የመሬት ይዞታዉ ባለይዞታ የሚያደርግ ዉሳኔ ነዉ በማለት ለሰበር ሰሚ ችሎት አቀርቦ ያስወሰነ ስለመሆኑ የሚያሳይ ማስረጃ ባላቀረበበት በተጠቃሾቹ መዛግብት ላይ የተሰጠዉን ዉሳኔ ሕጋዊ ዉጤት በሚያሳጣ አኳኋን ዉሳኔ መስጠቱ ሥነ ሥርዓታዊ አይደለም፡፡በተጠቀሱት መዛግብት ላይ የተሰጡ ዉሳኔዎች ስህተት እንኳ ቢሆኑ በሥነ ሥርዓት ሕጉ አግባብ በሰበር ሥነ ሥርዓት ወይም በሌላ ሥነ ሥርዓት አግባብ እስካልታረሙ ድረስ በስር ፍርድ ቤት በሌላ መዝገብ ላይ በሚሰጥ ዉሳኔ ሕጋዊ ዉጤት እንዲያጡ ማድረግ አይቻልም፡፡የተጠቀሰዉ የሰበር ሰሚ ችሎት የሕግ ትርጉም ለተያዘዉ ጉዳይ አግባብነት ያለዉ አይደለም፡፡ እንዲሁም በዚህ የፍርድ ዉሳኔ ላይ ሁከት ይወገድ ተብሎ ብቻ እንደተወሰነ በመቁጠር የፍርድ ዉሳኔዉን ሙሉ ይዘት በማስረጃነት ሳይመዝኑ ማለፋቸዉ ሊታረም የሚገባዉ መሠረታዊ የሆነ የማስረጃ ምዘና መርህ አተገባበር ስህተት ነዉ፡፡

ከዚህም በተጨማሪ አመልካች ባቀረቡት ክስ ላይ በግልጽ እንደተመለከተዉ አመልካች አከራካሪዉን ይዞታ በሕግ ሥልጣን በተሰጠዉ አግባብ ባለዉ አካል ሳይፈቀድላቸዉ የያዙት መሆኑን በገለጹበት እና በዚህ አግባብ የተያዙ ይዞታዎችን ወደ ሕጋዊ ሥርዓት ለማስገባት በወጣዉ ሕግ መሠረት እንዲወሰን ዳኝነት በጠየቁበት ሁኔታ የሥር ፍርድ ቤት አመልካች ይዞታዉን ከአርሶ አደሮች በግዥ መግዛታቸዉን ከመግለጽ ዉጪ በውርስ ፣በስጦታ ፣በምሪት እና በመሳሰሉት ሕጋዊ ኩነቶች ማግኘታቸውን በክሳቸው ያልገለፁ በመሆኑ ምስክር መስማት አስፈላጊ አይደለም በማለት ዉሳኔ መስጠቱ ከክርክሩ ይዘት ዉጭ ነዉ፡፡ እንዲሁም መሬቱ በአመልካች ያልተያዘና የመንግሥት ባዶ መሬት መሆኑ ተገልጾ በተጠሪዎች ክርክር በቀረበበት ሁኔታ አመልካች ከሚያዝያ 1997 ዓ/ም በፊት ጀምሮ አከራካሪዉ መሬት ላይ ቤት በመሥራት መያዝ አለመያዛቸዉን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 257 እና ተከታዮቹ ድንጋጌዎች መሠረት የግራ ቀኙን ሙግት እና ምስክሮች በመስማት ፍሬ ነገሩን ካረጋገጠ በኋላ መወሰን ሲገባዉ የአመልካችን ምስክሮች መስማት አያስፈልግም ተጠሪዎችም ሊያስተባብሉ አይገባም በማለት የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 33/2 ያለቦታዉ ተፈጻሚ በማድረግ ዉሳኔ መስጠቱም ሆነ ይግባኝ ሰሚዉ ፍርድ ቤት ይህንን ሳያርም ማለፉ በኢፌዲሪ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 37/1 እዉቅና የተሰጠዉን ፍትህ የማግኘት መብት አካል

የሆነዉን የአመልካችን የመሰማት ሥነ ሥርዓታዊ መብት እና በአንቀጽ 40 የተመለከተዉን የንብረት መብት የጣሰ በመሆኑ ሊታረም የሚገባዉ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ነዉ ብለናል፡፡

ሲጠቃለል በስር ፍርድ ቤቶች የተሰጡ ዉሳኔዎች መሰረታዊ የሆነ የክርክር አመራር ሥነ ሥርዓት፣ የማስረጃ አቀባበልና ምዘና መርሆዎች እና የሕግ አተገባበር ጉድለት ያለባቸዉ ስለሆኑ የሥነ ሥርዓት ሕጉን አስገዳጅ ድንጋጌዎችን እና ከላይ በተጠቀሱት መዛግብት ላይ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የሰጠዉን አስገዳጅ የሕግ ትርጉም የሚቃረኑ ናቸዉ፡፡በመሆኑም በፌዴራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀጽ 2(4/ሀ እና ሸ) እና 10(1/ሀ) መሰረት ሊታረም የሚገባዉ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመባቸዉ ስለሆኑ ተከታዩን ወስነናል፡፡

ዉ ሳ ኔ

1. የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 123489 ላይ በቀን 04/06/2014 ዓ.ም የሰጠዉ የፍርድ ዉሳኔ እና የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 288378 ላይ በቀን 07/03/2015ዓ.ም የሰጠዉ የፍርድ ዉሳኔ በሰበር ሥነ ሥርዓት መመሪያ ቁጥር 17/2015 አንቀጽ 9/1 መሰረት ተሽረዋል፡፡

2. የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የተዘጋዉን መዝገብ በማንቀሳቀስ ከላይ በፍርድ ሀተታዉ ላይ የተገለጹትን ጭብጦች እና ተጓዳኝ ጭብጦችን በመያዝ በጭብጦቹ ላይ የግራ ቀኙን ተጨማሪ ሙግት እና የተቆጠሩን ምስክሮች በመስማት እንዲሁም በፍርድ ሀተታዉ ላይ በተገለጸዉ አግባብ ተጨማሪ ምስክሮችን መስማት እንዲሁም እንደ ነገሩ ሁኔታ በትእዛዝ በሚያስቀርበዉ ተጨማሪ ማስረጃ ፍሬ ነገሮቹን በማጣራት አግባብነት ባለዉ ሕግ መሰረት በተጠየቀዉ ዳኝነት ላይ ዉሳኔ እንዲሰጥ ጉዳዩን በሰበር ሥነ ሥርዓት መመሪያ ቁጥር 17/2015 አንቀጽ 9/2 መሰረት መልሰንለታል፡፡

3. በዚህ ችሎት ያወጣ ወጭ ግራ ቀኝ የየራሳቸዉን ይቻሉ ብለናል፡፡

ት እ ዛ ዝ

- የዉሳኔዉ ግልባጭ ለስር የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ይተላለፍ፡፡ ግራ ቀኙ ሲጠይቁም ግልባጩ ይሰጣቸዉ፡፡የስር ፍርድ ቤት መዝገብ ይመለስ፡፡
- ዉሳኔዉ በቀን 05/10/2016ዓ/ም ተነበበ፡፡
- መዝገቡ ተዘግቷል፤ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ማ/ተ

የሰ/መ/ቁ 234339

መጋቢት 25 ቀን 2016 ዓ.ም

ዳኞች፡- ተፈሪ ገብሩ (ዶ/ር)

በእውቀት በላይ

ተሾመ ሽፈራው

ዋዚሞ ዋሲራ

ሰናይት አድነው

አመልካች፡- የኢትዮጵያ መንገዶች አስተዳደር

ተጠሪ፡- 1. የአቱጋ ማርያም ቤተ-ክርስቲያን

2. ሱር ኮንስትራክሽን - **የቀረበ የለም**

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

ፍርድ

በዚህ መዝገብ የተያዘው ክርክር የካሳ ክፍያን የሚመለከት ሲሆን የጀመረውም በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ነው፡፡ የአሁን 1ኛ ተጠሪ ከሳሽ፤ አመልካች ተከሳሽ እንዲሁም 2ኛ ተጠሪ ጣልቃ ገብ በመሆኑ ተከራክረዋል፡፡

1ኛ ተጠሪ በቀን 21/03/2011 ዓ.ም ጽፈው ባቀረቡት ክስ አመልካች በዱር ቤቴ ሻሁራ ያለውን የጠጠር መንገድ ሲያሰራ ይዞታነቱ የ1ኛ ተጠሪ የሆነውንና በይዞታ መለያ ቁጥር A/M/H/H/03/27/995 የተመዘገበውን 05 ገመድ መሬት ለጠጠር ማምረቻነት ከተጠቀመ በኋላ ወደ ነበረበት መመለስ ሲገባው ለሶስት ዓመት ካሳ ብር 40,181.40 (አርባ ሺ አንድ መቶ ሰማኒያ አንድ ብር ከ40/100) ቢከፍልም መሬቱን ወደ ነበረበት አልመለሰም፡፡ ከዚህም ባለፈ የ10 ዓመት ካሳ ለመክፈል ተስማምቶ ያልከፈለን በመሆኑ በአዋጅ ቁጥር 455/97 አንቀጽ 8(1) መሰረት ከመሬቱ በቋሚነት እንድፈናቀል ሲደረግ በሚከፈለው ስሌት መሰረት ተሰርቶ ብር 1,347,318.60 (አንድ ሚሊዮን ሶስት መቶ አርባ ሰባት ሺ ሶስት መቶ አስራ ስምንት ብር ከ60/100) ከህጋዊ ወለድ ጋር እንዲከፍል ወሰንልኝ በማለት ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡

አመልካች በበኩሉ ለክሱ መቃወሚዎችን ያቀረበ ሲሆን በፍሬ ነገሩ ላይ በሰጠው መልስ መሬቱ ሙሉ ለሙሉ ለግብዓት ማምረቻ የዋለና ወደ ነበረበት ለመመለስ የማይቻል ስለመሆኑ ማስረጃ አልቀረበም፤ እንዲከፈል የተጠየቀው የካሳ ገንዘብ እጅግ የተጋነነ እና የካሳ አሰላል ስርዓቱን የተከተለ

አይደለም፤ ካሳውን የመክፈል ኃላፊነት አለባቸው ብንባል እንኳን መሬቱ ወደ ነበረበት ሊመለስ ይችላል ወይስ አይችልም የሚለው በባለሞያ ሊጣራ ይገባል እንዲሁም በውላችን መሰረት ካሳውን የመክፈል ኃላፊነት ያለበት 2ኛ ተጠሪ በመሆኑ ወደ ክርክሩ ጣልቃ ይግባልን በማለት ተከራክሯል፡፡

2ኛ ተጠሪ ወደ ክርክሩ ጣልቃ ገብቶ ባቀረበው መልስ ለ1ኛ ተጠሪ በቅድሚያ ካሳ የተከፈለው በመሆኑ ልንከሰስ አይገባም የ1ኛ ተጠሪ ጥያቄ የካሳ ይከፈለኝ እንዲ መሬቱ ወደ ነበረበት ይመለስልኝ የሚል ባለመሆኑ ኃላፊነት የለብንም የመንገድ ስራውን በውል አስቀድሞ የያዘው ሌላ ተቋራጭ በመሆኑ ካሳ የመክፈል የውል ግዴታ የለብንም፤ ለስራው ግብዓት የማቅረብ ኃላፊነትም የአመልካች በመሆኑ ልንጠየቅ አይገባም በማለት ተከራክሯል፡፡

ጉዳዩ በዚህ መልኩ የቀረበለት የስር ፍርድ ቤት በመጀመሪያ ደረጃ የቀረቡትን መቃወሚያዎች ውድቅ በማድረግ የግራ ቀኙን ክርክር እና ማስረጃ ከመረመረ እንዲሁም የካሳው መጠን በባለሞያ ተሰልቶ እንዲቀርብለት ካደረገ በኃላ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡ በሰጠው ውሳኔ አመልካች የ1ኛ ተጠሪን የእርሻ መሬት ለመንገድ ስራ አገልግሎት የሚውል ጋራጋንቲ (ጠጠር) ለማውጣት ለመዋዋል ለ3(ሶስት) አመት ካሳ መክፈሉ በማስረጃ ተረጋግጧል፤ የተከፈለው የካሳ ገንዘብም የሶስት አመት እንጂ ዘላቂ ከእርሻ ወይም ከመሬቱ ለሚፈናቀል ባለመሬት የሚከፈል የ10 ዓመት ካሳ አለመሆኑን ችሎቱ አረጋግጧል፡፡ መሬቱም ወደ ነበረበት ሊመለስ የማይችልና ለምንም ዓይነት ለሰብልም ሆነ ለሌላ የግብርና ሥራ እንደማይውል በማስረጃ ተረጋግጧል፡፡ ኃላፊነቱን በተመለከተም 1ኛ ተጠሪ ከይዞታ ማፈናቀያ ካሳ እንዲከፈለው ላቀረበው ጥያቄ 2ኛ ተጠሪ ኃላፊነት እንዳለበት አመልካች ያላሰረዳ ሲሆን በቀረበው ማስረጃ የተረጋገጠው ኃላፊነት ያለበት አመልካች ሰለለመሆኑ ነው፡፡ የካሳ መጠኑን በተመለከተም በባለሞያ ተሰርቶ የቀረበው የ10(አስር) አመት የካሳ መጠን ብር 3,466,333.44 (ሶስት ሚሊዮን አራት መቶ ስላሳ ስድስት ሺ ሶስት መቶ ስላሳ ሶስት ብር ከ44/100 ቢሆንም 1ኛ ተጠሪ እንዲከፈለው የጠየቀው ብር 1,347,318.60 (አንድ ሚሊዮን ሶስት መቶ አርባ ሰባት ሺ ሶሰስት መቶ አስራ ስምንት ብር ከ60/100 በመሆኑና ዳኛነት ከተጠየቀው በላይ ሊፈርድ ስለማይችል በጠየቀው ዳኝነት ልክ ይኸው ገንዘብ ይከፈለው በማለት ወስኗል፡፡

አመልካች በዚህ ውሳኔ ባለመስማማት ይግባኝ ለፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ያቀረበ ቢሆንም ውሳኔው ጉድለት የለበትም ተብሎ ይግባኙ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 337 መሰረታዊ ተሠርሟል፡፡

የሰበር አቤቱታ የቀረበው በዚህ ነው፡፡ አመልካች ባቀረበው 5 ገጽ የሰበር አቤቱታ በስር ፍርድ ቤቶች ተፈጽመዋል ያላቸውን ስህተቶች በመዘርዘር ውሳኔው የህግ ስህተት የተፈፀመበት ነው ተብሎ እንዲታረም ጠይቋል፡፡ ቅሬታው በሰበር አጣሪ ችሎት ተመርምሮ ቀደም ሲል ለ1ኛ ተጠሪ የሶስት ዓመትካሳ ታስቦ የተከፈላቸው ስለመሆኑ ባልተካደበት የስር ፍርድ ቤት ይህንን ታሳቢ ሳያደርግ የ10

ዓመት ካሳ እንዲከፈላቸው የወሰነበትን አግባብ ለማጣራት በሚል ጉዳዩ ለዚህ ሰበር ችሎት እንዲቀርብ እና ተጠሪዎች መልስ እንዲሰጡበት ተደርጓል፡፡

በዚሁም መሰረት 1ኛ ተጠሪ በሰጡት መልስ አመልካች ለተጠሪ የሶስት ዓመት ጊዜያዊ ካሳ የከፈለ ቢሆንም የተጠሪ የይዞታ መሬት ሙሉ በሙሉ በማያገግም ሁኔታ ጉዳት የደረሰበት ጊዜያዊ ካሳ በተከፈለ ከዓመታት በኋላ በመሆኑ አመልካች ለደረሰው ዘላቂ ጉዳት ካሳ እንዲከፍል ሲወሰን ጊዜያዊ የሶስት ዓመት ካሳ ክፍያው ታሳቢ ተደርጎ ተቀናሽ አለመደረጉ ተገቢና ህጉን የተከተለ ነው ቋሚ የመፈናቀያ ካሳው የተጠየቀው ውልን መነሻ በማድረግ ሳይሆን በተጨባጭ ጉዳቱ ከደረሰ በኋላ የቀረበን ጥቅም መነሻ በማድረግ የቀረበ ከመሆኑም በላይ የጉዳቱ መጠን ምን ያህል ጥቅም እንዳስቀረብን በማስረጃ ተደግፎ በቀረበበት ሁኔታ በውል የካሳ አሰላሉን እንደተስማማን አስመስሎ አቤቱታ ማቅረቡ ህጋዊ መሰረት የለውም በማለት ተከራክረዋል፡፡

2ኛ ተጠሪን በሚመለከት መጥሪያ የደረሰውና ጠበቃው ቀርቦ መልስ በማቅረብ እንዲችል ተለዋጭ ቀጠሮ እንዲሰጠው ጠይቆ በቀጠሮው መልስ ያላቀረበ በመሆኑ መልስ የመስጠት መብቱ ታልፏል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ በአጭሩ ከላይ የተገለጸው ነው፡፡ ይህ ችሎትም በሰበር አጣሪው ችሎት ሊጣራ ይገባዋል ተብሎ የተያዘውን ጭብጥ ከግራ ቀኙ ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸው ህጎች ጋር በማገናዘብ መርምሯል፡፡

እንደተመለከትነው የማስቀረቢያ ነጥቡ ለክርክሩ መነሻ የሆነውን ይዞታ አስመልክቶ ለአሁን 1ኛ ተጠሪ የሶስት ዓመት ካሳ ተከፍሎ እያለ ይህ ታሳቢ ሳይደረግ የ10 ዓመት ካሳ እንዲከፈላቸው የተወሰነበት አግባብ ሊመረመር ይገባል የሚል ነው፡፡

እንደሚታወቀው የመሬት የይዞታ መብት በህግ መንግስት ጥበቃ ከተደረገላቸው መሰረታዊ መብቶች ውስጥ አንዱ ስለመሆኑ በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ህገ መንግስቱ አንቀጽ 40 ድንጋጌ መረዳት ይቻላል፡፡ ይህ መብት ሊታጣ የሚችለው ይዞታው ለህዝብ ጥቅም አስፈላጊ ሆኖ በተገኘ ጊዜ ነው፡፡ በዚህ ጊዜም ቢሆን ይዞታው በዘፈቀደ የሚነጠቅ/የሚወሰድ/ እና ጥቅም ላይ እንዲውል የሚደረግ ሳይሆን ለህጋዊ ባለይዞታው በቅድሚያ ተመጣጣኝ ካሳ በመክፈል ስለመሆኑ ከዚሁ የህገ መንግስቱ ድንጋጌ ንዑስ አንቀጽ 8 ይዘት መገንዘብ ይቻላል፡፡ ይዞታው ወይም ንብረቱ ለሚወሰድበት ባለይዞታ/ባለመብት ቅድሚያ ካሳ የሚከፈልበት እንዲሁም ተጓዳኝ መብቶች የሚጠበቅበትን ስርዓት አስመልክቶ ክርክሩ በተነሳበት ጊዜ ስራ ላይ በነበሩት በአዋጅ ቁጥር 455/1997፣ ደንብ ቁጥር 135/1999፣ መመሪያ ቁጥር 19/2006 ላይ በዝርዝር ተመልክቷል፡፡ አንድን ባለይዞታ ወይም ባለንብረት ለህዝብ ጥቅም በሚል ምክንያት ከይዞታው ለማስለቀቅ እንዲሁም በጊዜያዊነትም ሆነ በቋሚነት በይዞታው የመጠቀም መብትን የሚያሳጣ ሁኔታ ሲከሰት ሊከፈል ስለሚገባው ካሳ በዝርዝር ተደንግጓል፡፡

በአዋጅ ቁጥር 455/1997 አንቀጽ 8(1) ስር እንደተመለከተው የመሬት ይዞታውን በቋሚነት እንዲለቅ የሚደረግ የገጠር መሬት ባለይዞታ መሬቱን እንዲለቅ ከመደረጉ በፊት የነበረው አመታዊ ገቢ በ10 ተባዝቶ የመፈናቀያ ካሳ ይከፈለዋል። በአንቀጽ 8(2) ስር እንደተመለከተውም የመሬት ይዞታውን ለተወሰነ ጊዜ እንዲለቅ ለሚደረግ የገጠር መሬት ባለይዞታ አመታዊ ገቢው መሬቱ እስከሚመለስ ድረስ ባለው ጊዜ ታስቦ የማፈናቀያ ካሳ ይከፈለዋል።ሆኖም ይህ ክፍያ በአንቀጽ 8(1) መሰረት ከሚከፈለው ካሳ መብለጥ የለበትም።

ከፍ ሲል ከተመለከተው የህግ ማዕቀፍ ይዘት መገንዘብ እንደሚቻለው በይዞታ መሬቱ በቋሚነት ጥቅም እንዲያገኝ (እንዲለቅ) ለሚደረግ የገጠር መሬት ባለይዞታ አመታዊ ገቢው በ10 ተባዝቶ የሚከፈለው የማፈናቀያ ካሳ ላይ በተጨማሪ ይዞታውን ለተወሰነ ጊዜ እንዲለቅ በተደረገ ጊዜ መሬቱ እስከሚመለስ ድረስ ያለው ጊዜ ታስቦ ተደራቢ የማፈናቀያ ካሳ ሊከፍል እንደማይችል ነው።

በተያዘው ጉዳይ 1ኛ ተጠሪ ይዞታውን በጊዜያዊነት ሲለቅ ለሶስት ዓመት ካሳ ብር 40,181.40(አርባ ሺ አንድ መቶ ሰማኒያ አንድ ብር ከ40/100) የተከፈላቸው መሆኑ አላከራከረም። ባቀረቡት ክስም ይኸው ተመልክቷል። ይሁንና መሬቱ ወደ ነበረበት አልተመለሰም ተብሎ የቋሚ ማፈናቀያ ካሳ ሲጠየቅ አስቀድሞ ተወሰደው ሳይታሰብ የ10 ዓመት ካሳ መጠየቁና የስር ፍርድ ቤቶችም ከሳሽ በጠየቁት መሰረት እንዲከፈላቸው የደረሱበት መደምደሚያና ያሳለፉት ውሳኔ ከፍ ሲል የተገለጹትን በህጉ ስለ ቋሚ እና ጊዜያዊ የማፈናቀያ ካሳ የተደነገገውን መሰረት ያደረገ ባለመሆኑ ውሳኔው ሊቃና ይገባል ብለናል። ተከታዩንም ወስነናል።

ውሳኔ

1. የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመ/ቁ 01-02066 የካቲት 15 ቀን 2014 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጠው ውሳኔ እና የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመ/ቁ 225343 ሀምሌ 6 ቀን 2014 ዓ.ም ያሳለፈው ትእዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 348(1) መሰረት ተሻሽሏል።
2. 1ኛ ተጠሪ ይዞታውን በጊዜያዊነት ሲለቁ ብር 40,181.40(አርባ ሺህ አንድ መቶ ሰማኒያ አንድ ብር ከ40/100) ካሳ የተከፈላቸው መሆኑ ያላከራከረ በመሆኑ የቋሚ ማፈናቀያ ካሳ ሲጠየቅ አስቀድሞ የተወሰደው ይኸው ገንዘብ ሳይታሰብ የ10 ዓመት ካሳ መጠየቁና የስር ፍርድ ቤቶችም 1ኛ ተጠሪ በጠየቁት መሰረት እንዲከፈላቸው ያሳለፉት የውሳኔ ክፍል የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነው ብለናል። ስለሆነም ይኸው ይዞታው በጊዜያዊነት ሲለቀቅ የተከፈለው ገንዘብ ተቀናሽ እንዲሆን ወስነናል።
3. ቀሪው የውሳኔ ክፍል አልተነካም።
4. ጥቅምት 30/2015 ዓ.ም ተሰጥቶ የነበረው የእግድ ትእዛዝ ተነስቷል። ይጻፍ።
5. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ።

መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መ/ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ፍ/ደ

የሰ/መ/ቁጥር 210819

ታህሳስ 26 ቀን 2015 ዓ/ም

ዳኞች፡- ተፈሪ ገብሩ(ዶ/ር)

ሌሊሴ ደሳለኝ

ተሾመ ሽፈራው

መላኩ ካሳዬ

ነፃነት ተገኝ

አመልካች፡- የንግድ ውድድር እና ሸማቾች ጥበቃ ባለስልጣን፡- አልቀረቡም

ተጠሪ፡- ሐያት ሆስፒታል ሜዲካል ኮሌጅ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር፡- ጠበቃ ፍቅሬ ሞያ - ቀረበ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍርድ

ጉዳዩ በአክስዮን ማህበር አባላት መካከል የአክስዮን ድርሻ በሽያጭ ሲተላለፍ እንደውህደት ተቆጥሮ ለአመልካች የውህደት ማስታወቂያ የሚሰጥ መሆን ያለመሆኑን የሚመለከት ነው፡፡ ክርክሩ የተጀመረበት በንግድ ውድድር እና ሸማቾች ጥበቃ ባለስልጣን የዳኝነት ችሎት የአሁን አመልካች ከሳሽ ተጠሪ ተከሳሽ በመሆን ተከራክረዋል፡፡

አመልካች በግንቦት 26 ቀን 2011 ዓ.ም ጽፎ ባቀረበው ክስ ተጠሪ በትምህርት አገልግሎት የንግድ ስራ ዘርፍ የተሰማራ ሲሆን በአሁኑ ሰአት ካፒታሉ ብር 132,000,000 ደርሷል፡፡ ከማህበሩ አባል አንዷ የሆኑት ወ/ሮ ዳንሴ ጉርሙ የአንዱ ዋጋ ብር 1000 የሆነ 95,000 አክስዮኖች በድምሩ የብር 95,000,000 የአክስዮን ድርሻ የነበራቸው ሲሆን በተጨማሪም ከአቶ ኢብራሂም ናውድ 22,400 አክስዮኖች አጠቃላይ ዋጋቸው ብር 22,400,000 የሆነ እና ከዶ/ር አህመድ ኢብራሂም 4,800 አክስዮኖች አጠቃላይ ዋጋቸው ብር 4,800,000 የሆነ ገዝተዋል፡፡ በአዋጅ ቁጥር 813/2006 አንቀጽ 9/3/ለ መሰረት የንግድ ማህበር አክስዮኖች በሽያጭ ከአንድ ሰው ወደሌላ ሰው ሲተላለፍ የውህደት ድርጊት እንደተፈጸመ ተቆጥሮ የውህደት ማስታወቂያ ለአመልካች መቅረብ አለበት፡፡ ተጠሪ የውህደት ማስታወቂያ ለአመልካች ባለማቅረቡ ውህደቱ በንግድ ውድድር ላይ ሊያስከትል የሚችለው አሉታዊ

ተጽኖ እንዳይጠና አድርጓል፡፡ በመሆኑም ተጠሪ በአዋጅ ቁጥር 813/2006 አንቀጽ 42/4 መሰረት ከአመታዊ የሽያጭ ገቢው 10% እንዲቀጣ ይወሰንልኝ በማለት ዳኝነት ጠይቋል፡፡

ተጠሪም በሐምሌ 11 ቀን 2011 ዓ.ም አሻሽሎ ባቀረበው መልስ የሕክምና አገልግሎት እና የህክምና ትምህርት መስጠት ስራ ከማንም ሌላ ድርጅት ጋር ሳልዋሀድ ብቻዬን በመስራት ላይ እገኛለሁ፡፡ ተጠሪ ተጠቃሚውን በአገልግሎት ዋጋም ሆነ በሌላ ሁኔታ ለመጉዳት እና የገበያ የበላይነት ለማግኘት ከማንኛውም ግለሰብ ነጋዴ፣ድርጅት ወይም ሽሪክ ጋር የንግግርም ሆነ የድርጊት ግንኙነት አላደረኩም፡፡ ይህ በሌለበት አንድ ድርጅት ውህደት ፈጥሯል ሊባል አይችልም፡፡ ወ/ሮ ዳንሴ ጉርሙ ያደረጉት የአክስዮን ሽያጭ ግብይት እንጂ የንግድ ግብይት አይደለም፡፡ የአክስዮን ገዢም ሆኑ ሻጭ ነጋዴዎች አይደሉም፡፡ የአዋጁ አንቀጽ 9/3/ለ ተፈጻሚ የሚሆነው አክስዮኖቹ በአንድ ባለአክስዮን ተጠቃለው ሲያዙ እንጂ አብላጫ እና አናሳ የአክስዮን ባለድርሻዎች ባሉበት አይደለም፡፡ ወ/ሮ ዳንሴ ጉርሙ ከፍተኛ ባለአክስዮን ቢሆኑም በማኔጅመንት ስራ ውስጥ ስለሌሉ ውህደት ፈጥረው ገበያ አዛብተዋል ወይም ሸማቾችን ጎድተዋል የሚያስብል አይደለም፡፡ የአክስዮን ሽያጭ ውሉም ውህደት መደረጉን የሚያስረዳ አይደለም፡፡ ውህደት አለ ቢባል እንኳን በጅምር ያለ እና ያልተጠናቀቀ ነው፡፡ በመሆኑም ክሱ ተገቢነት የሌለው ስለሆነ ውድቅ ይደረግልን በማለት ተከራክሯል፡፡

የሸማቾች ጥበቃ ባለስልጣን የዳኝነት አካል የግራ ቀኙን ክርክር መርምሮ የአዋጁ አንቀጽ 9 እና 10 የማስታወቅ ግዴታን ያስቀመጠው ማንኛውም ነጋዴ በሚል ነው፡፡ የአክስዮን ሽያጭ እና ግዢው የተፈጸመው በተጠሪ ሳይሆን በተጠሪ ማህበር አባላት መካከል ነው፡፡ አባላቱ ደግሞ ነጋዴ ስለመሆናቸው አመልካች በማስረጃ አላረጋገጠም፡፡ የአዋጁ አንቀጽ 9/3/ለ ተፈጻሚነትም የንግድ ማህበር አክስዮኖች በቀጥታ ከማህበሩ በመግዛት የራስ ሲደረጉ ወይም የሌላ ሰውን የንግድ መደብር መቆጣጠር ሲቻል ነው፡፡ ከዚህ ውጪ በአክስዮን ማህበር አባላት መካከል የአክስዮን ሽያጭ ሲደረግ ድንጋጌው ተፈጻሚነት የለውም፡፡ በመሆኑም ተጠሪ ማስታወቂያ ሳያቀርብ የውህደት ድርጊት ፈጽሟል ሊባል አይችልም በማለት የአመልካችን ክስ ውድቅ በማድረግ ወስኗል፡፡ አመልካች በዚህ ውሳኔ ላይ የይግባኝ ቅሬታውን ለባለስልጣኑ ይግባኝ ሰሚ አስተዳደር ፍርድ ቤት አቅርቧል፡፡ ይግባኝ ሰሚው የአስተዳደር ፍርድ ቤትም ግራ ቀኙን አከራክሮ በአዋጁ አንቀጽ 9/3/ለ መሰረት በባለአክስዮኖች መካከል የአክስዮን ሽያጭ ሲደረግ የውህደት ስምምነት የተፈጸመ በመሆኑ ይህን የውህደት ድርጊት በአዋጁ አንቀጽ 10/1 መሰረት ተጠሪ ለአመልካች የማሳወቅ ግዴታ አለበት፡፡ በመሆኑ ተጠሪ የውህደት ማስታወቂያ ሳያቀርብ በውህደት ተግባር መሳተፉ ጥፋተኛ ስለሆነ በአዋጁ አንቀጽ 42/4 መሰረት ከአመታዊ የሽያጭ ገቢው 5% ሊቀጣ ይገባል በማለት የስር የዳኝነት አካሉን ውሳኔ ሽሯል፡፡ በዚህ ውሳኔ ላይ ደግሞ ተጠሪ ለፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የይግባኝ ቅሬታ አቅርቦ ፍርድ ቤቱ ግራ ቀኙን ካከራከረ በኋላ የአክስዮን ሽያጩ በአባላት መካከል መደረጉ አከራካሪ አይደለም፡፡ በዚህ የሽያጭ ሂደት ላይ ተጠሪ ስለመሳተፉ በአመልካች የቀረበ ማስረጃ የለም፡፡ ባለአክስዮኖች የአክስዮን ሽያጭ ላይ

መሳተፋቸው ተጠሪ በውህደት ስምምነቱ ወይም በቅንብሩ ተሳትፏል የሚያስብል አይደለም፡፡ በመሆኑም ተጠሪ የማስታወቅ ግዴታ ሳይኖርበት በስር የዳኝነት አካሉ የተሰጠው ውሳኔ መሻሩ ተገቢ አይደለም በሚል የአመልካች መስሪያ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሰጠውን ውሳኔ ሽሮ የስር የአመልካች የዳኝነት አካል የሰጠውን ውሳኔ አጽንቷል፡፡ አመልካችም ይህንን ውሳኔ በመቃወም የሚከተለውን የሰበር ቅሬታ አቅርቧል፡፡

አመልካች በሐምሌ 08 ቀን 2013 ዓ.ም በተጻፈ የሰበር ቅሬታ ለተያዘው ጉዳይ አግባብነት ያለው ድንጋጌ አዋጅ ቁጥር 813/2006 አንቀጽ 9/3/ለ ነው፡፡ በዚህ ድንጋጌ ላይ አንድ ሰው ወይም ብዙ ሰዎች በግዢ ወይም በሌላ በማንኛውም መንገድ በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ ሁኔታ የንግድ ማህበር አክስዮኖችን የራስ ሲያደረጉ የውህደት ድርጊት እንደተፈጸመ እንደሚቆጠር ተደንግጓል፡፡ ይህንን ድንጋጌ ከአዋጁ አንቀጽ 2/16 ጋር አጣምሮ በማንበብ በአንድ ወይም በብዙ ሰዎች አማካይነት የንግድ ማህበር አክስዮኖች የራስ ሲደረጉ እንደውህደት ስምምነት እንደሚቆጠር መረዳት ይቻላል፡፡ አክስዮኖች የራስ ሊደረጉ የሚችሉት ደግሞ በነጋዴዎች ብቻ ሳይሆን በማንኛውም ሰው ነው፡፡ በውህደት መመሪያም አክስዮን የሚገዙ አባላት ነጋዴ ሊሆኑም ላይሆኑም እንደሚችሉ ተደንግጓል፡፡ የአክስዮን ዝውውር የተደረገበት የተጠሪ ማህበርም ነጋዴ ነው፡፡ የውህደት ማስታወቂያ መቅረብ ያለበት አንድ ማህበር ከሌላ ማህበር ጋር ሲዋሀድ ብቻ ሳይሆን በአንድ ማህበር ውስጥ ያሉ ባለአክስዮኖች ሌላ ነጋዴ ላልሆነ ሰው ሲያስተላልፉ እንደውህደት ስለሚቆጠር በአዋጁ አንቀጽ 10/1 መሰረት ተጠሪ የውህደት ማስታወቂያ ለአመልካች የማቅረብ ግዴታ አለበት፡፡ ተጠሪ የውህደት ማስታወቂያ ማቅረቡ አመልካችን ውህደቱ የሚኖረውን ተጽኖ ለመመርመር ያስችለዋል፡፡ በመሆኑም የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ውሳኔ አመልካች የውህደት ምርመራ እንዲያከናውን በህግ የተሰጠውን መብት የሚያሳጣ መሰረታዊ የህግ ስህተት የፈጸመ ስለሆነ ሊታረም ይገባል የሚል ነው፡፡

የአመልካች የሰበር ቅሬታ በሰበር አጣሪ ችሎት ተመርምሮ የተፈጸመው የአክስዮን ሽያጭ ውህደትን ስለማያስከትል ለአመልካች የውህደት ማስታወቂያ ማቅረብ አያስፈልግም በሚል የተወሰነበትን አግባብ ከአዋጅ ቁጥር 813/2006 አንቀጽ 9/3/ለ፣ 10/1 እና ሌሎች አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች አንጻር ለማጣራት ያስቀርባል ተብሎ ተጠሪ መልስ እንዲያቀርብ ታዟል፡፡

ተጠሪም በጥር 05 ቀን 2014 ዓ.ም ጽፎ ባቀረበው መልስ አዋጁ የውህደት ማስታወቂያ የመስጠት ግዴታ የጣለው ለነጋዴ ግለሰብ ወይም ማህበር ነው፡፡ አላማውም ተገቢ ባልሆነ የንግድ ውድድር የሸማቾች መብት እንዳይጎዳ ለመከላከል ነው፡፡ በተጠሪ ድርጅት የአክስዮን ዝውውር የተደረገው ነጋዴ ባልሆኑ ግለሰቦች መካከል ስለሆነ ተጠሪ የማስታወቅ ግዴታ የለበትም፡፡ በመሆኑም በስር ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት የተፈጸመ መሰረታዊ የህግ ስህተት የለም በማለት ተከራክሯል፡፡

አመልካችም በየካቲት 17 ቀን 2014 ዓ.ም የተጻፈ የመልስ መልስ በማቅረብ የሰበር ቅሬታውን አጠናክሯል፡፡

የክርክሩ አመጣጥ ከላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም ያስቀርባል ሲባል የተያዘውን ጭብጥ ከግራ ቀኙ ክርክር፤ በስር ፍርድ ቤቶች ከተረጋገጠው ፍሬ ነገር እና ከተገቢው ህግ ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለው መርምረናል፡፡

እንደመረመርነው የተጠሪ የካፒታል መጠን ብር 132,000,000 መሆኑ፤ የተጠሪ አክስዮን ማህበር አባል የሆኑት ወ/ሮ ዳንሴ ጉርሙ ከነበራቸው የብር 95,000,000 አክስዮን በተጨማሪ ከሁለት የአክስዮን ማህበሩ አባላት አክስዮኖችን ገዝተው ያላቸው የአክስዮን ዋጋ መጠን ወደ ብር 122,000,000 ከፍ ማለቱ፤ ወ/ሮ ዳንሴ ጉርሙም ሆኑ የአክስዮን ድርሻቸውን በሽያጭ ያስተላለፉት ግለሰቦች ነጋዴ አለመሆናቸው፤ የአክስዮን ሽያጩ ተጠሪ ባደረገው የባለአክስዮኖች ስብሰባ ላይ ጸድቆ የአክስዮን ዝውውሩ በሰነዶች ማረጋገጫ እና ምዘገባ ኤጀንሲ የተመዘገበ መሆኑ በስር ፍርድ ቤቶች የተረጋገጠ ፍሬ ነገር ነው፡፡ አመልካች በተጠሪ የአክስዮን አባላት መካከል የአክስዮን ሽያጭ መደረጉ እንደ ውህደት ስለሚቆጠር ተጠሪ ለአመልካች የውህደት ማስታወቂያ የማቅረብ ግዴታ እያለበት ግዴታውን አልተወጣም በሚል የሚከራከር ሲሆን ተጠሪ በበኩሉ የአክስዮን ሽያጭ የተደረገው ነጋዴ ባልሆኑ የማህበር አባላት መካከል ነው፡፡ በህጉ የውህደት ማስታወቂያ የመስጠት ግዴታ የተጣለው ደግሞ ነጋዴ ለሆነ ግለሰብ ወይም ማህበር በመሆኑ ተጠሪ የማስታወቅ ግዴታ የለብኝም በማለት ተከራክሯል፡፡ በመሆኑም ለዚህ የግራ ቀኙ ክርክር እልባት ለመስጠት በህጉ እንደውህደት የሚቆጠሩት ድርጊቶች ምንድናቸው? ለአመልካች የውህደት ማስታወቂያ የመስጠት ግዴታስ የተጣለው በምን ሁኔታ እና በማን ላይ ነው? የሚሉትን ነጥቦች መመርመር ያስፈልጋል፡፡

በመጀመሪያም እንደ ውህደት የሚቆጠሩ ድርጊቶች ምንድናቸው? ወይም ወህደት ተደርጓል የሚባለው መቼ ነው? ለሚለው ነጥብ ምላሽ ለማግኘት ውህደት (Merger) ማለት ምንማለት ነው የሚለውን መመልከቱ ተገቢ ይሆናል፡፡ በ2004 ዓ.ም የወጣው የምስራቅ እና የደቡብ አፍሪካ ሀገራት ነጻ የንግድ ቀጠና ስምምነት የንግድ ውድድር ደንብ (The common market for Eastern and Southern Africa/COMESA/ competition Regulation) በአንቀጽ 23 /1 ውህደት ማለት ምን ማለት እንደሆነ እንደሚከተለው ተተርጉሞ እናገኛለን፡፡

«Merger means the direct or indirect acquisition or establishment of a controlling interest by one or more person in the whole or part of the business of a competitor, supplier, customer or other person whether that controlling interest is achieved as a result of;

a. The purchase or lease of the shares or assets of the competitor, supplier, customer or other person;

b. The amalgamation combination with a competitor, supplier, customer or other person; or

c. Any means other than as specified in sub-paragraph a or b.»

ይህም በግርድፉ ሲተረጎም ውህደት ማለት አንድ ድርጅት ወይም ግለሰብ የሌላ ድርጅት አክስዮን በሙሉ ወይም በከፊል በመግዛት ወይም በየግላቸው ሲሰሩ የነበሩ የንግድ ማህበራት በመቀላቀል ወይም አንድ በመሆን ወይም በሌላ መንገድ የአክስዮን ማህበሩን ውሳኔ አሰጣጥ እና አጠቃላይ የንግድ እንቅስቃሴውን ለመቆጣጠር የሚያስችል ተግባር ነው፡፡ በአውሮፓ ዩኒየን የውህደት ደንብ (European Community Merger Regulation) በተመሳሳይ ሁኔታ የውህደት ትርጉም ተሰጥቶ እናገኛለን፡፡

በሀገራችን የንግድ ውድድር እና የሸማቾች ጥበቃ አዋጅ ቁጥር 813/2006 ከአንቀጽ 9-13 ውህደትን ስለመቆጣጠር የተደነገጉ ድንጋጌዎች ሲሆኑ በአንቀጽ 9/3/ሀ እና ለ የውህደት ድርጊት ተፈጸመ የሚባለው መቼ እንደሆነ ተመልክቷል፡፡ ከዚህ ድንጋጌ ይዘት ውህደት ማለት ምን ማለት እንደሆነም መገንዘብ ይቻላል፡፡ በዚህም መሰረት ውህደት ማለት ግላዊ ተቋምነታቸውን ይዘው የነበሩ ሁለት ወይም ከዚያ በላይ የሆኑ የንግድ ማህበራት ተቀላቅለው አንድ ማህበር ሲሆኑ ወይም አንድ አላማ ያለው የንግድ ስራ ለማከናወን ሁሉንም ወይም ከፊሉን ሀብታቸውን ሲያቀላቅሉ ነው፡፡ በተጨማሪም ለዚህ አዋጅ አፈጻጸም በአንድ ሰው ወይም በብዙ ሰዎች በግዢ ወይም በሌላ በማንኛውም መንገድ የንግድ ማህበር አክስዮኖች፤ ሴኩሪቲዎች ወይም ንብረቶች የራስ ሲደረጉ ወይም የሌላ ሰው የንግድ መደብርን አመራር መቆጣጠር እንደውህደት የሚቆጠር ይሆናል፡፡ በተለይም በተያዘው ጉዳይ የመጀመሪያው አከራካሪ ነገር በአክስዮን ማህበር አባላት መካከል የሚደረግ የአክስዮን ሽያጭ እና ግዢ እንደውህደት ይቆጠራል ወይስ አይቆጠርም የሚል ሲሆን የአዋጁ አንቀጽ 9/3/ለ ድንጋጌ በአንድ አክስዮን ማህበር አባላት መካከል የተደረገ የአክስዮን ሽያጭ እና ግዢ የውህደት ተግባር ተደርጎ እንደሚቆጠር በግልጽ የሚያመለክት ነው፡፡ በመሆኑም የአክስዮን ሽያጭ የተደረገው በማህበር አባለት መካከል ቢሆንም ህጉ ለአዋጅ አፈጻጸም ሲባል እንደውህደት እንዲቆጠር የፈለገ በመሆኑ ተጠሪ በአባላቱ መካከል የተደረገ የአክስዮን ሽያጭ እንደ ውህደት አይቆጠርም በሚል የሚያቀርበው ክርክር ተቀባይነት የለውም፡፡

በውህደት የተለያዩ የንግድ ማህበራት ወይም ግለሰቦች የንግድ ማከናወኛ ግብአቶች በአንድ ላይ አቀናጅተው የተሻለ አቅም በመፍጠር የተሻለ የንግድ ተወዳዳሪነት እና የንግድ አቅርቦት እንዲኖር በማድረግ እንዲሁም የሀገርን ኢኮኖሚ በማሳደግ ረገድ በተናጥል የንግድ ስራ ከመስራት የተሻለ ጥቅም እንዳለው የሚታወቅ ቢሆንም በተቃራኒው ውህደት በሀገር ኢኮኖሚ እና በተጠቃሚ ማህበረሰብ/ሸማቾች

ብሎም በሌሎች የንግድ አካላት ላይ ያልተገባ ውድድር(unfair competition) በመፍጠር አሉታዊ ተጽኖ ሊያስከትል የሚችልበት ሁኔታ ስለሚኖር ውህደትን መቆጣጠር ያስፈልጋል፡፡ የውህደትን አሉታዊ ተጽኖ መቆጣጠሪያ መንገድ ከሆኑት ውስጥ አንዱ የውህደት ማስታወቂያ(merger notification) ለተቆጣጣሪ ባለስልጣን መስጠት ነው፡፡ ይህም እንደየ ሀገራቱ የህግ ማእቀፍ በግዴታ ወይም በፍቃደኝነት የሚፈጸም ሲሆን ለምሳሌ በምስራቅ እና ደቡብ አፍሪካ ነጻ የንግድ ቀጠና ሀገራት(COMESA) እና በአውሮፓ ዩኒየን(EU) አባል ሀገራት የውህደት ማስታወቂያ መስጠት ግዴታ ሲሆን በእንግሊዝ ግን የውህደት ማስታወቂያ መስጠት በፍቃደኝነት ላይ የተመሰረተ ነው፡፡ ኢትዮጵያም የምስራቅ እና የደቡብ አፍሪካ ነጻ የንግድ ቀጠና አባል ሀገራት መካከል አንዷ እንደመሆኗ እንዲሁም በአዋጅ ቁጥር 813/2006 አንቀጽ 9/2 እና 10/1 መሰረት ለአመልካች የውህደት ማስታወቂያ ማቅረብ ግዴታ መሆኑን መገንዘብ ይቻላል፡፡

ከውህደት ማስታወቂያ ጋር ተያይዞ የውህደት ማስታወቂያ የማቅረብ ግዴታ የተጣለው ነጋዴ በሆነ ግለሰብ ላይ ብቻ ነው ወይስ ነጋዴ ያልሆነ ግለሰብም ማስታወቂያ የመስጠት ግዴታ አለበት የሚለው መታየት አለበት፡፡ የምስራቅ እና የደቡብ አፍሪካ ነጻ የንግድ ቀጠና የንግድ ውድድር ደንብ አንቀጽ 24/1 ውህደት እስካለ ድረስ ለሚመለከተው ባለስልጣን ማሳወቅ ግዴታ መሆኑን ተመልክቷል፡፡ ይህም የውህደት ተግባር እስከተፈጸመ ድረስ የማስታወቅ ግዴታ በነጋዴ ማህበር ወይም በነጋዴ ግለሰብ ላይ ብቻ የተጣለ አለመሆኑን ይልቁንም በውህደት ድርጊቱ የተሳተፈው ነጋዴ ባይሆንም እንኳን የማስታወቅ ግዴታ እንዳለበት የሚያስገነዝብ ነው፡፡

በአዋጅ ቁጥር 813/2013 አንቀጽ 10/1 የማስታወቅ ግዴታ የተጣለው ነጋዴ በሆነ ማህበር ወይም ግለሰብ ላይ ብቻ እንደሆነ በሚመስል መልኩ ተደንግጓል፡፡ ይህ ድንጋጌ ከአዋጁ አንቀጽ 9/3/ሀ ጋር ተገናዝቦ ሲታይ በአንቀጽ 10/1 ማንኛውም ነጋዴ በሚል የተገለጸው በአንቀጽ 9/3/ሀ ላይ የተመለከቱትን የንግድ አካላትን ብቻ የሚመለከት ይመስላል፡፡ ነገር ግን በህግ አተረጓጎም ረገድ ጥቅም ላይ ከሚውሉ የአተረጓጎም መርሆዎች ውስጥ አንዱ ወርቃማ የአተረጓጎም ዘዴ (Golden rule of interpretation) ሲሆን የዚህ አይነት አተረጓጎም መሰረተ ሀሳብ ህጉ በአጠቃላይ ወይም በህጉ በተወሰኑ ድንጋጌዎች ለማሳካት የታሰበውን አላማ(purpose) ተግባራዊ ማድረግ የሚያስችል ትርጉም መስጠት ነው፡፡ ይህን የአተረጓጎም መርህ ተግባራዊ ለማድረግ ህጉን ለማውጣት ያስፈለገበትን አጠቃላይ ምክንያት ከህጉ መግቢያ፣ ህግ አውጪው ህጉን ሲያወጣ የተወያየበትን ሰነድ (ሀተታ ዘምክንያት) እና መሰል ሰነዶችን እንዲሁም በህጉ በተለያዩ ድንጋጌዎች ላይ የተመለከቱትን መሰረተ ሀሳቦች ከግምት ውስጥ በማስገባት አንዱን ከሌላው ጋር በማዛመድ መመልከት ያስፈልጋል፡፡

በዚህም መሰረት አጠቃላይ የአዋጅ ቁጥር 813/2006 አላማ ተገቢ ባልሆኑ የንግድ ውድድሮች ሽማቶች ወይም ተጠቃሚዎች እንዳይጎዱ መከላከል ነው፡፡ በተጨማሪም የውህደት ስምምነት ወይም ቅንብር በአዋጁ

አንቀጽ 11 መሰረት ከባለስልጣኑ(ከአመልካች) ፍቃድ ሳይገኝ ተፈጻሚ ሊሆን እንደማይችል በአዋጁ አንቀጽ 9/2 ተመልክቷል። ባለስልጣኑ ፍቃድ የሚሰጠው ደግሞ ውህደቱ በንግድ ውድድር ላይ አሉታዊ ተጽኖ የሌለው መሆኑን ካጣራ በኋላ ስለሆነ አሉታዊ ተጽኖ መኖር አለመኖሩን ለማጣራት ባለስልጣኑ ውህደት መደረጉን እንዲያውቀው ማድረግ የግድ ነው። ስለዚህ በአዋጁ አንቀጽ 9/3/ለ መሰረት በአንድ ሰው ወይም በብዙ ሰዎች በተዘዋዋሪ ወይም በቀጥታ የንግድ ማህበር አክስዮኖችን፤ ሴኩሪቲዎችን ወይም ንብረቶችን የራስ ማድረግ እንደውህደት ተግባር ይቆጠራል እስከተባለ ድረስ ይህ ውህደት ተፈጻሚነት እንዲኖረው በአዋጁ አንቀጽ 9/2 መሰረት የውህደቱ ፈጻሚ/አድራጊ ነጋዴ ቢሆንም ባይሆንም ውህደቱን ለአመልካች ማስታወቅ ግዴታ ያለበት መሆኑን የሚያሳይ ነው። በመሆኑም ነጋዴ ባልሆኑ አክስዮን ማህበር አባላት መካከል የተደረገ የአክስዮን ሽያጭ እንደወህደት የሚቆጠር በመሆኑ ይህንን ውህደት በአዋጁ አንቀጽ 9/2 መሰረት ለአመልካች ማሳወቅ የአዋጁን አጠቃላይ አላማ የሚያሳካ ይሆናል።

ሌላው መታየት የሚገባው በአንድ ነጋዴ ባልሆኑ የአክስዮን ማህበር አባላት መካከል በተደረገ የአክስዮን ሽያጭ ምክንያት የውህደት ድርጊት ሲፈጸም ለባለስልጣኑ ወይም ለአመልካች የማሳወቅ ግዴታ የማነው? ወይም የአክስዮን ማህበሩ ውህደቱን የማስታወቅ ግዴታ አለበት ወይ? የሚለውን ስንመለከት የአክስዮን አባላት የሚያደርጉት የአክስዮን ሽያጭ የአክስዮን ማህበሩ በገዢው ስም እንደሚመዘገብ ግልጽ ነው። ይህም የአክስዮን ማህበሩ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ በውህደት ሂደቱ ላይ መሳተፉን የሚያሳይ ነው። በተጨማሪም የአንድ የአክስዮን ማህበር አባል የአክስዮን ድርሻ መጠን እየጨመረ መሄዱ የአክስዮን ገዢው በማህበሩ ውስጥ ያለው ድምጽ(vote) እንዲጨምር የሚያደርገው በመሆኑ በማህበሩ አባላት በድምጽ ብልጫ በሚወሰኑ ጉዳዮች ላይ በሚፈልገው መልኩ ወይም በንግድ ውድድር ላይ ተገቢ ያልሆነ ተጽኖ የሚፈጥር ውሳኔ ለመስጠት ያስችለዋል። ማስታወቂያ የመስጠት አላማ ደግሞ እንደዚህ አይነት ተጽኖዎች ሊፈጠሩ የሚችሉ መሆን ያለመሆኑን ገምግሞ ውህደቱን መፍቀድ ወይም መከልከል በመሆኑ የአክስዮን ማህበር በአባላት መካከል በተደረገ የአክስዮን ሽያጭ ምክንያት የተፈጠረውን ውህደት የአክስዮን ማህበሩ የማሳወቅ ግዴታ ሊኖርበት ይገባል።

በተያዘው ጉዳይ ወ/ሮ ዳንሴ ጉርሙ ያደረጉት የአክስዮን ግዢ የተወሰነው የማህበሩ አባላት ተገኝተው ባደረጉት ስብሰባ መሆኑን በአመልካች የተገለጸ ሲሆን ተጠሪ ይህንን በግልጽ በመካድ ያቀረበው ክርክር የለም። የአክስዮን ግዢው በስብሰባ እንኳን አልተወሰነም ቢባል ግለሰቧ የአክስዮን ግዢውን ከፈጸሙ በኋላ በማህበር ውስጥ ያላቸው የአክስዮን መጠን በአመልካች እንደተገለጸው ወደ ብር 122,000,000 ማደጉን ተጠሪ በመካድ ያቀረበው ክርክር የለም። ግለሰቧ በተጠሪ ማህበር ውስጥ ያላቸው የድርሻ መጠን ከአጠቃላይ የማህበሩ ካቲታል አንጻር ሲታይ ከ92 በመቶ በላይ እንዲሆን ያደርገዋል። ይህም የግለሰቧን የድምጽ መጠን ከፍተኛ የሚያደርገው በመሆኑ ግለሰቧ የማኔጅመነት አባል ባይሆኑም እንኳን በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ በተጠሪ ማህበር ውሳኔ አሰጣጥ ላይ ተጽኖ እንዲፈጥሩ ሊያደርጋቸው ይችላል። በመሆኑም አመልካች የውህደት ማስታወቂያ ደርሶት የአክስዮን ግዢው ምን ተጽኖ ሊኖረው

እንደሚችል ባልመረመረበት ሁኔታ ተጠሪ የአክስዮን ሽያጩ በንግድ ውድድር ላይ የሚያስከትለው ተጽኖ የለም በሚል የሚያቀርበው ክርክር ተቀባይነት የለውም፡፡

ሲጠቃለል በተጠሪ ማህበር አባላት መካከል የአክስዮን ሽያጭ የተደረገ ቢሆንም ሽያጩ እንደ ውህደት ድርጊት እንደሚቆጠር በህግ በግልጽ የተመለከተ በመሆኑ፤ ማንኛውም የውህደት ድርጊት ሲፈጸም ለአመልካች የውህደት ማስታወቂያ ሊሰጥ እንደሚገባ በአዋጁ አንቀጽ 9/2 ላይ ተመልክቶ እያለ ለጉዳዩ አግባብነት የሌለውን የአዋጁን አንቀጽ 10/1 በመጥቀስ እንዲሁም ተጠሪ በውህደቱ ሂደት ያደረገው ተሳትፎ በማስረጃ ስላልተረጋገጠ ተጠሪ ማስታወቂያ የመስጠት ግዴታ የለበትም በሚል የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የስር ይግባኝ ሰሚ አስተዳደር ፍርድ ቤት ውሳኔን መሻሩ የአዋጅ ቁጥር 813/2006 ድንጋጌዎች ይዘት እና አላማ የሚቃረን መሰረታዊ የህግ ስህተት በመሆኑ የሚከተለውን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

ውሳኔ

1ኛ. የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 185245 በሚያዝያ 11 ቀን 2013 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348/1 መሰረት ተሽሯል፡፡

2ኛ. የንግድ ውድድርና የሸማቾች ጥበቃ ባለስልጣን ይግባኝ ሰሚ አስተዳደር ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 00039 በጥቅምት 19 ቀን 2012 ዓ.ም ሰጠው ውሳኔ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348/1 መሰረት ጸንቷል፡፡

3ኛ. በዚህ ፍርድ ቤት የተደረገው ክርክር ያስከተለውን ወጪ እና ኪሳራ ግራ ቀኝ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሠ/ኃ